አራተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፩
4 me ANNÉE № 1

ሐሙስ ታኅሣሥ ፳፯ ቀን ፤ ፲፱፻፳ ዓ ም ።
JEUDI 5 Janvier 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት
Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሰምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ጸሐፊው ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ለፊስን በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers, Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ቅዱስ ገብርኤል በዓል አከባበር ።

ታኅሣሥ ፲፱ ቀን የቅዱስ ገብርኤል ዓመት በዓል ስለ ሆነ ልዑል የኢ. መ አ ወ ተፈሪ መኰንን ከክቡራን መኳንንቶቻቸው ጋራ በብዙ ሠራዊት ታጅበው በዓልን ለማክበር ወደ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ወረዱ ። ከሰው ብዛት የተነሣም ሜዳው ተጨንቆ ነበር። ከዚህ በኋላ ከቤተ መንግሥቱ በስተ ምስራቅ ባለው መስክ ታቦቱ በከብካብ ወርዶ ከሜዳው ላይ በተሰናዳው ድንኳን ገባ ልዑልም በተሰናዳላቸው በታ ሆኑ ። በዚያን ጊዜ ካህናቱ የከብካብ ሥራቸውን አደረሱ ።

ካህናቱ የከብካብ ሥራቸውን ካደረሱ በኋላ ታቦቱ በከብካብ ወደቤተ ክርስቲያኑ ተመለሰና ዑደት ተደረገ ከዑደቱ በኋላም ብፁዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ስለ በዓሉ ተርከው ሕዝቡን የሚጠቅም ምክር መክረው አሳርገው ባርከው አሰናበቱት ። ስድስት ሰዓት ሲሆንም ስለ በዓሉ ክብር መድፍ ተተኰሰና በዓሉን ለማክበር የተሰበሰበው ቍጥሩ የበዛ ሰው እየቤቱ ተመለሰ ።

የቅዱስ ገብርኤልና የሌሎች መላእክት አጭር ታሪክ ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደተገኘው ።

ቅዱስ ገብርኤል ከትልልቆቹ መላእክት አንዱ ነው ። በመላእክት መካከል ለሆነው ፈተናና ውሽት አቸንፎ እግዚአብሔር የሰጠውንም ሹመት ጠብቆ የተገኘ ነው ። ይህ መልአክ በብሉይና በሐዲስ ኪዳን ይነገርለታል ።

በዳንኤል ምዕ ፰ ፲፮ ፳ ምዕ ፱ ፳፩ ፳ ምዕ ፲ ፥ ፳፩ የእግዚአብሔር የፈቃዱ ምስጢር ነቢዩን ዳንኤልን ሊያስተምርና ሊገልጥለት ከአምላክ እንደተላከ ይናገርለታል ። ዳንኤልም የተገለጠለትንና በዚህ መልአክ በኩል ያገኘውን አምላካዊ ትምህርት ተጠንቅቆ ጽፎ አስቈይቶልናል ።

በሐዲስ ኪዳንም የዮሐንስ መጥምቅንና የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መጸነስ የምስራች ለመንገር እንደተላከ ይነገርለታል ። ዘካርያስ ካህን የሃይማኖት መምሕር ሊታመን የሚገባውንና የሚቻለውን ነገር አለተአምራት ሊያምን አልቻለም ። በዚሁ ምክንያት ባለማመኑ የቅጣትን ተአምራት ወረደበት ፲፰ ቅድስት ማርያም ግን ከተፈጥሮ ሕግ በላይ የሆነውን ብርቱ ነገር አለ አንዳች ተአምራት ለማመን ቻለች ። በዚህ ነገርም ትልቅነትዋ በእግዚአብሔር ዘንድ ብዙ ነው ። በርሱ ዘንድ የሚከበር ትልቅ ሃይማኖት ያለው ነውና ።

በዘካርያስ ነገር ግን የቅዱስ ገብርኤል ትልቅነት ይመሰክርለታል ። እኔ ገብርኤል በእግዚአብሔር ፊት የምቆም ነኝ ፤ በማለቱ ። ገብርኤል ማለት የእግዚአብሔር ሰው የእግዚአብሔር ኃያል ማለት ነው ። በምድራዊው ንጉሥ ፊት መቆም ትልቅ ሞገስ ከሆነ በንጉሠ ነገሥት በእግዚአብሔር ፊት መቆምስ ስንት መጠን የሌለው ክብር ይሆናል ? ። እንግዴህ ገብርኤል በእግዚአብሔር ፊት ትልቅ ሥራና ትልቅ ከበሬታ እንዳለው እርግጥ ነው ። በእግዚአብሔር ፊት የምቆም ሲልም የውሸተኝነትን ነገር አንድ ስንኳ እንዳይገኝበት ስለዚህ ተልከ የመጣበትን መልእክት እጅግ የሚታመን መሆኑን ሲያስረዳ ነው ። እንዴሁም እኛ ከእግዚአብሔር የመጣልንን ቃል እንዴት አጥብቀን ልንይዘውና በትጋትና በእውነትም ልንፈጽመው እንዲገባን ያስተምረናል ። (ዕብ ፡ ፪ ፣ ፪ ።)

መላእክት ብዙዎች ናቸው ። (ራእ ፡ ፭ ፣ ፲፩ ።) በርሳቸው ውስጥም ልዩ ልዩ ማዕርጋትና ሹመት አላቸው ። (ኤፌ ፫ ፣ ፲ ፣ ቆሎ ፩ ፣ ፲፮) ። ከነዚሁ መላእክት በሰይጣን ሽፍትነት እርሱን ተከትለው ያመጹ ሲሶ መሆናቸው አቡ ቀለምሲስ ምዕ ፲፪ ፣ ፱ ፣ ያመለክታል ። እነዚሁ ሹመታቸውን ያልጠበቁ መላእክት ጌታ ከሰማያዊ ስፍራ አባሮና አውጥቶ ታስረው በእንጦርጦስ

ለኋለኛው ቀን ፍርድ ጠብቋቸዋል ። ይሁ ፮ ፣ ፪ ፣ ጴጥ ፪ ፣ ፬ ።

መላእክት ብርቱዎች ናቸው (መዝ ፻፫ ፣ ፳ ። ባሕርያቸውም መንፈስ ነው ። መዝ ፻፬ ፣ ፬ ። በአእምሮና በእውቀት በማስተዋል በጥበብም የሞሉ ናቸው ።

ሥራቸውም ልዩ ልዩ የእግዚአብሔር ትእዛዝ በሰማያትና በምድር መፈጸም ነው ። (መዝ ፻፫ ፣ ፳ ።)

ይልቁንም በምድር የእግዚአብሔርን ሰዎች ይጠብቃሉ ። (ዕብ ፩ ፣ ፲፬ ፣ መዝ ፺፩ ፣ ፲፩ ፣ ፲፪ ፣ መዝ ፴፬ ፣ ፯ ።)

የእግዚአብሔር የቅጣቱ ትእዛዝም ይፈጽማሉ ። ስለ ነፍሳት ደኅንነትም ብርቱ መሻትና በጎ ፈቃድ አላቸው ። ስለዚህ ኃጢአተኞች በንስሐ ክፉ ሥራውን በመተው ወደ እግዚአብሔር ሲመለሱ መጠን የሌለው ደስታ ያደርጋሉ ። (ሉቃ ፲፭ ፣ ፲ ፣) ሕፃናትንም ይጠብቃሉ ። ማቴ ፲፰ ፣ ፲ ። በክርስቶስ በኩል ስለ ሰው ልጆች በተደረገው ቤዛነት ሊመረምሩም ብዙ ይጓጓሉ ። በክርስቶስ ሞትም የእግዚአብሔርን ፍቅር ለወደቀው ዓለም ብዙ መሆኑን ተረድተውታል ፩ ጴጥ ፣ ፩ ፣ ፲፪ ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ከመወለዱ ጀምረው እስከ ዕርገቱ ከቶ አልተለዩትም ። የመድኃኔ ዓለም ልደት መላእክት የምስራች ነገሩ ። (ሉቃ ፪ ፣ ፱ ፣ ፲፬ ። ፩ ጢሞ ፫ ፣ ፲፮ ። በምድረ በዳ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ከዲያብሎስ ሲፈተን ያገለግሉት ነበር ። (ማቴ ፬ ፣ ፲፩ ። ማር ፩ ፣ ፲፪ ።)

በጌቴ ሴማኔ ሲጨነቅ የሚያበረታው መልአክ ተላከበት ። (ሉቃ ፳፪ ፣ ፵፫ ፣) በትንሣኤው ዕለት መላእክት ትንሣኤውን ለተቀደሱት ሴቶች የምስራቹን ነገሩ ። (ማቴ ፳፰ ፣ ፭ ፣ ፯ ።) ወደ ሰማይም ሲወጣ ሁለት መላእክት የዳግመኛ መምጣቱን ለሐዋርያት አስተማሩ ። (ግ ሐ ፩ ፣ ፲ ።) በዳግመኛ በክብር መግለጡም የማይቆጠሩ መላእክት አጅበውት ይመጣሉ ። (ማቴ ፳፭ ፴፩ ፣ ምዕ ፲፱ ፣ ፳፰ ።)

እኛም በዚች ዓለም ስንኖር የመላእክትን ጥበቃና መሪነት ብዙ ያስፈልገናል ። ስለዚህም የርሳቸውን በሕሪና ሥራ ልናስተውል ግድ ይገባናል ። መላእክት አንዳች ነገር እንደ ማያስፈልጉን ማሰብ ትልቅ ስሕተት ነው ፤ እንግዴህ እርሳቸውን ዕለት ዕለት እንዲሰድልን እግዚአብሔርን ልንለምን ይገባናል ግ ሐዋ ፲፪ ፣ ፯ ፲፩ ፣ ፲፰ ። ግ ሐዋ ፳፯ ፣ ፳፫ ።

በምጽአት ወይም በዓለሙ መጨረሻም ጻድቃንን ከኃጢአተኞች ማኸል ለይተው ወደ ክርስቶስ የሚያቀርቡዋቸው መላእክት ናቸው ። ማቴ ፲፫ ፣ እርሳቸውም ስራችንና አሳባችን ሁሉ ያውቃሉ በሕይወታችን ሁሉ ይከተሉናልና ። በሕይወታችንም ምስክር ይሆኑ ብናል (ምሳ ፰ ፣ ፰ ፣) እንግዲህ እርሳቸው እንዳይዝኑብን አካሄዳችንን ሁሉ እንደ እግዚአብሔር በጎ ፈቃድ እናሳምር ።

የፍቅርና ያገልግሎት ማሕበር ሁለተኛ ዓመት በዓል ።

ታኅሣሥ ፲፯ ቀን የፍቅርና አገልግሎት ማኅበረተኞች ማኅበራቸውን የተመሰረተበትን ቀን በአለቃቸው ቤት አክብረውት ውለው ነበርና በምርቃቱ ጊዜ ሁሉም የአሳቡን ሲመርቅ እንደ መልካም ባለቅኔ ደስ ያሰኝ ነበር ። የአንድነታቸውንና የፍቅራቸውንም አኳኋን ለተመለከተው በጣም የሚያስቀና ነበር ።

በመጀመሪያ የማኅበሩ አለቃ ክቡር ሐኪም ወርቅነህ የሚከተሉትን ቃላት ለመናገር በተነሡ ጊዜ ሁሉም በጸጥታ ቆሞ ያዳምጥ ጀመር ።

ክቡራን ወዳጆቼና ወንድሞቼ ።

ማኅበራችን የተመሠረተበትን ሁለተኛውን ዓመት ለማክበር ዛሬ ሁላችሁን ከዚህ ተሰብስባችሁ በማየቴ ብዙ ደስ ይለኛል ። ባለፈው ዓመት ስለ አገራችን አገልግሎት ፤ ነፃ የወጡ ባሮችንና ድሆች ልጆችን ከፊተኛው ዓመት ይልቅ ብዝዎች ሰብስበናል ፬ ሴቶች ፲፫ ወንዶች ልጆች ነበሩ ። አሁን ግን ፲፫ ሴቶች ፴፩ ወንዶች ልጆች ሆነዋል ። እነዚህንም ያማርኛ ንባብና ጽሕፈት ሸማኔነትና መኪና ስፌት እንዲማሩ አድርገናል ሴቶቹም የቤት ሥራና ፈትል ይማራሉ ።

ከሰበሰብናቸው ልጆች ፲፱ኙ በፈቃዳቸው ሄደው አሁን ያሉት የምናሳድጋቸው ፳፭ ናቸው ።

ጌታችን ልዑል አልጋ ወራሽ በሰጡን ቦታ ላይ የተጀመረው የተማሪ ቤቱ ሥራ በቶሎ ተፈጽሞ ልጆቹን ከዚያ አግብተን ሥራችን እንዲከናወንልን ተስፋ አደርጋለሁ ። አሁን ሁሉን ቤት ለመስራት የሚበቃ ገንዘብ የለንም ግን ሥራችን እግዚአብሔር የሚወደው ስለሆነና አገራችንንም የምናገለግልበት ስለሆነ ገንዘብ ለማግኘት እግዚአብሔር እንዲረዳን ተስፋ እናደርጋለን ።

ባለፈው ዓመት የማኅበረተኞቻችን ቁጥር ፵ነበር አሁን ፹፩ሆነናል ቁጥራችን እንዲህ እየበዛ በመሄዱ የአገራችን ሰዎች ሥራችንን እንደወደዱትና ደስ እንዳላቸውም ያስረዳል ።

የማኅበራችን አሳቡና ምኞቱ እንደ ሌላ ማኅበር እንዳይዶለ አዲሶቹ ወዳጆቻችንና ማኅበረተኞቻችን በጣም ማወቅና ማሰብ ይገባቸዋል የማኅበራችን ትምክሕት ሌላው ሊያደርግልህ የምትወደውን አንተም ለሌላው አድርግ ነው ። መለዮቻችንም እንደምታውቋቸው ሃይማኖት ፣ ቅንነት ነፃነት ፣ እውነት ፣ ንጽሕና ፣ ፍቅር ፣ አገልግሎት ናቸው ። እነሆ የማኅበራችን አሳቡና ምኞቱ ከሌላው ልዩ እንደሆነ በዚህ ይገለጻልና እኛ ማኅበረተኞች ሁሉ አካሄዳችንን በነዚህ ቃላት ልናደርግ ይገባናል ። ወደዚህ ማኅበር መግባታችንም ለየራሳችን ጥቅም ሳይሆን አገራችንን ለማገልገልና ወንድሞቻችንን ለመርዳት ፤ የምንወዳትን የአገራችንን ነፃነት ለመጠበቅ ነውና ይህንኑ አሳባችንን ለመፈጸም እግዚአብሔር እንዲረዳን እለምናለሁ ።

8 NOV 59

በዚህም በዓላችን ደኅና ምግብ ያሰናዱልንን ሴትወይዘሮች ማኅበሩ ስም አመሠግናቸዋለሁ ። ስለ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ። ስለ ልዑል አልጋ ወራሽ ጤና ፤ ስለ ኢትዮጵያ ነፃነት ሁላችን ተነሥተን ጽዋችንን እንድንጠጣ እለምናችኋለሁ ብለው ሲጨርሱ የደስታ ጭብጨባ ተጨበጨበ ።

ከዚሁም በኋላ የማኅበሩ ምክትል አለቃ (ቪ ፕሬዚዳን) ክቡር አቶ ከበረ ኃይለ ሥላሴ የሚከተለውን ቃል በተከናወነ አነጋገር አነበቡት ።



አቶ ከበረ ኃይለሥላሴ ።

ስለ መንግሥት ሥራ ከከተማ ውጭ የሚኖሩ ወንድሞቻችን ሁሉ የዛሬ በዓላችን ቀን የሁለተኛው ዓመት መጨረሻና የሶስተኛው ዓመት መጀመሪያ መሆኑን ሳይዘነጉት፣በዛሬው ቀን ብቻ ከኛ ከወንድሞቻቸው በመለየታቸው ቅር ቢላቸውም ማህበራችን ሥራው ሳይታጐልበት ዕንቅፋት አልባ ሁለተኛው ዓመት መጨረሻው በመድረሱ ደስታቸው ከልክ ያለፈ ሳይሆን አይቀርም።ወደፊትም ለሶስተኛው ዓመት መጨረሻው በዓላችንን በምናከብርበት ጊዜ በዋናው ከተማ አዲስ አበባ ተሰብስበው አብረውን ሊውሉ በፈቃድ ልንቀበላቸው ተስፋ አለኝ ።

ልዑል እግዚአብሔር ለግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱና ለልዑል ተፈሪ መኰንን ጤንነትና ዕድሜ እንዲሰጥልን እለምናለሁ። ስለ ማሕበራችን አለቃ አባታችን ሃኪም ወርቅነህና ይህን መልካም መሰናጃ ላዘጋጁ እናታችን ስለክብርት ወይዘሮ ቀጸላ ወርቅ ስለሁላችሁም ወንድሞቼ ጤንነትና ብርታት ጽዋዬን እጠጣለሁ ብለው ሲጨርሱ ተጨበጨበ ።

ከዚህ በኋላ ስማቸው ከዚህ በታች የተጻፉት ሰዎች የተወደደ አሳባቸውንና ደስታቸውን ሲገልጹ የሚከተለውን ቃላት ተናገሩ ።

ከአዳም ጀምሮ በኖኅ በአብርሃም የምሕረት ፈሳሽ ውሀ ቃል ኪዳንን የተጠማው ሁሉ የሚጠጣው ተስፋ የተፈጸመ በመሠረተ ሕይወት ወላዲተ አምላክ ነውና እኛም በሱዋ አማላጅነት ያሰብነው ይፈጸማል ። የጀመርነው ይጨረሳል ስንል ፍቅርና አገልግሎት ማህበር የታኅሣሥ ኪዳነ ምሕረት ፲፱፻፲፰ ዓ ም ተመሠረተ ። ከዚያ ቀን ጀምሮ እስከ ዛሬ በመንግሥት ትእዛዝ የሄዱት ወንድሞቻችንና በአለ ማዕርግ ጌቶቻችንም በማናቸውም ነገር መሰናከልና በሞት ጥፋት አልደረሰብንም ። እኛም ፍቅር አድነትን ዋጋ ሳያወጣ የሚገዛ ሁሉ ከዕንቍ የከበረ ፍሬ ልጅነትን ያገኘንበት ቀን ስለ ሆነ እናከብረዋለን ። የፍቅር ንጉሥም ምስጋና እንዲገዛት አገራችንን ደጅዋን ከፍተን እንጠብቃለን ። ኤ ፌ ም ፭ ቁ ፩ ተመሰሉ በእግዚአብሔር ከመ ውሉድ ፍቁራን ወሑሩ በተፋቅሮ ከመ አፍቀረክሙ ክርስቶስ ። የፍቅር መሠረት ጌታችን ራሱን መሥዋዕተ ቍርባን አድርጎ ስለኛ እንዳቀረበልን እኛም በፍቅር መሠላል ብርሃን ስንወጣ ስንወርድ ጊዜ ባህርየ መለኮት በሥጋ ገመድ መጐተቱን እንመልከትና ዋጋ በማናወጣበት ድካም በሌለበት ፍቅር እንገዛ ።

ቸር ለማኝ ለሕዝብ የሆኑ ግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱን ትጉሕ የማያንቀላፉ እረኛችንን ልዑል ተፈሪ መኰንን ያኑርልን ማህበራችንም በፍቅር ጋሻ መከታ ባንድነት ልብ ተመሥርታ የአገራችንም ፍሬ ከልጆቿ እጅ እንዳይወጣ ያድርግልን ። ክቡር ሐኪም ሆይ ፍጹም ልብ በማህበር ዘርተን እንደስምዎ በሥራዎ ላይ ወርቅ ፍሬውን ለመልቀም ያብቃን ። መሠረት ሃይማኖት ፍቅር አንድነትን ፍሬ ጽዋዕ ሕይወትን እንጠጣለን

ደስታ ደርሰህ ።

ክቡር የፍቅር አገልግሎት ፣

ናፋቂ ሐኪም ወርቅነህ ሆይ ለኢትዮጵያ በፍቅር አገልግሎት የሚመሩን የትሁትነት መልካም ሥራዎ እንደ ሐዋርያ መልእክት ሁነው አገራችንን ኢትዮጵያን በዕውቀት ፍሬዎች ሁላችንንም በፍቅር በስምምነት ሥራ ባንድ ልብ ሁነን መንግሥታችንን እንድናገለግል የቅንነት ምክርዎ ይመስክራል።ስለዚሁም ይህ የደግነት ሥራዎ እግዚአብሔርን በመፍራት ስለተጀመረ ንግግሮችዎ በግልጽ ልባችንን ወደ መልካም መንገድ ይስበናል።እንዲሁም የሰማይን ንጉሥ በመልካም ምግባር ሥራ የሚያገለግል ሰው ሁሉ የምድርንም ንጉሥ በሥራው የሚፈራ ነው።በውነት ለእግዚአብሔርና ላገሩ ክብር የሚሆን እርሱ ነው።ነገር ግን የሰማይን ንጉሥ በምግባሩና በሥራው የማይፈራ ግፈኛ ሰው የምድርንም ንጉሥ በፉ እንጂ በልቡ አይፈራም። እርሱ ግን የግፍና የተንኮል ከፍተኛ ነው።

መቸውንም አገርን መውደድ አፋአዊ ሆኖ ከልብ ርቆ አይደለም በፍቅር በተመሠረተ ልብ አንድ ሆኖ መረዳዳት ነው እንጂ፤የብርሃን መሪ ግርማዊት ንግሥታችን የሰላም ጠባቂ ልዑል አልጋ ወራሻችን በሰየሙት በሁለቱ ስም ኢትዮጵያ እስከ ዘለዓለም ትጽና ብለን ጽዋችንን እንጠጣለን ።

ኤፍሬም ወ ያሬድ ወ ።

ስለ ሞያሌ አደጋ ።

ሞያሌ የሚባል ትንንሽ ቁንጫ የሚመስል በሞቃት አገር ሁሉ በእግርና በጥፍር ውስጥ እየሰረሰረ ያ፩ ሳንቲም ሩብ ያህል ይገባና እንደ ዓተር ተድበልብሉ እንደክርታስ ሀተሸፈነ ከረጅ ውስጥ እንቁላል ይሰራል ። ይኸውም በየገባበት አግድሞ ያለውን አካላት ሁሉ ያሳክክል ንብ ነድፎ መርዙ ሳይነቀል እንደ ቀረም ያደርጋል ። ድብልብሉን የሞያሌ ከረጅ በእሾህ ሰርስሮ በትዕግሥት ቀስ ብሉ ያወጡት እንደሆነ በከረጅው ውስጥ ተቋጥሮ የሚገኘው እንቁላል ከ፶ የሚያንስ አይመስለኝም ። ለመሰር ሰሩ ትዕግሥት ያላደረገ ግን ጫፉን የዘነጠለው እንደሆነ ግማሹ ይወጣና ጥቂቱ እንቁላል ከነከረጅው ከውስጡ ሲቀር ወዲያው በጥቂት ቀን በየጐኑ ብዙ የእንቁላል ከረጅ ተክቶ ይገኛል ። ይህነኑም ፩ ፩ ሰው በቀን በቀን ከ፡ ፫ ያነሰ ሳያወጣ አይውልም ። ደግሞም ወዲያው በዚሁ በወጣበት ቁስልና በሌላውም ውስጥ ሳይታወቁ ሰርስረው ይገባሉ ይኸውም ሞያሌ መላልሶ የገባበት ቁስል መዘንጠልና ዝምብም ሲያስፋፋው ጫዌ የሚባል የቆላ ቁስል ይሆናል ። በ፩ዱ ሰው ላይ የቆላ ቁስል ሲሆን በት ያንን ዝምብ እየቀሰመ ለቤቶቹ ሰዎችና ለጐረቤቶቹ ሲያጋባ ብዙዎችን የቆላ ቁስል የሚባል ይሆንባቸዋል ። በዚሁ ምክንያት ብዙ ሰዎች ሥራቸውን ፈተው ይህንኑ ሲታመሙ አየሁ። ቁስሉም እየጠዘጠዘና እያብላላ ሌትም ቀንም ጤና ያሳጣቸዋል ይልቁንም የጉዳቱን ኃይል በማይችሉት በሕጻናቱ ይብሳል ። ይኸውም ሞያሌ እንደዚህ እያደረገ የሰውን ጤንነት ሁሉ ማወኩን ከሰማን ብዙ ቀን ይመስለኛል ። አዲስ አበባም በብዙ ቀን ፩ ፩ እግራችን ውስጥ እየገባ እናወጣዋለን። ይሁን እንጂ ከዚህ ያለን ሰዎች ትልቅ ጉዳት መሆኑን የታሰበን አይመስለኝም ።

ዘንድሮ ካለፈው ነሐሴ ጀምሬ ዘመዶቼ ወዳሉበት ወደ አንድ ክፍል ሞቃት አገር ውስጥ ሄጄ ፫ወር ያህል ብቆይ የሞያሌ አደጋ በጣም የሚጐዳ መሆኑን ተረዳሁት ። አገባቡና አጐዳዱ ሁሉ እላይ ከመለከትኩት ይልቅ ብዙዎች አብዝተው ያውቁት ይሆናል ። እኔም በዚያ አገር ያሉትን ሰዎች ይኸ ሞያሌ የሚባል አደጋ በዚህ አገር ከመጣ ስንት ዘመን ይሆነዋል ። የመጣበትንስ ምክንያት ታውቁታላችሁን ብዬ ብጠይቃቸው በዚህ አገር ከመጣ ፳ኛ ዓመቱ ነው አስቀድሞ ግን በየዳር አገር መነዛቱን ወሬ እንሰማ ነበር ። የመጣበትንና የሚያድነውን መድኃኒት እኛ አላወቅነውምና አንተ አዲስ አበባ ስትወጣ የሚቻላቸው ቢሆን ብልሆችን ጠይቀህ አስታውቀን አሉኝ እኔም እሺ የመጣበትን ምክንያትና ለመልቀቂያውም ጊዜ እንዳለው የሚያሽልም አብነት ቢኖረው ብርሃንና ሰላም የሚባል የማይሰለች መላክተኛ አለና በየብልሆች ዘንድ እሱን ልኬ የምሰማውን መልስ አስታውቃችኋለሁ አልኳቸው ። ክቡራን የብርሃንና ሰላም ወዳጆች ይልቅም ሐኪሞች በሞቃት አገር ለሚኖሩ ወንድሞቻችን ሁሉ ከሞያሌ አደጋ የሚድኑበትን እርዳታችሁን ተግታችሁ እንድታስቡላቸው አስታውሳችኋለሁ ።

ተፈራ ይፍሩ ።

ማሰብ መናገር መሥራት ።

ያለፈ የያዝነው የመጭ ዘመን ታሪክ ።

ትልቅነትና ትንሽነት ።

ፈረንጆች ሲተርቱ የሚአብለጨልጭ ሁሉ ወርቅ አይደለም ይላሉ ። እነሱ የወርቅን ጣም የወርቅን ዓይነት ስላወቁት ማንኛውም ነገር እንደወርቅ ስለተብለጨለጨ በመልኩ ማማር የወርቅ ባሕርይ የሌለው ነገር ሁሉ የወርቅን ክብር እንዳያገኝ ፍሬ ያለውን ንግግር ሰምና ክር አርገው ተናገሩት ። እውነት ንግግር በምሳሌ ሲነገር ለሰሚውም ለተናጋሪውም እጅግ ደስ ይላል ። ነገር ግን መልካም ምግብ የምግብን ጣዕም ለማያውቅ ሰው ቢሰጡት ይህ መልካም ምግብ ከንቱ ሆኖ መቅረቱ ውልውል የለውም እንደዚሁም ሁሉ መልካምን ነገር የመልካምን ነገር ጣም ለማያውቅ ሰው ቢሰጡት ይህን በመሰለ ሰው አሳብ ይህ መልካም ነገር ዋጋ አለማግኘቱ ውልውል የለውም ። ሥጋችን ምግብ ይፈልጋል ግን የሥጋችን ምግብ መጀመሪያ ሊበላ የተገባ ሁለተኛ ሥጋን የሚአፋፋ ሶስተኛ በንጹሕ የተሠራ መሆን የግድ የሚአስፈልግ ነው ። ሰው አፈር ሆኖ ሥጋ ብቻ አይደለም ዘለዓለም ሕያው ሆኖ የምትኖር ነፍስ ደግሞ አለችው ። ሥጋ ፈራሽ ነፍስ ዘለዓለም ነዋሪ ከሆነች ከስጋ ጥቅም የነፍስ ጥቅም የሚበልጥ መሆኑ ውልውል ስለሌለው የነፍሳችንን ጥቅም አጥብቀን መመራመር ከሁሉ የሚበልጥ ጥቅም ያለው ሥራችን ነው ። ነፍሳችን ረቂቅ የማትታይ የማትጨበጥ መንፈስ ስለሆነች እንደ ሥጋችን ግብዝ መኖ አትመገብም እርሱዋ ምግብ እንደሱዋ መሠረቱ የማይፈርስ ፍሬው የማይጎድፍ ዘለዓለም አብሮአት የሚኖር መልካም ሥራ ብቻ ነው ። ነገር ግን መላሳችን የምናስበውን ሁሉ አከናውኖ ለመናገር የማይችል ስለሆነ ነፍስ በሥጋ ሥጋ በነፍስ እንዴት እንዴት ያለ አገባብ እንዳላቸው መናገር አንችልም ። ያቅማችንንም እንዳን ሞክረው ይህንን የመሰለ አሳብ ለጊዜው መናገር አያስፈልገንም ።

ሰውን ከንስሳ ፈጽሞ የሚለይ ፩ይነተኛ ፀሀሬው ክፉና በጎን ለይቶ ማወቅና አለማወቅ አላዚያም ሰው ነፍስ አለው እንስሳ ግን ደመ ነፍስ ነው እንላለን ። ሰው ክፉና በጎን ለይቶ ያውቃል አለዚያም ሰው ነፍስ ያለው ፍጥረት ነው እንስሳ ግን ክፉና በጎን አይለይም አለዚያም ደመነፍስ ነው ስንል እንስሳን የተዋረደ ፍጥረት ያደረግንበት ክፉና በጎን ባለመለየቱ ወይም ደመነፍስ በመሆኑ እየሆነ የሰው ልጆች ክፉና በጎን ለይተን እናውቃለን እያልን በጎ ነገር የምንለው በክፉ ነገር እጠገብ ፈጽሞ አቅመ ትንሽ መሆኑን እያወቅን ስለምን ይሆን። ሁላችንም አንድ አካል አንድ አምሳል ሆነን ልንሠራ የሚገባንን ነገር ሥራችን እንዳልሆነ ነገር ሁሉ ችላ እያልን የምንተወው ። እግዚአብሔር መልካም ነገር ብቻ ፈጠረ እንጂ መጥፎን ነገር ከቶ አንድም አልፈጠረም ። ግን የሰው ልጆች ልባችን ትልቅ እውቀታችን ትንሽ ስለሆነ የተሰጠኝን መልካም ነገር ሁሉ በሚገባ እያዘጋጁ ጥቅሙንም ሆነ ፍሬውን መውሰድ ስለአቃተን ከሺህ ዘጠኝ መቶ የሚሆነውን ነገር መጥፎ ነው ብለነው ቁጭ አልን ፣ አባቶቻችን ሲተርቱ ሞኝ ከሚአመሰግን ብልህ

ቢሳደብ ይሻላል ይላሉ ፤ እንደዚሁም ሁሉ እኛ በዚህ ዓለም የምናየውን ነገር ሁሉ አገባቡን አሠራሩን ያወቅንበትን እየሠሬ፤ አገባቡንና አሠራሩን ያላወቅነውን ነገር ለምን እንደሚሰጅና እንደምን እንደሚሠራ ብልሀቱን መፈለግ መመርመር ብቻ ነው እንጅ ያለብን ልንነቅፍ የበቃ እውቀት የለንም ፤

ባለፈው ብርሃንና ሰላም እንደጻፍኩት የሰው ልጅ ተብሎ በመንፈሳዊም ሆነ በሥጋዊ መንገድ ለሚኖር ሰው የስስት መንፈስ የሌለበት ይገኝ አይመስለኝም ስስት ማለት ደግሞ የክፋት የኀጢአት ሁሉ ምንጭ ወይንም እናት ማለት ነው ፤ ሰው ክልስስተ በሰው አይቀናም በሰው ካልቀና በሰው ክፉ ለመሥራት አያስብም ፤ ሰው ደግሞ ከመሰሰት ከመቅናት የሚከለከለውን ትምህርት ለማግኘት በዚች ዓለም የሚኖርበት እድሜው ፈጽሞ ትንሽ ሲለሆነች ማወቅ ነው ይህም እጅግ የሚአሳዝን ነገር ነው ፤ ይህም ስለሆነ የሰውን ልጅ አኑዋዋር ታሪክ እየመረመሩ ከአሳብ ጋራ ሲጫወቱ ልማድ የሚሉ ነገር የጥበብ ምን ያህል እንቅፋቱአ መሆኑን እየተረዱ ብዙህም ያሳዝናል ልማድ ማለት ሐሰት የክፋት ጋሻ ማሰብ ማለት የመልካም ነገር ሁሉ ጋሻ መሆኑን ያስመሰክራል ። የክፉና የበጎም ሆነ የማንኛውም ዓይነት ጥበብ ትምሕርት ባልሰፋበት አገር ብቻ አይዶለም ይህን ዓይነት ትምሕርት በሰፋበት አገርም ቢሆን እንደ ህዝቡ ስልጣኔ መጠን ልማድ የጥበብ እንቅፋት መሆኑ ልብ እያደረገ ለመረመረው ሰው ግልጽ ነው ። በአውሮፓ ከታላቁ ጦርነት ወዲህ በጣሙ ከልማድ ጥቅምን ማመልከት ወደዋልም ይሠራሉም ። አውሮፖች ከስልጣኔ ደረጃ እስልጣኔ ደረጃ ሲዘሉ ከግል ጥቅም እማሕበር ጥቅም ከማህበር ጥቅም እጠቅላላ ፍጥረት ዓለም እመመልከት እንደደረሱ እንደዚሁም ልማድ የውነት መንገድ ስከላ እንቅፋት መሆኑአን አሳምረው ስለ ተረዱ በልማድ የሚኖሩ እንስሳ እንጂ የሰው ልጅ በልማድ ለመኖር አይገባውም በማለት ለሰው ልጅ እንደ ዘመኑ ስልጣኔ መጠን በሚገባ የጠበቀ ሕግ እንዲኖር ሐሳባቸው በያለበት ሥራውን ወጥኑአል ።

የሰው ልጅ ልበ ትልቅ እውቀት ትንሽ ልቡ መልካም እየተመኘ እውቀቱን ግን የልቡን አሳብ አያስፈጽመውም ስለዚህ መልካም አሳብ አስቦ የአሳቡ ኃይል እውቀቱ ስለሆነ የድኩም እውቀቱ ከመከራ ጉድጓድ ይጨምረውና ቢድን ከዚያ ወጥቶ ትንሽ ከፍ ወዳለ ደረጃ ይወጣል አለዚያም የሱን ሞት ያይ የነበረ መስሉ እንደሱ እንዳልወድቅ ሲል የተሻለ መንገድ ይይዛል ። ይህን በመሳሰለ ምክንያት ሰው ከትምህርት ይልቅ መከራን በማየት ዕለት ዕለት ከክፉ ወደ በጎ እየተጠጋ ይሄዳል ። ይህንም ልብ ብለው ሲመለከቱት የሰው ልጅ ከድንቁርና ማለት ከግፍ ሥራ መሥራት ወደ ፍርድ ሥራ ለመሥራት አሳቡ በብዙ እየተሻሻለ መሄዱን ያለፈ ዘመን ታሪክ ያሳየናል ። እንደ ምልክት ከብዙ ዘመን በፊት በአውሮፓ የጋብቻ አኳሆን አለመጠን ይደንቅ ነበር ማለት የበታች የሆነ ሰው ሚስት ባገባ ጊዜ የልጅቱአን ክብርና የሚገስ በማንኛውም መንገድ ቢሆን ያገቢው ሰው አለቃ ነበር ። በወታደር በነጋዴ በገበሬ በቀሳውስት በሴት መነኰሳቶች በኩል የዚህ ሥራ እንደምን ይሠራ እንደ ነበር ዝርዝሩን ሲመለከቱት አለመጠን ይደንቃል። ይህንም በመሰለ መንገድ ሰው ብዙህ መጥፎ አመሉን እያሻሻለ በመሄዱ ብዙ ደስ ያሰኛል ። ያለፈው ቀርቶ ዛሬ በዘመናችን እየርስበራሳችን የምንሠራራውን ልብ ብለው ሲመለከቱት ስንት የሚአሳዝን ነገር አለ ። ብቻ የሆነው ሆኖ ለሰው ልጅ አመል ማሻሻል ምንም መከራ የግድ የሚአስፈልገው ስለሆነይህም መከራ እንደምንም ብሎ ሳይመጣ የሚቀር ነገር ስለሆነ የሰው ልጅ መከራ ቁጥሩም ያነሰ መራራ ወይም ከበድነቱ የቀለለ እየሆነ እንዲሄድ ሁላችንም በየበኩላችን ፈራሄ እግዚአብሔር እያደረብን በልባችን ውስጥ የዳኘነትን ነገር መሠራት በአሳባችን ውስጥ እውነት ለውነት መልካምን ለመልካም ደግነትን ስለ ደግነት ይህን የመሳሰለውን ሁሉ እንደምንችል እየሠራን ለመሥራት ያልቻልነውን ለመሥራት ብንፈልግ ታላላቆች ፈላስፋኖች እንደሚሉት የሰውን አመል ለማወቅ ያንተን አስቀድመህ ሳታውቅ አትመኝ ነውና ስለዚህ ሁላችንም በየበኩላችን ሰውነታችንን መመር መርና ማራቅ ከቻልን እጅግ እንጠቀማለን ።

በአፉሆሙ ይድኅኑ ወበልበሙ ይረግሙ እንዳለ ቅዱስ ዳዊት የምንናገረውም ሆን የምንሰማው እውነትን ነገር ልባችን እያወቀ ግን በክፋት ወይም በደካማነት በልባችን የተረዳ ነውን ነገር በትጋትና በድፍረት በጥንካሬ ባንሠራው ጉዳት ለማነው ዞሮ ለኛው ነው ቢሠራስ ጥቅሙ ለማነው ዞሮ ለኛው ነው ። ነገር ግን ማንምሰው ቢሆን እውቀቱ እጅግ ድኩም እየሆነበት ነው እንጅ መልካምን ነገር ለመሥራት የሚጠላ ሰው ምንም ቢሆን አይገኝም። መጥፎ ሁን ቢሉት ማን ይወዳል ቆንጆ ሁንስ ቢሉት ማንይጠላል ነገር ግን ያለዕድል ማንኛውም ነገር አይሆንምና ምን ይደረግ ።

በመጀመሪያው ገጽ ስለነፍስና ስጋ ትንሽ የተናገርኩም በኃይማኖት መንገድ ብቻ አይዶለም በጠቅላላው ስለሰው ልጅ ጥቅም ነው እንጅ ። እግዚአብሔር ወሰን በሌለው ደግነቱ የምናይ የምንሰማ የምናስብ የምንናገር የምንሠራም አርጎ አሳምሮ ፈጠረን ። እጅግ የሚደንቅ ነገር ደግሞ የምናደርገውን ነገር ሁሉ መልካም ነው መጥፎ ነው ብለን የምንመዘዝንበት ኃይል ያለው ረቂቅ ምስጢር ሰጥቶናል ። ይህን የመሳሰለ ነገር እየለየን የምናውቅ ሰዎች ምንም የማናውቅ መስለን ዝም ብንል ፍጥረታችንን ማዋረድ ማስናቅ ነው ። ከዚህ በፊት በብዙ ዓይነት አሳብ እየለዋወጥኩ እንደ ተናገርኩት የሰውን ልጅ የሚአስከብርና የሚአዋርድ መልካምና መጥፎ ሥራ ነው ። መልካም ሥራ እውነትነት ያለው ነገር ነው መጥፎም ሥራ ሐሰትነት ያለው ነገር ነው ይህ እንግዲህ የማይሻር የማይፈርስ ነገር ነው ። እንዲህም ከሆነ የሰው ልጅ ክብሩን መፈለግ የግድ የተገባው ነገር ነው ። ግን የሰው ልጅ ክብሩ መልካም ሥራ ነው የቀረው ከንቱ ነው ። ንጉሥ ጳጳስ ጌታ ድኃ ወታደር ገበሬ ቢሆኑ ይህ ሁሉ እንደ ጥላ ከንቱ እየሆነ ሐላፊ ነው ። የዚህ ሁሉ ነገር ማሰሪያው እኛ የኢትዮጵያ ልጆች በማንኛውም ነገር የምታስከብር አገር ይዘን የምንከበርበት አገር የሌለን ሰዎች እንምሰል ማለት ነው ።

ልሳነ ወርቅ

የከተማ ወሬ ፤

ስለ ዘበኞች ትጋት ፤

በከተማ ውስጥ ሌቦች እንደ ዘበኞች ኮት ለብሰው መለዮ አድርገው እየሰረቁና አቍስለው እየቀሙ በጣም አስቸግረው ነበር ፤ ሌቦቹና ተቀብለው ዕቃ ያስቀምጡላቸው የነበሩ ሰዎች በዘበኞች ብርታት ተይዘው በብዙ ምርመራ ኃጢአታቸውን አምነው በታኅሣሥ ፲፩ ቀን እችሎት ቀርበው እንደ ኃጢአታቸው እየታየ ተፈረደባቸው ። የተያዙት ፲ ናቸው ከነዚሁ ፫ቱ የሞት ፍርድ ተፈርዶባቸው ሞቱ አምስቱ ተገርፈው ታስረዋል።

ማመልከቻ ፤

አንድ ሰው ስለ ፍቅርና አገልግሎት ማኅበር የምክር ቃል ስሙን ሳይጽፍ ላከልን ምንም እንኳ ስሙ በጋዜጣ ተጽፎ እንዲወጣ ባይፈልግ ሐላፊነቱን የሚያስታውቅ ደብዳቤ ወደ ጋዜጣው ዲሬክተር ፈርሞ እንዲሰጥ ያስፈልገው ነበር አሁንም ይህ ስለ ፍቅርና አገልግሎት የጻፈ ሰው ማን መሆኑ እስኪያስ ታውቀን ድረስ የጻፈውን ቃል አቈይተነዋል ስሙን ጽፎ ባስ ታወቀን ጊዜ ይታተማል ።

በጋዜጣ ስለመጻፍ ማስታወቂያ ።

ክቡራን የኢትዮጵያ ልጆች የአገራችሁን ደህንነትና ሰላም የምትሹ ከዚህ ቀደም በዚሁ ጋዜጣ ትጽፉ የነበራችሁ አሁንም በምንም በምንም ብሎ አገራችሁን የሚጠቅም ነገር ከጋዜጣው የሚገባ ከመጻፍ እንዳትቦዝኑ በማክበር እናስታውቃችኋለን ። በደገኛ አሳብ ስለ አገሩ እውነተኛ ጠቀሜታ አንዳች የሚናገር ወይም የሚጽፍ ወይም ደግሞ የአቅሙን ያህል ትንሽም ስራ የሚሠራ ሰው በእግዚአብሔር ፊት ትመሰገን ለታለች ። በርሱም እያንዳንዱን እንደስራው መጠን ደመወዝን በሚሰጥ ዋጋውን ሳያገኝ አይቀርም ።

ስለ መሐመድ ዓሊ ዕረፍት ።

ሞላ ሙሐመድ ዓሊ ዓብድልሑሴን ራሱልጂ በታሕሣሥ ፳፫ ቀን በተወለዱ በ፶፪ ዓመታቸው ዓረፉ ።

ብርሃንና ሰላም ለሙሐመድ ዓሊ ዘመዶችና ወዳጆች ሁሉ እግዚአብሔር ያጥናችሁ ይላል ።

ማስታወቂያ ፤

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
ደግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፫ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር	፱ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ	፩ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጤ	፩ሩብ
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ብር
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሚው	፪ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ተኩል
የቁጥር ትምርት	፩ብር
ያማሪኛ ሰዋስው	፭ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	አላድ
ወዳጄ ልቤ	፫ሩብ
አጭር የዓለም ታሪክ	አላድ
ያማሪኛ ፊደል	ሩብ
አሳብና ምኞት	ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት	ሩብ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር	፪መ

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፱ ብር ከ፫ ሩብ
የሲዳሞ ቡና	፩	፰ ብር ከ፫ ሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፪ ብር ከ፫ሩብ
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፪ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺ ብር ።
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፰ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፱ ብር ተኩል
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፰ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፵፩ ብር
። ባለሰይጣን	።	፻፵ ብር
። ባለ ድመት ።		፻፵፪ ብር ።
። ባለአህያ	።	፻፳፫ ብር
። ባለሳቢ ግመል	።	፻፴፫ ብር
ባለ አንበሳ	።	፻፵፫ ብር ።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፳፲ ብር ።
ቻይ	፩ ነጥር	፲፪ መ

ስለ ምንዛሪ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ ከ፴ ሳንቲ
አንድ ብር	ሊሬ
ባንድ ጊኒ	፲ ብር ከ፺ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፬ ብር

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ፡፡

COGNAC S. E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት አሜጋ የሚባል ባለአንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

ሺብሮሌ አቶሞቢል ።
በኢትዮጵያ ወኪል ።
ሐ ሜ ዜርቦስ ኩምፓንያ ።

Automobiles CHEVROLET
AGENTS
H. M. ZERVOS & Cie.

ሩግቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

“ሩግቢ” የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያየዚህአቶመቢልበተለይወኪል“አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ”ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

RUGBY

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፥ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፥ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል ።



ማስታወቂያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጅ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልካም ባርኔጣ ፣ ሸቱ ፣ ለስዮን ፣ አድከሎኝ ፣ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፣ ክኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፣ ከፊይ ምንጣፍ ፣ ደግሞ በያይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስመጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሸምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክታችኋለሁ ፤ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ዓለም

ዓለም የወርቅ ጥልፍ ሥራ ሁሉ በውስጠ ብር ሆኖ ይሠራል ።

ኒኮላ ።

ማመልከቻ ።

በብርሃንና ሰላም ውስጥ ማስታወቂያ ማሳተም የሚፈልጉ ነጋዴዎች እስከ ፈለጉት ጊዜ ድረስ ባማርኛም ሆነ በፈረንጅ ቋንቋ በርካሽ ዋጋ እንደምናትምላቸው እናስታውቃቸዋለን

ጉድይር ግዙ



ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው በሌላጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ፤ ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አራተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፪
4 me ANNÉE № 2

ሐሙስ ጥር ፫ ቀን ፲፱፻፳ ዓ ም ።
JEUDI 12 Janvier 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ስፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ልደት በዓል አከባበር ።

ታኅሣሥ ፳፱ ቀን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የልደቱ በዓል ተከበረ ። በዚሁ ቀን ወደ ማታ የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ልጆች ብዙ ሕፃናት ከወላጆቻቸው ጋራ አብረዋቸው በደስታ እንዲያመሹ ጠርተው ነበር ። የልዑል አልጋ ወራሽ ግቢም ስለ ልደት በዓል ክብር በልዩ ልዩ ዓይነት ጌጥና መብራት ተጊጦ ከቤት ውስጥም የገና ዛፍ ተተክሎ በኤሌክትሪክ ተበርቶ ነበር ። አሥር ሰዓት ሲሆን የተጠሩት የኢትዮጵያ ወይዛዝርና መኳንንት የውጭ አገር ሰዎችም ከልጆቻቸው ጋራ አምሮ በተሰናዳው ድንኳን ገብተው ተቀመጡ ።

ከዚህ በኋላ የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ትምሕርት ቤት ተማሪዎች ሰልፋቸውን አሳምረው ገብተው ቴአትር ሊደረግበት አምሮ በተሰናዳው ስፍራ በልዑልና በልዕልት በወይዛዝርና በመኳንንት ፊት የልደት መዝሙር ዘምረው የቴአትርን ጨዋታ አሳምረው አሳዩ ። የጨዋታውም አኳሆን ቀጥሎ እንደ ተጻፈው ነው ።

የቲያትሩን ጨዋታ ባጭሩ የሚያስረዳ
በጨዋታው ውስጥ ያሉ ሰዎች

፩ደኛ የቬኒስ ከተማ ዱክ (ዳኛ) ።
፪ተኛ አንቶኒዮ የቬኒስ ከተማ ነጋዴ
፫ተኛ ባሳንዮ ፤ የፖርቲዮ ጮኛ የሆነ የአንቶንዮ ወዳጅ
፬ተኛ ግራቲያኖ
፭ተኛ ሣላዮኒ — የአንቶኒዮና የባሳንዮ ወዳጆች
፮ተኛ ሣላሪኖ
፯ተኛ ሻይሎክ ፤ እስራኤላዊ
፰ተኛ ቱባል ፤ የሻይሎክ ወዳጅ እስራኤላዊ
፱ኛ ፓርቲዮ ሐብታም ሴት
፲ረኛ ኔሪሳ የፓርያ ገረድ
፲፩ኛ ያደባበይ መኳንንት ፤ የፖርቲዮ አሽከሮችና ፤ አጋፋሪ ሌላም ሠራዊት ።

ስለ አንድ የቬኒስ ከተማ ነጋዴ——— የጨዋታው አኳኋን ባጭሩ

መጀመሪያ ጨዋታ ።

አንቶኒዮ ገና ወደፊት የሚገጥመውን ድንገተኛ አደጋ አስመልክቶት በሐዘን ተኵራምቶ የመርከቡን ነገር እያወጣ እያወረደ ሲተክዝ ሁለት የንግድ ጓደኞቹ ሲያጽናኑት ባሳንዮ ወዲያው ከመካከላቸው ከተፍ ይላል ። አመጣጡም ከአንቶን ከወዳጁ ገንዘብ ተበድሮ በቤልሞን ከተማ ፓርቲያን ከሌላ እጮኞቿ አስጥሎ ፤ በገንዘብ አባብሎ አብሯት ለመኰብለል ነው ። አንቶኒዮ መርከብም ገዝቶ በተረፈው ገንዘቡ ሼቀጥም ለንግድ ስለላከ ፤ ለጊዜው መርከቡ እስኪመለስ የሚያበድረው ገንዘብ በማጣቱ ፤ ከየዋህነት የተነሣ ወዳጁን ደስ ሊያሰኝ ሻሎክ ከሚባል እስራኤላዊ ወዳጁ የተቸገረበትን ያህል ገንዘብ ተበድሮ ሊሰጠው ይነጋገራል ።

እስራኤላዊው ከወገኑ በቀር ክርስቲያን የሆነን ሁሉ ለማጥፋት ይጥር ነበርና ቂሙን የሚያርስበት ወጥመድ ይፈልጋል ፫ትሺህ ብር (ዱካትስ) እስከ ፫ት ወር የሚመለስ ለአንቶንዮ ሲያበድረው ፤ በዚያው በተወሰነው ጊዜ ገንዘቡን ሳይከፍል ቢቀር ፤ ከጭኑ አንድ ንጥር ሥጋ ቆርጦ ሊወስድ ነው ውለታው ። አንቶንዮም ከተቈረጠው ጊዜ በፊት መርከቡ የሸቀጡን ሽያጭ እንዲያመጣለት አውቆ የወዳጁን ችግር ለመምላት ሲል በፍጥነት ፈርሞ ገንዘቡን ይወስዳል ። ነገር ግን ይህ ሁሉ ሲሆን እስራኤላዊው ቂሙን በልቡ አድርጎ ፤ ምንም ክርስቲያኑን ስለጠላው እንዳይታወቅበት ለወዳጅነት አስመስሎ ገንዘቡን በዚያ በቀኑ ከመለስህ ካንተ ወለድ አልጠይቅም ይለዋል ።

ሁለተኛ ጨዋታ ።

የባሳንዮና የአንቶንዮ ወዳጆች ሣላኒዮና ሣላሪኖ የተባሉ በመጠያየቅ አንዱ ላንዱ የአንቶን መርከብ በባሕር ውስጥ ተሰብሮ መቅረቱን ይነግረዋል ። ለጥቆ ሻሎክ እስራኤላዊው ሲገባ ምን ወሬ አለ ሲል አንዱን ይጠይቀዋል ።ለጥያቄውም መልስ ፤ ሻሎክ ፣ ልጄ ገንዘቤንና የወንድ ጌጥ ይዛ ከሌለሁ በት ኮብለለች ሲሉ ሰማሁ ሌላ ወሬ አላውቅም እያለ ሲጫወት ፤ አንድ ከአንቶን የተላከ አሽከር ፤ ሣላኔዮንና ሣላሪኖን ጠርቶ ይወስዳቸዋል ለጥቆ ቱባል የተባለ እስራኤላዊ የሻሎክ ወዳጅ ሲገባ ሻሎክ የልጁን መገኘትና አለመገኘት ይጠይቀዋል ፣ ቱባል ልጅቱ በሩቅ አገር መኖርዋን ከነገረው በኋላ ፤ ከመርከበኞች አንዱ ከሞት የተረፈው የአንቶንን መርከብ መሰበር ያወራውን ይነግረዋል ። ሻሎክ ይሄን በሰማ ጊዜ ደስታው ተስፋፍቶ ነገሪውን ያመሰግናል ።

ሶስተኛ ጨዋታ።

ሻሎክ ፤ እስራኤላዊ የአቶኒዮ ወዳጅ ሣላሪኖና አጋፋሪው ይገባሉ ሻሎክ ገንዘብ ለአንቶኒዮ ማበደሩን ላጋፋሪው ሲነግረው፤ አንቶኒዮ ፤ ሌላ አትፈልግብኝ እንጅ ደጉ ሻሎክ ገንዘብህን ልክፈል ሲል ይለምነዋል ሻሎክ ግን ምንም ውሌን አፍርሼ እንዳልምር ምያለሁና በውሉ ተቀጣ ሲል አንቶኒዮን ይይዘዋል ፤ ሣላሪኖ ነገሩን ለማብረድና ቅጣቱን ለማስማር ሻሎክን ሲለምነው ምንም ቢሆን ፤ የጭኑን ስጋ ሳልቆርጥ አልተወውም ይላል ። ይሄን ጊዜ አንቶኒዮ በወደቀበት አደጋ እያዘነ ፤ በባስንዮ ይማረራል በመጨረሻው እንደውሉ ከጭኑ ስጋ አላስቆርጥም ስላለ ተከሰው ወደ ዳኛ ይሄዳሉ ።

አራተኛ ጨዋታ ።

በፍርድ ቤት ዳኛው የአንቶኒዮና የባሳንዮ ወዳጅ ጊሬቲያኖ ፤ ሳላሪኖና ማሊሪዮ ፣ ሌሎቹም ያደባባይ መኳንንቶችና ባሳንዮ አንቶኒዮ ይገባሉ፤

ይሄን ጊዜ ሻሎክ አቤቱታውን ለዳኛ ያመለክታል ። ዳኛውም ያገኘውን አደጋ ተመልክተህ ለኔ ስትል ተውልኝ ብሎ ጭንቅ ጥብብ አድርጎ ቢለም ነው ምያለሁና ውሌን አልተውም ይላል አንቶኒዮም በመቆረጡ ስለቆመ በማናቸውም ስለቤቱ ወዳጁን ባሳንዮን አደራ ይለዋል ባሳንዮ ግን እኔ እያለሁ ያንተ ጭን አይቆረጥ ብሎ ጭኑን ለማስቆረጥ ይገለገላል ።

ዳኛውም የሚያደርገው ቢጨንቀው ባላሪዮ ወደ ሚባል ተማጋች (አቦካ) በፍጥነት ድረስ ብሎ ደብዳቤ ይልክል የፖርቲዮ ገረድ ኒሬሳ የወንድ ልብስ ለብሳ የተማጋቹ ጸሐፊ ወረቀት ይዠ የመጣሁ እሰኘች ፓርቲያ የባሳኒዮ እጮኛ የሆነች አንድ ሐብታም ሴት ነች ከጠበቃው ተላከው ወረቀት ውስጥ ፓርቲያ እንዳይል ስምና መልክ አዛውሮ እኔን ስላመመኝ ፣ ባልታዛር የሚባል ምሑር ተማጋች ነገሩን ደህና የተረዳ መጥቷልና ይቀበሉት የሚል ነው ። ልብሷን እንደወንድ ለውጣ ነው እንጅ ። ባልታዛር የተባለው ወንድ የባሳንዮ እጮኛ ፖርቲያ ነች ይሄም ተማጋች በገጠመ ጊዜ ሻሎክ እስራኤላዊ ገንዘቡን አልወስድም ብሎ ይከራከራል ጠበቃው ብልህ ስለሆነ ውሉን አገላበጦ መርምሮ አይቶ አንድ ነጥር ሥጋ ይላል እንጅ ደም አላለምና ስትቆርጥ ደምም ቢፈስ ካንድ ነጥርም አብልጠ ብትቆርጥ በነፍሱ ታልፋለህ እያለ ሲሞግተው እስራኤላዊው መውጫ ቢአጣ ገንዘቤን መልሱልኝና ይጋር ልሂድ ሲል ይጠይቃል ኋላ ግን እስራኤላዊው የከተማ ሰው በንደዚህ ያለ ውል ሰው እንዳይገል የሞት ፍርድ ተቀብሎ ከገንዘቡ እኩሌታው ለአንቶኒዮ ነፍስ ዋጋ ሌላው እኩሌታ ለመንግሥት እንዲገባ ይፈረድበታል ለጥቆ ዳኛው በገንዘቡ ቀጥቶ ሲምረው ይታያል በንደዚህ ያለ ሲለያዩ የወንድ ልብስ ለብሳ ስሟን ለውጣ ጥብቅና የቆመችው ተማጋች የባሳንዮ እጮኛ ፓርቲያ መሆንዋ ንሲያውቁ ሁሉም ገርሟቸው አንድነት ሲሳሳቁ መጋረጃው ሲወድቅ ጨዋታው ይፈጸማል

ከዚህ የምናገኘው ትምሕርት ይህ ነው የሰው ፈላጊ የራሱን ያጣል አሳ ጉርጓሬ ዘንዶ ያወጣል ።

የሞሊዬር ኮሜዲ ፤

የፍልስፍና መምሕርና ሙሴ ዧርደን ፤

ይኸ ሙሴ ዧርደን ዘሩ ከመኰንን ወገን ያልሆነ ከበርቴ ትምሕርት ሳይማር ያደገ ነበር ። ሰውነቱ ከጠናና ገንዘብ ካገኘ ወዲህ እንደ መኰንን ፣መሆንና እውቀትንም ለማግኘት አስቦ ፈላስፋን የሆነ መምሕር ቀጥሮ ከቤቱ ጠርቶ አስተምረኝ አለው ፤ መምሕሩም መጥቶ ምን ለመማር ይፈልጋሉ ብሎ አሳቡን ጠየቀው ። እርሱም አባትና እናቴ በሕጻንነቴ ሳለሁ ጥበብን ሳያስተምሩኝ ቀርተው ብዙ ስለጸጸተኝ የምችለውን ሁሉ ለመማር አስባለሁ ብሎ መለሰለት ። አሳቡም መልካም ነው ፣ በላቲን ቋንቋ ያለ እውቀት ሕይወት የሞት አምሳያ ነው ተብሎ የሚተረከውን ያውቁ የለምን አለው ። አዎን አውቀዋለሁ ይኸም ላቲን እውነቱን ነው ሲል መለሰለት ። ጥቂትስ የጥበብ ጅምር የለዎትም አሁንስ ምን ለመማር ይፈልጋሉ ፣ ሎጂክ ላስተምርዎት ብሎ ቢጠይቀው ። እኔም ጽሕፈትና ማንበብ እውቃለሁ ፣ ይኸችስ ሎጂክ ምንድናት ብሎ መለሰለት ። ይኸችም ሎጂክ ሶስቱን የአንጎል ሕዋሳት ሥራ የምትአስተምር ነች ።

እነዚሁም የሕዋሳት ሥራዎች አንደኛ ሐሳብን በ፣ ክክል በልቡና መፍጠር ሁለተኛው ያሰቡትን በትክክል መርዳት ሶስተኛ ያሰቡትን ተከትሎ የሚሰራውን በትክክል ማስኬድ ነው አለው ፤ እዚህ ውስጥ ብዙ ጭቅጭቅ ነገር አለበት ይኸን አልፈልግም ሌላ ጥቂት የሚሻል እንዳለ አስተምረኝ አለው ።

ደግሞ ሞራልስ ለመማር ይፈልጋሉን ቢለው ይኸች ሞራል ምን ትላለች አለው

ይኸች ሞራል የደግነት ሥራን ትነግራለች ከክፉ ማድረግም መታገሥን ታስተምራለች አለው ።

የለም ይኸንን እንተው እኔ ሞራል አልፈልግም እንዲህ ተሆነ የሚአስቆጣኝና የሚአበሳጭ ነው አለ።

ፊዚክ ነውን ለመማር የሚፈልጉ ብሎ ጠየቀው

ይኸች ፊዚክ ምን ትዘፍናለች አለው ።

ይኸኛ ፊዚክ የስነፍጥረትን ሥራና የአካልን ሥራ የምትአስተምርና የቀስተ ደመናን የጅራታም ኰከብን የሰማይ ተግታን የመብረቅን የዝናምን የበረዶን የነፋስን የአውሎ ነፋስን የምታለመለክተን ነች አለው ።

እዚህ ውስጥ ብዙ ውካታ አለበት ይኸንንም አልፈግልም አለው እንግዲያው ምን ላስተምርዎት ይፈልጋሉ አለው ።

የፊደላትን አጻጻፍ ያስተምሩኝና በኋላ ጨረቃ ያለችበትንና የሌለችበትን ጊዜያት ለማወቅ አልማንያክ ያስተምሩኛል አለው

አስተማሪውም ሐሳብዎን በትክክል ለመመልከትና ወደ እውቀት ደረጃ ለመድረስ ፊደላት በጣም መለየትና ልዩ ልዩ አጠራራቸውን ማወቅ ያስፈልጋል ። ስለዚህም ፊደላት በስድስት በዬልና በክንሰን እንደተከፈሉ አስታውቅዎታለሁ አለው እርሱም ልዩ ልዩ አጠራራቸውን ከተማረ በኋላ አንዲት ትልቅ እመቤት ወድጄ ትንሽ ወረቀት ጽፌ እግሯ ላይ ልጥልላት አስቤአለሁና እንዲአግዙኝ እለምንዎታለሁ የምጽፈውም ቃል ውብ ማርኪዝ ሆይ አይኖችሽ በፍቅር ሊገሉኝ ነው ብዬ ነበር ። ነገር ግን በጣም ያማረ እንዲሆንና የሚአራራ እንዲሆን እፈልጋለሁ ። እሺ ማለፊያ ነው ግን እርሰዎ በግጥም ነው ወይስ በዝርዝር ሊጽፉላት የሚፈቅዱ ብሎ ጠየቀው ። በዝርዝርም በግጥምም አልፈልግ አሁን ያልኩትን ቃል ብቻ አቀማመጡን በትክክል እንዲአደርጉልኝ ነው የምፈልገው አለው ።

ተሁለቱ አንዳቸው ሊሆን በጣም ያስፈልጋል ። ስለምን ቢሉ በትክክል ለመነጋገር ከዝርዝር ንግግርና ከግጥም በቀር ሌላ ስለሌለ ዝርዝር ንግግር ያልሆነው ሁሉ ግጥም ነው ግጥም ያልሆነው ሁሉ ዝርዝር ንግግር ነው አለው ፤

አዬ ፈጣሪዬ ዝርዝር ንግግር እያልኩ ስነጋገር ከአርባ አመት በለጠኝ ምን ማለት እንደሆነ ሳላውቀው አሁንም የኸንኑ ስለአስጠኑኝ አመሰግንዎታለሁ አሁን የነገርኩዎትንም ቃል ልዩ ልዩ አቀማመጡን እንዲነግሩኝ እለምንዎታለሁ ።

ከዚህበኋላ እያዘዋወረ ልዩ ልዩ አቀማመጣቸውን ካሳየው በኋላ ከነዚህ ሁሉ ማናቸው ይሻላል ብሎ ጠየቀው አስተማሪውም እርሰዎ ያሉት ይሻላል አለው ። እርሱም ብዙ ቀን ሳልማር ይኸነን በአንድዬ ተናገርኩት እያለ እራሱን እየአመሰገነ ለነገ እንዳይቀሩብኝ ብሎ ለመነው መምሕሩም እሺ አልቀርም ብሎ ወጥቶ ሄደ ።

አስተማሪውን ሸኝቶ ሲመለስ አንድ ሰፊ ልብስ ሰፋና አምጣልኝ ብሎት ነበርና መምጣት መቅረቱን አሽከሩን ጠየቀ ።

አሽከሩም የለም ጌታዬ አልመጣም አለው ።

ከዚህ በኋላ ሰፊውን ይኸ እርጉም ሰፊ አስቀረብኝ ብዙ ጉዳይ ነበረኝ ምን ሰይጣን የሆነ ሰፊ ያኸ አስቀያሚ ውሻ ይኸ ቀጣፊ አሁን ባአገኘሁት እያለ እያጉረመረመ ወደ ውጪ ወጣ እንደዚሁምበከንቱ ጊዜያቸውን ያሳለፉ ሰዎች በሰው ስለአዩ ነው እንጂ ትምሕርትን እንዳይፈልጓት ቢፈልጓትም የሰው መሳቂያ ለመሆን እንጂ እንዳያገኙዋት ያስረዳናል ።

የዛሬው የኢትዮጵያ መንግሥት ። መኳንንትና ሕዝብ ።

የትምሕርት ፍቅር እንደተሰማው ።

የተማረ ልጅ ፤ እባክህ ጌታየ ወሬ ልጠይቅህ ፣
ሳያንስ ኬምስተሬ ደግሞ ጆግራፊ ምንነው አለማወቅህ ።
ሂሳብ አሪትሜቲክ አልጀብራ ጆሜትሪ አለመመርመርህ ።
ላንተም ብቻ አይደለ ጉዳት ነው ላገርህ
ይህን ሁሉ ነገር ስላለመማርህ
አንተ ተቀምጠህ ለባዕድ ያልፋል ክብርህ ።

ብልህ መኰንን ፤ አረ እውነትህ ነው ነገሩ ገብቶኛል ።
ይህስ ያልከው ነገር በጣም ቆጭቶኛል ።
አለ መማራችን እጅግ ያሳዝናል ፣
ባለመስራታችን ማንም ይንቀናል ።
ስለዚህ ሁላችን ተባብረን ባንድ ቃል ።
ስንፍና ኩራትን አውጥተን እንጣል ።

የተማረ ልጅ ፤ ጌታዬ ዛሬ እርስዎን እንዲህ እንዳጸጸተዎ ፣
በቅጡ ያስረዱት ለመላ ህዝብዎ ።
የርስዎ ጊዜ አልፎዋል በዕድል በሀብትዎ ።
ነገር ግን ያስቡ ለልጅ ልጆችዎ
ጥበብን ይማሩ ዛሬ ሳሉ እርስዎ ፣
እርሱ ያውቃልና አእምሮ ልብዎ

ብልህ መኰንን ፤ እንኳን የኔን ልጆች ሳላስተምር ልቅር
ሴቱንና ወንዱን ሕጻናቱን ባገር
ሁሉንም ሰብስቤ አንድም ልጅ ሳላስቀር
በጣም እጥራለሁ ለትምሕርት ነገር ፣
በዚህ ይገለጻል ንጉሥ መውደድ አገር ።
ኋላም ይቆጠራል ከታላቅ ቁምነገር ።

የተማረ ልጅ ፤ እናንተ ካሰባችሁ በሙሉ ልባችሁ ።
ልታገለግሉ ለውድ አገራችሁ
ጉልበታችሁ ኃያል ሚሊዮን ከብታችሁ
ለሌላም ይተርፋል እንኳን ለልጃችሁ
እንኳን ተማሪ ቤት መርከብ በሰራችሁ ፣
ሁላችሁ ሰትሆኑ ያውም አንዳንዳችሁ ፣

ብልህ መኰንን ፣ እስከ ዛሬም ድረስ ዝም ማለታችን ።
ስንፈክክር ነው አንዳችን ከአንዳችን ።
አሁን ግን ጸጽቶን ይኸው ስንፍናችን ።
ለትምሕርት ነገር ተነሣን ሁላችን ።
ለዚህ የማይረዳ ከመካከላችን ።
ባላጋራ ሆነው ለነጻነታችን ።

የተማረ ልጅ ፤ እንዲህ ካሰባችሁ እላንት መኳንንቶች ።
የትም ተከፈቱ የተማሪ ቤቶች ።
በጥበብ ያድጋሉ ብዙ ሕፃናቶች ።
በፈተናም ጊዜ ተመርጠው አዋቆች ።
ዩንቤርሲቴ ሄደው ይበላሉ ሊቆች ።
ስማቸው ይጠራል የኢትዮጵያ ጌቶች ።

ብልህ መኰንን ፤ አሁን አንተ ከኛ በጣም ሕፃን ነህ ።
ከዋቂ ይበልጣል ጥልቁ አሳብህ ።
ለመንግሥትህና ለውድ አገርህ ።
በጣም ትረዳለሁ ስለመማርህ ።
እንዴህ አናገረህ መልካሙ እውቀትህ ።
ባይደረግ እንኳ ከንተ ወጣልህ ።
ብዙ አስረድተሃል ጸጸትም የለህ ።
ቶሎ አልሆነ ብለህ ወንድሜ አይከፋህ ።

ነገርህን ሁሉ ሰው እስቲቀበልህ ።
ቸልታ አታግባበት ለማስታወስህ ።
ገልጸህ ብትናገር ለአገርህና ለወንድሞችህ ።
ኋላ ይወዱሃል ዛሬ ቢጠሉህ።
የተማረ ልጅ ፤ እንኳን እርስዎ እንዲህ እያጸናኑኝ ፡ ዱሮውን
ላገሬ ይሉኝታም የለኝ።ሁሉን እነግራለሁ እንደሚመስለኝ
ባገሬ ላለግም ግዝት አለብኝ
እርስዎ እንዲህ አሁንቢያመሰግኑኝ ።
ሰነፎች ግን አሉ የሚቀየሙኝ ።
ብልህ መኰንን ፤ ማንም አይቀየም እውነት ብትናገር ፡
መርዳት ይገባናል ሁላችንም ላገር
በስንፍና ብዛት ሳይደረግ ቢቀር
ቆይቶ ይቆጨናል ወደ ኋላ ስንቀር
የኢትዮጵያ ሰዎች እንዲህ ስንፋቀር ።
በልጆች ቅናትን ይዘን እንዳንቀር ።
ሊቀ ፤ ትንሽ ልውቀሳችሁ እናንተ መኳንንቶች ።
ዛሬ ለልጃችሁ የምታደርጉት ።
በመብል በመጠጥ በሳቅ በጨዋታ ማሳደግ ከቤት ።
ጥቂትም ከፍ ሲል ብዙ ጭፍራ መስጠት መዐርግ ሹመት
ፈረስና በቅሎ እምቢልታ ነጋሪት ቀንደ መለከት ፡
ይህ ሁሉ ተገኘ አላንድ ልፋት ፡
ከጥንቱ አልተማረ ትንሽ ትምህርት ።
ዘልቡ ያድራሉ እነ አቶ ትዕቢት ።
ከርሱ ይርቃል ትሕትና ትዕግስት ።
ርህራኄ የለው ድሃ ማጉላላት ።
በዚህ በክፋቱ ሰው ሲያለቅስበት ።
በተሎ ይመጣል የእግዚአብሔር ቅሥፈት ።
መኳንንቱ ሁሉ ፤ አሁን ሊቁ ያሉት አይደለም ሐሰት ።
እንዲህ እንደሚሉት ይሆናል እውነት ።
ጉልማሶች ሲሾሙ ሳይማሩ ፊት ፡
ድሆችም ማጉላላት በግፍ በጭንቀት ፡
ስለዚህ ወደ ፊት ደንብ እናድርግለት ፡
ሰባት ዓመት ዕድሜ ያሉ ሕጻናት ፡
ተመልምለው ይግቡ ከተማሪ ቤት ፡
ይህን የማያደርጉ እናትና አባት ፡
ወህኒ ይታሰሩ አስራምስት አመት ፡
ገንዘባቸው ይሂድ ለተማሪ ቤት ፡
በዚያ ይማራሉ እኒያ ሕፃናት ፤
በንዲህ ያል ይሰፋል የጥበብ ትምህርት ፡
የኢትዮጵያ ሕዝብ ፤ የመኳንንቱን ቃል በጣም እንወዳለን ፤
ልጆቻችነንም እናስተምራለን ፡
ከገንዘባችንም አስራት እንሰጣለን ፡
ለሀገር ለመንግሥት በጣም እንረዳለን ፡
ለገንዘባችንም ምንም ስስት የለን ፤
በልጆቻችን እጅ ኋላ እናገኛለን ፤
ንጉሥ ፤ የጥበብን ጥቅም እናንት ካወቃችሁ ፡
ልጆች ለማስተማር ካሰበ ልባችሁ ፤
ለሁሉም ረዳት እኔ አለሁላችሁ ፤
በጣም ፈቃዴ ነው ሕግ ልሰጣችሁ ፤
የመንግሥት አዋጅ ። ልጅ የወለድህ ሁሉ ወንድም ወይም ሴት
እምጥተህ አስተምር ከተማሪ ቤት ።
እንዲህ እየሰማህ ዝም ብትል አንት ።
ቶሎ ይደርስሃል ሁለት ጉዳት ።
አንደኛው የልጅህ ድንቁርናነት ።
ሁለተኛው ደግሞ እንደ ቅድሙ ደንብ ታላቅ እስራት ።
ስለዚህ ቶሎ በል እርዳ ለትምርት ።
ለቸገረህ ሁሉ እኔ አለሁ መንግሥት ።
ይህ ስራ እንዲፈጸም መኳንንቶች ሁሉ ቶሎ በርቱበት ።
በነገሩ እስቡ በፍጹም ትጋት ።
ላገር ይህ ነውና ዋና መሠረት ።
በጎደኞቿ ፊት የሚያስሞግሣት ።
ወንዶች ልጆች ፤ ትምህርት የሚባል ሐኪም ካገኘን ።
ዕውር የነበርነው አየነ ብርሃን ።
መለየት ጀመርነ ክፉ መልካምን ።
ስንኳን ከውስጣችን ከየዙሮችን ።
መስማትም ጀመርነ ሐሜታችነን ፡
እኛ በጣም ተምረን ብንሠለጥን ፤
ሞገስ እንሆናለን ለሀገራችን ፤
ደግሞም አገልጋዮች ለመንግሥታችን ፤
በፍጹም ልባችን በሐኬት ሳይሆን ፤
በቶሎ እንዲፈጸም ደግ ምኞታችን ፤
የጃፓን ግስጋሴ ያስብ ልባችን ፤
ይኸ ነው ዛሬ ለኛ ዋና ሥራችን ፤
ሴትልጆች ፡ ልዑል መንግሥታችን እናት አባታችን ምነው ምን በደልነ ።
ወንዶች ብርሃን ሲያዩ እኛ እንደታወርነ ።
በዕዶች እንዳንበል ልጆቻችሁ ነነ ።
ወንዶች ሲማሩ እኛ ካልተማርነ ፤
አቅመ አዳም ስንደርስ ምኑን ትዳር ሆነ ፤
ምን አጠፋን ይሆን ከእውቀት ተለየነ ፤
እርሰን እንዳንበላ አቅመ ቢሶች ነኔ
ጥበብ እንዳንማር አሰተማሪ አጣነ ፤
ጉዳት ቢጠናብን አፋችን አውጥተን አቤት አቤት አልነ
ጨኸታችን ሰምተው እንዲታደጉነ ፤
በሊህ ጌቶቻችን ታላቅ ተስፋ አለነ ፤
በተሎ እንዲፈጸም ይህ ልመናችነ ፡
ልዑል እባክዎ አሰታዋሽ ይስጡነ ።
ልዕልት ወይዘሮ መነን ፡ ደናግለ ኢትዮጵያ በውነትም ይገባል አላንት ልትጮሁ።
ዘወትር ልሰራ በጣም እያሰብሁ ።
አስታዋሽ አጥቼ እስታሁን ቆየሁ ።
አሁን ብታለቅሱ በጣም ተሰቀቅሁ ።
አሳቤን ሳልፈጽም ስለ ዘገየሁ ።
አሁን ግን በውነትም ቃል ኪዳን ገባሁ ።
ላገሬ ለስሜ ማስታወሻ ትምሕርት ላቀርብላችሁ ።
ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ ይርዳችሁ ።

የኢትዮጵያ ልጆች እንዲህ ታስባችሁ ።
ጥበብን ለመማር ከተጣጣራችሁ ፤
አሁን ተማሪ ቤት ያው ከፈትሁላችሁ ።
በሚያስፈልግ ሁሉ አለሁ እናታችሁ።
የኢትዮጵያ ሕፃናት ፤ ክበር ተመስገንም ያለም ሁሉ ጌታ።
ዛሬ ያሰማኸን ይኸን ታላቅ ደስታ ፤
ቆጨር መልበስ ጠልተን ስንመኝ ደግ ኩታ ።
ጥበብ ታለብሰን ነው መነን አሰርታ ።
ፈጣሪ ደግፋት ኃይሏ እንዲበረታ ።
ከመልካም ሽቱ መልካም ስም ይሻላል የሚለውን አይታ ።
ገንዘቧን ናኘችው ለታላቅ ውለታ።
ሞት እንዳይቀር አውቃ ለድሃም ለጌታ ።
መነን ለኢትዮጵያ አበዛች ውለታ ።
እድሜዋን ያርዝመው ቸሩ የኛ ጌታ ።
በቅጡ እንዲጠበቅ ዳር ድንበራችን ።
በዓለሙ ሁሉ ተፈሪ መነን ።

በመጨረሻም ክቡር ሐኪም ወርቅነህ ለበዓሉ የተስማማ የሚከተለውን ንግግር ተናገሩ ።

ልዑልና ልዕልት ሆይ፤

ክቡራን ወይዛዝርና መኳንንትም ሆይ፤

ይህ የልደት በዓል የዓለም ፈውስ እንደሆነ እናምናለን ይልቁንም የሰማይና የምድር ፈጣሪ የዓለም ንጉሠ ነገሥት የኛን በደል ሊደመስስና ካበቱ ሊያስታርቀን የኛን ሥጋ ለብሶ የሰውን ሕግ ከኃጢአት በቀር የፈጸመበት ቀን ስለሆነ እኛም ለክርስቶስ ያመነ ሁሉ እውነተኛ ክርስቶሳውያን እንድንሆን ይህን የተደረገ በዓል በቅን ልቡና በፍቅርና በሰላም አንድነት ሆነን ማክበር ይገባናል።ደግሞ ፍቅር ከሁሉ የበለጠች እንደሆነች እናምናለን ስለዚህ ሁላችን በዚች በተከበረች ጉባኤ በፍቅርና ባንድነት እንደተሰበሰብን እንዲሁ በየዓመቱ ዘማዕርግና በክብር እየተመላን ደስታችንን ለመግለጽ ረጅም እድሜ ለልዑልና ለተወላጆቻቸውም ለሕዝባቸውም እንዲሰጥልን እንመኛለን፣

ክቡራን ሆይ ፤

ይህ አሁን በዚህ በጨዋታ የምናሳያችሁ ምንም እንኳን የድንገተኛ ማዘጋጀት ቢሆን እም አፈ ደቂቅ ወሕጻናት አስተዳሎክ ስብሐተ እንደተባለ እንዲሁ ይህ ጨዋታ በሕጻናት አንደበት ስለተነገረ በጣም ደስ እንዲያሰኛችሁ እንመኛለን።

ደግሞም በንደዚሁ ያለ ባልተተካከለ ጨዋታ ውድ ሰዓቶቻችሁን ስላሳለፋችሁ በኔና በተማሪዎቹ ስም ሆኜ ጥልቅ ምስጋናየን ከልብ አቀርባለሁ ። ይልቁንም ልዑል ጌታችን በዚህ በታላቅ በዓላችን ቀን በተከበሩ መኳንንቶችዎ ፊት ከልዕልናዎ ዘንድ የደስታዎ ተካፋዮች ልንሆን ስለታደምን የደስታ ደስታ ይሰማናል ።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ሕያው ትሁን ግርማዊት ንግሥተ ንግሥታችንን ይጠብቅልን ለልዑልና ለልዕልት ረጅም ዕድሜ ይስጥልን ስል የፍቅር መንፈስ ከኛ ጋራ ይሁን።እንደ እውነተኞች የታመኑ ክርስቲያን ሆነን ወደዚህ ዓለም የመጣበትን ቀን ለማክበር ብለን በተሰበሰብንበት በጌታችን ስም እርስበርሳችን በፍቅርና በትዕግሥት እንድንኖር ያድርገን ።

ከዚህ በኋላ የተጠሩ ወይዛዝርና መኳንንት ከልጆቻቸው ጋራ የገና ዛፍ በተሰናዳበት ቤት ገብተው ሻይ ተጋበዙና የልዑል አልጋ ወራሽ ልጆች በዚያ ለነበሩ ሕፃናት ሁሉ ያማረ ያማረ የልደት ስጦታ ሰጥዋቸው ።

በዚሁ ቀን ከማታው በ፪ ሰዓት ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንና ልዕልት ወይዘሮ መነን የልደትን በዓል ለማክበር ብዙ የኢትዮጵያና የውጭ አገር መኳንንትና ወይዛዝሮች ጠርተው ነበርና የተጠሩ ሰዎች ሁሉ አምሮ በተጌጠና በኤሌክትሪክ ብርሃን ባንጸባረቀ ድንኳን ገብተው የደስታ ግብዣ ተጋብዘው ሻምፓኝ እየተጠጣ ፒያኖ እየተመታ ዳንስ እየተደረገ ጨዋታው እጅግ አምሮና ደምቆ አመሸ ። በዚያን ጊዜም የዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ገብተው የልደት መዝሙር ዘምረው የቴአትር ጨዋታ አሳዩ የድግሱና የሥርዓቱ ማማርም ዕፁብ ድንቅ ነበረ እንደዚሁ ሆኖ የልደት በዓል በደስታ ተፈጸመ ።

ማሰብ መናገር መሥራት ።

ያለፈ የያዝነው የመጭ ዘመን ታሪክ ።

ትልቅነትና ትንሽነት።

አባቶቻችን ሲተርቱ « ያለፈ ነገር አይቈጭህ የሚአድግ ልጅ አይጥላህ ወይም የሚአልፍ ዝናም አይምታህ « ይላሉ። አነጋገር ከማሳመር አሠራር ማሳመር ከሁሉ ይበልጥ ይጠቅማል። አነጋገር እያሳመሩ ሥራን ችላ ቢሉ በገዛ እጅ መከራ እየፈለጉ ስለመሞት ያህል ነው ። አሠራርን እያሳመሩ መልካምም መጥፎም ቢናገሩ እንዲያውም ምንም ቢናገሩ ከሁሉ ይበልጥ የሚአምር ስለተናገሩ ያህል ነው ። መሥራት ማጥፋት አይደለም መናገርም መዘብረቅ አይደለም ። መሥራት ማለት ልንሠራ የሚገባንን መስራት ነው መናገርም አስተካክሎ አስቦ ይህ መልካም ነው ይጠቅማል ይህ መጥፎ ነው ይጎዳል እያሉ ወደመልካም አሳብ እየመሩ ከክፉ አሳብ የሚመልስ ነው ። ደግሞ እጅግ ልንጠነቀቅበት የሚገባን ነገር የይስሙላን መሥራትና መናገርን ንቆ መተው ነው ። የዘገየ ታሪክ የተከበረ ዘር የሚአክራ አገር ያለን ሰዎች ሁል ጊዜ በውነት መንገድ እንጅ በግብዝነት መንገድ መሄድ አይገባንም ።

የውነት የመልካም ነገር ሁሉ መምሕር በምሳሌ እነግራችኋለሁ እንዳለ ይህ መጥፎ ግብዝነት የሚባል አመል ላላቸው ሰዎች አሳባቸው ከንቱ መሆኑን የሚአስረዳ አንድ የእስያ አገር ተረት እተርትላችኋለሁ ። አንድ ሰውየ በድሜው የገፋ ጠጉሩን ሽበት እኩል በኩል የወረረው የልጅነት ሚስቱ ስለሞተችበት እኩያ የምትሆነው እንዴት ጠና ያለችና ደግሞ ለሰውነቱ ደስታ የምትሆነውን እንዴት ልጅ እግር ሴት አግባና ተቀመጠ ይላሉ ። ነገር ግን ስጋ ክፉ ነችና ይህ ሰውየ ሁለቱን ደስ አሰኝ እያለ አንዱ ከንዲቱ ጋር አንዱ ከንዲቱ ጋር ሲሄድ ሁለቱም በየበኩላቸው የጠናቸዋም ሴትዮ እንደሱዋው የጠና እንዲመስልላት ጥቁሩን ጠጉር

ስትነጭ ልጅ እግሩዋም ሴትዮ እንደሱዋው ልጅ እንዲመስ ልላት ሽበቱን ስትነጭ ከትንሽ ቀን በኋላ የሰውየው ጠጉር በጭራሽ አለቀና እራሱ በራ ቀረ ይላሉ ። መጨረሻው ደግሞ ከዚህ የሚአሳዝን ስለሆነ አልጽፈውም ይህ ነገር ተረት ይመስላል ነገር ግን በጊዜአችን የምንሠራውን ሥራ ልብ እያልን ብንመለከተው ከዚህ ይበልጥ የሚአሳዝን ሥራ እንሠራለን። የምንሠራውም በገዛ አገራችንና እራሳችን ላይ ነው ። ይህንን የሚመ መሳስል የሚአሳዝን ሥራ መሥራታችንን ደግሞ ሁላችን ባንድ አይቀር ባንሆን ብዙህ ነን የተረዳነው ሰዎች። የዚህን ጊዜ ከሁሉ ይበልጥ የሚአሳዝነው እኛው የተረዳነው ሰዎች ክንደዚህ ያለ መጥፎ ሥራ መታደግ መከልከል አይሆንልንም ። ደግሞ እን ዋሽም ብለን አናውቅም እንዳንል ብርሃንና ሰላም ያሳፍረናል የሆነውን ሆኖ ስለምንድነው እንግዲአስ አገራችንና ሰውነታችን የምንጎዳበትን ነገር እኛው እራሳችን የምንሠራው ብሎ የሚጠይቅ ሰው ቢኖር መጽሐፍም ለሚመለከት ሰው ብዙም ሳይደክም እያዩ እየሰሙ እያወቁ እንዳላዩ እንዳልሰሙ እንደማያውቁ ይመስላሉ የሚለውን ቃል ጠቅሶ የቅዱስ መጽሐፍ ትንቢት በሰው ላይ ካልተፈጸመ በማን ላይ ሊፈጸም ይችላል ብሎ ይመልሳል ።

ትንሽ የፈላስፋኖች ቃል ። ሁል ጊዜ መፈራት መከበር አይዶለም ። ጊዜ በሰዓት በደቂቃ በሳምንት በወር ባመት ብቻ አልተወሰነም ይልቁንም ከሁሉ ይበልጥ በሚአስቡትና በሚሠሩት ሥራ ተመሥርቶ ተወስኑአል ። ማታ ማታ ታዝናለህ የዋልከውም ቀን ይጸጸትሐል የሠራኸው መጥፎ ሥራ እንኳን የለህም እንግዲአስ ሰውነትህን ሰውነትህ ስለምንድነው የሚወቅሰው ? ሰው ደንቆሮ የምድር ትል ልትሠራ የሚገባህን ሥራ ስላልሠራህ መሆኑን ተረዳው ።

የዚች ዓለም ብልሐት ውሉ እየጠፋብን
ማሰብ አለማወቅ መከራ ሆኖብን ፤
ተፈጥረን ለመልከም ስንጠፋ በከንቱ ፤
እንዴት ማዘን ማልቀስ ይቅር በየቤቱ ፤
ሰውነት ሲበሳጭ በጣም እያዘነ ፤
ትንሹን ትልቁን ሁሉን ሰው መዘነ ፤
አትከፋ ልቤ እጅግ አትበሳጭ ፤
ዓለም ቀጣፊ ነች ጊዜነው ሰው ገሳጭ ፤
አወይ ሰውነቴን እንዴት እጅግ ናቅሁት ፤
በቀን ስንት ጊዜ ፈጽሜ እረሳሁት ፤
አሳብየን ፍቅሬን የኔን ስለ አጣሁት ፤
ጠላቴን ፍጥረቴን ሥጋየን አረግሁት ፤

ልሳነ ወርቅ ።

ማስታወቂያ ፤

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ	፭ ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ	፭ሩብ
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ብር
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ተኩል
የቁጥር ትምርት	፩ብር
ያማሪኛ ሰዋስው	፩ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	አላድ
ወዳጄ ልቤ	፫ሩብ
አጭር የዓለም ታሪክ	አላድ
ያማሪኛ ፊደል	ሩብ
አሳብና ምኞት	ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት	ሩብ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር	፪መ

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲ ብር
የሲዳሞ ቡና	፩	፱ ብር ከሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፪ ብር ከ፫ሩብ
ሰም	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር ከ፫ሩብ
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፲ ብር ።
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፳ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፯ ብር ተኩል
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፯ ብር ተኩል
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፯፵፪ ብር
፡፡ ባለሰይጣን	፡፡	፻፵፫ ብር
፡፡ ባለ ድመት ።		፻፵፪ ብር ።
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻፳፪ ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፻፴፭ ብር
ባለ አንበሳ	፡፡	፻፵፭ ብር ።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፳፯ ብር ።
ቻይ	፩ ነጥር	፲፪ መ

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ ከ፴፰ ሳንቲ
አንድ ብር	ሊሬ ፱ ከ፲፭ ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፱ ብር ከ፺፯ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፩ ብር

COGNAC S.E.A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



የእጅ ሰዓት ።

በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ኦሜጋ የሚባል ባለአንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

ሺብሮሌ አቶሞቢል ።
በኢትዮጵያ ወኪል ።
ሔ ሜ ዜርቦስ ኩምፓንያ ።

Automobiles CHEVROLET
AGENTS
H. M. ZERVOS & Cie.

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያየዚህአቶመቢልበተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤት በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኒዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፥ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በየይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፥ ቤንዚን በየይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል ።



ማስታወቂያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጀ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልካም ባርኔጣ ፡ ሽቱ ፤ ለስዮን ፡ አድኮሎኝ ፡ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ክኬ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስመጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሽምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ዓለም

ዓለም የወርቅ ጥልፍ ሥራ ሁሉ በውስጠ ብር ሆኖ ይሠራል ።

ኒኮላ ።

ማመልከቻ ።

በብርሃንና ሰላም ውስጥ ማስታወቂያ ማሳተም የሚፈልጉ ነጋዴዎች እስከ ፈለጉት ጊዜ ድረስ በማርኛም ሆነ በፈረንጅ ቋንቋ በርካሽ ዋጋ እንደምናትምላቸው እናስታውቃቸዋለን

ጉድዬር ግዙ



ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው ። በሌላጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ፤ ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አራተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፫
4 me ANNÉE № 3

ሐሙስ ጥር ፲ ቀን ፲፱፻፳ ዓ ም ።
JEUDI 19 Janvier 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d'Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ጸሐፊትሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ስፈስገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

እውነተኛውና አሰተኛው ሥልጣኔ በሥልጣኔው ስምም የገቡብን ልዩ ልዩ ጉዳዮች ፡፡ እንዲሁም የከተማውን ሕይወት በጤንነት እንዲጠብቅ የሚያሳዩ ምክሮች ።

፩ ፤ እውነተኛውና አሰተኛው ሥልጣኔ ።

በዚሁ ማኸል ያለውን ልዩነት ልንለይ ይገባል ልዩነቱም እጅግ ታላቅ ነው። እንግዴህ እውነተኛው ሥልጣኔ ምንድር ነው በእንዴትስ ይገለጣል? ሥልጣኔ ለሚለው ቃል ወይም ንግግር አሳቡ እንደሚገባው አልታወቀለትም እያንዳንዱም ይህን ቃል ለገዛራሱ እንዴት አድርጎ እንደሚያስተውለው ወይም እንዲያስበው አናውቅም። ይህሳይቀር ግን ብዙዎች በሥራቸውና በሕይወታቸው እንደሚታይ በጣም እንዳስተዋሉት እናያለን ፡፡ ሁሉም እንደሚያውቀው ሥልጣኔ ሠለጠነ ሥልጣን መሠልጠን ከሚለው ቃል ከአረብ ከግዕዝ ከዕብራይስጥ ሲያያዝ የመጣነው። በማርኛም ሠለጠነ በረታ አየለ ገዛ ነገሠ የሚል አሳብ እንዳለው አጠይረጠርም። እንዲሁም ይህ ቃል በአሁኑ ንግግራችን ሁሉ እንደሚያውቀው በሠለጠኑቱ አገሮች ቋንቋ ስቢልሻይሸን ለሚለው ቃል ትርጓሜው አድርገነዋል፡ ይህም ቃል በነዚሁ አገሮች እንደሚያስተውሉት አሳቡ የሥርዓት አናኑዋር ፡ እንደ ሰው መኖር ማለት ነው። በአእምሮ በማስተዋልም በዕውቀትም ከፍ ያለ የተገባ ሕይወት ወደመኖር የደረሰ። ስለዚህ እውነተኛ ሥልጣኔ በባሕርይ ማሳመር ነው የሚታሰብ ። የባሕርይን ቅንነት ወይም ደግነት (ሞራል) እየጠበቀ በዚህ የሚሄድ ለወደፊትም በዚህ እየተሻሻለ በትክክል ለመኖር የሚገፋ እንዲህ ያለ ነው ሰው እውነተኛም ሥልጣኔ ይህ ብቻ ነው፡፡

አሰተኛው ሥልጣኔ በውጭ በሚታይ ሲሆን ነው ። ብዙዎችም ማጌጽና መብላት መጠጣትም እንደሆነ ያስቡታል እንዲሁም በሌላዎች ሥጋውያን ደስታ መኖር በኩራት በትዕቢትም መታየት ከሥራም ነፃ መሆን ሥልጣኔ ይህ እንደሆነ ይመስላቸዋል። እውነተኛ ሥልጣኔ ግን ሶስቱ የሰው ጠባያት በሚገለጥበት አናኑዋር በትክክልነት መኖር ነው ፤ በነፍስ በሥጋ በመንፈስ። እውነተኛውም ሥልጣኔ እንዲያው በጥሬ ትምሕርት የሚደረስ ነገር እንኳ አይደለም ። እጅግ ከፍ ያለ ነው ብዙዎች ምንም ባንዳች ነገር ቢማሩ የሥልጣኔ ነገር እንደሌላቸው ያሳያሉ ምንም ቢያጌጹ ቢለብሱ ይህንም ያንንም ቢያደርጉ ከአራዊት ሕይወት ወይም ከዝቅተኞች ሰዎች ኑሮ ይኖራሉ። ለእግዚአብሔርና ለጓደኞቻቸው ሊፈጽሙት የተገባቸውን አግባብ አንዳች አያስቡም በጠባያቸው በአካሔዳቸው በሰው ሕይወትም መካከል እንደ ቸነፈር የሆኑ ሁከተኞች ሰዎች ሞልተዋል ። በሚዳዊ ለዓይን ሲገጥሙ ሥልጣኔ እንዳላቸው ያስመስላሉ ። ዳሩ ግን ከሁሉ የባሱ ሆነው ይገኛሉ ። የሕዝብንም ሰላም ሲያናውጡ ይኖራሉ ፣ የሰዎች ኑሮ በዓለም በሠለጠኑቱ አገሮች አከፋፈል በሶስት ተከፍልዋል። የአራዊት የባርባር የስቢል ይባላል እንግዴህ ባነጋገሩ በሥራው በሁሉ አካሔዱ በፍጹም ትክክልነት እንደ ሰው ሆኖ ባይኖር በሁለቱ ፊተኞች ስም ይጠራል። እውነተኛ ሥልጣኔ በጸጥታና በሰላም እየኖረ ሥራውን የሚሠራ በዕውቀት በአእምሮ በጥበብም እየገፋ መሄድ የገዛራሱን ሕይወትና የቤተሰዎቹንም ኑሮ እንደ አቅሙ መጠን እያሻሻለ የሚሔድ ይልቁንም ከገዛ አካሔዱ ይልቅ የወጣቶችን ሕይወት የሚያሻሽል ሰው እርሱ ነው እውነተኛ ሥልጣኔ ምንመሆኑን አጥብቆ የተረዳ አሰተኛ ሥልጣኔ ግን ከልዩ ልዩጉዳዮች ያደርሳል ።

ሰዎች ይልቁን ወጣቶች ሊሸሹዋቸው የሚገባቸው ልዩ ልዩ ጉዳዮች፡፡

፩፡መቅለጥ ሰውነትን የሚያደክም ምኞት መሻቶችን አለመግዛት።

ሥልጣኔ ሲገባ አስቸጋሪ ነው፡፡ ሰው ከውነተኛው መንገድ ይዘነብላል፡ ሥልጣኔውን ሳይጀምር ሥልጣኔ በሚመ

ስሉ መንገድ መሔድ ይጀምራል ሥልጣኔም ይህ እንደሆነ ይመስለዋል ።እንግዲህ ይህንን እንደ ደስታና እንደ ዓይነተኛ ነገር እንደሆነ ያየዋልና በዚህ ለመኖር ብቻ ይፈልጋል እጅ እግር አካላት ሁሉ እንዲሰለስሉት ይተጋል ሳያውቀውና ሳያስበው የማያስፈልጉና ያልተገቡ መሻቶች አንድ አንድ እያሉ ሊገዙት ይጀምራል ፡ በለማሰብ በማየት በመስማት በክፎች ሰዎች ክፉ አብነትም ሁለንትናውን ወደሚጎዳ ነገር ይደርሳል ። እንዲህ በመኖርም በመቅለጥ ሰውነቱ ይደክማል የነፍስንና የመንፈስን ደግ አብነቶች አጥፍቶ ወደ ሥጋ ደካምነትም ይደርሳል ። አስቀድሞ የሥጋው ኃይል ብዙ አካሉ ብርቱ የነበር በእንደዚህ ያለ አኗኗር ግን መልካካሞቹ የሥጋው አብነቶች ይጠፉበታል ፡ በዚሁም መንገድ መጀመሪያው የሚጎዳና የሚጠፋ ያለ ጀግንነት የተባለ የሕዝብ አብነት ነው ።እንግዲህ በሥልጣኔው መልክ ያችየነበረችን ጀግንነት የኢትዮጵያ አንደኛይቱ መኩሪያችን እየጠፉች ትሄድ እንዳለች ካያሌዎች በሕዝባችን ሕይወት ከሚመለከቱ የምንሰማው ነው።የሠለጠኑት አገሮች ጅግንነትን እንዳያጠፉ ዘወትር ይጣጣራሉ ። እኛ ግን ያለችንን ጀግንነት ወደ ማጥፋት በሚያደርስ መንገድ እንዳለን ይታያል ።

እንግዲህ እንዴህ ከሆነ ይህን ትልቅ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብነት የሚያጠፉ ምክንያቶች መመርመር ብዙ ይገባናል ። የሕዝብን ሕይወት የሚያደክሙ ነገሮች ምንድር መሆናቸውን ማወቅ ብጣም ያስፈልገናል ፤ ይልቁንም ሠራዊት በብርታትና በኃይል በወታደርነት ሥርዓትም በጽኑ እንዲጠበቁ እንዴሁም ወጣቶች በዚሁ መንገድ ማሳደግ ለሕዝብ ሕይወት ዋና ነገር ነው ።

ላኋላው ለወታደርነት የሚሆኑ ያገራቸው ጽኑ ቅጥር የሚሆኑትን ወጣቶች ከመጀመሪያ ዕድሜያቸው ጀምሮ በተለየ አስተዳደግ ማሳደግ በቀድሞዎቹ ሕዝብ ጀምሮ የታወቀ ነበር ፡ በእስጳርት በቀድሞ አንድ የግሪክ ሕዝብ ሊኩርጉሥ የሚባል ብልህ ሰው ወጣቶችን የሚያሳድግበት ጽኑ ሕግ አውጥቶ ነበር ፤ ችግርንና ልዩ ልዩ ዓይነት መከራ መቀበል ራብና ጥማትን ብርድና ሙቀትን መንገድንም ድካምንም ማጣትንም መቻል ፡ በጭሩ ሁሉን መቻል ። ይህም ሕግ ምንም ባያሉ ነገር ይልቁንም ባንድ አንድ የደግነት (ሞራል) ነገር የመጣ ስናስብ ጎደሎ ቢሆን ስርቆትን እንደ ጮሌነት አድርጎ ይቆጥረዋልና በጅምላ አሳብ ግን የታወቀና የተፈተነ ነው ፡ በቀድሞዎቹ ሰዎች ብቻ አይደለም ባሁኑ በሕዝብ መሪዎች ሰዎችም ሳይቀር ዓይናቸው ጥለውበታል ። መቅለጥ የሕዝብን ሕይወት እንደሚያጠፋ አውቀዋል ። ስለዚህ ከዚሁ ሕይወት ሕዝባቸውን ሊያነሱ ይተጋሉ ፤ ወደ ሥልጣኔ የምትራመደውን መንግሥትም ከዚያ ብዙ ከሚያስፈልግዋት መሻቶቹዋ አንዱ ይሄውነው ፤ ሕዝባችንም ከዚህ ቀደም በትምሕርት አሳብ እንኳ ባያደርገው በአኗኗሩ ተምሮት ነበር ። በዚህ ጀግንነትም እስከአሁን ሲመሰገን ኖርዋል።ለወደፊቱ ግን እንዴህ ያለ ጀግንነት እንዳይጠፋብን ብዙ ያስፈራል ።

፪፡ መጠጥ ይልቁንም የብርቱ ዓልኮሆል ዓይነቶች።

እነዚሁ በአገራችን ብዙ ተዘርግተዋል። አረቂውና እርሱን የመሰሉ መጠጦች በኢትዮጵያችን እስታቲክ ቢደረግባቸውና ብናውቀው ባመት የሚፈጀው እጅግ ሆኖ በተገኘ።እንግዴህ ይህ ነገርእጅግእንዲቀነስ ማድረግ ግድነት ነው።ከሁሉም የሚያሳዝን ነገር ሕዝባችን የአረቂውና የአልኮል ኃይልና ጉዳት እንደሚገባው ስለ አላስተዋለው ነው ። እውነተኛ ማስተዋል የሌለው እንዲህ ያለ መጠጥ እንደ ሌላዎች መድኃኒት በሐኪም እጅ ብቻ የሚያዙቱ እንደርሳቸው ተቈጥሮ ሊያዝ እየተቀነሰ እንደ ፈውስ በልክ ሊሸጥ ብቻ በተገባው ። እንግዴህ አልኮልን እንደ የሕዝባችን ዋና ጠላት አድርገን ልናየው ይገባናል። በማናቸውም መንገድ መዘርጋቱን እንዲወሰን ማድረግ።በዚህ የሚመጣውን ጉዳት ማን ይህ ያህላል ብሎ ሊገምተው ይቻለዋል ? አልኮሆል ባንድ መንገድ ብቻም አይደለም ጉዳቱን የሚያመጣ በብዙ መንገድ ነው እንጂ ። በዓለም በጎም ክፉም ሆነ የማይራባ ነገር የለም ። አንድ ነገር ቢሆን ሌላው ነገር ያስከትላል ። እንዴህ ያሉ የአረቂ መጠጦች ሥልጣኔ የሚባለውን ተከትለው መግባታቸው ያሳዝናል ። ሕዝባችን እውነተኛውን ሥልጣኔ ሳይማር እኚህን መማር ጀምርዋል ። እጅግ የሚጎዱ ነገሮች በሕፃን እጅ እንድናያቸው እንደማንፈቅድ እንዴሁም በአእምሮና በተምክሮም ሕፃን በሆነ ሕዝብ መካከል ሲዘረጉ እንዴት ያለ ጉዳት ያወርዳሉ ። በዚሁ በኩል ከሚመጡቱ ጉዳቶች ልናመለክት ፤ ፩ ፤ የገንዘብ ጥፋት ። አልኮሆል ገንዘብን ሙልጭ አድርጎ ያጠፋል ። ትዳርን ያስቸግራል ። ቤተሰዎች የሚበሉትን የሚጠጡትን የሚለብሱትንም ያጣሉ ። በመጨረሻም እርሱ ራሱ ራቁቱን ይሔዳል ። በዚህ በአልኮሆል ምክንያት በዓለም ስንት ቤቶች ናቸው ደስታንና ብጽዕናን ሳቅንም በማግኘት ፈንታ ኃዘንና ልቅሶ ዋይታም የሞሉ ? ፪፡ አልኮሆል ለገዛ ጠጪው ጤናውን ያጠፋበታል ። በጤና ፈንታ በሽታ በኃይል ፈንታ ድካም ያመጣበታል ። ፫ ፡ እንዴህ ያለጥፋትም በጠጪው ሕይወት ብቻ አይወሰንም ወደ ትውልዱም ያልፋል ። ጤናና ኃይል ደስታ አእምሮ ማስተዋልም በጎም ፈቃድ የጐደለባቸው መከረኞች ልጆች ይወለዳሉ ። ይሄው እንዴት የሚያስፈራ ርስት ነው ። ፬ ፤ አልኮሆል የምሕረትንና የፍቅርን የረድኤትንም ሥራ ለማድረግ አያስብም ። የድሆችንና የቤተክርስትያንንም ክፍል ያስቀራል በጎነገር ማድረግ ከቶ አይችልምና ። ባልኮሆል የተሞላ የክፉ መሻቶች ባርያ ሆኖ ብቻ ይቀራል ። መጥፎ ስራዎችንም ወደ ሥራት ይዘነብላል ፡ ጨካኞችና ሐኪምን የሚያምጹ በሽቶች ይገዙታል ። የአካልነት መደንዘዝ ወይም መሞት ። የሳምባ የልብ በሽታ የአእምሮ ማጥፋት ሰነፍነት ድንቁርና የማይቈጠሩትንም ጉዳት ይሸከማል። እነግዴህ እንዴህ የሚያመጣው ነገር መሸሸት ሰው ራሱን እንዲያከብር ። የሚወዱትንና የሚወዳቸውን ማሰብ ። አልኮሆል የገንዘብን ከረጢት ራስንም ልብንም ባዶ ያደርጋል ።

፫ኛ ፡ ትምባሆ ወይም ሲጋራ

ይህ ክፉ ልማድ ቀድሞ በኢትዮጵያችን እጅግ የተጸየፈ ሥራ ይቈጠር ነበር ፡ እንዴህ ያለ አመለኝነትም ያለው ይህን ልማድ ሳይለቅ የተቀደሰውን ቍርባን አይሰጡትም ከቶውንም ትምባሆና ሲጋራ የሚጠጣ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አይገባም ብለው ያስተምራሉና ይኸው ትምሕርት አሰትን ይሆን?

ክርስቲያን ነፍስንና ሥጋን መንፈስንም ከሚያረክስነገር አልተከለከለምን? ትምባሆ ሲጋራ ሱረት የአመልን ነገር ብቻ እንደሆነ እንጅ ባንዳች ነገርም ለሰውነት ጠቀሜት አለው ብሎ የሚታመን ማን አለ? በዚሁ ነገር ጉዳት እንዲሆን የሚጠራጠርኀት የለም ሰውነቱን ባንዳች ነገር የሚጐዳስ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት ይፈቀድለታልን ?

ይህ አመል ያለው ሰው ደምግባቱ ይበላሻል እስትንፋሱ እስተሆዱ ውስጥ ይሸታልና ይገማል ጥርሶቹ ያድፋሉ የጥርሶቹ ስር ይጐደጐዳሉ ገዛ ጥርሱም ይፈነቀላልና ሕማምም ያሰድራል ድዱም በታመመና በተበላሸ ደም ይሞላል ። ይሄው የተበላሸውም ደም በደም ሥር ሁሉ እየገባ ደሙን ፈጽሞ ያበላሻል ። የሳምባው ቀዳዶች ይደፈናሉ የሥርዓት ማስተንፈስ ያንስበታል ። ማለት ማስተንፈሱ ይወሰንበታል ፡ እንዲህ ብሎም ሰውነቱ ይናወጻል በዚህ ፈንታ ልቡ አለልክ ለመምታት ብዙ ይቸኩላል ልቡም ይፈነዳልና ይሞታል እንዳንድም ቍጡ ወደ መሆን ይደርሳል ። ቍጣም ልኩን ሲሻገር ወደ ዕብድነት ያደርሳል። ይህ አመል አታላይ ነውና ለጊዜው አንዳች አብነትን የሚጨምር ያስመስላል ፡ የሰውን ሕዋሳቶች ግድ ከተፈጥሮዋቸው ኃይል በላይ እንዲነቁ ያግዳቸዋል። ይህንንም ሲያጣ ከአሳቡና ከአእምሮው ይወጣል የሚያስበውንና የሚፈልገውን ነገር ይጠፋበታል እንዲያው ይጨልመዋል። በነዚሁ ብዙ ጉዳቶች አጠገብ ደግሞ የገንዘብ ክንቱ ጥፋት ይከተላል። እንግዲህ ሥልጣኔ ያመጣልንን ጥቅም ይህን ልማድ ነው? ትንንሾች ልጆች ከሰው የተጣለችውን ሲጋራ ለማንሳት ይሮጣሉ ትልልቆችም ሳይቀሩ ከሰው የወደቀችውን ሲጋራ ይጠባበቃሉ ደግሞ የሲጋራውን አመለኛነት ብቻ አይማሩም ያችው በዚሁ መንገድ የሚያገኙዋትና ከፋቸው የሚያገቡዋት ከንዴት ያለ አፍ እንደነበረች አያስተውሉም።በዚህም ያላሰቡትን ሌላውን ጉዳት ይደርስባቸዋል። ይሄ ጥፋት መሆኑን እናስተውለው ይልቁንም ወጣቶች ያልዋቸው ሰዎች በዚሁ ነገር የልጆቻቸውን ሕይወት ተግተው እንዲጠብቁ ሊጠነቀቁ ይገባቸዋል። እንዲህ ያለ አመለኛነት በሕዝብ ጥቂት በጥቂት ነው የሚጀምር፡ትምባሆ ዛሬ በውጭ አገር እንዲህ የሠለጠነው ቀድሞ አይታወቅም ኑሮዋል።ትምባሆ ወይም ሲጋራን ወደ እንግሊዝ አገር አስቀድሞ ያገባ ሴርዋልተር ረላይ (Sir Walter Raleigh) እንደሆነ ይባላል ፡ እርሱ በጽፈት ቤት ተቀምጦ ሲጋራን ሲያጤስ ገረዱ ጠላ ይዛለት መጣች እርስዋም ከጌታዋ አፍ ጢስ ሲወጣ ባየች ጊዜ ደንግጣ በሳት ተቃጥለዋል ብላ ታጠቀችና እሳቱን ልታጠፋ ስትል ያመጣችው ጠላ በግምባሩ አፈሰሰችለት ወድያውም ሩጣ ወርዳ ቤተሰዎችን እሳት ተቃጥለዋል እስከምትደርሱትም በሳት ተፈጅቶ ይቈያችኋል እያለች አስታጠቀቻቸው ። ይሄው ማጤስ ወደታላቁ እሳት እንዳያደርስ ያስፈራል ስለዚህ ሰውነታችንና መሻቶቻችን ባለመግዛት ባይሆን እንዲህ ያለ ልምድ ምን ይጠቅመናል ?

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል።

መልእክት ፤

ይድረስ ለአቶ በቀለ ሀብተ ሚካኤል። ሰላምና ጤና ለቅድስት አገርዎና ለመንግሥትዎ ለርስዎ ይሁን። ነሐሴ ፳፮ ቀን በግሌጌዝ ሆቴል የእምዬ ምኒልክ ተማሪ ቤት ተማሪዎች በመምህሮቻቸውና በርስዎ መሪነት የቴአትር ጨዋታ ለሰሎሞን ጌታችንና ለመኳንንቱ ለሕዝቡ ካሳዩ በኋላ የተናገሩት ቃል በቁጥር ፫፪ (3ፀ) ብር (ሶስተኛ) ባመት ደርሶኝ የጠቀሱት መልካም ጥቅስ በልቤ ሲያበራ የኖረ ሆኖ የሚከተለውን ቃል ለእርስዎና ለተማሪዎች ሁሉ እንዳመለክት ቀሰቀሰኝ ።

ወንድሜ እውነትዎ ነው ይህቺን ብርሃንና ሰላም የሆነች ጊዜአችንን የኢትዮጵያ ሕፃናት ሁሉ ወደ እውቀትና ወደ ትምህርት ማዘንበላችን ከገንዘብ እውቀት በመረጠው ዳግማዊ ሰሎሞን ጌታችን መሪነት ነው ። ኢትዮጵያና ሕዝቧ በርሳቸው ልክ የሌለው ደስታ ማድረግ ይገባናል ። ዕድሜያቸውን አርዝሞ ላገራቸውና ለወንድሞቻቸው ወደሚአስቡት የእውቀት ደረጃ ለማድረስ ያብቃቸው ሰሎሞን ፈጣሪውን እውቀት ቢለምነው ክብረትን አክሎ እንደሰጠው የተረዱ ጌታችን እርሳቸው ብቻ ናቸው እንግዴህ ዳግማዊ ሰሎሞን መባል ይገባቸዋል ።

እውቀት ካለ ሁሉ አለ ፤ ጉልበትና ነፃነት አለ ፡ ገንዘብና ክብረት አለ፤ በሰማይ እንኳ በእውነተኛ እውቀት መንገድ አለ። እግዚአብሔር ለሰሎሞን የሰጠው ጸጋ በርሳቸው ሊደገምና እንደማይናወጽ በየሕጻናቱ ልብ ሲተክሉት ሁላችን በሥራቸውና በምክራቸው እናያለን ። የውጪ አገርም ሰዎች እየተመለከቱ ያደንቃሉ ። በ፲፱፻፲፬ ዓ ም ልዑል ተማሪ ቤታችንን ሲጐበኙ እርስዎ እንደሚያውቀት ከሁለቱ ባልንጀሮቼ ጋር በተማሪ ቤቱ ነበርኩኝ ልዑልም በነበሩት በሶስቱ ክፍሎች ዙረው የጥቂቶቹ ተማሪዎች ሥራ ደስ ቢያሰኛቸው ይህቺን ከልቤ ላይ ተቀርጻ የምትኖረውን ምክር ሰጡን ።"ከዚች ተማሪ ቤት ያላችሁ ልጆች ከባላባት አልተወለድንም በገንዘብ አልከበርንም አልበዛንም ብላችሁ አትዘኑ ትምህርቱን ሳይመረር እስከ መጨረሻው የደረሰ ሰው ይኸንን ሁለቱን ማዕርግ ያገኛል። ሰሎሞን ከዕንቍ ጥበብ ትበልጣለች ያለውን ተመልከቱ።ከለማወቅ ነፃነትን አገር መውደድን ባለማወቅ ማፈርን የሚፍቁ እውቀትና ፍቅር ናቸውና እውቀትን ፍቅርን ለማግኘት እስከሚቻላችሁ ጣሩ» ሲሉ ልዑል ጌታችን ከብሩህ ልባቸው የሰጡን ጣፋጭ ምክር ሥጋችንንና አጥንታችንን አልፎ በነፍሳችንና በልባችን ተቀረጸ ። እርስዎና ባልንጀሮቻችን ሁሉ እንደምታውቁት እኔንና ሁለቱን ጓደኞቼን እስከ መጨረሻው ለመድረስ አስመኝቶ ሩቅ አገር ለመሄድ ከማይፈቅዱልን ዘመዶቻችን ወደ ክፉ ሥራ እንደሚሄድ ወስላታ ሸፍታ ተሸሽገን ስለ እውቀት ለመሰደድ ቆርጠን ፡ ባካል ሶስት ብንሆን በልብ አንድ ነበርን ። በልባችን ያለው የጌታችን ምክር ብቻ ነበርን ። ምንም ጥግና ገንዘብ የሌለን የድኃ ወገኖች ብንሆን አሳባችን በልዑል ምክር ጸንቶ ጌታ በወንጌል ለምኑ ይሰጣችኋል ደጅ ምቱ ይከፈትላችኋል ያለንን እያሰብን ስልቹትን አባረን የሚያበረታ ቅናት ታጥቀን የሰሎሞንን ደጅ ብንመታ የብርሃን መዝጊያ እውቀት ለሚፈልጉ በልዑል ፍቃድ ክፍት ነኝና ግቡ የምትፈልጉትንም ታገኛላችሁ ሲል ወለል ብሎ ተከፈተልን ። ከሰላም ግቢ ገብተን ወደ እውቀት አገር ወደ ብርሃን መፍለቂያ ከተማ የሚወስደውን ጐዳና ብንመለከት እንደ ዘንግ ቀጭን ቀጥ ያለች እንደ ጸሐይ ስታበራ ትታየን ነበር ።

በግራና በቀኝዋ ሰፋፊ ጐዳኖች ብርሃን የሌላቸው ወለል ብለው ይታዩን ነበር ። በነዚሁም ጐዳኖች ላይ ብዙ የሰቡ አንስሶችና ጥቁር ልብስ የለበሱ ሰዎች ይመላለሱባቸዋል ። አልፎ አልፎም ለሚታዩን መብራት በማይበራባቸው ጨለማ በሸፈናቸው አድፋሞች ጎጆች ውስጥ ዘፈን ልቅሶ ሳቅ ጨዋታ ድብልቅልቅ ይዋኝባቸዋል ። ሆኖም ብርሃን በይኖራቸው ጐዳናዎቹ ወለል በማለታቸው ደስ ያሰኛሉ ። ብዙዎችንም ሰዎች ያታልላሉ ። በየጎጆቹ የሚንጫጩና የሚሳለቁ የሚስቁ የሚያለቅሱ አድፋሞች ሰዎች በደስታ የሚኖሩ ይመስላሉ ።

ወደ እውቀት አገር የምትወስደው መንገድ ግን ምንም ብርሃን ብትሆን ስለ ጠባብነቷ ወለል ብላ አትታይም ። አልፎ አልፎ ብርሃን እንደ ጉርፍ የሚያፈሱ ትልልቅ ፎቆችና አዳራሾች ይታያሉ ። ከተማዋን ግን በመራቷ የተነሳ ለማየት አልተቻለንም ። በነዚያ ቤቶች ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ምንም ብዙዎች ቢሆኑ ሁሉ የጠዱ ሠራተኞች ናቸው ። በስራ መውደዳቸው ብዛት በየር ሲበሩ በባሕር ሲሽሎኩሎኩ እናያቸዋለን ። በመንገዲቱ የሚመላለሰው ፍጡር እንደ ጢፍ ሲንተገተግ አንገቱን የደፋና የሚመድት ነው ። በቀኝ በግራዋ ግን የከሱ የደረቁ አራዊቶች ቆመዋል ። በመንገዲቱ መወጠንያ አንዲት ከሲታ አስቀያሚ ቀራጭ ቆማበታለች ። ከጐዳኖቹ ላይ ግን በዚህ እለፉ እንዳትለፉ እንቆ እንድትገፉ የሚሉ አድፋም ልብስ የተጐናጸፉ ቆንጆዎች ሞልተውባቸዋል።

ይኸንን ሁሉ ካስተዋልን በኋላ ልዑል ምክራቸውን ሲያቋርጡ «እስከ ሚቻላቸው ጣሩ» በማለት እንዴሁ አስበንለመጣር እንዴህ ስንል ቆረጥን ፤ የዜችን የዚያችን አሳቹ አድፋም ቆንጆ ምክር ሰምተን ያስቀያሚዋን ቀራጭ ክፋት ፈርተን ወለል ባለው ጐዳና ሂደን ከጨለማ ከመግባት ያች አስቀያሚ ቀራጭ እንኳ ከብርሃን ላይ ብታስቀረን ይሻላል ። መቼም የተፈጠርነው ለሞት ነው ፤ እነዚያም ቆሻሻ አራዊቶች ቢያስቀሩን የሞት ትራችንን መውጣታችን ነው እንጂ ሌላ አዲስ ነገር አይመጣብንም ከብርሃን መፍለቂያ ከተማም ብንደርስ ያለመፋቀር ድብልቅልቅ ያጠፏቸውን ከዕንቁ የሚበልጡትን የሰሎሞንን ጥበቦች እንደ ልዑል ምክርና ምኞት ከፍ ያለውን አምጥተን አገራችንንና ህዝቧን እናበራለን ስንል መንገዳችንንለመጀመር ተነሳን ።

አዬ ፡ ጉድ ፤ እንዴት ። እንዴት ። እናንት ቂሎች እንዴህ ተቃቅፋችሁ ቀረጥ ሳትከፍሉ በብርሃን መንገድ መሄድ መች ይሆንላችኋል ? ስትል ያች ከሲታ አሮጊት በመንገዱ ላይ ተንፈራጣ አላሳልፍ አለችን ። ይኸን ቢሰማ ከመኃል ዘሎ ኃይለኛው ትንሹ ወንድማችን በዩ እኔን ውሰጂና እነሱን አሳልፊአቸው ሲል ተሰጥቶ አደራችሁ ከጠፉት ጥበቦች ሁለቱን እንኳ አምጥታችሁ ለወንድሞቻችን ሁሉ አሳዩና የቀሩትን ለማግኘት ተማሩ እንማር በሉ እንድትታፈሩ እንድትከበሩ እንድትፈሩ እንድትጠነከሩ ተማሩ ተማሩ እንማር እንማር በሉ ሲል በማትጠረቃዋ ሴት እጅ ተይዞ ነፍሱ ከሥጋው ስትለይ ያለውድ በግድ ወንድማችንን ኃይላችንን ተነጥለን ኢያዘን ኢያለቀስን መንገዳችንን መጓዝ ጀመርን ።

እነዚያም አስቀድሜ አራዊቶች ሲያስፈራሩን እነዚያ ቆንጆ አሳቾች ሲወቅሱን በሚያጸናው ምክርና በቆራጭ አንጀታችን ጠንተን መከራችንን እየበላን ችግራችንን እየጠጣን ወደኋላ ሳናሸሽግ ወደ ጐን ሳናዘነብል ተጉዘን ተጉዘን አልፎ አልፎ ይታዩን ከነበሩት አዳራሾች አጠገብ ስንደርስ በሩቁ ብርሃን የሚፈልቅበት ከተማ ተንጣሎ በነጸብራቁ ኢያሰከረ ሲጋየን ስናደንቅ እንዴት ወዴት አረወዴት እናንተ የኢትዮጵያ ልጆች ከብዙ መቶ ዘመን በፊት የጣላችሁትን ጥበብ ከብርሃን ከተማ ብታገኙ እነአጅሬ መቼ ትቻሉና ነው ። ያለጥበብ እንኳ አልቻል ብላችኋል ሲል እንደ ቀስት ተወርውሮ ያንዲት አዳራሽ በረኛ ዘንዶ በወገባችን ሲጠቀለል እኔ ፈትለክ ብዬ አመለጥሁትና ሸሽቼ ወዳዳራሹ ገባሁ ። ወንድሜ ግን ቁመቱ ዘለግ ያለ ነበርና ለማምለጥ የማይሆንለት ሆኖ ተይዞ ቀረብኝ አሁን ተሽለኩልከሽ ብታመልጭኝ ለጭልፊት ነግሬ አስጠልፍሻለሁ ሲዝትብኝ ኢያዘንኩ በመከራ ውስጥ ያለውን ወንድሜን መጨረሻ ለማወቅ ሳዳምጥ እንዲህ ኢያለ ሲጮህ ሰማሁት ።

መ ሥ ወ

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል ።

ጥያቄና መልስ

ከሁን ቀደም በሶስተኛ ዓመት በቁጥር ፳፫ በ፫፻፶፰ ገጽ በምስተኛው መስመር ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ኢትዮጵያ አገራችን በውስጧ ያለ ብዙ ዓይነት እህል ነቀዝ በልቶት ሲፈስ ከህንድ እስያ የስንዴ ዱቄት መፈለጓ ምክንያቱ ምን ይሆን ሕዝባችንስ እህሉን የሚሸምትበት አጥቶ ክብር ማጣት የተነሣ ድህነት አጥቅቶት እያየነው ባንድ ጆኒያ ዶቄት በ፳፰ ብር ሸምተን መብላታችን ብልሐቱ ምንድር ነው ወይስ ቀርቡን ሩቅ ብዙውን ጥቂት አስመስሎ የሚያሳየን ያለ ስረ ነገሩ ምን ይሆን ኢትዮጵያስ በዚሁ ነገር ራሷን ትችላለች ወይም አትችል ራሷን በመቻልስ ምን ማድረግ ያስፈልጋታል ብዬ ስለጠየቅሁ መልሱን አግኝቼ ነበር ስለሆነ ግን በችግር ለሚያገኙት ሀብታሚቱ አገራችን ባንድ ሁለት ሰው ብቻ ተነግሮላት ይብቃ ማለት አንድ መለኪያ ውሀ ከህንድ ውቅያኖስ እንደመጨመር ወይም ከአትላንቲክ ውቅያኖስ አንድ መለኪያ ውሀ እንደመቅዳት ያህል መስሎ ስለ ታየኝ ይኸውና የጥያቄዬን መልስ አቅርቤአለሁና አንባቢዎች ልብ በሉ ። እውነትም አቶ ደነቀ ተክለ ጊዮርጊስ እንዳሉት ሁሉ በኢትዮጵያ ውስጥ የመንገድ ብረት ተዘርግቶ ማገናኛ ባቡር ባለ መኖሩ ነው በኢትዮጵያ ውስጥ ተመላላሽ ማገናኛ የምድር ባቡር ተዘርግቶ ኑሮ ሁኖ ቢሆን ግን እንኳንስ ኢትዮጵያ ከህንድ እስያ የመጣ አሥር ጊዜ የተነገደበትን የስንዴ ዶቄት ልትበላና የሚበቃትን አስቀርታ የተረፈውን አቅንታ ልክ ባሥር ዓመት እንደ በለጠጉ አገሮች እንደምትሆን ጥርጥር አልነበረበትም ። ስለሆነ ግን ከፈሰስ አይታፈስ እንደሚባለው ተረት ነውና በስንቱ ያለፈውን ጊዜያችንን ገልመጥ ብለን ብንመለከተው የትናየት ድብ ከሄደ ውሽጮኽ እንደሚባል ተረት ሁሉ ልክ እንደዚያ ሆኖ ታዬን ። ነገር ግን ያለፈውን ዘመናት አልፈዋል ስለሆነ ግን ጊዜ ያሳለፈው ጊዜን ያሠራዋልና ስለ ምድር ባቡር የጥቅም ነገር አካሄድ በሚከተለው መስመር ልብ በሉ አስተውሉም ፡ የምድር ባቡር በኢትዮጵያ ው

ስጥ አዲስ አበባ ወደ ወለጋ ጠረፍ ወደ ጋምቤላ ወደ ዓድዋ ወደ ጐንደር፣ ጐጃም ወረሞ ከፋ እንዲሁ በመሰላ ጠረፋችን ሁሉ የምድር ባቡር የዘረጋን እንደሆን የጥቅሙ ነገር የሚከተለው ነው ማለት በየጁ አውራጃ ጀምሮ እስከ ወሎ ጋላ ቤት ድረስ ጐጃም ጐንደር ጭምር ያለ ህዝብ ማርና ቅቤ እህልና ከብት በግና ፍየል ተርፎት ሳለ ተመላላሽ የምድር ባቡር ባለ መኖሩ የሚገዛለት አጥቶ በድህነት የሚኖር ሕዝባችን ስንት ይመስላችኋል ። ደግሞ ከኰርም ጀምሮ ማኽል ትግሬ እስከ ወልቃይት ድረስ ያለ ሕዝባችን ብር ተርፎት ሳለ እህልና ማር ቅቤ ስጋ እንዲሁ የመሰለ ሁሉ ከብሮበት ብሩን ይዞ ሲያበቃ መብልና መጠጥ ሲመኝ የሚኖር ህዝብ ስንትና ስንት ይመስላችኋል ። ስለዚህ በኢትዮጵያ ውስጥ የምድር ባቡር የተዘረጋ እንደሆነ የኢትጵያ ህዝብ ያለውን ይዞ የሚያስፈልገውን ለመግዛት ባሰበ ጊዜ የሰስት ወር ጐዳና በዘጠኝ ቀን አልቆለት ፍላጐቱን አግኝቶ ባንድ ወር ሰባት ጊዜ የተገበያየ እንደሆን የተራበ ጐርሶ የታረዘ ለብሶ ሁለቱንም በሀብት እንዲቀላቀሉ ጥርጥር የለበትም ። ማለት ከጋላ ቤት ወደ ትግሬ የሚሄድ ባቡር ማር ቅቤ እህል ከብት በሬ ፍየል መውሰድ ይገበዋል ፡ ከወሎ ሲደርስም እንዲሁ ማርና ቅቤ የመሰሉ ከየጁ ሲደርስም በርበሬ ቆዳ ጥጥም እንዲሁም የመሰሉ ጭራሽ እንደርታ ሲደርስ ጨውና ስንዴ ባሩድ ዲኝ መሽከም በጣም ያስፈልገዋል ።

ስለዚህ እነኝህ አሁን የቈጠርናቸው የንግድ እቃዎች ሁሉ በትግሬ ገብተው ሲሸጡ የመቶውን ብር አምስት መቶ ብር እንደሚሆን ማንም አይስተውም ። ደግሞ ባቡሩ ከትግሬ ወደ ጋላ ቤት ሲመለስ የባሕር ዓይነት እቃ ጨርቃ ጨርቅ የመሰለ የሚያስፈልግ ሁሉ ያገራችን ልብስ ጥጥ በጥጥ የተሠራ ዳጉሳ ማሽላ ጥጥ ሰሊጥ ይህን የመሰለ ሁሉ መያዝ ነው ። ደግሞ ከንደርታ ሲደርስም ጨው አሸዋል ባሩድ ዲኝ መያዝ በግድ አለበት ደግሞ ከየጁ ሲደርስም የቀረውን ተወት አድርጎ ጥጥን ብቻ አብዝቶ መያዝ በጣም ያስፈልገዋል ስለዚህ አሁን የቈጠርናቸው የንግድ ዓይነቶች እንደዚህ ብለው ከሚያስፈልጋቸው አገር ባንድ ወር ውስጥ አምስት ጊዜ ስድስት ጊዜ የተመላለሱ እንደሆን ኢትዮጵያ በጣም እንደምትበለጥግ የታወቀ ነገር ነው ። አሁን ግን የንግዱ አካሄድ አሁን እንዳልኩት ነውና አገሩንና ያገሩን እቃ በዝርዝር ለመጥራት ወይም ለመጻፍ በግድ አያስፈልግም ማለት አኳሆኑንና አካሄዱ አንድ ነውና ነገር ግን እግዚአብሔር ይቅር ብሎን የመንገድ ብረት ለመዘርጋት ያበቃን እንደሆነ የብረት መንገድ ፋብሪካና የእንጨት ፋብሪካ የምናቆምበት አላጄ የሚባል እንደ ድሬዳዋ የተመቸ ቦታ አለን አላጄ ማለትም ማዶ ጨው አልፎ የሚገኝ ትልቅ ተራራ ነው ደግሞ ከአላጄ ተራራ የሚፈልቅ ውሀ እስከ አንድ መቶ አሥራ ስድስት የሚሆን ኪሎ ሜትር ፈሶ ሄዶ የሚያጠጣው አገርና በርሱ የሚጠቀሙ ሰዎች አእላፋት ናቸው ደግሞ ከአላጄ ከበቢ ያሉ አገሮች ሁሉ ጥድና ወይራ የሞላባቸው ናቸው ስለዚህ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሁኖ አላጄ ላይ የብረት ፋብሪካና የንጨት ፋብሪካ ለማቆም የበቃን እንደሆን የአላጄ ውሀ ሶስት ዓይነት ጥቅም እናገኝበታለን ፤ አንደኛ የብረት ፋብሪካ ከፋፋ ላይ አቁሞ መኪናውን በውሀ ማስኬድ ነው ። ሁለተኛ የንጨት ፋብሪካ በበታቹ አቁሞ መኪናውን በወሀ ማስኬድ ነው ፤ ሶስተኛ በመኪኖቹ ውስጥ ሲሠራ የዋለ ወሀ እንደሚገባ በመሀንድስ አስበጅቶ እንደ ጥንተ ልማዱ ወደ ባላገር በቦይ መልቀቅ ነው ስለዚህ በኢትዮጵያ ውስጥ የምድር ባቡር የተዘረጋ እንደሆን ሕዝብና ሕዝብ በተሎ ተገበያይቶ በፍጥነት ይበለጥጋል መንግሥትም ተመላላሽ ነጋዴ ሲበዛለት ገቢ ገንዘብ ይበረክትለታል ሽፍታና ቀማኛም እያነሰ ይሄዳል ኢትዮጵያም ደግሞ እንዚህ ያለውን መልካም ነገር እየተመለከተች ብትሠራ ነው የሚያልፍላት እንጂ እህሏን ከጕድጓድ ቀብራ የህንድ እስያ ደሴት እንደ ሱካር ገባያ ገዝታ በመብላቷ ጉዳቷ እንጂ ጥቅሟ መስሎ አይታየኝም ። ስለሆነ ግን አንዱን የሚያውቀውን አንዱ አያውቀውምና ለኢትዮጵያ የሚጠቅም ሌላ መንገድ እንዳለ አስፍታችሁ አርማችሁ በብርሃን እንድትገልጹልን በብዙ ማክበር እንለምናችኋለሁ ።

ተማኑ ሮምሃ ፤

ሞላ መሐመድ ዓሊ አብዱላ ሁሴን ራሱልጂ ።

ሞላ መሐመድአሊ አብዱላ ሁሴን ራሱልጂ በተወለዱ በ፷፱ ዓመታቸው ፲፱፻፳ ዓ ም በታሕሣሥ ፳፱ ቀን ማረፋቸው በብርሃንና ሰላም ፬ኛ ዓመት ፩ኛ ቍጥር ተነግሯል እንዲሁም ሞላ መሐመድአሊ ኩባንያ በአዲስ አበባ ከነ ማ ያለው መሐመድ ዓሊ ኩባንያ ቤት ዋና ወኪል ነው በኢትዮጵያ ውስጥ ሁላሳ

አመት ሙሉ እየመጡና እየሄዱ በብዙህ አድርገው ለኢትዮጵያ አገልጋይ ነበሩ።የመሐመድ ዓሊ ኩምፓንያ ቤትንም ዋና ወኪል ሆነው ያቀኑ እሳቸው ነበሩ ስለማገልገላቸውም በ፲፱፻፳ ዓ ም ከኢትዮጵያ መንግሥት ኒሻን ተሸለሙ ይልቁንም ከሁሉ ለኢትዮጵያ በጣም አገልጋይ ነበሩ ።

በኢትዮጵያ ውስጥ ንግድ አቁመው ስላገለገሉ አዲስ አበባ ያለውን ቤታቸውን ለማየት ፈቃዳቸው ሆኖ አጐታቸው ሞላ መሐመድዓሊ ሼህ ሸሪፍዓሊ ከቦምቤይ አገራቸው ተነስተው አዲስ አበባ በህዳር ፳ ቀን ፲፱፻፳፮ ዓ ም ገቡ በዚህም ቀን ሞላ መሐመድ ዓሊ አብድልሁሴን ራሱልጂ አጐታቸው አዲስ አበባን ለማየት ስለመጡላቸው በጣም ደስ ብሏቸው ተቀበሏቸው ሞላ መሐመድዓሊ አብድልሁሴን ራሱልጂም ሀሳባቸው ከኢትዮጵያ ወደ ሀገራቸው ከአጐታቸው ጋራ ሊመለሱ ነበር አጐታቸው በመጡ በስምንት ቀናቸው ቤት ለማሳየት አቃቂ ወፍጮአቸው ሄደው ውለው በአስራ ሁለት ሰአት ተመልሰው በዚያው ቀን ኒሞኒአ በሚባል በሽታ በታመሙ በ፰ ቀናቸው ዓረፉ

ስለ በዓለ ጥምቀት አከባበር

ከቀደም አባቶች ጀምሮ በገራችን የጥምቀት በዓል ክብር ሁለት ቀን እንዲደረግ የተለመደ ነገር ነው ።መጀመሪያው ቀን ከተራ ይባላል ከተራ የተባለበትም ምክንያት በዚህ ቀን መኳንንቱና ካህናቱ ወደ ወንዝ ወርደው ፈሳሹን ውሃ ባሕር እንዲሆን ከትረው በወንዙ ዳር ድንኳን ተክለው የሚያድሩ ስለሆነ ነው ይባላል ።በዚህም ልማድ ዛሬ ወደማታ በመላ ኢትዮጵያ ያሉ ታቦታት ወደ ወንዝ ወርደው ያድራሉ ይህም መደረጉ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮርዳኖስ ሊጠመቅ ወደ ዮሐንስ እንደሔደ ለማሳሰብ ነው ።

ጥር ፲፩ ቀን ዓርብ ዕለት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የጥምቀቱ በዓል ይከበራል ስለ በዓሉ አኳኋንም በሚከተለው ቁጥር እንጽፋለን ።

ማስታወቂያ ፤

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
ድጓዋ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፫ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር	፱ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ብር
ጎሐ ጽባሕ	፭ብር
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፪መ
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ	፩ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ	፩ሩብ
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ብር
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ተኩል
የቁጥር ትምርት	፩ብር
ያማሪኛ ሰዋስው	፩ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	አላድ
ወዳጀ ልቤ	፫ሩብ
አጭር የዓለም ታሪክ	አላድ
ያማሪኛ ፊደል	ሩብ
አሳብና ምኞት	ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት	ሩብ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር	፪መ

ያዲስ አበባ ገባያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲ ብር ተሩብ
የሲዳሞ	፩	፱ ብር ከሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፪ ብር ከ፫ሩብ
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፩ ብር ከ፫ሩብ
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺ ብር ።
በሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፳፩ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፳ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፯ ብር ተኩል
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፰ ብር ተኩል
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፵፪ ብር
፡፡ ባለሰይጣን	፡፡	፻፵፯ ብር
፡፡ ባለ ድመት ፡፡		፻፵፪ ብር ፡፡
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻፳፫ ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፻፴፭ ብር
ባለ አንበሳ	፡፡	፻፵፯ ብር ።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፳፯ ብር ።
ቻይ	፩ ነጥር	፲፪ መ

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ ከ፵ ሳንቲ
አንድ ብር	ሊሬ ፱ ከ፲፯ ሳንቲም
በአንድ ጊኒ	፱ ብር ከ፺፫ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፬ ብር

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ፡፡

COGNAC S&E&A.METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ማስታወቂያ ።

ሺብሮሌ አቶሞቢል ።
በኢትዮጵያ ወኪል ።
ሔ ሜ ዜርቦስ ኩምፓንያ ።

Automobiles CHEVROLET
AGENTS
H. M. ZERVOS & Cie.



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የሚባል ባለ ፈ'ስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳየ ስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያየዚህአቶመቢልበተለይወኪል"አረቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው። ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፣በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፣ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል ።



ማስታወቂያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጅ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልካም ባርኔጣ ፤ ሽቱ ፤ ለስዮን ፤ አድከሎኝ ፤ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፤ ከኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፤ ከፈይ ምንጣፍ ፤ ደግሞ በያይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላ ከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስመጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሸምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክታችኋለሁ ፤ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ዓለም

ዓለም የወርቅ ጥልፍ ሥራ ሁሉ በውስጥ ብር ሆኖ ይሠራል ።

ኒኮላ ።

ማመልከቻ ።

በብርሃንና ሰላም ውስጥ ማስታወቂያ ማሳተም የሚፈልጉ ነጋዴዎች እስከ ፈለጉት ጊዜ ድረስ ባማርኛም ሆነ በፈረንጅ ቋንቋ በርካሽ ዋጋ እንደምናትምላቸው እናስታውቃቸዋለን

ጉድዬር ግዙ





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያደጥውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው ። በሌላጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ፤ ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አራተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፬
4 me ANNÉE № 4

ሐሙስ ጥር ፲፯ቀን ፤ ፲፱፻፳ ዓ ም ።
JEUDI 26 Janvier 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት
Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d'Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix ".

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ያስራ ዘጠኝ ገጽ ተከታይ

እውነተኛውና አሰተኛው ሥልጣኔ በሥልጣኔውም ስም የገቡብን ልዩ ልዩ ጕዳቶች ። እንዲሁም የከተማው ሕይወት በጤንነት እንዲጠበቅ የሚያሳዩ ምክሮች ።

፩፤ ብዙ ዓይነት የርኩሰት በሽታዎች ።

እንዲህ ያሉቱ በሽታዎች ከቀድሞ ዘመን ይልቅ አሁን ባገራችን ይልቁንም በከተሞቹ እንደ ተዘረጉ ሁሉ የሚያውቀው ነገር ነው ። እኒህም በነፍስ ብቻ አይጐዱም ። አስቀድመው በሥጋ ይጐዳሉ ።ቀጥሎም በነዚሁ በሽታዎች ባንዱ የተበላሸ ሰው ብቻውን አይጐዳም ። ሰው በራሱ ጕዳትን የሚያመጣ ክፉ ጕዳቱን ለገዛ ራሱ ወስኖ ማስቀረት የሚችል የለም ። ስለዚህ ሰው በሕይወቱ ለሰው ጠቀሜት ወይም ጕዳት ሳያመጣ አይቀርም ። ብዙዎች ግን ባደረጉት መጥፎ ነገር የገዛ ራሳቸውን ብቻ የሚጐዱ ይመስላቸዋል ። እንዲህ ያለ አሳብ ግን ቀን አይደለም ። የሕዝብን ሕይወት አንድነት ታሪክ ይህን ይገልጥልናል ። ሰው በሆነው ነገር ጕዳቱ ለራሱ ብቻ ቢሆን ይህ ሁሉ ክፉ ከወዴት መጣ? ባል ሚስቱን ሚስትም ባልዋን ወላጆችም ልጆቻቸውን ይበድላሉ ። በሌላዎች ሰበብ በነፍሳቸውና በሥጋቸው የተጐዱቱ ማን ይቈጠራቸው ። ይህ ሁሉ በሽታ በዛሬው ዘመን ሐኪሞቹ ሊለዩት የሚያኋቸግራቸው ያለ ካንዱ ወደ ሁለተኛው እየተራባ ይሄዳል ። አንዳንዱ በውድና በመተባበር ሌላዎቹን ግን ባለማሰብና ባለማወቅ ይጠጋባቸዋል ። እንያ በነዚሁ በሽታዎች የተበላሹም የገዛ ራሳቸውን ስላላከበሩ የሌላዎችን ጤንነትና ንጽሕናን አያከብሩም ።

የሚገርመውም ነገር እንደነዚህ ያሉትን በሽታዎች ፤ ሰዎች ከሚጸየፉዋቸውና ከሚሸሹላቸው ይልቅ እንደ ጌጽና እንደ ክብር አድርገው ሲያዩዋቸው ነው ።በዚሁ ምክንያት እውነት የሚጐዱ መሆናቸው እንደሚገባ ያወቃቸው የለም ። ስለዚሁ ሕዝባችንን እንዲጠበቅ እነዚህን በሽታዎች በጣም እንዳይዘረጉ ጦርን እናንሳባቸው ። ሕዝባችን በዚህም በዚያም የሚያጠፉ ምክንያቶች ብዙዎች ናቸው ። ሁላቸውንም ማየት ያስፈልገናል ይልቁንም ጋለሞቶቹን ሴቶች በጣም መለየት ይገባል ። በሠለጠኑቱ ሕዝብ እያንዳንዱ ሰው ጤንነቱን የሚጠብቅበት ጥቂት ዕውቀት የሌለው እምብዛ አይገኝም በወላጆቻቸው ቤት ጀምረው ይማሩታልና ። በሕዝባችን ግን ጤንነትና ሕግጋቶቹን ምን እንደሆኑ አንዳች የማያስብ እንዲህ ያሉ በሽታዎች በማኸሉ ሲሰራሰሩ የሕዝባችን መጨረሻ ማሰብ አያንቀጠቅጥምን ? በዚሁ የሐኪምነት ሥራና ምክር የአስተማሪዎችም መግለጫ ከበታቻቸው ላሉ ወጣቶች የመንግሥትም እርዳታ ብዙ ያስፈልጋል ሕዝብ ዓይኖቹን ሊከፍት የገዛ ራሱ ጕዳቶችንም እንዲመለከት ። እንዲህ ያሉ በሽታዎች ነውረኞች አጥፊዎች እንጂ የሚመሰገኑ እንዳልሆኑ ሊታወቁ ። በነዚህ በሽታዎች የተገዙ ስድብና ሐፍረት ብቻ ይገባቸዋል ። በነዚህ ልዩ ልዩ በሽታዎች የተበላሸ ሕዝብ ከሚወለደው የሚሞተው ከሚበረታው የሚደክመው እየበዛ የሕዝብም ቍጥር እያነሰ ይሄዳል ። ያለውም ሕዝብ ብዙ ደካማ ይሆናል ወደ ዝቅተኛ ኖሮ የሰውን የወገን ባሕርይነት ወደ ማጥፋት እስኪደርስ ይሆናል ። በመጨረሻውም ነፃነቱን ለመጠበቅ ኃይል አይቀርለትም ። የሥጋና የነፍስ የመንፈስም ኃይሎች ሁሉ ይጠፋሉ ። ጭንቀትን ችግርንም ሁሉ ለመታገሥ ብርታት ያጣል ፡ የዚህ ጥፋት እያንዳንዱ ቢታወቀው ።

፪፤ ነፍስንና ሥጋን የሚጐዱ ልዩ ልዩ ጨዋታዎች ።

እኒህ ጨዋታዎች ከዚህ ቀደም ባገራችን አይታወቁም ኑርዋል ። በሥልጣኔ ዘመን በሚባለው ብቻ ጀምረዋል ። ሥልጣኔ

ይህን ጉቶ አመጣብን ? ፍሬውን ጥለን ቅርፍቱን ። እረእንጃ እንዴህ ያሉ ነገሮች የሥልጣኔን ቅርፍት ሊሆኑ አይበቁም ። ቅርፊቱና ፍሬ በባሕሪያቸው ይገናኛሉ።እነዚህ ነገሮች ግን ከሥልጣኔ ጋራ ምንም መገናኘት የላቸውም ። ደግሞም አእምሮ ያላቸው የሚባሉ ሰዎች ወደነዚሁ ጨዋታዎች ሲገሰግሱ ብዙ ያስገርማል ። እነዚህ ጨዋታዎችስ ምንና ምን ናቸው ? ቴያትር ሲኒማ ፤ ሮሊት ወይም ቁማር እንደነዚህም የመሰሉ ናቸው ። ሲኒማ መንፈሳዊነት ሊጐዳ በማይቻል መንገድ በእጅግ ጥንቃቄ ተወስኖ ሲደረግ በጠቀመ ነበር ። ከዚህ ሕግ ሲወጣ ግን እንደ ሌላዎቹ ጥፋትንና መርገምን ብቻ ያወርዳል ። ሰው በእንደነዚሁ ጨዋታ ይልቁንም ወጣቶችን ምንና ምን ይማራሉ ? በዚሁ የብዙዎች ወጣቶች ታሪክ የተማሩትን ይመሰክራል ። ከዚህ ጋርም ብዙዎች ክፎች መጻሕፍት ሮማንሶች የተባሉ ይቈጠራሉ ። እንዴህ ያሉቱ ጨዋታዎች ስርቆት መግደል ዓመጽ ተንኰል ዝሙት ትዕቢት ስስት እንዴሁም የሚመስለውን መንገድና አደራረግ በተቀር ምኑን ጠቀሜታ ይገኝባቸዋል ? ቀን አሳቢ ይህን ነገር እሉ ሊለው አይሆንለትም ። ሰውም ሁለንትናው በሕርዩ ከተጐዳ የሚያገኘውን ጠቀሜት በየት እኩል ነው ? ስለዚህ ይህን ነገር እዳይዘረጋ እጅግ መጨቈን ያስፈልጋል ። በዚህ ነገር የመንግሥት ጽኑ ደምብና ብርቱ መጠባበቅ በጣም የተገባ ፈውሱ በሆነ ። እኛ የሚያስፈልገን ልዩ ልዩ ሥራ መልመድ ነው ። የሮሊንና የቁማሩ ጨዋታ ግን እንዲያው በፍጥነት እንዲቀር ማድረግ እንዲገባ ስለ ሕዝባችን ጉዳት ጩኸታችን እናሰማለን ። እንዴህ ያለ ጨዋታ ቅርብ በዓለሙ መንግሥታት ውስጥ ክልክል ነው ። በኢትዮጵያችንም በፍጥነት እንዲያው እንዲቀር በተስፋ እንጠብቃለን ። የሕዝባችን ሥልጣኔ ይሄው ሆኖ ቢቀር ድንቍርናን ልንመርጥ ግድ ይሆንብናል ። በዚሁ ነገር ሕዝብ በትምሕርትና በተምክሮ ያላስተዋለ ፤ የጸና ሕግ ሊጠብቀውና ሊጐበኘው ያስፈልገዋል ። ጕዳቶቹንና ጠቀሜቶቹን በትክክልነት ወደ ማወቅ ሲደርስ ግን እያንዳንዱ ይህን ጅልነት ሊያደርግው አይሻም ። እንዴህ ያለ ዕውቀት እስኪደርሰው ግን ረድኤት ያስፈልገዋል ።

በምንም በምንም ብሎ በመጨረሻ መጥፎ ሥራውን ወዴት እንዳደረሰው ሳይረዳ የሚቀር የለም ። ዳሩ ግን ምን ይሆናል ዘመኑ በከንቱ አልፎአልና የሚሻሻልበትን ጊዜና ኃይል እንግዴህ እንደማያገኝ አውቆ በኃዘኑ ይጠፋል ። ባያውቅም በድንቍርናው ተሸፍኖ ይጠፋል ። ስለዚህ ጊዜ ሳለ ሁሉን ማድረግ ። «ደመና የሚጠብቅ አያጭድም» ሊያጭድ የሚፈልግ በድርቁ ጊዜ በመታመን ዘሩን ሊዘራ ይገባዋል ።

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ደተታማል።

ማመልከቻ

ለተወለዱ ሕፃናትና ለሞቱ ሰዎች መጻፊያ ስፍራ እንሰጣለንና ለእንግዲሁ ልጅ የወለደ ሰው ስሙንና የባለቤቱን ስም ልጁም የተወለደበትን ቀን ቢያስታውቀን እንደሚሆን አድርገን በጋዜጣ እንጽፍለታለን እንደዚሁ ደግሞ ሰው ቢሞት ስሙንና የሞተበትን ቀን ካስታወቁን በጋዜጣ እንጽፍላቸዋለን

ስለ ጥምቀት በዓል አከባበር።

ጥር ፲፩ ቀን ከጧቱ በ፩ ሰዓት በልዑል አልጋ ወራሽ ግቢ ከውሥጥ ጀምሮ እስከ ውጪ እግረኛና ፈረሰኛ ወታደር ከመንገዱ በግራና በቀኝ ሆኖ ተሰልፎ የልዑል አልጋ ወራሽ መውጣት ይጠባበቅ ነበር ። በዚያን ጊዜ ነጋሪት መችዎችና ጋሻ ጃግሬዎች ደረሱና የልዑልን መውጣት የሚያመለክት የነጋሪት ድምፅ ተሰማ ። ወዲያውም ልዑል የወርቅ ዕቃ ባስጨነቃት በቅሎ ተቀምጠው ወርቅ ጥላ ተይዞላቸው በክቡራን መኳንንቶቻቸው ታጅበው ብቅ ባሉ ጊዜ ተሰልፎ የነበረ እግረኛና ፈረሰኛ ወታደር ጡሩምባ እየተነፋ የሚገባ ሰላምታውን ሰጠና ሰልፉ ልዑልን አጅቦ ወደ ጥምቀተ ባሕር ወረደ ።

ልዑልም ወደ ወረዱበት ጥምቀተ ባሕር አድረው የነበሩ ታቦታት ከዚህ ቀጥለው ያሉት ናቸው ። ሥላሴ መድኃኔ ዓለም ። የግቢ ኪዳነ ምሕረት ገብርኤል ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ ጊዮርጊስ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ናቸው ፤ በከተማው ያሉ ሌሎች ታቦታት ግን በየአውራጃቸው ባለው ወንዝ አድረው ነበር ። ብፁዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ አስቀድመው በነግህ ወደ ባሕር ወርደው በተሰናዳው ቦታ ተቀምጠው የልዑልን አመጣጥ ይጠባበቁ ነበርና ልዑል በመጡ ጊዜ ሥርዓተ ጥምቀቱን አድረሰው ውሃው ተባረከና መላው ሕዝብ ተጠመቀ ።

፪ ሰዓት ሲሆን ታቦታቱ ከደሩበት ተነሡና ሰልፉ ግራና ቀኝ ሆኖ ወደ ጃንሜዳ መጓዝ ጀመረ ። በዚያን ጊዜም የሰዉ ብዛትና የሰልፉ ማማር እጅግ ያስደንቅ ነበር ። እንደዚሁ ሆኖ ጃንሜዳ በደረሰ ጊዜ አጋፋሪዎቹ ሕዝቡንና ባለሰልፉንም ወታደር በሥርዓት እንዲቆም አደረጉት ።

ልዑልም አምሮ በተሰናዳው አጐበር ውስጥ ተቀመጡ በግራና በቀኝ የውጭ አገር መኳንንቶችና የኢትዮጵያ መኳንንቶች እንደ ማዕርጋቸው ተቀምጠው ነበር ። በዚያ መከከል ካህናቱ የጌጥ ልብሳቸውን ለብሰው ባማረ ዜማ እየዘመሩ ሲያሸበሽቡ እጅግ አምረው ታዩ ወረቡም በተፈጸመ ጊዜ ብፁዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ምሥጢረ ጥምቀትን የሚገልጽና የበዓሉን ነገር የሚያሳስብ ስብከት ሰብከው ሕዝቡን ባርከው መርቀው አሳርገው አሰናበቱት ። ከዚህ በኋላ ታቦታቱም ወደ እየቦታቸው ተለያዩ ። ልዑል ግን በግቢ ያሉትን ታቦታት አጅበው በክብር አስገብተው በታላቁ አዳራሽ ለሕዝቡ ሁሉ ሙሉ ግብር አድረገው በትልቅ ደስታ ሲበላ ሲጠጣ ዋለ ፤ እንዲህ ሆኖ የጥምቀት በዓል በደስታ ተፈጸመ ።

ስለ ቃና ዘገሊላ በዓል መታሰቢያ ።

ጥር ፲፪ ቀን ጧት ሲነጋ ነጋሪት እየተጐሸመ መለኸትና ጡሩምባ እየተነፋ ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በማረ አጀብ ሆነው ቅዱስ ሚካኤል ወደ አደረበት ወደ ቀበና ወንዝ ወረዱ ፤ በዚያን ጊዜ የተሰበሰበው ሠራዊት የጽዳቱና የብዛቱ ነገር እጅግ ያስገርማል ። ከብዛቱም የተነሣ አንዱ ባንዱ ትክሻ ላይ እየተንጠላጠለ ወደ ታቦቱና ልዑል ወዳሉበት ለማስተዋል ሲጨናነቅ ለተመልካቹ ሁሉ ያስደንቅ ነበር ።

በሙሴ ዮሴፍ ስቴደሌኔር ጀርመን እንሰሴ ፎቶግራፍ አንሽ ።

ወታደሩም ታቦቱና ልዑል ባሉበት ሜዳ ዙሪያ ክብ ሆኖ ተሰልፎ በዚያ መካከል ካህናቱ እንደሚገባ እያሸበሸቡ ዘመሩና ታቦቱ ወደቦታው ተነሥቶ ጉዞ ጀመረ ። ቦሌ ሜዳ በደረሰ ጊዜ ግራና ቀኝ አንደኛ ረድፍ ሰልፍ የተማረ ካኪ የለበሰ ወታደር ሁለተኛ ረድፍ መትረየስ አንጋች ዘበኛ በፊት በፊት ቀይ ከት የለበሱ ነጋሪት መቺዎች ቀጥሎ ነጭ ለባሽ ወታደር ቀጥሎ ጋሻ ጃግሬዎች ከዚያ ታቦቱ ልብሰ ተክህኖ የለበሱ ካህናትና መዘምራን አጅበውት። በመካከል ልዑል ወርቅ ጥላ ተይዞላቸው በፊት በፊትም የልፍኝ አሽከሮች በሚያማምሩ ፈረሶች ሆነው

ከልዑል በኋላም ክቡር ራስ ሥዩምና ክቡር ደጃዝማች ብሩ ነበሩ ። ከነሱ በኋላ በሁለት ክፍል ሆነው እንደ እየማዕርጋቸው ልዩ ልዩ ዓይነት ካባ የለበሱ መኳንንቶች ነበሩ ። ከዚያ በኋላ የልፍኝ ዘበኛ ቍጥር ስፍር የሌለውን ሠራዊት ወደ ኋላ እያገደ አረማመዱን አሳምሮ ይከተል ነበር ።

በሜዳውም መጨረሻ የከተማ ዘበኛ (ፖሊስ) ሰልፉን አደራጅቶ ይጠባበቅ ነበርና ባማረ ዜማ ሙዚቃ እያስመታ ሰላምታ ሰጠ በዚያን ጊዜ የሰልፉ ማማር ለተመልካቹ የሚያስደንቅ ልዩ ሆኖ ይታይ ነበር ።

ዘንድሮ ከወትሮ ይልቅ በልጦ መታየቱ ሰልፍ የተማረ ወታደር ስለ በዛ ነው ። ይኸውም ሊታወቅ ሰልፍ ያልተማረው ወታደር የተማረውን ወታደር ተመልክቶ አረማመዱ ልክ እንደተማረው ወታደር ስለሆነ ነው ። ይልቁንም ደግሞ በመንገዱ ዳር የሸተ አዝመራ አጥር የሌለው ነበርና ከዝመራው አንዲት ቅንጣት ሳትነካ የተማረው ወታደር አጥር ሆኖ ሠራዊቱ ሁሉ በጠባብ መንገድ በቀጥታ እንዲሄድ በማድረጉ እጅግ ይመሰገናል ። ይህም ላገሩ ድሀ እንዲራራና እንዲያዝን ያሰረዳል። ታቦቱም እንደዚህ ሆኖ ሰልፉ እንዳማረ ከቤተ ክርስቲያን ደረሰ ከዚያም ይጠባበቅ የነበረ ሕዝብ ልክ አልነበረውም ። ብፁዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስም ከዚያ ሆነው ይጠባበቁ ነበር ። ታቦቱ በደረሰ ጊዜ ልዑል በተሰናዳው ቦታ ተቀመጡ መኳንንቱም በግራና በቀኝ ተቀመጡ ።

በሙሴ ዮሴፍ ስቴደሌኔር ጀርመን እንሰሴ ፎቶግራፍ አንሽ ።

በዚያ መካከል ካህናቱ አሸበሸቡና ሲጨርሱ ብፁዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ሕዝቡን መርቀው አሳረጉና ታቦቱ ገባ ። ሰልፉም እንዳማረ ልዑልን አጅቦ ወደቤተ መንግሥቱ ተመለሰ እንዲህ ሆኖ የቃና ዘገሊላ በዓል አከባበር በሰላም ተፈጸመ ።

መቆርቆር

ታለሁበት ተነስቼ ዘመዶቼን ለመጐብኘት ወደ አዲስ አበባ ከተማ ስመጣ ብዙ ጋሎች ላሞቻቸውን እየነዱ ተአዲስ አበባ ከተማ ወደ ቤታቸው ሲመለሱ እመንገድ ተገናኘን ። ተነሱም አንዱ እንዴትዋልክ ተወዴት ትመጣለህ አለኝ ። እግዚአብ

ሔር ይመስገን እንደምን ውለሃል ፡፡ እኔስ ከወደ ኋላዬ እመጣለሁ እናንተስ ተወዴት ትመጣላችሁ አልኩት ፡ እኛማ ላሞቻችንን አዲስ አበባ ፍል ውሃ አምቦ አጠጥተን ወደ ቤታችን መመለሳችን ነው አለኝ ፡ አምቦውን ስታጠጡ ዋጋ እየከፈላችሁ ነው ወይስ በከንቱ ያለ ዋጋ ነው ፡ በከንቱስ አይደለም በላም ትሙን ትሙን እየከፈልን ነው ፡ ይህን ባለኝ ጊዜ በደቡብ ኢትዮጵያ በቦረና ወሰን በከንቱ የውጭ ዜጋዎች የሚያጠጡት ታሰበኝ አንድ የልብ ወዳጄ አጫውቶኝ ነበረና ፡ በቦረና በኢትዮጵያ ወሰን ውስጥ ብዙ ዔላዎች አሉ (ማለት የውሃ ጉድጓዶች) ከብዙዎችም የግማሾቹ ስም የሚከተሉት ናቸው ፡፡ ጉራር ደምቤ ኤልዲምቱ ሶሎሎ ኤል ዲምቱ ሐፎሌ በነኝህ ባምስቱ የውሃ ጉድጓዶች ጀምበር በሰረቀ ሳያቋርጥ ካምስት ሺ እስከ ስድስት ሽህ ከብት የሚጠጣበት ነው ፡፡ ይህም ደግሞ በያንዳንዱ የውሃ ጉድጓድ ነው ። የሚጠጣውም ከብት የውጭ አገር ዜጋ ከብት ነው ይህ ሁሉ ሲሆን ሳለ በላም ቤሳ እንኳ ክፈሉ ብሎ የጠየቀ የለም ይመስለኛል ፡ ካምስት እስከ ስድስት ሺ ያልኩት ከግመል ከፍየል ከበግ በተቀር ነው ፡፡ ዘግ ፍየል ግመል ውሃ የሚጠጣው ቁጥር የለውም።እንግዲህ እሌህ የውጭ አገር ዜጎች በኢትዮጵያ ውሃ በከንቱ ሲጠቀሙበት ፡ እነኝህ ጋሎች በላይ የተጻፉት ወንድሞቻችን ለአዲስ አበባ ከተማ ሕይወት የሆኑዋት በእህል በንጨት በሳር በኩበት በጭድ በስንበሌጥ በወተት በንቁላል ፡፡ ባመት አንድ ጊዜ ላሞቻቸውን አምቦ ለማጠጣት በላም ትሙን ሲከፍሉ ደግሞ ከዚህ ሌላ ላሞቻቸው የሚሰማሩበት ሳር ተባለ ቀላድ ላይ በብር ሲገዙ እረ ምነው ይህን እነኛ የውጭ ዜጋዎች የመርፌ ቀዳዳ የምታህል ጥቅም እንኳ ለኢትዮጵያ ያላደረጉ የኢትዮጵያን መሬት ሳርና ውሃ በከንቱ ማብላታቸው እንጂ ጥቅሙን የሚመረምረውና መርምሮ ለመንግሥት የሚያስገነዝብ ጠፍቶ ይሆናል ፡፡

አገራቸው ኢትዮጵያ ጥቅሟን አግኝታ በሰላም እንድትኖር በተፈጥሮም አንድ ከሚሆኑዋት ጓደኞቿ ጋር እንድትተከከል አጥብቀው የሚናፍቁ በውስጧ የሚገኝባትን ነገር ጽፈዋል ። እንዲሁም አቶ የሺ ጥላ ማሬ አሁን በቅርቡ ቀን በ፫ኛው ዓመት ቁጥር ፺፭ ገጽ ፫፻፺፬ እ፫ኛው ፓራግራፍ አሓዝ እስከ ገጽ ፫፻፺፭ ከሁሉይልቅ ያገር ነገር ይቆጫል ያነገበግባል በሚል መግብያ የጻፉትን አይቼ እንዴት በጣም ያቃጥላል አልኩ ያቃጥላል ያልኩበትም ነገር አቶ የሺ ጥላ ማሬ እንደጻፉቱ ሁሉ ቀጥሎ የሚጻፈው ነው ኢትዮጵያ ተወላጅ ልጆቿዋ ብዙዎች ናቸው ፡ማዕርጋቸውም እንደመወለዳቸው መጠን ነው ይሁን እንጂ እንደወለዶቻቸው ልጆችዋ ሁነው እንደ ማዕርጋቸው መጠን አግቧቸውን ጠብቀው አያገለግሏትም ከነኝሁም ከልጆችዋ ውስጥ እናታቸውን ለማገልገል የታጠቁ በግዛታቸውና በውራጃቸው የሚገኘውን ጥቅም መርምረው ያስታውቁ ጥቂቶች ሳይገኙ አይቀሩም ፡፡ አቶ የሺ ጥላ ማሬ በተለየ በኢትዮጵያ ወሰን ብዙ ልዩ ልዩ ጥቅምና ዕጣንም ከርቤም እንዲገኝ ጽፈዋል እንዲሁም በየወሰኑ ግዛት ያላቸው እንዲመረምሩ ሲሉ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኘውን ወርቅ ሉል አልማዝ ዕጣን ከርቤ ሽቱ የሰንደል እንጨት የሚመስል የተወደደና የተመሰገነ እንደሚገኝ መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክራል ፩ኛ ነገ ም ፲ ቁ ፲ ፲፫ ኢዮብ ፳፰ ቁ ፲፯ ፲፱ ዜናመዋ ፪ኛ ፱ቁ ፱ ፲፱

እንዲሁም ደግሞ በደቡብ ኢትዮጵያበቦረና በኢትዮጵያ ወሰን ውስጥ አራት ዓይነት ለመንግሥት የሚጠቅምነገር አለ ከራቱም ሶስቱ ጨው አራተኛው ባገሩ ቋንቋ መጋዶ ይባል አራቱም አራት ልዩነት አላቸው አንዱ ጨው በጣም ነጭ ነው በማናቸውም የሚበስል ነገር ሲጨምሩት ከበሰለ በኋላ እንክርድዶ እንደገና ጥሬ ያደርገዋል አንዱ ማናቸውንም ነገር ቶሎ ለማብሰል ቢፈለግ አለጊዜው በቶሎ ያበስለዋል እንደኛው ግን ጣዕ ናውም አመራረሩም መንምዘዙም ልክ የእንግሊዝ ጨው እንደሚባለው ነው መድኃኒትነቱም እንደዚያው ነው ። ያገሩ ሰው ሆዱን ባመመው ጊዜ ከዚያው ከጨው ውሃ አንዲት ብርጭቆ የጠጣ እንደሆነ ከእንግሊዝ ጨው ይልቅ ለሰሮ ነቱ ሁለት እጅ ይበጀዋል ፤ መጋዶ የተባለው ነጭ ኖራ የሚመስል ነገር ነው በማናቸውም ዓይነት ቀብዓት የተበላሸ ልብስ ከዚያ ከመጋዶ ዱቄት ጥቂት ላመል ቆንጥሮ ያጠቡበት እንደሆነ ሙሽልቅ አርጎ ያስነሳዋል ፡፡ደግሞም አገሬው ከመጋዶው ዝቆ ጭኖ ወደ ሌላ ግዛት ወደ ኪስማዩ ወደ ኖይሮቢ የወሰደው እንደሆነ ባንዱ ግመል ጭንት መጋዶ ሁለት ሶስት ግመል ገዝቶበት ይመጣል ፡፡ ግመል ደግሞ ምን ቢረክስ አንድ ግመል ከአርባና ከሃምሳ በታች አይሸጥም ይህ መጋዶ የሚባል ዱቄት ጣምናውና አኳኋኑ እንደ ፍሩት ሶልት ነው ፡፡

እንዲህ እንዲህ ያለው ነገር ሁሉ አልተመረመረም ይመስለኛል ወደ ፊት ተመርምሮ መንግሥት ጥቅሙን እንዲያውቀው ባውራጃው ያለውን አገረ ገዢ ያስገድደዋል።መርምሮ ለመንግሥት ባያስታውቅ የኢትዮጵያን የንጀራ ልጅ እንጂ እንደ ተወለዳት ሁኖ አይቆጠርም ምንም እናቴን ኢትዮጵያን እወዳታለሁ እሞትላታለሁ ቢል ባገባብ ካልሆነ ያፍ ልማድና ሞቅታ ይሆንበታል። በኢትዮጵያ ያለውን ጥቅም ከብዙ ሰው አፍ ስሰማ እኖራለሁ ይሄው የሚገኝባት ጥቅም ሲወጣና ሲሰራ ለማየት አጥብቄ እናፍቃለሁ ፡፡

እስራኤልን ከምስር ባርነትና ከባድ ቀምበር ያወጣ አምላክ እንዲሁም ኢትዮጵያን በማናቸውም ነገር እንዲታደጋት እለምናለሁ ።

ትንሹ ተማሪ ኃይሉ ለውጤ

የሀያ ገጽ ተከታይ

መልእክት

ለኢትዮጵያ ልጆች ንገራቸው ፡ ተማሩ እንማር በላቸው ። የተማርን እንደሆነ እንቻልም አሉ። ሁላችሁ ባንድነት ተዋዋሉ ፡ ደሀና ሁኑ ደሀና ዋሉ በፍቅር ተማማሉ ። በጠፉት ጥበቦች እንድትታፈሩ ። አደራችሁን ሳትሰለቹ ጣሩ ጋሩ ። ሞት እንደሆን አዲስ አይደለም ። ኢየሱስ ሙቷል ስላለም ፡ እኛም እንሙት ላገራችን ። ለነፍሳችን ለንጉሣችን ። ሞትስ ካለም በኋላ ያለው ነው ። ከቶ መዳኛ የሌለው ፡፡ ሞት ሸሽቶ የሚያመልጥ የለም ። የማይቀር ዕዳ ነው ለሁላችን ። መክፈል ይገባል በጊዜአችን ። ለነፍሳች ፡ ላገራችን ለመንግሥታችን ፡፡ ሰማዕታት ሆነዋል ጥንዘመዶቻችን ። በደም አጥበው ያቆዩን ጥሩ አገራችንን ፡፡ እስከብረው ኢትዮጵያችንን፡ አሳፍረው ጠላቶቻችንን፡ ብዙ አያቶቻችን ሞተዋል ስለ እስዋ።እኛም እንሙት ስለ ጥበብዋ ። ሰላም

ይዝነም ባጥረ ግቢዋ፣ ብርሃን ይሙላ በየሜዳዋ ። እኛ እንሙት
ስለ ነጻነትዋ።ለወርቅ አይል ለብር። ለኢትዮጵያ ሁኑ ቁም ነገር ።
ሕዝቧ ተነሣ ዳር እስከ ዳር ።
ለኢትዮጵያ ሁን ቁም ነገር ።

እያለ በጭንቀት መካከል ሲያንጐራጕር ይህ እርጉም አርዌ በንግግሩ ተበሳጭቶ በጅራቱ የወንድሜን እግሮች ጠመጠመና አንቺ እርጉም አሬሳሽ ከኔ ይራቅ ሲል በእራሱ ላይ አዙሮ ሲያሽገነጥረው የማደርገውን አጥቼ ኢየተንቀጠቀጥኩና እንደሴት ኢያዘነብኩ ያላጽናኝና ያለጠያቂ ተኰራምቼ ሳዝን ስጨነቅ ከራት ወር በኋላ ከብርሃን መዝጊያ በታች አቋጥኝ ላይ ወድቆ አናቱ የተበጠበጠ በድኑ ተገኘ የሚል ወሬ ደረሰኝ ።

ክቡራን አንባቢዎች ወንድሞቼ ሆይ እንደዚህ ከወንድሞቼ በድንገት ተነጥዬ ስቀር ልዑል ጌታችን የሰጡን » ካለማወቅ ነፃነትን ፥ አገር መውደድን ፥ ባለማወቅ ማፈርን የሚፍቁ እውቀትና ፍቅር ናቸውና እውቀትን ፍቅርን ለማግኘት እስከሚቻላችሁ ጣሩ ። » የሚሉት ቃላት ብቻ ናቸው ያጣኑኝ የሚያግዙኝ ከነሱ በተቀር አንድ የሚያጽናናኝ አላገኘሁም የለኝም ። ከሶስት አንድ ስቀር ተስፋ ወደመቁረጥና ወለል ብሎ ይታዩኝ ወደነበሩት ወደ ዘፈናም ጨዋታም ስልቹአም እንቅልፋም መንደር ጐዳኖች ባዘነበልኩ ነበር።ይህቺ ከሱካር ይበልጥ የምትጣፍጠኝ ነፍስና ሲጋዬን የምትመግብ የዳግማዊ ሰሎሞን ጌታችን ምክር ለኢትዮጵያና ለህዝቧ የሚጠቅም መልካም መልካም አመጣጥ የምታፈልቅ መሆኑዋ ለእናንተም ትታያችሁ ይመስለኛልና መሬ እንድታደርጓት ዋና ምኞቴን እገልጽላችሁ አለሁ ።

ክቡር አቶ በቀለ ይህችን ምክር ያን ጊዜ ጽፈውልን እንደነበረው በጉልህ ከልዑል መከሬአችን ስዕል(ሬትራቶ)ግርጌ አሳትመው በኢትዮጵያ ያሉ የእስላም ክርስቲያኑ የሚሳዩኔር የባላገሩ ተማሪ ቤት ሳይቀር ኢየገዙ በየክፍሉ የንጉሣቸውን ስዕል እንዲይዙ ያስደርጉ ያገራቸውን ካርታና የመንግሥታቸውን ስዕል መያዝ የተገባቸው ነው ።

በዚያ በአምዬ ምኒልክ ተማሪ ቤት አ ቤ ሴ ዴ የቆጠርን ልጆች ሁሉ አሰበን አንድ ሀውልት እንኳ ለእናታችን ማቆም የተገባን ነበር ምንም ብዙ እውቀት ባይሰጠን የኢትዮጵያ ሕፃናት ዓይናችንን የከፈትነው በሱ ነው ፥ እኛ ለምኒልክ መታሰቢያ ያላሰብን ሌላስ ስለእውቀቱ ብዛት አያስበውም በዚህስ እረገድ እርስዎና ልጅ መኰንን ክንፈ ነበራችሁ አለ ማንቀላፋት ያልተገባችሁ ። እስከ ዛሬም ችላ በማለታችሁ የዚህን ሀዘን የሚካፈሉኝ ወንድምቼ ጋር ኢያዘንኩ ለወደፊቱ አስታውሳችኋለሁ ከእንግዳህም ወዲያ እንቅልፍ ይወስዳችሁ እንደሁ ጉድ እያለሁ ።

ትንሹ ተማሪ መ ሥ ወ፣

ደግ ምክር ።

፬ት ነገር አገኘሁ ፥ እሊሁም የዚህን ዓለም ነገር የሰበሰበች ናት ። መጀመሪያዋ ጥበብ ናት ። ፪ኛዋ አእምሮ ፫ኛዋ ንጽሕና ፬ኛዋ ፍርድ ማስተካከል ፥ ዕውቀትና ትዕግሥት ። አውጥቶ አውርዶ አደላድሎ አርቆ ማሰብ ከጥበብ ይቈጠራል ። መታገሥ መቻል ዝግታ ከአእምሮ ይቈጠራል ። ሰውን ማክበር አፋርነት ቸርነት ሰውነትን ከውርደት በታ መጠበቅ ከንጽሕና ይቈጠራል ። እውነት መናገር ለሰው በጎ መዋል ደግነት እግዚአብሔርን መፍራት ግብረ መልካምነት ከፍርድ ማስተካከል ይቈጠራል ። መልካም ሥራ በጎ ግብር እነዚህ ናቸው ለውጣቸው ክፋት ነው ። የሰው አእምሮው የሚፈተነው በ፰ ነገር ነው ። ፩ኛው ዝግታ ነው ፥ ፪ኛው ሰው የራሱን ልኩን አውቆ ሰውነቱን መጠበቅ ነው ፥ ፫ኛው ነገሥታት የሚጠሉትን ነገር ትቶ ደስ የሚያሰኛቸውን ሠርቶ በቅን ለነሱ መገዛት ነው ። ፬ኛው ሰው የሚሥጥሩን ስፍራ አውቆ ለወዳጁ ሲያካፍል የሚገባውን ነገር ማወቅ ነው ። ፭ኛው በነገሥታት ደጅ ተቀምጦ አንደበቱን መጠበቅ በመልካም ቃል በፍቅርና በትሕትና መናገር ነው ፥ ፮ኛው ሰው የራሱንም ቢሆን የሌላውንም ቢሆን ምሥጢርን መቻል ነው ። ፯ኛው አንደበቱን በትክክል ለመናገር የሚቻለው መሆን መጨረሻውም በትክክል ማሰብ ። ባለማወቅ ነገር አለመናገር ። ምሥጢሩንም ለሚታመኑ ሰዎች እንጂ ለማንም አለማካፈል ነው ።

፰ኛው ሰው ከተሰበሰበበት በታ ባልጠየቁት ነገር አለመናገር።ይህችም ባሕሪ ባንድነት የተዘጋጀችለት ሰው ለሰውነቱ የሚጠቅመውን በጎ ነገር አያጣም ለነፍሱም ለሰማይ ቤቱ የሚሆነው ነገር አይጐድልበትም።የትዕግሥት ሁሉ መሠረት ምሥጢርን መቻል ነው ምሥጢርንም ለሚታመን የነገሩት እንደሆን በውነት ከጥፋት የተጠበቀ ይሆናል ። ምሥጢርንም የነገሩት ሰው ለሌላ ሰው ያነን ምሥጢር አውጥቶ መናገር አይገባውም በሁለትም ሰዎች መካከል ምሥጢር አይደበቅም ። ሁለት ሰዎች በምሥጢር ነገር የተናገሩ እንደሆነ ከሁለቱ አንዳቸው ወገን ፫ኛ ሳይጨምር አይቀርም ከሶስትም ሰው ከደረሰ በኋላ በውነት ተበትኖ አገሩን ያደርሰዋል ባለቤቱም ሊክድ አይቻለውም።በሰማይ ላይ ተቈራርጦ እንደሚታይ ደመና ፩ ሰው ይህ ደመና ተቈራርጧል ብሎ ቢናገር ፩ ሰው እንኳን አሰትህ ነው ሊለው አይችልም ።

ከነገሥታት ፊት ቆሞ ጥቅም የማይገኝበትን ሊናገሩት የማይገባውን ትርፍ ቃል ከመናገር ዝምታ ይበልጣል። ሥጋህን በኃጢአት እንዳያስተው ለአፍህ አርነት አትስጠው ። ሐኪሞች ሊያድኑት የማይቻላቸው ለሰው ልጅ እጅግ የሚያስቸግረው መድኃኒት የሌለው በሽታው መላሱ ነው ። ክፉውን ነገር በመናገር በራሱ ጥፋትን ያመጣልና ክፉ ነገር ከመናገር ዝምታ ይሻላል አለ ። ነገሥታትና መኳንንቶችን ግን ምሬሃለሁ ሰጥቼሃለሁ ከማለት ዝም አይበሉ መምሕራንንም ተናገር እስከ ትመርር ከመ ከርቤ ይላል ። ከማስተማር አትቦዝኑ ዝም አትበሉ ። ዝምታ ደግ ነው የተባለው ክፉ ነገር ከመናገር ነው እንጂ በጎውን ነገር ለመናገር ዝምታ አይጠቅምምና ዝምታን አትውደዱ አስተምሩ ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ሑሩ ወመሐሩ ብሎ አዟችኋልና የታዘዛችሁትን ልትፈጽሙ ይገባችኋል በብዙ ነገር ምክንያት ወደ ሰይጣን ምርኮነት የሄዱትን ትመልሷቸው ዘንድ፣

ቀምጸሐፊ ገብረጻዲቅ

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል ።

በባቡር መሳፍር ።

ጥር ፲፮ ቀን ክቡር ራስ ሥዩም ከዲስ አበባ ወደ ተቀበሉት ግዛታቸው ወደ አድዋ ለመሔድ በባቡር ተሳፈሩ።

ወደ ሔዱበት ግዛታቸው በደህና እንዲገቡና ሥራቸውንም እምላክ እንዲያከናውንላቸው ብርሃንና ሰላም መልካም ምኞቱን ያቀርባል ።

የደጊቱ እናታችን ኢትዮጵያን ልጆች ስለ ማነቃቃት

የቀድሞ አባቶቻችን ልጆቻቸውን ሲመክሩ ሲያስተምሩ በምሳሌ ነበር ፣ ከምሳልያቱም አንዱ ውርጭ የሚያስፈራ በጥቅምት ጠላት የሚያስፈራ በውድቅት ነው እያሉ ሌሊት ሳልቀለለ ብርሃን ካልቀላቀለ ትጥቅ አይፈቱ አያንቀላፉም ነበር ይባላል ። እኛ አውሬ ዶሮ ከጮኸ በኋላ ብርሃን በዓለም መልቶ ሳለ ብዙውን ሰዓት በንቅልፍ ያሳለፍነው አንሰን ከነጋ በኋላ ሰላምታ እየተነጋገርን አገራችንን እንደ መጠበቅ እንቅልፍ ብቻ መሆናችን እጅግ ይገርማል ።

ስለ ምሑራን ሊቃውንት ማመልከቻ

በብርሃንና ሰላም መጽሐፍ ከተጻፈው የንግድ ዕቃ ነጋድያን የሚገባቸውን መኳንንት የሚገባቸውን ወይዛዝር የሚገባቸውን ዕቃ እየተመለከቱ በየሳምንቱ ይገዛሉ ። ምነው እኛስ ልዑል አ ወ ተ መ ስለ ሀገርዎ ጥቅም አስበው ካሳተሙልን መጻሕፍት የተቻለንን ብንገበይላቸው ነውር ይሆን መጣፍ ያልተማርነውም ከራሱ ጀምሮ ሳንጉላላ በቤታችን ተቀምጠን እየተመለከትን ራሳችንን ጠቅመን ለልጆቻችን ለዘመዶቻችን ብናቆያቸው በመንፈሳዊም በሥጋዊም ክብር መሆኑ የታወቀ ሰማያዊ ድልብ መሆኑን ሁሉም ያውቀዋል።የተማሩትም ሊቃውንት ባርእስት በጎዳግ ማስታወሻ ከማመልከት ጨርሶ ከንባብ አቀናን ጀምሮ እስከ ታሪክና ምሳሌ የያዘ መጣፍ ቢያገኙ ለልጆቻቸው ለተማሮች ጥቅም መሆኑን ማንም አይስተውም ። እኔም ይህ ማለቴ ለሰው ለማስተናበር ብቻ አይደለም ያቅሜን ያህል ጀምሬ ነው እንጂ እግዚአብሔር ሲፈትነን አሥራት በኩራት ማውጣት በቀረ በብዙ ዘመን መፍቀሬተ እግዚአብሔር ንግሥታችነን ዘውዲቱን አንግሦ ስለ ዳግማዊ ምኒልክ ስም መታሰቢያ ወርቅ አዝንሞልናል አንዳንድ መጣፍ ብናስቀር ይሻል ነበረ ከዚህ ቀደም የታተመውን ችላ ካልነው ሌላ ሕዝብ የገዛው እንደሆነ ምዕመናንም እንደ ገና ሌሎችን ለማሳተም አበጋዛቸውን ለመከተል ይደክማሉ ለኛም ጠጠቱ ይወጣልን አይመስለኝም

አለቃ መርስዔ ኃዘን ።

ማስታወቂያ ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ብር
ግር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅዓላማ ያጌጠ	፩ ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ	፭ሩብ
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ብር
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ተኩል
የቁጥር ትምርት	፩ብር
ያማሪኛ ሰዋስው	፭ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	አላድ
ወዳጄ ልቤ	፫ሩብ
አጭር የዓለም ታሪክ	አላድ
ያማሪኛ ፊደል	ሩብ
አሳብና ምኞት	ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት	ሩብ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር	፪መ

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን ።

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲ ብር ተሩብ
የሲዳሞ ،	፩	፱ ብር ከሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፪ ብር ከ፫ሩብ
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፪ ብር ሩብ ም
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺ ብር ።
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፳፭ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፳ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፰ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፰ ብር ተኩል
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፵ ብር
፡፡ ባለሰይጣን	፡፡	፻፵፫ ብር
፡፡ ባለ ድመት ፡፡		፻፷፩ ብር ።
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻፳፪ ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፻፷፩ ብር
ባለ አንበሳ	፡፡	፻፵፩ ብር ።
ሱካር	፩ ጁኒያ	፳፯ ብር ።
ቻይ	፩ ነጥር	፲፪ መ

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ ከ፴፮ ሳንቲ
አንድ ብር	ሊሬ ፱ ከ፲፭ ሳንቲም
ባንድ ጊኒ	፱ ብር ከ፺፫ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፬ ብር

COGNAC S&E&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ፡፡

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የሚባል ባለ ፈ ረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

ሺብሮሌ አቶሞቢል ።
በኢትዮጵያ ወኪል ።
ሖ ሜ ዜርቦስ ኩምፓንያ ።

Automobiles CHEVROLET
AGENTS
H. M. ZERVOS & Cie.

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሰያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያየዚህአቶመቢልበተለይወኪል"አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዎርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፡ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፥ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል ።

RUGBY



ማስታወቂያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ። ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጀ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልክም ባርኔጣ ፣ ሽቱ ፣ ለስዮን ፣ አድኮሎኝ ፣ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፣ ከኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፣ ከፈይ ምንጣፍ ፣ ደግሞ በያይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላ ከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስመጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሽምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክታችኋለሁ ፣ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ዓለም

ዓለም የወርቅ ጥልፍ ሥራ ሁሉ በውስጠ ብር ሆኖ ይሠራል ።

ኒኮላ ።

ማመልከቻ ።

በብርሃንና ሰላም ውስጥ ማስታወቂያ ማሳተም የሚፈልጉ ነጋዴዎች እስከ ፈለጉት ጊዜ ድረስ ባማርኛም ሆነ በፈረንጅ ቋንቋ በርካሽ ዋጋ እንደምናትምላቸው እናስታውቃቸዋለን

ጉድደር ግዙ





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው ። በሌላጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ፤ ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አራተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፬
4 me ANNÉE № ፫

ሐሙስ ጥር ፳፬ ቀን ፤ ፲፱፻፳ ዓ ም ።
JEUDI 2 FEVRIER 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen , Héritier du trône d' Ethiopie , profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix , a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

◆

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የሀያ ስድስት ገጽ ተከታይ

እውነተኛውና አሰተኛው ሥልጣኔ በሥልጣኔውም ስም የገቡብን ልዩ ልዩ ጕዳቶች እንዲሁም የከተማውን ሕይወት በጤንነት እንዲጠበቅ የሚያሳዩ ምክሮች

፮ ሥጋ

፩ የሥጋ ሥራ አሁን ቅርብ ደምብ ተደርጎለት በከተማው ውስጥ የሚታረዱት ከብቶች በሐኪም ታይተውና ተመርምረው እንዲታረዱ ተጀምርዋል በዚሁ ደምብም ስንት በጎ አእምሮና እውነተኛ ያገር ፍቅር ያላቸው ሰዎች በጣም ደስ ብልዋቸዋል መንግሥታቸውንም አመስግነዋል ለወደፊትም በሁሉ በሚያስፈልገው ነገር በየጊዜው የማሻሻልና የማደስ ሥራ እንዲደረግ በተስፋ እየጠበቁ ስለመንግሥታቸው ደህንነት የሰማዩን አምላክ እየለመኑ ይኖራሉ

ዳሩ ግን ይህ በላይ የተነገረውን ብቻ አይበቃም ፡ ደግሞም ለዚሁ ለሥጋ ሥራ ፪ ፤ ሥራዎች ያስፈልጉዋል ። ፩ ፤ በከተማ ለሚታረድ ከብት ሁሉ የተለዩ ቦታዎች ወይም ቤቶች ማቆም ። ቤቶቹም ለሥጋ ሥራ እንዲመች እንዲሰራ በሠለጠኑቱ አገሮች እንዳለ ። እንዲህ ሲሆን ብዙ በሽታዎች እንዲወገዱ አይጠረጠርም ። አሁን ግን በማናቸው ስፍራ ደም ሲፈስ እንዲሁም የሥጋው ቅሬታ በማንላቸው ቦታ ሲጣል ። በመሬት ላይም እየታረደ የተገባ መሰቃቀያም እያጣ አፈርንና ቍሻሻውን እየነካ ቍጥር የሌላቸውም ውሾች ወራር እየገቡበት ብርቱ ጉዳት ይሆናል ። ፪ ፡ በእንዲህ ያለ ደምብና ስፍራ የታረደውም ለሥጋ መሸጫ በበቃ ቤት እንዲሸጥ ማድረግ ። ሥጋው የሚሸጥበት ቤት ደግሞ ከላይኛው ደምብ የተስማማ እንዲሆን ግድነት ነው ። ሥጋ የሚሸጠው ቤት ብዙ ጥዳት ያለው እንዲሆን ከጊዜ ወደ ጊዜ ቤቶቹን መጐብኘት ይገባል ። ይልቁንም የቤቱን ጥዳት የሚጠብቅ በመጥረግና በሌላም ስፉ በማንጻት ከሁሉ የበለጠ በኖራ ከጊዜ ወደ ጊዜ ቢለቀልቅ እጅግ መልከም በሆነ ። የጤንነት ደምብ እንደሚፈልገው አድርጎ ሥራውን ማስኬድ የማይችል ይህን ሥራ ሊፈቀድለት አይገባውም ።

፯ ፤ ውኃ

ውኃ ለሰው ሕይወት ዓይነተኛ ነገር ነው ከእንጀራ በኋላ ውኃ ያስፈልገናል ። በሰውነታችንም ውስጥ በተፈጥሮዋችን ውኃ ይዘናል ፡ ውኃም ጥማታችንን እንድንቈርጥበት ብቻ አልተሰጠንም ። በብዙ ነገር ይጠቀመናል እንጅ ፡ ስለዚህ ጥሩ ውኃ ከሁሉ አስቀድሞ ያስፈልገናል ። እንግዴህ እንዲህ ያለ የከበረ ውኃ የምናገኝበትን መንገድ እንድንሻ ግድ ይሆንብናል ። ፩ ፤ አስቀድሞ ጥሩ ቦታ መምረጥ ይገባል ። ከመቈፈር በፊት የቦታውን አቀማመጥ መመልከት ። ከበላዩ ወይም በጐኑ ያለ ቦታ እንዴት መሆኑን ማየት ። እድፍ ሠገራት ሌላም የጕድፍ መሰብሰብያና መጣያ ያለበት እንዳይሆን ። ፪ ፤ እጅግ ጥልቅ ማስቈፈር ። ፫ ፤ መልከም መዝግያ አድርጎ አንዳች ነገር እንዳይገባበት ማድረግ ። ፬ ፤ ሲቀዳ የሚፈሰው ውኃ በምንጩ ዙሪያ እንዳይሰበሰብ ። የሚፈስ ውኃ ሽው ብሎ እንዲያልፍ ብቻ ማድረግ ። ለዚህ የምንጩ ዙሪያ ቦታ እስከ ሶስት እስከ አራት ሜትር ከሌላው ቦታ ከፍ ቢያደርጉት ወይንም ዙሪያውን በተጋጠመ ድንጊያ በመገናኛው በስሚንት እየሞሉ ቢገጥሙት ይሆናል ። ፭ ፤ ከሁሉም እጅግ የሚያስፈልግ ነገር ቢረዝም ምንጩ በሁለት ወይም በሶስት ዓመት ቢጠረግና ቢወለወል ነው ብርቱ ምንጭ ያልሆነም ባመት አንድ ጊዜ ቢጠረግ ደግ ነው ። እንኳን ሰው ባለ ትልቅ አእምሮ እንስሳዎችም ሳይቀሩ ጥሩ ውኃ እንዲሹ ይታወቃል ። ሰውም በሚችለው ሁሉ ቸል

ሳይል ጤንነቱን የሚጠብቅበትን ነገር ሊያውቅ ይገባዋል ። ስለዚሁ አንዱ እንዳለው ነው ፤ «በሕመማችን ራሳችንን እንጅ እግዚአብሔርን ልናማ አይገባንም ፡ »

፫፡ ሠገራት ።

የሠገራት ሥራ ለከተማው ሕይወት ከዓይነተኞቹ ነገር ነው መጀመሪያ አሳባችንን ልንጥልበት የሚገባው እንደሆነ አይጠረጠርም ። ይሄው ነገር እንዴህ መሆኑን በጣም የተረዱትና በጣም ያስትዋሉበት ሰዎች እምብዛ አይበዙም ። ላስተዋለው ግን ብዙ ያንቀጠቅጣል ። የተገባ የሠገራት ሥራ ስላልተደረገ በዚሁ ምክንያት በጊዜው በእንዴህ ያለ ትልቅ ከተማ ብርቱ ብርቱ የሆኑትን ጉዳቶች ሳይመጣ አይቀርም ። ይሄው ጉዳት መንግሥት እንደሚያውቀው እርግጥ ነው ። ለማድረጉም አይቸግረውም ነበር ። ችግሩ በሕዝቡ ላይ ነው ያለ ። የሚበዛው ሕዝቡ ደሀ ነው ። እጁ የማይሞላለት ስለሆነ ቤቶችን በትክክልነት አይሠራም ። መንግሥትም በሁሉ ነገር የሕዝቡን ጠቀሜት ይወዳል እንዴሁም ጉዳቶቹን ይጠላልና በተተካከለ ሕግ ሊከየደው አይሆንለትም ። ቢሆን ግን በእንዴህ ያለ መንገድ ባይቻል ሕዝቡ ብቻ በራሱ ሰንፍዋልና ለጥዳት ብዙ ኪሳራ እንደ ማያስፈልግ የተረዳ ነው ። የጥዳት ጐዳና አጭር ነው ። ቤቶችን በወርቅና በብር በሐርም በሌላውም በከበረ ነገር መስራት አያሻም ። ጥዳት የሚገኝበት በመጥረግ መላልሶ በመጥረግና በማጠብ በመታጠብ ነው ። ፈጣሪ ሁሉን ቀላል ነገር አድርጎታል በወርቅና በብር ውኃ ወይም በወርቅ መጥረጊያ እንዴህም በሚመስል ነገር ድሀ ሊያገኘው በማይችል ማድረጊያ አላደረገው ። ከሁሉ አስቀድሞ የተከፈቱ ዓይኖችና በጎውን ፈቃድ ያስፈልጋል

እያንዳንዱ በቤቱ ውስጥና ዙሪያ ባጥሩ በርሱም አቅራቢያና ጥግ በመንገድም ዳር ቢሆን ወይንም ባጠገቡ ያለ መተላለፊያ በጥዳት እንዲጠበቅ የርሱ ኃላፊነት ሊሆን ይገባል ። በዚህ ነገርም የመንግሥት ኃይልና ትእዛዝ በጽናት ሊገለጥ ያስፈልጋል ። እንዴህ ያለ ስፍራ ተበላሽቶ ሲገኝ በሠለጠኑቱ አገሮች ዕለት ዕለት እንደሚደረግ ብርቱ ብርቱ መቀጮውን ቢጥሉበት እጅግ ይጠቅሙታል እንጂ ባንዳች ነገር ከቶ አይጐዱትም ። ጤንነቱንና ደህንነቱን ጠበቁለት እንጂ፣ ሠገራት በተገባ ማድረግ የሚችሉትን ግን መንግሥት ሊያግዳቸው ይገባል ። የሚችሉቱ ባይጀምሩ ሌላዎቹ እንዴት ብለው ይማሩ ? ይህም ካለማሰብ እንጅ ከማጣት አይሆንም ። እንዴሁም ዕለት ዕለት የታመኑ ዘበኞች አጥሩን መከበብያውን ሳይቀር የሚጠብቁ መቀጮቻቸውን አስጽፈው ለመንግሥት ቢያስረክቡ ደግ ነበር ። የሚጠረግ በመጥረግ በእሳት የሚቃጠለውን በእሳት እያቃጠሉ ከተማውን ዘወትር እንዲጠዳ ጽኑ ትጋት ብቻ ያስፈልጋል እንጂ የገንዘብ ኪሳራ አያመጣም ። እንግዴህ እንዴህ ሳይሆን የሕዝቡ ጤንነት እንዴት ሆኖ ይጠበቃል ?

፬፡ ቤቶች ።

ቤቶችም ጤናን የሚጠብቁና የሚሰጡ ሆነው ሊሰሩ ያስፈልጋል ። ዓይነተኛው ጥያቄ ሊሆነው የሚገባ ለጤንነት የተሰማሙ መሆናቸው ነው እንጅ ማጌጻቸው አይደለም ። ስለዚህ እነዚህ የሚከተሉትን ማሰብ ያስፈልጋል ። ፩፡ የቤቶቹ አቀማመጥ ። ሁሉ ስፍራ ስለሆነ ለጤንነት የሚሰማማ ሊሆን አይቻልም ። ስለዚሁ የቤቱ አቀማመጥ መምረጥ ዓይነተኛ ነገር ነው ። ከሁሉ የተሻለ የቤት አቀማመጥ ጀምበር ስትገባና ስትወጣ የጸሐይ ሙቀትና ብርሃን ሊገባባቸው የሚቻል ሲሆን ነው ። እንደነዚሁ የሆኑ ቤቶች ለጤንነት ከሁሉ የተሻሉ ቤቶች መሆናቸው አይጠረጠርም ። ጸሐይ የጤንነት ዋና ነገር ነው ።

ጉዳት የሚያመጡ የማይቈጠሩ ፍጥረታት በጸሐይ ትኩሳት ይሞታሉ ። በአውሮጳም አንድ ምሳሌ ፤ ጸሐይ በሚገባበት ቤት ሐኪም አይገባም የሚል አለ ። ይህ እጅግ የተረጋገጠ ነው ። ጸሐይ የጤንነት ምንጭ ነው የጸሐይ ሙቀት የማይደርስላቸው ቤቶች እጅግ የተጐዱ ቤቶች ናቸው ። በሽተኞች ቤቶችም ሊባሉ ይገባቸዋል በአውሮጳም ሰሜን የጸሐይን መታጠብ የሚባል ሳይቀር ይደረጋል አካላቶችን በጸሐይ ሲሞቁ ጤናን ያበዛሉ ። እንግዲህ ጸሐይ ንፋስን ጨምሮ እስከቤቱ ማጀት ውስጥ ሲገቡ በረከትን ይዘው ይገባሉ እንጅ አንዳች ነገር ይዘው አይወጡም ። ፪ ፡ የቤቱ አሠራራትና አከፋፈል ቢሆን በሥርዓት ሲደረግ ጤንነትን ይጠብቃልና ያበዛል ። ፫ ፡ የማዕድም ቤት ለብቻው ከሌላው ቤት በውስጥ የማይገናኝ ሆኖ እንዲሰራ ጢስ ሆነ ሌላውንም ነገር በርሱ የሚሠራ በሌላዎች ክፍል ቤቶች እንዳይገባ ማድረግ ። ጢሱም በአንድ መንገድ ተሰብስቦ ለርሱ በተሠራ ቀዳዳ እንዲወጣ እንጅ ቤቱን እንዳይሞላው ማድረግ ፬፤የቤቶቹም ዙሪያ በንጨት ባጥር ወይንም በመንደቅ የተከበበ ቢሆን በውጭና በግቢው ዘወትር የጠዳ እንዲሆን መመልከት እስከቤቱም መሬቱን በሥርዓት ማደላደል ወጣገባ እንዳይሆንእንዲሁ አድርጎም የሚገባውን መልክ መስጠት ለዓይን ጣዕም መስጠት ፭ ፤ የእንስሳዎች ቤት ሰው ከሚቀመጥበት ቤት እጅግ ራቅ ያለ አሰራሩም ጠዳፋ እንዲሆን ይገባል ዘወትርም እየተጠረገ ጸሐይና ንፋስ ብዙ የሚገባበት ማድረግ።የተጠረገውንም ጥራጊ ባንድ ጥልቅ ጉድጓድ ከምሮ ማስቈየት መቸም በፍጥረቱ ላስተዋለው አንዳች የሚጣል ነገር የለምና ለርሻም ሆነ ለአትክልት በረከቱን ያመጣል ክፍትና ከሰው ቤት አጠገብ ሲሆን ግን ጉዳት ይሆናል

፯ ፡ ዛፎች

ዛፎች የሆነውንም ተክል መውደድ እጅግ መልካም ነገር ነው እርሳቸውም በገባባቸው ሲደረጉ ለብዙ ጤንነት ይረዳሉ ለተመለከተውም የከተማው ሕይወት የሚጠበቅበትና የሚታደስበት የሚበዛው በነርሳቸው ሥራና ጸጋሳይሆን እንኳ አይቀርም ምባም ሆነ ሌሎችንም በሽቶች ያሳዳሉ።የፊተኛው ሰው አዳም በገነት በአትክልት ዛፎች በሞላበት ቦታ እንጅ በድርቅ እንዳልተቀመጠ የሰውም ሕይወት ከአትክልት ጋራ የተሳሰረ መሆኑ እርግጥ ነው።ቢሆን ግን በአተካከላቸው ሥርዓት ያስፈልጋቸው ነበር ምንም በራሳቸው ጤናነትን የሚጠብቁ ቢሆኑ አለቅጥ በማንላቸውም ስፍራ ልክ በሌላው ቍጥርም ሲተክሉ በሌላው በኩል የሚመጣውን የጤንነት ረድኤ

ሳያስወግዱ አይቀሩም የቤቶችንም ጌጥ ይሠውራሉ በሥርዓት በቀና ትክክልነት በልክነት ሲተከሉ ንፋስንና ጸሐይን ለማስገባት መንገድ እንዲተዉ ሆነው መልካም ነበር።ቤቶቹ ዘወትር ቀዝቃዦች እርጥቦች ሲሆኑ ስንቱን ሕማም ያመጣሉ ቍርማትና ሌላዎችንም በሽቶች የዚሁ ዓይነት እንዴት ብለው ይመጣሉ? በእንደዚህ ነው።እንግዴህ አንዱን ጥቅም ስለማግኘት ሌላውንም ጥቅም እንዳይጐድልብን ማሰብ ይገባል አበባዎችም በመንገዳቸው ሲሆኑ ብዙ ይጠቅማሉ ሕይወትን ያድሳሉ አየሩንም ያጠራሉ ሰውንም በበጎና በደገኛ አሳብ ይሞላሉ ።

፲፩፤ውሾች ።

ውሾች ከእስራኤል ባገኘነው ልምድ በኢትዮጵያችን ይልቁንም እስላሞች እንደ እርኩሶች ያይዋቸዋል ። ክርስትያንም ምንም ውሻውን እንደ እስላሙ አድርጎ ባይጠላው ከውሻ ጋር ግን ወዳጅነት ሊያደርግ እምብዛ የሚፈልግ የለም ፥ ስለዚህ ማንም ቢሆን ውሻ ሊነካው የሚፈቅድ የለም ። በዚሁ በአሁኑ አናንዋራችን ይህልማድ ለኛ ይበጀናል ። የውሾችን አያያዝ ባናውቅበት እርሳቸውን መጥላት ብዙ ይጠቅመናል እንደ ሌላዎች ሰዎች አገር ከርሳቸው ጋራ ብንጫወት ጕዳት እንጂ ጥቅም ባላገኘነላቸውም ። ምክንያቱም ውሾችን በሥርዓት መያዝ ስለአለ መልድን ነው ። እንግዲህ ስለ ምግባቸውና ስለ ጥዳታቸው ስለ ጤንነታቸውም በሚደርስ ነገር አንዳች ባናስብላቸው ጥላችን ይሻለናል ።

እነዚሁ ከጌቶቻቸው በቀን አንዲት ቍራሽ የማይጣልባቸው ስንት በራብ ያልቃሉ በረሐብም ምክንያት ጠጕራቸው ተገፎ ቈዳቸውም ተልጦ ጥቂት ይቀረዋል ። ለሚያያቸውም ይልቁንም የሠለጠኑቱ ሰዎች ሲያይዋቸው ስንት ይጸየፉዋቸው ይሆን እንዴህ ሆነው የልዩ ልዩ በሽታዎች ማሳደሪያ ሆነው ይቀራሉ ። ከሁሉም የከፋ በሽታ የውሻ ዕብደት ነው ። ይሄው ሁሉ መከራ የሚደርስባቸው በሰው ጭከና ስበብ ነው ።በሠለጠኑቱ ሕዝብ ግን የሰብአዊነት ርኅራኄ ለሰው በቅቶ ለእንስሳዎችም ተርፎላቸዋል ። ስለዚህ የእንስሳዎችን ሕይወት በሚገባው አኖኑዋር እንዲጠበቅላቸው ማሕበሮች ቈመዋል ያምላክ ቃልም የተገባ ደምብ አውጥቶላቸዋል እንዲህ በማለቱ፤ጻድቅ ሰው ለእንስሳ ይራራል ( )፥ የእንስሳ ሆነ የአትክልት ተፈጥሮም በሰው ጭከና እጅግ ተበድልዋል ከዚህም የሰዎች ግፍ ነፃ የሚወጣበትን ቀን ብቻ ይጠባበቃል ። (ሮሜ ፰) ።

የሆኑቱ ዓይነት እንስሳዎች ለሰው ጥቅም ተፈጥረዋል ። ይልቁንም ውሾች የታመኑ የሰው ረዳቶች መሆናቸው የሚስተው የለም ። ሰውን በሄደበት ይከተሉታል ። ደግሞም የውሾች ልዩ ልዩ ዓይነቶች በዓለም ሞልተዋል ። በሰው ሕይወት በሚታየው ልዩ ልዩ ስራ የሚፈጽሙ አሉ ። ውሾችም ከሌላዎች በውስጣቸው በሚሆን በባሕርይ መድፋት (ኢስቲንክት) ከፍ ያለሥራ ሊፈጽሙ እንደሚችሉ ታይተዋል ። በሕዝባችን ግን እንደ ፍጥረት የሚያስባቸው የለም ። ሌላዎችንም እንስሳዎች ቢሆን ማገልገላቸውን በጊዜውና ባለጊዜው ብቻ እንፈልጋለን እንጂ በትክክልነት መሻታቸውንና ጕዳቶቻቸውን የሚያውቁላቸው ስንት ያህል ይሆናሉ እንግዴህ ሥልጣኔው በየት አኩል ነው?ያለ ዛሬም በውስጣችን ያሉቱ እንስሳዎች ማንላቸውም ቢሆኑ እንደ በልዓም ወልደ ባሦር አህያ አፋቸው ቢከፈትላቸው መጠን የሌለው ወቀሳቸውን እንዲህ ብለው ባስታወቁ ነበር ምን አደረግሁህ።እንዴህ ያሉ መከረኞች ውሾች በከተማው ቍጥር የላቸውም ። የሚበዙቱ ባለውሾችም ከለማሰብና ግድነት ከለማድረግ ነው እንጂ የሚሰጡዋቸውን ስለአጡ አይደለም ። ልምድ ክፉ ነው ደግ ነው ። መጥፎ ልምድ ክፉ ደግ ልምድም መልካም ነው ። በሕማም ከታወሩ ዓይኖች በመጥፎ ልምድ የታወረ አእምሮ ይብሳል ።

ስለ ሕዝብ ጤንነትና ስለ እንስሳ ርኅራኄ ጽኑ ደምብ ሊደረግላቸው ይገባል ። ፩ ፤ ውሾች ያልዋቸው በተገባ ሥርዓት እንዲመግቡዋቸው አለዚያ እንዳይዙዋቸው ።፪፤የውሾች ዋናዎችተና ውሾቻቸው በኑምራ እየተጻፉ በመንግሥት መዝገብ ሊጻፉ ፫ በሥርዓት የማይኖሩና በደምብ ያልተለዩ ውሾች ሁሉም መግደል።ስድ ሲሆኑ ግን በዚሁ ትልቅ ከተማ የብርቱ ቸነፈር ምክንያት ሳይሆኑ ይቀራሉ ተብሎ አይጠረጠርም ። በማንላቸውም መንገድ በሽታዎች ከመጡ ወዲያ መድኃኒትን ከመፈለግ ይልቅ አስቀድሞ በሽታዎች እንዳይመጡ አጥብቆ መጠንቀቅ ዓይነተኛ ጥበብ ነው ።

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል ።

የሀያ፪ገጽ ተከታይ

ወከነ ከመ እንስሳ ዘአልቦ ልብ ወተመሰሎሙ ።

የዚህ ዓለም ሰው የነፍሱን ነገር ለሰማይ ቤቱ የሚጠቅመውን ሥራ ትቶ የሥጋውን ብቻ በመከተሉ የዚህን ዓለም ነገር አውጥቼ አውርጄ ባስበው በዚህ ዓለም ከፍጥረት ሁሉ የሚበልጠው የተከበረው የሰው ልጅ ነው ። ደግሞ የሰው ልጅ ዘወትር ከሐሳብና ከመከራ አለመውጣቱን ከክፉ ሥራ አለመከልከሉን ለሰማይ ቤቱ ለነፍሱ የሚጠቅመውን ለበጎ ሥራ አለመትጋቱን እያየሁ በዚህ ነገር እጅግ አድርጌ ተደነቅሁ ።

አእምሮ ያለው ዕውቀት ያደረበት ሰው ሁሉ ነፍሱን ከቅጣት ለማዳን ብልሃት የሚፈልግ ለበጎ ሥራ የማይተጋ የለም።

አእምሮና ዕውቀት ያለው ለሰማይ ቤቱ የማያስብ ሰው የሚጠቅመውንና የሚጐዳውን የማያውቅ ሰው ሁሉ ሐሳበ ጐዶሎ ዕውቀተ ትንሽ ደካማ ይባላል ።

ደግሞ የነፍስን ነገር ሰው ሁሉ እንደተወው ያለመጠን በዚህ ነገር እየተደነቅሁ የዚህን ምክንያት ስፈልግ ተገለጠልኝ።ምክንያቱም እንዲህ ነው የሰው ልጅ ለነፍሱ የሚሆነውን ለሰማይ ቤቱ የሚጠቅመውን ነገር ለመሥራት ከቅጣት የሚያድነውን ብልሃት ከመፈለግ የሚከለክለውን ነገር በዓይኑ ከሚያየው በጆሮው ከሚሰማው ባፍንጫው ከሚያሸተው በምላሱ ከሚቀምሰው በጁ ከሚይዘው በቀር የማትጠቅም የሆነች የምትጣፍጠው ትንሽ ነገር ናት ምናልባት ከሷ ትንሽ የሚያገኝ መስሎት ወይም ትንሽ የሚያኖርለት እየመሰለው ይህ እያታለለው ለነፍሱ የሚጠቅመውን ከቅጣት የሚያድነውን ነገር ከማሰብ የሚከለክለው ነገር ይህ ነው ።

የሰው ልጅ ምሳሌው እንዲህ ነው

፩ ሰው ኃይለኛ ዝሆን ተነሥቶበት ሲሸሽ አምልጦ ወደ አንድ ጕድጓድ ውስጥ ገብቶ ከጕድጓድ አፋፍ ላይ ባሉ በሁለት ሐረጎች ላይ ተንጠለጠለ በእግሮቹም በጕድጓድ ውስጥ ቈሉ ባንድ ጐን በኩል በላይ ተረገጠ ። ከዚህም በኋላ ፬ አባቦች ከጕድጓዳቸው ውስጥ እራሶቻቸውን ብቅ ብቅ አድርገው አየ ። ደግሞ ከጕድጓድ ውስጥ ከመጨረሻው ዓዘቅት ላይ ትልቅ ዘንዶ አፉን ከፍቶ በወደቀ ጊዜ ሊውጠው ሲጠብቀው አየ ። ደግሞ ወደ ፪ቱ ሐረጎች ቢመለከት ፪ አይጦች መልካቸው ጥቁርና ነጭ የሆነ አንድ ጊዜ እንኳን ሳይበዝኑ ዘወትር የሐረጎቹን ስር ሲቀረጥፉ አየ ።እንደዚህ ሆኖ መውጫ ብልሃት እየፈለገ ለሰውነቱ እያሰበ ፈርቶ ተጨንቆ ሳለ ዘወር ብሎ ቢመለከት ከጠገቡ ማር የሠራ ንብ አየ ከዚያውም ማር ቆርጦ በቀመሰ ጊዜ መጣፈጡ አታሎት መዓዛው አዘንግቶት ከዚያ ከተከበበበት ጠላቶቹ የሚያመልጥበት ብልሃት መፈለጉን ትቶ ለራሱ ማሰቡን ረሳው ፪ቱ እግሮቹ ፬ቱ አባቦች ላይ መሆናቸውን ሳያስብ ምን ጊዜ እንደሚረግጠው ሳያውቅ ፪ቱ አይጦች አንድ ጊዜ ስንኳ ሳያርፉ ዘትር የ፪ ዛፍ ሐረጎች ሥር መቀርጠፋቸውን ሳያስታውስ ሐረጎቹም በተቈረጡ ጊዜ ከዘንዶው አፍ ውስጥ መውደቁን ሳይመለከት ቀርቶ ይኸነን ሁሉ የከበበውን መከራ ረስቶት በዚያች በሚቀምሳት በምትጣፍጠው በትንሽ ነገር ተታሎ ሳለ ሁለቱ የዛፍ ሐረጎች ተቈርጠው እሱም ከዘንዶው አፍ ውስጥ ወድቆሞተ።

የጕድጓድ ምሳሌ ።

ክፋትና መከራ ፍርሃትና በሽታ ሐሳብና ድካም የመላባት የዚች የምድራዊት ዓለም ነገር ናት ። ያ፬ቱ አባቦች ምሳሌ በውስጥ ያሉ ያ፬ቱ ሐሞት ባሕርያት ፬ቱ ደዌያት ናቸው ሳፍራና ሳውዳ ደምና ነፍስ እነዚህ ፬ ወይም ከ፬ቱ አንዳቸው በሰውነት ላይ የበረቱ እንደሆነ እንደ እባብ መርዝ በፍጥነት ወግተው የሚገድሉ ናቸው ። የ፪ቱ የዛፍ ሐረጎች ምሳሌ ወደፊት እስከ ጊዜው ያለው ዕድሜ ነው ። ደግሞ ብዙ ዘመን ስንኳ ቢኖሩ ዕድሜ አልቆ መቆረጡ አይቀርምና ፡ የ፪ቱ አይጦች ምሳሌ መልካቸው ነጭና ጥቁር የሆነ ፡ ሌሊትና ቀን ነው ዘወትር የማያርፉ ዕድሜን የሚጨርሱ እነሱ ናቸውና የኩል ከረብታ ዓይን በመኳል ያልቃል እንዲሁም የሰው ሕይወቱ በየዕለታቱ ያልቃል ። የዘንዶው ምሳሌ የማይቀር ሞት ነው ። የማሩ ምሳሌ የሰው ልጅ በዚህ ዓለም የሚያገኛት ይህች ዓለም የምትጣፍጠው ትንሽ ነገር ናት አይቶ በሚሰማው በልቶ በሚጠጣው ይዞ በሚያሸተው ነገር ሐሳቡን ለዚሁ ብቻ አድርጎ እየተታለለ የኋላውን ነገር የሰማይ ቤቱን ለነፍሱ የሚጠቅመው የሚያስረሳውን ይህ ነው ።

ዘላዕለ ነፍሱ ይዔብስ ለመኑ ኄረ ይከውን ፡ ኢትክሉ ከመፈረስ ወበቅል እለ አልበሙ ልብ። ቁም ጸሐፊ ገብረ ጻድቅ ፤

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይተታማል።

የመጠጥን ጉዳት ስለ መረዳት ፤

የሰካራሙ ደግሞ ነው እንጂ ጥፋቱ የመጠጡ ብቻ አይደለም ፤

ያያሌ ሰዎችን ሕይወት የሚያጠፋና የሚጐዳ እንዲሁም ኃይላቸውንና እውቀታቸውን የሚከፍል (የሚያሳንስ) ዳግም ሰውነትን የሚያጠፋ መጠጥ ነው ። ከዚህ የሚመጡ ቁስሎች ዕባጮች ክፉ በሽታ በገዛጅ መሞት የሰላም መጥፋት ከሰው አለመስማማት ንብረት ማጥፋት ስንፍናና ክፉ ልማዶች ናቸው። ከመብል በኋላ በልጅነት ወራት ማናቸውም ሥራተኛ ጠጅ ይልቁንም አረቄ ከመጠጣት የታገሠ ከብርቱ ሰዎች ጋራ ይቆጠራል ፤ ይኸውም በውነተኛው ቃል ሰው ተብሎ ይጠራል በመብል ሰዓት አንድ ብርጭቆ ጠላ ወይንም ጠጅ ቢጠጣ እጅግ ክፉ አይደለም ። ግን አረቄ ሁሉ ሲጠጡት ያለመጥቀሙ ብቻ አይደለም ከብዙ ጊዜ በኋላ በአካላት ውስጥ እጉል ደዌ ይሰራል ሆድቃም ይበላሽና ያደክማል ምግብም ለመቀበል ችግር ይሆንበታል አረቄውም ከደም ይደባለቅና መርዝ ይሆናል እንግዲህ የልብ ስር ይበላሽና ለሕመም ይሰጠዋል ፡ በዚህም አይቀር ሥርንም አንጐል ውስጥ ያለውን ይለውጠዋል ። ከሙቀት በኋላ ስካር እንደሚገለጥ ዕብደት ይመጣል በዚሁም ዕብደት ከሚባለው በጦሱ የሚወድቁ ጠጭዎች ጥቂት አይደሉም አንዳንዶቹም በዚህ የተነሳ መጥፎ ኃጢአት ይሠራሉ ሌሎችም የስር ቤትና የሐኪም ቤት ወይንም መቃብር እስኪቀበላቸው ድረስ ሕይወታቸውንና የሰውን ፍቅር አያውቁም ልግጠና ቀልድ ይመስላቸዋል። ሰካራምም ሰው በድንቁርና አሳብ ሥራን ይጠላል ፤ ከበሬታና ጨዋነት ከሕሊናው አይሰማውም ስንፍናም በሐጢአቶች ክንድ ይወረውረዋል ፤ ስለዚህ ስርቆትና ማታለል ይህን የመሰለ ክፉ ሥራ ያደርጋል ፡ የሰው ሞቱ በመጠጥ የሰከረ ጊዜ ነው ፤ እሳትና ውሀ ዓለምን እንደሚያጠፉ ዳግም ፍቅርና መጠጥ የበለጌን ገንዘብ ይጨርሳሉ ። ሰካራም ሰው ከብዙ ዓመታት በኋላ የደህንነትን አሳብና የራሱን ፍቅር ይረሳል ፡ቍጡ ተራጋሚ ምቀኛ ይሆናል ፤ ለዚሁም ደግሞ አንድ ተረት እንደሚከተለው እጽፋለሁ ፡ አንድ መንፈሳዊ አእምሮ ያደረበት ልጅ ነበር ፡ ወደ ርሱም ቤት ሰይጣን በሰው መልክ ሆኖ ተገናኝቶት እንዲህ ሲል ምክር ሰጠው ፤ ልጄ ሆይ ብዙ ገንዘብ እንድታገኝ እህትኽን አግባ አባትኽን ግደል ወይን መጠጥ ውደድ አለው ። ልጁ ግን በጣም ደነገጠና እንዲህ ያለ ኃጢአት ለመስራት አልችልም አለ ፤ ይህ ክፉ የተረገመ በሚያታልል ንግግሩ እየመለሰና እየመላለሰ ፡ ስታወቀው ጊዜ መጠጥን ለመጠጣት ፈቀደ ። በዚህም የተነሳ እህቱን አገባ ። አባቱም ነገሩን ሰምቶ ቢገስጸው በዱላ መሐከል እራሱን በጥብጦ ገደለው ። ወንድሞቼ ሆይ የመጠጥ ልማድ በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ በሰው ፊት የሚያጸይፍ እራስን የሚጐዳ ሥራ ያሰራልና በብዙ እንድንታገስ አሳስባለሁ ።

አበበ በላቸው ።

ስለ ተሙን ምንዛሬ አዲስ አሮጌነት

አለቃ የማነ የሚባሉ ሰው ከአዲስ አበባ ሲመጡ ከመንገድ ተገናኜን መንገዱስ አገሩስ ደህና ነወይ አልኳቸው ። ልዑል የኢ መ አ ወ ተፈሪ መኰንን ሳሉ ምን ችግር አለ አሉኝ የውዱን በውድ የግዱን በግድ ለጥ አድርገው ገዙት ተአዲስ አበባ አንስተህ አቢጋር ድረስ ወርቅ በንቅብ ብትይዝ ጠያቂ የለህም ፤ ስለ ተሙን ብቻ ብዙ ችግር አለ አሉኝ ።

አዲስ አበባ ተሙን ልመነዝር ገባሁ አንድ ሴት የብር ተሙን እቃም በየዓይነቱ አላት የብር ተሙን አቅኒልኝ አልኳት ቆጥረ· ሰጠችኝ ፩ ተሙን መልሽና ሳሙና ልውሰድ ብላት አይሆንም ተሙኑን ጠልቼ አይደለም ያቀናሁልህ አለችኝ ምን አረጋለሁ ብዬ ተሙኔን ይዤ ተመለስኩ አሉኝ ። ተደቢ ደሎ ተነስቼ ደደሳ ከሚባል በረኃ ፩ ቡስጠኛ አገኘሁ ወንድሜ ምነው በጥዋቱ ደክመሃል አልኩት ተሙኔን አሮጌ ነው አንወስድም ብለውኝ ፪ ቀን ጦሜን አደርኩ አለኝ።ምን ይሻልሃል አልኩት እዚህ ላይ ጠላና ቂጣ ይሸጣል ብለውኛል እግዚአብሔር ቢያፈራቸው ቢሸጡልኝ ነዋ አለኝ እዚያም ቦታ ደረስን ጠላ ቂጣም የያዙ ሴቶች አገኘን ፣ ተሙን ቂጣ ሽጡልኝ አላቸው እስቲ ተሙኑን አሉት ፫ ተሙን ምረጡ ብሎ ሰጣቸው ፫ቱህም አይሆንም ብለው መለሱለት። ቢለምናቸውም እምቢ አሉት የራበው ሰው ክፉ ነውና ነጥቆ ለመሔድ አሰበ ፤ ዋ ወንድሜ እንደዬ ጨኸት እንደሆን ግራና ቀኝ በፈረስ ይመጣል ቢሆን ይገድልሃል ባይሆን በጦር እቂጥህ ላይ ወግተው ይይዙሃል ። ወደዳኛም ብትሄድ ፪ቀን ጦሜን አድሬ የብር ተሙን መርጣችሁ ውሰዱ ብላቸው እምቢ አሉኝ ቢርበኝ ነው ብትል ትቀጣለህ ነው የሚሉህ አልኩት ጅብ ሲበላህ በልተሸው ተቀደስ ነው አለ አደለም ወንድሜ ለኔም ትተርፈኛለህ ትንሽ ድርቆሽ አለችኝ እሷን በልተን ለነገውም እግዚአብሔር ያውቅልሃል ወንድሜ ኢትዮጵያ በሌባሻይ ተበጥብጣ ሲታለቅስ ስትኖር ልዑል የኢ መ አ ወ ተፈሪ መኰንን ለሕዝባቸው አዛኝ ናቸውና ሌባሻይን አጠፉልን ። ዛሬ ግን አማራ ጋላ ሻንቅላ ጊሚራ ለደግ አድራጊ ንጉሣችን ዕድሜና ጤናውን ይስጥልን እያሉ ይመርቃሉ ፤ አሁንም በየመንገዱ በተሙን ያለ ችግር ብዙ ስለሆነ የድኃውን ችግር የሚጠቅም መንግሥት ነውና ተሙን በገባበት አገር ሁሉ ባዋጅና በግዝ ፣ ቢነገር መልካም ይመስለኛል ። ክቡራን አንባቢዎች ሆይ ሐተታው ስለበዛ አማርኛው ስለአልጠራ ይቅርታችሁን እለምናለሁ።

ሊበን ጣፈጠ ደቢ ደሎ

አበባ ባፍንጫ ።

ብዙ ሰዎች የአበባውን ጥቅምና ጉዳት ሳይለዩ አበባውን ከፍንጫቸው ውስጥ አድርገው ሲሔዱ ይታያሉ እንዲህ ያለ ልማድ ግን ሰውነትን ይጎዳል አበቦች ሁሉ ለማየት መልካም ናቸው ይህ ስለሆኑ ግን እያሌዎች ከነርሳቸው ለጤናየሚጠቅሙ አይደሉም መርዝያ ለባቸውም ይገኛሉ።የተፈጥሮውን ነገርየሚመረምሩም ንብ ሳትቀር እንኳ ማርንዋና ሰፈፍዋን ስትቀስም የማትቀምሳቸው የአበቦች ዓይነት እንዳሉ ይላሉ ምነው መርዝያላቸው ስለ መሆናቸው ነው ።

ሰው ደግሞ በሚያደርገው ሁሉ የሚጎዳውንና የሚጠቅመውን ነገር ለይቶ ማወቅ ይገባዋል ። ደግሞም ብዙች መርዝ የሌለባቸው እንኳ ቢሆኑ አለልክ ማሽተታቸውም ብዙ ጉዳት ሊያመጡ ይችላሉ ፤ አበባዎች ዓይንን ደስ ያሰኛሉ ለጌጥም ይሆናሉ በልክ ሲሆን ደግሞ መዓዛቸው ደስ ያሰኛል ። ከልኩ ሲያልፉ ግን ጤናን ይጎዳሉ ። ጽጌረዳ መልካም አበባ ነው ። ዳሩ ግን እሾህ እንዳለበት ማሰብ ያስፈልጋል ። ሁሉ ጊዜ ከመልካሙ አጠገብ ክፉ አለ ። እንዲሁም ምንም የሚጠቅም ነገር ቢሆን ከልክ ሲያልፍ ሁሉ ይጎዳል ። ስለዚህ ቀኑን ሁሉ እንዴህ ያለ ብርቱ ሽታ ማሽተት ብዙ ይጎዳል ። ደግሞም ሰው በሚተኛበት ቤት ይልቁንም መስኮቶች ዘወትር የተዘጉ ሲሆኑ የአበባው ሽታ በርሱ ሲቀር እጅግ ይጎዳል። እንግዲያስ እንዴት እንድንጠቀምባቸው ማወቅ ያስፈልገናል።በቤት ዙሪያ በሥርዓት ተተክለውና በደህና ተጠብቀው ሲገኙ ቤቱን ያስከብራሉና ያስጌጣሉ ያስመሰግናሉም።ደግሞም ባለቤቱን ሳይቀር ያስከብራሉና እንዲሁም በቤት ውስጥ በገበታ ላይ ሲሆኑ ቤቱን ያሳምሩታል ። በተቀር እንደዚህ ብዞች እንደሚያደርጉት ለጤና አይበጅም ። ያ በሰው ሥራ የወጣ ልዩ ልዩ ዓይነት ሽታም ሳይቀር ከልክ ሲያልፍ ይጎዳል።

ከዚህ ሁሉ ጋር ግን አበባዎችን እጅግ መውደድና መትከል በብዙ ጥንቃቄም እንዲጠበቁ ማድረግ የሥልጣኔን ባሕርይ ይገልጣሉ ። አእምሮው የተከፈተና በጎውንና መልካሙንም ነገር ሁሉ የሚወድ መሆኑን አበባዎችን በመውደዱ ያሳያል ። በነርሳቸውም የፈጣሪውን የማያልቀውን ጥበብና ቸርነት ሊመለከት ይችላል ፍጥረትንም በማወቅና በመመርመር ፈጣሪውን ወደ ማመስገን ይደርሳል።ጌታችንም የሱስ ክርስቶስ አበባዎችን ተመለከተ እንጅ አልረሳቸውም በቅዱስ ወንጌሉም ደግሞ ከርሳቸው ትምርት ልንወስድ እንደሚገባን ያስታውሰናል ፤ የምድረ በዳውን አበባዎች እዩ ይለናል ። አይሠሩም አይፈትሉም ሰማያዊ አባታችሁ ግን እንዲህ አድርጎ በልዩ ልዩ ስብቅል ቀለሞች ያስጌጣቸዋል። ቀጥሎም ይላል ፤ ሰሎሞን እንኳ በዚህ ሁሉ ክብሩ ከነዚህ አበባዎች እንዳንዲቱ አድርጎ አለበሰም ። እግዚአብሔር ሜዳውን እንዲህ የሚያለብሰው ከሆነ እላንት ሃይማኖት የጎደላችሁ እናንተን ይልቅ አያለብሳችሁምን ። አሁንም ምን እንበላለን ምንስ እንለብሳለን አትበሉ አሕዛብ ሁሉ ይህን ይሹታልና ። እላንት ይህን ሁሉ እንደምትሹ ግን የሰማይ አባታችሁ ያውቃል ። ስለዚህ እንዴህ ያለውን መጨነቅና አሳብ ተዉት እግዚአብሔር ባለቤቱ ያስብላችኋል ልባችሁ በዚህ አሳብ ቢጨነቅ እንደ አረማውያን መሆናችሁ ነው ። እናንትስ አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም እሹ ይህ ሁሉ ግን (ምድራዊው መሻታችሁ) ይጨምርላችኋል ። ይህ ከሆነ አበባዎች ሆኑ ሌላውንም አትክልት የሆነውንም ፍጥረት እግዚአብሔር የሰጠንን እንደ ፈጣሪው አሳብ እንጠቀምበት እንጅ አናበላሸው ወይም ባለማስተዋላችን በርሱ ባንዳች ነገር ሰውነታችን አንጎዳ ።

የከተማ ወሬ ።

በእሁድ ቀን ለመናፈስ ወደ ጃን ሜዳ ሂጄ ነበር ።

፪ ጎበዛዝት እንቀዳደም እያሉ ሲፈካከሩ ስመለከት ቄይቼ ፩ኛው ኃይለኛ ጎበዝ ነበርና አንተን እንዲያውም አንተን ፊት ለፊት አልቀዳደምህም ። ፊቴን ዙሬ በኋሊት ሩጬ እቀድምሀለሁ እንጂ አለው ። ፪ኛውም ጎበዝ እንኳን የኋሊት ሩጠህ ልትቀድመኝ በፊት ለፊትም ሩጠህ አትቀድመኝ ቢለው እንሩጥ እንሩጥ ተባባሉና ሩጫቸውን ጀመሩ ። አሚሮጡትም

ከታች ወደ ላይ ነበር ። ለጊዜው በፊት ለፊት የሚሮጠው ጕበዝ ቀድሞ አለ ። ገና እመካከል ሳይደርስ እንቀፈውና ወደቀ ።

ያ ግን ወደ ኋላው የሚሮጠው ጕበዝ ቀድሞት እላይ ቁሞ እየሁት ወዲአውም ይኸውልህ እኔ ጕበዙ ወደ ኋላዬ ሩጬ ቀደምሁህ አለው ። አዬ ወዳጄ አነቅፎኝ ብወድቅ ነው እንጂ መቅደምህ ቀርቶ መቼ ትደርስብኝ ነበርህ ቢለው ። ይህስ እኔም ገርሞኛል ወደ ኋላ እምሮጠውን እንቅፋት ሳያገኝኝ እያየሁ ወደፊት እምትሮጠው መሰናክልህ አለው ። ይህማ ጊዜ ነው ቢለው ግድ የለም እንኳን ቀደምሁህ እንጂ ብቻ አሁን ውርርዱን አምጣ አለው ።

እሱም እሺ ወንድሜ እሚገባህን እስከ አመጣልህ ድረስ ልብሴን ውሰድ ቢለው ልብሱን ተቀብሎ ደርቦ ለብሶት ሄደ ። ወደፊት የሮጠው ግን ልብሱን ተገፎ ሄደ ግሩም ነው ይገርማል ይደንቃል ፡ እያየ እሚሮጠው መሰናክል እንዲአው በመላ ሳያይ የሚሮጠው አለመሰናከል ይህ ነገር ቢደጋገም እስከመቸውም ቅይን አያስመኝ ነበር እያልሁ ስደነቅ ቆይቼ ወደቤቴ ተመለስሁ። ይህንስ ነገር ብቻዬ ተደንቄበት አልቀርም ብዬ በብርሃንና ሰላም ለምትኖሩ ባለ አእምሮዎች ወንድሞቼ ላስታውቃችሁ ወደድሁ በምሥጋና እንድትቀበሉኝ እለምናለሁ።

ተመልካች የነበርሁት ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ።

የውጭ አገር ወሬ

ከዴይሊ ታይምስ የተተረጐመ

የአሬዎፕላን ረዳትነት።

በማሮኮ በጕርፍ በሆነ አደጋ ብዙ ጕዳት ተገኘ ሩፊይራ የተባለ ወንዝ ከውሃ ሙላት የተነሣ ፫ ጫማ የሚያህል ከፍ አለና ባጠገቡ የነበሩ አገሮች አጥለቀለቃቸው ። ዊዘን በተባለ ከተማ ሦላሳ ቤቶች አፈረሰ በዊዘን የነበረ አዲስ ድልድይም ጕርፍ ይዞት ሄደ። ጃምዓ ጨርሳ በውኃ ተከበበች ከኬንቲራ ወደ ሱክእልአርብ የሚወስድ ዋና ዋና መንገድ ስለፈረሰ የሚገባና የሚወጣ ንግድ አቋረጠ። ስለዚህ ጕርፍ ለከበባቸው አገሮችና መንደሮች የሚለቴር አሬዎፕላን ረዳቸው መስጠም ላሰፈራቸው ሰዎችም በአሬዎፕላን ጀልባ ያቀብሏቸው ነበር ። ደግሞ ራባትና ሱክ እልአርባ የሚያገናኝ መንገድ ስለፈረሰ ለተቸገሩ ሰዎች ምግብና ልብስ በአሬዎፕላን ያመላልሱ ነበር። ሱክ ኤልቴታ ጨርሳ በውኃ ስለተሞላች ብዙ ሰዎች ከከብቶቻቸው ጋራ ከከተማው በውጭ ባሉ ተራሮች ላይ እስከ ሶስት ቀን ድረስ ምግብ አጥተው ተገኙ ።

ማስታወቂያ

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኮንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
ደግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፭ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር	፱ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፲ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ብር
ጎሐ ጽባሕ	፭ብር
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፪መ
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ብር
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ተኩል
የቁጥር ትምርት	፩ብር
ያማሪኛ ሰዋስው	፩ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	አላድ
ወዳጄ ልቤ	፫ሩብ
አጭር የዓለም ታሪክ	አላድ
ያማሪኛ ፊደል	ሩብ
አሳብና ምኞት	ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት	ሩብ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር	፪መ

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲ ብር ተሩብ
የሲዳሞ ቡና	፩	፱ ብር ከሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፪ ብር ከ፫ሩብ
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፪ ብር ተኩል
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፴፩ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጂ	፯ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጂ	፲፰ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጂ	፻፴፱ ብር
: : ባለሰይጣን	: :	፻፵ ብር
: : ባለ ድመት : :		፻፵፰ ብር
: : ባለአህያ	: :	፻፴፩ ብር
: : ባለሳቢ ግመል	: :	፻፵፬ ብር
ባለ አንበሳ	: :	፻፵፯ ብር
ሱካር	፩ ጁኒያ	፴፯ ተኩል
ቻይ	፩ ነጥር	፲፪ መ

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ ከ፵ ሳንቲ
አንድ ብር	ሊሬ ፱ ከ፲፭ ሳንቲም
ባንድ ጊኒ	፱ ብር ከ፹፭ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፵፬ ብር

CꝹGNAC S. E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ፡፡

ማስታወቂየ ።

ሺብሮሌ አቶሞቢል ።
በኢትዮጵያ ወኪል ።
ሔ ሜ ዜርቦስ ኩምፓንያ ።

Automobiles CHEVROLET
AGENTS

H. M. ZERVOS & Cie.



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የሚባል ባለ ፈረስ ስዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩግቢ

RUGBY

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚሁ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያየዚህአቶመቢልበተለይወኪል"አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ"ብቻነው

የዚሁም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፣በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፣ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፣ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ማስታወቂያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ፣ ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጅ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልካም ባርኔጣ ፣ ሽቱ ፣ ለስዮን ፤ አድኮሎኝ ፤ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፣ ካኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፣ ከፈይ ምንጣፍ ፣ ደግሞ በያይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስመጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሽምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክታችኋለሁ ፣ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ዓለም

ዓለም የወርቅ ጥልፍ ሥራ ሁሉ በውስጠ ብር ሆኖ ይሠራል ።

ኒኮላ ።

ማመልከቻ ።

በብርሃንና ሰላም ውስጥ ማስታወቂያ ማሳተም የሚፈልጉ ነጋዴዎች እስከ ፈለጉት ጊዜ ድረስ ባማርኛም ሆነ በፈረንጅ ቋንቋ በርካሽ ዋጋ እንደምናትምላቸው እናስታውቃቸዋለን

ጉድይር ግዙ





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም፡ ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው ። በሌላጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ፡ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ፤ ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን፡ ትሬዲንግ፡ ኩባንያ ቤት ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አራተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፮
4 me ANNÉE № 6

ሐሙስ የካቲት ፩ ቀን ፤ ፲፱፻፳ ዓ ም ።
JEUDI 9 FEVRIER 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ ፀ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የሰላሳ አምስት ገጽ ተከታይ

፲፩፥ እስረኞች ።

የእስረኞች አኗኗር ደግሞ ራሳቸውን ብቻ አይጐዳም ። የሕዝብ ጉዳትም ሳይሆኑ አይቀሩም ። ደግሞም ራሳቸው ብቻ እንኳ ቢጐዱ የሕዝቡ ጉዳት ነው ። ዘወትር እስረኞች የማይቀሩ ናቸው ። ኃጢአትና ዓመጻ ሳለ እስር ቤት ባዶ ሊሆን አይችልም ። ቢሆን ግን ጥዳትን በማጣት እለ ጊዜያቸውና ፍርዳቸውን ሳይቀበሉ ዝም ብሎ በከንቱ እንዳይሞቱ ወይነም ባንዳች ነገር ምክንያት እንዳይታመሙ መትጋት ያስፈልጋል ። ብዙዎች ሰዎች የሚሰበሰቡበት ሥፍራ ለልዩ ልዩ በሽታዎች የተመቸ ምክንያት እንዲያመጣ የተረጋገጠ ነው ። እንግዴህ ስፍራቸው ንፋስና ጸሐይ ብርሃንም እንዲገባበት ዘወትርም እጅግ እንዲጠዳ ማሰብ ይገባል ። ሠገራትንም በተገባ እንዲለይላቸው ። እስር ቤቶችም ከጊዜ ወደ ጊዜ ኖራ ሊቀቡ ያስፈልጋል ።

እስረኞች ጤንነታቸውን ሊጠብቁበት ከሚችሉበት ነገር አንዱ ይህ ነው ፤ እሥሮችን ብዙ ብርቱ ገመን የሌላቸውን በመንግሥት ሥራ ሲሠሩ እንዲውሉ ። እርሳቸው የገዛ ራሳቸውን ጤንነት ይጠብቁበታል ። መንግሥትም በሥራቸው ይጠቀማል ደግሞም መቀለባቸውን ላይቀር ነውና ። ደግሞም ቀለባቸውን ለማሸሻል በሚሠሩት ሥራ ይቻላል ። ሕዝብም በርሳቸው ጠቀሜቱን ያገኛል ። የሕዝቡም ቊጥር አያንስም ። በርሳቸውም ምክንያት በሕዝብ የሚራብ በሽታ አይሆንም ።

ግርፋታቸውን ማስቀረት እንዲገባ ስለማለት ። ብዝዎች ይህን ነገር ቢቀር ቅጣቱም በሌላ ዓይነት ባልተሻለምን ብለው ያስባሉ ይህንንም በማሰባቸው ስለ የሕዝባችን ክብርና ስም በማለት ነው በሌላ አሳብ አይደለም ። ቢሆን ግን ሕዝባችን ከዚህ በሮማውያን ሆነ በሌላዎች በቀድሞ ሕዝብ የነበረ ልማድ ዛሬ ነፃ ሊወጣ የሚቻል ጊዜ ወይም የሚጠቅም ነገር ይሆናልን ? ይህስ ሕዝብ ክብረቱ ሲታወቀው እንጅ በሌላ መንገድ ሊሆን አይቻልም ። ስለዚህ የአሁኑ ኑሮዋችን እያሰብን እስረኞችን ከዚህ ቅጣት ነፃ ሊሆኑ ለማለት ብዙ አስቸጋሪ ነው ።

የደግነት ትምሕርትና እውቀት ሳይሠለጥንበት ቅጣቱን በሌላ በደግነት መንገድ ቅጣት ቢቀበል ቅጣት መሆኑን አያውቀውም ። ስለዚህ ይህ ቅጣት ከቶ ሊለወጥ ጊዜው አይደለም ። በጎ ዕውቀት በሕዝብ ከሠለጠነ ወዲያ የሚመኝ ነገር ነው ። ዳሩ ግን ግርፋት የሚሆንበትን ምክንያትና ጊዜን መወሰን የሚቻል ነገር ነው ። እንዴህ ያለ አሳብም ከደገኛ አሳብ የተገኘ ሊሆን ይቻላል ። ሰው ራሱን ብቻ ሊያስብ አይገባውም ። ሰው ከሆነ የሰብአዊነትን ጭንቀትና ኃዘን ሊሰማው ይገባዋል ። የሌላ ሰዎችን ኃዘን እሰኪረሳ ድረስ በራሱ ደስታ ልቡ ሊደነዝዝ አይገባም ። የመልከሙንም ሆነ የክፉውንም ነገር በሰው ላይ ሲገጥመን የዚሁ ነገር ተካፋዮች ልንሆን የሰብአዊነት ተፈጥሮ ግድ ይልብናል ። የተቸገሩትን ሕይወት በረድኤታችን ሥራ ከፍ ለማድረግ ወደ አዘነተኞች ልቦችም እውተነኛው ማጽናናት ልናገባ የሰብአዊነታችን ባሕርይ አግበ መሆኑን እንወቅ ። ስለዚሁ በማንም በማንም ልባችንን በጭክና እንዳንዘጋ ይሁን ። እንዲያው አንዳች ነገር ለማድረግ እንኳ ኃይል የሌለን ብንሆን የሰዎችን ችግርና ኃዘን እደሚያሳዝነን ብናሳይ የኃዘናቸው ተካፋዮች መሆናችን ስለ ተረዱት ችግረኞቹ ኃዘናቸውን ይቀልላቸዋል ። ብቻ ልባችን ስላልተከፈተ ዓይኖቻችንም በቅን መመልከት በሚከበን ነገር መመልከት ስለአቃታቸው እንጅ ብዙ ነገር ልናደርገው የሚገባንና የምንችለውን በተገለጠልን ።

አሁን በዓለሙ በሰፊዉ በሠለጠኑቱ አገር ሕይወት ብናይ በእንደዚህ ያለ ትልቅ የዓለም ወይም የሕዝቦች ጭንቀት በገነነበት ጊዜ እርሱ በርሳቸው በአንድነትና በፍቅር ማኅበረተኞች ሁነው በልዩ ልዩ ዓይነት ማሕበር እየተሰሰሩ በውስጣቸው ያለ

ውን የሕዝባቸውን ጭንቀት ለማቅለል ዘወትር ይጣጣራሉ ልዩ ልዩ ዓይነት አዲሶች ማሕበሮች በየዓመቱ ይቆማሉ ልዩ ልዩ እያደገ የሚሔድ የሕዝባቸውን መሻት እያዩ እንዴህ ያለ መተባበርና የፍቅር ሥራ ስንት የማይቈጠረውን ችግርና ኃዘን አቀለለ ስንት የሚፈሰውን እንባም አበሰ ። ለሰው በቅዶ ለእንስሶችም ተርፎላቸዋል ። ስለእንስሶች አኗኑዋር የሚጠብቁ ማሕበሮች እስኪነሡ ሆነዋል ። ስለዚህ እኛም ወደዚሁ ደረጃ ልንደርስ በዚህ መንፈስ የተሠራና የቆመ የሕዝብ ሕይወት ልንይዝ ያስፈልገናል ። እንግዴህ ዓይነተኛውን ነገር ልንይዝ አዲስ የሕዝብ ሕይወትመሠረት ካልጣልን በእንዴህ ያለ መሠረትም የራሳችንና ይልቁንም የአዲሱ ትውልድ የወጣቱ ሕይወት ባይመሠረት ከንቱ ነው ።

ጦርና ብርቱ የሕዝብ ጥፋት ።
የጦርነት ምክንያት በዓለም ምንድር ነው?

ይህ የሕዝብና የመንግሥት ሕይወት በሚደርስ ነገር ትልቅ ጥያቄ ነው ፣ የታመመ ሰው በሽታውንና ፈውሱን ሊያውቅ ዋና ነገሩ አይደለምን ጦርነትም በዓለም ቢቀርብ ቢርቅ የማይታገድ መሆኑን እናውቃዋለን ። ታድያስ ጦርነት በዓለም የማይቀር ነገር መሆኑን ስናውቅ ምክንያቱን ማወቅ ዋና ነገር አይደለምን እንግዴህ ጦርነት ስለ ምን ይመጣል ?

የዓለም አዋቂዎች የመንግሥትም ትልልቆች የፖለቲክ ሰዎች ሳይቀር የዚህን ውጡራ መልስ ሊያገኙት ከቶ አይቻላቸውም ። በዓለሙ ስለ ሚሆነው በቅንና በትክክልነት ሊያውቅና መልስ ሊሰጥ የሚችል አንዱ እግዚአብሔር ብቻ ነው ። ስለ ዚህ ሰውነትን የሚያሳርፍ እውነተኛ መልስ ከዓለም አዋቂዎች መቈየት ከንቱ ነው ። ምንም ብዙዎች ሰዎች በቀድሞና በአሁኑ ዘመን ከሌላዎችም ጓደኞቻቸው ከፍ ያለ ዕውቀት ቢኖራቸው ዕውቀታቸው እጅግ የተወሰነ ነው። ወይም የሚበዛው በአሰት ዕውቀት የሚባለው ነው ። እነዚህ በገዛ ራሳቸው ይታመናሉ ከርሳቸው ሌላ ከፍ ያለ ዕውቀት ከቶውንም ሊዘልቁበት የማይቻላቸው እንዳለ ይሄው እውቀት ተመርምሮ ሊጨርስ የማይቻል መሆኑን ወደ ማወቅም ሲደርሱ በዚሁ ከአእምሮ ሁሉ ከፍ ያለውን ዕውቀት እግርጌ ወድቀው የገዛ ድንቁርናቸውን እየታመኑ ይሰግዳሉ ።

በቀድሞ ሰዎች ዕውቀት የተባለው ባሁኑ ሰዎች ግን የሚያስቅ ብዙ ነገር ይገኛል ። ጥሩ እውቀት ባንድ ቦታ ብቻ ይገኛል ። ስለ ዚሁ የከበረ ቦታ ዕውቀት የሚገኝበት ኢዮብ መረመረ ፡(ኢዮ ፳፰)እንግዴህ በሌላ ስፍራ መፈለጉ ከንቱ ነው ። እውነተኛው ዕውቀት ከእግዚአብሔር ብቻ ይመነጫል ። የመንግሥት ሰዎች በፖለቲክ ሥራ የገነኑ በዚሁ ረገድ እንደ አሳባቸው ብዙ ነገር ሊናገሩ ይችላሉ ። በዚህ መንገድ በዚህ ምክንያት እንዲህ ስለ ሆነ እንዲህ ሆነ ይላሉ ። ወደ እውነተኛው የነገሩ ምክንያት ግን ሊደርሱ ከቶ አይቻላቸውም ። ስለ ዚሁ አንዳንዱ ሲጨንቃቸውና ሲከብዳቸው እውተኛውን ምክንያት ለማግኘት ከፍ ወዳለው ዕውቀት ጠጋ ሊሉ ይወዳሉ ።

፩ ከብዙ ሳምንት በፊት አእምሮ ጋዜጣ በሕዝብ ማሕበር አንድነት ሥራ የዓለም ሰላም ሊጸና እንደማይችል አመልክተዋል ። ብዙዎች ሌላዎችም ጋዜጦች እያሌ ጊዜ ይህን ጥርጥር ይገልጣሉ ፡ ይህም ዕውቀት አቅንተው ከእግዚአብሔር ቃል በየመጡት በዓለም ከሚሆነው ነገር ከመጨነቅ የሰው ነፍስ ትወጣለች እንዲል በሉቃስ ፳፩፣ የሰው መንፈስ በዓለም ስለ ሚሆን ነገር አንዳች ነገር ይጫነዋልና ። የነገሩ አኳኋን ከሩቅ ይታየዋል ። በዓለም የሚሆነውን ነገርና ምክንያቱ ግን አምላክ በለቤቱ በቃሉ እንዲህ ብሎ ያስታውቃል ፤

፫ ስምዑ ነገሥት ወአጽምዑ መኳንንት ፤ አኀሊ ለእግዚአብሔር ወአንሰ እዜምር ለእግዚእ አምላከ እስራኤል ። ፬ እግዚኦ በፀአትከ እምነ ሴይር።ሶበ ተንሣእከ እምነ ሐቅለ ኤዶም ምድር አድለቅለቀት ወሰማይ አንጠብጠበ ጠለ ፤ ወደመናትኒ አንጠብጠቡ ማየ ። ፭ ወአድባር ተከውሱ እምነ ቅድመ እግዚአብሔር ዝንቱ ሲና እምቅድመ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ።

፮ በመዋዕለ ሴመገር ወልደ ቄነት በመዋዕለ ኢያኤል ኀደጉ ነገሥት ፍናዋተ ወሖሩ ፍናዌ መብእሰ ፍናዌ ግፍቱአተ ። ፯ ፣ ወኃልቁ ኃያላን እምነ እስራኤል ። ወኀልቁ እስከ ተንሥአት ዲቦራ እስከ ቆመት እም ለእስራኤል ። ፰ ወሠምሩ በአማልክተ ከንቱ ሶቤሃ ተቃተልዎን ለአህጉረ መሳፍንት ። ወኢያስተርአየ ወልታ ወረምሕ ፣ በአርባዕቱ እልፍ በውስተ እስራኤል ። »(መሳ ፭ ፣ ፫ ፤ ፰ ።)

የጦርነትና የመከራ ምክንያት እነሆ ። ይልቁንም ፫ቱ ኋለኞች ቍጥሮች ገልጠው እንደሚያመለክቱት ። ሕዝብ የእግዚአብሔርን መንገድ ሲተው ባልሆነውም ሲሔድ «ወሖሩ ፍናዌ መብእሰ ፍናዌ ግፍቱዓት» ካለ ወዲያ ቀጥሎ ወኃልቁ ኃያላን እምነ እስራኤል አለ ። ጨምሮም ፣ ሠምሩ በአማልክተ ከንቱ ፤ ሶቤሃ ተቃተልዎን ለአህጉረ መሳፍንት» አለ ። እስራኤል እግዚአብሔርን ስለተዉ ጦርነት በደጃቸው እንደሆነ ያመለክታል ። በመሳፍንት ትጐበኝ የነበረች አገር በኃጢአትዋ ምክንያት የሚረዱዋት ኃያላንዋ ጠፉባት ። ለጠላትም ክፍት ሆነች ። ዛሬም ክብርት ኢትዮጵያችን እግዚአብሔር አጥርዋና ምሽግዋ ሊሆን ይወዳል ። በውነትም እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ብትዘረጋ መድኃኒቱዋ ቅርብ ነበር ቢሆን ግን ከተቀደሱት ከእግዚአብሔር ሕግጋቶች እየራቅን እርሱ ያድነናል ብንል እስራኤልን ያጠፋ መታለል እንዳያጠፋን እንጠንቀቅ ። ሕይወቱን የማያድኗና የማያሻሻል ሕዝብ ጠፊ ነው ።

እግዚአብሔር ከኛ ምን ይሻል ? እመቦ ዘነገረከ ሰብእ ምንት ሠናይ ወምንት ይፈቅድ እግዚአብሔር እምኔከ ፡ ዘእንበለ ከመ ትግበር ጽድቀ ወታፍቅር ምጽዋተ ወትኩን ጥቡዓ ከመ ትትልዎ ለእግዚአብሔር አምላክከ ቃለ እግዚአብሔር ትስሚ በሀገርከ ከመ ያድኅኖሙ ለእለ ይፍርሁ ስሞ ። ስማዕ ሕዝብየ መኑ ያስተሬሲ ሀገረ ። (ሚክያስ ፮ ፰ ፱)

እግዚአብሔር ከኛ የሚሻውን ገልጦልናል ። በጽድቅ ጐዳናና በቃሉ እንድንመላለስ ይወዳል ። እርሱን ትቶ በሌላው መታመንና የተቀደሱቱ ትእዛዛቱን በመተላለፍ ሕዝብ ጦርነት

ይነግበታል ። ክቡር አንባቢ ሆይ ፤ ከጥፋትና ከጦርነት የሚጠብቅ ሌላ የተሻለና የታመነ መንገድ ሊያመለክት የሚችል አስን ? ባልሆነ ነገር ጆሮን ደስ በሚያሰኝ ማታለል ሕዝብን የሚያሰማ የሕዝብ ጠላት ነው እንጅ ወዳጅ ሊሆን አይችልም ።

ቀድሞ በእስራኤል አሰተኞች ነቢያት የጽዮን ልጅ ሰብራት ባልሆነ መንገድ ሊጠግኑ ጆሮችን ደስ ያሰኙዋቸው ነበር ሕዝብም በጅምላ እንዲህ ያለውን እንጅ የውነት ጠቀሜቱንና ጉዳቱን የሚገኙበቱን ነገር የሚነግረውን ደስ አያሰኘውም ። የጣፈጠ ነገር መታለልም እዩልን ይሉ ነበሩ ።

ሕዝቡን ማነጽ የሚሻ ግን እውነትን ብቻ እንጅ ሌላ ነገር አይችልም ። ወደ በሽተኛ የሚመጣ ሐኪም አስቀድሞ የበሽታውን ዓይነት በርግጥነት ማወቅ ይፈልጋል ሁለተኛም ለበሽታው የተገባውን መድኃኒት ይሰጠዋል ። ልበቅን ሐኪም በሥራው የበሽተኛውን ደህንነት ብቻ ይፈልጋል እንጅ የታመመውን ለጊዜው በማታለል ደስ ሊያሰኘው አይሻም ። በተገባም መድኃኒት አድርጎ ወደ ጤንነት ያደርሰዋል ። እንዲሁም የሕዝብም ሕይወት እጅግ የተረጋገጠ የደህንነት መንገድ እንዲይዝ ያስፈልገዋል ።

ኃጢአት ብቻ ነው ሕዝብን በብዙ መንገድ ጉዳቶቹን የሚገልጥ በዚሁ ነገር የብዙዎች የውጭ ሕዝብ ሁከት ባለፉቱ መቶዎች ዓመታት የሆነውን ብንመለከት እርግጥ መሆኑን እናገኛለን ። ሕዝብን የሚገለባብጥ ኃጢአት ብቻ ነው ። ከሕግ የሚወጣ ሕዝብ ቅጣቶቹን ሳያገኝ አይቀርም ። ላመጸኞች ከሕግ ለወጡ ሰላም የላቸውም ከዚህም ቀጥሎ ኃጢአት ይልቁንም ሕዝብንና መንግሥትን የሚያጠፉ ዓይነተኞች ምክያቶች እናስታውሳለን።

የምትጠፋ መንግሥት ።

፩ መለያየት ሕዝብንና መንግሥትን ያጠፋል

እርስ በርሷ የምትለያይ መንግሥት እርስዋ ትጠፋለች (ኢየሱስ) ጌታችን የቤተ ክርስቲያን ነገር ብቻ አይደለም፣ የሚያውቅ የመንግሥትንም ነገር አኳኋን ብጣም ያውቃል፡ ይህ እርሱ የተናገረው ነገር እጅግ የሚደንቅ ነው ። ሕዝብና መንግሥት ከውጭ ከሚጠፉ በውስጥ ከሚመጣው ምክንያት ይልቅ እንዲጠፉ ያስረዳል ።

ጌታችን ኢየሱስ እንደ ቀድሞዎቹ የጣዖታት ካህናት ኦራክል የተባሉ እንደ ሚሰጡት በአሰት ጥበብ በተደረገ መልስ አይሰጥም ። እኒሁ ካህናቶች በቀድሞ ዘመን አንዳች ስለሚሆነው ነገር ሲጠየቁ አጕል የሆነ መልስ እየሰጡ ሕዝባቸውን ያታልዋቸው ነበሩ ከነዚሁ መልስ ለምሳሌ እንሆ እንደ ሚከተለው ክሬሴዎስ የተባለ የሊድያ ንጉሥ (በቀድሞ ዘመን ከትንሽ እስያ አንድ ክፍል አገር ።ከታላቁ መንግሥት ከፋርስ ጋር ጦርነት ሊገጥም አሰበ ስለዚህ የዴልፊን ካህናቶች ድል እነሣለሁን ብሎ ጠየቃቸው እርሳቸው የፋርስ መንግሥት አደጋ ስትወድቅበት አንድ ታላቅ መንግሥት ታጠፋለህ ብለው መልስ ሰጡት ንጉሡም የመልሱን ነገር ሳይመረምርበት እጅግ ደስ ብሎት ሔደ ወዲያው ጦርነት ገጠመና ድል ተነሣ ።

ከዚያ በኋላ ተመልሶ የጣዖታትን ካህናት እንዲህ ብሎ ጠየቃቸው፡ «ምነው አንድ ትልቅ መንግሥት ታጠፋለህ ብላችሁኝ አልነበረምን ?» እርሳቸውም እንዲህ ብለው መለሱለት ታዲያሳ ከመንግሥትህ ታላቅ የሆነን ነበር ? መንግሥትህን እንጅ አጠፋህ «የሚሆነውን ነገር አስቀድመው አላወቁምና የማናቸው መንግሥት እንድትጠፋ ለይተው አልገለጡለትም ብቻ አጕል የሆነ መልስ ሰጡት ሁለት መንግሥታት ሲጋጩ አንዱ ድል እንዲነሣ እርግጥ ነው ።

የጌታችን የየሱስ ክርስቶስ መልስ ግን የተረጋገጠ ነው እርሱ ከወቀውና ከሰጠው መልስ ሊያመልጥ የሚችል የለም ስለዚህ በዚሁ በላይ በተነገሩቱ ቃሎቹ የማናቸውም መንግሥት ብትሆን የጥፋትዋ ምክንያት ምን መሆኑን ገልጦ አሳየ ። የምትለያይ መንግሥት እርስዋ ትጠፋለች አለ።መለያየት የጥፋት ታላቅ ምክንያት ነው ። መለያየትም ምክንያቶቹ አሉበት ። እንግዴህ በሆነው ነገር መለያየት የሚያመጡ ምክንያቶች ምንድርናቸው ? እያንዳንዱ የሚያስበውና የሚፈልገው ነገር ለብቻው ሲሆን ጊዜ መለያየት ይወለዳል ። የገዛ ራሱን አሳብና መሻትም ሲፈልግ ይህን አሳቡንና መሻቶቹን የሚፈጸሙበትን ሥራም ሊሠራ ይወዳል ። ከዚህም ጋር ጠብ ቅናት ምቀኝነት የተባሉ እየተቀላቀሉ መለያየቱን ያሰፋፋሉና ያበረታሉ ። መለያየትም የርሱ በርሱ ጥፋት ያወርዳል ። የጌታችን የየሱስን ምክር ልብ አድርገን እናስተውለው ። አንድ ሕዝብና አንድ መንግሥት ሆነን ልንኖር ብንፈልግ መለያየትንና የመለያየትን ዋናነገሮች ከመካከላችን እናርቅ ። ከነዚሁ ዋናዎች ምክንያቶችም ጥቂት እናመለክታለን !

፩ የመለያየት ዋና ምክንያት ራሱን መውደድ ነው ።

የክፋትና የመለያት ምንጭ ይህ ነው ። ሰው ራሱን ከወደደ በሚያስበውና በሚያደርገው ሁሉ የራሱን ጠቀሜት ብቻ ያስባል ። በሕይወቱ ሁሉ ለራሱ ተወስኖ ሲኖር ሌላ ነገር አያስብም ።

ከዚያ ወዲያ የባሕርዩ መሻቶች ብቻ ወደ ማግኘት ይተጋል ምንስ የሰው መሻቶች በጅምላ አሳብ አንድ ቢሆን በብዙ ነገር ግን እጅግ የተለያየ ነው ። አንዱ ሹመት ይወዳል ሌላውም ገንዘብ እንዲሁም በሌላው በሐጢያትና በሚያስጸይፍ ነገር አንዱ ይህን ሁለተኛውም ያንን ይሻል ። በመግደል ደስ የሚለው አለ በስርቆትም በሐሰትም ደስታውን የሚያይ አለ ። በእንዲህ ያለ እንግዴህ ሲንከረተት ይኖራል ። በጎ ነገርም ለማድረግ ጊዜ አያገኝም ። እንግዴህ ራሱና መሻቶቹን የሚወድ አገሩን ሊያስብና ሊወድ አያስብምና በአሳቡና በዓይኖቹ የገዛራሱን ጠቀሜቶችና እርሱ ራሱ ደስ የሚልበትን ብቻ ይገዛዋል ። የራሱ ጠቀሜትና የገዛ ሕዝቡ ጠቀሜት ወይንም ጉዳት ሲያይ የራሱን እንጅ የሕዝቡን ክፉ አይጠነቀቅበትም ። ብዙዎች ሰዎች አሉ በስራቸው ሆነ ባሳባቸው አገራቸውን አሳልፈው የሚሰጡ ። ክሰርክሰስ የፋርስ ንጉሥ ከእስጳርታ (አንድ የግሪክ ሕዝብ) ጋራ ሲዋጋ ሳለ አንድ የግሪክ ሰው ኤፊያልቴስ የተባለ ወራዳ ሰው ለክሰርክሰስ ግሪኮች ምንስ ትንሽ ሕዝብ ቢሆኑ እጅግ በርትተውበት ነበሩና የግሪክን ሠራዊቶች በስተ ኋላ

ቸው እንዲወድቅባቸው መርቶ አመጣው። የግሪክ ም ሕዝብ ክፉኛ ጽኑ ነበር ። በሕዝቡና በሹማምንቶቹ መካከል እንኳ አንድ አንድ መለያየት ቢገኝ ላገራቸው በሚደርስ ነገር ግን ፍጹም መሰማማት ነበራቸው ። እያንዳንዱ ምንም የራሱን ሹመት እንኳ ቢፈልግ ያገሩን ጠቀሜት በሚጠፋበት ወይንም የአገሩን ጕዳት በሚፈጽምበት መንገድ ምንም አይፈልግም ነበር ። ሁሉ አገሩን አጥብቆ ይወድ ነበረና ። ስለዚህ አገሩ ከምትጐዳበት የገዛ ራሱ ጠቀሜት እንዲጐድልበት ራሱንም እንዲጐዳ ይመርጥ ነበር ። እንሆ በዚያን ጊዜ ጠላቶችም ቢሆኑ እርሱ በርሳቸው የሚመቀኙ የነበሩትን በዚያን ዘመን ስለ አገራቸው እንዴት ያለ አሳብ በሁላቸው ልብ ይገዛ እንደ ነበር የአሪስቲደስ ቃል የሚመሰክር። አርሽቲደስ በምቀኝነት ምክንያት ሕዝቡ አባረውት ነበረ አገራቸው በፋርስ ንጉሥ መከራ በመጣበት ጊዜ ግን ሊረዳቸው ልከው አስመጡት ። እርሱ ያን ጊዜ ተሚስቶክሌስን እንዲህ አለው። አሁን እንግዲህ ሌላ ጦርነት በመካከላችን ሊሆን አይችልም ከዚሁ አሽቅድድም ከማድረግ በቀር ማን አጥብቆ ለአገሩ ጥቅም እንዲሆን። ዛሬም በሹማምንቶችና በሕዝብ በያንዳንዱ መካከል መለያየት ምቀኝነት እንዲሁም የሚመስለውን ክፉ ነገር ብይርቅ አገር የምትጠፋ ያን ጊዜ ነው ። እውነተኛ ያገር ፍቅር መጥፎውን ሁሉ ያጠፋዋል ። የኢትዮጵያ ሕዝብ መኳንንቶች አገረ ገዦችም በግርማዊት ንግሥታችንና በልዑል አልጋ ወራሻችን ዙሪያ እውነተኞች አገራቸውን የሚወዱ ወታደሮች ሆነው ቢቆሙ ኢትዮጵያ እንድትከበርና እንድትሰለጥን ጥርጥር የለውም ።

ከዚህ የቀረው በሚከተለው ይታተማል ።

ትጉ ጠባቂ ።

ወገን ጠባቂ ሙሴ ለበጎቹ እረኝነቱ ምስጉን ነበረ ሲጠብቃቸውም ዝንጥል ዘንጥሎ ቅል አንጠልጥሎ አይደለም ። ከግብጽ ደዝዋት የወጣ ገባሬ ተአምር በትር ነበረችው ይትከላታል የለመለመ ሣር የጠራ ውሀ ይገኝላቸዋል ያነን ተመግበው ሠራዊት ንጉሣቸውን ደቀ መዛሙርት መምራቸውን እንዲከተሉ እየተከተሉ ይመገቡ ነበር ተብሎ ይተረካል ። ይኸውም ጠባቂነቱ በእግዚአብሔር ዘንድ ተመስግኖ የእስራኤል ወገኖች ወገን ጠባቂ ሆኖ አርባ ዘመን ኖረ ።

ዳዊት ወገን ጠባቂ ነበረ በጎቹን ከነጣቂ ከናቂ በወንጭፍ ጠብቆ ኖረ ተብሎ ይተረካል ። ይኸው ጥበቃው በእግዚአብሔር ዘንድ ተመስግኖ የወገኖቹ የእስራኤል ዋና እረኛ ሁኖ አርባ አመት ጠበቀ። እንደዚሁም ሁሉ የክህነትና የመንግሥት ጠባቂ ልዑል አ ወ ተ መ መጻሕፍትን በትርጓሜ አስወጥተው ከመመከልትዎየተነሳ ወገን ጠባቂ መሆንን ልብዎ እስቦ እስበውም አልቀረ ለበጎች ለብቻ አጥር አጥረው ቅጥር ቀጥረው አምስት እረኞች አቆሙ ። ለፍየሎችም እንዲሁ አደረጉ ። ነገር ግን አንበሳም ነብርም ጅብም ተኩላም ፈርተው ከወገን የማይደርሱ ከሆነ በኋላ አንድ አውሬ መልኩና ፍጥነቱ የሳት ራት የሚመስል አካሄዱ እንደባብ በልቡ የሚሳብ ስሙ ጉብ ይባላል ። አጥር ቅጥር አያስፈራው ጨለማ ይደፍራል በዝግ ደጅ በተአምራት እየገባ ፈጃቸው የሚያዩትን እደማያዩ የሚያውቁትን እንደ ማያውቁ አድርጎ ያታልላቸዋል። ልዑልም በዚህ ነገር ተጨንቀው ብርሃንና ሰላም የሚባለውን ፈላስፋ ምክር ቢጠይቁት ይህስ አይቸግርም ይህ አውሬ ራስ ምታት አለበት ጩሆ አልፈልግህም ያሉት እንደ ሆነ ድራሹ ይጠፋል አለ ። ምሳሌ ፤ ቀድሞ ያርማጭሆ ዘሆን ደም ቢያ ወጥቶ ሰው ሲያድን ጃን ጃን ያሉት እንደ ሆነ ጥሎ ይሄዳል ።

አንበጣም በራላ ዘመን ጥሎህ ሂደ ጥሎህ ሂደ ያሉት እንደ ሆነ ከሀሉ ተነሥቶ ተከታትሎ ይጓዛል ። ነምርም ግራ ዓይኔን ግራ ዓይኔን ያሉት እንደ ሆነ ጠቡን ትቶ ዘወር ይላል ተብሎ ይነገራል ። ይኸም አውሬ በሹክሹ፦ መድፍ ከሚያልቡበት ጩሆ ቢናገሩት ይሸሻል ካለዎ በኋላ ጩኸው የሚናገሩ ደረቅ ደረቅ ሰዎች በየቅጥሩ አቁመው ፊቱን መልሶ መሄድ ጀምሮ አል፡ ምኞትዎ እግዚአብሔር ይፈጽምልዎ ብሎ ብርሃንና ሰላም ተስፋ ሠጠ ።

አለቃ መርሻ ዘውእቱ መርስዔ ኀዘን ።

የሰላሳ ስድስት ገጽ ተከታይ

ዘይሜህሮሙ ለሰብአ ጥበበ ።

የሰው ዓይነቱ ፫ነው ይባላል አንዱ ብልህ ነው ሁለተኛው የብልህ ብልህ ነው ። ፫ተኛው ሰነፍ ነው ። ብልህ የሚባለው መከራን ባገኘው ጊዜ የማይደነግጥ ልቡናው የማይበተን ዕውቀት የማያጥረው የሚያወጣው ብልሃት የማይጠፋው የብልህ ብልህ የተባለው ከዚህ የሚበልጠው ሰውነቱ የማይሳሳ በሚሆነው ነገር ሁሉ የሚደፍር የሚመጣውን ነገር ሁሉ በየዓይነቱ የሚመልስ ብዙ መሣሪያ ያለው መከራ ሳያገኘው በፊት አስቀድሞ አለብኝን አውቆ ምናልባት ወደፊት ይመጣብኛል ብሎ የሚጠረጥረውን መከራ ሳይንቅ ትንሹን ስለ ትልቅ ቆጥሮ መከራ ሳያገኘው በውነት ያገኘው አስመስሎ የሚያወጣውን ብልሐት አዘጋጅቶ ተጠንቅቆ የሚመጣውን ነገር የሚጠብቅ ሕመም ሳያገኘው ለደዌ መድኃኒት አሰናድቶ የሚኖር የሚመጣውን የሚመጣውን ነገር ሁሉ ሳይደርስበት የሚመልስ ሰው ነው ።

ሰነፍ የተባለው ልሂድ ልቅር ልበል ልተው የሚል በልቡናው ቆርጦ ፲ ንዱን ሳይዘው በመሃል ቤት እየዋለለ ምኞትና ችልታ ሲያበዛ ሥራውን በፍጥነት ሳይፈጽም ቀርቶ ሲጓደድ ጥፋት የሚያገኘው ሰው ነው ። ከሥራ ደጉ መጨረሻው ያማረ ነው ከሴትም ደጓ የባሏን ፈቃድ የምትፈጽም ናት ፤ ከምስጋናም ደጉ በጻድቃን በበጎ ሠሪዎች አንደበት የተነገረው ነው ከነገሥታትም በልዕልና የሚበልጥ ንጉሥ የጥጋብ ሥራ የማይሠራ ኩራትና ትዕቢት ያልተዋሃደው ነው ምክርንም ለመስማት የማይኰራ ነው ። ነገር ግን ሰምቶ የሚያደርጉትና የሚተውት አለ ከባሕርይም ደጉ እግዚአብሔርን ለመፍራት የሚረዳ ነው። የዚህም ምሳሌ የ፫ዓሦች ምሳሌ ነው ። ሶስት ዓሦች ያሉበት የጠራ ትልቅ ባሕር ነበረ ይላሉ ከነዚያም ከ፫ቱ ዓሦች አንድዋ አእምሮ ያላት ብልህ ነበረች ፪ኛዋ ከሷ የበለጠች

ዕውቀት ያላት የብልህ ብልህ ነበረች ። ፪ኛዋ ግን ዕውቀት የሌላት ሰነፍ ነበረች ። ያም ጥልቅ ባሕር ከፍ ያለ በገለልታ ቦታ አንድ ሰው ስንኳ የማይደርስበት ካጠገቡ ፈሳሽ ወሀ ያለበት ነበርና ከዕለታት አንድ ቀን ሁለት አሥጋሪዎች በፈሳሹ አጠገብ ሲያልፉ ያነን ጥልቅ ባሕር አዩ ወደዚያ ባሕር ተመልሰው መጥተው በሱ ውስጥ ያለውን ለማደን ተቃጠሩ ዓሣዎችም ያዳኞችን ነገር ሰሙ አሳባቸውንም ዓወቁ ዕውቀት ያደረባት የብልህ ብልህ ያልናት ያዳኞችን ንግግራቸውን በሰማች ጊዜ ጠርጥራ ደንግጣ ፈርታ ዛሬ ነገ ሳትል ሳታወላውል ወዲያው በፍጥነት ተነስታ ከፈሳሹ ውሀ ወደ ጥልቁ ባሕር ገብታ ሰውነቷን ከመያዝ አዳነች ። ፪ኛዋ ብልህ የተባለችው ይህን ነገር ችላ ብላ ከቦታዋ ተቀምጣ ሳለች ሁለት አዳኞች ዳግመኛ መጡ እሷም እነሱን አይታ የሚፈልጉትን ነገር ሐሳባቸውን ባወቀች ጊዜ ውሀው በሚገባበት ቦታ ለመውጣት አስባ በፍጥነት ሄደች ያነን ቦታ አዳኞች ዘግተውት አገኘችው እሷም እነሱ እንደደረሱባት የምታመልጥበት መውጫ እንዳጣች ባወቀች ጊዜ አዝና ተክዛ በብዙ አድርጋ ተጸጽታ አለችም እጅግ አድርጌ አጠፋሁ ቸል የማለት መጨረሻው ይህ ነው ነገሩም እንደዚህ ሆኖ ተፈጥኖ ባየች ጊዜ ምን ብልሐት ይገኝልኛል የነገሩ መፈጸሚያው ጊዜው ካለፈ በኋላ የተገኘ ምክርና ጥበብ የፍጥነት እውቀትና ብልሀት እጅግም አይጠቅም ።

አእምሮ ያለው ሰው ግን ብዙ ችግርም ሳያገኘው በማናቸውም ባሕሪ ቢሆን ከዕውቀት የሚገኘውን ምክርና ብልሐት አይጠቅመኝም ብሎ ተስፋ አይቈርጥም ። የተቻለውን ያህል ብልሐት መፈለጉን አይተውም ብላ የሞተች መስላ አንድ ጊዜ በጀርባዋ ፩ ጊዜ በሆድዋ እየተገላበጠች በውሀው ላይ እያሰፈፈች ትሄድ ጀመር።አዳኞቹ በእንደዚህ ያለ አኳሆኑዋ ባዩዋት ጊዜ የሞተች መስሏቸው አንስተዋት በትልቁ ባሕርና በፈሳሹ ውሀ መካከል ባለ በደረቅ መሬት ላይ አስቀመጥዋት ። እሱዋም ወደ ፈሳሹ ውሀ ዘላ ገብታ አመለጠች ። ፫ኛዋ ዕውቀት የሌላት ደካማ ሰነፍ ግን ልሂድ ልቅር ስትል አንዷን ሳትይዘው በመካከል ቤት ሳታወላውል ታድና ተያዘች ።

ኩኑ የዋሃነ ከመ ርግብ ወኩኑ ጠቢባነ ከመ አርዌ ምድር ።

ቁም ጸሐፊ ገብረ ጻድቅ ።

ትንሽ ተረት ።

ስለ ናሥር እልዲን ሖጃ ።

አንድ ጊዜ ሖጃ አህያው ሊሸጥ ወደ ገበያ ሲአወርደው አህያው በመንገድ አዳልጦት ወድቆ ጭራውን ጭቃ አበላሸው ሖጃም ወይ አሲዳም ከብት ልሸጥህ ባመጣሁህ ሰዓት ገና መከራ ልታሳየኝ ትፈልጋለህን ብሎ ወዲያው ሰንጢውን መዞ ያህያውን ጭራ ቈረጠ ፣ በገጋርዎቹ ፊት ክፉ መልክ እንዳይሆንብትና እንገዛውም እንዳይሉት ብሎ ።

ገበያም በደረሰ ጊዜ ግማሾቹ ሰዎች ፤ አንት ሖጃ ደህና ንነህ አህያ ያለ ጭራ ልትሸጥልን ያመጣኸው ምን እናደርገዋለን አሉት።እርሱም ወንድሞቼ እናንተ በዋጋው ተስማሙ እንጅ ጭራውስ እሩቅ አይደለም ይሄውላችሁ ከዚሁ ነው አላቸው ።

የፈሎሶፎች ንግግር

ነገርና ደንጊያ ከሄዱ አይያዙም
ሳያስብ የሚናገር ሳያነጣጥር ይተኲሳል ።
በነፃነትም ልንኖር ሁላችን በቃላችንና በሥራችን ብዙ እንድንጠነቀቅ ይገባናል ።

ሚካኤል ማክራስ ፣

ገጸበረከት ።

አንድ ጠንካራ ገበሬ ባታክልቱ ውስጥ በትጋትና በደስታ ይሠራ ነበር ። አንድ ቀን በአታክልቱ ውስጥ በጣም ትልቅ የሆነች እንደርስዋ ያለ ትልቅነት ያለው ፍሬ ባገሩ ታይቶ የማይታወቅ ፍሬ አገኘና በመገረሙና በደስታው መካከል ይህችንስ ፍሬ ለንጉሥ ላበርክታት የሚል አሳብ አሰበ ። እንደ ደግ አሳቡም ሒዶ ለንጉሥ አበረከታት ። ንጉሥም የሥራው ፍሬና ደግ ሐሳቡን በማየት ደስ አላቸውና መርጠ ከፈረሶቻቸው አንድ ፈረስ እንዲወስድ አዘዙለት ። እርሱም ደስ ብሎት ስጦታውን ተቀብሎ አመስግኖ እጅ ነስቶ ሔደ ።

በዚያን ጊዜ ይህ ወሬ በከተማው ውስጥ ተሰማና አንድ ሃብታም ሰው ንጉሡ አንዲት ፍሬ ለሰጣቸው እንዲህ አድርገው በለጋስነት ከሰጡ ጥሩ ፈረስ ላበረከተ ምን በሰጡት ይሆን ብሎ አሰበና ወዲያው ከፈረሶቹ የበለጠውን ፈረስ መርጠ ወስዶ ለንጉሥ አበረከተ።

ንጉሥ ደግሞ የሃብታሙን ሰውዬ ተንኰል አወቁና ስጦታውን አመስግነው ተቀብለው አዛዣቸውን አስጠርተው ለዚህ ጥሩ ፈረስ ላመጣልኝ ሰውዬ ያችን ጥሩ ፈረስ የሰጠ ሁላትን ፍሬ ስጥልኝ ብለው አዘዙለት።

በአቶሞቢሎች ስለሚሆን ጉዳት ።

ይህ ጉዳት የከተማው ሰው ሁሉ ዕለት ዕለት የሚመለከተው ነገር ነው ። በነዚሁ አቶሞቢሎች ስንት ሰዎች ይጐዳሉ ኦቶሞቢሎቹ ቀጥ ከሌለው ፍጥነት የተነሣ ቅርብ ተነጥለው ለመገልበጥ ወደ መድረስ ይቀርባሉ ። በዚህ ልክ የሌለው ሩጫ በሳምንት ብዙዎች ሰዎች ይጐዳሉ ። ስለዚህ አቶሞቢሎቹ ከሚያመጡት ጥቅምነት የሚጐዱበት እንደሚበዛ ይመስላል ። ሰው ከተጐዳ ምን ጥቅምነት ተገኘ ?።

እንግዲህ የአቶሞቢል ነጂች የሰብአዊነት ርኅራኄ ሊገታቸው ይገባል ። ስለዚህ ለዚሁ ነገር ሌላ ከልካይ ሕግም ባላስፈለጋቸውም ነበር ። የሰው ልጓሙ ወይም እዛቡ አእምሮውና በጎ ሕሊናው ሊሆነው ይገበዋል ። ሰው ሁሉ የባልንጀራውን ሕይወትና ጠቀሜቱን እ ደ የገዛራሱ አድርጎ መጠንቀቅ ይገባዋል።ሰዎች ሊያደርጉላችሁ እንደ ምትወዱት እናንትም እንዲሁ አድርጉላቸው።ይህ የጌታችን የክርስቶስ ሕግ ዘወትር የሕይወታችን ድንጋግ ብናደርገው ሕዝባችን በብርሃንና ሰላም በኖረ ።

በሆነው ነገር የገዛራሱን ጉዳት የሚፈልግ ሰው አለን?ከቶ የለም ። እንደ ዚሁም በርሱ ሰበብ ለባልንጀራው ጉዳት ወደ መሆን የሚደርስ በእግዚአብሔር ዘንድ ሰው አይቈጠርም።ዳኑ

ግን ሁሉ አንድ ሆኖ እንዴህ ያለ ጥሩ ባሕርይ ሊገዛው አይሆንለትምና እንደነዚሁ ላሉት የሰብአዊነት ሕግ የሌላቸው በመንግሥት ሕግ በጽኑ ሊያዙ ይገባቸዋል ።

ቅዱስ ጳውሎስ እንዲል፡ሕግ ለሐጢአተኛ እንጅ ለጻድቅ አልተሠራምና ፡፡ መጥፎ ባሕርይ ያለው ሰው ክፋቱ በሕግ ሊወሰን ይገባዋል ። ቅን ወይም ጻድቅ ሰው ግን ለራሱ ሕግ ነውና በሥራውና በአኗኗሩ ማነንም አያሰለችም ። እንግዴህ እንዴህ ላሉት ይልቁንም የሰውን ሕይወት የማያከብሩ ብርቱ ሕግና ብርቱ መቀጮ በላያቸው ሊፈጸም ይገባል ፡፡

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል ።

ሀብቶቻችን ።

በዚሁ ስም ንጋት የሚባል ጋዜጣ እኒህ የሚከተሉትን የሌምን ቶልስቶይ አሳቦች በይፋ ያወጣል ።

አንድ ጐበዝ ሰማያዊው አባት ገፋኝ ብሎ ያጕረመርም ነበር ቸሩ አምላክ ይል ነበር በዙሪአዬ ብዙ ሀብት አከፍልዋል እኔን ግን አንዳችም አልሰጠኝም ። አንዳች ነገር ሳላገኝ የሕይወቴ መንገድ እንዴት አድርጌ እዘልቀዋለሁ ?

ይህን ይሰማ የነበረ አንድ ሽማግሌም ጠየቀው ፡ እውነት እንደዚሁ እንደምትለው ፍጹም ድሀ ነህን እግዚአብሔር ፍጹም አንዳች አልሰጠሽምን?፡፡ ጕብዝናና መልካም ጤንነት እንዳለህ ይመስለኛል።

አሆ ፤ በዚህስ አላጕረመርምም ብዙ ጤንነት የጕበዝም ብርታት አለኝ፡በኩራትም እሔዳለሁ አለ ።

ሽማግሌውም የጐበዙን ቀኝ እጅ ይዞ አለው ፤ ሽሕ ብር ቢሰጡህ ይህች እጅህን ባስቈረጥካትን ? አሆ፡ ምንም አይታሰብም ፡፡ ግራ እጅህንሳ ? ይህችንም ከቶ አይሆንም ፡፡

አሥርሺ ብር ቢሰጡህሳ ዓይኖችህን ባወጣኻቸውን?እግዚአብሔር ይጠብቀኝ ፡፡ ትልቅ ዕድልም ባገኝ በዚህ ባልለወጥሁትም።

ሽማግሌውም እንግድያስ ስለምንድር ነው ማጕረምረምህ ብሎ ጮኸ ። እግዚአብሔር ብዙዎች የከበሩ ነገሮች ሰጥቶሀል ። ልጄ ሀይ ጌታን አመስግን ።

መሞት

ክቡር ነጋድራስ ታፈሰ በሰኔ ፯ ቀን ፲፱፻፲፰ ዓ ም የተወለደው ልጃቸው የሳምባ በሽታ ታሞ ጥር ፳፩ ቀን ዓረፈ ።

ብርሃንና ሰላም ለክቡር ነጋድራስ ታፈሰና ለባለቤታቸው ለክብርት ወይዘሮ ሙላትዋ እግዚአብሔር ያጥናችሁ ይላል።

ማስታወቂያ ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
ደግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፭ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር	፱ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ብር
ጎሐ ጽባሕ	፭ብር
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፪መ
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ብር
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ተኩል
የቁጥር ትምርት	፩ብር
ያማሪኛ ሰዋስው	፩ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	አላድ
ወዳጄ ልቤ	፫ሩብ
አጭር የዓለም ታሪክ	አላድ
ያማሪኛ ፊደል	ሩብ
አሳብና ምኞት	ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት	ሩብ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር	፪መ

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲ ብር
የሲዳሞ ቡና	፩	፱ ብር
ዝባድ	፩ ወቄት	፪ ብር ከ፫ሩብ
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፩ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፪፻፭ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፳፮ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፳ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ክረጃ	፯ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ክረጃ	፲፰ ብር ተኩል
አቡጀዲ መነጽር	፩ ክረጃ	፯፴፭ ብር
፡፡ ባለሰይጣን	፡፡	፪፴፭ ብር
፡፡ ባለ ድመት ።		፪፴፪ ብር
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፪፳፰ ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፪፴፩ ብር
ባለ አንበሳ	፡፡	፪፵፭ ብር
ሱካር	፩ ጁኒያ	፳፯ ብር
ቻይ	፩ ነጥር	፲፪ መ

ስለ ምንዛሪ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ ከ፴፭ ሳንቲ
አንድ ብር	ሊሬ ፱ ከ፳፭ ሳንቲም
ባንድ ጊኒ	፱ ብር ከ፺፩ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፫ ብር

COGNAC S.a E.a A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



ከአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብ
የተመሰከረለት ዝኒት የሚባል ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

ሺብሮሌ አቶሞቢል ።
በኢትዮጵያ ወኪል ።
ሔ ሜ ዜርቦስ ኩምፓንያ ።

Automobiles CHEVROLET
AGENTS
H. M. ZERVOS & Cie.

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ግልጸ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያየዚህአቶመቢልበተለይወኪል"አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ"ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።



ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፥ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፥ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ማስታወቂያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ፤ ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጅ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልከም ባርኔጣ ፤ ሽቱ ፤ ለስዮን ፤ አድኮሎኝ ፤ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፤ ከኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፤ ከፈይ ምንጣፍ ፤ ደግሞ በያይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስመጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሽምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ እመለክታችኋለሁ ፤ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ዓለም

ዓለም የወርቅ ጥልፍ ሥራ ሁሉ በውስጠ ብር ሆኖ ይሠራል ። የምትፈልጉት ሁሉ ወደዓለም ቤት ይገኛል ኒከላ ።

ማመልከቻ ።

በብርሃንና ሰላም ውስጥ ማስታወቂያ ማሳተም የሚፈልጉ ነጋዴዎች እስከ ፈለጉት ጊዜ ድረስ ባማርኛም ሆነ በፈረንጅ ቋንቋ በርካሽ ዋጋ እንደምናትምላቸው እናስታውቃቸዋለን

ጉድይር ግዙ





ከሁሉ የሚገልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንከራ ነው ። በሌላጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ፤ ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ [መኰንን ማተሚያ ቤት] ታተመ ።)

አራተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፯
4 me ANNÉE № 7

ሐሙስ የካቲት ፰ ቀን ፲፱፻፳ ዓ ም ።
JEUDI 16 FEVRIER 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለ ሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d'Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé "Lumière et Paix".

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የባቡር ማረፊያ ቤት መሠረት።

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ ከወሰን ጀምሮ እስከ አዲስ አበባ የምድር ባቡር እንዲሠራ ስለ ፈቀዱ ከ፲፱፻፪ ጀምሮ እስከ ፲፱፻፱ ሲሠራ ቆይቶ በ፲፱፻፱ አዲስ አበባ ከተማ ደረሰ ። ከዚያም ጀምሮ እስከ ዛሬ በባቡር መቋሚያው እንደሚገባ ሆኖ የመንገደኞች ማረፊያ ቤት አልተሠራም ነበረና አሁን በ፲፱፻፳ ዓ ም የፍራንኮ ኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኩምፓንያ ይህን የመንገደኞች ማረፊያ የሚሆን ቤት ለመሥራት ስለ አሰበ ፕላኑንና መሐንድሱን ከፓሪስ አስመጥቶ ነበርና ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የመሠረቱን መጀመሪያ ድንጋይ በማዕዘኑ ላይ እንዲያኖሩ የምድር ባቡር የኩምፓንያ ጠቅላይ ዲሬክተር ሙሴ ካሚ በማክበር አስታውቆ ነበር ። ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንም በየካቲት ፰ቀን ፲፱፻፳ ከጧቱ ባራት ሰዓት የኢትዮጵያ መኳንንቶችን አስከትለው ወደ ባቡር መቋሚያ ወረዱ ።

ደግሞ በአዲስ አበባ የሚኖሩ የውጭ አገሮች የዲፕሎማቲክ ሰዎችና ትልልቆቹም የውጭ አገር ሰዎችና ወይዛዝሮች ሁሉ በዚሁ በዓል እየተጠሩ መጥተው ነበር ።

ከዚህም በኋላ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ለዚሁ ተብሎ በከፍተኛ ደረጃ በተሠራው ስፍራ ላይ ወጥተው በወንበር ተቀመጡ ። በስተ ግራም ብፁዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ተቀምጠው ነበር ። ሰዓቱም በደረሰ ጊዜ የፍራንኮ ኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኩምፓንያ ጠቅላይ ዲሬክተር ወደ ልዑል አልጋ ወራሽ ቀርቦ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ዲስኩር ተናገረ ።

ጌታዬ ፤

በአዲስ አበባ ባቡር መቋሚያ ላይ በባቡር የሚሳፈሩትን መንገደኞች መቀበያ ቤት ሲሠራ የመጀመሯውን ድንጋይ ለማስቀመጥ ልዕልናዎ በዛሬ ቀን በመምጣቱ ለኢትዮጵያና ለፈረንሳዊ የምድር ባቡር ኩምፓንያ ለተደረገለት ታላቅ ክብር ከሁሉ በፊት ለልዕልናዎ ምሥጋናዬን ማቅረብ ይገባኛል ።

ለኢትዮጵያ ጥቅም የሚገኝበትን መንገድ ለማስፋትና የኤክስፕሏታሲዮኑም ሥራ በለማቋረጥ እየተሻሻለ እንዲሄድ ፍጹም አሳቡ ስለሆነ ኩምፓንያችን ለንጉሡ ዋና ከተማ የተገባ የባቡር ማቋሚያ ሠርቶ ፤ ይኸውም የሚሠራው የባቡር ማቋሚያ ለጀመርነው ታላቅ ሥራ አክሊል ይሆነው ዘንድ ፈቀደ ። ይህ ታላቅ ሥራ ሲሠራ በብዙ ሀውከት መካከል እየተጋፋ ሲሄድ ፤ ብዙውንም ጊዜያት እንኳ የምድር ባቡሩን መንገድ እየተከተሉ በሚገኙት መቃብሮች እንደ ሚመሰክረው ፤ እጅግ የሚያሳዝን መሥዋዕት በማድረግ እየቀጠለ መሄዱን ጌታዬም አይስቱት ። ስለሆነ ግን ይህን ሥራ ለመፈጸም በመቻላችን ፤ ለአገሩ ልማትና ጥቅም የሚገኝበትን መንገድ እንዲቀና ለማድረግ ዋና መጀመሯ የሚያስፈልግ ነገር መሆኑ በየቀኑ እየተገለጸ በመታየቱ ደስታችንን የሚያበዛው ሆነ ።

ስለዚህም ታላቁ ንጉሥ ዳግማዊ አጼ ምኒልክ መጭውን ቀን በሚመለከት ታላቅ እውቀታቸው የኢትዮጵያንና የፈረንሳዊን የምድር ባቡር ኩምፓንያ አስበው አቆሙ ። የተገባቸውም ወራሾቻቸው ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ልዑልም የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና እንደራሴ የተጀመረው ሥራ እንዲፈጸምና የሥራውም አካሄድ እንዲከናወን አደረጉ ።

ለሥራው ጀማሪዎችና መልካም አድራጎች ደግሞም ምሥጋና ለማቅረብ ሲል በሚመጣውም ዓመት ግርማዊትንግሥት በተቀመጡበት ያዲስ አበባን ባቡር ማቋሚያ በታላቅ ክብር ለማስመረቅ ማሰቡን ኩምፓንያችን ምኞቱን ሲገልጽ ተስፋ ያደርጋል።

በዚያም ጊዜያት፣ የሥራው መልክ መጠንኛነት የፈረንሳዊን የጥበብ ሥራ ተከትሎ የተራሮችዎን ዙሯ ከሚወስነው ከሰማዩ ሰፊ ጠፈር ጋራ የተስማማ ሆኖ ባሪያስ የሚባለው መሐንዲስ ሥሎት ልዕልናዎም ፈቃዱ ሁኖ የተቀበለው ሥራ ተፈጽሞ ይገኛል ።

ይልቁንም ደግሞ የመሬቱ መሠረት ውሀ የተኛበት በታ ለሚያመጣው ችግር ሁሉ በተለይ ሥራው ለመሆኑ ምስክር ወረቀት ላለው ሶሴዬቴ ቴክኒክ ኤ አንዱስትሪዬል ዳንት ረፕሪዝለሚባለው ኩምፓንያ ይህንን ሥራ መስጠታችን ሥራው በመልክም ሆኖ እንዲፈጸም አጥብቀን ማሰባችን በዚያንጊዜ ከዛሬው ይበልጥ ተገልጾ ይታያል።

ኢትዮጵያ በመንግሥትዎ ከፈጸመችው የሥልጣኔ ሥራ ይልቁንም እመንግሥታት ማኅበር ከገባች ጀምሮ ማኅበረተኞች በሆኑት መንግሥታት መረዳዳት ይህን የሥልጣኔ ሥራ ባለማቋረጥ እየቀጠለ በፍጥነት ከሠራው ሥራው ሁሉ ይህ ልዕልዎና አትሞት የሚያኖረው ደንጊያ እንደኛው የሥልጣኔ ሥራ ምልክት መሆኑን ለሚመጣው ትውልድ ምስክር ይሆናል ።

ስለዚህ ፡ እዚህ በዓል በመምጣታቸው ከማመስገናቸው ከእነዚህ መንግሥታት እንደራሴዎችና ከተወላጆቻቸው ጋር ሁኜ ለግርማዊት ንግሥት ፣ ለልዕልናዎና ለኢትዮጵያ ልማት የምናቀርበውን መልካም ምኞታችንን ጌታዬ ሆይ፤በመልካም ፈቃድዎ እንዲቀበሉን እንለምንዎታለን ።

Discours prononcé par
Mr.CAMUT, Directeur Général de la Compagnie du Chemin de fer

MONSEIGNEUR,

Je dois tout d'abord remercier VOTRE ALTESSE I. & R. du très grand honneur qu'Elle veut bien faire au Chemin de fer Franco-Ethiopien en venant, aujourd'hui, poser la première pierre du Bâtiment à Voyageurs de la gare d'ADDIS—ABEBA.

Soucieuse de favoriser le développement économique de l'Ethiopie tout autant que de perfectionner sans cesse ses moyens d'exploitation, notre Compagnie a tenu à doter la capitale de l'Empire d'une gare digne d'elle et qui marque, en quelque sorte, le couronnement de l'œuvre que nous avons entreprise. Cette œuvre qui s'est poursuivie, comme vous le savez MONSEIGNEUR, au milieu des difficultés de tous ordres auxquelles elle s'est heurtée et souvent même, ainsi qu'en témoignent les tombes qui jalonnent la ligne, au prix des plus douloureux sacrifices, nous éprouvons à l'avoir réalisée une satisfaction d'autant plus grande qu'apparaît plus nettement chaque jour le rôle primordial qu'elle joue dans l'économie du pays et l'essort qu'elle a donné à sa prospérité.

C'est bien ainsi, d'ailleurs, qu'avec sa haute vision de l'avenir le grand Négus, S.M. L'EMPEREUR MENELICK. avait conçu le chemin de fer Franco-Ethiopien et que ses dignes succeurs. S.M. L'EMPERATICE ZAODITOU et VOTRE ALTESSE IMPERIALE & ROYALE en ont facilité l'achévement et la mise en exploitation.

pour rendre à l'impérissable mémoire de son créateur et a ses bienfaiteurs un solennel hommage, notre Compagnie se propose de procéder, l'année prochaine et, elle veut l'espérer. sous la haute présidence de S. M. L'IMPERATRICE. à l'inauguration solennelle de la gare d'ADDIS-ABEBA.

Alors seront réalisées les projets de l'architecte Barias, que VOTRE ALTESSE a bien voulu approuver, dont la sobriété des lignes allie si heursement la simplicité de l'art français à celle des larges horizons que limitent les contours de vos montagnes.

Alors. aussi, apparaîtra mieux encore qu'aujourd'hui le scuci que nous avons eu d'une exécution parfaite dans ces travaux que nous avons confiés à la SOCIETE TECHNICUE & INNOUSTRIEJLE D'ENTPRISES parce que ses brevets de construction s'appliquaent précisément aux difficulés d'un sol qui tire sa fécondité des narpes d'eau souterraines qu'il recéle.

En attendant, la pierre que va scéller VOTRE ALTESSE IMPERIALE et ROYALE marquera, pour les générations futures, l'un des nouveaux prégrès que l'Ethiopie sura réalisès sous son Gouvernement et qu'elle poursuit si rapidement depuis son entrée dans la SOCIETE DES NATIONS avex le concours des Etats qui en font partie.

C'est pourquoi, avec les Représentants de ces puissances et leurs ressortissants que je remercie d'avoir bien voulu honorer de leur présence cette Cérémonie, je vous prie, MONSEICNEUR, de vouloir bien agréer les vœux sincères que nous formons pour S.M. L'IMPERATRICE. pour VOTRE ALTESSE. IMPERIALE, commo pour la prospérité de l'ETHIOPIE.

ቀጥሎም የዲፕሎማቲክ ሰዎች ተቀዳሚ የሚሆኑ የቤልጅክ ሚኒስቴር ሙሴ ጀራር ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ዲስኩር ተናገሩ ።

ልዑል ጌታዬ ።

ክቡር ጠቅላይ ዲሬክተር ሆይ ፤

እጅግ መልካም የሆነ መሬቱና ዘፍጥረት የሰጠው ችሮታ እጅግ ከፍ ካለ ጥቅም ያደረሰው መስሎ የሚታይ አገር ፣ ለማድረግ የሚችለውን በግልጽ በሚመሰክርበት የዛሬውን ቀን በመሰለ የበዓል ቀን የዲፕሎማቲክ ሰዎች ክፍል ዝም በማለት ማሳለፍ የሚችለው ነገር አይደለም

ከብዙህ ሺ ዘመናት ጀምሮ የንጉሦች ርስት ለሆነው አገር በሥራም በእውቀትም ዘወትር እየገፋ የሚሄድ ልማት በማምጣቱ ታላቅነቱ የሚመዘንለት መልካም ሥራ የመፈጸሚያው ጊዜ ሲደርስ ከመገኘት ይበልጥ ለኢትዮጵያ ወዳጆች መንግሥቶች እንደራሴዎች ምን ደስ የሚያሰኛቸው ነገር አለ ። በእርግጥም ምንም የለ ።

ይልቁንም ደግሞ ከውጭ ዓለም ሕይወት ጋር አቀራርቦ በማስተቃቀፉና እንደዚህም በማድረጉ ከታላቁ ከመንግሥታት ቤተ ሰብ ውስጥ የተሰጠውን የክፍሉን ሥራ ፍሬ እንደሚያፈራ አድርጎ ለመፈጸም እንዲችል በመፍቀዱ ከኔ ይልቅ ሌሎች የኢትዮጵያና የፈረንሳዊ የምድር ባቡር ኩምፓንያ ለዚህ አገር የሠራውን ቁጥር ስፍር የሌለውን መልካም ሥራ ለማንሳት ይችላሉ ።

በዛሬው ዘመን እንደሚሠራው ዓይነት የባቡር ማረፊያ አዲስ አበባ ላይ መሥራት ፥ አሁን ላሉት ወደ ፊትም ለሚመጡት ትውልዶች ያለፈው ትውልድ በማናቸውም ረገድ የሚመሰገን ጥረት መጣሩን ብቻ የሚመሰክር ሳይሆን በማይዘነጉት በዳግማዊ ምኒልክ ፤ በስመ ጥሩዋ ልጃቸውና አላፊነታቸውን የሚገባቸውንም ሥራ በጥልቅ በሚከተሉት መስፍን እርዳታና ጥማ በየጊዜው እየበረከተ በሚሄድ መጠን አዲስ መልክ የምትቀበለውና በዚህም ምክንያት በዓለም ውስጥ በየስፍራው ሁሉ አገርን ለማየት የሚፈቅዱትን ለምታነቃቃዋ ዋና ከተማ ከሁኑ በአሳባችን ውስጥ ይህ የባቡር ማረፊያ እንደ መግቢያ በር ሆኖ ይታየናል ።

በዚህ አሳቤ ተማምኜ የኢትዮጵያና የፈረንሳዊ የምድር ባቡር ኩምፓንያ በሥራው ሁሉ በቀናው ቁጥር በማፍቀር ደስታ ማጨብጨባችንን በዲፕሎማቲክ ሰዎች ስም ሆኜ ጠቅላዩ ዲሬክተር ካሙ እንዲያምን ስለምን ፥ ከእርሱ ጋር ባንድነት ተባብሬ አክብሮት ከመላበት ማድነቃችን ጋር ፥ ታላቅ ለሆኑ ለክቡሩ ሰውነቶቻቸው ደስታን እንዲያገኙና ብርሃን ለሆነ ፍቅራዊ አሳባቸው ሁሉን የሚችል እግዚአብሔር አደራ ለሰጣቸው ባለዕድሊቱ መሬት ልማትን እንድታገኝ ምኞታችንን ከግርማዊት ንግሥትና ከልዑል እምልዑላን አልጋ ወራሽና እንደራሴ ጫማ ሥር እናኖራለን ። የካቲት ፰ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓመተ ምሕረት ።

Allocution prononcée
par Mr Gérard,
Ministre de Belgique en Ethiopie
Doyen du Corps Diplomatique,

MONSEIGNEUR,

Monsieur le Directeur-Général,

Le Corps Diplomatique ne pouvait être indifférent à une cérémonie qui, comme celle de ce jour, témoigne éloquemment des possibilités d'un pays qu'un sol merveilleux et une nature prodigue semblent appeler aux plus brillantes destinées d'ordre économique.

Rien ne pouvait, en effet, intéresser davantage les Représentants des Puissances Amies de l'Ethiopie que d'assister au parachèvement d'une œuvre dont la grandeur peut se mesurer au développement matériel et moral, toujours plus accentué, qu'elle a apporté au Patrimoine millénaire des Négus.

D'autres que moi retraceront les innombrables bienfaits dont le chemin de Fer Franco-Ethiopien a doté ce pays, notamment en l'associant plus intimemnt à la vie du monde extérieur et en lui permettant ainsi d'accomplir plus efficacement le rôle qui lui est assigné dans la grande famille des Nations.

Je me bornerai à constater que l'édification d'une gare moderne, a Addis-Abeba, non seulement attestera aux générations présente et future l'effort, en tous points remarquable, qui fut déployé par la génération passée, mais elle apparaît, d'ores et déjà, à notre esprit comme la "Porte d'Entrée" d'une Capitale qui, sous l'égide tutélaire de l'illustre Fille de l'Empereur Ménélik, d'impérissble mémoire, et d,un Prince profondément conscient de Ses dévoirs et de Ses responsabilités se pare tous les jours de nouveaux attaits, et élveille dans une mesure sans cesse grandissante la curiosité de touristes de tous les coins du globe.

C'est devant cette perspective que, au nom du Corps Diplomatique, je prie Mr le Directeur-Général Camut de croire à l'intérêt sympathique avec lequel nous suivrons toujours les progrès ininterrompus de la "Cie du Chemin de Fer Franco-Ethiopien", et que je me joins à lui pour déposer aux pieds de Sa Majesté l'Impératrice et de Son Altesse Impériale le Prince-Régent, avec l'hommage de notre respectueuse admiration, l'expression des vœux que nous formons pour le bonheur de Leurs Augustes Personnes et la prospérité de cette Terre privilégiée que le Tout-Puissant a confiée à Leur Sollicitude éclairée.

መሐንድሱ ሙሴ ሸቢላርድ የተናገሩት ቃል

ልዑል ጌታዬ ሆይ ፤

እላንትም ወይዛዝርና ጌቶች ፤

ሶሲዬቴ ቴክኒክ ኤስእንዱትሪዬል ዳንትርፕሪዝ የሚባለው ማሕበር ፤ አዲስ አበባ ላይ የሚሠራውን የባቡር መቋሚያ ለመሥራት በመታዘዙና ፤ ይህም በመሆኑ የፈረንሳዊና የኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኩምፓንያ የሠራው ታላቅ ሥራ በሚያደርገው እርምጃ ፥ የሥራው ተከፋይ ሆኖ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ፥ በሥራ ተከፋይነት ክፍል ለማግኘት ምክንያት ስለ ገጠመው ምስጉን ነው ።

ፓሪስ ላይ የሚያምሩ ቤቶች መሥራት በመልመድ በተገለጸልን እውቀት ያባቱን የታላቁ ሥዕል ቀራጺ የጥበብ መንፈስ ወራሽ ለመሆን የተገባው መሐንድስ ሙሴ ባሪያስ የሠራውን የተዋበ ፕላን ተከትለን ከሁሉ በበለጠ ጥንቃቄ አስመስለን ለመሥራት ደስ ይለናል ።

ጥቅም ያላቸው ብዙ የሚሠሩ ሥራዎች ያሉባት በምትመስል ወደ ሀገረ ኢትዮጵያ መጥተን ሥራችንን ለማቆም በመቻላችን ምስጋና አለን ። በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚሠሩት ሥራዎች መሠረቶቻቸውንና በግንብ የሚሠሩትን ቤቶች ሌሎችንም ለሕዝብ ጥቅም ያላቸውን ታላላቅ የመንግሥት ሥራዎች ሁሉ በፈረንሳውያን የሥራ ጥበብ ለመሥራት እንችላለን ።

ልዑል እምልዑላን አልጋ ወራሽና ከፍ ያሉ የኢትዮጵያ ሹማምንቶች በደረጉልን መልካም አቀባበል ልባችን ተነክቷል ጥንታዊ ሥልጣኔ ለአላት ለክብርት ሀገር ኢትዮጵያ ልማቷን የሚያሰፋትን ታላላቅ ሥራዎች ሁሉ የምንሠራው ከልባችን በሆነ በመልካም መረዳዳት ነው ።

Discours de M. Chevillard
directeur de l'entreprise

Monseigneur, Mesdames, Messieurs,

La SOCIETE TECHNIQUE ET INDUSTRIELLE D'ENTREPRISES se félicite d'avoir été chargée de la construction de la gare d'ADDIS-ABEBA et de trouver ainsi l'occasion de participer à une étape marquante de la grande œuvre dans l'histoire de l'ETHIOPIE qu'a entreprise la

Compagnie du Chemin de Fer FRANCO-ETHIOPIEN.

Nous serons heureux, avec notre expérience de la construction des beaux immeubles de Paris, de nous attacher à réaliser de la façon la plus soignée, le plan harmonieux établi par Monsieur l'Architecte BARRIAS, digne héritier de l'esprit artistique du célèbre statuaire, son père.

Nous nous félicitons encore d'avoir pu venir nous installer en ETHIOPIE où il parait y avoir à réaliser tant d'œuvres intéressantes dans lesquelles nous pourrons appliquer la technique française pour les fondations, les bâtiments, et tous autres grands travaux publics.

Nous avons été touchés de l'aimable accueil qui nous a été réservé par Son Altesse Impériale le Prince Héritier et par les houtes autorités éthiopiennes, et c'est de tout cœur que nous appliquerons notre meilleurs collaboration à l'exécution des grandes œuvres devant développer la prospérité du noble pays de si ancien ne civilisation qu'est l'ETHIOPIE.

የፈረንሳዊ ጉዳይ ፈጻሚ ሙሴ ደ ስዩ ሞበሊያር የተናገሩት ቃል ፡

ልዑል ጌታዬ ሆይ ፤

አዲስ አበባ ላይ ለሚሠራው የባቡር መቋሚያ መጀመሯውን ደንጊያ ለማስቀመጥ በመፍቀድዎ ለዛሬው በዓል ያዘጋጁለትን ከፍ የማድረግ ሥራ ለመግለጽ ፈቃድዎ ሆነ ።

የውጭ አገር መንግሥታት መልክተኞች በቀደምትነት የበላይ የሆኑትን የሥራ ጓደኞቻቸውን ይዘው የኢትዮጵያና የውጭ አገር መኳንንቶችም በመምጣታቸው የዚህን ቀን ታላቅነት ያገነዋል።

ከእንግዲህ ወዲህ አዲስ አበባ ለኢትዮጵያ ዋና ከተማ የተገባ የባቡር ማረፊያ ታገኛለች ።

ሥራውም እዚህ መድረሱ በፈረንሳዊና በኢትዮጵያ መካከል ባለው በፍቅር ስምምነት የተነሳ በመሆኑ በእኔ ወገን ስለተረዳሁ ልገልጸውም በተለየ ደስ ይለኛል ።

ግርማዊ አጤ ምኒልክ ከፍ ያለ ተራራማ ሀገራቸውን ከባሕር ጋራ የሚያገናኝ የባቡር መንገድ የሚያመጣውን ታላቅ ጥቅምና አገልግሎት ተረድተውት ነበር ።

ይህም የተመረጡ ሠራተኞች በፈረንሳዊ ገንዘብ የፈጸሙት የምድር ባቡር ሥራ የሚሠራው ታላቅ ቤት በተፈጸመ ጊዜ የሚገባውን አክሊል ሊያገኝ ነው ።

በሥራ ለሥራም በመጠንከር ለሚገኘው መልካም ፍሬ ምሳሌና ለሚመጣውም ጊዜ ትምሕርት ሆኖ ይኖራል ።

ሁለቱን ሀገሮቻችንን የሚያስተሳስሩ መልካም የፍቅር መገናኛዎች ከብዙ ዘመናት በፊት ጀምረው ይኖራሉ ።

እጅግም ወደ ራቀው ዘመን ለመሄድ ሳልፈልግ በግርማዊት ንግሥትና በልዑል አያት በንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ደግሞ በፈረንሳዊ ንጉሥ በሉዊ ፊሊፕ መካከል የተቋጠሩትን የወዳጅነት መገናኛዎች አሳስባለሁ ።

እነዚህም የፍቅር መገናኛዎች ከዚያ ቀን ጀምረው ጥላ ሳይጥልባቸው ጸንተው ኖሩ ። ለሚመጣውም ጊዜ እንደዚሁ ጸንተው እንዲኖሩ የአምላክ ፈቃዱ ይሆናል ብዬ እምናለሁ ።

የወዳጅነት ማስተሳሰሯዎች ዘወትር ከፍ ያለ ዋጋ ያላቸው ናቸው ።

ሁላችንም እዚህ ስንመለከተው ደስ የሚለን የሥራ ፍሬና አፈጻጸም በወዳጅነት ማስተሳሰሯዎች ሲገኙ እነዚህ ማስተሳሰሯዎች ባለማቋረጥ እየጠበቁ ይሄዳሉ ።

ልዑል ጌታዬ ሆይ ፡ ንግግሬን ስጨርስ ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ለልዑል እምልዑላንነትዎ ለኢትዮጵያም ልማት ምኞቶቼን ሁሉ ለማቅረብ ይህ የዛሬው ቀን ምክንያት ስለሆነኝ ደስ ይለኛል ።

Discours prononce M. de SCEY-MOBBELIARD

Monseigneur, Mesdames, Messieurs,

vous avez bien voulu montrer la valeur que vous attachez à la cérémonie d'aujourd'hui en daignant acceptor de pecer la première pierre de la Gare d'Addis-Abeba.

L'importance de cet évenanant marquée par la précence du Corpa Diplomatique. présidé par son distingué aeyen, et celle des notabilités aussi bien Ethiopiennes qu'Etrengères.

La ville d'Addis-Abeba possèdera dèsermais une gare digne de la capitale de l'Ethiopie.

Je me borne en ce qui me concerne à constater. ce qui m'est particulièrement agréable, que ce résultat acquis l'a été grâce à une cordiale entente franco-éthiopienne.

L'Impereur Ménélik avait compris l'importance d'une voire ferrée unissant les hauts plateaux de son Empire avec l'Océan.

Et cette ouvre accomplie par des techniotens d'élte et avec le conure de capitaux frangais va trouver un digne couronnement dans l'édification du moment qui va s'élever.

C'est un boi exmple des fruits du travail et de la persevérance en même temps qu'un enseignement pour l'avenir,

Les bonnes relations qui unissent nos deux pays datent déjà de longues années.

Et sans chercher à remonter plue haut. je n'ai qu'à rappeler les rapporte noués entre le roi Sahlé-Sallaccié, encétre de Sa Majesté l'Impératrice et aussi de Votre Aletesse Impériale. et le roi Louis-Philippo.

Ces rapqorts se sont contiués depuis lors sans ombrage et j'ai confiance que la Providence permettra qu'il en soit de même à l'venir.

Les liens de l'amitié sont toujours précieux en eux mêmes. Ils se resserent encore quand ils aboutssent à un réoultat effectif et pratique comme celui que tous ici nous nous félicitons de constater.

En terminant. Monseigneur. je suis heureux de saisir cette occasion de Vous dire tous les vœux que je fais pour Sa Majesté l'Impératrice. pour. Votre Aletesse Impériale et pour la prospérité de l'Empire d'Ethiopie./.

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የተናገሩት ቃል ።

ክቡር ዋና ዲሬክተር
ክቡራን የውጭ አገር መንግሥት መልክተኞች።
ክቡራን ወይዛዝርና መኳንንት ።

ይህ ከጅቡቲ አዲስ አበባ የተዘረጋው የምድር ባቡር አገራችን ከውጭ አገሮች ጋር በቀጥታና በትክክል እንድትገናኝ አደረጋት።እንደዚህም በመሆኑ አገሩ በንግድም በእውቀትም እየተፋጠነ ወደ መልማት ደረሰ ።

የታላቁ ንጉሠ ነገሥት የዳግማዊ ምኒልክ አሳብ በምድር ባቡር ምክንያት የመፈጸሚያውን መንገድ ይዟል የውጭ አገር ሰው ዘወትር ያለችግር ከሕዝባችን ጋራ ይገናኛል ። ሕዝባችንም ከአውሮፓ አዲስ ሥልጣኔ ጋራ ለመላመድ የሚቻለው ሆነ ።

አገሩ በሥልጣኔ እየገፋ እንዲሄድ በሚጥረው በድካሙ ሁሉ የኢትዮጵያና የፈረንሳዊ የምድር ባቡር ኩምፓንያ ከዚህ ቀደም ያደረገለትን ወደፊትም በየቀኑ የሚያደርግለትን መልካም እርዳታ ፡ የኢትዮጵያ መንግሥት በታላቅ ዋጋ ይገምተዋል።

ይህነን የምድር ባቡር መንገድ ሥራ በመልካም አኳሆን ስለ ሠራው መንግሥቱ የሚገባውን ምሥጋና ያቀርብለታል ። ይኸን ም ሥራ ለመፈጸም ችግርን ለማሸነፍ ስለቻለ ያደንቀዋል።

የምድር ባቡር መንገድ ሲሠራ ሕይወታቸውን ባጡ ሰዎች የሆነውን እጅግ የሚያሳዝን ታላቅ መሥዋዕት የኢትዮጵያ መንግሥት አይዘነጋውምና ዋናው ዲሬክተር በተናገረው መልካም ቃሎች በፍጹም ይተባበራል። ስለዚህም ከባሕር ጠረፍ አንስቶ እስከ ዋናው ከተማ እስከ አዲስ አበባ ብረቱን ዘርግቶ ለማድረስ እጅግ ያለመጠን የሚያደክመውን ሥራቸውን ለመፈጸም በልፋታቸው ለሞቱት ሁሉ የኢትዮጵያ መንግሥት በግልጽ ምሥጋናውን ያቀርብላቸዋል ።

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ የምድር ባቡር ምክንያት አዲስ አበባ ታላቅ ከተማ ለመሆን በቃች በዕለትም እያደገች ትሄዳለች ።

ሥራቸውንም ለመፈጸም ዛሬ የመጀመሯውን ደንጊያ ለማስቀመጥ የመጣንበትን ቀን የማይረሳ ዋና መታሰቢያ አድርገን እናኖረዋለን ።

የኤክስፕሏታሲዮኑም ሥራ እጅግ እየተሻሻለ መሄዱን በማየቴ በተለይ ደስ ብሎኛል ። በመጀመሯም ጊዜያት ከፍተኛ ተራሮች ባለ ባት አገራችን የሚመጡትን እንግዶች ለመቀበል ዋና ከተማችን የተገባች ትሆን ዘንድ ይህ ታላቅ ቤት በፍጥነት ተሠርቶ አልቆ ለማየት በሙሉ ልቤ እመኛለሁ ።

ለአገራችን የሚስማማውን በጥልቅ እውቀት ተረድቶ ስለ ሠራው መልካም አሳቡ ባሪያስ የሚባለውን መሐንዲስ በጣም እናመሰግነዋለንና ይህን ምሥጋናችንን እንዲያደርሱለት እንለምንዎታለን ።

ሶሲዬቴ ቴክኒክ ኤ አንዱስትሪዬል ደንትረፕሪዝ የሚባለውም ማሕበር በኢትዮጵያ የሥራ መጀመሯው የሆነ ይህ ሥራ በፍጹም እንዲቀናው እመኛለሁና ይህ ታላቅ ማሕበር የመሐንዲሱን የሙሴ ባሪያስን አሳብና ሥዕል በመልካም ለመፈጸም ይቻለዋል ብዬ ተረድቻለሁ ።

በዛሬውም ቀን የውጭ አገሮች መንግሥቶች መልእክተኞች ቀዳሚ የሆኑ ክቡር የቤልጋርክ መንግሥት ሚኒስቴር በእነሱ ስም ሆነው በዚሁ ምክንያት በተናገሩት መልካም ቃሎችና በመምጣታችሁ የኢትዮጵያ መንግሥት በደስታ ተነክቷል ።

ደግሞም ክቡር የፈረንሳዊ መንግሥት ጉዳይ ፈጻሚ ለኢትዮጵያና ለፈረንሳዊ የምድር ባቡር ኩምፓንያና በእርሱም በኩል ወደፊት ላገራችን ልማት እንዲሆን መንግሥታቸው በትጋት ማሰቡን ለሚያስረዱ ለተናገሯቸው እጅግ ለተወደዱ መልካም ቃሎች በተለይ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ።

በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና በኔም በራሴ ስም በኢትዮጵያም ሕዝብ ስም ሁኜ የፈረንሳዊና የኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኩምፓኝያ ላደረገው መልካም አድራጎትና አሳብ ጥልቅ የሆነ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ ።

ለአገሩ ጥቅም የሆነ ሥራውን ባለማቋረጥ እየሠራ እንዲሄድ በፍጹም እመኛለሁ ። የኢትዮጵያ መንግሥት በማፍቀር የሚያደርግለትን የወዳጅነት እርዳታውን ያረጋግጥለታልና ኩምፓንያው ወደፊት እየለማ እንዲሄድ ሙሉ ምኞቴ ነው ።

Discours prononcé par Son Altesse Impériale et Royale

Le Prince Tafari Makonnen

Héritier du Trône et Regent de l'Empire d'Etiopie

Monsieur le Directeur général;
Messieurs les Representants du corps diplomatique,
Mesdames et messieurs,

Le Chemin de Fer de Djibouti à Addis-Abeba a permis à notre Pays d'entrer en relations directes et régulières avec le monde extérieur.

Il a favorisé ainsi le développement de l'Empire au point de vue commercial et intellectuel.

Les vues du Grand Empereur MENELICK sont, grâce à lui en pleine voie de réalisation: l'étranger entre en contact fréquent et immédiat avec notre peuple, et celui-ci se familiarise avec l'Europe moderne.

Le Gouvernement Impérial apprécie hautement l'aide efficace que la Compagnie du Chemin de Fer Franco-Ethiopien lui a apportée et lui apporte chaque jour dans les efforts qu'il accmplit pour le progrès de l'Empire.

Il lui exprime toute la gratitude qu'il lui doit pour avoir mené à bien la construction de cette ligne, et toute son admiration pour la manière heureuse dont il a surmonté toutes les difficultés que comportait cet ouvrage.

Le Gouvernemen Ethiopien connaîtles douleurs et sacrifices qni ont été consentis au cours des travaux d'édification du chemin de fer et s'associant aux paroles de Monsieur le DIRECTEUR GENERAL, il tient à rendre publiquement hommage à la mémoire de ceux qui sont morts à la peine dans l'accomplissement de leur devoir harassant et obseur pour amener le rail de la mer à notre capitale Addis-Abeba.

Grâce à la Compagnie Franco-Etiopienne, Addis Abeba est devenue une ville importante et qui grandit chaque jour.

Voulant parachever votre oeuvre, vous avez décidé d'édifier la gare dont nous posons aujourd'hui la première pierre. Ce jour restera dans notre mémoire comme un souvenir impérissable.

Je suis particuliérement heureux de cette amélioration si importante de l'exploitation et je souhaite de tout coeur voir s'élever ce bâtiment très rapidement, afin que Notre Capitale soit à même d'accueillir dignement l'étranger qui pour la première fois accède sur Nos Hauts-Plateaux.

Nous exprimons, et vous prions de transmettre à Monsieur l'Architecte BARRIAS nos félicitations très vives pour le bon goût dont il a fait preuve dans son projet et pour la compréhension profonde des besoins de notre pays.

Au seuil de ses travaux en Etiopie, je souhaite à la Société Technique et Industrielle d'Entreprise un plein-succès et je suis convaincu que cette grande Société saura réaliser complètement les idées et les plans de Monsieur l'architecte BARRIAS.

Le Gouvernement Impérial est très sensible à la présence des Représentants des Puissances Etrangères à cette cérémonie et à la sympathi qu'ils lui ont témoignée à cette occasion et qui a été exprimée en termes si chaleureux par S. E. le Ministre de S. M. le Roi des Belges, Doyen du Corps Diplomatique.

Je remercie également d'une façon toute spéciale, Monsieur le Chargé d'Affaires de la République Française pour les aimables paroles qu'il a prononcées, et qui prouvent toute la sollicitude de son Gouvernement pour le développement de la Compagnie du Chemin de fer Franco-Ethiopien et par là même pour le développement utfur de notre Empire.



ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በባቡር ማረፊያ ለማሠራው የመንገደኞች ማረፊያ ቤት የመሠረቱ መጀመሪያ ድንጋይ እንዳስቀመጡ ።

Au nom de Sa Majesté l'Impératrice,
En mon nom personnel.
Au nom du peuple Ethiopien,

J'adresse à la Compagnie du Chemin de Fer Franco-Ethiopien, l'exeression de notre profonde gratitude pour la bienveillance et la sollicitude dont elle a toujours fait preuve envers l'Ethiopie.

Je souhaite ardemment qu'elle continue son activité bienfaisante pour le Pays et je forme des vœux sincères pour sa prospérité future en lui renouvelant ici, l'assurance de la sympathie et de la collaboration amicale et active du Gouvernement Impérial.

ማመልከቻ ።

የብርሃንና ሰላም ያለፉ ዓመታት ያልከፈሉ ሰዎች ዋጋውን እንዲከፍሉ ደግሞ ያራተኛውን ዓመት በመጀመሯ ከዚህ በፊት ለከፈሉ እያመሰገነ ላልከፈሉ ሰዎችም እንዲከፍሉ በማክበር እናሳስባቸዋለን ።

ጋዜጣው እንዲሰፋና ዋጋውንም ዝቅ ለማድረግ ገዥዎቹ እንዲበዙ ያስፈልጋልና የብርሃንና ሰላም ወዳጆች ሁላችሁ የብርሃንና ሰላም ማሕበረተኞች እንዲበዙ በሚቻላችሁ ሁሉ እንድትረዱ በፍቅር እናሳስባለን ።

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፱ ብር ተኩል
የሲዳሞ ቡና	፩	፰ ብር ተኩል
ዝባድ	፩ ወቄት	፪ ብር ከ፫ሩብ
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፩ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፪ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፰ ብር ተኩል
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ከረጂ	፱ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ከረጂ	፲፰ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ከረጂ	፻፴፮ ብር
:: ባለሰይጣን	::	፻፴፰ ብር
:: ባለ ድመት ።		፻፴፪ ብር
:: ባለአህያ	::	፻፳፪ ብር
:: ባለሳቢ ግመል	::	፻፴፭ ብር
ባለ አንበሳ	::	፻፵፭ ብር
ሱካር	፩ ጁኒያ	፳፯ ብርተኩል
ቻይ	፩ ነጥር	፲፪ መ

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ ከ፴፭ ሳንቲ
አንድ ብር	ሊሬ ፱ ከ፰ ሳንቲም
ባአንድ ጊኒ	፱ ብር ከ፺፯ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፫ ብር

COGNAC S&E&A.METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከበሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

ሺብሮሌ አቶሞቢል ።
በኢትዮጵያ ወኪል ።
ሔ ሜ ዜርቦስ ኩምፓንያ ።

Automobiles CHEVROLET
AGENTS
H. M. ZERVOS & Cie.

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለ
የተመሰከረለት ዝኒት የሚባል ባለ ፈረስ ስዓት ከሙ
ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቅዎታል

“ሩግቢ”— የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ሳገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳም ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶመቢል በተለይወኪል “አሬቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ” ብቻነው።

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፣ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፣ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ማስታወቂያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ፡ ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጅ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልከም ባርኔጣ ፡ ሽቱ ፡ ለስዮን ፤ አድኮሎኝ ፤ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ከኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስመጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሽምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ዓለም

ዓለም የወርቅ ጥልፍ ሥራ ሁሉ በውስጠ ብር ሆኖ ይሠራል ። የምትፈልጉት ሁሉ ወደዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ማመልከቻ ።

በብርሃንና ሰላም ውስጥ ማስታወቂያ ማሳተም የሚፈልጉ ነጋዴዎች እስከ ፈለጉት ጊዜ ድረስ ባማርኛም ሆነ በፈረንጅ ቋንቋ በርካሽ ዋጋ እንደምናትምላቸው እናስታውቃቸዋለን

ጉድይር ግዙ





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያደጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው ። በሌላጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ፤ ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አራተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፰
4 me ANNÉE № 8

ሐሙስ የካቲት ፲፮ ቀን ፤ ፲፱፻፳ ዓ ም።
JEUDI 23 FEVRIER 1928

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት
Son Altesse Impériale Teferi Makonnen , Héritier du trône d' Ethiopie , profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix , a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስተድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie
Un an 5 Thalers
Etranger
Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

መለያየትና የመለያየት ምክንያቶች

የኢጣሊያን ሕዝብ አንድነት ብዙ የሠራ ስሙ የማይሞት ጁስፔ ጋሪባልዲ የተባለ ጅግና ስለዚሁ በመለያየት ስለሚመጣ ብርቱ የሕዝብ ጕዳት ሲናገር እንዲህ ይላል ፤ መተቃቀፍን ትተን በተለያዩና በማይጠቅሙ አሳቦች ኃይሎቻችንን ብንበትን ወዮልን ። በመካከላችንም የመለያየትን ዘር ብንዘራ ደግሞ ከሁሉ የባሰ ነገር ነው ።

እኛ የኢትዮጵያ ሰዎች የሕይወታችንን ደረጃ ገና እንደሚገባን አላወቅነውም አጥብቀን ብንመለከት እጅግ ዝቅ ብለናል ። ይህንንም እንደሚገባ ቢታወቀን መንቃትን በመጣልን ። አሁን ግን አንዳች እንዳልሆነ ደህና ብቻ እንደሆን ይመስለናል ። እንዲህ ያለው ማመን ግን ጥፋት ያመጣል ። ስለዚሁ ሕዝባችን በእውነት የሚነቃበትን መንገድ መፈለግ ይገባናል ። በእንዴት ያለ ዘመንም እንዳለን ለማወቅ ልንዘጋጅ ። ብዙ መንቃት በልማዳችን በአናኗዋራችን በአሳባችን በሥራችንም ብዙ ብዙ መታደስ ያሻናል ።

ከሁሉ በፊትም በአለነው ኑሮዋችን፣ የኢትዮጵያ አሳብ በልባችን እንዲገዛ ለርስዋ እንድንኖር ለርስዋም እንድንሠራ ። የገዛ ራሳችን ጠቀሜቶች በኢትዮጵያ መሠውያ እንሠዋ ። በያለንበት ስፍራና ሥራ ታምነን አገራችንን እናድን ። የሚበጃትንም ነገር ተግተን እንመርምር ። ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር እንድትዘረጋ ተጽፍዋል ። ይህም እጅግ በጎ ነገር ነው ። ዳሩ ግን እጆችዋን ወደ ገዛ ልጆችዋም ትዘረጋች እግዚአብሔር በገዛ ልጆቹዋ በኩል ባያድናት በማን በኩል ያድናት ? በዚሁ ነገር የኢትዮጵያ ሰው የሆነ ሁሉ እጅግ የታመነ በአገሩ ፍቅርም እጅግ የተቃጠለ ይሁን ።

አገርን የሚያድን ኃይል በልብ ነው የሚገለጥ እንጅ በዐቃ ጦር አይደለም ። ልብ በፍቅር እሳት ሲቃጠል ያን ጊዜ ሰው አንዳች ነገር ለማድረግ ይፋጠናልና ኃይል ይሞላበታል ። መኪናንና ሰውን ብናስተያያቸው ትምሕርት እናገኝባቸዋለን። መኪና በእሳት ሙቀት ነው የሚነሣና የሚሠራ ይህ የእሳት ሙቀት ሲጐድልበት ግን ይበርዳልና ይቆማል ። በብርድ ሥራ የለም ። ሰውም በልቡ የአገሩ እውነተኛ ፍቅር ያልተቃጠለበት እንደሆን የሞተ ነው ላገሩ ጥቅምም አንዳች ሊያደርግ አይችልም ። እንግዲህ አስቀድመን ባልንጀራችንና አገራችንን በእውነተኛው ፍቅር ለመውደድ ልባችንን እናዘጋጅ ። እንዲህ የሆነ ፍቅር ብቻ ኢትዮጵያን ይጠቅማታል ። መጥፎውንም ነገር ሁሉ በእደዚህ ፍቅር ይርቃል ። የኢትዮጵያ ልጅ ሆይ ኢትዮጵያን አገርህን ከሚጠቅማት ነገር ምን አደረግህላት ?

የሃይማኖት ነፃነት መከልከል ወይም መወሰን ሕዝብንና መንግሥትን ያጠፋል ።

እኛ በዚሁ ነገር በሕዝብ ሕይወት ተመልክተን ስናበቃ ወደ ኢትዮጵያችንም ስንመለስ ኢትዮጵያችን የሃይማኖትን ነፃነት ከሌሎች ሕዝብ ይልቅ እንዳ ከበረች የተገለጠ ነገር ሆኖ ይገኛል ። ስለዚህ በዚሁ ነገር አንዳች ልትታማ አይገባም ። ብዙዎች ሕዝቦች በዚሁ በሃይማኖት ነፃነት የመጣ የደም ታሪክ ይገኝባቸዋል ። ይልቁንም በቀድሞ ዘመን ፤ አንዳንድ ጊዜም እንዲህ ያለ አለ መታገሥ በአሁኑ ዘመን ባያሌ ስፍራ ይገለጣል ።

በአገራችን ግን ስለሃይማኖት ወደ እስር ወይም ወደ ሞት የደረሰ ብዙ የሚገኝ አይመስለንም በዚሁ ነገር ይልቁንም በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በዳግማዊ ምኒልክ ጀምሮ እንደነዚያ እንደሠለጠኑት አገሮች የኢትዮጵያ መንግሥት ምሉ ነፃነትን እንደ ሰጠች የታወቀ ነገር ነው ። አሁን ግን ይህ የሃይማኖት ነፃነት ከዚህ የምንነካው ምክንያቱ የሃይማኖት ነፃነት ከሕዝብና ከመንግሥት ሕይወት ከዋና ነገሮች አንዱ ስለ ሆ

ሕዝብም በዚሁ ነገር ልቡን እያስፋፋና እጅግ እየተረዳው እንዲሔድ ስለማለት ነው ።

የሃይማኖት ምሉ ነፃነትን የሚጠላ በምንም በምንም መንገድም የሚቃወም፣ ምንም እንኳ እርሱ ለራሱ በጎ ነገር አደርጋለሁ ቢመስለው የገዛ አገሩንና የገዛ መንግሥቱን ሥልጣኔ ይጐዳል። የሃይማኖት ነፃነት መስጠት የምሉ ሥልጣኔ ፍሬ ነው። ባልሠለጠነ ሕዝብ የሃይማኖት ነፃነት ከቶ አይዘረጋም ። የሃይማኖት ነፃነት መስጠት ሲጀምርም ሕዝብ ወደ ሥልጣኔ ክፍታ ይራመድ እንዳለ ያሳያል ።

ሃይማኖትን ስለ መዘርጋት ግን በማስተማር እንጂ በሌላ መንገድ እንዲዘረጋ ከቶ በእግዚአብሔር አልተፈቀደም ከቶውንም እግዚአብሔርን ደስ አያሰኝም። የበጎ ሃይማኖትና የእውነት አምልኮት ታላቅ ሐዋርያ ጌታችን የሱስ ክርስቶስ ወታደሮች በጌተ ሴማኒ ሲይዙት ጴጥሮስ ጌታየን እረዳለሁ ብሎ ሰይፉን መዞ የሊቀ ካህናቱን ባርያ ጆሮውን ቈረጠ ። ጌታችን ግን ምን አለው ? ሰይፍ የሚያነሡ በሰይፍ ይጠፋሉና ሰይፍህን ወደ አርቱ መልስ ።

መድኃኔ ዓለም ትምሕርቱን ልቦችን በእግዚአብሔር ቃል በማስተማርና በመስበክ በማስረዳት ብቻ ዘረጋው እንጂ በኃይል ወይም በጦር አይደለም ። ሐዋርያቱም ተከታዮቹ የክርስትና ሃይማኖት የዘረጉ ለገዛራሳቸው እየተሳደዱ እንጂ ሕዝቦችን በማገድ አይደለም ። እውነተኛ የአስተማሪነትና የስብከት መንፈስ ክርስቶስና ሐዋርያቱ እንዳሳዩት ነው ። ለሃይማኖት እውነተኛና የተገባ መዘርጋት ይህ ብቻ ነው ።

እንዴህ ያለ መንፈስና ነፃነት መስጠትም የቤተ ክርስትያንና የሰውን ሁሉ አሳብ ሊገዛ ይገባዋል ።

እንዴህ ያለ የነፃነት መንፈስ ማግኘት በሰው ሕይወትም ሲገለጥ የሥልጣኔ አናኑዋርን ያሳያል ። እንዴህ ያሉ ምሉ ነፃነት የሠረጸባቸው ሰዎች በሕዝባችን መካከል እየበዙ ስለሚሔዱ ሥልጣኔን የሚወዱ ሰዎች እጅግ ደስ እንዲላቸው ይገባል ። ብዙችም በጋዜጣ በጎ አሳባቸውን አስታውቀዋል ።

የሃይማኖት ነፃነት በተወሰነበት ሕዝብ መካከል ሁከትንና ጸብን ብዙ ብዙ መለያየትም እንዲሆን ታሪክ በጣም ገልጦ ያሳየናል ። እንዴህ ያለ ነገር በሚገዛበት አገር ደግሞ በጎውን ሥራ ለገዛ አገሩና ለገዛ መንግሥቱ ሊያደርግ የሚችልም የለም ። ማዕበል በበዛበት ወይም በሌላ ምክንያት ብርቱ መናወጽ በሚሆንበት ባሕር መርከብ እንዲጐዳ እንዴሁም የሕዝብ ሕይወት መርከብ በሁከት ማዕበል ምክንያት ተሰብሮ ይቀራል ።

የሃይማኖት ዋና ስፍራ ልብ ነው ። ሰውም ልቡ ካልተለወጠ በልቡም ካልተቀበለ ሃይማኖቱ እንዳይጠቅመው የታወቀ ነው ።

በአጼ ዮሐንስ ትእዛዝ በእስላሞች ላይ የተደረገውን ሥራ ብዙ ያስተምረናል ። እርሳቸው በቅን ልቦናቸው ከኢትዮጵያ ሕዝብ እስላሙን ወደ ክርስትና ሃይማኖት እንዳገዱት ታሪኩን አያሌዎች የሚያውቁት ነው ። ይህ ማገድ ግን ለክርስትና ሃይማኖት መዘርጋት ምን በጎ ፍሬ ተከተለው ? በግድ በሚሆን ነገር ይልቁንም በሃይማኖት በሚደርስ ሲሆን መልካም ነገር አይከተለውም የአጤ ዮሐንስ ሞት ተከትሎ በኢትዮጵያችን የወረደውን መዓትም ከእንግዴህ ወዲህ እግዚአብሔር ያርቅልን ።

በአጼ ምኒልክ ዘመንም በእግዚአብሔር ኃይል ብቻ በእስላሙ መካከል በበጌምድር በሰቆጣ በሌላዎችም አውራጆች የተሠራውን እጅግ የሚያስደንቅ የአምላክ ሥራ የሆነውን ከዚህ ልናስታውሰው ስፍራው ነው ። ከእስላሞች መካከል ሼህ ዘከሪያ የሚባሉ ሰው አንስቶ ከክርስትያ መምሕራን ሳይማሩ ከገዛ ቍርዓናቸው አይተው ተመልክተው ከወንጌል ቃልም አነጻጽረው የክርስትናውን ሃይማኖት ተቀብለው በዳግማዊው ልደት ስማቸውን ንዋየ ክርሰቶስ ተብለው በወገኖቻቸው መካከል የክርስቶስን ወንጌል ሰበኩ ። በማስተማራቸውና በስብከታቸውም ወደ ክርስትና ሃይማኖት የገቡ ብዙዎች ናቸው ። የመንግሥት ሰይፍ ያልቻለውን የክርስቶስ ወንጌል አደረገው ። ስለዚህም ስለሃይማኖታቸው ቅናት የሞላባቸው ያሉ በጸጥታና በጥንቃቄ በማስተማር ብቻ ሊያደርጉት ይገባቸዋል ።

በእንደዚህ ባለ መንገድ ብቻ የክርስቲያን ሃይማኖት ሊዘረጋ ይገባዋል። ቤተክርስትያንም በውነት ንቅታ ሑሩ ወመሀሩ ኵሎ አሕዛበ ተብላ ከጌታ የታዘዘችውን ጽኑ አግበዋን በመፈጸም ብቻ ሃይማኖት ሊሰፋ ይገባል ።

ሰው ለነፃነት እንጂ ባንዳች ነገር ለባርነት አልተፈጠረም ፈጣሪውም ራሱ ፍጥረቶቹን በመጨቈንና በኃይል ወደ ፈቃዱ አያግዳቸውም። የመረጡትን ነገር ሊከተሉ ምሉ ነፃነት ሰጥቶ ፈጥሮአቸዋል ። የእግዚአብሔር ባሕርይ በፍጥረቶቹ በሚደርስ ነገር ይህ እንደሆነ እጅግ ማስተዋል ይፈለግብናል ። ዛሬም እግዚአብሔር የውድና የፈቃድ ማገልገል እንጂ የግድ አይሻም ። እውነተኛው የሥልጣኔ መንገድ ይህን መያዝ ነው ። እንዴህ ሲሆን ኃይሎቻችን በመለያየት በከንቱ አያጠፉም ። ኃይላችን አሳባችን ፍቅራችን ወደ አገራችን ብቻ ይታሠራል ። እንዴህ ከሆነም ሕዝባችንን የምንጠቅምበት ሥራ እንድንሠራ የታወቀ ነው ።

፫፤ የማኅተም ሥራ ያልሠለጠነበት ሕዝብ ወደ ክፍታ ሊደርስ አይቻለውም ።

ማኅተም የሕዝብን ዕውቀት ባጭር ዘመን ያበዛል ። ሁሉም አሳቡን ሲገልጥ አእምሮና ማስተዋል ትምሕርትም ይበዛል ። የሕዝብን ልብ ካንድ ላይ ይሰበስባል።እያንዳንዱ ተለያይቶና ተራርቆ የነበረ ልብ በቅን መንገድ ሊሔድ ይጀምራል ። እያንዳንዱ የገዛ ሕዝቡን ጠቀሜትና ጕዳት ያውቃል ። የአገሩንም ፖለቲክ መከተል ይቻለዋል ።

የማኅተም ሥራ የሌለ ሲሆን ወይም በገሩ ውስጥ ብዙዎች ባይቆሙ እያንዳንዱ ለራሱ ብቻ ተወስኖ ይኖራል ። በሰፊው ዓለም የሚሆነውን ነገርም ሊያውቅ አይቻለውም ። እንዴህ ያለ ሕይወት የሞተ ነው ። ማኅተም የሕዝብን ሥራና ሕይወት ያስተዋውቃል ። በዚህ ሥራም ካንዱ ሕዝብ ወዳንዱ ሕዝብ ዕውቀትና ሥልጣኔ ይሸጋገራል።

በጎ መጻሕፍት ጋዜጦችም በአገሩ ሁሉ ይዘረጋሉ ። ሰው አእምሮውና ማስተዋሉ ከበራ በሥልጣኔ አናኑዋር ለመሔድ

ይችላል ። በሚያስፈልጉ ዕውቀቶች ይልቁንም ስለ ገዛ አገሩና ስለ መንግሥቱ በሚያደርስ ነገር ተተክክሎ በሕዝብ ሲዘረጋ እንዲህ ያለ ዕውቀት ወደ አንድነትና ወደ ኃይል ያደርሳል ።

ከፍ የምትል ወይም የምትሠለጥን መንግሥት ።

ጽድቅ ሕዝብን ከፍ ታደርጋለች (ሰሎሞን) ከዚህ ቃል የበለጠና እጅግ የተረዳ ነገር አለን ? ይህም ከጌታ ከየሱስ ቃል ፊት ከተጠቀሰው በጣም ይስማማል ። ኃጢአት ሕዝብን ሲያዋርድና ሲያጠፋ ጽድቅ ግን ሕዝብን ከክፉ ሁሉ ያድናል ። ጽድቅ ምን ማለት ነው ቅዱስ ዳዊት ለዚሁ ጥያቄ እንዲህ ብሎ መልስ ይሰጣል ፤ «ትእዛዛትህ ሁሉ ጽድቅ ናቸው ።» ጽድቅ ደግሞ ቅንነት ማለት ነው ። እንደ ተገለጠው የእግዚአብሔር ትእዛዛት መኖር ብቻ ነው ሕዝብን የሚያሠለጥን ሕዝባችንም በዚሁ መንገድ ቢራመድ ጀምሮበት ወዳለው የሥልጣኔ ደረጃ እንዲደርስ እርግጥ ነው ።

ከነዚህ ሕዝብን ከሚያሠለጥኑ ዋና ነገሮች ከዚህ እንነካለን ፤

፩ ፤ ጋብቻ ፣ የሕዝብን ሕይወት ከፍ ከሚያደርጉ ነገሮች አንዱ ጋብቻ ነው ። በሕዝቦችም ሕይወት ስንመለከት የሕይወታቸው ደረጃ የሚመዘንበት በጋብቻው ሕይወት ነው ። ይኸው የእግዚአብሔር ሥርዓት በተበላሸበት ብርቱ ጥፋት እንዲሆን ማሰብ ይገባናል ። በአረመኔዎች የሕዝብ ብርቱ ዝቅተኝነት ሕይወት ምልክቱ በዚሁ ነው የሚታይ ። እንዲህ ከሆነ ሰዎቹ እንሀ እንስሳ ይሆናሉ ፣ በጎውንም ነገር ይጠፋባቸዋል ። አእምሮዋቸውም ይጨልማል ።

ጋብቻ በሚጸናበትና በሚቀደስበት ሕዝብ መካከል ግን ሕዝቦቹ ነቃ ነቃ ያሉና የበረቱ ሆነው ይገኛሉ ። በዚሁ በሰፊው በአፍሪቃ ክፍል ያሉ ሕዝቦች እንኳ ብንመለከት ከአረመኔዎቹ መካከል ሳይቀር የተሻለ ወይም የጸና የጋብቻ አኗኗር ያላቸው ሕዝብ ከሌሎች ጓደኞቻቸው ሕዝብ በጣም እንዲሻሉ ታይትዋል ።

የጋብቻውን ሥርዓት አጥብቆ ማጽናቱ ግን ከሁሉ አስቀድሞ የክርስቲያን ሕዝብ የሚባል እጅግ ያስፈልገዋል ። በሠለጠኑቱ አገሮችም ሕዝባቸውን ወደ ሥልጣኔ ደረጃ ሊያደርሱ ሲፈልጉ ይህ የጋብቻ ሕግ ለሕዝብ ሕይወት ዋና መሠረቱ መሆኑን ስለተረዱት በዚሁ ነገር በሕዝባቸው የተገባ የጋብቻ አኗኗር እንዲቆም ብዙ ይጣጣራሉ ። ስለዚህ ከጊዜ ወደ ጊዜ የሕዝባቸው ሕይወት እንዲታደስ ይሠራሉ ።

በኢትዮጵያ ሕዝብም እንኳ ሳይቀር የጋብቻው ጽናት በሁሉ ስፍራ አንድ አይደለም ። በንዳንዱ ስፍራ ጋብቻ ምን ነገር መሆኑ ጭራሽ የማይታወቅበት አለ ። በንዳንዱ ግን ጥቂት የተሻለ ሆኖ ይገኛል ።

በሐማሴን በብዙ ምክንያት ይህ ሕግ የጸና ነው ፣ ከነዚህም ብዙ ምክንያቶችንም አንዱ ይህ ነው ፤ የደብረ ቢዘን አባቶች ከሌላዎች ገዳሞች ይልቅ የጋብቻን ሕግ በጣም እንዲያጸኑት ብዙ ደክመዋል ። የፕሮቴንስታንቶችም ወገን በወገናቸው ያስተምራሉ ፣ የካቶሊክም ማሕበር የጋብቻ ሕግ እንዳይፈርስ ይጠባበቁታል ። ስለዚህ የጋብቻ ሥርዓት በዚያ የተሻለ ነው ለማለት ያስደፍራል ።

ሌሎችም ገዳሞች ሆኑ መምሕራን ቀሳውስትም ይህን የተቀደሰውን ሕግ በማስተማራቸውና በመምከራቸውም ሆነ አጥብቀው ቢያጸኑት ኢትዮጵያ ወደ ተሻለው ዘመን ተሸገረች ለማለት ይቻል ነበር ፣ በዚሁ ነገር ብዙ ብዙ መታደስ ያስፈልጋል ። ጋብቻ የበጎ ሥርዓት ሁሉ እውነተኛ መሠረት ነው ። ይኼው ነገር የሕዝብ ሕይወት ወይንም የጥፋት ምክንያት ይሆናል እንጅ የዋዛ ነገር ሆኖ አይቀርም ።

፪ ፤ ሥራ የእግዚአብሔር ሕግ ሆኖ ለሰው በኤድን ገነት የተሰጠ ነው ። እንግዲህ ሥራ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ከሆነ የእግዚአብሔር ትእዛዝም ጽድቅ ከሆነ ሥራ ጽድቅ መሆኑን አገኘን ። ስለዚህ በሥራ እጅግ የሚተጋ ሕዝብና መንግሥት ወደ ከፍታ ይደርሳል ።

ሥራን በሚወዱ ሕዝቦች ብንመለከት ይህን ነገር አጥብቀን እንረዳዋለን ። ለነዚሁ ጊዜ እጅግ ክቡር ነው ። ጊዜን ኪያጠፉ ገንዘብን ሊያጠፉ ይመርጣሉ ። ለገዛ ራሳቸው ይሠራሉ ። ለሚያሠሩዋቸውም ሥራቸውን በትክክልነት እንዲሔድ ይተጋሉ ። ሥራ በትክክልነትና በጽኑ ትጋት በሚፈጸምበት ስፍራ ሥርዓት በሌለበት ሥራ ከሚፈጽሙት መቶ ሰዎች አሥር ሰዎች ብቻ ይበቁታል ። ሥራን ከሚወዱ ሰዎች መካከልም ሥራን የማይወዱ ታካቾች ሲቀላቀሉ ሥራውን አጕል አድርገው ሊያቆሙት ይችላሉ ። ሥራ ወዳጆችም ሳይቀሩ ለገዛ ራሳቸውና ለሥራቸው ከንደነዚህ ካሉቱ ጉዳት ያገኛሉ ። በሥራቸው ታካችነትን የሚያሳዩ ሰዎች ሊጸየፉዋቸው ይገባልን

ሥራ የማይወድ አይብላ ተብሎ በእግዚአብሔር ሕግ ተጽፎዋል ፤ የዕውቀትና የአእምሮ ብቻም አይደለም ፣ የእጅ ሥራም እንደ ዕውቀትና እንደ አእምሮ ሥራ በእግዚአብሔር እጅግ የከበረና የተመሰገነ ነው ፤ በሕዝባችን ግን ሥራ የተገባው ክብረቱን ገና እንደሚገባው አልታወቀለትም ፣ የሕዝባችን ዓይኖች በሹመትና በክብረት እንጂ በሥራ አልተንጠለጠለም ። ሥራ በሕዝባችን እስከ ዚህ የተናቀ ነው ፤ ማንም ሰው ትንሽ ነገር በጁ ቢይዝ ወይም ቢያንጠለጥል በዓይኖቹ ፊት እንደ ውርደትና ኃፍረት ሆኖ ይታየዋል ። በሚያዩቱም ሰዎች ፊት እንዲሁ ሆኖ ይታያል ። የሚለብሳትን ልብስ በራሱ የሚያገባትን ቆብ በጁ የሚይዛትንም በትር ሆነች ወይም ሌላውንም ነገር አስይዞ ባይሔድ እንደ ውርደት ሆኖ ይታየዋል ። ይህ ሁሉ ልምድ ሥራ በሕዝባችን ዘንድ ክፉ እንዳልታወቀ ያሳያል ።

በዚሁ ነገር ያለው የሕዝባችን ጉድለት እጅግ የጠለቀ ነው ። የሚያስፈልገንም የባሕርያችንና የአእምሮዋችን ምሉ መታደስ ነው እንዲህ ሳይሆን ሥራን መሥራትም ብንፈልግ እጆቻችን እንኳ በጅ አይሉም በውነትም ሥራን የምንወድ ብንሆን በአዲስ አበባ ውስጥ ያለችውን መሬት በትጋት ብትሠራ ለከተማው ሰው ሁሉ በመገቦች እንግዲህ በዙሪያ ቤታቸው አንድ ቀላድ የሚሆን ስፋት መሬት የያዙ ውኃም በትርፍ ሊያገኙ የሚችሉ የአታክልት ሥራ ቢሞክሩበት ጥቅሙን

በተረዱት በስድስት ወይም በሰባት ዓመት አንድ ባሕር ዛፍ ከማግኘት በሁለት በሶስት ወር በአታክልት የሚያገኙትን ረብ ባዩ ነበር ። የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ሆይ ሥራ መውደድ የሥልጣኔ መሠረት መሆኑን ለራሳችን እንረዳው ለሕዝባችንም እናስረዳ፥ እኛ ሥራን ስንጸየፍ ሌሎች ሥራን እንዴት አድርገው ያከብሩት ?

ሥራ አያሳፍርም የሚያሳፍር ኃጢአት ብቻ ነው ። ፊተኛው ሰው በኃጢአት ከወደቀ በኋላ አፍሮ ከእግዚአብሔር አምላክ ፊት በገነት ዛፎች ሊሰወር ሞከረ ። በሥራ ማፈርም እግዚአብሔር ጽድቅ ያለውን ሥራ እንደ ኃጢአት መቍጠር ነው።ይህም ነገር በእግዚአብሔር ፊት ብርቱ ዓመጽ ሆኖ ይቈጠራል ። ሥራ መልካም ጽድቅ ክብር በረከት መሆኑን በሥራ ደስ ማለታችንንም ለሕዝባችን እናሳይ። በሥራችንና በሕይወታችን ልንገልጠው የማንደፍርበት ነገር ያለን ቢሆን አንዳች በጎ ዕውቀትና ማስተዋል እንደ ሌለን እናሳያለን ። ጸሐፊውም በቃልና በጽሕፈት ብቻ ሕዝቡን ሊመክር አይወድም በከተማው ውስጥ አንዲት ግማሽ መሬት ለአትክልት የምትሆን ሊያገኝ የሚችል ቢሆን በእጁም ሥራ ክብር መሆኑን ሊያስተምርም ባላፈረም ሥራን እጅግ አክብረን ባናየው ወደ ምንመኘው ሥልጣኔ ልንደርስ አይሆንልንም ።

ሥራ የሚወድ ሕዝብ ስለመኖርማ ይኖራል ፤ ኑሮ ብዙ ዓይነትና ብዙ ማዕርግ አለውና ። ዳሩ ግን ክብርና የገዛ ራሱ ጌታ ሆኖ ሊኖር አይቻለውም ፤ ለራሱ በትጋት ባይሠራ ከሌሎች ሥራን ከሚወዱ በታች ሆኖ የሎሌ ወይም የባርያ ሥራ ሠርቶ እንጀራው ሊበላ ግድ ይሆነዋል። ሕዝባችን የሎሌነትን ኖሮ እንጅ በራሱ ቆሞ ሥራውን ይዞ ሊኖር አይወድም። ይኸው ባሕርዩም ባይለወጥ ሕዝባችን ነፃነቱን ሊያስረግጥ አይቻለውም ።

አንድ ቀን አንድ ላጪ በፈረስ እየተናጠቀ ሲሔድ አንድ የሕዝባችን ሰው የላጪውን መሳሪያ ተሸክሞ በእግሩ እየተጣደፈ ሲከተለው ታየ ። ሌላውም የሕዝባችን ልጅ ቆሞ እየተከዘ ይመለከተው ነበር እንዲህ እያለ ፤ የላጪውን ዕቃ ተሸክሞ እንዲህ ከመሆን ከዚህ የቀለለ ሥራ የለምና በገዛ ራሱ ላጪ መሆን ባልተሻለውምን? ሕዝባችን ለሥራ ዓይኖቹ ስላልተከፈቱ ነው እንጂ ሌሎች የሚችሉትን ማድረግ አቅቶት አይደለም ። እንግድያስ ሥራ በጣም እንዲከብርና እንዲወደድ እናድርግ እንዲህ ከሆነ በውነት የሥልጣኔ መንገድ እንደምንሔድ እርግጥ ሆኖ ይገኛል።በሠለጠኑት አገሮችም ሳይቀር ብንመለከት የሥልጣኔ ማዕርግ በመካከላቸውም ልዩ ነው ሥልጣኔአቸውም እንደ ሥራቸው ልክነት ነው። ለዚሁ የእስጳንያን ሕዝብ ብንመለከት ያስረዳናል።ክቡራን አንባቢዎችም ሊመረምሩት ከዚህ እንጠቅሰዋለን ፤ «ንድግ ፡ የእስፓንያ አገር የጅዎግራፊ ቀጥ ለውጭ አገር ንግድ እጅግ የተስማማ ነበር ፤ መስማማቱም በግራና በቀኙ በአትላንቲክ ውቅያኖስና በሜዴቴሬኒያን ባሕር ስለተከበበ ነው። ዳሩ ግን በእስፓንያ ይህንን የሚያህል የማዕድንና የእርሻ ሲሳይና ሀብት ሳለ ስለሕዝቡ ስንፍና በዓለም ካሉት ንግድ ከሚያውቁት ሕዝብ አገር አትተካከለም ። ሕዝቡም የሰነፋበት ምክንያት አሜሪካን በመጀመሪያ የያዙ (ያገኙ)እስፓንያዎች ነበሩና አገር ለማቅናት ለጦርነት እያሉ ዋና ዋናውንሰው ወደ አሜሪካ ስለ ሰደዱት ነው ደግሞ ለዚሁ ጕዳይ ብዙ ገንዘብ ስለ አጠፉ ነው።ይልቁንም በዚያ አገር ያሉ ካህናት ካቶሊካውያን ናቸውና ይህን በዓል አክብሩ በዚህ ቀን አትሥሩ እያሉ በላያቸው ሠልጥነውባቸው ስለ ኖሩ ነው ደግሞ ይህንን ያደረጋችሁ እንደሆን እንዲህ ይሆንብናል እያሉ ክፉ አምልኮ(ጥንቈላ) ተምረዋል እንደዚሁ ሁሉ ዛሬም በየአገሩ ዛሬ ምሉ ቀን ነው ፤ነገ ጎዶሎ ቀን ነው እያሉ ሥራ የሚፈቱ ብዙ ሕዝብ አሉ እንደዚህ ያለው ኑሮ መንግሥትንና ሕዝብን ያደኸያል በእንደዚህ ያለ ምክንያት የእስፓንያ ሰዎች ከዩሮፕ ሰው በታች ሆነው ቀሩ።

(በክቡር ዶክቶር ወርቅነህ ተጽፎ ይታተም ከለው የጅዎግራፊ መጽሐፍ ፤ ገጽ ፩፻፲፫–፩፻፲፬ ።)

በትግሬም አንድ እንዲህ የሚል ምሳሌ አለ ፤ «እንዳንራብ ጀዓል እንዳንሠራ በዓል አድርግልን ፤» ጀዓል ማለትም ከዓረብኛ የመጣ እንደ ጥጋብ ማለት ነው ሕዝባችን ሥራን እንደሚገባ እንዳላወቀው ይህ ምሳሌ ያሳያል ። የሕዝባችንም መንፈስ በዚህ በሥልጣኔው ዘመን ባይነቃ ብዙ የሚያስፈራ ጥፋት አለበት ። አሳባችን ከሥራ ማምለጥ ብቻ ቢሆን በረከትን እንዴት አድርገን እናግኘው ?

ሥራ በብዙ ዓይነት በረከት ያመጣል ። እርሱን ተከትለው የሚመጡ ጠቀሜቶችም እጅግ ናቸው ። ታካች ግን የገዛ ራሱ ሆን ሕዝቡንም ይበድላል ። ታካቾች የሆኑ ሥራ ያመጣውን ጠቀሜት ብቻ ተቀምጠው ይጨርሳሉ ። ሌሎችንም የሚበጅ አንዳች ሳያደርጉ ከሌላዎች ብዙ ያገኛሉ ። ለሌላዎች የሚሰጡትን ግን አንዳች የላቸውም ። ክፉ ምሳሌያቸውን ብቻ ይተዉላቸዋል ። የሚወዱዋቸውንም ደስ አያሰኙም ።

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል ።

ዘበ ዕዝነ ልብ ሰሚዓ ለይስማዕ ።

ባራተኛው ዓመት ብርሃንና ሰላም ቍጥር አምስት አቶ ማሕተመ ወርቅ እሸቴ በዕሁድ ቀን ለመናፈስ ወደጃን ሜዳ ሒጄ ነበር ብለው ፪ት ጕበዛዝት ተፈክክረው የተቀዳደሙትን ቅድሚያ (እሽቅድድም) ተናገሩ ፤

ለልቡ ጆሮ ያለው ሰው ሁሉ ሰምቶ እኩሉ እንዴት የኋሊት እየሮጠ እያየ የሚሮጠውን ዓይናማ ይቀድመዋል ለሰሚው ግራ ነው ይላል ፤እኩሉ ደግሞ እንዴት ይህ ሰው ጃንሜዳ ወጥቶ በጉባዔ እንደግመል ሽንት ወደኋላ መሮጥ ያስለምድብናል እየተባባሉ መሐል ሰፋሪዎቹም እንደሆኑ አላውቅም (እንጃ) በነገራቸው ሲሐፋፉሉ ሰማሁና እኔም ጋዜጣው እመጣልኝ ድረስ ቸኩዬ ወደማተሚያ ቤት ሔጄ ከአቶ ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ተቀብዬ በብርሃንና ሰላም የተጻፈውን ቃል እንደመጠኔ ተመለከትኩት ፤

ብመለከተውም ይህ ወደኋሊት የሚሮጠው ሰውዬ እስመ ለመላእክቲሁ ይኤዝዞሙ በእንቲአከ ከመ ይዕቀቡከ በኵሉ ፍናዊከ ከመ ኢትትዓቀፍ በዕብን እግርከ ብሏልና እንዳትሰናከል

ላንተ ጠባቆች ይታዘዙልሃል ብሎ ለዝብብት የተናገረውን ይመስላል እንጂ ወደኋሊት እሩጦ ወደ ፊት የሚሮጠውን ዓይናማ እቀድማለሁ ለማለት አልመሰለኝም ።

፬ተኛም ባንድ እንሩጥ ማለት በል ከመ እላ አዕባን ይኩና ኅብስተ እኔንም አንተንም እርቦናል ድንጊያውን ዳቦ አድርግና ባንድ እንብላ ብሎ የተፈታተነውን ይመስላል እንጂ እውን ዓይናማውን ለመቅደም አልመሰለኝምና ምርመራ ያስፈልገዋል።

ልብሱን ተገፎ ስለ መስጠቱም ከዳንከሂ ኢትክልአ ነውና ከትሩፋት እንቈጥርለታለን ገፋፊው ግን ይህቺን ልብስ ከወገኖቹ ጋራ ለዘረከቦ ይርከቦ ሳይባባሉበት አይቀርምና ወደፊት ለመሮጥ ያሰበ ሰው ሁሉ ይመልከትብኝ ።

ወደ ኋላዬ የምሮጠውን እንቅፋት ሳያሰናክለኝ ወደፊት የምትሮጠውን ዕንቅፋት አገኘህና ተሰናከልህ እኔም ቀደምኩህ ብሎ ይዘባበታል ይላሉ ። እኔ ግን አሰብኩና ከመቀደሙ በቀር አለመቅደሙን ከብዙ በጥቂቱ የሚያስረዳ ምሳሌ አሳያለሁ ።

አንደኛ ዛሬ እንደምናየው ባቡር ተሳፍሮ ለሚሔድ ሰው ሁሉ ባቡሩ አለመደው ድረስ ባቡሩን በቀጥታ ቆሞ በምድር ላይ ያለው እንጨትና ምድርም ሆኖ የሚታየው ሁሉ የሚጓዝ ይመስለዋል እንጂ ባቡር የሚሔድ አይመስለውም ስለዚህ የቀደምኩ ይመስለዋል ቀድሞት እንደሔደ ግን አላወቀውምና ቀደምኩህ ይላል ።

ሁለተኛም ያ የዚህ ዓለም አበጋዝ ፈጣሪውን እያስጌጠ ሲፈጥር አይቶ እሱም እንደሱ ለመፍጠር ከጭፍሮቹ አንዱን ተሸከመኝና ብቅ በልልኝ አለው ያም ተሸክሞ ወደላይ የወጣሁ ሲመስለው ወደታች መውረዱን ሳያውቀው ቈይቶ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ዘቅዝቆ መውረዱን ተረዳው ። እንዲሁም የቀደምኩ መሰለው እንጂ መቀደሙን አላወቀውም ።

ሶስተኛ ዓይናማው ወደ ፊት እየሮጠ በዓይኑ ሳያይ በመላ የሚሮጠው ቀደምኩ ማለቱ የሐሰት ፈረሱን ለምኖ የልማድ ኰርቻውን ጭኖ የጊዜውን እርካብ ተረግጦ ውዳሴ ከንቱን አፈናጦ በሕልሙ የነጭ እንጀራ ፍትፍት በልቶ መጥገቡ ነውና አለመቅደሙን በሕልም እሩጫና በሕልም እንጀራ ይረዳው ።

ይህም ልብሴን ተገፈፍኩ ያለው ሰውዬ ጩኸቱ ልብሴን ያየህ ስለ አቦና ወዲህ በለኝ የማለት ያህል ነው እኔም የገብረ መንፈስ ቅዱስ ሎሌ ነኝና ስማቸው ሲጠራ እንዴት ዝም እላለሁ ብዬ ነው እንጂ ልብሱን እተካዋለሁ ብዬ አይዶለም፤በማለት ነገሬን አሳጥራለሁ የአቦ ወዳጅ ።

ዮፍታሔ ንጉሤ

ስለ ተማሪ ቤት የታሰበ አሳብ
አለ መፈጸሙ ምክንያቱ ምንድር ነው?

ወንድማችን ፊታውራሪ ዴሬሳ ላሳሰቡት የተማሪ ቤት ማሕበር መጀመሪያ ዓመት ብርሃንና ሰላም ፳፩ ቁጥር ፹፬ ገጽ ግንቦት ፲፫ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓ ም እንደተባለው ገንዘብ እንሰጣለን ያሉ ሰዎች መቶ ዘጠና ዘጠኝ ናቸው ከዚያም ወዲህ ባ፲፱፻፲፰ ዓመተ ምሕረት ግንቦት ፲፫ ቀን ሥራውን የሚያስሔዱ ሰዎች ምረጡ ብለውን እኛም መርጠን አስታውቀን ነበር ። መርጠንም ካስታወቅን ወዲህ የመረጥናቸው ሥራ ይዘው ቢሆን ባመት ባመቱ ገንዘብ እንሰጣለን ብለው ፊርማቸውን ከሰጡ ሰዎች ገንዘቡን እየተቀበሉ እባንክ እንኳን ባያስቀምጡት ከ፰ሺ ፫፻፶ ብር ያነሰ አይመስለኝም ። አሁን ግን ስጦታው የምኞት መሆኑና ተሰብስቦ ሥራ ባለ መያዙ በጣም ያሳዝናል ። ያሳዝናልም ማለቴ ከኛ በኋላ የጀመሩ የፍቅርና ያገልግሎት ማሕበርና የሠረቀ ብርሃን ማሕበር ተማሪ ቤት ያቆሙ ወንድሞቻችን ግርማዊት ንግሥትንና ልዑል አልጋ ወራሽን መሪ አድርገው በእግዚአብሔር ቸርነት ሥራቸውን ያስሔዳሉ ። ጌቶቼና ወንድሞቼ ሆይ፤ እንዴት ይኸን ያህል ገንዘብ እያለን ፫ ዓመት ሙሉ ሥራ እንፍታ ። በሌላው አገርስ እንኳን ፫ ዓመት ፫ ደቂቃም ቢሆን ሥራ እንዳይፈቱ እናንተም ታውቁታላችሁ ። እኛም ሥራ ጀምረን ቢሆን የሥራውን አካሔድ እያዩ ብዙ ሰዎች እዚህ ማሕበር በገቡ ነበር ። ደግሞም ለሥራ ጊዜ ማሳለፍ እንዳይመች ያንድ ጥንቸልና ያንዲት ዔሊ ተረት ምሳሌ ያሳስበናል ።

አንድ ቀን አንዲት ዔሊና አንድ ጥንቸል በሩጫ ለመሸቀዳደም ተወራረዱ ውርርዱም በሩቅ አንድ ዛፍ አለና እዚያ በፊት ለመድረስ ነበረ ። ጥንቸሉም በሯጭነቱና በቀላልነቱ ተመክቶ ውርርዱን ተቀብሎ መንገድ ሲጀምሩ ጥንቸሉም እመንገድ እየተጫወተ ያለ ችኰላም ሳሩን ሲግጥ ዔሊዋ ግን ከባድነቷንና በጣም አለ መሮጧን አውቃ እንዳቅሟ እየሔደች ከጥንቸሉ በፊት እዛፉ ስር ስትደርስ ጥንቸሉ ቀና ብሎ ቢመለከት ዔሊዋ ቀድማው አየ ይባላል። የዚህም ምሳሌው የሚሠሩትን ነገር ሁሉ እንደ ዔሊዋ ባለው አቅም መሥራት ነው እንጂ ። እንደ ጥንቸሉ አንድ ጊዜ በፍጥነት ያደርሰኛል ማለትና ከንቱ ትምክህት አይገባም የሚል ይመስላል ። ለያዝነው ሥራ ጊዜ አንስጠው ሰዓትንም በከንቱ እናሳልፍ ጊዜንም በከንቱ ማሳለፍ እንዳይገባ የማቴዎስ ወንጌል ም ፳፭ ቁጥር ፩ ስለ ፲ ቆንጃጅት የተባለውን እስከ ፲፬ ቁጥር መመልከት ነው ። እንኳን እኛ እጅ የሌላት ወፍ ባቅሟ ባፍዋ ፩፩ ሣር አመላለሳ ቤት ትሠራለች። እንደሚመስለው ግን ባገራችን ሥራ በቶሎ አለመጀመሩ ሰርተው መብላት የማይወዱና በሌሎች ሰዎች ድካም የሚመገቡ ይበዛሉና እነኚህ ሲበዙ ከሠራተኛው ቀለብተኛው ይበዛል ቀለብተኛው ሲበዛ አገር ይደኸያልና ሁሉም በየወገኑ ቢሠራ ይሻላል ። ሰውም ሁሉ በየወገኑ ቢሠራ ግን የሰው እጅ ከማየት ይድናል ይልቁንም እዘመድ ቤት ተቀምጦ በገዛ ወንድሜ ቤት ብሎ በሰው አዳራሽ ከመኰራትና ባሽከሮች ፊት ከመገጠጥና በስጋት ከመሞት ሥራ ከሠሩ የራስ ጠማማ ጎጆ ትበልጣለች ። ደግሞ ባሁኑ ሰዓት ሥራ አለመሔዱ የጉልበትና የእውቀት ብልጫ ያላቸው ሰዎች የተፎካከሩበት ይመስላል ።

ግን የእውቀት መሪያችን የጉልበት መመኪያችን ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ሁሉንም በየሥራቸው ሊያስኼዱልን ይችላሉና እኛም ባለን አቅማችን ብንረዳቸው መልካም ነው። እንዴት እሳቸውን ብቻ እናሳስብ ። ግን ጥሩ መንጽር ማለት እድሜ ነው

የሩቁን አቅርቦ የሚያሳይ ለልዑል ጌታችን እድሜ ከሰጠልን እኛም ሥራ ከወደድን እንዳየናቸው አገሮች ሳያረጉልን አይቀሩም ። ደግሞም አሳብ ፩ ዓለም ነው መሥራት ግን ሌላ ዓለም ነው ። ያሰቡትን አለ መፈጸም ምንኛ ችግር ነው እውነትማሰብ በርግጥ መሥራት ነበር ያለውን የፈላስፋውን ቃል እናስብ ። ይኸን ሁሉ ማለቴ እላይ ለተናገርሁት ለተማሪ ቤታችን ማሕበር ነውና ሥራ ከልያዝንበት የነሱ ማሕበር አሳብና ምኞት ነው ብለው ስም እንዳያወጡለት ያስፈራል

ልጅ አበበ ወልዴ



ይህ ከዚህ በላይ ያለ ሥዕል ልዑል ዲስኩር አድርገው በወርቅ ማንካ የተላቄጠ ኖራና አሸዋ አንስተው የመሠረቱን መጀመሯ ደንግያ አኑረው ሸምፓኝ ተጠጥቶ የተመረቀ በአዲስ አበባ ባቡር ማረፊያ የሚሠራ የመንገደኞችን ማረፊያ ቤት ያሳያል ።

ይህም የፍራንኮ ኢትዮጵያ የምድር ባቡር ሥራ የኢትዮጵያንና የፈረንሳዊን ሕዝብ በጣም የሚያቃርብ በመሆኑ የመንገደኞቹ ማረፊያ ቤት በቶሎ ተጨርሶ ለማየት የሕዝባችን ሁሉ ዋና ምኞቱ ነው ።

ማስታወቂያ

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
ደግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፰ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክደስታና ክብር	፱ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ብር
ኀሐ ጽባሕ	፰ብር
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፪መ
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ብር
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ተኩል
የቁጥር ትምርት	፩ብር
የማሪኛ ሰዋስው	፩ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	አላድ
ወዳጄ ልቤ	፫ሩብ
አጭር የዓለም ታሪክ	አላድ
ያማሪኛ ፊደል	ሩብ
አሳብና ምኞት	ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት	ሩብ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር	፪መ
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ	ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ	፩ሩብ

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲ ብር ተሩብ
የሲዳሞ ቡና	፩	፱ ብር
ዝባድ	፩ ወቄት	፪ ብር ከ፫ሩብ
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፩ ብር
ያዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፰ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፳ ብር ተኩል
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ከረጂ	፱ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ከረጂ	፲፰ ብር ተኩል
አቡጀዲ መነጽር	፩ ከረጂ	፻፴፯ ብር
፡፡ ባለሰይጣን	፡፡	፻፴፯ ብር
፡፡ ባለ ድመት ፡፡		፻፴፪ ብር
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻፳፪ ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፻፴፰ ብር
ባለ አንበሳ	፡፡	፻፵ ብር
ሱካር	፩ ጁኒያ	፳፯ ብርተኩል
ቻይ	፩ ነጥር	፲፪ መ

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ ከ፴፰ ሳንቲ
አንድ ብር	ሊሬ ፱ ከ፲፰ ሳንቲም
ባአንድ ጊኒ	፱ ብር ከ፺፯ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፫ ብር

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

COGNAC SaEaA.METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA



OMEGA

በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የሚባል ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

ሺብሮሌ አቶሞቢል ።
በኢትዮጵያ ወኪል ።
ሔ ሜ ዜርቦስ ኩምፓንያ ።

Automobiles CHEVROLET
AGENTS
H. M. ZERVOS & Cie.

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ገምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶመቢል በተለይ ወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

RUGBY

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፡በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፡ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፡ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ማስታወቂያ ።

እኔ ቃድር አሊ ስለ ሴት ወይዘሮች የሚሆን ጥሩ ሐርና ከች ዓይነት ጨርቅ ፤ ደግሞ ስለ ትልልቆች መኳንንቶች የሚሆን የእጅ ጠባብ ጨርቅ በያይነቱ ። ከፈረንሳዊና ከኢጣልያን አገር የሚመጣ በያይነቱ ። መልካም ባርኔጣ ፡ ሽቱ ፡ ለስዮን ፤ አድኮሎኝ ፤ በያይነቱ እጅግ ጥሩ ይገኛል ፡ ከኪ መብሩቅ ይኸን የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ይገኛል ደግሞ ቀጭን ድርና ማግ ለኩታ የሚሆን በያይነቱ ሐር ፤ የአልጋ ልብስ ፡ ከፈይ ምንጣፍ ፡ ደግሞ በያይነቱ ያልተጻፈ ጥሩ ዕቃ አለና ከሁሉ መደብር በቀላል ዋጋ ይሸጣል በድሬ ዳዋም መጋላ ከሙሴ ያኒ ቤት አጠገብና እሙሴ አሰን አሊ ቤት እመካከሉ ላይ ባለው ሱቅ ይገኛል ። ደግሞ በወረቀት ለማስመጣት ለምትፈልጉ ሰዎች አድራሻውን ቃድር አሊ ሽምሱዲን ድሬ ዳዋ ብላችሁ እንድትጽፉ አመለክታችኋለሁ ፡ የፖስታው ሳጥን ንምራው ሰላሳ አራት ነው ።

ዓለም

ዓለም የወርቅ ጥልፍ ሥራ ሁሉ በውስጠ ብር ሆኖ ይሠራል ። የምትፈልጉት ሁሉ ወደዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ማመልከቻ ።

በብርሃንና ሰላም ውስጥ ማስታወቂያ ማሳተም የሚፈልጉ ነጋዴዎች እስከ ፈለጉት ጊዜ ድረስ ባማርኛም ሆነ በፈረንጅ ቋንቋ በርካሽ ዋጋ እንደምናትምላቸው እናስታውቃቸዋለን

ጉድይር ግዙ



ከሁሉ የሚገልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው ። በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ፤ ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አራተኛ ዓመት ፤ቁጥር ፱
4 me ANNÉE № 9

ሐሙስ የካቲት ፳፪ ቀን፤፲፱፻፳ ዓ ም።
JEUDI 1 MARS 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት
Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

፫፣ ወጣቶችን ለኋላው ለሕዝባቸው ጠቀሜት ሊሆኑ እንዲችሉ የሚያስችላቸውን የበቃ አስተዳደግና ትምሕርት ቢያገኙ ያን ጊዜ ብቻ መንግሥታችን ከፍ ልትል ይሆንላታል ።

አሁን በሕዝባችን መካከል በጅምላ አሳብ ብንናገር ትምሕርት እንዲወደድ ተገልጥዋል ለማለት እንደፍራለን ።ቢሆን ግን የትምሕርቱ ጣዕምና ጠቀሜት በሚገባ ያወቁቱ የደሀው ሕዝብ ክፍል ናቸው ። ስለዚህ ልጆቻቸውን ለማስተማር ዐቅም ስለ ጐደለባቸው አዝነው ይቀመጣሉ። በዚሁ ትይዩ ግን ሀብታሞቹና ትልልቆቹ ሰዎች ብዙ ዓቅም ያላቸው አንዳንድ ባይሆኑ ይህን መሻት ከቶ አልታወቃቸውም ። ስለዚሁ ልጆቻቸውን በፍጥነት ከማስተማርና ለአገራቸው ጠቀሜት ከማሰደግ እጅግ ቸል ብለዋል ። እንዲህ ቸል በማለትም የኋለኛው ወይም የገዛ ልጆቻቸው ዕጻ ሊሆን ይችል የነበረውን ጠቀሜት ያጠፉላቸዋል ። ከልጆቻቸው ዕድልና ጠቀሜት አብሮ የተሳሰረውንም የአገራቸውን የኢትዮጵያን መልካም ዕድል ያጠፋሉ ። እንዴህ ያለ ኃይል ያላቸው ሰዎች ምነው የማይነቁ? ምነው ልጆቻቸውንም ዕድሚያቸው ሳያልፍ በፍጥነት የማያስተምሩዋቸው? እንደ ለዚህ ያሉ ሰዎች በአሁኑ ባላቸው ኑሮዋቸው የገዛ ራሳቸውን ያታልላሉ እንጅ በውነት ያሁኑ ኑሮዋቸው ሳይለወጥላቸው እንዲኖርላቸው ዋስ የቀጠረላቸው የለም ። በሰማይ አንድ አምላክ አለ ዘመናትንና ጊዜያትን የሚለውጥ ሕዝብን የሚያፈልስ መንግሥታትንም የሚነቅልና የሚተክል ። እንዴሁ የያንዳንዱ ሰው ዕድልም ሳይቀር ቸል ሳይል ባለቤቱ ይመድብዋል ። ስለ ዚህ ለራሳቸው ሆነ ለትውልዳቸው ለአገራቸውም ጠቀሜት የሚያስቡ እንደሆን ከትምሕርትና ወጣቶችን ከማሳደግ በቀር ሌላ የጸናና የሚጠቅማቸው ነገር ሊያገኙ እንዳይችሉ እንዲረዱት እናሳስባቸዋለን ።

በድንቁርና ቦታ ሆኖ የትምሕርትን ጠቀሜትና ክብረት ሊያውቅ የሚችል የለም ። ዕውር የብርሃናትን ማዕርጋት ሊለይ እንዳይሆንለት እንዴሁም አሳቡ በድንቁርናና በሞኝነት በብዙ ስሕተትም የጨለመ የጥበብን ብልጫ ሊያስተውል አይሆንለትም ። እንግዴህ እያንዳንዱ በዚሁ ረገድ የሚቻለውን ያህል በእጅግ ፍጥነት እንዲያደርግ ልቡን ቢያዘጋጅ ኢትዮጵያ ወደ ሥልጣኔ ደረጃ ትራመድ እንዳለች በታየ ፤

ድንቁርና ታካችነት ጽኑ መጥፎ ልምድ ከአገራችን ሊያባርሩ የሚችሉ ወጣቶች በብዙ ፍጥነት አሳድገንና አስተምረን ለማዘጋጀት ባንተጋ ኢትዮጵያ አትድንም ። እስራኤል በመሳፍንት ዘመን በኃጢአታቸው ምክንያት የሚረዱዋቸው ኃያላን ሲጠፉዋቸው ጊዜ ጥፋት መጣባቸው ፤ ዛሬም የሥራና የዕውቀት የልዩ ልዩ ትምሕርት የሃይማኖትም ኃያላ የሚበቁን ባናገኝ ደህንነቱ እንዴት ብሎ ይምጣልን? ላይ ላዩን ከመናገር አጥልቀን መናገር ይበልጣል ። በውነት ሕዝብን የሚያድን የተረጋገጠ መንገድ ብቻ እንያዝ። ከነዚሁም ኃያላን አገራችንን የሚያስፈልጋት ደገኞች እጅግ የበቁ አስተማሪዎች ነው ። እንዲህ የሆኑቱ ባይገኙበት ተማሪ ቤት ሥራው ዝምብሎ ልፋት ሆኖ እንደሚቀር የታወቀ ነው ።

ወጣቶችን ለማስተማር እጅግ የታመኑና የተፈተኑ አስተማሪዎች ማቆም ከዋና ነገሮች ነው። እንግዴህ አግቦዋቸው ምን መሆኑን ያልተረዱትን ማንም አስተማሪዎች አድርጎ ማቆም ጕዳት እንጅ ጠቄሜት አይገኝበትም ። በዚሁ ነገር ለተማሪ ቤቶች በውነት የበቁ አስተማሪዎችን እየመረመሩ ማቆም በጣም የሚያስፈልግ ፊተኛ ነገር ነው ። የመምሕራን መምረጥ ዋና ነገር መሆኑን በብዙ ሕዝብ ታሪክ ይታያል።በቀድሞዎቹ ደግሞ እንጅ ባሁን ዘመን ባሉት ሕዝቦች ብቻም አይደለም ። ከዚህ አንድ ይህን የሚያስረዳ ታሪክ እናሳያለን ።

በጥንታውያን ዓረቦች አስተማማር ።

ዓትበት የአቢ ሲፍያን ልጅ የልጆቹን መምሕር ዓብድን የአሳማድን ልጅ አለው ፣ ልጆቼን በምታስተምርበትና በምታሳድግበት መሠረት ፊት ገዛ ራስህን በማስተማር እንድትጀምር ይሁን ። ዓይኖቻቸው አንተከ ምትመለከተው ነገር ጋር ሲተሳሰሩ ያ አንት መልካም ያልከው መልካም ያ አንት ክፉ ያልከውም ክፉ ይሆናቸዋል ። የእግዚአብሔርን መጽሐፍ አስተምራቸው ግን ይሰለቻቸዋልና እጅግ ማንበቡን አታግዳቸው ። ደግሞም ይተውታልና ችላ እንዲሉት አትፍቀድላቸው ።

በመስማት ብቻ ብዙዎች ቃላት ማጠራቀም አእምሮን ያጨልማል የአዋቂዎቹን ሕይወት የትልልቆቹም የስመ ጥሩዎችን ሰዎች በጎ ባሕርያት ተርክላቸው አስቀድሞ በሽታውን ሳያረጋግጥ መድኃኒት እንደማይሰጥ ሐኪምም ሁኑላቸው ሊቅነታቸውን አብዛላቸው እኔም እግዚአብሔር ቢፈቅደው ደመወዝህን ከፍ አደርገዋለሁ (ካታን)

በእንደዚህ ያለ መንፈስና መንገድ የሚያስተምሩ አስተማሪዎች ያስፈልጉናል ስለዚህ በአስተማሪነታቸውና በጠባያቸው በካሔዳቸውም ሁሉ ያልተፈተኑ ወደ ተማሪ ቤቶች በመልቀቅ ወይም በመፍቀድ የሚገኘው ፍሬ ጥቂት ይሆናል አስተማሪዎቹ የሚያስተምሩቱን ነገር አስቀድመው ባለቤታቸው በካሔዳቸው የተመላለሱበት እንዲሆን ወጣቶችንም በአርአያነታቸውና በደግነታቸው ሊመሩዋቸው ልቦናቸውንም ደገኛውን ነገር ለመሻት እንዲከፍቱላቸው የወጣቶቹ ልብ በጎውንና ቅኑን ነገር መከተልን ባይማርና በርሱም ባይመራ የትምሕርታቸው አሳብ የተሳሳተ ትምሕርታቸውንም ፍሬ የማይገኝበት ሆኖ ይቀራል ስለዚህ ከሁሉ አስቀድሞ አስተማሪዎች የሆኑ እጅግ ጽኑ የሆነ አግበ እንዳላቸው ይታወቃቸው ዘንድ ይገባቸዋል ።

ይህንንም አደራ የተሰጣቸውን ሥራ በእንዴት ያለ ጠቀሜት በሚገኝበት መንገድ ሊፈጽሙት እንዲገባቸው ራሳቸውን በጣም ማዘጋጀት ያስፈልጋቸዋል ።

ወጣቶችን ማስተማር ንባብንና ጽሕፈትን ቍጥርንም እንዲያውቁ ብቻ ማድረግ አይደለም ። አሳቡ ከዚህ እጅግ ከፍ ያለ ነው እንጂ ። የተማሪ ቤት ማቆም እውነተኛ አሳቡ ወጣቶችን በነፍሳቸውና በመንፈሳቸው በሥጋቸውም ተምረው የሚያድጉ በትና ራሳቸውን ሆነ ባልንጀራቸውንም እንዲረዱ ዓቅም ሊያገኙበት የሚችሉበት ስፍራ ነው። በእንዲህ ያለ መንፈስ ያልተማሩና ያላደጉ ሕዝባቸውን ከቶ በአንዳች አይጠቅሙም ። እንግዲህ የተማሪ ቤትና የአስተማሪነት መንገድም የአስተማሪዎቹ ሕይወትም ዘወትር የማሰበቸውና የምርምር ዋና ምክንያት ሊሆናቸው ይገባል ። ስለዚህ በመንግሥት ውስጥ ያሉትን ተማሪ ቤቶች የመንግሥት ሆኑ የልዩ ልዩ የሚስዮናውያን የሥራም ተማሪ ቤቶች ቢሆኑ አካሔዳቸው ዘወትር በትጋት መጐብኘትና መፈተሽ ያስፈልጋል ። ስለተማሪዎቹ ግን ብዙ መናገር አያስፈልግም ። ተማሪው እንደ መምሕሩ ነውና ።

ስለማዘጋጃ ቤት ገቢ

የአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ገቢ ስንት ዓይነት እንደ ሆነ የታወቀ ነው በአውሮጳም ሕግና ደምብ እንደምንሰማው የከተማ ማዘጋጃ ቤት ሥራው የሕዝብን ጤንነት ጠባቂና የመንግሥቱን ጉዳይ ፈጻሚ ስለሆነ በከተማ የሚገኘው ልዩ ልዩ ገቢ ገንዘብ የማዘጋጃ ቤት ነው ይባላል ። እንዲሁም ደግሞ ይህን በመሳሰለ መልካም አሳቡ የመንግሥቱን ጉዳይ ፈጻሚና የሕዝቡን ጤንነት ጠባቂ በመሆኑ መንግሥት የታማኝነት ሥልጣን ለማዘጋጃ ቤት ይሰጠዋል ይባላል ። በለዚህ ማዘጋጃ ቤት የመንግሥቱ ሥልጣን በላዩ ሲያድርበት ለከተማው የሚያስፈልገውን የሥልጣኔ ሥራና የሕዝብን ጥቅም የከተማውንም መንገድ በንጹሕ ሊሠራ ማሰቡን ትጋት ሊሰጠው የተገባው ነው።

አሁንም ይህ ሊታወቅ የከተማው ገጋር ክቡር ከንቲባ ነሲቡ ከተሾሙ ዘመን ጀምሮ እስካሁን ድረስ በተሰጠው ደምብና ሥርዓት የከተማውን ሕዝብ በሰላም ጠብቀው ፀጥ በማድረጋቸው የምስጋና ስማቸው ሳይጓደል በመሄዱ የብርሃንና ሰላም ወዳጆች በየጊዜው ያመሰግንዋቸዋል ። ነገር ግን ክቡር ከንቲባ ነሲቡ ምንም አሳባቸውን በፍጹም ልባቸው አቃንተው ሥራቸውን በትጋት ቢሰሩ የማዘጋጃ ቤቱ ገቢያቸው ለዚህ ለመልካም አሳባቸው እጅግ የሚያንሳቸው ስለሆነ በዚህ ምክንያት ይህ የሚሠሩት የበጐነት ሥራቸው እየተጠቃለለ ለመሄድ ሲዘገያባቸው ቅር ይላቸው ይመስለኛል ። ስለዚህ እላይ እንደተባለው ለከተማ ማዘጋጃ ቤት የሚገባው ልዩ ልዩ የሆነ ገቢው በጠቅላላው ቢገባላቸው በከተማ ያለው የሕዝብ መተላለፊያ መንገድ ሁሉ በመልካም ሆኖ እንዲሠራ ቀን ባልዘገየባቸውም ነበር ። አሁንም ከብዙ በጥቂቱ በተለየ በኔ አሳብ የማዘጋጃ ቤትን ገቢ እናገራለሁ ።

፩ኛ በከተማ ውስጥ ያለው ቦታ ሁሉ ቢሸጥ ቢገዛ ቢሰጥ ቢለወጥ እንደ ደምቡ እማዘጋጃ ቤት የሚገባውን ክፍሎ ነው ። ይኸውም የከተማ ቦታ ሁሉ ለባለርስቶች ከርታ የሚነሳው እማዘጋጃ ቤት ነው ።

፪ተኛ በከተማ ውስጥ ያለ ልዩ ልዩ ግብር ፯-፰ ክፍል ። በከተማ ውስጥ ያለ የመሸታ ግብር በገባያም ውስጥ ያለ የሸቀጥ ንግድ የዚህ ግብር ሁሉ በየወሩ የሚገባው እማዘጋጃ ቤት ነው ። ነገር ግን አሁን አልፎ አልፎ ቦታ ቢሸጥና ቢገዛ ንግድም ቢነግድ የሰፈሩ ሻለቃ የማዘጋጃ ቤት ገቢ የሆነውን ለኛ አምጣ እያለ አላገባብ ይቀበለዋል ። ሕዝቡም ለሻለቃው የሚገባውን ክፍሎ ቦታውን ካርታ ለማስነሳት ወደ ማዘጋጃ ቤት የሔደ እንደሆነ አሹራውን ለኛ ሳትከፍል ካርታ አይነሳም ይሉታል ። ለሻለቃ መክፈሉን ያስረዳ እንደሆነ እንሱ የተቀበሉህ አላገባብ ነው ይሉታል ። ስለዚህ ያ ሰው በዚህ ምክንያት በርስቱ ችግር እንዳይመጣበት እንደገና አሹራውን ለማዘጋጃ ቤት ከፍሎ ርስቱን አጽንቶ ካርታውን ተቀብሎ ይሄዳል ። ለሻለቃ የከፈለውም እንደተከፈለ ይቀራል ።

፫ተኛ የከተማ ንግድ ግብር የማዘጋጃ ቤት ሠራተኞች እንደ ክፍላቸው ሥራ አምጣ እያሉ ሥራቸውን በሚገባ ይሠ

ራሉ ። ደግሞ በነሱ ላይ ሻለቃ አምጣ እያለ ይቀበለዋል ። ደሀ ግን ይበላው ነው እንጅ ይከፍለው አያጣም የሚባለው ምሳሌ እርግጥ ነው ። ይህ ደሀ ወይ የማዘጋጃ ቤት ዜጋ አልሆነ ፤ ወይ የሻለቃ ዜጋ አልሆነ በሁለት ወገን መክፈሉ በምን ምክንያት ነው ? ስለዚህ በሉቃስ ወንጌል በ፲፮ ምዕ በ፲፫ ቁጥር ያለውን መመልከት ነው ። አሁንም የዚህን ነገር ክቡር ከንቲባ አስበውት ደሀው በሁለት ፊት እንዳይከፍል በማዘጋጃ ቤት ደምብ ከየሻለቆቹ እየተከራከሩ እንዲያድኑት ስል ድፍረት በመሰለኝ አሳቤ አመለክታለሁ ።

፬ተኛ ይህንንም ለመጻፍ ያሳሰበኝ አንድ ቀን የቤት ኪራይ ስፈልግ ከቤቱ ጌታ ስነጋገር የማዘጋጃ ቤት ሠራተኞች መጥተው የመሸታ ግብር አምጣ አሉት። ወረቀት አውጥቶ ይኸውና ለሰፈሩ ጌታ ከፍያለሁ ቢል እኛ ይህን አናውቅም ብለው በሚገባው ደምብ ተቀበሉት ። እኔም በዚህ ነገር ሲጨቃጨቅ ብዙ ጊዜ የሚያሳልፍብኝ ቢሆን በሌላ ቀን እጠይቀዋለሁ ብዬ ወደ ቤቴ ሔድሁ ።

፭ኛ፡በሌላ ቀን ደግሞ እንደዚሁ ቤት ለመፈለግስሄድአንድ ሰውዬ የከርታ ግብር አምጣ ብለውት ኑሮ ይዘውት ሲሄድ ምንድነው ብለው በግብር ነው አለ ። እኔም ግብር ካልገበሩ አይኖሩም ካገሩ ብዬ ምሳሌ ነገርሁትና ክፈልና ተመለስ አልሁት እሱም እስቲ ወረቀቱን አንብብልኝ አለኝና ልስጥ ቢለኝ መንገዴን ትቼ አነበብሁለት ። ቃሉም እንዲህ የሚል ነው ፤ ይድረስ ካቶ እገሌ በከተማ ቦታህ በንደዚህ ያለ ቁጥር የተነሳው ያመት ግብሩን ክፈል እስከ ፲ ቀን ያልከፈልህ እንደሆነ በእጥፍ ትከፍላለህ የሚል ነው ። ይህንን ካነበብሁለት በኋላ ወደ ቤቱ ሔደ ገንዘቡን ለማዘጋጃ ቤት ሰጥቶ የደረሰኝ ተቀብሎ እንዲመጣ መከሬው ነገሩ በዚህ ካለቀ በኋላ ፤ እረ በል ወንድሜ እዚህ ግድም የቤት ኪራይ ይገኛል ወይ ብለው ፤ አይጠፋም እንጠይቃለን ፤ ለወደፊቱም አንተ ጐረቤቴ ከሆንኽ ወረቀት ማንበብ አላውቅምና ወረቀት ታይልኛለህ እንዲያው በየጊዜውያም አንጣ ያም አንጣ ነው ፤ ወይ ለማዘጋጃ ቤት አልሆንን ወይ ለሻለቃ አልሆንን በዚህ ነገር ተቸግረናል አለኝ። ከዚህ በኋላ ወረቀቱን ሁሉ ቢያሳየኝ የማዘጋጃ ቤትም የሰፈሩም አለቃ ወረቀት በያይነቱ የከፈለበት አለ ። እኔ ግን ነገሩ ሰለቸኝና ከዚህ ይልቅ ይህን ወረቀት ሰብስበህ ለክቡር ከንቲባ አሳያቸውና በዚህ ምክንያት ለወደፊቱ ለሕዝቡ ደምብ ያወጡላቸዋል ብዬ ነገሬን ጨረስሁ ። እንግዲህ ወደፊተኛው እንመለስ ።

፮ኛ፡ክቡር ከንቲባ ነሲቡ ለዚህ ለበጐነት ሥራቸውና አሳባቸው የማዘጋጃ ቤቱ ገቢያቸው ያንስባቸዋል የተባለው በዚህ ምክንያት ነው ። ደሀውም ለማዘጋጃ ቤት ብዙ የወር ገቢ ይከፍል የነበረው እየተመረረ ንግዱን ይተዋል ። እንግዲህ የማዘጋጃ ቤት ለሕዝቡ ማሰቡን ሳይተው በገቢ ምክንያት ሥራው ሳይከናወንለት ይቆያል ። ሰው በመንገድ ሲሄድ ብቻ ያማረውን መንገድና ያማረውን ድልድይ አይቶ ዛሬ ይኸ መንገድ አምሮአል ዛሬ ይኸ ድልድይ አምሮአል ለያለ በተረት ከመሄድ በቀር በብዙ ችግርና ድካም ታስቦ መሠራቱን አያውቀውም።

አሁንም የልዑል ራስ መኰንን ድልድይ በመልካም ሆኖ ግራና ቀኝ የተሠራውን አይቼ ፤ ሁለት ወር ያህል ወደ ውጭ ሰንብቼ ነበርና ለዚህ ሥራ የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች በተለየ የሥራውን ማማር ምሥጋና እስቲጽፉለት ድረስ የእኔ ደስታ ጊዜ አልሰጠኝ ብሎ ከምን ጊዜው እንደዚህ ያለ መልካም ሥራ አደረጉት ብዬ አደነቅሁ ። ዛሬ ግን ሕዝቡ ያለ ሥጋት አቶሞቢል ቢመጣበትም እንደልቡ ዘወር ብሎ ለመሄድ አያሰጋውም ። በዚህም በተሠራው መንገድ ላይ ሁለ ጊዜ በብርሃን እየሄድን በሰላም እንድንመለስ ለሚያስቡልን ለግርማዊት ንግሥትና ለልዑል ተፈሪ መኰንን ረጅም ዕድሜና ጤና ይስጥልን ብዬ ወደ እግዚአብሔር እለምናለሁ ።

ይህንንም የድልድይ ሥራ ለሕዝቡ አስቦ ለሠራው ለማዘጋጃ ቤትና ለክቡር ከንቲብ ነሲቡም ምሥጋና ይግባቸው ክቡራን አንባቢዎች ሆይ ፤ ትንሽ መንገድ ወስዳ ወደ ትልቁ መንገድ እንድታደርስ እንደዬሁ እኔም የመሰለኝ አሳብ በትንሽ ዕውቀቴ ለእናንተ አበረክታለሁ ብዬ ነውና ሰው በመሰለው አሳብ ቢያመለክት አይነወርም ። ባይሆን ቢሳሳትና ስሕተት ቃል ቢኖርበት የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ልታቃኑት ትችላላችሁ ።

የብርሃንና ሰላም አንባቢ ፤ ኃይለ ኢየሱስ ።

ስለ ኢትዮጵያ ጕዳት

ኢትዮጵያ ራሱዋን ችላ የቆየች መንግሥት መሆኑዋን ዘመንዋን በብዙ ሺህ ዓመት ነው የምትቆጥር ። በኢትዮጵያም ወንጌል ከተሰበከ ዘመኑ እጅግ የራቀ ነው ። በዚህም የተነሣ በሆድዋ ውስጥ ተነዝተው የሚታዩት ቤተ ክርስቲያኖች ቁጥራቸው አለመጠን ብዙ ነው ። ሕዝቡም የክርስቲያን ሃይማኖት በጣም በልቡ ስለተመሠረበት በሥለትም ሆነ በማናቸውም ምክንያት ለቤተክርስቲያን የሚሰጠው ገንዘብ መጠን የለውም ። ቤተክርስቲያንን ለሚያገለግሉ ካህናቶች ደግሞ ያሰጣጡ ዓይነቱ ይብዛ እንጂ ቀለባቸውን የሚሰጥ መንግሥት ነው። ያለፈውን አይደለም የዘመናችንን በዚህ ዓለም የሚኖር ሕዝብ አኑዋኑዋር ሲመለከቱት በማንም ክርስቲያን አገር ቢሆን እንደ ኢትዮጵያ የሕዝብ ገንዘብ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚፈልቅበት አገር የለም ። የሆነው ሆኖ ሕዝብ ቢማርና ብልሃተኛ ቢሆን ጥቅሙ ለመንግሥቱና ላገሩ መሆኑ ውልውል የለውም ።

ስለዚህ ከብዙ ዝርዝር ሳንገባ ባጭሩ በኢትዮጵያ ያሉ ቤተ ክርስቲያናት በየውስጣቸው እንደአቅማቸው ስለምን የተማሪ ቤት አያቆሙም በማለት ሁልጊዜ እመራመራለሁ ። አሁንም ይህን የማያውቅ አለ ብዬ አይደለም ብቻ የኢትዮጵያ ጥቅም ጥቅሜ ስለሆነ ባለኝ አቅሜ ላስታውስ ልረዳ በማለት በንጹሕ ልቦናዬ ነው ይህን ያሰብኩት ። በኢትዮጵያም ያሉ ካህናቶች ይህን ኢንበው የቀረው ቢቀር በሥሬት ረገድ ብቻ ወደ ቤተክርስቲያን የሚፈሰውን እውነተኛ የሕዝብ ገንዘብ የመሪ ጌታ የገበዝ የታቦት ድርሻ እያሉ ከማባከን ምስጋና ላለው ለማይጠፋ ነገር ለሕዝብ ማስተማሪያ እንዲሆን ያስቡበታል በማለት ትልቅ ተስፋ አለኝ ። ከዚህም አብልጬ ዝርዝሩን እንደውቀቴ ብጽፈው አዝኖ ማሳዘን ስለሆነ ትርፉ ጊዜውን ይጠብቅ በማለት ተወት አድርጌዋለሁ ።

ክቡራን የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ሆይ ፤ ብርሃንና ሰላም ከወጣ አንስቶ እስከሁን ድረስ እንኳ አገራችንን እራሳች

ንንም ብዙ ይጠቀመናል አሁንም ወደፊት ያገራችንንም የራሳችንንም መጠቀምያ እያሰፋን መሄዳችንን ውልውል የለውም ስለዚህ ሁላችንምእንዳቅማችን ለብርሃንና ሰላም ባለወረታዎች እየሆን ውለታ መላሾች ለመሆን እንትጋ እንጂ እንደ ጋላ ተራች የባለቤትን ወጭት ሰባሪ እንዳንባል እንጠንቀቅ ።

አርመን ያዕቆብ ።

ስለ መታገሥ

ይድረስ ለክቡራን የኢትዮጵያ ተወላጆች ለክብራችሁ የሚገባ ሰላምታዎቼን አቀርብላችኋለሁ ከዚህም ቀጥዬ ትንሽዋን አሳቤን አሳስባችኋለሁ ግድፈትም ቢገኝበት ብታርሙት ፍቃዴ ነው

ጥንት አያቶቻችን ወተት ጠላና ጠጅ እየጠጡ ይኸንንም ባጡ ግዜ ቅራሪና ውሃ እየጠጡ ግዜአቸውን በተድላና በደስታ ማሳለፋቸውን ሁላችሁም፤ታውቁታላችሁ።አሁን ግን ለግዜው አገርም እየቀና እውቀትም እየሰፋ ስለሄደ ብዙ አያቶቻችን የማያውቁት መጠጥ ሁሉ ከኤውሮፓ እየመጣ ይሸጥ ጀመር፡ደግሞም እንዲሁ የሃገራችን ጠጅና ጠላም ይሸጣል ። ነገር ግን እኒህን ፈረንጆች ተመልከቷቸው ከዚያው ከዝማዳቸው ሆቴል በተቀር ምንም ያማረና የጣፈጠ ደግሞም ዋጋው ከዝማዳቸው ሆቴል ሁለት እጅ ያነሰ መጠጥና መብል ከሃበሾች ሆቴል ቢሼጥ ገብተው ከሃበሾች ሆቴል አለመብላታቸውና አለመጠጣታቸው ለምን ይመስላችኋል የሰው አገር መጠጥና መብል እየገዛን ባዳ ከማክበር ውድም ቢሆን ከዘመዶቻችን ላይ እየገዛን እንጠጣ ያገር ልጃችን እንዳይከብር የማለት ሃሳብ ይመስላል እንጂ አረቄአቸው ከጠጃችን ቢራቸው ከጠላችን በልጦ አይደለም። ለዚሁም አንድ ያየሁትን ነገር ላመልከታችሁ ሃዋሽ የሃበሾች ሆቴል አለ በመጠጥና በመብልም ልክ እንደ ፈረንጅ ቤት ያማረ ደግሞም ድሬዳዋ ያቶ ወርቁ ሆቴልና ያበሻ ልጆች በማህበር ያቆሙት አለ ሉክ መብሉም እንደ ፈረንዶች ሆቴል የሆነ እዚያ እንኳን ገብተው የሚበሉና የሚጠጡ ፈረንጆች አላየሁም እነሱ እንደዚሁ ያገራቸውን ሰዎች ለማክበር ባገራቸው ሰዎች ሆቴል በተቀር በኛ ሆቴል ካልገቡ ምነው ጌቶቼ እኛም ቢከፋም ቢበጅም በሃገራችን ልጆች ሆቴል ጠላና ጠጅ እየጠጣን በውድም በረኪሱም ግዜ ከነኛው ብንገዛ ሁለት ጥቅም አለን ምንና ምን ትሉኝ እንደሆነም አንደኛው ስለጤንነታችን ሁለተኛውም ያገራችን ሰዎች በመከበራቸው ይህ ሁለቱም ያገር ጥቅም ነው ውስኪ መዳከሳ መስቲክ የሚባለውን ሁሉ መቼም አሁን በቅርብ ግዜ ነው ያገኘነው አለወረት እንሰስርበታለን እንጅ ደግሞም አንድ ደሃ አንድ አላድ ብትኖረው ያቺን ለግዜው አንድ መለኪያ ውስኪ ገዝቶ ቢጠጣበት ምንድነው ጥቅሙ በዚህ በውስኪው ልክ እየቆጠበ ጠላ ቢገዛበት ላንድ ወር ይበቃዋል ለዚሁም ባንድ ቀን ወደ ድህነት አድራሼ ከመሄዱ ኤኮኖሚ ፖለቲክ የሚባለውን መመልከትና አስተዳደርን ማወቅ ይሻላል ስል አሳስባችኋለሁ ። ከውስኪ መደቀሳ ይሻላል ጠጃችን ።ከቢራ ደቦኔ ይበልጣል ጠላችን፡፡ ከሰዳ ሎሚናት መልካም ቀራሪያችን ። አረ ለምንድነው እኛ መክሰራችን ፡፡ ላንድ ጠርሙስ ቢራ አላድ መክፈላችን ፡ ጠርሙሱ ባንድ ቤሳ ይሼጣል ጠላችን ፡፡ ላንድ መለኪያ ውስኪ አላድ ማውጣታችን ። በተሙን ሲገዛ ብርጭቆው ጠጃችን ፡፡ ጌቶቼ እንሞኝ ለሰው አገር መጠጥ ምነው መክሰራችን ። እነሱ ሳይፈቅዱ የኛን ጠጅ ጠላችን ። እኛ ለምድነው ባዳ ማክበራችን ። ይሻል ይመሬለኛል ክብረትን ብናስብ ላገር ልጆቻችን ። ቢያገኙም ቢከብሩ ቀሪ ላገራችን ፡፡ የባዳማ ክብረት ይሻገራል እንጅ አይቀር ባገራችን ፡፡ ይሻላል ቢከብር ያገር ልጅ ወንዛችን። ከንግዲህስ ወዲያ ይቅር ቀልድ ዋዛችን ። ጠጅ ጠላን እንጠጣ እንዳያቶቻችን ። የውስኪ ወዳጆች እንዳትቆጡኝ ። ያገራችን መጠጥ ረክሶ ቢታየኝ ይኸን ጻፍኩኝ እንጅ ስለአሳዘነኝ ። ተናገርኩ ይበቃል ይቅርታ ስጡኝ

በቀለ ዘለቀ

ያልታወቀ ጥቅምና ጉዳት ።

ጥር ፳፰ ቀን ፲፱፻፳ ዓ ም ተምሽቱ እኩል ስዓት ሲሆን እቤቴ በራንዳ ተቀምጬ ሳለ ባሻጋሪዬ ጨረቻ ጫካ ትልቅ ቃጠሎ ተነሳ ባለፉቱ ወራቶች ውስጥም ወደዚያው ለመናፈስ ሂጄ ነበረና ባለፈው ዓመት የተቃጠሉ ብዙ ደን አየሁ አንድ እንኳ ሕይወት ያለው ዛፍ አልነበረበትም።ባለፈው ዓመት የተቃጠሉትን የጥድና የዝግባ ቃጠሎ አይቼ በጥፋታቸውና ከንጨትና ከዛፍ ማነስ በላያችንና በምድራችን እንዴት ያለ ጉዳትና ችግር እንደ ደረሰብን ሳስብ ደግሞ ዘንድሮ የዛፍ ሕይወት ማጥፋት ይበልጥ ሁኖ ተደገመ በአዲስ ዓለም ዙሪያ ያሉ አገሮች ላይ ላዩን ይዞ ጀምጀም በርጫ ጨረቻ በጣም በዛፍ የከበሩ አገሮች ነበሩ ለመኖሪያ ለጤና የሚስማሙ ግን ወደፊት የድርቅና ለጤና የማይስማሙ አገሮች እንዳይሆኑ በጣም ያጠራጥራል ማለት ዛፍ የሌለበት አገር ድርቅ ይበዛዋል ዝናማትን የሚስቡ ዛፎች ናቸውና ብዙ ልዩ ዓይነት ዛፎች ያሉባቸው አገሮች ለማየት ደስ እንደሚያሰኙና ለጤናም እንደ ሚስማሙ ያየ ይመሰክራል ። በላይ እንደ ተወሱቱ ያሉ አገሮች ጉዳታቸው ለዓይን ደስ ስለ ማያሰኝ ብቻ አይደለም እንዲሁም ለመኖሪያ ። ግን ልዩ ልዩ ጉዳቶች አሉባቸው፡፡ለማብሰያ የሚያነዱት በስንት ኃይል ለሚሄዱ ፋብሪካዎች ለቤት መስሪያ ለሳንቃ ለቤት መሳሪያ ማለት እንደ ወንበር እንደ ጠረጴዛ እንደ ለዚሁ ላሉቱ ነገሮች ሁሉ የሚሆንና የሚሠራበት ሁሉ በጣም ይቸግራል፡፡ለምሳሌ አዲስ አበባ አንድ ጭነት እንጨት አንድ ብር ነው ፩ ለበር የሚገጠም ሳንቃ ፪ ብር ፩ ሸክም ጠርብ ፩ ብር ባለ ፲፪ ክንድ አራት ማዕዘን ፪ ብር ይሸጣል ። ግን እዚህ ደኑ በማናቸውም ሰው የዛፍንና የንጨትን ጥቅም በማያውቅ ሰው እጅ ስለ ሆነ። በ፱ ብር ፱ ሸክም ጠርብ በ፩ ብር አስር ጭነት የሚነድ እንጨት ባ፩ ብር ፪ቱ ባለ አስራሁለት ክንድ የማዕዝን በ፩ ብር ሁለት ሳንቃ ይሸጣል ። በማናቸውም ሰው እጅ ስለሆነ እንደ ምንም ይደረጋል ። ይህ ነገር ባገባብ ቢሆን በአዲስ አበባ ከተማ ለምንኖር ሰዎች አላይ በተጻፉቱ መሳፈያዎች ብዙ ችግር ባልደረሰብንም ነበር፡፡በንደዚህ ያለ ነገር በጣም የተቸገሩ ዛፍን ያላገባብ መቍረጥና ይህንን ማቃጠል ትልቅ ያገር ጉዳት መሆኑን ሳያስ

ተውሉት አይቀርም ይልቁንም ብዙ ግብረ በላ አሽከሮች ያሉዋቸውና መልክክም ቤት ለመሥራት የሚጥሩ ታላላቆች የንጨት ጥፋት ችግር ምን እንደሆነ በጣም ይረዱታል ። ስለዚህ የሆነ እንዳልሆነ ሊሆን አይችልምና ወደ ፊት በዚህ ነገር ላይና በሌላውም ተቀብያ ያላቸው ባለ ማዕረግ በመንግሥት እጅ ወይም ባንድ ሰው እጅ ሁኖ ባገባብ እንዲ ሠራበት ይታሰባቸው። በሌላ አገር ፩ ሰው ከገዛ መሬቱ ላይ አንድ ዛፍ ሊቆርጥ ቢፈልግ በዛፉ አጠገብ አምሳያውን ችግኝ ካልተከለ ሊቆርጥ መንግሥት አይፈቅድለትም ቆርጦም ቢገኝ መንግሥት በብርቱ ይቀጣዋል ምነው ዛፍ ያገር ሕይወት ነውና ያደገውን በመጥረቢያ ሊያድግ ያጐነቆለውን በእሳት ሲያወድሙት ስላየሁ ሳይደክምበት የተገኘ ጥቅም ለቆየ ሳያደክም አይቀርም ብዬ አእምሯቸውን ለማስተዋል ያዘነበሉ የብርሃንና ሰላም ወዳጆች አመለከታለሁ ። ትንሽ ተማሪ ኃይሉ ለውጤ

ትንሽ ማስታወሻ ።

አንድ ቀን ማታ ሁለት ልጆች አንደኛው ኮት የለበሰ አንደኛው ግን እንደ ሃገራችን ኩታ የለበሰ በትንሽ ነገር ጥል አነሡና ግብ ግብ ገጠሙ ያ ኮት የለበሰ ልጅ ያንን ኩታ የለበሰውን ልጅ በኩታው አከናንበና እንደ አንድ ነገር ከመሬት አፍርጦ በማለፊያ ክርን ይጐበጉበው ጀመር ከጥቂት ጊዜ በኋላ የጣለው ልጅ ከላዩ ተነስቶ በረረ ያኛውም እከተለዋለሁ ብሎ ተነስቶ እሩጫ ጀመረ።ያው በፊት የጣለው ልብስ ዳግመኛ ጠላት ሆነውና እየጠለፈ ያጋድመው ጀመር ። ትንሹም ጎበዝ የሆነው ልጅ በጥቂት ጊዜ ከርሱ በጣም ራቀ ባለልብሱም እንደገና ተሰናዳና ለመሮጥ ቢያስብ ጅብ ተኼደ ውሻ ጮኸ እንደሚሉት የረባው ነገር የለም ከዚያ ተሰብስበ የሚያይ ሰው ሁሉ ወየውጉድ ልብስም እንደዚህ ያደርጋል?እያለ ይደነቅ ነበር ይህም ቁመቱ የተጅወለወለ ልጅ በታናሹ እጅ ውርደቱን ተቀብሎ ቀረ ከዚህ ሁሉ ያደረሰው ይህ አጉል ልብስ ነው እንጂ ለዚያስ ለትንሹ ልጅ የበቃ ጉልበት አጥቶ አይደለም ለዚሁ ለተሸነፈው ልጅ ሰዎች ቢጠይቁት ልብሴ ነው እንጂ መች ያሸንፈኝ ነበር ብሎ እያጉረመረመ ራሱ መስክሮታል ። እንባቢ ሆይ፣ የዚህን የሁለት ልጆች አኳኋን ተመልክተን የትንሹን ልጅ ልምድ መከተል ይገባናል ። ማለት በሃገራችን ይህን አጉል የሆነ ጋቢ ወይም ኩታ እንጅቦነቦንና ትክሻችንን ከመገንጠል በስተ ቀር ብንመለከተው ያገኘነበትን ትርፍ አጣነው ስለዚህ ይህን ያረጀ ልምድ ትተን እንደተማሩ ሰዎች እንደ ዋጋው መጠን እንደ ኤሮፓ ዓይነት ስፌት ኩታ ሳንደርብ ለመልበስ ያስፈልገናል ። ይህ የምንወደው ልብስ እንደ ምን ሥራ ያስፈታ ይመስላችኋል ። ባንድ እረኛ አገር ውስጥ እንደዚሁ ጥምጥምና ዘርፋፋ ልብስ የከበደም ጠርቡሽ በራሳቸው ላይ ለማድረግ እስከሁን ልምዳቸው ነበር። አሁን ከጥቂት ዘመን በኋላ አንድ ኃይለኛ ሹም ተነሥቶ ይህንን ሁሉ ልምድ አስትቶ እንደ ባልንጀሮቻቸው የኤውሮፓን ሰዎች ልብስና ባርኔጣ ልምድ አድርገው ሥራ ቢጀምሩ ከፊተኛው ይልቅ ሥራቸውና አረማመዳቸው መቶ ጊዜ የሚበልጥ ሆኖ ተገኘ ይባላል።ይህ ሁሉ ከቀልጣፋነት የደረሱበት ይህንን ስላጠፉ መሆኑን ተመልከቱት። አሁንም የኢትዮጵያ ልጆች የሆንን ሁሉ ይህን የመሳሰሉ ነገር ሁሉ እያስወገድን ወደ ኋላችን ከልጣልነው ምኑንስ ለሥራ መቀልጠፍን ከዚያ ከራቀንስ ደረጃ ለመርገጥ እንደርሳለን ። በሃገራችን ይህንኑ እንጀምረው ብንል ብዙዎች አበዱ ጨርቃቸውን ጣሉ የሚሉ አይጠፉም ነገር ግን አምተው ለፍተው አፋቸውን አኮማትረው ይቀራሉ እንጂ የሚያደርጉትስ ነገር የለም። እንኳን በኛ ዘንድ በብልሆቹም አገር ቢሆን እንደዚሁ አንድ የሚጠቅም ነገር ቢጀመር ሕዝቡ ሲያንጓጥጥና ሲያሽሟጥጥ ይውላል ይህም የተጀመረ ሥራ እየገፋ የሔደ እንደሆነ እነዚያ ያሙ ሰዎች ከጀመረው ይልቅ ይብሱበታል።አሁንም የብርሃን ልጆች የሆንን ሁሉ ልንጀምረውና ልንገፋበት ያስፈልገናል እኛስ ያልጀመርነው ማን ሊጀምርልን ነው?ሐዋርያቶች እየተጋደሉና ደማቸውን እንደ ወሀ እያፈሰሱ ወንጌልን ስለዘረጉልን እስከሁን ቆይቶልን መድኃኒታችንና ብርሃናችን ሆናልናለች እኛ ደግሞ እንደዚሁ በተቻለን ለኋላ ለማቆየት ብንጣጣር ልጆቻችንም ጠቀሜታ የሚገኙበት ይሆናል ። ስለዚህ የሰው አፍ ፈርተን ሃሳባችንን እንዳናሳጥራት ይህችን ማስታወሻ ከኪሳችሁ እንድትአረጉአት አሳስባችኋለሁ ። ጥሩነህ ከ ።

ሕይወት ስለምን ይከብዳል ?

ብርሃን ከተባለ ጋዜጣ እኒህ የሚከተሉትን አሳቦች እንወስዳለን ፤

የዚህ ጥያቄ መልስ ከአሜሪካ ይመጣልናል ፤ በርበሬ ሆነ ጨው እውነትም አይጐድልበትም ፤ ሕይወት የከበደ ነው ፤ ስለ ምንድርን ሕዝብ አይቈጥብምና ።

,, የሰማይን ምሳሌ አይቀበልምና ፤

,, ፍሬ ከሚሰጡ የተገኘውን ፍሬ ብቻ የሚጨርሱ ይበዛሉና

,, ብዙዎች በሌሎች ደንደስ የሚመገቡና የውሻ ዓሦች የሚባሉ ትንንሹን የሚበሉ በዝተዋልና ፤

,, ምንድር ደግነት ጠፍትዋልና ፤

,, ኪሳራ በዝትዋልና ፤

,, ማበደር በዝትዋልና ፤

,, ዕዳ በዝትዋልና

,, ቅምጥልነት ሠልጥንዋልና ፤

,, ከንቱነት ተለምድዋልና ።

,, ስስት በዝትዋልና ።

,, ወንድ ብዙ ሲለብስ ሴት እጅግ ጥቂት ትለብሳለችና ፤

,, ብዙ መልበስ ለሰው ያከስራልና ።

,, እጅግ ጥቂት መልበስ ለሴት የባሰ ያከስራልና ።

ነጋዴዎችን ጠይቁ አንጠረኞችን ባለ ሽቶችንም ዓሚሎቻቸው እያነሱ ይሔዱ እንደሆን ጠይቁ ።

ቴያትርን ሲኒማንንም ጠይቁ ። የማያስፈልጉ የትርፍ ዕቃዎች የቅምጥልነት ያሉ ወይም የሌሉ እንደሆን ጠይቁ ።

ባለ አረቄዎችን ጠይቁ ። ሽቃጮችንም የአረቄዎችና የአልኮሆል የወይን ጠጅንም መሸጥ የሚያቋርጥ ቢሆን ። (ምስክር ከተባለ ጋዜጣ የተቀዳ)ያልተገቡና የማያስፈልጉ መሻቶች ሲበዙ ስለ ዚህ ሕይወት እጅግ ይከብዳል ፤

ማስታወቂያ ።

ሺብሮሌ አቶሞቢል በኢትዮጵያ ወኪል ።
ሔ ሜ ዜርቦስ ኩምፓንያ ።



Automobiles CHEVROLET

H. M. ZERVOS & Cie
REPRESENTANTS
BAS PRIX HAUTE QUALITE

ማስታወቂያ

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚ፲ጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
ደግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፮ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር	፱ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ብር
ኀሐ ጽባሕ	፮ብር
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፪መ
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ብር
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ተኩል
የቁጥር ትምርት	፩ብር
ያማሪኛ ሰዋስው	፩ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	አላድ
ወዳጄ ልቤ	፫ሩብ
አጭር የዓለም ታሪክ	አላድ
ያማሪኛ ፊደል	ሩብ
አሳብና ምኞት	ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት	ሩብ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር	፪መ
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ	ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ	፩ሩብ

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲ ብር ተኩል
የሲዳሞ ቡና	፩	፲ ብር
ዝባድ	፩ ወቄት	፫ ብር
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፩ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፬ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር ተኩል
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፯ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ከረጃ	፱ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ከረጃ	፲፰ ብር ተኩል
አቡጀዲ መነጽር	፩ ከረጃ	፻፴፫ ብር
፡፡ ባለሰይጣን	፡፡	፻፵፯ ብር
፡፡ ባለ ድመት ፡፡		፻፴፫ ብር
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻፳ ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፻፴፫ ብር
ባለ አንበሳ	፡፡	፻፵፫ ብር
ሱካር	፩ ጁኒያ	፳፰ ብር
ቻይ	፩ ነጥር	፩ ብር

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ ከ፴ ሳንቲ
አንድ ብር	ሊሬ ፱ ከ፲፫ ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፲ ብር ከ፲ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፫ ብር ተኩል

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

COGNAC SaEsA.METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ማስታወቂያ

መጽሐፍና ደብተር የሚያስጠርስ ሰው በርካሽ ዋጋ በል ዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ይጠረዝለታል ።

ያረጀ መጽሐፍና መዝገብ ማሳደስ ለፈለገ ሰው በርካሽ ዋጋ እንደ አዲስ አድርገን እንጠርዝ ለታለን ።

የእጅ ሰዓት ዝኒት



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የሚባል ባለ ፈረስ ስዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩግቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶመቢል በተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው። ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፡ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፡ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ኒለሣም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ማመልከቻ ።

በብርሃንና ሰላም ውስጥ ማስታወቂያ ማሳተም የሚፈልጉ ነጋዴዎች እስከ ፈለጉት ጊዜ ድረስ ባማርኛም ሆነ በፈረንጅ ቋንቋ በርካሽ ዋጋ እንደምናትምላቸው እናስታውቃቸዋለን

የሚከራይ ቦታ ።

A LOUER

ጉድይር ግዙ





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው።በሌላጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ፣ ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አራተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፲
4 me ANNÉE № 10

ሐሙስ የካቲት ፳፱ ቀን ፲፱፻፳ ዓ ም።
JEUDI 8 MARS 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d'Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል።
በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ቅዱስ ጊዮርጊስ በዓል አከባበር ።



ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ፥ በዑደት ጊዜ በመኳንንት መካከል እንጀ ተቀምጠው

በጀርመን ፎቶግሬፍ አንሺ ጉሉሌ የተነሣ ፎቶግራፍ

ስለ ቅዱስ ጊዮርጊስ በዓል አከባበር



በጀርመን ፎቶግራፍ አንሺ ጉሉሌ የተነሣ ፎቶግራፍ

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት በዓሉን አክብረው ከቅዱስጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሲወጡ

የካቲት ፳፫ ቀን በጧት ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በክቡራን መኳንንትና ሠራዊት ታጅበው ወደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ገቡ ።

በዚያን ጊዜም በዓሉን ለማክበር የመጣ ሰው የቤተ ክርስቲያኑ ውስጥና በውጭ ያለው ሜዳ ሞልቶ አልበቃ ብሎት ይጨናነቅ ነበር፣ የዑደቱ ጊዜ እስኪደርስ ካህናቱና መዘምራኑ ባማረ ሥርዓትና አቋቋም እየዘመሩ ሥርዓታቸውን ፈጸሙ ። አምስት ሰዓት ተኩል ሲሆን ታቦቱ ወጣና ቆመ ። ልዑልም አምሮ በተሰናዳው ቦታ መኳንንቱ ግራና ቀኝ ከበዋቸው በመካከል ተቀመጡ ።

ካህናቱና መዘምራኑ በልዑልና በመኳንንቱ ፊት ሲያሸበሽቡ እጅግ አምረው ታዩ ።

በዚያን ጊዜ ክቡር ሐኪም ወርቅነህ በዓሉን ለማክበር ከስተማሪዎቹ ጋራ ተማሪዎቹን አሰልፈው መጡ ። ዑደቱ ከተፈጸመ በኋላ ብፁዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ሕዝቡን መክረው አስተምረው ባርከው አሰናበቱት ።

ከዚህ በኋላ መድፉ እየነጐደ ታቦቱ ገባና ጥቂት ቈይተው ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ወጡና ባማረ አጀብ ታጅበው ወደ ቤተ መንግሥቱ ተመለሱ ።

ይህ ቀን በዓድዋ ጦርነት የታወቁና ያልታወቁ የኢትዮጵያ ጀግኖች ስለ ሀገራቸው ስለ ኢትዮጵያ ደማቸውን ያፈሰሱ ሕይወታቸውን አሳልፈው የሰጡ የሚታሰቡበት ቀን ነው፣ ስለዚህ በመላው የኢትዮጵያ አድባራትና አገሮች ዋና በዓል ነው እንጂ የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በዓል ብቻ እንዳልሆነ ልናስብ ይገባናል ።

የዓድዋ ጦርነት ከሆነ ፹፪ኛ ዓመት ዘንድሮ አለፈ ።

መልስ

ይህንን የሚከተለውን ማስታወሻ ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ደግሜ ልጽፍ ያነሳሳኝ ቁም ጸሐፊ አቶ ገብረጻድቅ በ፵፫ኛው ንምራ በ፫ኛው ዓመት የጻፈውን ማስታወሻ ካነበብኩ በኋላ መሆኑን ልገልጽ ፈቃዴ ነው ።

አቶ ገብረጻድቅ የጻፈውን ምክር ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን የጥንታዊ አርቶ ዶክስ ሃይማኖትዋን ለሚወድ ለቀናተኛ ኢትዮጵያዊ ሁሉ እየመረመረ የችሎቱን ቢሠራ የተገባ ነው ። ግን አቶ ገብረጻድቅን ትንሽ አሳብ በስህተት ያመለጠችውን ላቃና እደፍራለሁ የእስላም ሃይማኖት እንዳይሰፋ ስላሰበ ይህን ቃል ይጨምራል የእስላምም አስተማሪ ጋላውን እንዳያስተምር በአገረ ጉጀው በአዋጅ ቢከለክል ደግ ነገር ይመስለኛል ይላል ማናቸውንም ሃይማኖት ቢሆን ማስተማር መከልከል ትልቅ ወሰን የሌለው ጥፋትና ያለማወቅ ይሆንብናል ። ለምኑ ተብሎ ይከለከልና ያልቁን የኛ ካህናቶች ቁርዓንን በአማርኛ አስተርጉመው ወንጌልና ቁርዓንን አብረው ማስተማር ይሻል ነበር ማለት ለእስላሞቹ ሁሉቱንም በምሉ ካወቃቸው በኋላ የሚሻል ወደ መሰላቸው ይግቡ አንድ አንድ ሰዎች ይመስላቸው ይሆናል ። ሁለቱን ሃይማኖቶች እኩል ማስተማር አይገባም ግን እነሆ ዓይን ያለው ሰው ቁርዓንን አንብቦ ገብቶት ከክርስቲያን ሃይማኖት ይሻላል እንዳይል ግልጽ የሆነ ነገር ነው ብዙ እስላሞች እንዲህ ይላሉ የክርስቲያን አምላክ ተሴት ተወልዶ ሰው ሆኖ በሹሞች ፊት ቁሞ ተመርምሮ ተገርፎ ተሰቀለ ባመት ባመት ይሰቀላል ማነው የሱን ሥራ የሚሠራለት በዚያን ቀን እያሉ ይቀልዳሉ ።

የሃይማኖታችነን ምሥጢር የሚያስረዳቸው ገና አላገኙም ። ካህኖቻችን ተከርክር በተቀር ቁጭ ብለው ታሪኩን ለማስረዳት ዋ ክረዋቸው ያውቁ ይሆን ወይ? ብሎ ለመጠየቅ የሚያደርስ ነው ።

የስላሞች አስተማሪያዎች ያነን የሚያሰክር ቅጠል ይበሉ ይበሉና ሲሞቃቸው መጽሐፉን ማንበብ ይዠምራሉ ሲያነቡም እንባቸው እንደውሀ ይንቆረቆራል የሚወርደውንም እንባ ሕዝቡ በተመለከተ ጊዜ የተነበበው ቃል ሳይገባው አብሮ እያለቀሰ «ያሞሐመድ ያሞሐመድ» ይላል በውኑ ሲያነቡትስ የሚያስለቅስ ታሪክስ በክርስቲያን ወንጌል በ፳፫ኛ ምዕራፍ በሉቃስ ወንጌል ይገኛል የዓለም ጌታ የሰው ልጆችን ለማዳን በዓለማዊ ዳኛ ሲፈረድበት መስቀል አሸክመው ሲነዱት መሄድ ተስኖት በመንገድ ድፍት ብሎ ሲወድቅ በመስቀል ላይ ሰቅለው ሲቀልዱበት ውሀ ጠማኝ ሲላቸው ከምጣጤ ሲያጠጡት ይህን ሁሉ ሲያደርጉበት ወደ አብ ሲጸልይላቸው በዚህ ምዕራፍ ያለውን ታሪክ አንብቦ እየገባው እንባው የማያንቀው ደንጊያ ነው፤

ብዙ የሚያውቁኝ ወዳጆቼ አሁን ለሃይማኖት ምን አታከተው እሱ የሚማረው ሥራ ለብቻው እያሉ በየጊዜ በተናደደ ልብ የምጽፈው ቃል ያስገርማቸው ይሆናል፤

አንባቢዎች ሆይ፣ የዘመኑ አዲስ ትምሕርትና የኢትዮጵያ ሃይማኖት እንዳልተማመኑ ገብቶናል ትንሽ ቋንቋ እያወቁ ዓይናቸውን መግለጽ የጀመሩ ሕጻናቶች ሃይማንታቸውን እየነቀፉ ወደካቶሊክና ፓርስትንታት ሃይማኖት ስለ ዘሩ ካህናቶቻችን ይናደዳሉ ግን ንዴት አይረባም ይልቅስ ከንቅልፋችን ተነስተን የጐደለንን መሙላትና ሃይማኖታችንን ከዘመኑ እንዲስማማ ማድረግ ነው ። እኛ የምንማረው ሃይማኖት አይደለም የሃይማኖትንም ነገር ከናንተ ይልቅ ለማወቅ አናስብም የምንማረው ላገራችን ኃይል መኩሪያ ክብረትና ፍቅር አሽከሮችና አገልጋዮች ለመሆን ብቻ ነው እንጂ እናንተ የማታውቁትን እናውቃለን እያልን ልንፈክርባችሁ አይደለም ስለሆነ ያገልግሎትና ያገር ፍቅር መጀመሪያው ሃይማኖት ነውና በዚህ መንገድ እንደሚታዩን ልናስታውሳችሁ እንደፍራለን ። የክርስቲያን ሃይማኖት ነገሩን ሁሉ ፈጽሞ ይዞታል ከሁሉ አብልጦ መፋቀርን ያስተምራል ፍቅር ብቻ ሥራውን ሁሉ ይፈጽመዋል እውነት ኢትዮጵያ ባንድ ልብ ሁና የልዑል ተፈሪ መኰንንን ልብ እኛ መርምረን እንደምናውቀው አውቃ በቀጥታ ብትከተላቸው ብዙ የዋሆች የቤታቸውና የራሳቸው ጥቅም ያሸነፋቸው ሁሉ ባንድ ልብ ሆነው ቢከተሏቸው ኢትዮጵያ በጥቂት ዘመን ራስዋን ችላ ለመቀመጥ ትችል ነበር ይህ ሁሉ የሚመጣው በፍቅር ብቻ ነው ።

አሁን አቶ ገብረጻድቅ ቁም ጸሐፊው ያስታወሰውን መልከም አሳብ የድኃ ነገር ብሎ ከመርሳት በርትቶ እንዳለው በየ

ወረዳው አስተማሪ እየቀጠሩ የእግዚአብሔርን ፍቅር እንዲሰብክ ቢያደርጉ ጥቅሙ ከሚመስላችሁ ይልቅ ይሆናል ።

ስለዚህ ፍቅር ይስፋ ላገራችን እንጸልይ ኢየሱስ ሐዋ ርያቱን ወዳጆቹን ትቷቸው ሊያርግ ሲል እነሆ አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ እርስ በርሳችሁ ተፋቀሩ ያለውን ቃል ብናስብ ሸክማችን ይቀላል ።

ክቡራን የኢትዮጵያ ክርስቲያኖችና ካህናቶች እረ ባካችሁ ተነሱ ስንት ዘመን ተኝተን እንኖራለን ።

የኢትዮጵያ ካህናቶች ቢበረቱ የኢትዮጵያ ሰዎች ባንድ በዋና ነገር ከዓለም ሁሉ ሳይበልጡ አይቀሩም ይኸው እንዲህ ነው በዓለሙ ያሉ የሠለጠኑ ሕዝቦች በክርስቲያንነት ሲኖሩ እምነታቸው በጣም ተከፋፍልዋል ። አሁን ወደ አንድ ከተማ ብሄድ አራት አምስት ቤተ ክርስቲያኖች ጐን ለጐን ቁመው ተሰርተው አገኛለሁ በያንደአንዳቸው ብዙ ሺህ ብር ተከስሮባቸዋል ። ግን እዚህ እንደዚህ ያማሩ ቤተ ክርስቲያኖች ቁመው እያሉ ብዙ ክርስቲያኖች የኩል ሰዓት ያንድ ሰዓት መንገድ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ፍለጋ ይሄዳሉ ምነው ለምን እዚህ እቅርቡ አትሄዱም ስንላቸው ይህ የኛ ቤተ ክርስቲያን አይደለም እምነታችን ይለያያል ይላሉ ይኸውም ለሕዝቡና ለመንግሥቱ ከንቱ ጉዳትና ገንዘብ ማባከን ሆኖበታል ባንድ ቤተ ክርስቲያን የሚሰግድ ሕዝብ በነበረ ሶስት አራት ቤተ ክርስቲያኖች ባንድ ግድም ከመሥራት አንዳንድ ቦታ ይበቃቸው ነበር ።

እንዲህ ማለቴ በኢትዮጵያ ያሉትን ካቶሊኮችና ፓርትስትአንቶች አጥፏቸው ማለቴ አይደለም ። ያመኑትን ባመኑበት ሃይማኖት መተውና በፍቅር አብሮ መኖር ይገባናል ።

ካቶሊክና ፓርትስትአንት አንባቢዎች የምናገረው ለኢትዮጵያ መሆኑን እየመረመሩ ይቅርታቸውን ሳይሰጡኝ አይቀሩም ።

ሃይማኖታችን እየተሻሻለ እንዲሄድ እንመኝ እንጂ ሁላችንም በያለንበት ይህ ይሻላል ለማለት አይገባንም ። የክርስቶስ ሃይማኖት ፍቅር ነው በፍቅር እንተሳሰር ፍቅር በመካከላችን ይንገሥ ። የኢትዮጵያን ጥቅም እየረሳ የራሱን ጥቅም የሚያስብ በእግዚአብሔር ፊት የተዋረደ ይሁን ነጻነታችን ለዘለዓለም ትሁን ።

መልአኩ በያን ።

ማስታወሻ ።

የሥልጣኔ መንገዳችንን ወደፊት እንዳንራመድ ወደ ኋላ የሚጐትተን ንፍገትና ስንፍና እንደምን ይሆን ብዬ ለፍቅር ማሕበረተኞቼ ለመናገር አሰብሁ ።

ክቡራን ሆይ፤በስንፍና ወይም ባለማወቅ በኖርነ ጊዜ እያንዳንዳችን የድህነት ባሕሬ ሠልጥኖብን የችጋርን ነገር ለማጥንከር በሰውነታችን ትኖር ነበረችና ዛሬ ግን ሥራውን እንኳ በንሡራው በስንፍና መኖራችንን የሚገልጥ ብርሃንና ሰላምን የሰጠን ጌታ ክብርና ምስጋና ይገባዋል ። እኔ ግን በስንፍና ትምርትን በማጣት የተዘጋሁ ባሳቤ ትምርትን እመኛለሁ ። ነገር ግን ትምርትን አላገኘሁም ትምርት የሕይወቴን ብርሃን ደጉን ነገር ሳልፈልግ በከፉ ሐሳቤ ልቤን እበትናለሁና ፤ መቸም በብርሃንና ሰላም ምክር ደስ ሲለኝ ልቤም በፍቅሩ እንደሳት ሲቃጠል ቃሉን በመርሳቴና ባከኼዴ ግን ምክሩን እንደተቃወምኩት ይታየኛል አስቀድሜ በራሴ ልፍረድን በስንፍና የታሰርኩትን ማን ያስፈታኝ ይሆን እላለሁ።

ስለሆነ ግን እግዚከብሔርን አጥብቄ አመሰግነዋለሁ ። የሀገር ፍቅር ካለባቸው ከየወንድሞች ልብ አፍርቶ የሚገኘውን ጥቅም በብርሃንና ሰላም መሰቡ ለቅሞ አጠራቅሞ የሚመግበን ልዑል ተፈሪ መኰንንን የሰጠን አሁንም ክቡራን ወንድሞሞቼ አንባቢዎች ሆይ፡ሁላችሁም ፈጽማችሁ የድንቍርናን ሥራ እንደ ምትጠሉት ያለጥርጥር እናውቃለን ይህ የምንመኘው መልካም ሥራ ሁሉ በቶሎ ቢጀመር ሐሳባችሁ ነውና የትምርትን ቤት ለማቆም እንዳቅም እንዳቅማችን እንረዳዳለን ብለን ማሕበር ያደረግነው እስከ አሁን ሳይቆምና ሥራው አለመጀመሩ እንደፍቅርና አገልግሎት ማህበር ለሥራው ሐላፊ የሚሆን ሰብሳቢ ባለመኖሩ ነውን ወይስ በምን ይሆን ብዬ አራተኛ ዓመት በቁጥር ፳ የካቲት ፲፫ ቀን ፲፱፻፳ ዓ ም በወጣው ብርሃንና ሰላም ክቡር ልጅ አበበ ወልዴ ለሐገር ፍቅር የሚያስበ በፍቅር እንደጠየቁ እኔም ቃሌን ከፍ አድርጌ የልቤን ፍቅር ገልጬ በትሕትና የልመናዬን ጥያቄ አቀርባለሁ ። አገርን መውደድ ከልብ ቆርጦ ሥራውን መፈጸም ነው እንጅ ባፍ ብቻ ይህን አደርጋለሁ ማለት እንዳይጠቅም ጌታችን መድኃኒታችን በቅዱስ ወንጌሉ ያስረዳናል በደሙ ያለምን ኃጢአት ሊያስወግድ በተዋህዶ ሥጋ ለብሶ ወደኛ የመጣውን መለኮት የኦሪት ሰው ሊፈትነው ተነሣ እንዲህም አለው፤ መምሕር ሆይ ምን ላድርግ የዘላለም ሕይወት እወርስ ዘንድ ቢለው ጌታም አለው በሕግ የተጻፈ ምንድ ነው እንዴትስ ታነባለህ እርሱም መለስ አለም እግዚአብሔር አምላክህን ውደድ በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም ኃይልህም በፍጹም አሳብህም ባልንጀራህንም እንደነፍስህ አለውም በውነት መለስህ ይህነን አድርግ ትድንማለህ እርሱ ግን ሰውነቱን ጻድቅ ያደርግ ዘንድ ወደደ ጌታንም አለው ባልንጀራዬስ ማነው ጌታም መለሰ አለም ሰው ነበረ ከየሩሳሌም ወደ ያሪኮ የወረደ በወንበዶች መካከል ወደቀ ገፈፉትም አቆሰሉትም ሄዱም በሕይወትና በሞትም መካከል ተውት ካህንም በዚያች መንገድ ሲወርድ አገኘው አይቶትም አለፈ እንዲሁም ደግሞ የሌዊ ወገን ሰው ወደዚያ ስፍራ መጣ አይቶትም አለፈ ሳምራዊ መንገደኛ ግን አለፈበት ባየውም ጊዜ አዘነለት ወደ ርሱም ቀረበ ቁስሉንም አጋጠመለት ዘይትና ጠጅም አፈሰሰበት ባህያውም ላይ አስቀመጠው የሚያደርገውንም ነገር አሰበበነገውም ሲወጣ ፪ ድሪም አወጣ ለመንገደኛ ቤት ጠባቂም ሰጠው አለውም አገልግለው እጅግም ስለ ርሱ ብታወጣ በተመለስሁ እሰጥሃለሁ ከነዚህም ከሶስቱ ማናቸው ይመስልሃል በወንበዶች መካከል ለወደቀው ባልንጀራ የሆነው እርሱም አለ ምሕረት ያደረገለት ።

አሁን የዚህን ትርጓሜ ለመዘርዘር ንባብ ይበዛብናል ባጭሩ ኢትዮጵያ እናታችን ስንፍናን በሚባለው ሰንሰለት አስረው

ንፍገትና ምቀኛነት የሚባሉ ወንበዶች ደብድበው ጥለዋት በተጠላ ሳምራዊ ጥበብ ትምሕርትን ቁስሏን አጋጥሞ የሚያድናት ባልንጀራዋን አሰናክይ በጭር ቃል አንድ ምሳሌ እናገራለሁ።በንድ በለመለመች አገር አንድ ትልቅ ወርካ ፍሬው ለሁሉ የሚበቃ አለከፍሬውም የሚመገቡ በማናቸውም ነገር ጉዳት እንዳያገኘው የሚያስቡለት በሥሩም ተጠግተው የበቀሉ ሐረጋቸው የበዛ ቅጠላቸው የወዛ ቀኝና ግራ በስፋት የተንሰራፉ ዛፎች ስፍር ቁጥር የሌላቸው ሞልተዋል በዛፎችም መሐከል ብልግያ ተመችቷት ያደገች ሰንበሌጥ ነበረችና በወርካው ቅናት አደረባት ስለቅናቷም ዛፎቹን ሁሉ እንዴህ አለቻቸው በዚህ በወርካ ልምላሜና ፍሬ ልንኖር ነውን እባካችሁ እሳት ከኔ ይውጣ እናንተ እያይዙ ወርካውንም በልተነው እንጥፋ ብትላቸው ሰማሽ ሰንበሌጥ ሆይ ምንም ስርና ልምላሜ ከባሕሪሽ ባይኖር በጥላው ውስጥ አድገሽ ሕይወትሽን የሚጠብቀ ወርካ ምን ደረሰብኝ ስለ ቃገስሽ ቅጠሉን እንኳ አይጥልብሽ ምን አደረገሽ ክንፍና ልምላሜ ዘር የሌለሽ የጊዜሽን ያህል በቅለሽ በማናቸውም ነገር ብትጠፊ ሐሳብ የለሽምና እኛስ ጥላው ልምላሜ ፍሬው ምግብ የሆነንን ወርካ አጥፍተን ለማጥፋት ቢሱን ያርቀው እንዳፍሽ አያድርግብን አርፈሽ ተቀመጭ ብለው ቢመክሯት ምክራቸውን ንቃ ክብሪይት ፍለጋ ስትንከራተት ወርካው ሳይንቀሳቀስ ሰንበሌጥ በገዛጅዋ ተነቅላ ወደቀች ። ለወርካው የሚሳሳ የጥላውን ረዴት የተመረኮዘ ፍሬውን ለመብላት ፈጣሪውን የሚለምን ተስፋ የሚያደርግ ርግብ የዋህ እንዲህ አንጐራጐረ ይባላል ።

ብዙ ያስደንቃል የዚህ ዓለም ነገር ። ሰንበሌጥ ተወርካት ወዳደር ጀመር ፡ ወይ አእምሮ ማጣት ሰንበሌጥ ፋጠለ ። ከብላጊ ሳይደርስ ወድቆ ተነቀለ ፡ እንግዴህ አትክልቶች ብዙ ተጠንቀቁ ። ከጥላው እረፉ ወርካን አትናቁ ። እንድትለመልሙ በጣም እንድትሰፉ ። አትነቅንቁ ወርካን በጥላው እረፉ ፡ እያሉ ሲያወጉ ምግባርና ዕውቀት ፡ እሰማቸው ነበር ምንም ሳልታክት ይህንን መጻፌ እንዳልባል ሞኝ ፡ ፈጣን መልክተኛ እንዳያመልጠኝ ብርሃንና ሰላም እንዲያደርስልኝ ፡ ነገሩን ግን በጣም የሚደንቅ ነው ምን ይሆናል አንባቢ ከማሸልቸት ስሚ ጆሮ ላለው ይህ ይበቃል።

መክብብ ደስታ ።

ትንሽ የጉዳት ማመልከቻ ።

አቶ ጥሩነህ ካብትህ ይመር ስለ አንድ አንድ ለኛ ይድላን የሚባሉ ፲፻፶ ብር ባንድ ዓመት ያገኛሉ ብሎ ስለጻፈው ጋዜጣ አንብቤ አነሰንስ በዛ እያልኩ ካቶ ጥርጣሬ ጋር ስናወጣ ስናወርድ ሳለ ወዳጄ ቀኛዝማች ሃሳብ ከተፍ አለና ከዚህ ይበልጣል እንጂ አያንስም ብሎ ነገሩን ፈጸመልኝ ወይ ግሩም እያልኩ ስደነቅ ሳለ ደግሞስ አቶ ሚካኤል ተሰማ በየአገሩ አውራጃ በየራስ ከተማው ሁለት ዓይነት ትምሕርት ቤት ይቆማል አንዱ እድሜአቸው ትንሽ ለሆነ የእውቀት ትምሕርት የሚማሩበት ። ሁለተኛው የትምሕርት ቤት እድሜአቸው ከፍ ያለ ብረት መኪና ማጋጠም ሸማ መሥራት ጫማ መስፋት ማነጥ የሚማሩበት አገረ ገጋርም ባይበልጥ በዚሁ ልክ ያቁም ማቆም እልችልም ገንዘብ የለኝም ቢል ግን መንግሥት ጸሐፊና ተቆጣጣሪ ከየአውራጃው ይላክበት ብሎ ስለ ጻፈው አላነበብክምን ? ደግሞ ከዚህ በታች ያለውን ብትሰማውና ብታውቀው አይረባህም ባለህበት አገር ስንኳን መቀሌ የብልሁ ረቂቁ የደጃዝማች አብርሃ ቤት የተሰጠበትን የገንዘቡን ልክ ሰምተሃልን አለኝ ። የጨረሰውማ እኔ እንደራሴ እስከ ፹፻ ብር ይወስድ ይመስለኛል ። ይልቁንም በጣም የሚያሳዝነኝና የሚያናድደኝ ይህንን የመሰለ ያማረና የተዋበ ቤት በትንሽ ገንዘብ አሳድሶ ለትምሕርት ቤት ወይም ለውጭ አገር ሰው እንግዳ መቀበያ በማድረግ ፋንታ የከተማ ሌባና ወስላታ በሩንና መስከቱን በብልህ ሰው እጅ እንዳልተሠራና እንዳልተከሰረበት ያለሃሳብ ይበዘብዘዋል ። ይህንን ያህል የተከሰረበት እንዴት በከንቱ ይቅር ። ?

አይ አይ አይ እንዲያውስ በአፋችን እየተጀረርን ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ ብንላት ለርሷ ይህንን የመሰለ ቅያሜ እያቀረብንላት ሆድን እያበሸቅን ላይ ላዩን ብንደልላት ከምንጐዳት በተቀር ትርፏ ምን ይሆን ። እኔስ እንደራሴ ይህንን ቤት አሳድሶ ለትምሕርት ቤት እያልኩ ስወዛወዝ ሳለ ያው ልምደኛው ቀኛዝማች ሃሳብ አንተስ ወንድሜ ነገርህ ብዙ ነው ። የአገርህን ልማድ ትተህ ወደ ሌላ ትቀባጅራለህ አለኝ ። ያገሬ ልምድ ምንድነው አልኩት ያገርህማ ልምድ ያለውን ታቅፎ አድብቶ ሲመለከት በደጅ ያለውን ሲዛረፉት አያስጥልም ብሎ መርዝ የሆነ ነገሩን በሰውነቴ ነዝቶብኝ ጥፍት አለብኝ የተነዛብኝንም መርዝ እንዳላበርር ሃኪም ስለሌለ ዘግየት ብያለሁኝና ድንቁርናም እንዳይከተለኝ በሽታየም ሳይጠናብኝ አስታጋሽ የሚባል ሃኪም ቆሞ ለመወጋትና ለመዳንትምሕርት የሚባል ሥልጣኔ ተደርጎ ብርሃኑን ለመመልከት ያብቃኝ እያልኩ ረዘም ያለ ተስፋ አደርጋለሁኝ ።

ትንሹ ልጃችሁ ኃይሉ ገብረ ማርያም ።

ስለ ክቡር ራስ ሥዩም መንገሻ ጉዞ በኤርትራ ።

በጥር ፲፮ ቀን ፲፱፻፳ ዓመት በብርሃንና ሰላም ስለ ራስ ሥዩም ጉዞ የታተመውን አነበብኩ መልካም እንደተመኘላቸውም በደህና አገራቸው ገቡ ።

በኤርትራ ግዛት በክብር ማለፋቸውንም እነሆ ባጭሩ ጽፌ አለሁ ።

በመጀመሪያ ከሜንዳቶሬ ሉዊጂ ታላሞንቲ ዲሬቶሬ አፋሪ ቺቢሊ ኤፖሊቲቺ ዳስመራ ። ራስ ሥዩምንና ወይዘሮ ዓፀደ አስፋውን ዳርጌን ከኢትዮጵያ ቆንስል ካቶ ዓለሙ ጋር ለመቀበል ምጽዋ ድረስ ወረዱ ። ራስ ሥዩምና ወይዘሮ ዓፀደ ማሪን ሳኑዶ በሚባል መርከብ ቅዳሜ በ፱ ሰዓት በጥር ፲፱ ቀን ምጽዋ ደረሱ ።

ነገር ግን ምጽዋ በመርከብ ብዛት የመጣለትን ዕቃ በማውረድ የሚሄደውን ዕቃ በመጫን በክብረት ታውካ ነበር ። የመርከቡ መቋሚያ ስፍራ ተይዞ ስለዚህ ሮሞሎ ከሚባለው መርከብ ጋራ አጋጥመው በመሰላል እየተሻገሩ ገቡ ።

ራስ ሥዩምና ወይዘሮ ዓፀደ ከተቀባይ መኳንንቶች ጋራ ተገናኝተው ስለ ክብር ጥቂት ስፍራ በአቶሞቢል ሄደው ከባ

ቡሩ ገቡ ። ወዲያው ሰውና እቃውም ተሳፍሮ ባቡር መንዝ ፎ መረ፡፡ጊንዳ ከሚባለው ግቢያ ሲደርሱ ደብረ ቢዘኖች መስቀል ይዘው መጥተው ተገናኙ ።

አስመራ ሲደርሱ ጨልሞ ነበር ። ያስመራ ኮሚሳርዮ ሌሎችም ትልልቅ መኳንንቶች እባቡሩ መቋሚያ ድረስ መጥተው አክብረው ተቀበሉ፣ በአቶሞቢል አብረዋቸው ሆቴል ዲ አስመራ ወደ እሚባለው ሄዱ፡፡ ጥቂት ካረፉ በኋላ እራት ተጋብዘው ወደ አገረ ገዢው ዘንድ ሄዱ ።

በዚሁም ስፍራ ለመንገደኞቹ የሚበቃ እራት ተደግሶ ነበር ። ብዙ ካሚዎኖች ቀርበው ሰዎችን በየማዕርጋቸው እያሳፈሩ ። የሚበሉትን እየሰጡ ሌሊቱን ሲሄዱ አድረው ሲነጋ አዲኋላ ደረሱ ።

ራስ ሥዩምና ወይዘሮ ዓፀደ ከመኳንንቶቻቸው ጋር አስመራ ቆይተው ነበር እሁድ ትልቁን ሆፒታል አሳይዋቸው ። ሆፒታሉንም እየዞሩ አይተው በየክፍሉ የተኙትን በሽተኞች አይተው ፻ሺ ፍራንክ እሰጣለሁ ብለው ተናገሩ ።

በዚሁ ቀን በ፱ ስዓት በለዛ ወደ እሚባለው አገር ስለ ኢሌትሪክና መኪና ማዞሪያ የተከተረውን የዝናብ ወሀ ኩሬ ለማየት ሄዱ. የኩሬው ውሀ በኤሌትሪክ መኪና ፴ ሜትር ወደላይ እየተሳበ ሳያቋርጥ እንደ ጉርፍ ሲፈስ ወደ ኢሊትሪክ መኪና በቦምባ ሲወርድ አዩ፡፡

ከዚያ ሲመለሱ ራስ ሥዩምና ወይዘሮ ዓፀደ ኮሜንዳቶር ታላሞንቲ ኮሜንዳቶር ፖሴራ ሌሎችም መኳንንቶች አብረው ወደ ኢትዮጵያ ቆንስል ቤት ገቡ ።

በዚሁ ቀን የማዕርግ ልብስ እየለበሱ እራት ተጋበዙ ሲ ኤቸሌንሳ ካባሊዬር ያኮፖ ጋስፓሪኒ ከመኳንንቶቻቸው ጋር በኢትዮጵያና በኢጣልያ ኒሻን አጊጠው ነበር ።

በገበታ አቀማመጥ

ባገረ ገዢው ቀኝ ራስ ሥዩም በግራ ብላታ ባራኪ ፡ ባገረ ገዢው ፊት ለፊት ወይዘሮ ዓፀደ በወይዘሮ ዓፀደ ቀኝ ያገረ ገዢው እንደራሴ ከእንደራሴውም ቀጥሎ የኢትዮጵያ ቆንስል ሌሎችም ብዙ ትልልቅ መኳንቶች ነበሩ ። ክቡር ያኮፖ ጋስፓሪኒ ቆመው በኢጣልያ ቋንቋ ብዙ ተናገሩ ። የተናገሩት ባማርኛ ተጽፎ ኖሮ የተነበበው ይህ ነው ።

ክቡር ሆይ ፤

በኤርትራ በማለፍዎ በጣም ደስ አሰኝቶኝ እንኳን በደህና መጡ ለማለት የጠበቀ የወዳጅነት ሰላምታዬን አቀርባለሁ ። በደስታ የተመሠረተ የ፪ ፡ ትልቅ አገሮች የኢጣልያና የኢትዮጵያ ወዳጅነት እየሰፋና እየጠበቀ መሄዱ ነው። ስለዚህ ለክቡር ለትግሬ ትልቅ ደጋፊና ጌትነትዎ ። የጥንት የኢጣልያ ወዳጅዎ ሰላምታዬን ሳቀርብ የ፪ቱ ትልቅ አገሮችና ወዳጅነት የ፪ቱም ጥቅም እየሰፋ ይሄዳል በማለት በርግጥ አምናለሁ ።

ስለ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ስለ ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ጤና ብዬ ጽዋዬን ሳነሣ ለክቡር ጌትነትዎና ለክብርት ባለቤትዎ የወዳጅነት ምረቃዬን አቀርባለሁ ።

ካባሊየር ያኮፖ ጋስፓሪኒ ።

የኢትዮጵያ ቈንስልም ስለ ራስ ሥዩም ሆኖ ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን አነበበ ።

ክቡር ሆይ ፤

ከኤርትራ በከበሬታ ስለ ተቀበሉኝ ፤ አሁን ደግሞ ስለ ተናገሩት ቃል ክቡር ኤቸሌንሳን በጣም አመሰግናለሁ ። ከልዑልዱካ ዲ አብሩሲ ጋር ክቡር ኤቸሌንሳ መጥተው ሳሉ እኔም አዲስ አበባ ነበርኩ ። ክቡር ኤቸሌንሳ ስለ ፪ መንግሥት ለወዳጅነትና ለጥቅም ሲያስቡ የተናገሩትን ቃል ሰማ ነበር ።

እኔም የትግሬ አገር አውራጃ ገዢ የኤርትራ ድምበረተኛ ይኸ መስማማትና ወዳጅነት በጣም እየጠበቀ እንዲሄድ አሳቤ መሆኑን እገልጥልዎታለሁ ። በዚሁም አሳቤ ለግርማዊ የኢጣልያ ንጉሥና ለግርማዊት ንግሥት እድሜና ጤና ይሁን ለማለት ጽዋዬን አነሣለሁ ።

ራስ ሥዩም መንገሻ።

በማግሥቱ እካቶሊክ ቤተክርስቲያን ሄደው ካቡኑ ተገናኝተው የቤተክርስቲያኑን ሥራ አይተው ፫ሺ ፍራንክ ሰጥተው ወጡ።በዚሁ ቀን ወደዚያው የሥጋ መኪና ለማየት ሄዱ ቆርቆሮው ሲሠራ የተቀቀለው ሥጋ በቆርቆሮው እየተከተተ ሲታተም አዩ።በዚሁ ቀን በ፱ሰዓት ኮሜንዳቶሬ ሉዊጂ ታላሞንቲ ኮሜንዳቶሬ ፓፖሴራ ከራስ ሥዩምና ከወይዘሮ ዓፀደ ጋር በአቶሞቢል ሆነው ወደ አዲኋላ ለመሄድ ተነሡ መንደፈራ ከሚባለው ከተማ ሲደርሱ የከተማው ሰው ሁሉ ታዞ ኖሮ ወታደሩ ተሰልፎ ካህናቶቹ እየዘመሩ ሴቶቹ በከበሮ በጭብጨባ በልልታ እየዘፈኑ ሠርግ አስመስለው አክብረው ተቀበልዋቸው ።

ማታ አዲኋላ ደረሱ አዲኋላም አክብረው ተቀበልዋቸው።በማግሥቱ ራስ ሥዩምና ወይዘሮ ዓፀደ አስፋው ዳርጌ ከኮሜንዳቶሬ ፖሴራ ጋራ ሆነው ወደ አድዋ ለመሄድ ተነሡ ኮሜንዳቶሬ ታላሞንቲና የኢትዮጵያ ቆንስል ወደ አስመራ ተመለሱ ።

ራስ ሥዩም መንገሻ ወይዘሮ ዓፀደ አስፋው ዳርጌ ቀዳሚት ማታ አስመራ ገብተው እሁድን ውለው ሰኞ በ፱ ሰዓት ወደ አዲኋላ ሄዱ ። የነገሩ ሁሉ ፍሬ ፻፶፯ ራሳቸውን ሆነው ከጅቡቲ በመርከብ ምጽዋ ድረስ ከምጽዋ አስመራ በልዩ ባቡር ካስመራ እስከ አዲኋላ ባ፲፭ ካሚዎንና አቶሞቢሎች ተጓዙ ።

የብርሃንና ሰላም ወዳጅ ።

ሹመት ።

የካቲት ፳፩ ቀን ክቡር ደጃዝማች መኰንን ወሰኔ ወለጋ የደጃዝማች ብሩ የነበረውን ተሾሙ ። ክቡር ፊታውራሪ ደስታ ዳምጠው ደጃዝማች ተብለው ጥንት በያዙት በጉማ ላይ ከፋን ጌራን ቆራጭነት ተሾሙ፡፡ክቡር ፊታውራሪ ዓምዴ የፈረስ ዘበኛን አለቅነት ዱረኒን የደማዝጃች መኰንን ወሰኔ የነበረውን ተሾሙ ።

ብርሃንና ሰላም አዲስ ሹመት ለተቀበሉ መኳንንት አዲስ ጥበብና ብርታት በሹመታቸው ላይ እግዚአብሔር እንዲሰጣቸው እየተመኘና ደስታውን እየገለጸ እንኳን ደስ አላችሁ ይላል ።

ማስታወቂያ ።

ሺብሮሌ አቶሞቢል በኢትዮጵያ ወኪል ።
ሔ ሜ ዜርቦስ ኩምፓንያ ።



Automobiles CHEVROLET
H. M. ZERVOS & Cie
REPRESENTANTS
BAS PRIX HAUTE QUALITE

ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከንትርጓሜው	፪ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ተኩል
የቍጥር ትምርት	፩ብር
ያማሪኛ ሰዋስው	፩ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	አላድ
ወዳጄ ልቤ	፫ሩብ
አጭር የዓለም ታሪክ	አላድ
ያማሪኛ ፊደል	ሩብ
አሳብና ምኞት	ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት	ሩብ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቍጥር	፪መ
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ	ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ	፩ሩብ

ማስታወቂያ

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚገኙ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከንትርጓሜው	፲፪ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከንትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከንትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከንትርጓሜው	፲ ብር
ደግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፫ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር	፱ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከንትርጓሜው	፯ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከንትርጓሜው	፯ብር
ጎሐ ጽባሕ	፫ብር
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፪መ
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከንትርጓሜው	፫ብር
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከንትርጓሜው	፪ብር

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲ ብር ተኩል
የሲዳሞ ቡና	፩	፲ ብር
ዝባድ	፩ ወቄት	፫ ብር
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፩ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፯፬ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፰ ብር ተኩል
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፯ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፰ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፰ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፴፫ ብር
:: ባለሰይጣን	::	፻፴፯ ብር
:: ባለ ድመት ::		፻፴፪ ብር
:: ባለአህያ	::	፻፳፪ ብር
:: ባለሳቢ ግመል	::	፻፴፪ ብር
ባለ አንበሳ	::	፻፵፫ ብር
ሱካር	፩ ጁኒያ	፳፯ ብር
ቻይ	፩ ነጥር	፩ ብር

ስለ ምንዛሪ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ ከ፴ ሳንቲ
አንድ ብር	ሊሬ ፱ ከ፩ ሳንቲም
ባአንድ ጊኒ	፲ ብር ከ፲
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፬ ብር

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ፡፡

COGNAC S&E&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ማስታወቂያ

መጽሐፍና ደብተር የሚያስጠርስ ሰው በርካስ ዋጋ በልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ይጠረዝለታል ።

ያረጀ መጽሐፍና መዝገብ ማሳደስ ለፈለገ ሰው በርካሽ ዋጋ እንደ አዲስ አድርገን እንጠርዝ ለታለን ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የሚባል ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩግቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚሀ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቀቅዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶመቢል በተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዘህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው ።

RUGBY

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፡ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በየይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፡ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ማመልከቻ ።

በብርሃንና ሰላም ውስጥ ማስታወቂያ ማሳተም የሚፈልጉ ነጋዴዎች እስከ ፈለጉት ጊዜ ድረስ ባማርኛም ሆነ በፈረንጅ ቋንቋ በርካሽ ዋጋ እንደምናትምላቸው እናስታውቃቸዋለን

የሚከራይ ።

A LOUER

ጉድይር ግዙ





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንክራ ነው ።በሌላጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ፤ ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አራተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፲፩
4 me ANNÉE № 11

ሐሙስ መጋቢት ፮ ቀን ፲፱፻፳ ዓ ም ።
JEUDI 15 MARS 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ መላው ሕዝብ ጤንነት ።

ካያሌ ጊዜ ጀምሮ ክቡራን ያዲስ አበባ ሐኪሞች ስለ ሥራቸው መመካከር ጀምረዋል ። አሁንም በየካቲት ፳፫ ቀን ዶክቶር ገብሬሎፍ ዶክቶር ሴንያቢን ። ዶክቶር ኪክቶን ዶክቶር ሐነር ዶክየር ጎጕን ። ዶክቶር ኤግሊስባሕ ዶክቶር ሬኖ ። ዶክቶር ሳርኪሲያን ዶክቶር ፖሎክ ። ዶክቶር ካሌዲጃን ዶክቶር ካራኬቴሳኒ ። ዶክቶር ሴዶስትሬም (የነቀምቴ) ዶክቶር አጌ (የሐረር) ዶክቶር ሐራልድ ኒስትሬም ። በክቡር ዶክቶር ሐነር ቤት በቤተ ሳይዳ ዘተፈሪ መኰንን ሆፒታል ስለ ሥራቸው እንዲመካከሩ ተሰብስበው ነበር ። የምክሩ ፕሬሲደንት ዶክቶር ሬኖ ናቸው የፕሬሲዳን እንደራሴ ዶክቶር ፖሎክ ናቸው ሴክሬቴር ዶክቶር ሳርኪሲያን ናቸው ።

በዚያን ጊዜም ዘወትር እንደሚያደርጉት በየጊዜውና በየቦታው ስለሚገኝ በሽታ የሚቃወመው መድኃኒት እንዴት እንደሆነ በፍቅር እርስ በርሳቸው ይከራከሩበት ነበር ። የኢትዮጵያ ሐኪሞች ስለሆኑ ዋና ንግግራቸው ስለሕዝቡ ጤንነት ነበረ እንዲህ አድርገው ያሰቡትንና ያከናወኑትን ለሕዝብ ጤንነት የሚበጅ ነገር ደግሞ በየጊዜው እያሳተሙ ሳያስታዉቁን አይቀሩም ። የሕዝብ ጤንነት ላገር ልማት ለመንግሥት ብርታት ዋና ነገሩ ነውና ። እንደዚህ አድርገው የሚያስቡልን ሐኪሞች በማግኘታችን ደስ ሊለን ይገባናል ።

ግን በሀገራችን ውሥጥ ያልተመሰከረላቸው መድኃኒት ቀማሚዎችና ሐኪሞች አይጠፉምና ብዙ ዕውቀት የሌለው ሕዝብ የመድኃኒቱን ርካሽነት እንጂ እውነተኛ መድኃኒት መሆኑን ሳይመረምር ያልሆነ መድኃኒት እየገዛ ይጠጣል ይታከማልም በስሕተትም ብዙ ሰው ይጐዳል ። ለዚሁም መንግሥታችን ከዚህ በፊት ካደረገው ይልቅ አጠንክሮ ሕጉ እንዲጠበቅ አድርጎ ትእዛዙን እንዲሰጥ ተስፋ እናደርጋለን ።

ሕዝባችን ወደ ሥልጣኔ ደረጃ እንዲደርስ እንጣጣራለን ግን ለዚሁ መሠረት ጤናማ ሕዝብ ማግኘት ነውና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሙሉ ጤንነት ለሚሥሩና ለሚደክሙ ሐኪሞች በሥራቸውና በሐሳባቸውም ሁሉ እግዚአብሔር እንዲያከናውንላቸው መንግሥትም እንዲረዳቸው ተስፋ እናደርጋለን ።

በዳራገር የተደረገ አደጋ።

ለስሒት መኑ ይሌብዋ ብሎ ። ስሕተቱን ማን ያስተውላል ያለው ትልቁ ነቢይ ዳዊት ። መዝ ፲፱ ቁጥር ፲፪ ሁልጊዜ በያንዳንዱ በሰው ሲደርስ ይኖራል ።

አሁን በዚሁ ወራት በጥር ፪ ቀን አንድ ሰው ከአዲስ አበባ ብቻውን ሲሄድ ያበሻ ሰው ሁኖ ሳለ ከየት አገር የሆነ ያልታወቀ ከደጅ አዝማች ሀብተ ማርያም ግዛት ሲደርስ ከነቀምት ከተማ ሊገባ የ፫ት ሰዓት መንገድ ሲቀረው ከሚሔድበት አውራ መንገድ ሳይርቅ የሚለብሰው ጨርቅ የተመዘዘ አቡጀዲ ኖሮ ያንኑ በነጠላ ጠምዝዞ አንዱን ጫፍ በብሳና ዛፍ አስሮ አንዱን ጫፍ በገዛ አንገቱ ቋጥሮ በዚሁ ታንቆ ሞቶ ተንጠልጥሎ ተገኘ ። በነጋው ባላገሮች ወጥተው ቢአዩት ሱሪውንና እጀጠባቡን እንደለበሰ የመንገድ ገንባሌውን እንደ ጠመጠመ ተንጠልጥሎ ቢአዩት መንገደኛ ሰው መሆኑን አውቀው ለዳኛ አሳይተው አውርደው ቀበሩት ። በንደዚህ እስከ ዛሬ ከየት አገር ሰው የሆነ ሳይታወቅ ሙቶ ቀረ ።

ይህ ሁሉ ብቻውን ከመሄዱ የተነሳ ነው ። ለሰው ብቻውን ከመሆን ሁለት መሆን ይሻላል ። አንዱ ቢወድቅ ሁለተኛው ያነሳዋል አንዱ ቢታመም ሁለተኛው ያስታምመዋል ። አሁን ወንድሞቼ ሆይ ይህ ሰው ሁለተኛ ጓደኛ ቢኖረው ይህ የሚያሳዝን መከራ ባልወረደበትም ። በገዛ እጁ ታንቆ እንደሆን ተው ወንድሜ ብሎ ይጋብዘው ይከለክለው ይበጥስለት ያድነው ነበር

ወይም ሰው ገድሎ አንጠልጥሎት ቢሆን ቢችል ይዋጋለት ባይችል ይጮኽለት አለዚያ ከየት አገር ሰው እንደሆነ ያወራ ነበር ። አሁን ግን ብቻውን ከመሆኑ የተነሳ የወዴት አገር ሰው መሆኑ ሳይታወቅ ስሙ ወድሞ ቀረ ። እንዲያውም ለሰው ሶስት ሰው ሁኖ መሄድ ይገባል አንዱ ቢታመም አንዱ ከበሽተኛው ዘንድ ይቀራል ሶስተኛው እህል ውኃ ይገዛለት ይሄዳል ፡ ቢታጣ ሁለት መሆን ይሻላል ። አሁንም ወንድሞቼ ሆይ ከናንተ አዋቂ ሁኜ ልመክራችሁ አይደለሁም እለምናችሁአለሁ ብቻችሁን እንኳን እሩቅ መንገድ ከቅርብም ቢሆን ለብቻ እንዳትሆኑ በሁለትና በሶስት የተከረረ ገመድ ቶሎ አይበጠስም ።

ስለዚህ ንጉሥ ሰሎሞን በመክበቡ ይላል ፤ መክ ም ፬ ቍ ፱ ፲፫ አንድ ብቻ ከመሆን ሁለት መሆን ይሻላል ድካማቸው መልካም ዋጋ አለውና ቢወድቁም አንዱ ሁለተኛውን ያነሳዋል ወዮለት አንዱ ብቻውን በወደቀ ጊዜ ሁለተኛ የሚያነሳ የለውምና ሁለቱ ባንድ ቢተኙ ይሞቃቸዋል አንድ ብቻውን ግን እንዴት ይሞቀዋል አንዱም አንዱን ቢያሸንፍ ሁለቱ በፊቱ ይቆማሉ በሶስትም የተከረረ ፈትል ፈጥኖ አይበጠስም ።

ንባብ አስተማሪና ትርጉም ነጋሪ ወልደ ማርያም በወለጋ

ስለ ሥራ ነገር መጻጻት ።

በሀገራችን ስለ ምቀኝነት እየተባለ ብዙ ሰዎች ከደህና ሐሳብ ወደ ክፉ ሐሳብ ለመሄድ ይመኛሉ ። ለምን ማለት ከምቀኝነት የተነሳ ብዙህ ሰዎች ለሐገራችን መንግሥት ጥቅም እና በረከታለን መንግሥታችንን እናስከብራለን እያሉ በየተቀመጡበት ሥራ ላይ ይኸን ሲያወጡ ሲያወርዱ በዚህ መሐከል አንድ አቶ ምቀኝነትና አቶ ምንልሥራ የሚባሉ ያደሩበት ይነሱና ያንን ለሀገሩ መንግሥት ጥቅም የሚፈልገውን ሰው ያስቀይመዋል ። ያም ሰው እንግዲህ ይኽ ምቀኝነትና ወሸከታነት ያደረበት ሰው ከለ ምን ምስጋና አገኛለሁ ምንስ ደስ ይለኛል ምንስ ጥቅም ይሆነኛል ብሎ ክፉ ያስባል ። ነገር ግን ክፉም ብሠራ ደግም ብሠራ የሚያየኝ እግዚአብሔርና የመንግሥት እንጀራ አይደለም ይልና ለዚያ ለሰው ብዙ የክፋት መንገድ ይመክኝለታል ።

ነገር ግን ያም ሰው ለጊዜው እንደ ተመቀኘና እንደ ተናገረበት ጊዜ ብዙ ተስፋ ያገኘ ይመስለዋል ፡ ግን ሕያው እግዚአብሔር ነውን ሊያጠፋ ስለፈለገና ስለ ክፉ ምኞቱ ሕያው እግዚአብሔር እሱን ሊያጠፋው አይዘገይም ።

እበብ የልቡን አይቶ እግር ነሳው ፡ እንደሚባለው ሁሉ ይሆናል ።

ዓሣ ጕርጓሬ ዘንዶ ያወጣል የሰው ፈላጊ የራሱን ያጣል
እልክል ሞኖፓል ሠራተኛ ፋንታዬ ማንከልክሉ ።

ተረት ።

ለምሳሌ አንድ አንበሳና ዘጠኝ ጅብ ሁነው ወደ አደን ሄዱ ይባላል ፡ ሲያድኑ ሲያድኑም አሥራቸው አሥር ፍሪዳ አገኙ ነገር ግን ምንም ቢዋደዱ እየድርሻ መካፈል አይቀርምና እንካፈል ተባባሉ ያንጊዜ ከዘጠኞቹ አንዱ ብድግ ብሎ መቸም ፈሪ አይጸድቅምና ዘጠኙ ፍሪዳ ላቶ አንበሳ አንዲቷን ለዘጠኛችን ይሁን ብሎ ተናገረና እየድርሻቸው ተካፍለው ወደ ቤታቸው ሄዱ ፡ ዳሩ ግን ውጭ ለዋለ መጠየቅ አይቀርምና ከከተማ የዋለ የንደራ አበታቸው የዋሉበትን ምክንያት ቢጠይቃቸው ፤ ይሄው አንድ አንበሳና ዘጠኝ ጅብ ሁነን ወደ አደን ሄደን ዋልን ለሥራችንም አሥር ፍሪዳ አግኝተን አሁን እንደምታየን ለዘጠኛችን አንድ ፍሪዳ ተካፍለን መምጣታችን ነው አሉት ፡ እንዴት እንዴት ያለ ነገር ነው ዥሮ እንጅ የማይሰማው የለም ላንድ አንበሳ ዘጠኝ ለዘጠኝ ጅብ አንድ እንዴት ያለ መከፈል ነው ላሚቷን ንዱና አንዷን ሰጥቼ ዘጠኙን አስመልሳለሁ እያለ ወደ አንበሳ ቤት እየፎከረ ደረሰና እውነትም ያንበሳ ፊት ቢመለከተው እንኳንስ አንዲቷን ተቀብሎ ዘጠኙን ሊመልስና ከሥር ፍሪዳ አንዲት ስለጐደለችበት ለካ በሆዱ ውስጥ ጸጸት አድሮበት ኑሮ እሳት ለብሶ እሳት ጐርሶ ቈየውና እህ የመጣንበትን ጉዳይ ተናገር ብሎ ቢለው ዋ ጌታዬ ሆይ ያች የዘጠኝ ድርሻ ትሁን የተባለቸውን ፍሪዳ አሥረኛ አድርገው እንዲቀበሉኝ በልጆቼ ስም ሁኜ እለምንዎታለሁ ብሎ ጨርሶ አበረከተው ። አቶ አንበሳም ከብልህ ቀንሶ ከሞኝ ጨርሶ የሚኖር ብልጥ ነውና እግዚአብሔር ይስጥልኝ ብሎ በሳቅና በጨወታ ሸኘው ይባላል ብለው አንድ ትልቅ የአፍሪቃ ሰው አጫወቱኝ ስለ ጨዋታውን እገልጽላችኋለሁ ።

ተማኑ ሮምሃ ፡

ትንሽ የሥልጣኔ ምልክት ።

በሃገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ አንድ የሚያሳዝን ነገር ይገኛል ። ሽፍታ ጕስጓሽ ወይም በርባሪ ተብሎ ካገረ ገገር ተልኮ ወይም በደምብ ተሹም ከብዙ ሠራዊት ጋር ለመበርበር ይሄዳል የሄደበትንና የታዘዘበትን ይተውና ወደባላገር ቤት ይገባና ከሽፍታ የባሰ ይሆንና በዚህ በኩል ሽፍታ ገብቶባችኋልና አምጡት እያለ ሲያስጨንቃቸውና ሲያሸብራቸው የበዛ መብልና መጠጥም ሲመገብ ያድራል ። በማለዳውም ባላገሮችም በሃገራቸው ይህ በርባሪ እንዳይቀመጥና ሃገራቸውን እንዳይጐዳባቸው ሲሉ ገንዘብ ይይዙና ጌታዬ በሃገራችን ውስጥ ሽፍታ አልገባብንምና ወደሌላ ሒደህ ፈልግ ብለው የያዙትን ገንዘብ ጉቦ ያቀርቡለታል ። የገንዘቡን መብዛትና አለመብዛት ተመልክቶ ያነሡበት እንደሆነ ገና እበረብራለሁ ይላል ። ባላገሮችም ተጨንቀዋልና ይጨማምሩለታል ። ከዚህ በኋላ ተነስቶ ይሔድና ወደ አልደረሳቸው ይደርሳል ። ሽፍታውም ወዳለበት ሥፍራ የደረሰ እንደሆነ አስቀድሞ ባንድ መልክተኛ ወንድሜ ሆይ እኔና አንተ ደም እንዳንጋባ ወደሌላ ራቅ በልልኝ ብሎ ያስታውቀዋል ሽፍታውም እንዳስታወቀው ትእዛዙን ይፈጽምለታል ከዚህም በኋላ ይህ ሊበረብር የሔደ ሰው ወደሃገሩ ይመለስና ለጌታውም ቢሆን ወይም ለሌላ ጀብዱውን ሲነሰንስ እኔ ብሔድበት ወደዚህ አገር ሸሽቶ አመለጠኝ ብሎ ያማረ ወሬውን እያደበለቀ ይፈተፍታል ።

ከትንሽ ጊዜ በኋላም እንደዚሁ እንደ ለመደው ሽፍታው በዚህ በኩል ሔዷልና ልሒድ ብሎ ይጓዝና እየደጋገመ ባላገሮቹን ያጣጥማቸዋል ከሽፍታው ይልቅ በዚህ በርባሪ በሚበላቸው የቤት ጅብ የባሰ ጉዳትና መበላት በደህና ይበጣበጣሉ ።

በዚህ ነገር በትግሬ አውራጃ አምስት አገሮች በሁለት ነገር መጎዳታቸውን ተመልክተው ምክር አድርገውና ተማምለው ሽፍታ በውስጣቸው የገባ እንደሆነ አገሩ ሁሉ በጩኸት ይነሣና ያንን ከውስጣቸው የገባ የመንግሥት ጠላት አትልቀቁ ብለው የወንድነታቸውን ሥራ ያሳዩታል።በማህበራቸውም ውስጥ ኖሮ ወደሌላ ሥፍራ የሸፈተ እንደሆነ ከብትም ያለው እንደሆነ ከብቱን አርደው ይበሉበታል።እህልም እንዳለው እንደዚሁ ላስፈለጋቸው ነገር ያደርጉበታል የሸፈተውንም እየፈለጉ ያገኙት እንደሆነ አስረው ለዳኛ ያስረክባሉ በነዚህም በምስቱ አገር ውስጥ ይህ በርባሪ ምንም ቢሆን አይገባም ለመግባትም የማይደፍራቸው እንደዚሁ ሽፍታ የመረረ መድኃኒት እንዳያገኝ ይጠነቀቃል ።

እኚህም ማህበር የገቡ አገሮች እጅግ ሠራዊትና ብረት ያገኛሉ ይህንም አዲስ ደምብ በገዛ ራሳቸው ፈልስፈው ስላቆሙ የመንግሥትም ጠላት የመጣባቸው እንደሆነ ደማቸውን ለማፍሰስ የሃገርም ፍቅር ያደረባቸው እንደሆነ በዚህ ይመሰክራል ሃሳባቸው ሁሉ ወደ ሥልጣኔ ያቀና መስሎ ስለ ታየን እየሰፋና እየለማ እንዲሄድላቸው የቀሩትም ወንድሞቻቸውና ጎረቤቶቻቸው የሆኑት አገሮች የነሱን መንገድ ተከትለው እንዲጓዙ በብዙ እንመኛለን ።

ጥሩነህ ክ

ለቤተ ክርስቲያን ስለሚገባ ገንዘብ ።

ስለታቦት ስለት ገቢ ገንዘብ ታቦቱ የሚጠቀምበት ስለሌለውና ለመንግሥትም ዋና ጉዳት ስለሆነ ከዚህ ቀጥየ አስታውቃለሁ ። ለማናቸውም ኦርቶዶክሳውያን ቤተ ክርስቲያናት በለስለቱ ተስሎ ብር ሆነ ወርቅም ሆነ ይህንንም የመሰለች በየዓይነቱ በገባ ጊዜ መቸም ለየቤተ ክርስቲያኑ አንድ አንድ ገበዝ አለና ያ ገበዝ ያንን ለታቦት የገባ ስለት ተቀብሎ የቀን ገቢ ፪፻ ፫፻ም ቢገኝ ገንዘቡ ለዚያው ለቤተክርስቲያኑ ንዋየ ቅድሳት በማናቸውም ምክንያት ለቤተ መቅደስ ሳይበቃ ይቀርና እንደገና መንግሥት ያሳስባል ።ነገር ግን መንግሥት በማናቸውም ምክንያት ቢሰጥ የሚአስጎዳው ሆኖ አይደለም ይህ የታቦቱ ገንዘብ ቦታ ስላጣ ጉዳት ተባለ መንግሥትም ለታቦቱ ምንም ቢሆን ላመት የሚበቃውን መገበሯና ጧፍ ዕጣን በያመቱ ሳይሰጥ ይቀር አይመስለኝምና ለየታቦቱ ገቢ በየሥፍራው አንዳንድ ተቋጣሪ ጸሐፊ እየተደረገለት በክርኒ እየተሰራ በወር በወሩ በመንግሥት ቤት በተለየም በየታቦቱ አንድ አንድ ደብተር ተደርጎለት ባንድ ሹም እጅ ገቢ እየሆነ ዳኛም ተደርጎለት ተዚሁ ገቢ ገንዘብ በሚአስፈልገው ነገር ሁሉ ለጉደለው ወጪ እየሆነለት የቤተ ክርስቲያኑ ሹም ገበዝ መጥቶ ይህ ይህ ጐደለ ባለ ጊዜ ደብተሩን በስሙ አይቶ ያለውን ገንዘብም በዚያላይ ወጪ አስደርጎ ቢወስድ ደግ ይሆን ይመስለኛል ። ከቤተ ክርስቲያኑም ትርፍ ሆኖ ተቀማጭ የሆነውን ገንዘብ ቤተ መቅደሱ እንዳይራቆት የገቢውን ማነስና ብዛቱን አይቶ ብዙ የተጐዱ በቅጽረ ቤተ ክርስቲያኑን ወድቀው የሚለብሱት ይቅርን የሚበሉት ያጡ ብዙ ትምህርትና ሃይማኖት የሚፈልጉ የኦርቶዶክስ ልጆች ቢታሰብላቸውና ደግሞ በውጪ አገር ላሉ አስታዋሽ ለሌላቸው ቤተ ክርስቲያናት ሊተርፉቸው ይችል ይመስለኛል ።

በቀለ ።

» ስለ ተማሪ ቤት ለብርሃንና ሰላም ወዳጆች ትንሽ ማስታወሻ ።

ክቡራን የብርሃንና ሰላም ወዳጆች ሆይ ፤ ከዚህ ቀጥየ የምጽፍላችሁ ነገር ብርሃንና ሰላም አሁን ከራተኛው ዓመት ወዲህ በሚጽፈው ቃል በሶስተኛው ቁጥር በ፲፯ኛው ገጽ ጀምሮ የተመለከትሁትን ቃል ምንም በሙሉ አጋገፉ ለመሆንና ሀሳቤን ለመጻፍ ጊዜ ስላላገኘሁ ከብዙ በጥቂቱ ከረጅሙ በጭሩ ይህችን ትንሽ ማስታወሻ ጻፍኩ እንጂ ቃሉ ደስ ያሰኛል በማለት አይደለምና ነቀፌታ እንዳታደርጉብኝ ስል እመኛለሁ ። ፩ኛ ብርሃንና ሰላም በ፫ኛው ቁጥር በ፲፯ ገጽ በ፪ኛው አምድ ለእግዚአብሔርና ለጓደኞቻቸው ሊፈጽሙት የተገባቸውን አግባብ አንዳች አያስቡም በከሄዳቸው በሰው ሕይወትም መከከል እንደ ቸነፈር የሆኑ ሁከተኞች ሰዎች ሞልተዋል ይላል ። ፪ኛ በ፫ኛው ቁጥር በ፴፩ገጽ በመጀመሪያው አምድ ስለ ውሾች በተጻፈው ቃል በሠለጠኑቱ ሕዝብ ግን የሰብአዊነት ርኅራኄ ለሰው በቅቶ ለእንስሳም ተርፎላቸዋል ስለዚህ የእንስሳዎችን ሕይወት በሚገባው አኑዋኑዋር እንዲጠበቅላቸው ማህበሮች ቁመዋል ይላል። ግሩም ነው በሌሎች አገር ለእንስሶች ሳይቀር ርኅራኄ ሲገኝ በኛ ዘንድ እንዴት ለሰው ልጅ ይቅር ።

ይልቁንም በዚሁ ገጽ በ፪ኛው አምድ ዛሬም በውስጣችን ያሉ እንስሳዎች ማንላቸውም ቢሆኑ እንደ በለዓም አህያ አፋቸው ቢከፈትላቸው መጠን የሌለው ወቀሳቸውን ባስታወቁ ነበር ሲል እጅግ ያሳዝናል ። ፫ኛ በ፮ኛው ቁጥር በ፪ኛው አምድ ሰው ራሱን ብቻ ሊያስብ አይገባውም ሰው ከሆነ ረሰብአዊነትን ጭንቀት ሊሰማው ይገባዋል የሌላዎችን ሀዘን እስኪረሳ ድረስ በራሱ ደስታ ልቡ ሊደነዝዝ አይገባውም ብሎ እስከ መጨረሻው ቃል ድረስ የጻፈው በጣም ያሳዝናል ።

እውነት ነው ስንኳን ለሰው በአርአያ ሥላሴ ለተፈጠረው ለአዳም ልጅ ለገዛ ወንድማችንና ለእንስሶችስ መራራት እንዴት ይቅር ?

ነገር ግን ሕዝባችን እስካሁን ድረስ ይህንን የርህራኄ ሥራ ሳይፈጽም ለምን ዘገየ ? ቢባል የተማሪ ቤት ባለማግኘቱና በትምሕርት ባለመጐልመሱ ነው ማለትን ማንም ይዘነጋው አይመስለኝም ። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር በፈቃዱ መርጦ ለሕዝብ ጠባቂና መሪ ያደረጋቸው ጌቶቻችን መጀመሯ ግርማዊ አጼ ምኒልክ ሁለተኛም ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ይህን ስለ ተረዱት የተማሪ ቤት በብዙ ደክመው አቁመው ከውስጡ አያል ሰዎች ተገኝተዋል ወደፊትም ብዙ ያገኛሉ ።

የሀገራችን ታላላቆች ሰዎችና መኳንንቶች ግን ምነው የጌቶቻቸውን ፍለጋ ተከትለው ተማሪ ቤት ያለማቆማቸው ? ገንዘብ አጥተው ነው እንዳንል እንኳን ላንድ ተማሪ ቤት ማቆሚያና ብዙም ለማቆም እንደሚችሉ አንጠራጠርም ። ዳሩ ግን ጌታ በቅዱስ ወንጌሉ የተናገረውን ቃል ይልቁንም በዮሐንስ ወንጌል በ፲፫ኛውና በ፲፬ኛኛው ቁጥር በ፲፫ ምዕራፍ እላንተ ትሉኛላችሁ መምሕር ጌታም መልካምም ትላላችሁ እኔ እንዲሁ

ነኝና ። እንኪያስ እኔ ጌታ መምሕር ስሆን እግራችሁን ካፀብሁ እላንትም ደግሞ ይገባችኋል የባልንጀሮቻችሁን እግር ታፅቡ ዘንድ እርሱ በርሳችሁ ። ሁሉን እንዳልጽፈው ወንጌል ያላነበበ የብርሃን ወገን አይገኝም በማለት ትቼዋለሁና መላውን ለመረዳት የፈለገ አንባቢ የዮሐንስ ወንጌል ም፲፫ ቁ፫ እስከ ፲፯ ይመልከት። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከወዳጆቹ መካከል እሱን የማይመስል አንድ ሰው (ይሁዳን) ብቻ አገኘ እንጂ የቀሩት ወዳጆቹ የጌታቸውን ፍለጋ ተከትለው አንገታቸውን ለስለት ጀርበቸውን ለግርፋት ሰጥተዋል ፡

አሁን ግን በርኅራኄ ሥራ የጌታቸውን ፍለጋ ለመከተል ክቡር ራስ ናደው የተማሪ ቤትን ለማቆም አስበዋል ማለትን ብርሃንና ሰላም የምስራቹን ስላስታወቀን መላው የኢትዮጵያ ተወላጆች በደስታ ተሳክረን በተስፋ እንጠብቃለን፡ እስኪ እንግዴህ ከኢትዮጵያ መኳንንቶች ጌቶች ሁሉ አንድ ሰው ብቻ የጌታውን ፍለጋ የተከተለ በመገኘቱ አያሳዝንምን የተጠሩ ብዙ ናቸው የተመረጡ ግን ጥቂት ያለው የወንጌሉ ቃል የደረሰ ይመስላል ።

አሁን በቅርብ ጊዜ እንኳ የኢትዮጵያ ልጆች ላገራቸው፣ ተቆርቍረው ፍቅርና አገልግሎት ሠረቀ ብርሃን የተባሉ ሁለት ማህበሮች በልዑል መሪነት ቆመው ወንድሞቻቸውን የኢትዮጵያን ልጆች ከባርነት ወደ ነፃነት ካለ ማወቅ ወደ ማወቅ እናደርሳለን ብለው በብዙ ድካም ይታገላሉ ።ለወደፊቱም እንዳች መሰናክል ሳያገኛቸው ሥራቸው እየሰፋ እንዲሄድ እግዚአብሔር ይርዳቸው።

የኢትዮጵያ ኃያላን ጌቶች እጅግ ብዙ አይደሉምን ምነው ዝም አሉ መንግሥት በከበረ ሥፍራ ያስቀመጣቸውና በገንዘብ ያከበራቸው ታላላቆች ጌቶች ለተማሪ ቤት አለማሰባቸውና አለመርዳታቸው ምክንያቱ ምን ይሆን? እንጃ ያጠራቀምኩት ገንዘብ ለራሴና ለልጄ ይበቃል በማለት ለድሆች እንዳይደርሳቸው ለገንዘብ ይሆን ይህን እንዳንል ደግሞ አሁን በኛው እድሜ እንኳ እጅግ ባለገንዘብ የሆኑ ትልልቆች ሰዎች ለልጆቻቸው ብዙ ገንዘብ ትተው ሂደው ነበር ልጆቻቸው ግን እንኳን እንዳባታቸው ሊሆኑ ከስስት አንድ እንኳ እንዳልወጣቸው ታይቷል ይህ ሁሉ መሆኑ ለኔ እንደሚመስለኝ ለትምሕርት ባለመማርና ለድሀ ባለማዘን ለኔ ብቻ ይመች በማለት ይመስላል ።

እነዚያም ትልልቆቹ ያጠራቀሙት ገንዘብ ወራሹ ብዙ ሆኑ እንጂ ለልጆች ብቻ አልቀረም ። አሁንም ክቡራን ጌቶችና መኳንንቶች ሆይ ደሀ ያለ እናንተ አቅም የለውም ። ደግሞ ልጅ ማለት በሥጋ የወለዳችሁት ብቻ አይደለም ። እንግዲያስ ያላስተማሩት ልጅ ስም አያስጠራም ። ያልተማረና ሰነፍ ልጅ ተክቶ ከመሄድ ድንጋይ ወይም ዛፍ መትከል ይበልጠዋል ። ከሰው ድንጋይና ዛፍ ይበልጣል ለማለት አይደለም ። ያልተማረና ሰነፍ ልጅ ያባቱን ስም ያስወቅሳል እንጂ አያስመሰግንም በማለት ነው ፡ ኢትዮጵያ የሆነው ሁሉ ልጃችሁ ነውና ተማሪ ቤትን ለማቆምና ይህንም ለመርዳት ቸል አትበሉ ። ገንዘብ አላፊ ነውና የማያልፍ ስም ግዙ ስል በሙሉ ያኢትዮጵያ ወጣቶች ስም ሆኜ ባነስተኛይቱ እውቀቴ ሳስታውስ ይቅርታችሁን ጭምር እለምናለሁ ።

ተስፋዬ ካሣ ።

ግሩም ነገር ።

ባንድ እርሻ ውስጥ ፴፯ ገበሬዎች አንዱ ሳይበልጥ እርሻቸውን በትክክል ሲያርሱ ውለው በምሳ መብያው ጊዜ ስድስቱ ገበሬዎች ፪፻፺፰ እንጀራ ሲበሉ፣ ፴፩ ገበሬዎች ፫፻፸፬ እንጀራ ሲበሉ አየሁ ብሎ አንድ ሰው አጫወተኝ በሥራ ሳይበልጡ ፮ቱ ሰዎች ከ፴፩ዱ ሰዎች በልጠው መብላታቸው ምክንያቱ ምን ይሆን ? ስል ለብርሃንና ሰላም አስታውቃለሁ ። ሰሎሞን የ።

የፈረስ እሽቅድድም ።

የካቲት ፳፱ ቀን የፈረስ እሽቅድድም በጃን ሜዳ እንደሚደረግ ተወርቶ ነበረና በዚሁ ቀን ከጥዋቱ በሶስት ሰዓት ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በክቡራን መኳንንትና በሠራዊት ታጅበው እሽቅድድሙን ለማየት አምሮ በተሰናዳላቸው ስፍራ ሒደው ተቀመጡ ። ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ወደ እሽቅድድሙ ቦታ ሲሔዱ በየመንገዱ ተሰልፎ የቆየ ወታደር ሁሉ ጥሩምባ እያስነፋ የተገባ ሰላምታውን ይሰጥ ነበር ።

፩ኛ እሽቅድድም ።

የሜዳው ርዝመት ስምንት መቶ ሜትር ።

ፊተኛ ቀዳሚ የክቡር ደጃች ደስታ ዳምጠው ፈረስ ሆነና ሠላሳ አምስት ብር ተቀበለ ።

ሁለተኛ ቀዳሚ የሙሴ ጋሴብ ፈረስ ሆነና አሥራ አምስት ብር ተቀበለ ።

ሶስተኛ ቀዳሚ የልዑል አልጋ ወራሽ ፈረስ ሆነና አሥር ብር ተቀበለ ።

፪ኛ እሽቅድድም ።

የሜዳው ርዝመት ሺሁለት መቶ ሜትር ።

ፊተኛ ቀዳሚ የማርኪስ ዴሴይ ሞንቴቤ ያርደ ፈረስ ሆነና አርባ ብር ተቀበለ ።

ሁለተኛ ቀዳሚ የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ሆነና ሀያ ብር ተቀበለ ።

፫ኛ እሽቅድድም ።

የሜዳው ርዝመት ሺአምስት መቶ ሜትር ።

ፊተኛ ቀዳሚ የኢጣሊያን ሚንስቴር የሙሴ ኮራ ፈረስ ሆነና ትንሽ ዋንጫና አርባ ብር ተቀበለ ።

፬ኛ እሽቅድድም ።

የሜዳው እርዝመት ሺሁለት መቶ ሜትር ።

ፊተኛ ቀዳሚ የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ሆነ።

፭ኛ እሽቅድድም ።

የሜዳው ርዝመት ሺ አምስት መቶ ሜትር ።

ፊተኛ ቀዳሚ የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፈረስ ሆነና የሀሬንግቶን ዋንጫና አርባ ብር ተቀበለ ።

ሁለተኛ ቀዳሚ የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ፈረስ ሆነና ሀያ አምስት ብር ተቀበለ ።

፫ኛ እሽቅድድም ።

የሜዳው ርዝመት ሁለት ሺ አምስት መቶ ሜትር ።

ፊተኛ ቀዳሚ የማርኪስ ዴሴይ ሞንቴ ቤያርድ ፈረስ ሆንና አምሳ ብር ተቀበለ ።

ሁለተኛ ቀዳሚ የመዳም ቤንቲንግ ፈረስ ሆንና ሠላሳ ብር ተቀበለ ።

፬ኛ እሽቅድድም ።

የሜዳው ርዝመት ሁለት ሺ ሜትር ።

ፊተኛ ቀዳሚ የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ፈረስ ሆንና የሙሐመድ ዓሊ ዋንጫና አምሳ ብር ተቀበለ ።

ሁለተኛ ቀዳሚ የሙሴ ክሮሴ ፈረስ ሆንና ሰላሳ ብር ተቀበለ።

ሶስተኛ ቀዳሚ የሙሴ ኤያሰን ሐነር ፈረስ ሆንና ሀያ ብር ተቀበለ ።

እሽቅድድሙ ከተፈጸመ በኋላ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፣ማረ አጀብ ወደ ቤተ መንግሥት ተመለሱ ወዲያውም ዝናብ ዘነበ ።

ስለ አገር ጥቅም ማሻሻል።

ለሕዝብ የሚሆን ጥቅም ደጃዝማች መኰንን ደምሰው በግዛታቸው ከሶስት ዓመት ወዲህ ቡን አትክልት መትከል ሥራ ማሠራት ጀምረዋል። ሕዝቡና ባላገሮች የእርሳቸውን እርምጃ እያዩ መልካም የቀና መንገድ ይዘዋል።ደግሞ ርስት ለሌለው የዱር አራዊትን ርስታቸውን ነቅለው ለሰው ልጆች ርስት አድርገው እያካፈሉ እስከ ሶስት ዓመት ድረስ ግብር አይንካህ ከሶስት ዓመት ወዲያ ግን እስከ አምስት ዓመት ካገኘኸው እኩል ግብር ትገብራለህ።ነገር ግን ከአምስት ዓመት ወዲያ በስንፍናህ ቀርቶብሃልና እንደ ጕረቤትህ ትሆናለህ ብለው ደምብ ሰጥተዋል ።

ይኸውም የሰጡት ደምብ ለሕዝብና ለባላባቶች ተስማምቶ አንድ ያልተያዘ ጫካ አይገኝም ። ባለ አገሩም ሥልጣኔ መንገዳቸውን እየተመለከተ መልካም አካሄድ ይዟል እርሳቸውም ለራሳቸው አግበልታ ጫሮ ገተማ ጉራንጉር ፋኖ ሳቃ የሚባሉትን ጠፍ ጫካ መንጥረው ብዙ ለቁጥር የሚያስቸግር ቡና አስተክለዋል ። ይኸውም የተተከለው ቡን ባሁኑ ዓመት ፍሬ ግብሩን ሊሰጥ የምስራች ይላል ይባላል ።

ደግሞ ለሳቸው ቡን የመስኖው ውሀ ቢያንሳቸው አሥራ አምስት ጋሻ መሬት አልፈው ታላቅ ውሀ አምጥተው ከ፪ ሜትር በላይ ስልሳ ሜትር የሚሆን ገደሉን እንደ አክርማ አሰንጥቀው ታላቁን ውሀ በገንዳ አሸጋግረው ከትንሽዋ ምንጭ ከሳቃ አገናኝተው አሥር ጋሻ መሬት የሚሆን አምስት መቶ ሺ እግር አጽድቀው ለመለቀም ደርሶአል ባላገሩም እንደ መጠኑ ለህዝቡም መቋቋሚያ ላጣ ደሀ መሬት የርሳቸው ሆኖ በሬ ለመሬት ሳም ለወተት የሚያረባው በግና ፍየል ሰጥተው በገዛ አሳቡ እየሠራ ከድኅነት አውጥተው ወደ ብልጽግና ሊያደርሱት ተቃርቧል። የቡን ችግኝ ለሚፈልጉ ሁሉ ቢኖር ከራሳቸው ቢታጣ ገንዘብ እየሰጡ እየገዙ ያስተክሉታል እርሳቸውም ለሥራ የተዘጋጁ የመሆናቸው ምልክት ከእጃቸው አንክሴ ተክል የሚተከልበት በተለየ ደምበኛ ሁኖ ጋሻ ጃግሬው ይይዛል ጾማ ለመቈፈፈር መጥረቢያ ጫካውን ለመቁረጫ ማጭድም ጥቃቅኑን ጫካዎች መቁረጫ እንዲያዝ ደምብተዋል።ሰነፎች ለሥራ የማይተጉ ከጠገባቸው ለመቈም አይችሉም ለመኳንንቱና ለባላገሩ ርስትም ላለው ቡን ትክሉ እያሉ ስለ አዘዙ መልካም ጥቅም መሆኑን አውቆ ደስ እያለው ይሠራል። አሁን ለጊዜው ቃላቸውን ተቀብሎ አትክልት ተክሎ የሠለጠነ ከላይ ከዋማ በመለስ ከታች ከዲዲሳ በላይ ሌቃ በሞላው የሰባቱ ቈሮ አገር ሠልጥኖአል።

ደግሞም ነጋዴ ባላገር ወታደር የሆንህ ሁሉ መሬት ግዛ አትክልት ትከል ዋጋውን በልክ አድርጌልሃለሁ ያጣህም ገዝተህ በኋላ ትከፍላለህ ብለው ደምብ ሰጥተዋል ። ባላባቶችና ባላገሮች መኳንንቶችና ወታደሮች ነጋዶች ጭምር ተስማምተው እንደዚህ ያለ ጥቅም አዋቂ ዳኛ የሰጠኸን እግዚአብሔር ተመስገን እድሜም ለመንግሥታችን ይስጥልን እያሉ ይመርቃሉ። በሀገራቸውም ሁከት ነገር የለም ማማለጃ መቀበልም በሳቸው ዘንድ የተጠላ ነው። እንደዚህ ያለው ሐሳብ በልቡናቸው አድሮ ድሀውን ከእንቅልፉ ስለ አነቁት ኢትዮጵያን ለሚወዱ ብርሃንና ሰላምን ለሚያነቡ ወንድሞቼ ጻፍሁላችሁ። ለሌሎችም መኳንንቶች እንደዚህ ብታደርጉ የተወደዳችሁና የተመሰገናችሁ ትሆናላችሁ

ይኸንንም መጻፌ ባይኔ ያየሁትን ከባላገሩም የሰማሁትን ነው ። የኢትዮጵያ መንግሥት አገልጋይ ፊ ፊ ወ ።

ያንድ ባለጠጋ ውል ከሞት ጋር ።

አንድ ባለጠጋ ከሞት ጋራ ወዳጅ ሆነ። ሞት መጣሁ ብሎ ሳይነግረው እንዳይመጣበት ተማማሉ ። መጣሁ ባለው ጊዜ ተዘጋጅቶ ንስሐ ገብቶ እንዲቆይ አስቦ ነው።እንዲህ ሆነው ሳሉ ሞት አንዲት ታናሽ ግልገል ገደለ ። ባለጠጋው አላሰበም ዝም አለ ። ከዚህ በኋላ አንዳንድ እያለ ከብቱን ሁሉ ፈጀበት ፤ ከዚህ በኋላም ቤተ ሰቦቹን ልጆቹን በመጨረሻም ሚስቱን ገደለ ፤ ባለጠጋው አላሰበም ፤ በኋላ ወደርሱ መጣ ምነው መሐላ አፈረስህ አለው ፤ ሞትም መሐላ አላፈረስሁም አለ መሐላችን ሳትነግረኝ እንዳትመጣ አልነበረምን አለው ። እርሱም አለው ፣ እኔስ በመጀመርያ በታናሽ ግልገል ነገርሁ ከዚያ በኋላ ዕለት ዕለት እነግራለሁ ። አንት የዝሆን ገሮ ይስጠኝ ብለህ እምቢ ብትል እኔ ምን ልበል ብሎ ይዞ ሔደ ይባላል ።

(ከሉድዊግ ማህለር የተሰበሰበ ታሪክ)

ጥንቃቄ ከማጣት የሚደርስ ጉዳት ።

የካቲት ፳ ቀን ከአዋሽ ወደ አዲስ አበባ በሚያልፈው ደንበኛ ባቡር ተሳፍሮ የነበረ የእንግሊዝ ዜጋ የሆነ አንድ ሱማሌ ፫፻፳፱ ኪሎ ሜትር ላይ ሲደርስ ባቡሩ ሳይቆም ዘልየ አወርዳለሁ ሲል ወድቆ መሬት መትቶት ሞተ ።

እንደዚህ የመሰለ አደጋ እንዳይደርስባችሁ በባቡር የምትሳፈሩ ሰዎች ሁሉ በምትሳፈሩበት ጊዜ የባቡሩን ማስጠንቀቂያ ደንብ ልትጠብቁና ራሳችሁን ልትጠብቁ ብርሃንና ሰላም ያሳስባችኋል ።

ማስታወቂያ ።

ሺብሮሌ አቶሞቢል በኢትዮጵያ ወኪል ።
ሖ ሜ ዜርቦስ ኩምፓንያ ።



Automobiles CHEVROLET
H. M. ZERVOS & C^ie
REPRESENTANTS
BAS PRIX HAUTE QUALITE

ማስታወቂያ

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚገኙ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
ደግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፫ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር	፬ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ብር
ኀሐ ጽባሕ	፫ብር
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፪መ
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ብር
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ብር

ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትርሚጓው	፪ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ተኩል
የቁጥር ትምርት	፩ብር
ያማሪኛ ሰዋስው	፩ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	አላድ
ወዳጄ ልቤ	፫ሩብ
አጭር የዓለም ታሪክ	አላድ
ያማሪኛ ፊደል	ሩብ
አሳብና ምኞት	ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት	ሩብ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር	፪መ
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ	ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ	፩ሩብ

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲ ብር ፲ መ
የሲዳሞ ቡና	፩	፲ ብር ተሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፫ ብር
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፩ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፪፺፬ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፯ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ከረጂ	፳ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ከረጂ	፲፱ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ከረጂ	፪፻፫ ብር
፡፡ ባለሰይጣን	፡፡	፪፻፳ ብር
፡፡ ባለ ድመት ፡፡		፪፻፪ ብር
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፪፻፹፪ ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፪፻፪ ብር
ባለ አንበሳ	፡፡	፪፺፫ ብር
ስካር	፩ ጁኒያ	፳፯ ብርተኩል
ቻይ	፩ ነጥር	፩ ብር

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ ከ፳፭ ሳንቲ
አንድ ብር	ሊሬ ፱ ከ፭ ሳንቲም
ባአንድ ጊኒ	፲ ብር ከ፲፭
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፫ ብር ተኩል

COGNAC S. E&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ማስታወቂያ

መጽሐፍና ደብተር የሚያስጠርዝ ሰው በርካሽ ዋጋ በል ፀል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ይጠረዝለታል ።

ያረጀ መጽሐፍና መዝገብ ማሳደስ ለፈለገ ሰው በርካሽ ዋጋ እንደ አዲስ አድርገን እንጠርዝ ለታለን ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የሚባል ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

RUGBY

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶመቢል በተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፡ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፡ ቤንዚን በያይነቱ ቶበት ዘወትር ይገኛል



ሰላም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ማመልከቻ ።

በብርሃንና ሰላም ውስጥ ማስታወቂያ ማሳተም የሚፈልጉ ነጋዴዎች እስከ ፈለጉት ጊዜ ድረስ ባማርኛም ሆነ በፈረንጅ ቋንቋ በርካሽ ዋጋ እንደምናትምላቸው እናስታውቃቸዋለን

የሚከራይ ።

A LOUER

ጉድይር ግዙ





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው ። በሌላጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ፤ ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አራተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፲፪
4 me ANNÉE № 12

ሐሙስ መጋቢት ፲፫ ቀን ፲፱፻፳ ዓ ም ።
JEUDI 22 MARS 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d'Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ትንሽ ምክር ለሴቶች።

በሃገራችን ውስጥ ብንመለከት የሴቱ ሥራ ፈትነት ከወንዱ ይልቅ መቶ እጅ የበዛ መስሎ ይታየናል መቶ እጅ ማንሱም ከስንፍና መብዛትና የቡን መጠጥ በየመንደሩ በማሳደድና አንዱ ያንዱን ሐሜት በተማለ መላስ ስታወራርድ አንዱም ይህንኑ የመሳሰለ ስም ያለመልኩ መልክ ስትቀባና ስታሽሟጥጥ በመዋሏ ብዙ ሥራ ይተጓጐልባታል። ባሏ ሌት ተቀን ዋቶ ባመጣው ገንዘብ ይህንን ዓይነት ግዛልኝ የዚህ ዓይነት አምሮኛልና እያለች ያስፈለጋትን ሁሉ ታስገዛና ማለፊያ የሆነ ከፍጫማ)ትረገጥና መልከም የሆነ ልብስ ትለብስና እንደዜሁ በብዙ ዓይነት ጌጥ እየተረቀቀች በባቡር መንገድ ውስጥ ወዲያና ወዲህ ስትሽቀረቀር ትውላለች።በመሸባትም ጊዜ ወደ ቤቷ ታስባለችና ገረዶችም እንዳሉ ትእዛዝ አልሰጠቻቸውምና እንጀራና ወጥ ሳይሰናዱ ይቈያሉ ፡ እሷም ወየው በሞትኩት ትልና ለገረዶቿ ትእዛዝ ትሰጣለች ገረዶችም እንደ ሌላት እሷ ራሷ ጐንበስ ቀና እያለች ሥራውን ላድርገው ብትል ጊዜው ተላልፏልና አይሳካላትም።ባሏም ከሥራው በተመለሰ ጊዜ እንደ አንድ ጋራ ተቆልላ በመከረፍ ፊቷን አንጠርብባ ትቆየዋለች ጥያቄም ቢያደርግላት ያልሆነ ነገር ትመልስለታለች ። እርሱም ምን ሆና ይሆን ብሎ እስከ ጦም ማደር ይደርሳል ፡ አንድ አንዶችም ከነዚህ ይልቅ በክብረት ያሉ ሴቶች የደነደነች በቅሎ ያስጭኑና የበዛ ገረድና ብረት ያስከትሉና እንደማለፊያ መከዳ በኮርቻው ላይ ዘርፈጥ ይሉና እንደታመመ ሰው በሁለት ደጋፊ ይመረኰዙና ፊታቸውም እንዳይታይ ይጀቦነቦኑና የጐርፍ ውሃ መስለው ሲጅበለበሉ ያስገርማሉ።ይልቁንም ይህ ሁሉ ሥራፈት እህል ቀምሶ በማደሩ ያስደንቃል

ይህን ሁሉ መጻፋችን ለስድብ አይምሰላችሁ ለጥቅማችሁ ነው እንጂ ይህን ሁሉ ማድረጋችሁ ትንሽ ትምሕርት ባትማሩና እንደዚህ ጋዜጣ ለማንበብ ባትሞክሩ ነው እንጂ ይህ ልምዳችሁ ብትመለከቱት ስንኳንስ ልታደርጉት ላለፈውም ይቆጫችሁ ነበር ። ማለት በኤሮፕ የሚደረገውን ብትሰሙ ባሏ ባንድ ሥራ ተቀጥሮ ሲያገለግል ወይም የንግድ ነገር ቢያደርግና እንደዚህ ሁኖ በተሰጠው ዓይነት ሲለፋ እርሷ ደግሞ እንደዚሁ በውጪ ባንድ ኩምፓኒያ ቤት በጽሕፈት በሰዓት በሽማ ሥራ በፖስታ ቤት ቴሌግራፊስትና ቴሌፎኒኀት በምታወቀው ዓይነት ሥራ ሁሉ እየለፋችና እየደከመች ባሏ ባንድ ፊት እርሷም እርሱም እንደዚሁ ገቢ እያገቡ ሃብታቸው ሳያቋርጥ ይኖራል ። ቤተሰቦቻቸውም እጅግ ቢበዙ ከሁለትና ከሶስት አይበልጡም ፡እናንተ ግን ባላችሁ ያመጣውን እያከሰራችሁ ገንዘቡም ሲያልቅ ወደ ሌላ ትዘምቱና ብታገኙ አገኛችሁ ባታገኙም ኀመን ልመና ትሰዳላችሁ ። ትምህርትና ማስተዋል ብታገኙ ብልሆች በሠሩት ሻሽ ብንጉነበነብና ባነጠሩት ሽቶ ብንሸሞነሞን እንደዚህ በመሰለ ሁሉ ብንረቀቅ ምን ያደርግልናል ብላችሁ ትነቅፉት ነበር።እኛ ጌጥ ይቅር ብለን አይደለም ይህንን ሁሉ የዘበዘብን እንደሌሎቹ እየሠራችሁና እየለፋችሁ ብታጌጡ ያምርላችኋል አሁን ግን በማለፊያ ቀሚስና ኩታ ላይ ኬሻ የመደረብ ያህል መስሎ ታይቶብችኋልና እንድታውቁት ምክር ልናከፍላችሁ ስለማለት ነው ። አሁንም ላለፈ ነገር በመቆጨት የፈሰሰ ወሀ እመልሳለሁ የማለት ነውና ላለፈው ሳትነደዱ ለወደፊት ይህንን አሮጌ ልምዳችሁን ተወት አድርጋችሁ እንደ ኤሮፕ ሴቶች ሃፍረት የሚባለውን አታላይ አስወግዳችሁ የሚአስፈልገውን ሥራ ሁሉ ማጣደፍ ነው።አሽከርስ ለናንተ ከንድ የበለጠ ምን ያስፈልጋችኋል እናንተ መሬ ካልሆናችሁ ልጆቻችሁስ ይህንን ልምድ እንደምን ይተውታል ብላችሁ ትጠረጥራላችሁ እንደዚሁ እያደረጋችሁ እናታችን ኢትዮጵያን ደስ ብታሰኙዋት ምርቃቷንና በረከትን ልትወስዱ በተገባችሁ ነበር እንደዚሁ ልምዳችን ይሻለናል ብትሉ አሁን የኢትዮጵያ ልጆች የሆንን እንደኤሮፖች ለመሆን ወይ

ሥልጣኔ ለመጓዝ ጀምረናልና በሥልጥንና ውስጥ ያሉት ወንዶችም ቢሆኑ ሴቶችም እነዚህ ወደ ሥልጣኔ የሚጓዙት እንደዚህ ሆነው ነወይ እያሉ እንዳያንጓጥጧችሁና እንዳይስቁባችሁ የባሰውንም እንዳታፍሩ ዛሬ ብትጠነቀቁበት የሚሻል ይመስለኛልና ባጭር ታጥቃችሁ ወደ ሥራው ቀደም ቀደም ማለትና መላቅጡን የማይታወቀውን ልምዳችሁን እንድትተውት ስል ደግሜ ደጋግሜ አስታውሳችኋለሁኝ ።

ጥሩነህ ከ ።

ስካር የሚያጸይፍና የሚያስፈራ ነው ።

፲፱፻፳ ዓመተ ምሕረት የካቲት ፳፬ ቀን ከኩል ቀን በኋላ በ፲፩ ሰዓት የ፩ሰው ስካር ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው፤አንድ ሰው ሰክሮ በመንገድ እየለፈለፈ ሲሄድ አንድ ልጅ መጽሐፍ ይዞ ሲሔድ ተገናኙ ። ያየሰከረ ሰው በመንገድ እየለፈለፈ ሲሔድ አይቶ ባካሔዱ ተገረመና ብዙ አዘነ፣ በኃዘኑ ቃል ሰማህ ወንድሜ አለው የሰከረውም ሰው ልብ ገዝቶ አቤት አቤት አለው ያም ልጅ አንድ ጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል ስማና ያለ ገንዘብ ጠጅ እሰጥሀለሁ አለው ። ያም የሰከረ ሰው በደንጊያ ቁጭ ብሎ ያደምጥ ነበረ ያም ልጅ የሚከተለውን ቃል ከመጽሐፍ ምሳሌ ከምዕራፍ ፳፫ ከቁጥር ፳፱ አነበበና እንደዚህ ብሎ ሰበከለት ። እንግዲህ ለነፍስህና ለሥጋህ የሚመቸውን ወደገርነት ሊጐትትህ የፈለገውን ሞኝነትን ተቃወመው በአምላክ ኃይልም ድል ንሣ የአምላክ ቃል በሰካሮች ላይ የሚፈርደውፍርድ አጭርና የተቆረጠ ነው « ሰካሮች የእግዚአብሔርን መንግሥትአይወርሱም » የአምላክ ቃል ስለ ኃጢአታችንና ስለ ስህተታችን ክፉምኞታችንን እየገሠጸ የምናሸንፍበት መንፈሳዊ ኃይል አሳይቶ ድል አድራጎች ያደርገናል ።

ይኸ ያነበብኩልህ መጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ስፍራ ስለ ስካር ያስጠነቅቀናል ። ስካር ብዙ ዓይነት ኃጢአት ያመጣል ሰው ሲሰክር የሚአደርገውን አያውቅምና ለመላ ህይወቱ በሚአሳፍረው ኃጢአት ይወድቃል ። ስለዚህ ቅዱስ ጳውሎስ መንፈስ ይሞላባችሁ እንጂ ጥፋት ባለበት በጸጅ አትስከሩ ይላል መድኃኒታችን ደግሞ ያ ቀን ድንገት እንዳይደርስባችሁ ልባችሁ በስካር እንዳይደነድን ተጠንቀቁ ብሎ ይመክረናል ። በዘፈንና በስካር አይደለም በቅን ነገር በቅኑም እንሂድ በሮሜ መልክቱ በምዕራፍ ፲፫ በቁጥር ፲፫ ተመልከት ።

ስካር ጤና ያጠፋል ሰውነትን ያደክማል በመጠጥ ለሚሰክር በቤቱ መርገም ይወርድበታል ። ሆዳምና ሰክር ችጋረኛ ይሆናል የአንቅልፍም ብዛት ጨርቅ ያለብሳል ። ሰው ሲሰክር በሆዱ ውስጥ ያለ አራዊት ይፈታል ወጥቶ ሌሎቹን ይጐዳል እስከ ዕለተ ሞቱ የሚጸጸትበትን ኃጢአት ያደርጋል ። ሰማህ ወንድሜ ለሰውነትህ የሚጠቅምህና የሚመችህን አሳብህ አስተውል ሕይወትህ ከአምላክ የተሰጠኸው ክቡር ስጦታ ነው ። እለ ልክ በመብላትና በመጠጣት ገላህን አትጕዳው አልጠግብ ባይ ሲተፋ ያድራል እንደ ሚሉት ተረት አትሁን እንስሶች እንኳን በልተው ጠጥተው ሲጠግቡ ይተኛሉ ከጠገቡ በላይ የሚበሉና የሚጠጡ ሰዎች ግን አሉ ። ከሰካራም ሰው አእምሮ የሌላቸው እንስሶች ይበልጣሉ ። ማስተዋል የተሰጠው ሰው ሳይጠማ ያለ ልክ እየጠጣ የሚሰክር ስለ ምንድነው ቢሉ ከሰከረ በኋላ እንደ ሞኝ ነው የሚሆን ስካር ክብረቱ የጠፋበትና የተዋረደ ሰው ነው እንደ ዕብድ በመንገድ እየለፈለፈ የሕፃናት መሳቂያ ይሆናል የማይረባ ንግግር እየተናገረ ከአነጋገሩና ከሥራው ዕብድነቱ ለሁሉ ይገለጣል ። ደህና ሁኖ ጭምት የነበረ ሰው ሰክሮ ያለ ኃሳብ እየለፈለፈ ለዚህ የሕፃናት መሳቂያ ይሆናል ። ባገራችን በኢትዮጵያ ስለ ትምህርት አብነት እያሉ አንድ አንዶች አብሾ የቀመሱ ሰዎች ትንሽ በጠጡ ጊዜ ምድርና ሰማይ ይዞርባቸዋል ፡ ለሕዝቡ ሁሉ የተመረጡ ሊአስተምሩና ምሳሌ ሊአሳዩ የተመረጡ አንድ አንድ ቀሳውስቶችና መነኲሴት መስቀል ይዘው ያለ አእምሮ እየለፈለፉ በመንገድ እየተንገደገዱ ሲሔዱ እጅግ የሚአሳዝን ነው ሞኝ ይስቅባቸዋል አስተዋይ ግን ያለቅስላቸዋል ።

ኢሳይያስ በዘመኑ እንዲህ አለ፤ ካህኑና ነቢዩ ከስካር የተነሣ ተንገድግደው ይሄዳሉ በወይን ይጠልቃሉ ከስካር የተነሣ ይቅበዘበዛሉ በትንቢት ይስታሉ በፍርድ ይወድቃሉ ብሎ አለ (ኢሳ ፳፰ ፯) ሰሎሞን በምሳሌ ሲአስጠነቅቀን ስለ ስካር እንዲህ ይላል፤ዋይታ ለማነው ኃዘን ለማነው ጸብ ለማነው ጩኸት ለማነው ያለምክንያት መቍሰል ለማነው የዓይን ቅላት ለማነው ጸጅ ለመጠጣት የሚዘገዩ የወይን ጸጅ ይፈትኑ ዘንድ ለሚሰበሰቡ አይደለምን በቀላ ጊዜ ፏ እያለ በብርሌ እንደ እሚአንፀባርቅ እየጣፈጠ ወደ ሆድ ይገባል ። ወደወይን አትመልከት ከጠጣህ በኋላ እንደ ባብ ይነድፍሃልና እንደ ጉበና መርዙን ያፈሳል (ምሳ ፳፫ ፳፱ ፴፪) ከሁሉ የሚከፋ የሚጎዳ ገውጭ ሰዎች የሚሸጡት እንደ አረቄ የሚመስል መጠጥ ነው ፣ እርሱ እንደ እሳት አድርጎ ሆድ ይፈጃል ያቃጥላል ሲጠጡት መጀመሪያ የሚአነቃቸው ይመስላቸዋል እየቆየ ግን ሰውነታቸውን ይፀላዋል ይሰቀቀዋል ምኞት ከተነሳባቸው ለዚህ ዓለምና ለወድያኛው የማይጠቅሙ ክንቱዎች ሆነው ይቀራሉ ። ውሀ ጠጥቶ ወደሥራ ጨዋ ሁኖ ከሚሔድ ወይስ አረቄ ጠጅ እስቲሰክሩ ጠጥቶ ዓይንን በርበሬ አስመስሎ ከመሄድ ክፉና በጎ ነገር እየቀባጠሩ ከመሔድ የቱ ይሻላል ? ይልቁንም ሰው የሚሰክረው በበዓል ቀን ነው በዓል የተሠራልን በርሱ ከሰማይ የአምላክ በረከት ልንቀበል ነው በስካር ብንውል ግን ያ በረከት ይቀርብናል በትልቅ በዓል እንኳን ባዶ ሆነን እንቀራን ።

አሁንም ወንድሞቼ በዚህ ቃል የሰማችሁ ጠጥታችሁ አትስክሩ ለመጠጥ ገንዘባችሁን ከምታጠፉ ብሉይና ሐዲስ ገዝታችሁ መርምሩ ዋጋውም እርካሽ ነው፡፡ይኸ ሰው ለዘለዓለም እንዳይሰክር ተስፋ አደርጋለሁ ብሎ ፩ ኩባያ ውሀ ለመነና እጠመቀው ያም ሰውዬ ስካሩ ለቀቀው፡፡ብዙ ልጆች መጽሐፍ ይዞ የሚሔደውን ልጅ ተከትለው ሰካር አጥምቅ ተስፋ የወንጌል መልከተኛ አሳብህን ጥለህ እርፍ ብለህ ተኛ እያሉ ይጫወቱ ነበሩ እሱም ምላሽ አልሰጣቸውም ዝም ብሎ ሔደ ። ብዝዎች ሰዎች ያሰው ስካሩ ስለ ተሻለው ገረማቸው እኔም ይኸንን ቃል ሰምቼ ለክቡር ብርሃንና ሰላም ማህበሮችና አንባቢዎች ለመጻፍ ግድ ሆነብኝ ክቡራን የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ጸያፉን አርማችሁ እንድትቀበሉኝ በማክበር እለምናችኋለሁ ። መክብብ ተክለ ማርያም ።

ኢትዮጵያን ለማገልገል ወደ ብርሃን እንሩጥ ።

ኢትዮጵያ ንግሥተ ሳባ ዓይኖቿን ወደላይ ፈጣሪዋን ታምና እጆቿን ዘርግታ ለኢትዮጵያ ሕይወት ትለምናለች አሁንም እንደ ንግሥት ማከዳ የመሰለች አንዲት ዳግማዊት የኢትዮጵያ ግርማዊት በእግዚአብሔር ቅብዓት ለኢትዮጵያውያን ሁሉ ለናትነት የተመረጠች አምላኳን በመፍራት ልጆቿን በታላቅ ተስፋ በመስማማት መንፈሳዊ ለማኖር የምትሰበስብ ለማዳን የተወሰነች ናት ፤ እርሷም በመንፈሳዊ ሥራ በሰላም ፍቅር ቁማ አገሯን ሁሉ በሐዘን ጸሎት ትጠብቃታለች ።

እነሆ የብርሃን ቅንነት የምታለመልም የወይን አትክልት ወዳለችበት ስፍራ ዘወትር እያፈራች ትመራለች ። በንጽሕና ታላቅነትን እንደ ልብስ የለበስሽ ግርማዊት ሆይ ምስጋና እስከ ዘለዓለም ላንቺ ይድረስሽ ከሷም የበቀሉ የኢትዮጵያ የዕንቍ ፍሬዎች ሀገሯን ሰላም ለመስጠት በማገልገል የሚከቧት አልማዞች በዙፋንዋ ከለላ ሁነው ኢትዮጵያ ሳባን በዜማ ይወድሱዋታል እርስዋም የተቀበለችውን የዘለዓለም የሕይወትን ፍሬ የምታኖር የኢትዮጵያ ግርማዊት ኃይልና ጥበብ ቅንነትን ጨምራ ፍጻሜ የሌለው የኢየሱስን ክብር በቃለ ኪዳኑ ግርማ ሞገስን ለብሳ ለዘለዓለም ተድላ ስሟ ይባረክ ።

ኢትዮጵያን ለመጠበቅ የተወለደ ዕንቁ አባታችን የሆነ ዕውቀትን ለማስፋት ብርሃንና ሰላም ብሎ የሰየማቸውን ሁለት ትላልቅ ሀብታቶች የውቀት ፍሬዎችን እየተከተልን የብርሃንን ምንጭ ለመቀበል ወደፊቱ እንቅረብ ። ጨለማም እንዳይነካን ብርሃን የፊት መሪ ሰላም የኋላ ተከታይ ልዑል በዙሪያው ከለላ ሁኖን ኢትዮጵያውያን ሁሉ በመስማማት ሀገራችንን ከልብ እንድናገለግልለት በሰላም ደጅ ይጠራናል ።በትምሕርትና በብርሃን መንገድ እንድናውቅለት በቀኝ ቁሞ ይጠብቀናል በውነት ኢትዮጵያን በውቀት የሚመሠርት የሕይወትና የውቀት ጌጽ በዚህ ትሁት ሰላም ደጅ ነው ። ለመንግሥታችሁ በመከችነት እየጠበቃችሁ የምትኖሩ የኢትዮጵያ ልጆች ሁሉ ፍቅርና ሰላም ያደረባችሁ ክብር ምስጋና ይግባችሁ ።

ሰው ከሞት ተራ አጠገብ እስኪደርስ ድረስ ደግ ሥራ ይሠራል ሰው ግን ለደግ ሥራ በእግዚአብሔር እጅ እንዲህ ተፈጠረ ።

እግዚአብሔር ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ ጽድቅንና ኩነኔን ለይተን ለማወቅ ዕውቀትን መልቶ ሰው ብሎ ፈጠረን ። እግዚአብሔር በቸርነቱ ብዛት የጽድቅን ሥራ ለመሥራት በቃሉ ንግበር ሰብአ በአርያነ ወበአምሳሊነ ብሎ ፈጠረን እንስሳንና አራዊትን የክፉውንና ፣ደጉን ያለማወቅ ሳይለዩ እያደባለቁ እንደሚሠሩት በሕርይ ለመሥራት ስላልፈጠረን፤ እግዚአብሔር አእምሮውን መልቶ የሰጠን ስሙ እስከ ዘለዓለም ይባረክ እያልን የፈጠረንን በማወቅ የአዳም ልጅ ምስጋና ያቀርባሉ ፡፡

እውቀትን እግዚአብሔር መልቶ የሰጠው ፡፡ ከኃጢአት እርቆ መንግሥተ ሰማያትን እንዲወርስ ነው ። ነገር ግን አንድ ጊዜ ለደግ ተፈጥሮ ፈጣሪውን በጥጋብ ረስቶ በነውር ሥራ በማይገባ ባልታዘዘ ቃል በሥጋ ልደት በደም ጥልቀት ሰውነቱን በርኩሰት እንደ እንስሳ በግብር ሥራ እያሰኘው በሚደበለቅ ሥራ መሥራትን እግዚአብሔር ይጸየፋል እንጂ እግዚአብሔር የፈጠረውን ፍጡር አይጸየፍም ስለዚህ በሰው ሁሉ በመልካም ሥራው አይፈረድበትም ኃጢአት በመስራቱ እግዚአብሔር ይቀየማል እንጂ ።

ወዮለት እግዚአብሔርን በጥጋብ በኩራት የሚረሳ ግፈኛ ሰው ዝሙት ሐሜት ተንኮል ያደረበት እንደ ዲያብሎስ በሥራው የመሰለ ሰው የዋሆችን ከንጹሐኖች ለማጋጨት እንደአዘየጠረሰ ልቡን ሸፍኖ መላሱን አለስልሶ ጥቅሙን ለማስፋት ሐሰትን እውነት እውነትን ሐሰት አስመስሎ እየሰበከ እያሰበከ ብዙዎችን ለጥፋት የሚያስብ ከዚህ ጀምረው እስከ እርጉቅ ድረስ በስውር ድብቅ ሥራ ተባብረው ንጹሖችን በተንኮል ለማጥፋት በፊታቸውም በስተኋላቸውም እንደተኩላ ከበው የቅኖችን ቤት ጐረሮ ዘግተው በእህል ናፍቆት በረኃብ ተጨብጠው በመታረዝ ተከማትረው የመከራ ቀንበር በግድ ተሸክመው ከሥራቸው ተመንግለው በዓጽም ቁመው እንደዚህ ያለውን ግፍ የሚሠራ እግዚአብሔርን የጠላ ነው ። የክፉ ሰው ምልክቱ በደግ ሥራ አይጸናም ተንከለኞችን እንደሥራው እየመረጠ ለርኩሶች አጋጣሚ ሥራውን የሚአድል ቀጣፊ የሆኑ የአድመኞችን ምስክር የሚለብስ የሐሰተኞች ደጃፍ የሚአደምቅ መሪ ሰው የሆነውን ነው እግዚአብሔር የሚአጠፋው ።

ሰው ሆይ ።

ለወንድሞቼ በመልካም ፍቅር ሥራ የዋሆችንና ቅኖችን የሚሰበስብ ሁሉ የእግዚአብሔርን ቤት መንግሥተ ሰማያትን የሚወርሱ ናቸው ነገር ግን ተንኮለኞችን እየሰበሰቡ ሰውን በኃጢአት ለማጥፋት በስውር ውስጥ ለውስጥ የሚሔዱ ሁሉ በሰይጣን ውስጥ ይቀራሉ ።

ዮሐንስ መ ።

ስለ ተማሪ ቤት ማቆም ።

በ፩ኛ ዓመት በ፰ኛ ቁጥር ብርሃንና ሰላም በማህበር እናቆማለን ያልነው የትምህርት ቤት እንደ ፍቅርና አገልግሎት ማህበር ብርትተን ሥራውን ሳናቆም መዘግየታችን በምን ምክንያት እንደሆነ ልጅ አበበ ወልዴ ጠየቁ ። ደግሞም በ፲ኛ ቁጥር ብርሃንና ሰላም እንደ ፍቅርና አገልግሎት ማህበር ለሥራው ሰብሳቢና ሐላፊ የሚሆን ሰው ባይኖር ነው ወይስ በምን ምክንያት ነው ሥራው ያለመጀመሩ ብሎ አቶ መክብብም ጠይቋል ። መቼም እኛ ማህበርተኞቹ እንሰጣለን ያልነው ገንዘብ ከ፮ሺ ብር አልበለጠም ተስፋ የምናደርገው መንግሥታችን ለትምህርቱ ቤት እንረዳለን ያለውን ገንዘብ ነው ስለዚህ ትልቁ ክፍል እርዳታ ከመንግሥት ስለሆነ ሥራውም በቶሎ እንዲጀመር መንግሥት ያደርግልናል በማለት ሙሉ ተስፋ አለን ። ደግሞም ስለ ስልጣኔ ትምህርት ቤት ማስፋት ነገር የኢትዮጵያ ታላላቆች የትምህርት ቤት በየአገሩ አውራጃ ቢያቆሙ ጥቅምና እርዳታ መሆኑ ብዙ ሰዎች ጽፈው አንብበናል ። በውነትም ይኸ የሚቻል ቢሆን መልካም ነበር ።ነገር ግን እኔ እንደማስበው አይቻልም ይመስለኛል ያለመቻሉም ከኢትዮጵያ ህዝብ ውስጥ ፩ም (ካፒታሊስት) ማለት ባለ ብዙ ገንዘብ የሆነ ነጋዴ ወይም ባለ

ብት ለዚህ የሚበቃ ገንዘብ ያለው የለም ህዝቡ ደሀ ነው ። ደግሞ አገረ ገዦች መኳንንትም ቢሆኑ የሚገብሩቸው ህዝብ የሚበልጥ የሥራ ጊዜው በከንቱ የሚጠፋበት ስለሆነ ደሀ ብቻ ነውና የሚያገኙት ገንዘብ በጣም ትንሽ ነው ። ለዚህ የሚበቃ ገንዘብ አያገኙም የሚያገኙት ገንዘብ ከትዳራቸው አይተርፍም ግን ለዚህ የሚበቃ ገንዘብ የሚያገኙ ምናልባት ፪፫ ሰዎች ይኖራሉ እነሱም የሥልጣኔ ትምህርት ያገር ጥቅም መሆኑን አልተረዱትም ይሆን ይሆናል ።

ደግሞም ፩ ፮ ብርቱ መኳንንት አሽከሮቹን ሹሞቹን አርዱኝ ብሎ ለጊዜው ቢያቆም እንኳን አይረባም እሱ ሲሽር ወይም ሲሞት ይቀራል ። ስለዚህ የሥልጣኔ ትምህርት ለማስፋት ዛሬ ፩ መንገድ ብቻ ነው ያለን እሱም መንግሥታችን ከዚህ ቀደም ለትምህርት ቤት በጉምሩክ እንዳቆመው ደንብ ያለ በሌላውም ሕዝብ እንደሚቻል ለትምሕርት ቤት የሚወጣ ገንዘብ ደምብ አቁሞ ፣ ደግሞም ገንዘቡ ሥራ እንዳይፈታ እንደ ማህበር ሆነው ተማክረው ይኸንንም ደንብ የሚያወጡ ዘወትር በሥራውም የሚማከሩ ለዚህ ሥራ የሚሆኑ ሰዎች ቆጥሮ በዚሁም መከከል ለሥራው ሐላፊንትና ሙሉ ሥልጣን ያለው ሹም አድርጎ እነዚህ ስራውን ቢያስሄዱት ከየአገሩ የሚወጣውም ገንዘብ በዚያው በወረዳው በየሻለቆቹ ከተማ የሥልጣኔ ትምሕርት ቤት ቢቆምበት በትክክል የቆመ ሥራ ይሆናል ። ግን የሥራው ሹምና አማካሪዎች በጐን ሌላ ትርፍ ሥራ የሌለባቸው በሥራውም ከመፈተሽ በቀር ሌላ ሰው የማይገባባቸው ይኸኑ ብቻ የሚሠሩ ካልሆኑ ሥራው አይከናወንም ቀን ሳይቈረጥለት ታስሮ እስታዋሽ ዘመድና ወዳጅ ያጣ እስረኛ ይሆናል ። ከዚህ መንገድ በቀር የኢትዮጵያ ሕዝብ በሌላ መንገድ የሥልጣኔ ትምሕርት ለማግኘት ብንፈልግ አናገኝም።የሥልጣኔ ትምሕርት ቤት የሚሠራው በገንዘብ ነው ።

ደግሞ ገንዘብ የሚገኘው በሥልጣኔ ትምህርት ስለሆነ የተሳሰረ ነገር ነው ። ከነዚህ ፩ን አስቀድሞ ለማግኘት ትልቅ ችግር አለበትና በጣም ብርታት ያስፈልጋል ። ህዝቡና ያገር ታላላቆች ትምህርት ቤት ለማቆም የሚችሉ የሥልጣኔ ትምህርት ሰፍቶ በቡር በየአውራጃው ተዘርግቶ ህዝቡ የሚሰጠው ግብር በቍርጥ ደንብ ሆኖ ህዝቡ የሥራ ጊዜ እንደሚገባ አግኝቶ አርሶ ነግዶ ከብት አርብቶ ያረሰውን እህል ያረባውን ከብት ወደሚያስፈልገው አገር ያለችግር አመላልሶ ከብቱ በከንቱ እንዳያልቅ ሐኪም ለእርሻው ሥራ እውቀት ሀብት ባገኘ ጊዜ ነው ይኸም ጊዜ አሩቅ አይምሰላችሁ። መንገዱ በር ዝግ ቢሆን ነው እንጂ ቅርብ ነው ያለው ይኸ በር የተዘጋበትም ቁልፍ መክፈቻው ብረት ወይም ገንዘብ አይምሰላችሁ የሥልጣኔ ትምሕርት ቤት ነው።ይኸም የጻፍሁት ቃል ዋና ቁም ነገር ፩ብቻ ነው እሱም ይኸንን የድንቁርና በር መክፈቻ ቁልፍ ለመያዝ የሚታመንና በሩን ለመክፈት የሚችል ሠራተኛ መንግሥታችን መርጦ በሥራው ላይ ለሥራው ሐላፊነት ያለው ደግሞም ለመሥራቱም ሥልጣን ያለው ሰው ያደርግልናል ስንል እንመኛለን ።

ፈ ዱሬሳ

ሙሴ አርመን ያዕቆብ ስለ ጻፉት ቃል ።

ባራተኛው ዓመት በ፱ነኛው ቁጥር በ፺፯ ገጽ ሙሴ አርመን የጻፉት ጋዜጣ የእኛን የልጆቹን ልብ እንዲህ አድርጎ የነካን ለብርሃንና ሰላም ወዳጆች ለታላላቆች አዋቂዎች እንደ ምን ይጠልቃቸው ይሆን።ማለት ከዚህ ቀደም ምንም በብርሃንና ሰላም ውስጥ የበላለጡ ብዙ ፍሬዎች ቢኖሩ ይህ የሙሴ አርመን ኃሳብ በሁሉ ልብ ሲወጣ ሲወርድ እንደሚኖርና የሁሉ ሃሳብ እንደሆነ ለኔ እንኳን ለትንሹ ልጅ ይሰማኛል።ለመሆኑ ብዙ የሚያሳዝንና የሚያስገርም አለበት።በንድ ታላቅ ገዳም ቤተ ክርስቲያን በውስጡ ብዙ ገጠሮች ችግረኞች ቤተ ክርስቲያኖች አሉ በዚያ ገዳም የተጠራቀመው ገንዘብ ለማስተማሽ መታሰቡ ይቅርና ለዚያ ለችግረኛ ለገጠር ታቦት ይህ ይሰጠው አይባልም ከቶውንስ ማን አስቦት የቤተ ክርስቲያኑ ዕቃና መሰሺ እንኳ ቢበዛ ብል ከሚበላው ይበልና ተሸጦ ብሩ በገበዝና ባለቃ በመሬ ጌታ እጅ ይመከርበታል ይሠራበታልም ይሆናል።ማለት አንድ ሰው የስለትም ቢሆን ወይንም በፍቃዱ ለቤተ ክርስቲያን እርዳታ ቢሰጥ የት እንደሚሄድ ምንክ እንደሚሠራበት አይታወቅም ። እስቲ እንግዲያውማ እነዚህ ከሰው አገር ድረስ እየመጡ በኢትዮጵያ በየአውራጃዋ እየተሳደዱ የተማሪ ቤት አቁመው የሚያስተምሩና የሚሰብኩ ካቶሊካውያንና ፕሮቴስታንት ሁሉ እንዲሁ በየገማዳቸው የተሰበሰበና በእርዳታ የመጣ ነው እንጂ በየራሳቸው ገንዘብ ብቻ አይደለም ይህንኑም ገንዘብ እንደምናያቸው ያስተምሩበታል እንጂ ለራሳቸው ጥቅም አይነግዱበትም በከንቱም አያስቀምጡት ደግሞ አንዱን ሲያስቡት ሌላው ትዝ ይላል በ፬ተኛው ዓመት በ፫ቁጥር ፺፩ገጽ ልጅ አበበ ወልዴ የጻፉትን ስንመለከት ስለ ተማሪ ቤት ማቆሚያ እንሰጣለን ብለው ፊርማቸውን የሰጡ ሰዎች ገንዘብ ከ፳ ሺ፩፻፶፬ ብር የሚያንስ አይመስለኝም ብለዋል ።

ስለ ጻፉት ሰጭዎችም ተቀባዮችም መልስ አልሰጡም ይህ ስህተት የማናቸው ይሆን መቼም ጥፋት የሁለት አይሆንምና ወይንም ሰጭዎች አምጡ ብለው ሳያስቡት ለምን ብለን እንሰጣለን አስበው አሰናድተው የተመረጡት ሰዎች መጠየቅ አለባቸው ይሉ ይሆናል።ወይንም ደግሞ ተቀባዮቹ ፊትም ላገራቸው ጥቅም ሲሉ አስበው ፊርማቸውን እንደመጠናቸው አንድ ጊዜም የሰጡ በየዓመቱም እንሰጣለን ብለው የፈረሙ እኛን እያተጉ ገንዘቡን አስበው መስጠት አለባቸው ይሉ ይሆናል ። እንግዲህ እውነት ይህ እንደሆነ የሁለት ሰነፍ ቤት መሆኑ ይመስላል ። እንዲህ እንዳልሆነ ግን ፫ኛ አንድ ነገር ሊመስለን ነው ምናልባት ገንዘብ ሰብሳቢው አትግቶ ተቀብሎ ሥራውን ሳያቆም ዝም ብሎ እንደሆነ ያው የካህናትን አካሄድ የተመለከተ መሆኑ ይመስላል ።

ይሁን እንጂ ምሳሌ ነገርን ከመጀመር መፈጸም ይሻላል ይላልና እንዲሁ ልጅ አበበ ወልዴ ፺፱ ገጽ ላይ አጻፉት መጨረሻ መስመር የሚለው ቃል የሚደርስባችሁ እንዳይሆን ወደ ፊተኛው እንመለስ።ሙሴ አርመን ሆይ አሁን ይህንን የማያውቅ አለ ብዬ አይደለም ብቻ የኢትዮጵያ ጥቅም ጥቅሚ ስለ ሆነ ባለኝ አቅሜ ላስታውስ ልረዳ በማለት በንጹህ ልቦናዬ

ነው ያሰብኩት ስላሉ እኔም እንደ መጠኔ ከልብ የመጣና ካንገት በላይ በየስሙላ ያልሆነ ምንም ባልማርና ልጅ ብሆን ጥቂት ጥቂት ይታወቀኛል ከዚህ አብልጬ ዝርዝሩን እንደ እውቀቴ ብጽፈው አዝኖ ማሳዘን ስለሆነ ትርፉ ጊዜውን ይጠብቅ በማለት ቱወት አድርጌዋለሁ ያሉት ጥቂት ቅር ያሰኛልና ከብርሃን የበለጠ ደስታ ከሰላምስ የበለጠ ጊዜ የታል በጀመሩ ይጨርሷል በተለሙ ያርሷል የሚባለውን ተረት አሳስብዎታለሁ በተቀረማ የክህናት የአበል አባቶቻቸው የመሠረቱት መሠረት እንዲህ በቅርብ ቀን የማይገፋ ነውና ካሁን ጀምረን ብርሃንና ሰላም የሚባለውን መሐንዲስ ሠራተኞቹን እውቀትንና ጥበብን በፍጥነት እያዘዘ እንዲያሳድስልን በሳምንት በሳምንት ቶሎ ቶሎ ማሳሰብና ማስታወስ የሚያስፈልገን መሆኑን ለብርሃንና ሰላም ወዳጆች በደንቆሮው ኃሳቤ አስታውሳለሁ ።

የሺጥላ ማሬ

መልስ

ለመልእክቱ በያን ፥ ሕይወትና ሰላም ላንተ ይሁን ። ጥበብ ሥጋዊና ጥበብ መንፈሳዊ ተምረህ መጥተህ ለሀገርህና ለወገኖችህ ልትረዳ ከሀገርህ ስለወጣህ እግዚአብሔር ጥበቡን ይግለጥልሕ ኅሡ ትረክቡ ሰአሉ ወይትወሀበክሙ ብሏልና።

ማናቸውንም ሃይማኖት ማስተማር መከልከል ትልቅ ወሰን የሌለው ስሕተት ይሆንብናል ስላልከው ቃል ። የስላም ሃይማኖት እየሰፋ እንዳይሄድ ባዋጅ ቢከለከል ደግ ይመስለኛል ያልኩበት ምክንያቱን ልጻፍልህ ። የኛ መምሕራን እስኪነሱ ነው ከባዕድ አገር ዓረቦች መጥተው ሕዝባችንን ወገናቸው እንዳያደርጉ ለኛም ጠላት እንዳይሆኑን ከፊርን የገደለ እስላም ይጸድቃል የሚሉ አሉና ።

እስላም ከሆኑ በኋላ ወደክርስትና መመለስ እጅግ አድርጎ ይጨንቃቸዋልና ሳይሰልሙ በረመኔነት ቢቆዩ ለሁሉም ጊዜ አለውና የክርስቲያን አስተማሪ በየጋላው አገር ገብቶ ባስተማራቸው ጊዜ በቶሎ ይነሳሉ ይመስለኛል ።

በአፄ ዮሐንስ ጊዜ እስላም ሁሉ ክርስትና ይነሣ ብለው ባዋጅ ቢነገር አልነሣም ያሉ በሰይፍ አለቁ። ፈርተው የተነሡት በኋላ ተጸጽተው እንዲህ ብለው ገጠሙ ።

ታናሽ ታላቅ በላን ከርካ አደባባይ ።
ወሀውን ታጠብን ማተብም አሰርን ክርስቲያን ሆይ ።
አሉልብ ሥጋ ይጣፍጣል ወይ ።

ይሆንም ቃል ለንጉሡ ቢነግሩቸው በግድ አታሥነሱ ተውዋቸውኒሉ ።

እንደዚህ እንዳይሆንብን ቀድሞ የሰለሙትን በትምህርት ቀስብሎ መመለስ ልጆቻቸውን የኛ መምሕራን ቢያስተምሩ የነሱን ከልክሎ ያልኩበት ምክንያት ይህ ነው ።

ንጉሥም በመንግሥቱ ውስጥ ያሉትን ሕዝብ በ፩ ሃይማኖት አስተባብሮ ቢገዛ መልካም ጸጥታ ይሆንለታል ። በየወገኑ እየተፍረቀረቀ ባንበ ኅሮ አይተላለቅም ።

ነጋዴንና መጣተኛውን ሠራተኛ ግን እንደ ሃይማኖቱ ሊያኖር ይገባል እንጂ ተመለስ ወደኛ አይልም ።

ከማስተማር የማይከለከሉ ግን ወረደ ተወለደ ሲሉና ሲያምኑ ጥቂት በጥቂት ነገር የሚለያዩን ወገኖች መካከል አይገባም ።» — —

ስለ ሃይማኖት መለያየትም ፩ የኛ ሃይማኖት ይበልጣል ቢል አንዱም የኛ ይበልጣል ቢል በአፍ ክርስቲያን ነኝ ቢል የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ካልሠራ አይጠቀምምና ሁሉም ለየራሱ ይጠንቀቅ ሁሉም ለየአንዳንዱ የሥራው ብድራት ይቀበላልና እንዲያው በአፍ ብቻ ክርስቲያን ነኝ አባት እናቴ ክርስትና አስነሥተውኛል ቢል ሴት ካገባ በኋላ በ፩ሴት ተወስኖ ሥጋውን ወደሙን ሳያቀበል ትእዛዝ እግዚአብሔርን ሳይጠብቅ እግዚአብሔርን አምናለሁ ቢል ሐሰት ነው የሰይጣንን ሥራ የሚሠራ የሰይጣን ባሮ ነው ። ወረደ ተወለደ ተሰቀለ ሞተ ተነሣ ለኛ ሲል ይኸን ሁሉ መከራ ተቀበለ መድኃኒተ ሥጋ መድኃኒተ ነፍስ ሊሆነን ሥጋውን ደሙን ሰጠን ፥ እንግዴህ ክርስቲያን ማለት ክርስቶሳውያን የክርስቶስን ሥጋና ደም ተካፋዮች በፍቅር ተባብረው ነዋሪዎች ማለት ነውና ፀብንና ምቀኝነትን ቂምን ትተን ተፋቅረን ግሩም የሆነውን የክርስቶስ ማዕድ ተካፋዮች ልንሆን ነውና ይህን ዕወቁ ። እኔም ሥራ አጥቼ እንዲያው ከመቀመጥ ለሕይወቴ የሚበቃኝን ያህል ትዳር ባገኝ አንድ እጋላ ቢሰዱኝ ግዕዝና አማርኛ የተቻለኝን ያህል እያስተማርኩ እቀመጥ ነበር ።

ቁም ጸሐፊ ገብረ ጻድቅ ።

ሹመት ።

መጋቢት ፱ ቀን ክቡር ልጅ መኰንን እንዳ ልካቸው ነጋድራስ ተብለው የንግድ ሚኒስትርነትን ተሾሙ ።

ክቡር ልጅ ፍቅረሥላሴ ከተማ የልጅ መኰንን የነበረውን የባቡር ተቈጣጣሪነትን ተሾሙ ።

ብርሃንና ሰላም አዲስ ሹመት ለተቀበሉ የሥራቸውን መክናወን እየተመኘላቸው እንኳን ደስ አላችሁ ይላል ።

ያገር ፍቅር መዝሙር።

፩ ገና አሉ አርበኞች
በመሐከል ሐበሾች
በጦርነት ጀግኖች
በድካምም ጠንካሮች
እንደርስት
ብርትነት
ኃይል በእጅ በልብ ድፍረት
ካባቶች ወረሱ
ይኖራሉ ሳይፈሩ ።

፪ ኢትዮጵያ ከጥንት
ነበረባት አርነት
መንግሥቱ ጠነከረ
አገሩ በለጸገ
ይለማል
ያብባል
ፍሬውን ያንጀረግጋል
ሀብታም አገር የሰጠን
እናመስግን አምላክን።

፫ እንታገል ለእምነት
እናሳይ ለጽድቅድፍረት
በሥራችን ትጉህነት
ለሰው ሁሉ በጎነት
ሁሉ ቀን ታጥቀን
እንጥቀም ለህዝባችን
አገር ሊለማ
እናርግለት ውለታ።

(ከ Gloire à Dieu)



ማስታወቂያ ።

ሺቦሮሌ አዮሞቢል በኢትዮጵያ ወኪል ፡
ሐ ሜ ዜርቦስ ኩምፓንየ ፡

Automobiles CHEVROLET
H. M. ZERVOS & Cie
REPRESENTANTS
BAS PRIX HAUTE QUALITE

ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትርሜጓው	፪ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ተኩል
የቁጥር ትምርት	፩ብር
ያማሪኛ ሰዋስው	፩ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	አላድ
ወዳጄ ልቤ	፫ሩብ
አጭር የዓለም ታሪክ	አላድ
ያማሪኛ ፊደል	ሩብ
አሳብና ምኞት	ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት	ሩብ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር	፪መ
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ	ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ	፩ሩብ

ማስታወቂያ

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚገኙ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
ደግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፰ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር	፱ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ብር
ኀሐ ጽባሕ	፰ብር
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፪መ
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ብር
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ቅንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ብር

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲ ብር ፲ መ
የሲዳሞ ቡና	፩	፲ ብር
ዝባድ	፩ ወቄት	፫ ብር
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፩ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፬ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፯ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ክረጅ	፫ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ክረጅ	፲፱ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ክረጅ	፻፴፰ ብር
:: ባለሰይጣን	::	፻፴፯ ብር
:: ባለ ድመት ::		፻፴፬ ብር
:: ባለአህያ	::	፻፳፪ ብር
:: ባለሳቢ ግመል	::	፻፴፰ ብር
ባለ አንበሳ	::	፻፵፰ ብር
ሱካር	፩ ጆኒያ	፳፫
ቻይ	፩ ነጥር	፭ ብር

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ
አንድ ብር	ሊሬ ፫ ከ፺፰ ሳንቲም
በአንድ ጊኒ	፲ ብር ከ ፰
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፬ ብር

COGNAC S.E.A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ማስታወቂያ

መጽሐፍና ደብተር የሚያስጠርዝ ሰው በርካሽ ዋጋ በልፁል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ይጠረዝለታል።

ያረጀ መጽሐፍና መዝገብ ማሳደስ ለፈለገ ሰው በርካሽ ዋጋ እንደ አዲስ አድርገን እንጠርዝ ለታለን ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብሶጠ የተመሰከረለት ዖሜጋ ቦቢ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩግቢ

RUGBY

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

“ሩግቢ” የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶመቢል በተለይወኪል“አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ”ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው። ደግሞ በኒዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፣በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፣ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፣ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒከላ ።

ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻው በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ ።

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህ በካፕሱሉ ያለ ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በካፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ጉድይር ግዙ





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው።በሌላጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ፤ ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

አራተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፲፫
4 me ANNÉE № 13

ሐሙስ መጋቢት ፳ ቀን፣ ፲፱፻፳ ዓ ም ።
JEUDI 29 MARS 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d'Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix ".

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ጸሐፊዉ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ሰፊስገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ከየዋህ ጨዋታ የተገኘ የቁም ነገር ንግግር ።

«መ» አጻጻፉ ለዓለም ቃል ነው ።

ማታ ጊዜ የተወደዱ ቄስ መጡ እኔን ለማየት እንደ የቀኑ ልማድ አንዳንድ ከኛክ መጠጣት ይወዱ እንደ ነበረው ይህንንም በቀረብኩላቸው ጊዜ በአንዳፍታ ጨለጡት ፡፡

እንዲህም አሉኝ ፡፡ ፍቅሬ ከፒቴን ሆይ ከዚህቀደም ብዙ እውነተኛ ነገር ክርስዎ ዘንድ አግኝቼ እንደነበረው ምንም እውነተኛ ነገር የሚናገሩ ሰዎች ውለታ የሚገባቸው ስለ ሆኑ ግን አለምንዎታለሁ ዛሬ ቀን በልዩ የሆኑ የከበሩ ነገር ያገኙ ይመስለኛል ።

እኔም መለስኩላቸው እንዲህ ስል ፤ የተወደዱ ቄስ ሆይ መ የሚባለው ቃል ትልቅ የነገር ፍች ያመለክተናል ላለፈው ጊዜና አሁን ላለነበት ጊዜ ሁሉ ትልልቆች ሰዎች ሁሉ የቁም ነገር ሥራ የሠሩ እንደሚገባቸው ያደርጉና ደግ ነገር አብሶም ላገራቸው የተመቹ ናቸው ። የነዚህ ይህን ሥራ የሚሠሩ ትልልቆች ሰዎች ሁሉ ስማቸውና ያባታቸው ስም የሚጀምረው በ መ ፊደል ነው የዚህን ነገር በልክ አስቲ ያስረዱኝ አሉኝ ። ለጊዜው ይህን ሲሉኝ ዓይናቸው ከከኛኩ ጠርሙዝ ሳይለይ ትኩር ብለው እያዩ ነው እኔም ባንድ ወገን ባንድ እጄ የክኛኩን ጠርሙዝ ይዤ ወዲያው ቀድቼ ይህንስ አስታውቀምታለሁ አልኳቸው ፤ ይስሙኝ የግብጽን አገር የመሠረተ ስሙ ሚናስ ይባል ነበር ።

ከሁሉም ይልቅ በጣም የበለጡና በጣም የበረቱ ከፈረዖን ነገሥታት ሁለት ሰዎች ነበሩ ስማቸውም ሚኔሬንና ሚሬሶ ይባሉ ነበር የግሪኮችን ሕዝብ ከጭንቅና ከመከራ ያዳናቸውም ሚልትያደስ ይባል ነበር ። ትልቁ እስክንድር ቄሣር መንግሥቱ በጠፋ ጊዜ የበረታ ስሙ ማኒቶናሲ ይባል ነበር በሮም አገር ብዙ የሰፋ እውቀትና ብርታት የነበራቸው ሰዎች ስማቸው መጊዎስና ማሪዎስ የሚባሉ ነበሩ ፡፡ ባንዶስ በሚባለው መንግሥትም እጅግ ብርቱና ጨካኝ የነበረ ስሙ ሚህርታት ነበር በአርመንያ አገር መንግሥት ነግሦ የነበረው በጣም ብርቱና የወታደርነት ሞያ የነበረው ስሙ ማንጎንያ የሚባለው ነበር ። የቱርክም መንግሥት እውቀት የሞላበትና ብርታት የተሰጠው ስሙ ሱልጣን ሞሐመድ ይባል ነበር ይህን ሁሉ ለክበሩ ቄሴ በነገርኳቸው ጊዜ በርገግ ብለው አንጋጠው በመደነቅ እንዲህ አሉ፤ ኢትዮጵያስ ? ሲሉኝ ጠምቷቸው ጉሮሯቸው ደርቆ ነበርና ደግሚ አራተኛ ኩኛክ ቀዳሁላቸው ይህንንም በፍጥነት ጨለጡት አልኳቸውም አይጣደፉ ኢትዮጵያ አንድ ትልቅ ልጅ ወለደች የኢትዮጵያን ሕዝብ ሁሉ ባንድ ላይ አጋጥሞ ያቀናና ያለማ የጥቅምን መንገድ ሁሉ የከፈተ ስሙ ንጉሠ ነገሥት ምኒልክ የሚሉት ነው ። ደግሞም እጅግ ብልህና እውቀት የዘለቃቸው አገራቸውን በጣም የሚወዱ በጅግንነትም ሥራ ሁሉ በልዩ የተመሰገኑ የታወቁ ስማቸው ራስ መኰንን ነበሩ እነዚህም ሁሉ በዋነኛው በዓለም ታሪክ ውስጥ አይቼ ያወቅኋቸው ናቸው አልኳቸው ። በዚያን ጊዜ አቤቱ ጌታዬ እንዴት ያለ የሚያስደንቅ እውቀት ነው አሉኝ ፡፡

ከዚህ ወዲያ ደግሞ አምስተኛ ከኛክ መቅዳት እንደሚያስፈልጋቸው አየሁ ብሰጣቸው ወዲያው ጨለጡት ። አልኳቸውም ይታገሡ ይኸ ያለፈውስ አለፈ ወደፊት የምነግረዎ ሌላ አለኝ ።

እንግሊዝ ዋና ትልቅ ሰው ማክዶናልት የሚባል አላቸው ፡፡ ኢጣሊያኖችም ዋና ትልቅ ሰው ሙሶሊኒ የሚባል አላቸው ። የቱርክም መንግሥት ሙስጠፋ ኬማል የሚሉት አላቸው ። የቦልሸቢክ መስከብ መንግሥት አንድ ትልቅ ሰው ሚኮያን የሚባል አላቸው ፡፡ አሁንም በብርቱ በማድነቅ አንጋጠው ደረትን ገልብጠው ላሁኑ ጊዜ ግን ይህንስ አልከኝ ለኢትዮጵያ

ላሁኑ ጊዜ የሚሆንዋቸው እለማናቸው ? እንዲህ ቢሉኝ አይቸ ኩሉ በትዕግሥት እያደመጡኝ ይቆዩኝ ስድስተኛውን ከኛክ ይጠጡ አልኳቸው ። በዚያን ጊዜ ክፒቴን ሆይ አይደለም ላሁኑ ጊዜ አኳኋን የሚችሉ የኢትዮጵያን ሰዎች ካልነገሩኝ አልጠጣልዎትም ቢሉኝ እንዲህ አልኳቸው ለኢትዮጵያ ሉብቻዎ ሆኖ የተገለለ ተስፋ አላት ያውም ለኢትዮጵያ ብርሃን የሆነ ነው እሱም ለሁላችን ውዴታ በፍቅር የተካከለልን ተፈሪ መኰንን ነው ። ትልቁ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ አስተካክሎ በከፈተው ጐዳና ላይ በጥንክሬ ተጠንቅቆ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ትንፋሽና ብርሃን እየሰጡ የቆዩ አሉ ።

እኒህ አልጠጣም ብለው በገዛ ራሳቸው ተከልክለው ታግደው የነበሩት መምህር ስለ ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ የሞላና የተካከለ ነገር በሰሙ ጊዜ ወዲያው ግጥም አርገው ከንፈራቸው ስንኳ ሳይረጥብ ጨለጡት ።

ከዚያ በኋላ የካህናትንስ ነገር ምነው ብታስታውቀኝ ቢሉኝ ትዕግሥት አይጡ ትንሽ ይቆዩኝ ለዚህም ይኸው የእሥራኤል አስቀድሞ ነቢያቸው ሙሴ አልነበረምን ወይ ? የክርስቲያኖች ሃይማኖት ከደቀ መዛሙርቶቹ መሀከል መጀመርያ ማቴዎስ ዳግመኛውም ማርቆስ አይዶሉሞይ ? ይኸንንም ቃል ስናገር ሁሉ አሁንም ያኑን የከኛከን ጠርሙዝ ይመለከቱ ነበር ። የሚነጋገሩኝ በኋላ አጥብቄ ብመለከታቸው ፊታቸውን አጥቁረው ግንባራቸውን ሰግጠው አየኋቸው ።

ስድስተኛውን መለኪያ ከኛክ ሞልቼ ብሰጣቸው ስለ ኢትዮጵያስ አሉኝ በክርስቶስ የምጠይቅህን ሳትመልስልኝ አልጠጣም ቢሉ ምንቢሆን ይህን የምጠይቅህን አደራ እባክህ ንገረኝ ሲሉ ጊዜ ምነው የየሱስ ክርስቶስስ ስም በ መ ፊደል ያለ መጀመሩ ምክንያቱ ምንድርነው አሉኝ ።እባክዎ ትንሽ ይታገሡኝ ኢየሱስ መሲሕ ይባል የለምን ዋናውን ስሙ ማኑኤል አይደለምወይ የንጽሕት እናቱስ ስም ማርያም አይደለችምን? ይህን አሁን የተናገርኩትን በነገርኳቸው ጊዜ ሰባተኛውን መለኪያ ከንፈራቸውን ሳያስነኩ ጭልጥልጥ አርገው በጀርባቸው ተንጋለው ይልቁንም ይህን በሰሙ ጊዜ በዘለቃ እውቀት የሚያስገርም ነው ብለው መለሱልኝ ፥ነገር ግን ከዚህ ከነገርከኝ ውስጥ የጐደለህ ነገር አለ ይህነንም እኔ ልፈጽምልህ ። ካለፉት አቡነ ማቴዎስ ካሉት አሁን እኔ ሚካኤል ነኝ አሉኝ ። የተጠጡትን ከኛክ መለኪያ የቁጥሩን ልክ ረስተነው ነበር።ክቡር ቄስ ግን በተካከለ ቁም ነገር እንግዴህ ለመሄድ ፍቃድህ እንዲሆን ብለው አሉኝ ።

እኔን ግን በተዘረጋ በሰፋ በዋና ከዘለቀ አሳብ ውስጥ ትተውኝ ሄዱ ።

ክፒቴን ባቢኪያን ።

የምታስጐመጅ ምክር ።

ምክር ሠናይት ለኵሉ ዘይገብራ ያለውን ተመልክቼ ይህችን ቃል ለክቡራን አገረ ገዢዎች ላስታውቅ ፈቀድኩኝ።ክቡራን አገረ ገዢዎች ሆይ ፥ ምክር አይናቅምና ይህችን ምክር እንድትቀበሉኝ ከምለምናችሁ በስተቀር ነገሩን ባረዝመው ምንም ያህል ፍሬ የለውም ። መጀመሪያ ደጉ የኢትዮጵያ መንግሥት ሰጭና ብልህ ስለሆነ በሁሉም ነገር እናንተን እየመረጠ አስተዋዮችና እውቀትም ያደረባችሁ ስለሆናችሁ ድኃቸውን እንድትጠብቁላቸውና እንድትጠቅሙላቸው አገር አሲዘዋችኋል ። ነገር ግን በምትገዙት አገር ብንመለከት ሽፍታው ባንድ ፊት መጥቶ ድኃውን ሲያጉላላና ገንዘብም ሲወስድ ይገኛል ። እንዲሁም የሚያደርገውን ከግዛታችሁ ውስጥ በቶሎ ብላችሁ እንደምታጠፉት ፋንታ በርቅ ገብቶ ከመዘባበት በፊት እንድታስቡበት ያስፈልጋችኋል ። ሁለተኛም መንግሥታችን ጠብቁ ብሎ የሰጣችሁን ድኃ ሳታስመርሩ ግብር በልክ እያወጣችሁ አርሶ ቆፍሮም እንዲበላ በመከርም በዝመራም ጊዜ ሥራ ሥራልን ከማለት ተወት ብታደርጉት ከስጋት ያርፍና የርሱን ሥራ እየፈጸመ በከሌ ጊዜ እርፈት አገኘን እያለ ምስጋናውን እየደረደረ መንግሥታችንንም ያሰንብትልን እያለ በደስታ ይተዳደር ነበር፥ እናንተም ከምታገኙት ገንዘብ ፪ እጁን ለሃገር ሥልጣኔ ሥራና እንዲሁም ለከተማችሁ የሚያስፈልጋችሁን መንገድ ማስበጀትና አልፎ አልፎም ትንሽ ትንሽ ብታቆሙ በከተማችሁ ወስላታና ቀጣፊ በጠፋ ነበር ይህንኑ የመሰሉ ዓይነት ሁሉ ብታደርጉ መልካም ነው ። ይልቁንም ከሁሉ የሚበልጥ የማሳስባችሁ ለወታደሮቻችሁ በልክ ቀለቡንና ደሞዙን እንዳይራቡና እንዳይጠማ እያደረጋችሁ እንደ ኤሮፓ ሥርዓት እያስደረጋችሁ የሰልፍ አኳኋን በስተማሪ ብታስተምሩት ብልሁ የኢትዮጵያ ወታደር እንደምን በሆነ እንደምንስ የሃገር ፍቅር እንዴት በጣም በጣም በነገበገበው ነበር ። ከዚህ በፊት የኢትዮጵያ ወታደር የሃገር ፍቅር አያውቅምና ለወደፊት እንዲማር ስለማለት ብለን አይደለም በሃገር ፍቅር እንሚቃጠል በኤሮፓም እጅግ ይደነቁበታል ። ነገር ግን ሳይማር እንደዚህ የሆነ ቢማርስ እንደምን ይሆን ስለማለት ነው ። እንደዚሁ እያደረጋችሁ በኃይል ብተነሡ እናንተ ከላችሁ የሚያውክ ነገር የለምና ባንድ አሳብ ሆናችሁ ይህንን ሁሉ ብትፈጽሙ ከናታችሁ ምርቃት ከወንድሞቻችሁ ምስጋና እንድትቀበሉ ጥርጥር የለበትም ። ነገር ቢያበዙት ባህያ አይጫንምና ይህንን የፊት የፊቱን ሳትፈጽሙት እየተመለከትን ያለመሠረት ቤት እንደማይረጋ ታውቁታላችሁና ምንም ብልህ ብትሆኑ መከሪ ያስፈልጋችኋልና ይህንን የመሳሰለ ምክር ልንሰጣችሁ የተሰናዳን ነን ።

ጥሩነህ ከ

ደግና ክፉ ።

ሰው ሁሉ ያየውንና የሰማውን ለብርሃንና ሰላም ለማመልከት ማሰቡ አይቀርም ነገር ግን ያመለከትኩትን ነገር ያልተከናወነ ሆኖ የታያቸው እንደሆን ይነቅፉኛል በማለት ፍርሃት እያደረበት ያሰበውን ይተው ይመስለኛል።ስለዚህ ያዩትንና የሰሙትን በሆድ ማስቀረት ለሰውነት ህመም ይሆናልና ይልቅስ ለብርሃንና ሰላም ማህበረተኞች አመልክቶ ያልተከናወነውን አርሙልኝ ብሎ በትህትና ልመናን ማቅረብ ይሻል ይመስለኛል ብዬ ያየሁትን ነገር እጀምራለሁ ።

ከቤቴ በታች እመንገድ ላይ ትልቅ ማጥ ነበረ ከዕለታት አንድ ቀን ከደጅ ቆሜ ስመለከት ደግ ለራሱና ክፉ ለራሱ የሚ

ባሉ ሁለት ሰዎች አብረው ሲሄዱ ትልቅ ዝናብ ዘነበባቸው በሚሄዱበት መንገድ ላይ በጣም ጭቃ ሆኖባቸው መሽቶባቸው ለጨለማ ሽሽት ሲሮጡ ከዚያ ከትልልቅ ማጥ ውስጥ ሁለቱም ገብተው አየኋቸው የገቡበት ማጥ በጣም ትልቅ ኖሮ ሁለቱንም አንገት አገንታቸው ድረስ ዋጣቸው ደግ ለራሱ የሚባለው ግድ የለህም ወንድሜ አትደንግጥ እንደምንም ብለን ከዚህ ከገባንበት ማጥ ውስጥ መውጣታችን አይቀርምና ሳትበሳጭ ሰውነትህን በትዕግሥት አድርገህ ወደ ፊትህ ካለው ሜዳ ለመውጣት ተጣጣር ብሎ ክፉ ለራሱ ምክር ደግ ለራሱ ከዚያ ከማጥ ውስጥ ለመውጣት ሁለንተናውን በትዕግሥት አድርጎ ይጣጣር ጀመር። ክፉ ለራሱ የሚባለው አዬጉድ ያንተ ነገር በጣም ይገርማል ይኸንን የገባንበትን ማጥ ትልቅ መሆኑን እያየኸው ከዚህ ውስጥ ለመውጣት እንችላለንና ተጣጣር እያልክ የምትቀልድብኝ ለመውጣት የማልችለውን ነገር ሰውነቴን በከንቱ እንዲመላለጥ ብለህ ነው ይልቅስ በከንቱ አትልፋ ይሆናል ብሎ ተመልፋት አይሆንም ብሎ መተው ይሻላል ብሎ ሰው ይዘ በግድ ያገባው ይመስል አፉን እየነከሰ እየተበሳጨ ይናደድ ጀመር። ደግ ለራሱ ግን እዬ ወንድሜ ይህ ዝናብ ደመናውን የምታየው ነው ደግሞ ለመዝነብ ይፈልገዋል ይልቅስ አትናደድ አይዞህ መውጣታችን አይቀርም ተጣጣር ብሎ ደግ ለራሱ በጁም በግሩም በሁለንተናው ሁሉ አንድ ጊዜ እንኳን ሳይቦዝን ከዚያ ከማጥ ውስጥ ለመውጣት ተጣጥሮ እውነትም የኋለኛው ዝናብና ጐርፍ ሳይደርስበትእዳር ወጥቶ ከሞት ድኖ አየሁት ። ክፉ ለራሱ ግን እዚያው እማጡ ውስጥ ቆሞ ልቡን አስንፎ እየተናደደ ሲያመናታ እንደገና ከዚያ የበለጠ ዝናብ ዘንቦ እዚያው እማጡ ውስጥ እንደቆመ ሳይንቀሳቀስ በላዩ ላይ ትልቅ ጎርፍ መጥቶበት ከዚያው ሞተ ።

እንግዴህ ሁለቱም የገቡበት ማጥ አንድ ነው ደግ ለራሱ የወደቀበትን መከራ ሁሉ በትዕግሥት ተቀብሎ ልቡን ሳያስንፍ ከዚያ የገባበት መከራ ለመውጣት ተጣጥሮ ወጥቶ ከሞት ዳነ ። ክፉ ለራሱ ግን መቸም አንድ ጊዜ እዚህ እመከራ ውስጥ ገብቻለሁ ለመውጣት አልችልም ብሎ እዚያው ቆሞ ሲያመነታ እንደገና ከዚያ የበለጠ መከራ በላዩ ላይ መጥቶበት ከዚያው ሞተ እንግዴህ ክፉ ለራሱ ክፉ ሥራ ሠርቼ ለንሥሐ አባቴ ነግሬ ንሥሐ ብገባ ንሥሐዬ ተወርዶልኝ አልድንም እያለ በክፉ ልማድ እየተጠራጠረ ደግሞ ብታመም መቸም አንድ ጊዜ ታምሜ አለሁና ከሞት አልድንምና አሁኑ በሽታዬ በጣም ሳይጠናብኝ ወስዳችሁ ቅበሩኝ ብሎ መቀበር ነው ብዬ ክፉ ለራሱ በሞተበት ነገር እማጡ ዳር ቆሜ ሳዝን መሰንበቻውን በኃጢአት የተከሰስኩበት ነገር ነበረና የተፈጣጠምኩበት ቀን ቀጠሮው ደርሶብኝ ጠበቃ የሚሆነኝ ሰው በሆዴ ሳሰላስል በጣም የሚያስፈራ የበረዶ ዝናብ መጥቶብኝ እዚያው እማጥ ውስጥ ሊደባልቀኝ መስሎኝ ቢያስፈራኝ ፍየል የበላ ነብር በግም ቢያገኝ አይለቅም ብዬ ሸሽቼ ወደቤቴ ሮጬ እምልጬ ገባሁ ። በኃጢአት ስለተከሰስኩበትም ሥጋዬ እየሞገተችኝ በምታታልለኝ ነገር ሁሉ ጠበቃ ከልወደድሁበት ያለጥርጥር በመልቴ እንድትረታኝ ማንም አይስተው ነገር ግን ንጽሕና የሚባለው የበግ እረኛ ፈልጌ ጠበቃ ወልጄ ከሞገትኳት የኋላ ኋላ በመጋቢያ እረትቻት ያስገባችኝን ዕዳ ሁሉ ማዘሬም አይቀርም ብዬ ነገሬን ጨረስሁ ።

ሺፈራ ወልደየስ ።

ስለ ዛፎች ዓለም ተስፋና ሕይወትነት ።

በትልቁ ንጉሠ ነገሥት በዳግማዊ ምኒልክ ጊዜ ከመልካሞች ፍሬዎች የበቀሉ ትልልቆች ዛፎች ባዲስ አበባ ከተማ ተተክለውና ለምልመው አብበው አፍርተው ። ለከተማው ሰው የሕይወት ነፋስ ሰረገሎች ። ለመንገድ አላፎች ጥላዎች ሁነው በተድላ በደስታ ከኖሩ በኋላ የመከር ጊዜ ደረሰና ታጨዱ። ከዚህም በኋላ መልካካም ወጣቶች በግራቸው ተተክተው በቀሉ ። የከተማ አገልጋዮችና የግቢ ቋሚዎች ቅጥያና ቅጠላቸውን በገጀሞ እየመለመሉ ብቻ ዘንጋቸውን እያስቀሩ ማገዶ እያደረጉ ብዙ ዛፍ አበላሹ። በዚህም ልማድ አንድ እጅግ ያማረ ደልዳላ ወጣት ዛፍ ከግር እስከ ራሱ ያፈራ ቅጠሉ ንብብር አለ ። ገጀሞ ይዘው ሲመለምሉ ሲቀርቡ የታዘዘ መልአክ መጥቶ ይቈረጣልስ ቢሏችሁስ እንዲህ ያለውን መስሏችኋልን ብሎ የብትር ዘፈን አሳይቶ መለሳቸው ። ያም ዛፍ በተአምራት ቅጥያውንም ቅጠሉንም ፍሬውንም ጠቅልሎ አንድ ግንድ መስሎ ቆመ ፤ ለምሳሌ ያገራቸውን የኢትዮጵያን መሠረት ቋንቋ ግዕዝ ለሚያውቁ በግዕዝ ለማያውቁት ባማርኛ አስረዳለሁ ።

፳፱ ዜና ሀሎ ፩ዱ ዕፅ በሀገረ ደንደራ ዘይሰመይ ጋስ በምድረ ጽዒድ ወዕፁኒ ኢኮነ ነዊኃ ወኢሐፂረ ወቄጽሉ ስፉሕ ወህብሩ ሐመልሚል ወሶበ የሐውሩ ሰብእ ወይብልዎ አዕፅ ጋስ መጽአ ኀቤከ ፋስ ዘውእቱ ማዓፄ ውእተ ጊዜ ያስተጋብዕ ቄጽሎ ወፍሬሁ ወይመስል ፩ደ ጕንደ ።

ይህም ባማርኛ ዜና እስክንድር ስመለከት በሀያ ዘጠኝኛው ዜና ወሬ ደንደራ ወረዳ ጽዒድ በሚባል አገር ጋስ የሚባል እንጨት ነበረ ። ቁመቱም እንደ ዝግባ ያልረዘመ እንደ ችፍርግ ያላጠረ ቅጠሉ ሰፋፊ መልኩ የለመለመ የሚያምር ነበረ ። ሰው ሂዶ ዕፀ ጋስ ገጀሞ የሚሉት ፋስ መጣብህ ሲሉት ቅጠሉን ቅጥያን ሸልሎ ጠቅልሎ ቆመ ። ስምዑ ዘንተ ኵልክሙ አክብሩ መንግሥተ ። ስምዑ ዘንተ ከመ ትርከቡ ሕይወተ ። የብርሃንና የሰላም ወዳጆች የውጭ አገር ባይናችን ባናይ ። እንግዳ ቋንቋ ባንናገር ብዙ ጥልቅ ምስጢር በግዕዝ ከተጻፉት መጻሕፍት እንዲገኙ ሁላችሁም ያለ ጥርጥር ታውቁታላችሁ ። እኛም የቅኔ መምራችን ብርሃንና ሰላም ሲዘርፍልን ጊዜ ያገር ፍቅር ጉባኤ ቃናን ማጋጠም ይዘናልና መንገዱን የለመዳችሁ እንድታርሙልን በማክበር እማልዳችኋለሁ ።

አለቃ መርሻ ዘውእቱ መርስዔ ኀዘን ።

እርሱ በርሱ መረዳዳት ።

ፍትሁ ለነዳይ ወለእጓለ ማውታ ። ወአጽድቁ ግፉዓ ወምስኪነ ። ወአድኅኑ ባሕታዌ ወዕኑሠ ። አንትሙሰ ከመ ሰብእ ትመውቱ ። ወከመ አሐዱ እመላእክት ትወድቁ መዝ ፹፪ ቁ ፫ ፬፯ ።

ለብርሃንና ሰላም ወዳጆች ቀጥሎ ያለውን ትንሽ ማመልከቻ ስጽፍ የመሰለኝን ነገር ሁሉ ለመግለጽ ብርሃንና ሰላም ለሰጡን ጌታችን ለልዕልናቸው የሚበቃ ምስጋና ባለማግኘቴ እያ

ዘንኩ ሁሉን የሚችል እግዚአብሔር ዋጋቸውን ይክፈላቸው ብዬ ምኞቴን ከጨረስሁ በኋላ ነገሬን እጀምራለሁ ።

መዠመሪያ ማናቸውም መልካም ነገር ሁሉ ሲመሠረት በእምነትና በፍቅር እንጂ በጠብና በክርክር አለ መሆኑን የሚጠራጠር ሰው ይገኝ አይመስለኝም ። አንዳንድ ተከራካሪዎች ግን ቢሆንሳ ምናልባት ቢደረግሳ ብለው የሚጠራጠሩ ይገኙ ይሆናል ። እውነታቸው ነው ። አይመጣምን ትተሽ ይመጣልን በጨሠርሽ የሚባል ተረት አለና ቢጠነቀቁ አይከፋም ።

ይሁንና በዚህ ዓለም አማኙም ታማኙም ሰዎች ናቸውና እርስ በርሳቸው ተማምነው መልካም ሥራቸውን መሥራት ነው እንጂ ሌላ የሚታመን ከሰው በቀር መልአክ አይመጣላቸውም ። ስለዚህ ለሰው ልጆች ሥራ መሠረቱ እርስ በርስ መተማመንና መፋቀር መሆኑ የተረገጠ ነገር ነውና መጠራጠር አያሻም ። ለዚሁም ማስረጃ ስማቸው የማይሞት ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ከጻፉት መጽሐፍ ጥቂት ቃል እጠቅሳለሁ ። የሰው ኑሮ መሠረት እምነት ነው ። ሰው እጸድቃለሁ ብሎ ከማመኑ የተነሣ በጎ ሥራ ይሠራል ። ዳኛም የምስክርን ቃል አምኖ ይፈርዳል ። ሴትም ባሏን አምና ወላጆቿን ትታ ትሄዳለች። ተማሪም መምሕሩ የነገረውን ቃል አምኖ የተማረውን ትምሕርት የአሳቡን መሠረት ያደርጋል ። አስተማሪው የነገረውን ቃል ተጠራጥሮ የተማረው ነገር እውነት መሆኑንና አለመሆኑን የሚጠራጠር ተማሪ ከሺህ አንድ አይገኝም ። በዚህ ዓለም የሚሠራው ሥራ የሚበዛው በእምነት ነው ። ከሰው ልብ እምነት ቢጠፋ አንዳችም ሥራ አይሠራም ነበር ። እውቀት የሌለው ሕዝብ እርስ በርሱ አይተማመንም ። ስለዚህም የሚሠራው ሥራ ጥቂት ነው ። መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር ከሚባለው መጽሐፍ ምዕራፍ ፲፪ ገጽ ፻፳፫ ተመልከት ።

እንግዲህ ወደ ቀደመ ነገሬ ልመለስ፤አሁን በቅርብ ጊዜ ክሥር ዓመት ወዲህ ከመተማመንና ከመፋቀር የተነሣ የኢትዮጵያ ልጆች መልካም ብልሃት እርስ በርስ መረዳዳት ዠምረዋል ። ይኸውም መልካም ብልሃት ስሙ እቁብ (የገንዘብ መቆጠቢያና የችግረኛ መርጃ) ይባላል አኳኋኑም ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው ። ከተማመኑ ወገኖች አንዱ ሰው ችግር ያገኘው እንደሆነ ችግሩን ለወገኖቹ ያዋያቸዋል።ለምሳሌ፡ሀያ የተማመኑ ወገኖች ቢኖሩት አምስት አምስት ብር አዋጥተው ዕለቱን ለባለ ችግሩ መቶ ብር ይሰጡታል ። ይኸንን ማለቱ በጥቂቱ ለማስረዳት ነው እንጂ እስከ አሥር እስከ ሀያም ብር ለተቸገረ ወገናቸው የሚረዱ ሰዎች አሉ ። ይህንንም የከፈሉት ገንዘብ ማሕበሩ ወስነው በሥራ አምስት ቀን ወይም በወር እንደሚከፈል አድርገው ለዚሁ ሥራ አንድ ወገን የሆኑት ማሕበሮች ሁሉ እስኪዳረሱ ድረስ እጣ እየጣሉ በእጣቸው ተራ ገንዘባቸው ይቀባበላሉ እንጂ ያ መዠመሪያ ለችግረኛው ሰው ያመጡትን ገንዘብ አይቀርባቸውም።እዩት እንዴት ያለው መልካም መንገድና ጥሩ አሳብ ነው? ተቀባዩን ለጊዜው ከችግሩ ዳነ ሰጭውም ገንዘቡን አከማቸ ማለት ነው ። እንኳን በኋላ ለሚመለስ ገንዘብ ላገር ልጅ ችግረኛ እንዲያውስ ስለ እርዳታ ቢሰጥ መልካም አይደለምን ለማለት እደፍር ነበር ። ዳሩ ግን የአሳቡን መልካምነት ለማስረዳት ስል ይህንን ቃል ስለ ጻፍኩ አንተ እራስህ ለንደዚህ ያለው እርዳታ ስንት የችሮታ ሥራ ሠርተሃል ብሎ የሚጠይቀኝ ቢገኝ የምመልስለት ነገር ምንም የለኝም ። ይሁን እንጂ አሁንም ቢሆን እላይ የጻፍኩትን ነገር በጣም መርምረው ያወቁት ሰዎች ጥቂቶች ስለሆኑ ብዙዎቹ ሰዎች ነገሩ ገና አልገባቸውምና አለመዱትም ። መልካም አሳብ መሆኑን የተረዱት ሰዎች ግን ለጊዜው ችግረኛ ወንድማቸውን እረድተውበት ለራሳቸውም ተጠቅመውበታል ።

ለወደፊት ይህን የመሰለ መልካም አሳብ እርስ በርስ መረዳዳት እየሰፋ ቢሄድ የኢትዮጵያ ልጆች ብዙ ጥቅምና መልካም ስም እንዲያገኙ ተስፋ እናደርጋለን ። የራስን ጥቅም ብቻ ከማሰብ የችግረኞችንም እርዳታ ማሰብ የሚገባ ነው ። በመጽሐፍ እንደተባለው፤ ባገርህ ደጆች ውስጥ ከሚኖሩ ከወንድሞችህ አንዱ ወደ ድህነት ቢደርስ እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጥህ ምድር ልብህን አታጽና እጅህንም አትጨብጥ በድሀው በወንድምህ ላይ ነገር ግን እጅህን ለርሱ ክፈት ብድርም ቢሻ አበድረው እንደሚሻው መጠን ዘዳግ ም ፲፭ ቁ ፯ ፰ ማቴ ም ፭ ቁ ፵፪ ። አሁንም ወደፊት ኢትዮጵያውያን ክቡራን ጌቶችና ወንድሞቼ ሆይ እንደዚሁ ሁሉ ችግረኛ ወገናችንን ከችግር እንድናድነውና ወደፊትም አንድነት ሆነን እርስ በርሳችን እንድንተጋገዝ ተስፋ አደርጋለሁ ።

ትንሽ ወንድማችሁ ተስፋዬ ካሣ።

ቋንቋችን በውጭ አገር ።

አገራችን የሚወደዱት መሬታችንና ፀሐያችን ብቻ አይደሉም ቋንቋችንም ያጠኑታል ።

ከፓሪስ ኡኒቬርሲቴ ቋንቋ ክፍል ወዳጅ ያገሬ ልጅ ይዞኝ ሄደ የፕሮፌሶር (መምህር) ማርሴል ኮሄን ማስተማርያ ቦታ ገባን ከትልቅ አዋቂ ትህትና አይጠፋምና ተነስተው ተቀበሉኝ በአማሪኛችን ኩስትር ባለች ቋንቋችን ቢያናግሩኝ ድንግር አለኝ ። አባ ተክለ ማርያም ሰምሃራይ ብዙ መጻሕፍትና ሰዋስው በግዕዝ አሳምረው ስለጻፉ በወረቀት ይተዋወቁ ነበረና የሳቸውን ሰላምታ ነገርኳቸው ዞር ብል ከግድግዳው ላይ «ረከበ ይረክብ ይርከብ» እያለ አንድ ተማሪ ይጽፍ ነበር ። ይኸንንም አሳምረው በሰዋስው አካሄድ ይፈቱት ነበር ። ፕሮፌሶር ኮሄን በአማሪኛም እንደዚሁ በብዙ ትጋት ከጥንት ጀምረው ያስተምራሉ ። ተማሮቻቸውም አለመሰልቸት በብርታት ይማራሉ እኛንም በደስታ ነው እምያዩን ።

የሚማሩባቸው መጻሕፍቶች የግዕዝ ያማሪኛ በቋንቋቸው የተተረጐመ ሰዋስውና ግሥ መጻሕፍት ናቸው ። ይልቁንም ልቤን ነክ ያረገኝ በብራና ላይ ያገራችን ደብተራ የጻፈውን ባየሁ ጊዜ ነው ። ክፍ ያለና ለክታብ እሚሆኑ መጻሕፍቶች ነበር ። ትንሹን ሳይ ብዙ ትዝታ ከልቤ ላይ ይዋልል ጀመር ። ሳቅም ይከጅለኝና ፊቴ ፈገግ ይላል ቅርም ይለኝና እንገቴን አቀረቅር ነበር ።

እንገቴን ያስቀረቀረኝ ግን ኢትዮጵያ የአውሮጳ ጐረቤት ሁና ብትሆን ስንት ትንግርት በሠራች ነበር እያልኩ እያሰብኩ ታሪኳ በግርማ አያቶቻችን በጀግንነትና በፊሊጥ የሠሩት እየ

ታየኝ ነው ። በፈርዖንና በፋርስ በግሪክ ዘመን የነበረች ኢትዮጵያችን ዛሬ ያለችበትን ስመለከት መቼ እማየውንና እምሰማውና እጥንቼ ላገሬ እበቃ ይሆን ? እያሰኘኝ ነው ።በተራራ ላይ መተከልሽ የናፍቆት መኩርያዬ ኢትዮጵያ ሆይ ዝቅታን እንዳታውቂ እንደሆነ በአንድነት በሥራ በትጋት ትዝ ይበልሽ ።

ገላግላቸው ደስታ የሶርቦን ተማሪ ፍትሐ ነገሥት ክፍል ።

የኢትዮጵያ ልጅ ገንዘብ እያለ በውጭ አገር እየሄደ የሚቀርበት ምክንያት ።

ነገሩም እንደዚህ ነው ።መቸም ሹመትና ቁመት ከልክ አያልፍም በሚባል ተረት አገር ካለ ሹመት አታድርምና እነዚያ ያገር ሹማምንት የነበረውን ትተው ያልነበረውን እየተከተሉ ደግሞም ሁለተኛ ነጭ ድሃ ነጭ ማር ይወልዳል የሚባል ተረት አለ ስለዚህ ደሀ ካላሰሩት ገንዘብ አያመጣም እያሉ እጁንና እግሩን በእግርብረት እያሰሩ በቤት ያለ ገንዘቡን አሸጠው ይቀበሉታል፡ከዚህ በኋላ ያ ደሀ ገንዘቡ ባለቀ ጊዜ እስከሁንስ ባለ ገንዘቤ ወጣሁ ለወደፊቱሳ ማን ያወጣኛል ብሎ አገሩን ጥሎ በሰው አገር ይሄዳል ።

ከዚያም ከሄደበት አገር በጭንቅና በመከራ ሳለ ደግሞ እነኛ የሄደባቸው ሰዎች ወደሀን መጣህ በግድ ቢቸግርህ ነው እንጂ ለኛ ምን ታደርግልናለህ እያሉ ይዘብበቱበታል በዚሁም ነገር መስቀ መሮት ያገኘሁትን ይገር ከአገሬ እገባለሁ ሲል ደግሞ የገራችን ያገር ሹማምንት ከትሪፖሊ የመጣ ነው ያዙት እያሉ በ፲ምክንያት ገንዘቡን ያስፋሩበታል ።

ያም አገሬ ልግባ ብሎ የመጣ ሰው ገንዘቡ ባለቀ ጊዜ እያዘነ የደም እንባ እያለቀሰ ወደ ነበረበት ይመለሳል ደግሞ እነዚያ በረኞች ሰው አይለፍ ተብሏል እያሉ የለበሰውን ጨር ሰው ገፈው ይሰዱታል፡ከዚህ በኋላ እነዚያ ሁለተኛ ደግሞ የሚሄድባቸው ሰዎች ለዚህ ነው አገሬ ልሂድ ያልከው ከኛ ያወጣሽውን ለመጨረስ ራቁትህን ለመመለስ ነው እያሉ ይስቁበታል እሱም ያገኘውን ጭንቅና መከራ አገሬ ብየ ሂጄ እንደዚህ ያለ ነገር አገኘኝ እያለ ያወራል የቀሩትም ለዚህማ ምን ይወስደናል እያለ የኢትዮጵያ ልጅ እንደወጣ ቀረ።እንግዴህ ብርሃኑን ገልጾ መንግሥቱን አስፋፍቶ ከሰጠን ግርማዊት ንግሥታችንና ልዑል አልጋ ወራሻችንን እያመሰገን የኢትዮጵያ ሰዎች ዘመዶችንን ወገኖችንን ገንዘብ እያለ በሰው አገር እየሄደ ከሚዋረደውና ከሚቀረው እያሰብንና እያስተዋልን ብንመረምረው ያገራችን ልጅ ስደት ባልሄደም ነበር ፡፡

አሁንም በዚህ ነገር እናስተውል እንመራመር፡፡ማስተዋልና መመርመር ማለት መንግሥት በወጣው ገንዘብ ገበያ ማድረግ ነው ። አሁን እንኳ በዚሁ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ከመቀሌ ገበያ የዳግማዊ ምኒልክ ስዕል ያለበትን አይቀበሉትም ይልቁንም ይህ የድንቁርና በሕርይ ያሰኛል ደንብ ያለ መስማት ያህል ነው አሁን እንኳን በምሳሌ በአገራችን ችግሮች ገንዘብ ላገኝ ብሎ በውጭ አገር የሄደ በ፩ወረቀት መቸም ቃሉ የማይጣስ ነውና ፩ዓመት ያገለግላል ያም ወረቀት የንጉሥ ቃል ነውና ብዙ ገንዘብ ያወጣል። አሁን ግን ንግሥታችንና ልዑላችን ለኢትዮጵያ ለአገራቸው ማስተዳደርያ የሚሆን ሸክሙ የማይከብድ በንግሥታችን ስምና በልዑላችን ስም የታተመ እንደ ፍራንክ ዓይነት የሆነ ወረቀት ክቡር ገንዘብ አውጥተው አዋጅ አድርገው እሱን የያዘ ብር የፈለገ ብር እህል የፈለገ እህል እንደ ሩብና እንደ መሐለቅ ቢመነዘር እጅግ መልካም በሆነ ።

ደግሞ ይህ አዲስ የሚወጣ የመንግሥት ገንዘብ ሰው በግድ ሳይሆን በውድ እንዲ ለምደው ። የኢትዮጵያ ልጅ ገንዘብ እያለ ወደ ውጪ ባልሄደ ሥራም የሚፈልገውን ከአዲስአበባ እስከ ደሴ ። ከደሴ እስከ ደብረ ታቦር የመንግሥት መዛወሪያ የኦቶመቢል መንገድ የትልልቅ ውሃም ድልድይ ቢሠራ መልካም ይመስለኛል ፡፡ ያም የወጣ ገንዘብ አዲስ ዓይነት በዚህ ይለመዳል።ገንዘቡም አስቀድሞ ከመኳንንትና ከወታደር ይጀመራል ደግሞ ሽፍታ ቀማኛ ያለበት አገር ራያ አዘቦ ዋጃ ትከዜ ጨጨሆ ውጫሌ ጥራሪ በዚህ አገር ብዙ ወታደር ቢቀመጥ ነጋዴ አይቀማም ነፍስ አይሞትም ሕዝብም ይጠበቃል ቀለቡም ያ የመንግሥት አዲስ ዓይነት ገንዘብ ይሆናል ። ያንም ያገር ዘበኛ ከአለበት አገር ሸምቶ ይበላል ። እንደዚህ ሲሆን ያ ወደ ሌላ አገር የሚሄደው ሕዝብ ከዚሁ ይቀራል ። ሕዝብ ሲበዛ ጠፍ መሬት ይቀናል ። ጠፍ መሬት ሲቀና እህል ይበዛል ። እኔም ይህንን ነገር ያሰብኩት ከዚህ ከተናገርኩት ሁሉ አንድ ቃል ቢገኝ ለመንግሥት እርዳታ ይሆንልኛል ብዬ ነው እንጂ እውነት እኔ ድሃ ቃሌ ከመንግሥት የሚነገር አይደለም ግን በመሰለኝ ተናገርኩ ።

ትንሹ ልጃችሁ ኃይሉ ገብረ ማርያም ፡፡

ስለ ሹመት ።

መጋቢት ፲፮ቀን ፲፱፻፳ ዓመት ክቡር ፊታውራሪ ሣህሉ ጊንርን ተሾሙ

ክቡር ፊታውራሪ ዋጋቁ በሩድ ቤትን ተሾሙ
ክቡር ቀኛዝማች ደስሜ ፊታውራሪ ተባሉ
ክቡር ግራዝማችክልክሌ ቀኛዝማች ተባሉ
ክቡር ግራዝማች ወልደ ዮሐንስ ቀኛዝማች ተባሉ
ክቡር ባላንባራስ ዘውዴ ቀኛዝማች ተባሉ
ክቡር ባላንባራስ ኃይሉ ቀኛዝማች ተባሉ
ክቡር ልጅ በዛብህ ስለሺ ግራዝማች ተባሉ
ክቡር ባላንባራስ በቀለ ግራዝማች ተባሉ
ክቡር ልጅ ክብረት በንትይርጉ ባላንባራስ ተባሉ
ክቡር ኃይለ ማርያም ማንከልክሉ ባላንባራስ ተባሉ
ክቡር ፊታውራሪ አበበ ሽልማት ተሸለሙ ።

ብርሃንና ሰላም አዲስ ሹመት ለተቀበሉ ክቡራን መኳንንት የሕዝቡን ጠቀሜትና ለሀገራቸው ልማት እያሰቡ ለመንግሥታቸው እንዲያገለግሉ እየተመኘ እንኳን ደስ አላችሁ ይላል ።

ማስታወቂያ ።

ሺብሮሌ ኦቶሞቢል በኢትዮጵያ ወኪል ።
ሔ ሜ ዜርቦስ ኩምፓንያ ።

Automobiles CHEVROLET
H. M. ZERVOS & Cie
REPRESENTANTS
BAS PRIX HAUTE QUALITE

ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትርሜጓው	፪ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ተኩል
የቁጥር ትምርት	፩ብር
ያማሪኛ ሰዋስው	፩ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	አላድ
ወዳጄ ልቤ	
አጭር የዓለም ታሪክ	አላድ
ያማሪኛ ፊደል	ሩብ
አሳብና ምኞት	ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት	ሩብ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር	፪መ
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ	ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ	፩ሩብ

ማስታወቂያ

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚገኙ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
ደግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፫ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር	፱ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ብር
ጎሐ ጽባሕ	፫ብር
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፪መ
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ብር
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ብር

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲ ብር ፲ መ
የሲዳሞ ቡና	፩	፲ ብር
ዝባድ	፩ ወቄት	፫ ብር
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፩ ብር ተኩል
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፬ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፯ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ክረጃ	፰ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ክረጃ	፲፰ ብር ተኩል
አቡጀዲ መነጽር	፩ ክረጃ	፪፻፱ ብር
፡፡ ባለሰይጣን	፡፡	፪፺ ብር
፡፡ ባለ ድመት ።		፪፻፫ ብር
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፪፳፬ ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፪፻፫ ብር
ባለ አንበሳ	፡፡	፪፺፫ ብር
ሱካር	፩ ጁኒያ	፳፰
ቻይ	፩ ነጥር	፩ ብር

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ
አንድ ብር	ሊሬ ፰ ከ፲፰ ሳንቲም
ባንድ ጊኒ	፲ ብር ከ ፲፭
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፬ ብር

COGNAC S&E&A.METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ፡፡

ማስታወቂያ

መጽሐፍና ደብተር የሚያስጠርዝ ሰው በርካሽ ዋጋ በልውል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ይጠረዝለታል ።

ያረጀ መጽሐፍና መዝገብ ማሳደስ ለፈለገ ሰው በርካሽ ዋጋ እንደ አዲስ አድርገን እንጠርዝ ለታለን ።

OMEGA



፤አውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዖሜጋ ቦቢ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

RUGBY

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኀይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኀይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶመቢል በተለይ ወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፡ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፥ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ባርባሬሶ

ኮ ኛ ክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ ።

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህ በካፑሱሉ ያለ ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በካፑሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ጉዶደርጎዙ





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው ።በሌላጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ፤ ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት እልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አራተኛ ዓመት ፤ ቍጥር ፲፬
4 me ANNÉE № 14

ሐሙስ መጋቢት ፳፯ ቀን፥ ፲፱፻፳ ዓ ም ።
JEUDI 5 AVRIL 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

ባዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ አዲስ አበባ ከተማ ችግር ።

፩ኛ አሁን በከተማ እህል በጣም ውድ ከሆነ ፪ዓመት ሊሆን ነው ። በመጀመሪያው ጊዜ እህሉን ዝናብ ስለጐዳው መስሎን ነበረ. አሁን ግን ውሎ አድሮ ያው ሆነ ።ደግሞ እህል ብቻ አይደለም ማር ቅባኑግ ቅቤ ሳር ዕንጨት ሁሉም ነገር ውድ ሆነ ምክንያቱም አስተውለን ብናየው በከተማው ሰው ስለበዛ ነው ።ዛሬ በከተማ ውስጥ ያለው ሕዝብ እንደ ቀድሞው ፲ ዕጥፍ ይሆናል ወደፊትም ቢሆን የባላገርን አኑዋኗር ተመሮ የከተማው ኑሮ የሚሻል እየመሰለው ያለ ልክ እየበዛ ያድራል ። ስለዚህ ቀድሞ የከተማውን ሰው ዓመት የሚበቃው እህል በአቢቹ በጊዳ በሙሎ በበቾ በአዳ በምንጃር በነዚህ ክበብ የታረሰው እህል ነው ። አሁን ግን በዚህ ክበብ የታረሰው እህል የከተማውን ሰው ለ፫ ወር እንኳ የማይበቃ ነው ። ስለዚህ በግድ እህል ከአሩሲ ከጨሊያ ከሰላሌ ሩቅ ካለው አገር ሁሉ ማምጣት የሚያስፈልግ ሆነ ። ያ እህል ጭኖ የሚያመጣው ነጋዴ ደግሞ የበቅሎውን ኪራይና ትርፍ መቍጠር በግድ የሚያስፈልገው ነው ። አሁን ዛሬ እህል ውድ ስለሆነ ብቻ አይምሰላችሁ የነጋዴውን የበቅሎ ኪራይ ጨምረን የምንሸምት ስለሆነ ነው ስለዚህ በአራቱ ማዕዘን ሁሉ ቀጫጭን የሆኑ የብረት መንገዶች እንኳ ካልተሠሩ ወይም በሐዲድ የሚሄድ ትራሞይ ወይም በሐዲድ የሚሄድ ካሚዮን በወሀ ፏፏቴ በኤሌክትሪክ የሚሄድ ካልተሠራ እስከ ጥቂት ጌዜ ሕዝቡም በዝቶ ፩ ቁና እህል በ፪ በ፫ብር እንዳይሸመት ያስፈራል ። በኢትዮጵያ የውሀ ፏፏቴ ለኤሌክትሪክ የሚሆን ሞልቷል በሱ የሚሄድ ትራሞይና በቡርም ዋጋው እርካሽ ነው ለሚሠራውም ኩምፓንያ ጥቅሙ ብዙ ነው ይኸ ካልሆነ ግን የአዲስ አበባን ከተማ ወደ ፊት ብዙ ችግር ያገኛታል ።

፪ኛ አሁን ወደ ውጭ በየማዕዘኑ ባቡር ቢሠራ እህል እንጨት ማር ቅቤ በኢትዮጵያ አውራጃ ሁሉ መጥቶ ለከተማው ይረክስለታል ደግሞ እህል አርሶ ከብት አርብቶ ለሚሸጠውም ባላገር በፍጥነት ስለመጣ ከብቱ ሳይከሳ ቅቤው ሳይበላሽ እህሉም ሳይጉላላ በደህና ዋጋ ይሸጥለታል መኳንንቱም ከዳር አገር ያላቸው ሰንጋ ማር እህል በፍጥነት በርካሽ ይመጣላቸዋል ስለዚህ ያ ሲመጣላቸው እዚህ ከገበያ ገዝተው ደኻውና ደጅ ጠኚው አይወደድበትም ።በከተማ ውስጥ ትራሞይ ቢሠራ ሁሉም ሰው በየቤቱ በቅሎ ፈረስ አጋሰስ ማሰር ይቀራል በቤሳ በተሙን አቃቂ ቀበና ሂዶ ይመጣል ያንየ የሰርድርቆሽ መግዛት ይቀራል የሳር ክልክል የሚሆነውም መሬት ሁሉ እህል ይታረሳል ሳሩ ለላሞች ይሆናል አታክልት ይተከልበታል አሁን ዛሬ ለሳር ክልክል የሚሆነው ብዙ ሽህ ጋሻ መሬት በእርሻና በጥቅም ይጨመራል የከተማው ሰውም በየስፍራው ሁሉ ጉዳዩን በፍጥነት ይጨርሳል የሚበዛውን የከተማ ችግር ሁሉ ያስቀራል ። አሁን ዛሬ በከተማ ያለው ችግር ብዙ ነው እንኳንና ሌላ ስለ መንገዱ መጥበብ በአቶመቢል የመጣው ችግር ስለ ፩ መቅሠፍት የሚቆጠር ሁኖዋል ።

ነጂዎችም መንዳቱን ያውቁታልና እንደ ጥይት ይለቁታል ገባያተኛው ሳር እህል እንጨት ጭኖ በግ ነድቶ የጉንደን ጉዞ መስሎ ከአራዳ በቀር በከተማው ሌላ ገቢያ ስለሌለ ወደ አራዳ ይጓዛል ። ያንየ ትንሽ እንኳ ፍርሃት የሌለበት የ፳ ፈረስ ጉልበት ያለው አቶመቢል ገቢያው ህዝቡ ትንኝ እንኳ ሳይመስለው ተቀኝና ተግራ እንደ ጥይት እየበረረ ሲመጣበት ሕዝቡ የጭነቱን ከብት በጉን ሸቅብ ቁልቁል ሲያሸብረው መንገደኛው ፳፳ ሜትር ሳይሄድ ግራና ቀኝ ሲሸሽ ሲሸበር ቆሞ ያየ ሰው በከተማው ወሬሳ የገባበት ይመስለዋል ከመንገዱ ዳር ቆሞ ሲያዩት በጣም የሚያሳዝን ነው ሕዝቡ ከወደ ፊት አቶመ

ቢል መጥቶበት ሲሸሽ ሌላ አቶሞቢል ድምጡ ሳይሰማ በጐኑ ወይም በስተኋላው ሌላው ይመጣበታል ያንየ ገባያተኛው ሲሸሽ የመንገደኛ በቅሎ ባለቤቱን ጥሎ ሲሮጥ የነጋዴ የጭነት ከብት ከነጭነቱ ደንብሮ እኩሉ የተጫነውን ጭነት ከምድር ጥሎ እኩሉ እንደ ተጫነ በከተማ ውስጥ ሲበታትን ነጋዴዎቹ እኩሉ የሸሸውን ከብት ሲያባርር እኩሉ የወደቀውን ጭነት ሲሸክም ብዙ ችግር ነው በመንገዱ የሚሄደውም ሰው ብዙ ይታወካል ዕለት ዕለትም ሰው ይሰበራል ይሞታል መቼም ይኸ ሁሉ መሆኑ ድንጋይና ብረት ሲጋጭ ቡላድ ሆኖ እሳት እንደሚወጣው ሁሉ የኤውሮፓ ሐዲስ የሥልጣኔ አኑዋኖርና የኢትዮጵያ አሮጌው አኑዋኖር ስለተጋጨ ነው በአቶመቢል መሔድ ሐዲሱ የኤውሮፓና የአሜሪካ የሥልጣኔ አኑዋኖር ነው ደግሞ ለሰው ለእግረኛና ለአቶመቢል ክፍል ሳይበጅለት በጠባብ መንገድ መሔድ እህል ሳር እንጨት ባህያ በበቅሎ ጭኖ በአንድ ገቢያ ውስጥ መሰብሰብ የኢትዮጵያ የቀድሞው አኑዋኖር ነው ድግሞ ቀድሞ የነበሩ ከተሞች ፩ሺ ፪ሺ ቤቶች ያሉበት ፲ሺ ፳ሺ ሕዝብ የሚኖሩባቸው ከተሞች ናቸው ምንም ያህል ጉዳት አያገኛቸውም ነበር በዚያ ግምት አይቻልም የዛሬው አዲስ አበባ ግን ምንም እርግጡ ባይታወቅ እ^ከ ፪፻ሺ የሚሆን ሕዝብ ወይም የሚበልጥ አለበት አዲስ አበባ ስፋቱም ከሾላ ሚካኤል እስከ አቃቂ ፋሊ ዶሮ ቤት የ፪ ሰዓት መንገድ ነው እንደዚህ ሰፊ በመሆኑ ሕዝብ በመብዛቱም አልፎ አልፎ መልክም ቤት መሥራቱ የድንጋይ መንገድ መሥራቱ የኤውሮፖች ከተማ አኳሆን ነው።ደግሞ በከተማ ትራሞይ የኤሌክትሪክ መብራት በበምቦ የተከፋፈለ ውሀ ያለመኖሩ ከተማው እንደሌላው የዓለም ከተማ ያለመጥዳቱ ገቢያው በየከተማው አውራጃ የተከፋፈለ ያለመሆኑ እንደ ቀድሞው የኢትዮጵያ ከተሞች አኑዋዋር ነው። ስለዚህ ይኸ የሁለቱ አኳሆን ሲጋጭ ግጭቱ ህዝቡን የሚጐዳ እሳት ይወልዳል። መቼም ዛሬ ባቡር በ፩ ፳መንገድ ለመሀርጋት ደግሞም በከተማ ውስጥ ትራሞይ ኤሌክትሪክ ለማበጀት የውሀ በምበ ለመጠጥና ቆሻሻ ለመጥረግ ከምድር ውስጥ ለመቅበር የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚበቃ ገንዘብ አያገኝም ኩምፓንያ ለማቆምም ለዚህ የሚበቃ ትምህርት የለውም የኢትዮጵያ ሕዝብ (የኤጁኬሽን) የሥልጣኔ ትምህርት አግኝቶ የሚበቃ ገንዘብም አግኝቶ ይኸን እስቲሠራ ፴ ፵ ዓመት ይቆያል

ደግሞ ለውጭ ሰው ኩምፓኒያ ቢሰጥና የውጭ ሰው ቢሠራው የአገራችነን ጥቅም ሁሉ ለሌላ ህዝብ ሰጥተን በኋላ መጠጠት ይሆናል ይመስለናል ግን ሳይሠራ ቢቆይም ለኛ ጥቅም አይሆነንም ይልቁን የውጭ ሰው ሠርቶት በባቡርና በትራሞይ የምናገኘው ጥቅም ይቀርብናል ስለዚህ ባይሠራም ጉዳት እንጅ ጥቅም እንዳናገኝበት ገምተን የታመነ ባለ ብዙ ገንዘብ የውጭ ኩምፓኒያ አምጥተን እኛም የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚቻለንን ያህል ከኩምፓንያው ውስጥ ገንዘብ ጨምረን ብናሠራው መልካም ይሆናል ይኸን የሚሠራ ኩምፓኒያም የማይወሳልት መልካም ኩምፓኒያ ካገሩና እንሥራ ብለን ጠርተን አምጥተን ነውእስከ ፶ና ፷ዓመት ለኛ ይገባ የነበረውን ጥቅም የውጭ ህዝብ ሊበላው ነው ብለን ብንገምተው እውነት ይመስላል ደግሞም እርምጃችነን ብንገምተው እኛ ችለን ይኸን ሥራ እስትንሠራ ፶ና ፷ዓመት የሚቆይ ይመስላል።ስለዚህ ዝም ብሎ ከሚቆይ ደግሞ የውጭ ሰውም ተጠቅሞበት እኛንም አገልግሎቱ ቢጠቅመን ይሻለናል ሸማኔ ፈትል ፈትሎ የፈትልም ዋጋ የእጅ ሥራም ዋጋ የሚያገኝ ቢሆን መልካም በሆነለት ነበር ግን ይኸ የማይቻል ስለሆነ ፈታዩቱ ሌላ ሆና ሸማኔው የእጅ ሥራ ዋጋ ብቻ ያገኛል ደግሞ ፈትሉንና ሥራውን አንድ ላይ በማኪና የሚሠሩ ህዝቦች የሁለቱም ሥራ ሠርተው የ፪ንም ዋጋ ያገኛሉ ግን መኪናን በብዙ ድካም ካገኙት በኋላ ነው ደግሞ በፊትም መኪናው ፪ቱን ፩ላይ የሚሠራው እስቲገኝ ብለው ሥራ አልፈቱም እጅ ሥራ ዋጋ ብቻ አገኝተው ሲሠሩ ነበሩ እንጂ

ጥቂት ልበ ወለድ ተረቶች
ገንዘብ ስጡኝ ባይ ሠራተኛ ነው
ገንዘብ እንኩ ባይ ግን አታላይ ተንኮለኛ ነው
ሐሳብ ይታመማል ወይ ?
አዎን ማመናታት ሲበዛ እመም ይሆነዋል
ሐሳብ ይሞታል ወይ
አዎን ተስፋ ሲያጣ ይሞታል
ሥራ ይታመማል ወይ ?
አዎን ሠሪው ፪፫ ሥራ ሲሠራ ይታመማል
ሥራ ይሞታል ወይ
አዎን ሠሪው ያለ ኦርጋንዜሽንና ያለ ፕሮግራም ፳፮ ሥራ ሲሠራ ይሞታል
ሥራ ይቀበራል ወይ
አዎን መርሳት መቃብሩ ነው
መርሳትንም የሚያመጣ ብዙ ዓይነት ሥራ መሥራት ነው
ሥራ ከሞተ በኋላ ትንሣኤ አለው ወይ
አዎን ኦርጋንዜሽንና ፕሮግራም ትንሣኤው ነው

ኦርጋንዜሽን ማለት ለሥራ ሁሉ ክፍል ማበጀት ነው ፕሮግራም ማለትም ወደፊት ለዕለት ለሳምንት ለወር ለዓመት የሚሠራውን ሥራ በተራ ጽፎ ማሰናዳት ነው ።

ፌ ዴሬሳ

ደስ እሚአሰኝ ወሬ ።

አዲሱ ትውልድ የትምሕርትን ነገር በጣም እንደፈለገ አውቀው ቅንነት ያላቸው መኳንንት በየግዛታቸው የትምሕርት ቤት ለማቆም አስበዋል መቸም ራስ ናደው የመጀመሪያውን ዕድል ተቀብለዋል ። ደግሞ አሁን ደጃዝማች ብሩ ወልደ ገብርኤል በሲዳሞ አውራጃ የተምሕርት ቤት ለማቆም አስበዋል መምሕራንም ከኤውሮፓ ሊአስመጡ ቴሌግራም አሳልፈዋል ብሎ እማይጠረጠር ሰው ነገረኝ በሲዳሞ ያሉ ጋሎች ያመትና የወር ቁጥር አማያውቁ የዋሆች ቀኖች ናቸው ይባላሉ ሕፃናቱ በትምሕርት አድገው ለቁም ነገር በበቁ ጊዜ አገሩን ለሚወድ ሰው ሁሉ ምን ያህል ደስ ያሰኙት ይሆን ።

ደግሞ ደጃዝማች ደስታ ዳምጠው በከፋ የትምሕርት ቤት ሳያቆሙ አይቀሩም ብለን ተስፋ እናደርጋለን ። ስለ ሀገራቸው መልካም አሳቢዎችን ሁሉ እግዚአብሔር ይርዳቸው ።

መንፈሳዊት ቤተ ክርስቲያንም በኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖት የምታምነውን ሰው አማርኛና ግዕዝ እንዲአስተምር የላከች እንደሆነ ልጆችም ይጠቀማሉ።የሮፕ ትምሕርት ባገራችን የበዛ እንደሆነ ሃይማኖት ይጠፋል የሚሉ የዋሆች አስመሳይና የጽድቅ ጠላትም ያርፋሉ ። መቸም የውቀት መድፈኛው የሃይማኖት ምክንያት ነው ። ይህንም ካህን ለቅናቱ ሃይማኖተ ያለብሳ ብሎ ባለ ቅኔ ወስዶታል ። ደግሞ ባራተኛው ዓመት በቁጥር ፲፩ ብርሃንና ሰላም ከወንድማችን አቶ ተማኑ ሮምሃ የተጻፈውን ተረት ባነበብሁ ጊዜ አንድ ሰው የተናገረው ቃል ትዝ አለኝ ። አባ ምንይዋብ እንደልባቸው ሲናገሩ ሰምቶ ወይ አእምሮ የኒህን ሽማግሌ ያህል ነፃ አጣህን? አለ ። አንዱ ደግሞ አእምሮ ነፃነት ታገኘማ ብርሃንና ሰላም ያገኝ አልነበረምን? አለ ። ይህ ሰው እውነቱን ነው እኮ አእምሮ ነፃነት ቢአገኝ ብርሃን ያይብናል ብሎ ሰው ሁሉ ተኃጢአት ይርቅ ነበር ። አሰትም ነገር ቢጽፍ እንደ ደምቡ ጸሐፊው ያልፍበታልና ለጋዜጣው ነፃነቱን እንዲመርቁለት አመለክታለሁ ።

የብርሃንና ሰላም አማላጅ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ።

በድሀይቱ ጎጆ ።

ጠይቀውኝ የነበረውን የተወደዱ ቄስን ብድር መመለስ እንዲገባኝ እኔም በተራዬ ሰኞ ሰለት በ፱ ሰዓት ከማታው ወደ ቤታቸው ሄድሁ ቤታቸውም በትንንሽ ክፍል ቤቶች የተከፋፈሉ ነበሩ እነሱም ጠባቦችና የጨለሙ ነበሩ እንደመስኮት ትንንሽ ቀዳዶች ነበሩባቸው፡ ባየሁዋቸው ግዜ ከሲቤሪ መስኮብ አገር ያየሁዋቸውን ቤቶች አሳሰቡኝ ለመሆኑ የሚበቃ ያህል እንዳቅማቸው ጥዳት ነበራቸው የቤቱ ሰቃ አመሳሰል ሕግጋቱም እንደኢትዮጵያና እንዳውሮጳ ከ፪ቱም ጥቅስ ያመጡ ነበር።

በደረስሁ ግዜ የተወደዱ ቄስ በደስታ ተቀበሉኝ ፊታቸውንም ብመለከት የድፍረትና የደስደስ ያለው ሆኖ ታየኝ።ጥያቄና መልሳቸውም በፍጹም ብርታት የመላበት ነው ንግግራቸው ሁሉ በትእዛዝ ነው።እጄንም ይዘው የኢትዮጵያ ሥራ በመሰለ መቀመጫ ላይ አስቀመጡኝ ከተቀመጥሁ በኋላ እዚህ መቀመጫ ላይ ተቀመጥ ያልኩበትን እነግርሃለሁ አሉኝ።ይህንንም ባሉኝ ግዜ ምን አዲስ ነገር ይነግሩኝ ይሆን ብዬ እጠባበቃቸው ነበረ ። እርሳቸው ከዚህ ቀጥሎ እንደተጻፈው ይነግሩኝ ጀመረ።

ክቡር ካፒቴን ሆይ የኢትዮጵያን ጠላ እጋብዞታለሁ እምቢ እንዳይሉኝ ፈቃድዎን እለምናለሁ ይህንንም ስላልኩዎ የኤሮፖን መጠጦች የነቀፍኩ አይምሰልዎ አሁን አይደለም በእጂ ጣት እንዲጠጡት ምልክት ሰጥዎት ይጠጡታል።በትንሺቱ ጐጆዬ ውስጥ ሳሉ በአራቱ ግድግዳ ላይ የተሰቀሉትን ጽሕፎች አሳይዎታለሁ የጠለቀውን የልቤን አሳብ ሁሉ እገልጽልዎታለሁ በፊትዎ ያረጀውን የጎጆዬን መዝግያ እከፍታለሁና አለማማሩን አይመልከቱ ይህ ለልጅ ልጅ የሚያልፍ አይደለም ድንገተኛ የዓለም ጨዋታ ነው እንጂ ።

ይህንንም ካሉኝ በኋላ እጃቸውን ከፍ አደረጉና ብርጭቆህን አሳየኝ አሉኝና ጠጣው አሉኝ።ይህም ሁሉ ሲሆን ንግግራቸው በትእዛዝ ነበረ ።

ከዚህም በኋላ እበሩ ላይ ሰቅለውት የነበረውን ጽሕፈት በጣታቸው አመለከቱኝ ጽሕፈቱም እንዲህ ይል ነበረ ፤ በመንግሥቴና ባገሬ እታመናለሁ ከሁሉ በፊት ከሁሉ በላይ መንግሥት ነው መንግሥትም ማለት አንድ ላይ የተሰበሰበ በፍቅር የተሳሰሩ ወንድማማቾች ወይም ጓደኞች ማለት ነው ። ይህም የተለመደው ጠባያችንና ከጥንት የነበረው ልምዳችን ነው ። መንግሥታችን ያለችበት ምድር የተዋበች የታወቀችና የተቀደሰች ናት የኢትዮጵያ መንግሥት ከብዙ ዘመን በፊት የነበረች ናት ታሪኳንም መሥርታለች በቀደምትነትዋ ከሁሉ የበለጠች ለኛም የመጀመሪያዎቹን አባቶቻችንን ያፈራችልን ናት።የቀደሙትም አባቶቻችን ዛሬ የሉም ሲወርድ ሲዋረድ የቆየን ሥራቸውና ጠባያቸው ነው እንጂ ። ስለዚህ በግምባራችን የህፍረት ምልክት ጥላት አንቀበም አባቶቻችን በሄዱበት መንገድ እድንሄድ ይገባናል ።

እልቅ መሳፍርት በሌላቸው በሞቱት ቅዱሳን አባቶቻችን ስም ስለት እንሳላለን ኑዛዜዎቻቸውንም እናከብራለን እናስበውማለን የረገጡትንም መሬት እንመዝናለን። ከዚህም በኋላ ንብቡን ስጨርስ የተወደዱት ቄስ እጃቸውን ከፍ አድርገው ሁለትኛውን ብርጭቆ እንድጠጣ አዘዙኝ እኔም ትዛዛቸውን ፈጸምኩ።

ደግሞ እጃቸውን ወደ አንደኛው ጽሕፈት አመለከቱኝና እንዲህ አሉኝ፤ አንተው ራስህን እወቅ ይኸው እንግዴህ የምናውቅበት ግዜ ደርሶአለን የሰው መተባበር መንግሥትን ያቆማል

ባለመታደል ብዙዎቹ ታላላቅ ሰዎቻችን የዚህን ጽሕፈት ፍችና ፍልስፍና አላወቁም እውቀት ስላነሳቸው የነገሩን ፍቺ ጠልቀው መመርመር ተሳናቸው ይህም የሚያሳዝን ነው ባለመማራቸው ይልቁንም የተማሩትን ልጆቻቸውን ባለማቅረባቸው ወደ ጥፋትና ውርደት ተመሩ።

እንግዴህ ይህ እንዳይሆንብን የመጀመሪያዎች አባቶቻችን በጊዜያቸው እንዴት እንደነበረ ልማዳቸውን እንመረምራለን ይልቁንም ታሪኮቻችንን ስናነብ አባቶቻችን እንደምን በሚመጣባቸው መከራ ሁሉ በንቀትና በድፍረት ወደ ፊት እየገፉ እንዲሄዱ እናውቃለን።ለነጻነታችንም በብርታትና በጉብዝና እንደተዋጉ እናያለን ከዚህም በኋላ ሕዝባችን በየቤቱ ከትንንሽ መከራት በታች ተቀምጦ የፈሎሰፍ ዘፈን ይዘፍን ነበረ በቤቱም ውስጥ የጢስ መውጫውን ይጠብቅ ነበረ።እኛም የነዚህ የደፋሮች ሕዝብ ዘር ነንና የዛሬውን ኑሮዋቸውን እንመርምር የሚያስፈራራንንና የሚዝትብንን አደጋ እንድንመልሰው ኃይላችን እና እውቀታችንን እንመርምር።የሚያስቸግር ቀን በመጣብን ጊዜ በፍጥነት እንድንገባበትና እጅ ለጅ ተያይዘን አንድ ጋር ሆነን አገራችንን ነጻነቷን እንዳናስደፍርባት ማድረግ የግድ አለብን ለሥልጣኔዋም እንዲሁም መጣር ይገባናል ።

ያለፉት ታሪኮቻችንን ሲነገሩ ጆሮቻችንን አዘንብለን ብናዳምጣቸው በነጻነት እንኑር በነጻነት እንኑር ሲሉ ጩኸታቸው ይሰማል ።

እነሆ ስለቶቻችን እነዚህ ናቸው ።

ይህንንም ካነበብሁ በኋላ ክቡር ቄስ ሶስተኛው ብርጭቆ ጠጣ አሉኝ በተናገሩም ጊዜ ሁሉ ንግግራቸው ትእዛዝ ነበረ

እኔም ለቃላቸው ከመታዘዝ በተቀር ምንም ማድረግ አልቻልኩም ፡

ወደ ኋላቸው ዞር አሉና ከጢስ መውጫው አጠገብ የተሰቀለውን ጽሕፈት በእጃቸው ጣት አንብብ ብለው አመለከቱኝ የተሰቀለውም ጽሕፈት እንዲህ ይል ነበረ ፤

ወደ ብርሃን ምንጭ ከብዙ ዘመን ጀምረን እንሮጣለን ግን እኛው ራሳችን በውስጣችን ይልቁንም በውጭ በምናደርገው አካሄዳችን እንቅፋት አብጅተን እንዳንደርስበት እንከለከላለን ።

አረመኔዎች ከነበሩበት ዘመን ጀምሮ የቆየን የሥልጣኔና ያስተዳደግ እሳት እስከ ዛሬ ድረስ ለአዝያና ለአፍሪካ እመኸክል የቆመ ብርሃን አይሆንም የሚል ማነው ለአፍሪካና ለአዝያ አንድ ቀን ከፍ ያለ ትልቅ ብርሃን የሚሰጥ መብራት አይሆኑም የሚለንስ ማነው ። የዓለም ዋና ዋና ታሪኮችና መንግሥታት በብዙ ይመሰክሩልናል ከነሱም መጀመሪያው ዣፖን ነው እርሱም እጅግ የበዛ ሥልጣኔ አግኝቶአልና ።

እንበለ ብርሃን ማናቸውም መንግሥት ሊኖር ኃይል ለማግኘት አይችልም ድል በሚነሣው ታሪካችን ላይ መጋረጃ መጋረድ አይገባንም ይልቁንም የብርሃን ጋኖቻችን ባዶ ናቸው መበላችን ለኛ እጅግ ከሃሞት ከሬት ይልቅ የመረረ ነው ።

ወደ ብርሃን ምንጭ በደስታ ከከንፈሮቻችን ከሚወጡት የናፍቆት ዜማ እያዜምን እንሮጣለን ።

ይህንንም አንብቤ ከጨረስሁ በኋላ ክቡር ቄስ እጃቸውን ወደ ላይ ከፍ አድርገው አራተኛውን ብርጭቆ እንድጠጣ አዘዙኝ ቀጥለው ወደ ግራ እግርግዳ ላይ በግራ በኩል የተሰቀለውን ጽሕፈት ተመልከት አሉኝ ። ጽሕፈቱም እንዲህ ይል ነበረ፣ በነጻነት መኖር አለዚያ በደስታ መሞት ። ይህንንም ካየሁ በኋላ የብርጭቆዬን ሳልጠጣው በጄ እንደ ጨበጥሁት ድንገት አንዲት ትኋን ጥልቅ አለችበት ላወጣትም ብሞክር ክቡር ቄስ በኃይልና በቁጣ ቃል ቀጥሎ ያለውን ተናገሩኝ ። ይተውት ይተዋት በጠላው ውስጥ ትሙት ማናቸውም መሰናክል ሁሉ አልፈልግም ለነጻነታችንና ለሥልጣኔያችን ማናቸውንም መሰናክልና እንቅፋት የሚያደርግ ሁሉ እንደዚች ትኋን መሞት ይገባዋል ወደ ዕውቀት ያስተዋለና የዕውቀትንም መንገድ ያገኘ ሕዝብ ማናቸውም መሰናክሉና መጫን ሁሉ አያግደውም ። እኔም መልሼ አልኳቸው ይህን የመረረ መጠጥ የምጠጣ እኔ ነኝ ? እርሳቸውም ይህ ላንተ የከበሬታ ደስታ የሚሰጥህ ነው ብለው መለሱልኝ ።

የተሰቀለውን ጽሕፈት እየተመለከቱ ይነግሩኝ ጀመር ። አስቀድሞ የጦር ምልክት ነበረ ዛሬ ግን የመመከቻችን ወይም የመከላከያችን ግዜ ነው የድል ነሺነታችን ታሪክ በጠረጴዛችን ላይ አለ እሱም መልስ ይሰጠው ዘንድ የማይችል ምስክራችን ነው ። በዋናው የዓለም ታሪክ ውስጥ እንደሚቻለን ያህል በወርቅ ቀለም የተጻፈ ቃል እናገኝ ዘንድ ይገባናልና እንጣር ።

በዚህ በጻፍነው ላይ ነቀፌታ የሚያወጣለት ኃጢአተኛ ነውና እንደ ትኋኒቱ መሞት ይገባዋል ።

እኔም ከዚህ በኋላ በደስታ ያችን ብርጭቆ ከጠጣሁ በኋላ እንዲህ ብዬ መለስኩላቸው ። የተወደዱ ቄስ ሆይ ፡ የሚነግሩኝ ሁሉ የፍልስፍና የፖለቲካ አማርኛው ስውር ነውና እንደሚገባኝ አድርገው ገልጸው እንዲነግሩኝ እለምንዎታለሁ ።

እርሳቸውም ቀጥለው አሉኝ ፤ እንዴት እስካሁን አልገባህ ምን ? ልባድርግ አሁንም ዓይነተኛውን ነገር እነግርሃለሁ ። መጀመሪያ ከሁሉ ይልቅ በአገሬና በመንግሥቴ እታመናለሁ ሁለተኛ አንተው እራስህን ምን እንደሆንህ እወቅ ።

ሶስተኛ ከብዙ ዘመን ጀምረን ወደ ብርሃን ምንጭ መንገድ እንሮጣለን ፤ አራተኛ በነጻነት መኖር አለዚያ የደስታ ሞት ።

በጠቅላላው ላራቱም ንግግር ፤ትምሕርት ትምሕርት ።

ይህንንም ባሉኝ ጊዜ እንዴት ያገራቸው ፍቅር ያደረባቸው ናቸው ብዬ ተደነቅሁ ደግሞም አልኳቸው የተወደዱ ቄስ ሆይ ከቅስናዎ በተቀር ለካ ሌላም ሞያ አልዎትና ፈላስፋም ያማርኛ ቅኔ አዋቂ የዓለምን ታሪክ አዋቂ ኖረዋል ከበሬታ ለርስዎ ይሁን ደግሞም ወታደርነትም አለዎት እርሳቸውም አሉኝ ይህን ወታደርነቱን ለራስዎ ጠብቁት ።

እኔም ቀጥዬ አልኳቸው አደራዎን ይተው የፍርዱን አንጫወት ፍርድ ከኋለኞች ዘንድ ነውና አሁን ለጊዜው ለዚሁ አንድ ምስክር ልስጥዎ ለኔ አራት ብርጭቆ ጠላ ሰጡኝ እርስዎ ግን አራቱን ጠርሙስ ባንድ ጊዜ ጨለጡት ይህ ፍርድ ነውን ?

የቄሱም ሐሳብ በደስታ ተናወጠና ጠላውን ጠጅ አደረጉት በዚያም የተጠጡትን ብርጭቆች ቁጥር ለማወቅ አልቻልንም ። ከዚህም በኋላ ዓለሙን ሁሉ የገዛን መሰለን ማናቸውንም ከኛ በላይ ያለውን ትእዛዝ መቀበል አልፈቀድንም ። ክቡር ቄስ ሳልጋብዛቸው ወዳጄ ከፒቴን በሚመጣው ሰሞን እርስዎ ዘንድ ነውና ይጠብቁኝ አሉኝ ። መጋቢት ፳፱ ቀን ፲፱፻፳ ዓም

ከፒቴን በቢግያን

ጥንቃቄ ።

በሃገራችን ውስጥ የበዛ የቂጥኝ በሽታ ስለገነነ የህዝባችንን ጉልበቱንና ኃይሉን የሚቀንስ በሰውነቱ ሁሉ የከፋ ቁርጥማት እየተተከለ በስቃይና በመከራ ሲኖር እናያለን ይህም በሽታ የሚገኘው የሥጋ ነገር በማድረግና እንዲሁም ከልብስና ከወዝ ከሚበላ አጥንት ከሆነ ነገር ሁሉ ይገባል እጅግ ላይን የረቀቁ እባብ የመሰሰሉ በመነጽር ለመታየት የሚቻሉ ትንንሽ ትልቁ በሰውነቱ ከረቡና ከተሰራጩ በኋላ ሁለት ወይም ሶስት እስከ አራት ሳምንት ቆይቶ እንደ እባጭ ሆኖ ይፈነዳና እየመገለም ቆይቶ አካላቱን ሁሉ ይወርሰዋል ። የበሽታውም ልዩ ልዩ ጠንካራና የደከመ በሽታ አለ አንድ አንዱም እስከ አጥንት ድረስ ለመስበር ይችላል ይህም በሽታ ተተክሎባቸው የቆዩ ሴቶች ልጅ በጸነሡ ጊዜ ያስወርዳቸዋል ወይም ሙቶ ይወለዳል ህይወትም አግኝቶ ቢወጣ ምንም ያህል ብርታትና ጤና ሊያገኝ አይችልም ። ለዚሁ ሁሉ ቂጥኝ ያጠቃቸው ሁሉ ሰውነታቸውን ለኃኪም ማሳየትና የሚያሰቅዩአቸውን ትሎች በደም ስራቸው እየወጋና መድኃኒት እያስገባላቸው እንዲጨረሱላቸው ያስፈልጋቸዋል ። ይልቁንም ይህ መርዝ የሆነ በሽታ በህዝቡ አብልጦ የሚጋነነው ከከተማ ሴትኛ አዳሪ ስለሆነ በየከተማው የሚገኙትን ሴትኛ አዳሪ የሆኑትን ሴቶች ሁሉ በትእዛዝ አስታ

ውቅ አንድ የተመሰከረለትና በጣም የበሽታ ልክ የመረመረ ኃኪም ለዚሁ በተለየ አቁሞ በሽታ እንዳለባትና እንደሌለባት ከመረመረ በኋላ ያለበሽታ የወጣች እንደሆነ ሰርቲፊካ የምስክር ወረቀት ሰጥቷት ይህንን ወረቀት ለማዘገጃ ቤት አሳይታ በቀን በቀን የጉርድ ወረቀት ተቀብላ በዋና ከተማ ለመኖር ያስፈልጋታል ። ይህም ስለሆነ አንድ ጊዜ ያለበሽታ ስለተገኘች በየጊዜው ኃኪም ሊያያትና ሊመረምራት ያስፈልጋል።መጀመሪያ ያለበሽታ ተገኝታ ሁለተኛ ኃኪም ሳያያት በሽታዋን ደብቃ የተገኘች እንደሆነ የተገባትን ቅጣት ሰጥቶ ከከተማ አስወጥቶ የተለየ ሥፍራ መስጠትና ለሕመሟ እንደዚሁ ኃኪሙ እንዲመለከታትና የሚያስፈልገውን መድኃኒት ሊያደርግላት ያስፈልጋል፣ በሽታም እንዳደረባት አውቃ ለሠራተኛው ያመለከተች እንደሆነ ያለቅጣት ወደዜሁ ሥፍራ መደባለቅ ያስፈልጋል ። በሽታም ያልያዛት የያዛትም ብትሆን ከነዜህ በደንብ ከተመረመሩት ተደባልቀው የተገኙ እንደሆነ ለባለጤናዋ እንደ ተገባት ቅጣት አድርጎ እንደገና ጉርድ ሰጥቶ ከባለፍቃዶች ጋራ መደባለቅ ያስፈልጋል ። በሽታ የተገኘባትን ግን የበዛ ቅጣት አድርጎ ከዚሁ ከተለየ ሥፍራ መጨመር ያስፈልጋል።እንደዚሁ እያደረጉ የሕዝቡን ጤንነትና ሥቃይ የተጠበቀ እንደሆነ ይህ ልክ የሌለው በሽታ ትንሽ ይቃለል ነበር ። እንግዲህ ይብቃን ይህ የጻፍነው ሲፈጸምልን እየተመለከትን የተሰጠንን ያህል ምክር ልናደርግ ፈቃዳችን ነው ።

ጥሩነህ ከ ።

ምቀኝነትና ስስት ።

መጋቢት ፮ ቀን በ፹፪ኛው ዓምድ በ፫ኛው ገጽ እንደተባለው ስለ ሥራ ነገር መጻጻት ።

ባገራች ምቀኝነትና አለመማር የሚባሉ ሰዎች ያደሩባቸው አሉ ይባላል ። እንደምን ይኖራሉ ቢባል ለሀገራችን መንግሥት ጥቅም እናበርክት ሀገራችንን እናስከብር ስንፍናን እናርቅ ያልተማሩትን እናስተምር ያልሠለጠኑት እናሠልጥን ብለው ከማሰብ ይልቅ አብልጠው ወደ ክፉ ምክር ይመራሉ ማለትን እንሰማ ነበር ። ነገር ግን ይህ ነገር እውነት መሆኑን ያስረገጥነው ይመስለኛል ። ለምን ማለት መጀመሪያም ዳግማዊ ምኒልክ ትምሕርት ቤት አቁመው የሀገራቸው ልጅ ምቀኝነትና ስንፍና እንዳያድርበት ብለው ከሁለት ሶስት ቋንቋ ያለበት ትምሕርት ቤት አድርገው ስለነበር ። የሚበልጠውም በድሀነት ያሚያንሰውም በባለጠግነት ተምሮ እናቶ ምቀኝነት ያደሩባቸው ። ሰዎች ይበዛሉና ስለዚህ ትምሕርቱን እመጨረሻው ሳይደርስ እስከ ዛሬ የተማርኋት ለሀገሬ መንግሥት በሠራለት ዕራት አታሳጣኝም ስለ ማለት ትምሕርቱንም የፍጻሜዋን ልክ ሳያይ ልቡ ወደ ሥራ ልያዝ በማለት ይፎካከረዋል ። ነገር ግን ወደ ሀገሬ መንግሥት ሥራ ልያዝ በማለቱ በብዙህ ይደነቅለት ። ግን ከብዙዎች የሚያንሱት ለውጪ አገር ሰዎች የሠራን እንደሆነ ብዙ ደመወዝ ይታሰብልናል ጉርሻም እናገኛለን እያሉ ለሐገራቸው መንግሥት ተርበው ተጠምተው ባለማደራቸው ያልተመሰገኑ መሆናቸውን ያሳስበናል ።

ግን ለኢትዮጵያ አሳቢ ለሕዝቧ ጠባቂ አስከባሪዋን ሕያው እግዚአብሔር ስለ ሰጣት ፍቅር ትሕትና ሥልጣኔ ሥራ መውደድ ብርሃን የሚመራ ጌታ ስለሰጣት እኒህን ከዚህ ቀጥሎ የሚጻፈውን ምስጋና ግጥም ተቀበሉኝ ።

የኢትዮጵያ ልጅ ። ኢትዮጵያ አትፍሪ አትጠራጠሪ ። ሥላሴ ከሰጡን ዕውቀትን መርማሪ ። ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር ከረዳ ተፈሪ ። ታምኘለሽ በጣሙን ጠፍተሽም አትቀሪ ።

የኢትዮጵያ ልጅ ። ኢትዮጵያ አትፍሪ አትጠራጠሪ ። መልካም የውቀት መምሕር ተወልዷል ተፈሪ ። ኢትዮጵያ አትፍሪ አትጠራጠሪ ። ብርሃን መሪ ጌታ አለልሽ ተፈሪ ። እድሜ ለምኚለት ቆመሽ ለፈጣሪ ።

የኢትዮጵያ ልጅ ። ሐዲሱ ተፈሪ የጥበብ ኩታችን ። ቢለብሱት አማሩ ንግሥት እናታችን ።

የኢትዮጵያ ልጅ።አልክል ሞኖፖል ሠራተኛ ፋንታዬ ማንክልክሎት ።

በዳር አገር ላለ ሕዝብ አስተዳደር ።

ስለ ክዳትና ስለ ስንፍና።የሚያርስም ምድሩን እያረሰ የሚነግድም ሰው እየነገደ እንዳይኖር ሕዝቡ ሁሉ ሥራ እየጠላ ወምበዴ እየሆነ ከጫካ እየገባ ያጠፋው አገርና ያለቀው ሕዝብ መጠን የሌለው መሆኑን ሁሉም ያውቀዋል ።

ፊትም ስለከብቱና ስለ ገንዘቡ የሚያልቀው ሕዝብ በኋላም በነፍሰ ገዳይነትና በሽፍታነት እየተያዘ በፍርድ የሚሞተው ሕዝብ ሁሉም ወንድማማች ነውና ለተመለከተው እጅግ ያሳዝናል።ሞተ ነፍሱን የማያውቅ አረማዊ ጋላ ሞተ ሥጋን አይፈራም ቢሰቅልም ቢደበድብም ያለው ከክፉ ሥራ አይመለስም ዛሬ በልተን ጠጥተን ነገ ብንሞት ግድ የለም ነው የሚል ። ሰውና ሰው እሚተዛዘንበት ጊዜ እስቲገኝ ድረስ በዳር አገር ያለው ሕዝብ ባንድ ቀላድ ምድር ላይ ያለ ሰው ዋናውን ባለምድሩን ከበ አንድ ግድም ቤቱን ሠርቶ አጥሩንም አያይዞ አጥሮ ቢቀመጥ ወምበዴና ሌባም በመጣበት ጊዜ ተጠባብቆ ተረድቶ ይድናል በሬውና ላሙ እህሉ በግና ፍየሉ ማርና ቅቤው እሚገኘው ከከተማ ውጭ ባለው በዳር አገር ነው ። ዳር ዳሩ ከጠፋ መሐከሉን ብቻ ብንጠብቀው ምን ይጠቅመናል ። አገርንም እሚገዛ ሻለቃና ባላባት በየአውራጃው ለገባሩና ለጢሰኛው ረዳት እሚሆን ዘበኛ መስጠት ያስፈልገዋል ።እምገዛውን አገር ሽፍታ አጠፉብኝ ምድረ በዳ ሆነብኝ ቀለቤን ስጡኝ ከማለት ይድናል ። ነጋዴም ሲሄድና ሲመለስ ለመሳፈሪያ በተሰጠው ቦታ ላይ ዘበኛ ማቆም ያስፈልጋል ። ይኸው የመሳፈሪያ ቦታ ለሐዳርና ለሴትኛ አዳሪም ቤት እሚያሠራ ለነጋዴም ከብት ማቆሚያ እሚበቃ ቦታ ቢሰጥ እሚለማ ይሆናል ። ነጋዴም ጭኖ ሲጓዝ መንገዱ እሚያስፈራ በሆነበት ቦታ ዘበኛ ሸኝቶ ወደ ፊት ላለው ሠፈር ዘበኛ እያደረሰው ቢመለስ ነጋዴው ጉዳት አያገኘውም ። ለሕዝቡና ለሀገሩ የቀን እረኛው የሌት ዘበኛው መንግሥት ነውና አገረ ገዢውን ሻለቃና ባላባቱን በርትቶ እንዲያስብበት ቢሆን ደግ ነው ።

ተክለ ማርያም ።

ማስታወቂያ ።

ሺብሮሌ አቶሞቢል በኢትዮጵያ ወኪል ።
ሖ ሚ ዜርቦስ ኩምፓንያ ።



Automobiles CHEVROLET
H. M. ZERVOS & Cie
REPRESENTANTS
BAS PRIX HAUTE QUALITE

ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትርሚጓው	፪ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ተኩል
የቁጥር ትምርት	፩ብር
ያማሪኛ ሰዋስው	፭ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	አላድ
ወዳጄ ልቤ	
አጭር የዓለም ታሪክ	አላድ
ያማሪኛ ፊደል	ሩብ
አሳብና ምኞት	ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት	ሩብ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር	፪መ
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ	ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ	፩ሩብ

ማስታወቂያ

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚገኙ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
ደግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፭ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር	፬ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፰ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፰ብር
ጎሐ ጽባሕ	፭ብር
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፪መ
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ብር
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ብር

የወዳጅነትና የሥልጣኔ ሥራ ።

በመጋቢት ፳፫ ቀን ወደ ማታ በ፲ ሰዓት ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በአዲስ አበባ የሚኖሩትን የውጭ አገር የዲፕሎማቲክ ሰዎችንና ቆንስሎችን ፤ ከኢትዮጵያም መኳንንት አንዳንዱን ጨምረው ለሻይ ጋብዘው ነበርና በግብዣው ላይ የወዳጅነት ንግግር እያነጋገርዋቸው አንድ ሰዓት ያህል ከቆዩ በኋላ በደስታ በየቤታቸው ተመለሱ ።

የከተማ ወሬ

የእሳት አደጋ

መጋቢት ፳፩ ቀን ወደማታ ከጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በስተ ምዕራብ በኩል ባለው ቦታ እሳት ተነሣና አምስት የሚያህሉ ቤቶች አቃጠለ በዚያን ጊዜ ክቡር ግራዝማች አማረ ጭፍሮቻቸውን አስከትለው በቶሎ ደረሱና ወደ ሌላ ቦታ ሳይሻገር እሳቱን አጠፉት እሳቱ በምን ምክንያት እንደ ተነሣ አልታወቀም ነበርና ቤቱን የተከራዩ ጋለሞቶችእንዲመረመሩ እያስያዙ ወሰዱዋቸው ።

በዚያን ጊዜም የውሀ ፖምፕ ያለው የእሳት ማጥፊያ መኪና በቶሎ ስላልደረሰላቸው ይቸገሩ ነበር ግን ዘበኞቹ ተጠናክረው እሳቱን በማገዳቸው ሊመሰገኑ ይገባቸዋል ።

COGNAC S.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ማስታወቂያ

መጽሐፍና ደብተር የሚያስጠርዝ ሰው በርካሽ ዋጋ በልውል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ይጠረዝለታል።

ያረጀ መጽሐፍና መዝገብ ማሳደስ ለፈለገ ሰው በርካሽ ዋጋ እንደ አዲስ አድርገን እንጠርዝ ለታለን ።



የእጅ ሰዓት ዝኒት

በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጥ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳም ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶመቢል በተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

RUGBY

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፥ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፥ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ ።

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህ በከፕሱሉ ያለ ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በከፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ጉድይር ግዙ





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው።በሌላጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ፤ ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አራተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፲፭
4 me ANNÉE № 15

ሐሙስ ሚያዝያ ፬ ቀን ፤ ፲፱፻፳ ዓ ም ።
JEUDI 12 AVRIL 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲረክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie
Un an 5 Thalers
Etranger
Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ዳግማዊነት ለነገሥታት አለመታደል ነው

የቀወደዱ ቄስ አለመጠን ቸኩለው ከተቀጠርንበት ግዜ አስቀድመው እኔ ዘንድ መጡ ። እኔም በቤቴ በጽሕፈት እልፍኝ ውስጥ አንድ ኢትዮጵያዊ ወንጀለኛ ዘበኛ መልኩን ብቻ ተመልክቶ ወንጀለኛ መሆኑን እንደምን አድርጎ እንዲያውቅና እንዲይዘው የሚያስረዳ የእውቀት ትምህርት አካሄዱን በምጽፍበት ጊዜ ደረሱ።ይህነንም የእውቀት ትምሕርት ሎንዶን ላለው ለቀድሞው ወዳጄ ለማይክል አርለን ለምኖኝ ነበርና ልልክለት ፈቅጄ ነበር።ይህም ወዳጄ ማይክል አርለን የተማረ ብልህ ሰው ነው ውልደቱ ከአርመን፤ዜግነቱ ግን የእንግሊዝ ነው። ይህነንም የእውቀት ትምህርት አካሄድ ከብዙ ቀን ጀምሮ በሚጽፈው መጨረሻ የጨዋ ልጅ በሚባለው መጽሐፉ ውስጥ ሊያገባው ይፈልጋል ከዛሬ በፊት በጻፈው መጻሕፍቱ የዓለምን አዋቂዎች እጅግ አድርጎ አስደንቆአለ ።

ክቡር ቄስ በደረሱ ግዜ ይቀመጡ ፈቃድዎን ሁሉ እፈጽማለሁ ብዬ ወምበር አቀረብሁላቸው እርሳቸውም ቃልም ሳይናገሩ በወምበሩ ላይ ተቀምጠው በቤቱ ዝምታ ውስጥ ባማረ ዜማ ድምጽ የሚፈላውን ሳማባር (የሻይ ማፍሊያ መኪና) አተኩረው ይመለከቱ ነበረ ቀና ብዬ ባያቸው ንጹሕ ልብስ ለብሰው መልካቸውን አሳምረው ተጊያጊጠው ተሰናድተው ኑሮዋል የመጡት።ወዳጄ ካፒቴን ሆይ እንደልማዳችን የእውቀትዎን ኪስ መክፈት ይፈቅዳሉን? ደስ የሚያሰኘው የሚጠቅመው ንግግርዎ ናፍቆት ስቦ አመጣኝ አሉኝ ።

እኔም መለስኩላቸው ክቡር ቄስ ሆይ፤ዳግማዊነት ለነገሥታት አለመታደል ሆኖ አገኙት ይህንን ቃል በሰሙ ጊዜ ከተቀመጡበት ብድግ አሉና በድንጋጤ ወዳጄ ካፒቴን ምንድነው ብለው ጠየቁኝ።ይቀመጡ ነገሩን አስረዳዎታለሁ ብላቸው አላስችል አለኝ ነገሩን በቶሎ አስረዳኝ ብለው ተቀመጡ እኔም ነገሬን ወዲያው ጀመርሁላቸው ።

የባቢሎን ንጉሥ ዳግማዊ ናቡ ከደነፆር አብዶ ነበረ ከአርመን ነገሥታት ዳግማዊ አርዳባሶት በእስክንድርያ ታረደ ዳግማዊ አርዳሺሶ ባለሚሎቹ ገደሉት ዳግማዊ ክስሮፍ ሕዝቡ ገደለው።ዳግማዊ አርሻክ በምሽግ ውስጥ በገዛ እጁ ጥይት ጠጥቶ ሞተ ዳግማዊ አኪኮ ከአልጋው ተሻረ ዳግማዊ ሌዎን በእስጠንቡል ተማርኮ በምርኮው ውስጥ ሞተ።ይህነንም ከሰሙ በኋላ ዓይናቸው በመደነቅ ይገለባበጥ ጀመረ በዚያ ጊዜ የቤቴ ገረድ ቻይ ልታቀርብልን መዝጊያውን ከፍታ ገባች እኔም ይህ የቻይ ግብዣ ለቄሱ ደስ እንደማያሰኛቸውና እልባቸው እንዳይደርስ አወቅሁት ነገር ግን ምንም ደስ የማያሰኝ ቢሆን አእምሮ ያላቸው ነበሩና በትዕግሥት ይጠጡ ጀመረ እኔም ቀጥየ አልኳቸው ከፒዛንቲዮን ነገሥታት ዳግማዊ ሌዎን በተወለደ ባራት ዓመት ነግሦ በነገሠ በ፲ወሩ ሞተ ዳግማዊ ሁስቴኖስ አበደ ዳግማዊ ክስድንት በስደት ሞተ ዳግማዊ አናስታስ ተገደለ ዳግማውያን ሮማኖስና ይስሃቅ ዓይኖቻቸውን አወጥዋቸው ዳግማዊ አንትርኔጎስ ከልጋው ተሻረ ከፈረንሳዊ ነገሥታት ዳግማዊ ሽልደርክ ተገደለ ዳግማዊ ደጎበር ተገደለ ዳግማዊ ሻርል በመርዝ ሞተ ዳግማዊ ሐንሪ በቀስት ዓይኑን ተወግቶ ሞተ።ዳግማዊ ናፖሌዎን ሳይነግሥ ሳይገዛ በስደት ሞተ ከእስኮች ነገሥታት ዳግማዊ ጀይምስ በጦርነት ውስጥ ሞተ ከእንግሊዝ ነገሥታት ዳግማዊ ጁክ ከአልጋው ተሻረ ከመስኮብ ነገሥታት ዳግማዊ አሌክሳንድር ተገደለ ዳግማዊ ኒኮላ ከልጋው ተሻረ ወዲያው ተገደለ የባቢርያ ንጉሥ ዳግማዊ ሉትፌክ ተገደለ የሳክሶን ንጉሥ ዳግማዊ ሐርልድ በጦርነት ውስጥ ሞተ የፖርቱጋል ንጉሥ ዳግማዊ ማኑኤል ተገደለ የዳንማርክ ንጉሥ ዳግማዊ ክርስቲያን ከልጋው ተሻረ የጀርመን ንጉሥ ዳግማዊ ዊልሄም ከልጋው ተሻረ የግሪክ ን

ጉሥ ዳግማዊ ዮርጊዮስ ከልጋው ተሻረ ከቱርክ ነገሥታት ዳግማዊ በያዚት በመርዝ ሞተ ዳግማዊ ሰሌም በመጠጥ ብዛት ሞተ ዳግማዊ ዑስማን እቤቱ ውስጥ ሙቶ ተገኘ ዳግማዊ አሕመድ በጦርነት ውስጥ ሆኖ ሞተ ዳግማዊያን ሙስጠፋ ሐሚድ መጂድ ከልጋቸው ተሻሩ ።

ይህነን ከሰሙ በኋላ ክቡር ቄስ ከመቀመጫቸው ተነሡና አምላክ ይመስገን እኛ እንደነዚህ ያሉ ዳግማዊያን ነገሥታት የሉንም እንዲህ ያለም ጣጣ አልደረሰብን አሉ፤ እስቲ ይታገሡ ኢትዮጵያም ከዓለም ሕዝብ መለየት አትችልም ዳግማዊ ዮሐንስ ከደርቡሽ ጋራ ተዋግተው ሞቱ።ከዚህ በኋላ ቄሱ አሉኝ አጤ ምኒልክም ዳግማዊ ነበሩ እርሳቸው ምን ሆኑ ይሉኛል? ብለው ጠየቁኝ። እኔም መለስኩላቸው ዳግማዊ ምኒልክ ባገራቸው ለመጣው መከራ ሁሉ ደረታቸውን ሰጥተው የኢትዮጵያን አንድነት መሠረቱ ከሞቱም በኋላ ሥጋቸውን ለመሬት አስረከበው ነፍሳቸውን ግን በኢትዮጵያ ነፋስ ላይ ትሰፋለች ብዬ ነገሬን ጨረስሁ።ክቡር ቄስ ከዚህ በኋላ በደስታ ቃል የተወደዱ ክፒቴን ዛሬም ደግመው እጅግ አድርገው አስደነቁኝ ግን መስተንግድዎ አለመጠን ደኽየ አሉኝ በሚመጣው ሳምንት ከርስዎ ዘንድ አንድ መሠረት ያለው የእውቀት ጥያቄና መልስ እናደርጋለን ክልኳዋቸው በኋላ ተነስተው ሄዱ ። በነገሬ እጅግ አድርጎ ልባቸውን ደስ ብሎት ነበር ነገርግን እንደልማዳቸው የግብዣው ነገር ከንግግታቸው ስላልደረሰ ሰውነታቸው ጭብጥ ብሎ ቅርብኋቸው ነበረ።ሚያዝያ ፩ ቀን ፲፱፻፳ ዓ ም

ክፒቴን ባቢግያን ።

ያገር ልማት ።

በሀገር ግዛት ውስጥ ከባላገር በከብት ምልመላ በሬና ላም በግና ፍየል ለመንግሥት ከሚወጣው ከብት ወደ መንግሥት እሚገባው ገብቶ የቀረውን ከብት በየ ሀገሩ ግዛት ውሥጥ ለመንግሥት ሁዳድ የሚሆን ምድር እየተነሣ በሬውን ለኩል አራሽ ለገበሬ ቢሠጡት አገር ይለማል ። እማይነቅዘው እህል ድልብ እየሆነ በጐተራ ይቀመጣል ። እሚነቅዘው እህል እየተሸመተ ገንዘቡ የመንገድ መስሪ ይሆናል ።

ወደጠረፍ አገር ለመጐብኘትም የመንግሥት ወታደር ታግዞ በሄደም ጊዜ በየደረሰበት አገር ስንቁን ሳይቸገር ይቀበላል ። የመስኖም ወሀ እሚወጣበት ምድር የተሠራ እንደሆነ ቡና ጥጥ አታክልቱ ሁሉ በየዓይነቱ ይተከልበታል ። ይኸውም ሥራ ለሀገር መርህ እየሆነ ሕዝቡ ሁሉ ውስልትናውን እየተወ የሥራን ጣዕምና ትርፍ እንዲያውቅ ኃሆናል ። በያገሩም ግዛት ውስጥ ወምበዴና ሌባም ሲያዝ በእግረ ሙቅ እየታሠረ በዘበኛ እየተጠበቀ ያታክልት ቦታ እየቆፈረ መንገድ እያበጀ ያንኑ ያጠፋውን አገር እንዲያለማ ይሆናል ። የመንግሥት አገር እያጠፋ ሕዝቡን ፈጅቶ በልቶ እንደ ወፈረና እንዳጐፈረ ናቁም መከራ ሳያገኘው እየተያዘ ከሚሞት ። በጽኑ እየታሠረ ሥራ ሲሠራ የወስላታው ጉልበት ሁሉ እየደከመ ይሄዳል ።

ተክለ ማርያም ።

የሚያስገርምና የሚያሳዝን

በሃገራችን ሁለት ዓይነት ልምድ ከማሳዘኑ ብዛት እጅግ የሚያስገርም ነገር ይገኛል እርሱም በጥንት ንግግር ተሰሪ ይባል ነበረና ዛሬ ግን ተለውጦ ድርጎኛ ወይም ምሪተኛ ይባላል ። ይህም ድርጎኛ ወይም ምሪተኛ ከዋና ሹም በጭቃ ሹም ይረከከብና እያንጋጋ ወስዶ የፈቀደውን ያሀል ዘባላገር ቤት ያጉርበታል እኛም ተመሪዎች የሚያደርጉትንና የሚያጉላሉትን ስንቱን ብለን ልንቆጥረው እንችላለን ለመጻፍም በግምት ሌላ ሥራ ሳንጨምር ጊዜም ሳናስተላልፍ እስከ ፫ቀን ለመጨረስ የሚያስፈልግ ይመስለኛል ። የሆነ ሁኖ አብልቶም አጠጥቶም በደህናም ቢቀበል በመጨረሻው አንድ አንዱ በምሽቱ እስከመገላገል ይደርሳል ይህም የሚደረገው በባላገር ቤት ብቻ አይደለም በከተማም ጭምር ነው ። ሁለተኛም በብዙ ገንዘብ አንድ ያማረ ቤት ያሠራና ከፈጸመ በኋላ ሊገባበት ሲዘጋጅ ሳለ አንድ መልክም መኰንን ሰው ይመጣና በጭቃ ተመርቶ ይገባበታል ያም ሰው እንደዚያ ለፍቶና ተንገላቶ ሌት በቀን ዋቶ የሠራውን ቤት ሊገባበትም የተጣደፈበትን እንደዚህ ያለ ዱቤ ዕዳ ያልከሰረ ያላሰበ አንድ ቀን ስንኳ ለሥራው ያልረዳው ሲገባበትና እርሱም ወደ ደጅ ሲወድቅ እንዴት አንጀቱ ይቆመጥ ሃዘኑስ ለተመለከተው እንደምንያለ ይሆን ። እንደዚሁ አንድ ሰው ባንድ አገር ቤት ሠርቶ ከመግባት በፊት ምሪተኛ አምጥተው ቢያገቡበት እየገረመው እስከ ትንሽ ቀን ቆየና ዶማውን ያዘና እየቆፈረ የቤቱን ግንብ ድንጋዩን እየፈነቀለ ማፍረስ ጀመረ ነገር ግን ሳይጨርሰው በዳኛ ተከሶ ወጣና ከዚህ በፊት ለማፍረስ ያልፈለግኸውን ጌታዬ እገሌ ቢገቡበት ልታፈርሰው ወደድኸ ብሎ ለዳኛው ከሳሹ አመለከተ ዳኛውም እውነት ነውን ብሎ ጠየቀው ያም ተከሳሽ ባለቤት ፈራና ጌታዬ ሃሳቤን ለሰው አላሜወትኩም እንጂ ይህችን ቤት ስሠራ አላማረችኝም ነበረና ለጊዜው መቀመጫ ትሆነኛለች ብዬ ነው እንጂ ያደረግኋት አሁን የሰዎቹን ቤት ብመለከተው ከኔ ቤት እጅግ ይበልጥ ያማሩናቸውና ስለዚህ ከሰው ይበልጥ እሠራለሁ ሞትም አይቀር ብዬ ላፈርሰው የጀመርኩኝ ስለዚህ ነው ባፈርሰውስ ምን አለበት ብሎ መለሰ ያም ከሳሽ ከዚህ በፊት ያላፈረስከውን ጌታዬ እገሌ ሲገቡ ታፈረስክ ቅጣት ይገባሃል አለው ያም ሰው ፈራና ይጅበረበር ጀመር ተገላገሉ ተብሎ ሽማግሌ ገባቸውና ስላፈረሰ ባለቤት ከሰና መቀጮውን ጐርሶ ገባ ይባላል ። ቤትስ መሥራቱ አከራይቶ ለማትረፍ ቢፈቅድም ለመቀመጫ ነበር ምሪት በሚባል ነገር ብዙ ትርፍ በመገኘቱ ተመልከቱት ። ስለ ድርጎኞች ወይም ምሪተኞች ነገር ከብዙ በጥቂቱ ከረጅም በጭሩ ይህ ይበቃናልና ጨርሰንም ለመጻፍ ወረቀት አለቀብንና እርሳችንን ቁጭ አድርገን አገጪችንን ተደግፈን ብንገረም ይሻላል ።

ጥሩነህ ክ ።

አነሂ እሴዓለክሙ አሐተ ነገረ ።

ብዙ ገንዘብ ያላትና እግዚአብሔርን የምትወድ ቸርነት የተመላት አንዲት ሴት ነበረች ልቧም አንድ ልጅ አላት እሱም አፉን አልፈታም ነበረ የእንጀራ ልጆቿ ግን ብዙዎች ናቸው

ብልጦችና የሰው ገንዘብ ፈላጊዎች ውዳሴ ከንቱ ወዳጆችም ነበሩ ስለናቱ ገንዘብም ይህን ልጅ አይወዱትም ነበር ይላሉ ይህን ልጅም እናቱ አፉን ሲፈታና ለቁም ነገር ሲበቃ አይታ ልጄ ሆይ የቤት ልጆቼን ከተማሪ ቤት አግብተህ እያስተማርህ አለቃ ሆነህ ቤቴን ይዘህ ተቀመጥ አለችው ።

ይህን ሰምተው የእንጀራ ልጆቿ እናሳ ቢሏት እናንተስ ብትወዱ በጢሰኝነት ተቀመጡ ባትወዱ አገራችሁ ግቡ አለቻቸው ።

እነሱም እሱ ካንቺ ቢወለድ እኛስ ብንሆን ከሱ የተለየነው ምንይሆን ወራሾች እኛውነንና በግድ ልጆችሽ መሆናችን አይቀርም እያሉ ቢያታልሏት እሷም አይ እንዲያውም አትፋጁብኝ ብላ ወደ ዳኛ ወሰዳ ጣለቻቸው ።

ከዳኛውም ላይ ቆመው ይህ ልጅ እስቲ በሉ ምንእምጣ ትሉኛላችሁ ቢላቸው እኛማ የምንልህ ጥንትም የኛ አባት ያንተን እናት አግብቶ ሳለ በገንዘቡም ሁሉ በቤቱ ሰልጥኖበት ከሱ እየተረፈ በናትህ ገንዘብ መጻተኞች ዘመዶቹን ሲረዳበት ይኖር ነበር ። የኛም አባት ቢሞት ይኸውና እኛ ተተክተናል ቤትም ገንዘብም የቤት ልጆችን ለማስተማርም ለኛ እንዲገባ እልቅናም እናትህ ብትሰጥህ የናትህ ገንዘብ ጣፍጭ ነውና አንተ በተወለድህ ፋንታ ውርስ ለኛ እንዲገባ ብለው ውርርድ ተከሉ ።

እሱም ርስቱ ጒልቱ ቤቱ ንብረቱ የናቴ ከሆነ ለኔም እናቴ እልቅናውን ጨምራ የቤት ልጆቼን ባዕድ እንዳይገባቸው አንተው አስተምር እልቅናውንም ላንተ ሰጥቸሃለሁ ብላ ከሰጠችኝ ወጥ ቢጣፍጥ እጅ ያስመጥጥ እንዲሉ አባታችሁ ሲዘርፍ የኖረው አነሰና ባይሆን አገራችሁ ግቡ ትባላላችሁ እንጂ እየተወለዳችሁ አታሉና ዝረፉ አይሉም ለቆ መሔድ እንዲገባ ብሎ ወደረ ።

ከዚህ በኋላ ዳኛው እረ አንተ አገራችሁ ግቡ ትላቸዋለህ አገራቸው የትነው ብሎ በቍጣ ቃል ጠየቀው ። እሱም ጥንት አባታቸው ለሜቱ የሻለቃ ሆኖ ሜቱን ሲገዛና ሲበላ ሲጠጣም ይኖር ነበር አሁን ቢሆን እነሱ ያሉበትም አይታወቅ ቢሔዱም አገር የላቸውም ለሰው ተሰጧል አለው ። ዳኛው አነጋገሩን አይቶ ስትሟገትስ ቢሆን ከዳኛ ፊት ቆመህ ክንድህን ስለምን ነጠቅ ታደርጋለህ ቢለው ክቡደ መዝራዕት ነኝና እኔ ምን ልበል ትለኛለህ አለው ።

በዚህ ጊዜ ዳኛው ይህ ልጅ በዋዛ የሚለቅ አይደለምና ይህን ነገር ብቻየን አልፈርደውም ብሎ ብዙ ሰው ካለበት እንዲፈረድ አሳደረውና ፍርዱን ሳልሰማ መጣሁ ብሎ አንድ ተማሪ ነገረኝና እኔም ሰማሁ ከቶ ምን ይፈረድ ይሆን ?።

ዮፍታሔ ንጉሤ ፡

መልስ ለጥሩነህ ካብትህ ይመር ።

ይድረስ ለክቡር ወንድሜ ከልጅ ጥሩነህ ካብትህ ይመር የማክበርና የመናፈቅ ሰላምታዎቼን አቀርብልሃለሁ ።

ወንድሜ ሆይ ፤ ምንም የሃሳብህን ጥልቀትና የውቀትህን እርቀት መርምሬ ባላውቀው አዲስ አበባ ሳለህ ስለ ኢትዮጵያ የሃገርህ ፍቅር ሰውነቶችህ ብዙህ ጊዜ በትጋት ሲያስቡበት እመለከት ነበር ይኸውም ሃሳብህ የውነተኛ ሃሳብ ስለሆነ ለሃገርህ ጥቅምና ጉዳት የመሰለህን ቃሎች በየጊዜው በብርሃንና ሰላም እየጻፍክ ማስረዳትህ ያሳስበናል ። ደግሞም በመጋቢት ፳ ቀን ፲፱፻፳ ዓ ም በራተኛው ንመት በ፲፫ ቁጥር በ፺፰ኛው ገጽ በ፪ ዓምድ እናንተም ከምታገኙት ገንዘብ ፪እጅ ለሃገር ስልጣኔ ሥራና ለከተማችሁ የሚያስፈልጋችሁን መንገድ ማስበጀትና አልፎ አልፎም ትንሽ ትንሽ ብታቆሙ የሚለውን ባነበብኩ ጊዜ እጅግ ደስ አለኝ ። እንደምንሰማውማ የውጭ አገር ከበርቴዎች ላገር ልጆቻቸው መማሪ የትምህርት ቤቶች በገንዘባቸው ያሠሩ ደግሞም ብዙዎቹም ሆርታል እያቆሙ ለሀገር ልጆቻቸው መታከሚያ ይረዳሉ ይባላል ። ይኸውም ሥራቸው የሃገር ፍቅር ያደረባቸው ያስረዳል ያገራችን ባለጠጐች አመድ ውስጥ ለማከማቸት ነው ። እንዲመች ለንደዚህ ያለውን የሃገር ጥቅም ያሰቡበት ይመስልሃል ደግሞስ እከሌ ባለጠጋ እከሌ ባለገንዘብ ነው ቢባል ሃገርና መንግሥት ሰላም ካልሆነ ያ የከበርቴ ገንዘብ ለዘራፊ መሆኑ አይደለምን። ይሁንና ወንድሜ ሆይ ሌላው ቀርቶ ስለዚህ በማህበር ለሚቆመው ትምህርት ቤት ከባለጠጐቹና ከጌቶቹ ይልቅ ደሃዎቹ እንደተጉበት እርዳታቸውን እንረዳለን እያሉ በብርሃንና ሰላም ከጥዑም ምክራቸው ጋር የተጻፉት ያስረዳናል ።

ግን በወጣቶች የደሃ ልጆች ላይ የተከናወነው የሀገር ፍቅር በባለጸጎች ዘንድ ቢያድር ኖሮ እስከ ትንሽ ጊዜ የሃገራችን እርምጃ በኤውሮፓዎች እንዲጠጋ አይጠረጠርም ነበር ። በሃገራችን ስንት አገረ ገዢዎችና ባለጠጎች አሉ እርሳቸውም አራት አምስት (ኮሌጋ) በገንዘባቸው መሥራትና ማሠራት የሚችሉ በየግዛታቸው ውስጥ እንኳን (ኮሊጋና ኤኮል) የትንሽ ህጻናቶች መማሪያ ያቆሙ አይገኙም ከሁን ቀድሞ ግን የእስራኤል አምላክ ልዑል ተፈሪን ያቆይልን እንጂ ችግረኞችና የሀገር ፍቅር ያደረባቸው የኢትዮጵያ ልጆች በተፈሪ ኃይሎች ከኤውሮፕዎች ትክክል እርምጃቸውን ሳያደርሱም አይቀሩ በማለት የማያቋርጥ ተስፋ አለን ። ክቡር ወንድሜ ልጅ ጥሩነህ ሆይ ፤ የምታስጐመጅ ምክር የሚለውን ቃሎች ለማንበብ ፈጥነው ባለጠጎቹ ሲያነቡ ፪እጅ የሚለው ላይ በደረሱ ጊዜ ብዙዎቹ ለማንበብ እየጠሉ የተውት አይታጡም እልሃለሁ የሆነ ሁኖ አሁን ብዙው የሀገር ፍቅር ያደረበት ወጣት ሁሉ በዚህ በሃሙሱ ገበያ ጥቅምና ጉዳት የመሰለውን እየተመለከተስ ለሚናገር ተውት ሥራ ፈት ነው የጻፈው እየተባለ ይባላል። ይሁንጂ ለሃገርህ ጥቅም የመሰለህን በየጊዜው እየጻፍክ ትልክልናለህ በማለት ወንድሞችህ ሁሉ ባለተስፋ ናቸውና ያለመፈጸሙን እያሰብክ ለመጻፍ እንዳትዘነጋ ለሁሉም ጊዜ አለውና ስል አሳስብሃለሁ ጤናውን ይስጥህ አሜን ።

በቀለ ዘለቀ ፡

ለትምሕርት ስለ ማሰብ ።

የብርሃን አትክልት የሆነች ኢትዮጵያ ብርሃን የሆነ ተማሪ ቤት አብቅላ ዕውቀት የተባለ ጣፋጭ ፍሬዋን ለሙሉ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ልትመግበን የተዘጋጀች መሆኑዋን ከስረ

ዳችን በኔው ዕድሜ ለንኳን ብዙ አድርጎ የዘገየ ይመስለኛል ።

ከዚህም ብርሃን ከሆነ ተማሪ ቤት ዕውቀት የተባለውን ጣፋጭ ፍሬ ለመመገብ በታላቁ ንጉሠ ነገሥት በዳግማዊ ምኒልክ ጀምሮ በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ባልጋ ወራሻቸው በልዑል ተፈሪ መኰንን ሐሳብና ብርታት ይህንን ዕውቀት የተባለ ጣፋጭ ፍሬ ሊመገቡ ብዙ የሆኑ የኢትዮጵያ ወጣቶች ተጣጥረዋል ። ይህነንም ዕውቀት የተባለውን ጣፋጭ ፍሬ እስኪጠግቡ ድረስ ለመመገብ ስንፍና የሚባል እንቅፋት እንዳይመታቸው ትጋት የተባለ ፈረሳቸውን ጭነው ለሚጣጣሩ የኢትዮጵያ ወጣቶች እግዚአብሔር እረድቷቸው እስከ መጨረሻው ደረጃ እንዲደርሱና የኢትዮጵያን ክብሯንና ረድኤቷን ወራሹዋ እንዲሆኑ በፍጹም ልቤ እመኛለሁ ።

ነገር ግን በሀገራችን ውስጥ እንደዚህ ያለ ብርሃን የሆነ ተማሪ ቤት ሲበቅልልንና ያላየነውን የሚአሳየን ትምሕርት የሚባል ኤሊቴሪኩን አብርቶ ዕውቀት የተበለ ጣፋጭ ፍሬውን አዘጋጅቶ የሀገራችንን ሕዝብ ለመመገብ ከሐር ምንጣፍ የለሰለሰ ትሕትናውን አንጥፎ ሲጠብቀን መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህነን ዕውቀት የተባለ ጣፋጭ ፍሬ የሚገኝበትን መንገድ ወዴት እንደሆነ ያለመፈለጉ በጣም አድርጐ ያሳዝናል ።

ስለ ዚህም እኔ ትንሹ ልጅ የኢትዮጵያን ሕዝብ የምመክርበትና የማስረዳበት ዕውቀት አገኛለሁ በማለት አይደለም እኔ እንደሚመስለኝ እግዚአብሔር የምንጠቅምበትንና የምንጐዳበትን እንድናውቅ ኅሊና ሰጥቶ ከፈጠረን በኋላ እርሱ በፈቃዱ በደዌ ክልወሰነንና ሕይወታችንን ጨርሶ ካላሳለፈብን በተቀር ዕውቀት የሚገኝበት ጐዳና ለመፈለግ መጣጣራችን እንዴት ይቀር ? ። አሁንም ከዚህ ቀጥዬ የምጽፈውን በኔ ዕድሜ ጓደኞቼ ለምትሆኑ የኢትዮጵያ ወጣቶች ይህቺን ትንሽ ምክር አካፍላችኋለሁ ። ድንቁርናችንን በራሳችን ላይ ተሸክመን ብልሆች ሲጠይቁንና ሲአጫውቱን ለብልሆች የምንሰጠው መልስ እያጣን ከምናፍር ባለማወቃችን ማፈራችንንና ድንቁርናችንን እንዲፍቅልን ይህነን ዕውቀት የተባለ ጣፋጭ ፍሬ የሚገኝበትን ጐዳናውን እግዚአብሔር በሰጠን አቅማችን ተጣጥረን አይሻልምን ? ።

ነገር ግን እኛ በጣም ተምረን ዕውቀት ብናገኝ ለተወዳጅ ሀገራችን ለለምለሟ ኢትዮጵያ በተቻለን ሁሉ ረዳቷ ለመሆንና መንግሥቷንም አስከብረን ደግሞ ለየራሳችን የሚበቃን እንጀራ እናተርፋለን እንጂ ዕውቀት ወደ ክፉ መንገድ የሚአደርሰን አይመስለኝም ። ሰውማ መቸስ በዓለም እንደማይኖር አለ በሀገራችንም ውስጥ አንድ አንዱ ሰው ራሱን እንኳን እቤት የሚአውለው ዕውቀት እያጣ ወረቀትና ቀለሙን ይዞ ጸሐፊ ለመፈለግ መንደር ለመንደር ሲዞር ይውልና ወደ ማታ ሲሆን እሰፈር የዋለ አንድ ጽሕፈት የሚአውቅ ሰው ያገኘ እንደሆነ ሲሆን በልመና ሳይሆንም በገንዘቡ ገዝቶ ለማያውቀው ሰው የሆዱን ምሥጢር ይገልጽለትና ይሄዳል ። ያም ሰው ለጊዜው የጉዳዩን መፈጸም ይመለከታል እንጂ የሆዱን ምሥጢር ሌላ ሰው እንደሚሰማበት አያስብም፡ እንደዚህ ያሉት ሰዎች ሁሉ የየራሳቸውን ድንቁርና እንቧቸው ልጆቻቸውን እንኳን በሥልጣኔና በትምሕርት ለማሳደግ አይጣጣሩም ፡ አሁንም ክቡራን ወንድሞቼ ሆይ ምንም በዛሬው ጊዜ ለየራሱ ነፃነቱን የማያስብ ሰው ባይኖር ከሁን ቀደም በየዕድሜአችኒ የምናያቸው ዕውቀተኞችና ብልሆች የሆኑ ሰዎች ሁሉ ሲጠቀሙ እንጂ ሲጐዱ አላየናቸውምና ዕውቀትን ከመጀመሯው ተነስተን መጨረሻውን እስትናገኘው ድረስ ነፃነት የሚገኝበትን የብልሆችን መንገድ እንከተል ።

በትረ ማርያም ወልደ ትንሣኤ

ሆድና ሕዋሳት

ሕዋሳት ሁሉ አንድ ሆነው በሆድ ላይ በነገር ተነሡበት ስንሠራ የምንደክምበት ከሞት የምንደርስበት ባንት ነው ፤ አንት በትኖር ሞት ባልነበረብንም ድካምም ባላገኘነም አሉት ፤ ሆድም እኔስ ካወክኋችሁ እተውላችኋለሁ በናንተ የደረሰ ይደርሰኛል ብሎ ምግብ አልቀበልም አለ ። በግድም ቢያገቡበት እያስመለሰ ይጥለው ጀመር ፤ ከዚህ በኋላ ዓይንም አላይ አለ ዠሮም አልሰማ አለ ፤ መላስም ኩልትፍትፍ አለ ። እግርም የገዛ አካላቸው ክብደዋቸው መንቀሳቀስ ቸገራቸው ። ከዚህ በኋላ አስታራቆች መጥተው ተበድለሀል ተውልን ስለኛ ተገፋልን ምንም የሚበቃ ካሣ ባይገኝ መደገፊያ ድግ ይስጡህ ብለው አስታረቁት ድግ ከዚያ ወዲያ የተዠመረ ነው ይባላል ።

የሰው ብድር አይቀር በምድር እንዲሉ ደግሞ ብድራቸውን ዓይንንና ዠሮን ነቀፉዋቸው ፤ እኛ ሁላችን እናድጋለን እንወፍራለን እላንት ምንድር ናችሁ አታድጉ አትጠረቁ በልቶ ከጀች ምግብ መና አሉዋቸው ፤ ዓይን ወትሮ ክፉ እያየሁ በዜት ልጠርቃ አለ ። ዠሮም ወትሮ ክፉ እየሰማሁ እንዴት ልጠርቃ የሰው ነገር የቆረቀዛል እርጥብ ያደርቃል እላንተ አትሰሙ አትለሙ በልቶ ተኝቶ ታላቅ ጤና አለማየት አለመስማት ነው ።

ከሉድዊግ ማህለር የተሰበሰበ ልብ ወለድ ታሪክ

ልዑል ተፈሪ መኰንን የመሰለ ጀግናና የነፃነት አባት አውራ መሪጌታ ኢትዮጵያ እናታችን ስለወለደችልን ደግሞም በርሳቸው መሪነትና በእግዚአብሔር ቸርነት ከባርነት ወደ ነፃነት ከሞት ወደ ሕይወት ተሻግረን ከዚሁ ሰዓት ስለደረስን ክብርና ምስጋና ለእግዚአብሔር አምላካችን ይሁን ።

ከሁን ቀደም አባቶቻችንና አያቶቻችን ከብዙ ዘመን ጀምረው ያላገኙትን ያንድነት ኃይልና የሥልጣኔ እርምጃ ይኸውና ልዑል አልጋ ወራሻችን እንደራሴና ወራሴ መንግሥት ተብለው በመንታ ስም ተሰይመው አውራ መሪያችን ከሆኑ በኋላ ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ሕዝብ በዚሁ ባዲሱ ዘመን ስምምነት በሚባል በተፈሪ ሰንሰለት ተሳስረን ያንድነት ኃይል በማግኘታችንና የሥልጣኔ ቀዳሚዎች በመሆናችን ተፈሪን የሰጠን አምላክ ይክበር ይመስገን ።

ለወደፊቱም በርሳቸው መሪነትና በተከታዮቸዎ ረዳትነት ኢትዮጵያ አገራችን ከሁን ይልቅ ለሚመጣው ዘመን በትምህ

ርትና በሥልጣኔ እርምጃ ከፍ ከፍ እያለች እንድትሄድና ለወደፊቷ እንድትገፋ ጥርጥር በሌለው በሙሉ ሃሳባችን እየተመኘን በብዙ ተስፋ እንጠብቃታለን። መኳንንቶቻችንና እገረ ገዧዎቻችንም ያልጋ ወራሻችን በረከት ተከፋዮች ሁነው ለኢትዮጵያ አገራቸው በተቻላቸው መጠን የማገዛቸውን ስጦታ ስላሳዩ የተለየ ምስጋና እናቀርብላቸዋለን። አሁንም ለወደፊቱ ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ህዝብ ባንድነትና በእውቀት ጎዳና እየገፉ እንዲሄዱ ለግርማዊት ንግሥታችንና ለልዑል አልጋ ወራሻችን እድሜና ጤና ለጅግኖቻችንና ላርበኞቻችን ኀይልና ብርታት ይሁንልን በማለት ምስጋናዬን አቀርባለሁ ፡፡

ለታዘዘበት ሥራ ተሰናብቶ የሚሔድ ታመኑ ረምኅ ።

በልዩ የቆመው የፍርድ ቤት ዋና ዳኛ ነገር ።

ነጋድራስ አፈወርቅ የዛሬ ስድስት ዓመት ለድሬደዋና ለሐረር አውራጃ ነጋድራስነት ተሾሙ። ከሁለት ዓመት በኋላ በ፲፱፻፳ ዓ ም ነጋድራስነታቸውን እንደያዙ በልዩ ለቆመው የፍርድ ቤት ዋና ዳኛ ሆነው ተሾሙ።ከዚያ ቀን ጀምረው እስካሁን ድረስ በሥራቸው ጠንክረው መንግሥታቸውን አገለገሉ አሁን ግን መቼም የሰው ጉልበት እያደረ መድከሙ አይቀርምና አራት ዓመት ሙሉ አለ ዕረፍት ይኸን ያህል ትልቅ የዳኝነት ሥራ ስለሠሩ ሰውነታቸው ደከመ ጤናቸውም ተበላሸ።በዚህ የተነሣ ብዙ ጊዜ ልዑል አልጋ ወራሽን ልረፍ ሥራውን ልተው እያሉ ለመኑ ነገር ግን በመታመናቸውና በመጠንከራቸው የተነሣ ይኸን ሥራ ሊለቁ ልዑል ሳይፈቅዱላቸው ቆዩ ። አሁን ግን በጥር መጀመርያ ነጋድራስ አፈወርቅ ጤናቸው እያደረ ስለተበላሸና በጣም ስለደከሙ እንደገና ለልዑል ጽፈው አጠንክረው ለምነው ልረፍ አሉ። ልዑል አልጋ ወራሽም ነጋድራስ በውነት በዚሁ ሥራ መድከማቸውንና ጤናቸው መበላሸቱን አውቀው እሺ እንድታርፍ ፈቅጀልሃለሁና ሌላ ሰው እስከሾም ድረስ ለጥቂት ጊዜ ስትሠራ ቆይ አሏቸው ሲሉ ሰምተናልና ስለዚህ እስከ ጥቂት ቀን ሌላ ዋና ዳኛ በልዩ ለቆመው የፍርድ ቤት ሳይሾም አይቀርም ።

La Présidence du Tribunal Spécial.

Le Nagadras Afework fut appelé, il y a six ans, au poste de Directeur Général de la Douane pour la Province de Harrar, à Diré-Daoua. Deux ans plus tard, le Gouvernement Impérial le désigna comme Président du Tribunal Spécial.

Le Nagadras Afework exerça donc simultanément ces deux importantes fonctions, dans lesquelles il se distingua particulièrement et rendit à l'Empire de signalés services.

Mais, malheureusement, les forces humaines ont des limites, et la santé du Nagadras Afework fut fort éprouvée par le travail énorme qu'il eut à fournir et par le souci que lui causaient les nombres procès dont est encombré le rôle du Tribunal spécial.

A plusieurs reprises, le Nagadras Afework sollicita Son Altesse Impériale d'accepter sa retraite de la Présidence du Tribunal Spécial, mais jouissant de la plus grande estime et de la confiance entière du Gouvernement, le Nagadras Afework fut prié de demeurer à ce poste important entre tous.

Le premier janvier dernier, le Nagadras Afework renouvela sa démission en insistant particulièrement sur le fait que sa santé l'oblgeait fermement à obtenir le repos qu'il demandait depuis longtenps.

Son Altesse Impérial reconnut alors la nécessité où Elle se trouvait de déférer au désir exprimé, et accepta bien à regret, la démission du Nagadras Afework, en le priant toutefois de continuer sa fonction jusqu'à ce que son successeur soit désigné.

La désignation du futur Président du Tribunal Spécial est imminentet, et jusqu' à ce qu'elle ait lieu, le Nagadras Afework assure le fonctionnement du Tribunal.

ማስታወቂያ

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
ደግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፫ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር	፱ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፭ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ብር
ኀሐ ጽባሕ	፫ብር
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፪መ
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፭ብር
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትርሜጓው	፪ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ተኩል
የቁጥር ትምርት	፩ብር
ያማሪኛ ሰዋሰው	፩ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ብር
የልዑል አልጋ ወራሽየአደን መንገዳቸው አኳኋን	አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	አላድ
አጭር የዓለም ታሪክ	አላድ
ያማሪኛ ፊደል	ሩብ
አሳብና ምኞት	ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት	ሩብ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር	፪መ
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ	ሩብ

ማስታወቂያ ።

ሺብሮሌ አቶሞቢል በኢትዮጵያ ወኪል ።
ሔ ሜ ዜርቦስ ኩምፓንያ ።



Automobiles CHEVROLET

H. M. ZERVOS & Cie
REPRESENTANTS
BAS PRIX HAUTE QUALITE

የሚከራይ ።

A LOUER

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ አቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጦጦን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።



አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባ ኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወድያም ባለማግኜቶና ባለባተሪ ነው ካምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል «ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው

ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ፡፡

COGNAC S.ᴀE.ᴀA. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ማስታወቂያ

መጽሐፍና ደብተር የሚያስጠርዝ ሰው በርካሽ ዋጋ በልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ይጠረዝለታል ።

ያረጀ መጽሐፍና መዝገብ ማሳደስ ለፈለገ ሰው በርካሽ ዋጋ እንደ አዲስ አድርገን እንጠርዝ ለታለን ።



የእጅ ሰዓት ዝኒት

በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶመቢል በተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፣ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፤ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል

RUGBY



ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ ።

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህ በካፕሱሉ ያለ ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በካፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ጉድየር ግዙ





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው።በሌላጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ፤ ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አራተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፲፮
4 me ANNÉE № 16

ሐሙስ ሚያዝያ ፲፩ ቀን፤ ፲፱፻፳ ዓ ም ።
JEUDI 19 AVRIL 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ቢገዛ ለፊስን በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የትንሣኤን በዓል አከባበር።

ሚያዝያ ፯ቀን ማታ ሰው ሁሉ የትንሣኤን የምስራች ቃል እንዲሰማ በየ ክፍሉ ወዳለው ቤተ ክርስቲያን ተሰበሰበ በጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን እንደ ሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የከተማው ሰው ሞላውና ክቡር መላክ ገነት ወልደ ሐና ሊቃውንቱንና ካህናቱን የበዓሉን አከባበር ሥርዓት እንዲያሳምሩ በሥርዓት አሰናድተዋቸው ቆይተው የበዓለ ትንሣኤን ሥርዓት ሁሉ በማረና ደስ በሚያሰኝ አደራረግ ፈጸሙ ። በዚያን ጊዜም ደብተራ ወልደ ኪዳን የሚከተለውን ቅኔ ቀኙ ።

ክብር ይእቲ ።
አይሁድ አኃዙ በቀራንዮ ግዕዘ ሰማርያ በለሰ ።
በዘሰማርያ ልማድ እስመ ገደፉ ንጉሠ ።
ወአስቆሮታዊ ዋህድ በነገረ አይሁድ ፈለሰ ።
እመኒ ተሰቅለ ከመ አግአዚ እስመ ኢያድኃኖ ርእሰ ።
እጣነ ሞገር ።
ትንቢተ ዳዊት ፈጸመ ትንሣኤ ቃለ አብ ኄር ፡፡
እምጣነ አልቦ ዘተርፈ በመቃብር ።
ሞት እንዘ ቀታሊ ወእንዘ ትዘግብ ምድር ።
እምቅድም እስከነ ድኅር ።
ወእመ መቃብር ወሞት ትንሣኤ ቃለ አብ መንክር ።
ንዋዮሙ እስመ ኢያጽገበ ለዋህድ ቀትር ።
አሠረ ንጉሥ ።
እስከለ ማርያም ንብረ ለዓለም በዘ ምኒልክ መንበር ።
ኃይለ ሥላሴ ወልድኪ አኮ ዘኢይትመዋእ ለፀር ።
ወስመ ፈረሱ ያስተጻምር ።
እስመ ለፍቁሩ ውእቱ ፀዓዳ መዓር ።
ወለፀሩ እም ሐሞት መሪር ።

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የትንሣኤውን በዓል ለማክበርና ስለ ትንሣኤው የሚነገረውን የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት ከትልቁ ቤተ መንግሥት ግቢ ባለችው የኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን አድረው ነበር ። ብፁዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስም እዚያው ነበሩ እንደዚሁ ሁሉ ልዕልት ወይዘሮ መነን ከልዑል አልጋ ወራሽ ግቢ ባለው በቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን አደሩ ።

ቅዳሴውም በተፈጸመ ጊዜ ስለ ትንሣኤው የምሥራች ሰባት ጊዜ መድፍ ተተኰሰ ሰው ሁሉም እየቤቱ ሄዶ በደስታ በዓሉን አክብሮ ዋለ ።

ብርሃንና ሰላም ለወዳጆቹ ሁሉ እንኳን ብርሃነ ትንሣኤውን አሳያችሁ ይላል ።

ሲቻለው የማይወድ ሲወድ አይቻለውም ጊዜ የከበረች ገንዘብ ናት ። ሲቻለው ለማይወድ ለሚወድ አይቻለውም ሕይወትም ሕልም ነች ጊዜም አላፊ ጥላ ነች ።

ለሚወዳት ሰው እንደ ሕይወት ከሁሉ የምትበልጥ ክብር ያላት የሚቆናቆኑላት ነገር በዚች ዓለም ከቶ አንድ የለም መኖርን ሕይወትን ለጠላ ሰው ደግሞ በዚች ዓለም እንደሷ የሚሰለችና የሚጠላ ነገር አንድም ነገር የለም ። በዚሁም ምሳሌ የነገርን ምስጢር ለሚመረምር ሰው ከዚህ በላይ የተጻፈውን የመሳሰለ የፈላስፋዎች ንግግር ከሁሉ ይበልጥ ለሰው ልጅ መንፈስ ደስ የሚያሰኝ ነገር የለም ። የነገርን ምስጢር ለመመርመር ለማይችል ወይም ለማይወድ ሰው ደግሞ ይህንን የመሳሰለ የፈላስፋዎች ንግግር ከንቱ ጥቅም የሌለው ሚሰለች መስሎ ይታየዋል ። ከልደት በፊት ይኖሩ ከነበሩት አንድ ትልቅ የግሪክ ፈላስፋን ሰውን በቅጡ አርጎ ስለ መረመረ መሬትን ወይም ይህችን ዓለም ከብዱአት ያለ ደንቆሮ ሰው ብቻ ነው አሉ

እከስት በምሳሌ አፋፍ እንዳለ ቅዱስ ዳዊት ነገርን በምሳሌ ሲያቀርቡት በጣም ደስ ይላል ።

ከዕለታት አንድ ቀን ሳላስበው በድንገት አንድ የሂንድ ፈላስፋ መጽሐፍ አግኝቼ እጄ እንዳመጣ ገላጥ ብደርገው ብልህ ሰው ጥቅም ያለውና ወይም ሊአፈራ የሚገባውን ፍሬ የሚሰጥ አትክልት ነው።ደንቆሮ ሰው ደግሞ ጥቅም የሌለው ቅጠላ ቅጠልን የመሰለ አረም ወይም ሊአፈራ የሚገባውን ፍሬ ሳያፈራ በከንቱ ቦታ የሚአጣብብ ከንቱ ነገር ነው የሚል ቃል ተጽፎ አየሁ የዚህንም ማስረጃ ዝርዝር አያቸ ከቶውንም ሰውነቴ በጣም ያዝን ነበር ። ከቀን ብዛት በብርሃንና ሰላም ከዚህ በላይ በመጀመሪያው መስመር የተጻፈውን ቃል አይቼ የረሳሁትን ነገር እንደገና አስታውሼ ይህን ለመጻፍ አበቃኝ ።

ሲቻለው የማይወድ ሲወድ አይቻለውም። ሲቻለው ለማይወድ ለሚወድ አይቻለውም ይህም ነገር እውነት ይሁን ሐሰት እውነትነቱም ሆነ ሐሰትነቱ በሙሉም ይሁን በገሚስ መጠያየቃችን ቀርቶ በጠቅላላው ይህን የፈላስፋን ቃል እውነት እናርገውና ይህ የሚሆንበትን ምክንያት ልብ ብለን እስቲ እንመርምረው ። ይህንን ለመመርመር ለዚህ ባጭሩ ማስረጃ የሚመስለኝ ሌላ የፈላስፋ ንግግር አለ።ይህም እንዲህ ነው ሰው ልበ ትልቅ እውቀተ ትንሽ ነው ማለት ትልቁ ልቡ የሚመኘውንና የሚአስበውን ትንሹ እውቀቱ አክናውኖ ሊሠራለት አይችልም ይለናል ።

ይህን ነገር ለመመርመር የግድ ወደ ተፈጥሮ ባህርይ ሕግ መሠረት መግባት የሚያስፈልገን ይሆንብን ይመስለኛል የዚህን ጊዜ ለተንቀሳቃሹም ሆነ ለማይንቀሳቀስ ፍጥረት ሁሉ በትምህርትም ሆነ በልማድ የማናውቀው ሳናውቀውም የሚገዛን ሕግ እንዳለ እንረዳዋለን ነገር ግን ይህን ሕግ ይኑር አይኑር ለማወቅ ሁላችን አንችልም ብቻ ለሚአውቀውም ለማያውቀውም ለሁሉም ስለሆነ የምጽፈው አንበቢዎቼን በትግሥትና ብርቀት ይህን የምጽፍላቸውን እንዲመለከቱት አሳስባቸዋለሁ።

በዚች ዓለም ከምናየው ከምንሰማው ይህን በመሰለ ነገር ከምናውቀው ፍጥረት ሁሉ ለኛ እንደሚመስለን ሰው ነው ከሁሉ የበለጠ ፍጥረት። እውነትም የሰውንና የቀረውን ፍጥረት አትኦኖር ልብ ብለው ሲመለከቱት የሰው ፍጥረቱ እጅግም የሚደንቅ እጅግም የሚገርም ነው በዚሁም በሚደንቀውና በሚገርመው ፍጥረቱ የሰው ልጅ ሰው ለመሆን ከበቃበት አንስቶ እስካሁን ድረስ ጥበብን እንደፈለገ እንደመረመረ ነው ። ይህን ያህል ዘመን የሰው ልጅ ጥበብን ሌት ተቀን ሲፈልግ ምንም ላይኑና ለጆሮ የሚደንቅ ነገር ሁሉ ቢሠራ ውሎ ውሎ ከመፍረስ ለማምለጥ አልቻለም ። ከሞት ለማምለጥ ቀርቶ እንዳይመጣበት ለማድረግ ከሚችለው መከራ ለመከልከል አልበቃም።የዚህን ጊዜ በዚች ዓለም ላይ ከምናየው ፍጥረት ሁሉ የሚበልጥ ሰው ነው እያልን በምን ምክንያት ነው የሰው ልጅ ሊታገድ ወይም ሊአስቀረው በሚችለው መከራ ባህር ውስጥ ገብቶ የሚዋኘው ? ።

በመጽሐፍም በምናየው በውቀታችንም በምንመረምረው ነገር ሁሉ ይህች ዓለም ለሰው ልጅ መፈጠርዋ እርግጥ ይመስላል።ግን ለሰው ልጅ ይህችን የመሰለች ታይታ የማትጠገብ ዓለም ፈጣሪው ሲሰጠው ሰውን ጎደሎ ፍጥረት አድርጎ ፈጥሮ ነው እንጂ ሙሉ ፍጥረት አድርጎ አልፈጠረውም ይህን ስላደረገ ግን ጎደሎ ፍጥረቱን የሚሞላበት የውቀት መንፈስ በሰውነቱ ውስጥ ያሳደረበት ይመስላል ። ግን ይህች የውቀት መንፈስ ባንድ ዓይነት ሚዛን በየሰው ሰውነት ውስጥ እየገባች ስለማትገኝ እንኳን ሰውን አርስበርሱ ይቅርና ሰው ራሱ ለራሱ መከራና እንቅፋት እየሆነ በሚአስበው ሐሳብ በሚሠራው ሥራ ሌላም ሰው እየጨመረ እየራሱንም እያጠፋ ተቀምጡአል ። በንዲህ ያለ ሐሳብ የውቀት መንፈስ ስለምን ባንድ ሚዛን ባህርይ ሁሉ አትገባም በሰውነታችን ውስጥ ያለች የውቀት መንፈስስ ስለምን በትክክል መልክም መንገድ አትመራንም ብሎ ለመመርመር ለሐሳባችን የሚከብድና የሚረቅ ነገር ስለሆነ ይህን ዘሎ ማለፍ ብቻ ነው። ዘለን እንለፈው ስላልኩ ግን ሁላችንም በየበኩላችን ያቅማችንን ያህል ይህን ጥያቄ በራሳችን ውስጥ አርገን ይህን ለመርዳትና ማስረዳት ማሰባችንን አንተው። ይህን የመሰለ የረቀቀ ምስጢር መመርመር ለሚፈልግ ሰው ሁሉ ይህን የመሰለ ሥራ ቢጀምር የሐሳብ መነሻውን ሰው የተባለ ሁሉ በትክክል በማናውቀው በተፈጥሮ ባህርይ ሕግ በውድም ሆነ በግድ ታስረን መመራታችን ተገንዝቦ ይህን ሕግ እንዴት እንደሆነ መመርመር ነው ።

ይህን ሁሉ ሐሳብ ለማሰብ ያስጀመረን ሲቻለው የማይወድ ሲወድ አይቻለውም አለዚያም ሲወድ ለማይቻለው ለሚወድ አይቻለውም የሚለው ቃል ነው ። ይህን ባጭሩ ለሚመለከተው ምስጢሩ ቀላል ነው ። መሠረቱን ይዞ ለሚመለከተው ግን ምስጢሩ ረቂቅ ነው።ምሥጢሩ ቀላል ነው ማለቴም ። አንድ ሰው ሲቻለው ሲመቸው ሥራ ካልሠራ በማይቻለው በማይመቸው ጊዜ ልሥራ ቢል አይቻልም ለማለት ነው ነገር ግን ሰው በማንኛውም ጊዜ ቢሆን በለው አቅሙ መልክም መልክም ለመሥራት የተገደደ ነው።ነገር ግን ይቻለዋል ይመቸዋል በምንልበት ጊዜ መልክም ሥራ አልሠራም ለማለት እንዴት እንችላለን ? ማለት ከዚህ በላይ እንደተናገርኩት ሁሉ ሰው ሲባል ሁሉም በየሰውነቱ ውስጥ አንድ ዓይነት የውቀት መንፈስ አላደረበትም።ለኔ መልክም መስሎ የሚታየኝ ላንዱ መጥፎ መስሎ ይታየዋል።ላንዱ ጥቅም መስሎ የሚታየው ላንዱ ጉዳት መስሎ ይታየዋል።አንዱ ለኔ ኃይልና ጥበብ ያለው መስሎ ቢታየኝ አንዱ ደግሞ ኃይልና ጥበብ ያለው መስሎ አይታየውም።አንዱ ለኔ የተቻለውና የተመቸው ቢመስለኝ ያለኔ እንዲህ የመሰለኝ ሰው ሰውነቱን ስለሚያውቀው ያልተቻለውና ያልተመቸው መሆኑን ተረድቶት እስቲቻለውና እስቲመቸው ጊዜ ይጠብቅ ይሆናል፡ይህን የመሳሰለውን ነገር ሁሉ ከተመለከትን በኋላ በጊዜ ለኩሉ የተባለውን ቃል ልብ ማለት ይገባናል።ማንኛውም ነገር ያለጊዜው ሊሠራ አይችልም ጊዜውም የደረሰ ነገር እንኳን ተግተውበት ባይተጉበትም እሱ ሠሪውን ይፈልጋል።በዚሁም ምክንያት ተንቀሳቃሹንም ሆነ የማይንቀሳቀሰውን ነገር ሁሉ የተፈጥሮ ባሕርይ ሕግ እንደምትገዛው ሰውነቴ ስለተረዳው ይህችን የተፈጥሮ ባሕርይ ሕግ እንመርምር አሰኘኝ ።

የተፈጥሮ ባህርይን ሕግ ለመመርመር ብዙህ ስንክሳር ነገር ማወቅ የግድ ይገባናል ከነኝህም ስንክሳር ነገሮች ዋና የሥራ መጀመሪያችን ምንድነው ብንል የዚህ የሥራ ዋና መጀመሪያው ሰው ምንድነው የሰው ኃይሉ ምንድነው ብለን እንጠይቅ ። ይህም ሁለት ክፍል ነገር ነው መጀመሪያው ሰው ምንድነው ስንል ተፈጥሮአችንን ለማወቅ ኃይማኖትን በመሰለ መንገድ ፍጥረታችንን መመርመር ሁናቴአችንን ማወቅ ነው። ሁለተኛ ኃይላችን ምንድነው ስንል ድንጋይን ብረትን ዕንጨትን ተመልክተን ልጅ ማንበብ መጻፍ ሲማር መጀመሪያ ሀ ብሎ እንደሚጀምር እኛም እነኝህን ነገሮች ከመሠረታቸው መማር የግድ ያስፈልገናል ። ይህን የመሰለውን ነገር ከመሠረቱ ይዘን በየደረጃው እየወጣን ስንሄድ ማነኛውም ነገር ሁሉ በየማዕረጉ ግማሹም ጉልህ እየሆነ ብዙውም እየረቀቀ ለማሰብና ለመፈለግ እየተመቻቸ ይቀርባል ። ይህን በመሰለ መንገድ ጥበብን በጥበብ ካልፈለግን ያሥር ብርን ጣም ለማያውቅ ሰው ሺህ ብር ቢሰጡት የዚህ የሺህ ብር ዋጋ ከዚህ ካሥር ብር ይበልጣል ለማለት አይችልም ። ማለት ከንቱ ድካም ነው ።

ቢነሱ እንዳልካቸው

የቅንነት ስራ አገሩን መውደድ ነው ።

ለኢትዮጵያ መልካም ሥራ ሰሪ እነማን እንደሆኑ ለማወቅ ኢትዮጵያን በውቀት ለማስፋት በእሙንነት ሥራ ለመሥራት ከልባቸው ለማገልገል ንጹሆች የሆኑት ናቸው ለሐገራቸው ሁሉ ብልሃተኞች አስተዋይ ተብለው ክብራቸውን ለመቀበል የሚጠሩት ናቸው ። የሀገራቸውንም ክብር ለማስፋት የሚጥሩ ሁሉ የሰላም ምንጮች የውቀትን ሥራ እየመሉ ለሀገራቸው ልጆች የነውትን ትምሕርት ይገልጻሉ እነዚህ በውነት ለመንግሥታቸው የጥበብ ምንጭ የሆኑ ናቸው ።

ሁለተኛ ።

አገራቸው ክብር እንድታገኝ ኢትዮጵያን በመከችነት እየጠበቁ እሙኖቻቸውን እየሰበሰቡ አዋቂዎችን በፍቅር እያከበሩ እውነትን አስፍተው የተካከለውንም የቅንነት ሥራ አቅርበው የሚኖሩ ሁሉ ኢትዮጵያን የሚመሠርቱ ናቸው እነዚህ በውነት ኢትዮጵያን በክብረትና በውቀት ለመኖር ሁሉም በአንድነት ሁነው በዕንቁና በወርቅ መንግሥታቸውን ባገልግሎት ከፍ ከፍ አድርገው የሚያድሱ ክቡራኖች ናቸው ።

ሶስተኛ ።

እላንት የኢትዮጵያ አገልጋዮች የሆናችሁ ብልሃተኞች ለኢትዮጵያ መልካም ሥራ የሠራችሁበት ክብራችሁ በብርሃንና ሰላም አባታችን ስም እሙኖች የተባላችሁ ናችሁ ። ለመንግሥታችሁም መካችነት የምታስተውሉና በጀግንነት የምትውሉ ለሀገራችሁ በምነት የምትጠሩ እላንት ናችሁ የኢትዮጵያንም ስም የሚያመስግኑ ሁሉ በመንግሥ ታቸው ፊት የተባረኩ ናቸው በእግዚአብሔር መንግሥት ከጻድቃን አንድነት ትባረክ አሜን ።

አራተኛ ።

የከፋት ሥራ እንደ ሥራይ በውስጥ ናት ።

የከፋት መሠረት የሚባሉት እለማን እንደሆኑ ለማወቅ ለጥቅማቸው ተስማምተው ተንኮልን ደርበው ሐሰትን አንጥፈው ያሃገራቸውን ጥቅም ቀንሰው እውነተኞችን ረግጠው እኛ ካገኘን መንግሥትና ሕዝብ ይቸገር ይጨነቅ እያሉ እንደ ጅብ አፋቸውን ከፍተው ክርማቸውን ወጥረው ጥጋብ አስክሯቸው አፍንጫቸውን እንደ ክርማ ወይፈን እየነፉ እክልክል ገብተው እያናፈሩ እንደ ወጠጤ ፍየል የሚደባለቁት ናቸው አሁን አሁን ባድማ እየታደሰ የኢትዮጵያን ቅንነት ሥራ ሠሪ የሚባሉትን ክልክል ጠባቂዎችን በጠንቅ ሥራ ተይዘው አዳሪው መሀከል ወድቀው እንባቸውን በልቅሶ እያፈሰሱ ወደያ ወዲህ በጩኸት እየተንቈራጠጡ ወደላይ ያለቅሣሉ ከተንኮለኞችም የሚያድናቸውን ይለምናሉ ።

አምስተኛ ።

እለዚህ ሰዎች እንደ ነቀርሣ ውስጥ ውስጡን እያቆሰሉ በሀገር ተተንዙ ጀምሮ ለሰው ሁሉ ጤንነትንና ፍቅርን አጥፍተው እንደ አንበጣም የመንግሥቱን ስንዴ የሚቃርሙ ትሎች ስላሉ እስኪ ጠፉ ድረስ አንድም የሚድን እንደሌለ በትሎች ሥራይ የታመሙት ለሀገር የሚጥሩ ብልሃተኞት እለማን ይሆኑ። አታላዮች ተረድተውታል ነገር ግን በውነተኞች እጅ ወሰካቸውን ቢመረምሩት እንደ ሽንፍላ ቢገላለጥ የማይጠሩት ናቸው ። እለዚህ ጥጋብ ከሸፈናቸው ወዲህ በሀገር አገልጋዮች ላይ እንደ ሳል ከልብ ተተክለው እንደ አለቅት ተተክለው መርዝ ሁነው ጕረሮ ዘግተው ሰውን ያበላሹት እንደ ትሎች ያሉ ። በሽቶች እንደሆኑ ለተገለጻላቸው ለመንግሥታቸው መካችነት የሚያስተውሉ የውቀት ምንጮችን ለማጥፋት የነገር ሰበካ የሚጐነጉኑት ናቸው ።

ስድስተኛ ።

እነዚህ የተንኮል ምንጮች የጠንቅ ሥራ የሠሩ እንዳይመስል የበግ ጠጉር ለብሰው ባፋቸው ይለሰልሣሉ ነገር ግን ውስጡ ውስጡን በነገር እንደ ተስቦ እየጠረጉ ልክ የሌላቸው የሥራቸውን ዘር ስር ቢለኩት ሁለት ጊዜ መቶ ተንኮል ሁነው ክፋትን እየጨመሩ ሐሰት እየደባለቁ ጥቅምን በድምር እንደ ፍራሽ ጐዝጉዘው መከራን እያሸከሙ ሲኖሩ ንማም አይችለን ኃይልና ጉልበት የገንዘብ ብዛት ሸፍኖናል እያሉ እኛ ካገኘን መንግሥትና ሕዝብ ይቸገር ይጨነቅ የሚሉ ሁሉ የእግዚአብሔር ቁጣ እንደ ሰም ያቀልጣቸዋል ለመንግሥታቸው እሙኖች የሆኑትን ለማውደም የነገር እሾህ የሚበትኑት ናቸው።

ሰባተኛ ።

ኤድመኞች ተንኮል ከምግብ እየጣመቻቸው የክፋትና የጥቅም ፈለሥፉ ሁነው እየወሰለቱ ባፈ ታሪክ ነገር እየሰበኩ እንደ ሣጥን አይጥ ሁነው የተንኮል ጐተራን አስፍተው ክልክሉን ስንዴ በልተው ሲጨርሱ የማይገባውን ክቡር በልቶ ማስታወክ አይቀርምና ከዘረፋት ክልክል ሜዳ መሬት አጕንብሰው

አፋቸውን ከፍተው ማስታወክ እየለበቀ ብር ብር እያለ ይህ ያው የታመመ ሆድን የሠራ ሰውነትን እሌባ ጣት ስር ሲነኩት ሀሊና ተከዞ ጥርስ ተከፍቶ ዓይን ተጨማዶ ያለቅሳል እንደዚህ የታመመ ሆድ ማስታወክን ያመጣል ። ነገር ግን በተንኰል መብላትን የማይወድ ሆድን እየዞሩ ቢነኩት የሆድ በሽታ የሌለበት ሰውነትን በተንኮል ቢቀሰቅሱት ያልታመመ ሆድ ተደንቆ ጥርስ ይስቃል ማስተወበም የለበት ።

ስለ እዚህ ክዚህ በላይ ክፋትን የሚሰሩ ጠንቀኞች እሌማን ይሆኑ ለማወቅ በተንኮል የሚዘርፉትን ጥቅምና ዓመፅን ያጸኑ ሁሉ የሚሰሩትን ግፍ ሥራ በምግባራቸው ሰውነታቸውን ስለ እሚነካቸው ስለምን የክፋት ስውር ሥራችንን ገለጸብን ብለው አሁን ወደ ፊትም ለማጥፋት መርዝ ጕርሰው በአድማ የሚሳለቁት ናቸው ። ሰው ሆይ ለሰላም ለፍቅር ተፈጠርን እንጂ ለተንኮልና ለአድማ አልተፈጠርንም ።

ዮሐንስ መ

የምሥራች

በከፋ አውራጃ ታከለ ወልደ ሐዋርያት የሚባል አገሩን የሚአደና መርምሮ የሚያስታውቅ ተወለጋ ወደከፋ በልዐል ቃል ታዝዞ አለፈ በከፋ ደህና እየመሰሉ ጉቦ እየሰጡ ሃገረ ገዦዎችን እያታለሉ በውስልትና የሚኖሩ ሰዎች ኖረዋል የቀረቡት እንደልምዳቸው ጉቦ ይዘው ቢሄዱ እንቢ አላቸው አሉ ። የራቀውንም እያሰለለ ብዙ ሌባ አሲዞ አገሩን አማን አደረገው አሉ ። ባቅራቢያው ያሉት አገሮችና ባገሩ ላይ ያሉት ሕዝቦች አመስግነው ቢነግሩኝ ደስ አለኝ ይልቁንም ባቅራቢያው ያሉ አገሮች ሁሉ የሱን መበርታት ሰምተው ጌራ ጅማ ኮንታ በጣሙ ሰላም ሆኑ ተሊሙ በቀር ። ሊሙና ከፋ ልዩ የላቸውም የከፋ ጭላንጭል ስሊሙም ቢደርሰው ደግ ነገር ይመስለኛል እኔም ይኸነን ጻፍሁ ለብዙ ኃይለኞች ያሳቸገራቸውን ።

ቀጥ አረገው ከፋን ታከለ ብቻውን
ኃይል መስሎኝ ነበር እኛን የቸገረን
እሱስ ጉቦ ኖሯል ያጠፋው አገሩን
ሰራዊት ተማብዛት መድፍ ተመጪን
ገንዘብን ጨርሶ መማር ጥበብን
ምሎ ተገዝቶ መተው ነው ጉቦን
ጥቅሙን በታከለ አየሁት አሁን
መታመን አንድ ትርፍ መፈራት ግርማ፣
ይህ ሁሉ አይገኝም ታልተውት ጉቦን
በሥራ ላይ ሁሉ ከፋ የነበርን
እንዴት ተቃጠልን የፍረት ሞት ሞትን
ተብዙ መሳሪ ተብዙ ሰራዊት እንድ ሰው በልጦን
ባንዲት ወር ተከፋ አጠፋው ሌባን

ታከለ ወልደ ሐዋርያት ተከፋ ወደ ጅማ አገር ለማየትና ጅማ አባ ጅፋርን ለመገናኘት የካቲት ፳፩ ቀን ጅማ መጥቶ ነበር ነገር ግን በከፋ ያለውን ሌባ ሰብስቦ ይዞታል እየተባለ ሰንብቶ ነበር ጉቦም አይበላም እያሉ ጅማ ላይ የገባ ጊዜ ጅማንም ሊፈትሽ ነው ብሎ ደሃው የፖለቲክ ወሬ አወራ ቢአወራ ተሊሙ አዲስ የመጡ ፊት በውስልትና የሚኖሩ ጅማ አባ ጅፋር ያላወቋቸው ሰውም በጣሙ ያለመዳቸው ኖረዋል እሱ የገባ ለት ሌቱን ጠፍተው አደሩ አሉ ስለዚህ ይኸነን ጻፍሁ

ምነው ቀበጥ አለ ይኸ ልጅ ዘለለ
ግርማው ተጉበዘች ልክ ሆነ ታከለ
የጅማ ሌቦች ስለተሰደዱ
ከፋ ያለ ሌባ ታከለ የሚሉ ተስቦ ወርዶበት ።
ጅማ ተሰደደ እንዳይገበበት

ሊሙ ወስላታ ስለበዛበትና ሕዝቡ ቤቱን እየተወ በያቅራቢያው ባለ አገር ስለተሰደደ አይቼ

የከፋ ተስቦ ተሊሙ ቢወርድ
በውነት ማግኘት ነበር የሥላሴን ፍርድ
የሊሙውስ ነገር መቸም አላማረ
ከፋ ደስታ ሲአገኝ እሱ አልቅሶ ቀረ
ጓደኞች ነበሩ ወይ ሊሙ ወይ ከፋ ተጧት እስተማታ
ከፋ ኩራት ይዞት ተለየ በደስታ
ልዑል ተወንድሙ አይለዩት ደስታ አይገፈጉት
እድሜም ይለምናል ለመንግሥቱም ሃብት
አንድጋ ደባልቀው ጠሩን ያስማሙት

ጠሩ በ፺፮ ዓመት ተለያየን የቤት ልጅና ወርዋሪ በማደሯ ብንለያይ ጠሩ ባንድ አለቃ አንዘምትም ኖሯል ወይ ። ራስ ተቆርጦ እግር እንዴት ይኸዳል ።እናት ተልጁ እንዴ ይለያል። እያለ ሲአዝን ስለ ሰማሁት ይኸነን ጻፍሁ

መሐሪ ረታ

ስለ ዕውቀትና ድንቁርና መለየት

ከዕለታት አንድ ቀን ኢየሩሳሌም ሰማያዊትን ለማየት ስገሰግስ የራስ ምሉ ጌታ ልጅ አቶ ልቡና አራቱ መዓዝን በሚገናኝበት ቤት ሰርቶ ወዳጅ ጠላቱ ሳይል የመጣውን እንግዳ ሲቀበል አገኘሁት አጋፋሪውም አቶ ሥልጣኔ የጌታየ ምግብ ለሆድ የማይከብድ ረቂቅ ሃሣብ ነውና ግድ የለም ተጋበዙ ሲል ቶሎቶሎ የሚበሉ ሃብታሞች አንዳንድ ሰው ነበሩ የሚበዙት ድሆች ግን ንቀው ተጸይፈው ሽታውንም ጠልተውት አፍንጫቸውንም በጨርቅ ሸፍነው ልማድ ከሚባል ከረብታ ወጥተው አሻገረው ይመለከቱ ነበር ከሚመገቡትም ሰዎች መካከል ያገር ቅንዓት የሚባል አዝማሪ ቁሞ ነበርና በሠርግ ቀን የምትመታውን ምት እየመታህ እንግዶቹን አጫውት ተብለ እሱ ምታጥቆ እጅ ነስቶ መሰንቆውን ይዞ ገና አፉን ሲከፍት ውብታም ድምፀ መልካም መሆኑን አየሁና በጭንቅ በመጣጣር ከመካከል ገብቼ ቀረብ ብየ ለመስማት ጆሮየን ጣል አደረግሁ ከልብ እየነካ ሲያፈሰው የነበረውም መዝሙር ልክ የሌለው በጣም ብዙ ነበረና ሁሉንም ጨርሶ ለማጥናት ባይሆንልኝ አልፎ አልፎ ያጠናሁት ከዚህ በታች እንደሚከተለው ነው ።እናንተ የጽዮን ልጆች ተፈሪንና እናቱ ዘውዲቱን ለማየት ውጡ በሠርጉ ዕለት በደስታው ቀን ያደረገችለትን አክሊል ተመልከቱ

እልል በሉ የምስራች ስጦታ ተቀበሉ መኃ ፪ ፲፩ እነሆ ክረምት ድንቅ‐ርና አለፈ ወደኋላውም ተመለሰ የትምርት ቤት አበባ በኢትዮጵያ ተገለጠ የዕውቀት ብዛት ጊዜ ደረሰ የዋልያ ብርሃንና ሰላም ቃል በምድራችን ተሰማ በዘውዲቱ ዘመን ሃማባችን በለስ ጨበጨበ በተፈሪ ወራት ወይኖች ተማሪዎቻችን አበቡ የሽቶቻቸውን መዓዛ ሰጡ ርግቤ ሆይ ኢትዮጵያ ከዋሻው ልማድ ከደንጊያው ቸልተኝነት ንቂ መልክሽ ሥልጣኔን አሳዪ ብርሃንና ሰላም ድምጽሽን አሰሚ ድምፅሽ መልካም ፊትሽም ያማረ ነውና መሃልይ ፪ ፲፩እስከ ፲፬ ። ወደከርቤ እውቀት ተራራ እኼዳለኹ ወደዕጣንም ማስተዋል ኮረብታ ከሣኔር ራስና ከኤርሞን ከነበሶች መኖርያ ከነብሮችም ተራራ ተመልከች እቴ ሙሽራ ኢትዮጵያ ሆይ ፍቅርሽ ማስተዋል ምንኛ መልካም ነው ፍቅርሽ ማስተዋል ከወይን ይሻላል የርህራኄሽም ቅባት ከጭከኔ ሽቱ ሁሉ ይበልጣል ከንፈርሽ ቸርነት የማር ወለላ ያንጠባጥባል የልብሽም ደግነት መዓዛው እንደ ሊባኖስ ሽታ ነው ብሎ ያማረኛውን ቃል ጨረሰና ቀጥሎ በግዕዝ ቃል ገነት ዕፁት ዓዘቅት ሕትምት እህትየ መርዓት ኢትዮጵያ መኃ ፬ ፰ ፱ ፲ ፲፩ ፲፭ እያለ ሲዘምር ያነጋገሩና ያደራረሱ ምልዓት ልብ አድርጎ ለሰማውና አስተውሎ ለተመለከተው እጅግ አድርጎ ያስደንቅ ነበር ። ክቡራን የብርሃንና ሰላም ወዳጆች ጌቶች ሆይ ሃብታሞቹ እንደ ራበውና እንደ ቸገረው ሰው ቶሎ ቶሎ ሲበሉ ከቤታቸው ቀሩ ሺ የሌላቸው ድሆች ጣፋጩን ምግብ መጸየፋቸው ምን ይመስላቹህ ይሆን ? አሁንም የጐደለውን ሞልታችሁ የጠመመውን አቅንታችሁ በብርሃን እንድታስረዱኝ በሰላም አስታውሳለኹ ።

የኔ ቅኔ ባያደርሰኝ ያንድ ሊቀ መወድስ አስከትላለኹ። ቴጽለ ዕፀ በሰስ ሞተ እምድህረ ፈረየ ተውላጠ በለስ ረከቡ አስካለ ማርያም ወይኖሙ ሥጋ ወነፍስ እለ ፃመዉ ቀዲሙ ። ከመ ይትከፈሉ በዕፃ ርስቶሙ ። እስመ ውስተ ገነት ሃገሮሙ ፤ በእመደ ልእኩ ኂሩት ኀይለ ሥላሴ መርሆሙ ለሕዝብኒ አዕፁቀ ዘይት ጣዕመ አስካለ ወይን ዘቦሙ ኀበ ሙኀዘ ማይ እእምሮ ምኒልክ ተከሉሙ ። ወበበጊዜሁ ሰላመ ከመ ይፍረዩ ኵሎሙ ሥርው ኀይለ ሥላሴ ለአዕፁቀ ይፀውሮሙ በላይ ሐጐስ።

ሎተሪ ።

በሙሴ ዜ ሐሻዱሪያን ዋና ፈታሺነት ።
የተሰናዳ ትልቅ የዕድል እጣ ።

እጅግ የከበረና ጥቅም ያለበት ሁለት መቶ ኃያ እጣ ሎተሪ በውስጡ የሚገኘው ሁለት አቶመቢል ጥሩ ጥሩ ፈረሶችና በቅሎች ጠመንጃ እረሺ ሺጉጥ ሲንጀር መኪና ሰአት የኪስም የጠረጴዛም እጅግ ጥሩ ጥሩ የሆነ ሥጋጃና ጁህ ካባ በያይነቱ ሱፍ የኮት ጨርቅ እጀጠባብ የወርቅ መስቀልን የመሳሰለ ጌጥ እንደዚሁም በያይነቱ ጥሩ ጥሩ እቃ በድምሩ ዘጠኝ ሺህ ብር ዋጋ ያለው እቃ ነው ያንዱ እጣ ዋጋ አራት ብር ነው ሁል ጊዜ እንዲህ በጥራትና በትክክል ሆኖ የማይገኝ እድልን መፈተኛ ነገር ስለሆነ የማታለያ መስሏችሁ ችላ ስትሉ ያመልጣችሁና እንዳይቆጫችሁ እናመለክታችኋን ይህን ሎቶሪ የሚአደርጉ ሰዎች ሐሣባቸው የእቃቸውን ዋጋ ለማግኘት ነው እንጅ ሌላ ትርፍ አይፈልጉም ስለዚሁም የሚሸጠው ወረቀት ብዛት በዚያው በቃው ዋጋና ለዚህ ስራ በሚአስፈልገው ክሣራ ልክ ተወስኑዋል

የዚህን ዕቃ ጥሩነት ለማስረዳት ማንኛውንም ማመልከቻ መጻፌ ትርፍ ነገር ስለሆነ ዓይን የሚአየው ነገር ይሻላል በማለት የዕቃውን ጥራት ለመረዳት የሚፈልግ ሰው ሁሉ ዓይኑ እንዲያይ እንዲረዳ በሎተሪ የሚወጣውን ዕቃ ሁሉ በሙሴ ዜ ሐሻዱሪያን ቤት አስቀምጠነዋል ቤቱም ከዱሮው ማዘጋጃቤት ግርጌ ነው ከዚህ በፊት በየወጣው ወረቀት ላይ እጣው የሚታይበትን ቀን አለ ማመልከታችን ምን አልባት በቶሎ ማይሸጥ ይቀርና ቃል አባይ ያደርገናል በማለት ነበር አሁን ብናየው የዕቃ ብዛትና ማማር ሰውን ደስ ስላሰኘው ወረቀቱ በፍጥነት ብዙ ተሸጠልን ትንሽም ቢቀር የቃው ጥሩነት ጋር አያማጣንም በማለት እጣው የሚወጣበትን ቀን ባስራሁለት ግንቦት በሙሴ ቴራስ ሆቴል መሆኑን እናመለክታለን እድላችሁን ለማየት የምትፈልጉ ሰዎች ሁሉ ወረቀቱ ተሸጠ ማያልቅባችሁ ቶሎ ቶሎ ተሻሙ ።

ስለ ሕዝብ ጤንነት

ይድረስ ለክቡር ወንድሜ ልጅ ጥሩነህ ለማእርግህ የሚገባ ሰላምታዎቼን አቀርብልሃለሁ ። ወዳጄ ሆይ ባራተኛው ዓመት ፲፩ኛው ቁጥር በመጋቢት ፳፯ ቀን ለሃገርህ ሰዎች ጉዳት የመሰለህን የጥንቃቄ ምክር ጽፈህ ስላመለከትከን በጣም አመሰግንሃለሁ ። ነገር ግን የሕዝቡን ጤንነትና የከተማውን ጽዳት ጠባቂና አከናዋኝ የማዘጋጃ ቤት ነበር ለዚሁም አንተ በጻፍከው በሽታዎች መርማሪና ጠባቂ የማዘጋጃ ቤት ስለ ሆነ መጀመሪያ አንድ የተሃከለ የህክምና ቤት አቁሞ አንተ እንደጻፍከው ሴትኛ አዳሪዎችን በየጊዜው ጤንነታቸውን ማስመርመር ይገባዋል ሁለተኛም ሴትኛ አዳሪዎች ኑሮአቸው በንዲሁ ከሆነ እንደ ገቢአቸው መጠን ትህክለኛ የወር ግብር ለማዘጋጃ ቤት የሚከፈል ደንብ ማቆም ያስፈልጋል ፤ ባዲስ አበባ ላይ ብዙ ገቢ ያላቸው ሴትኛ አዳሪዎች ናቸውና ፫ኛም ባንድ ቀን ካንድ ሰው ላይ ሴትኛ አዳሪዋ የምትቀበለውን ያህል የማዘጋጃ ቤት መወሰን ይገባዋል ማለት ካንዳንድ ከውጪ ባላገር የመጣውን ሰው አታለው ገንዘቡን ባንድ ሌሊት ያለውን ሁሉ ቢወስዱበት ያም ሰው ቢደኸይ ጉዳቱ ለመንግሥት ነውና ግን የማዘጋጃ ቤት በሴትኛ አዳሪዎች ላይ ትህክለኛ የወር ግብር ቢያደርግ ከየት አምጥተው ይከፍላሉ እንዳይባል ጠጅ ጠላ ይሸጣሉ በዚሁም ላይ እንደ ሃምሳ ስልሳ ደግሞም ከዚሁ የበለጠ የወር ገቢ እንደ ማእርጋቸው አያጡምና ስለዚህ የተተሃከለ ግብር እነሱ ላይ ማቆም ያስፈልጋል ለዚህ ልጅ ጥሩነህ ለጻፈው በሽታ የማዘጋጃ ቤት እውቀቱ የተመሰከረለት ሃኪምና ሆስፒታሉንም ካቆመ በኋላ እነኚህ ሴትኛ አዳሪዎች ሁሉ በየጊዜው ከተፈተሹ ይኸውም በሽታ ከከተማው ውስጥ እንዲቃለል አይጠረጠርም ለዚሁም ልጅ ጥሩነህ ለጻፋቸው ነገሮች የከተማው ከንቲባና የማዘጋጃ ቤቱ ዲሬክተር አስበው እንዲያከናውኑት ስል ብርታታቸውን እተማመናለሁ ። በቀለ ዘለቀ

ማስታወቂያ ።

ሺብሮሌ ኦቶሞቢሏ በኢትዮጵያ ወኪል ።
ሔ ሚ ዜርቦስ ኩምፓንያ ።



Automobiles CHEVROLET

H. M. ZERVOS & Cie
REPRESENTANTS
BAS PRIX HAUTE QUALITE

የሚከራይ ።

A LOUER

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ ኦቤርላንድ ኦቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጦጦን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ፥ ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።



አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባ ኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወድያም ባለማግኜቶና ባለባተሪ ነው ካምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ ኦቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል «ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው

ወዲያውም የኦቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

COGNAC S&E&A.METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ፡፡

ማስታወቂያ

መጽሐፍና ደብተር የሚያስጠርዝ ሰው በርካሽ ዋጋ በልውል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ይጠረዝለታል ።

ያረጀ መጽሐፍና መዝገብ ማሳደስ ለፈለገ ሰው በርካሽ ዋጋ እንደ አዲስ አድርገን እንጠርዝ ለታለን ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠሪው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩግቢ

RUGBY

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶመቢል በተለይ ወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፥ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፥ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ ።

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህ በካፕሱሉ ያለ ምልክት መር ምሩ ይህ ምልክት በካፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ጉድይር ግዙ





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው።በሌላጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ፤ ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አራተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፲፯
4 me ANNÉE № 17

ሐሙስ ሚያዝያ ፲፰ ቀን፣ ፲፱፻፳ ዓ ም ።
JEUDI 26 AVRIL 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

አንብቡት እወቁት ልመዱት ።

በተቃጠርንበት ጊዜ ልክ ሳልቀር እክበሩ ቄስ ዘንድ ሄጂ ነበረ ። በደረስሁም ጊዜ ፊታቸውን ብመለከተው እንደ አንድ ትልቅ ፍሎዞፍ መልክ ሆኖ አገኘሁት ። እርሳቸውም በቃላቸው ሳይናገሩኝ በጣታቸው እንድቀመጥ አመለከቱኝ ። ከተቀመጥኩ በኋላ ወዳጄ ከፒቴን ሆይ ዛሬ የጥያቄው ተራ የኔ ነበረ ። ነገር ግን ባለፈው ሳምንት የጠለቀ የእውቀት ንግግርና ወይም ሞራል እንጫወታለን ስላሉኝ አሁን እሰማዎት ዘንድ እፈቅዳለሁና ይጀምሩልኝ አሉኝ ። ቤታቸው ምንም ጫጫታ የማይሰማበት እጅግ ዝምታ የመላው ነበረ ። በመስኮቱ ብቻ የአንድ ድምጹ ያማረ ዘፋኝ ወፍ መንጫጫት አንድ አንድ ጊዜ ይሰማኝ ነበረ ። ደግሞም የሄድሁበት በቀትር ነበረ ዝናብ ዘንበ በቤቱ ውስጥ እንደ ወርቅ የሚያንጸበርቅ ጠብታ ሲንጠባጠብ ልዩ ልዩ የሆነ ድምጽ ይሰማኝ ነበረ ። በዚህ ጊዜ ነገሬን ስጀምር የነዚህ ጩኸት መሰማቱ ቀረ ። እኔም መልክም መሆኑን አይቼ በደስታ እየቀጠልሁ አልኋቸው ።

መጀመሪያ ፡ ክፍታ ፤ ክብር ፤ ችሎት ፤ ፍቅር ፤ እነዚህ አራቱ ነፍስን ከፍ ማድረግ አይችሉም ። የልብ ንጽሕና ነው እንጂ ፤ ያለ ጉብዝና ደስታ የለም ፣ ያለ መጋደል ጽድቅ አይገኝም ፤ በማይረባ ነገር የማይገሥጽ አስተምሕሬ ማስተማር አይገባውም ። በራሱ ደስ የማይለው የድካም ምልክት ነው ። በራሱ ደስ የሚለው የዕብደት ምልክት ነው።።

በክፉ ነገር ቢያነሱህ አንተ መንገድህን አሳምር ከንቱ ነገርም ቢናገሩህ ስቀህ ማለፍ ነው አስቀድሞ መልክም አስተዳደግ ለከበርቴው ጌጥ ነው ለድኃም ዋና ገንዘብ ነው ለሃሳብህ ያልተስማማ ነገር አብዝተህ ብትዘራ ያነሰ መከር ታጭዳለህ አስቀድሞ ደግ መሆን ያስፈልጋል ከዚያ በኋላ ደስ ይለናል፡ድል ሳንነግ ሽልማት ስጡን ብለን መለመን አይቻለንም ሳትሠሩ የቀን ደመወዛችሁን አትፈልጉ ከልዝብ መላስ በተቀር ምን የተከበረ ነገር አለ ? የእውቀት መክፈቻ የእውነት መሥሮ የደስታም ምንጭ እርሱ ነው ይህ ሁሉ በደግ አስተዳደግ ነው የሚገኘው ደግሞ በርሱ ዓለምን መግዛት ከልተመቸ ነገር መካከል ላምላክም የሚገባውን ምስጋና መስጠት ይቻላል ይልቁንም ደግሞ በዓለሙ ሁሉ የጥፋትና የክፋትን ነገር ሁሉ የሚመጣው በዚሁ በመላስ ነው የጠብ ዘመድ ነውና የመከሰስም መክፈቻ የጦርነትም ምንጭ ነው በርሱ ነው ከተሞች የሚፈርሱ የአምላክ ክህደት የሚደረገው ።

ከማናቸው ሰው ጋራ በደግም በክፉም አትነጋገሩ የከበረ እንቋችሁን በእሯ ፊት አትጣሉት እውቀት ያላችሁ ሰዎች እውቀት ከሌለው ሰው ጋር ስትነጋገሩ የውቀታችሁን መክፈቻ እንደ ዚያው እውቀት እንደሌለው ሰው ዝቅ አድርጉት ይህን የምታደርጉት ዕውቀት የሌለውን ሰውልቡ በኃዘን እንዳታቆስሉት ነው ይልቁንም አንዳንድ የአበባ ቅጠል ከፊቱ ጣሉለት እንጂ የዜህን ከፊቱ የጣላችሁትን አበባ ሽታ ሳይሸተው የቀረ እንደሆን የጣላችሁለትን ያበባ ቅጠል አንስታችሁ ከርሱ ተለዩ ማለት ገና ቀኑ አልደረሰምና ነው ያችን ያበባ ቅጠል አንስቶ ያሸተታት እንደሆን ግን እጁን በፍቅር ይዛችሁ ወደአበባችሁ አታክልት ውሰዱት ከዚያ የአበባውን አታክልት ከያይነቱ ያለውን ሁሉ አሳዩት

የቀሩትን ሰዎች የውቀታቸውን ዋጋ ልክ አትንቀፉ የእውቀታችሁን ዋጋ ልክ እወቁ እንጂ አካሄዳችሁ ሁሉ በተከከለ በተመቸ መንገድ እንደሆን አድርጉ በየቀኑ የተዋረዳችሁ ሰዎች አትሁኑ የተከበራችሁ ሁኑ እንጂ በሴት በመጠጥ በቁማር ጨዋታ ሰውነታችሁን በውርደት እንዲጠመድ እንዳታደርጉት በንደዚህ ባለ ነገር ባርነት መግባታችሁ መሆኑን እወቁ የቀጣፊዎች የወስላቶችና የክፉተኞች መንገድ መብራት ከአንድ ሰዓት ይበልጥ አያበራም እስኪነጋም ድረስ አይቆይም።በአፍለኝነ

ት ጊዜ በእርጅና እና በሞት መከከል ያለ አለመስማማት አፍለኝነት ጦርነት ነው እርጅና ጠብ ነው ሞት ጸጥታ ነው ።

ሁል ጊዜ ፍቅርን ሙሉ ።

ልጆችም ብትሆኑ አፍለኞችም እንደሆናችሁ ሽማግሎችም እንደሆናችሁ ሁሉ ጊዜ አንድ ጎደሎ ወይም ባዶ የሆነ ነገር ባገኛችሁ ጊዜ ሁሉ ፍቅርን ሙሉበት ማናቸውም ክፋት የሚያሳዝን የሚያስቸግርም ነገር ሁሉ ስታገኙ አይጭነቃችሁ በፍጥነት ፍቅርን ወዳለበት ፈልጉት እንጂ የቶቻላችሁን ያህል ለሁላችሁም አጥብቃችሁ እርስ በርሳችሁ መፋቀርን አበርቱ የፍቅር አዠማመር ከእግዚአብሔር ልብ ድረስ አንስቶ እስከ በጣም ትንሽ እሆነችው ወፍ ድረስ ነው እውነተኛው ፍቅር እንደ መቃብር ዝም ያለ ነው ።

ቄሱ መለሱልኝ አሉኝም ይህ የነገሩኝ ሁሉ ሥጋ ለባሲ ለሆነ የተከከለ የእውነተኛ መንገድ ነው ። እንዲሁም ብለው ጠየቁኝ ብዙ የምጠይቅዎ ነገር አለኝ ። ግን በፊት እስኪ የቦልሽቢክን ነገር ያስረዱኝ ። በዓለሙ ሁሉ ሕዝብ የሚጠላቸው ስለ ምንድር ነው ቤተ ክርስቲያን ሁሉ እያስለቀቁ የዘፈን የጨዋታ ቤት የሚያደርጉት ክፉ መሥራትና ሰው መግደል ቤተ ክርስቲያን ማቃጠል የቅዱሳንንም ስዕልና መጽሐፍ የሚያቃጥሉበትን የዚህን ሁሉ የክፋታቸውን ነገር ለሚመጣው ሳምንት እንዲያስረዱኝ አሉኝ ።

እኔም መልሼ አልኳቸው የዛሬ አራት ዓመት ከነድ ሰውየ ጋር ወደ መስኮብ አገር ሂጄ ነበረና እኔው ባይኔ የገዛ ራሴ ያየሁትን ልንገርዎ ይህም ያየሁት ነገር ሁሉ እጅግ የሚቀፍ በብርቱም ግንን የሚል የሚያስፈራና የሚያስጠላ የሆነነው እሱም ይህ ነው ። ያየሁት ሀያ አራት አቡኖችና ስልሳ ራሶች እና ደጳዝማቾች በልሽቢኮች በጠመንዣ እየተኮሱ እንደ ገደሏቸው ስላቸው ጊዜ ። ቄሱ አሉኝ አደራዎን ይኸ የሚናገሩት ነገር እጅግ ለኛ ጥቅም ያለው ነገር ስለ ሆነ ይልቁንም አብሶ ለዛሬ ዘመን ላሉት ለወጣቶች ልጆች ላፍለኞቻችን ሁሉ እንዲያውቁት የሚያስፈልግ ስለ ሆነ ይንገሩኝ አሉኝ ። የሚመጣው ሳምንት የዚህን ነገር ጨርሼ እነግርዎታለሁ ብያቸው በፍቅር ሰላምታ ተሰጣጥተን ተቀጣጥረን ተለያየን ።

ከፒቴን ባቢግያን ።

ትምሕርት ቤት ።

አገሩን የሚወድ የኢትዮጵያ ልጅ የሚገናኝበት ለሀገሩ ጥቅም ባሰቡ ያለውን ለሕዝብ የሚገለጽበት ለመንግሥቱም የታየውን የሚያመለክትበት በበደሉም የሚጮህበት ብርሃንና ሰላም በዘመናችን ስለ ወጣልን በጣም እድለኞች ነን ። እንዲሁም በቅርብ አድጎ ጋዜጣው ከዓለም ካሉቱ ከበለጡቱ ጋዜጦች ጋራ ትክክል ሁኖ እንዲታይ የበለጠ ምኞቴ ነው።

የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ትምሕርት ቤት በያገሩ እንዲሆን ተስፋ እናረጋለን እያሉ ይጽፋሉ ብርሃንና ሰላምም ያልጋ ወራሽ ትምሕርት ቤት ለማየት የመጡትን መኳንንት ያኑ አይተው በተሾሙበት አገር አምሳያውን እንዲያረጉ ለንረቤቶቻቸውም አርአያ እንዲሆኑ ይመኛል ተስፋም ያረጋል ይህንም የመሰለ ማንቀቃት ሁሉ እጅግ ደስ ያሰኛል የሚሰማና የሚያደርግ ግን ሲታጣ እንዴት ቢሆን ይሻላል ትምሕርት ቤት በኢትዮጵያ ሁሉ በየአውራጃው ሊከፈት ይገባል ። ያገሩ ገዦ ግን ታልከፈተው ማን ይችላል ያገሩ ገዦ ግን ይለወጣል ወደ ሌላ አገር ይሾማል ባገሩም ሌላ አዲስ ሹም ይሾምበታል ። ስለዚህ በተቻለው ሁሉ ለራሱ ጥቅመት ገንዘቡን ይሰበስባል እንጂ ላገሩ ጥቅምና ልማት የሚያስብ አይመስልም ባገሩም የተሾመ ገዢ ለሀገሩም ጥቅም ቢያስብና ቢጥር የትምሕርት የላየኛው ደረጃ አልተማረምና ባለማወቅ ይቀርበታል ይህ ታልሆነ ወዴት አለ ሌላ ይቅር ባሕር ተሻግረው ሒደው ተዓለም የሠለጠኑትን መንግሥታት የመኳንንቱን የሕዝቡን የቤተ ክህነቱን አስተዳደር የትምሕርት ቤቱም የወታደሩም ሥርዓት ሁሉ አይተው የመጡት ሹማምንቶች በሚገዙት አገር ልማትና እውቀት እንዲሰፉ ይህን ሥራ ሠሩ ሲባል እስከዛሬ ድረስ አልተሰማም እንዲህ ተሆነ ወዴት እንጠጋ በሀገራችን በቶሎ ትምሕርት እንደጎርፍ እንዲገባ የደረቀውም መሬታችን በቶሎ እንዲያጠጣ የሚበላ አታክልት ሁሉ እንዲያበቅል ተፍሬው አሁን በዘመናችን እንድንጋበዝ ተጥላውም ሥር እንድናርፍ ወደ ምንጩ ወደ አልጋ ወራሽ እንቀርብ እንለምንም በኢትዮጵያ ሁሉ በየአውራጃው ለትምሕርት ቤት የማስገደድ ሥርዓት እንዲያወጡልን እንደሀገሩ ስፋትና ልማት እየታየ የትምሕርት ቤቱ ቍጥርና የሚማሩበት እውቀት (ፕሮግራም) በትእዛዝ የወጣ እንደሆን በፍጥነት እንሠለጥናለን ።

መንገደኛ ሲሔድ ውሎ ተበረሃ ሲመሽበት አንዲት ሌት የሚያርፍበትን ቦታ ያበጃጃል እሾሁን ቆርጦ ደንጊያውን ለቅሞ ከልቶ ጠርጎ ያድርባታል ። እንዲሁም የድንቁርና እሾህ ደንጊያ እድፍ የሚቆርጥ የሚለቅም የሚጠርግ አያቶቻችን የኖሩበት እኛም ያለንበት የልጅ ልጆቻችን የሚኖሩበት ተዓለም ሁሉ አብልጠን የምንወዳት ብሩኪቱ ኢትዮጵያ የሚያዘጋጅልን አንድ ትምሕርት ነው ። አስቀድሜ እንዳልሁ በየአውራጃው ከተሞች ትምሕርት ቤት ቢከፈት የትምሕርት ቤት ፈታሾችም በየስፍራው እየዞሩ ቢጐበኙ በጽፈት ለመንግሥት በትክክል የሆነውና የጐደለውን ቢያስታውቁ በቶሎ በጥቂት ዘመን ተሠለጠኑ መንግሥታት አንዱ እኛ እንሆናለን የኢትዮጵያ ልጆች አእምሮ ይበልጥ እንጅ ተሌሎች አይሰንፍም አእምሮዎችን ብሩህ ተሆነ ምን ይጐድልብናል ገንዘብም ላሁኑ ለመጀመሪያ በኢትዮጵያ ሁሉ እንደአቅሙ በጢስ በመት በመት የሚያወጣውን መንግሥት ቢጥልበት ብዙ ገንዘብ በተሰበሰበ ። አሁን ያሉት የኢትዮጵያ ሀብታሞች ላገራችሁ ትምሕርት አስር ብር ስጡ ቢባሉ ይከብዳቸዋል ልጆቻቸው ግን በግዴታ ቢማሩ በእውቀት አድገው በስልጣኔ ሸምግለው የሚበልጥ ገንዘባቸውን ለሀገራቸው ትምሕርት ቤት ለሌላ ጥቅምም ባወረሱ ስል ያለ ጥርጥር አምናለሁ ። በገራችን ውስጥ የኢትዮጵያ ልጆች ብዙ አይሁድና እስላም ቀማንት አረሚ አሉብን በየእጁ ሃይማኖቱን ተምሮ በኋላም በየከተማው የሥልጣኔ ትምሕርት ቤት ገብቶ ታገሩ ልጅ ተክርስቲያኑ ጋራ አንድነት በግዴታ ቢማር ያገሩ ፍቅር ያድርበታል መሬታችን አንድ አየራችን አንድ እንደሆነም ይ

ገለጽለታል ላገሩና ለንጉሡም ሕይወቱን ይሰጣል ከዚያ በኋላ አንድ ቋንቋ አንድ ሕዝብ ባንድ አሳብ እንታሰራለን ሁላችንም ላገራችን ደህንነት ብቻ እናስባለንና እንሠራለን ከዚያም በኋላ ጠላት መግብያ አጥቶ በመጣበት ይመለሳል ። የነጻነታችን ደህንነት እምነን ለዘላለም በሰላም እንኖራለን ።

ክቡር ነጋድራስ ደስታ እንዳሉት ኢትዮጵያ እራቀቀትዋ ናት ክፉውንና መልካሙን የምታስታውቅ ዓይንንም የምትከፍት የእውቀት ዛፍ ፍሬ ታልቀመሰችም ራቁትነትዋን ሳታውቀው ትኖራለች ።

አሁን ግን እግዚአብሔር ይመስገን ልዑል አልጋ ወራሽ የእውቀት ዛፍ ፍሬ ቀመሱልን በከተማውም ማእዱ ተሰናዳልን እንጋበዝበትም ጀምረናል የማእዱንም ድግስ በየአውራጃው ከተሞች እንዲደርስ ከከተሞችም ለየገጠሩ ከዚያ በኋላ በእርግጥ ኢትዮጵያ በሞላዋ አንድነት በእውቀት ወደ ምሉ ሥልጣኔ ትገሰግሳለች ። ከጥቂት ዓመት በኋላም ከፍ ክሉቱ መንግሥታት ጋራ ትክክል ሁና በነጻነትዋ ኰርታ ለዘላለም እንድትኖር ለጀማሪው ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ዕድሜና ጤና እንዲሰጥልን እንለምናለን ።

ኢትዮጵያ በእውቀት በሥልጣኔ ከፍ እንድትል በዘመናችሁ ። ልታዩ ትምሕርት የቀመሳችሁ ፡፡ ቀን የምትመኙላት ሴት የምታልሙላት ሀገራችሁ። ጐበዞች ደፋሮች በየከተማው ጩሁ በየሰፍራችሁ ። ትምሕርት ቤት ትምሕርት ቤት ኢያላችሁ። በየጋዜጣው ጻፉ መጻሕፍትን ጻፉ እየተረጐማችሁ ። የመጽሐፉን ዋጋ አታብዙ ሊቅ እስከ ደቂቅ እንዲያነብላችሁ ። ኢትዮጵያ ዓይንዋን ብትከፍት ነውና ትርፋችሁ። እውነትን አትሸሽጉ እገሌ ይነቅፈኛል ይጠላኛል ይቀጣኛል ብላችሁ ። የእውቀት ሁሉ መሪ አልጋ ወራሽ ሳሉላችሁ ማንን ትፈራላችሁ ።

ጊ ፡ ሰ ።

ጆሮ አላቸው አይሰሙም ።

አንድ ያገር ቤት ሰው አዲስ አበባ በመጣ ጊዜ ከዚሁ ከተማ ብዙ ቀን ኖሮ ከነበረ ከታላቅ ወንድሙ ቤት እንግድነት ለማደር ቢሄድ ብዙ ዘመን ተለያይተው ነበርና በሕይወት ስለ ተገናኙ ደስታ ሆኖ አምሽተው ምግብ ቀርቦላቸው ከበሉ በኋላ እንግዳው ሰው እግሩን ታጥቦ ጫማውን ተጫምቶ ወደ ጓሮ ቢዞር የወንድሙ ቦታ ሰፊነት ሳለው አትክልት ያልተተከለበት እንዲያው ወለል ያለ ሜዳ ብቻ ባጥሩ ዙሪያ አልፎ አልፎ ግራዋ ተተክሎበት ባየ ጊዜ ትዕግሥት የማይሰጥ ንዴት አድሮበት እየተፋጠነ ወደ ወንድሙ ተመልሶ ምነው ወንድሚ ሆይ እንዲህ ያለ ችልታና ስንፍነት ያደረብህ ከቦታህ ላይ የቀረው ቀርቶ ጐመን ስንኳ ያልተከልክበት ብሎ ቢጠይቀው ወንድሚ ሆይ ምን አደከመኝ ገንዘብ አለኝ ገዝቼ እበላለሁ ብሎ ቢመለስለት ጃንሆይ አጼ ምኒልክ ከፍልወሀ ሜዳ ጤፍ አዝርተዋል ሌላውንም ብዙ ዓይነት አትክልት ከግቢ አቸው አስተክለዋል ይህንን ሲአደርጉ ለጧት ለማታ ትጋታቸውና ድካማቸውን ያላየኸው አይደለህ አይተኸዋል ይህ ሁሉ ድካማቸው አንተን ለማስተማር ነው እንጂ በቆና ምንጃርን ይሁን ያሀል ዳውላ ጤፍ ቡልጋን ይሁን ያሀል ሽንኩርት ማረቆን ይሁን ያሀል በርበሬ ከጐተራዬ ያለውን ለዚህ ቀን አግበ ቢሉት የሚሳናቸው ሁኖ ነውን ? የእግዚአብሔር እንደራሴ ንጉሥ መምሕር ሆኖ ሲአስተምርህ የማይገባህ ልቡና አለህ ብዬ አንተ ቤት አላድርም ብሎት ሄደ የማለትን ወግ አጥንቼ ነበረና በአሁኑ ዘመን የሆነውን አኳኋን ያንን ሳመዛዝነው ሚዛኑ የመሰለ መሆኑን ተመለከትኩ ።

ቢነግሩት ቢነግሩት የማይሰማ ሰው የዘሆን ጆሮ ሰጠው ይባላል የዘሆን ጆሮ የማይሰማ አይደለም በጣም ንቁ ነው ። ሰምቶ እንዳልሰማ የሚሆነው በቁመቱ እርዝመት ባካሉ ውፍረት የተመካ ነውና ማን ይነካኛል ከኔስ የሚበልጥ ምን ሌላ ፍጥረት አለ እያለ ተግንድ ሲታገል ወጣት ሲገነጥል ደስ ብሎት አዳኞች እስከ እሚመጡበት ሰዓት ይቆያል የዘሆን ጆሮ የተበለው በዚህ ምክንያት ይመስላል ።

እኔ ምሳሌ መሰልኩ የሚተ ፡ጉም ይተርጉም ።

ማህሉ ጽጌ ።

በአኩስም ያየሁት የሕዝባችን ጉዳት ።

አኩስም ከጌታችን ከክርስቶስ ልደት በፊት እጅግ ብልህና የሥልጣኔ ስፍራ የነበረ አሁን በኤሮፓ የሚሠራው ዓይነት ሁሉ እንደሚደረግ በብዙ ዓይነት ሥራ ይመሰክርልናል ። መጀመሪያ እስከ ዛሬ ድረስ ካንድ ትልቅ ባህርዛፍ የሚበልጥ ቁመቱ እስከ ሠላሳ ሁለት ሜትር የሚሆን ሃውልት ቆሞ ይታያል እንዲሁም አንድ የወደቀ ትልቅ ሃውልት ቁመቱ እስከ ስልሳ ሜትር ጐኑ እስከ ሶስት ሜትር ተኩል የሚሆን ይገኛል ። አልፎ አልፎም እንደዚሁ አነስ አነስ ያሉ ቆመውም ወድቀውም ይገኛሉ እኘህም ሃውልቶች ያማሩ ያማሩ ቅርጾች ናቸው እንጂ እንደዚሁ በሌላ አገር እንደምናያቸው ተረኛ ድንጋይ አይደሉም ።

የሆነ ሁኖ ያገራችን ሊቃውንቶች ግማሾቹ እስከ መቶ ሃያ ሃውልት ነበረ ይላሉ ። ግማሾቹ እስከ ስልሳ ነበረ ይላሉ ሞሪዬ የሚባል የፈረንሳዊ ሊቅ ግን ፳፬ሃውልቶች ነበረበት ብሎ ጽፎአል ። ለዚሁ ሁሉ እርግጠኛ ምስክር በትክክል አላገኘንበትም ይህም ሃውልት ያለመኪና እንደማይቆም አይታሰብም አይጠረጠርም መኪናም ስላልን በገዛ ራሱ ጐትቶ የሚያነሣ አይምሰላችሁ በኤሌትሪክ ኃይል የሚደረግ ነው እንጂ ማናቸውም መኪና ይህንን ትልልቅ ሃውልት ሊያንቀሳቅሰው ምንም አይችልም ። ሁለተኛ እንደ ገንዘብ ያለ የሰው መልክ ስዕል ያለበት በሃገራችን በግዕዝና በዕብራይስጥ የተጻፈበት እስከ ዛሬ ድረስ አንድ አንድ ጊዜ ከመሬት ይገኛል ጊዜው ስለበዛ ግን በትክክል የተጻፈበት ሊለይ አይቻልም ። ዝናም በዘነበ አንድ አንድ ጊዜ መሬቱን ጐርፍ ከገለባበጠው በኋላ ወርቅም ጥንትም የቀሠራ የጌጥ ዓይነት ሁሉ ይገኛል ።

ሶስተኛም ባንዲት ሃውልት ድንጋይ ከሥር እስከ ጫፍዋ በሬቷም በጀርባዋም የተጻፈባት ትገኛለች ። ይህችም ድንጋይ ጊዜዋ ስለበዛ በፀሐይና በዝናም ስለተጐዳች ጽሕፈቷ እንደመደምሰስ ብሏል ። አገር ለማየት የመጡ የደፍመን ሰው ፕሮ

ፌሰር ሊትማን የሚባሉ ይህች ጽሕፈት ለንባብ ችግር ብትሆንባቸው የማሕተም ኮፒ ወረቀት ከውሀ አርሰው እላዩአ ላይ ለጥፈው ጽሕፈቱ ተነሥቶ በትክክል ተነበበ ። ከድንጋዩ ላይ ያለው ጽሕፈት የሚናገረው አንድ ከክርስቶስ ልደት በፊት የነገሡ ንጉሥ ተዋግቶ ድል ያደረጋቸውና ያስገበራቸው ሁሉ እንዳይረሳ ኢትዮጵያም እንዴት ያሉ ኃይለኞች ልጆች እንዳሏት ለዘላለም ምስክር እንዲሆን ብሎ በዚህ ሃውልት ይህ ብልህ ንጉሥ የበዛ ምስክር አድርጎ ተክሏል ። አራተኛም ያጼ ካሌብ ቤት የሚባል እንደ ኤውሮፓ ሥራ የሚያምር በሥራው ጥንክርናና አኳኋን ከኤሮፓ ሥራ የሚበልጥ የደረጃው ሥራ እጅግ እጅግ የሚያስደንቅ በአፈር ተደፍኖ ሰው ሳያውቀው የሚኖር ፕሮፌሰር ሊትማን ብዙ ገንዘብ ለሠራተኛ እየሰጡ አስቆፍረው ከሁለት ቦታ ላይ ሁለት ቤት አገኙ ። ይህም ቤት እያንዳንዱ ብዙ ክፍል የያዘ ነው ከንደኛው ቤት ክፍል ውስጥ የሣጥን ድንጋይ ቅርጻቸው በጣም ያማረና ቁመታቸው እስከ ሁለት ሜትር ተኩል የሚሆን ሶስት የድንጋይ ሣጥን አለበት ።

እንደዚሁም የተቀበረውንና የተሸሸገውን ሁሉ ለማውጣት ብዙ ገንዘብ ያስፈልጋል እያሉ ብዙሆች እንግዶች ተናግረዋል ይባላል ። እኚህ የጀርመን ሰው ፕሮፌሰር ሊትማን የዚህን ሁሉ አኳኋን ልክ ያወቁት የኢትዮጵያ የታሪክ መጽሐፍ በጀርመን አገር አለ ይባላል ። የጥንት ዘመን የግዕዝ መጽሐፍ በነሱ ዘንድ የሚገኘው ገብረ መስቀል ሲል ገብረ መሰቀለ ይላል ብለው ብዙሆች ሰዎች ሲያወሩ እንሰማለን ። ብዙሆች ጀርመኖች ይህንኑ ግዕዝ የተማሩ ይገኛሉ ይባላል ። ይህንን ከዚህ በላይ የጻፍነው ባጭር ቃል ማመልከታችን ኢትዮጵያ ጥንት እንዴት ያለች በሥልጣኔ የተንተራሰች በመሆንዋ በነዚህ በሚያስደንቁ ሥራ ሁሉ ይመሰክርላታል ። የተገኘውንና ያየነውን ሁሉ ለመጻፍ እጅግ ብዙ ቀን ያስፈልገናል ።

እንደዚህ ለሁሉ ቀደምት የነበረችና ምስክር የሆነች አገር ከዚያ የሚኖሩ እስከ ፲፬ሺ ህዝብ የሚሆኑ በውኃ ችግር እጅግ የተጐዱና የሚያሳዝኑ ናቸው ።አንድ ትልቅ ኩሬ አስገንብተው ከጉርፍና ከዝናም እያጠራቀሙ እድፍ የበዛበት ውኃ ይጠጣሉ ይህም እድፍ የበዛበት ውኃ ግንቡ ስላነሰና በጥሩም ስላልተሠራ በመኃከለኛው በጋ ይደርቅና ይህን ያህል ሰው በወሀ ጥም ይቸገራል ። በየቤታቸውም የጉድጓድ ውሀ እንዳይጠጡ ከመሬት የሚገኘው ምንጭ የጨው ውሀ ነውና በዚህ ብዙ ስቃይ ያገኛሉ ። ያለፈውስ አለፈ ለወደፊት መንግሥታችን በተገባ የዚህን የኩሬ ግንብ በማለፊያ ገንቢዎች ለዘላለም እንዳይበላሽ አድርጎ ህዝቡን ሊረዳውና ሊመግበው ያስፈልገዋል ። ደግሞ አንድ የሚያስገርም ነገር ይገኛል ህዝቡ ይመስለኛል ውኃ ቢወደድበት አረቂ ልክ እንደወሀ ይጠጣል ይህ ሰራርቶ መድኃኒቱን አስታጋሽ ውኃ ሳያገኝ በግልጽ ሲንሸረሸር ዛሬ በሚያስፈልግ ሁሉ እንደሚበጅ ካላደረጉበትና ካላሰቡበት ለኋላ ለኋላ በጣም የሚያስፈራ ነው ።

ጥሩነህ ከ ።

የሥጋ ምርመራ ለኢትዮጵያ የግድ እንደሚያስፈልግ ።

እንደሌላው አገር ሁሉ እዚህም በኢትዮጵያ የታረደ ሥጋና የቁም ከብትም ቢሆን ምርመራው እጅግ የሚጠቅም ነገር ነው ስለምን በብዙህ ጠላቶች ተከበናልና ይኸውም ታልተከላከልናቸው በማናቸውም ጉዳታችን ላይ ኃይላቸው እየበረታብንና እየበረከተ ይሄዳል ።

ለሕዝቡ የሚያስፈልገው ሥጋ በሰውነት መጠን የተመዛዘነ ሆኖ ኃይሉ በጐደለ ጊዜ እንዲተክለትና ጤና እንዲሰጠው ነው ግን ለጤና የማይስማማው ሥጋ ብዙህ ጊዜ ጤና ከማሳጣቱም በስተቀር ለሞት አደጋም ይሰጣል ማለት በሥጋ ላይ ብዙህ ልዩ ልዩ አኳኋን ስለሚገኝበት ውሎ በማደሩና ጠረን በመለወጡ ምክንያት ለሰውነት የሚጐዳ ይሆናል አንድ አንድ ጊዜም ከሙቀት የተነሣ ትል ስለሚሠራ ሌሎችም የሚተላለፉ በሽታዎች እንደ ተስቦ (ቲፎዩድ) ያሉ ይገኙበታል።በኤሮፕ እንኳን የዚህን የምርመራ ሥራ የከብት ሐኪሞች በትክክል ስለሚሠሩና ይኸ በሽታ እንደ ኢትዮጵያ አገር ምንም ያልበዛ ስለሆነ እንደ ተስቦ እያደረገ ሕዝቡን ብዙህ ጊዜ እንዳይጐዳ ታይቷል ።

በዚህም በስድስት ወራቶች ውስጥ የሠራሁት የሥጋ ምርመራ ለሕዝብ ከተሰናዱ ሥጋዎች ውስጥ እጅግ ተላላፊ በሽታ ያለባቸውና ለጤና የማይስማሙ ሥጋዎች እንዳሉ ተረድቼዋለሁ ።

(የከብት በሽታ (ደስታ) አንጉርባ) ፋሮ ደግሞ ሌላዎች ተላላፊ የሳንባ በሽታዎች እንደ አባ ሠንጋ ያሉ ናቸው ። እነዚህም በሽታዎች ሳይመረመሩ ከታረዱ ከብቶች ላይ ወደ ሰው የሚጋቡ ናቸው ።

ከዚህ በላይ ያለውን ባጭሩ ካመለከትኩ በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጤና እንደምን ትሆን እያልኩ እጠይቅአለሁ ። የሚበዙት ሰዎች ምግባቸው ዘወትር ሥጋ ያውም ጥሬ ሥጋ በመሆኑ ያዲስ አበባን ከተማ ሕዝብ ብቻ ጤና በዝርዝር የሚያስረዳ እስታቲስቲክ በነበረን ከዚህ በላይ ለተጻፈው ጥያቄ መልስ ለመስጠት ያለ ችግር በተቻለን ነበር ። በሉካንዳዎች የሚሸጡት ሥጋዎች ለጤና የማይስማሙት የጉዳታቸውንና ያጥፊነታቸውን ልክ በግልጽ ልንረዳው እንችል ነበር ።

ከዚህ በላይ ለተጻፈው የእርሻ ሚኒስቴር ፈጥና የከብት ሃኪም ለሥጋ ምርመራ በማቆም ያዲስ አበባ ከተማ ወሰን የሌለው ምስጋና ልታቀርብላት ይገባል ። የእርሻ ሚኒስቴር የዚህን ሥራ በማቆሟ ወደ ፊትም በመንግሥትም በኩል ጥቅሙ የታወቀ ሆኖ የዚህ ሥራ በፍጥነት እንዲደላደል ተስፋ አለን ። የኢትዮጵያም አገር በከብት በኩል ብዙህ ጥቅም ስለ ምታገኝ ይኸ ሥራ የግድ የሚያስፈልጋት ነውና ።

የከብት ሐኪም ሚህራን ከይማኪያን ።

ሎተሪ ።

በሙሴ ዜ. ሐሻዱሪያን ።

የተሰናዳ ትልቅ የዕድል ዕጣ ።

እጅግ የከበረና ጥቅም ያለበት ሁለት መቶ ሀያ ዕጣ ሎተሪ በውስጡ የሚገኘው ሁለት አቶመቢል ጥሩ ጥሩ ፈረስ

ችና በቅሎች ጠመንጃ ረሺ ሺጉጥ ሴንጀር መኪና ሰዓት የኪስም የጠረጴዛም እጅግ ጥሩ ጥሩ የሆነ ሥጋጃና ጃ.ህ ነባ በያይነቱ ሱፍ የኮት ጨርቅ እጀጠባብ የወርቅ መስቀልን የመሳሰለ ጌጥ እንደዚሁም በያይነቱ ጥሩ ጥሩ ዕቃ በድምሩ ዘጠኝ ሺህ ብር ዋጋ ያለው ዕቃ ነው ያንዱ ዕጣ ዋጋ አራት ብር ነው ሁል ጊዜ እንዲህ በጥራትና በትክክል ሆኖ የማይገኝ እድልን መፈተኛ ነገር ስለሆነ የማታለያ መስሏችሁ ችላ ስትሉ ያመልጣችሁና እንዳይቆጫችሁ እናመለክታችኋለን ይህን ሎተሪ የሚያደርጉ ሰዎች አሳባቸው የዕቃቸውን ዋጋ ለማግኘት ነው እንጂ ሌላ ትርፍ አይፈልጉም ስለዚሁም የሚሸጠው ወረቀት ብዛት በዚያው በቃው ዋጋና ለዚህ ሥራ በሚአስፈልገው ከሣራ ልክ ተወስኑዋል ፡፡

የዚህን ዕቃ ጥሩነት ለማስረዳት ማናቸውንም ማመልከቻ መጻፌ ትርፍ ነገር ስለሆነ ዓይን የሚአየው ነገር ይሻላል በማለት የዕቃውን ጥራት ለመረዳት የሚፈልግ ሰው ሁሉ ዓይኑ እንዲያይ እንዲረዳ በሎተሪ የሚወጣውን ዕቃ ሁሉ በሙሴ ዜሐሻዱሪያን ቤት አስቀምጠነዋል ቤቱም ከዱሮው ማዘጋጃቤት ግርጌ ነው ከዚህ በፊት በየወጣው ወረቀት ላይ ዕጣው የሚታይበትን ቀን አለ ማመልከታችን ምን አልባት በቶሎ ሳይሸጥ ይቀርና ቃል አባይ ያደርገናል በማለት ነበር አሁን ብናየው የዕቃ ብዛትና ማማር ሰውን ደስ በላሰኘው ወረቀቱ በፍጥነት ብዙ ተሸጠልን ትንሽም ቢቀር የቃው ጥሩነት ገ፡ሮ አያሳጣንም በማለት ዕጣው የሚወጣበትን ቀን ባስራሁለት ግንቦት በሙሴ ቴራስ ሀቴል መሆኑን እናመለክታለን ዕድላችሁን ለማየት የምትፈልጉ ሰዎች ሁሉ ወረቀቱ ተሸጦ ሳያልቅባችሁ ቶሎ ቶሎ ተሻሙ ፡፡

ማስታወቂያ ፡፡

እኔ ሐንስ ኤሪክሰን ወደ ገሬ የምገባ ስለሆነ ጋሪ የሚስብ ፈረስና አንድ ጥሩ ጋሪ ምሉ ዕቃ ያለው በርካሽ ዋጋ እሸጣለሁና የሚገዛ ሰው በእንጦጦ መንገድ ዳር ከደጃዝማች ደስታ ያምጠው ቤት አጠገብ ካለው የሚስዮን አስተማሪ ቤት እየመጣ ይጠይቅ ፡፡

ያገር ውስጥ ወሬ ፡፡

በየካቲት ፳ ቀን ፲፱፻፳ ዓመተ ም ማክሰኞ ከጧቱ በ፱ ሰዓት ከቤታችን አንድ ምዕራፍ በሚሆን ቦታ ላይ ማታ ከከዋክብት ተሸርፎ እንደሚወረወረው ኮከብ ሆኖ ቀን በቀን ሲወርድ አየነው ነገር ግን ማታ ከሚወርደው ከፍ ያለ የፋኖስ ብርጭቆ የሚያህል ነው ከወደ በላዩም እንደዚያው ረዘም ያለ ወይም በነሲብ ፫ ክንድ የሚሆን ተከታይ የተየያዘ ጅራት ነበረው ፡፡ መጀመሪያ እንዳየነው በቀጥታ ቁልቁል ነበር አመጣጡ ከምድር በነሲብ ሠላሳ ሜትር የሚሆን ሲቀርብ በዚያው አኳያ አግድም ተወርውሮ መጀመሪያ ካየንበት ቦታ ሁለት ምዕራፍ ያህል ሲርቅ ተሠወረን ከአየር ቁልቁል በወረዱ ጊዜ በአንዳች ነገር ተጅመልምሎ የሚወርድ እሳት መስሎን ነበር በኋላ አግድም ሲወረወር ብንመለከተው ከብሩህነቱ በቀር ቀስተ ደመና መሰለ ፡፡ አኳሆኑም ከፍ ያለ ነው እንጂ የጅራቱ አያያዝ ገምቢዎች ግምብ የሚለኩበትን ብረትና ገመድ አይቶ መረዳት ነው ፡፡ እኛም ፩ ሆነን ነበር ያየነው እኛ ብቻ ነን ብለን ስንደነቅ ብዙ ሰዎች አይተው ኖሮ ሰማን ደግሞ ከኛ የ፱ የ፫ ቀን መንገድ በራቀው በግዳሚና በአንፌሎም ሰዎች እንዲሁ እንዳዩ ተወራ ዛሬ በድፍን ወለጋ ይህ ነገር ተደንቋል ፡፡ ይልቁንም እኛ ካየንበት የ፱ ሰዓት መንገድ በሚሆን ቦታ አንድ ልጅ ባረፈበት ለማየት ቀርቦ ኖሮ የነጸብራቁ ኃይል ጐድቶት ሳያይ ሳይሰማ ሰውነቱን ስቶ በአራተኛውም ቀን ትንሽ ተሽሎታል የሚሉ ወሬ ሰምተናል ግን ወሬው ባይመጣልን ነው እንጂ በያገሩ ሁሉ እንደዚሁ እንደታየ ይመስለናል ፡፡ ስለዚህ የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች እንዲሰሙት ብለን ይህችን አጭር ማስታወሻ ልከናል ግን በወለን አንድ አስትሮኖመር ቢኖር ነገሩ ምን እንደሆነ ገልጦ ያስታውቀን ነበር ፡፡ የካቲት ፳፩ ቀን ፲፱፻፳ ዓ ም ሰዎ ፡፡

የብርሃንና ሰላም ተላላኪ ፡፡

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፩ ብር
የሲዳሞ ቡና	፩	፲ ብር ተኩል
ዝባድ	፩ ወቄት	፫ ብር ተሩብ
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፩ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፬ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ከረጂ	፱ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ከረጂ	፲፰ ብር ተኩል
አቡጀዲ መነጽር	፩ ከረጂ	፻፴፱ ብር
፡፡ ባለሰይጣን	፡፡	፻፴፱ ብር
፡፡ ባለ ድመት ፡፡		፻፴፮ ብር
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻፳፮ ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፻፴፭ ብር
ባለ አንበሳ	፡፡	፻፵፭ ብር
ሱካር	፩ ጁኒያ	፳፮ ብር ተኩል
ቻይ	፩ ነጥር	፩ ብር

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ
አንድ ብር	ሊሬ ፰ ከ፺፭ ሳንቲም
በአንድ ጊኒ	፲ ብር ከ ፳፪
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፬ ብር

ማስታወቂያ ።

ሺብሮሌ አቶሞቢል በኢትዮጵያ ወኪል ።
ሔ ሜ ዜርቦስ ኩምፓንያ ።



Automobiles CHEVROLET
H. M. ZERVOS & C^ie
REPRESENTANTS
BAS PRIX HAUTE QUALITE

የሚከራይ ።

A LOUER

ኦቤርላንድ



ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሽ አቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጦጦን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባ ኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወድያም ባለማግኔቶና ባለባተሪ ነው ክምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማነደሻ መሣሺም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል «ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው

ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

COGNAC S&E&A.METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ

መጽሐፍና ደብተር የሚያስጠርዝ ሰው በርካሽ ዋጋ በልዩ ልዩ አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ይጠረዝለታል ።

ያረጀ መጽሐፍና መዝገብ ማሳደስ ለፈለገ ሰው በርካሽ ዋጋ እንደ አዲስ አድርገን እንጠርዝ ለታለን ።

ሩግቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶመቢል በተለይ ወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፣ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ ።

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህ በካፕሱሉ ያለ ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በካፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ጉድይርግዙ





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው ። በሌላጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ፤ ከሁሉም ርካሽ ነው ፥ ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አራተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፲፰
4 me ANNÉE № 18

ሐሙስ ሚያዝያ ፳፭ ቀን፤ ፲፱፻፳ ዓ ም ።
JEUDI 3 MAI 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d'Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ደከፈላል ።
በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ኢትዮጵያ ወደ ፊት ምን ብታደርግ ይሻላታል ።

በኢትዮጵያ ፩፩ ጊዜ ጥቂት ችግሮች ይታያሉ እነዚህም ችግሮች ከኢትዮጵያ ምድር ወይም ከጊዜ መለወጥ ወይም ከሌላ ሕዝብ አይመጡብንም እነዚህን ጥቂቶች ችግሮች እኛው በገዛ እጃችን (ኤጁኬሽን) የሥልጣኔ ትምህርት ከማጣት የተነሣ እናመጣቸዋለን ።

መጀመሪያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀድሞ እንኳ በአፍሪካ ውስጥ ሆነን የሥልጣኔን ባህል መስማት ስለራቀን (ኤጁኬሽን) የሥልጣኔ ትምሕርት ያለማግኘታችን አያስነቅፈንም ብለን ብናወራ በዛሬ ጊዜ የዛሬውን የዓለም ኮፒ ያለማንሳታችን አያስመሰግነንም አሁንም ወደ ፊት በቀድሞው አኳሆናችን እንኑር ማለት ትልቅ ስህተት መሆኑን ብንረዳው ይሻለናል መቼም ዕለት በዕለት አኳሆናችንን እንለውጥ ማለት ክፉ ጉዳት እንዲያመጣ በብዙ የዓለም ታሪክ የታወቀ ነገር ነው ። ስለዚህ የዓለምን ታሪክ አስገልብጠን እየመረመርን የጠፋውን ሕዝብ እርምጃ ትተን የለማውን ሕዝብ ኮፒ ማንሳት ይሻለናል ፤ እንደሌሎቹ እንኳን ሐዲስ ሥራ ባናወጣ እንዴት ኮፒ መገልበጥ ይሳነን ይኸ ይገርማል ዛሬ ኢትዮጵያ ለማድረግ የሚገባት መጀመሯ ጉዳዩዋ ይኸ ነው ።

፪ኛም ከዚህ በፊት ፪ ፫ ጊዜ መላልሼ እንደ ጻፍሁት በቶሎ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ማድረጉ የሚገባን ለሥራችን ኦርጋንዜሽን ማቆምና በፕሮ ግራም መሥራት ነው ይኸውም ኦርጋንዜሽን የተባለው የቀድሞውን ደንብና አኳሆን በድንገትና በፍጥነት መለወጥ አይደለም ፤ በድንገትና በፍጥነት መለወጥስ ትልቅ ስህተትና ጉዳት ያመጣል ኦርጋንዜሽን ማቆም ይሻላል ያልሁት ሥራ በፍጥነት እንዲሠራ በቀድሞው አናኖራችን ኦርጋንዜሽን ካላበጀንና በፕሮግራም ካልሠራን ወደ ፊት መራመድ አንችልም፤

፫ኛም የኢትጵያ ልጆች ለማድረግ የሚገባን ዋና ነገር ከሁሉም ነጻነታችንን ማክበር ነው ነጻነትንም ማክበር በአፍ ብቻ አይደለም ነጻነት የሚከበረው የማይገባ ገንዘብ ማግኘት በመናቅና ለራስ ጥቅም ብቻ ባለማሰብ ነው ደግሞም ያገራችንን ነገር አይተክክልም እኔ ፩ ሰው ብቻየን መልካም ሥራ ሠርቼም እጠቅማለሁ አትበል ይኸ ትልቅ ስህተት ጥፋት ነው አንተ ብቻ የሚቻልህን ያህል ያገርህን ነጻነት አክብር እንጂ ለአገርህ ነጻነት በጣም አስብ ለአገር አንድ ሰው አይጠቅምም ብለህ ተስፋህን አታድክም በእርግጥ ፩ ሰው ለአገሩ ሊጠቅም ይችላል ፤ ይኸም በብዙ በቀድሞም በዛሬም የታሪክ መጽሐፍ ይገኛል ደግሞም ቁጥር የሚጀመር በ፩ ነው ከዚያም በኋላ እየበዛ ለሚሊዮን ለሚሊያርድ ይደርሳል ስለዚህ አንተ በበኩልህ በያዝከው ሥራ ለአገርህ ነጻነት በውነት ሥራ እንጂ ሌሎቹ መልካም ላይሰሩ ላይሆን እኔን ምን አደከመኝ ብለህ የጥፋት ነገር ወደሚሰሩ ሰዎች ተጨምረህ አብረህ አትቆጠር ፤ ሲሆን ምንም ፩ ብትሆን ለአገርህ ነጻነት ትጠቅማለህ ሌሎቹ አንተን አይተው ካንተ ይማራሉ ባይሆንም ስምህን በመጥፎ ስም ከመጠራት ታድናታለህ በቀረ ሁላችንም በየቤታችን ሌሎቹ ያላደረጉትን እኔን ምን አደከመኝ የራሴን ጥቅም ብቻ ልሥራ ብንል ይኸ ልክ ፍርድ አይደለም ።እኔስ እራሴ ተውሁት ክልሁ ሌሎቹ ባያደርጉ ነው ብዬ በሌሎቹ መፍረድ አይገባኝም እኔም አጥፊ ነኝና ።

ደግሞም ይኸ የራሴ ጥቅም የሚባለው ነገር ከአገር ነጻነትና አንድነትን ከማግኘት ጋራ የሚያመዛዝኑት ዕቃ አይደለም በጣም እርካሽ ዕቃ ነው ። ያገር ነጻነት ለዘለዓለም ነዋሪ የተከበረ ነው የአንድ ሰው ጥቅምና ገንዘብ ግን በትንሽ ሰበብ በአገር ሽብር በመሬት መናወጥ በባንክ መክሰር ወይም ባለገንዘቡ ሲሠራበት በመክሰር ወይም ባለ ገንዘቡ ሞቶ መልካም

ወራሽ በማጣት ጠፊ ነው።ይኸ በብዙ የታሪክ መጻሕፍትም ይገኛል እኛም በእድሜአችን ብዙ አይተናል ሁላችሁም በልባችሁ ባለ እርስትንም ባለ ብርንም ቁጠሩ በልባችሁም የ፩ ሰው ጥቅም ጠፊ መሆኑን አስረግጡ፤ስለዚህ የራስ ጥቅም እርከሽ ዕቃ ነው የዕለትን ምኞት ለሚከተል ሰው ብቻ ክቡር ሆኖ ይታየዋል እንጂ ጥልቅ ሐሳብና እውቀት ላለው ሰው የለት ጥቅም ከምንም አይቆጠርም።ከዚያ ወዲያ ይኸነን በዓይናችን እያየን የራሳችንን ጥቅም ከአገራችን ነጻነት ማመዛዘን ልባችን እንዴት ችሎ ይደፍርልናል ።

፪ኛም ልናደርገው የሚገባን መረዳዳት ነው ። ይልቁንም ለአገር ነጻነት ለአገር ጥቅም የሚሠራውን ሰው መርዳት በጣም ያስፈልገናል።አሁን በታሪክ መጻሕፍት እንደሚወራው ለራሳቸው ትልቅ ነገር ከሠሩ ሰዎች ይልቅ ፩ባልንጀራቸው ለመሥራት ጀምሮ በችግር ወይም በሞት ምክንያት ሳይጨርስ የቀረውን ሥራውን አስፍተው የጨረሱ ሰዎች ይበዛሉ ስማቸውም ከሥራውም ጀማሪ ይልቅ እንኳ የፈጻሚው ስም ይከበራል።የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ይኸነን እስካሁን አላወቅነውም እኛው እራሳችን ከሠራነው ሥራ በቀር ፩ዱ ባልንጀራችን የሠራውን መርዳትና መጨረስን ቁምነገር መሆኑን አልተረዳነውም ሥጋዊ ሰው ደካማ ፍጥረት ነውና ለአንተም የጀመርከውን ለመጨረስ ረዳት እንዲያስፈልግህ አስብ።ከዚያም በኋላ ይኸ ፍርድ ለሁሉም እንዲገባ አስበህ ፍረድ የምዕራብ ሰዎች የበለጡን በዚህ ነገር ነው ግን እኛ የምሥራቅ ሕዝብ ዋናው በሕርያችን ሁሉም ሰው የራሱን ጥቅም ብቻ ያስባል፡እኔ እራሴ ካገኘሁ ይበቃል ይመስለዋል ግን ይኸ አይበቃም ጭራሽ ጐደሎ ሐሳብ ነው ሰው ከወገኑ ከአገሩ ጋራ ደስ ካላለው ካልተረዳዳ ብቻውን በዓለም ላይ ሊኖር ተስፋ የለውም።ብቻ መሆንም አንተ ተመችቶህ ዘመድና ወገንህ የሆኑት ሲጠቁ ነው የምሥራቅ ሕዝቦች የባልንጀራችንን ጥቅምና ሥራ በመቃወም ትልቅ የምንሆን ይመስለናል ይልቁንም የሌላው ሰው ስምና ክብር ቀርቶ በአገር ላይ የኔ ስም ብቻ ቢጠራ ትልቅነት አገኛለሁ ከማለት የተነሣ ሌላ ሰው የሠራውን ሥራ የአሰበውን ሐሳብ ለመቃወም እንደክማለን ይህችም ትልቅ ስህተት ናት ።

የፊተኛው የደረጃ መሠረት ከፈረሰ በምን ላይ ቁሞ ከፍ ማለት ይቻላል የሰው ስም የሚከበረው መልካም ሥራ አስቦ በመስራት ነው እንጂ የአንዱን ሰው ሥራ በመቃወም አይዶለም ስሜ የሚነሣ በዚህ ነው መስሎት የሰውን ሥራና ሐሳብ የሚቃወም የስሙም የአገሩም መጥፊያ በዚህ ነገር መሆኑን ቢያውቀው እጅግ መልካም ነው ። የምዕራብ ሰዎች (ማለት ኤውሮፖች) ዋናው መሠረት ያለው ዕውቀታቸውና ብርታታቸው ሁሉም ሰዎች ይልቁንም ብልሆች ከራሳቸው ይልቅ ለአገራቸው ያስባሉ አገራቸውን በሚጐዳ ነገር ትንሽ ትልቅም ቢሆን የራሳቸውን ጥቅም አይፈልጉም።ለባልንጀራቸውም ምቀኝነት ቢሆን ለእልክም ቢሆን ገንዘብ ለማግኘትም ቢሆን ለራሳቸውም ክብርና ማዕርግም ቢሆን ነጻነታቸውን አገራቸውን የሚጐዳ ነገር አይሠሩም።በዚህ ነገር ሁሉም እንደ ንብ ይረዳዳሉ ስለዚህ መንግሥታቸው ዘወትር ብርቱ ነው ። አሁንም የኢትዮጵያ ሕዝቦች ዋና ጉድለታችን ይህቺ እንደ ሆነች ማወቅ ያስፈልገናል ደግሞም ይህች ክፉ ጉዳት ያለችው በኛ በኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ አይዶለችም በወደቁት በምሥራቅ ሕዝብና አገሮች ሁሉ ነበረች የጣለቻቸውም ይህችው የራሴ ጥቅም ብቻ የምትባለው መርዝ ነች ። ደግሞም ይህች ነገር ዛሬ ሐዲስ የመጣች ነገር አትመስለኝም ምስር ድረስ በምባስ ድረስ የነበረችውን ሰፊ ምድራችንን በመርከብ በአዱሊስ በር በአሰብ በኩል በመርከብ ተሻግረን የዓረብ አገር የመንን መካ ድረስ ይዘን የነበርነውን ሁሉ ይህቺው ክፉ ጠላታችን ያስቀረችብን ይመስለኛል።ስለዚህ አጥብቀን ከሷ መጠንቀቅ ይገባናል ። ደግሞም ከዚህ አስከትዬ ትንሽ ማመልከቻ እጽፋለሁ ። ብርሃንና ሰላም መታተም ከተጀመረ ወዲህ አንድ አንድ የኢትዮጵያ ልጆች ለአገራቸው ለኢትዮጵያ ምክር የሚሆን መልካም መልካም አርትክል ሲጽፉ ነበረ። ባኋላ ግን መጻፉን ችላ አሉት ምክንያቱም በ፪ነገር ይመስለኛል ።

መጀመሯው እነሱ የጻፉት ሐሳብ በቶሎ ስላልተፈጸመ አዝነው ይሆናል።ነገር ግን ወንድሞቼ በዚህ ነገር ማዘን አይገባንም እንኳን ጥቂቶች ሰዎች በጆርናል አርትክል የጻፍነው ነገር ይቅርና በሠለጠነ አገርም በስንት ዩንበርሲቲ የተማሩ ሊቃውንት የመከሩትን ምክር እንኳን የአገር ሕዝብ በስንት ክርክርናበስንት ድካም ይቀበላቸዋል የሚበዛውም ነገራቸው ለጊዜው ተንቆ መጥፎ ነገር ነው ተብሎ የተጠላው ቆይቶ የሚያስፈልግ ሁኖ ይገኛል።የሚያስፈልግ ሆኖ እየተገኘ ይፈጸማል።ስለዚህ ለአገራችን ጥቅም የምንጽፈውን ነገር በቶሎ ተደርጎ ካላየን ብለን መሰልቸት አይገባንም ግማሹ በቅርብ ቀን ግማሹ ውሎ አድሮ የሚጠቅም ነገር ሆኖ ይገኛልና በትዕግሥት ለአገራችን የሚጠቅመውን ነገር መጻፍ ይገባናል ።

፪ኛም የጻፉትን አርትክል አንድ አንድ ፌዘኞችና ሐሜተኞች ሲነቅፉባቸው ሲያሟቸው ሲንቁአቸው ይሰሙና ተናደው ይተዉታል።በዚህም ቢሆን መተው አይገባንም ብቻ ለ፩ ሰው ጥቅም ወይም ለ፩ ሰው ጉዳት ሳይሆን ለኢትዮጵያ የሚጠቅማትን መጻፍ ይገባናል እንጂ አንድ ሐሜተኛ ሰው ማማት ልማድ ሆኖበት ወይም የሱን ጥቅም ለመጉዳት የጻፍን መስሎት የጻፍነውን ቃል ያለ አገባብ ግራ ተርጉሞ ቢያወራ የሱን ሐሜትና ወሬ ፈርተን ለአገራችን ጥቅም የሚሆን ነገር መጻፍ ብንተው የኛ ስህተት ነው ነገር ግን ከጻፍነው ቃል ይኸ ስህተት ይመስለኛል ብሎ በቃሉ ወይም በጆርናል በትክክል ፩ ሰው ቢጠይቀን ደስታችን ነው አሳስተንም ተናግረን እንደሆነ አወን አጥፍተናል ብለን የሱን እንቀበላለን የኛው እውነት ቢመስለንም እንቃወማለን በቀረ የሐሜት ልማደኛ የፈለገውን ቢናገር ለአገራችን ጥቅም የሚሆነውን ነገር መጻፍ መተው አይገባንም ሐሜተኛውም ሰው ማማት ሥራ ቢመስለው ይሠራል ።

እናንተም ያገር ጥቅም አርትክል መጻፍ ሥራ ቢመስላችሁ ጀምራችኋልና እንዳትተውት እለምናችኋለሁ ።ነገር ግን የምትጽፉት ቃል ብቻ እውነተኛ ያገራችሁ ጥቅም ይሁን እንጂ ሐሜተኛ የአፈቀደውን ቢያወራ ጉዳያችሁ አይደለም ከአንባቢዎች ምስጋና የለት ጥቅም አገኛለሁ በማለት የሚሠራ ሰው

አትሁኑ እንጂ ለአገራችሁ በመርዳት አትጐዱም ። ስለ አገር ጥቅም እንኳን በቃል የተናገሩትን በግልጽ በእጃቸው ሠርተው ያላዩትን ሰዎች ሲንቋቸው ይኖራሉ ። መጀመሪያ ባቡር ሲሠራ በእንግሊዝ አገር ጆርጂ እስጢፋን የሚባል ሰው ነው የሠራው ባቡርም ሊቨርፑል ከሚባል እንግሊዝ አገር ተነሥቶ ማንቼስተር ሲገባ ሕዝቡ እኩሉ ዝናብ ያስቀርብናል ብሎ ያወራል እኩሉም እህል አይበቅልም ይላል እኩሉም በቅሎቻችን ክራይ ለመጫን ዋጋ ያጣሉ ይላል ። ጆርጂ እስጢፋኑንም በሐሜት መከራ አሳዩት ባቡርንም እንደ ክፉ ነገር አዩት በኋላ ግን ባቡር ለዓለም ሁሉ ተዳረሰ ከሁሉም የተወደደና የሚጠቅምም ሆኖ ተገኘ ። ሳሙኤል ክሮምቶንም የፈትል መኪና ባወጣ ጊዜ ብዙ ተነቀፈ ብዙም ተሰደበ እንደዚሁም ብዙ ትልልቅ ሥራ ሠርተው ለጊዜው የተጠሉና የታሙ ብዙ ናቸው ። እንግዲህ እንደዚህ ያለውን ትልልቅ ሥራ ያወጡ ሰዎች ሲወቀሱና ሲታሙ እየሰማን እኛ የጻፍነውን ትንንሽ አርትክል ሰዎች ቢንቁና ቢአሙን ከቁም ነገር መቁጠር አይገባንም እሱን ንቀን ወዲያ ትተነው ለአገራችን የሚጠቅም ነገር ማሰብና መሥራት ይገባናል ።

ፊ ዴሬሳ

የማይታሰብ ጉዳት ።

በሀገራችን ውስጥ የበዛ ላም ባይገኝና እጅግ ቅቤ ባናተርፍ እንደ ኤሮፓና እንደሌላው አገር ቅቤ ችግር ቢሆንብን እንደምን በሆንን ነበር ። አሁንስ በኛም ብንመለከተው እንደ ኤሮፓ ሊሆን ምንም ያህል አይቀረውም ። ማለት የሀገራችን ሴቶች ከቤት የሚገኘውን ሶስት እጁን ወደራሳቸው ላይ እየለኩ በብላሽ ያላንድ ጥቅም ገደል ይሰዱታል ። ስለዚህ ከምን በላው ይልቅ ሶስት እጅ ከነሱ በመዋፋቱ በገባያ የቅቤ ግዢ በጣም ጕድሎም ከብሮም ይታያል ። ይህም የሚበዛው በሴቶች ልምድ ስለሆነ አንድ አንዱም ከወንዶች ውስጥ አልፎ አልፎ የሚልኮሰኮስ አይጠፋም ። የሆነ ሁኖ ይህ ነገር ስለምን ይረባል ለምንስ ይጠቅማል ባንድ ድንጋይ ላይ ቅቤ ቢያስቀምጡ እየቀለጠ ፈሶ ያልቃል እንጂ የሚረባ ነገር የለም ።

አሁንም ለተመለከተው ሰው የዚያን ያህል ነው ። ላታክልትስ ላይ ላዩን ከሥር ሳያደርሱ ውሀ ቢያጠጡት ትንሽ ቆይቶ ከመጠውለግ በስተቀር ብርታት ያገኛልን? አሁንም እንደዚሁ ለሚያደርጉ ላይላዩን ተቀብተው ከውስጥ ግን ቅባት ሳያገኝ ሰውነታቸው ለመንቀሳቀስና ብዙም ብርታት ሊያገኙ አይችሉም ። አንድ አንድ ሰነፍ ሞኝ የሆነ ግን የተቀባኸው ነው እንጂ የበላኸው ምን ይረባል ብሎ በነገሩ የሚደርቅ አይጠፋም ።

ይህ እንደዚህ የሚል አእምሮውን የማያውቅ የመንፈቅ ሕፃን ልጅ ይመስላል ። እውነትስ ዘልቆ ገብቶ የሚጠቅም ቢሆን ከኛ አገር ሴቶች ይልቅ የኤሮፓ ሴቶች በባሱበት ነበር ። እንደዚህ ጥቅም የሌለውና የማያስፈልግ በመሆኑ አይተው ብልሆች እያነጠሩ ከማለፊያ ምግብ ጋራ ወደ ሆዳቸው ይከቱታል ። የኛ አገር ሰዎች ባንድ በኩል ብቻ አይደለም ጉዳታቸው በሁለት ወገን ነው ፡ ይህ የለደፉት ቅቤ በፀሐይ እየቀለጠ ሲፈስና ሲንጠፈጠፍ ልብስ ሲያበላሽ ይውላል ። ከቅቤው ከሳራ ይልቅ ስንት የሳሙና ግዢ ያስፈጋል ።

ባንድ አንድ አገርስ ሆነ ብለው አዲስ ልብስ ተሠርቶ መጀመሪያ ብዙ ቅቤ ይቀልጥና ልብሱ ተነክሮ ይለበሳል ። እስኪያልቅም ድረስ ምንም አይታጠብም የሚጨርሰውም ቅቤ እጅግ ብዙ ነውና ከእድፉም ብዛት ሰውየውም በብዙ ጤና ሊኖር አይችልም ፡ ይህ የሚጣፍጥም ቅቤ በእንደዚህ ያለ ሥፍራ ሲገባ ግማቱ እጅግ ያጸይፋል ። ይህን ቅቤ ማበላሸታቸውን እውነትስ እነሱ በኛ ነው የተወደደ ብለው እራሳቸውን ሊታዘቡትና ሊመለከቱት ሊተውት አይችሉም ። የበሰውን ያጠፉሉ እንጂ የሚጠቅማቸውና የሚረባቸው ቢሆንስ ስንኳን ሶስት እጁን አራት እጁን ቢያደርጉት አይጐዳም ነበር ። ከጉዳቱ ይልቅ የማይረባ የሚያስቀይም የሚያጸይፍ ሆኖ ታይቶባቸዋልና የኢትዮጵያ ሴቶች የሆናችሁ ሁሉ ይህንን አጉል ነገር ልትተውትና እንደ ኤሮፓ ሴቶች ልምድ መከተል ያስፈልጋችኋል ስል በጣም አሳስባችኋለሁ ።

ጥሩነህ ካ ።

ማስታወሻ ።

ባዲስ አበባ ከተማችን አሁን ሰንጋም ሙክትም እየተወደደ እንደ ሄደ ሁሉም ተረድቶታል ። ጥንት ባሥር የሚገዛው ሰንጋ አሁን እስከ አርባ ይገዛል ። ጥንት በሁለት ብር የሚገዛው ሙክት አሁን ባሥራ ሁለት ድረስ ሆኖአል ። በአንድ መሐለቅ የሚገዛው ዶሮ አሁን እስከ አምስት መሐለቅ ድረስ ይሸጣል ። በቤሳ ስድስትና ሰባት የሚሸጠው እንቁላል አሁን ሁለቱ በቤሳ ይሸጣል ። ይኸውም አሁን በከተማ ኑዋሪው እየበዛና ሕዝቡም እየሠለጠነ ስለ ሄደ ሁሉም ነገር ይወደድ ጀመረ ይበልጡንም ምድር ሳይታረስ ከብት አርቢም እያነሰ በላተኛውም እየበዛ ስለ ሄደ ይመስላል ።

ደግሞም አንዳንድ ሰዎች ዘወትር ወዳቃቂ እንጦጦ ሱሉልታ የካ መናገሻ ድረስ ለሽርሽር እያሉ የሚሄዱ እናያለን ። እነኝህንም ሰዎች የት ነው የሚሄዱት እያልን አሽከሮቻቸውን በጠየቅናቸው ጊዜ ሽርሽር ነው የሚሄዱት ይሉናል ። ደግሞ ሥራ ያለባቸው ሰዎችም እሁድ እሁድ ቀኑ የርፌት ቀናቸው ስለሆነ ሲሄዱ እናያለን ። ከቤታቸውም ሲሄዱ ያለ ባዶ ቦርሳና ጠመንጃቸው በተቀር ምንም ይዘው አይሄዱም ።

ወደ ማታም ከሽርሽራቸው ሲመለሱ ጥንቸሎች ዝዪዎች እርግቦች አሞራዎች እነኝህን የመሳሰሉ አውሬዎች ሁሉ እየገደሉ ቦርሳቸውን ሞልተው ከቦርሳቸው የተረፈውን አሽከሮቻቸውን አሸክመው የሚገቡ ሞልተዋል ።

ዶሮ እንኳን ባቅሟ አምስት መሐለቅ ስታወጣ እንዴት በእነዚህ አንድ አንድ ቤሣ እንኳን ታክስ ለመንግሥት ሳያወጡ ይቀራሉ ። እነኝህስ የሚገደሉ አውሬዎች ያገር ሀብቶችና ፍሬዎች የመንግሥት ገንዘቦች አይደሉም ወይ ።

የውጭ አገርን ወሬ እንደምንሰማ ያለ ፈቃድና ታክስ ሳይከፍል እንኳንስ እነኝህን ትልልቆች እንስሳዎች ወፍ እንኳን የሚገድል የለም ይባላል ።

እዚሁም በየ ጊዜው ከከተማ ውስጥ ለሽርሽር እያሉ እየወጡ ወፎቻችንንና አውሬዎቻችንን ለሚገሉ መኳንንቶች የሚከፈል የታክስ ግብር ደንብ ማዘጋጃ ቤት እንዲያደርግበት ስል አሳስባለሁ ።

በቀለ ዘለቀ

የሰውና የፍቅር አኑዋኑዋር ።

ፍቅር ከሰው ጋር እንዳይኖር ለፍቅር ሁለት አሰናካዮች አሉት ። እነሱውም በሰው ላይ ሲደርሱ የኖሩ ናቸው ። ስማቸውም ስብቅና ሐሜት የሚባሉ እነዚሁም ሁለት የፍቅር አሰናካዮች ከአንድ አንድ ከግልፍተኛ ትዕግሥት ከሌለው ሰው ቤት ይገቡና በምክራቸው ብዛት ከወለደችና ከከበደች ሚስቱ ከሚወደውና ከሚአፈቅረው ዘመድ ወዳጁ በፍጥነት ሊአለያዩት ይችላሉ ። ይህም የነዚህን ምክር የሰማና ትዕግሥት የሌለው ሰው አንድ ጊዜ በልቡ ሐኬት ይገባበትና ዘለዓለም ንብረት ሳይዝና ሥራውን በትክክል ሳይሠራ ይኖራል ። እነዚሁም ሁለት የፍቅር አሰናካዮች የተባሉ ባንድ ስፍራ አይቀመጡም እንደዚሁ ሁሉ የፍጥረት ዓለሙን ቤት እየዞሩ ይጐበኛሉ ። ሲሄዱም አንድ ሥራ ፈት ሰው አስከትለው ነው እንደዚሁም በዓለሙ ሁሉ ሲዞሩ አንድ አንድ ቀን በጥንቃቄና በትዕግሥት ተወስነው ከተቀመጡ ሰዎች ቤት ይደርሳሉ ከደረሱም በኋላ ደኅና ነገር እንደያዘ ሰው አንገታቸውን ቀልሰው አፋቸውን አለስልሰው በምቀኝነት መንገድ ከሥራቸውና ከንብረታቸው ለማፈናቀል ይሰልሏቸዋል ። ከዚህም በኋላ እነኛ በጥንቃቄና በትዕግሥት ተወስነው የተቀመጡ ሰዎች በክፉ መንገድ ፈትና እንደመጡባቸው ያውቁና ምክራቸውን ሳይቀበሏቸው ይቀራሉ ምክራቸውንም ስላልተቀበሏቸው አፍረው ይመለሳሉ ። ፍቅርም ምቀኞቹና አሰናካዮቹ አፍረው በተመለሱለት ጊዜ በጣም ደስ ይለውና ከነኛ በጥንቃቄና በትዕግሥት ተወስነው ከተቀመጡ ሰዎች ጋር አብሮ ለመኖር ይችላል ። ሲኖርም ጠላቶቹንና አሰናካዮቹን የሚጠብቁለት ዘበኞቹ ጥንቃቄና ትዕግሥት ናቸው ስለ ዚህም በዓለም የሚኖሩ ሰዎች ለኢትዮጵያም መልካም ነገር የሚመኙላትና የሚሰሩላት በልባቸውም ብዙ ደግ ሐሳብ ያላቸው ሰዎች ሁሉ መጀመሯፍቅርን በጥንቃቄና በትዕግሥት መጠበቅ ያስፈልጋቸዋል ይመስለኛል ። ነገር ግን ከዚህ በኋላ ደግ ሐሳባቸውን በቶሎ ሊፈጽሙ አይዘገዩም ። ይልቁንም ብዙዎች የኢትዮጵያ ሰዎች ዛሬ የእውቀትን መንገድ ለመፈለግ ልባቸው በፍጹም ትጋት ስለ ተነሣ መሰናከል እንዳያገኛቸው ከሐሳባቸው በፊት ፍቅርን በጥንቃቄና በትዕግሥት ከጠበቁ ዘንድ ለሚአስፈልጋቸው ሐሳብና ሥራ ሁሉ መሪ ሊሆናቸው አይጠረጠርም ። እንደምን ማለት ማናቸውም ሐሳብና ሥራ ሁሉ ትንሽ መሰናከል ካገኘው በቶሎ ሊፈጸም አይቻልምና ስለ ዚህም በማናቸውም መንገድ ቢሆን ሠራተኞች የሆኑ ሰዎች ሁሉ በሰውነታቸው ሐኬት እንዳይገባባቸውና ሥራቸውንም መሰናከል እንዳያገኝባቸው የክፉዎችን መምጫ መንገዳቸውን መርምረው ያወቁ እንደሆነ ሥራቸውን በትክክል ለመሥራትና ንብረታቸውን ለማቆም ይችላሉ ። ሥራቸውንም ሲሠሩ ባንድ ልብ ሁነው ተጠንቅቀው የሚአስቡ ሠራተኞች ለሀገርና ለመንግሥት የሚጠቅም ሥራ እየሠሩ ደግሞም ለብዙ አዋቆች ምሳሌ ይሆናሉ ። እንደዚህም ባንድ ልብ ሆኖ ሥራውን የሚሠራ ሰው የልቡን ንጽሕና ተመልክቶ እግዚአብሔርም በትክክል ይረዳዋል ስል በዝቅተኛው ዕውቀቴ ያገኘሁትን ሐሳቤን ለክቡራን የብርሃንና ሰላም ወዳጆች እገልጽላችኋለሁ ።

ትንሹ ልጃችሁ በትረ ማርያም ወልደ ትንሣኤ ።

ከኢስት አፍሪካ ጋዜጣ የተገለበጠ ።

በክሊማንጃሮ ላይ የተቀበረ መዝገብ ፡ (የከበረ ዕቃ በያይነቱ) አበሻዊ አፈ ታሪክ

ሚስተር ፒ ጂ ሲንክለር በሞሺ አቅራቢያ ባለው ቦታው ሆኖ ከዚህ በታች ያለውን በጣም ብርቅ የሆነ ቃል ለታይምስ (ጋዜጣ) ይጽፋል

በክሊ ማንጃሮ አቆልቋይ ሆኜ እንደ ተቻለኝ መጠን ደህና አድርጌ የቡና አትክልት አረባለሁ ፈረንጆች እየመጡ ወደ ተራራው በወጡ ቁጥር ብዙ ከባላገሮች እየመጡ እነዚህን ነጮች ምን ይፈልጋሉ ቦታው በረዶ ነው መዝገቡን ለማግኘት ይሻሉን እያሉ በችኮላ ይጠይቁኛል ዋናው ጥያቄያቸውም መዝገቡን ይሻሉን ነው እኔም በዚያ ለማለት የሚያስፈልገውን የደስታ አስተያየት ለመርዳት ነው ያልኳቸውም እንደሆነ እውነት መሆኑን አያምኑኝም የባላገሮች አፍ ታሪክ በጣም የሚያስገርም ነው ግን በንትሽ እውቀቴ ብዙ ጊዜ የጠነከረ ምክንያት አለበት የመዝገቡ ነገር እምነት መዘዋወር በቅርብ የሆነውን ለመናገር የሚያስደንቅ ነው በዚህ አገር ያሉት ባላገሮች ዋጨጋዎች ናቸው መዝገቡ አለ ከማለት የተነሣ እዚያ እንደምን መጣ ብለው ቢጠይቃቸው ምንም አያውቁ አንዳችም ሊመልሱ አይችሉም ከዕለታት አንድ ቀን ሚስተር ሬውሽ የሚባል ሚሲዮናሪና በሱ ማኅበር የሚኖሩ ሰስት አበሾች በኡሳ ወንዝ አጠገብ ከተራራው በስተ ደቡብ ምዕራብ አርባ ምዕራፍ ያህል ራቅ በሚል የሚኖሩ ወደኛ መጡ

እነዚህም አበሾች ቀድሞ የጀርመን ወታደሮች ነበሩ ወደ ዚህም አገር ከመጡ ብዙ ጊዜ ሆኖአቸዋል ያገራቸው ሰዎች ቀዳማዊ ምኒልክ የሸዋ ንጉሥ የሰሎሞንና የንግሥተ ዓዜብ ልጅ ወደዚህ አገር መጥቶ ይኸን አገር በመላው እስከ ሩፊጂ ወንዝ ድረስ እንደ ገዛው ያምናሉ ብለው ነገሩን። ደግሞም ባረጀም ጊዜ ሠራዊቱን ሁሉ ሰብስቦ ወደ ክሊማንጃሮ ግርጌ መጥቶ ከዚያም ሆኖ ጊዜው እንደ ቀረበ አውቆ ከጦር አለቆችና ከመኳንንቱ ጋራ ሆኖ ባሮቹን መዝገቡን (የከበረ ዕቃውን) አሸክሞ ወደ ተራራው ጫፍ ወጣ ። የሰሎሞንም ቀለበት በጣቱ ነበረ (ይኸም በተራራው ተከቷል) ከዚያም ከተራራው ጫፍ ከበረዶው ሲደርስ አዩት ወዲያውም ደመና መጥቶ ሠወረው ። በመሸም ጊዜ የጦር አለቆችና መኳንንቶቹ ንጉሥ አልባ ተመለሱ ። እሱም በፈቃዱ ከተራራው ጫፍ ባለው መሰወሪያ ቀረ ። እነሱም ወደ አበሻ ተመለሱ ። ስለዚህ የኋላ ኋላ የዚህን ንጉሥ መንፈስ ተከትሎ ይኸን እስከ ዛሬ ኢትዮጵያ የሚሉትን አገር እንደገና የሚገዛ ንጉሥ ይነሣል ሲሉም እምነት አላቸው አሉን።

ዛሬም አንድ ያበሻ ሰው የሚስተር ዚዴለር አሽከር ሚስተር ዚድላክን ተከትሎ መጥቶ በአፍሪካ ውስጥ ሲጓዝ አገኘሁት። ይኸውም ባለፈው ጥቅምት በ፳፪ኛው ቀን በድንገት ወደ ተራራው ወጣ የሱዋህሊ ቋንቋ ያውቃል ። እሱም ይህ ታሪክ በአበሻ ምድር በጣም የታወቀ እንደሆነ ነገረን ። ነገር ግን

ንጉሡ መዝገቡን በዋሽ ከቶት ወደ አበሻ እንደተመለስ እንጂ በዚያ እንዳልቀረ አስረዳ ። ይህ ነገር በዚህ አገር እንደ ታሪክ ጉዳይ ሆኖ ይናፈቃልና አንባቢዎችህም አበሻን እንዲያውቋት እምናለሁ በዚህ ነገር ላይ ትኩስ ብርሃን ጣል ቢያደርጉበትና ቢጸጻፉልኝ የጠለቀ ምስጋናዬን አቀርብላቸው ነበር ።

ከብርሃንና ሰላም ተላላኪ።

ሰላም በወላሞ ።

በወላሞ አውራጃ በቀን በቀኑ የሚቃጠለው ቤት የሚሞተው ሰው ቁጥር የሌለው ነበር ይባላል ። ሌባው ቤት እየማሰ አገልጋዩን ልጁን ከብቱን ባለቤቱን እየገደለ በከንቱ ሕዝቡ እያለቀ ይኖር ነበረ ። አሁን ግን ክቡር ደጃዝማች ይገዙ ከተሾሙ ባገሩ ዙሪያ አሽከሮቻቸውን ዘበኛ አቁመው እንኳን ቤት ሊቃጠል ቀድሞ እየእንስቱ ውስጥ ያድር የነበረው ጥንት ዘበኛ የሌለውን በከተማና ባገሩ ውስጥ ዘበኛ አቁመው ሰው እድሚ ለክቡር ደጃዝማች ይገዙ እንስት ውስጥ ከማደር ቤታችን ከመቃጠል ዳንን እያለ ነፍሱ ሳይጠፋ ክቡር ደጃዝማች ይገዙን ከተሾሙ ጀምሮ መዝጊያውን ሳይዘጋ ያለአሳብ በደስታ እያመሰገነ ይኖራል።ለክቡር ደጃዝማች ይገዙ ለኢትዮጵያ ለመንግሥታቸውና ለሕዝብ ስለማሰባቸው እድሜና ጤና ይስጣቸው

ብዙነህ ወልደ ትንሣኤ ፡

የከተማ ወሬ ።

ሚያዝያ ፳ ቀን ክቡር ሊጋባ ወዳጆ ለመኳንንቱና ለወታደር ሙሉ ግብር አድርገው መልካም ግብዣ በመጋበዛቸው ሕዝቡን ሁሉ እጅግ ደስ አሰኙት ።

ሚያዝያ ፳፪ ቀን ክቡር ከንቲባ ነሲቡ አዲስ ያሠሩትን ቤት ለማስመረቅ መኳንንቱንና የከተማውን ትልልቅ ሰዎች ሁሉ ጠርተው ግሩም አድርገው ጋበዙ።እዚያ የዋለ ሰው ሁሉም በቤቱ ማማርና በሥርዓቱ አኳኋን እጅግ እያደነቀና እያመሰገነ መርቆ እየቤቱ ሄደ።ማታም በቤቱ ውሥጥ አዝማሪ ቀርቦ ጨዋታው ደምቆ ነበር ።

ስለ ዝናብ ።

ዘንድሮ በጋው ስለ ጠና ሐሩር በርትቶ በጣም ድርቅ ሆኖ ነበር ። ግን አሁን ከሚያዝያ ፳፪ ቀን ሌሊቱ ጀምሮ ዝናብ መዝነብ ስለ ጀመረ ዓየሩ በርዷል ። አቧራውም ቀርቶ ባንዳንድ ባልተሠሩ መንገዶች ላይ ጥቂት ጥቂት ጭቃ ይገኛል ። ዝናብ በመጀመሩም ሕዝቡ ሁሉ ደስ ብሎታል ።

ሎተሪ ።

በሙሴ ዜ ሐሻዱሪያን ።የተሰናዳ ትልቅ የዕድል ዕጣ ።

እጅግ የከበረና ጥቅም ያለበት ሁለት መቶ ሀያ ዕጣ ሎተሬ በውስጡ የሚገኘው ሁለት አቶሞቢል ጥሩ ጥሩ ፈረሶችና በቅሎች ጠመንጃ ረሺ ሺጉጥ ሴንጀር መኪና ሰዓት የኪስም የጠረጴዛም እጅግ ጥሩ ጥሩ የሆነ ሥጋጃና ጁሀ ካባ በያይነቱ ሱፍ የኮት ጨርቅ እጀጠባብ የወርቅ መስቀልን የመሳሰለ ጌጥ እንደዚሁም በያይነቱ ጥሩ ጥሩ ዕቃ በድምሩ ዘጠኝ ሺህ ብር ዋጋ ያለው ዕቃ ነው ያንዱ ዕጣ ዋጋ አራት ብር ነው ሁል ጊዜ እንዲህ በጥራትና በትክክል ሆኖ የማይገኝ እድልን መፈተኛ ነገር ስለሆነ የማታለያ መስሏችሁ ችላ ስትሉ ያመልጣችሁና እንዳይቆጫችሁ እናመለክታችኋለን ይህን ሎተሪ የሚያደርጉ ሰዎች አሳባቸው የዕቃቸውን ዋጋ ለማግኘት ነው እንጂ ሌላ ትርፍ አይፈልጉም ስለዚሁም የሚሸጠው ወረቀት ብዛት በዚያው በቃው ዋጋና ለዚህ ሥራ በሚአስፈልገው ከማራ ልክ ተወስኑዋል ።

የዚህን ዕቃ ጥሩነት ለማስረዳት ማናቸውንም ማመልከቻ መጻፌ ትርፍ ነገር ስለሆነ ዓይን የሚአየው ነገር ይሻላል በማለት የዕቃውን ጥራት ለመረዳት የሚፈልግ ሰው ሁሉ ዓይኑ እንዲዓይ እዲረዳ በሎተሪ የሚወጣውን ዕቃ ሁሉ በሙሴ ዜ ሐሻዱሪያን ቤት አስቀምጠነዋል ቤቱም ከዱሮው ማዘጋጃቤት ግርጌ ነው ከዚህ በፊት በየወጣው ወረቀት ላይ ዕጣው የሚታይበትን ቀን አለ ማመልከታችን ምንአልባት በቶሎ ሳይሸጥ ይቀርና ቃል አባይ ያደርገናል በማለት ነበር።አሁን ብናየው የዕቃው ብዛትና ማማር ሰውን ደስ ስላሰኘው ወረቀቱ በፍጥነት ብዙ ተሸጠልን ትንሽም ቢቀር የቃው ጥሩነት ገጋ አያሳጣንም በማለት ዕጣው የሚወጣበት ቀን ባስራሁለት ግንቦት በሙሴ ቴራስ ሆቴል መሆኑን እናመለክታለን ዕድላችሁን ለማየት የምምትፈልጉ ሰዎች ሁሉ ወረቀቱ ተሸጦ ሳያልቅባችሁ ቶሎ ቶሎ ተሸሙ ።

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፩ ብር ተሩብ
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፩ ብር ሩብ ም
ዝባድ	፩ ወቄት	፫ ብር ተሩብ
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፩ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፬ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፰ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፯ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጇ	፱ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጇ	፲፱ ብር ተኩል
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጇ	፻፵ ብር
፡፡ ባለሰይጣን	፡፡	፻፵፩ ብር
፡፡ ባለ ድመት ፡፡		፻፴፬ ብር
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻፳፮ ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፻፴፫ ብር
ባለ አንበሳ	፡፡	፻፵፫ ብር
ሱካር	፩ ጁኒያ	፳፱ ብር ተኩል
ቻይ	፩ ነጥር	፩ ብር

ስለ ምንዛሬ

አንዱ ብር	፲፪ ፍራንክ
አንድ ብር	ሊሬ ፰ ከ፲፫ ሳንቲም
ባንድ ጊኒ	፲ ብር ከ ፳፪
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፰ ብር

ስለ አንበጣ አመጣጥ ።

ሚያዝያ ፲፱ ቀን ብዙ አንበጣ አዲስ አበባ ደረሰ።አንዳች ጉዳት ግን አላደረገም ፡፡ ነገር ግን ምናልባት አንበጣው አሮጌ ነውና በቈላ ወርዶ አሸዋ ባለበት ቦታ ዕንቍላሉን የጣለ እንደ ሆነ ኋላ ኩብኩብ እንዳይነሣ ያስፈራልና ስለ ዚህ መንግሥትና የሀገራችን ትልልቆች አስተዋዮች ሊያስቡበት ይገባል ።

COGNAC S.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክላስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ፡፡

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶመቢል በተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፡ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፣ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ማስታወቂያ ።

ሺብሮሌ አቶሞቢል በኢትዮጵያ ወኪል ፡
ሒ ሜ ዜርቦስ ኩምፓንያ ።

Automobiles CHEVROLET
H. M. ZERVOS & Cie
REPRESENTANTS
BAS PRIX HAUTE QUALITE

የሚከራይ ።

A LOUER

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ አቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጦጦን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ፡ ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።



አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባ ኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወድያም ባለማግኜቶና ባለባተሪ ነው ካምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል «ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው

ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ ።

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህ በከፕሱሉ ያለ ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በከፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ጉድይር ግዙ





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው።በሌላጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ፤ ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አራተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፲፱
4 me ANNÉE № 19

ሐሙስ ግንቦት ፪ ቀን ፤ ፲፱፻፳ ዓ ም ።
JEUDI 10 MAI 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት
Son Altesse Impériale Teferi Makonnen , Héritier du trône d' Ethiopie , profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix , a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ደረክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie
Un an 5 Thalers
Etranger
Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የቦልሽቢኮች የከፋ አውሬነት ጠባይ ።

ክቡር ቄስ ቅዝ ብሏቸው ተክዘው በወንበር ላይ ተቀምጠው አገኘኋቸው ። እንዲኽም አሉኝ እነግርዎትአለሁ ያሉኝን የቦልሽቢኮችን የአውሬነት ጠባያቸውን ከፒቴን ሆይ እባክዎን እስቲ ይንገሩኝ እኔ መልሼ አልኳቸው ክቡር ቄስ ሆይ ነገሩ ዛሬ በአንድ ጊዜ ቀጠሮ የሚያልቅ አይደለም ። ግን ልጀምርልዎትና በሌላ ቀን በዬጊዜው እየተቀጣጠርን ሁሉንም እነግረዎታለሁ

መጀመርያ

ጨለማና ጣረ ሞት ይሙት በቃ ተብሎ የተፈረደባቸውን ሰዎች በዝግታ ይከተሏቸዋል። እነዜኽም ይሙት በቃ ተብሎ የተፈረደባቸው ፸፱ ትልልቆች ሰዎች ናቸው ።
እነዜህንም ሰዎች ከአንድ ካልታወቀ ቦታ ሲመሽ በጨለማ ጊዜ አዙርዋቸው ብለው ዘበኞቹን ዋና የበረታ ትእዛዝ አዘዙዋቸው የተፈረደባቸውም ሰዎች በጠበቀ በብርቱ አስተሳሰር ታስረው ነበሩ ከዜህም ውስጥ ፬ አቡኖች በጣም አድገው ያረጁ ነበሩ። እነዜህ እስራት አልጠበቀባቸውም ነበር ከንገታቸው ላይ ተንጠልጥሎ እስተ ደረታቸው የሚወርድ ትልልቅ የአቡኖችን መስቀል አድርገው ነበሩ ይኸንን እንዳታወልቁብን ብለው ለመኑ መስቀላቸውን ሳያወልቁባቸው ተውላቸው አፍለኛ የሆኑትን ጐበዛዝቱን ጋሪናሮችን ፪፪ ሆነው ተራ መትተው እንዲሰለፉና ወደ ፊት ቀዳሚ ሆነው እንደሄዱ አደረጉዋቸው

በእድሜ ጠና ያሉትን ሰዎች ግን በስተኋላ ተራ አስመትተው ኳሰለፍዋቸው እና ያስሄዷቸው ጀመር ። የዚያን ጊዜ የሚያስፈራ ጭርታና ዝምታ ሆነ ብርቱም ጸጥታ ። አንድ የቦልሽቢክ ሹም ወረቀቱን እያነበበ የየ ፩ ፩ዱን ሰውስ እየጠራ አለንጋውን እንሥቶ ከብት እንደሚቆጠረው ሁሉ ይቆጥራቸው ጀመረ። ከእስረኞች መኻል ፩ዱ ልጅነት ያለው አቡን ደፍሮ እንዲህ ብሎ ጠየቀው ቦልሽቢኩን ። አንተ የክርስቶስ ልጅ ሆይ አሁን በጨለማ ወዴት ነው የምትነዳን ምነው ሲነጋ በብርሃን አትወስደንም ከኛ መኻከል የሸመገሉ መሄድም የማይችሉ አቡኖች አሉብን ባለ ጊዜ የቦሽልቢኩ ሹም በብልግና እና በቁጣ ቃል እንዲህ ብሎ መለሰለት ከዚህ ፩ም ነገር መጠየቅ አይቻልም ከማክበርና እንዳሉት ከመሆን በቀር አለ ።

ተራ እንደመቱ ተሰልፈው ሲሄዱ የቦልሽቢኩ ዘበኞች ሁሉ ግራና ቀኝ ከበዋቸው ከየጠመንዣቸው ላይ ሳንጃ ሰክተው ይነዷቸው ጀመር ።

አካኼዳቸውም በዝግታና በከባድነት ነበር ከዚሁ የሞት ፍርድ ከተፈረደባቸው ሰዎች መካከል አንዱ ሰው ለሞት መሄዳቸው ታውቆት ይገነግን ጀመር። ከነሱም መኻከል ፩፩ዱ ሰው ተአምራት እግዚአብሔር ሳይገልጽልን አይቀርም እያሉ ተስፋ የሚያደርጉ ነበሩ ፩፩ዱም ሰዎች ይኸን የደረሰባቸውን ነገር አፅተው በድፍረት ጠንክረው ምን ቀን ደረሰብን እያሉ የደረሰባቸውን ጊዜ እየተሳደቡ ከጉዳይ ሳይቆጥሩት ይሄዱ ጀመሩ ። አቡኖች ግን ሁሉም መቁጠሯቸውን ይዘው ወደ አምላካቸው ይጸልዩ በዝግታ እግዚአብሔርን ይለምኑ ነበር ። ፩፩ዱ ደግሞ ውሀ ጠምቷቸው በድንጋጤ የደረቀ ከንፈራቸውን እየመጠጡ ይሄዳሉ ፩፩ዱ ፍዝዝ ብለው በመቅዘዝ የተነሣ ተቸግረው ይኸ እንዲህ የምንሆነው ሁሉ በውናችን ነው ወይስ በሕልማችን ነው እያሉ እያሰላሰሉ ይሄዱ ነበር ። የነዚህ የተፈረደባቸው ሰዎች አኳኋን ለመታረድ ጉሮሮዋን ተገዝግዛ ገና ነፍሷ ያልወጣ የምትንደፋደፍ ዶሮ ይመስላል። ፍዝዝ ብለው ሲሄዱ ፩፩ ጊዜ ወታደሮቹ በብርቱ ጩኸት ቁጣ ተጠጋጉ ፈጥናችሁ ሂዱ ሲሏቸው ነታ ይላሉ በዚያን ጊዜ ለእርድ እንደሚነዳ ከብት ወደ መታረጃው ቦታ በደረሰ ጊዜ የደሙ ክርፋት እንደሚከረፋው ሁሉእን

ደዚያ ይሆናሉ ። ፩፩ ጊዜም እርስ በራሳቸው ይጠጋጋሉ ፩፩ ጊዜም የፊተኛው ሸልፍ ተራ አልፎ እስኪሄድላቸው ቁመው ትንሽ ይቆያሉ ።

የፊተኞቹ አፍላኞች ገርኒናሮች ግን የሞቱ ጣር እንዳይታወቃቸው ብለው ለግጠና የቀልድ ጨዋታ እያነሡ ይሳሳቃሉ ።

የመስኮብ አገር ከተማ መንገዶች ሁሉ ብርቱ ጨለማና ጸጥታ የመላበት ሆነ ። በአገሩም ያሉ ሰዎች ሁሉ በድንጋጤና በፍርሃት አስቀድመው ተኝተው ነበር ።ተአሁን አሁን እኛንም ይጨምሩን ይሆን በማለት አንድ እንኳን ጥንት ዘወትር ይጮሁ የነበሩት ወፎች እንደጉጉት ያሉ ሁሉ ድምጣቸው ጠፋ ፤ ቀድመው በተራ ከሚሄዱት ጋርኒናሮች እንዲህ ይባባሉ ነበር ሸሽተን እናምልጥ አይሆንም ከዚህ ከከተማው ውስጥ በያለበት ዘበኛ ሞልቶአልና አይቻለንም ። እንግዲያስ ቆዩ ከከተማው ስንወጣ ነው ነጥቀን የምንሸሸው ቢገሉንም ኋላም ቢሆን መቸም ከሞት አላመለጥነም ይባባላሉ ወታደሮችንም ለማታለል ያላግጡ ነበር እየቀለዱ በዘነጉላቸው ጊዜ አምልጠ ለመሄድ ፊታቸውን ግምባራቸውን የተጨነቁ እንዳይመስሉ ሳቅ ሳቅ ፈገግ ፈገግ እያደረጉ ግን ይኸ ብርቱ ጨለማ ፊታቸው እንዲታይ ይከልላቸው ነበር። ምንም ደስ ያላቸው እንመስልም ቢሉ ጨለማው ፊታቸውን ይሰውረው ነበር ። እንደ ማናቸውም ቢሆኑ የሞት ነገር ቀለም መቀቢያ መሳርያውን ይዞ ፊት ፊታቸውን ይወዘው ዛቸዋል።

ለሚመጣው ወደፊት ከዚኽ ቀጥሎ ጽፈን የምንልከው አለ
ከፒቴን ባቢክያን ።

ቲንሽ እርዳታ ።

ባራተኛ ዓመት በ፲፬ ቁጥር በ፪ ፭ ገጽ በብርሃንና ሰላም ክቡር ፊታውራሪ ዴሬሳ ለጻፉት ቲንሽ እርዳታ የምትሆን ከዚህ ቀጥሎ እጽፋለሁ ። በቀድሞ ዘመን ደብዳቤ ሲጻፍ በብራና ። ጸሐፊው በቅርብ አይገኝ ከሩቅ ተፈልጎ መሸፈኛው (ሰም) ማለት ጧፍ ጉዳዩ የሚያስቸኩል ቢሆን በፈረስ የማያስቸኩል ቢሆን በበቅሎ ሄዶ ነበር መላከተኛው የተላከበትን ጉዳይ የሚፈጽመው ብዙ ስንቅና ብዙ ድካምም ነበረበት ።ዛሬ ግን በመማርና በመሥራት ደብዳቤ የሚጻፍበት ወረቀት የሚጽፍ ለየአንድ አንዳችን ያገሩን ጽፈት ይቅርና የውጭ አገር ጽፈት የሚያውቅ ልጅ የተጻፈውን ደብዳቤ መሸፈኛ እንፖለፕ እንዳይገለጥ ማተሚያ ቀይ ሸማ የተጻፈው ጉዳይ የሚያስቸኩል ቢሆን በቴሌግራም የማያስቸኩል ቢሆን ፖስታ በባቡር ተልኮ ጉዳይ መፈጸም ተገኘ ። ክቡር ፊታውራሪ ዴሬሳ እንዳሉት ከመተው መሥራት ይሻላልና ሌላው እንኳ ቢቀር በከተማው ዙሪያ ካሉት የእህል አገሮች ለከተማ የሚያስፈልገውን ሁሉ በያይነቱ እዲያመላልስ የርሻና የንግድ ያገር ግዛት ሚንስቲሮች ከመንግሥት ተማክረው የሥራ ሚንስቴሩ የባቡር መንገድ ለማሠራት ከውጭ አገር የታመነ ኩምፓንያ ተዋውለው እንዲያስመጡ ይኸውም በቶሎ እንዲፈጸም ተስፋ አደርጋለሁ ። ተስፋ ለሰው እስከ ዘለዓለሙ ደህንነት እምትሰጥ ናትና ለመንገዱ ማሰሬያ ባንድ ጋሻ መሬት አንድ አንድ ብር አውጣ ቢሉት ምን ጊዜም አከተማ የማይሸምት ሰው የለምና ከቤተ ክርስቲያን ያገባ ባለመሬት ይቅር ቢያዙት በተከፋው ሰው ሁሉ ደስ እያለው ነው የሚሰጥ ። መድኃኒታችንም ኢየሱስ ክርስቶስ ለነገ ይሆናል ብላችሁ አታሳድሩ የነገውን ነገ ታስቡታላችሁ ብሎ በምዕራፍ ፮ በቁጥር ፴፬ በማቴዎስ ወንጌል መክሮናል ። የቀድሞ አባቶቻችንም ከዚሁ አያይዘው የሥራ ነገ ማለት አይጠቅምም ብለዋል ይባላል ጠንክሮ መሥራትም ከመሥራት አንድ ነውና ስለሆነ በኮንትራቱ ውስጥ ጥቅም የሚገኝበት ቢሆን እላይ እንደተባለው በከተማው ዙሪያ ባሉት አገሮች በየክፍላቸው የሚሰራውን መንገድ ውሉን እሮፓን አይተው ለመጡ ለታመኑ ለኢትዮጵያ ልጆች ማድረግ ነው ። ቢሆንም ምን አልበት ውሉ እንዳይላላና የውጭ አገር ሰዎች እንዳይጠብቁት ዋና ዋናውን ባለውል ባለጸጋ ሰው ማድረግ ያስገድዳል ማለት የገንዘብ ባለጸጋ አይደለም የልብ ባለጸጋ ነው እንጂ የገንዘብስ ባለጸጋ ከሁን በፊትም ብዙ ሰዎች ነበሩ ይበቃናል ብለው ሲተው አላየንም ። የኔውስ እርዳታ ጠጅ የለበት አበጋዝነት እንደሚባለው ተረት ያለ ነውና ክቡር ፊታውራሪ ዴሬሳ ባራተኛ ዓመት በ፲፬ ቁጥር በ፪ ፮ ገጽ ፵፫ኛ መስመር ላይ እንደጻፉት ብዙ ገንዘብና ብዙ ዕውቀት ያላችሁ ሰዎች እርዳታችሁን በፍጥነት ለመንግሥት እንድታቀርቡ ብርሃንና ሰላምን አማላጅ ይዤ እማልዳችኋለሁ ። የብርሃንና ሰላም ወዳጆች ሆይ አላዋቂነቴን አይታችሁ ሳትንቅፉ ቲንሽ የምንጭ ውሀ ከታላቅ ፈሳሽ ውሀ ጋራ ተደባልቃ ባንድነት ሥራ መሥራቷን አስባችሁ ታላቅ የሆነ እውቀታችሁን ለወንድሞቻችሁ ለኢትዮጵያ ልጆች ብርሃንና ሰላም በሚባለው ጉባዔ እንድታስተምሯቸው ባማረ ተስፋ አሳስባችኋለሁ ። ምኑን በኅበ ሰብእ ወትሁት በውስተ ሕዝብ አንድ ኢትዮጵያዊ ወንድማችሁ

መ አ

አይጥ እንኳን መንገዷን ከሳተች የጠላቷ ሲሳይ ትሆናለች ።

ሰው እንግዴህ አእምሮ ሲያውቅ ነገር ሲገባው ሐሳቡን ሁሉ ከምን ይጥለዋል ቢሉ የዚህ ጥያቄ መልሱ ጥቂት ነው ።

ሰው አእምሮ ካወቀ ነገር ከገባው (ማለት የሚጠቅምና የሚጐዳ) ሐሳብን ሁሉ ከሀገሩ ላይ ይጥለዋል።ሀገሩንም በፍጹም ልቡ ይወዳታል የሚጠቅማትንም ነገር ለማድረግ ይጣጣራል የማይጠቅማትንም ሊያጠፋ ።

እንግዴህ እኛ ኢትዮጵያውያን ለሀገራችን የሚጠቅማትን ነገር ሁሉ በቶሎ ለማድረግ እናታችንም ከትክክል ደረጃ ለማድረስ በጣም መጣጣር ይገባናል ። ለዚሁም ያለ ጥርጥር በቶሎ የሚያደርሰን መንገድ እነሆ እንገልጻለን ። ይኸውም መንገድ ለነፃነታችን የሚያከራን በጣም የበለጠ ደረጃ የሚያደርሰንና እንደ ቀሩት ወንድሞቻችን ጉዞ የሚያስጉዘን የምድር ባቡር በያውራጃው መዘርጋት ነው ። በዚሁም ላይ የሚገኙትን ጥቅሞች እንደሚከተሉት ከብዙው በጥቂቱ እገልጻለሁ ።

አሁን በኢትዮጵያ ከዋናው ከተማችን ጀምሮ ከዚህ በታች በምንቆጥራቸው አገሮች ላይ የምድር ባቡር ቢዘረጋ ኢትዮጵያ እንዴት ያሉ ጥቅሞች ትጠቅም ይመስላችኋል እኔ ግን

እንደሚመስለኝ ሀገራችን ከላይ እንዳልሆነው ሁሉ ቢቶሎ ደኅ በሚያሰኝ ጉዞ ተጉዞ እንደቀሩት ባልንጀሮችዋ ለመሆን አያውካትም ። ለምሳሌ አሁን ብናስበውና ብንመለከተው የሕዝብን ማለቅና መደህየት የንግድን ማነስ የሽፍታን መብዛት የመንግሥትን ገቢ ማነስ የሚያመጣ ምን ይመስላችኋል ። እነሆ ሁሉ ለደጅ ጥናት ለንግድ ወይም ይህንን ለመሳሰሉ ነገሮች ሁሉ ከጐንደር ከትግሬ ከጐጃም ከወለጋ ከቦረና ከጐሬ ከቀሩትም እነኚህን ከመሳሰሉ አገሮች ሁሉ የሚመጡና የሚሄዱ ነጋድያንና መኳንንት እንደምን ያሉ ጉዳዮች እንደሚጐዱና ስንትና ስንት ገንዘብ እንደሚከስሩ ታውቁታላችሁ ። እኔም በጥቂቱ አገልጻለሁ ያ በበጋ ሁሉ ፀሐይና ድርቅ በክረምት ያ ሁሉ ዝናብ ውሃ ሙላት ከብዙ መከራና ሞት ያደርሳቸዋል ። ደግሞ ለብዙ ዘመን የሚበቃ ገንዘባቸውን በመንገድ ይፈጁታል ብዙ ሥራ የሚሠሩ ሰዓታቸውን (ጊዜ በከንቱ መንገድ ለመንገድ ይጨርሱታል ። ደግሞ ወደ አንዲት አረባዳ ሲደርሱ ሽፍታ ደብድቦ ያንን የተረፈውን ገንዘባቸውን ይቀማቸዋል ወይንም ይገላቸዋል ። እንግዴህ ይህ ለኢትዮጵያ በጣም ዋና ጉዳይ ነው ማለት ለቢ ጥቅምዋና ግርማዋ የሕዝብ ደህንነትና ክብረት ነው እንጅ የሕዝብ ማለቅና መጐዳት ምንም ጥቅሟ እንዳይሆን ሳይታለም የተተረጐመ ነው።እንግዴህ በየአውራጃው የምድር ባቡር ቢዘረጋ ሕዝብስ ይጠቀማል ? ሽፍታስ ይጠፋልን ቢሉ ለዚህ መልስ በጭሩ እናገኛለን ። ይህ አሁን ከአዲስ አበባ ወደ ጅቡቲ የሚሄድ የምድር ባቡር ያንን ሁሉ በረሃ ቆርጦ ሲሄድ አንድም ቀን ሽፍታ ድል መቶትና ገንዘብ ተቀምቶበት አይታወቅም ደግሞ ሽፍታ ሰውን ለመግደል የሚፈልግና የሚገል ሰው ገዳይ ብሎ ሊፎክር አይደለም ማለት ገንዘብ ሊቀማና በዚያ በቀማው ገንዘብ ሊነግድበት ወይም ያለ አንድ ብልሃት ሊያጠፋው ነው እንጅ ሰው መግደልና ገንዘብ መቀማት እንዳይጠቅመው አያስተውልም ደግሞ ሰውስ ሽፍታ ከመሆን ድረስ የሚደርሰው ገንዘብ ከማጣትና ወዲያ ወዲህ ብሎ የሚነግድበት ገንዘብ የሚጭንበት ከብት ሲያጣ ሰውነቱ ሲበሳጭ ተነሥቶ ሽፍታ ይሆናል ። እንግዴህ የዚህ መድኃኒቱ የምድር ባቡር በቶሎ መዘርጋት ነው ። ደግሞ በጣም የሚገርምና ሕዝቡ የሥልጣኔን መንገድ ለመያዝ ትጉህ መሆኑን የሚገልጽ አሁን የምድር ባቡር ይህ ወደ ጅቡቲ ከሚወርደው ሌላ በሌለበት ዘመን በአገራችን ብዙህ ነጋድያን ከሩቅ አገር በከብት ጀርባ እየጫኑ ከወንበዴ ጋር እየተጋደሉ ንግድ በአገራችን በጣም ሰፊ ነው በእንደዚህ ያለ መከራ ላይ ንግድ እንደዚህ የሰፋ የምድር ባቡር ቢኖርና ይህንን መንገድ ቢያገኙ እንዴት የሚሆን ይመስላችኋል ። ደግሞ በዚህ ላይ የሚገኘው የመንግሥት ገቢ ይህ ቍጥርህ ባልተባለ ይህስ አዲስ አበባ ለደጅ ጥናትና ለነገር(ማለትበርስትሙግት)የመጣው ሠራዊት ምን የሚያህል ገንዘብን እከተማ ይጨርሳል ። ግን ይህ መንገድ ቢኖር ምንም ያህል ገንዘቡን እያጠፋም ማለት እንደፈለገው እቤቱ ደርሶ እንደፈለገው ይመለሳል ። ገንዘቡን ለበቅሎና ላጋሰስ እያለ አያባክንም ከድህነትም ይርቃል ።

እንዴት እንደሚሆን እንናገር ይህንን ለማድረግ ከቶ መንግሥታችን ምንም አይቸግረውም አሁን ብናየውና ብንመለከተው የኢትዮጵያ ያንዱ ቀን ገቢ ከነኚህ ከቆጠርኳቸው ያንዱን አውራጃ አያሠራምን ደግሞስ መንግሥት ለሚጠቅም ነገር ገንዘብ ቢያወጣ ምን ይጐዳል ።

ክቡራን የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ይህንን እስካሁን ሳታመዛዝኑት ቀራችሁ ብዬ አይደለም ነገር ግን ለአገራችን ከዋናው ጥቅሞችዋ አንዱ ይህ ነውና አስቡበት በንግሥታችንና ባልጋ ወራሻችን ኃይል በቶሎ ይደረግልናል ስንል በተስፋ እንጠባበቃለን ።

ዓ ወ ዘ ።

የፍቅር ሰላምታ ።

ይድረስ ለክቡራን ወዳጆቼ የብራሃንና ሰላም ተላላኪዎች ጐዳናውን ለምትከተሉት ናሐሳባችሁ እንዲፈጸም ለምትተጉ ወንድሞቼ በትንሹም እውቀቴ የጻፍኩትን እንድትመለከቱልኝ ፍጹም ፈቃዳችሁን እለምናለሁ ። መቸም ሰው በዚህ ዓለም መድከሙ በኦሪትና በወንጌል የተጻፈውን የክርስቶስን ፈቃድ ለመፈጸም ነው ። አሁን እንኳ በሆነው በመድኃኒታችን በክርስቶስ ትንሣኤ በዓል ማክበር ሁሉም በየወገኑ በኋለኛው ዘመን ለኛ ትንሣኤ ለሚሆነው ምስክር የጌታችንን የትንሣኤውን በዓል ለማክበር ሁሉም በየቤቱ አፍቅር ቢጸከ ከመ ነፍስከ ያለውን ለመፈጸም ምስሐ በዓል ሊያደርግ ወዳጁን እየጠራ ያደረገውን ምሳሌ አይቼ ነበረ ። በመጨረሻው ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ለሀገራቸውና ለመንግሥታቸው ከመድከማቸው የተነሣ የውጭ አገር ሰዎች ሳይተዋወቁ ስምምነት ማድረጋቸውን አይተው ለኛ ምሳሌ ሊሆኑን ወንድሞቻቸው ሁሉ ደስ እንዲላቸው በቀን በቀኑ ከፍለው ፡ምስሐ በዓል ሲያደርጉ ቆይተው ነበርና በሚያዝያ ፳፰ ቀ ፤ ፲፱፻፳ ን ም የምሥጢር መገኛው ከሊቃውንት ነውና በዚሁ ቀን ሊቃውንቱን ጠርተው ነበረ ። ሊቃውንቱም በተጠሩበት ሰዓት መጥተው እስቲገቡ የመጣው ሊቀ ዙሪያውን በአበባና በጠጅ ሣር ሽቱ በታጠረች ዓረፍት ጥቅም ባለበት ቤት ውስጥ በያይነቱ መጻሕፍት ቀርበዋልና መምሕራኑ ያነን እያዩ ሲጫወቱ አይቼ ከደስታው ብዛት የተነሣ ሁሉም በየቤቱ ምነው እንደዚህ በሆነ ብሎ ወዳጄ ብርሃንና ሰላም አሳሰበኝ ። ከዚህ በኋላ በማዕርግ የተጠሩት ሊቃውንት ወደተዘጋጀው ቤት ገቡ ። የመብሉንና የመጠጡን ዓይነት የነበሩት ሰዎች ይንገሩዋችሁ እንጅ እኔ ምኑን እናገረዋለሁ። በዚሁ መካከል ስለደስታው ብዛት ሙዚቃ በያይነቱ ይመታ ጀመረ የደስታ መጨረሻ የሚባል ርዕሰ መኳንንት ሽምፓኝ በተከፈተ ጊዜ አንድ የብላቴን ጌታ ተማሪ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል አነበበ ።

ክቡር ሆይ ።

ጌታችን እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰውን በመውደዱ ፍቅርን መሠረት አድርጎ ለወዳጆቹ ለሐዋርያት ምስሐ በዓል እንዳደረገላቸው እርስዎም ጌታችን ለኛ ለወዳጆችዎ ፍቅርን መሠረት አድርገው በዚህ ቀን ለትልልቁ ወንድሞችዎና ለትንሹ ልጆችዎ የምሳ በዓል ስላደረጉልን በብዙ ደስታ እናመሰግንዎታለን ።

ሐሳብዎም እንጅ የሐዋርያ የጳውሎስ ሥራ ነው ። እርሱም በመጀመሪያ መልእክቱ ስለ መጽናናታቸሁ መንፈሳዊ ስጦታ

አከፍላችሁ ዘንድ እላንተን ማየት እወዳለሁ እርስዎም ይህቺ ናት በንድ ደስ ይለኝ ዘንድ በሃይማኖታችሁና በሃይማኖቴ በመከከላችን ያለችው ይላል ። እርስዎም ፍቅርና መውደድን መሠረት አድርገው ከጣዕሙ መልካምነት የተነሣ ልብ የሚነካካ ማዕድዎ ስለተዘጋጀልን አሁንም ሁለተኛ ደስታችንን አብዝተን እናመሰግንዎታለን ።

ከዚህም ቀጥሎ ሐዋርያ ጴጥሮስ እውቀትን መሠረት ሲያደርግል፡ በመጀመሪያ መልእክቱ በሃይማኖታችሁ በጎነትን ጨምሩ በበጎነትም እውቀትን በእውቀትም መሻትን መግዛት በመግዛትም ትዕግሥትን በትዕግሥትም አምልኮን በአምልኮም ወንድሞችን መንደድ ወንድሞችንም በመውደድ ፍቅርን ይህ በላንተ ዘንድ ቢሆንመልካም ነው ስላለ እርስዎም ይህነን ለመፈጸም ብለው እኛን ሰብስበው አምሳለ ገነት በመሰለች ቤትዎ የፍቅር ማዕድዎን ስላፀገቡን አሁንም በፊት ከሰጠነዎ ምስጋና አብልጠን እናመሰግንዎታለን ።

ለኛም ተፋቀሩ በበይናቲክሙ ያለውን ንባብ ማጽናት ይገባናልና ጌታችንን እንምሰላቸው ።

እንተ ታውኅዝ ሐሊበ ወመዓረ የተባለችውም ሀገራችን ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑርልን ግርማዊት ንግሥታችንን ያቆይልን ።

ለኢትዮጵያ ብርሃን ልዑል ጌታችንም ሕሊናችን የተመኘው ተፈጽሞልን የልዑል ጌታችነን ፈቃድ እንድንፈጽምና ወአርትዕ እገሪነ ውስተ ፍኖተ ሰላም ብለው ጐዳና ለመሔድ እኢደንቸኩል እድሜ እንለምናለን ። ከዚህ ቀጥዬ የሁላችሁም ፈቃድ ሆኖልኝ ስለ ወዳጅነትና ስለ ፍቅር የተዘጋጀውን ጽዋ በቀኝ እጄ ይገሮ ወአልዓልኩ ኅሩይየ እምሕዝብየ ያለውን ንባብ እየደገምሁ ለከበሬታቸው የተገባ ምስጋና እያቀረብሁ የወይኑን ጽዋ እጠጣለሁ ብሎ በተናገረ ጊዜ ከዚያ የነበረው ሰው ሁሉ የወይኑን ጽዋ እንደያዘ ቆሞ ተጨበጨበ። ቀጥሎም ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ እንደዚህ ብለው ተናገሩ ከልጅነቴ ጀምሮ አባቴን አለቃ ወልደ ጊዮርጊስን ያደከምሁት የመንግሥተ ሰማይን ጐዳና ለመከተል ነበረ ክርስቶስ በቸርነቱ ለዚህ አብቅቶኝ እላንተን ወንድሞቼንና አባቶቼን ለፍቅር ምሳ ለመሰብሰብና ለዚሁ ክብር አበቃኝ አሁንም ወደፊት ናሁ ሠናይ ወናሁ አዳም ሶበ ይሔልው አሐው ኅቡረ ያለውን ቃል እየተመለከታችሁ ይህ ዓለም ሐላፊ ነውና በዚያን ጊዜ እንድታስቡኝ አሳስባችኋለሁ ብለው በተናገሩ ጊዜ ከዳር እስከ ዳር ተጨበጨበ። ይኸውም ንግግራቸው በልበናው ተስሎ ያዘነ ሰው ሞልቷል አሁንም ወንድሞቼ ሆይ ይዘግቡ «ኢ. አምሩ ለዘያስተጋብዕ ያለውን እያነበባችሁ የቀድሞ ልማዳችሁን ትታችሁ ሰውን አንድ ጊዜ ጠርታችሁ ከማጉላላት በቀን በቀኑ ምሳ እያደረጋችሁ ወንድሞቻችሁን ብትጋብዙ እንደምን በተመሰገናችሁ? ትሑት ወንድማችሁ በ ዘ ተ

ለጤንነት የማይሰማማ ወተት ሕዝቡን እምብዛ እንደሚጐዳ

ባራተኛ ዓ ቍ ሥጋ ከመመገብ ወደሰው የሚተላለፉትን በሽታዎች እንዳስታወቅሁኝ ሁሉ አሁንም ወተት በሚመገቡ በኢትዮጵያ ሕዝቦችና ዘወትር ወተት ብቻ በሚቀምሱ ሕፃናቶች ያለባቸውን አደጋ አመለክታለሁ ።

ወተት

ከምግብ ሁሉ መጀመሪያ ወተት ነው ማለት ኃይልና ጉልበት በመሆኑና ገና ለተወለዱ ሕፃናቶች ምግብ ሆኖ እያፋፋቸው ለሰውነት በማብቃቱ ስለዚህ ለጤንነት የማይስማማውን ወተት በመመገብ ስንት ዓይነት አደጋ ይገኝበት ይሆን ማናቸውም ዓይነት በሽታ ካለበት ላም የታለበ ወተት ከፊተኛውም ይልቅ የባሰውን ጤንነት የሚያሳጣ እንደሆነ የታወቀ ነው ። ምንግዜም ቢሆን ወተትን ዘወትር የሚመገቡ ሕፃናቶችና ሙሉ ጤና የሌላቸው ጉልማሳዎች ስለሆኑ በሽታውን በፍጥነት ይይዛቸዋል ።

ከነዚህ በሽታዎች መጀመሪያው (ተቤርኩሎዝ) የሳንባ በሽታ ነው ይኸው በሽታ በአውሮፓ እንኳን እጅግ ስለሌለ ብዙህ ሰው ማበላሸቱ አልቀረም በዚሁ ምክንያት የታመሙ ሰዎች በመብዛታቸው ሃኪሞች መርምረው የዚሁ የሳንባ በሽታ መጋበትና መጉዳት የመጣው ከከብቶች ላይ መሆኑ ታወቀ ፤ ስለዚህም ጥንቃቄ ተብሎ በሽታ ያለባቸውን ከብቶች በየገሩ ያሉትን የወተት ነጋዴዎች ላሞቻቸውን በከብት ሃኪም እንዲያስመረምሩ ታወጀ ። ከዚያም በኋላ ወተታቸውን በነጻ ለመሸጥ ተቻላቸው በአውሮፓም ይኸ በሽታ ያነሰውና ከመቶ ፳፫ መገኘቱ በዚሁ ጥንቃቄ ምክንያት ነው ይኸውም ጥንቃቄ ሳይበቃ ቀርቶ የወተት መመርመሪያ ቤት ለዚሁ ተብሎ ቋሚል ለወተት ንግድ በተለየ በታ ጥገት ብቻ አበርክተው ወተቱን የሚሸጡ ነጋዴዎች ወተቱን አስቀድመው ከመመርመሪያው ቤት ድረስ እየወሰዱ ከተመረመረ በኋላ (ቢብሮን) በሚሉት የላስቲክ ጡት የሕፃናት ማጠጫያ እየተለከ ሕፃናቶችና ደካማዎች ሰዎች እንደዚሁ በጥንቃቄ በመመጋበቸው ከዚሁ በሽታ ለመከላከል ተቻላቸው ።

እስከዚህም ድረስ የተናገርኩት የሳንባን በሽታ ብቻ ስለሆነ ከዚህም ወዲያ ሌላ ብዙህ አደጋዎች ይገኙበታል። ትኩሳት የሚያስነሱና (ሚክሮብ) ማለት ረቂቅ ትሎች በሰውነት እየነዙ ለታላቅ ደዌ የሚሰጡ ።

፪ኛ ደግሞም ፊሊዮብር እፍትዝ በሀገራችን ከፊር የሚሉት የከብቶች በሽታ ወደ ሕፃናት እየተጋባ ኃይለኛ ተቅማጥ እያስቀመጣቸው ለምች ይሰጣቸዋል ይኸውም ከሚመገቡት ወተት የተነሣ ነው ።

፫ኛ(ቶክሲክ)የሚባል በሽታ ያለባቸው ከብቶች ሁልጊዜም በመላ አካላቸው የሚበተን ስለሆነ ይልቁን በተለየ የዚህ በሽታ ትል የሚበረክተው በጡት ሥራቸው ላይ ነው ስለዚህ የእንደዚህ ያሉ ከብቶችን ወተት መመገብ ድርቀትና በሆድ እቃ ሁሉ እመም ይሰጣል። ይኸውም እመም ይልቁን ደግሞ ወተት ብቻ የሚመገቡትን በብርቱ ያሙቸዋል ። አንድ አንድ ግዜም እውከትና ተቅማጥ ጭምር ይሆናል ሕፃናትን ግን እመሙ የበረታ ስለሆነ መርዝ ሊሆንባቸው ይችላል ደግሞም ከጥሩው ወተት ላይ ሚወጣው ጉዳት በስተቀር ወተቱ እንዲወፍርና እንዲበረክትላቸው የእህል ዱቄት ደባልቀው እንደምንም በርካሽ ዋጋ የሚሸጥ ወተትም አለ በዚሁ ሳምንት ፍተሻዬ እንዲሁ የእህል ዱቄትና በወሀ የተከለሰ ወተት ብዙ ጊዜ ገጥሞኛል ።

ስለዚህ ሁሉ ከዚህ በላይ ባጭሩ እንደማስረዳው ያገሩ ሰው ይልቁንም ያዲስ አበባ ከተማ ሕዝብ የዚንን የታላቅ ጉዳት ነገር እንዲገነዘበውና መንግሥትም የከብተ ሃኪምን እንደማቆሙ ከዚህ በላይ ያመለከትኋቸው ጥንቃቄዎች ላገሩ ሕዝብ ጤንነት እጅግ ጥቅም ያላቸው መሆናቸውን እንዲያስብበት ተስፋ አደርጋለሁ።

የርሻና የመሥሪያ ሚኒስተር የከብት ሃኪም ፡፡

ሚህራን ካይማኪያን

የሚስተር ሲ ኤፍ ሬ ሐተታ ።

ሚስተር ሲ ኤፍ ሬ የጥቁር ዓባይ አገርና የማትሸነፍ አበሻ የተባሉት መጻሕፍቶች ጸሐፊ አሳቡን እንዲገልጽ ቢኢስት አፍሪካ ጋዜጣ ስለ ታደመ ከዚህ በታች ያሉትን ሐተታዎች ያመለክታል ።

በአበሻ ምድር እስከ ነበርሁበት ቀን ስለ ገናናው ንጉሥ ምንም እንኳ ቁጥር የሌላው ወሬና አፈ ታሪክ ብሰማ የምኒልክ መዛግብት በክሊማንጃሮ ላይ የመኖራቸውን አፈ ታሪክ ከቶ አልሰማሁም ። እንዲህ ያለ ሰው ከቶ አልነበረም ። ብልጽግናውንም ይኸን ያህል መንገድ ተጉዞ በክሊማንጃሮ ተራራ ላይ ከተተ ማለትም እስከ መቼም የማይታመን ወሬ ነው ። የከበረ መዝገብ በየአምባው ላይ መክተት በአበሻ የተለመደ ነው ። ታሪካቸውም በእንደዚህ ያሉ ነገሮች የሞሉ ናቸው። ምኒልክም በገዛ አገሩ ውስጥ ሰው የማይኖርባቸውን አምቦች ብዙ ለመምረጥ ይችል ነበር ። እሱም በሰሜን አኩስም ይኖርና ይገዛም ነበር ይኸዉም ከክሊማንጃሮ በስተ ሰሜን በአሻጋሪው አገር ማዶ እንደ ቁራ መብረር (በቀጥታ) ፪ሺ ኪሎ ሜትር ነው። እሱም ወደ ደቡብ ጉዞ ማድረጉን ከቶ አልሰማሁም። ደግሞም ሰሎሞንም ንግሥተ ሳባም ወርቃቸውን ከአፌር ነበር የሚያስወጡ (ይኸም ምናልባት ሶፋላ ይሆናል) ይኸም ከክሊማንጃሮ በስተ ደቡብ በቀጥታው ፪ሺ ኪሎ ሜትር ይሆናል ። ግን ጊዜ እየለየ በሚነሳው በጽኑ ንፋስ ምክንያትም የሰሎሞን መርከቦች በጠረፉ ደርሰው ለመመለስ ፫ ዓመት ይወስድባቸው ነበር ። ሰሎሞንንም እንኳ ስለ አፌር ማዕድን ነገር ከወላጆቹ ቢረዳ ለወርቅ ሲል ወደ ሶፋላ መሄዱ እንዲመስል ጭንቅ ነው ። ወደ አኩም ግማሽ መንገድ አምጥቶ ይኸን ሁሉ አገር ጠልቆ (ተጉዞ በክሊማንጃሮ ደበቀ ማለትና በሁሉም ነገር የዚህ የሰሎሞን የንግሥተ ሳባ አፈ ታሪክ ከቀድሞው ይልቅ የማይመስል ነውና የመንደር ወሬ እንደሆነ ይመስለኛል ። በአፍሪካ በልዩ በልዩ ቦታ እንዲህ ያለውን አፈ ታሪክ ለራሴ ጉዳይ እንድፈልግው የሚያውቁ ባላገሮች አግኝቻለሁ ።

ከብርሃንና ሰላም ተላላኪ) ።

ሎተሪ

በሙሴ ዜ ሐሻዱሪያን ።የተሰናዳ ትልቅ የዕድል ዕጣ ።

እጅግ የከበረና ጥቅም ያለበት ሁለት መቶ ሀያ ዕጣ ሎተሪ በውስጡ የሚገኘው ሁለት አቶሞቢል ጥሩ ጥሩ ፈረሶችና በቅሎች ጠመንጃ ረሺ ሺጉጥ ሲንጀር መኪና ሰዓት የኪስም የጠረጴዛም እጅግ ጥሩ ጥሩ የሆነ ሥጋጃና ጃሀ ካባ በያይነቱ ሱፍ የከት ጨርቅ እጀጠባብ የወርቅ መስቀልን የመሳሰለ ጌጥ እንደዚሁም በያይነቱ ጥሩ ጥሩ ዕቃ በድምሩ ዘጠኝ ሺህ ብር ዋጋ ያለው ዕቃ ነው ያንዱ ዕጣ ዋጋ አራት ብር ነው ሁል ጊዜ እንዲህ በጥራትና በትክክል ሆኖ የማይገኝ እድልን መፈተኛ ነገር ስለሆነ የማታለያ መስሏችሁ ችላ ስትሉ ያመልጣችሁና እንዳይቆጫችሁ እናመለክታችኋለን ይህን ሎተሪ የሚያደርጉ ሰዎች አሳባቸው የዕቃቸውን ዋጋ ለማግኜት ነው እንጂ ሌላ ትርፍ አይፈልጉም ስለዚሁም የሚሸጠው ወረቀት ብዛት በዚያው በቃው ዋጋና ለዚህ ሥራ በሚአስፈልገው ከማራ ልክ ተወስኑዋል ፡

የዚህን ዕቃ ጥሩነት ለማስረዳት ማናቸውንም ማመልከቻ መጻፈ ትርፍ ነገር ስለሆነ ዓይን የሚአየው ነገር ይሻላል በማለት የዕቃውን ጥራት ለመረዳት የሚፈልግ ሰው ሁሉ ዓይኑ እንዲዓይ እንዲረዳ በሎተሪ የሚወጣውን ዕቃ ሁሉ በሙሴ ዜ ሐሻዱሪያን ቤት አስቀምጠነዋል ቤቱም ከዱሮው ማዘጋጃቤት ግርጌ ነው ከዚህ በፊት በየወጣው ወረቀት ላይ ዕጣው የሚታይበትን ቀን አለ ማመልከታችን ምንአልባት በቶሎ ሳይሸጥ ይቀርና ቃል አባይ ያደርገናል በማለት ነበር።አሁን ብናየው የዕቃው ብዛትና ማማር ሰውን ደስ ስላሰኘው ወረቀቱ በፍጥነት ብዙ ተሸጠልን ትንሽም ቢቀር የቃው ጥሩነት ገዥ አያሳጣንምበማለት ዕጣው የሚወጣበት ቀን ባስራሁለት ግንቦት በሙሴ ቴራስ ሆቴል መሆኑን እናመለክታለን ዕድላችሁን ለማየት የምትፈልጉ ሰዎች ሁሉ ወረቀቱ ተሸጦ ሳያልቅባችሁ ቶሎ ቶሎ ተሻሙ ።

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፩ ብር
የሲዳሞ ቡና	፩	፲ ብር ተኩል
ዝባድ	፩ ወቄት	፫ ብር ተኩል
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳ ብር ተኩል
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፬ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፹ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፱ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፱ ብር ተኩል
አቡጀዲ መንጽር	፩ ኮረጃ	፻፵፪ ብር
፡፡ ባለሰይጣን	፡፡	፻፵፬ ብር
፡፡ ባለ ድመት ።		፻፵፪ ብር
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻፳፮ ብር
፡፡ ባለ ሳቢ ግመል	፡፡	፻፴፫ ብር
ባለ አንበሳ	፡፡	፻፵፫ ብር
ስካር	፩ ጁኒያ	፹፱ ብር
ቻይ	፩ ነጥር	፭ ብር

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ
አንድ ብር	ሊሬ ፰ ከ፹፬ ሳንቲም
ባአንድ ጊኒ	፲ ብር ከ ፳፮
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፮ ብር

የከተማወሬ

ሚያዚያ ፳፯ ቀን ክቡር ደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ከክብርት ባለቤታቸው ከወ ይዘሮ ተናኘ ወርቅ ጋራ አዲስ ወደተቀበሉበት ግዛታቸው ወደ ከፋ ለመሄድ ተነሡ የስንብት ፈቃድ ተቀብለው ካዲስ አበባ በተነሡ ጊዜ ለመሸኘትና ለመሰናበት ተከትሎ የነበረ መኳንንትና ሠራዊት አበዛዙ እጅግ ያስደንቅ ነበር፡

ብርሃንና ሰላም ለክቡር ደጃዝማች ደስታና ለክብርት ወይዘሮ ተናኘወርቅ እግዚአብሔር መንገዳቸውን እንዲያቀናላቸውና በሚሄዱበትም አገር ሥራቸውን እንዲያከናውንላቸው፤ይመኝላቸዋል፡

COGNAC S&E&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቀሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩግቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

“ሩግቢ” የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶመቢል በተለይወኪል “አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ” ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው ደግሞ በኔዮርክ በፊላዴልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፡ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

RUGBY

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንዳርድ ኩምፓንያ ጋዝ፤ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ማስታወቂያ ።

ሺብሮሌ አቶሞቢል በኢትዮጵያ ወኪል ።
ሐ ሜ ዜርቦስ ኩምፓንያ ።

Automobiles CHEVROLET
H. M. ZERVOS & Cie
REPRESENTANTS
BAS PRIX HAUTE QUALITE

የሚከራይ ።

A LOUER

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ ኦቤርላንድ ኦቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጦጦን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ፡ ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።



አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባ ኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወድያም ባለማግኔቶና ባለባተሪ ነው ካምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ፟ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል «ዓረብያን፟ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው

ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

[illegible]

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒከላ ።

ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ ።

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህ በካፕሱሉ ያለ ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በካፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ጉድይር ግዙ





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው።በሌላጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ፤ ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አራተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፳
4 me ANNÉE № 20

ሐሙስ ግንቦት ፱ ቀን ፲፱፻፳ ዓ ም ።
JEUDI 17 MAI 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d'Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት የተደረገ የሚንስትሮች መጐብኘት ።

ግንቦት ፪ ቀን በ፱ ሰዓት ክቡር ደጃዝማች ወልደ ጻዲቅ ያገር ግዛት ሚኒስትር የሚመጡ ስለሆነ የዳግማዊ ምኒልክን ትምህርት ቤት ጐብኝተው በትምህርቱ ቤት ቻይ እንዲጋበዙ ክቡራን የኢትዮጵያ ሚኒስትሮችና መኳንንቶች ተጠርተው ነበር። ሰዓቱም በደረሰ ጊዜ መምህራኑ ተማሪዎቹን ግራና ቀኝ አሰልፈው የመጡትን ሚንስትሮችና መኳንንቶች ተቀበሉ ።

ከዚህ በኋላ ተማሪዎቹም በሚኒስትሮቹና በመኳንንቱ ፊት የጂምናስቲክ ጨዋታ ሲያደርጉ አምረው ታዩ ፤ ወዲያው ሚንስትሮቹና መኳንንቶቹ ለቻይ ግብዣ ወደ ተሰናዳው ቤት ገቡና ተማሪዎቹ ስለ ኢትዮጵያ አንድ መዝሙር ዘመሩ ። ከመዝሙሩ በኋላ የቻይ ግብዣ ተደረገ ። በዚያን ጊዜ ተማሪዎቹ ስለ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ስለ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ደስ የሚያሰኝ መዝሙር በመዘመራቸው በጣም የደስታ ጭብጨባ ተጨበጨበላቸው ። በዚያን ጊዜ መጥተው የነበሩ ሚንስትሮችና መኳንንቶች ከዚህ በታች የተጻፉት ናቸው ።

ክቡር አፈ ንጉሥ ከተማ የፍርድ ሚኒስትር የነበሩ ።
ክቡር ደጃዝማች ሙሉ ጌታ የጦር ሚኒስትር ።
ክቡር አፈ ንጉሥ አረጋይ የፍርድ ሚኒስትር ።
ክቡር ከንቲባ ነሲቡ ።
ክቡር ነጋድራስ መኰንን የንግድ ሚኒስትር ፡
ክቡር ሐኪም ወርቅነህ የኢ. መ አ ወ ተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ዋና ሹም ።
ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዋና ዲሬክተር ።
ክቡር ነጋድራስ ታፈሰ ።
ክቡር አቶ ወልደ አማኑኤል ፡
ክቡር አቶ መኰንን ሀብተ ወልድ የእርሻ ሚኒስትር ዲሬክተር ።
ክቡር ሙሴ እንድርያስ ከዋድያን የአእምሮ ጋዜጣ ዲሬክተር ናቸው፡

በሻምፓኝም ጊዜ ክቡር ደጃዝማች ወልደ ጻዲቅ ያገር ግዛት ሚኒስትር ቀጥሎ ያለውን ንግግር ተናገሩና በጣም ተጨበጨበላቸው ።

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና የኢትዮጵያ መንግሥት ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የትምሕርት ምንስቴርነትን ሥራ እንድጠብቅ ስላዘዙኝና ሥልጣን ስለ ሰጡኝ ለሥራ ጓደኞቹ ለሆናችሁ ክቡራን ምንስቴሮችና መኳንንቶች ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን ቃል እናገር ዘንድ አሳሰበኝ ።

አገራችን ኢትዮጵያ በአፍሪካ መካከል ያለች ከኤውሮፓም መንግሥታት ጋራ መገናኛዋ እየተቋረጠባት ስለምትቸገር በአሕዛብ ጦርነት እየተዋጋች ሳትሸነፍ ልጆችዋን በትምሕርት እያጠነከረች በጀግንነትና በጉብዝና በፈቃደ እግዚአብሔር ነፃነቷን ይዛ የኖረች ናት ። ዳሩ ግን ሰዎች ተራርቀው ስለማይቀሩ በየጊዜው አንዱ ካንዱ የዓለም ሕዝብ ሁሉ ይገናኛልና ስለዚህ ታላቁ የማይረሱት ንጉሠ ነገሥታችን ዳግማዊ ምኒልክ አገራችንን ኢትዮጵያን ከታላላቆች ሕዝቦች ጋራ እንድትገናኝ አደረጉዋት ። ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትም ሕዝባቸውን ለማስተማርና ለማሠልጠን ትልቅ ሐሣብ ስለ ነበራቸው ይህን የተማሪ ቤት አቆሙ ። ያገር ትምሕርት ብቻ አለመብቃቱን ስላወቁ የውጭ አገር ቋንቋ ትምሕርት የሚያስተምሩ አስተማሪዎች ከውጭ አገር ጐረቤቶች ከሆነው አስመጡ ።

ይህም የዳግማዊ ምኒልክ ተማሪ ቤት ከቆመ ዠምሮ ፳፬ ዓመት ያህል ሆኖታል ። አንዳንዱም ልጆች ዛሬ አዋቂዎች ሆ

ነው ለመንግሥታችን እያገለገሉ ለሕዝባችን እየጠቀሙ መልካም አረዳቶች ሆነዋል ። ይህም ትልቅ የተማሪ ቤት የሰጠውን ፍሬ እንድትረዱት በአለፈው ዓመት ባ፲፱፻፲፱ ዓ ም ሐምሌ ፲፬ተኛ በተደረገው ፈተና ብልሁ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የተናገሩትን ንግግር አሣሥባችኋለሁ ። የኢትዮጵያ መንግሥት ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የተናገሩትም ንግግር የተማሪ ቤቱ ሥራ እየተሻሻለ በመሄዱ እጅግ ደስ ስላቸው ይህንን የተማሪ ቤት ያቆሙትን ታላቁ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክን በጣም አመሰገኑ ። ይኸውም ልጆቻችንና መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ትምሕርት ለመማር የዳግማዊ ምኒልክ የተማሪ ቤት ችሎት ያለው ታላቅ ምሳሌ የሚሆን ነው ።

አሁን ዛሬ አገራችን ኢትዮጵያ በልዩ ልዩ ጉዳዮች የተሻሻለችና በሥልጣኔም ከፍ ከፍ ያለች እንደሆነች ያለ ጥርጥር እናገራለሁ ። የሕዝቦች ማሕበር ወገን ኢትዮጵያ ወንድሞቹዋ የሆኑትን ሕዝቦች አዲስ የሥልጣኔ መንገድ እየተከተለች ሕዝቧን ለማሠልጠን ትልቁን ደረጃ ለማግኘት በመሥራት ትጣጣራለች ። እንደምናየውና እንደምንሰማው መጀመሪያ የሚተጉበትና የሚጠነቀቁበት ሕዝባቸውን ለማስተማር ትምሕርትን ለማስፋት ብዙ የተማሪ ቤት በያገሩ በያውራጃው እያቆሙ ስለ ሚያስተምሩ ነው ። የሰው ልጅ እንደሚገባው በመንፈሳዊም ሆነ በሥጋዊ ትምሕርት ካልተማረ በጨለማ ውስጥ እንደሚኖር ያህል ይቆጠራል ። ተክል ከግልግልነቱ ጀምረው በየጊዜው እየተጠነቀቁ ወሀ እያጠጡ እየኰተኰቱ ያሳደጉት እንደሆነ አስተዳደጉ እያማረ ሥሩ እየጠነከረ ቅርንጫፉ እየሰፋና እየበዛ ያድግና ደህና ደህናውን ፍሬ ይሰጣል ።

ከግልግልነቱ ጀምሮ ሳይኰተኩቱት ያደገ ዛፍ ግን አስተዳደጉ ይበላሽና ፍሬ አልባ ይኖራል ። እንደዚሁ ሕፃናት በሕፃንነታቸው ወራት አስተዳደጋቸው እንዲያምር በአእምሮ እንዲጎለምሱ በሥልጣኔ እንዲዳብሩና መልካም ፍሬ እውቀትን እንዲያፈሩ በየጊዜው ወደ ተማሪ ቤት ሊገቡ ይገባል ።

ትምሕርታቸውም አስቀድሞ ያገርን የናት ያባትን ቋንቋ አነጋገር አጻጻፍ መሠረት አድርገው ካወቁ በኋላ ከአዲሱ የዓለም ሥልጣኔ የተገኘውን ጥበብና ብልሃት ሊማሩ የተገባ ነው ። ይህንኑም የኢትዮጵያ መንግሥት ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የሀገርን ትምሕርት ሳይማሩ የውጭ አገር ቋንቋ መማር በድቡሽት ላይ እንደተሠራ ቤት ነው ብለው በዲስኩር ተናግረውታል ። እውነት ነው አገርንና ንጉሥ መውደድን ሃይማኖት ማጽናትን የሚያስገነዝብ አስቀድሞ የአገርን ትምሕርት በመማር እንደሆነ አይጠረጠርም ።

ከተማሪ ቤት በመማር ልጆች እግዚአብሔርን ይፈራሉ ንጉሥን ያፈቅራሉ አባቦቶቻቸውን ለማስከበር አገራቸውን ይወዳሉ ጠላትም በመጣ ጊዜ ለንጉሣቸውና ለሀገራቸው ራሳቸውን አሳልፈው ይሰጣሉ ።

ከተማሪ ቤት በመማር ልጆች ለመንግሥት የሚጠቅሙ ደጋግ ሰዎች ይሆናሉ ። በተማሪ ቤት ልዩ ልዩ የእጅ ሥራና ልዩ ልዩ ዕውቀት ይማራሉ ። የእጅ ሥራ ማለት በሀገር ውስጥ የሚአስፈልገውን ነገር የልብስ ሥራ የወርቅና የብር ሥራ ። የብረት ሥራ ። የመሣሪያ ሥራ ሌላም ልዩ ልዩ ሥራ ሁሉ ማለት ነው ። ዕውቀት ማለት ደግሞ ተምሮ ሐኪም (አቡካት) መሐንዲስና ሌላም ይህንን የመሳሰለ ሁሉ ማለት ነው ። በተማሪ ቤት ሰው ጻድቅ ሃይማኖታዊ ቸር እሩኅሩኅ መሐሪ ልበ ቅን ትሑት ይሆናል ፡ ስለዚህ ምክንያት ይህንን የተማሪ ቤት ያቆሙ የዳግማዊ ምኒልክ ልጅ ደጓ እርኅሩኂቷ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ልበ ቅኑ ብልሁ የኢትዮጵያ መንግሥት ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያን ሕዝብ ለማስተማር ዘወትር የሚቻላቸውን ያደርጋሉ ። ግርማዊት ንግሥታችን በሚያስፈልገው ሥራ ሁሉ ይህንን የተማሪ ቤት ይረዳሉ ።

ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንም ይህንን የተማሪ ቤት እየደገፉ የኢትዮጵያን ልጆች ለማሠልጠን በገዛ ከሣራቸው ትልቅ ተማሪ ቤት አቆሙ ። እነዚህም የተማሪ ቤቶች ብዙ መልካም ፍሬ ሰጥተዋል ።

ግርማዊት ንግሥትና ልዑል አልጋ ወራሽ ይህ የዳግማዊ ምኒልክ የተማሪ ቤትና የልዑል ተማሪ ቤት ብቻ የማይበቃ መሆኑን ስላሰቡ በአዲስ አበባ በያውራጃውና በየአገር ግዛቱ ውስጥ የተማሪ ቤቶች እንዲያቆሙ ፍጹም ፈቃዳቸው ነው ። እንደዚሁ ልጆቻችን በመጀመሪያ የሀገራችንን የኢትዮጵያን ትምህርት ተምረው ሁለተኛ የሚያስፈልገውን የኤሮፓን ትምህርት ይማሩልናል ። ይህን ሁሉ ትምህርት ከፈጸሙ በኋላ ልጆቻችንን ከፍ ወዳለው ትምህርት እንዲችሉ ያደርጋቸዋል ። ዛሬ ይህንን የተከበረ የዳግማዊ ምኒልክን የተማሪ ቤት ስንመርቅ ለአዲሶች አስተማሪዎች ደምቡን ስንሰጥና ሥራችሁን ሰናስረክብ ይህ ቀን ትልቅ የደስታ ቀን እንደሆነ በጣም ይሰማኛል ።

ተማሪዎቹም ትምህርታችሁን አስተማሪዎቹም ማስተማራችሁን እግዚአብሔር እንዲያቃናላችሁ ስል በፍጹም እመኛለሁ ። ይህንን የተማሪ ቤት ያቆሙ የዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ለዘለዓለም ይኑር ።

እግዚአብሔር ግርማዊት ንግሥታችንንና ልዑል አልጋ ወራሻችንን ይጠብቅልን ። ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር አሜን ።

ከዚህ በኋላ ከግብፃውያን አስተማሪዎች አንደኛው ሙምህር ደስ የሚያሰኝ ንግግር ተናገሩና ተጨበጨበላቸው ።

ከዚያም በኋላ አቶ በቀለ ሀብተ ሚካኤል የትምህርት ቤቱ ዋና ሹም ደስ የሚያሰኝ ንግግር ተናገሩና ተጨበጨበ ።

ከዚህ በኋላ በዚያ የነበረው ሁሉ ክቡር ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ ያገር ግዛት ሚኒስትርን እየተሰናበተ ሄደ ።

የሰዮ ጉምሩክ ገቢ መሻሻል ።

በወለጋና በአቢጋር በዓረብ በየቦምብ አውራጃ ላለው የንግድ ሥራ ዋናው ጉምሩክ በወለጋ ውስጥ ሰዮ ነው በነዚህም አገሮች የሚመላለሰው ዋና ንግድ ቡን ሰም ጨው አቡጀዲድ ሌላም በያይነቱ ጨርቃ ጨርቅ ነው ። ከሱዳንም የንግድ መውጫው በር ገምቤላ ነው ። ሰዮም የመናገጃ ቦታ ከሆነች ፳፫ ዓመት ይሆናታል ፡ ነገር ግን በጉምሩክ ገቢ የመንግሥቱ ግምጃ ቤት የተጐዳ ይመስላል ። ምክንያቱም ሥራውንና ነገሩን የጥንት ሠራተኞች በቅጡ የተመለከቱት አይመስልምና ነው ።

ይኸውም መታወቂያው ዛሬ ክቡር ነጋድራስ ታፈሰ ሥራውን ከተሾሙት ከኅዳር ወር ጀምሮ እስከ ጥር ወር ያለውን ገቢና እርሳቸው ሳይሾሙ የነበረውን የመንፈቁን ገቢ ብናመዛዝነው ያሁኑ የሶስት ወር ገቢ የጥንቱን የመንፈቁን ገቢ ፩ሺ መቶ ዘጠና ሰባት ብር ከሁለት መሐለቅ መብለጡ ነው ። ለዚህም ብልጫ መግለጫ ከዚህ በታች ያሉትን ሰንጠረዦች እናደርጋለን ።

የሰዮ ጉምሩክ ያ፲፱፻፲፱ ዓ ም ያመት ገቢ ፲፫ሺ ብር ነበር ይባላል ። ያ፲፱፻፳ ዓ ም ከህዳር ፩ ፡ ጥር ፴ ። ፳፫ሺ ፯፻፺፯ ብር ከ፱ መሐለቅ ሆነ ። አስራምስቱን ሺ ከሁለት ብንከፍለው ለ፯ቱ ወር ፯ሺ ፭፻ ብር ይደርሰዋል ። ያ፲፱፻፳ውን ዓ ም የ፫ቱን ወር ገቢና ያ፲፱፻፲፱ኙን የመንፈቁን ገቢ ብናመዛዝነው የ፫ወር የመንፈቁን ፩ሺ ፻፺፯ ብር ከ፱መሐለቅ ይበልጠዋል ።

እንግዲህ የቀድሞው ሥራ በጥንቃቄ አለመሄዱን ይኸ ብቻ ያስረዳ ነበር ሌላም እንጨምራለን ። ያሁኑ ነጋድራስ ሌላ ደምብና ግብር ጨምረው በነበር ላለፈው ገቢ ማነስ ምክንያት ይሰጠው ነበር ይህ ክፉ አልታሰበም ። አልተጨመረም የምንለውም ከሠራተኞች በጊዜ መገኘትና ነጋዴ ወደ ጉምሩክ በመጣ ጊዜ ሠራተኞች አጥቶ ከመጉላላቱ መቅረት በቀር ነው ። ይልቁንም በጣም የሚያስገርመው ጥንት ጥቂት ገንዘብ የሚያገባው በርና ገበያ ዛሬ ብዙ በማግባቱ ነው ። ለምሳሌ ከዚህ በታች ያሉትን በርና ገበያዎች ጽፈናል ።

ነጋድራስ ታፈሰ ሳይገቡ የነበረው የሊልሞ በር የወር ገቢ ።

የመስከረም ወር ፫ ብር ፳፩ መሐለቅ ።

የጥቅምት ወር ፯ ብር ፸፰ መሐለቅ ።

ቅዳሜና ማክሰኞ ገበያ ሰየማና ባቡ በር ፡

የመስከረም ወር ፲፯ መሐለቅ ።

የጥቅምት ወር ፰ መሐለቅ ።

ማክሰኞ ቅዳሜ ገበያና ቃቂ በር ።

የመስከረም ወር ፳፩ ብር ፪፻፲፪ መሐለቅ ።

የጥቅምት ወር ፲፫ ብር ፩፻፶፬ መሐለቅ ።

ሰርባ ቅዳሜ ገባያና በር ።

የመስከረም ወር ፩ ብር ፺፯ መሐለቅ ።

ነጋድራስ ታፈሰ ከገቡ የሊልሞ በር ገቢ ።

የኅዳር ወር ፻፩ ብር ሺ፬፻፪ መሐለቅ ።

የታኅሣሥ ወር ፪፻፵፯ ብር ሺ፻፳፱ መሐላቅ ።

የኅዳር ወር ፫ ብር ፻፲፯ መሐለቅ ።

የታኅሣሥ ፳፪ ብር ፲፰ መሐለቅ ።

የኅዳር ወር ፺፱ ብር ፫ሺ ፹ መሐለቅ ።

የታሕሣሥ ወር ፻፳፱ ብር ፪ሺ ፱፻፰፫ መሐለቅ ።

የኅዳር ፺፯ ብር ፫፻፹፫ መሐለቅ ።

እንግዲህ ከዚህ በላይ ያሉትን ሰንጠረዦች አይቶ በጥንቱ ሥራ የመንግሥቱ ግምጃ ቤት መጐዳቱን ያረዳል እነዚህንም ለምሳሌ አደረግን እንጂ ብዙ በርና ገበያ አሉ ።

ክቡር ነጋድራስ ታፈሰ በተሾሙበት አገር ሁሉ ለመንግሥታቸው ትክክለኛ ሥራ በመሥራታቸው በጣም ያስመሰግናቸዋል ። በያገሩም እንዲህ ያለ መንግሥቱና የሕዝቡ አገልጋይ ቢገኝ ኢትዮጵያ ጸጸት አይገባትም ነበር ። ለክቡር ነጋድራስ ታፈሰም አንድ ነገር አመለክትዎታለሁ ተዘንግትዎትም ይሁን ባይመችዎም አላውቅም እንጂ ለሠራተኞቹ ቀለብ ሳያደርጉ ቆይተዋል ሥራ ሁሉ ገቢ ሲፈልግ መጀመሪያ ወጭን አስቦ ነውና ይኸም በጾሙ የሚያስፈልግ ጥና ነገር ነውና እንዲተጉበት ያስገድድዎታል ያለዚያስ ሥራው እንደዚህ ቀደሙ በትክክሉ ለመሄድና ለመንግሥት ግምጃ ቤት ገቢ ማብርከትን ያዳግትብዎታል። እነዚህም ከበታችዎ ሆነው ሥራውን የሚረዱዎ ሠራተኞች ማብዛትን ትተው ወደ ማጉደል የተመለሱ እንደሆነ ከጥንቱ የባሰ እንዳይሆን ያሰጋል ። እውነትም ሠራተኞቹ ተጽናንተው ሥራው እንዳሁኑ አካሄድ ቢሠራ ታላቅ ገቢ እንዲገኝ አያጠራጥርም ። የጥንቱን ማለት ያ፲፱፻፲፱ኙን ቀጥል ገቢ ከዚህ በላይ በነሲብ አመልክተናል ጉምሩኩም ከዚያ በላይ አግብቶ አያውቅም ይሉናል ። የጉምሩክ መዝገብ አዲሱ ሹም ሲገቡ ስለ አልተገኘ እርግጡን ለማግኘት አልቻልንም ። ነገር ግን የ፫ወር ቀፈፍ በምን ተዘነግታ እንደ ቀረች አናውቅም እሷንም በሰንጠረጋር አግብተናታል ። ግን ያሁኑን ዓመት ገቢ እስከ ሥልሳ ሺ እናስበዋለን ። ይኸንም ያሳሰበን የወሩ ገቢ ደረጃ ከፍ እያለ መሄዱ ነው ይኸንንም ቀጥሎ ባለው ሠንጠረዥ እንገልጻለን ።

ክቡር ነጋድራስ ታፈሰ ነጋድራስነቱን ከተሾሙት ወዲህ ያለው ገቢ ።

የህዳር ወር ገቢ ሺ ፱፻፵፩ ብር ከ፲፩ መሐለቅ ።

የታሕሣሥ ወር ገቢ ፪ሺ፰፻፹፬ ብር ከ፲፩ መሐለቅ ።

የጥር ወር ገቢ ፫ሺ፰፻፸ ብር ከ፱ መሐለቅ ።

የየካቲት ወር ገቢ ፬ሺ፯ ብር ከ፰ መሐለቅ ።

አንባቢዎች ሆይ ይኸን ሁሉ መዘርዘሬ ላገራችሁ የምትጸጸቱላትና ደህንነቷን የምትመኙላት ብዙ ናችሁ በየአውራጃው ደህና ደህና ልጆች ስታፈራና ከብቱዋ ሲጠበቅላት ለመስማት ደስ ይላችኋል ስል ተስፋ በማድረግ ነው እንጂ ማንንም ለማሞገስ ወይም ለመንቀፍ ልማዴ አለመሆኑን በትሕትና አመለክታለሁ ፤

የብርሃንና ሰላም ተላላኪ

በኢትዮጵያ መንግሥትና ። በሆላንድ መንግሥት መከከል የተደረገ የንግድ ውል ።

የኢትዮጵያ መንግሥትና የሆላንድ መንግሥት በመስከረም ፳ቀን ፲፱፻፲፱የዓመት የንግድ ውል ተዋውለዋል ። ይኸውም ውል የተደረገው የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና እንደራሴ ልዑል ተፈሪ መኰንን በግርማዊት ንግሥትና በራሳቸው ስም ሆነው ። ደግሞ የጄዳ ቆንስል ሙሴ ባንዴር ፕላስ በግርማዊት ዊልሄልሚና ስም ሆነው ነው ።

ውሉም ቀጥሎ የተጻፈው ነው ።

፩ኢትዮጵያ ነገሥታት ንግሥት ዘውዲቱና የሆላንድ (ፔይበ)ንግሥት ዊልሄልሚና በሁለቱ አገሮች መካከል ያለውን የንግድ ሥራ መገናኘት ለማስፋትና ለማልማት ፈቃዳቸው ስለሆነ የንግድ ውል ለመዋዋል ቍርጥ አደረጉ ።

ባንድ ወገን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና እንደራሴ ተፈሪ መኰንን በኢትዮጵያ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ስምና በራሳቸውም ስም ሁነው ደግሞ ባንድ ወገን የጅዳ ቈንስል ሙሴ ባንዴር ፕላስ በሆላንድ ንግሥት ዊልሄልሚና ስም ሁነው ቀጥሎ በተጻፈው ቃል ተስማምተው ተዋውለዋል ።

መጀመሪያ ክፍል ።

የሁለቱ መንግሥት ዜጐችና የንግድ ዕቃ አንዱ ወደ አንዱ ሲመላለስና ሲገባ በየራሳቸውም ጉዳይ ቢሆን ። ለነግድም ለቀረጥም ቢሆን።ከዚህ ቀደም ለሌላ መንግሥታት ዜጐችና የንግድ ዕቃ አብልጦ እንደ ተፈቀደውና ለንግዴሁም እንደሚፈቀደው በትክክል አድርገው ከዚያም ሌላ ሳይበልጥ ለወደፊቱም እንደዚሁ ያኖሩዋቸዋል ።

ሁለተኛው ክፍል ።

በዚህ ውል የተጻፈው ቃል ለሂንድ ኔዩርላንዲዝ ለሱሪናምና ለኩራሳዎም አገሮች ይጸናላቸዋል ።

ሶስተኛ ክፍል ።

ይህን የተጻፈውን ውል የሆላንድ ንግሥት መንግሥት ወዶ መቀበሉን ለኢትዮያ መንግሥት ካስታወቀበት ቀን ጀምሮ ከአንድ ወር በኋላ ይረጋል ። የዓመታቱም ልክ ውሉ ጸንቶ የሚኖርበት አምስት ዓመት ድረስ ነው ። የዚህ ውል ዘመን ሊፈጸም አሥራ ሁለት ወር ሲቀረው ከሁለቱ መንግሥቶች አንዱ ለአንደኛው ይለወጥ ይፍረስ ወይም እንዳለ ይርጋ ብሎ በጽሕፈት ያላስታወቀ እንደሆነ ይህ ውል እንደገና አንድ ዓመት ድረስ ይረጋል ። ከዚያም በኋላ አንዱ መንግሥት ለሁለተኛው መንግሥት አሳቡን ካላስታወቀ በቀር ከዚህ በላይ እንደ ተባለው ይህ ውል በየመቱ አንድ አንድ ዓመት ድረስ ይረጋል ።

ይህ ውል በአማርኛና በፈረንሣዊ ቋንቋ በትክክል ሁኖ ከሁለት ላይ ተጽፎ በአንድ ወገን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና እንደራሴ ተፈሪ መኰንን በኢትጵያ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ስምና በራሳቸውም ስም ሁነው ይፈርሙበታል ። ደግሞ በአንድ ወገን የጅዳ ቆንስል ሙሴ ባንዴር ፕላስ በሆላንድ ንግሥት ዊልሄልሚና ስም ሁነው ፈርመውበት አንደኛው በኢትዮጵያ መንግሥት እጅ ደግሞ አንደኛው በሆላንድ መንግሥት እጅ ይቀመጣል ። መስከረም ፳ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓመተ ምሕረት አዲስ አበባ ከተማ ተጻፈ ።

ውሉም ከተፈረመ በኋላ እንደ ዓለም መንግሥታት ሕግ ከመንግሥቱ ተልኮ የመጣ መልክተኛ ወደ ውጭ አገር ሄዶ ከሌላ መንግሥት ጋር የተዋዋለውን ውል በተመለሰ ጊዜ ውሉን ለንጉሡ አቅርቦ ንጉሡ መርምሮ ተቀብዬዋለሁ ብሎ ካልመሰከረ ውሉ አይጸናምና የጅዳ ቆንስል ሙሴ ባንዴር ፕላስ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር የተዋዋለውን ውል እንደሕጉ ለግርማዊት ዊልሄልሚና አቅርቦ ካስመረመረ በኋላ ግርማዊት ንግሥት ዊልሄልሚና መቀበላቸውን በመጋቢት ፳፯ቀን ፲፱፻፳ ዓመት በተጻፈ ደብዳቤያቸው አስታወቁ ።

የደብዳቤውም ቃል እንደዚህ የሚል ነው ።

እኛ ዊልሄልሚና የሆላንድ ንግሥት የኦራንጋ ናሶ ልዕልት ።
ሥይመተ እግዚአብሔር ።
ይህንን ወረቀት ለሚያዩ ሁሉ
ሰላምታ ።

በ፴ መስከረም ፲፱፻፳፮ ዓመት አዲስ አበባ ላይ ኢትዮጵያና ሆላንድ ስለ ንግድ ነገር የተዋዋሉትን ውል ደግሞ በዚሁ ከተማ በጥቅምት ፩ቀን ፲፱፻፳፮ ዓመት የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና እንደራሴ ተፈሪ መኰንንና በጅዳ ያለው የሆላንድ ቆንስልና ባለ ሙሉ ሥልጣን የተጻጻፉትን ወረቀት አይተንና መርምረን ።

ከዚህ በላይ በተጻፉት ወረቀቶች ያለውን መቀበላችንን ማጽናታችንን ፤ መፍቀዳችንን ፤ ሳይፈርስም እንዲፈጸም እናደርጋለን ማለታችንን በዚህ ወረቀት እናስታውቃለን ።

ስለዚህ ይህንን ወረቀት በእጃችን ፈርመን ሰጥተናል። መንግሥታችንም ማሕተም እንዲደረግበት አዘናል ።

በመጋቢት ወር ባምስተኛው ቀን ፲፱፻፳፯ ዓመተ ምሕረት በላሂ ላይ ተሰጠ ።

ማኅተም ፊርማ ዊልሄልሚና በስሩ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ፊርማ አለበት ።

ይህም አደራረግ ማናቸውም የመንግሥት ጉዳይ ሁሉ በንጉሥ ሥልጣንና ፈቃድ መፈጸሙን ያስረዳል ።

TRAITE DE COMMERCE CONCLU ENTRE LE GOUVERNEMENT IMPERIAL ETHIOPIEN ET LE GOUVERNEMENT ROYAL DES PAYS-BAS.

Le Gouvernement Ethiopien et le Gouvernement des Pays-Bas ont conclu, le 30 septembre 1926, un traité de commerce. Ce traité a été conclu par SON ALTESSE IMPERIAL TAFARI MAKONNEN Hèritier du Trone et Règent de l'Empire, d'Ethopie au Nom de SA MAJESTE L'IMPERATRICE et en Son Nom Personnel, d'une part; et Sa MAJESTE WILHELMINA, REINE DES PAYS-BAS, d'autre part; Reprèsentèe par Mr. VANDER PLAS Consul á Djeddah

Le texte du traité est ainsi conçu :

Sa Majesté Zaouditou, Reine des Rois d'Ethiopie et Sa Majesté Wilhelmina, Reine de Pays-Bas Animées du désir de favoriser et de développer les relations commerciales entre les deux Pays ont décidé de conclure un traité de commerce et à cet effet:

Son Altesse Imperiale et Royale Tafari Makonnen Héritier du Trône et Régent de l'Empire d'Ethi-

opie au nom de Sa Majesté Zaouditou et en Son propre nom, d'une part et Monsieur Ch. O. Vander Plas, Consul des Pays-Bas à Djeddah au nom de Sa Majesté Wilhelmina d'autre part ont convenu ce qui suit:

ARTICLE I.

Les ressortissants et les produits de chacun des deux pays jouiront reciproquement dan l'autre du même régime et des mêmes avantages en matière d'établissement, de commerce et de douane que ceux qui sont actuellement accordés ou qui seraient accordés à l'avenir aux ressortissants et aux produits de la nations la plus favorisée.

ARTICLE II.

Les dispositions du présent traité sont également applicables aux Indes Neerlandaises, au Suriman et au Curaçao.

ARTICLE III.

Le présent traité restera en vigueur pendant cinq ans, qui commenceront à courir un mois après le jour où sa ratification par le Gouvernement de Sa Majesté la Reine des Pays-Bas aura été communiquée au Gouvernement Impérial Ethiopien.

Si ni l'une ni l'autre des Hautes Parties ne fait connaître formellement à l'autre douze mois avant l'expiration de ces cinq années son intention de fairecesser les effets de ce traité ou de le modifier, il restera en vigueur encore une année et ainsi de suite jusqu'à l'expiration d'une année après sa dénonciation dans la forme ci-dessus indiquée' En foi de quoi, le présent traité a été rédigé en deux exemplaires identique en langue française et en langue amharique et signé d'une part par Son Altesse Impériale et Royale Tafari Makonnen Héritier du Trone et Régent de l'Empire D'Ethiopie au nom de Sa Majesté Zaouditou Reine des Rois d'Ethiopie et en Son propre nom et d'autre part, par Monsieur Ch.O. Vander Plas, Consul des Pays-Bas à Djeddah au nom de Sa Majesté Wilhelmina Reine des Pays-Bas un exemplaire devant rester entre les mains du Gouvernement Impérial Ethiopien et l'autre entre les mains du Gouvernement de Sa Majesté la Reine des Pays-Bas.

Fait à Addis Abeba le 20 Maskaram 1949 an de Grâce.

(30 Septembre 1926)

Suivant les Lois Internationales un Envoyé d'un Gouvernement chargé de négocier un traité auprés d'un Gouvernement Etranger présente à son retour, à l'examen de son ROI le traité qu'il a conclu afin que le ROI après examen donne Son approbation, nécessaire à la mise en vigueur du traité, qui, sans la ratification ne serait pas rendu valable. Conformément à ces Lois Mr. VANDER PLAS, a présenté, le traité qu'il a conclu avec le GOUVERNEMENT ETHIOPIEN, à l'examen de SA MAJESTE WILHELMINA qui, par un acte en date du cinq mars mil neuf cent vingt huit a fait connaitre Son approbation.

Le texte du dit acte est ainsi concu:

NOUS WILHELMINA, par la grâce de Dieu, Reine des Pays-Bas, Princesse d'Orange-Nassau, etc, etc, Etc.
A tous ceuux qui les présentes verront,
Salut

Ayant vu et examiné le traité de commerce conclu à Addis Abeba, le 30 septembre 1926, entre les Pays Bas et l'Ethiopie, ainsi que les notes échangéds dans cette ville, le 2 Octobre 1926, entre le consul et Plénipotentiaire des Pays Bas à Djeddah et Son Altesse Impériale et Royale Tafari Makonnen, Héritier du Trône et Régent de l'Empire d'Ethiopie, aete dont la teneur suits:

Approuvons par les présentes les actes susmentionnées, Déclarons qu'ils sont acceptés, ratifiés et confirmés, et Promettons qu'ils seront inviolablement observés.

En foi de quoi, Nous avons donné les présente, signés de Notre main, et avons ordonné qu'elles fussent revêtues de Notre sceau Royal.

Donné à La Haye, le cinquième jour du mois de mars de l'an de grâce mil neuf cent vingt huit.

Signé: WILHELMINA.

Sceau.

Contresigné par le Ministre des Affaires Etraggères.

Ces formalités montrent que n'importen quelles question d'Etat dépendent de la volonté et du Pouvoir du Roi, pour leur exécution.

የከተማ ወሬ

ግንቦት ፯ ቀን ክቡር ነጋድራስ መኰንን እንዳልካቸው የንግድ ሚኒስቴር ያዲስ አበባ ነጋዴና ወዳጆቻቸውን ሁሉ ጠርተው ያማረ ግብዣ ስለ ጋበዙ በዚያ የነበረ ሰው ሁሉ የሲሳዩን አበዛዝና የሥርዓቱን ማማር እያደነቀ የክቡር ጌታችንን ሹመት ያዳብርልን እያለ እጅግ ደስ ብሎት እያመሰገነ ሁሉም በሰላም ወደቤቱ ሔደ።

ስለ ዓየር

በዚህ ሰሞን ያዲስ አበባ ዓየር ይልቁንም ብራ በሆነ ቀን ደስ የሚያሰኝ ሆኑዋል ተራራውና መስኩም ሁሉ ልምላሜ ለብሰው ይታያሉ ዝናቡም ልከኛ ስለሆነ አይሰለችም ዝናብ በሌለ ጊዜ ሌሊትም ብርድ ስለሌለ ሽርሽሩ ደስ የሚያሰኝና ጤና የሚያድስ ነው ።

COGNAC S.&E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩግቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶመቢል በተለይ ወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው ፡

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፡በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፡ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፡ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ማስታወቂያ ።

ሺብሮሌ አቶሞቢል በኢትዮጵያ ወኪል ፡
ሖ· ሜ ዜርቦስ ኩምፓንያ ።



Automobiles CHEVROLET

H. M. ZERVOS & Cie
REPRESENTANTS
BAS PRIX HAUTE QUALITE

የሚከራይ ።

A LOUER

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ ኦቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጦጦን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ፣ ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።



አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባ ኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባተሪ ነው ክምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል «ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው

ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ ።

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህ በከፕሱሉ ያለ ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በካፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ጉድዬር ግዙ





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው።በሌላጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው፤ ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አራተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፳፩
4 me ANNÉE № 21

ሐሙስ ግንቦት ፲፯ ቀን ፤ ፲፱፻፳ ዓ ም ።
JEUDI 24 MAI 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d'Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የኢትዮጵያ አንድ ብልጥግናዋ ። (ሀብት)

የኢትዮጵያ የምድሯ ስፋት ፩፻፳ ኪሎሜትር ስለሆነና የሕዝቧ ቁጥር ፲፪ ሚሊዮን ያህል ስለሚሆን የከብትና የእህል አገር ናት እንጂ የመሥሯ አገር ሳትሆን ትኖራለች ። በጅዖግራፊም ሆነ በታሪኳም እንደምናየው ሁሉ ግን በኢትዮጵያ እጅግ የሚያሳዝነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ያገሯን ጥቅምና ሀብት ባለመፈለጓና ይልቁን ጥቅሟን በማጥፋቱ ነው ።

ዛሬ የሱዳን ዋና ንግዱ የጥንት ዘሩ ከፍሪካ በነበረው(ባርብ) በሚባለው ፈረስ ዘር ነው ። ይኸውም ፈረስ የኢትዮጵያ ፈረስ እየተባለ የሚወራው ነው ። የሂጃዝና የየመን ግዛት ሕዝቦች ከእውነተኛው ያረብ ፈረስ ይበልጥ ይኸንን የኢትዮጵያን ፈረስ ዘር ያስወድዳሉ ማለት ። የዚህ ያረብ አገር ፈረስ ዋጋው የበዛ ስለሆነ አሳዳጊዎቹ ሰዎች የዚህን (ባርብ) የሚባለውን የኢትዮጵያ ፈረስ ያስበልጣሉ ስለምን ያካሉና የፊቱ አወራረድ ካረብ ፈረስ መልክ ከ፻፸፭ እጅ በመመሳሰሉ ።

አሁን ግን በኢትዮጵያ የዚህ ፈረስ ዘር ጭራሹን አይገኝም የሸኛማ በሬ ዘርም እንዲሁ ጠፍቷል በዓረብ አገር ሙሱልና ባግዳድ በሚባሉ ግዛቶች በዚሁ በሬ የሚደረገው ንግድ ልክም የለው ግን ዘሩ ከነሱ አገር የተገኘ አይደለም እንደፊተኛው ሁሉ የዚህም በሬ ዘር ጥንት ከኢትዮጵያ የሄደ ነው እንጂ ስለሆነ ዛሬ ደህና አድርገው እያረቡ በኢትዮጵያ አገር በነበረ ጊዜ ከለው ሁናቴ ከ፻፵ እጅ በለጠ ኢትዮጵያ ግን ፈጽማ አጣች ባንድ ወገን ተላላፊው የከብት በሽታ ሲፈጃቸው ባንድ ወገን የከብት ሐኪም ባለመኖሩና ጥንቃቄ በማጣት ከዚህም ጉዳት የተነሣ ቁጥራቸውና ኃይላቸው እያነሰ ሄደ የነዚሁም ፈረሶችዘር ያው የጥንቱ ነው ለማለት እንኳን እስኪያጠራጥር ድረስ ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ ከሄድኩባቸው አንድ ክፍል አገሮች ውስጥ አሳይ ያመለከትሁትን የበሬ ዘር ያላቸው አንድ አንድ ሰዎች መኖራቸውን ተረድቼዋለሁ ።

ግን ምን ያደርጋል የነዚሁ አሳዳጊዎች ሀብታቸው ይኸው ብቻ ስለ ሆነ በሁለት በኩል ተስፋ ያጡ ናቸው ። ማለት ባንድ ወገን በሽታው ሲፈጅባቸው ባንድም ወገን ሸጠው ጥቅም ባለማግኘታቸው እነዚህም ድሆች የድካማቸውን ዋጋ ሳያገኙ እንዳያው ይቀራሉ አውሮፓ ብቻ እጅግ የከብት ሃገር ባለመሆኑና በመላው የመሥሯ ሃገር በመሆኑ ከያገሩ የደህናን ከብት ዘር እያጠራቀመ ለማርባት ይጣጣራል ማለት በሥጋና በወተት በኩል የሚያስፈልገውን ያህል እንዲያገኝና ወደያውም እንዲበራከት ዛሬ ከሱዬስና ከሆላንድ በስተቀር የቀሩት የመሥሯ ብቻ ሃገሮች ዋና ሀብታቸው በዚሁ ስለሆነ በመሣሯቸው ከሚያገኙት ጥቅም ሌላ በከብትም በኩል ብዙህ ትርፍ ለማግኘት ተቻላቸው ።

የደቡብ አሜሪክ ለሰሜን አሜሪካን በመላ እንደሚበቃው ከብት ትሰዳለች ብዙም የመርከብ ኩምባንያዎች ብዙ ሚልያርድ ኪሎ በበረዶ እንዳይሸት የተሰናዳ ሥጋ ከአንዱ ሀገር ወደ አንዱ የሚወስዱ አሉ ይኸውም ሁሉ ሆኖ ኢትዮጵያ ለምና የከብት አገር በመሆን ከአውሮፓና ከአሜሪክ እንድትበልጥ የታወቀ ነው ።በዚህም ላይከብት የሚያረቡ እጅግ ሰዎች ይገኙበታል ስለሆነም ለሀገሩ የሚበቃውን ሥጋ ለማግኘት ገና ጀምራለች

እነዚህ ሁለት ነገሮች ለሃገሩ ዋና ጥቅምና ሀብት ስለሆኑ የእርሻ ሚኒስቴር ተግቶ ያስብበታል ስንል ተስፋ አለን ፤ መጀመሯ ከብቱን ያለ ልክ ስለሚፈጀው በሽታ ሁለተኛ ከብት የሚያረቡትን ሰዎች እንዳይበሩቱ ተስፋ ስለሚያሳጣቸውና የከብትን ዘር እንዲሻሻል ለማድረግ የሚያስፈልገውን ከዚህ በላይ የተጻፉትን ሁለት ነገር የከብት ሃኪምን ሥራ በማጠናቀቅ በእርሻም ወገን ትልቅ እርዳታ ይሆናል ስለምን ለኢትዮጵያ ስለ እርሻ መኪና ሁነው የሚያገለግሏት በሬዎች ስለሆኑና ያሉ

እነሱ ሊታረስ ስለማይቻል ከብት ማበርከት በእህልም ወገን ጥቅም እንድታገኝ ትሆናለች።

በጭሩ ለማስረዳት የከብት ሃኪምን ሥራ ማደላደል በእርሻ በኩል ለሚገኘው ጥቅም የግድ የሚያስፈልግ ነው፤

የእርሻ ሚኒስቴር የከብት ሃኪም ሚህራን ክይማኪያን ።

የሁለት ልጆች ሐሳብ

ስለመልካም ትጋት ሐሳብና ስለምቀኝነት አሰናክይ ሐሳብ እነጋገር አንድ ልጅ ወደንባብ ተማሪ ቤት የሚሄድበት ሰዓት ተዳርሶበት ቸኩሎ እየሮጠ ሲሄድ ደግሞ አንድ ምቀኛው የሚባል አሰናክይ ተንኰለኛ ልጅ ከመንገድ ላይ አሸዋ እየጨፈጨፈ ሲጫወት አገኘው። ምነው ከልጠፉ ሥራ ከመንገድ ላይ አሸዋ ትጨፈጭፋለህ ብሎ ጠየቀው አሸዋ ከመንገድ ላይ ማጠር ሥራየነው ያንተ ሥራ ለኔ ሥራ አይሆነኝም አለው ። ከመንገድ ላይ አሸዋ መጨፍጨፍ ሥራ ይሆናል ቢለው አወን አለጊዜው የሚሮጠውን ሰው አሸዋ ቃልወጋው ለወረንጦ ዋጋ ገንዘብ ወጭ አያደርግም ብሎ መለሰ የወረንጦውን ዋጋ አንተ አታገኘው ምን ያደርግልሃል ቢለው ወረንጦ ሰራተኞቹ በዓመትም ሆነ በዕለትም ለመንግሥት ግብር ተሚያገቡት ገቢ ተግምጃቤት ወጭ ሲሆን በተሰጠኝ ሥራ ሳላገኝ አልቀርም አለው ። ጠረንጦ መግዣ የሌለው ድኃ ሰው ለሥራ ቸኩሎ በሚሮጥበት ሰዓት ሁሉ እንዴት ጊዜ ጠብቆ ይችላል አለው ፤ ጊዜ ታልጠበቀ እንኳን አሸዋ መውጋት መውደቅ አለበት አለው ። ለሁሉም ጊዜ አድራሹ እግዚአብሔር ነውና ያለጊዜም ሲሮጥ የወደቀም እሾህም የወጋውቢሆን በሥላሴ ኃይል እሾሁም ይወጣል በጥሩ ልቡና ሲወድቅም ይነሳል በብርሃን ተመልከች ጠቅልሎ ጠባቂ ወልደአምላክ ሰጥቶናል አለ እሁን ትሮጥ የነበርው ተኋላህ ምን ዓይተህ ወዴት ለመድረስ ተማን ለማምለጥ ነበር አለው ። እኔማ የምሮጥ ከወደኋላዬ ከለው ጨለማ ለማምለጥ ወደብርሃን ለመድረስ ድንቁርናን ለመተው እውቀት ለመፈለግ ነበር ቢለው ተኋላህ የነበረ ጨለማ ወደፊት ብትሮጥ ይለቅሃልን ድንቁርናስ ለቆ በሩጫ እውቀት ይገኛልን አለው ። ለሥራ ማከናወን ፈጥኖ ከልተገኙበት እድሜና ጨርሶ እንደምንም ያልቃል ያለብልሃት እኔስ እንደሐሳቤ እውቀትንም አገኝ ጨለማውንም አመልጥ ነበር አንተ ከዚህ እንደእንቅፋት ሆነህ አቆየኸኝ እንጂ ቢለው ከተገናኙበት ሥፍራ ጉታጉቶ ዛፍ ነበረና ጉታጉቶ ዛፍ እነበት ቦታ እንቅፋት መሆኑ የት ይቀር ይመስለሃል አለው ። ለሩጫም ተዘጋጅቶ የነበረው ልጅ ትጉህነት ቃለምነው እንቅፋት አይቀር ጉታጉቶውን ዛፍ ተስሩ እየቆረጠ ከመንገድ ላይ እያነሱ ቢያስገልሉት መንገዱ ወለል ያለው የጠራ ሆኖ ይታያል ብርሃን ከታዬ እንቅፋት ይቀራል አለው ምን ሐሳብ ረጅም ነህ እንቅፋት ይቀራል ብለህ ታስባለህ አለው ወደብርሃን መሮጤ ሐሳቤን ለማሳጠር መሰለህ እኔስ የምመኘው ለሀገራቸው ጠቃሚ ለሕዝባቸው መሪ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን በጅጅጋ ላለን ሕፃናቶች ሁሉ የመንፈሳዊና የሥልጣኔ ተማሪ ቤት ያቆሙልናል የእውቀትሥልጣኔ ደረጃ ያደርሱናል ብዬ የማይቀር ሐሳብ እመኛለሁ ምቀኝነት ተሚሰራ ሰው ተመጨዋት መልካም ከሚሰራ ይሻለኛል አብዝቶ መጣላት ሲታረቁም ቢሆን የሚያስረዳ ይገልጻል ብልሃት ደጉን ሐሳብ ከልብ አለማጥፋት ብሎ ፈጸመና ወደቀድሞ ሐሳቡ እየሮጠ ሄደ እኔም ተሄድሁበት ጉዳይ ስመለስ ይኸንን ንግግራቸውን ሰምቼ በመደነቅ ሳዳምጥ ቆይቼ ነበርና ነገራቸውን ተጨረሱ በኋላ እቤቴ እስትገባ ንግግራቸው እንዳይዘነጋኝ ተኪሴ ትንሽ ደብተር አውጥቼ ለብርሃንና ሰላም ወዳጆች አመለክታለሁ ብዬ ልጽፍ አሳሰበኝ ። መ ሸ ግሬ

የምሳሌ ትርጉም ።

በ፰ኛው ዓመት በ፲፯ ቁጥር በሚያዝያ ፲፰ ቀን ክቡር አቶ ማህሉ ጽጌ ለጻፈው ቃል መልስ መጀመሪያ ባላገሩ ሰውዬ በከተማ ነዋሪው ሰው ቤት ተቀምጦ ሳለ በዚህ በሰፊ ቦታህ ላይ አትክልት አለመትከልህ ስለ ምንድን ነው ብሎ ገሥጸው፥ በከተማ ነዋሪው ሰው ገዝቼ እበላለሁ ገንዘብ አለኝ ምን አደከመኝ ብሎ መልስ ሰጠ ይላል ።

ምሳሌው ግን ለኔ እንደሚመስለኝ ባላገሩ የዛሬዎቹ ወጣቶች የኢትዮጵያ ልጆች በከተማ ነዋሪው የኢትዮጵያ ታላላቅ መኳንንቶችና ጌቶች ማናቸውንም ነገር ለማድረግና ለመሥራት የሚቻላቸው ናቸው ይመስለኛል ።

ነገር ግን ገንዘብ አለኝ ገዝቼ እበላለሁ ያለው ሰውዬ ወርቅ የያዘ ቀበዝባዛ እህል (እውቀት) የያዘ ፈርዛዛ የሚባለውን ተረት ዘንግቶታል እንጂ እውቀት (እህል) ከሌለ የሚገዛው ምን ይሆን ።

ሆኑንና አቶ ማህሉ ጽጌ የጻፈው ዋነኛው ምሳሌ አስቀድሞ ንጉሠ ነገሥቱ ታላቁ ዳግማዊ ምኒልክ የእግዚአብሔር እንደራሴ አሁንም ልዑል ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ ብርሃን መምሕር ሆነው አትክልትን መትከል (ተማሪ ቤትን ማቆም) መሪ ሆነው ሲያስተምሩ በከተማነዋሪ (መኳንንቶች ፍለጋቸውን ተከትላችሁ አትክልት መትከልን እርሻ ማረስን (ተማሪ ቤት ማቆምን እውቀት መዝራትን) ለምን ቸል አላችሁ ማለቱ ይመስለኛል ።

ዳግመኛም ስለ ዘሆን ዠሮ የጻፈው ምሳሌው እውነትም ዘሆን በአካሉ ግዙፍ በጉልበቱም ትልቅ በጥርሱም ብርቅ ነው ። ጆሮውም አቶ ማህሉ ጽጌ እንዳለው ለራሱ መጠንቀቂያ ሲሆን በጣም ንቁ ነው ። ለማይጎዳው ነገር ግን ሰምቶ እንዳሰማ ዝም ይላል ሞኝነቱ ነው ሰው በቁመት ከሱ ያንሳል በአእምሮ ግን ይበልጣል ስለዚህ እሱም በሰው እጅ ይወድቃል ከሰው የሚያልፍ ነገር የለም ነገር ግን ዘሆን ለጊዜው ይስማ ያሸትት እንጂ አያይም ከየማ ስንቱ ኢልሞሴ (ልጆቹ) በአዳኞች እጅ (በድንቁርና) ተነጥቀው ያልቁ ነበር አስተምሮ ይጠብቃቸው አልነበረምን አሁንም ሁሉንም ጨርሼ ለመተርጎም ሰነፍ ዘሆን ወጣት ሲገኝ ደስ ይለዋል ከሚለው ቃል ስደርስ ደንግጬ የዘሆንን ቁጣ ስለፈራሁ ነገሬን እተዋለሁ በጉደለውም የብርሃን ልጆች ያግዙኛል ስል ተስፋ አደርጋለሁ ።

ተስፋዬ ካሣ

ተወዳጅ ወዳጄ ብርሃንና ሰላም ሆይ ።

ከዚህ በታች የምጽፍልህን ያየኋትን ነገር ለክቡራን ወዳጆችህ እንድታቀርብላቸው ስል አለምንሃለሁ ።

አንድ ቀን በጧት ከቤቴ ደጅ ጥናት ወደሚባለው ሥራዬ ሂጀ እሥራ ቆይቼ በስድስት ሰዓትም የሥራ የሰጠኝ የእሽታ ተስፋ ምሳ አቅርበውልኝ ምሳዬን ተጋብዤ ከዚያም በኋላ ሥራዬን ሥሡራ ውዬ ማታም ወደቤቴ ገብቼ ቁጭ ብዬ ከንድ ሽማግሌ ጋራ ስንጫወት ቆየን ወደዚያው አንድ ያሳደጉት ድመት አንድ አይጥ ያዘና አጠገባችን በለችው ሜዳ ዓይኑዋን አጠፋና ለቋት ወዲህና ወዲያ እየበረረ አንዳንድ ጊዜም ወደላይ እየወረወረ ይጫወትባት ነበር ።

እኔም እኛን ሽማግሌ ይህችን ያገኘችን ሲሳይ አርድ እንደመብላት እንዴት ያለ ጡር የሚሠራ ድመት ነው ብዬ አልኋቸው ።

እሳቸውም እንዲህ ብለው መለሱልኝ ልጄ ሆይ የተመቸው ሁሉ እንዲህ ነው የሚያላግጠው በዚህ ምን ያስደንቅሃል እስኪ ብዙ የተቻላቸውን ሰዎች ተመልከት መፈጸምና መቁረጥ የሚቻላቸውን ነገር ነገ ዛሬ እያሉ ሰው ሲያጉላሉ ማላገጥና መጫወቻ ማድረግ በገኘ ሁሉ ላይ መሆኑን ተረዳው ብለው እኛ ሽማግሌም አጫወቱኝ ክቡራን የብርሃን ሰላም ወዳጆች ሆይ ።

ይህ ነገር ለኔ አዲስ ስለመሰለኝና ነገሩም ስለገረመኝ የጸፍኩላችሁን ቃሎች የተገደፈ ነገርም ብታገኙበት ይቅርታ እንድታደርጉልኝ ስል ልመናዬን አሳስባችኋለሁ ።

በቀለ ዘለቀ

የአቶሞቢል ነገር በኢትዮጵያ ።

በኢትዮጵያ አገር ከአንዱ አውራጃ ወደ አንዱ አውራጃ ለመዘዋወር ያለውን ችግርና የበቅሎን ማነስ የኑሮን እያደር መወደድ መንግሥታችን ስለ ተረዳው ዋናዋን ከተማ አዲስ አበባን ከሌሎቹ አገሮች ጋራ የሚያገናኛት መንገድ መሥራት በጣም የሚያስፈልግና የሚያስቸኩል ነገር መሆኑን አውቆታል።ስምንት መቶ ኪሎ ሜትር ብቻ የምድር ባቡር በተዘረጋበት እንደ ኢትዮጵያ ባለ አገር ውስጥ የሚያስፈልገው በቀላል ዋጋና በፍጥነት የሚያደርስ መንገድ መሥራትና የሚጫነውም ዕቃ በአቶሞቢል እየተጫነ ሰውም በአቶሞቢል እንዲመላለስ ያስፈልጋል ።

መንግሥታችን ለሕዝቡ በጐ ሐሳቢና ለአገሩ ልማትና ጥቅም የሚሆነውን ነገር ፈላጊ መሆኑን ሁሉም ተረድቶታል ስለ ዚህም ይኸውና ወደ አንድ አንዱ አውራጃ የሚሄድ መንገድ ከአዲስ አበባ ጅማ ከጐሬ ጎንቤላ ድረስ የሚሄድ መንገድ አስጀምሯል ። ከዚህም በቀር ከአዲስ አበባ ፊቼ ድረስ የሚሄድ መንገድ ለመሥራት አሳብ አለው ሲሉ እንሰማለን ። ደግሞም ከአዲስ አበባ እስከ ወላሞና እስከ እንግሊዝ ግዛት ወሰን ድረስ ኤስት አፍሪካ ድረስ የሚሄድ መንንገድ ለማሠራት ውል ሰጥቷል ይባላል ። ባሁን ጊዜ የእህልንና የሌላ የሌላውን ነገር ሁሉ መወደድ የተመለከተው ሰው መንገድ ያለመኖርና የሚጫንበት ነገር ችግር በመሆን የተነሣ እንደሆነ ሊረዳው ይችላል።ስለ ዚህ መንግሥቱ ለመንገድ ሥራ ነገር ቶሎ መትጋቱ እውነት አለው ነገሩን ሳናስረዝም ብጭሩ እንኳን ብንመለከተው በዛሬ ጊዜ ከዚህ እጐሬ ድረስ ያንድ አጋሰስ በቅሎ ክራይ ፳፫ ብር ነው ። መንገድ ቢሰራና በአቶሞቢል የሚጫን ሆኖ ቢሆን ዋጋውም ከዚህ ያነሰ ሆኖ ዕቃውም በቶሎ የሚደርስ ዘሆን ነበር ። ከሁኑ እንኳን አዲስ አበባ(ከ፲፱)ሰስት መቶ አምሳ የሚበልጥ አቶሞቢል አለ ። በየግዜውም እየበረከተ ሲሄድ እናየዋለን። ዓምናም ልዑል ዱክ ዴዛብሩዝ ሲመጡ ከኢጣልያን አገር አንጥተው ለግርማዊት ንግሥት ያገቡትን ድንቅ የሆነ አቶሞቢል ሁላችንም አይተን አድንቀንዋል በዚህም አቶሞቢል የኢጣልያን ፋብሪክ ያስመሰገነው ታላቅ ክብር አገኘ ።

ይሁን እንጂ ሰው ሁሉ እንደዚህ ያለ አቶሞቢል ለመግዛት ገንዘቡ አይፈቅድለትም ስለ ምን እንዲህ ያለው ኢዞቶፍራሽኒ የሚባለው አቶሞቢል ዓይነት ዋጋው በጣም ውድ ነው ።

ስለ ሆነም የኢጣልያን ፋብሪክ ዋጋው ቀላል የሆነ ሌላም አቶሞቢል ይሠራል።ይኸውም አቶሞቢል ፊያት የሚባለው ነው ። የፊያትን አቶሞቢል እንደራሴነት የንግድና የሥራ የኢትዮጵያ ማህበር የሚባሉ ማህበር ወስዶታል ። ይህም ማህበር የቆመው በሐበሻዎች ገንዘብና ማህበሮቹም የኢትዮጵያ በሆኑ ሰዎች ነው ሌላም የልዩ ልዩ ዓይነት አቶሞቢሎች ፋብሪካዎች እንደራሴነቱን ለፈረንጅ ነጋዴ ሲሰጡ እንደ ፊያት ያለ ትልቅ የአቶሞቢል ፋብሪክ በኢትዮጵያ አገር እንደራሴነቱን ለዚህ ለኢትዮጵያ ማህበር በመስጠቱ ለሁሉም ደስ ያሰኘው ነገር ሆኑዋል ።

ይህም የንግድና የሥራ የኢትዮጵያ ማህበር በእንግሊዝ ባንክ አጠገብ አዲስ ያማረና ሰፊ የሆነ ቤት አሰርቶ ካሁኑ ያስመጣቸውን አቶሞቢሎች በዚሁ ቤት ውስጥ ለማየትና ለማድነቅ ይቻላል ። የፊያት አቶሞቢል የውስጡ መኪና በጽኑ ሆኖ የተሠራና ውጭውም ሳይን የሚያምር ነው ። ከዚህም በቀር ቤንዚን የሚፈጅ ባለ መሆኑ ከሌላው አቶሞቢል ያስመርጣል። ፭፻፱ የሚባለው አዲሱ ዓይነት አቶሞቢል የሚፈጀው ቤንዚን ቢታሰብ በሁለት መቶ ኪሎ ሜትር አንድ ታኒክ ቤንዚን ብቻ ነው የሚያስፈልገው ከዚህ ካዲስ አበባ እስከ ሞጆ ድረስ መንገድ ቢኖር አንዱን ታኒክ ቤንዚን ሳይጨርስ ሞጆ ደርሶ ለመመለስ ይችላል ።

ይህም ፭፻፱ የሚባለው አቶሞቢል ዓይነት እዚሁ እማህበሩ ቤት አለና የሚፈልጉ ሁሉ መጥተው ለማየት ይችላሉ ። ሥራውም ባለ መስተዋት ሆኖ መቀመጫው ያማረ ዋጋው የቀለለ ነው እጅቡቲ ላይ (፪ሺ.) ፪ሺ፻፳፭ ሁለት ሺ መቶ ሀያ አምስት ብር ብቻ ነው የሚሸጠው ። ቢተሰበረም ቢተበላሸም ጊዜ የሚታደስበትና የሚበጅበት ቤት ይኸው የኢትዮጵያ ማህበር ትልቅ የመኪና ቤት መሥራት ጀምሯል። የሚለዋወጠውንም በጐደለም ጊዜ የሚተካውን መኪና ሁሉ በያይነቱ ያስመጣልና ፊያት አቶሞቢል የገዙትም ሆኑ ወደ ፊት የሚገዙትም ሆኑ የሚያስፈልጋቸውን መኪና ሁሉ ለማግኘት ይችላሉ ቢተበላሸ

ባቸው ጊዜ የሚያበጅላቸው ሥራቸው የሆን ደህና ደህና ሠራተኞች አሉት ።

ይህም ማህበር በወር በወሩ እያስከፈለ በዱቤ ለመሸጥ ወደ ፊት ለመጀመር ያስባል ።

ምሳሌ

አበቴና እናቴ ተረት ሲጫወቱ እሰማ ነበር ጅብ አህያን እንጋባ ደማችን ይድረቅ አላት አህያም ለባሏ ዛሬ ትልቅ ነገር ሰማሁ አለችው። አቶ ጅብ እንጋባ ደማችን ይድረቅ አለኝ አለችው ለባሏ ባሏ አይደለም ጌታና ሎሌ ተማግቶ ጅብና አህያ ተጋብቶ ይሆን አይመስለኝም አላት እርስዎ ዱሮም ምክር አይገባዎትም ጨሌና ሰርዶ እያሎን በውርጭ ብናድር እንበለ ሐሳብ የምንኖረውን ነዎይ አይደለም እንጋባ አለችው ታልሺማ ይግነው አለ ተጋቡም የጅብ ጉረምሶችም ዛሬ እራታችንን እንብላት አሉኝ ብላ ሙሽራይቱን ተማከሩበት ሽማግሎች አይደለም ሁሉንም አንድ ቀን እንበላቸዋለን አሉ በመሐከል የጅብ አባት ሞተ ወደ አህያ ተላከ አህያም ዘመዶቹን ይዞ ሒደ እቤት በታች ሲደርሱ እንዲህ ብለው አለቀሱ፤ምን ጨለማ ቢሆን ብርሃን ነው ዓይነዎ፤ ምን እሩቅ ቢሮሁ ይሰማል ድምጥዎ፡ የኛን ብላቴና ምን አገኘብና እያሉ አለቀሱ የጅብ ደግሞ የወዲያውን ወዲህ ብለሽ ያለቀስሽ ዩኽ ሁሉ አዘነተኛ ምን ይባላ ብላ አለቀሰች አዘነተኞች ቁጭ አሉ የጅብ ሽማግሌ ወንድማችን በድንገት ሞተ አሁንም ለአዘነተኛ አዋጥታችሁ አንድ አህያ ስጡን አለ አንድ ሽማግሌ ጌቶቹ ሆይ አህያ ይቆይ እተኩላለሁ የሚደርሰብኝን እሰጣለሁ ቢል አይደለም የምንማክረው ነገር አለን አሉት ተማክረው እቤት የደረሰብንን እንልከለን አሉ አይደለም የተሰበሰበው አዘነተኛ ምን በልቶ ይህይ ብላችሁ ነው ታልሆነ የላይኛውን ከንፈራችሁን እየቆረጣችሁ ስጡን አሉ እየቆረጡ ሰጡ ተሰናብተን ስንለያይ ዘወር ብላችሁ ሰላምታ ስጡን አሉ ሰጡም የኔ አባት ትላትና ሞቶ የናንተ መሳቅ ምን ይባላል አሉና ጅብም እንደ አባትህ ዘርጥ አህያ እንደ አባትህ እሩጥ ተባለ አህዮች እንደ ዋሉ ቀሩ ይባላል አስቀድሞ አይሆንም አለ አህያ ልጆቼ ሆይ በብልኃት የገባ ባላጋራ ሸሽተው ሊያመልጡት ከንቱ ነው ብሎ ተናገረ፤ምሳሌ ሰሎሞን ። ፩። ምዕራፍ ። ፲ ። ቁጥር አወል ደዮ ሰበ ያስሕቱከ ኃጥአን አሆ ኢትብሎሙ ብሎ ያስረዳናል

ደምቢ ዶሎ ሊበን ጣፈጠ።

የመንግሥት ማስታወቂያ

የኢትዮጵያ መንግሥት ከውጭ አገር መንግሥቶች ሚኒስትሮችና ቆንስሎች ጋራ ለሚነጋገርበት ጉዳይ ሁሉ አሁን ለጊዜው በተለየ አምስት አስተርጓሚዎች አደርጓል፡

የነዚሁም ስማቸው

ተስፋዬ ተገኝ፤
ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ ።
ዘለቀ ንጋቱ ።
ዳባ ብሩ ።
ይልማ ገብረ ኪዳን ናቸው ።

ወደ ፊት ግን ለመጨመር የሚያስፈልግ ቢሆን እየታየ ይጨመራል ።

NOTE OFFICIELLE.

Pour les entrevues entre le Gouvernement Ethiopien et les Représentants des Puissances Etrangères (Ministres, Consuls) ont été désigné cinq interprétes officiels dont les noms suivent:

TESFAE TEGUEGNE.
WOLD-GUIORGUIS WOLD-YOHANNES.
ZELLEKE NEGUATOU.
DABA BEROU.
YELMA GUEBRE-KIDANE.

Le nombre de ces interprétes pourra être augmenté suivant la necessité.°].

ስለ ሹም ሽር ።

ግንቦት ፲፪ ቀን ክቡር ደጃዝማች ሀብተ ማርያም ራስ ተብለው የራስ ደምሰው የነበረውን ወለጋን ተሾሙ ።

ክቡር አዛዥ መታፈሪ ደጃዝማች ተብለው ጐላን ተሾሙ

ክቡር ሹም ተምቤን ገብረ መድኅን ደጃዝማች ተብለው አክሱምን ተሾሙ ።

ክቡር ፊታውራሪ ገብረ ሚካኤል የሹም ተምቤን የነበረውን አገር ጉድሩን ተሾሙ ።

ክቡር ልጅ ጣሰው ፊታውራሪ ተብለው የቀኛዝማች በየነ የነበረውን ተሾሙ ።

ክቡር ልጅ ሥዩም ግራዝማች ተብለው ቀወት ውስጥ ተሾሙ

ብርሃንና ሰላም አዲስ ሹመትና መዓርግ ለተቀበሉ እንኳን ደስ አላችሁ እያለ መልካም ምኞቱን ይገልጻል ።

የፈረስ እሽቅድድም

ግንቦት ፲፰ ቀን የፈረስ እሽቅድድም በጃንሜዳ እንደሚደረግ ተነግሮነበረና በዚሁ ከጧት በሶስት ሰዓት ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በክቡራን መኳንንትና ሠራዊት ታጅበው እሽቅድድሙን ለማየት አምሮ በተሰናዳው ቦታ ሒደው ተቀመጡ ።

አንደኛ እሽቅድድም

የሚጋደው እርዝመት ፰፻ ሜትር ።

ፊተኛ ቀዳሚ የመዳም ደሴይ ሞቤላርድ ፈረስ ሆነና ኖቢስ ዋንጫ ተቀበለ።

ሁለተኛ እሽቅድድም ።

የሚጋደው እርዝመት ፲፭፻ ሜትር።

ፊተኛ ቀዳሚ የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፈረስ ሆነና የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትን ዋንጫ ተቀበለ ።

ሁለተኛ ቀዳሚ የሙሴ ደሴይ ሞቤላርድ ፈረስ ሆነና ፴ ብር ተቀበለ ።

፫ኛ እሽቅድድም ።

የሚጻው ርዝመት ሺ፫፻ ሜትር ።

ፊተኛ ቀዳሚ የሙሴ ክራ የኢጣልያ ሚኒስትር ፈረስ ሆንና ሁለት ዋንጮች ተቀበለ ።

ሁለተኛ ቀዳሚ የሙሴ ደሴይ ሞቤላርድ ፈረስ ሆንና ፴ ብር ተቀበለ ።

፬ኛ እሽቅድድም

የሚጻው ርዝመት ሺ፱፻ ሜትር

ፊተኛ ቀዳሚ የመዳሚዜል የውብ ዳር ብሩ ፈረስ ሆንና ፺ ብር ተቀበለ ።

ሁለተኛ ቀዳሚ የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ፈረስ ሆንና ፴ብር ተቀበለ ።

፫ኛ ቀዳሚ የሙሴ ደሴይ ሞቤላርድ ፈረስ ሆንና ፲፱ብር ተቀበለ ።

፭ኛ እሽቅድድም ።

የሚጻው ርዝመት ፪ሺ ሜትር ።

ፊተኛ ቀዳሚ የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ፈረስ ሆንና የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንን ዋንጫና ሃምሳ ብር ተቀበለ ።

፪ተኛ ፡ ቀዳሚ የሙሴ ቤንቲንግ የእንግሊዝ ሚንስትር ፈረስ ሆንና ፴ ብር ተቀበለ ።

፫ተኛ ፤ ቀዳሚ የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ፈረስ ሆንና ሃያ ብር ተቀበለ ።

፮ተኛ እሽቅድድም የዝላይ ፤

የሚጻው ርዝመት ሺ፰፻ ሜትር

ፊተኛ ቀዳሚ የሙሴ ዣንፒክ ፈረስ ሆንና የልዑል ዱክ ዴዝአብሩዝን ዋንጫና ፺ ብር ተቀበለ ።

ሁለተኛ ቀዳሚ የግርማዊት ንግሥተ ንንሥታት ፈረስ ሆንና ፺ ብር ተቀበለ ።

፫ኛ ቀዳሚ የሙሴ ክራ የኢጣልያን ሚኒስትር ፈረስ ሆንና ፴ ብር ተቀበለ

እሽቅድድም ከተፈጸመ በኋላ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ልዑል አ ወ ተፈሪ መኰንን ባማረ አጀብ ሆነው ወደ ቤተ መንግሥቱ ለመሄድ ተነሡ የተሰበሰበው ሕዝብ ባለአቶሞቢልም ባለከብትም ብዙ ነበረ በዚያን ጊዜ ባለአቶሞቢሉ ሲነዳ አንድ ሰው አስዳጠና የተዳጠው ሰው ጓደኞች ባለ አቶሞቢሉን ደበደቡት ይኸነን ባዩ ጊዜ ክቡር ከንቲባ ነሲቡ ደረሱና አቶሞቢላቸውን አቁሙ ራሳቸው ወርደው ጠቡን አብርደው የዚያም የነዚያም ጥፋት እስቲመረመር ድረስ ብለው በዘበኛ አሲዘዋቸው ቈይተዋል ።

ቀኝ ቀኝህን

ያዲስ አበባ ዘበኞች በከተማው ውስጥ በዋና በዋናው መንገድ እየቆሙ ሰው በአውቶሞቢል እንዳይዳጥና እርስ በርሱ እንዳይጋጭ በማለት ባሌላ በትልልቆች ከተሞች እንደሚደረግ አላፊ አግዳሚው ለእግረኛ በተሰናዳው በመንገዱ ዳር ዳር ቀኝ ቀኙን እየያዘ እንዲሄድ ብዙ ይደክማሉ ግን አንድ አንድ ሰው ግራ እየገባው ያስቸግራቸዋል ። አንድ አንዱም ስለ አለመልመዱ ይዘነጋና ቀኙን ትቶ ወደ ግራው ይመለሳል ግን በየመንገዱ ሰው ሁሉ ለእግረኛ በተሰናዳው መንገድ ቀኝ ቀኙን ይዞ ተጠንቅቆ የዘበኞቹን ፈቃድ እየፈጸመ ቢሄድ ከመጋጨትና በአውቶሞቢል ከመዳጥ ይድናል ።

ስለዚህ ብርሃንና ሰላም ቀኝ ቀኛችሁን እየጠበቃችሁ ተጠንቅቃችሁ እንድትሄዱ ያሳስባችኋል።

ግን ዝናም በዘነመ ጊዜ ባንዳንድ ቦታ የእግረኛው መንገድ ደኅና ሆኖ ስላልተሠራና ዳር ዳሩ ጭቃ ስለሆነ ግድ ግራ ያገባልና የተከበረ ያዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት የጀመረውን ሥራ በቶሎ እንዲፈጽም ተስፋ እናደርጋለን ።

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፩ ብር
የሲዳሞ ቡና	፩	፲ ብር ተኩል
ዝባድ	፩ ወቄት	፫ ብር ተኩል
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳ ብር ተኩል
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፩ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፳ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ከረጃ	፳፱ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ከረጃ	፲፱ ብር ተኩል
አቡጀዲ መነጽር	፩ ከረጃ	፻፺፱ ብር
፡፡ ባለሰይጣን	፡፡	፻፺፩ ብር
፡፡ ባለ ድመት ፡፡		፻፺፱ ብር
፡፡ ባለአህያ	፡፡	፻፳፯ ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል	፡፡	፻፴፫ ብር
ባለ አንበሳ	፡፡	፻፺፫ ብር
ሱካር	፩ ጁኒያ	፳፱ ብር
ቻይ	፩ ነጥር	፩ ብር

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ
አንድ ብር	ሊሬ ፲ ከ፹፩ ሳንቲም
በአንድ ጊኒ	፲ ብር ከ ፳፯
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፯ ብር

ማስታወቂያ ።

ሺብሮሌ አቶሞቢል በኢትዮጵያ ወኪል ።
ሐ ሚ ዜርቦስ ኩምፓንያ ።

Automobiles CHEVROLET

H. M. ZERVOS & C^ie^
REPRESENTANTS
BAS PRIX HAUTE QUALITE

ዓለም ሱቅ ፲፪ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል ። ሙዚቃም በየ ዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል ።

ኦቤርላንድ



ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ አቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባ ኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባተሪ ነው ካምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል «ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው

ወዲያውም የኦቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

A LOUER

COGNAC S. E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሰ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩግቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬዱባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይ ወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሉንዶን ከተማ ነው፥ ደግሞ በኔዮርክ በፊላዴልፊአ በቦስቶን በማድራስ፡በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፡ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፥ ቤንዚን በያይነቱ ቀባት ዘወትር ይገኛል



ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ባርባሬሶ

ኮ ኛ ክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ ።



ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህ በካፕሱሉ ያለ ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በካፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ጉድይርግዙ





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው።በሌላጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ፤ ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አራተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፳፪
4 me ANNÉE № 22

ሐሙስ ግንቦት ፳፫ ቀን ፲፱፻፳ ዓ ም ።
JEUDI 31 MAI 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የንግድና የሥራ የኢትዮጵያ ማኅበር ቤት ምረቃ ።

ግንቦት ፳ ቀን የንግድና የሥራ የኢትዮጵያ ማህበር በተለየ የፊያት አቶሞቢል ወኪል ስለሆነ የንግድ ቤቱን ለማስመረቅ ክቡራን ሚንስትሮችንና መኳንንቶችን ትልልቅ ነጋዴዎችንም ጠርቶ ነበር በዚሁ ቀን ፲ሰዓት ሲሆን ልጅ አስፋ ወሰን የልዑል ተፈሪ መኰንን ልጅ ባማረ አቶሞቢል ሆነው መጡና በተሰናዳላቸው ቦታ በሚንስትሮቹ መካከል ተቀመጡ ።

በሽምፓኝ ጊዜ ክቡር አቶ ብርሃነ ማርቆስ የፖስታና የቴለግራፍ ዋና ዲሬክተር የሚከተለውን ቃል ተናገሩ ።

ክቡራን ሚንስትሮችና መኳንንቶች ።

በዛሬ ቀን እንድትመጡልን የጠራናችሁ አዲሱን የማኅበራችንን ቤት እንድትመርቁልን ስንል ነው ማኅበሩም በኢትዮጵያውያን ገንዘብ ብቻ ሆኖ ከቆመ ፫ዓመት አልፎታል ፤ አሁን በቅርብ ቀን በተለየ በኢትዮጵያ የፊያት ኩባንያ ወኪልነቱን ወሰደ ፤ ይህም በመሆኑ ማለት ፊያትን የሚያህል ታላቅ የኤውሮፓ ኩባንያ ፈቃዱ ሆኖ ውክልናውን በአገራችን ብዙ የኤውሮፓውያን ኩፓንያ እያለ ባንድ ለኢትዮጵያ ማኅበር መስጠቱ ለኩባንያችን ክብሩ ነው።የዚህንም የፊያት ኩባንያ እንደራሴ ለመሆን መቀበላችን ክብር ለማግኘት ብቻ አይደለም ነገር ግን አቶሞቢል ካምዮን የእርሻ መኪና ይኸንንም የመሰለ ነገር ሁሉ ለአገር ልማት እጅግ የሚረዳ መሆኑን ስለ ተረዳነው ነው እንጂ ደግሞም ማኅበራችን አቶሞቢል ብቻ፤ በመሸጥ አይወሰንም ፊያትም ሆነ ሌላም ዓይነት አቶሞቢል ሆነ ሚያድስበት ቤት ያቆማል መኪናቸውን ለማሳደስ የሚያመጡልንን ሰዎች ሁሉ ደስ ለማሰኘት እንደተቻለን መጠን እንጥራለን ለዚሁ ለመኪና ማደሻ የሚያስፈልገውን መሳሪያ ሁሉ አዘናልና ይኸው በቅርብ ቀን ይገባልናል ሥራውንም በመልካም ለማስኬድ የሚችሉ ደኅና ደኅና ሰዎች አሉን የአገሩን ልማት ለመርዳት የሚያስፈልጋችሁን ማነኛውንም ዓይነት የአቶሞቢል ጋሪና ይልቁንም ደግሞ የፊያት ማኅበር በተለየ ሥራው የሆነ የእርሻ መኪና ሁሉ ልናስመጣ የተዘጋጀን ነን ።

ማኅበራችንም እንደዚህ ያለውን መሣርያ ሁሉ በመልካም ሒሳብ ሊሸጥና በሚቻለው ረገድ ሊረዳ የተዘጋጀ ነው ።

መልካም ፈቃዳችሁ ሆኖ ጥሪያችንን ተቀብላችሁ አክብራችሁን ስለ መጣችሁልን እናመሰግናችኋለን፡ ይልቁንም በተለየ ልጅ አስፋ ወሰን ተፈሪንና ክቡር የኢጣልያ ሚንስትርን እናመሰግናለን ።

ከዚህ በኋላ ክቡር ኮማንዳቶሬ ኮራ የኢጣልያን መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ተነሥተው ስለ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ስለ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ስለ ማኅበሩም ቀደምት ሆኖ ለተቀመጠው ስለ ልጅ አሰፋ ወሰን ጤና ብለው ጽዋቸውን አንሥተው መረቁ ።

ንግድና ሥራ ለኢትዮጵያ ዋና የሚያስፈልግ ነገር ነውና ይህ የቆመ ማኅበር ሥራውና ንግዱ እንዲከናወንለት ብርሃንና ሰላም ጥልቅ ምኞቱን ያቀርብለታል ።

የእውነተኛ ቅናት ።

ቅናት ማለት ሁለት ዓይነት ነው ። አንደኛው ቅንዓት ሰው ለኑሮው ብሎ ራሱ የሚጠቀምበትንና ጥቅም የሚገኝበትን ለመፈለግ በተንኰል ጉዳና ስለ ሚደክም ነው ። እውነተኛ ቅንዓት ማለት ግን ለሀገርና ለመንግሥት መቅናት ነው ።(እንደምን ማለት)የብርሃንና ሰላም ተላላኪዎች አገረ ገዦችን ዘወትር በወቀሳ ቃል ሲናገርዋቸውና በሀገራቸው ውስጥ ያለውን ወምበዴና ሽፍታ እንዲያጠፉ ሲመክሩዋቸው ደግሞ ለድ

ቃ ጥቅም የሚሆን ነገር እንዲሰሩ ማሳሰቢያ ጽፈውላቸው ነበረ ቁይፈጽሙት በመቅረታቸው ቅንዓት ይገባል ። እውነተኛ ቅንዓት የሚባል ሰው ለንግድም ሆነ ለቤቱ ጉዳይ ወደ ውጭ አገር ይመላለስ ኑሮ በመንገድ ላይ ያገኘውን አደጋ ለብርሃንና ሰላም ወዳጆች እነዳስታውቅለት ለመነኝ ። ቃሉም እንደዚህ ነው ። መቼም ለሕዝቡ የሚያዝንና የሚቸገር ንጉሥና እግዚአብሔር ናቸው ። ደጉ ንጉሣችን አጼ ምኒልክ ባንዳንድ በታ ትንንሽ ወንዝ እየተገኘ ሕዝባቸው ሊሻገረው የሚቸገር መሆኑን አውቀው እንዳሁኑ ጠቢባን አልበዙምና ከጨረቃ ታላላቅ የጥድ ግንድ እያስመጡ ብዙ መሻገሪያ ድልድይ አሠርተው እስካሁን ኖረ ። አሁን ግን ሕዝቡ ከሰለጠነ ወዲህ ስንኳን በእንጨት የተሠራው በኖራና በአሸዋ የተሠራው ድልድይ ብዙ ጊዜ ሳይቆይ እየፈረሰ እንደገና የታደሰ ሞልቷል ። ይህ በጥድ ግንድ የተሠራ ድልድይ ይህን ያህል ዘመን ኖሮ መሻገሪያው ግንዱ ሳለ በላዩ ላይ የተረበረበው ጠርብ ሲፈርስ አገረ ገዢ የሆነው ሰው ለራሱ ጥቅም ቀረጥ ሆነ ሌላም ነገር ሆነ ሲወስድ የመንገዱ መበላሸት ሳይታየው ቀርቶ ኑሩዋል ። እኔ ግን ሐሳቤን ሁሉ በገረ ገዢው ላይ ጥዬ ደህና ጎዳና መስሎኝ ሥጋ ሜዳ ከሚባል በታ ካለው ድልድይ ደረስሁ ። እርሱስ አፉሮ አልሮ ጠርቡ ተበላሽቶ ኑሮ የኔን መረጋገሚ አስቤ የበቅሎዬን ሳላስብ በቅሎው መንገድ መስሎት ሲሔድ እግሩ ሰቶ ከፈረሰው በታ ላይ አራት እግሩ ገባ ። ወደታች ወደ መሬቱ ሳይደርስ ከላይ ቍንቱ አንቀውና ተንጠለጠለ ። እኔም የመሬቱን መቅረብ አይቼ ከላይ መጫኛውን ፈታሁለት ወደታች ወረደ ። ስልቻውን ከነእህሉ ወደ ማዶ አሻግሬ በቅሎው ደህና መስሎኝ ለማውጣት ወደ ዱሉሉው ውስጥ ብገባ ሆዱን ጠርብ ሠግቶት አንጀት ዕቃው ወጥቶ አገኘሁት ። ከዚህ ወዲያ እረ ብዬ ጮህኹ ። በዚያ ወረዳ ያለ ሰው ሁሉ መጣ ነገሩን ባስታውቃቸው እኛ ምን እናድርግ ለመንገድ ማሰሪያ ገንዘብ አውጡ ይሉናል እንሰጣለን የሚሆነውን አናውቅም ። አገረ ገዢውም ለራሱ እንጂ ለሀገሩና ለመንግሥቱ አስቦ በራሱ ገንዘብ ያሰራውን ድልድይ አላየንም አሉኝ ። እወይ ቀረጥ መክፈሉ ባሰኝ ጊዜ ብዙ ገንዘብ ስለ ሚሰበስቡ ሰዎች የተጻፈ ይሆን ብዬ ምሳሌ ምስ ፳፫ ቁጥር ፲፯ ማር ባገኘህ ጊዜ የሚበቃህን ያህል ብላ ። አጥብቀህ እንዳትጠግበ ትተፋዋለህ ያለው ትዝ አለኝ ። ይህን ነገር በእውቀት መሰላል ብናመላልሰው አገረ ገዢ ከገሩ የሚያገኘውን ጥቅም ሁሉ ለመንግሥት ይልቀቅ ወይም በገሩ ውስጥ የተበላሸውን ጎዳና ይሥራ ያሰኘናል ።

ከዚህ የበለጠ ቅናት ።

መ,ግሥት ለሀገሩ ጥቅም ብሎ ብዙ ያዋጅ ቃል አውጥቷል ። ዋና የሀገር ጥቅም አንዱ ባንዱ ላይ በሐሰት መስክሮ እንዳያጠፋው ስላፈርሳታ ነገር ላገረ ገዢው የጠነከረ ደምብ መስጠቱን ሰምተናል ። ለጕረቤት ያስቸገረ ሰው ነበረ ይላሉ አንድ ቀን ከንድ በታ በሬ ሠርቆ ከጕረቤት ለማስቀመጥ ቢወስደው አታምጣብን ብለው መለሱት ። እርሱም ከቤቱ አግብቶ ሰው ከሚያየው ስፍራ ቢያስቀምጠው ምንም እንስሳ ቢሆን ከወገኑ መለየቱን ያውቃልና ቢጮህበት መላሱን ቆርጦ አውሎ አሳድሮ እንደ ጉዳዩ አደረገው ። ደግሞ እንደ ለመደ ወዳንድ በታ ሔዶ አንዲት ላም ሠረቀ ። እንደበሬው እንዳትጮህበት ምላሱዋን ቆርጦ አውሎ አሳድሮ አረዳት ። በኋላ ግን አፈርሳታ ይውጣ ቢባል አገር የማያውቀው የለምና ከነጓደኞቹ ተይዞ ወዳገረ ገዢው ሔደ ። አገረ ገዢውም በመልካም አቀባበል ተቀብሎ እስከ ስምንት ቀን አስሮ መርምሮ ለመንግሥት እንደ መርዳት እያለ ከነጓደኞቹ ፈቶ ለቀቀው ። እዩ ናችሁ እስኪ ለነዚያ ለምስክሮች ማን ይዘንላቸው በከንቱ ጠፉ ። የበሬውንና የላሚን ነገር በምሳሌ አድርጎ መናገር ነው እንጂ አፍን ከሰሩት በምን ይናገሩዋል ስለ ዚህ ነገር ባገረ ገዢዎች ላይ ጠንክሬ ደምብ ቢደረግ መልካም ስለ መሰለኝ ለበጎቹ ለእስራኤል እረኛ ያሳስባል ።

የብርሃንና ሰላም ተላላኪ ኃ እ በ ተ ዛ

የሰው ልጅ ክብረትና ውርደት ክፉና በጎን ለይቶ በማወቁ ነው ።

የሰው ልጅ በሕይወቱ እስ ደረሰ ዓይኑን ከማየት ጆሮውን ከመስማት በሚያየውና በሚሰማው ነገር ሁሉ እያሰበ ይህ በዚህ ይሻላል ይህ ከዚህ ይበልጣል ከማለት ከቶ ሊመታገድ አይቻልም ነገር ግን እንደ ፍጥረቱ ትልቅነትና ትንሽነት መጠን እየመዘነ የሚፈርደው ፍርድ መልካምና መጥፎ እየሆነ እንኳ ሌላ ሰው ቀርቶ የገዛ ራሱን ያጠፋል እውነት መማር ብዙ ነገር ማወቅ ብዙህ ጊዜ የሰውን ልጅ ወደ መልካም አኗኗር መምራቱ ውልውል የለውም ስለሆነ ግን የሰውን ልጅ እሰው ልጅ ክብር የሚአደርሱ ሶስት ነገሮች ናቸው ከሶስቱ አይነተኛው ዋናው ነገር የተፈጥሮ ባሕርይ እውቀት ቀጥሎ በመካከሉ ከሚኖሩበት አኗኗር የሚመጣ የልምድ እውቀት ሶስተኛው ከዚህ በፊት እንዳልነው በመማር ብዛት የሚገኝ እውቀት ናቸው የሆነ ሆኖ ምንም ከሶስት ታላላቅ ክፍል ከፍተኛ ዝቅተኛ አገርን ብንከፍለው እነኝህ ሶስት ዓይነተኛ ነገሮች እንደ ሸረሪት ድር እርስበራሳቸው የተወሳሰቡ ናቸውና አንዱ ያለ አንዱ ዋጋ ሊአገኙ አይሆንላቸውም ስለዚህ ከፍ ወደ አለ የስልጣኔ ደረጃ ለመድረስ የሚፈልግ ሰው ሁሉ እነኝህ ሰወስት አይነተኛ ነገሮች ማግኘት ያስፈልገዋል ።

ይህን የመሰለ ነገር ስንመረምር አጥብቀን በሰው ልጅ ፍጥረት እንጸጸታለን እንደምንም ቢባል የሰው ልክ ምክንያቱ እንደምን እንደሆነ ሊአውቀው በማይቻለው የተፈጥሮ ባህርይ ሕግ ልጓም ተይዞ ወዳላሰበው ጎዳና የባሕር ላይ ኩበት ይመስል ሊንቀዋለል በዚች ዓለም የሚኖርበት ዘመን ፈጽማ ትንሽነችና በድንገት ሳያስበው ያች አጭር ጊዜው ተደርስና የሰማይ ከፍታ ያጠረው የምድር ስፋት የጠበበው ሐሳቡ በስንዝር መሬት ይወሰንና የትንሽ ትልቁ ፍጥረት ከንቱ ይሆንና ጥርኝ አፈር ሆኖ ይቀራል ። ባለፉት በሁለት ሳምንት ብርሃንና ሰላም ውስጥ ዓይነተኛ ዓይነተኛ ነገሮች አይቼ እየመላለስኩ ከነበብኳቸው በኋላ ስለ ሰወስት ነገሮች ሰውነቴ በጣም አድርጎ አዘነብኝ ። እነኝህም ሶስት ነገሮች ስለ ሀገራችን ስለ ሕዝባችን ስለ መንግሥታችን ጥቅምና ጉዳት ነው ። እንዲህ አገጣጣሚ ሲሰጥ

አበት ያቆየውን ተረት ሲጠቅሱት በጣም ደስ ይላልና አባቶቻችን ሲተርቱ ላይጥም ሞቷ ነው፣ ለድመትም ጨዋታዋ ነው ይላሉ። አሁንም የሀገራችንን የሕዝባችንን የመንግሥታችንን አለዚያም በጭሩ ያኑአኖራችንን ቅጥ ሲመለከቱት ከዚህ በላይ ለጠቀስኩት ተረት ድመትስ ሆኖ ተጫዋቹ ማነው አይጥስ ሆኖ ሙአቹ ማነው ይህን ለይቶ የሚአውቅ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዴት የከበደ ኃዘን ያድርበት ለማያውቀውም እንዴት ከታላቅ ጭንቅ ዳነ የበዕድም ሕዝብ ለሆነ ምን ያህልስ ይህን ከመሰለ ሞኝነት የተላለፈ በመሆኑ ደስታውና ምስጋናው እየበዛ ላገሩ ጥቅም አስተሳሰቡ እየጠነከረ ይሄድ ? ።

ሰው መከበርን ከወደደ መዋረድን መጥላቱ ነው መከበርን ከጠላ ደግሞ መዋረድን መውደዱ መሆኑ ውልውል የለውም ነገር ግን መዋረድንና መከበርን ለይቶ ማወቅ ከልቻለ አእምሮ ያለየ መሆኑ ውልውል የለውም አለዚያም ደግሞ የመከበሪያንም የመዋረጃንም ሥራ እየሠራሁ ልቀመጥ ቢል ለሁለቱም ዓይነተኛ ነገሮች ዋጋ እንዳሳጣ ሁሉ እሱም ቅጥ አጥቶ ከንቱ ሆኖ መቅረቱ ውልውል የለውምና እስከሁን ሲወርድ ሲዋረድ የወጣ የሰው ልጅ አኑአኖር ታሪክ የዚህን ምሥጢር ሊአስረዳን በትክክል ይችላል ።

ብዙ ቤተሰብ ያለው ሰውየ ነበር ይላሉ ሰፊ መሬት ብዙ ገበሬና በሬ እያለው በሬውን ወይፈን ሆኖ ሳለ ሳይገርፍ እየተወ ገበሬውን በጊዜው ማሳረስና ማዘራት እየተወ የገዛ ከብቱን ላሙን የኩል በሬውንም የኩል እየሰጠ መሬቱንም ለርበ እያጋዛ የጎረቤቶቹ ቤት እየገነነ እየሞቀ ሲሄድ የሱ ቤት እየደኸየና እየቀዘቀዘ ሲሄድ እያየ በዚህ እየተቆጨ የጥሩቱን መንገድ እያሰፋ እየሄደ ቆይ ከዛሬ ነገ እበልጣቸው የለምን እያለ ይፎክራል።አንዳንዶቹም ከቤተ ሰቦቹ ምነው ቤታችን አለመደርጀቱ ቤተሰባችንስ አለመከበሩ ከሰው ባንበልጥ ከሰው እኩል አለመሆናችን እየተባባሉ ይወያያሉ ለጎረቤቶቻቸውም ያዋያሉ ከጎረቤቶቻቸው በታች መሆናቸውን ሁሉም እያወቁት በታች መሆን ብቻ አይደለም ከድህነታቸው ብዛት ብሎ ብሎ አን ድቀን እርስታቸውም ከብታቸውም ለጎረቤት አልፎ እነሱም እራሳቸው የሰውግዙ ሆነው መቅረታቸውን ልባቸው እየተረዳው ወደ እንደዚህ ያለመከራ ቦታ የሚገፋቸው በሽታ ምን እንደሆነ እያወቁት ይህ በሽታና መከራ በነሱ ላይ የሌለ ይመስል እንደትልቅ ነገር እንደትልቅ ሥራ እህል ለምን እቋጥኝ ድንጋይ ላይ ተዘርቶ አይበቅልም ጤፍ ሲዘሩ ለምን ገብስ አይበቅልም ሽምብራ ሲዘሩ ለምን ስንዴ አይበቅልም በዝራ ላም በግ አትወልድም ላም ለምን ፍየል አትወልድም አንበሳ ለምን ዶሮ አትወልድም በግ ለምን ዘሆን አትወልድም እያሉ እንደሚጨቃጨቁበት ነገር ይህን በመሳሰለ በከንቱ ነገር ጊዜአቸውን ሲአጠፉ ይውላሉ ። አንበሳን አንበሳ ዘሆንን ዘሆን ላምንም ላም በግንም በግ እንዲወልዳት ይህ የተፈጥሮ ባህርይ ሕግ ነው የተፈጥሮ ባህርይን ሕግ መመርመርና ማወቅ ቀርቶ አንኳቸው ያወቁትን ሕግ መከተል አልቻሉ የቀረውን ምን ያጠያይቅ ነበር ። ደግሞ ይህን ባለትልቅ ቤተሰብ አድህነት ያደረሰ ይህን የመሳሰለ ክንነቱ ነገር አለማወቅ አይደለ እግዚአብሔር ያዘዘውን ሕግ ሠርቶ መብላትን ስለጠላ ነበር ።

ሠርቶ መብላት ሲባል በግዙፉ ለተመለከተው ምስጢሩ አጭር ነው በረቂቁ ለተመለከተው ግን ምስጢሩ ረጋርም ነው አንድ ትልቅ ፈላስፋ ጊዜየን በከንቱ አሳልፍኩት የሚባልበት ቀን ሥራ ሳይሠሩ የዋለበት ቀን አይደለም የማይገበን ሥራ ሲሠሩ የዋለበት ቀን ነው እንጂ አለ ። እንደዚሁም ሁሉ ሠርቶ መብላት ማለት ሁሉም በየክፍሉ በየታዘዘበት ሥራውን በጥንቃቄ በትጋት በንጽሕና በቅን ልቦና መሥራት ነው። ብርሃንና ሰላም እያለፈ እያለፈ ሀገራችን ምድረ በዳ እየሆነች ሕዝባችን እየደኸየ መንግሥታችን ኃይሉ በረድ እያለ የሚየሄድበትን አንዳንድ ያመለክተናል አነሰ ሲሉት ተቀነሰ ይህንኑም ሥራየ ብሎ የሚመለከተው ብዙህ ሰው ይገኝ አይመስለኝም፣ትልቅን ዛፍ በየለቱ የሥሩን አቃፊ አፈር ሲአነሳሱት ሥሩንም አንድ በነድ እያሉ ሲቆርጡት ይህ ዛፍ ቅርንጫፉ እየጠወለገ ቅጠሉ እያነሰ ለዛ እያጣ ወደ መድረቁ ወደ መውደቁ ኃዳል እንጂ ወደ ማበብና መፍራት አለመኃዙ ውልውል የለውም እንደዚሁም ሁሉ ሀገር እንዲለማ ሕዝብ እንዲደረጅ መንግሥት እንዲጠነከር የሕዝብ አኑአኖር ሥልጣኔ በትክክል እያማረ እንዲገባ እንዲከናወን ሁሉም በየክፍሉ ላሠራሩ ሕግ መወሰን አለበት ይህንም ሕግ ዘርዝረን ብንናገረው እጅግ መልካም ነበር ነገር ግን ይልቅ ከኛ ከድሆቹ ጌቶቻችን ይልቁንም ነገሥታቶቹ በትክክል እንዲአውቁት ልባችን እየተረዳው ዝም ብለን ሁላችንም በየበኩላችን እንዳቅማችን ብንረዳ ነው እንጅ የቀረው ምን ይጠቅመናል ብቻ ባጭሩ መልሚአችንም ሆነ መጥፊአችን ለየሥራው ሁሉ ሕግ እያመጡ በመሥራትና በለመሥራት መሆኑን በትክክል ተረድተን መቀመጥ ነው በተረፈ ግን ምቀኛና ጠላት እንጎዳ ይመስል በገዛ ራሳችን የመከራ ዘውድ እያሠራን እንቆቅልሽ የምንጫወት ይመስል የነገር አረቄ እያወጣን ጊዜአችንን በከንቱ ብናሳልፈው ተፈጥረን እንዳልተፈጠሩ መሆን ነው ወዮልን ለኛው ።

ቢነሱ እንዳልኸቸው ።

ስለ አገር ፍቅር ።

ምክር ለክቡራን ወንድሞቼ የኢትዮጵያ ወጣቶች እናንተ ለምታስቡትና ለምትመኙት ማስታወሻ ከብዙ በጥቂቱ የሚከተለውን ቃል አመለክታለሁ ።

እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር ሳያደላ ለሁሉም ትክክል አድርጎ አእምሮ ሰጥቷል ምነው የሰራተኞች እንጀራ ተመመልከት እነሱ እንደምን ሰርተው እንደተከበሩ ማወቅ አይሻል ምን ሰው ከባትና ከናቱ ሲወለድ ምንም የተለየ ነገር ይዞ የሚወለድ የለም እነሱ አውቀው በተማሪ ቤት ታላሳደጉት ወይም ከፍ ታለ በኋላ ጠቀሜታውን ታልተረዳው ከሰው በላይ እንጂ ከሰው በታች መሆኑን እንደማይረዳው የታወቀ ነው ። ግን የኢትዮጵያ መንግሥት ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ስለ አገራቸው ፍቅር ብዙ ነገር ጀምረው ስንፍናችሁን ታስረዱዋችሁ በኋላ ስለምንድነው ስንፍናን ጋሻ አድርጋችሁ የምትኖሩ እኩሎቹም ኢትዮጵያን የመሰለች አገር ለእግርጫማ ለራስ ጥላ የማትፈልግ አገር ጥለው ስራውን ጠባብ እን

ይሆኑ ሳያውቁ ባላሰቡት አገር እድሜያቸው ይጨራረሳል ። ከሞት የተረፉትም ቀጨንቀው በመከራ የሚደርሱበት አጥተው አገሬ በደረሰኩና ለምኜ በበላሁ እያሉ ይኖራሉ ነገር ግን ሁሉንም አገር ታልደረሱትና ታላዩት ክፉው ሚልከም መልከሙ ክፉ ሆኖ ይታያል አሁንም ወንድሞቼ በዚሁ ጥቂት ዕድሜዩ ተጽፎ የማይዘልቅ ብዙ ነገር አይቻለሁና ረዳት ሳትይዙ ውጭ አገር ወጥታችሁ ሕይወታችሁን እንዳታጠፉ ለጥቅማችሁ ፅል አመለከታችኋለሁ ግን መከራን ድሀ ሁነው ታላዩዋት እንደ ሕልም ያለ ነውና አስረጅ ያስፈልጋል ደግሞ ሰዎች ሲሉን እኩሌቶቹስ አገራቸውን ጥለው የሚሄዱ ያገር ሹሞች ቢያጨንቋቸው ነው አሉ እንደዚህ አርገው የሚያስጨንቁ ሹማምች ትርፋቸው ምን ይሆን ? ሰው ተሌለ ከባዶ መሬት ምን ያገኙበታል ። ደሀስ ተሌለ ጌትነታቸው መቸ ይታወቅላቸው ነበር እንደዚህ የሚያደርጉ ሹሞች ጉልበታቸው በደሀ እንደሆነ ባያስተውሉ ይሆናል ። የወጡቱ በጥቂት ቢቆጥሩዋቸው ከነሱ የሚወለዱቱ ብዙ እንደሆኑ ባለማስታወሳቸው እጅግ ያሣዝናል ። ሰዎቹ እንደ ሚናገሩት እውነት እንደሆነ በኢትዮጵያ የስህተት እውቀት ይሠራልና በኢትዮጵያ መንግሥት ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ ብርታት የጨለማ ብርሃን ያስቀረዋል ስል ተስፋ አደርጋለሁ ።

ካሣ አብርሃ ።

ስለ ክቡር ሙሴ ጴጥሮስ ቦያጅያን ዕረፍት ።

ትልቅ ጉዳት ።

በ፲፰፻፺፯ ዓመተ ምሕረት ሙሴ ጴጥሮስ ቦያጅያን ምስር ካለው ከዋናው የአርመን ሊቀ ጳጳሳት ዘንድ ከክቡር ቄስ ቻልኽዲያን ጋር ስለዋና ጉዳይ ወደ ኢትዮጵያ ተልከው መጡ። የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ጃንሆይ ዳግማዊ አፄ ምኒልክ እነዚህን ሁለት እንግዶች በታላቅ የከበሬታ አቀባበል ተቀበሏቸው ። የተላኩበትንም ጉዳይ ከደረሱ በኋላ ሙሴ ጴጥሮስ ቦያጅያን ከክቡር ቄስ ቻልኽዲያን ጋር ወደምስር አገር ተመልሰው እንዳይሔዱና ከዚሁ ከኢትዮጵያ ቀርተው እንዲኖሩ ጃንሆይ ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ከልባቸው ፈቀዱ. ሙሴ ጴጥሮስ ቦያጅያን በፎቶግራፍ ሥራ ታላቅ የዕውቀት ችሎት እንዳላቸው ገምተው በ፲፰፻፺፱ ዓመተ ምሕረት የከቲት ፭ቀን ታላቁን ንጉሠ ነገሥት ጃንሆይ ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ለራሳቸውና ለኢትዮጵያ መንግሥት ዋና ፎቶግራፍ አንሽ እንዲባሉ በማኅተማቸው ሰየሙአቸው ። ሙሴ ጴጥሮስ ቦያጅያን ከዚህ ዘመን ጀምረው ለኢትዮጵያ መንግሥትና የቤተ መንግሥት ለሆኑ ሰዎች ዕፁብ ድንቅ የሚባሉ ረቂቅ ጥበባት ሲአዘጋጁና ሲሠሩ ኖሩ

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ሙሴ ጴጥሮስ ቦያጅያን በፎቶግራፍ ሥራ ታላቅ ችሎት እንዳላቸው ተረድተው በታሕሣሥ ፱ቀን ፲፱፻፲ ዓመተ ምሕረት ታላቁ ንጉሠ ነገሥት ጃንሆይ ዳግማዊ አፄ ምኒልክ የኢትዮጵያ መንግሥት ዋና ፎቶግራፍ አንሽ ብለው የሰየሙአቸውን አረጋግጠው አጸደቁላቸው ። በርግጥ የኢትዮጵያ ንጉሦች ደህንን የተሻለ ምርጫ ለማድረግ ችሎት በማድረጋቸው ብርቅ ድንቅ ይባላል ።

ሙሴ ጴጥሮስ ቦያጅያን ትልቅ የሚያስደንቅ ጥበብ ሥራ ሠራተኛ መሆናቸውን የሚመሰክርላቸው በሐይ ሁለት ዓመት ውስጥ የሠሩአቸውን የነገሥታት ስዕሎች በሙሉ ሰብስበው ማዘጋጀታቸው ይመሠክርላቸዋል እነዚህንም ስዕሎች ባይኔ እንዳየሁአቸው ጭራሽ የሚያስገርሙና የሚያስደንቁ ናቸው ።

በዚሁም ሥራቸው ሙሴ ጴጥሮስ ቦያጅያን የኢትዮጵያን ነገሥታት ክብር እንደገለጹ ይታወቀኛል ከዚሁም ከሥራቸው በተቀር ስለኢትጵያ ልማትና ደህንነት ያስቡ ነበር እንደዚሁ የተሻለውን ልማት በማሰብ ያለአረፍት ዘወትር ሐሳባቸውን አንቅተው ይደክሙ ነበር ይሁን እንጂ ድካማቸው በሚአውቁት የጥበብ ሥራቸው ብቻ አልነበረም ከዚህም ይልቅ ደግሞ ኢትዮጵያን ልክ እንደተወለዱበት አገራቸው አድርገው ከልብ ይወዱት ነበር ።

በዚህ ዓለም ሰው ምንም ብልህ ትልቅ አዋቂ ቢሆን ከሞት አያመልጥምና የኢትዮጵያ መንግሥት ዋና ፎቶግራፍ አንሺ ሙሴ ጴጥሮስ ቦያጅያን በግንቦት ፮ ቀን ፲፱፻፳ ዓመተ ምሕረት ከልጆቻቸውና ከባለቤታቸው መከከል ዓይናቸውን ከደኑት።



ሙሴ ጴጥሮስ ቦያጅያን ።

ይህ የሚአሳዝን ነገር ሲሆን እኔው ራሴ እዚያው ነበርኩና ከዓይኖቻቸው እንባ ተደቅኖ አየሁ ። ይህ የአየሁት እንባ ከባለቤታቸውና ከልጆቻቸው መከከል ተነጥለው ከዚህ ዓለም በመለየታቸው አይደለም ። ነገር ግን ሙሴ ጴጥሮስ ቦያጅያንን ብዙ

ዘመን አብሬአቸው ኑሬአለሁና ይህ እንባቸው ለኢትዮጵያ መንግሥት ባለመከራከርና ፈቃደኛ ታዛዥ በመሆን ብዙ ዘመን አገልግለው ለድካማቸውና ለአገልግሎታቸው ወረታ በማግኛቸው ጊዜ ሳያገኙና ለልጆቻቸው መደገፊያና ለሥራቸው መታሰቢያ የሚሆን ሳያኖሩ ከዚህ ዓለም በመለየታቸው ይመስለናል

ነገር ግን ወየው ። ለጋሲቱ ኢትዮጵያ ለዚሁ አድራጎት ምነው ለጥቂት ዘገየች ይሆን እኒህ የከበሩ የስድስት ልጆች አባት በሕይወታቸው ሳሉ ቢደረግላቸው ኖሮ ደስ ይላቸው ነበር ።

አቤቱ አምላክ ሆይ ቤተ ሰባቸውን ሰብስቦና ደግፎ እንዲጠብቅ አደራ የተሰጠው የበኵር ልጃቸው እንደ ምን ይችለው ይሆን ፡፡

በፍጻሜውም አስከትዬ እናገራለሁ ። ብርቱ ትዕግሥተኛ የሰዎች ምሳሌ የሚሆኑ ሙሴ ጴጥሮስ ቦያጂያን የኢትዮጵያን መንግሥት አክብረው ሲአገለግሉ እንደኖሩ እሳቸውም ከሞቱ በኋላ እንዲከበሩ ታውቋቸው ነው ታላላቅ ሰዎች ምሳሌ የሚሆን የደግ ሥራ ትልልቅ ምልክት እያኖሩ ይሔዳሉ በዚህ ዓለም የሚኖሩም ሰዎች ሰው በሕይወቱ ሳለ ጥቅሙ ሳይታወቃቸው ከመከከላቸው ተነጥሎ ለዘለዓለም ከዚህ ዓለም ሲለያቸው ማጉደሉን አውቀው ሲአከብሩት ይኖራሉ ።

በሕይወትዎ ለደግ ሥራ አምድ የነበሩ ተወዳጅ ሙሴ ጴጥሮስ ቦያጂያን ለዘለዓለም ዓጽምዎ ይለምልም ።

የሙሴ ጴጥሮስ ቦያጅያን ቤተ ሰቦች ስለ ኀዘናቸው መጥተው ያጽናኑአቸውን በወረቀትም እግዚአብሔር ያጥናችሁ ያሉአቸውን ክቡራን ጌቶች ወይዛዝሮች ያመሰግናሉ።

እስቲፋኖ ፓፓዚያን ፡ የኢትዮጵያ መንግሥት የእርሻና የመስኖ ሚኒስቴር የመሐንድሶች ክፍል አለቃ ።

የአማርኛ ማዕርግ ።

በኢትዮጵያ ትምሕርት ቤቶች(ከንድ በተቀር)ከውጭ አገር ቋንቋዎች አንዳንድ ብቻ ስለሚያስተምሩ ከነዚህ ተማሪ ቤቶች ወደ እንግዳ አገር የሚሄዱት ልጆች በደረሱበት ሁሉ ሌላ ቋንቋ ጨምሮ መማር የግድ ሆኖባቸዋል በቋንቋ ምክንያት ግን ጊዜና ገንዘብ ማጥፋት ምንኛ ያሳዝናል እንደዚህ ያለ ነገር የሚደርሰው ለኢትዮጵያውያን ተማሮች ብቻ ነው ። የምሥራቅ አገር ተማሮች በገዛ ቋንቋቸው ወደ ትልልቅ ትምሕርት ቤቶች (ዩኒቤርሲቶች) ለመግባት ይችላሉ ። የምሥራቅ አገር ቋንቋዎችን በዮኒቤርሲቲዎች ከተቀበሉ የንጉሠ ነገሥቱንም አገር ቋንቋ እንዲቀበሉ አይጠረጠርም ።

ወደፊት ወንድሞቼን ወደ ዮኒቤርሲቲዎች ለመግባት እንዳይቸግራቸው ባለፈው ወር ወደ አምስት ዮኒቤርሲቲዎች ጉዳይ ፈጻሚ አማሪኛን ለትምሕርት ቤቶች መግቢያ ፈተና እንዲቀበሉ በጠይቅ ነገሩን በምክር ቤታቸው አቅርበው ከዮኒቤርሲቲዎች ሹማምንት ጋር ከተማከሩ በኋላ ቀጥሎ የተጻፈውን መለሱ ከዛሬ ጀምሮ አማሪኛ በማንቼስቴር ሊቤርፑል ሼፊልድ ሊድስና በርምንገሐም ዮኒቤርሲቲዎች መግቢያ ፈተና የተቀበለ ቋንቋ አድርገን መቀበላችንን እናመለክታለን ።

እንግዲህ ወደ ማናቸውም ዩኒቤርሲቲ ለመግባት ለፈለጉት ተማሮች የትምሕርት ቤቶች ካዲስ አበባ የፈተናውን አኳሆን ጠይቀው ወረቀቶቹን እዚያው አስመጥቶ ለማሠራት ይቻላል ።

ደግሞም ከሎንዶን ዩንቤርሲቲ ጉዳይ ፈጻሚ ጋር ተገናኝቼ ነበርና እርሳቸውም እንደዚህ አሉኝ ባገርህ ባሉት ትልልቆች ትምሕርት ቤቶች ተምረው በመጨረሻ ዓመት ፈተናቸውን ያለፉትን ልጆች የኢትዮጵያ ምስለኔ (በእንግላንድ) እውነተኛ የምስክር ወረቀት መያዛቸውን የመሰከሩላቸው እንደሆን የሎንዶን ዩንቤርሲቲ መግቢያ ፈተና እንዲሠሩ እንፈቅድላቸዋለን ።

እንግዴህ ማንም ተማሪ ትምሕርቱ ተቀናው የእድሚ ነገር አያስቸግርም ትምሕርታቸውን በፈረንሳይ ቋንቋ ለጀመሩት ልጆች እንደዚሁ ያለ ነገር እንዲደረግላቸው በብዙ እመኛለሁ ።

እያና ብሩ (እንግሊዝ አገር) ።

እርዳታ

ግንቦት ፲፰ ቀን ፲፱፻፳ ዓ ም ክቡር ፊታውራሪ ዓምደ ሚካኤል ለሆፒታል ቤተ ሳይዳ ዘተፈሪ መኰንን ፭፻ ብር እርዳታ ሰጡ ። ክቡር ፊታውራሪ ዓምዴ ይህንን ልክ የሌለው እርዳታቸውን ለቤተ ሳይዳ ስለ ሰጡ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ አገራቸውን የሚወዱ ልበ ቀን ቸር መሆናቸውን በርግጥ ያስረዳል ። እንዲሁ የኢትዮጵያ ብልሆችና ባለጸጎች እርዳታቸውን ለሆስፒታልና ለተማሪ ቤት ቢገልጹ ስማቸው በብርሃንና ሰላም ታትሞ በታሪክ መጽሐፍ ተጽፎ ሲታሰብ ይኖራል ።

የእስላሞች በዓል

ግንቦት ፳፩ ቀን የእስላሞች በዓል ስለሆነ እስላሞች ሁሉ ተሰብስበው መድፍ አስተኩሰው ብዙ ፈንጠዝያ አደረጉና በዓላቸውን አክብረው ዋሉ ።

የውጭ አገር ወሬ ።

ምድር በመናወፅ የሆነ አደጋ ፡፡

በግሪክ አገር ቆሮንቶስ የምትባል ከተማ ምድር ከመናወጿዋ የተነሣ እንደ ፈረሰች ከብዙ የውጭ አገር ጋዜጦች ተሰምቷል አእምሮ ጋዜጣ እንደሚጽፈው ብዙ ነገሥታትና ሀብታሞች ሰዎች በደጋው ለተጐዳች ከተማ እርዳታቸውን አድርገዋል ባዲስ አበባ ያሉ ግሪኮችም በዶክቶር ዚርቦስ የግሪክ ጀኔራል ቆንስል አለቃነት በምድር መንቀጥቀጥ አደጋ ለተጐዳች ከተማ እርዳታ መሰብሰብ ጀምረዋል በዚሁም አደጋ ከተማው ፈረሰ እንጂ ብዙ ሰው አልጠፋም ምክንያቱም እየተንቀጠቀ ስለዘገየ ሰዎቹ እየሸሹ አመለጡና ነው ።

ማስታወቂያ ።

ሺብሮሌ አቶሞቢል በኢትዮጵያ ወኪል ።
ሖ ሜ ዜርቦስ ኩምፓንያ ።



Automobiles CHEVROLET

H. M. ZERVOS & Cie
REPRESENTANTS
BAS PRIX HAUTE QUALITE

Odeon

ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል ። ሙዚቃም በየ ዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል ።

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።



አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ አቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባ ኪሎ ሜትር ያስኬደዋል፤ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባተሪ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚሀ አቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል «ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው

ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

A LOUER

COGNAC S.&E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሰ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጠ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጸ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው፣

ደግሞ በኒዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፣በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፣ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪክን የታወቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፣ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ባርባሬሮ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ ።

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህ በካፕሱሉ ያለ ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በካፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ጉድ ያ ር ግዙ





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው ። በሌላጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

አራተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፳፫
4 me ANNÉE № 23

ሐሙስ ግንቦት ፴ ቀን ፤ ፲፱፻፳ ዓ ም ።
JEUDI 7 JUIN 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIÈRE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d'Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

በኢትዮጵያ ከብት ያለ ልክ በማለቁ የኑሮ ችግርና ስለ ሥጋ መወደድ ።

ከትንሽ ቀን ወዲህ በድንገት ሥጋ ከብት ወተትና ቅቤ እጅግ ስለተወደደ የዚህ ዋና ምክንያቱ ምን እንደሆነ ልጠይቃችሁ ፈቀድሁ። ከዚህ ቀደም ባለፈው ሳምንት እንዳስታወቅሁኝ ሁሉ ዛሬም ደግሜ የዚሁ ምክንያቶች ቀጥለው የተጻፉት መሆናቸውን አመለክታለሁ ።

አንደኛ ተላላፊ በሽታ ከብቶችን ያለ ልክ ስለፈጃቸው ነው ሁለተኛ በሀገሩ ውስጥ የሚታረዱትን ከብቶች የሚቆጣጠር የከብት ሐኪም ባለመኖሩ ነው ።

ከብትን የፈጀውን ተላላፊ በሽታ ለማስወገድ የርሻ ሚኒስቴር ለዚሁ ሐሳብ ስለጀመረና ደግሞም የኢጣልን ማኅበሮች ለዚሁ ሥራ ታዝዘው በሐረር አውራጃ ሥራውን በመጀመራቸው እጅግ ደስ ብሎናል እነዚሁን እስከትንሽ ቀን ድረስ ወደዚህ ሃገርም ይመጣሉ ብለን እንጠብቃለን ።

ይኸ አንደኛው ዋና ሥራ ስለተጀመረ ደግሞም እንዲሁ የግድ የሚያስፈልገን ስለሆነ ሁለተኛውን ሥራ የርሻ ሚኒስቴር መፈጸም ቀርቶታል ። ይህን ሥራ ያልሠራ እንደሆን ጉዳቱ ከፊተኛው እኩል ነውና ።

በሃገሩ ስለሚታረዱት ከብቶች መቆጣጠር ።

በሌላው ሃገር ሁሉ እንደሚሠራው እዚህም በኢትዮጵያ በሀገር ውስጥ የሚታረደውን ከብት የከብት ሐኪም እየፈተሸና እየተቆጣጠረ ቀጥሎ የተጻፈውን ደምብ ማቆም ግድ የሚያስፈልግ ነው ያልጠና ከብት እንዳይታረድና የሚታረደው በልክ እንዲሆን ማድረግ በሉካንዳም ሆነ ወይም በየቤቱ የሚታረደውን ከብት አስቀድሞ በከብት ሐኪም እንዲፈተሽ የማትወልድ መሲናና የጠና አሮጌ ከብት ካልሆነ በተቀር ወይፈንና ኮርማ ሙሉ ከብት እንዳይታረድ ማስከልከል ነው የቀረ ማናቸውም ልጅ እግር ከብት እንዳይታረድ ስለዚሁ ምክንያት ብቻ የሃገሩ ከብት ከ፻ ፴ እጅ ጉድሏል ለማለት እችላለሁ ስለዚህ ዛሬ ከብት ስለጠፋ ዋጋውም እጅግ የራቀ ሆነ በገበያም የሚቆመው ከብት የሚበዛው ኮርማና ሙሉ ከብት ብቻ ነው ከበሽታው ይልቅ ከብትን ያስወደደና ያሳነሰ ዋናው ጉዳት የዚህ ምክንያት ነው የሚታረደው ከብት በከብት ሐኪም እየተፈተሸ የሆነ እንደሆነ ግን ቀጥሎ የተጻፈውና ከዚህ በላይ የተጻፈው ጉዳት እንዲቀር የታወቀ ነው ።

ከብት ለግዜው ስላነሰ የሚታረደው ሥጋ በልክ የተወሠነ እንዲሆን የግድ ያስፈልጋል እንዳለፉት ዓመታት ልኩ ቢገመት ብዛቱም ሆነ የዋጋው ልዩነት ከመቶ ፳ እጅ ይሆናል

ዛሬውኑ ይኸን በልክ ማድረግ ካልጀመርን በኋላ ከብትም ሥጋም ይልቁን እየተወደደ በመሄድ ግድ ሆኖ መወሠኑ የማይቀር ነው ግን ይኸ ሳይደረግ ከዘገየ ሥጋንም ቅቤንም ከውጭ አገር ማስመጣት የግድ የሚያስፈልግ ይሆናል ለዓመት በዓል ተብሎ የሚታረደው ከብት ብዛቱ ከሉካንዳው ምንም ያህል ስለማያንስ ይኸንንም በልክ እንዲሆን ማድረግ ነው። ከብትም ሥጋም ቅቤም ማናቸውውም በከብት ምክንያት የሚገኘው ፈጽሞ እንዳይጠፉና የኑሮ ችግር እየባሰ እንዳይሄድ ከዚህ በላይ የተጻፈውን ነገር የርሻ ሚኒስቴር ይተጋበታል በማለት ተስፋ አለን ።

የርሻ ሚኒስቴር የከብት ሐኪም ሚህራን ከይማኪያን ።

ስለ እህል ሥራ በሐረርጌ መሬት ።

መንግሥት ሥራው ሁሉ ተከክሎለት የህል ሥራ እየጐደለ ያወከው ይመስለኛል ። ጥንት በደጉ ንጉሥ በጼ ምኒልክ

መንግሥት በርእሰ ርኵሳን በራስ መኰንን ጊዜ ቀድሞም ባረብ አሥራት ካ፲ ፩ ነበር። ዛሬም ካ፲ ፩ መሆኑ አልቀረምና እስላሞችና ጌታ የሌለው አራሽ ብቻ እውድማ ሳይገባ እያሸ ይበላል ተብሎ ካ፳ት ፩ አሥራት ያፈሳል። ይኸ ቲንሽ ቀር ያሰኛል መንግሥት እቤቱ የተቀመጠውን ይዘው ካላመጡለት እንዴት ይመረምራል ሌብነትስ በባሕሪ ነው እንጂ በእስላምና ባማራነት ደምብ በመግባትና ባለ መግባት መች ይለያያል እላይ እንዳልነው በቀድሞው ዘመን ዘመቻውም ጢት ማታ ነበረ ። ዘመቻ ከበዛ ሞትም ብዙ ነበረና ለዚሁ ለሞተው ሰው ተዝካር ማውጫ ለወላዱዋ መታረሻ ጠዋት ማታ ጉርሻ እየተባለ የህል ወጭ እጅግ ብዙ ነበር ። ቀለብተኛውም እጅግ ብዙ ነበር ። ይኸን ሁሉ ወጭ ችሎ እህሉ ካመት ዓመት ይተላለፍ ነበር ይላሉ ። አሁን በኋለኛው ዘመን እህል እየጎደለ ቀለብ እየታጎለ ተቸግርን እያለ ሰው ያጉመተምታል ። ምናልባት የእህሉ መጉደል አሥራት ካ፲ር ፩ መሆኑ ቀርቶ ካ፳ ፩ ቢሆን ይሆን ኋላ በምን እናመኻኛለን ካ፲ር ፳ ጉደሎ ነውና እንዲሁ ቢሆን ይሆናል ። ምናልባት ጠያቂ ጥንት ወታደሩ እንደዛሬ አልበዛም ነበርና ዛሬ በልዑል ዘመን ያ፬ አህጉር ሠራዊት ተሰብስቦ ቀለብተኛውም መልከኛውም ሁሉም ቀለብ ተሰፋሪ ስለ ሆነ ነው ትለኝ እንደሆነ የመልከኛ ቀለብ መሰፈር አገር ስላነሰው ጨምረውለት እንደሆነ አይታወቅምና በጌቶቹ ፈቃድ የሆነውን መልስ ለመስጠት አልችልም ።

ይሁን እንጂ አሁንም የገባሩን ቁጥር ነግሮ አገር አነሰኝ ይላል እንጂ ባገሩ ላይ ይኸን ያህል ዳውላ ቀለብ እበላለሁ ብሎ ማደሮዬ በቃኝ አይልም አገር ላነሰው አገር እንደማእርጉ ቢጤመርለት እህልን እሚያርስበት ቦታ ለሌለው ወታደር ቢጠቀለልለት መልካም ይመስላል ይሁን እንጂ ከጥንቱ ቀለብተኛ ብዙው ሰው መልከኛ ሆኑዋል ስለሰው ብዛት ቢሆን ጥንት እህሉ ካ፲ር ፩ ሲሰፈር አገሩም አልቀና አራሹም አልበዛ ነበር ያውም የሆነው እርሻ እስላሙም ባካፋ ነበር የሚቆፍረው አማራውም ዘመቻ ስለበዛበት የሐረርጌንም እርሻ ጣዕሙን ስላልተረዳው ከገባሬነት ለወታደርነት ነበር የሚያደላው ዛሬ ግን በደጃ ግርማዊት ንግሥታችንና በልዑለ ልዑላን ጌታችን ጊዜ እርፊት ስለተገኘ ፍቅር ስለተናኘ እስላሙ እስካማራው ልጅግሩ እስከ ሽማግሌው ሁሉ አራሽ ሆኑዋል ያገሩም መቅናት የመታረሱ ምልክት ዱሮ ሚዳው በገመድ ደኑ በሰደድ ነበር የሚታሰለው ዛሬ እንጨቱ በቁጥር ሚዳው በድግር ሆኑዋል እንጨቱ በቁጥር ያልኩት ዱሮ እደር እምናቃጥለውን ዛሬ ላ፩ ድስት ማውጫ እነስ ያላት ሽክም በ፪ መሐለቅ ገዝተን ነው ባነድ መሐለቅ የተገኘ እንደሆነ ይኸስ ንጥቂያ ነው ይባላል ይኸውም ባገር ቤት ነው እንጂ በከተማውስ ሸክሙ ፬ና ፭ መሐለቅ ነው እንግዲህ የእንጨቱ ማለቅ መሬት እንዲቀና እህል እንዲለማ በምንጥር አለቀ እንጂ በማገዶስ ቢሆን ድፍን ሸዋ ባልጨረሰውም ነበር ። ሚዳውም በድግር ያልኩትም ዱሮ በጠፉ ጊዜ አገር ሲደለደል ጉልማሳ ሲታደል የገራዳ ቁጥር እንጂ የገባር የጭሰኛ የረኛ ስሙም አይነሳ ነበር ዛሬ ያገር ድልድል ተዳር ዳር አገሩ ስለቀና ገባር ጭሰኛ እረኛ ተቆጥሮ እንደሚዕርጉ ይሰጣል ምናልባት መልከኛው ከፍቶበት የተሰደደ ፩፩ መንቁጥ የተገኘ እንደሆነ መልከኛው ጌቶቹን ያታልልበታል ለራሱ ይጠቀምበታል አገሬ መንቁጥ ነው እያለ ጌቶቹን እያሳሰበ መሬቱን ለርቦ አራሽ በበርጫ ይተክልና እህሉን እየተካፈለ ያው እርቦ አራሽ ኩዳዱንም ያርስለታል ልኩንም በርጫ ብሎ ተቀብሎታልና እንግዲህ መሬቱ ታረሰ እንጂ ጦም ካላደረ ጠፍም አይባል አሁንስ የእህልን ነገር ሳወጣ ሳወርድ መልከኞችን ማሳጣት መሰለብኝ እስኪ ወደዘከዬ ልመለስ መልከኛን ስፈር ቢሉት ምንም ቢሆን ክርስቲያን ግዝት ይፈራልና በጥንቃቄ ይሰፍራል ወደጎተራ ጫኑ የተባለለት ሰፋሪዎች እንዳያከስሩን ይባልና ፻ውን ፺ ፶ውን ፳፭ ብሎ ያጽፍና ይወስደዋል የጎተራም ሠራተኞች የሰፈርከው እንደምንድነው ብለው ይጠይቁና ስፍሩን እንዳሳያቸው ያንኑ በጽፈት ያስታወቃቸውን ያህል ይቀበሉና ጨረስክ ይሉታል መልከኛም ከላሉን ተቀብሎ ከጋሎቹ ጋራ ደስ ደስ እያለው ይሄዳል እህሉ ግን በገሚስ ቀረ ማለት ነው መልከኛም እውድማ በጥንቃቄ ሰፍሯልና በሱቤት ግዝት አይሰላበትም ፩፩ዱም መልከኛ ለፍቶ ተጠንቅቆ ያወጣውን እህል ወይም ሎሌው ወይም የልመና ጸሐፊ ነውና የጻፈው ያ ጸሐፊ ተጋላ ጋራ ይዋዋልበታል እንግዲህ ጥፋቱ በየዋሁ መልከኛ ነው ፩፩ዶችም መልከኞች ብልሆች ሞልተዋል በትጋት አስወቅተው በጥንቃቄ አስመርተው በምነት አሰፍረው ። እራሳቸው ጽፈው ፊርማቸውን ፈርመው እሚያስገቡም ቢኖሩ ጽፈት እማያውቁት የዋሆቹ ይበዛሉና እንግዲህ የነኝህን ሥራ የነኛ ሥራ ድምጥማጡን ያጠፋዋል ኋላ ምን ይበጃል ያላችሁኝ እንደሆነ ልጅ ከርጣጣ እህል ከዘበጣ እንደሚሉ ሁሉ ምክር ከባላገር ነው ማርከከር እኔም የታየኝን ላመልክትና ልረፈው መልከኛም ጽፈት ባለማወቁ ተቸግሯል ።

ገበሬም ገሚሱ ካ፲ር ፩ ሲያወጣ ገሚሱ እንደ ባዕድ ካ፳ ፩ድ ማውጣቱ ቆርቁሮት የገዛ እህሉን እንደሰው እህል እያድፋፋ መንግሥት የተጎዳ መስሎት እራሱ በረከት እያጣ ሄደ ። ድሀው በረከት ካጣ አስራቱም በጥንቃቄ ካልወጣ እውነትም መንግሥት መጉዳቱ አልቀረም ። እንደኔ ቢሆን መንግሥት አዋጅ አድርጎ ዘካ ካ፲ር ፩ ይሁን ይኸንኑም ዘካ አራሽ የሆነ ሁሉ እሱው እራሱ ይስፈር ። አስቀድሞ ሳይሰፈር ያራሹን ልክ መልከኛና ገራዳ በማላና በግዝት ቆጥሮ ያጽፍ ከዚህ በኋላ ያ የተቆጠረ አራሽ እስላሙ እንዳባቱ ክርስቲያኑም መንግሥት በፈቀደው ማላ እየማለ ይስፈር ። የመንግሥት ጸሐፊ አበጋዝ ደጅ ተቀምጦ በገራዳ ያስታወቁትን ዘካ ዕለቱን በካርኒ ዝርዝር ከድምር እየጻፈ እልሚውን ይስጠው ከዚህ በኋላ ያ ጸሐፊ የታዘዘበትን አገር ጽፎ ሲጨርስ ለጎተራው ጸሐፊ ቢያስገለብጠውና ከርኒው እህሉ ብላቴን ጌታ ጽፈት ቤት ቢቀመጥ መልካም ይመስለኛል ። አሁን ለምሳሌ ፩ ያስቸገረ ሌባ በቤት ያለ እንደሆነ ያንኑ እሚጠረጠርበትን እቃ ጠብቅ ቢሉት እንጣ ያሉኝ እንደሆነ ይታወቅብኛል ሲል በጥንቃቄ ይጠብቃል እንጂ በማን ሊያመኻኝ ይሰርቃል ። ይኸስ አራሽ እምኜሀለሁና አንተው ሰፍረህ አስታውቅ ቢሉት ካ፲ር ፩ ዘካ በዛ ብሎ ያጠፋ አይመስልም ። ይልቅስ ወረት ነውና ላ፩ና ፪ ጊዜ ደስ ደስ እያለው በጥንቃቄ ያወጣል ፥ ከዚያም በኋላ ዝቅ ዝቅ ቢል በፈ

ቃዱ ያወጣውን መንግሥት ረቂቅ ሊያደርግበት ይችላል ። ለዚሁም መልከኛና ገራዳ ታዛቢ መሆናቸው አይቀርም ። ይኸ እማይሆን የሆነ እንደሆነ ደህና ደህና የመንግሥት ሠራተኛ ወጥቶ ያበጋዙም ዳኛና ጸሐፊ አብረው እየተቀጣጠሩ ፳፭ ፡ወታደር እየተከተላቸው መንደሩና ጉድጓዱ ጎተራው እየተፈተሸ ቢሠራ መልካም ነው ለሠራተኛውም እሚገባ መብል ወይም ከመንግሥት አለዚያም ጥንት እንደተለመደ ከባላገሩ ላይ በልክ መፍቀድ ነው ። በፈቃድ ካላገኘ ግን ምሳ የሌለው እረኛ እራት የሌለው ሠራተኛ እረኛውም በዱር ሰራተኛውም በብር ማጥፋታቸው ይቀር አይመስለኝም ።

እንግዲያውማ በትክክል ካሰሩት አለሴት ማጀት አለጸሐፊ መንግሥት መቸ ይደምቃል ከዚህ በኋላ መንግሥት ከፊጥ ደለት በቀር ተላልፎ ቢገኝ የሠራተኛ ተጠባባቂ ብዙ ነውና በዚያም በሠራተኛ ይዘግቡ ወኢየአምሩ ለዘያስተጋብኡ ያለው ቅዱስ ዳዊት ይደርስበታል ። ይኸን ነጭ ወረቀት ሆዴም አልወደደው ፤ብርኒ ይሠራ እንደተለመደው፤ ነጭ ወረቀት ሥራው ከፍና ዝቅ ነው ፤ ለብርኒ የሰጡት አደራው ጥብቅ ነው ፤ ችጋር እንዲጠፋ ጥጋብም እንዳይሆን በብርሃን ተፈሪ በሰላም አኑረን ዘውዲቱ ለስሟ ምንም አትሳሳ ። ተፈሪ ቄስ አባት ሰይሞ እሚያነሳ ። ዘውዲቱ ለስሟ ምንም አትሰጋ ፡ ተፈሪን ወልዳለች እሚቀመጥ ባልጋ ። በብርሃን እግዚአብሔር እዚህ ከደረሰኝ፡ እንግዴህ ተፈሪ በሰላም መልሰኝ ። ለተፈሪ አንድነት እሳሳለታለሁ ። ጠፍቶ ከመለጠ እንዳይገኝ እውቃለሁ ። ተፈሪን ሲፈጥር የላይኛው አምላክ ። ጠባቂ እንዲሆነን አድርጎ ነው መልአክ ። ኢትዮጵያ እንዳትሰጋ እንዲሆናት ምትክ ። ኋላም በዘውዲቱ ዛሬም በምኒልክ ፡ ደንቆሮ ብቻነው ተፈሪ ጠላቱ፤ ብልህ ወንድሙነው ተወልዷል ከቤቱ ። ብልህ እንዴት ይሙት ነገር ሳይሳተው ። በጥርስ እሚሸኘው በጉልበት ቢያቅተው ። ጠቅል ምስጋናውን ስንቱን ላደርሰው ነው ፤ በመዝገብ እንዲጻፍ ለሮፓ መልአክ ነው ። ባገር ውስጥ ያለውን ነገር ባስታውስ ባለውቀት ያቃናልኛል ብዬ ነው እንጂ እኔስ እውቀትና ትምርት እንደሌለኝ ንግግሬም ይመሰክራል ትምርት ባልከፈተው ራሴ ቀለም ባላለሰው ምላሴ ያበረከትኋችሁን የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች እንዳትንቁብኝ ምስጋናችሁን እለምናለሁ ብርሃንና ሰላም ቀልጡ ስለጣፈጠኝ ድግሡ ስላመለጠኝ ፩ብር ዋጋውን ከፍዬ ከማኅበሩ እንድካፈል የብርሃንና ሰላም ዲሬክተር ፈቃድዎ ይሁንልኝ ልውል አዲስ ለከፈቱት ተማሪ ቤት እርዳታ ፪ ብር እንዳቅሚ እረዳለሁ የገንዘቡንም ማግቢያ እንዲያመለክቱኝ ወይም ደሩ እስልክ ቤት እንዳገባ ይሁንልኝ ስል በማክበር አመለክታለሁ ።

መንገሻ አብተ ሥላሴ የወርጅ ጎተራ ጸሐፊ ደሩ።

አንድ ከትልቅ ዛፍ በታች የተደረሰ ጸሎት ።
ስለ ትንሹ እስከ ድሬዳዋ ድረስ ለሄድኩት መንገዴ

ፍሎዘፋዊ ንግግር

ታላቂትዋን ከተማ መራቅ ጀመርሁ የከተማውንም ጫጫታ ሸሸሁ ። መጥፎውን ዓየርና የገማውን ነፋስ የማይቻለውን ተንኰልና እስቸጋሪውን ሕይወት ወደ ኋላዬ ትቼአቸው በፈጣኑ ባቡር ተጓዝሁ ።

ጥቂት እንደተጓዝን ወደ ኋላዬ ዞር ብዬ ብመለከት የከተማውን ጠባቂ ትልቁን የቅዱስ ጊዮርጊስን ቤተ ክርስቲያን ከከተማው መካከል ከፍ ብሎ ከከተማ የሚኖረውን ሕዝበ ክርስቲያን የሚባርክበትን መስቀል እኔም ይህን ሁሉ ትቼ ስለሄድሁ ዕዳ ቀለለኝ ብዬ ነበረ ድንገት ዓይኔን ወደ ባለቤቴ ጣል ባደርግ ዓይን ላይን ማጥም አልኔ የሚገላበጠው የሐሳብ ሕማሜ ተነሳብኝ በልቤም አልኩ አዬ አንቺ መታመኛ ሴት የሳምባሽን መተንፈሻ ክፈችና መልካሙን አየር አሽትቺ ዋዋ ይኸ ሳምባሽ ' ' ' ' ' ' ' ' ይቅርታሽን እንድታደርጊልኝ ሺጊዜ እለምናለሁ ። አየ ጉድ ይህን ሁሉ ያመጣው የወታደርነት እብደት ነው የጥፋቴ ትርፍ ነው ። በሰው ሕይወት ውስጥ ጥፋት አደጋ ደግ ነው የለ ማው ይሁን እንጂ እርስዋ ከኔ ጋር የምትጨነቀው በአደጋ ምክንያት አይደለም ምን መሆኔ ነው አሁንስ እእምሮዬን አጣሁ እብድ ነኝ ? ይህን በሆዴ እያሰብሁ የእብደት ሳቅ ሳቅሁ ደግሞ አልሁ አይደለም ማናቸውም ሰው አደጋ ሳያገኘው ከትልቅ ማዕርግ አይደርስም አደጋን የማያውቅ ሰው አይረበም ።

ሚዳውን አቋርጠን ትንንሽ የመንደሮች መንገዶች እየሁ እዬ መልከሞች የመንደር መንገዶች እናንተንና ሕዝባችሁን እባርካለሁ ናናንተ ሕዝብ ከምላክ ጋራ ሲሠራ ይውላል ከናንተ ዘንድ የደስታ እጅ መንሳት አለ ደጎችና ክፎችን የምትመግቡ እናንተ ናችሁ ይሁን ካልኩ በኋላ ቀና ብዬ ብመለከት አዳማ ከሚባለው የባቡር ማረፊያ ጣቢያ ደርሰናል ባቡሩም ከዚያ እኩል ሰዓት ያህል ያርፋል አሉኝ ። ደግሞ ከዚያም የሰው ጫጫታ ንግድ መሸጥ መለወጥ ለሕይወት ደስ የሚያኝ እኳኋን ሁሉ አለ ግን በዚሁ ስፍራ አንድ ትልቅ ምሥጢር ያለው ዛፍ አለ ከብዙ ዘመን ጀምሮ የሆነውን ያገሩን ታሪክ ያውቃል ። እኔም አልኩት አዋቂ ነህ አዋቂ ነህ እኔ አንድ ድኃ መንገደኛ ነኝ ከጥላህ በታች ጥቂት ጊዜ እንዳርፍ ፍቀድልኝ ደግሞ ታላቁ ዛፍ ሆይ የምነግርህን ስማኝ ። እኔም ትንሽ ቁጥቋጦ ትንሽ ዛፍ ነበርሁ ። መሬቴ ይመግበኛና ጥዋትና ማታ ከፍ ከፍ እያልሁ አድግ ነበር ጥላም ነበረኝ መንገደኞችም ከበታቼ በጥላዬ ውስጥ ያርፉ ነበሩ አንድ ሰይጣን ዓውሎ ነፋስ የኔን የወገኖቼን ሥር ነቀለው ። አሁን ስፌ ስለተነቀለ በዓለም መንገዶች መካከል ጠፍቼ እኖራለሁ እንደ ደረቅ ሳር ነፋስ እንደሚወስደውና ወደ አንድ ጐን እንደሚጥለው እኔም እንዲሁ ነኝ ጥላዬም በመሬት ላይ ይንከባለላል ደመና በሰማይ እንደሚንከራተት እኔም እንዲሁ እንከራተታለሁ ። ከእግሬ በታች የምረግጠው መሬት የለኝም ።ከራሴም በላይ ጣራ የለኝም ። መልካሙ ዛፍ ሆይ ተቀበለኝ ቤት ሁነኝ እድሌ ከጥላህ በታች እስኪያባርረኝ ድረስ ከጥላህ ውስጥ ጥቂት እረፍት ይበቃኛል የደከሙትን ሕዋሳቴን አሳርፍበት ዘንድ እርግ አንተ ዝግባ ነህን የቅጠሎችህ ሽታ ከብዙ በሽታ ያድናል የሕክምና ብልሃት ከንዳንተ ያለው ቅጠላ ቅጠል መድኃኒቱን አዘጋጅቷል ። ይህን ስል ባቡር ተነሣ።

ሐዋሽ ደረስን

ሰማዩ ድፍርስ ነው በሩቁ አንዲት ኮከብ በሰማይ ወደ መሬት ስትወድቅ አየሁ ። አየሩ ጥላ ያለውና ጭጋግ የመላው ነው ጸጥታና ዝምታ ከዚያ ነበረ ። ጊዜው ለጉጉት ብቻ የተመቸ ደስ የሚያሰኝ ነበር በዚያ ጊዜ የእረኞች ዋሽንት ድምጽ እንዴት ያምራል

ፍጥረት ሁሉ በዝምታ ውስጥ ነው ሁሉም ያሰባል
የጸሎት ጊዜ ነው
ዝምታና ጸጥታ በዚያ ነግሠዋል
መልአኬ ሆይ እስኪጸባ ልተኛ ልረፍ አትቀስቅሰኝ እኔ እንደ ድኃ መንገደኛ ነኝና ።
በእልፍኜ ውስጥ ነኝን ?

አወይ ሚስቴና አራቱ ልጆቼ እንደ መልአክዊ መኝታ ተኝተዋል እኔም በመስኮት ፊት ለፊት ሆኜ አየሩንና ሰማዩን እመለከት ነበርሁ ሰደጃና እዚህ አቤት ከተኙት ማናቸው ያምሩ ይሆን እልኩና ለመምረጥ ሞከርሁ ። እነዚህም በዓለም ውስጥ ፍጥረቶች ናቸው እስቲ ልይ እልኩና ባለመተገብ ተንደርድሬ የልጆቼን ከንፈርና የተወደደችዋን የናታቸውን ከንፈር ሳምሁ ።

ስሜያቸው ከተመለስሁ በኋላ ኃይለኛ ነፋስ ነፈሰ ያለሁበት ቤት መስኮቱ መዝጊያው ተንቀጠቀጠ እኔም ወደ ነፋሱ ዞር እልኩና ስለምን ታውከኛለህ ለምንስ ከልጆቼና ከናታቸው ጋር ያለንን መልአካዊ ፍቅር ማቀዝቀዝ ትፈልጋለህ መከራችንን እስታውሰህ ነውን በዚህ በአስማተኛ ድምጽህ የምታስፈራራን ጭንቃችንን አለምኸውን ወይስ የፈሰሰውን ደማችንን አሸተትከውን

አሁን ምን አለ የተቃጠለ ነገር አለን ንገረኝ እባክህ ዛሬ ደግሞ አደጋ እንዳለ ሚስቴንና ልጆቼን እንድሸሽግ ደግሞ ፍርሃትና ጭንቀት አገኘን ዛሬም ሽሽት ነውን አይደለም ተወነ እባክህ አታይምን የእግዚአብሔር መልአክ ሰይፉን ይዞ በተኙት ልጆቼና በሚስቴ ላይ ቆሟል ።

እረግ ይህን ሁሉ የማየው በህልሜ ኖሯል ዛሬ ግንቦት ፳፰ቀን የአርመን ነጻነት ቀን ነው ። ዛሬ በዲስ አበባ በአርመኖች ክሉብ ጸሎት ለተያዘ ነው ። እንዲህ የሚያደርገኝ የተወደድህ ኃይለኛው ነፋስ ሆይ አንተ ጥሩና ደግ ነህ ለክ አንተ አዲስ አበባ የተጸለየውን ጸሎት ለኔ ማምጣት ነው ። በውኔ ዛሬ እዚህ ከለነበት ስፍራ በሁለተኛዪቱ አገራችን በኢትዮጵያ ምንም የሚያስፈራ ነገር የለም በኢትዮጵያ የሐበሾች ትውልድ አይዳ የምትባለዋ ንግሥት ዘር ናቸው አባትዋም የኢትዮጵያ ንጉሥ አምስሮስ የሚባለው ነው እርሱም ላገሩ ነጻነት በግብጽ ንጉሥ በፈርዖን ጊዜ አያሌ ጦርነት ከግብጾች ጋራ ይዋጋ ነበረ ።

ከነቃሁ በኋላ ፶ደቂቃ ያህል በጭለማው ውስጥ ዝም እልኩኝ ወዲያው የዕጣን ሽታ ሸቶኝ እንዴ ከወዴት ነው ስል ቀጥሎ የጽና ድምጽ ይሰማኝ ጀመር ወዲያው ደግሞ የእልፍኜ መዝጊያ ቆሎ ቆሎ ይመታ ጀመር ። እባካችሁ እኔ እንድ ድኃ መንገደኛ ነኝ ልጆቼንና ባለቤቴን ይገር በዚች ጭለማ ቤት ውስጥ ተኝተናል አታውኩኝ ። ይህን ስል አንድ ድምጽ እንዲህ ሲል ሰማሁ ። ክፈት ክፈት ኢትዮጵያ ሰላምና ጸጥታን ልክላችኋለችና ይገር መጥቻለሁ ። የተወደዱ ቄስ ሚክኤል ኖረዋልን ብዬ ከልጋዬ ዘልዬ በፍጥነት ከፈትሁላቸው ። በከፈትሁላቸውም ግዜ ክቡር ቄስ የቤተ ክህነት ልብሳቸውን ለብሰው ጽና ይዘው እኔን ሚስቴን ልጆቼንም ባረኩ ።

ለመሄድ በተነሱ ግዜ ክቡር ሆይ ምን ልስጥዎት ብላቸው ኢየሱስ ክርስቶስ ከጠጣው ከቀዩ ወይን በተቀር ሌላ አልሻም አሉኝና ወዲያው ተሰወሩኝ ልብ ባደርግ ይህም ደግሞ በሕልሜ ነው።በሁላ ነገሩን አወቅሁ ይህ ኃይለኛው ነፋስና ቄሱ የመጡት የአርመንን ነጻነት ሊያስታውሱኝ ነው ግን ይህን ባስታወስሁ ግዜ ያለፈውን ፍርሃትና አደጋ ሁሉ የግድ ማሰብ አለብኝ ።

ዛፎች እሾህ እንዲት ጠብታ ውኃም መሬት አላቸው ። ታናናሽ ወፎችም በዛፎች ላይ ጎጆች አሉዋቸው ጉንዳንና ትንንሽ ነፍሳት እንኳ በመሬት ውስጥ መኖሪያ ቤቶች አሉዋቸው ።

ግን እኛ ያልታደልን አርመኖች ዝናብ ዘንቦ ከተራራ ላይ የሚፈሰው ኃይለኛ ጐርፍ በፊቱ ያገኘውን እንደሚጠርግ እንዲሁ ከገራችን ተነቅለን እንደ ትቢያ በመላው ዓለም ተናኝተን ቀረን ።

አየ ጉድ የዓለም ፖለቲካ እንዴት ከፉና የሚያስጠላ ነው

እንዲሁም እንዳንል ፖለቲካ የዓለም ሥልጣኔ ያፈራው አይደለምን አዬ እንዴት ያለ ውርደት ነው ።

ትልቁ ዛፍ ።

አዬ መልከሙ ዛፍ ።

ያገሬን ዛፍ ትመስላለህ እባክህ እቀፈኝና አወዛውዘኝ በመንፈሴ ውስጥ አውሎ ነፋስ አለና በሰውነቴም ውስጥ ድንጋይና ፍርሃት አለ ታላቁ ዛፍ ሆይ ስማኝ ልንገርህ ልቤ ሙሉ ነው እኔም ትንሽ ቦታ ስሬን የምተክልበት እፈልጋለሁ እንዳንተው እንድ ዛፍ መሆን እፈልጋለሁ የቅርንጫፎቹ ጥላ ላገራቸው ለሞቱት ላገሬ ሰዎች በመቃብራቸው እንዲያጠሉ እፈቅዳለሁ ብዬ የሚታመኑብሽ አገሬ ሆይ አንቺን ሳልጠግብሽ ተለይቸሽ ቀረሁ ።

ምን ክፉ ያገር መለየት ነው ።

አገሩን የማይወድ ሰው ከሰውነት የወጣ አእምሮ ያጣ ነው ።

ካፒቴን ባቢኪያን።

ሥራ መውደድ ጥቅምና ክብረትን ያመጣል ።

ሰው ሁሉ ሊሠራ የተገባው ነው ። እግዚአብሔር እንኳን አዳምን ወደ መሬት እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ ትሠራለህ ብሎ አለው ከእንግዲህ ወዲህ ሃብታሞችም ቢሆኑ ወይም ድሆች ሁሉንም የሚጠቅምና የሚያበረታ ሥራ ነው ።

ስንፍና የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መተላለፍ ነው ። እግዚአብሔር በጸጋው የሰጠንን እንድ ሰንቀ የከበረ ጊዜያችንን በማይረባ አንድ ሥራ ሳንሠራበት በከንቱ የምናሳልፈውን ጊዜ እያሰብን እያስተዋልን እንቀመጥ ።

እግዚአብሔር አምላካችን እንዲህ ያለ ያማረና የተዋበ ጊዜ እያላችሁ ለውዲቱ ለለምለሟ ለሃገራችሁ ለኢትዮጵያ ምን የረባና የስማችሁ ማስነሻ መልካም ሥራ ሠራችሁላት ብሎ የጠየቀን እንደሆን ምን ብለን እንመልስ ይሆን ።

እሱም ባለቤቱ የሚፈርድብን ደግሞ ባደረግነው ክፉ ሥራ ብቻ አይደለም ልናደርገው ልንሠራው እየተቻለን በማ

ናደርገውና በማንሠራው በጐ ሥራ ይፈርድብናል እንጂ ሌሎች ቀን ከሌት ላባቸውን ጠርገው በለፉበት ያለ ሃሳብ እየበሉና እየጠጡ ጥቅም ያለው አንድ መልካም ሥራ ሳይሰሩ ። የእገሌ ተወላጆች የእገሌ ዘር ነን እያሉ ቀማኛ ወንበዴ አገር አጥፊ ሆነው የሚኖሩ ብዙች ናቸውና ተቀነዩ ለእግዚአብሔር በፍርሃት ወተኃሠዩ ሎቱ በረዓድ አጽንዕዋ ለጥበብ ከመ ኢይኅመዕ እግዚአብሔር ያለውን ክቡር ዳዊት መዝሙር ፪ ቁጥር ፲፩ ፲፪ እናስብምን ደግሞስ እናስተውልምን ።

እንስሶች እንኳን ሳይቀሩ እስከ ጊዜ ሞታቸው ድረስ ያገለግሉናል እኛም ደግሞ ከአምላክ እውቀትን ማስተዋልን ማሰብን ያህል የሚመስል ትልቅ ስጦታ የተቀበልን ሰዎች እንዴት ለመንግሥታችንና ለውዲቱ ለለምለሚ ለሃገራችን ማገልገል ያቅተን (ያስደንቃል ለተመለከተው) ጥቅም የሚሆን ለስማችን ማስጠርያ አንድ መልክም ሥራ ሳንሠራ ከዚህ ዓለም ብንሰናበት እጅግ አድርጐ የሚያሳዝን የሚያስለቅስ ነው ። ምንም እንኳን አሁን ለጊዜው እጅግ ክቡር መሆኑን ባናስተውልና ባንመለከት እያለቀስን የምናስተውልበትና የምንመለከትበት ጊዜ ይመጣብናል ። ለዚህ ሁሉ ሳይቃጠል በቅጠል እንደሚሉት (አሁን ማድረግ ነው) ቁጭ ብለን በከንቱ በዋዛና በፌዝ በጨዋታ የምናሳልፈው ጊዜ በጣም የጠፋብን ቀን ነው በከንቱ ያሳለፍነው ጊዜያችን ተመልሶ አይመጣልንም በፍርድ ቀንግን እንደሚቀጣ ዳኛ ሆኖ ይቈየናል ለመንግሥት አገልግሎትና ለቤተ ሰዎቻችን ለባልንጀሮቻችን ለለምለሚ ለሃገራችን ጥቅም ብለን በፍቅርና በእምነት እየሠራን የምንውልበት ቀን ግን ደሞዝናቀለብ ይዞ በመጨረሻ ይቆየናል ።(መልክም ነገር) ሥራ መስራት የሚወድ ሰው ደስታንና ኃይልን ይዞ ይመጣል ሃኬትና ስንፍና ግን ገላን ያደነዝዛል መጽሐፈ መ ም ፯ ቁ ፲፯።

ሥራ መስራት የሚያከብርና የሚያሳድግ ነው እንጂ የሚያሳፍርና የሚያሳንስ የሚያዋርድ አይደለም ሳይጸየፍ ለሥራ የሚጣጣር ሰው ከፍ እያለ እየከበረ ወደ ማእረግ በታ ይደርሳል እንጂ አይደኸየም አያሳፍርም ደግሞ ለቤታቸውና ለንብረታቸው ለሃገራቸው ሃብትን ያመጣሉ (ወይ ግሩም እንደ ዚህ እያለ ምን ወደበረሃ ያስፈልጋል) እናታችን ለምለሚ ኢትዮጵያ ለራስዋ ሃብታም አገር ናት በመሬትም ሆነ በሌላም በ ያይነቱ ለሥራ የሚደክምላት ብታገኝ በእጥፍ አድርጋ ለግሳ ትመልስልናለች እንጂ አታሳፍረንም እኛ ልጆችዋ ተግተን ብንማርላትና ብንሠራላት ቶሎ ብላ ልክ እንደ ጐረቤቶቻችን በሆነች ነበር እንዴት እንናቃት መቸም ያለፈው ጊዜያችን እንዳይመለስ አውቀን ለወደፊቱ ለሚመጣው ከአምላክና ከመንግሥታችን ፈቃድ ጋር እርስ በራሳችን እየተበማማን እንደ አክሊል በራሳችን ላይ የደፋነውን ምቀኝነትና ትዕቢትን ተንከልን ኩራትን ድንቁርናን ከራሳችን ላይ አውርደን እንጣለው መክብብም ፪ ቁ ፲፫ ኃይሉ ገብረ ማርያም

ስለ ፈረንሳዊ መንግሥት ሚኒስትር መግባት ።

ግንቦት ፳፰ ቀን ክቡር ሙሴ ደ ሬፌ የፈረንሳዊ መንግሥት ሚኒስትር እቤተ መንግሥት ገብተው ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ከልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ተገናኙና ስለ ከበሬታ መድፍ ተተኰሰላቸው ።

ሹመት ።

ግንቦት ፳፬ ቀን ግራዝማች ለጥ ይበሉ ቀኛዝማች ተብለው የቀኛዝማች ዓለማየሁ የነበረውን ተሾሙ ።

ግራዝማች ሺፋው ቀኛዝማች ተብለው የርስት ሹም ሆኑ

ግራዝማች ዘውዴ አረጋይ የግራዝማች ለጥይበሉ የነበረውን እልፍኝ አስከልካይነት ተሾሙ። ልጅ ግርማ ማሞ ግራዝማች ተብለው የዘበኛ ዲረክተርነትን ተሾሙ ።

ባሻ ረታ የልዕልት ወይዘሮ መነን ጓዳ በጅሮንድነት ተሾሙ

ግራዝማች አባ ንጋት የወህኒ ቤት አለቅነት ተሾሙ ።

ግንቦት ፳፯ ቀን ክቡር ልጅ ሥዩም ወልደ ያሬድ ግራዝማች ተብለው ኘእ ምስለኔነት ተሾሙ ።

ግራዝማች ዘውዴ ተክለ ማርያም ቀኛዝማች ተብለው በልዕልት ወይዘሮ መነን ሠራዊት ጠቅላይ እንደራሴ ተሾሙ ።

ባላምባራስ ዘለቀ በፈረስ ቤት ሻንበልነት ተሾሙ ።

ብርሃንና ሰላም አዲስ ለተሾሙትና ለተሸለሙ ወዳጆቹ እንኳን ደስ አላችሁ እያለ መልካም ምኞቱን ያቀርባል ።

ሠርግ

ግንቦት ፳፫ቀን ክቡር ደጃዝማች ግርማይ መንገሻ የንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን የልጅ ልጅ የራስ መስፍንን ልጅ አግብተው የሠርጋቸው ደስታ ደምቆላቸው ዋለ ፡ ብርሃንና ሰላም ለክቡር ደጃዝማች ግርማይና ለክብርት ባለቤታቸው መጋባታቸውን እግዚአብሔር እንዲባርክላቸው ምኞቱን ያቀርባል ፡

የአዲስ አበባ ገበያ ።

የቀንድ ከብት	
የሚታረድ በሬ ዋጋ	፺ ብር
የእርሻ በሬ	፴፭ ብር
ያሩሲ ድልብ በሬ ፺፭-፻	ብር
የምትረባ ላም	፵፭ ብር
መሲና ላም	፵፱ ብር
የምትረባ በግ	፫ ብር
መሲና በግ	፭ ብር
ሙክት በግ	፲፫ ብር
የምትረባ ፍየል	፬ ብር
መሲና ፍየል	፯ ብር
ሙክት ፍየል	፲ ብር
የጋማ ከብት	
ሰንጋ ፈረስ ዋጋው	፳፭ ብር
ባዝራ ፈረስ	፳-፳፭ ብር
አጋሰስ ፈረስ	፳፯ ብር
የከርቻ በቅሎ	፻፶ ብር
ስናር ዓይነት በቅሎ፻፹	ብር
አጋሰስ በቅሎ	፷ ብር
የምትረባ አህያ	፲፯ ብር
የጭነት አህያ	፳፯ ብር
ዶሮ ዋጋው	ከሩብ-አላድ
ዕንቍላል ሠላሳ	፩ብር
የእህል ገበያ	
ስንዴ ፩ ጆኒያ	፲፪ ብር
ገብስ	፱ ብር
ጤፍ	፲፫ ብር
ሽንብራ	፲ ብር

A LOUER

COGNAC S. E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK METAXA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኀይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኀይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው፣

ደግሞ በኒዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፣በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፣ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፣ ቤንዚን በያይነቱ ቀባት ዘወትር ይገኛል



ማስታወቂያ ።

ሺብሮሌ አቶሞቢል በኢትዮጵያ ወኪሏ ፤
ሐ ሜ ዜርቦስ ኩምፓንያ ።

Automobiles CHEVROLET

H. M. ZERVOS & C^ie^
REPRESENTANTS
BAS PRIX HAUTE QUALITE

Odeon

ዓለም ሁሉ ፲፪ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል ። ሙዚቃም በየ ዓይነቱ እንደ ሴንፎር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል ።

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለሙሽ ኦቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።



አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባ ኪሎ ሜትር ያስኬደዋልንወዲያም ባለማግኜቶና ባለባተሪ ነው ካምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል «ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው

ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ ።



ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህ በካፕሱሉ ያለ ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በካፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ጉድይር ግዙ





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ፡፡ በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው።በሌላጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ፤ ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አራተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፳፬
4 me ANNÉE № 24

ሐሙስ ሰኔ ፯ ቀን ፤ ፲፱፻፳ ዓ ም ።
JEUDI 14 JUIN 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ
ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት
Son Altesse Impériale Teferi Makonnen , Héritier du trône d' Ethiopie , profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix , a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ስፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የሥልጣኔን ጕዳና ስለመቀዳደም ።

ይህ ዓለም የተፈጠረው በጎ ሥራ ልንሠራበት እንጅ ለክፉ ሥራ አለመሆኑን ሁላችሁም ታውቃላችሁ ።

በብርሃንና ሰላም ጐዳና የሚመላለሱ ብዙ ሰዎች እያገኘሁ እነጋገራቸው ሁሉ ለሀገራቸውና ለመንግሥታቸው ጥቅም ስለሆነ እግዚአብሔር በቸርነቱ ለልዑል አልጋ ወራሻችን ብዙኅ እድሜ እንዲሰጥልን ። ደግሞ የወዳጆቻችን ሐሳብ ሁሉ እንዲፈጸም እመኛለሁ ። እኔም በተቻለኝ ጥቅም የጻፍኩትን ቃል አይታችሁ የተሳተ ቃል ብታገኙበት እንድታርሙት እለምናችኋለሁ ።

አንድ ቀን ከወዳጄ ከብርሃንና ሰላም ጋራ ሁኜ በ፬ኛው ዓመት በ፲፮ ቊጥር በ፻፳፫ ገጽ በ፫ክፍል አቶ ዮሐንስ የጻፈውን ቃል እየተመለከትሁ ሳዝን ከምሥራቅ አገር የመጣ ሰው ወደኔ ቀርቦ ምን ታደርጋለህ ብሎ ጠየቀኝ የአድመኞችና የተንኰለኞች ሥራ ነገር ከዚህ ተጽፎ አግኝቼ ከብርሃንና ሰላም ጋራ እንጫወታለን አልኩት ። እነሱ ናቸውን? እነሱማ እለ ይመጽኡ በልብሰ አባግዕ ፤ ወእንተ ውስጠሙሰ ተኵላ ወመሰጥ ይላቸው የለምን ይልቁን የሚበዙት በሥራ ፊቶች ውስጥ ነበረ ። አሁንማ በሥራ ላይ የተቀመጡ ሰዎች የያዙትን ሥራ መሥራት ሲያቅታቸው ጊዜ እገሌ ካለ እንዴት ሥራ እንሠራለን እያሉ በየወገናቸው የምቀኝነት መርዛቸውን ይነዛሉ ። ግን የሚያሳዝነው የነዚህን ሰዎች ሥራ አዋቂና ብልሃተኛ ሰው አግኝቶ በጠየቃቸው ጊዜ ሥራቸውን ትተው የከንቱ ውዳሴ ወሬ ያወሩት ሥራ ይይዝላቸው ይሆንን ። መልስማ መቼም አያገኙምና ። ለነሱም ምክር ሠናይት ለኵሉ ዘይገብራ የተባለችውን ። ደግሞ ጥበብ ትኄይስ እምኵሉ መዛግብት ያለውን ንባብ ቢመለከቱ መልካም ይመስለኛል ብሎ የሐሳባቸውን ነገር ቢያጫውተኝ ። ወንድሜ ሆይ ይህስ ነገር የበረታው ለሀገራችንና ለመንግሥታችን ጥቅም ብለው በሚደክሙት ላይ ነው ። ግን እነዚሁ ተንኰለኞች አሁን በቅርብ ጊዜ ሳይጠፉ አይቀርም ይመስለኛል ። ወዳጄ ሆይ ከሆነማ የሚሻለው ያንዱን እውቀት ከመንቀፍ ያነን መሠረት አድርጎ በላዩ የእውቀት ጐዳና እየጨመሩ ለሀገርና ለመንግሥት ረዳት መሆን መልካም ነበር አልኩት ከሆነማ ደግ ነበር ከተንኰል በቀር ማን ቢያስብ ለዚህም እንደምሳሌ አድርጌ አንድ ነገር ልንገርህ ሰው ቤቱን በኰረትና በድንጋይ ብቻ ለመስራት አስቦ ሠራው ። ያንጊዜውን ፈረሰ በኋላ ግን ወደብልሃተኛ ዘንድ ሔዶ ቢጠይቅ ኖራና አሸዋውን በእውቀት ወንፊት ለይተህ በዚያ ሥራው ይጠንክራል ነገር ግን እንደ ነገርኩህ ሳታደርግ ቀርተህ ወስኩን እየጨመርህ ብትሠራው ግምቡ ይነቃል ። እንደገናም ልትሰራ ያሳስብሃል ብሎ ተናገረው ባለኝ ጊዜ ንግግሩ በልቡናዬ አድሮ ለዚህ ነገር መልሱን የምሰጥህ ከብልሃተኞች አባት ጠይቄ ነው ብለው ይህስ ይሁን የሰውን ስም ከንቱ ማድረግ እንጅ በእግዚአብሔር ዘንድ የተጸላ ነው አለኝ ። የሚሰማ ቢኖር አልኩት ። ሁለተኛም አንድ ነገር ይገርመኛል አለኝ እንደምን ብለው መንግሥት አምኖት በሥራ ላይ የተቀመጠ ሰው ነበር ያንድ ሰው መዝገብ ለማስነበብ ሲያስጀምር ድንገት ከሥራው ላይ ደረስሁ እርሱም በመልካም አቀማመጥ ተቀምጧል ያ መዝገብ ሲነበብ ሳለ ወዳጁ የሆነ መጣ የተጀመረው ቀርቶ ከዚያ ጋራ ጨዋታ አደረገ ቀጥሎ መዝገቡ እንደገና ሊነበብ ተጀመረ አሁንም እንደዚሁ አንድ ሰው መጣ እንደቀድሞው ሆነ ሶስተኛም መዝገቡ መነበብ ሲጀመር የባሰ እንግዳ መጣ ያነን ሲያነጋግር ጊዜው አለፈ ይህ ባይኖር የስንቱ ድኃ ነገር በተፈጸመ ነበር? ። ባራተኛውም ያ መዝገብ በግድ ተነበ አለቀ እኔም የዚህን ነገር ልኩን ሳላይ አልሔድም ብዬ ቆይ

ቹ ነበርና በመጨረሻው የናንተ ነገር ዛሬ የሚጨረስ አይደለም ለሌላ ቀን ይሁን ብሎ በቁጣ ቃል አሰናበታቸው ሁለተኛ መድረሳቸውን እንጃ ለዚህም መክብብ ም ዕ ፲ ቁጥር ፭ ከፀሐይ በታች ክፉ ነገር አለ ፡ እርሱም ከሹም ፊት የሚወጣ ግድፈት ነው ይላልና በጻኝነት ነገር መጠንቀቅ ይገባል አለኝ እዬ ድኃ ሐሳቢህ አንድ ሆንና ተቸገርህ ነገር ግን እርሱም ብዙ እድሜ አግኝቶ ይቆይልህ ደግሞ አጋዠ እንሆናለን እያሉ ጥቂት ጥቂት የሚተጉ ሰዎች አይታጡምና እንቅፋት ሆነው ለሚመጡባቸው ክርስቶስ ወልታ ጽድቅ እንዲሆንላቸውና ጆሮ ጠቢ እንዲጠፉ እመኛለሁ ምሳሌ ምዕ ፳፮ ቁጥር ፳፪ ፳፫ ተመልከት ። ወንድማችሁ ኃይሉ አጋዕዝት ዘ ተ ዘ ።

የክቡር ቄስ ምክር ።

ለአዲሲቱ የኢትዮጵያ ትውልድ ።

የጥቢ ወራት ምንም ቢሆን በጥቂት አበቦች አይመጡም

የተወደድህ ወዳጄ ከፒቴን ሆይ ያለ ትዕግሥት እጠብቅህ ነበር አንተ ከሄድህ ወዲህ ያገኘኝ ብስጭት ብዙ ነው ያንተ መታጣት የልቤን ቁስል ቀርፎት ላጠው ብለው ክቡር ቄስ ከቤቱ መጥተው ቆመው ነገሩኝ እኔም እስቲ ይቀመጡ ምነው ዛሬ ደስ አላለዎትም ተቆጥተዋልን አልኳቸው ። አይደለም አዝኜ ነው አሉኝ ቀጥዬ ደግሞ ፊትዎን ብመለከተው ብዙ የኃዘን ምልክት አሳየኝ እስቲ ፩ መለኪያ ኮኛክ ልስጥዎት ይጠጡ ባልኳቸው ጊዜ ቤቱን ግራና ቀኝ ተገላምጠው አዩና ከኔና ከሳቸው በተቀር ሰው አለመኖሩንና ጭር ያለ መሆኑን አይተው እንዲህ አሉ መልከም ጊዜ ነው ታውቃለህ ንግግራችን እኮ በጋዜጣ ይታተማል ጋዜጣ አንባቢዎች አለመጠንቀቆች ናቸው እነሱም ንግግራችን ለመጠጥ ነገር መስሎአቸው ቄስ መጠጥ አይገባውም እያሉ ያስባሉ እኛስ ለዚህ አልጻፍንም ይህ የአእምሮ ጉድለት ነው እኔም አልኳቸው እንባቢዎቹን እሁለት መክፈል ነው ለመጀመሪያው ክፍል ምሕረት ያድርጉለት አልተማረምና በሁለተኛው ግን መፍረድ ይገባል ክቡር ወዳጄ ስማኝ ልንገርህ ብለው የተወደዱ ቄስ ደግሞ አሉ እኛ ተዋጊዎች መሆናችን የታወቀ ነው ደግሞ በማናቸውም ዋጋ ነጻነታችንን እንጠብቃለን (፩) ነገር ግን ስንት ሰዎች ይሆኑ የነጻነትን መርምረው የሚያውቁ ? የነሱ ቁጥር አያስቸግርም በእጃችን ጣቶች ብቻ እንቆጥራቸውና ልክቸውን እናገኛቸዋለን ቢሆንም ምንም እንኳ ነጻነት መርምረን ባናውቅ በኛው መካከል ነጻነትን አንዱ ላ'ዱ አይፈቅድም ።

ስለዚህ ማንም የሕዝብን ሀሳብ የሚያውቅ የለም ምንም ቢሆን አንዱ ያንዱን ሀሳብ ማወቅ አይችልም ማናቸውም ሰው የሚጠቅም ሀሳብ ቢኖረው ሊገልጸው አይችልም ። ሊገልጸውም እኳን ቢወድ ወዮለት የመከራ ዝናብ አጉርፎ ይዘንብበታልና ሲሆን ፊት ለፊት ሳይሆን በስሙ ወይም ባድራሻው ልንቃወመው እናስባለን ወይም ጀርባውን በክፉ እመቃት እና ቄስለዋለን ነጻነት ብዙ ልክና ሚዛን ያለበት ቃል መስሎ ይታያል በሁለት ወንድማማች መሐከል እንዲገኝ የማይፈቀድለት ይመስላል ።

አንድ የነፃነትን ብልሃት ምርምር ያወቀ ሰው በጤና ለመኖር ቢፈልግ በልቡ የሚወጣውንና የሚወርደውን አስቸጋሪ ሀሳብ እንደ ድንጋይ የማይንቀሳቀስ አድርጎ አፉን ዘግቶ መቀመጥ ያሻዋል ።

እንግዴህ እንዲህ ከሆነ ፈጽሞ ጥፋት ነው ሺጊዜ ማናቸውንም የእውቀት ነገር ለመንግሥታችን ማመልከት ይገባናል የማሻሻል ሥልጣኔን ሁሉ ለመንግሥት ማስታወቅ ያስፈልገናል ። አንዳንድ ጊዜም ባልሆነ ነገር መንግሥታችንን እና ማዋለን መንግሥትና አምላክ የሕዝብ ጠባቂዎች ናቸው ልንሞግታቸው አንችልም እለምንዎታለሁ እስቲ ንገሩኝ መንግሥት የቆመው በምን በምን ነው ? መንግሥት ማለት ራስ ማለት ነው ። ራስ ሲያስብ እጅና እግር ካላገዙት ካልረዱት ምን ማድረግ ይችላል ከዚህ ላይ ነው የነፃነትን ትምሕርት ማወቂያ የነፃነትን ትምሕርት ማለት በነፃነት ውስጥ ያለውን ነገር ማወቅ ብንፈቅድ በትክክል ሰው መሆን ያስፈልገናል የዛሬው ዘመናችን በፍጥነት የሚጠይቀው ይህ ነውና ችላ አለማለት ነው ። አንድ ጊዜ በሰው መንገድ ከቆምን መንግሥታችንን ማገዝና ኃይላችንን ማሳየት እንችላለን ፩ መንግሥት የሚቆመው በገዛ ሕዝቡ ነውና ስለዚህ እርስ በራሳችን ያለንን ሐሳብ እንመካከረው እንደብቅ መንግሥቱን የሚወድ ሰው ስላገሩ ፍቅር ቢናገር በደስታ ከሐሳቡ ጋር የሚስማማ ነገር መመለስ ነው እንጂ ብንመቀኘው ደግ አይደለም ።

ደግሞ ሐሳባችንን ፲ ፲ ጊዜ መለዋወጥ አይገባንም ከበላዮቻችን ሥር መንከባለል እግራቸውን መላስ አይገባንም እንድ የበላያችን ሲመጣ በፊቱ መስገድ በኋላው ግን በሱ መሸመቅ ከሁሉ የከፋ ነውና ይህን ማድረግ መተው ነው ።

ክቡር ከፒቴን ሆይ ከሁሉ ይልቅ በለመታደል ማታለል የሚያውቅ ሰው የሚዋሽ የተከበረ ሰው ስለእውነት ዳኝነት የሚናገረው ሰው ፍርድን እሱው ራሱ ሲያጠፋ ይገኛል ። ስለ ደንብ የሚናገረውም ደምብ ሲያፈርስ ይገኛል። ክብረት ያለው ከአታላዮች ዘንድ አቆላማጮች ዘንድ ከውሸተኞች ዘንድ ነው ስድብና ውርደት ግን አገሩን በሚወድና በእውነተኛ ሰው ላይ ናቸው ።

የተወደዱ ቄስ ሆይ ነገርዎን እዚህ ላይ ላቁመው ምንም ቢሆን መልካም ሐሳብ በክፋት ፊት ማጕንበስ አይችልም ክፋት ውሸት ማታለል ሁሉ ለጥቂት ጊዜ ይረባሉ መጨረሻቸው ግን እጅግ ያሳዝናል ።

ወዳጄ ከፒቴን ይህስ እውነትህ ነው በማናቸውም የመንግሥት ሥራ ላይ መዋሸት ፤ መንግሥት መታለል ፤ በመንግሥት ገንዘብ መኖር ፡ ይቻላል ከዚህ በላይ ሊዘፍንበትም እንኳ ይቻላል ግን በቶሎ የሚጠፉ የማታለያ መሣሪያዎች ናቸው ።

ደግሞ የተወደድህ ከፒቴን ልንገርህ ጥቂቶች የውጭ አገር ሐሰተኞች ወዳጆች አሉን ሁልጊዜ ከኛ ጋር ናቸው በውስጣቸው ጠላትነት አለ እኛም እንደምትጠልቅ ጨለማ የምታመጣ የማታ ፀሐይ መሆናችንን ተረድተነዋል።

ክቡር ቄስ ሆይ እኔም ደግሞ የውጭ አገር ሰው ነኝ በኔም ላይ ይናገራሉን ብዬ ብጠይቃቸው እንዲህ ብለው መለሱልኝ አይደለም አንተ አንድጊዜ ተለይተሃል ደግሞ አሉ መቼ ይሆን

ዓይናችንን ከፍተን ለማየት የምንችልበት ጊዜ መቼ ይሆን ? የነዚህን ክፎች የጦር ልብስ የምንገፍ አዲሱ ትውልድ መንግሥቱን ማገዝ ሲጀምር ብርሃን እናያለን ከዚህም በኋላ ክፋት ውሸት ማታለል የጦር ልብሳቸው ይቃጠላል ።

እኔም አልኳቸው የተወደዱ ቄስ ሆይ ንግግርዎ እውነተኛ አሳዛኝ ነው ሕዝባችን ጸጥታና ደህናውን ኑሮ ቢፈልግ አንድ ነገር ብቻ መጠበቅ አለበት የነፃነትን ሁናቴ ለማወቅ አገርን የመውደድ ፍቅር ለማግኘት አእምሮን በተማሪ ቤት መፈተን ያስፈልጋል ።

ደግሞም በመንግሥት ሥራ ቤቶችና በሕዝብ መሐከል በእውነት መሥራት ነው ። የመንግሥትን ደንብ አለመጣስ ። በደምብ ላይ እቡይ አለመሆን ።በውጭ አገር ሰዎች ፊት ባሪያ አለመሆን ነው ። ከጉያችን ያለውን ጥለን ከውጭ የመጣውን ማቀፍ አያስፈልገንም ። ይህን እንኳን ሰው ከብትም አያደርገውምና ። ጽጌረዳችንን ጨብብጠን ጥለን ከውጭ የመጣውን እደረታችን አጠገብ ሆኖ ልባችንን ወግቶ ደማችንን ለማፍሰስ የሚጥረውን እሾህ መውደድ አይገባንም ። የውጭ አገር ሰዎች አገራቸውን እንደሚወዱ እኛም ደግሞ እንደነሱ አገራችንን መውደድ ያስፈልገናል ።

ከዚህ በኋላ ክቡር ቄስ አሉ መንግሥቴንና ይልቁንም ብልሁን ለእውቀቱ መጠን የሌለውን ልዑል አልጋ ወራሽን እባርክለሁ በእግዚአብሔር ኃይል ሁሉን ይመለከታል ይሰማል ያስባል በርትቶም ከልክ አልፎ በማይወሰን ትጋት ይሠራል እራሱ በእውነት የተከፈተ ነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥላው እንዲያርፍበት እጁን ከፍ አርጎ ይለምነዋል። ይህን ካሉ በኋላ እኔም ከመቀመጫዬ ብድግ አልኩና እጄን አንስቼ ተናገርሁ ቸርነት ለኢትዮጵያ ተሰጠ እግዚአብሔር ከኢትዮጵያ ትልቅ ልጅ ፈጥሮ አልና ። እጅግ የሚያስደንቅ ነው በእውነት ይህ የእውቀቱ ማኖርያ ራስ ሌላ ነገር ቢሆን ፩ ቀን ይሰበር ነበር ። እንግዲህ ወንድሞች እንተጋገዝ እንተጋገዝ አንድነት ታበረታለች መለያየትም ታሰንፋለች ውርደትንም ታመጣለች ካልኩ በኋላ ነገሬን በዚህ ወሰንሁ የተወደዱ ቄስም የተወደድህ ካፒቴን ሆይ የጥቢ ወራት ማግኘት ብንፈልግ የአታክልት ቦታችንን ዘር ብለን ያበቡትን ዛፎቻችን መመልከት ይገባናል

ካፒቴን ባቢኪያን

የፍቅርና የደስታን መንገድ ስለሚከተሉ ኢትዮጵያዎች።

የአውሮጳ ሰዎች ሲጋቡ ሳሉ ደሀውም እንደ ድህነቱ ጌታውም እንደጌትነቱ መጀመሪያ ሚስት ለማግባት ሲያስብ የልመና ጥያቄውን ወደ ቤቶቿ ያመለክታል ይባላል እነሱም የጥያቄውን ቃል ተቀብለው ለልጅቷ ያመለክቷታል ልጅቷም ፈቃድዋ እንደሆነ ሰውዬውን ካወቀችው ይሁን ትላለች የማይስማማትም ቢሆን አይሆንም ብላ መልሷን ትሰጣለች ሰውዬውን ካላወቀችው ሰውዬውን አይታ የሐሳቧን መልስ ለቤቶቿ ታስታውቃለች አባትና እናቷም የልጅቷን መልስ ከተቀበሉ በኋላ እንደሷ ቃል ያስታውቁታል ይባላል የጋብቻቸውም ቀን የደረሰ ጊዜ ፍቅር በምትባለው መንገድ አብረው እጅ ለእጅ ተያይዘው እፍረትና ይሉንታን ንቀው ከቤት ዘመዶቻቸው ጋራ ወደ ቤተክርስቲያን ይገባሉ በተክሊል ቆርበው ሊጋቡ እቤተክርስቲያን በገቡ ግዜም ቄሱ እንዲህ ብሎ ወንድየውን ይጠይቀዋል እገሊትን ይህችን አጠገብህ ያለችውን ወደሃታል ወይ ይሉታል እሱም አዎን ብሎ ለቄሱ ምላሽ ይሰጣል እሷንም ይህንን እገሌ የሚባለውን ወደሽዋል ወይ ብለው ይጠይቋታል እሷም አዎን ስትላቸውም ከዚያ በኋላ የተክሊሉን ሕግ ያደርሱላቸዋል ወደዚያውም ቄሱ በምድርም ለሥጋቸው በሰማይም ለነፍሳቸው የሚሆን መንፈሳዊ ምክር ይሰጧቸውና ከቆረቡ በኋላ እሷና እሱም ሊጋቡ ቄሱ ሊጠይቃቸው ፍቃድ ማድረጋቸውን የሰሙት ሽማግሌዎች እቤተክርስቲያኑ መዝገብ ላይ የምስክርነታቸውን ፈርማ ይፈርማሉ ባልና ሚስቱም ፈርመው በቀጥታዋ ፍቅር በምትባል ጐዳና ወደቤታቸው በዘመዶቻቸው ታጅበው ይሄዳሉ በኋላም እንፋታለንንና እንለያያለንን ሳያስቡ ባልየውም ለሚስቱ ሚስትየዋም ለባሏ እየተሳሰቡ ይኖራሉ ።

በሃገራችን ግን የሚያጨው ሰውዬ ልጅቷን ሳያያትና እሷም እሱን ሳታየው ሳይፈቃቀዱ ሁለቱም ፈቃዳቸው ሳይሆን የወንድየው አባት ለሴትየዋ አባት ለልጄ ልጅህን ስጥልኝ ብሎ አማላጅ ይልክና ነገሩን ጨርሶ ሠርጉ ከተደገሰ በኋላ ለልጁ ሚስት ታገባለህ ብለው አባቱ ያስታውቁታል ልጁም እምቢ አይሆንልኝም እንዳይል ፈርቶ ያባቱን ፈቃድ ለመፈጸም ያለውድ በግድ ያገባል ።

ሴቷም ልጅ አቅምና ጉልበት የላትምና ፈቃዷ ሳይሆን ዘመዱ እንደ ሞተበት ሰው ሁሉ እንባዋን እያዘነመች ያለውድ በግድ ታገባለች በዚሁም ጋብቻ ላይ አባቶቻቸውና እናቶቻቸው የተክሊሉንና የሕጉን ሥራት በፍጹም ስለዘነጉት እንዲያው ያጋቧቸዋል። መቼም በግድ የሆነ ነገር መሠረት የለውምና ከትንሽ ቀን በኋላ ባልና ሚስቱ ይለያያሉ ሲጀመርም በግድ የሆነ ነውና ያም ባሏ ከልጅነቱ ጀምሮ ያጠራቀመውን ገንዘብ አክፍሎ ይሰደታል ይኸውም ሰው ሁለተኛ ሚስት ለማግባት አቅምና ገንዘብ ያጣና ብዙህ ጊዜ ሲወጣ ሲወርድ ይኖራልበመለያየት የተነሣ ብዙህ ጉዳትና ችግር ያገኘዋል ስለዚህ በጋብቻ ነገር ችግርና ጉዳት እንዳያገኘን ከዚህ በላይ እንደ ጻፍኩት ሁሉ ያለሕግና ያለቁርባን እንዳይገባ የሚከለክል ደንብ ሊቃውንቶቻችን ቢያቆሙልን እንዴት ደግ ሥራ በሆነ ነበር ።

ስለዚሁም ይኸንን አሮጌውን ሥልጣኔ እንደ ኤሮፓ ሕዝቦች ለውጠን እያሻሻልን ብናስብበት ይህን ሕግ ሕዝባችን ከለመደውና ከያዘው ወዲያ እንዲሁ ሲፈጽመው ይኖራል እንዲያውም ቢሆን የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ትንሽ ትልቁ የክርስቲያንን ደምብና ሕግ ሲፈጽሙ በመኖራቸው የተመሰገኑ ናቸው ፡

የሃገራችን እስላሞች እንኳን ከተጋቡ ያለመለያየታቸው በጋብቻ እረገድ ያስመሰግናቸዋል ሊቃውንቶቻችን ሆይ በዚህ በሕግ ነገር ከሌሎች ወገኖች ዝቅ ያልን ሆነን እንዳንታይ አመለክታለሁ ።

በዚህ በምንኖርበት ምድር እስከ እምንኖርበት ዘመናትና እስከ ፍጻሜያችን ድረስ ወንድ ያለሴት ሴትም ብቻዋን ያለወንድ እንዳይሆንላት እስቦ ትልቁ አምላካችን ለአዳም ሔዋንን

ፈጥሮ ሰጠው ሴት ለወንድ ወንድም ለሴት የታዘዘ መሆኑን ለምሳሌ ይህ ብቻ ይበቃል ስለሆነ ግን የአዳምንና የሔዋንን ታሪክ ለነገሬ ምሳሌ አደርገዋለሁ ብዬ ሳስብ ሳለሁ ነገሩ የሚያታክት ስለሆነ በቅርብ አሳጥረዋለሁ ። እንግዲህ ከሊቃውንትና ከመጻሕፍት እንደምናገኘው የተከሊል ሥርዓት ባንፈጽም እንኳ ዳለን ስለዚህ ሁሉ ስለሚስትና ባል ጋብቻ ያለሕግ እንዳይጋባ ክርስቲያን የሆነውን ሁሉ የሚከለክል ደንብ ማቆም ያስፈልጋል ። ይኸንኑም የጻፍኩላቸው በወንድሞቼና በንደኞቼ ላይ በጋብቻ ምክንያት የሆነውን ነገር አይቼ ቢያሳዝነኝ ነው እንጂ እንዲያው ላብ ወለድ ወሬ ልጻፍ ብዬ የተለዋወጠ ነገር ማምጣቴ አይደለም ። ግን ቢደረግ በተሻለን ነበር ይኸውም ሐሣቤ በተመልካቾች ዘንድ ያልተወደደ ንግግር መስሎ ቢታያቸው ገና ከሚማር ተማሪ ስተትና የሚታረም ነገር ብዙ እንዳገኝ እርግጥ ነውና ንባቡንና ቃሉን አይታችሁ የተገደፈ ነገር እንዳለ ብታርሙት እወዳለሁ ። በቀለ ዘለቀ

ስለ ተማሪ ቤት ለመኳንንት ሁሉ
ማስታወሻ መቀስቀሻ ።

አምና ሐምሌ ፲፩ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓመት የዳግማዊ ምኒልክ ትምርት ቤት ስለ ክረምትና ስለ ተማሮች እርፈት ሊዘጋ የኢትዮጵያ መኳንንቶችና የውጭ አገር ሚኒስትሮች ወይዛዝርትም በተማሪ ቤት ተሰብስበው የኢትዮጵያ መንግሥት ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ግሩም የሆነ ብዙ ምክር ያለው መንፈሳዊና ሥጋዊ ትምህርትን የሚሰጥ ቃል ተናገሩ ። የአገራችንን ትምህርት በአማርኛና በግዕዝ መማር ትልቅ ጥቅም ያለበት ነውና መኳንንቱ ሁሉ በየግዛታቸው የንባብና የጽሕፈት ትምህርት ቤት እያሰሩ እንዲያስተምሩ ይሁን ብለው በክቡር ቃላቸው ተናገሩ ።

ይኸንን ያማረና የተፈቀደ ቃል ሰምተው ክቡር ራስ ናደው የመንግሥት ቃል የቀረበውን አያስቀርስም የቆረሱትን አያስገርስምና ክቡር ራስ ናደው ከዕለታት አንድ ቀን ምሳ አድርገው መኳንንታቸውንና የውጭ አገር ነጋዶች ጠርተው በክብር ለምሳ አስቀምጠው በራሳቸው ኪሳራ ተማሪ ቤት እንዲያቆሙ ቢያጫውቷቸው ሁሉም በየአንድ አንዱ በፈቃዱ ተነሥቶ እንደ ችሎቱ ለተማሪ ቤት ገንዘብ ቢጥል ድምሩ ከ፫ሺ የሚያንስ አይመስለኝም ። አሁን ዛሬ በጎሬ ዙሪያ ያለ ባላገር ሁሉ እድሜ ለዛሬ መንግሥታችንና ለክቡር ራስ ናደው እያሉ ልጆቻቸውን ወደ ተማሪ ቤት ይሰዳሉ ። ክቡር ራስ ናደውም በቶሎ እንዲህ ማድረጋቸው እግዚአብሔርን ስለፈሩና የመንግሥትን ቃል ስላከበሩ ነው ።

እንደዚሁም ሁሉ በዙሮቻቸው በነረቤታቸው ያሉ መኳንንት ሁሉ በአገራቸው ውስጥ ያለውን ባላባትና የአገር ሽማግሌ ሰብስበው የተማሪ ቤት እናቆማለንና ምን ያህል ገንዘብ በፈቃዳችሁ ለመጣል ትችላላችሁ ብለው ቢጠይቋቸው ከ፳ና ከ፲ ያነሰ የሚሰጥ ያለ አይመስለኝም ።

ዝንጉነት ባያግዛቸው ስለዚህ ነቢይ ዳዊት ያስጠነቅቃቸዋል ። ኢትኩኑ ከመ ፈረስ ወበቅል እለ አልቦሙ ልብ ። እለ በሕሳል ወበልጓም ይመይጥዎሙ መላትሒሆሙ ከመ ኢይቅረቡ ኀቤከ ። ልብ እንደሌላቸው እንደ ፈረስና እንደ በቅሎ አትሁኑ ። በልጓምና በልባብ ጉንጫቸውን የሚለጉሙዋቸው ወዳንተ ለመቅረብ ባልፈቀዱ ጊዜ መዝ ፴፪ ፱ ይህንን እንዳልፈታ ስፍራ ይጠባል ለናንተም አይሰወራችሁም ። ከዚህ ቀደም የኢትዮጵያችን ልማድና ያለንበት ትምሕርት ለ፫ ነገር ብቻ ይጠራል ። ፩ኛ ተምሮ ቀድሶ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎ ቀላዱንና ደመወዙን ይጠበቅበታል ። ፪ኛ ተምሮ ጽፎ ቤተ መንግሥት አገልግሎ ደመወዙን ይጠብቅበታል ።

፫ ተምሮ መምሕር ሁኖ አስተምሮ ዋጋውን ይቀበልበታል ። በዚህ መካከል ሕዝብና አሕዛብ ተነዳ ፤ መንግሥታችን አልጋ ወራሽ ያሉ በኢትዮጵያ ሁሉ የተማሪ ቤት ቁሞ ገበሬም ነጋዴም ሸማኔም ፋቂም አናጺም ሰፊም እረኛም ሎሌም ገረድም ጌታም እመቤትም ሁሉ ተምሮ የጌታን መውረድ መወለዱን ወልደ አብ ወልደ ማርያም መሆኑን መገፈፍ መገረፉን በመስቀል መሞቱን ዕርገቱን ዳግም ምጽአቱን አውቀው ወደስራቸውና ወደ ክፍላቸው እንዲመሩ ነው ያሉ ።

ወይወፍር ሰብእ ውስተ ተግባሩ ይውዕል ወይትቀነይ እስከ ይመሲ ። ሰውም ወደ ተግባሩ ይወጣል ። እስኪመሽም ድረስ ወደ ሥራው መዝ ፻፬ ፳፫ ። ነገር ግን ውሎ ውሎ ከቤት ኑሮ ኑሮ ከሞት ነውና ከሞቱ በኋላ ሁሉ እንዳይከተል ለማንም አይጠፋውም ። ወጸውዐ ወይቤ አቡ አብርሃም ተሣሃለኒ ፈንዎ ለአልዓዛር ከመ ይጥማዕ ጽንፈ አጽባእቱ ማየ ወያቍርረኒ ልሳንየ እስመ ሐመምኩ በዛቲ እሳት ወይቤሎ አብርሃም ተዘከር ወልድየ ዘከመ ፈጋዕከ ወተፈሣሕከ በሕይወትከ ወአልዓዛርሰ ከማሁ ከመ በተጽናስ ወይእዜሰ ከማሁ ከመ ውእቱ ይትፌሣሕ በዝየ ወአንተሰ ተሐምም ።

እሱም ጸራ አለም አባቴ ሆይ አብርሃም ማረኝ አልአዛርንም ስደድልኝ የጣቱን ጫፍ በውሀ ነክሮ ምላሴን ያበርድልኝ ዘንድ በዚህ ነበልባል እሳቀያለሁና ፣ አብርሃምም አለ ልጄ ሆይ አስብ አንተ ተድላህን ፈጽመህ እንደ ተቀበልህ በሕይወትህ ሳለህ አልአዛርም እንዲሁ መከራ አሁንም እሱ ደስ ይለዋል አንተ ትሳቀያለህ ሉቃ ፲፮ ቁ ፳፭ ። በዚህ በዘመናችን ያለ መኳንንት የአምላክን ስጦታ ዋጋ ምን ይዞ ይሄድ ይሆን ። መድኀኒታችን ይላል ወምንትኑ ይበቊዖ ለሰብእ ለእመ ኵሎ ዓለመ ረብሐ ወነፍሶ ኀጕለ ወምንተ እምወሀበ ሰብእ ቤዛሃ ለነፍሱ ።

ለሰው ምን ይጠቅመዋል ዓለሙን ሁሉ ቢገዛ ነፍሱን ግን ቢያጎል ወይስ ምን ይሰጣል ሰው የነፍሱ ቤዛ ፡፡ ማቴ ፲፮ ቁ ፳፮ ፡፡ ሰው ሁሉ ከተሰጠው እውቀት ሁሉ አስቀድሞ ፈጣሪውን ቢያውቅ ቢፈራ ።

ቀዳሚሃ ለጥበብ ፈሪሃ እግዚአብሔር ምክር ሠናይት ለኵሉ ዘይገብራ የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው ለሚያደርጓትም ሁሉ ደህና ልቡና ትሆናቸዋለች። መዝ ፻፲፩ ፲

ወድቂ እለምናቸዋለሁ ። ተነሥቼ አቤት አቤት እላለሁ የዳር አገርን መኳንንት እለምናቸዋለሁ። የተማሪ ቤት ሲያቆሙ እረዳለሁ ።

አባ ትርጉም ።

የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ምኞት ።

ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ጠቀሚታ የማይተኛ ሐሳብ ስላላቸው አሁን በቅርቡ የሚቆሙትን አዲስ ፋብሪካ እናያለን ። እንዲፈጽሙትም ምንም የሚአውካቸው ነገር የለም ።

ያገራቸውን ሕዝብ ጥጥ ለመትከል እንዲበረታ ብለው ከእንግሊዝ አገር አንድ ጥሩ ፋብሪካ ከአዲስ መኪኖች ጋር ለአራት ልዩ ልዩ ሥራ የሚሆን አስመጡ ከጥቂት ሳምንት በፊት ፋብሪካውን ለማቆምያ ቤቶች ግምቦች ይገነባሉ ይህ ፋብሪካ የኢትዮጵያ መጀመሪያ መልካም የሥራ ምሳሌ ሆኖ ያገለግላል ።

እነዚህን መኪኖች ለማቆም የተቀጠረው የማዘጋጃ ቤት የኤሌክትሪክ መኪና መሐንድስ ሙሴ መ አ ሱርኪያሲያን ጥቂት ማመልከቻ ሰጡን ። እኛም ከንባቢዎቻችን ጋራ ብንካፈለው ልዑል ላገራቸው ጠቀሜታ እንዴት እንደሚደክሙ መግለጽ እንችላለን ። ይህ ፋብሪካ አዲስ አበባ ከደረሰ ብዙ ግዜው ነው ። አራት ዓይነት ሥራ በውስጡ አለው ። የላበቱ ሞተር ጉልበት የመቶ ሀያ ፈረሶች ጉልበት ይሆናል ። ይህ ሞተር መኪኖቹን ቀን ቀን የእንጨቶች ሥራ እንዲሠሩ ወፍጮ እንዲፈጩ አቡጀዲድ እንዲሰሩ ማዞር ይችላል ።

ሌሊት ሌሊት ደግሞ በጠቅላላው የሞተሩ ኃይል የመቶ ክ፲ ፈረስ ጉልበት ላለው ኤሌክትሪክ ዋና እመክክል ቋሚ መኪና ይሰጣል በዚሁ ከብዙ ስፍራ መብራት ማቆም ይቻላል ።

የአቡጀዲድ ፋብሪካ ብዙ ጥጥ ያስፈልገዋል እንግዲህ ባንድ በኩል አቡጀዲዳችንን እናገኛለን ባንድ በኩል ደግሞ ይህን በመላው ዓለም የተወደደውንና የተፈለገውን የጥጥ ተክል ሥራ ይልቁንም ለዚህ ሥራ ሰፊ መሬት ላላት ለኢትዮጵያ በጣም የሚያስፈልግ ስለሆነ ባለመሬቶቻችንን ይህን ተክል እንዲያበዙ ያስገድዳቸዋል ። ሞተሩ ከማናቸውም አገር ከሚመጣው ነዳጅ ነገር መስራት ይገባዋል ይህ ሲሆን እንዴት ያለ ደስታ ነው የመብራት ምንጭ በመገኘቱ ነገሩ ለገናው የታሰበ አይደለም ያለ ነገር ነው እንጅ መኪኖቹና መሣሪያዎቹ ሁሉ ገና ድሮ አዲስ አበባ ገብተዋል ይልቁንም ሳጥናቸው መከፈት ተጀምሮአል በጥቂት ወራት ውስጥ ከተማችን ሌሊት ሌሊት በመልካም እንድታበራ እንመኛለን ።

ይህ ዛሬ የሚደረገው የልዑል የደስታ ሐሳብ ለወደፊቱ መልካሙን ፍሬ ይሰጣል ፋብሪካውም በቶሎ ቆሞ ሥራው እንዲጀመር እንመኝ ባለገንዘቦቻችን ይህን መልካም ምሳሌ እንዲከተሉ ያበረታቸዋልና ፡

መቶ አስር የፈረስ ጉልበት ያለው መሐከል የሚሆነው የኤሌክትሪክ መኪና ለመጀመሪያው እስከ አምስት ዓመት ማብራት ይችላል በኋላ ግን መጨመር ነው ። ሀይ ምንም አያስቸግር መጀመሩ ብቻ ነው የሚቸግር ።

እንግዲህ ያለጥርጥር እመኻከል ቋሚውን የኤሌክትሪክ መኪና ለውጭ ባለገንዘብ ሳንዋዋል እኛው እራሳችን ሁል ጊዜ በጥቂት ጠቀሜታ ማቆም እንችላለን።

ካፒቴን ባቢክያን ።

የአዲስ አበባ ገበያ ።

የቀንድ ከብት

የሚታረድ በሬ ዋጋ	፺ ብር
የእርሻ በሬ	፴፭ ብር
ያሩሲ ድልብ በሬ	፶፭-፹ ብር
የምትረባ ላም	፴፭ ብር
መሲና ላም	፴፪ ብር
የምትረባ በግ	፫ ብር
መሲና በግ	፭ ብር
ሙክት በግ	፲፫ ብር
የምትረባ ፍየል	፬ ብር
መሲና ፍየል	፯ ብር
ሙክት ፍየል	፲ ብር

የጋማ ከብት

ሰንጋ ፈረስ ዋጋው	፳፭ ብር
ቢዝራ ፈረስ	፴-፵፭ ብር
አጋሰስ ፈረስ	፴፯ ብር
የኮርቻ በቅሎ	፻፶ ብር
ስናር ዓይነት በቅሎ	፻፹ ብር
አጋሰስ በቅሎ	፸ ብር
የምትረባ አህያ	፲፯ ብር
የጭነት አህያ	፴፯ ብር
ዶሮ ዋጋው	ከሩብ-አላድ
ዕንቍላል ሠላሳ	፩ ብር

የእህል ገበያ

ስንዴ ፩ ጆኒያ	፲፪ ብር
ገብስ	፱ ብር
ጤፍ	፲፫ ብር
ሽንብራ	፲ ብር

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፩ ብር ተሰስት ሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፫ ብር ተሩብ
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳ ብር ተኩል
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፲፬ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፰ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፳፭ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፱ ብር
አቡጀዲ መነጸር	፩ ኮረጃ	፻፵፩ ብር
፡፡ ባለሰይጣን	፡፡	፻፵፩ ብር
፡፡ ባለ ድመት ።		፻፵ ብር
፡፡ ባለአህያ	።	፻፳፯ ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል	።	፻፴፭ ብር
ባለ አንበሳ	፡፡	፻፵፭ ብር
ሱካር	፩ ጁኒያ	፵ ብር
ቻይ	፩ ነጥር	፩ ብር

ስለ ምንዛሪ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ ፳፭ ሳንቲም
አንድ ብር	ሊሬ ፫ ከ፹፩ ሳንቲም
በአንድ ጊኒ	፲ ብር
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፬ ብር

A LOUER

COGNAC S&E&A.METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኒዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፡በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፡ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል .



ማስታወቂያ ።

ሺብሮሌ አቶሞቢል በኢትዮጵያ ወኪል ፡
ሐ. ሜ ዜርቦስ ኩምፓንያ ።

Automobiles CHEVROLET

H. M. ZERVOS & C^{ie}
REPRESENTANTS
BAS PRIX HAUTE QUALITE

Odeon

ዓለም ሱቅ ፲፪ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል ። ሙዚቃም በየ ዓይነቱ እንደ ሲንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል ።

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ አቤርላንድ ኦቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጦጦን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።



አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባ ኪሎ ሜትር ያስኬደዋልንወዲያም ባለማግኜቶና ባለባተሪ ነው ካምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል «ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው

ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒከላ ።

ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ ።

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህ በከፕሱሉ ያለ ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በከፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ጉዶይር ግዙ





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ ቢልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንከራ ነው ።በሌላጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ፤ ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አራተኛ ዓመት ፤ ቍጥር ፳፭
4 me ANNÉE № 25

ሐሙስ ሰኔ ፲፬ ቀን ፤ ፲፱፻፳ ዓ ም።
JEUDI 21 JUIN 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ጸሐፊተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ስፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ክረምት ።

በጋው ስለ ጸናና ድርቅ ሆኖ ስለ ባጀ ሰው ሁሉ በጣም ፈርቶ ነበር ። በዚህ ምክንያትም እህሉና ሥጋው ወተቱም ቅቤውም ሌላም ልዩ ልዩ አይነት ለምግብ የሚሆን ነገር ሁሉ ተወደደ ።

አሁን ግን በጋው አልፎ ክረምት የሚገባበት ጊዜ ስለ ደረሰ ዝናቡ በትክክል እየዘነበ መሬት ታድሶ ከአቧራነቱ ወደ ርጥበት ተመልሷል በያለበት ልምላሜና የተክል ቡቃያ ይታያል ።

ይኸንን ማየትም ለዓይናችን ደስታ ለልባችንም ተስፋ ይሰጠዋል ። ዝናብ በዘነበ ጊዜ ጐርፍ ያጐርፍና ብዙውን ነገር ካለበት ቦታ ወዳልነበረበት ይወስደዋል ። እኩሌታውን ፍሬ ወደ ደኀና መሬት አድርሶ ከለስላሳ አፈር ጋራ ሲያቀላቅለው ማለፊያ ቡቃያ ሆኖ ይነሣል ወደ አበባና ወደ ፍሬ ይደርሳል ።

እኩሌታውንም ዓዘቅትና አባሕር ውሥጥ ይጨምረውና በስብሶ ይቀራል ይህም አለመታደል ነው።ዝናብ ያንዳንዱን አገር የለዘበ መሬቱን እየላጠ በጐርፍ ሰብስቦ አሸዋ ለሆነ አገር ያበረክተውና ያም አገር በዚህ ምክንያት ፍሬያማና የበረከት አገር ይሆናል ። ይዘን ለሚያደርግላቸው ሰዎችም መልካም አገልጋይ ነው ። እንዲህ ባለ መንገድ በረከት የሚያገኙ አገሮችም ጐርፉን በዕልልታ ይቀበሉታል ።

እውነትም እነዚህ አገሮች ጐርፍ ሲደርስላቸውና ሲቀበሉት ደስታቸው ምን ይገርም ይሆን ?።

ደግሞ የሚገርም ነገር አለ ክረምት ሲሆንና ዝናብ ሲዘንብ አንድ አንድ ዛፎች የለበሱት ለምለም ቅጠል ይረግፍና ባዶ ሆነው ተራቁተው ይቀራሉ ። አንድ አንዱን ግን በጋ ተክረምት ቅጠል አይለያቸውም ። ማለት ዘወትር ለምለም ናቸው ይህን ለመመርመር ከየዓይነቱ ዛፎችን ማየት ይበቃል ። እንደዚሁ ሁሉ በክረምት ብዙ ያልታደሉ ድሆች ተራቁተው ተቸግረው በብርድ ተኰራምተው ይከርማሉ ።

ብዙ የታደሉ ሀብታሞችም የበጋ በረከታቸውና ልምላሜያቸው ጌጣቸውም አይቀርባቸውም ። ዛፎች ቡቃዮች ናቸውና የባልንጀሮቻቸውን ዕራቁትነትና ችግር አይመለከቱም ስለ ራሳቸውም አያስቡም ።

ግን እኛ ሰዎች ይልቁንም የታደልን እንደ እኛ እድል ላላገኙ ወንድሞቻችን ልናስብላቸውና ከበን ዕድላችን ልናክፍል ግዴታ አለብን።በዚህ ክረምት ምን ያህል ነፍሳት ምን ያህል ወንድሞቻችን እንዴት እንደ ተራቈቱና በብርድ የሚርገበገቡ በችግርም ምክንያት የሚጐዱ አሉና በእድላችን ሳንኰራ ከለጋስ አምላክ ከተቀበልነው እንለግስ ለተቸገሩና ለተራቈቱ ወንድሞቻችን ብንረዳ የተቀበልነው በረከትና ልምላሜ ለኛም ለብፅዕና ለባልንጀሮቻችንም ጥቅም ይሆናል እንደዚህ ብናደርግ እንደ ሰዎች እንጂ እንደ ዛፎች አንሆንም ።

አብርሃን ዘበአማን ፤ ወሰላም ለቅሩብን ።

መልካም ሐሳብና ክፉ ሐሳብ ወደፈቀዱበት ስፍራ ሲሔዱ ድንገት በመንገድ ላይ ተገናኝተው የሚሔዱበትን ቦታ ሲጨዋወቱ በመካከሉ የጥበብ መኖሪያ አቶ ልቡና የሚባል ዘበኛ ደርሶ ሁለቱንም ይዞ አስሮ ቢመረምራቸው ክፉ ሐሳብ የሚባለው አደጋ አይችልምና ደንግጦ ሲለፈልፍ ወደ ከተማ ሔጄ አንዱን ካንዱ ጋራ ለማጣላት የፖለቲካ ወሬ ለመንዛት እሔዳለሁ። የኔም ጓደኞች እነትዕቢትና እነኩራት እነተንኰል በባዶ ቤት ተቀምጠው ወደ እውቀት ጐዳና የሚሔዱትን ሁሉ እናስኬድም ብለው እንቅፋት ሆነው ይከለክላሉና ከነሱ ጋራ ሆኜ ምክር ላክፍል እሔዳለሁ አለው ። ሁለተኛም መልካም ሐሳብ አንተ

ስ ወዴት ትሔዳለህ ቢለው በጸጥታ ቃል ሲመለልስለት የኔ ትውልዴ ከቤተ ክህነት ወገን ነው በተማሪ ቤት አድጌ እሱ ለ ኑሮ ባይመቸኝ ወደ ቤተ መንግሥት ገብቼ አማክሬ ሁኜ ሳለሁ የሚያስቆጭ ነገር አግኝቼ በጠረፍ በጠረፉ የሚሆነውን ነገር ለ መመርመር ስሔድ ከዚህ ከክፉ ሐሳብ ጋራ በመንገድ ስለተገናኘን ይኸው ሁለታችንም ባንተ እጅ ተይዘን ጉዳዩ ተሰናክሎ ቀረ አለው ።

ከምትሔድበት ቦታ የሚገኘውን ነገር አንደኛውን እንኳ አጫውተኝና ልልቀቅህ ክፉ ሐሳብማ መቼም ደግ አይሰራ ባነ ጋገሩ ታስሮ ኑዋሪ ነው ቢለው እኔማ መልካም ሐሳብ አገር ገዢ የሆነው ሁሉ ባገሩ ውስጥ የሚኖረውን ሽፍታና ወምበዴ ሌላም እየፈለገና እየያዘ ወደ ቅጣት እንዲያሳልፍና እንዲያጠፋ ይህን ሳይሰራ ቀርቶ ባገሩ ሽፍታና ወምበዴ ሌባም ቢገኝ በርሱ እንዲቀጣ የጠነከረ አዋጅ ቢወጣ አገር እንዲሰለጥን የታወቀ ነውና ባማከሪዎች ቤት እየሔድሁ አሳስባለሁ ። እዚሁም በቅርቡ ከተማ ንጹሕ እንዲሆን ዙሪያውን የዘበኛ ቤት ሆኖ የሚወጣውና የሚገባው አለቃውም እንዲታወቅ ወስላታ እንዲጠፋ (ፓስፖርት ማለት) የምስክር ወረቀት እንዲይዝ ፡ ያለዚህ ማንም ሰው በከተማ እንዳይቀመጥ አጉብኛለሁ ። የቸርቻሪዎችም አዋጅ እየጠነከረ የንጉሥ አዋጅ እየፈረሰ ተናድጃለሁና አንድ ሁለቱ ተይዘው በብርቱ ቅጣት ቢቀጡ ይሻል ይመስለኛል ። ደግሞ ዋናው ሐሳቤ ያገሬን ጠረፍ ዞሬ ዞሬ ከትግሬ ጠረፍ ስደርስ የምሰራው ነበረኝ ግን ወሬውን ሰምቻለሁና ላውጋህ ከበሩ ጥቂት እልፍ ብሎ ብዙ ወርቅና ብር የሞላበት ቦታ አለ ይላሉ በወታደርነት ሔዶ ብዙ ወርቅና ብር ያገኛል ነገር ግን የሔደው መመለሱን እንጃ ብለውኛል ምሳሌ ምዕ ፲ ቍጥር ፲፰ ።

የባለጠጋ ገንዘብ ለርሱ የጸናች አገር ናት የድኆች ጥፋት ግን መሻታቸው ነው ደግሞ ምሳሌ ምዕ ፳፩ ። ቍጥር ፫ ። የትጉ ሐሳብ ሁልጊዜ ለጽጋብ ነው ለከብት የሚፈጥን ሰው ግን ብቻ ለመጉደል ነው ይላልና ወንድሞቼ በዚህ ምክንያት እንዳያልቁ ለዚህ የሚሆን ነገር አስባለሁ አለው ። አቶ ልቡናም ሩቅ ጉዳና ለምን ታስባለህ ጥበብ እዚህ ባጭሩ አታስረዳህም ቢለው ። ካገኘሁ ነውን አለው ። ጥበብም መናገር ጀመረች ምሳሌ ፺ ። ቁጥር ፲ ። ተግሣጼን ውሰዱ ። ብርም አይደል ። ከምዝምዝ ወርቅም ይልቅ እውቀትን ምረጹ ። ጥበብ ከሉል ትበልጣለች ። ያማረ ነገር አይተካከላትም ፤ እኔ ጥበብ በምክር ተቀምጫለሁ ። የእውቀትንም ሐሳብ አግኝቻለሁ ብላ ተናግራ ወዲያው ከንዱ አገር ወዳንዱ አገር የሚተላለፉ ሰዎች እንደምን ይሄዳሉ አለችው ። መልካም ሐሳብም እናቴ ጥበብ ሆይ አንቺ እስረጂኝ እንጂ እኔ ምን አውቃለሁ አላት እርሱዋም በመልካም ቃል ከንጉሥ ቃል ወጥቶ የሚተላለፍ የለምና በፈቃድ ይሄዳል ፤ አዛገሩም የምስክር ወረቀት ይባላል አለችው ይህማ ከሆነ እናቴ ኢትዮጵያ የሰሎሞን ምሳሌ የሆነ ልጅ ወልዳለች እሳዳጊውም ጥበብ ነሽ ፣ ስለምን እቸገራለሁ አውሮፓን ጐብኝተው የመጡ ወዳጆች አሉት እነሱን አተጋለሁ አላት ፡ ከዚህ ወዲያ አቶ ልቡና የሁሉንም ነገር መርምሮ መልካም ሐሳብን አገር እንዲጐበኝና እንዲያለማ ፈቶ ለቆ ክፉ ሐሳብን ታስሮ እንዲኖር አደረገው መልካም ሐሳብም እቤ አዓቅብ አፉየ ከመ ኢይስሐት በልሳንየ ወአንበርኩ ዓቃቤ ለአፉየ ሶበ ይትቃወሙኒ ኃጥአን ከፋት ። ምቀኝነት ። ተንኰል ። ቅንዓት ቅድሜየ የሚለውን ንባብ እየደገመ ። ደግሞ ኢትሚጦ ለልብየ ውስተ ነገር እኩይ እያለ ወደ እውቀት ተራራ ሔደ ፡ ብፁዕ ዘይሴቡ ።

በቀለ ኃይለ አጋዕዝት ዛ ።

ስለ ነጋዴዎች ነገር ።

ብዙ ነጋዴዎች የበሬ ቆዳ የበግ ቆዳ የፍየልና የነብር ቆዳ ይህነን የመሰለ ብዙ የንግድ ዕቃ ሁሉ ከጐጃምና ከቤጌምድር በየዙሪያው ካለ ዳር አገር ሁሉ ትርፍ እናገኛለን ብለው ይዘው መጥተው ከደላላና ከታጁሩ ቤት ይህነኑ ያመጡትን ዕቃ ለመሸጥ ይገቡና ግማሹ ገንዘቡን ጀምሮልን ጨርሶ ሳይሰጠን ቀረ እያለ ግማሹም አንድ ብርም ሳይሰጠን የገዛበትን ገንዘብ ከለከለን እያሉ ብዙ እሩቅ አገር ነጋዴዎች ያነን ሰው ለመክሰስ ይመጡና ከብቶቻቸውን የሚያበሏቸው አጥተው እነሱም ከሀገራቸው ሲመጡ እቃችንን ቶሎ ሸጠን እንመለሳለን እያሉ ብዙ ስንቅ ሳይዙ መጥተው በመካከሉ እንደዚህ ያለ አደጋ ነገር እያገኛቸው እንኳንስ ትርፍ ገንዘብ አትርፈው ይዘው ሊሄዱ እነሱም የሚበሉት አጥተው ገንዘባቸውን ትተው እንዳይሄዱ ቸግሯቸው እንደዚህ ባለ ነገር ተጨንቀው የተቀመጡ ሰዎች አሉ ። ይልቁንም ከ፲፱፻፲፱ ዓመተ ምሕረት ከመስከረም ወር ጀምሮ እንደዚህ ባለ ነገር ከሳሹ በዝቷል ለዚህ እንደሚያስፈልገው ነገር ደምብ ቢደረግበት መልካም ነው ።

እንደኔ እንደራሴ ሐሳብ ግን ቀጥሎ የተጻፈው ቢሆን ደግ ይመስለኛል መጀመሪያ ማናቸውንም የንግድ ዕቃ ሁሉ ለመንግሥት ሚዛን የዘረጋ የውጭ አገርም ሰው የኢትዮጵያም አገር ሰው ሆነ ማናቸውንም የንግድ ዕቃ ሲገዛና ሲሸጥ ገንዘቡን ለገዛበት ሰው መስጠቱን የሚመሰክርለት ጉርድ ከጉምሩክ መቀበል ይገባዋል ። ይኸውም ስለተባለ ከውጭ የንግድ ዕቃ ይዞ ነጋዴ ሲመጣ በፊት ዋጋውን ተነጋግሮ የተስማማው እንደሆነ ወደ ጉምሩክ ሄደው ገንዘቡን እጉምሩክ ተቀብሎ ገንዘቡን በትክክል በሰጠ ጊዜ ያ የጉምሩክ ሠራተኛ የገዛበትን ገንዘብ በትክክል መስጠቱንና ነጋዴውም መቀበሉን የሚመሰክር ጉርድ መስጠት ነው ። ይህም ስለተባለ እዚያ ጉርድ ወረቀት ላይ ገንዘቡን በትክክል መቀበላቸው እንዲታወቅ ዕቃ የሸጡት ነጋዴዎች ቁጥራቸው ብዙ ቢሆን ነጋድራስ አበጅተው ነውና የሚመጡ ነጋድራሳቸው ይፈርምበት ሁለተኛ በየሀገሩ ያለ ነጋዴ ማናቸውንም የንግድ ዕቃ ለመሸጥ ወደ አዲስ አበባ ሲመጣ ምናልባት ይህነን የንግድ ዕቃ እመንገድ የሚገዙ ሰዎች አይጠፉምና መንገዱ ከቀረበን እዚሁ ሸጠን እንመለሳለን ብላው የጉምሩክ ሠራተኛ በየበሩና በየኬላው ተበጅቷልና ይህነኑ የጉምሩክ ጉርድ የሚሰጥ ሠራተኛ ሳይዝ ሲሸጥና ሲገዛ የተገኘ ሰው መቀጫ እንዲከፍል ደምብ ተደርጎ ይህነኑም ደምብ በሀገሩ ውስጥ ላሉ ነጋዴዎች እንዲያስታውቅ ለሀገረ ገዥው ማስታወቅ ደግ ነው ።

አሁን ባከተማ ውስጥ ለብዙ ደላሎች ነጋዴ ቆዳ ሰም በያይነቱ የንግድ ዕቃ ሁሉ ይዞ ሲመጣ ዋጋውን ተነጋግረው ዕቃውን አራግፎ ገንዘቡን እንሰጣችኋለን እያሉ ነጋዴዎችን ቁጭ አድርገው ያንን የንግድ ዕቃ ለመሸጥ ወደ ቱጃር ቤት ወስደው ትርፍ ቢያገኙ ሸጠው ትርፋቸውን አስቀርተው ገንዘባቸውን ለነጋዴዎች ሊሰጡ ትርፍ ባያገኙ ግን ዛሬ ነገ እንሰጣችኋለን እያሉ ገንዘባቸውን ሳይሰጡ ስላጉላሏቸውና ኑብቶቻቸው በረሐብና በችጋር የሚያልቁባቸው ስለሆነ መቸም ገንዘባችንን በፍቅር አላገኘነውምና በክስ መንገድ እንሂድ ብለው ያለውድ በግድ እንደዚህ ያለ ችግር ስላገኛቸው ለመክሰስ ይመጣሉ ለዚህ ሁሉ የሚያስፈልገው አላይ የተጻፈው ቃል ቢሆን ለገዢም ለሻጭም ለሀገርም ጥቅም ይሆናል ይመስለኛል ።

በልዩ የቆመው የፍርድ ቤት ሠራተኛ ከበደ ገሠሠ ።

ለባልና ሚስት የተሰጠ የክቡር ቄስ ምክር

አሥሩ ትእዛዞች

መጀመሪያ ክፍል ለሴቶች

፩፤ የጋብቻችሁ ጊዜ ሲደርስ ለመጋባት የለመንዋችሁን ባሎች የሚስማማችሁና የሚሆናችሁን መሆኑን በጥቂቱ እስከ ፯ ወር ድረስ መመርመር ይገባችኋል

፪፤ ከጋብቻ በኋላ ባልን ደስ ማሰኘትና መለማመጥ ይገባችኋል እስከ ጊዜ ሞታችሁም ድረስ ለባሎቻችሁ የታመናችሁ መሆን ይገባችኋል በሰው ፊትም ከማክበር ይልቅ ፍቅራችሁን መግለጽ ነው

፫፤ በዘመዶቻችሁ ፊት የባሎቻችሁን ፍቅርና ክበሬታ አትርገጡት ሁለጊዜ የባሎቻችሁን ዘመዶች ባላችሁ አቅም አክብሯቸው

፬፤ ሁልጊዜ ባሎቻችሁን ይሀን ግዛልኝ ይሀን ግዛልኝ በማለት አታስቸግሩ ለቤታችሁ የሚያስፈልገውን ሁልጊዜ ከባሎቻችሁ ጋራ ተማከሩት ።

፭፤ በባሎቻችሁ ላይ ማዘዝ ሥልጣን አይኑራችሁ ገንዘብም የራሳችሁ ቢኖራችሁ አለፈቃዳቸው ይኸን በገንዘቤ አደርጋለሁ አትበሉ ባሎቻችሁ እኪበሳጩ ድረስ መላስ አታብዙ

፮፤ ልጆች ቢኖሯችሁ ሁልጊዜ ንጹህ እዲሆኑ የሚያስፈልጋቸውንሁሉ አድርጉላቸው እንዲያገለግሉም ደህና አድርጋችሁ ቅጧቸው በኋላ መልክም አስተዳደግ እንዲኖራቸው

፯፤ በቤት ውስጥ ዋና ሠራተኛ መሆን ይገባችኋል ።

፰፤ ልጆቻችሁ ፰ ዓመት እስኪሆናቸው ድረስ እንዲያስቡ አሳቢዎች እንደሆኑ አድርጉ ደግሞም መልክም ምሳሌ ሁልጊዜ አስተምሩአቸው በልጆቻችሁ ፊት ባሎቻችሁን አታስቆጡ ልጆቻችሁ አምስት ዓመት ከሆናቸው በኋላ በመልክም ተማሪ ቤት እንዲገቡና የመጀመሪያው ትምርታቸውን ጨርሰው ከትልቁ የጥበብ ተማሪ ቤት (ኡኒቢርሲቴ) ገብተው (ዶክቶርነት መሐንዲስነት) ይህን የመሰለ ሥራ እንዲማሩ ባለ ዓቅም መጣር ነው ። ባሎቻችሁም ልጆቻችሁን እንዲወዱዋቸው ማድረግ ነው በቤታችሁ ውስጥ የቤተ ዘመድ ፍቅር እንዲመላ አድርጉ ።

፱፤ ጋብቻችሁ በቤተ ክርስቲያን ፈቃድ እንዲሆን ውደዱ በቤተ ክርስቲያኑም ውስጥ የሰጠሽውን ቃልሽንና በእግዚአብሔር ፊት የተሰጠሽን ፈቃድ ፈጽሚ

ሁለተኛ ክፍል ለወንዶች ።

፩፤ ሚስት ለማግባትና ንብረት ለመያዝ የምትችሉ እስክትሆኑ ድረስ አታግቡ አባቶቻችሁ እንኳ ሐብታሞች ቢሆኑ ገንዘቡ የናንተ አይደለም ያባቶቻችሁ ነው እንጂ የሚጋባ በሽታ ያለባችሁም እንደሆነ እስክትድኑ ድረስ አታግቡ ስታገቡም ከእኩያችሁ ወይም በእድሜ ፲ ዓመት ከናንተ የምታንስ አግቡ ዕድሜአችሁ በዝቶ ከትንሽ ልጅ ጋራ ብትጋቡ በጕርናፍ መንገድ ላይ አትክልት እንደ መትከል ያለ ነውና ።

፪፤ ሚስቶቻችሁን በተቻላችሁ መጠን ውደዱ አፍቅሩ ዘመዶቻቸውንም አፍቅሩ አክብሯቸው ካንተም ዘመዶች ራቅ ብለህ ተቀመጥ ።

፫፤ በቤታችሁ ብቻችሁን ተቀመጡ እንጂ ደባል አታስቀምጡ ይህ ላንተና ለሚስትህ አጉል ነውና ።

፬፤ ሚስቶቻችሁን የሚያስፈልጋቸውን ነገር በተቻላችሁ መጠን አታሳጧቸው

፭፤ በውጭ ያደረጋችሁትንና የሆናችሁትን ሁሉ ለሚስቶቻችሁ አትንገሩ

፮፤ ለሚስቶቻችሁና ለልጆቻችሁ ብቻ ኑሩ መንግሥት በቤተ ዘመድ ነውና የሚቆመው ።

፯፤ በሚስቶቻችሁ ሥራ ላይ አትግቡ አትደባለቁ ።

፰፤ ሐሳባችሁ ሁሉ ለልጆቻችሁ ይሁን መልክም አስተዳደግ እንዲያገኙ ።

፱፤ በአሽከሮቻችሁና በልጆቻችሁ ፊት ሚስቶቻችሁን አትገሥፁ ።

፲፤ አንድ ጊዜ ሚስቶቻችሁን ካመናችኋቸው አትጠርጥሯቸው ነፃነት ስጧቸው ሁል ጊዜ እንዳትጨቃጨቁ ።

እኒህ ክቡር ቄስ የሰጡንን ትእዛዝ ባልና ሚስት የሆኑ ሰዎች ቢፈጽሙ አሥሩንም ሳያጕድሉ ጸጥ ያለ ደስ የሚአሰኝ ኑሮ ያገኛሉ መንግሥትንም ይደግፋሉ ያቆማሉም ።

ካርቴን ባቢክያን ።

የቀድሞ የመስኮብ ንግሥት ።

ምሥጢር የሆነ የሕይወት ታሪክ ።

መጀመሪያ ክፍል ።

በሺ፱፻፲ ዓ ም ሐምሌ ፲፩ቀን (በኤሮፓ ቁጥር) ታይምዝ በሚባለው የእንግሊዝ ጋዜጣ አንድ አንድ ምሥጢር ያለው ወሬ ተጽፎ ነበረ ።

ታላቁ የሎንዶን ከተማ ዳኛ አንድ ዳኝነት አድርጎ ነበረ ይህም ዳኝነት ባንድ እራሱን በመርዝ የገደለ ሰው ላይ ሆነ ። ይህም የሞተ ሰው ገና ወጣት ልጅ እግር ነበረ መልኩም አለመጠን የተዋበ ነበረ ስሙ ዳንት ይባላል ፥ ራብን በሚባለው ሆቴል ሙቶ ተገኘ ።

ይህ ሰው የውጭ አገር ሰው ነበረ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ወደ ሎንድር መጣ ።

ሊሞት ፩ ቀን ሲቀረው ወደ ጀርመን አገር በጀርመን ቋንቋ ፩ቴሌግራም አሳለፈና ወዳረፈበት ቤት በእኩል ሌሊት ገባ በማግሥቱ ዘበኞችና ባለ ሆቴሉ በሩን በግድ ክፍተው ቢገቡ በሚጽፍበት ጠረጴዛ ላይ ሙቶ ሰውነቱ ደርቆ አገኙት በቤቱ ወለል አሳንቃው ላይ አንዲት ትንሽ ቢልቃጥ የተረፈው የመርዝ ጭላጭ የነበረባት አገኙ እሬሳው በተጋደመበት አጠገብ ደግሞ ከጠረጴዛው ላይ ሳይሞት በሕይወቱ ሳለ የጻፈው አንድ ወረቀት በአምቦሎፕ የተዘጋ አገኙ ዳኛውም ይህ ወረቀት እንዳይነበብ ከለከለ ለሕዝብ የሚረባ አይደለም ብሎ ።

የእንግሊዝ ጋዜጣ የጻፈው ይኸነኑ ብቻ ነበረ ቢሆንም ይህ ነገር የሞት ታሪክ ያለው የማይረሳ ነው ግን የእውነተኛው ነገር የሆነ እንደሆነ ይህች ማስታወቂያ ምሥጢር ያላት ነገር እንደሆነች ታመለክታለች ይህን ምሥጢር የእንግሊዝ መንግሥ ቢገልጸው ኖሮ በጀርመን አገር የቤተ መንግሥቱ ክብረት ይዋረድ ነበረ የጋዜጣው አንባቢዎች ሁሉ ይህ ምሥጢር እንዲገለጽ ይፈልጉ ነበረ ግን መገለጹ አልተቻለም ሕዝቡም ይህ ሰው ዘሩ ምን እንደሆነ ለማወቅ ይፈቅዱ ነበረ የእንግሊዝ ቋንቋ አስተካክሎ ያውቅ ነበርና ።

ይህ ሟቹ ሰውዬ ሆቴል ሲገባ ስሙን በሆቴለኛው መዝገብ ቻርልስ ዳንት ብሎ ጽፎ ነበረ ነገር ግን ምንም ስሙ ቢገኝ ዋናው የከተማ ዳኛ ከሞቱ በፊት የጻፈውን ወረቀትና ወደ ጀርመን አገር ያሳለፈውን ቴሌግራም ቃል ለመግለጽ አልወደደም ይህ ነገር ቢገለጽ መልክም ነበር የእንግሊዝ መንግሥት አልወደደም እንጂ ። የተሰበሰቡትም ዳኞች የዚህን ሰው ውልደቱንና አገሩን ወይም ሥራውን አልመረመሩም ነበረ ብቻ በምን ምክንያት ራሱን እንደገደለ ይመረምሩ ነበሩ እንጂ ነገሩን በሚመረምሩበት ቤት መጋረጃ ስለ ነበረ ከውጭው ያለ ሰው አንድም የሰማና ያወቀ አልነበረም ከዚያም በተለየ የዚህን ነገር ለመጠየቅና ይህቺን ብርቅ የሆነች ወረቀት ከዳኛው እጅ ለመቀበል ከምሥጢር ጽሕፈት ቤት በዋናው ሹም ትእዛዝ የመጣ የምሥጢር ጽሕፈት ቤት ሥራ ሹም ከመጋረጃው ውጭ ቆሞ ነበር

ደግሞ ባንድ በኩል አንድ ሰው ከጀርመን አገር ወደ እንግሊዝ አገር ላለው ወዳጁ ይህ የሞተ ሰው ደህና ሆኖ እንዲቀበርና በመቃብሩም ላይ ፩መስቀል ተደርጎ ከመስቀሉ እግርጌ የቻርል፡ዳንት ማስታወሻ ቻርል ዳንት ባ፲፰፻፺፯ ዓ ም ሐምሌ ፫ቀን ሞተ የሚል ጽሕፈት እንዲጻፍበት ብዙ ገንዘብ በቴሌግራም ላከለት ።

የእንግሊዝ ሕዝብ ከቤተ መንግሥቱ በተቀር የሚያውቀው ከዚህ በላይ የተጻፈውን ነገር ብቻ ነው ።

እኔ ዛሬ ይህን ምሥጢር ለመግለጽ ተሰናድቻለሁ ። ይህንኑም ምሥጢር ሳልገልጸው በፊት በአንባቢዎች ፊት ለመግለጽ እለምናለሁ ።

አባቱ ዱክ ካማንስኪ ይባል ነበረ ዘሩም መስከብ ነው ። ካዘን በሚባለው አውራጃ ተወለደ ከ፩ዓመት ይበልጥ በጀርመን አገር በቤተ መንግሥቱ በሄስ ግቢ ዋና ደጅ አጋፋሪ ነበር እኔም አባቱ በዚያ አገር ይኸን ያህል ማእርግና ክበሬታ ስለነበረው በልጅነቴ ትንሽ ሆኜ አልጋ ወራሽቱን አልክሰን ለመተዋወቅ ቻልሁ ይህቺም አልክስ የእንግሊዝ መንግሥት የታላቂዋ የቢክቶሪያ ልጅ ናት እርሱዋም በኋላ የመስከብ ንግሥት ሆነች።

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል

ስለ ገፈርሳ ወንዝ ድልድይ ሥራ ።

ገፈርሳ ወንዝ ከአዲስ አበባ ተነስቶ ወደ አዲስ ዓለም ሲሄዱ በአቶሞቢል ሃያ ደቂቃ ያህል የሚያስሄድ በታ ነው ይህም ወንዝ ከዚህ ቀደም በታላቁ ንጉሥ ባፄ ምኒልክ ጊዜ ድልድይ ተሠርቶበት እስከ ጊዜው ድረስ ብዙ አገለገለ ግን አሁን በቅርቡ ስለ አረጀ ብርቱ ጐርፍና ዝናብ አፈረሰው ። በዚሁ ምክንያት ወደ አዲስ ዓለምና ከዚያ አልፎ ለሚሄድ ነጋዴና መንገደኛ ዝናብ በሚዘንብበት ወራት ለመሸጋገር ብዙ ችግር ሆኖ ነበር ይልቁንም በአቶሞቢል ወደ አዲስ ዓለም በፍጥነት ለመድረስና በጋሪና በካሚዮን ዕቃ ለማስመጣት በጣም ችግር ነበረ።ስለዚህ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ደኅና ሆኖ በኖራ እንዲገነባና እንዲሠራ አደረጉና አሁን በቅርቡ የድልድዩ ቅስት ተፈጸመ ። ከቅስቱ በላይ ቁመቱ ብዙ ከፍ ያለ ነውና ከመንገዱ ልክ እስኪተካከል ድረስ ብዙ ደንጊያና አፈር የሚያስፈልገው ስለሆነ ያዲስ አበባ መኳንንትና ሠራዊት ታዘ ሄዶ ሥራውን እየተከፋፈለ ከሰኔ ፬ቀን ጀምሮ እስከ ፲፩ ቀን ሲሠራው የሰነበተ እጅግ ያስገርማል ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንም ሠራዊቱን ለማተጋጋት ሥራውንም ለማየት ዘወትር ይመላለሱ ።

መኳንንቱና ሠራዊቱም የኔ ይብለጥ የኔ ይብለጥ እያለ በሥራ ሲቀዳደም ለሚያየው ደስ ያሰኛል እንዳሁኑ እያያዘ ወይም ፯ቀን የተሠራ እንደሆነ ይፈጸማል ብለን ተስፋ እናደርጋለን

በከተማ ያለው ትንሽ ሠራዊት በሁለት ሳምንት ይህን ያህል ሥራ የሚሠራ ከሆነ በየአውራጃው ያለ የኢትዮጵያ ሠራዊት በያለበት ስፍራ ዓመት ሙሉ እንደዚህ ቢሠራ ስንት መንገድ በቀና ይሆን ? ።

እንደዚህ ሆኖ በያውራጃው መንገድ እንዲሠራ የልዑል ጌታችንና የክቡራን መኳንንቶቻችን ሙሉ አሳባቸው እንደሆነ አይጠረጠርም ።

የዘበኛ መታመን ።

አንድ የከተማ ዘበኛ ያምሳ አለቃ ።

በሰኔ ፱ ቀን በሥራው ላይ ያደረገው ነገር እጅግ ደስ የሚያሰኝ ነገር ነው ከአንድ ሰዓት ተኩል በኋላ በአራዳ ውስጥ ፫ትና ፬ የሚያህሉ ሰዎች አገኘ ። አንደኛው ነገሩ ገና ሳይመረመር ቸኩሎ ፈርቶ እባክዎ ወደ እሥር ቤት አይስደዱኝ ብሎ ሰላምታ እንደሚሰጥ አርጎ በእጁ ላይ አንድ ብር ሰጠው ። ይህም አስተዋይ ዘበኛ የሰውነታቸውን ልክ አየና ሁለተኛ አይድገማችሁ ሰዓትም እንዳታሳልፉ ። አንተም ገንዘብ በእጄ ላይ ያረግህልኝ ሰው የሰውነትህን ልክ ነው እንጅ የምፈልግ ገንዘብህን አልፈልግም ጊዜው በጣም ስላልመሸ እለቃችኋለሁ ግን

ያለ ጊዜው ባልሆነ ቦታ ባገኛችሁ ገንዘብም ብትሰጡኝ አልቃችሁም የምሠራውም ለመንግሥት ነው እንጅ ጉቦ አጠራቅሜ እንድበላ አይደለም ብሎ ገንዘቡን በነበሩትና በዘበኞች መካከል ሰጥቶ ሸኝቶ ሰደደው እንዲህ ያለ መልካም ሥራ የሚያስመሰግናልና እጅግ መልካም ነው ።

ማስታወቂያ

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆን ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲	ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲	ብር
ደግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፭	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር	፱	ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫	ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
ጎሐ ጽባሕ	፭	ብር
ፊደልና ፊደል ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፪	መ
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫	ብር
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪	ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪	ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትርሜጓው	፪	ብር
የሕይወት ታሪክ	፪	ብር ተኩል
የቁጥር ትምርት	፩	ብር
ያማሪኛ ሰዋስው	፩	ብር
ወዳጄ ልቤ	፩	ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን		አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ		አላድ
አጭር የዓለም ታሪክ		አላድ
ያማሪኛ ፊደል		ሩብ
አሳብና ምኞት		ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት		ሩብ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር	፪	መ
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ		ሩብ

ማስታወቂያ ።

የንለም ጅዖግራፊ በአማሪኛ የታተመ በልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ይሸጣል

ደኅና ሁኖ የተጠረዘ ዋጋው	፯ ብር
መናኛ ጥራዝ ዋጋው	፭ ብር

የአዲስ አበባ ገበያ ።

የቀንድ ከብት

የሚታረድ በሬ ዋጋ	፺ ብር
የአርሻ በሬ	፴፫ ብር
ያሩሲ ድልብ በሬ	፺፫–፻ ብር
የምትረባ ላም	፴፫ ብር
መሲና ላም	፴፪ ብር
የምትረባ በግ	፫ ብር
መሲና በግ	፭ ብር
ሙክት በግ	፲፫ ብር
የምትረባ ፍየል	፬ ብር
መሲና ፍየል	፯ ብር
ሙክት ፍየል	፲ ብር

የጋማ ከብት

ሰንጋ ፈረስ ዋጋው	፹፫ ብር
በዝሬ ፈረስ	፳–፳፭ ብር
አጋሰስ ፈረስ	፳፯ ብር
የከርቻ በቅሎ	፻፺ ብር
ስናር ዓይነት በቅሎ	፻፹ ብር
አጋሰስ በቅሎ	፸ ብር
የምትረባ አህያ	፲፯ ብር
የጭነት አህያ	፳፯ ብር
ዶሮ ዋጋው	ከሩብ–አላድ
ዕንቍላል ሠላሳ	፩ ብር

የእህል ገበያ

ስንዴ ፩ ጆኒያ	፲፪ ብር
ገብስ	፱ ብር
ጤፍ	፲፫ ብር
ሽንብራ	፲ ብር

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፩ ብር ተሶስት ሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፫ ብር ተሩብ
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳ ብር ተኩል
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፴ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፰ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፰ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፰ ብር ተኩል
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፺፪ ብር
፡፡ ባለሰይጣን	፡፡	፻፺፩ ብር
፡፡ ባለ ድመት ።		፻፺፬ ብር
፡፡ ባለአህያ	።	፻፹፰ ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል	።	፻፴፫ ብር
ባለ አንበሳ	፡፡	፻፺፫ ብር
ሱካር	፩ ጁኒያ	፴ ብር
ቻይ	፩ ነጥር	፫ ሩብ ከሁለት መ

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ ፲፭ ሳንቲም
አንድ ብር	ሊሬ ፳ ከ፳ ሳንቲም
በአንድ ጊኒ	፲ ብር ፯ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፬ ብር

A LOUER

COGNAC S.&E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



የ እ ጅ ሰ ዓ ት ዝ ኒ ት ።

በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

RUGBY

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆን በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፣በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ማስታወቂያ ።

ሺብሮሌ አቶሞቢል በኢትዮጵያ ወኪል ።
ሔ ሜ ዜርቦስ ኩምፓንያ ።



Automobiles CHEVROLET

H. M. ZERVOS & C^ie^
REPRESENTANTS
BAS PRIX HAUTE QUALITE

ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል ። ሙዚቃም በየ ዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል ።

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ ኦቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።



አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባ ኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባተሪ ነው ክምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እና ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል «ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው

ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ ።

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህ በካፕሱሉ ያለ ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በካፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ጉድይር ግዙ





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው።በሌላጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ፤ ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

አራተኛ ዓመት ፣ ቁጥር ፳፮
4 me ANNÉE № 26

ሐሙስ ሰኔ ፳፩ ቀን ፤ ፲፱፻፳ ዓ ም።
JEUDI 28 JUIN 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir **regner** dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ሰለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres



የአዲስ አበባ ሠራዊት የገፈርሳን ወንዝ ድልድይ ሲሰራ



ግርማዊት ንግሥት ነገሥታት ዘውዲቱና ልዑል የኢ መ እ ወ ተፈሪ መኰንን የገፈርሳን ወንዝ ድልድይ ሥራ እንዳዩ

(ጀርመን ፎቶግራፍ አንሺ ጉስሌ)

የክቡር ቄስ የሚያስቅ አማርኛ ያለው ንግግር

እወዳጄ እክበር ቄስ ዘንድ ተነስቼ ሄድሁ ሰላምታም ሰጥቻቸው በቀረበልኝ ወምበር ተቀምጬ ፊታቸውን ብመለከት እጅግ ደስ ብሎአቸው አገኘሁት በልባቸውም ኃዘን ናለም ኑሮ አል ከተቀመጥሁ በኋላ ንግግር ጀመሩ አሉም የተወደድህ ወዳጄ ካፒቴን ሆይ የዛሬው ንግግራችን የአገር ጠቀሜታ የሥልጣኔ የተማሪ ቤት አይደለም ግን ቢሆነም እንዲያዳምጡኝ እለምንዎታለሁ ዛሬ በምሥራቅ የተደረገው ትንንሽ ጭውውት አጫውትሃለሁ ባንድ የቱርክ እስላም ተማሪ ቤት ፩ ቀን አንድ ተማሪ ላስተማሪው እንዲህ አለው ክቡር ሆይ ትላንትና ሌሊት በህልሜ ከእግርዎ ጀምሮ እስከ እራስዎ በማር ውስጥ ጠልቀው አየሁ ደግሞ እኔ ባንድ አዛባ ውስጥ ጠልቄ አየሁ አስተማሪውም የህልሙን ፍቺ እንዲህ ብሎ ነገረው ልጄ ሆይ ይህ አይገርምም እኔ ጻድቅ ነኝ አንተም ኀጢአተኛ ነህ ያም ተማሪ መልሶ አለ ይፍቀዱልኝ ህልሜን ጨርሼ ልንገርዎ ንገረኝ ፈቃዴ ነው ብሎ አስተማሪው ለልጁ ፈቀደለት ተማሪውም ልጅ የህልሙን መጨረሻ ነገር እንዲህ ብሎ ነገረ በመጨረሻው እርስዎ የኔን አካላት ሲልሱ እኔም የርስዎን አካላት ስልስ ዓየሁ

ክቡር ቄስ ይህን በነገሩኝ ጊዜ ሁላታችንም ሆዳችንን እስኪያመን ድረስ ሳቅን ።

ይህ ብቻ አይምሰልህ ወዳጄ ካፒቴን ሆይ ደግሞ አምሳ ሴቶች የመልካም ሥራ ማኅበር ለማቆም ፈቀዱ ለዚሁ ሥራ ምክር ባንድ አዳራሽ ውስጥ ተሰብስበው ከማኅበሩ ውስጥ ፩ ዋና የማኅበር አለቃና ፩ ዋና ጸሐፊ ለመሾም አሰቡ ከዚህ በኋላ ከሁሉም በዕድሜ የምትበልጠዋን ዋና የማኅበር አለቃ እንድትሆን ደግሞ ከሁሉ በዕድሜ የምታንሰዋን ዋና ጸሐፊ ለማድረግ ቁርጥ ነገር አደረጉ ። ወዲያው ከሁሉ በዕድሜ የምትበልጥ ሴት ትነሳና ትቁም ተባለ ግን አንድም ሴት የተነሳች የለችም ደግሞ ከሁሉ በዕድሜ ያነሰች ትነሳ ሲባል ሁሉም ባንድ ጊዜ ተነሱ ። ይህንንም በሰማሁ ጊዜ ሁለታችንም ረጅም ሳቅ ከሳቅን በኋላ እንዲህ አልኳቸው ሴቶችን ዕድሜአቸውን አለመጠየቅ ነው ምንም ቢሆን እውነት አይናገሩም ክቡር ቄስ ቀጥለው ደግሞ ሌላውን አመጡ የቱርክ ንጉሥ ዳግማዊ ሱልጣን መሐመድ ለእንግሊዝ ንግሥት ብዙ ዋጋ ያለው ፪ የጆሮ ጉትቻ መተያያ ላከላት እርስዋም በእንግሊዝ አገር ያለው የቱርክ ቆንስል በቀረበላት ጊዜ በደስታ ተቀበለችና እግዚአብሔር ይስጥልኝ ግን ሱልጣን ሌላ ነገር እንደመላክ ስለምን ጉትቻ ላኩልኝ ብላ ጠየቀችው የቱርኩም ቆንስል ልዑል ሱልጣን ይህን መላካቸው የምሥራቅ አገር ነገር ከጆሮዎ እንዲንጠለጠል ብለው ነው ብሎ መልስ ሰጠ ።

በዚህ ከሳቅን በኋላ ፩ ሐጂ ስራቴን (የእስላም ቄስ) ፩ ቀን ከልጁ ጋራ በመንገድ ሲሄዱ ብዙ አጀብ ሆኖ እሬሳ በሳጥን ተሸክመው የሚሄዱ ሰዎች ተጋጠሙ ከነሱም መሐከል ፩ ዘመዱ የሆነ አለመጠን እየጮኸ ያለቅስ ነበር እንዲህ እያለ ዛሬ ማታ እንጀራ ከሌለበት አልጋ ወደ ሌለበት ብርሃን ወደ ሌለበት ወኃ ወደሌለበት ወዳጅ ወደ ሌለበት ስፍራ ይወስዱሃል ይህን ጊዜ የዚህ የሰላም ቄስ ልጅ አባባ ይህን ሰው ወደኛ ቤት ሊያመጡት ነውን ብሎ ጠየቀው ድሆች ነበሩና ።

ደግሞ ካፒቴን ሆይ አንድ ሰው አንዱን ገንዘብ አበድረኝ ቢለው ባለገንዘቡ አልሰጥም ብሎ ቢከለክለው ክሶ ወደ ዳኛ ወሰደው ለዳኛውም እንዲህ ብሎ አመለከተ ጌታዬ መቶ ብር አበድረኝ ብላው ከለከለኝ ዳኛውም ምስክር አለህ ወይ ሲል ጠየቀው ተበዳሪው ምስክሬ እግዚአብሔር ነው ብሎ መለሰ ቀጥሎ ይህ ዳኛ ባለገንዘቡን ይህ ሰው ለሚልህ መልስ የለህም ምነው ዝም አልክ አለው ያም ባለገንዘቡ ለዳኛው እንዲህ ሲል መልስ ሰጠ ይህ ባላጋራዬ ፩ ምስክር ዳኛው ሊያውቀው የተገባ ጠርቷል።

ከዚህ ንግግራቸው በኋላ ክቡር ቄስ ዛሬ ስለምን እነዚህ በምሥራቅ የተደረገ ታሪክ የሚናገሩ ምን ቢያስቡ ይሆን አልኳቸው እሳቸውም መለሱልኝ ወዳጄ ካፒቴን ሆይ በየሰምንቱ ደስ እንዲለን ያስፈልገናል ደስ የሚያሰኝ ነገርና የሚያስቅ እንደ ሙዚቃ ያለው ሁሉ የሰውን ሐሳብና ራስ ያበረታል ይልቁንም በክረምት ማታ ማታ የሚያስፈልግ ነው

አዬ ክቡር ቄስ ይህስ አይመስለንም ከላንት ብዙዎች ሰዎች ማታ በቶሎ ይተኛሉ ለነገ ይህን እናደርጋለን ብለው እያስቡም ሌሊቱን ሁሉ በጤና ተኝተው ያነጋሉ ብዬ በነገርኳቸው ጊዜ በቁጣ አስተያየት ተመለከቱኝና በቁጣ ቃል በውሸት ስማችንን ታጠፋለህ ሁለተኛ እንዲህ ያለ ነገር አይልመድህ እኛስ ብዙ ንቁዎችና ይልቁንም ፩ አለን ለነገ ለተነገወዲያ ብቻ የማያስብ ወደ ፊት ለትውልደ ትውልድ የሚያስብ አለን

ካፒቴን ባቢኪያን ።

ኢትዮጵያ ልታደርገው የሚገባ።

ሀገራችን ይዛው ባለች ሃብትና ማዕድን እንመካባታለን ። እውነትም እንደ ለምነቷና በውስጥዋ የሚገኘውን ነገር ሁሉ ሠሬና አሠሬ ተስማምተው መሐንዲስ እያቆሙ ቢያከናውኑዋት አገራችን እንኳን ለልጆችዋ መጦሪያ ያንሣት ራሱዋን ችላ ለሌላም ትተርፍ ነበር ።

አሁን ግን ዋና ከተማችን በልጆችዋና በሌሎች በየ ሳምንቱ ከሚመጡት ከውጭ አገር ሕዝብ ቁጥሩዋ እየበዛ ስለ ሔደ በዙሪያዋ ካሉት አገሮችና መንደሮች የሚመጣው እህል ሸመቱ አንሶት ከተመኛው የእንጀራ ችግር በዝቶበታል ረኃብም እንገላትቶታል ።

ለዚህም ነገር መንግሥታችን ሕዝቡ እንዳይጐዳበት የማዘጋጃ ቤቱን ሥርዓት እንደ ጊዜው አይቶ እያሻሻለ ቢሔድ ላገራችን ታላቅ ረድኤት ይሆናል ። ይልቁንም ወታደሮች አርበኞች ወንድሞቻችን አገራችን ጠላት እንዳይገባበት ደማቸውን አፍስሰው አጥንታቸውን ከስክሰው እንደ ጻድቃን ሰማዕትነት ሊያልፉላት ተሰናድተው ያሉትን ፤ የወር ቀለባቸው ከያሌ ዓመታት በፊት አራትና አምስት ብር የተቆረጠው አሁን የሚቀበሉት የዕለት ምግብ እንዳልበቃቸው ረኃብም እንደ ሚያንገላታቸው ከብዙ ሰዎች አፍ እንሰማለን ። ሐሰት እንዳይባልም እርሻ የሌለው ሰው ደመወዘኛ ብቻ የሆነ ከሁለት ሶስት ዓመት

በፊት የነበረ ግዢ በማናቸውም ነገር ሁሉ ባሁኑ ጊዜ ባለው ግዢና ሽመት ቢያነጣጥረው ማነሱ ጉልህ ሁኖ እንደሚታየው አይጠረጠርም። እንግዲህ መንግሥታችን የወታደሮቹን ቀለብ ጊዜውን ተመልክቶ በአጠሬታ አድርጎ የሚበቃቸውን እየሰጠ በየሺ አለቃው እያዘዘ በአራት ማዕዘን መንገዶች በመሐንድስ እያስመነጠረ ቢያስጠርጋቸው፥ ሲሳያቸው ከበዛ ራቅ ካሉት አገሮች እህል በካሚዎን ፈጥኖ በመጣልን ጥቅማችን ሲበረክትም ችግር በተወገደልን ፤ ይህም ነገር አሁን በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ እመቤታችንና በልዑል አልጋ ወራሻችን ይህ የሰላም ጊዜያችን ገንዘብ ይቆጠብልን ጓዳችንም ይሙላልን ብለን ወንድሞቻችን ቢማግጡ በረከታችን መሸጋገሪያ አጥቶ ጠላት የመጣ ጊዜ እንደ ሚያጠቃን የታወቀ ነው። ያን ጊዜ ልንሠራ ብንታገልም የእስራኤል ልጆች ኢየሩሳሌምን በቂሮስ ዘመን ቤተ መቅደሳቸውን ሲሰሩ ባሰቡ ጊዜ አሕዛብ በሥራው እንቅፋት ሁነው ያስቸግሯቸው እንደ ነበረ ይሆንብናል። ስለዚህ ጊዜያችንን በሰላም አክብረን ይዘን ብንሠራበት ለጌቶቻችን ከበሬታ ለኛ ጠቀሜታ መሆኑን ከተረዳነው መፋጠን ነው እንጂ እሺ ነገ እያልን ጊዜያችንን ብናሳልፍ ነገ ከነገው መዓትና ቁጣ ሊያድነን አይችልም። ደግሞስ የሐዲስ ጌታችን ተመ ተከታዮች ከሆን በሐዲስ ትእዛዙ ኢትበሉ ለጌሠም ጌሠምሰ ትሔሊ ለርእሳ የአክላ ለዕለት እከያ ይለን የለም ወይ ።

የሚያገድ ነገር በግድ ማድረግ ያልኩት ከሰሪውና ከሰሪው ውድ እንዲጨመርበት ተስፋ እናደርጋለን። አንድ ምሳሌ እንዲህ ይላል ሥራ ለሰው የሚመነጭ የማያልቅ ከብቱና ሕይወቱ ነው። ስለዚህ መንግሥት ወታደሮቹን ዕረፍት አብዝቶ በትንሽ ከማሳደር እነሱም ያንጀታቸውን ብቻ ሲያዋዩ ሲናገሩ ከመኖር በቀኝ በግራ በፊት በኋላ እያለ ከሰኞ እስከ ቅዳሚት ቢያሠራ አገር ይለማል ሕዝብ ይበለጥጋል መንግሥትም ይደረጃል። ወታደሮቹም እንጀራ እንደ ልባቸው በልተው በጤናና በኃይል በርትተው ሕዝቡንና መንግሥትን እያገለገሉ ደስ ብሎዋቸው ቢሠሩ የራብ ሥጋት ባልነካቸውም። አለበለዚያ ግን አምስትና ስድስት ብር ባሁኑ ጊዜ የልብስና የሌላውን ጣጣ ከታ እንኳንና ልጆች ላሉት ቤት ላንድ ምግብ ከቶ አትበቃምና ለሠራተኛ ምግብ ይገባዋል የተባለውን አንዘንጋው ይህ ከተደረገ በኋላ ግን እንደ ሌሎቹ አገሮች የሚበልጡት መንገዶች በወታደር የሚሠሩ መሆናቸውን ብዙ ዘመን አይቶናል ።

በሚሠራውና በሚጠረገው በታም ወንዝ ቢገኝ በስሕ አለቃው ስም ድልድይ ይሠራልና ስሙ በሕዝብና በመንግሥቱ ሲመሰገንና ሲመረቅ ይኖራል። ይህ ካልሆነ ግን ሐዋርያ ጳውሎስ የማይሠራ ሰው አይብላ ሲል ሐኬተኞቹን ይፈርድባቸዋል። ደግሞስ በዓለም ማሕበር መግባታችንና መተባበራችን የማሕበር ጓደኞቻችን የሥልጣኔ አካሔዳቸውን ተከትለን የብርሃንና ሰላም ጊዜያችንን ሳናማልፍ ፋብሪካና ኢንዱስትርያ ጥበብ አቁመን ብንራመድ ነው ክብረት የምናገኝበት እንጂ ጥበብ አልባ ስማችን በዓለም ማሕበር ደብተር ቢፈረም ክብረት አይሆነንም። ምነው እነሱ የምድሩን ስልችተውት የዓየሩንና የሰማዩን ሲመረምሩ እኛ የምድሩን ባንመረምር ምድራችንን ለባዕድ አሣልፈን እንደመቀመጥ ቁጥር ያለ ነው። ጥበብ ብንማርም ሰማንያ የለብንም ጥበብ ትኄይስእምብሩር ወወርቅ አብዳነሰ ይሜንኑ ጥበበ ይላል ጥበበ ሰሎሞን

ረዳ ጻድቅ

በሽታን ማቃለያ ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በሞላው ጤንነቱን ለመጠበቅ ብዙህ ዓይነት በሽታ ከምን እንደሆነ ለማወቅ ያስፈልገዋል።

በሽታ ሲባል ባገራችን የእግዚአብሔር አደጋ ይመስለናል። አደጋ መሆኑ እርግጥ ነው ነገር ግን እኛ የንጽሕናን ደንብ ስላልተማርን ደግሞም የሚነሳበትን ሰበብ ስላላወቅን ነው።

ባገራችን እስከሁን ድረስ አንድም ወይም ሁለት የመንግሥት ሃኪሞች ቢኖሩ ሰው ሲታመም ተማከም በቀር ተበሽታ መራቅ ምን እንደሚሻል ለከተማ ነፃነት ወይም ሕዝቡን ተበሽታ እንዲርቅ ለመንግሥት ያመለክቱ አይመስለኝም ምናልባት ቢበዛባቸው ይሆናል ።

፩ኛ፡ እስከሁንም እንደምናውቀው ተስቦ በሽታ አዲስ አበባንና ሐረርን ያጠቃዋል ምክንያቱም ሕዝብ ስለበዛ ወሃው ንጹሕ ስላልሆነ ነው።

፪ኛ፡ ዓይነምድር በጓሮ በወህ ዳር እየወደቀ ያ ያይነምድር ትል በዝናብ ጐርፍ እየገባ የኛ መጠጥ ስለሆነ ነው በሥራት የንጽሕና ያይነምድር ሠረገላ ስላልተበጀ ነው ።

፫ኛ፡ የምንጭ ወሀ ይልቁንም ወሀ ሲባል የበሽታ መፈጠሪያ ነው ስለዚህ ባገራችን የተስቦ በሽታና ሌላ ዓይነት የሆድ በሽታ የሚነሳው ከዚህ ነው ።

ሕዝብ ሲበዛ በሽታና አድፋት እንዲበዛ የታወቀ ነውና ይህንን በሽታ ለማራቅ ለመጠጥ የሚሆን ወሐ ማጣራት ያስፈልጋል የከተማውን ሕዝብ ተክፉ በሽታ ለማዳን ግን ይህ ሥራ በመንግሥት አንድ ሹም ተሹሞ ሥራውን በሃኪሞች እርዳታና በመሃንዲስ ታልተሰራ ማናቸውም ሰው ሊያረገው አይችልም ደግሞም ለወሐ ማጣሪያ የሚሆኑ ቅመሞች እነዚህ ናቸው

1 chloride of lime 2 lineture of iodine 3 potassium permanganate

፬፡ ወሐውን አፍልቶ መጠጣት ነው ።

፭ኛ፡ ተስቦ የሚነሳው ተድፍ ወተት ነው ስለዚህ ወተቱን አፍልቶ ሲበርድ ለሕፃናትም ወይም ሳደገ ሰው ምግብ ቢያደርጉት ከክፉ በሽታ ይድናል ።

፮ኛ፡ ደግሞ እርጥብ ሥጋ መብላት ዋና በሽታ መሆኑን ልጅ በሻህ ጽፎ ጨርሶታል አሁንም እርጥብ ሥጋ በሽታ ተመሆኑ ይልቅ በውጪ አገር እረመኔ እያሉ ይሰድቡናል አሁንም ወደፊት የመንግሥት ሃኪሞች የበሽታን ማቃለያ በየሳምንቱ በብርሃንና ሰላም ቢያሳትሙ ብዙህ እርዳታ ይሆናል ግን እንዲጽፉ ማመልከት ነው።

ገብረ ጻድቅ ጋሻው ።

አያና ብሩ ስለጻፈው ቃል ምሥጋና ።

ለተወደደ ወዳጄ ልጅ አያና ብሩ ባለፈው ወር የጻፍከውን ቃል በብርሃንና ሰላም ስላየሁ የሚከተለውን ቃል እጽፍልህ ዘንድ የግድ ሆነብኝ ።

ወዳጄ ሆይ አያና ብሩ እንደ ሙሴና እንደ ዮሴፍ ደግሞም እንደ መርዶክዮስ ላገርህ የሚያኰሩና ለወገንህ ደስ የሚያሰኝ አሳብ አንተ ሕፃኑ ልጅ ለበሩ ሊቃውንቶች ስላተናገርህ የተረዳው እንዳንተ ያለ ሕፃን ወንድምህና ካንተ በላይ ያሉ ያገር ፍቅርና ላገራቸው አገልግሎት ያላቸው አስታዋዮችና መኰንኖች አብልጠው ያመሰግኑህ ዘንድ ደስ ይላቸዋል ።

ከዚህ ሁሉ ጋር ለጻፍከው ቃል ምኒክርና አስረጅ የሚሆን ሳታውቀው ትቀራለህ ብዬ አይደለም ግን ላስገነዝብህ እወዳለሁ በጀርመን ዩንበርሲቲ ያገርህ የኢትዮጵያ ቋንቋ (ማለት ግዕዙ ን) ትንሾች እንኳ ያይደሉ ብዙ ፕሮሰፌሮች የተለየ ክፍል አድርገውለት ይማሩታል ።

አንተ ደግሞ ያሁኑ የኢትዮጵያ ወጣት ልጅ ያማርኛ ቋንቋችን ተከበሩት ቋንቋዎች እንዳንዱ ሁኖ ዓለም ለመከበሪያ እንዲማረው የኢትዮጵያ ቋንቋም ለኢትዮጵያ ልጆች በዩንበርሲቲ እንደ ምዕራብውያን ቋንቋ ሁሉ ለፈተና አንደኛ አድርገው እንዲቀበሉ በትጋት ተከራክረህ በማስፈቀድህ አገራቸውን የሚወዱትና ትምሕርት የሚናፍቁ የኢትዮጵያ ወጣቶች የሚያውቁህና የማያውቁህ ጓደኞችህ በጣም እንዲያመሰግኑህ ጠልቆ ልቤን ይሰማዋል ፡ ይህንንም ድንገተኛ ነገር አስበህ በማድረግህ ስምህ በመታሰቢያ መጽሐፍ ሊጻፍ ይገባዋል። ደግሞ አንተ ብቻ አይደለህም ካንተም በፊት ወደ ፊትም ለኢትዮጵያ ታላቅ ውለታ አገራቸውን ሊያስከብሩ የሰሩና የሚሰሩም ስማቸው ለዘወትር ሊታሰብ ይገባዋል ። ደግሞ በድሜ ጓደኞችህ ለሚሆኑት ወጣቶች መልካም አሳብህ እንደ አምድ በፊታቸው ተተክሎ እንዲሁ እንዳንተ ላገራቸውና ለወገናቸው የሚጠቅምና የሚያስከብር እንዲያስቡ ምሳሌ ሆነሃቸዋል ።

የሆነ ሆኖ ይህ አስበህ የሰራኸው አድራጎት ቢደረግ ባይደረግም ቢጸና ባይጸናም አንተ ሕፃን ልጅ አስበህ አድርገኸዋልና አገርህና ስምህ በየለት ዘወትር ይመሰገን ዘንድ ይገባዋል ። ናፋቂ ወንድምህ ትንሹ ተማሪ ኃይሉ ለውጤ ።

የቀድሞ የመስኮብ ንግሥት ምሥጢር ያለው የሕይወት ታሪክ

በካፒቴን ባቢክያን ታርሞ ተጻፈ

መጀመሪያ ክፍል

የእንግሊዝ ንግሥት ስትሞት ይህቺ አሊክስ ገና ልጅ ነበረች እኔም በዚያን ጊዜ ከ፲ ዓመት አይበልጠኝም ለአሊክስ ባልንጀራና ባለሟል ተባልኩ ሁለታችን በትልቁ ደርፓሽታት በሚባለው ግቢ ትምርታችንን ተማርን ይህም ደርፓሽታት የሚባለው ግቢ በትልቁ ገበያ መንገድ ላይ ነው የተሠራው በዙሪያው ትልቅ ያትክልት ቦታ አለ ግማሹ የምግብ አትክልት ነው ግማሹ አበባና የሚያምር ዛፍ ባንድ በኩልም ደን ነበረበት የዚህ ግቢ ቦታ ሥራው አገነባቡ እንደ ጀርመን ሥራ ነው ብዙ መቶ ዘመን ተቀምጧል በውስጡ አንድ ትልቅ የደወል ቤት አለው በየክፍሉ ጥቂት ይጨልማል(ይህ ግቢ የተባለው አለመጠን ትልቅ ቤት ስለሆነ ነው እንጂ አጥር ግቢ አይደለም) ደግሞ ጥቂት ይበርዳል በየእልፍኙ ግድግዳ ላይ የቀድሞ ዘመን የእጅ ስዕል ይገኛል ። በዚህ ቤት ባንደኛው ክፍል ውስጥ ነው ከንግሥቲቱ ልጅ ከአሊክስ ጋር የተማርነውና ያደግነው

የዚያ የግቢ ኑሮ እጅግ ደስ የማያሰኝ ነው እዮ ጉድ የንጉሥ ቤት ዘመዶች እንደ እስረኞች በግቢው ውስጥ የተከበቡ ናቸው ሁልጊዜ በዚህ ግቢ ያሉ ሰዎች ሁልጊዜ ትህትና አለመጠን መጠበቅ አለባቸው ደግሞአንዱን አንዱ ከመተናኰል በተቀር ሌላ ምንም ሥራ የለባቸው ሁሉም ያለቃቸውን ፊት ለማግኘት ይጥራሉ ይኸውላችሁ የግቢ ኑሮ የዚያ ግቢ ኑሮ የሚለወጠው ታላላቅ ግብር በሆነ ቀን ነገሥታት ሲመጡ የንጉሥ ልጆች ሲመጡ ነው። አሊክስ ፮ ዓመት ሲሆናት እናትዋ ሞተች የናትዋንም ጥንቃቄ ሁሉ አጣች እንደ እናት ጥንቃቄ ያለ በዓለም ውስጥ የተወደደ ነገር ምን አለ አባቷ ባእውነት ይወዳት ነበረ ምንም ክፉ ብታደርግ ይምራታል ። ነገር ግን ሁልጊዜ ከርስዋ ጋራ አይውልም ብዙ ሥራ ነበረበት ትልቅ የንጉሥ ልጅ ነውና ፣ ስለዚህ እኛ ሁለታችን የሚቆጣን ስለሌለ እንደፈቃዳችን የፈለግነውን እያደረግን እድሜያችንን ገፋን በስተማሪያችንም እና ላግጥበት ነበረ የተሰጠንን ትምሕርት እንደ ማጥናት በግቢው ውስጥ እየዘርን ቴኒስ የሚባለውን ጨዋታ እንጫወት ነበር የአሊክስ አባት ትልቁ የንጉሥ ልጅ ከመስኮብ ነገሥታት ዝምድና ስለነበረው ልጁ የመስኮብ ቋንቋ እንድትማር ይፈልግ ነበረ ስለዚህ የኔ አባት መስኮብ ነበርና የመስኮብ ቋንቋ ያስተምረኝ ጀመር ጥቂት ጊዜ አስተምሮን ምንም የማይገባን ሲሆን ጊዜ ከመስኮብ አገር አንድ ብርቱ የሆነ ማሰሌኒኮፍ የሚባል መምሕር ለኛው ሲል አስመጣ ግን ይህቺ ትንሽዋ አሊክስ በጭራሽ የመስኮብ ቋንቋ አልማርም ብላ እምቢ አለች በኋላ ልትፈልገው በዚህ በሚያስከፋው ግቢ ብዙ ጊዜ ስምንት ፲ዓመት ተቀመጥሁ በመጀመሪያ የገባሁ እለት እጅግ አድርጎ ቀፎኝ ነበረ ሁልጊዜም አባቴን ወደ ቤቴ ስደደኝ እያልኩ አስቸግረው ነበርኩ እሱ ግን ከንጉሡ ነገሥታቱ ጋራ ከክዘር ዘንድ ትልቅ ሹመት ስለነበረው ከዚያ እንድሄድ አይፈቅድልኝም ነበረ ። ይልቁንም ከአልጋ ወራሺቱ ከአሊክስ ጋራ እንድቀመጥ አዘዘኝ የሁላችንም አሊክስ ፲፰ዓመት ሲሆናት ተለወጠ ከአስተማሪዎቻችንም ጭቅጭቅ አረፍን በጭራሽ ትልልቆች ልጃገረዶች ሆንናልና ነጻነትንም እኛው ራሳችን አገኘን ከአሊክስ አባት ጋር ተነስተን በአውሮጳ ያሉትን የንጉሡ ነገሥታት ግቢዎች ለመጐብኘት መንገድ ጀመርን የሄደንበትን አገር በኮፔንሃግ በዳንማርክ ከተማ በቢየና የነምሳ ከተማ ነበር በሆፍቡርግ ግቢ በቢየና ከተማ አልጋ ወራሽቱ አሊክስ ወይዘሮ ልዊዝን ተገናኘቻት ይህቺም ልዊዝ የሽማግሌው የዱክ ፌርዲናንድ ልጅ ናት የሳክሶን ንጉሥ አግብታ የሳክሰን ንግሥት ሆና ነበር በለመታደል ዓለም ሁሉ እንደ ሚያውቀው ተፋታች ። ወዲያው እንደተገናኘን ሶስታችንም ተፋቀርን በዚያ ያሉ የቤተ መንግሥቱ መኳንንቶች ትልቅ ደስታ አደረጉልን እኛምከዚያ ከነበርንበት ወጥተን ይህን ሁሉ በማየታችን ከወህኒ የወጣን መሰለን ሕይወታችን እጅግ ብርቅ ሆነብን በዚያ አገር ከወይዘሮ ልዊዝ ጋርና ካንድ ወጣት ልጅ እግር ጋር በደንም ባታክልትቦታውም እየሄድን ሕይወታችንን እጅግ አድርገን በደስታ አሳለፍነው ።

አንዳንድ ጊዜም እንደማናቸዉቱም ሴት እየለበስን በአውቶሞቢል ከውድ ወዳጆችን ጋር ወደሆቴል ወደ ሬሴቶሪን ወደጨዋታ ቤት ሁሉ ሄድን ይህንንም ስናደርግ ምን ይመጣብን ይሆን ብለን አናስብም ነበር በጥቂት ሰሞን ብዙ ሹማምንት እየመራረጥን ለልባችን ደስ የሚያሰኘውን እያየን ለዋውጠን በኋላ የመጨረሻው የአሊክስ ወዳጅ ፍቅሩ እጅግ ጸና እርሱም ዱክ ፋዜስካ ይባል ነበር የተዋወቁትም ስፍራ በሆፍኔር ሆቴል ይህም ዱክ ፋዚስካ ከወዴት የመጣች መሆንዋን አያውቅም የነም ሳውንጉሥ ፍራንሷ ዦዜፍ የምሥጢር ዘበኛ አውቆ ለፍራንሷ ዦዜፍ ነገረው ይህ ንጉሥ ደግ ነገር የሚወድ ስለሆነ የአልክስን ፋፉት ላባቷ ወደጀርመን አገር ቴሌግራም እንዲጠራት አሳለፈ ። ከዚህ የቀረ በሚከተለው ሳምንት ይታተማል።

ካፒቴን ባቢክያን ።

ማስታወቂያ

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሰተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
ደግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፭ ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር	፱ ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫ ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
የዓለም ጆዮግራፊ በአማሪኛ ደኅና ጥራዝ ዋጋው	፪ ብር
» » » መናኛ ጥራዝ ዋጋው	፭ ብር
ኀሐ ጽባሕ	፭ ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ ብር
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትርሜጓው	፪ ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ተኩል
የቁጥር ትምርት	፩ ብር
ያማሪኛ ሰዋስው	፩ ብር
ወዳጄ ልቤ	፩ ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	አላድ
አጭር የዓለም ታሪክ	አላድ
ያማሪኛ ፊደል	ሩብ
አሳብና ምኞት	ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት	ሩብ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፪ መ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር	፪መ
ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ	ሩብ

የአዲስ አበባ ገበያ ።

የቀንድ ከብት

የሚታረድ በሬ ዋጋ	፵ ብር
የእርሻ በሬ	፴፭ ብር
ያሩሲ ድልብ በሬ	፶፭–፸ ብር
የምትረባ ላም	፴፭ ብር
መሲና ላም	፴፪ ብር
የምትረባ በግ	፫ ብር
መሲና በግ	፭ ብር
ሙክት በግ	፲፫ ብር
የምትረባ ፍየል	፬ብር
መሲና ፍየል	፪ ብር
ሙክት ፍየል	፲ ብር

የጋማከብት

ሰንጋ ፈረስ ዋጋው	፳፭ ብር
ባዝራ ፈረስ	፳–፳፭ ብር
አጋሰስ ፈረስ	፳፪ ብር
የኮርቻ በቅሎ	፻፱ ብር
ሰናር ዓይነት በቅሎ	፻፹ ብር
አጋሰስ በቅሎ	፸ ብር
የምትረባ አህያ	፲፪ ብር
የጭነት አህያ	፳፪ ብር
ዶሮ ዋጋው	ከሩብ–አላድ
ሰንቍላል ሠላሳ	፩ ብር

የእህል ገበያ

ስንዴ ፩ ጆኒያ	፲፪ ብር
ገብስ	፱ ብር
ጤፍ	፲፫ ብር
ሽንብራ	፲ ብር

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፩ ብር ተሶስት ሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፫ ብር ተሩብ
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳ ብር ተኩል
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፶ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፰ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ከረጂ	፰ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ከረጂ	፲፰ ብር ተኩል
አቡጀዲ መነጽር	፩ ከረጂ	፻፵፪ ብር
፡፡ ባለሰይጣን	፡፡	፻፵፩ ብር
፡፡ ባለ ድመት ።		፻፵፮ ብር
፡፡ ባለአህያ	።	፻፳፰ ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል	።	፻፴፭ ብር
ባለ አንበሳ	፡፡	፻፵፭ ብር
ሱካር	፩ ጁኒያ	፴ ብር
ቻይ	፩ ነጥር	፫ሩብ ከሁለት መ

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ ፲፭ ሳንቲም
አንድ ብር	ሊሬ ፰ ከ፳ ሳንቲም
በአንድ ጊኒ	፲ ብር ፪ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፬ ብር

A LOUER

COGNAC S.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቀሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ፡ ሱቅ ይገኛል ።


የእጅ ሰዓት ዝኒት ።

በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቅዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይ ወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓኒያ" ብቻ ነው።

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው፡ ደግሞ በኒዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድሪስ፡በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፡ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ማስታወቂያ ።

በጋዜጣ ውስጥ በአማርኛም ሆነ በፈረንሳዊ በርካሽ ዋጋ እናትማለን ።

ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል ። ሙዚቃም በየ ዓይነቱ እንደ ሴንፎር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል ።

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ አቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።



አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባ ኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኜቶና ባለባተሪ ነው ካምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል «ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው

ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ ።

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህ በካፕሱሉ ያለ ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በካፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ጉድይር ግዙ



ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው።በሌላጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ፤ ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አራተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፳፯
4 me ANNÉE № 27

ሐሙስ ሰኔ ፳፰ ቀን ፲፱፻፳ ዓ ም።
JEUDI 5 JUILLET 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲረክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie
Un an 5 Thalers
Etranger
Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ገንዘብ ካለ በሰማይ መንገድ አለ ።

ገንዘብ ካልሠሩበት ገንዘብ አይደለም ።

ክቡራን የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ሆይ ከዚህ በታች የጻፍኳቸውን ቃሎች በትእግሥትና በማስተዋል እንድታነቡት ስል በማክበር እለምናችኋለሁ ፤ ነገሬንም ከቶ ሰው ካልሠራ አይሰለጥንም ወይም ራሱን አያድንም ብዬ እጀምራለሁ ።

ክቡራን አንባቢዎች ሆይ ፤ ስራ ካልሠራ የሚጠቅመውን ነገር በቶሎ ካልፈጸመ ሰው ከቶ ተገኝቶ አይሰለጥንም ። ዳግም ስልጣኔም የሚመጣው ወይም የሚገኘው ሥራ በመሥራትና የሚጠቅሙን ነገሮች እያሳደዱ በቶሎ በቶሎ በመሥራትና ነገ ዛሬ ባለ ማለት ነው እንጂ ሰምተው እንዳልሰሙ በመሆን አይደለም ። ሰምተውም እንዳልሰሙ የሚሆኑ ሰዎች ሁሉ ምንም እንዳይጠቀሙ ያለ ጥርጥር የታወቀ ነው ፤ ነገር ግን በየጊዜው ጉዳት ይጨምርባቸዋል ።

እንደዚህ የማያደርጉ ሰዎች ግን በየጊዜው ደስ የሚያሰኝ ነገር ያገኛሉ ፤ ስለምን ማለት ለሃገራቸው የሚጠቅማትን ነገር በቶሎ እንደሰሙ ያደርጉታል ሰምተውም እንዳልሰሙ አይሆኑም ። ዳግም በዚህ ነገር ጉዳት እንደሚመጣ ተረድተውታልና ።

አሁንም እኛ ኢትዮጵያውያን ሰምተው እንዳልሰሙ የሚሆኑትን ሰዎች መንገድ ትተን የሚጠቅማቸውን ነገር እንደሰሙ የሚያደርጉትን ሰዎች ብንከተል ይሻለናል ።

ዳግም ሰምቶ እንዳልሰሙ መሆን ከድንቁርና ይቆጠራል እንጂ ፈጽሞ ከእውቀት ምንም አገባብ የለውም ። የሚያስፈልግንና የሚጠቅምን ነገር በቶሎ አለ ማድረግ የምን ይመስላል ? ።

(እነኚህ ሁለቱም የኢትዮጵያውያን ሽማግሌዎች ተረቶች ናቸው)

ክቡራን ኢትዮጵያውያን ሆይ ከባልንጀሮቻችን ተለይተን ወደኋላ በመቀረታችን እያዘንን ብንቀመጥ ነው ? ወይንስ በቶሎ የሚያስፈልገንንና የሚጠቅመንን ነገር ብንሠራ ? ።

ትንሽ የሚቻላችሁ ጌቶቻችንስ በተቻላችሁ መጠን ተረዳድታችሁ ለውድ አገራችሁ ከሚያስፈልጓት ነገሮች አንድ አንዱን ለማድረግ ለምን ችላ ትላላችሁ ። ለናንተስ ክብራችሁና ግርማችሁ የሷ ነፃነትዋ ክብረት አይደለምን ዳግም እንኳን ከገንዘባችሁ ይቅርና ነፍሳችሁን አሳልፋችሁ የምትሰጡላት እናታችሁ አይደለችምን ።

ክቡራን ጌቶች ሆይ እንደዚህ ማለቴ ለሃገራችሁ ጥቅምና ክብር አታስቡም ብዬ አይደለም ነገር ግን ሃሳባችሁን ሁሉ ባንድ ሰው ላይ ጥላችሁ ዝም አትበሉ ማለቴ ነው እንጅ ።

ደግሞ ሃሳቡን ጥሎ በሚተኛ ሰው ላይ ካንድ ሽማግሌ የሰማኋትን ምሳሌ ከብዙው በጥቂቱ እሰጣለሁ ።

አንድ ቀን አንድ ሰው ከባህር ላይ በጀልባ ሲቀዝፍ ውሎ በኋላ መመለስ አይቀርምና ወደ ጠረፉ ሲመለስ ጥቂት ርቀት ሲቀረው ጀልባው በድንገት ተገለበጠበት ። ያም ሰው ምንም ዋና አያውቅም ነበርና ከውሀው ላይ ዝም ብሎ ጥቂት ጊዜ ቆየ ። በዚህም ጊዜ በጠረፉ ያሉት ሰዎች አለመንቀሳቀሱን ባዩ ጊዜ በሞቱ ተስፋ ቆረጡ ። አንዱ ግን አይዞህ በርታ ምንም እንኳን ዋና ባታውቅ በቶሎ ጀልባ እስኪደርስልህ ድረስ በእጅህም በእግርህም ትንሽ ተንቀሳቀስ እያለ ሲያጽናናው ፤ ያም ሰውዬ መቶም ወሃውን እየተጋተ ለጊዜው አልሞተም ነበርና በመከራ ይህቺን ቃል መለሰለት ግድ የለም እግዚአብሔር ያወጣኛል ከቶ ምንም አልንቀሳቀስም ፤ ዳንኤልን ከአንበሳ አፍ ያወጣ አምላክ እኔን ከውሃ ውስጥ አያወጣኝምን ብሎ ከዚህም የተረፉ ብዙ ቃሎች መለሰለት።

ይህም አጥናኙ ሰውዬ ብልህ ነበረና ሰማህ ወንድሜ እንዲህ ማለትህስ መልካም ይሁን እንጂ ጥቂት ጥቂት በእጅህም በእግርህም (እንደ ዋና ተንፈራገጥ እንጂ እንዴት እጥልቅ ባሕር ውስጥ ሆነህ ጥቂት እንኳን ሳትንፈራገጥ አምላክ ያወጣኛል ብለህ ትተኛለህ? እያለ ሲጠይቀው ያም ሰው ምንም አይንቀሳቀስም ነበረና ወዲያው ስመጣ ያም ከጠረፉ የሄደ ጀልባ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ደረሰ ነገር ግን እሬሳውን ይዞ ተመለሰ እንጂ በነፍሱ አልደረሰም ብለው አጫወቱኝ ።

አንባቢዎች ሆይ ይህ ሰው ሐሳቡን በእግዚአብሔር ላይ መጣሉን ጣለ ነገር ግን ዝም ብሎ ተኛ የሰውም ምክር ናቀ ምን ሆነ? ሞተ ። ሐሳቡን ሁሉ በፈጣሪው ላይ ለመጣል ማንም አይበዝን ስለሆነ ግን ምክር እየሰሙና እየተረዳዱ ቢሰሩ በጣም ደስ ያሰኛል ፡ ደግሞ ዝም ብሎ ተጋድሞ አቤቱ አቤቱ ቢሉት ያድናልን?

ክቡራን ጌቶቼ ሆይ አሁንም ሐሳባችሁን አንድ አድርጋችሁ በኢትዮጵያ የምድር ባቡር ለመዘርጋት የሚያስፈልግ መሆኑን እንዳትዘነጉት ። በተረፈ ግን ወደሥልጣኔ ምንም አለመረመዳችንን እንድታውቁት ስል አሳስባችኋለሁ ። ደግሞይኸውም በግርማዊት ንግሥታችንና በልዑል አልጋ ወራሻችን ኃይል ይፈጸማል ስንል ኢትዮጵያውያን እጃችንን ዘርግተን በሙሉ ቀስፋ እንጠባበቃለን ። እኔም ይህችን ቀጥዬ በኢትዮጵያና በልጅችዋ ስላለው ማጽናኛ እሰጣለሁ ።

(ኢ.) ተናግሮልኝ ነበር በመዝሙር ዳዊት እጄን መዘርጋቴን ለናንት ነፃነት ። ምነዋ ተኛችሁ የኔ ፍሬያት ።

(ል) አይዞሽ አገር እናት አንች የኛ ቅድስት ። ይኸው ልንጀምር ነው ልጆችሽ በውነት ። ታጥቀን ተነስተናል ላንች ነፃነት

(ኢ.) ይህ ከቶ ለኔ ምንም አይጠቅመኝ ነገ ልንጀምር ነው ሁልዬ ብትሉኝ ። ሁሉ ሲታገሉ ከበው ሊነጥቁኝ ።

(ል) ክብርት እናታችን ከቶ የዚህ አሳብ በልብሽ አይግባ ። ደማችን ሳናፈስ ማንም ባንች አይገባ ።

(ኢ.) ለገንዘብ ስትሳሱ ባይኔ እያየኋችሁ ። ደማችን ሳናፈስ ለምን ትላላችሁ ። ደም እንጅ ከገንዘብ ለናንተ ውዳችሁ ። አፈር ለሚሆነው እንዲህ የሳሳችሁ ደም እናፈሳለን ለምንትላላችሁ እባካችሁ ልጆች ስሙኝ ልንገራችሁ አገር ናት ለናንተ መኩሸና ግርማችሁ ።

(ል) አይዞሽ ክብርት እናት ፀፀት አይግባሽ ። ይኸው ተመርጠዋል ሁለት ልጆችሽ ። ታጥቀው ተነስተዋል ደስ ሊያሰኙሽ ። በጣም ደስ ብሎናል እኛም ልጆችሽ ።

(ኢ.) እነሆ አየሁሁ ፍፃሜ ነገሩን በዚሁ ዓመት ውስጥ መንገድ መጀመሩን ።(አንዱ ልጅ አትበሉ እንግዲህ ነገ እንጀምራለን ይህ ነው ደበኛችን እኋላ ያስቀረን ።

ክቡራን አንባቢዎች ሆይ ከቶ ገንዘብ ከሃገሩ አስበልጠ የሚወድ ሰው ይገኝ ይሆን ? እኔ ግን ይገኝ አይመስለኝም አሁንም ለሥልጣኔ መቸኮል ያስፈልገናልና ። በቶሎ የሚያስፈልጉንን ነገሮች እንስራ ስል በማክበር አመለክታለሁ ።

ኅ ወ ዘ

እንበይነ ጥቅመ ተንከተም ዘገፈርሳ ።

ዘተሐደሰ በ፲፱፻፳ ዓ ም በመበሕተ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ወለቱ ለዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ ። ወበትእዛዙ ለእግዚእነ ልዑል ተፈሪ መኰንን ወራሴ መንግሥት ዘኢትዮጵያ ።

በፍኖተ ሐዳስ ዓለም ፍና ደብረ ሎዛ ።
ኃይለ ሥላሴ ያዕቆብ ሰዋስወ ብርሃን ተከለ ።
ለዘይወርዱ ታሕተ ወለዘየዓርጉ ላዕለ ።
ዘእንበለ ያእምሩ ሰዋስወ ።
በመርህብ አለ ይዘርዑ ንዋዮሙ ቃለ ።
ሰዋስወ ብርሃን ሶበ ስሕቱ ።
በበፍናሆሙ ዘልፈ ይፍርሁ ማዕበለ ።
ለነሰ በፍኖትነ ስርወ አሜከላ በቈለ ።
ለሰማዬ ዘሰቀሎ ለገዚሞቱ ድኅረ ተሰቅለ ።
እስከነ ወራሲ ያግህድ ጉድበ አሜከላ ወንጀለ። (ጅ)
ያስተጋብእ ዝርዎነ ወይርዳዕ ዘተኀጕለ ።

አለቃ መርሻ ዘውእቱ መርስዔ ኀዘን ።

ስለ ገፈርሳ ድልድይ ።

ባለፈው ሳምንት ሠራዊቱ በትጋትና በንቃት የሠራ እንደሆነ የገፈርሳ ድልድይ እስከ አንድ ሳምንት ያልቃል ብለን በግምት ተናግረን ነበር ። አሁን እንዳልነው በሕዝቡ ንቃትና ትጋት ተሠርቶ ተፈጸመና መከከሉ አቶሞቢልና ካሚዎን ጋሪም ያስኬድ ጀመረ ዳር ዳሩም ሊሞላና ሊፈጸም ቀርቧል ። በጥቂት ቀን ይህን ያህል ድልድይ ተሠርቶ በመፈጸሙ አላፊ አግዳሚው እድሜ ለግርማዊት ንግሥታችንና ለልዑል አልጋ ወራሻችን እያለ ያመሰግናል በዚህም በክረምት ከውሀ አደጋ ስለ አዳኑን ለኢትዮጵያ ጀግኖችና አርበኞች በማናቸውም ነገር ኃይልና ጽናት ይስጥልን እያለ ምርቃቱን እያንጎደጎደ ያልፋል ።

ይህን ያህልም ቀን ማቈየቱ ዝናም እያስተጓጐለውና ጭቃ እያስቸገረው ነው እንጂ ሠራዊቱስ እንደ ብዛቱና እንደ ብርታቱ ሌላም በሠራ አሁን ክረምት ስለሆነ የመንገድ ሥራ መስራት ጭቃ እየሆነ በጣም ያስቸግራል ። ግን ለክረምት የሚያስፈልግ መንገድና ድልድዩ በበጋ ጊዜ ሊታሰብና ሊሰናዳ ያስፈልጋል ። ስለዚህ ለወደፊቱ በክረምት የሚያስቸግረው መንገድና ድልድይ በበጋ እንዲሰናዳ ተስፋ እናደርጋለን ።

ዓዋጅ ስለ መጠበቅ ።

ሰኔ ፲፬ ቀን በ፳፫ኛ ቍጥር ስላተሙልን ቤሳ የገባያውን ሕግጋትና አዋጅ የሚናገረውን ተግሣጽ ስመለከትሳለሁ ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ አንድ ጊዜ ሱካርና ወተት የምትባል ደብተር አሳትመው በዚሁ ዓዋጅ በሚጥሱት ነገር እንደዚህ ብላ ትገሥጽ ነበረች አንድ የጀርመን አገር ሰው የጦር ምኒስቴር ለጦርነት ታዞ ሲጓዝ ሳለ ጀንበር ከጠለቀ ሲጋራም እንዳይጠጣ መብራትም እንዳያበራ ዓዋጅ አድርጐ ነበርና አንድ ቀን ማታ ሰው ሲተኛ እየዞረ ሲያይ አንድ ሰው ለሚስቱ ወረቀት ሊጽፍ ሻማ ሲያበራ ቢያገኘው ምነው አዋጅ አፈረስህ ቢለው

ጌታዬ የምሄደው ወደ ጦርነት ስለ ሆነ ለሚስቴ አንድ ነገር ልጻፍላት ብዬ ነው ቢለው እንግዲያውስ ትንሽ ነገር ጨምረህ ጻፍላት አለው እኔ የመንግሥት አዋጅ አፍርሼ ላንቺ ወረቀት እጽፋለሁ ብዬ መስቀሌን እወቂ ብለህ ጻፍላት አለው እሱም ይህን ጽፎላት በማግሥቱ ተሰቀለ የምትለውን ቃል ብዙ ቀን አንብቤያት ነበር ለዘንጉት ወይም ጭራሽ ለማያውቁት ላስታውሳቸው ወዲያውም ትንሽ ዱቄት ይዘህ ከንፋስ ተጠጋ ነውና ምናልባት በዚሁ ምክንያት የኔውም ሐሳብ እንድትሰማና በሩን መግቢያ ብትሆነኝ ብዬ ነው ።

ሁለተኛ መንግሥት በየነጋው ዓዋጁን ከዚህ አይውጣ ከዚህ አይውረድ እያለ ሲያስታውቅ ጊዜ ፴፪ የነበረው ቤሳ ፳፪ መሆኑ ፲፮ የነበረው መሐልቅ አሮጌ አዲስ እየተባለ ፲፪ አዲስ ፲፯ አሮጌ እንዲህስ መሆኑ በምን ምክንያት እንደሆነ አንባቢዎችን እጠይቃለሁ ደግሞ የወላሞና የሲዳሞ ሕዝብ ያልተማሩ ናቸው እንላቸዋለን ምሳሌ አሽኰኰዎች ያልተማሩ ናቸው ብቻቸውን በድንጋይ ውስጥ ያድጋሉ እንዳለው ይልቅ እነሱ ዱሮውን ደንባቸውን ይዘው መልካም አኑዋኑዋር ይኖራሉ መርጬ የሚባል ብረት አበጅተው ቆብ ለማ ቆብ ስዶ አንድ ሁለት እያሉ በደነቡት ደንብ እስከ ዛሬ ድረስ ይገበያዩ በቃል መቼም ገንዘብ በጉተራ ቢሞላ መለዋወጫ ነው እንጂ አይፈጭ አይጋገር አሮጌ አዲስ ማለት ተዩት የመጣ ፈሊጥ ይሆን? የታደሉትስ ባንድ ብጣሽ ወረቀት አንዳንድ ሽክም ብር ይለውጣሉ እኔ ግን አዘጋጅቸው አለሁ እስቲ ምክንያቱ ምን ይሆን ስል እጠይቃለሁ ።

ኪዳኔ ካሣዬ

የጽዳት ማስታወሻ ።

በሀገራችን በኢትዮጵያ ውስጥ ለመንግሥት ብዙ ገቢ ገንዘብ የሚገኝበት ሥራ አልተጀመረም ። አልተጀመረም ያልሁትም ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን ነው ፤ ከውጭ አገር ሰዎች እንደምንሰማው ወሬ ሰው በሞተ ጊዜ ለመቃብር ዋጋ እየተከፈለ ነው ይሉናል ። በነሱ ወሬ ብቻ አይደለም ባዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ሆነው የተቀመጡት የውጭ አገር ሰዎች ጉለሌ ያለውን ለመቃብር ቦታቸውን ፤ የነሱ ወገኖች የሆኑት ሰዎች ሁሉ በሞቱ ጊዜ ገንዘብ እየከፈሉ ሲቀብሩ እናያለን ።

ይህ ሥራ ለኛም ቢደርሰን ክፉ አይመስለኝም(ማለት) አሁን ባዲሱ ሥልጣኔ ጊዜ ለኛ የሚያስፈልገን ለመንግሥት ገቢ ገንዘብ የሚገኝበትንና ተረስቶ ሳይጀመር የቀረውን ሥራ ማሰብ ነው ። ስለዚህ አሁን ወደፊት የኢትዮጵያ አገር ግዛት በሆነው አገር ሁሉ በከተማም በባላገርም ያሉት ሕዝቦች የውጭ አገር ሰዎችም ቢሆኑ በሞቱ ጊዜ ለመቃብር የሚሆነውን ቦታ ላንድ ሰው ሁለት ብር እየተከፈለ ቢሆን መልካም ነው ። ይህ ሥርዓት መጀመሸ ሲደነገግና ማስታወቂያ ሲወጣ አገሌ ድኃ ነው ፤ አገሌ ባለጸጋ ነው ፤ አገሌ የመኳንንት ወገን ነው ። ካህን ፤ ወታደር ፤ ነጋዴ ፤ ገበሬ ነው ማለትን በጭራሽ መከልከል ነው ። ለሁለት ብር ድኅነት የለም ፤ እንዲያውም በክቡራን መኳንንቶችና በየቱጃሮቹ ላይ በውጭ አገር ሰዎችም እንደ ማዕርጋቸው እየታየ መንግሥት ክፍል አድርጎ ቢወስንላቸው በጣም ደስ ያሰኘል ።

ነገር ግን ከባላገር ወደ ከተማ የመጣ ባይተዋር ድኃ ወይም ባገር ቤት ውስጥ ተቀምጦ የሚመገበውና የሚለብሰው ችግሮት የሞተ እንደሆነ እውነት ችግረኛ መሆኑ ተመርምሮ ከታወቀ በኋላ ምሕረት ማድረግ ነው ። ወይም ከዚያው ከገቢው ገንዘብ ወጭ አድርጎ ለድኃው ሰው መቃብር ገቢ ቢያደርጉለት ይሆናል ። ይህም ሲሆን ሬሳውን ቀብሮ ነው እንጂ ሬሳው ሳይቀበር ድኃ መሆኑንና አለመሆኑን ለመመርመር ችግር ነው ። ደግሞ ይኸንን የሚጠባበቁ ሠራተኞች እንዳይበዙ በልክ ማድረግ ነው ። በከተማው ውስጥ ላሉት ቤተ ክርስቲያኖች ለያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን አንድ ጸሐፊ ይበቃል ። በገጠር ላሉት ቤተ ክርስቲያኖች ግን ወጭ እንዳይበዛ ገበዝ ወይም ሊቀ ዲያቆን ሊሠራው ይችላል ። ነገር ግን ከስለት ገንዘብ ጋራ እንዳይደባለቅ መለየት ነው ። ይህ ገቢነቱ ለርሻ ሚኒስትር የሚሆን ይመስለኛል ።

ደግሞ ገቢው በርከት ሲል የመቃብሩ ስፍራ ዙሪያውን ጥሩ ሆኖ ቃጥሮ አትክልት እየተተከለ እንዲጸዳ አንድ ሠራተኛ ማድረግ ይገባል ፤ ሰው በሞተ ጊዜም ቦታው እንዳይበላሽ በሥራው ላይ የቆመው ሰው ገንዘቡን ጸሐፊው ተቀብሎ ወረቀቱን ባየ ጊዜ መሬቱን እየለካ በመደዳው እንዲሰጥ መጀመሸ ትእዛዝ ማሳለፍ ነው ። ምናልባት የመቃብር ቤት እንሠራለን የሚሉ ሰዎች ቢገኙ ከርሻ ሚኒስትር የተለየ ፈቃድ እንዲቀበሉ ማድረግ ነው ፤ ፈቃድ ከተቀበሉ በኋላ ባራቱ ማዕዘን ባንድ ካሬ ሜትር ሁለት ብር እንዲከፍል የተወሰነ ሕግ መስጠት ነው ።

እስካሁን ድረስ ባባቶቻችን የሌለውን በገዛ መሬታችን ምን ይሉናል ብለው የሚያጉረመርሙ ሰዎች ቢገኙ የመቃብር ዋጋ መኖሩን ከቅዱሳት መጻሕፍት ይመልከቱ። ይልቁንም እስከ ክርስቶስ ምጽአት ድረስ የሚኖርበት ርስቱ ነውና አንድ ሰው ለሚቀበርበት ሁለት ብር ቢከፍል ጉዳት የለበትም ። ያደራረጉንና የደምቡን ሥርዓት ከኔ ይልቅ በጣም የሚያውቁት ሰዎች እንዲጽፉት ተስፋ አደርጋለሁ ። ሥራውም በፍጥነት እንዲጀመር የማይረሳና የማይዘገይ ምኞት አለኝ ።

ይህ አሳብ በሁለት ወገን ይጠቅመናል ፤ መጀመሸ መቃብር እንደ ሚያምር ልዩ ሆኖ የሚሠራበት ገንዘብ ይገኛል ። ሁለተኛ በያንዳንዱ ዓመት ውስጥ የሚሞቱት ሕዝቦች ቁጥራቸውና የሞቱበት ዕድሜያቸው ታውቆ በመዝገብ ይጻፋሉ ። ይህ ትልቅ ጥቅማችን ነው ።

ይህ ሥራ በቶሎ ቢጀመር መልካም ይመስለኛል፡ምናልባት በቶሎ ሳይጀመር የቀረ(የቆየ) እንደሆነ ማን ያስጠይቅ ይሆን?

የብርሃንና ሰላም ተማሪ ፤ ደምሴ ወልደ ገብርኤል ።

የቀድሞው የመስከብ ንግሥት ምሥጢር ያለው የሕይወት ታሪክ ባለሙዋሏ ዘኒት የጻፈችላት በካፒቴን ባቢኪያን ታርሞ ታደሰ።

መጀመሪያ ክፍል ።

ከዚህ በኋላ ቀድሞ ከነበርንበት ደርምሾታት ከሚባለው ግቢ ሰደዱን ። ነገር ግን ምንም ከዚያ አግብተው ቢዘጉብኝ

እኛ የማንታዘዝና አቡዮች ሆነን አሽነፍን በቢየና ከተማ ሆነን የተማርነውን ብልግና ሁሉ እየቀጠልን እየጨመርን እንሂድ ጀመር ። ከዚያ በኋላ የአሊክስ አባት ሁለታችንንም ይዞ የአውሮፓን ነገሥታት ግቢ እያዞረ ያሳየን ጀመር። እውነት እንናገር ዘንድ እንደሚገባን ከመልካሙ ጠባያችን አውጥታ ወደ ክፉው ጐዳና የመራችን ወይዘሮ ሊዊዝ ናት ከሄድንበትም ሥፍራ ወይዘሮ ልዊዝ ከኛ ጋራ ስለመጣች የእርስዋን ምክርና ጠባይ ተከትለን ማታ ማታ ልብሳችንን እያወለቅን በስውር ሆነን እርስዋ እንዳሳየችን ሌላ ልብስ ለብሰን የትም እየሄድን የማይሰለቸውንና ደስ የሚያሰኘውን ሕይወት ባለመጥገብ አገኘን ወዲያውም ልዊዝ ለአልጋ ወራሺቱ አሊክስ አንዲት ገረድ አኔት ሚሾ የምትባል አገኘችላት ። ይህችም አኒት ሚሾ አለመጠን የዓለም ሰውና ብልሹ ይልቁንም በጣም በውስልትና ወይም በብልግና ሥራ የሠለጠነች ነበረች እኛንም እጅግ ወደክፉው መንገድ በብልጠትዋ ብዛት አዘነበለችን ። እርስዋ፡ እኛ ዘንድ ከገባች ፩ ወር እንደ ሆናት በኢጣልያን አገር በሮማ ንግሥቲቱ ማር ገሬታ ለግብዣ ጠራችን እኛም ገና መጀመሪያ መጐብኘታችን ነበረ በመጀመሪያ የቤተ መንግሥቱን ግቢ በገባን ጊዜ አለመጠን የተጌጠ ነበርና እጅግ አድርጎ አስደነቀን እስከዚያው ቀን ድረስ እርሱን የመሰለ የነገሥታት ግቢ አላየንም ። ንጉሡም እጅግ የከበደ ክብሬታ አደረገልን ነዚህ የተነግ ማለት ስለክብሬታው ብዛት ያነኑ የጀመርነውን ብልግና ሥራ እንድንጀምር ነፃነት ሰጠን ።

በዚያን ጊዜ አልጋ ወራሽ ኤማኑኤል ዛሬ የኢጣልያን መንግሥት ንጉሥ የሆነው አሊክስን ባየ ጊዜ እጅግ የተዋበች ነበረችና ፍቅር ጣለበት ከዚያ ቀን ጀምሮ ከርስዋ ጋራ መነጋገርና ደስ የሚያሰኝ ነገር ያቀርብላት ጀመር ። ለመሆኑ በእውነትም የአሊክስ ውበት ይልቁንም የዓይኖችዋ ዘርፍ የሚስብ ነበረ ንግሥቲቱም ማር ገሬታ አልጋ ወራሽ ልጅ ኤማኑኤል ሀሊናው ወደዚች የተዋበች ልጅ እንዳዘነበለ አልሳተችም ።

በዚያም ጊዜ የቡልጋርያው ንጉሥ ፈርደናንድ ገና ወጣት ነበርና ከኛው ጋር ግብዣ ነበረ ። እርሱም ልዊዝን ለማግባት ምኞት ነበረውና ይህ ግብዣ ከርስዋ ጋር ለመገናኘት ምክንያት ስለ ሆነው ግብዣውን በደስታ ተቀበለ ።

በውነት ንጉሡ ፈርደናንድ ስለመጣ ጊዜው ማታ ነበረና እጅግ ደስ የሚያሰኝ ሆነ ደግሞም በዚያ ባማረው አዳራሽ ውስጥ ብዙ የሚያምሩና የተዋቡ የነገሥታት ልጆችና ጐበዛዝት ሹማምንት ይታዩ ነበሩና ደስ ብሎን እያንዳንዳችን በአዳራሽ ክፍል ትንሽ ሽር ሽር ጀመርን ። በዚያ ሌሊት ያየነው ደስታና ሁናቴ (ውነት እስከ ጊዜ ሞት ድረስ የማይረሳ ነው ።

ጨዋታውንም ከጠገብን በኋላ በተሰጠን እልፍኝ ገብተን ጥቂት እንዳረፍን ወይዘሮ ልዊዝ ቀር ብሎዋት ነበረና ለአሊክስ ሆድዋ ደስ ሳይለው በላይ እየሳቀች ንጉሡ ፈርደናድ እጄን ለመያዝ በክበሬታ ጠየቀኝ አለቻት ማለት በኤሮፓ ማናቸውም ሰው ሴት ለማግባት በፈቀደ ጊዜ እጅዋን ለመያዝ ይለምናታል እሺ ብላ እጅዋን የሰጠችው እንደሆነ ፈቃድዋን ለጋብቻው መስጠትዋ ነው አልጋ ወራሺቱም አሊክስ ተቀበልሽው? ብላ ጠየቀቻት ልዊዝም መልሳ አለቻት ተቀበልሽው ትይኛለሽን አወይ ጉድ ብላ ከትከት አለችና ሳቀች ወዲውም እህቴ ሆይ እውነት ይመስልሻልን ታሚኛለሽ እኔ እንዲህ ያለ አፍንጫው ቀታራ ደግሞ ብጫ ጫማ ያደረገ ሰው ምሽት የምሆን? ምንም ቢሆን ከቶ አላደርገውም ብላ መለሰችላት ።

በማግሥቱ ናቤና በሚባለው ስፍራ ትልቅ በዓል ተደርጎ ነበር ሮማውያን ይህን ዓመት በዓል ሊፍና ይሉታል ሲያከብሩትም ብዙ ጸሎት አድርገው ነው ። በያመቱ ለዚሁ በዓል ለማክበር የሚመጣው ሕዝብ ከአስራ አምስት ሚሊዮን ሰው አያንስም ።

በዚሁ በበዓል ቀን ከንግሥቲቱ ጋር ደስ ብሎን ዋልን እራትም ከበላን በኋላ ልዕልት ንግሥት ሰላምታ ሰጥተውን ወደ እልፍኛቸው ለአረፍት ገቡ ወዲያው ብቻችንን ስንሆን አልጋ ወራሺቱ አሊክስ ዜኒት ሆይ ነገ ወደ ዓመት በዓሉ ስፍራ ብንሄድ እንዴት መልካም ነበረ አንቺ ምን ይመስልሻል ብላ ጠየቀችኝ ይህንንም ባለችኝ ጊዜ ከደስታዬ ብዛት መፈንደቅ አምሮኝ ነበር በነገታው ማታ ከሕዝቡ ጋራ ተደባልቀን እናመሻለን ብዬ አስቤ ነበረና እዲህ ብዬ መለስኩላት እኅቴ ሆይ በየጊዜው ቡርጊዝ የተባለችዋን የንጉሥ ልጅ ፒያኖ ከመስማት እዚያ ብንሄድ መልካም ፈቃዴ ነው ብዬ መለስኩላት አልጋ ወራሺቱም አሊክስ በማግስቱ ሉካ የሚባለውን ስፍራ ብቻችንን ሆነን ለመጐብኘት የግድ ሆኖባት ነበረ በማግስቱም ማታ በገረዳችን ምክር መገፋፋት በቶሎ ልብሳችንን በየሱቁ ውስጥ ዕቃ እንደሚሸጡት ትንንሽ ልጆች ለበስንና ከሌሊቱ ባምስት ሰዓት እንመለሳለን ብለን ለገረዳችን ፈቀድንላት ወዲያውም አሽከሮች በሚወጡበት በር በስውር ሆነን ወጥተን ሄድን በዚያም ጊዜ እንደ መላእክት ነበርን ከጐበዛዝት ጋር በነጻነት ከመጫወት በቀር ሌላ ምንም ፈቃድ አልነበረንም ናቢናም ከሚባለው ስፍራ ልንደርስ ስንቀርብ ልባችን ድው ድው ይል ጀመረ ።

በሚመጣው ሳምንት ይቀጥላል ።

ካፒቴን ባቢክያን ።

አውቶሞቢል በአዲስ አበባ ።

በአዲስ አበባ አውቶሞቢሉ እየበዛ ስለሔደ ለእግረኛ መንገድም በግራና በቀኝ ደህና ሆኖ ተሠርቶ ስለ አልተፈጸመ ላላፊ አግዳሚው በጣም ያስቸግራል ። ይልቁንም ክብት ጭነው ለሚሔዱና በቅሎ ተቀምጠው ለሚሔዱ ሴት ወይዘሮች በጣም ያሰጋል ። የባሰውም አውቶሞቢል ነጂዎች ማስጮኻቸውን ነው የሚመለከቱት እንጂ አውቶሞቢሉን በልክ አያስኬዱትም ። ግን አሁን ማዘጋጃ ቤት አውቶሞቢል ከሚገባ ፍጥነት አልፎ ያስሮጠ እንደሆነ በመንገድ የቆመ ተጠባባቂ ጥሩንባ ሲነፋ አልፎ እንዳይሔድ ደንብ አቁመዋል አልፎ ቢሄድ ግን መቀጫ እንዲከፍል አድርጓልና ወደ ፊት የአቶሞቢል ሁሉ አካሔድ በሥርዓት እንዲሆን ተስፋ እናደርጋለን ።

የውጭ አገር ወሬ ።

በፈረንሳዊ ሌጋሲዮን በኩል ከጅቡቲ የመጣ የዕለት ወሬ።

ፓሪስ፤ በኤውሮፕላን የሚበሩ ሰዎች በሌሊት ከናንስ ተነሥ ተው ወደ ቡጂ ሲበሩ ዝናብና አውሎ ነፋስ ተነሥቶ ብዙዎች ወድቀው ከሞት ዳኑ ፣ ግን አለቅዮው ሲዬተና ሲካር ሞተ።

ካይሮ ፤ ሙሐመድ ፓሻ ማሕሙድ የግብፅ መንግሥት የገንዘብ ሚኒስቴር የነበረ ሹመቱን ለቋል ።

ቶኪዮ፤ ከፓሪስ አንስቶ እስከ ቶኪዮ በራዲዮ ቴሌፎን መነጋገር ድምጹ በተለየ ሆኖ እንዲሰማ ሆኑዋል ።

ማስታወቂያ

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲	ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር	፱	ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
የዓለም ጅዖግራፊ በአማሪኛ ደኅና ጥራዝ ዋጋው	፯	ብር
» » » መናኛ ጥራዝ ዋጋው	፭	ብር
ደግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፭	ብር
ኅሐ ጽባሕ	፭	ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫	ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫	ብር
የሕይወት ታሪክ	፪	ብር ተኩል
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪	ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪	ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትርሜጓው	፪	ብር
የቁጥር ትምርት	፩	ብር
ያማሪኛ ሰዋስው	፩	ብር
ወዳጄ ልቤ	፩	ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን		አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ		አላድ
አጭር የዓለም ታሪክ		አላድ
ያማሪኛ ፊደል		ሩብ
አሳብና ምኞት		ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት		ሩብ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፪	መ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር		፪መ
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ		ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶ ግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ		ሩብ

የአዲስ አበባ ገበያ ።

የቀንድ ከብት

የሚታረድ በሬ ዋጋ	፵ ብር
የእርሻ በሬ	፴፭ ብር
ያሩሲ ድልብ በሬ	፶፭–፹ ብር
የምትረባ ላም	፴፭ ብር
መሲና ላም	፴፪ ብር
የምትረባ በግ	፫ ብር
መሲና በግ	፭ ብር
ሙክት በግ	፲፫ ብር
የምትረባ ፍየል	፬ ብር
መሲና ፍየል	፯ ብር
ሙክት ፍየል	፲ ብር

የጋማከብት

ስንጋ ፈረስ ዋጋው	፸፭ ብር
በግሬ ፈረስ	፳–፳፰ ብር
አጋሰስ ፈረስ	፳፯ ብር
የኮርቻ በቅሎ	፻፶ ብር
ስናር ዓይነት በቅሎ	፻፹ ብር
አጋሰስ በቅሎ	፸ ብር
የምትረባ አህያ	፲፯ ብር
የጭነት አህያ	፳፯ ብር
ዶሮ ዋጋው	ከሩብ–አላድ
ዕንቍላል ሠላሳ	፩ ብር

የእህል ገበያ

ስንዴ ፩ ጆኒያ	፲፪ ብር
ገብስ	፱ ብር
ጤፍ	፲፫ ብር
ሽንብራ	፲ ብር

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፩ ብር ተሰስት ሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፫ ብር ተሩብ
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳ ብር ተኩል
የ ዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፬ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፰ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ከረጃ	፰ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ከረጃ	፲፰ ብር ተኩል
አቡጀዲ መነጽር	፩ ከረጃ	፻፴፪ ብር
፡፡ ባለሰይጣን	፡፡	፻፴፩ ብር
፡፡ ባለ ድመት ።		፻፴፩ ብር
፡፡ ባለአህያ	።	፻፳፰ ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል	።	፻፴፭ ብር
ባለ አንበሳ	፡፡	፻፴፭ ብር
ሱካር	፩ ጁኒያ	፴ ብር
ቻይ	፩ ነጥር	፫ሩብ ከሁለት መ

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ ፲፭ ሳንቲም
አንድ ብር	ሊሬ ፰ ከ፳ ሳንቲም
በአንድ ጊኒ	፲ ብር ፯ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፬ ብር

A LOUER

COGNAC S.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም እንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በለንደን ከተማ ነው።

ደግሞ በኒዮርክ በፊላዴልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፣ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም ፤ የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ፤ የልብ ፤ የደረት ፤ የጉበት ፤ የኩላሊት ፤ የጅማት የጨብጥ፣ የቂጥኝና የቋቁቻ፣ የሚያዋልድ፤ በኤሌክትሪክየሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል

እደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ሱቅ ነው ።

ዓለም ሱቅ ፲፪ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል ። ሙዚቃም በየ ዓይነቱ እንደ ሴንፎር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል ።

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ ኦቤርላንድ ኦቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጦን፟ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።



አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባ ኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባተሪ ነው ካምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ ኦቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል «ዓረብያን ትሬዲንግ፤ኩምፓንያ» ነው

ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ያፅናኝነት ፈቃድ የተቀበለ ።

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህ በካፕሱሉ ያለ ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በካፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው ።

ጉድይር ግዙ





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው ።በሌላጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ፤ ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አራተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፳፰
4 me ANNÉE № 28

ሐሙስ ሐምሌ ፭ ቀን ፲፱፻፳ ዓ ም ።
JEUDI 12 JUILLET 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d'Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadairé paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ጸሐፊው ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ለአንድ ቁጥር ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie
Un an 5 Thalers
Etranger
Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres



የተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ተማሪዎች ልዑል የኢ መ አ ወ ተፈሪ መኰንንን ለመቀበል ሲጠባበቁ ።

ልዑል የኢ መ አ ወ ተፈሪ መኰንን ተማሪዎቹን ከዩ በኋላ ከትምህርት ቤቱ ዋና ሹም ከአዛዥ ወርቅነህ ጋራ እንደተነጋገሩ ።

የተማሪዎች ሽልማት ።

ሰኔ ፴ ቀን የልዑል አልጋ ወራሽ ትምርት ቤት ስለ ዕረፍት የሚዘጋበት ጊዜ ስለደረሰ ልዑል አልጋ ወራሽና ልዕልት ወይዘሮ መነን አስተማሪዎቹንና ተማሪዎቹን ደስ ለማሰኘት ወደ ትምርት ቤት እንዲሔዱ ታውቆ ነበር ፤ በዚሁ ቀን በ፱ ሰዓት ክቡራን የውጭ አገር ሚንስትሮችና ወይዛዝሮች የኢትዮጵያም ሚንስትሮችና መኳንንቶች በትምርት የበለጡ የበለጡ ተማሪዎች ከልዑል አልጋ ወራሽ ስጦታ ሲቀበሉ ለማየት ተጠርተው ነበርና ወደ ትምርት ቤቱ ተሰበሰቡ አስተማሪዎቹም ተማሪዎቹን አሰልፈው የልዑልን አመጣጥ ይጠባበቁ ነበርና ልዑል በመጡ ጊዜ የሰላምታ ሙዚቃ እየነፋ እጅ ነሡ ።

ከዚህ በኋላ ልዑልና ልዕልት በተሰናዳው ቦታ ተቀመጡ ሚኒስትሮችና መኳንንቶች ወይዛዝሮችም እንደ ማዕርግ እንደ ማዕርጋቸው በተሰናዳላቸው ቦታ ተቀመጡ ፤ ከዚህ በኋላ ክቡር አዛዥ ወርቅነህ የሚከተለውን ቃል ተናገሩና ተጨበጨበላቸው።

ልዑል ሆይ ።

ክቡራን ወይዛዝርና መኳንንት ፈቃዳችሁ ሁኖ ጥቂት እናግር ዘንድ እወዳለሁ ። መጀመሪያ ሽልማታችንን በምናድል በት ቀን ዛሬ ከዚህ በመሆናችሁና ባደረጋችሁልን ክብር በራሴና ባስተማሮቹ በተማሪዎቹምስም ሆኜ ምስጋና አቀርባለሁ እንደምታውቁት የውጭ አገርን ሥልጣኔ ለማስተማር ታስቦ የትምሕርት ቤቱ ከቆመ ፫ኛ ዓመቱ ብቻ ስለሆነ እጅግ የሚያኰራ ስራ ለመስራት የተቻለን አይመስለኝም ዳሩ ግን ተማሮች ዕውቀትን ለማግኘት በመትጋታቸው ደስ እንዳሰኙን አሳስባችኋለሁ ። ስለዚህም ስለ ትጋታቸው ሁሉ እኔ ልመሰክር ከምችለው ይልቁንም ክቡር ወዳጄ ዲረክተር ሊያስረዳችሁ የተዘጋጀ ነው

ባለፈው ዓመት ተማሪ ቤቱ ሲዘጋ እንደዚሁ ገቢና ወጪዉ አመዛዝነን ወደዚህኛው ዓመት ያሳለፍነው ቀሪ ገንዘባችን	፴፫ሺ፱፻፺፯ ብር ፲መ ፩ቤሳ ነበረ		
ደግሞ የዚህ ዓመት ገቢ ከልዑል	፶፱ሺ፫፻፴	፫	
ልዑል በለ አባትና እናት ሆነው የከፈሉላቸው ጭምር የተማሪዎች ገቢ	፱ሺ፬፻፺፯	፲	
እርዳታ	፺ሺ፫፻፶		
ከልዩ ልዩና ከትልቅት ከሹራብ ከሽማ ሽያጭ ገቢ	፩ሺ፫፻፺፯	፯	፩
የገቢ ድምር	፻፫ሺ፯፻፳፯	፲፱	
ከዚሁ ከእርዳታው ገቢ ውስጥ	፯ሺ፯፻፶ው		
የደጃዝማች ሀብተ ማርያም ገብረ እግዚአብሔር ያ፭ ዓመት እርዳታ የ፱፻ ወቄት ወርቅ ሺያጭ ነው			
በዚህ ባ፭ ዓመት ውስጥ ወጭ ገንዘባችንም ይህ ነው			
ለመምሕራንና ለሠራተኞች ደመወዝ	፲፱ሺ፫፻፯		
ለተማሪዎች ምግብና ልብስ ለመጻሕፍትና ለቤት ጉዳይ	፳፭ሺ፵፯	፯	
ለቤት መሥሪያና መጠገኛ ለማሠሪያም	፳፬ሺ፻፳፩	፲፫	፩
በልዩ ልዩ ምክንያት ለተማሪ ቤት ጉዳይ	ሺ፬፻፲፱	፫	፩
የወጭ ድምር	፷፫ሺ፭፻፱	፯	
አሁን በማኀን ቀሪ ገንዘባችን	፷፱ሺ፻፳፱	፯	

ዳግም ለወዳጆቼ ለተማሮች ጥቂት እናገር ዘንድ እወዳለሁ ። ከልዑል ርኅራኄና ማሰብ የተነሳ ይኸውና በድሎት ትምሕርትና ብርሃንን ስላገኛችሁ እንዲህ ያለውን ውለታ በልባችሁ ቀርጻችሁ እንድታኖሩት አሳስባችኋለሁ ። ልዑልም ይኸን ያህል ደክመው የሚያስተምሯችሁ ለወደፊት ሁለት ምኞቶች ስላሏቸው ነው ። ከነዚህም ከሁለት ምኞቶች አንደኛው የሚጠቅም ዕውቀት ካገኛችሁና በዚህም ከዳበራችሁ በኋላ አገራችሁን በእምነት በእውቀት በሥራት አካሄድ ትክክለኛውን መንገድ ይዛችሁ እንድታገለግሉ ነው ሁለተኛው እውነተኛ ክርስቲያን ከልሆኑ ትምህርትና እውቀት ሁሉ ከንቱ ነውና ሃይማኖታችሁን እንድታጸኑ ነው እንግዴህ እናንተን በስራት ለማሳደግና በድሎት ለማስተማር ልዑል የሚደክሙበትን ፍሬውን ምክንያት ካወቃችሁ ይኸን ያለባችሁን ውለታ የምትመልሱት በማናቸውም ታማኝና ምሁራን ሁናችሁ ስታድጉ የሥራ ፍቅር አድሮባችሁ ውነተኛዎቹ ኢትዮጵያውያን በመባል ነው

የትምህርት ቤቱን ጓደኞችን ክቡር ዲረክተሩንና አስተማሮችን ደግሞም ታዛዥና ፈቃድ ፈጻሚ ሁነው በዚሁ ባሁኑ ዓመት በቀን ላገለገሉን ሠራተኞች ሁሉ ጥልቅ ምስጋናዬን አቅርቤ አረጅም እድሜ ለግርማዊት ንግሥታችንና ለልዑል አልጋ ወራሻችን እመኛለሁ ።

የኢትዮጵያ መዝሙር ባማርኛ ።

፩ኛ ፤ እንደ ዓይን ብሌን ጠብቃት ።
የባዕድ እግር እንዳይረግጣት ።
ኃያል አምላክ ወዲያ ከልክላት ።
ይችን ለምለም ጠብቅ መድኃኔዓለም ።
፪ኛ ፤ አበበዋ መልክም የገነት ።
ከባሕር አልፎ የሚሸት ።
ተደነቁ የሩቅ ነገሥታት ።
ይችን ለምለም ጠብቅ መድኃኔዓለም ።
፫ኛ ፤ ይቺ ይቺ ቆንጆ ሀብታሚቱ ።
አጊጣለች አሁን በዘውዲቱ
መድኃኒት ሆነች ለፍጥረቱ
ይቺን ለምለም ጠብቅ መድኃኔ ዓለም
፬ኛ ታለብሳለች ደግሞ ልጆቿን
ጥሩ ጥበብ ሠርታ በመነን
የሚረዳት በጣም ይመስገን
ይቺን ለምለም ጠብብ መድኃኔ ዓለም
፭ኛ ወዲያም ወዲህ አትዙሪ
ሥራ ፈትተሽ በከንቱ እንዳትቀሪ
ተዪ ተዪ አረሬ በተፈሪ
ይቺን ለምለም ጠብቅ መድኃኔ ዓለም

ተጻፈ ከማኅተመ ወርቅ እሼቴ ።

ቀጥሎ በትምርት የበለጡ ልጆች በየስማቸው እየተጠሩ ልዩ ልዩ የሽልማት ስጦታና በልዑል አልጋ ወራሽ መልክ የተቀረፀ የወርቅ ሜዳይ በልዑል እጅ እየተቀበሉ በተቀበሉ ቍጥር ጭብጨባው ይቀልጥ ነበር ።

በፈረንሳይ ትምህርት የበለጠ ባሕሩ የተባለ ነው ።
በእንግሊዝ ትምህርት የበለጠ ናደው የተባለ ነው ።

ሕፃናቱ በመካከል ቁመው ምሥጢረ ሥላሴን ጥያቄና ምላሽ እያደረጉ አነበቡና ተጨበጨበላቸው·

ከዚህ በኋላ ልጆቹ ሙዚቃ ባማረ ዜማ መቱ።ወዲያው የቻይ ግብዣ ተደረገ ቀጥሎም ተማሪዎቹ በፈረንሳዊ አሳምረው ቲአትር አሳዩና ተጨበጨበ ፤ ዲረክተሩም ሙሴ ቶማዚኒ ቀጥሎ ያለውን ተናገሩና ተጨበጨበ ።

ልዕልትና ልዑል ሆይ ።

ክቡራን ወይዛዝርቶችና መኳንንቶች ሆይ ።

ከሁሉ አስቀድመን የዚህን የተማሪ ቤታችንን ታላቅ በዓል ለማክበር እዚህ ስለመጡልን ለልዕልት ወይዘሮ መነንና ለልዑል አልጋ ወራሽ ጥልቅ የሆነ ምስጋናችንን እናቅርብ ዘንድ ይፈቀድልን ።

ደግሞም ክቡራን ወይዛዝሮችና መኳንንቶች እዚህ አደራሽ ውስጥ መሰብሰባቸው የተማሪ ቤታችንን በዓል ለማክበር መሆኑን ያስረዳናል፡ይኸውም ለእኛ ታላቅ ክብራችንና በሥራችንም ላይ በጣም የሚያበረታን ነው ።

ክቡራን ወይዛዝሮችና መኳንንቶች ሆይ ይኸው ሌሴው ከተከፈተ አጀምሮ ሰስት ዓመቱ ነው ። አነዚህኑም ያለፍናቸውን ሰስት ዓመታት ብንመለከታቸው ከለፉት ዓመታት ሁሉ የበለጡና ፍሬያማ ሆነው ይታያሉ ።

ከተከፈተም አጀምሮ ሌሴው መስፋፋቱን አልተወም የቀድሞዎቹ አንድነት የሌላቸው ክፍሎችና የተማሪቤቱ ደምብ በትክክል የማይሄድ የነበረው አሁን የተስተካከለ ደምብ ተበጅቶላቸው ትምህርቱም በሁለት መቶ ተማሪዎች በጥብቅ ይሠራል።

ይኸውም መሆኑ ከኢትዮጵያ ብዙዎች የታወቁእናት አባቶች ልዕልናዎ ወደእርስዎ ዘንድ በጠራቻቸው አስተማሪዎች ላይ እምነታቸውን ስላደረጉ ነው፤በዜሁም ዓመት ስምንት የተማሪ ቤት ክፍሎች ከነዚሁም አራቱ የፈረንሳዊና አራቱ የእንግሊዝ የሆኑ በአሥራ ሰስት መምሕራን ጥበቃ በትክክል ሠርተዋል ።

የተማሪዎቹም ቁጥር እየበዛ መሔዱን አይተናል ይኸውም መሻሻል ከፍ ከፍ እያለ ይሔዳል እንጂ አይቀርም።በሥራቸውም ላይ በመጠንከር በጥቅል ድምር የተገኙበት ፶፭ሺ ፱፻፳፪ ጊዜ መሆኑንና የቀሩበትም ፱ሺ፪፻፷፫ ጊዜ ብቻ መሆኑን በመዝገባችን ላይ አግኝተናል እንዲህ ተሆነ ተማሪዎቹ አዘውትረው ተማሪ ቤት መጪናቸው እንዳአከሔዳችንም ጥንከሬ ብዙ ተመላላሽ ልጆችም አዘውትረው እተማሪ ቤት ከመምጣት አልቀሩም

በመጨረሻውም የልጆቹ ባሕሪና ሥራቸውም በጣም ያማረ ነው ይኸውም ሁሉ በጠቅላላው በአንድ ዓመት ትምሕርት ውስጥ የተሠሩትን ታላቅ መሻሻል ያስረዳል ለዚሁም የመምሕራኑን አገልግሎት ብቻ ሳይሆን ብርሃ ንየሆነና የተስተካከለ የአድምንስትራተሩን የአዛዡ ወርቅነህንም እውቀት ላመሰግን ይገባኛል ለእንግዲህ ወዲያው የጥበብን ትምሕርት ይልቁንም የታሪክንና የጂዖግራፊን ባጭሩ ለማድረግ ሲኒሞቶግራፊ ትምሕርትም ጥቅም ያለው መሆኑን ላስታውቅ ይገባኛል።

እንደዚሁም አንድ የተኒስ መጫወቻም ቦታ ተሠርቷል በብዙ ቦታ ሌሴውን ብዙ ስራ የሚሠራበት ቤት የሚያደርጉ የተጀመሩ ሕንፃዎችም ይታዩበታል እነዚሁም ሕንፃዎች ለመጪው ጥቅምት አዲሶች የትምሕርት ክፍሎችና ልዩ የታሪክና የሥዕል ክፍሎችም ጨምረን ለመክፈት ይፈቅዱልናል።

ደግሞም አዲስ መምሕራን አንድነታቸውም የመጀመሪያውን ሁለተኛ እረፍት የተባለ ትምሕርትን እንድንጨርስ የሚረዳን ይመጣሉ ብለን እንጠብቃለን ።

ክቡራን ወይዛዝሮችና መኳንንቶች ሆይ ይኸውም ልዕልናቸው የመሠረተው ሕንፃ አገሩን ለማሠልጠንና በውቀትና በእውነትም ለማሻሻል መሆኑን ያስረዳናል ።

ያለጥርጥር በታላቅ በማይገመት ፈቃድ ለሀገራቸው ጥቅም መማርን ስለወደዱና ሥራን መውደድም በእነሱ ዘንድ በጣም ታላቅ ሆኖ ስለሚታይ ይኸውም መልካም ሥራ ከታላቅ ብልህነት ጋር ስለተያየ፡ ልጆቹም በበኩላቸው ታላቅ ጠባቂያቸው የሚደክሙላቸውን ድካም ተረድተውታል ልንል እንችላለን

ይኸም ከሆነ ተማሪዎቹ እንደሚገባ አድርገው ለተወዳጅ አባትነትዎ ወረታቸውን እዲመልሱ ልዕልናዎ ልትረዳው ትችላለች ።

ከጥቂትም ዓመታት በኋላ መጪው የተሰናዳና ያማረ ሲሆንላቸው ልዕልናዎ የምታደርግላቸውን ደግነት በጣም ያልቁትና ዘወትር ኢትዮጵያ በምታድግበት መንገድ በማገልገል ብድራቸውን መመለስ በልበናቸው ያድርባቸዋል·

ክቡር ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ ያገር ግዛት ሚንስትር የተናገሩት ንግግር ከዚህ ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው ።

ልዑል ሆይ ።

ለኢትዮጵያ ለሃገርዎ ከሚደክሙላት ከብዙው ደጋግ ሥራዎ ሁሉ ሕዝቧ በሥልጣኔ ጐዳና እንዲሄድላት የትምሕርት ቤቶችን ማነቃቃት ሆንዋል ይልቁንም ይህ በስምዎ የቆመውን ተማሪ ቤት አስበው በብርታትና በትጋት እንዲሠራ በመጣጣርዎ መምሕራኑም በትጋትና በፍቅር እያገለገሉ ተማሪዎቹም በንቃት ትምሕርታቸውን እያጠኑ በሥራ በመሻሻላቸው ለወላጆቻቸውም ለኛም ታላቅ ደስታ ሆኖልናል ።

ልዑልንም ከልብ እንዲያመሰግኑት ጥርጥር የለበትም ከዚህ ከልዑል ተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት ያላችሁ አስተማሮቹ በትጋት በመሥራታችሁ ተማሪዎቹም በንቃት ትምሕርታችሁን በመማራችሁና እንደዚህ ደስ የሚያሰኘውን ነገር ስላሳያችሁን እጅግ ልትመሰገኑ ይገባል ።

አሁንም ሁሉን የሚችል እግዚአብሔር ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ለልዑል አልጋ ወራሽ ረጅም ዕድሜ አድሎልን ሐሣብዎን ሁሉ እንዲያስፈጽምዎ በፍጹም ልብ እመኛለሁ

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር ።

ቀጥሎም ክቡር የቤልጅክ ባለሙሉ ሥልጣን ሚንስትር በራሳቸውና በጓደኞቻቸው ስም ለልዑልና ለተማሪ ቤቱ ሹማምንቶች አስተማሪዎችም የምስጋና ቃል ተናገሩና ተጨበጨበ

ጌታዬ ደስ የሚሉትን የልጅነት ጊዜያቶቻችንን በያንዳንዳችን መንፈስ በእንደዚህ ያለ ውበት ወደምታስብ ወደዚች ትንሽ በዓል እንድንመጣ ፈቃድዎ ሆኖ በመጥራትዎ ስላደረጉልን ክብር በዲፕሎማቲኮች ክፍል የሥራ ጓደኞቼ ስም ሆኜ አመሰግንዎ ዘንድ እንዲፈቅዱልኝ ጥርጥር የለውም ።

ጌታዬ ልዕልናዎ ስለ ጥንታዊ ትምሕርት ነገር ያሰበውን ዘወትርም የሚያስብለትን ታላቅና ከልክ ያለፈ ሀሳብ ሁላችንም እናውቃለን ። ስመ ጥሩ የሆኑ የልዕልናዎ አባቶች ባደረጉት ትጋትና ጥንካሬ ባለፈው ጊዜ እንዳስረገጡት ሁሉ ለሚመጣው ጊዜ የንጉሠ ነገሥት መንግሥቱን ታላቅነት ጠብቆ ለመኖር የኢትዮጵያ መንግሥት የሚያገለግለውን መንገድ ማግኘት የሚገባው በትምሕርት ብቻ መሆኑን ከልዕልናዎ ይበልጥ ማንም ሰው አልተረዳውም ።

እንደዚሁም ደግሞ ልዕልናዎ ብርሃናዊ በሆነና ፍሬ ባመላበት በዚህ ጐዳና በሀሳቡ ለመጠንከር ምንም ነገር እንዳይከለክለው የምንመኘውን የበለጠ የወዳጅነት ምኞት እዚሁ ለመግለጽ በተለየ ደስ ይለኛል ። የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትን ከፍ ያለ ስም እያስተባበርሁ እነዚህን ምኞቶች በምገልጽበት ቃል የሥራ ጓደኞቼን ሀሳብ በታመነ አነጋገር እንደተናገርሁ እርግጥ ነኝ ። ደግሞ ዘወትር በሥራቸው ጐልማሳና ትጉህ ለሆኑ ለተፈሪ መኰንን የትምሕርት ቤት አለቃ ላዛጋ ወርቅነህ እንደዚሁም ለታመኑ ረዳቶቻቸው ለመምሕራኖቹ በመላውም በተደላደለ ልቡና በቁርጥ ሀሳብ በፊታችን በተራ ሲያልፉ ላየናቸው እያንዳንዳቸው በጊዜያቸው በሠሩት ሥራ ፤ እያንዳንዳቸው ዛሬ በሚያስቡዋቸው ታናናሽ ሀሳቦችና ለነገ በሚመኙአቸው ታናናሽ ምኞቶች አምላካዊ ንጉሥ በግርማዊትና በንጉሠ ነገሥታዊ ልዕልናዎ ጠባቂነት ያኖረውን መልካም አገር በግዙፍ ሰውነትና በረቂቅ አእምሮ ለማስፋትና ወደ ሥልጣኔ ለማስቀደም ሁላቸውን እንደ ተክል ሆነው ለሚታዩ ለነዚህ ለወጣት ተማሪዎች ሁሉ ይህን ጊዜ ምክንያት አድርጌ የወዳጅነት ሰላምና የሚበልጥ የጋለ ምስጋናችንን ሳላቀርብ ብቀር የተገባኝ አይደለም ።

ጌታዬ ወደዚህ ወደሚያምር በዓል እንድንመጣ እኛን ለመጥራት ልዕናልዎ ስላደረጉልን ደግነት የዲፕሎማቲኮችን ክፍል ምስጋና እንደገና ደጋግሜ የማቀርብልዎ እነዚህን ሀሳቦች በልቤ አኑሬ ነው ። ለበዓሉም ሁላችንም መልካም መታሰቢያ እናኖርለታለን ።

Monseigneur,

Vous me permettrez sans doute de Vous remercier, au nom de mes Collègues du Corps Diplomatique, de l'honneur que Vous avez bien voulu nous faire en nous invitant à cette petite fête qui évoque si grâcieusement dans l'esprit de chacun de nous les jours heureux de notre première jeunesse.

Nous savons tous, Monseigneur, l'intérêt puissant et passionné que Votre Altesse accorde et a toujours accordé à la question primordiale de l'enseignement. Nul, mieux que Votre Altesse, n'a compris que c'est dans l'instruction, et dans l'instruction seulement, que le Gouvernement Ethiopien doit trouver les moyens propres à assurer, dans l'avenir la grandeur de l'Empire, comme l'énergie et la ténacité de Ses illustres ancêtres l'ont si bien affirmée dans le passé.

Aussi bien, m'est-il particulièrement agréable d'apporter ici le témoignage des voeux les plus sympathiques que nous formons pour que rien n'empêche Votre Altesse de persévérer dans cette voie lumineuse et si pleine de promesses et je suis certain d'être le fidèle interprète de mes Collègues en associant l'auguste nom de Sa Majèste l'Impèratrice dans l'expression de ces souhaits.

Par ailleurs, je m'en voudrais de ne pas saisir cette occacion d'adresser un salut cordial et nos plus chaleureuses félicitations au toujours jeune et actif Administrateur de l'Institut Taffari Makonnen, l'Ázage Hakim Workeneh ainsi qu'à ses dévoués collaborateurs du Corps Professoral, et, en général, à tous ces jeunes étudiants que nous venons de voir défiler si crânement devant nous et qui, chacun dans sa modeste sphère d'action, chacun dans ses petits rêves d'aujourd'hui et ses petites ambitions de demain, portent tous en eux comme le germe du progrès et du développement matériel et moral du beau pays placé, par la Divine Providence, sous l'égide de Sa Majesté et de Votre Altesse Impériales.

C'est dans ces sentiments que je Vous réitère encore, Monseigneur, les remerciements du Corps Diplomatique pour la bonté que Votre Altesse a eue de nous convier à cette jolie cérémonie dont nous conserverons, tous, le meilleur des souvenirs.

ከዚህ በኋላ ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ለመናገር በተነሡ ጊዜ ሁሉም ቀጥ ብሎ ቆመ ። ንግግሩም የሚከተለው ነው ።

ክቡራን መኳንንትና ወይዛዝር ሆይ ።

የጃንሆይ ዳግማዊ አፄ ምኒልክን አሳብ ተከትዬ ይኸን የትምሕርት ቤት ከሰራሁ በኋላ በሀገራችን በኢትዮጵያ ብዙ የትምሕርት ቤቶች ተከታትለው እንዲሰሩ በትልልቁ መኳንንቶች እምነት ስላደረግሁ የዛሬ ሰስት ዓመት ይህ የትምሕርት ቤት በተከፈተ ጊዜ በዓሉን ስናከብር ኢትዮጵያን እወዳለሁ ማለት በሥራ ጭምር ነው እንጂ ፤ በቃል ብቻ አይደለምና ይህ በትንሹ የተጀመረው የትምሕርት ሥራ እያደር እንዲበዛና እንዲሰፋ በኢትዮጵያ በዋና በዋና አውራጆች አንድ አንድ የትምሕርት ቤቶች እንዲሰሩ እንደ መስታወት ተገልጦ ስለ ታየን ነገሩን አንስተን ተናግረነው ነበር ከተናገርነውም ነገር በእግዚአብሔር ቸርነት ወደ መፈጸም የቀረበው ብዙ ነው ።

፩ኛ ፤ ክብርት ወይዘሮ ስኂን እጅግ ብልህና አዋቂ እንደነበሩ ታውቃላችሁ· ጥልቅ የሆነ አሳባቸውን የሚያስረዳ ነገር ብሞታቸው ጊዜ ሲናዘዙ ። ለድሆች ልጆች መማሪያ እንዲሆን በገንዘቤ ደሴ ላይ የትምሕርት ቤት አሰራልኝ አደራህን ብለው ስለ ተናዘዙ ቤቱን የልጃቸውን የራስ ኃይለ ማርያምን ቤት አሳድሼ በፊታችን መስከረም ሊከፈትናትምሕርቱ ሊጀመርነው ።

፪ኛ ፤ ወይዘሮ መነን ደግሞ የኢትዮጵያ ወንዶች ልጆች ተምረው ሲጨርሱ የተማሩ ሴቶች እንዲያስፈልጓቸውና ያገር ጥቅም መሆኑን ስለተረዳችው ለሴቶች ልጆች የትምሕርት ቤት በገንዘብዋ ለማሰራት አሁን የቤቱ መሰረት ማለቁን ሳትሰሙት አልቀራችሁም ።

፫ኛ ፤ ደጃዝማች ብሩ በገንዘቤ አስተማሪና ሃኪም ቀጥሬ የትምሕርት ቤትና ሆስፒታል ሰርቼ በተሾምሁበት አገር የሚኖሩትን ሕዝብ ለመርዳት አስቤአለሁና እረዳታዎን ያድርጉልኝ ብሎ ቢያስታውቀኝ አሳቡን በደስታ ተቀብዬ አስተማሪና ሐኪም አስመጥቼለት አሁን በፊታችን መስከረም ልሰድለትና ሊከፈት ነገሩ ተቆርጧል ።

አሁንም ለኢትዮጵያ ልጆች ጥቅም የሚቆሙትንና የቆሙትን የትምሕርት ቤቶች ሁሉ ባለመለየት ልጠብቃቸውና ልረዳቸው ሥራዬ ስለሆነ ወደ ፊት ከመኳንንቱም ወገን ቢሆን ከሕዝቡም ወገን ቢሆን የትምሕርት ቤት አቆማለሁ ያለና የሚል ሰው ቢኖር በሚቻለኝ ሁሉ እርዳታዬን አላጎድልበትም ።

የተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤትን ልጆች ተምረው ወደ ትልቅ ደረጃ እንዲደርሱ በትጋት የሚያስተምሯቸውን የትምሕርት ቤቱን ዲሬክተርና የትምሕርት ቤቱን ዋና ሹም አዛዥ ወርቅነህን እናመሰግናለን ።

ተማሪዎቹም በትጋት ተምራችሁ ወደትልቅ እውቀት ደርሳችሁ ኢትዮጵያን በመርዳት ደስ እንድታሰኙ እንመኛለን ።

እናንተም ያገራችንና የውጭ አገር ወይዛዝርና መኳንንቶች የኢትዮጵያ ልጆች በትምሕርት ማደግ ለኔ የደስታዬ ቀን ነውና ፤ የደስታዬ ተካፋዮች ለመሆን ወደዚህ ሥፍራ ስለመጣችሁልኝ አመሰግናችኋለሁ ። ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር።

ንግሥት ነገሥታትን እግዚአብሔር ይጠብቅ ።

ብለው ተናግረው ሲጨርሱ ሶስት ጊዜ ጭብጨባው ቀለጠ ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያን ማርሽ ልጆቹ በሙዚቃ ዘመሩ· ልዑልም ከመኳንንቱ ጋራ ተማሪ ቤቱን በየክፍል በየክፍሉ አዩና ሁሉም ወደየቤቱ ሄደ ።

Traduction du discours prononce par SON ALTESSE IMPERIALE TAFARI MAKONNEN à la distribution des prix du Lycée TAFARI MAKONNEN; le Samedi 7 Juillet 1928:

Messieurs les Membres duCorps Diplomatique

Mesdames, Messieurs

En suivant la noble idée de Sa Majeste l'Empereur *MENELIK*, J'ai eu la joie de fonder cette école dèja vieille de 3 ans. Dans le discours que J'ai prononcè à la fête d'inauguration de cet Etablissement scolaire, Je déclarais, animé par la confiance que J'ai toujourrs eue dans nos grands Chefs, que l'amour de la Patrie ne devait pas s'exprimer seulement par la parole mais aussi par l'action. J'exprimais en même temps le voeu de voir les grandes provinces de l'Ethiopie crèer et multiplier les Maison d'education et d'instruction.

Avec la grâce de Dieu, mes Previsions sont en bonne voie de réalisation.

1- Vous avez, tous, pu apprécier la vive intelligence dont se distinguait la *Woyzero Sehine*. Cette superiorité intellectuelle trouve sa plus éclatante confirmation dans le fait qu'avant sa mort elle a exprimé par testament, sa volonté en me recommandant, pour que je lui crée une école avec ses propres deniers dans son pays d'origine, á Wollo, devant étre affectée à l'instruction de ses compatriotes orphelins. En consequ'ence j'ai fait déjà réparer la maison de son fils *Ras Haile mariam* qui servira dé cette école et louverture en aura lieu au mois de Septembre.

2 Son Altesse Imperiale la princesse *MANAN* se rendant compte de la nécessité de donner aux jeunes filles une instruction aussi soignée que possible, afin de les rendre dignes des garçons, leurs emules, a entrepris la construction, à Ses frais' d'une école destinée aux jeunes filles. Vous verrez, vous-même, que les fondations de cette école sont déjà achevées

5- Le Dedjazmatche Berrou M'ayant exprimé le désir de fonder, à ses frais, des écoles et des hôpitaux dans la Province dont il a l'admnistration, pour aider la population et propager l'instruction, J'ai accueilli avec une sincère joie cette généreuse proposition et J'ái décidé de lui envoyer en septembre des Instituteurs et des médecins.

C'est Mon devoir de protéger toutes les écoles sans distinction, car elles sont l'intérêt des enfants de l'Ethiopie. Toute proposition venant de la part de nos grands Chefs aussi bien que de celle du peuple pour la création des écoles recevra Mon appui le plus empressé et le plus complet.

Nous remercions l'Administrateur Général l'Azage *Workeneuh*, le Directeur et les Professeurs qui se sont attelés à la noble tâche. avec un touchant dévouement, de donner à leurs éléves un plus haut degré d'instruction.

Nous formons des voeux Pour que les eleves suivent avec assiduité leurs études pour pouvoir servir leur Patrie, l'Ethiopie.

Aujourd'hui Ma joie est grande de constater les progrès que les enfants de l'Ethiopie ont realisés dans leurs instructions, et Je remercie tout particulierement Messieurs les Membres du Corps Diplomatique, les Dames et les chefs de notre pays d'avoir bien voulu venir partages Ma joie.

Vive l'Ethioe.

Que Dieu protège Notre Auguste Souveraine Sa Majesté l'Imperatrice *ZEOUDITOU.*

ሹመት ።

ሰኔ ፳፱ ቀን ክቡር ሐኪም ወርቅነህ አዣጋር ተብለው በልዩ የቆመ ፍርድ ቤትን ተሾሙ ።

ክቡር አዣጋር ወርቅነህ ከዚህ ቀደም በተሾሙበትና በያዙት ሥራ ሁሉ ደኅና አድርገው በማስተዳደራቸውና ተግተው በማሠራታቸው የተመሰገኑ ናቸው አሁንም በልዩ የቆመ የፍርድ ቤትን የበለጠ እንዲያስተካክሉትና እንዲያስመሰግኑት ጥርጥር የለበትም ።

ብርሃንና ሰላም ክቡር አዣጋር ወርቅነህን እንኳን ደስ አለዎ እያለ መልካም ምኞቱን ያቀርባል ።

ማስታወቂያ ።

የልዑል አልጋ ወራሽ የትምሕርት ቤት ስለእረፍት ለሁለት ወር ሐምሌ አንድ ቀን ተዘግቶ መስከረም አንድ ቀን ይከፈታል ።

አዣጋር ወርቅነህ ።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም ፤ የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ፤ የልብ ፤ የደረት ፤ የጉበት ፤ የኵላሊት ፤ የጅማት የጨብጥ፤ የቂጥኝና የቋቁቻ፤ የሚያዋልድ፤ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል

አደጋዝማች ደስታ ዳምጠው ሱቅ ነው ።

ኦቤርላንድ



ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሽ ኦቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጦጦን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባ ኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባተሪ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል «ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው

ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ እሺቴ ሙዚቃሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሲንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

Odeon

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሰ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

COGNAC S.& E.& A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

RUGBY

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠንቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይ ወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኒዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፥ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ባርባሬዮ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬዮ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥት ነገሥታት ዘውዲቱና ከልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ ።

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህ በካፕሱሉ ያለ ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በካፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ጉዶደር ግዙ





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው።በሌላጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ፤ ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

አራተኛ ዓመት፤ ቁጥር ፳፱
4 me ANNÉE № 29

ሐሙስ ሐምሌ ፲፪ ቀን ፲፱፻፳ ዓ ም።
JEUDI 19 JUILLET 1928

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé "Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ጸሐፊቱ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

መልካሙ የክቡር ቄስ ስብከት ።

ታላላቅ ሰዎች ።

እሁድ ማታ በቀጠሯችን ከክቡር ቄስ ጋራ ተገናኘን መቸም ተላምደናልና ቀረብ ብዬ እተኰሬ ብመለከታቸው በሆዳቸው ብዙ የሚናገሩት ነገር እንዳለ አወቅሁ ወምበርም አቀረብ ሁላቸውና ከተቀመጡ በኋላ ወዳጄ ከፒቴን ሆይ ዛሬ የምንግርህን ስብከት ስማኝ የምናገረውም ስለታላላቅና ስለታናናሽ ሰዎች ነው አሉኝ እኔም መልሼ አልኳቸው የተወደዱ ቄስ ሆይ ምንድነው ታላላቅና ታናናሽ ሰዎች ማለት ? ። የዛሬው ንግግርዎ ትልቅ ነው ማለት ሰውነቱ ግዙፍ የሆነ ዣሮው የተንቀረፈፈ ራሱ ትልቅ ዱባ የሚያህል ሆዱ የተንዘረጠጠ ቁመቱ የረዘመ ዘበጣ ማለት ነውን? ። ደግሞ ትንሽ ሰው የሚሉት ከሳሳ ቀጭን ሴት አውል መሆኑን ሊያስታውቁኝ ነውን ? ወይስ ትልቅ ሰው ብዙ የሚበላ ስግብግብ ሆዳም የሆነ ነው ማለትዎ ይሆን ደግሞ ትንሽ ሰው የሚሉት ምንም የማይበላ ቁሽቢያም የሆነውን ሰው ይሆን ወይም ትልቅ ሰው ማለት ብዙ ገንዘብ ያለው አገረ ገጋር የሆነ ብዙ አሽከር በከብት ተቀምጦ ጨርቁን አፍንጫው ላይ አድርጎ በፊቱና በኋላው አስከትሎ ታጅቦ የሚሄድ ነውን ደግሞ የደኸየ ልብስ የሌለውን ሰው ትንሽ ሰው ሊሉት ይሆን ብዬ ብጠይቃቸው ቀጥሎ ያለውን መልስ ሰጡኝ ወዳጄ ከፒቴን ሆይ ስማኝ ልንገርህ ይህ ሁሉ አይደለም አንድ አንድ ጊዜ እግዚአብሔር ለሴቶች የተባረከ ልጅ እንዲወልዱ የሚሰጣቸው ቸርነት ነው ታላላቅ ሰዎች የበላዮች ሆነው ትሑቶች ናቸው ከበርቴዎችም ቢሆኑ ቸሮች ናቸው ድል ባደረጉ ጊዜ ግፍን ማድረግ አይወዱም በሰውነታቸው ለሰው ተዋራጆች ናቸው ችሎት እያላቸው በደልን አይወዱም ፍቅራቸው የጠራ ነው እነዚህ ታላላቅ ሰዎች ለመባል የተገቡ ናቸው ብርሃናቸው ለሰውና ይልቁንም ላገራቸው እጅግ የሚጠቅም ነው ከሞቱም በኋላ ማስታወሻቸው ለዘለዓለም ይኖራል ለዘራቸውና ላገራቸው ያማሩ ጌጦች ናቸው በነሱ መንፈስ ዘሮቻችው በጤና ይኖራሉ መሐላቸውንም በነሱ ያደርጋሉ በነዚህ ሰዎች ክፍል መሐከል ነገሥታት ከበርቴዎች ይገኙባቸዋል ደግሞም ወዳጄ ከፒቴን ሆይ ከነዚህ መልካም ዘሮች ለነጻነትና ለእውነተኛ ፍርድ የተጋደሉ ጀግኖች ለዓለም ብርሃን የሆኑ አዋቂዎች ይገኙባቸዋል ። ልብ አድርገህ ስማኝ ታናናሽ ሰዎችን ልንገርህ የበላዮች ሆነው ክፉዎች ናቸው ሐብታሞች ሆነው ንፉጎች ናቸው ድል ባደረጉ ጊዜ ግፈኞች ናቸው በሐሳባቸው ዓመፀኞች ናቸው ርኅራኄ የላቸውም እነዚህ ታናናሽ ሰዎች መባል ይገባቸዋል ከነዚህ መሸሽ ይገባናል ላገራቸው ነውርና እንቅፋት ናቸው አዬ ምን ያልታደለ ነው እንደነዚህ ያሉ ሰዎች ያሉበት አገር ።

እንግዲህ ታላላቅ ሰዎች መኳንንቶች አዋቂዎች ከበርቴዎች ላገራቸው ፀሐይ ካላበሩ ምን ይረባሉ እንዴት ያለ ትልቅ ሰው ነው ነገ የሚሆነውን የሚነግረን ወይም ለራሱ የሚሆነውን የሚያውቅ ከአምላክ በተቀር አባቶቻችን በከንቱ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ምሳሌ አልተናገሩም ። ጕርፍ ያልፋል አሸዋ ግን ይቀራል ብር ይጠፋል የተቀመጠበት ሣጥን ይቀራል ሰው ይሞታል ስሙ ግን ይኖራል የበላይነት ሳለው የመስኮብ ንጉሥ ታላቁ ጴጥሮስ ትሁት ነበር በሆላንድ አገር ዛንዳም በሚባለው አውራጃ ትልቅ መታሰቢያ ቤት ሐውልት አለው ይህ ንጉሥ በትንሽ ጐጆ ብዙ ጊዜ ተደብቆ እንደ አንድ መሳሪያ ሠራተኛ በወታደርነት ሥራ ውስጥ ይሠራ ነበር እንግዴህ ታላላቅ ሰዎችን እንደመከተል ታናናሽ ሰዎችን መከተል አይገባንም የተወደዱ ቄስ ሆይ እስቲ ነገርዎን እዚህ ላይ ላቁመው ታላቅነት የሚያገኘው በእግዚአብሔር ቸርነት የተወለደ ነው ካሉ በምን ይታወቃል ልጅ ሲወለድ ትልቅ ይሆን ትንሽ ይሆን ብዬ ጠየቅኋቸው እርሳቸውም በቁጣ አስተያየት ተመለከቱኝና በኃይል ቃል እንዲህ

ብለው ተናገሩኝ አታውቅምን ማናቸውም ልጅ በናቱ ይታወቃል ደግሞም አሉ እኛ ግን እናቶች የሉንም ለሰው መልካም አስተዳደግ የምትሰጥ እናት ነች የሰው መልካም አስተዳደግ ከተወለደበት ቀን ጀምሮ ነው እናቶች እንኳ ቢኖሩን ከሚሊዮን መካከል አለመጠን ያነሱ ናቸው ምናልባት ፪ ፫ ቢገኙ ነው አገርን ለመጠበቅ ሁለት ነገር ያሻል እነርሱም መልካሙ የናት አስተዳደግና የተማረ ቤት አስተዳደግ ናቸው ።

ይህንንም ሲሉ የተወደዱ ቄስ ሆይ በውነት ባለፈው ሳምንት ከደምብ የወጣ ነገር ሁሉ እንዳዩ አወቅሁ ። ደግሞ ሐሳብዎና ንግግርዎ የተሰወረ ነገር ነው ሰው ሁሉ ይገባው ይመስልዎታልን ከኃይለኛ ነፍስ ጋራ ጦርነት የሚያደርግ ሰው እንዳይሆኑ እፈራልዎታለሁ አሎኳቸው እሳቸውም መልሰው አሉ አይደለም ወዳጄ ክፒቴን ሆይ ተስቶሃል እኔ ከንድ ሚሊዮን ሕዝብ ውስጥ አንድ ባገኝ ደስ ይለኛል ። ደግሞ ብዙ የሚሰሙን እንዳሉን አልጠራጠርም እኔም መልሼ አልኋቸው ክቡር ቄስ ሆይ ይህ ንግግርዎ ጥቂት የሚያስደንቅ ነው ከንድ ሚሊዮን ሕዝብ ውስጥ አንድ ብቻ ቢያገኙ እርስዎ ምን ያህል ዕድሚ ያገኛሉና ነው ይህን ማግኘት አይበሉት ። የተወደዱም ቄስ መለሱ አሉም ግድ የለም እኔ ብሞት ሐሳቤ አይሞትም ሌላ ደግሞ ይተክበታል ።

እኛ በትሕትና እንሠራለን ይህም ሥራችን ለኢትዮጵያ ልጆች ድል ይሆናቸዋል እኔም መለስኩ አልኳቸውም ብፁዓት ናቸው ታላላቅ ሰዎችን የሚወልዱ እናቶች ።

ክፒቴን ባቢኬያን

ስለ ከተማ ዘበኞች ትጋት ።

አሁን ባለፈው ሰሞን ውስጥ እኔ የብርሃንና ሰላም ወዳጅ የዘበኝነትን ሥራ አካሄድ አያለሁ ብዬ ወደዋናው የዘበኝነት ሥራ ማስኬጃ ጽሕፈት ቤት ተመላልሼ ነበር በዚሁም በነበርሁባቸው ቀኖች ውስጥ ከዚህ ቀጥሎ የምጽፈውን የሌብነት ሥራ ምርምር ሆነ ብዬ አስረግጬ አስተውል ነበር ።

፩ኛ ፤ ባለፈው ሰሞን አንድ ቀን ሁለት ሌቦች ተይዘው አንዱ ሌባ ቢጠየቅ ሙሴ ኤድዋርድ የሚባል የፈረንጅ አሽከር ሆኖ ተገኘ እነዚህም ሌቦች ዘበኞቹ ሲይዟቸው በነሱ እጅ ተሰርቆ የተገኘው ፴ ጣቃ አቡጀዲ ሆነ ፤ አንደኛውም ሌባ ደግሞ አብደላ የሚባል የእንግሊዝ ዜጋ አሽከር የነበረ የፈረንሳዊ መንግሥት ዜጋ የሙሴ ላጋርድን የወጥቤት እቃ ሰርቆ ኖሮ ስለተያዘ ቢመረመር መስረቁን አምኖ በዘበኛ አለቃው ትእዛዝ ወደ ቅጣት ፍርድ ቤት ሲሄድ አየሁት ።

፪ኛ ፤ ለጋር ላይ የሙሴ ያኒ ካርሰቴሎስ ፪ቱ አሽከሮቹ ፬ ደርዘን ኮኛክ በሣጥን እንደተገጠመ ሰርቀውት ሌሊት በአቶሞቢል አድርገው ከነጅውም ተስማምተው ይዘው ሲሄዱ ዘበኞቹ ነቅተው አቶሞቢሉን በሩጫ አቁመውት የተሰረቀው እቃና ሌቦቹ አብረው ተያዙ ።

፫ተኛ ፤ ሙኢዲሳሊ ከሚባል ሰው ቤት ሌቦች ሌሊት ከቤቱ ገብተው ገንዘብ ሰርቀውት ኖሮ አንዱ ሌባ በአቶሞቢል ተከራይቶ ሌሊት ተጉዞ ወዳንድ ሴትኛ አዳሪ ቤት ሲገባ ዘበኞች ጠርጥረው ቢይዙት የሰረቀው ፻፺ ብር በጁ ስለ ተገኘ አብረው የሰረቁትንም ተመርምሮ ስላሲያዘ ለቅጣታቸው ወደ ፍርድ መሄዳቸውን በማየት አስረግጫለሁ ።

፬ተኛ ፤ እንደዚህ ፪ ሌቦች የሙሴ ሚሰልን ቤት ሰብረው አርባ ብርድ ልብስና ፳ ያህል ባርኔጣ ስለ ሰረቁ ጥፋታቸውን አምነው ወደ ቅጣት ቤት ገብተዋል ።

፭ተኛ ፤ የሙሴ ሎንዶ ጀናይ አሽከር ከጓደኛው ጋራ ሆኖ ሌሊት መስኮት ሰብረው ፩ ሰዓት ፪ ኮት ፬ ማህን ያልጋ ልብስ ሞረድና የከኪ ሱሪ መስረቃቸውን ስላመኑ ለቅጣት ቆይተዋል።

፮ተኛ ፤ ሁለት ሌቦች የመሐመድ አሊ ኩምፓንያ ኢገም የሚባል አሽከራቸው ባዶ ባዶ ጆንያ እያቀበለን ሸጠናል ስላሉ ወደ ቅጣት ፍርድ ቤት ሲላኩ እዚያው አስተውል ነበር ከዚህም ሌላ ደግሞ የግሪክ ዜጋ ሙሴ ኬርያኮ ጆርጌ የሚባል ፈረንጅ ወደ ሰላሌ ኖራ ለማውጣት ሲሄድ ወልደ ገብርኤል ለሚባል አሽከሩ ፭፻ ብር አሸክሞት ሳለ ይዞበት ጠፍቶ ኖሮ ለዘበኛው አለቃ ስላስታወቀ በሰላይ ተፈልጎ ተይዞለት መውሰዱን አመነ ነገር ግን ያልታደለው ሙሴ ኬርያኮ ጆርጌ ከሌባው እጅ ገንዘቡ አልተገኘለትምና ገና በፍርድ ዳኛ ሌባው ይመረመርለታል ።

ሙሴ ኩን የሚባል ሰው አሽከሮቹ አራት ሆነው ፵፰ የበሬ ቆዳ ሰርቀውት ተይዘው ለቅጣት ቀርበዋል።

ሙሴ በረሰምን ቤጋር ምትቢት የሚባል የፈረንሳዊ ዜጋ አበበ የሚባል የገዛ አሽከሩ እቃውን ሰርቆት በዘበኛ ስለተያዘ የተሰረቀው ነገርና ሌባው ወደፍርድ ቤት ሄደለት ።

ይኸ ሁሉ የስርቆት ነገር ሲመረመርና ሲገለጽ ጊዜ እያጋጠመኝ በዘበኝነት ሥራ ማስኬጃ ቤት ነበርሁ ከሥርቆቱ ይልቅ የገረመኝ የፈረንጆቹ ነገር ነው በገዛ እጃቸው ሌባን በሎሌነት እያሳደሩ የቤታቸውን ጓዳና ጉድጓዳ አሳይተው ተሰረቅን ተዘረፍን ከማለት ይልቅ ዱሮውን ሎሌ ሲቀጥሩ አገሩንና እርስቱን የኖረበትን አመሉን እያጠኑ እየጠየቁ የታመነ የታመነውን ሰው በተያዥ አያገቡትም ኖሯልን በብልህነት ያለ ሞኝነት ቁመቱ ተራራን ያህላል እንደሚሉት እነሱ ባጠፉ በዘበኛ ላይ ይፈርዳሉ ማለትን ስለሰማሁ በሰው ዓይን ያለ የመሰለህን ጉድፍ ታወጣ ዘንድ ብታስብ አስቀድመህ በገዛ ዓይንህ ላይ ያለውን ጉድፍ አጥራ ብሎ ጌታ በወንጌል የተናገረውን ቃል ላሳስባችሁ ጽፌያለሁ ።

የብርሃንና ሰላም ወዳጅ ።

ስለ መቃብር ቦታ መልስ ።

ተወዳጅ ወዳጄ ብርሃንና ሰላም ሆይ ።

ይህቺን ትንሽዋን የመልስ ቃል ለተወደደውና በናፍቆት ለዘገየው ተማሪህ ልሰጠው አሳቤ ስለሆነ በጥበብ አምሮና ደምቆ በሚታይ ፈቃድህ እንድታመለክትልኝ እለምንሃለሁ ።

ብርሃን ሆይ ።

የሐሙሱን ጉባዔህን ለመመልከት ስል ድህነት የምትባለውን በቅሎዬን ጭኜ ወዳለህበት ቦታ መጥቼ ሳለሁኝ አንዱ አገልጋይህ የሆነ ደቀ መዝሙር የጻፈውን አገኘሁና ወደዚያውም

ማስተዋል በሚባለው ጐጆዬ ይገር ሄጄ ብዙ ጊዜ መላልሼ ባነበው ቃሉ ላገርና ለመንግሥት የሚጠቅም መስሎ ታየኝ መጀመሪያውም መንግሥት ስለሚጠቅም ሁለተኛውም የርሻ ሚኒስቴር የምድሩን ፍሬ ስለሚያገኝበት ሶስተኛውም ያገር ልጅ በዚህ ሥራ ላይ ለአትክልቱና ለሥራው ለየሚያስፈልገው ሁሉ ተቀጥሮ እየሠራ የለት ደሞዙን ለመስሩሩ ስለሚያገኝ አራተኛም ያቺ ምድር ለሚአዩዋትና ለሚጐበኙዋት ትልልቆች ሰዎች ጸድታ በመልካሞች አበባዎችና አትክልቶች አምራ በቂያስ ስለም ትደረግ ነው ስል ነገሬን አሳጥረዋለሁ ።

በዚህ ባለንበት ምድር ላይ ጌታውም እንደ ጌትነቱ ደሃውም እንደ ድህነቱ መጠን ለትንሽ ጊዜ መኖሼ ቤት መስራት ያስብና ሳሩን አጭዶ እንጨቱን ቆርጦ አረጉን መዘ ጭቃውን አረግጦ ምድሩንም ከባለበታው ላይ ገዝቶ ወይም ተከራይቶ ማስኖ ደክሞ ቤት ይሠራል በዚሁም ብዙ ጊዜ ደክሞ በሰራው ቤቱ ውስጥ ትንሽ ጊዜ ተቀምጦ ትቶ ወደ ዘለዓም መኖሼው ይሄዳል ። ማለት ለትንሽ ጊዜ መኖሪያችን ይኸንን ያህል ደክመን በብዙ ጥረትና ድካመት በየተሰራው ቤት ባለቤቱ የሞተለት በድኑን አንድ ቀን እንኳን የሚያሳድረው የለም ያኔውኑ ነፍሱ ከሥጋው እንደ ተለያየ ወደሚቀበርበት ቦታ ይወስዱታል እንጂ

የኤውሮፓ ሰዎች እንኳን ሰው በሞተባቸው ጊዜ ለዘመድ ወዳጃቸው እስቲያስታውቁ ድረስ ከሞተ በኋላ አንድ ቀን በቤቱ በድኑን ዘመዶቹ እስኪሰበስቡ ያውሉታል እኛ ግን የግማሽ ቀን እንኳ በዚያ በለፋበት ቤት ውስጥ በድኑን ለማቆየት የሚፈቅድ የለም ይመስለኛል ።

ለዚሁም የብርሃንና ሰላም ተማሪ አቶ ደምሴ ወልደ ገብርኤል ለጻፈው የመቃብር ቦታ ዋጋ እንኳን ለሚኖርበት ቦታና ይኸውና ወደ መንገድ ሲኬድ ባንዳንድ ቀን ማደሪያ በሆቴል ሁለትና ሶስት ብር ይከፈል የለምን? ። ይህ የብርሃንና ሰላም ተማሪ የተናገረው ነገር አይፈጸም ይሆናል እንጂ ቢፈጸም መልከም ነበር አይፈጸምም እንጂ ያልኩበትም ምክንያት ከሁን ቀደም ብዙዎቹ የብርሃንና ሰላም ወዳጆች ያመለከቱትና የጻፉት ነገር ሳይደረግ እያየሁት እንደዚያው እየመሰለኝ ነው ።

በቀለ ዘለቀ ።

ደስ እሚያሰኝ ወሬ ።

መልከም ወሬ አጥንት ያለመልማልና የሰማሁትን መልከም ወሬ ለብርሃንና ሰላም ተከፋዮቼ እጽፍላችኋለሁ ።

ከሥራ ሁሉ አስቀድሞ የሚአስፈልገን የከተማው ጥዳት ወደ ኋላ በመቆየቱ እጅግ ስናዝን ነበርን ። አሁን ግን ማዘጋጃ ቤት አስቦ ለዚሁ ሥራ አቶ ተገኝ ኃይሉንና አንድ የሮፓ ሰው ። በሥራው ሹሞ አቁሟል ደግሞ በየመንገዱና በሚአስፈልገው ቦታ ሁሉ የሺንት ቤት መሥሪ የሚሆን ለጊዜው የሥራ መጀመሪ ፭ሺ ብር ያህል ሰጥቶታል አሉ ስለ መልካም አሳቡ ማዘጋጃ ቤትን እናመሰግናለን ። የጀመረውንም ቸሩ አምላክ ለማስፈጸም እንዲአበቃው እንመኛለን ። ነገር ግን የመሸታ ቦታ ታልተለየለት ከተማውን ንጹሕ ማድረግ ያስቸግራል ። ቀድሞም በጥንተ ከተማዎች ሁሉ የቅሬ መንደር (እየተባለ የመሸታና የጋለሞታ) ሰፈር ለብቻው ነበር ። በራስ ቢት ወደድ ተሰማ እንደራሴነት ለብቻ እንዲሆን ተመክሮ ነበር ግን የሴቶቹ ወዳጆች ብዙ ስለሆኑ እንዳይርቋቸው አማልደዋቸው ቆዩ ይባላል ።

አሁንማ እፍረትም ቀረ ትልልቆች ሰዎች ሁሉ በየመንገዱዳር ሱቃቸው እየሠሩ ለነሱ ማከራየት ሆነ አሽከሮቻቸው ገንዘባቸውን ጥይታቸውን ከዝናራቸው እያወለቁ ይሸጡባቸዋል ወዲያውም ይሰክሩና እረፍት አሳጥተዋቸው ያመሽሉ ።

በወር ኪራይ ይህን ያህል ገባ እያሉ ሲአታልሏቸው ገቢአቸውን እንጂ ወጪአቸውን አያሳስቧቸውምና እውነት እየመሰላቸው ደስ ይላቸዋል የሽፍታ መሰብሰቢያ እሱ ነው ብለው አባ ጅፋር ባገራቸው መሸታ እንዳይሸጥ ከልክለዋል ደጃዝማች ይገዙም በወላሞ ከልክለዋል ሲባል ሰምተናል ። በየዋና ከተማ ግን ጥቂት ነጻነት እሚአስፈልግ ስለሆነ በጭራሽ እንኳን ባይከለከል በከተማ ዳር ዳር ቤት ተሰርቶ አጥር ታጥሮ ጸሐፊና ዳኛ ዘበኛ ተደርጎበት ያበየቀኑ ጠጅ አመለኛ የሆነው ሁሉ በወር ገቢው ይታወቅለት ነበር ጥቅማችሁን እንጂ ጉዳታችሁን አልጻፍሁምና ወጣቶችና ባለሱቆች እንዳትቀየሙብኝ አለምናችኋለሁ ። የብርሃንና ሰላም ወዳጅ ።

ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ።

ሥራ ስለ መውደድ ።

መርህ በፍኖት ሞገሰሙ ለጻድቃን ዝንቱ ውእቱ መድኃኔ ዓለም ። እቤቱ ጌታችን መንገዳችንን አቅናልን ።

በመንገድና በድልድይ መሠራት ብዙ ጥቅምና ሕይወት መገኘቱን ብዙው ሰው ይስተው አይመስለኝም ።

ይልቁንም በዚህ በሰኔ ወር ውስጥ የተሠራው የገፈርሳ ተራራ ድልድይ ። በጥቂት ቀን መፈጸሙ ። የንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ ረድኤትና የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ኃይልና ትጋት ለልጅ ልጅ የማይረሳ መሆኑን ያስረዳል ። ያዲሳበባ ሰው ቤቱን የሚሠራበት ጊዜው በዚህ ወራት ስለሆነ ። የገፈርሳ ወንዝ ድልድይ በመፍረሱ ምክንያት ። የማዕዘንና የጠርብ የሳንቃ ችግር በሕዝብ ላይ ጸንቶ ነበር ። ከንግዴህ ወዲህ ለንግሥተ ነገሥታትና ለልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ እድሜ እየለመነ መንገዱን ያቀናል

የጌታቸውን ትእዛዝ ተቀብለው ሠራተኞቹ በግራርና በጋም ስር ሳይቀመጡ ። በቅን ልቡና የጉልበታቸው ኃይል እስቲደክም ድረስ ድንጋይም ሆነ አፈር እየተሸከሙ ድልድዩን ለሞሉ ለኢትዮጵያ ልጆች ስለ ሠሩ የንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክና የልዑል ተፈሪ መኰንን አምላክ ዋጋቸውን ይከፍላቸዋል ።

መንገድ እንኳን ንጉሥ ሲያዘንና እንዲያውም በየደጃችን መንገድ መሥራትና ደጃችንን ማጽዳት ይገባናል ። ሰው መላ ዘመኑን በጤና ለመጨረስ አይሆንለትም መከራና በሽታ በድንገት ሳያስቡት ይደርሳል ።

ይህን ማለቴም በየደጃችን ያልተከከለ መንገድና ድጥ ስለሆነ ። በበቅሎና በፈረስ ሳለን የወደቅን እንደሆነ ብዙ ጕዳት ይመጣብናል ። ሰው በእግሩ እንኳ ሲሄድ ቢወድቅ ፈጣሪው ካላዳነው የሚሠበረው ብዙ ነው ። ከዚህ በፊት ባለፉት ዘመናት ። በድጥ ምክንያት ከበቅሎና ከፈረስ እየወደቁ የተሠበሩ ብዙዎች ናቸው ። ወድቆ ተሰብሮ የሰው በታች ከመሆን ። እግዚአብሔር በሰጠን ጉልበት ደንጊያ ተሸክመን መልካም መንገድ መሥራት ይሻል ነበር ። የገናናዪቱ የኢትዮጵያ መንግሥት ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ትጋትና ሥራ ለማስተማር ይጣጣራሉ ያተጋጋሉ ሥራ መውደድና መሥራት የሰው ክብር እንደሆነ ግልጥ ነገር ነው ።

ጠጋ ሥላሴ ጌታሁን ።

ላገር ጥቅም ለሕዝብ ትርፍ ።

ቀጥሎ ያለውን የተስፋ ቃሎች ላገር ጥቅምና ለሕዝብ ብየ የጀመርኩትን ታዩልኝ ዘንድ ተስፋ አደርጋለሁ ስለ ኢትዮጵያ ጥቅም የሚያስቡ የሉም ብየ አይደለም ግን ሁሉ ካዩነቱ ቢያስብና የሁሉ ቢስማማ መስማማት ኃይል መሆኑ ጥርጥር የለውም ስለዚህ የኢትዮጵያ መኳንንትና ሐብታሞች እየተሻረኩ ላገርም ጥቅም ለባለገንዘቦቹም ትርፍ እንዲሆንላቸው ለምን የአቶሞቢልና የባቡር መንገድ እንደ አቅማቸው ከግዛት ወደ ግዛትና ወደ ከተማ የሚወስድ እየተሰራ ትርፉ ለራሳቸው ሆኖ ጥቅሙ ላገር አልነበረም ወይ ።

በኢትዮጵያ ከመቶ ፺፰ የማይታረስና የማይሠራበት መሬት ሞልተዋል እንደሚቻላቸው እያሣረሱ የሚወጣውን ፍሬ ወደ ውጭ አገር እየተላከ በፋንታው ለኢትዮጵያ የሚያስፈልገውን ማናቸውም ዕቃና ገንዘብ ቢመጣ ደግሞ ትርፉ ለራሳቸው ጥቅሙ ላገር አልነበረም ወይ ።

ምነው የኢትዮጵያ መኳንንቶች ባይናቸው እያዩ በጆራቸው እየሰሙ በአቡጀዲና በሌላ ይህን በመሰለ ሸቀጥ ከኢትዮጵያ የሚወጣው የሕዝብ ገንዘብ ከመጠን የበዛ አይደለም ወይ።

በዚሁ ፋንታ ኢትዮጵያም የሚቻላትን ሸቀጥ እየሰጠች ገንዘብዋን ብትመልስ የማይቻል ነገር ነው ለማለት አይሆንም ስለዚህ የሌላን ከማመስገን የራስን መጣጣር ይሻላልና የኢትዮጵያ መኳንንቶች ለንደዚህ ያለ ሥራ ገንዘብ ያጡ ይሆን ?።

ጃፖን በትንሽ ጊዜ ነው ለዚሁ የበቃው ተማሪ ቤትና ንግድን ስለ አስፋና ስላበረታ ነው እንጂ በሌላ ረገድ እንዳይመስላችሁ ከዚህ ቀደም ስለ ተማሪ ቤት ማበርቻ ትንሽ ቃል አስታውሼ ነበር ይህ ሁለቱ ነገር ላገር ዋና ማስፊያና ማበርቻ መሆኑን ሁላችሁም ታውቁታላችሁ ።

ዳሩ ግን ደፍሮ የሚሰራ ጠፋ እንጂ ከተጀመረ መፈጸሙ ያቅት አይመስልም ላደራጂ ።

አርመን ያዕቆብ

እጅግ የሚያስደንቅና ጥቅም ያለበት ሥራ ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የሀገራቸው በሽተኛ ከሕመሙ እየታከመ እንዲድን በብዙ ከማራ ሆስፒታል አቁመው ሐኪምና ለህክምና የሚያስፈልግ መሣሪያ አስመጥተው ብዙ በሽተኛ ከሕመሙ እየዳነ ልዑልን እየመረቀና እያመሰገነ መሄዱን ሁላችን እናውቃለን ።

ግን ልዑል ጌታችን በሆስፒታሉ በአጥንት ውስጥ ብርቱ በሽታ ያላቸውን ሰዎች ሳይቀደዱ በቅልጥማቸውና በአንገላቸው ውስጥ ያለውን በሽታ የሚያሳይ መኪና እንደሚያስፈልግ ተረድተውት ምንም ዋጋው ቢበዛ ለገንዘባቸው ሳይሰሱ በብዙ ዋጋ ገዝተው አስመጥተው መኪናው ገብቶ በክቡር ዶክቶር ሐነር ብርታትና ትጋት ደኅና ሆኖ ቆሞ ተሰናድቶ ሥራው ተጀምሯል።መኪናው በሰውነትና በአጥንት ያለውን ነገር ለማሳየት የሚችል በብርቱ ብልሃት የተሰናዳ በሰውነትና በአጥንት ዘልቆ ግልጥ አድርጎ ለማሳየት የሚችል የኤሌትሪክ ብርሃን እየተቀበለ ነው። ጥሩ ውሀ በተሞላ በሣህን ውስጥ የገባ ጠጠርና የእህል ፍሬ ሁሉ ወለል ብሎ እንደሚታይ እንደዚሁ ሁሉ ይህ የራዲዮግራም መኪና ብርሃን ያበራበት ሰውነት በአጥንት ውስጥ በቅልጥም ያለው ትንንሽ ነገር ሳይቀር ግልጥ ብሎ ይታያል ።

የሚመረመረው ሰው ተኝቶ በብርሃኑ ሲታይ ከሰውነቱ በታች የሚመረመረውን አካል ፎቶግራፍ የሚያነሣ መኪና አለውና የታመመው አካል ፍቶግራፍ ተነሥቶ ሐኪሙ በዝግታ ይመረምሩታል ።

ሊመረመርና ነገሩን ለማየት የፈለገ ሰው ሁሉ ወደ ቤተ ሳይዳ ሆስፒታል ዘተፈሪ መኰንን እየመጣ ክቡር ዶክቶር ሐነርን እየጠየቀ በሚመች ሰዓት ሊመረምርና ሥራውን ሊያይ ይችላል ።

ከጥቂት ቀን በኋላም በዚሁ መኪና ብርሃን እስከ ውስጡ ታይቶ ፎቶግራፍ የተነሣ አጥንት በዚንኮግራፍ አስነሥተን በጋዜጣ አትመን ላንባቢዎች እንድናሳይ ተስፋ እናደርጋለን ።

ስለ መሐለቅና ቤሳ ሸረፋ ።

ከዚህ በፊት የከተማችን ሰው ሁሉ ስለ መሐለቅና ቤሳ ሸረፋ ችግር ተጨንቆ ያዝን ነበር ብዙ ሰዎችም በብርሃንና ሰላም ጋዜጣችን ስለዚህ ነገር እየጻፉ አመልክተዋል ፡ ግን አሁን ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ልዑል የኢ መ አ ወ ተፈሪ መኰንን የሕዝባቸውን ችግር ለማቅለል ስለ መሐለቅና ቤሳ ሸረፋ ከዚህ በታች የተጻፈውን ትእዛዝ ለገንዘብ ሚኒስትሩ ሰጥተዋል ። ስለዚህ የመሐለቅና የቤሳ ሸረፋ የተሻለ እንዲሆንና በትክክል ያለ ችግር እንዲገኝ ተስፋ እናደርጋለን ።

ስለ መሐለቅ ሸረፍ ለገንዘብ ሚኒስቴር የተሰጠ ትእዛዝ።

መጀመሪያ ።

የወር ቀለብ የሚቀበል ሰው ሁሉ ቀለቡ ከአምሳ እስከ መቶ ብር የሆነ የሁለት ብር ቤሳ የሁለት ብር መሐለቅ ይውሰድ።

ቀለቡ ከአስር እስከ አምሳ ብር የሆነ የሁለት ብር መሐለቅ ያንድ ብር ቤሳ ይውሰድ ።

ቀለቡ ከአምስት ብር እስከ አስር ብር የሆነ የአንድ ብር ቤሳ የአንድ ብር መሐለቅ ይውሰድ ።

ቀለቡ ከአንድ ብር እስከ አምስት ብር የሆነ የአላድ መሐለቅ የአላድ ቤሳ ይውሰድ ።

ነገር ግን ባለ ቀለቡ ብሩን በሙሉ እወስዳለሁ ወይም ብጥቂቱ እሸርፋለሁ ቢል እንደ ወደደ ያድርግ እንጂ መሐለቅና ቤሳ ለመውሰድ ግዴታ የለበትም ።

ሁለተኛ

በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በሰባት ቦታ ላይ ግርግዳውም ጣራውም ቆርቆሮ የሆነ አራት ሜትር እየሆነ በ፪ በሁለት ሜትር ተከፍሎ ባንደኛው ክፍል መሐለቅ ሸራፊው በሁለተ ክፍል ጸሐፊው እየተቀመጡ ይሸረፉ ።

ሶስተኛ ።

ሸረፋውም ባንድ ብር አስራ ስድስት መሐለቅ ባንድ ብር ፴፪ ቤሳ ነው ። ይኸውም በጉልህ ተጽፎ ሰው ሁሉ እንዲያነበው በመሸረፊያው ቤት በስተውጭ ይሰቀል ።

አራተኛ ።

በአንድ ወር ውስጥ ላንዳንድ ሰው መሐለቅና ቤሳ ለመሸረፍ የሚፈቀድለት ከዚህ ቀጥሎ እንዳለው ነው ።

ለቀኛዝማቾችና ለግራዝማቾች የሶስት ብር መሐለቅ የሁለት ብር ቤሳለባላምባራሶችና ለሻንበሎች የሁለት ብር መሐለቅና የሁለት ብር ቤሳ ለተራ ሰው ያንድ ብር መሐለቅና ያንድ ብር ቤሳ ነው

መሐለቅ ሸራፊዎችና ጸሐፊዎች ጧት በሁለት ሰዓት ገብተው እስከ ሶስት ሰዓት መሐለቅና ቤሳ ይቆጥራሉ ።

ከሶስት ሰዓት እስከ ስድስት ሰዓት ብሩን እየተቀበሉ መሐለቅና ቤሳ ይሸርፋሉ ከስድስት ሰዓት እስከ ስምንት ሰዓት እረፍት ያደርጋሉ ከ፰ እስከ ፱ሰዓት መሐለቅና ቤሳ ይቆጥራሉ ከ፱ ሰዓት እስከ ፲፩ ሰዓት መሐለቅና ቤሳ ይሸርፋሉ ።

ከሰኞ እስከ ቅዳሜ ፮ ሰዓት ድረስ የሰሩትን ቅዳሜ ከ፮ ሰዓት በላይ ወደ ገንዘብ ሚኒስቴር ቤት ሔደውና ተሳስበው ገንዘቡን አስረክበው የደረሰኝ ይቀበላሉ ።

አምስተኛ ።

መሐለቅና ቤሳ የሚሸርፉ ሰዎች ለአንድ ዓመት የሚበቃ ክርኔ በገንዘብ ማለዋወጫ ቤት ማህተም የታተመ ከመሸረፊያው ቤት በአንዳንድ ቤሳ እየገዙ ይቀበላሉ ያንንም በየወሩ እያመጡና እያሳዩ መሐለቁንና ቤሳውን እየሸረፉ ይውሰዱ ።

ስድስተኛ ።

መሐለቅና ቤሳ ለመሸረፊያ የሚሰራው ቤት ሰባት ስፍራ ላይ ነው

አንደኛው በአገር ግዛት ሚኒስቴር ቤት አጠገብ ።
ሁለተኛው በዕቃቤቶች ሰፈር ።
ሶስተኛው በአቧራ ገበያ ።
አራተኛ አራዳ የጨው ተራ በነበረው ስፍራ ።
አምስተኛ በራስ ተሰማ ቦታ ዳር ።
ስድስተኛ ጉለሌ በእንጨት ጉምሩክ ።
ሰባተኛ በስድስት ኪሎ ላይ ነው ።

በእነዚህም በሰባቱ ስፍራዎች አንድ ሸራፊና አንዳንድ ጸሐፊ ደግሞ መሐለቅና ቤሳ የሚቆጥሩ ሁለት ሰራተኞች ጨምሮ ማድረግ ነው ።

ሰባተኛ ።

ለታወቁት ለታላላቅ ለውጭ አገር ሰዎች በወር ሺ መሐለቅና ሺ ቤሳ በንግድ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት አጠገብ በተለየ አንድ ቤት ተሰርቶ በዚያ ይሸረፉ ። ለሌጋሲዮኖች በወር የሐያ አምስት ብር መሐለቅ የሐያ አምስት ብር ቤሳ ።

ለትልልቅ ነጋዴዎች የሐያ ብር መሐለቅ የሐያ ብር ቤሳ ።

ለተራ የውጭ አገር ነጋዴ ወይም ሰራተኛ ያ፭ ብር መሐለቅ የ፪ ብር ቤሳ ይሸረፍ ።

ስምንተኛ ።

በያንዳንድ ስፍራ በቀን ከሶስት መቶ እስከ ፰፻ ብር ይሸረፍ ከዚህ የተረፈው ግን በማግሥቱ እየመጣ ይሸረፍ ።

ዘጠነኛ ።

በሰባቱ ስፍራ ላሉት ሸራፊዎችና ጸሐፊዎች ለመሐለቅ ቆጣሪዎቹም አንድ ዋና አለቃ ይደረግላቸው ። በዚህም ላይ ደግሞ የአድልዎ ሥራ እንዳይሰራና ሕዝቡ እንዳይጉላላ የገንዘብ ሚኒስቴር አንድ ተቋጣሪ አድርጎ ያስመርምር ። ፲፱፻፳ ዓመተ ምሕረት ።

የከተማ ወሬ ።

ሐምሌ ፫ ቀን ሙላ መሐመድ አሊ ሸኽ ሸሪፍ ዓሊና ሙላ አብደላቤይ ሙሐመድ ዓሊ ኬራ የኢትዮጵያ መንግሥት በየመዓርጋቸው የክብር ኒሻን ስለ ሸለማቸው በአዲስ አበባ ያሉ ሕንዳውያን ዓረቦችና አርመኖች ነጋዴዎች ደስታቸውንና፡ፍቅራቸውን ለመግለጥ ስለ እነሱ ክብር እምፔርያል ሆቴል የሻይ ግብዣ አሰናድተው ጠሯቸው ፤ ሆቴሉም በኢትዮጵያና በእንግሊዝ ሰንደቅ አላማ አጊጦ ነበር በቤቱ ውስጥ በየክፍሉ ሁሉ ጠረጴዛና ወምበር ተደርድሮ በላይ በላዩ አበባ ተነስንሶበት ላይን እጅግ ደስ ያሰኝ ነበር ። ፲ሰዓት በሆነ ጊዜ ብዙ ሰው ተሰበሰበና ከብዛቱ የተነሣ ይጨናነቅ ጀመር ። ጥቂት ቆይቶ የተሸለሙት ሙላ ሙሐመድ አሊና ሙላ አብደላ ቤይ ሙዚቃ እየተነፋ እንደተሸለሙ መጡና ወደሆቴሉ በገቡ ጊዜ ብዙ ተጨበጨበ እነሱንም ለማየት የተሰበሰበው ሕዝብ ነፋስ እንደነካው ሸምበቆ ይዋዥቅ ጀመር ። የተሸለሙት ሰዎች ግራና ቀኝ ሆኑና በመካከላቸው የእንግሊዝ ቆንሲል ተቀመጡ ። ወዲያው በህንድ ቋንቋ የምርቃት ንግግር ተነገረና በእንግሊዝ ተተረጐመ፡እንደዚሁ ሁሉ በህንድ በእንግሊዝና በፈረንሳይ በዓረብኛ ቋንቋ ንግግሩ ሲዘንብ ዋለ ንግግሩም በተጨረሰ ቍጥር ጭብጨባው ይቀልጥ ነበር ። በዚህ መካከልም እየቆየ እየቆየ ሙዚቃ ይመታ ነበር ።

ሙሐመድ አሊ ኩባንያ ይህን ያህል መከበርና መንግሥት ሙያውን አይቶ የክብር ኒሻን መሸለሙ በንግድ ሥራው ስለጠነከረና የታመነ ስለሆነ ነው ስለዚህ ነጋዴዎቹ ሁሉ ሊመስሉት ይገባቸዋል ።

ብርሃንና ሰላም ለተሸለሙት ለክቡራን ሙላ ሙሐመድ ዓሊ ሸኽ ሸሪፍዓሊና ሙላ አብደልቤይ ሙሐመድ አሊ ኬራ እንኳን ደስ አላችሁ ይላል ወደ ሀገራቸውም ሂደው በደኅና ደርሰው እንዲመለሱ ያመኘላቸዋል ።

አቤርላንድ



ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሽ አቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባ ኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኜቶና ባለባተሪ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሯም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል «ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው

ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

ማስታወቂያ

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር	፱ ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
የዓለም ጂዖግራፊ በአማሪኛ ደኅና ጥራዝ ዋጋው	፯ ብር
» » » መናኛ ጥራዝ ዋጋው	፮ ብር
ደግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፮ ብር
ኀሐ ጽባሕ	፭ ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫ ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ተኩል
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትርሜጓው	፪ ብር
ፍ፡ ገር ትምርት	፩ ብር
ያማሪኛ ሰዋስው	፩ ብር
ወዳጄ ልቤ	፩ ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	አላድ
አጭር የዓለም ታሪክ	አላድ
ያማሪኛ ፊደል	ሩብ
አሳብና ምኞት	ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት	ሩብ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፪ መ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር	፪መ
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ	ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶ ግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ	ሩብ

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቊረጥም ፤ የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምበ ሳል ፤ የልብ ፤ የደረት ፤ የጉበት ፤ የኵላሊት ፤ የጅማት የጨብጥ፤ የቂጥኝና የቋቁቻ፤ የሚያዋልድ፤ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል

እደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ሱቅ ነው ።

ዓለም ሁቅ ፲፪ ዓይነት የተሰማ አሼቴ ሙዚቃሸከላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

COGNAC S.&E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሁቅ ይገኛል ።

በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳም ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይ ወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

RUGBY

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፣ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ባርባሬስ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬስ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥት ነገሥታት ዘውዲቱና ከልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ ።

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በከፐሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በከፐሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ጉድይር ግዙ





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው ። በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ፤ ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አራተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፴
4 me ANNÉE № 30

ሐሙስ ሐምሌ ፲፱ ቀን ፲፱፻፳ ዓ ም ።
JEUDI 26 JUILLET 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት
Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d'Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé "Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሰምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ደረከተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ አፈለን በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ አደራ ጢቆ ሥላሴ በአል አከባበር ።

ሐምሌ ፮ ቀን ዋዜማ በ፬ ሰዓት ተደውሎ ካህናቶቹ ተሰብስበው ዋዜማ ከቆሙ በኋላ ከዚያ ደብተራ ሐዋዝ ዘዲማ የሚከተለውን ቅኔ ተቀኘ

ዋዜማ

እግዚአብሔር ለእመ ይቤ ፡ ጽጉብ አነ እምዘአብርሃም መሥዋዕት
ሥጋ ላሕም በሞቱ ደምሰሶ ለሞት
ወይቤ አብርሃም በዓለ መንበር ሐይመት
ከነ ሞዓብ ሥጋ እልሕምት
ገበዒሁ ለኤፍሬም ሕይወት

ሁለተኛ ዋዜማ

እሳት ዘገሞራ ፡ ወማየ ቀላይ ዘአይኅ ለእመ በዘመነ ኃብሩ
እምኢክህሉ መዓተ ሥላሴ ለደቂቅ ይንግሩ
እስመ በዋእዩ እሳት ወማየ ቀላያት በቁሩ
በገጽ ገጸ እንዘ ይትናጸሩ
ትእዛዘሙ ለነገሥት ያሩ ።

ከዚያ ወዲያ ዋዜማው ከተፈጸመ በኋላ ሥርዓተ ቅዳሴ ፈጽመው በዘጠኝ ሰዓት እንበዝ እመምሕር ወልደ ሚካኤል ቤት ከሌላ ደብር ማኅሌት ለመርዳት የመጡ እንግዶች ነበሩና የመጣ እንግዳ ሁሉ በደኅና ተጋበዘ ፫ኛ ከሌሊቱ በአራት ሰዓት ተኩል ደወል በተደወለ ጊዜ ተሰበሰቡ ወዲያው ክቡራን ሊቃውንት ማኅሌት ስቡሕ ብለው ጀመሩ ከዚያ ወዲያ የሥላሴን መልክ አግብተው ለሀላዌክሙን መረገዱ ይልቁንም አለቃ መኰንን ያነቃቋቸው ነበር ሌሊቱን በመልከም እያሸበሸቡ ፫ጊዜ ዑደት ዞሩ ከዚያ ወዲያ ከሌሊቱ በ፲፪ ሰዓት የሥላሴን በዓል ለማክበር ክቡር ደጃዝማች እምሩና ክቡር ደጃዝማች ወልደ ሥላሴ ከነሠራዊታቸው ገብተው ሥርዓተ ቅዳሴ ከተፈጸመ በኋላ ደብተራ ሐዋዝ ዘዲማ የሚከተለውን ቅኔ ተቀኘ ።

ክብር ይእቲ

ተአርቀ እግአዚ እግዘሬ ጽልመተ ገጽ መልዕልተ ፀሐይ ደመና
እመ ተመጠወት ምድር ለኮከበ ሰማይ ስና
ወወርኃ ሰማያት ኤልዛቤል ለእመ ተሠሕለት ዓይና
በሰሌዳ ዕረፍት ትነዝኅ ደመ ርእሳ ወኢተረከበ መከና

ዕጣነ ሙገር

ሕይወተ አካል ወሞት ውስተ መግዝዓ ላሕም ልሳን
ላሀመ ከለዳዊ ዘሆሴዕ ዓፀደ ወይን
አምጣነ ፈረየ ተገዚሞ እንተ ይትረአይ ለዓይን
ወበቃለ ነገሥት ይከውን ፤ ለመርዓተ አብርሃም እም ልደተ ይስሐቅ ምናን
ይሰመይ ዘርአ ተሐድሶ እምይስሐቅ ሕፃን
መካነ ሥላሴ ኅድግተ ኢትሰመይ በልማደ ካልዕ መካን
አኮኑ ሀለዉ ውስቴታ ኃይለ ሥላሴ ብርሃን
ወማኅቶተ ብርሃን ተክለ አሚን
ወውሉደ ቤታ በኑልቆ እንዘ ኅዳጣን
ይበዝኁ እምእእላፍ ባዕዳን

ከዚያ ወዲያ ክቡር ደጃዝማች እምሩ ወደ ታላቁ ቤተ መንግሥት ሲመለሱ ሕዝቡ በየቤቱ ተበተነ ።ተቀኑ በ፯ ሰዓት በልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን አዳራሽ በየአድባራቱ ያሉ ካህናቶች ተጠርተው ሙሉ ግብር ሆነ ሁሉም ግብራቸውን ተጋብዘው እያመሰገኑ ተመለሱ ።

የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ሠራተኛ ተስፋ ገብረ ሥላሴ

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን
ስለ ተወለዱበት ቀን መታሰቢያ በዓል ።

በሐምሌ ፲፮ ቀን ፲፰፻፹፬ ዓመተ ም ታላቁ ኮከብ የኢትዮጵያ ብርሃን ልዑል ተፈሪ መኰንን ተወለዱ።ዘንድሮም ሐምሌ ፲፮ ቀን፴፯ኛው ተጨርሶ ፴፰ኛው ተጀመረ።ይኸነኑም መላ ኢትዮጵያ በደስታ ልታስበው የሚገባ ነገር ነው ። ከሕፃንነታቸው ጀምረው ለሚወዷት ሀገራቸው ብዙ ውለታና ጠቀሜታ የሠሩላት ወደፊትም አብልጠው የሚሠሩላት ቡሩክ ልጅ ስላገኘች ደስታዋ የበዛ ሊሆን ይገባታል።ወደ ትልቁም ደረጃ እንድትደርስና በክብር እንድትኖር አብዝተው ይጣጣራሉ ። ይህንም የሚያሠራና የሚያስፈጽም፡ኑኃ መዋዕል ነውና ሁሉን የሚችል እግዚአብሔር በእድሜ ላይ እድሜ ሰጥቷቸው ያሰቡትና የጀመሩትንሥራ ሁሉእንዲከናወን፡ኢትዮጵያ ሙሉ ተስፋ ታደርጋለች ።፴፰ኛውን ዓመታቸውን ያሳየን አምላክ ልዑል ተፈሪ መኰንንን እስከ ፍጻሜ ይጠብቅልን።

፴፤በእንተ ምግብና እምቀኖና ነገሥት ወምክር።በእንቲአሃ መክ ፶፮ ዘ፷ወ፩ ፷ወ፫ ፻ወ፫ ፻ወ፰ ፺ወ፫ በከመ ይቤ እግዚአብሔር ልዑል በአሪት ውስተ መጽሐፍ ኃምስ ። ሚመ ለክሙ ፈታሕተ በኵሉ አህጉሪክሙ እንተ ይሁበክሙ እግዚአብሔር አምላክክሙ። ፷ወ፰ ወኃርዮቱ ኪያሁ ይኩን ዘከመዝ ዘቦቱ በቀኖናት መወድስ ።

ለበቀኖናተ መንግሥት ኅሩይ ለዘተኃረይነ ።
በኢኑፋቄ ይደሉ ንኅረይ በቀኖናተ ።
በመጻልወ ፍትሕ ንጽሉ ወርቀ ምኒልክ መንግሥተ ።
(ለተማይጦ ወለዘሠይጥ) ፡ እንዘ እምሕሊና ናሴስል ሐሰተ።
ዘ ዘይፍቁ መጻልወ ፍትሕ ርእዮሙ ይመንኑ ምናናተ።
ማኅውሂ ዘእማኅው ኃይለ ሥላሴ ተከሥተ ።
እምነፋሳተ ሮም ከመ ይዕቀብ አስከለ ማርያም ማኅቶተ።
ወፈታሕተ ነገር ያጽንዑ እንተ ዳንኤል ሥርዓተ ።
አጋዕዝተ ወሥልጣናት ኅረዩ ሊቃውንተ ።

አለቃ መርሻ ዘውእቱ መርስዔ ኀዘን ።

ያንድ የጋላ ፈላስፋ ነግግር።

አንድ ቀን በስድስት ሰዓት ከሥራ ምላሽ ምሳዬን በልቼ ቡን እስኪፈላልኝ ድረስ ተቀምጬ ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ስመለከት አንድ ቅልቅ ሰው አባ ረኪና የሚባል የቄለም ባላባት ነኝ ብሎ ድንገት እቤቴ ቢመጣ ስመለከት የነበረውን ጋዜታ አስቀምጬ ባክብሮት ተቀብዬ ሰላምታዬን ከጠየቅሁት በኋላ አጠገቤ የተቀመጠውን ጋዜጣ አይቶ ለቤቴ እንዲሆነኝ ይህን አጠገብህ ያለ ወረቀት ምንድነው እባክህ ስጠኝ አለኝ ። እኔም ይህ ብዙ ጥቅም ያለበት ነውና ብሰጥህ ያጐዳኛል ግን የምትፈቅድ ብትሆን ብዙ መልክም ነገሮች ከዚህ ላንብልህ አልኩት እርሱም እሺ ፈቃዴ ነው አለኝ ስለ ዚህ በኅንቦት ፪ ቀን በ፴ ኛው ዓመት በቁጥር ፲፱ የወጣውን ብርሃንና ሰላም ከዳር ጀምሬ ሳነብለት የርሻና የመሥሪያ ሚኒስቴር የክብት ሃኪም ሙሴ ሚህሬን ክይማኪያን ለጤንነት የማይስማማ ወተት ሕዝቡን እምብዛ እንደሚጐዳ ብሎ የጻፈውን መቅድሙን ገና ስጨርስ ምግባችንን የሚነቅፍ ነገር ከመጣ ተወው ይበቃሃል አለኝ እኔም በሽታ እንዳያመጣብን ያስጠነቅቀናል እንጂ አላጠየፈብንም ብለው ቢሆንም የመርዝ ክፋቱ ባይታወቅ ምግብ ይሆን ነበርና ማናቸውንም ስለ ወተት ክፋት የሚወራውን ባትነግረኝ እወዳለሁ ስላለኝ ነገሩን ተወት አድርጌ እህሳ ይህ ወረቀት ጥቅም የሚገኝበት አይደለምን ላንተስ ብሰጥህ የሚያጐድለኝ አይደለምን ብለው እሱም የሚያጐድል ክልጠፋ ወይም የሚጠቅም እስኪጠፋ አይታወቅም አለኝ እኔም የነገሩ አጀማመር ገረመኝና ለማስጨረስ እንደምን አልኩት ለሥራህ አትቸኩል እንደ ሆነ በሚሰማ ምሳሌ አድርጌ እነግርሃለሁ አለኝ አልቸኩልም አልኩት እሱም እንዲህ ብሎ ጀመረ ደጃዝማች ብሩ በዚህ አገር አሥራአንድ ዓመት ሙሉ ሳሉ ቢሄዱም የሚያጐሉን አልመሰለንም ነበር አሁን ግን ብዙ እንዳጐደሉን አወቅን ማለት ይህን ያህል ዓመት አብረን ስለ ተቀመጥን ከሹከሮቻቸው ጋራ በጋብቻ ባበልጅነትና በሌላም ብዙ ዓይነት ዝምድና ተሳስረን ነበር ። ስለ ዚህ በማናቸውም ችግራችን ያዝኑልን ነበርና አሁን ስለ ሄዱ በጋብቻና ባበልጅነት የተዘመዱት ከልጆቻቸው በመለየታቸው የሚያዝኑ ብዙዎች ናቸው።ደግሞም ደጃዝማች በመሄዳቸው ከሆሮና ከጅማ ብዙ ሰዎች ወደ ሌላ ሀገር ተሰደዱ አለኝ እኔም ከዘመዶቻችሁ በመለየታችሁ እዘኑ እንጂ ወደ ሌላ ሀገር መሰደዳቸውስ ሞኝነት ነው ማለት ደጃዝማች መኰንን በግዛታቸው ሁሉ አገር ያለማሉ እንጂ አያጠፉም በፊተኛውም ግዛታቸው በዳሬሙና በዱረኒም ቢሆን የሠሩት የደግነት ሥራ ሀገሩ መልማቱ ይመሰክርላቸዋል ይልቁንም አሁን ከሰዮ ጉምሩክ ገቢ እኩል እንዲከፈሉ ስለ ተፈቀደላቸው ግብራችሁን ሳያቀሉላችሁ አይቀሩም ስለዚሀ ከዱሮው አኑዋኑራችሁ ይልቅ የዛሬው ያማረ ሳይሆንላችሁ አይቀርም ይመስለናል ስለምን ክፋታቸው ሳይታወቅ ከሀገሩ ይሸሻል?አልኩት እሱም (ከታየ ያልታየ ይፈራል አለኝ ።

እንዴት ብለው እነዚህ ባላገሮች የተሰደዱበት ምክንያት ደጃዝማች መኰንን ክፉ ናቸው ብሎ አይደለም ማናቸውም አዲስ ሹም ሲገባ የእጅ መንሻ እራት እምጡ ቤት ሥሩ አጥር አጠሩ ወፍጮ ሸክላ አምጡ መባል አይቀርምና ወደዳር ቆይተን እርሳቸው ሲገቡ ግብር ፈርተህ የሸሸህ ምሬአለሁ አትነካም ግባ ብለው አዋጅ ሲያደርጉ እንመጣለን ብሎ ነው አለኝ።እኔም ደጃዝማች መኰንን ለሃገር የተመቹ ለድሀ የሚያዝኑ መሆናቸውንና ደግነታቸውን አጸናንቼ ከነገርኩት በኋላ እንግዲያስ እግዚአብሔር መልካም ገዢ አመጣልን ብሎ መቸም ይህን ሁሉ ለመጫወት ያደረሰን የዚህ የወረቀት ነገር ነውና እንግዴህ እንድሄድ ፍቀድልኝ አለኝ ። እኔም ጨዋታው ደስ ስላለኝ ተምረሃል ወይ ብለው እንደአባቶቹ ኑሮ ነው እንጂ አላውቅም አለኝ የፊት አናኑዋራችሁ እንዴት ኖሮዋል ብለው እና ኑዋርን ጊዜ ይወልደዋል ይህን እንዳልነግርህ ቸኩያለሁ ብሎ ተነሳ እኔም እንግዲያስ ቀጠሮ አድርገን እንድንጫወት የሚመችህን ቀን አስታውቀኝ ብለው ቀጠሮን የሚያደርግ ቀን ነው ደህና ዋል ብሎኝ ሄደ ።

እኔም አነጋገሩ ስለገረመኝ የብርሃንና ሰላም ወዳጆች የሆኑ ሁሉ እንዲከፈሉ ብዬ እርሳሴን አንሥቼ ለመጻፍ ጀመርኩ የገረመኝም እነዚህ ሶስት ቃላት ናቸው የሚያጐል ክልጠፋ ወይም የሚጠቅም እስኪጠፋ አይታወቅም ። አኑዋኖርን ጊዜ ይወልደዋል ቀጠሮን የሚያደርግ ቀን ነው እነዚህን ምሳሌዎች እሱ ለጊዜው ለጨዋታው ምሳሌ ያድርጋቸው እንጂ ለተመለከተው ሰው ምሥጢር አይጠፋበትም

ጥያቄ ክቡራን የብርሃንና ሰላም ወዳጆች ሆይ ይህ ያልተማረ ጋላ እንዲህ ሲናገር ቢማር እንዴት ይሆን ኖሯል ?

ኃይለ ጊዮርጊስ ወልዳማኔል

ከአንድ ሊቅ የተገኘ የኑሮ ፍልስፍና ።

ድኅነት የሚባል ታላቅ ንብረት ነበረኝ ። በድኅነቴም ምክንያት ለከበርቴ ልጆች ማላገጫና መተረቻ ሆኜ ነበር ። ብዙ ዓመታትም መራራ ኑሮ ከኖርሁ በኋላ አንድ መንገድ አገኘ

ሁ ። ምን ጊዜም ድኅነት የተሻለውን ኑሮ ለመፈለጊያ የሚረዳ መረማመጃና መሰላል ነውና የተገኘውን ሥራ ለመሥራት አጽናናኝ ። ስለዚህ ሠርቶ ገንዘብ ማፍራትን የሚበቃ ምግብን ማግኘትን የሚያከብር ልብስ መልበስን ከስተማረኝ በኋላ መራራ ኑሮዬ ተለወጠ ።

ከዕለታት አንድ ቀን ምድር ልክ ለሌለው ምግብ ማዕድ ሆና አየኋት ይህችም ማዕድ ብዙ ሰውነት የሚያዳብርና የሚያፋፋ ምግብና ቅመም ጣፋጭም ሁሉ ተቀልሎባታል ። በዙሯዋም ብዙ ሰዎች ታላቆችም ታናሾችም ከበዋት ነበር ። ሁሉም ከምግቡ ለመጋበዝ አሰፍስፈው ነበር ። ነገር ግን አንዳንዶቹ ሰዎች ደከም ያሉትን እየገፉ መልከሙን ነገርና የቀረበላቸውን ምግብ እንኳ ሳይቀር እንደ አሳማ ተሻሙት ሞኝነታቸው ነው እንጂ ሁሉም እያንዳንዳቸው የሚበቃቸውን ያህል በልክ ቢወስዱለት ኖሮ ምግቡስ በማዕዱ ዙሪያ ላሉት ሁሉ የሚበቃ ነበር ። ነገር ግን አየል ያሉት ሰዎች ከሚመገቡት ይልቅ አብልጠው ከምግቡ ስለ ወሰዱለት ተርፏቸው ከምረውታል ።

ደከሞችም እንደራባቸው ሄዱ ። እኔ ግን ይኸን ስመለከት ነገሩ አሳዝኖኝ ለኑሮዬ ከሚያሻኝ ይልቅ ሌላ ትርፍ ቢኖረኝ ከመከመር ይልቅ ለተራቡት ለመስጠት ቁርጥ አሳብ አደረግሁ ። ከምድርም ማዕድ ከሚያሻቸው አብልጠው ከምግቡ የሚወስዱ ሰዎች አሳሞች መሆናቸውን ዘወትር አይረዱትም እንጂ እኔስ አሳሞች ናቸው እላለሁ ። የአሳምነትንም ባሕሬ ጻድቅ ሊፈውሰው አይችልም ። ለዚህም ለተሰበሰበው ምግብ ራሳቸውን ታማኝና አላፊ ለሚያደርጉ ሰዎች መንገድ አለባቸው ። ወይም ሌሎቹም ከማዕዱ ቀርበው እንዲጋበዙ ፈቃዳቸው ይሆንና ወደ ማዕዱ እንዲደርሱ ይረዷቸው ይሆናል ። የእንደ ዚህ ያለውም ቀን መምጫው የተፋጠነ ይመስላል ። ስሙም ቸርነት ሊባል አይገባውም ። በጉልህ ፊደል ተጽፎ ፍትሕ ይባላል እንጂ ። የፍጡርም ፍቅር ይጨመርበታል ። ዓለምም የተፈጠረችው ለፍጥረት ሁሉ ደስታና ሰላም ነው ስስታሞች ከመሆን እንድንጠነቀቅ ይህን አመለክታለሁ ።

ከብርሃንና ሰላም ተላላኪ ።

ተጠንቀቆ ስለ መኖር ።

የከበራችሁና የተወደዳችሁ የብርሃንና ሰላም ማኅበረተኞች ተጠንቀቃችሁ ኑሩ የሚል ቃል መለኮታዊ ትእዛዝና ምክር ሁኖ በመንፈሳዊና በሥጋዊ የሚያስጠነቅቀን ቃለ እግዚአብሔር ነው።በዚች ዓለም ሳለንም በነፍስና በሥጋ ካልተጠነቀቅን ሰይጣን ጠላታችን የሚውጠውን ሰው ሽቶ በኃይልና በፉክራ በርትቶ ሊያጠፋን ይታገላል። ለዚሁም ጠላት በእምነት ጋሻ መክተን በጸሎትም ነቅተን ድል ልናደርገው ያሻናል ። ሁለተኛም ሰይጣን የሚነዳቸው በምክሩም የሚረካቸው ስስት ያሳደረባቸው በቃን የማይሉ ወዳጆች አሉብንና ከወዳጅ ጠላት እንድንድን ከመኻታችን ልንነሣ ያስፈልገናል።አለበለዚያ ግን ወለሊሁሰ ሰይጣን ይትሜሰል መልአከ ብርሃን ያለውን ቃል እንዘንጋው እኒህ ወዳጆቻችን የተባሉትም በአፉሆሙ ይድኅሩ ወበልቦሙ ይረግሙ ብ. ቅዱስ ዳዊት የተናገረው ቃል በኝህ ሳይሆን አይቀርም ከዚህ ጉዳትና መርገም እንድንድንም ሁለት ትልልቅ ዋና ነገሮች ይዘው የተሾሙትን ከዚህ ጥቃት ባስጣሉን ብዬ አረጋግጣለሁን።

፩ኛ ያገር ግዛት ምኒስቴር፣ ሁለተኛ የትምህርት ምኒስቴር ።

፩ኛ ክቡር ያገር ግዛት ምኒስትር ሆይ ሹመት ከእግዚአብሔር እንጂ ከሰው ብቻ አይሆንምና እግዚአብሔርና መንግሥት የሰጠዎን ሥልጣን ታላቅ ማዕርግዎን ይዘው ኢትዮጵያን አገራችንን በመላዋ አደራ የተቀበሏትን በሥርዓትና በጥንቃቄ ፈጥነው እንዲያከናውኑዋትና እንዲያደረጅዋት ልጆቹዋ በተስፋ እንጠባበቃለን ። ከነገሩ ፊተኛ ፩ ሰው ቤቱ ወይም ቀላድ የምንለው የገዛውን መሬቱንና ካባቱ የወረሰውን ርስቱን በካርታ ቢያስነሳው ደስ ይለዋል ይገፋኛል ይወስዱብኛል ከሚላቸው ያዋሰኝ ድምበርተኞቹም ሥጋት ተወገደለት ልቡ ያርፋል። ከዚህ በኋላም መልካካም ያማሩ ቤቶች ሰርቶ አጥርም አጥሮ በየዓይነቱ የሚያፈሩትን አዝእርትና አትክልት ተክሎ ደስ ብሎት ይመገብበታል እንዲሁም ይህች ለምለሚቱ አገራችን አጥርና ቅጥር አድርገው ካሰሩዋት የምንፈልገውን ፍሬ እንደምትሰጠን የታወቀ ነው ።

፪ኛ ክቡር የትምህርት ምኒስቴር ሆይ ። የኢትዮጵያን ወጣቶች ድሮ አንድ አንዱን በግንድ እያሰሩ ያስተምሯቸው ነበሩ አሁን ግን ትምህርት ፈልገው ከባት ከናት ተሸሽገው ወደ አራት የዓለም ማዕዘን ይበታተኑ ጀመር ። ስለዚህ ካንድ አንድ ያገር ገዢዎችና ምስለኔዎች መንግሥታችን ቢፈቅድልንስ ተማሪ ቤት በከፈትን ብለው የሚያወሩ ሰዎች አሉና በውነት ያደርጉት ወይስ አያደርጉት እንደሆነ ሊታወቅ እንኳንና እነሱ ይህን አውርተው ትምህርት በነፍስና በሥጋ ጠቀሜታ ያለበት ነውና በየአውራጃው ላሉት ገዢዎች በየበኩላችሁና በየግዛታችሁ ውስጥ ተማሪ ቤት ክፈቱ የሚል አዋጅ ተደርጎላቸው ፈቃድ ያለው ለፈቃዱ የማፋጠኛ ረድኤት ቢላክለት መልካም ይመስለኛል ።

መንግሥታችንም ዋናው ሐሳቡ ትምሕርት ባገራችን እንዲሰፋ ነውና ስለ ዚህ ባለ ሰፊ ግዛት የሆኑት ራሶችና ደጃዝማቾች ባዋጅና በማኅተም ትእዛዙን ቢልክላቸው ትእዛዙን በደስታ እንዲቀበሉ ጥርጥር የለበትም ። ምናልባት ከገዦቹ ፈቃድ የሌለው ቢኖር ተማሪ ቤቱ ያጎዳል የሚል ሰው ይኖር ይሆናል የኔው መልስ ባጭሩ ይህ ነው ተማሪ ቤት ሊከፍት ፈቃድ የሌለው አገረ ገዢ በማንላቸውም ነገር ይረዳል ብሎ መንግሥታችን የሚታመንበት አይመስለኝም ። ስለ ዚህ ያገር ግዛት ምኒስቴር ታዝበው ከመንግሥታችን ጋራ መክረው እርሱ ቀርቶ ሌላ ቢሾሙበት ይሻላል። ከመዝ ርእዮሙ ክልአን ይፍርሁ ።

ደግሞስ ቀዳሚ ነገር አገረ ገዢው ሕፃናቱ በሕፃንነታቸው ሣሉ ምን ይሆኑ?ገዢውስ በሚገዛው አገር አይነተኛ ሥራው ምን ይሆን?ሕዝቡን ሊጦር ነው ወይንስ እራሱ ሊጦር የተሾመ?በአውሮጳ ልጁን የማያስተምር አባት በሕግ ይቀጣል ። በኛስ ልጆች እንማር ሲሉ ገዢው ካላሰበላቸውና አስተማሪ

ካልሰጣቸው ቅጣቱ በማን ላይ ይሁን? አደራ በሰማይ አደራ በምድር ይህንእንብላ እንጠጣ ነገ እንሞታለን የሚለውን ሐሳብ አውጥተን እናስወግደው ለየስማችንም አንድ አንድ የማይጠፋና የማይረሳ ሐውልት እናቁምለት አለበለዚያ ግን ወፍኖ ቶሙሰ ለኃጥአን ትጠፍእ ይባልልናል ።

ረዳ ጻድቅ

የክቡር ቄስ የአናኑዎር ምክርና ስብከት።

፩ኛ ፤ ጊዜን አስጠብቁ ግን ሕይወታችሁን ለማደስ በርቱ ።

፪ኛ ፡ እድሜው ከተገኘ ወደ ትልቅ ማዕርግ ለመድረስ አይዘገይም ።

፫ኛ፤ አንድም ደቂቃ ብትሆን ሕይወትህንበከንቱ አታበላሽ

፬ኛ ፡ ሕይወትህንም ለማደስ ተቸገር መልካም(ደግም)ሁን እንደጊዜው ።

፭ኛ ፡ ደስ ይበልህ ደስ የምታሰኝ ሕይወትም ለማግኘት ልምድ አድርግ።

፮ኛ ፡ እውነተኛ ሁን እውነተኛ ሰው ገንዘብን ያገኛልና ። በሮች ሁሉ በፊታችሁ ይከፈታሉ ።

፯ኛ፤ በዚህ ዓለም አስቸጋሪን ሁሉ የሚአሸንፍ ይኸ እውነተኛ ሰው ነው ።

፰ኛ ፤ እርስ በራሳችሁ ተከባበሩ ወዳጆቻችሁንም እመኑት ። የቀሩትንም ማመን የሚገባ ነው ።

፱ኛ ፡ ሥሩ ወይም ሙቱ ይኸ የሕይወት እጣው ነውና ሥራን የተዋችሁ እንደሆን በሐሳብ ትሞታላችሁ ።

፲ኛ ፤ አመል ይኑራችሁ ከመልካም ጠባይ ጋራ ።

፲፩ኛ፤የምትጀምሩትንም ሥራ በፍጥነት ጨርሱት አዘጋጁት

፲፪ኛ ፤ አደጋም ባገኛችሁ ጊዜ አትበሳጩ ።

፲፫ኛ ፤ ቀልጣፋ ሁኑ ጥቂት ነገር የጀመራችሁ እንደሆነ በፍጥነት ጨርሱት ።

ካፒቴንባቢኪያን ።

ሠርግ ።

ሐምሌ ፲፯ ቀን ክቡር ፊታውራሪ ገብረ እግዚአብሔር የክቡር ደጃዝማች ሙሉ ጌታ የጦር ሚኒስቴርንልጅ አግብተው ሠርጉ እጅግ ደምቆ ዋለ ።

ክቡር ፊታውራሪ ገብረ እግዚአብሔርና ክብርት ወይዘሮ ሺ ወርቅ ትዳራቸውን እግዚአብሔር እንዲባርከው ብርሃንና ሰላም ይመኝላቸዋል ።

የሚዜዎች ጨዋታ ።

የየጁን ባላባት የስሜን ባላባት የጐንደር ባላባት የነማሮዋን ጌታ ። መልካም ጋብቻ ነው ይኸ ሙሉ ጌታ ። እቴ ወሰን የለሺ እሱ ሙሉ ጌታ ። የሸ ወርቅ ሰጠኝ እንዳልንገላታ ። የጦር ሚኒስቴር ልጅ ስራት የለመደች ገና ሳንሰለፍ ድል አድርጋን ሄደች ። ለመጣው እንግዳ እንዳይቸገሩ እኔ እጐዳ እንደሆን የሺ ወርቅ ሙሉ። እልፍና መሊዎን ነበረ ዋጋሺ ለምን አሳንሰው የሺ ወርቅ አሉሺ ። ብለው የምስራቹን ለመንገር የሄዱ ሚዜዎች ከነገት እየወረዱ በዜማ ተናገሩ ክቡር ደጃዝማች ሙሉጌታ የጦር ምኒስቴርና አክስቶቿም ይኸን ግጥም በሰሙ ጊዜ የደስታ ጭብጨባ አጨበጨቡና አክስቶቿ ከዚህ የሚከተለውን ቃል በወረቀት ጽፈው አቀረቡ ሥላሴ ሲፈጥሩን አ ንግበር ብለው።ምሥጢሩን ላወቀው ገብረ እግዚአብሔር ነው ፡ የመነን አስፋው ልጅ እንግዳችን ነው ። እሱም ሌላ አላለ ሽ ወርቅ ሰጠነው ፤በብዙኅ ተጨንቀን አስበን በሩቅ ፡ ገብርዬን ገዛነው ትላንት በሺ ወርቅ ፡ ብለው አሉ ።

ክብረት ባንት ይርጉ ።

የቀድሞ የመስኮብ ንግሥት ምሥጢር ያለው የሕይወት ታሪክ
ዝኒት የምትባለዋ በለሙዋሊ የጻፈችላት
በካፒቴን ባቢኪያን ታርሞ ተጻፈ።

መጀመሪያ ክፍል ።

በጦር ወራት በኩለ ሌሊት ጊዜው በራድ ሰማዩም በኮከብ የበራና እጅግ የጠዳ ነበረ ። እኛም ከብርድ ለመጠበቅ የሚሞቅ ወፍራም ልብስ ደርበን ነበር በሩጫ ሄደን ቢክቶር አማኑኤል ከሚባለው ስፍራ ደረስን ። ይህም ስፍራ በብርሃን ያጌጠ ነበረ ። እንዲህም መሆኑ የኤጲፋንያ በዓል ስለ ሆነ በሮማ ከተማ ያለ ሕዝብ ሁሉ በውስጡ ነፋስ ስለ መቀበል ሽርሽር ያደርጉ ነበረና ከዚህም በኋላ ብዙ እየሆኑ ወደ አንድ ልዩ ስፍራ የፈንጠዝያ በዓል ወዳለበት ሄዱ ።

የውጭ አገር ሰዎችም የፈንጠዝያ ልብሳቸውን እየለበሱ የከተማውን ሕዝብ ልዩ ልዩ ዓይነት ልብስ ለብሶ ሳፒና ወደ ሚባለው ተራራ ይጓዝ ጀመረ

ወታደሮቹ ግን ጅጉርጉር ኮት ለብሰው በኩራት አካሄድ እየተራመዱ ሕዝቡን ተከተሏቸው የቡና ቤቶችና የሕዝብ መሰብሰቢያ ስፍራዎች ሁሉ እጅግ ሰው ሞልቶባቸው ነበረ ።በያለበት የሙዚቃውና የጥሩምባው ድምጽ ጆሮአችንን አደከመው የሕዝቡም ብዛት መንገድ ስለ ከለከለን ሕዝቡ ወደ ሄደበት ያለፈቃዳችን እየተጋፋን እንጓዝ ጀመርን

በዚያ ጊዜምአልጋ ወራሽቱ አሊክስ ተመረረችና ይህ ስፍራ እንደዚህ ያለ አስቸጋሪ መሆኑን ባውቅ ከቦታዬ አልነቃነቅም ነበር ብላ በብስጭት ቃልተናገረች

ይህንም ካለች በኋላ ሰዉን እየገፋች በመሃከል ትሄድ ጀመረች ወዲያው ንግግሯን ሳታቋርጥ አንድ ባለጌ ልጅ ከጆሮዋ አስጠግቶ ጡሩምባ ነፋበት እኛም የምንነጋገረው በእንግሊዝ ቋንቋ ስለ ሆነ ደግሞ አንዱ እያፌዘ ጐሸማት በዚያን ጊዜ አሊክስ ተቆጥታ ቆመች የሕዝቡም ግፊያ ጣላትና ከመሬት ተንከባለለች ግን ሁለት ሰዎች ስለ ራሩላት ደግፈው አንስተው በብዙ ችግር ከሕዝቡ ማህል አወጡዋት እኔም ለሁለቱ ሰዎች ቀረብ አልሁና ምስጋና ሰጠኋቸው እህቴም ናት ብዬ አጫወትኋቸው ወዲያውም ወንድሞቼ ሆይ እባካችሁ ወደ ደህና ቦታ ወስደን እናሳርፋት ብዬ በትሕትና ለመንኋቸው እነሱም ፈቃዳቸው ሆኖ ይዘናት ወደ አንድ ትልቅ አዳራሽ ስንመጣ በነዚህ ደጎች ሰዎች ክንድ ላይ እንደሞተ ሰው ሆና ነበረ የዚያም አዳራሽ ጠባቂ አንድ መልካም ሽማግሌ ስለ ሆነ ኑ ግቡ ይህ ቤት ብራስኪ የሚባለው የንጉሡ ልጅ ቤት ነው ብሎ ጋበዘን

ካፒቴን ባቢኪያን

በሚመጣው ሳምንት ይቀጥላል

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ ኦቤርላንድ ኦቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጦጦን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።



አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባ ኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባተሪ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል «ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው

ወዲያውም የኦቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

ማስታወቂያ

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲	ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር	፱	ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
የዓለም ጅዮግራፊ በአማርኛ ደኅና ጥራዝ ዋጋው	፯	ብር
» » » መናኛ ጥራዝ ዋጋው	፭	ብር
ደግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፫	ብር
ኀሐ ጽባሕ	፫	ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪	ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፪	ብር
የሕይወት ታሪክ	፩	ብር ተኩል
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፩	ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፩	ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትርሜጓው	፩	ብር
የቁጥር ትምርት	፩	ብር
ያማርኛ ሰዋስው	፭	ብ
ወዳጄ ልቤ	፭	ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፭	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን		አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ		አላድ
አጭር የዓለም ታሪክ		አላድ
ያማሪኛ ፊደል		ሩብ
አሳብና ምኞት		ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት		ሩብ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፩	መ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር	፩	መ
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ		ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶ ግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ		ሩብ

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም ፣ የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ፣ የልብ ፣ የደረት ፣ የጉበት ፣ የኩላሊት ፣ የጅማት የጨብጥ፣ የቂጥኝና የቋቁቻ፣ የሚያዋልድ፣ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል

እደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ሱቅ ነው ።



ዓለም ሱቅ ፲፯ዓይነት የተሰማ አሼቴ ሙዚቃሸከላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንፎር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

COGNAC S.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም እንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩግቢ

RUGBY

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሰያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይ ወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፥ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ ።

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በካፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በካፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ጉድይር ግዙ





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው ። በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ፤ ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አራተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፴፩
4 me ANNÉE № 31

ሐሙስ ሐምሌ ፳፮ ቀን ፲፱፻፳ ዓ ም ።
JEUDI 2 AOUT 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thale:s
le numero 2 piastres

መድኃኒተ ፈነወ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ።

ባራተኛው ዓመት በ፳፱ ቁጥር በ፲፪ ሐምሌ በ፪፻፳፯ ገጽ አቶ በቀለ ዘለቀ በብርሃንና ሰላም ላሳተመው መልስ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል እጽፋለሁ ይህንኑም ለመጻፍ ያሳሰበኝ ለድሐው ችግር እንዳይበዛበት ስለማለት ለማሰብ ነው እንጂ ሰውነቴን ለማስታወቅ አለመሆኑን ለብርሃንና ሰላም ወዳጆች አመለክታለሁ ። ከቶ እነዚህ ሰዎች እስከ አሁን ድረስ በኢትዮጵያ ያፈር መዋጃ መሰጠቱን ሳያውቁ የቀሩ እማናቸው ሀገር ተወልደው በማናቸው ሀገር ኖሩ ለማለት እጅግ ያስደንቃል ግሩም እንጂ ነው በኢትዮጵያ ከቀድሞ አባቶቻችን ጀምሮ ሰው በሞተ ጊዜ ያፈር መዋጃ ማለት የመቃብር ዋጋ ሁለት ቁና ከንድ እፍኝ ስንዴ ስንዴ ቢታጣ ሌላ እህል ለገበዝ ይሰጣል ይህ መሰጠቱ እርግጥ መሆኑን በኢትዮጵያ ሀገር የተወለደ ሰው አይስተውም ስለሆነ ግን ይህ ግብዝና የሚባል ሥራ በቀድሞ ዘመን ማደሪያነቱ ለተማሩ ካህናት ነበር የሚሰጥ አሁን በቅርብ ዘመን ግን የግብዝናን ማደሪያነት ሀብታሞች ለሀብታቸውና ለሹመታቸው መርጃ አድርገውት ቆይተዋልና ይህንን ያፈር መዋጃ የሚቀበሉ የግብዝና ወኪሎቻቸው ስለሆኑ ይልቁንም በዚህ ተበድለዋል ብለው ስለ እርዳታ ጽፈዋል እንጂ፤እውንስ በገዛ ሀገሩ ሕዝቡ ከተለመደው ዋጋ አብልጦ እየገዛ እንዲቀበር ነውን ወይግሩም ጌታዬ ሆይ አታድርስ ዋጋ የሌለው ሰው እከ ሳይቀበር መቅረቱ ነው ። ይህስ ነገር ለከንቲባው ብዙ ችግር ያለበት ነው ። እማይሞትበት ይገኛል ብሎ ቢሄድ እማይቀበሩበት ደረሰ እሚባል ተረት ሊደርስ ሊፈጸም ነው መሰለኝ ይኸው እንኳ የተለመደው ያፈር መዋጃ የሌለው ሰው በግድ አምጣ ተብሎ ተይዞ አያውቅም ያለዋጋ ቀብሮ ይሄዳል ። አብርሃምም አባታችን በስደት ሣለ ነው ገዝቶ የቀበረ ያውም ቢሆን ካልገዛሁ አትቀብርም ብሎ የከለከለው ሰው የለም እሱ ግን እርስት እንዲሆንልኝ ብሎ አንድ ጊዜ ገዝቶ ርስት አድርጎ የሞተበት ሰው ያለዋጋ ሲቀብር ኖረ እንጂ ሰው በሞተበት ቁጥር እየገዛ እንዳልቀበረ በቆጠረው ምስክር እንደሚባለው ሁሉ ምስክሬ ያው መጽሐፍ ቅዱስ ነው በሚሆነው ሁሉ ነገርን ነገር ያስነሳዋል ደጅ ጥናት ወደሚባለው እማይቃለል ግብር ሄጄ ስመለስ ሁለት ሰዎች እየተጫወቱ ሲሄዱ እንደዚህ አሉ የካህኑንም የወታደሩንም ማደሪያ መኳንንት መውሰድ ወደመንግሥት ቀርበው የተሾሙትም ካህናቶች ከጉልቱ ከሹመቱ እከሉልን ከማለት በተቀር ግብዝና ማደሪያነቱ የካህን ነውና ለካህን ይሰጥ አለማለት መንግሥት ሀገሩ እንዲጠበቅ ሕዝቡ እንዲጠቀም ነውና ሃሳቡንና ድካሙን ሁሉ ካስታወሱት የኢትዮጵያ መንግሥት መስጠት ልማዱ ነው ምን ይሆናል የዚያ የእንጨት ተረት ነው እያሉ ሲነጋገሩ (ተስፋ አትቁረጥ እምትባል መጫሚያዬን አድርጌ ባጠገባቸው አለፋኩና እነዚህ ሰዎች እንደዚህ የሚያወጡትና የሚያወርዱት ለሀገራቸው ከማሰብ ልባቸው አሳርፍ ቢላቸው ነው እከ ። ግብዝና ማደሪያነቱ ወደ ካህን ይመለስ ቢባል እንኳ እነሱ የሚያገኙት አይደለም ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው ክታቡ በ፲ ምዕራፍ ፳፬ ቁጥር ማንም ለራሱ ብቻ የሚረባውን አይሻ ያም ለባልንጀራው የሚረባውን እንጂ ያለውን አስበው ነው ለሀገርና ለወንድም ማሰብ እንደምን ያለ ከሁሉ የበለጠ ታላቅ ጥበብ ነው አልኩና ፈቃዱ ሲሆን የምትባል ትንሽ ደብተር። ድሐው ጌታ መሆን የሚል ማስታወሻ የተጻፈባት ነበረችኝና እሷን ተኪሴ አወጣሁና እነዚህ ሰዎች እንዳሰቡት ሁሉ ግብዝና ለመንግሥት እጅ ሆኖ ከሱ የሚገኘውን ገንዘብ ለኢትዮጵያ ተማሪ ቤት መርጃ እንዲሆን ሰምተውት ዝም የማይባል በፍጥነት የሚፈጸም ረዘም ያለ ተስፋ እመኛለሁ ብዬ ጽፌ ደብተሬን እኪሴ መለስኩና ወደ ዠመርኩት ነገር ስመለስ ብርሃንና ሰላም

የሚባል የድሐ አስተማሪ የሀብታም መካሪ ሐሙስ ሐሙስ እቤቴ እየመጣ ያስተምረኝ ነበረና ያመጣልኝን ጋዜታ ስመለከት አቶ በቀለ ዘለቀ በመጀመሪያ እንደተጻፉት ቁጥሮች በ፳፰ኛው መስመር ላይ በብርሃንና ሰላም ላሳተመው መልስ የሚሆን ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ለመጻፍ አሰብኩ ሥራት እንዳመጣጡ ይታያል እንደተባለው ነውና በሲዳሞ በወላሞ ሰው በሞተበቸው ጊዜ ዘመድ ወዳጅ እስቲመጣ ሳይቀብሩ ፫ቀን ያቆያሉ ይባላል በትጉለትና በመንዝም ይህንንም በመሰለ ሀገር ሁሉ ሰው ያለ ጊዜ ቢሞት ዘመድ ወዳጅ እስቲመጣ ድረስ አንድ ቀን አሳድረው በማግስቱ መቅበራቸውን የዚያ ሀገር ተወላጅ የሆኑ ሰዎች ይስቱታል ብዬ አልጠረጥርም ይሁን እንጂ የሞተ ሰው ሳይቀበር ቢውል ቢያድር ወርዶ ነግዶ አርሶ ሰርቶ ለመቃብር መግዣ አያደርስም ሳይቀበር በመቆየት ምንድነው ጥቅሙ ይህ ለዚህ አንጻር አይደለም ደግሞ እንደዚህ ሁሉ በ፴፫ መስመር ላይ የተጻፈው በወዲያኛው ዓለም መብል መጠጥ አለ ማለት ይመስላል እንጂ መቃብር ለመግዛት ምሳሌው አይመስልም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው ክታብ ባ፭ ምዕራፍ ባ፩ ቁጥር እናውቃለንና የዚህ የምድራዊው የቤታችን ድንኳን ቢፈርስ ከእግዚአብሔር ቤት እንዳለን እጅ ያልሰራው እርሱም የዘላለም በሰማይ ብሏል ።

ባዲሱ ሥልጣኔ ምነው ይሆን የሕዝቡን መጠቀምና ነጻ መውጣቱን አይጽፉ በሕዝቡ ሸክም ማክበድን ብቻ ማሳመር ። መድኃኒታችንም ኢየሱስ ክርስቶስ በሉቃስ ወንጌል በ፲፩ ምዕራፍ በ፵፮ ቁጥር እርሱም አለ እላንተም ደግሞ የኦሪት ሰዎች ወዮላችሁ ለሰዎች ሸክም ታሸክማላችሁና ከመሸከም የሚከብድ እላንተም በንዴት ጸንታችሁ ሸክሙን አትነኩም ወዮላችሁ የነቢያትን መቃብር ትሰራላችሁና ብሎ አስተምሮናል ። ሸክም በመጀመሪያው ከበድ ቢሆን ከመሬት የሚያነሳው ይታጣና ወድቆ ይቀራል ቀላል ቢሆን ግን አንስቶ ሀሰበው በታማይረስ ይችላል።ድሐው መማለጃ በሚባለው ሰንሰለት እንደተያዘ ነው አልተለቀቀምና በመጀመሪያ ሸክም ቢያከብዱበት እላይ እንደተባለው ይቀራል እንጂ አይፈጸምም ። የተቆላ እሀል መዝራት ነው የተቆላ እሀል ቢዘሩት አይበቅልም ። በከንቱ ተበላሽቶ ይቀራል ስለ ማለት ነው እንጂ የናንተን የወንድሞቼን አሳብ አይሆንም ለማለት አይደለም።ወእፃዝ ዳግመ ኢትአብስ ዘየአኪ ኢይርከብከ የተባለው እንዳይደርስ እንጂ ከኢትዮጵያ ልጆች ወጭ እየሆነ ወደ መንግሥት ገቢ ያልሆነ ገንዘብ አለ ማለት ይሰማል በሆነው ሁሉ ሀብት የተሰጣቸው የኢትዮጵያ ልጆች ወደ ጉለሌ እየሄዱ ፭ ፭ ብር ይከፍላሉ ይባላል ። የኢትዮጵያ የካህናቱ ሹም በታ ወስኖ ከሕዝቡ ወጭ መሆኑ ካልቀረ ፭ ፭ ብር የሚከፈልበትን ጉዳይ እያስፈጸመላቸው ገንዘቡን ቢቀበል ላንድ ጉባኤ ተማሪ ቤት መርጃ ይበቃ ነበር ። የመቀናጆ በሬ ወደማታ ወደቤቱ ይስባል እንደሚባለው የኢትዮጵያ ልጆችም ከነሱ ገንዘባቸው ወጭ መሆኑ የማይቀር ስለሆነ ለሃገራቸው ተማሪ ቤት መርጃ ቢሆን በሙሉ ፈቃዳቸው ደስ ይላቸዋል እንጂ በነገሩ አያዝኑበትም ይህ እንደዚህ ያለው ወጪ ያለ ጥቅም ከንቱ ቀሪ ነውና እንደዚህ ያለውንና ይህን የመሰለ ሁሉ ለመንግሥት ማስታወስ የተሻለ ይመስለኛል አምስት አምስት ብርም ለበእድ እየከፈሉ የሚቀበሩ ሰዎችም የሚከፍሉት እያዘኑ ሳይሆን አይቀርም።የሀገሩን ሰርዶ በሀገሩ በሬ እንዲሉ የድሐን ጉዳት ደሐ ነውና የሚያውቀው የታሰበኝን አስታወስኩ እንጂ ለመስማት የሚያስደንቅ ለአእምሮ የሚረቅ አለመሆኑን አይታችሁ ለሃገራችሁ የሚጠቅም እርዳታችሁን ብርሃንና ሰላም በሚባለው ጉባኤ እንድታስተምሩ ክቡር ፈቃዳችሁን እለምናለሁ ። ብርንና ሰላም ላሳየን ጌታችን ምስጋና ይግባው እድሜ ለንግሥታችንና ለአልጋ ወራሻችን ሰላምም ለሃገራችን ።

ከድሆች አንዱ መ አ ዘብሔረ ተጉለት ።

ከፒቴን ባቢኪያን እክቡር ቄስ ዘንድ የተናገሩት ዲስኩር።

ቤተ ዘመድ ።

ቤተ ዘመድ ማለት እንደ አንድ ቲንሽ ቤተ መንግሥት ነው አገሩንና ሕዝቡን ይዘዋል ። ባያቶች ወምበር ላይ ቤተ ዘመዶች ይቀመጡበታል ። በዚሁ አኳኋን አባት እንደ አንድ ንጉሥ እናትም እንዳንዲት እቴጌ ናቸው ።በቤተ ዘመዶቻቸው ላይ ሥልጣን አላቸው በዚህም ቤተ መንግሥት ውስጥ ምንም ዘበኛ የለ ። አንድ ጕራዴ ይልቁንም አንዲት ብትር በውስጡ አይገኝም ። ደግሞ ተንኰልና የሐሰት ወሬ የለም ። በነዚህ ፈንታ ያባት ፍቅርና የናት ፍቅር ብዙ ናቸው ። ልጆች መልካሙን የናት አስተዳደግ ከተማሩ በኋላ አድገው እንደዓለም ማህበር ይሆናሉ ። እንደዚሁም ሁሉ የቤተ ዘመድ ሕይወት መልካም ቢሆን ወይም ክፉ ቤተ መንግሥትን ያሳስባል ። ይኸንንም ማለት ቤተ ዘመዶች መልካሞች ከሆኑ መንግሥት ክፉም ከሆነ መኖር አለመኖሩ በዓለም ውስጥ አይታወቅም ።

የሥልጣኔን ጕዳና የሚይዝ ሕዝብ መንግሥቱ እንደ ቤተ ዘመዶች አኳኋን እርምጃውን ያመለክተዋል ። ብርሃንም እንዳለው ለቤተ ዘመዶች ያበራል ። እርስ በርሱም ስምምነትእንኳ ባይኖረው የፍቅር ማስተማሪያ ቤተ ዘመዶች ናቸው ። ኃይልም ቢኖረው ኃይሉና መጨጊያው መረጋገጫው እግሩ ቤተ ዘመዶቹ ናቸው ። ባለጸጋ (ሀብታም) ቢሆን የግምጃ ቤቱ ሹሞች እነሱው ናቸው ። ቤቱም ሀብት የተሞላ ምግብ የበዛበት ተድላ ደስታ ያለውም ቢሆን ብንመረምረው ከቤተ ዘመዶቹ ይገኛል ።

በቤቱም ውስጥ ጋኑና እንስራው ቢሞላ ጠጁም ሲፈስ ቢገኝ ማሩና ቀፎው ቤተ ዘመዶች እንደሆኑ የታወቀ ስለሆነ ከማናቸውም የዓለም ክፋት ለመዳን ቢፈቅድ የሚያድኑት ቤተ ዘመዶች ናቸው ። ደግሞ ወደ ላይ ከፍ ማለት ቢፈልግ በቤተ ዘመዶች መልካም ኃሳብ አካሄድ ከፍ ይላል ።ለልጆቹም የመልካም አካሄድ አስተዳደግ መስጠት ቢፈቅድ መጀመሪያ የትምህርት ቤት ቤተ ዘመዶች ናቸው ። በዚህ ዓለም ጽዋ ያለውን ኑሮ ማግኘት ቢፈቅድ ሃይማኖቱን እንድ አድርጎ የቤተ ክርስቲያኑን እምነት እየጠበቀ መኖር ይገባዋል ። ይህም መልካም ኑሮ ለልጅ ልጅ የሚቆይ ቅዱስ (ልዩ) ልማድ ነው ።

አንድ መንግሥት ለመዋረድ ሲፈልግ ወይም ሲጀምር በገር ያሉት ቤተ ዘመዶች ይበላሻሉ ። መልካም ሐሳብ የሚያመጣው ቤተ ዘመዶች ሲጠፉ ነው ወደ ጥፋት የሚመራ መንገዱን የሚከፍቱለት ቤተ ዘመዶች ናቸው ። ቢደበደብም የተተደበደበው አንደኛው እጅ ቤተ ዘመዶች ናቸው ። በውጭ ጠላቶቹም ቢከበብ ከውስጡ ያሉት ጠላቶቹ የገዛ ቤተ ዘመዶቹ ናቸው ።በዓለምም በሥልጣኔ መንገዶች ውስጥ አካሔዱን ሁሉ ቢያደርግ ክፉ አድራጊዎቹ ቤተ ዘመዶቹ ናቸው ። ወጣቶች ልጆቹም የሚበሉትና የሚለብሱት በማጣት ቢደኸዩ የቤተ ዘመዶቹ ክፋት ነው ።

ያለ ጠባቂ ወደፊት የሚመጣበትን ክፉ ነገር ሳያስብ ገንዘቡን ያባከነ እንደሆነ ፤ ቤተ ዘመዶቹ ናቸው ይህን ክፉ ስሕተት ያስተማሩትና ልጆቹም መልካም ጤንነትና መልካሙን የጨዋ ልጅነታቸውን ስለቤተ ዘመዶቻቸው ትውልድ ክፋት ጥፋት አያገኙትም በመልካምም አይጠሩም ።

ያለመልካሙ ያባትና የናት አስተዳደግ አንድ አገር ወይም አንዱን መንግሥት ለማበርታት አይቻልም።የትምህርት ቤት ደጉን እውቀትና የአእምሮ ብርሃን መግለጹ እርግጥ ነው ። ነገር ግን የመልካሙ አስተዳደግና ሥልጣኔ መሠረት ቤተ ዘመድ ነው ።

ሁለቱ ታላላቆች የግሪክ ፍሎሰፋውያን አርስቶዲልና ሶክራት እስበሳችው እንዲህ ሲሉ ተጣሉ ይላሉ ። አርስቶዲል ለሕዝብ የሚያስፈልገው ሥልጣኔ ነው አሉ ። ሶክራትም አይደለም የጨዋ ልጅነትና መልካሙ የቤት ዘመድ አስተዳደግ ነው እንጂ አሉ ። ለዚሁም ሶክራት መልካም ምሳሌ አገኘና አንድ ዓመት አሥልጥኖ ሰዎች ከቤቱ ለመጋበዝ በጠራ ጊዜ የቡና ፍንጃል ማህን የሚያቀርብ ድመት ነበረ ። ደግሞ ባንዲት ትንሽ ማጥን አይጦችን ሰበሰበ ከዚያ በኋላ አርስቶዲል ተከራክረው ገብቶ እሱ ዘንድ በተቀመጠ ጊዜ ሶክራት ድመቱን ቡን እንዲያመጣ አዘዘው ። በዚያን ጊዜ አርስቶዲል ድመቱ ቡን ይዞ ሲመጣ አይቶ ተደነቀ ። ይኸውልህ የመልካም አስተዳደግ ትርፍ ብሎ ተናገረ ። በዚያ ጊዜ ሶክራት አይጦች የተሰበሰቡበትን ማጥን በፍጥነት ከፈተው። ያም ድመት የያዘውን ቡን ከነማህኑ ከመሬት በትኖ አይጦቹን ያበርር ጀመረ ። በዚህ ጊዜ ሶክራት መልካሙ አስተዳደግና የጨዋ ልጅነትን ቤተ ዘመዶችም ይነሩ ብሎ መረቀ (ተናገረ) ።

ክፒቴን ባቢኪያን ።

መጀመሪ ።

ኢትዮጵያን ከልብ በማገልገል የሚኖሩ ።

የኢትዮጵያን ሕግ የሚጠብቁ ሁሉ ስለ አገራቸው ጥቅም የሚሞቱ ኢትዮጵያን ያገኛሉ እነዚህ የመንግሥታቸውን ደንብ በማክበር ትክክልነት እየጠበቁ የሚኖሩ በእውነት ታላላቆች ናቸው ። ለአገራቸውም ልጆች እውነት አጽንተው የሚያጸኑ በጥበብና በፍቅር ከዳር እስከ ዳርቻው ድረስ ለተወለዱበት መሬት እንድትበለጽግ ማገልገልን የሚያተጉ ኢትዮጵያን የሚጠብቁ ናቸው ። የመንግሥታቸውን ገንዘብ የሚፈሩ ሉሉ አዋቂዎች ናቸው ላገራቸው ጥቅም ማስተዋልን የሚያውቁ የተመሰገኑ ናቸው ።

፪ኛ፤ እነሆ ስለ አገራቸው በናፍቆት እውቀትን የሚያቀብሉ የተከከለውን የትምህርት ፍቅር ለጥበብ የሚመሩ የብርሃንና ሰላም ምልክቶች ናቸው እነዚህ እውነትን ሥራ የሚያውቁ ለመንግሥታቸውም ሀብት የሚደክሙ ስለሆኑ ያገራቸውን ስም በገልግሎት ሥራ የሚያስመሰግኑ ናቸው ። የኢትዮጵያን ስም ለማክበር በሥልጣናቸው ጻፋጭ ሁነው በእሙንነት ከልብ እተከላከሉ የውነትን ፍሬ የሚያፈሩ ብልሀተኞች አስተዋይ ተብለው በኢትዮጵያ ስም እስከ ዘለዓለም መታሰቢያ የሚጠሩ የተባረኩ ናቸው እነዚህ እውነተኞች የተባሉት እግዚአብሔርን የሚፈሩ ስለሆኑና መንግሥታቸውንም በስርዓት ደንብ የሚጠብቁ እሙኖች ብፁዓን ናቸው ።

፫ኛ፤ ለኢትዮጵያ እስከ እድሜአቸው ድረስ በደግነት ሥራ መንግሥታቸውን በማገልገል የሚረዱና የመስማማት ፍቅር ሥራ ስለአገራቸው ጥቅም ስላለችባቸው ኢትዮጵያን ክብር ለማልበስ እንደ ዕንቍ የሚያበሩ በመታመን የተመረጡ ናቸው ። እነዚህ የኢትዮጵያ እሙኖች ወዳሉበት ሥፍራ እውነት ዘወትር ትመንጫለች ደጎች ወደሚሰበሰቡባት ሥራ በስማቸው ቅንነት ትፈልቃለች ለአገራቸው የሚደክሙ ሁሉ ከራሳቸው ጥቅም ፈጽመው የራቁና የማይፈልጉ ስለሆኑ የእውነት ማገልገል ሥራ ስለ እናታቸው ኢትዮጵያ ስም የሚደክሙ የአገራቸውን ፍቅር ይጠግባሉ ለዘለዓም ተድላ የሚጠሩ ናቸው ። አገራቸውን በንጽሕና ፍቅር ሥራ ላገለገሉት ሁሉ አምላክ በመንፈስ ቅዱስ ምክር እየመራ እስከ ዘለዓለም ተድላ እስኪደርሱ ድረስ ለኢትዮጵያ ለሚያገለግሉት በአብርሃምና በይስሐቅ እድሜ ይጠብቃቸው አሜን ።

፬ኛ፤ለጥቅማቸው አገራቸውን በአፍ የሚወዱ ።

መንግሥት የሚበቃቸውን ያህል እንደ አቅማቸው መጠን ወስኖ ከሰጣቸው ሕግ ተላልፈው የመንግሥትን ገንዘብ የሚደፍሩ ተንኰለኞች ወደ አሉበት ሥፍራ ዘወትር እንደውሻ መናከስ ይበዛል ምክንያቱም ሥውር ሌብነት እንዲመቻቸው እውነተኞችን ከሥራቸው ሲርቁ ደገኞች በደንብ ከሚቀበሉት ይልቅ የሚታይበትና የሚያጠፉት መቶ ጊዜ መቶ እጅ በ፴ ቀን ሲያበዙት እንደ ባሕር አሸዋ እንዳልታፈሰ እርግጥ ነው ። ስለዚህ የመንግሥትን ደንብ እያፈረሱ ያለስጦታ የሚገኙ ሁሉ የመንግሥትና የሕዝብ ጥቅም በምሥጢር ሌብነት የሚዘርፉ መሆናቸውን ተንኰል ሥራቸው ያስረዳል ። እነዚህ ያገራቸውን ጥቅም የሚያጕድሉ አታላዮች ፵ ጅራፍ ከሚያሸቱት ይልቅ የነሱ ይብሳል ። መንግሥታቸውን ለጥፋት የሚያደኸዩ በገዛ ሥራቸው ይጠፋሉ ።

፭ኛ፤የመንግሥትንና የሕዝብን ጥቅም ለማጥፋት ነውር ሥራ የሚወዱ ሰዎች ፍጥረታቸው እንደ ሰው ቢሆን የክፋታቸው ሥራ እንደ ተናካሽ ውሻ እንስሳ በርኩሰት ሥራቸው ይታወቃሉ ለጥቅማቸው እንደተራበው አውሬ ለሆዳቸው ከረጢት ጨብጠው ደንብን አፍርሰው ያገራቸውን ጥቅም ለመብላት እያሰከሱ ለሆዳቸው ይፈጥናሉ እነዚህ በግፍ ሥራ ያገራቸውን ጥቅም በሥውር ሌብነት በዘረፉት ገንዘብ ቤታቸውን ዘግተው

ጠርሙሱን በብርጭቆ ስክር ጨልጠው ዓይናቸው የቤሳን መልክ እስኪመስል ድረስ ብርጭቆን የሚስሙ ሁሉ ሚስቶቻቸውን አይስሙም ዕፍረት የሌላቸው ነውረኞች ወደ ክፉት ጉድጓድ የግማት መዝጊያ ይሆናሉ ዝሙትን የሚያሸቱ ወደ ዲያቢሎስ ሚዛን የሚያዘነብሉ ናቸው ። ወዮላቸው በፈጣሪያቸው ፊት ሲቆሙ መግቢያቸው መድረሻቸው ለገሃነመ እሳት ውስጥ እንደሆን ።

ሰው ሆይ ።

መንግሥትንና ሕዝብ ለማገልገል ጤንነት ሰላምን የሚሰሩትን እናጠፋለን በሐሰት ስብከት እንመሰክራለን ቢባል ሰውን በተንኮል ለጥፋት የሚፈልጉ ሁሉ በእግዚአብሔር ቁጣ ይጠፋሉ።

ዮሐንስ መ

ስለ ቦሰት መንገድ ሥራ ።

፲፱፻፳ ዓመተ ምሕረት ሐምሌ ፲፫ ቀን በግርማዊት ንግሥትና በልዑል አልጋ ወራሽ ትእዛዝ ክቡር ፊታውራሪ ጣሰው ዋለሉ በባቡር ተሳፍረው ውልንጭቴ ጣቢያ ድረስ ወረዱ ፤ የሄዱበትም ምክንያት ቦሰት በሚባለው አገር ሁለት ታላላቅ ተራሮች አሉ አንደኛው ተራራ ከምድር ወደላይ እርዝመቱ በግምት ሁለት መቶ ሃምሳ ሜትር ይሆናል ከመሬቱ ውስጥ የእሳትና የነፋስ ኃይል ይሰማዋልና ሰው ወደ ተራራው እራስ ለመውጣት ሲጀምር የላቡቱ እስትንፋስ ያደክመዋል ይላሉ ። ደግሞ አንዳንዶቹ ጋሎች ቀዝቃዛና ፍል ውሐ ከተራራው ላይ አለ እያሉ ያወራሉ ፤ ወደተራራው አጠገብ ለመድረስ የእኩል ሰዓት መንገድ ሲቀር በበጋና በክረምት እንደ አዲስ አበባ ፍል ውሐ ከመሬቱ ጢስ ሲወጣ ይታያል ይህ ጢስ ከሚወጣበት ቦታ ላይ በዚያ አገር የሚኖሩ ጋሎች ጎጆ ሰርተው ቆጥ አብጅተው በቆጡ ላይ ሲቀመጡ ከሙቀቱ ኃይል የተነሣ ላብ ከሰውነታቸው እንደውሐ እየተንቈረቈረ ልክ እንደወሸበ አይነት ሆኖ ፈውስ ይሰጣቸዋል ይባላል ፤ ልዩ ልዩ በሆነ በሽታ የታመሙ በቂጥኝ በጨብጥ በቁርጥማት በእሪህ ደዌ የተያዙ ሁሉ ጤንነት አገኘንበት እያሉ ሲናገሩ ሰማሁ ከውጭ አገርም ሰዎች አያሌ እየተመላለሱ አይተው ለሰውነት ጤና ይሆናል ብለዋል ይላሉ ነገር ግን የሙቀቱን ወዘት የሚፈልግ ከሀያ ደቂቃ በላይ ከውስጡ የተቀመጠ እንደሆን ለሰውነቱ ጉዳት ይሆናል አሉ ይባላል እውነትም ይህ የተናገሩት ቃል እርግጥ ነው አሁን አንዳንድ ሰው በአዲስ አበባ ፍል ውሐ ሲታጠብ ከውሐው ውስጥሳይወጣ ሁለት ሰዓት ያህል እሰይ ተሙኜ እያለ በሙቀቱ ውስጥ ቆይቶ ከውሀው ክበብ ለመውጣት እስኪሳነው ድረስ ይታጠባል ከውሐውም ሙቀት የተነሣ ይደክመውና ባልንጀሮቹ በአካላቱ ቀዝቃዛ ውሐ እያፈሰሱ ለሳንሳ እየደገፉ ወደ ቤቱ በድካም ይወስዱታል ይህ ሰው ከመጠኑ አልፎ ይህን ያህል ጊዜ በሙቀት ወላፈን ውስጥ መቆየቱ በምን ምክንያት እንደሆነ በጥያቄ ብመረምር ገንዘብ ከፍሎ ስለታጠበ የገንዘቡ ወጭነት ያለ አገባብ ሆኖ እንዳያሳዝነው በሕሊናው ከሀሣብ ለማረፍ ነው የሚሉ ወሬ ሰማሁ እንግዲህ ይህ ሰውዬ ከብርታት ወደ ድካም ከጤና ወደ ሕመም መድረሱ ባይመረመር ነውና እንደዚህ ያለውን ነገር ሁሉ እወቀት በተሰጠው መሐንዲስ እየተመረመረ ለሕዋሳታችን እንደሚያስፈልግ ማድረግ ይገባናል ይመስለኛል ።

አሁንም በሶስት አውራጃ ሐርቱ ከሚባለው ቦታ ላይ ለሕሙማን ፈውስ የሚሆን ሙቀት ስለተገኘበት ክቡር ፊታውራሪ ጣሰው በባቡር ሄደው ለሙቀቱ ወዘት አንድ የቆርቆሮ ቤት ለማረፊያ አሠሩ ይኸም ሐርቱ የሚባለው የሙቀት ቦታ ከውልንጭቴ ጣቢያ እንሥቶ የአራት ሰዓት ተኩል መንገድ ይሆናል ። ከጫካው ብዛት ከበረሃው ጽናት የተነሣ ውሀ የሌለበት ጥቅጥቅ ያለ ዱር ነበር በዚህ መንገድ ለማለፍ ለአራዊት ነው እንጂ ሰው ሊሄድበት በጣም ጭንቅ ነውና አይችልም አሁን ግን ክቡር ፊታውራሪ ጣሰው ሕዝቡን አዘው አራት ሰዓት ተኩል የሚሆነውን ዱር ጫካውን መንጥረው አፈሩን ደልድለው ደንጊያውን ወቅረው ለእረኛ እንኳ ብዙ ችግር የነበረውን አውቶሞቢል ያለሀሳብ እንዲመላለስ አድርገው ሥራው በተጀመረ በስድስተኛው ቀን ጨርሰው ሠሩት አከናወኑትም ይኸነንም ሥራ ከጨረሱ በኋላ መኳንንቱን ጋብዘው ነበርና በእራት ጊዜ ቀጥሎ ያለውን ሀሳብ ተናገሩ ቃሉም ይህ ነው ክቡራን ወንድሞቼ ሆይ በዚህ መንገድ ሥራ ደስ እንዳሰኛችሁኝ ከእግዚአብሔር ምሕረት ከመንግሥት ሀብት ከኢትዮጵያ ረድኤት ያድላችሁ እኔ ለዚህ፡ለመንገድ ሥራ|ከግርማዊትና ከልዑል ታዝዤ ስመጣ እስከ ሁለት ወር ድረስ ይጨረሳል ብዬ አልጠረጠርኩም ነበር አሁን ግን ቡብዙ ቀን የማይፈጸመውን በስድስት ቀን በፍጥነት ለሠራችሁት ለወደ ፊትም በትጋታችሁ መንግሥታችሁን በቅን እንደምታገለግሉ ያስረዳኛል አሁን አሩሲ አገር ማዶ አሻግረን ስናይ ቅርብ ነው ነገር ግን ለንግድ ሥራና ለማናቸውም ጉዳይ ለመተላለፍ የከለከለን መንገድ ባንሠራ ነውና እንደ አሁኑ አያያዛችን ደግሞ ከሐርቱ እንሥተን አሩሲ ድረስ መንገድ ብንሠራ ከ፳ቀን አያዘገየንም ነበር አሁንም ሁላችሁም በልቦናችሁ አስቡት ብለው ጨረሱ ሕዝቡም የግርማዊትንና የልዑልን ዕድሜ ያርዝምልን እግዚአብሔር በሠጠን ጉልበት ሀሳብዎን እንፈጽማለን ብለው መለሱ አሁን ይኸን ጋዜጣ የጻፍኩበት ምክንያት ክቡር ፊታውራሪ ጣሰው ለሀገራቸው ልማት ለመንግሥታቸው ሥፋት እንዲሆን ብለው የመንገድ ሥራን ነገር ስለአሣሰቡን እኔም የኢትዮጵያ ድሀ እንደአቅሜ ድጅኖ ተሸክሜ አካፋዬን ይዤ እየረዳሁ ስለመንገዱም ሥራ አምስት ብር እርዳታዬን አቀርባለሁ ክቡራን የሆኑ የኢትዮጵያ ልጆች የፊታውራሪ ጣሰው ዋለሉ ባልደረቦች እርዳታቸውን ያፋጥናሉ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ እስመ ርቱዓት ፍናዊሃ ጻድቃን የሐውርዎን ወኃጥአን ይስእንዎን ዘእንበለ ትብጻሕ ግብተ አሠንዩ ፍኖተ ። ይቤ በቀለ አቦዬ ።

ኃዘን ።

ስለ አቶ ጺጋዬ መድኅን ዕረፍት ።

አቶ ጺጋዬ መድኅን የልዑል አልጋ ወራሽ ማተሚያ ቤት ሠራተኛ በድንገት በሽታ ታሞ ሐምሌ ፲፱ቀን ዓረፈና በማግሥቱ እጴጥሮስና እጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን ተቀበረ ። ዘመዱ

ቹና ወዳጆቹ ጓደኞቹ የማተሚያ ቤት ሠራተኞችም በብርቱ ኃዘን ብዙ ተሰብስበው በክበሬታ ቀበሩት ። ለባለቤቱና ለልጆቹ ለወንድሞቹና ለወዳጆቹ ሁሉ ብርቱ ኃዘን ሁኑዋል ።

ባለቤቱና ወንድሙ አቶ ተወልደ ብርሃን መድኅን ኃዘናቸውን ተካፋይ ሁነው እስከ መቃብሩ ለሸኙዋቸው ወዳጆቻቸውና እቤት እየመጡ ላጽናኑዋቸው ሁሉ ከኃዘን ያድናችሁ እያሉ ምስጋናቸውን ይገልጻሉ ።

የከተማ ወሬ

ስለ መሐለቅና ቤሳ ሽረፋ

በብርሃንና ሰላም ቍጥር ፳፱ እንደ ተጻፈው የመሐለቅና የቤሳ ሽረፋ ተጀምሮ ሥራው ደህና ይሔድ ጀምርዋል መሐለቅና ቤሳም እየረከሰ መሔድ ጀምርዋል መሐለቅና ቤሳ መንዛሪዎችም እንደጀመሩት ወደፊት ቢገፉ ሽረፋው እልኩ ሳይገባ አይቀርም እያልን ተስፋ እናደርጋለን ። መሐለቅና ቤሳ የሚፈልግ ሰው በሰባቱ ሰፍራ ለመሐለቅና ቤሳ ሽረፋ በተሰናዳው ቤት ተሰብስቦ በተራ በተራው ብሩን ሰጥቶ እንደ ደንቡ መሐለቅና ቤሳ እየተቀበለ ሲሄድ ይውላል ።

የቀድሞው የመስኮብ ንግሥት ምሥጢር ያለው

የሕይወት ታሪክ ባለሙዋሏ ዘኒት የጻፈችላት

በካፒቴን ባቢኪያን ታርሞ ታደሰ ።

መጀመሪያ ክፍል

እኛም በውስጡ ገብንና ቀዝቃዛ ውኃ ለመንናቸው የዚሁም የበረኛ ሽማግሌ ሚስት ቀዝቃዛ ውሀ አመጣችልንና አልጋ ወራሽቱን አሊክስን ለማዳን ቻልን እሱዋም ከነቃች በኋላ ያለችበትን አደራሽ አየችና ከዚህ አዳራሽ ምን አመጣኝ ብላ ተደነቀች እኔም የሆነችውን ሁሉ በነገርኋት ጊዜ እንዲህ ብላ መለሰችልኝ አዬ ጉድ ከቶ እኔ እንዴት ያለሁ ነኝ እንዳንድ ደካማ ሰው የሞተ መስዬ ነበር ብላ ከተደነቀች በኋላ ተሸክመው ያመጧትን ሰዎች አብረው ያሉትን ወይዛዝሮችና የዚያኑ ቤት ጠባቂ አመሰገነች ወዲያው ከዚያ ቤት መጣንና ከሁለቱ ሰዎች ጋራ አንዱ ያሊክስን እጅ (ሁለተኛው የኔን እጅ ይዞ ተያይዘን ሄድንና ወደ አንድ ትንሽ የቡና ቤት ገባን አሊክስም ለነዚህ ሰዎች የንጉሥ ልጅ መሆኑዋን ሠውራ በሌላ ስም አሊክስ ዲትሞልድ እባላለሁ ይህችም እህቴ ማሪ ትባላች ብላ ነገረቻቸው እነዚያም ሰዎች በየተራ ካርት ቢዚታቸውን ሰጡን

አንዱም ከነዚህ ሰዎች ትልቁ ጀርመን ነበር ስሙም ሮዶልፍ ዋስቶርፍ ይባላል ሁለተኛው ባልንጀራውም አንድ ኢጣሊያን ነበረ ስሙም ካርሎ ፒሮንቲ ይባላል እኛም ለነዚህ ሰዎች ሌላ ምንም ነገር አላጫወትናቸውም በማግሥቱ ማታ እንገናኝ የማለት ቀጠሮ ሰጠናቸውና ተሰናበትናቸው በቤተ መንግሥቱም ውስጥ ባደረግነው ነገር ሁሉ ደስ ብሎን ተመለስን ።

ሁለተኛ ክፍል ።

በማግሥቱ ቦርጊዝ ከምትባለዋ የንጉሥ ልጅ ጋር ቅድስት እንድርያ ከሚባለው ቤተ ክርስቲያን ሂደን በዚሁ ቀን ምንም ደስ የሚያሰኝ ጨዋታ አላገኘነም ስለ ዚህ ቀኑ አለመጠን እረጋርም መሰለን ወደማታ ግን ለተወደዱ ወዳጆቻችን የሰጠናቸውን ቀጠሮ አክብረን ሄድን የቀጠሮውም ቦታ በከተማ ውስጥ ኮሎናይ በሚባለው ትልቅ ሆቴል ነበር ይህም ቀጠሮአችን የመጀመሪያው ጊዜ ሆነ ነገር ግን ይህ ሁሉ ሲሆን ከወዴት እንደሆነ ለወዳጆቻችን አልገለጽነውም እነዚህ ሁለቱ ሰዎች እውነተኛውን ነገር ከወዴት እንደመጣን ምንም እንደ ሆነ ሆኖ ለማወቅ ያወሩ ነበሩ ስለ ዚህ መጨረሻ የሌለው ጥያቄ ይጠይቁን ነበረ አልጋ ወራሽቱ አሊክስ አሰበችና አንድ ወሬ እንዲህ ብላ ነገረቻቸው አባቴ ያንድ ፋብሪካ ዲሬክተር ነው እሔንም እህቴ ናት ብላ አለቻቸው ከነዚያም ሰዎች ሮዶልፍ የተባለው ዳግም አባቴ እንዳንችው አባት ያንድ ፋብሪካ ዲሬክተር ነው ስሙም ሀይንሪክ ዋይስትሮፍ ይባላል ስለ አንደኛው ደግሞ ካርሎ ገርባቲ የተባለው እጅግ ሽንቅጥ ደስ የሚያሰኝ ስለ ሆነ በኔ ዘንድ እጅግ የተወደደ ሆነ እርሱም አንድ በመቶ አሥራ ዘጠነኛ ቁጥር ደምብ ውስጥ የጦር አለቃ ነበረ በዚያ ጊዜ ከለቃው ፈቃድ ተቀብሎ ተሰናብቶ ስለ ነበረ የሹመት ልብሱን ትቶ እንደ ማናቸውም ሰው ልብስ ነበረ አሁን እውነት ነው የምናገረው በዚያ ጊዜ በርሱ እጅግ ደስ ብሎኝ ነበረ ብዙውንም ቀናቶች ማታ ማታ አለመጠን ደስ ብሎን አብረን ኖርን እነዚህ ሁለቱ ጐበዛዝት አልጋ ወራሿቱ አሊክስ እንደ ነገረቻቸው ያንድ ፋብሪካ ዲሬክተር ልጅ መስለናቸው እኛን ደስ ለማሰኘት የተቻላቸውን አደረጉ እነዚሁም ወጣት ጐበዛዝት ያደረገልን ምን ጊዜም ለመርሳት አይቻለንም ።

ካፒቴን ባቢኪያን

በሚመጣው ሳምንት ይቀጥላል

ስለ አቶሞቢል ነገር ።

በአዲስ አበባ አቶሞቢል መከራየት በተጀመረበት ጊዜ የኦቶሞቢል ክራይ በጣም ውድ ነበረ ኋላ አቶሞቢል እየበዛ ስለ ሄደ ክራዩ እየቀለለ ሄደ ። ይልቁንም ዘንድሮ ከዱሮው የበለጠ በጣም ርካሽ ሆኑዋል ።

ድሮ አሥር ብር ይከፈልበት የነበረ መንገድ ዛሬ በአራት ብር አቶሞቢል ተከራይቶ ለመሄድ ይቻላል ።

እንግዴህ ካዲስ አበባ ወደ ባላገር የሚወስደው መንገድ ደኅና ሆኖ ተሠርቶ በተፈጸመ ጊዜ የብዙውን ቀን መንገድ በጥቂት ሰዓታት ደርሶ ለመመለስ ይቻላልና ለመንገደኛው ድካም ይቀልለታል ። ስለ ዚህ የመንገዱ ሥራ እንዲፋጠን ተስፋ እናደርጋለን ።

አቤርላንድ



ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሽ አቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጦጦን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባ ኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም በለማግኚቶና በለባተሪ ነው ካምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማኅደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እና ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል «ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው

ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

ማስታወቂያ

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከንትርጓሜው	፲፪	ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከንትርጓሜው	፲፪	ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከንትርጓሜው	፲	ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከንትርጓሜው	፲	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር	፰	ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከንትርጓሜው	፯	ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከንትርጓሜው	፯	ብር
የዓለም ጂዮግራፊ በአማሪኛ ደኅና ጥራዝ ዋጋው	፯	ብር
» » » መናኛ ጥራዝ ዋጋው	፮	ብር
ደግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፮	ብር
ኅሐ ጽባሕ	፮	ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከንትርጓሜው	፫	ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫	ብር
የሕይወት ታሪክ	፪	ብር ተኩል
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪	ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከንትርጓሜው	፪	ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከንትርሜጓው	፪	ብር
ቁጥር ትምርት	፩	ብር
ያማሪኛ ሰዋስው	፩	ብ
ወዳጄ ልቤ	፩	ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን		አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ		አላድ
አጭር የዓለም ታሪክ		አላድ
ያማሪኛ ፊደል		ሩብ
አሳብና ምኞት		ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት		ሩብ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፪	መ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር		፪መ
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ		ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶ ግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ		ሩብ

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም ፤ የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ፤ የልብ ፤ የደረት ፤ የጉበት ፤ የኩላሊት ፤ የጅማት የጨብጥ፤ የቂጥኝና የቋቁቻ፤ የሚያዋልድ፤ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል

እደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ሱቅ ነው ።

ዓለም ሁቅ ፲፫ዓይነት የተሰማ አሼቴ ሙዚቃሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

COGNAC S.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሁቅ ይገኛል ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

RUGBY

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው·

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፥ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ያሰናዷነት ፈቃድ የተቀበለ ።

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በከፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በከፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው ።

ጉድ ይር ግዙ





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው ። በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ፤ ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

አራተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፴፪
4 me ANNÉE № 32

ሐሙስ ነሐሴ ፫ ቀን ፲፱፻፳ ዓ ም።
JEUDI 9 AOUT 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲረክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የንግድ ሚኒስቴር ቤት ምርቃት ።

የንግድ ምኒስቴር አሁን በቅርቡ በጃን ሜዳ ዳር በልዑል ተፈሪ መኰንን ግቢ ፊት ለፊት እጅግ ያማረ ባለ ፎቅ አዲስ የጽሕፈት ቤት ከፍቷል።ይህንንም የጽሕፈት ቤቱን ለማስመረቅ ሐምሌ ፳፱ ቀን የኢትዮጵያ ሚንስትሮችና መኳንንቶች የውጭ አገር ሚንስትሮችና መኳንንቶች ዋና ዋና ነጋዴዎችም ሁሉ ተጠርተው ነበር።የጥሪው ሰዓት በደረሰ ጊዜ ሚንስትሮችና መኳንንቶች ሁሉ በአቶሞቢል እየሆኑ መጡና ሜዳውን አቶሞቢል ሞላው ።

ከዚህ በኋላ ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ባማረ አቶሞቢል ሆነው መጡ።የውጭ አገር ሚኒስትሮችና መኳንንቶች ከልዑል ጋራ ተገናኙና ወዲያው የቤቱን ክፍል እየዞሩ አዩ ፤ የቤቱ ክፍልም እጅግ ያማረ ሥርዓቱም የተከናወነ ነው በሥራቸው ጠንቃቅነት የተመሰገኑና የጸዱ የንግድ ሚንስተር ሠራተኞች በክፍል በክፍላቸው ሁነው ይታዩ ነበር በየበሩም የተሰናዱ የንግድ ሚንስተር ዘበኞች ቁመው ነበር ። የቤቱን መሰናዳትና የሥራውን አከፋፈል ያዩ ሁሉ ከማማሩ የተነሣ አጥብቀው አደነቁ ።

ይህን ሁሉ አይተው ከተመለሱ በኋላ ለሽምፓኝ ግብዣ በተሰናዳው ቦታ ሁሉም በማዕርግ በማዕርጋቸው ተቀመጡ ። በሽምፓኝ ጊዜም ክቡር ነጋድራስ መኰንን የንግድ ሚንስተር ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናገሩና በጣም ተጨበጨበላቸው ።

ልዑል ።
ክቡራን ሚኒስትሮች ።
መኳንንቶች ሆይ ።

በዛሬ ቀን በአዲሱ የንግድ ሚኒስቴር ቤት እናንተን በመቀበላችን ጥልቅ የሆነ ደስታና ታላቅ ክብር አገኘን ።

በየጊዜውም በግርማዊት ንግሥታችን ጠባቂነትና በአስተዋዩ በልዑል ተፈሪ መኰንን መሪነት የየክፍሉ ሚኒስቲሮች የአዲሱን ዓይነት ሥራ መዝገብ ለመከተል ጀምረዋል ። አዲስ ዓይነት ሥራዎችም ተጀምረው ይሠራሉ ። ቀዳማዊ በሆነው መንግሥታችንም ውስጥ አዲስ የሕይወት ደም ገብቶበት ሥራውን ማነቃቃት ጀምሯል ። ይኸውም የሥራ ድካም ከጥቂት ጊዜ በኋላ መልካም ፍሬ እንዲአፈራ በሙሉ ልባችን እንመኛለን ። ለመሰብሰብ አስቀድሞ መዝራት ነው ለማደግና ለመስፋትም መስራት ነው ።

ስለዚህ የሥራ ድካም ሁሉ ዋጋውን እንዳያጣ ስለ አወቅን በቁርጥ አሳብ ሥራውን ለመአቋቋም አደፋፈረን ።

ኢትዮጵያም በሌሎቹ መንግሥታት ዘንድ የሚገባትን የክብር ደረጃ ለማግኘትና ለመጠበቅ ስለ ፈለገች በአገርዋ ውስጥ የንግድ ሥራ በየጊዜው እየሠፋ እንዲሄድ ለማድረግ ፈቃድዋ ነውና የንግድ ሥራ የሚአገናኘው ነገር ሁሉ ያለ ችግርና ያለ ድካም እንዲፈጸም እንጥራለን ።

የንግድ ሥራ በደንብ እንዲሄድ መትጋት የተገባ ነው። ደንቡም በሕግና ግልጥ በሆነ ትእዛዝ እየተወሰነ በትክክል በመስራታቸው እሙን የሆኑት ነጋዴዎች እምነት በሌላቸው ነጋዴዎች እንዳይጠፉ የሚቻለንን እርዳታ እናደርግላቸዋለን ። ይህን የመሰለ ትልቅ ሥራ ሁሉ ምንም ለጊዜው ብርቱና አስቸጋሪ ቢሆን እስከ መጨረሻው ድረስ ለመግፋት ቁርጥ አሳብ ስላደረግን እግዚአብሔርም ይረዳናል ። ከዚህም ቀደም በግርማዊት ንግሥታችንና በሥራ መሪያችን በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ጊዜ የተሠራውን አዲስ ሥራ ሁሉ በዓይናችን ለማየት ችለናል።

የንግዱም ሥራ ወደፊት እየሠፋ እንዲሄድ ተስፋ እናደርጋለን ። አሁንም መኳንንቶቻችን የውጭ አገር ሚኒስትሮ

ቾና መኳንንቶች ይኸን የንግድ ሚኒስቴር ቤት የምርቃት በዓል ለማክበር ስለ መጣችሁ በራሴና በረዳቶቼ ስም ሆኜ ምስጋናዬን አቀርብላችኋለሁ ።

ለግርማዊት ንግሥትና ለልዑል ጌታችን እረጅም እድሜ ከጤና ጋራ ይስጥልን ብዬ ጽዋዬን አነሣለሁ ።

ቀጥሎም ክቡር ሙሴ ጀራርድ የቤልጅክ ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር በራሳቸውና በጓደኞቻቸው ስም የሚከተውለን ቃል ተናግረው ተጨበጨበ ።

ጌታዬ ።

በኢትዮጵያ የሥራ ቤቶች ሁሉ ለሥራና ለጥቅም መሪ የሚሆኑ አዳዲስ የሚሻሻል ሥራዎች በተደረጉ ቁጥር የውጭ አገር መንግሥቶችን እንደራሴዎች ደስ የሚያሰኛቸው ነው ።

የግርማዊትና የልዕልናዎ መንግሥት ይልቁንም ይህን የማሻሻል አሳብ ተከትሎ የንግድ ሚኒስቴርን ቤት አቆመ ። ይህነንም እጅግ ታላቅ የሆነ ሥራ መሪ ሆነው እንዲያስኬዱ ምስጉኑን ነጋድራስ መኰንንን መረጠ ።

የኢትዮጵያ ንግድ እየሰፋ በሚሄድበትና በአገሩም በልዩ ልዩ ሥፍራ የተቀመጡ ነጋዴዎች ሻጭና ገዢ ከሆኑት ከኢትዮጵያና ከውጭ አገር ጋራ ንግዳቸውን ለማስፋት በትጋትና ባለመሰልቸት በሚጥሩበት ባሁኑ ጊዜ የነጋዴዎቹን ሁሉ የመተባበር ድካም የሚያነቃቃ እየተቆጣጠረ ጥግ የሚሆን ዋናውን እስታቲስቲክ የሚሠራ ጠቅላይ የሥራ ቤት ማቆም ለመንግሥት የሚያስፈልግ ነገር ሆኖ ታየው ። ይህም እስታቲስቲክ ያለፈውን የሥራውን አካሄድ እያመለከተ ወደፊትም ሥራውን በልማትና በተሻሻለ መንገድ ለመፈጸም መሪ ይሆናል ።

ከሁሉ ይልቅ ጥቅም ያለው የንግድ ሚኒስቴር ሥራ ይህ ነው ። ጌታዬ ሆይ እነዚህን የሚያሳስቡ ሥራዎች የውጭ አገር መንግሥቶች እንደራሴዎች በደስታና በወዳጅነት አሳብ መከተላቸውን ሳረጋግጥልዎ ስለ ግርማዊትና ስለ ልዕልናዎ ጤና ኢትዮጵያም ሳታቋርጥ እየለማችና እያደገች እንድትሄድ በመመኘት በተራዬ ጽዋዬን አነሳለሁ ።

ከዚህ በኋላ የኢ መ አ ተፈሪ መኰንን ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናገሩና ሶስት ጊዜ ጭብጨባው ቀለጠ ።

ሚኒስትሮችና መኳንንቶች ።

በየክፍሉ ያሉት ሚኒስትሮቻችንሥራቸውን ሁሉ በመልካም አሳብና ትጋት በመሥራታቸው አገሩ እየሰፋና እያደገ ስለመሔዱ ታላቅ ደስታ አድሮብናል።ይልቁንም የንግድ ሚኒስቴር ሥራ በያመቱ በጣም እየተሻሻለ መሔዱ የታወቀ ሆኑዋል ።

ሚኒስትሮቻችንና ሌሎቹም ሹሞቻችን ከትልቁ እስከ ትንሹ ያገራቸው ፍቅር ስለ አደረባቸው ልባቸው ለሥራ እየተነሣሣ መንግሥታችን ያቆመውንና የደነገገውን የሕጉን መሠረት እንዳወቁትና እንደ ተረዱት አይተነዋል ።

እነዚህም የሕግ መሠረቶች ተጽፈው ብቻ ሳይቀሩ የሚሠራባቸው ሆነዋል ።

በመልካም መሬት ላይ የወደቀ ዘር ቡቃያው እንዲያምር የሚኒስትሮቻችንም ሥራ ሁሉ አጀማመሩ እጅግ አምሯል ። ወደ ፊትም የሚያፈራውን መልካም ፍሬ ለማየት ተስፋ እናደርጋለን ።

በሥራውም የሚደክሙ ሰዎች የድካማቸውን ዋጋ በሰፈው እንዲያገኙ እርግጥ ነው ። ይህም ሁሉ ለመንግሥታችን ታላቅ መጽናናት ይሆነዋል ።

እነዚህም በየክፍሉ የሚሠሩት ሚኒስትሮች እንደ አሁኑ በአንድ አሳብና በአንድ ልብ ሆነው በሥራቸው እየገፉ ወደ ፊት የሔዱ እንደሆነ ለቀዳማዊት መንግሥታችን በዓለም ሁሉ ፊት ምስክሮች ለመሆን ይችላሉ ።

አሁንም የንግድ ሚኒስትራችን ጊዜውን ሳያጠፉ ከረዳቶቹ ጋራ በትጋት መሥራቱን ስለ አስመሰከረ እናመሰግነዋለን ። ወደ ፊትም ለሚሠራው ሥራ ሁሉ ከመንግሥታችን ሙሉ እርዳታ እንዲያገኝ እንፈቅድለታለን ።

ደግሞ ያገራችን ልማትና ሥልጣኔ በየጊዜው እያደገና እየሰፋ መሔዱን ለማየትና የደስታችን ተካፋዮች ለመሆን ወደዚህ ጥሪ ለመጡት ለውጭ አገር ሚኒስትሮችና መኳንንቶች ምስጋናችንን እናቀርባለን ።

ለግርማዊት ንግሥታችን ረጅም እድሜ ከጤና ጋራ ይስጥልን ። ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ።

ግብዣውም በተፈጸመ ጊዜ ልዑል ወደ ቤታቸው ተመለሱና ሁሉም ወደ ቤቱ ሄደ ።

የንግድ ሥራ ሲሰፋና ሲከናወን ለመንግሥት ዋና ብልጽግናው ለሕዝብም ብዙጥቅም የሚገኝበት ነው ።

መንግሥት ብልጽግናው የበለጠ የሚሆንበት የገዛ ሕዝቡ ዋና ዋና ነጋዴ ሆኖ በንግድ ሥራ ሲበረታና በትርፉ ሀብታም ሲሆን ነው ። ከዚህ በፊት ግን በንግድ ሥራ ሀብቱ ሰፍቶ በታጃርነት ስም የሚጠራ እጅግ ያለ አይመስለኝም ። ለወደፊቱ ግን በንግድ ሚንስትሩ ብርታትና ትጋት ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ እየላኩ ከውጭም የሚያስፈልጋትን ዕቃ እያስመጡ የሚነግዱ ኢትዮጵያውያን፣ እንደሚገባ ዋና ዋና ነጋዴ እንዲገኙ ተስፋ እናደርጋለን የሆነም ቢሆን ለክቡር ሚንስትርና ለንግድ ሥራ አለቆች ለሠራተኞቹም ሁሉ የተከናወነ ሥራቸው እየገነነ እንዲሄድ እንመኛለን ።

የዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሽልማት ።

ሐምሌ ፴ ቀን የዳግማዊ ምኒልክ ትምርት ቤት ስለ ክረምቱ ዕረፍት የሚዘጋ ስለ ሆነ ለተማሪዎቹ ፈተና ተደርጎ በትምህርት የበለጡ ሲሸለሙ ለማየት ሚኒስትሮችና መኳንንቶች ሁሉ ተጠርተው ነበር በ፱ሰዓት ልዑል በአቶሞቢል ሆነው መጡና ተማሪዎቹ ተሰልፈው የኢትዮጵያ ማርሽ እየተመታ አምረው ታዩ ።

ከዚህ በኋላ ልዑልና መኳንንቱ ሁሉ ተማሪዎቹ ሲሸለሙ ወደሚታዩበት ትልቅ አዳራሽ ገቡ ። በዚያን ጊዜም ማርሽ ተፈሪ ተመታና ክቡር ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ ያገር ግዛት ሚንስቴር የሚከተለውን ቃል ተናገሩና ተጨበጨበ ።

ዛሬ ከዚህ ለተሰበሰባችሁ ክቡራን ምንስቴሮችና መኳንንቶች ወይዛዝሮችም። በዚህች ዕለት ይህንን በዓላችንን ለማክበር

ስለመጣችሁ የደስታ ምስጋናችንን እናቀርብላችሁ ዘንድ ይገባናል ። ይህ በታላቁ ንጉሠ ነገሥት በዳግማዊ ምኒልክ ስም የቆመ ትምሕርት ቤት በሥራው እንደዚህ በመሻሻሉና የኢትዮጵያም ልጆች በትምህርት እየተጉ በቁጥር እየበዙ በመሄዳቸው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ሆኖልናል ።

ይልቁንም ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ያባታቸውን የታላቁን ንጉሠ ነገሥት የዳግማዊ ምኒልክን ትክክል ሐሣብ ተከትለው ይህን ተማሪ ቤት እንዲሻሻል በማድረጋቸው ብዙዎችን ደስ የሚያሰኝ ሆነ ።

እንደዚሁ በኢትዮጵያ ላሉት ወደፊትም ሊቆሙ ለታሰቡት ተማሪ ቤቶች ሁሉ በሥራቸው እንዲሰፋፉና ትምሕርት በኢትዮጵያ እንዲበዛ ፍጹም ምኞታቸው እንደሆነ በግልጽ ይታወቀኛል።

ለኢትዮጵያ ልማትና ደህንነት ያለእረፍት የሚጥሩ እጅግ አስተዋይ ትጉሕ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ባለፈው ዓመት ሐምሌ ፲፱ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ ም ከዚሁ ተማሪ ቤት የፈተና በዓል ለማክበር ተሰብስበን ሣለን አገረ ገዢዎች በያሉበት የትምሕርት ቤቶችን እንዲያቆሙ ልብ የሚነካ መልካም ምክር አሰሙ ። እነሆ ይኸው በዚች ባንድ ዓመት ውስጥ የልዑል ጥዑም ምክር ከልባቸው የደረሰ አንድ አንድ የኢትዮጵያ ታላላቆች እንደሚያስፈልግ ተረድተውት ተማሪ ቤቶችን ያቆሙና ሊያቆሙም ሐሣባቸውን ያነቃቁ ብዙዎች ሆነዋል ።

እውነት ነው አሁን ለሀገራችን ዋናው የሚያስፈልጋት ነገር በያውራጃው ተማሪ ቤቶችን ማቆም የትምሕርትን ሥራ ለማስፋትና ለማበራታትም እንደሆነ ጊዜ እራሷ እንደመስታዋት ገልጻ እነሆ ታሣያለች ።

እንግዲህ ይህችን ለትምሕርት የተለየችና የተሰጠች ጊዜ በከንቱ እንዳታልፍብን እንደግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና እንደ ልዑል አልጋ ወራሽ መልካም ሐሣብ ተከትለን ሁላችንም በተቻለን መጠን እየተረዳዳን ተማሪ ቤቶችን በየግዛታችን ማቆምና በቁጥር እንዲበዙ በሥራም እየተሻሻሉ እየበረቱ እንዲሄዱ ልጆቻችንም ተግተው እንዲማሩ ማነቃቃት የሚያስፈልግ መሆኑ ታይቶኝ ለኢትዮጵያ ታላላቆች መኳንንቶችና ሚንስቴሮች አሣሥባችሁ ዘንድ ወደድሁ ።

ስለሆነ ለኢትዮጵያ በክብሯ ላይ ክብርን የሚያክልላት የልጆቿ መማር እንደሆነ በግልጽ እንደሚታወቃት በፍጹም ልቤ አምናለሁ ። ይህ ከሆነ እንግዴህ ሁላችንም ሐሣባችንን ባንድነት አስተባብረን ለትምሕርት ሥራ መጣጣር ይገባናል ።

የትምሕርት ቤት ማለትም የቋንቋ ብቻ አይደለም ። ደግሞ የእጅ ሥራ ጥበብና ብልሃት ተማሪ ቤቶች በያለበት ማቆም በእጅግ የሚያስፈልገን ነው ።

የሃገራችን ልጆች የውጭ አገር ቋንቋ እየተማሩ ሲሠለጥኑ ደግሞ እንደዚሁ የብልሃት ሥራ ሁሉ የብረት የእንጨትም የሌላ የሌላም ሥራ ሕንፃውንና ጌጡን እየተማሩ እራስ በመቻል መንግሥታችን አገልጋዮች ጥቅምን አትራፊዎች በውቀታቸው ምበደስታ ነዋሪዎች ለወገናቸው ጠቃሚዎች ሆነው ይገኛሉ።

አሁንም እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ ሀብትና ልማት ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክና ለልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ረጅም ዕድሜ ሰጥቶልን ምኞታችንን ሁሉ እንዲያስፈጽመን ስል ሙሉ ተስፋ አደርጋለሁ ።

ኢትዮጵያ ለዘላለም እንደከበረች ትኑር ።

ቀጥሎም ሴሙ ዋዲዕ ዜካ በፈረንሳዊ ስለ ትምህርት ቤት ያማረ ንግግር ተናገሩና ተጨበጨበ ።

ወዲያው ልጆቹ የኢትዮጵያን መዝሙር ዘመሩናበትምህርት የበለጡ የበለጡት ተሸለሙ ።

ላገር መዝሙር ።

አገራችን ጥሩ ወንዛችን
ኢትዮጵያ እንልሻለን
መመኪያችን ውድ እናታችን
ከልባችን እንወድሻለን
አርበኞችሽ አባቶቻችን
እንዳታጪ ነጻነትሺን
ጠላት ታግለው ብዙን ዘመን
አስከበሩት ምስጉን ስምሽን
አገራችን ለም ምድራችን
ድምቅ ጌጣችን ውበታችን
እያስተዋልንሽ በዓይኖቻችን
እጅግ ይበዛልናል ደስታችን
ወደአምላክሽ ዘርጊ እጆችሽን
ለሚሰማልሽ ልመናሽን
በክፉ ዓይን የሚአዩሽን
ይጣልልሽ ጠላቶችሽን

ከበቀለ ሀብተ ሚካኤል

ከሽልማቱ በኋላ ክቡር ሙሴ ጀራርድ የቤልጅክ ሚኒስቴር ትምህርትን የሚያነቃቃ ንግግር ተናገሩና ተጨበጨበ ።

ወዲያውም ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የሚከተለውን ቃል ተናገሩና ከግቢ እስከ ውጭ እያስተጋባ ሶስት ጊዜ ተጨበጨበ ።

ክቡራን ሚኒስትሮችና መኳንንት ።

የኢትዮጵያ ታላቅነትና የሥራዋም ታሪክ ሁሉ ምንም በብዙ አዋቂዎች መጽሐፍ ሁሉ ተጽፎ ቢገኝ ይህንኑ ያለፈውን ታሪኳን እየመላለስን መናገራችን በቀድሞ ዘመን ባገር ውስጥ ተነስቶ የነበረው ሁከት ትንፋሹዋን ወደ ኋላ እየሳበ ስለ አስቀረባት ነበር አሁን ግን ልጆቹዋን በማስተማር ድምጡዋ እየበረታ ትንፋሹዋም በደህና እየተመላለሰ ስለ ሐዲ ታሪኳ በሥራ ለመገለጽና የብርሃኑዋ ጭላንጭል ለመታየት ጀመረ ።

አሁንም ዛሬ ወደዚህ እንድትሰበሰቡ የጠራናችሁ ይህ የኢትዮጵያ ብርሃን የሚገለጥበት ጊዜው መቅረቡን እንድትከተሉትና በየዕለቱ የሚሠራውን እያሰባችሁ የደስታችን ተካፋዮች እንድትሆኑ ነው ። የኢትዮጵያም ብርሃን ለመገለጥ መቅረቡን ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነገር ያስረዳናል ።

የዳግማዊ ምኒልክ ትምሕርት ቤት መጀመሪያ በተከፈተበት ዘመን የተማሪዎቹ ቁጥር እጅግ ጥቂት ነበር ያውም ቢሆን ጃንሆይ በቤተ መንግሥታቸው ያሳደጉዋቸው የመኳንንቱ ልጆች በግድ እየታዘዙ ነበር ። አሁን ግን ከየከተማውም ከየ

ባላገሩም እውቀት እየናፈቃቸው ትምህርት እየፈለጉ በፈቃዳቸው እየመጡ በዳግማዊ ምኒልክ ትምሕርት ቤት የሚማሩ ልጆች ቁጥራቸው እስከ አራት መቶ ደርሷል ።

ገበሬ በርሻው ላይ ዘር ከዘራ በኋላ ዘሩ መብቀሉንና ማደጉን ብቻ ያያል እንጂ በየቀኑ ምን ያህል ማደጉን ምን ያህል ርዝመት መጨመሩን አያውቅም ። ነገር ግን እንደዚሁ ጥዋትና ማታ እርሻውን ሲጐበኘው ዘሩ ከቡቃያነት ወደ አበብ ከአበባ ወደ ፍሬ ደርሶ ያገኘዋል ። በዚያም ጊዜ የገበሬው ደስታ ይበዛል ።

እኛም እነዚህ በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት የሚማሩ ልጆች እንደዚሁ በየዓመቱ በትጋት እየተማሩ በእውቀት እያደጉ በቁጥር እየበዙ መሔዳቸውን ባየን ጊዜ ለሀገራቸው ለኢትዮጵያ ትልቅ ኩራት ይሆናሉ በማለት ልባችን ተመልቷል

ከነዚህም ልጆች መካከል በትጋት ተምረው በትምሕርት በልጠው የሚገኙትን ለዩንቤርስቴ ትምሕርት ወደ ውጭ አገር ለመስደድ ሙሉ ፈቃዳችን ነው ።

ወደ ፊት ለሚነሱት ልጆች ግን ከጥቂት ዘመናት በኋላ ትልቁን ትምሕርት የሚማሩበት ዩንቤርስቴ በዚሁ በሀገራችው በኢትዮጵያ እንዲቆምላቸው ተስፋ እናደርጋለን ።

ክቡር ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ ያገር ግዛት ሚኒስቴር ። ስለ ንግግራቸው በ፲፫ኛ ገጽ ተመልከት ።

እሁንም በዳግማዊ ምኒልክ ትምሕርት ቤት የሚያስተምሩት መምሕራኑና ረዳቶቻቸው ሥራቸውን በትጋት ስለ ሠሩ እናመሰግናቸዋለን ።

ደግሞ የኢትዮጵያ ልጆች በትምሕርትና በዕውቀት ማደጋቸውን ለማየትና ከኛ ጋራ ደስታ ለማድረግ ወደዚህ የመጡትን የዲፕሎማቲክ ሰዎች እናመሰግናለን ።

እንደዚሁ በኢትዮጵያ አውራጆች ሁሉ የትምሕርት ቤት እንዲቆም ምኞቴን እየገለጽሁ ለግርማዊት ንግሥት ረጅም እድሜ እንዲሰጥልን ኢትዮጵያም ለዘለዓለም እንድ ትኖርልን እግዚአብሔርን እየለመንሁ ጸዋዬን እነሳለሁ ።

ከዚህ በኋላ ሙዚቃ እየተመታና በሙዚቃ እየተመሩ ብዙ ሕፃናት የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ የሚመስል ልብስ የለበሱ የጅምናስቲክ ሰልፍ በሳዩ ጊዜ ከማማራቸውና ከቀለጣጠፉቸው የተነሣ ሰውን ሁሉ እጅግ እያስደነቁ ደስ አሰኙት ።

ቀጥሎም ባማርኛ በፈረንሳይ በእንግሊዝ በኢጣልያ ብዙ ጨዋታ ተጫወቱና በጣም ተጨበጨበ ።

ወዲያው የሻይ ግብዣ ተደረገ ። ግብዣውም ሲፈጸም ልዑል ወደቤታቸው ሔዱ ። ሁሉም ወደ እየቤቱ ሔደ ።



ክቡር አቶ በቀለ ሀብተ ሚካኤል የዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ሹም ስለ ትምህርቱም በትጋት የሚያስቡና የሚሠሩ ናቸው ። የገጠሙትንም መዝሙር በ፲፫ኛ፲ ገጽ ተመልከት ።

ክቡር ነጋድራስ መኰንን የንግድ ሚኒስቴር ስለ ንግግራቸው በ፪፻፵፱ገጽ ተመልከት

አ ዋ ጅ ።

ክቡር የንግድ ሚኒስትር ።

በ፲፪ ሐምሌ ፲፱፻፲፮ ዓመተ ምሕረት የወጣው ደምብ በሁለተኛው ክፍል ከሶስተኛው ዓመት ጀምሮ የአልኮሉን የአክሲዝ ቀረጥ አንድ ብር መወሰኑን አይተው ከዚህ በታች ያለውን ቆርጠዋል ።

አንደኛ ክፍል ከነሐሴ ፱ ቀን ፲፱፻፳ ዓመተ ምሕረት ጀምሮ የሚመጣው አልኮል በያንዳንዱ ሊትር አንድ ብር ቀረጥ ይከፈልበታል ።

ተጻፈ አዲስ አበባ ነሐሴ ፩ ቀን ፲፱፻፳ ዓመተ ምሕረት

የንግድ ሚኒስትር ነጋድራስ መኰንን ።

DECRET

SON EXCELLENCE LE MINISTRE DU COMMERCE

Considérant que l'article 2 de l'édit du 19 Juillet 1924 fixe le taux des aeeises snr l'alool à un thaler à partir de la troisiéme annèe ;

Arrête :

Article unique.- Qu'à partir du 15 Août 1928 les alcool importés seront soumis à une taxe de thaler un par litre.

Fait à Addis-Abeba, le 7 Août 1928.

LE MINISTRE DU COMMERCE.

የመርከብ አደጋ ።

ዳንትረካስቶ D'Entrecastaux የሚባል የሻርዠር ሬውኒ charguers réunis መርከብ ባውሮፓ ቁጥር በሰኔ ፳፮ቀን ጂቡቲ ደርሶ ወደ ሺን ሄደ ።

የእሳት አደጋ ስላገኘው በስምንተኛው ቀን ጅቡቲ ተመልሶ ገባ ነገር ግን እሳቱ እቃ ከነበረበት ክል ውስጥ ነበረና የተነሳው በመቃጠል ምክንያት የሚንጣጣ ድምጥ ሰምተው ምንድነው ብለው ክሉን ቢከፍቱት የታፈነው ጭስና ነበልባል ሁለተኛውን ከማንዳንና ሁለት ሠራተኞች ማርከ አስቀራቸው አንዱን ሰው እዚያ ሞተና ሬሳው ወዲያው ተገኘ አንደኛው ቆስሎ ነበረና ጂቡቲ ሆሲፒታል በሶስተኛ ቀኑ አረፈ የሁለተኛው ከማንዳ ሬሳ ግን አሁን በቅርብ ቀን እሳቱ ከተዳፈነ በኋላ ቴንንሽ አጥንት ተለቅሞ ተቀበረ ። መርከቡም እስካሁን የተቃጠለውን ከመሬት እያራገፈ ደህና ደህናውን ወደ ሺን ለማዝለቅ ይሰራል ። የተቃጠለው ዕቃ ወደ ፲፫ ሚልዮን ይገመታል ፡ ከዕቃውም የተቃጠለው ስድስት አውሮፕላን ብዙ ካሚዎን አቶሞቢል ልዩ ዓይነት ብረታ ብረት ይልቁንም ልዩ ዓይነት መሣሪያና (መትረዬስና ጠመንጃ) ጥይት ነው የተሸፈነበትን ጥይት ብቻ ለብልቦት የውስጡን አላገኘውም እንደምን እንደ ሆነ ያስገርማል ደህና ደህናውን እየመለሱ ወዳውሮፓ ይመልሱታል።

ያዲስ አበባ ገባያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፩ ብር ተሶስት ሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፫ ብር ተሩብ
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳ ብር ተኩል
የ ዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፬ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፰ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፰ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፰ ብር ተኩል
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፵፪ ብር
፡፡ ባለሰይጣን	፡፡	፻፵፩ ብር
፡፡ ባለ ድመት ።		፻፵፩ ብር
፡፡ ባለአህያ	።	፻፳፰ ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል	።	፻፴፫ ብር
ባለ አንበሳ	፡፡	፻፵፫ ብር
ሱካር	፩ ጁኒያ	፴፫ ብር
ቻይ	፩ ነጥር	፫ሩብ ከሁለት መ

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ ፲፫ ሳንቲም
አንድ ብር	ሊሬ ፰ ከ፳ ሳንቲም
በአንድ ጊኒ	፲ ብር ፮ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፬ ብር

ዓለም ሱቅ ፲፺ዓይነት የተሰማ እሺቴ ሙዚቃሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንፆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

COGNAC SA.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል።



ዝኒት የእጅ ሰዓት

በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል።

ሩ ግ ቢ

RUGBY

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞች ና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፥ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር የ.ገ[illegible]



ኦቤርላንድ



ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውኻ ኦቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባ ኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኚቶና ባለባተሪ ነው ካምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል «ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው

ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

ማስታወቂያ

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲	ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮፓ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር	፰	ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
የዓለም ጅኦግራፊ በአማሪኛ ደኅና ጥራዝ ዋጋው	፮	ብር
» » » መናኛ ጥራዝ ዋጋው	፫	ብር
ደግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፫	ብር
ኅሐ ጽባሕ	፫	ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫	ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫	ብር
የሕይወት ታሪክ	፪	ብር ተኩል
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪	ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪	ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትርሜጓው	፪	ብር
ደቁጥር ትምርት	፩	ብር
ያማሪኛ ሰዋስው	፩	ብር
ወዳጄ ልቤ	፩	ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን		አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ		አላድ
አጭር የዓለም ታሪክ		አላድ
ያማሪኛ ፊደል		ሩብ
አሳብና ምኞት		ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት		ሩብ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፪	መ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር	፪	መ
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ		ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶ ግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ		ሩብ

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም ፤ የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ፤ የልብ ፤ የደረት ፤ የጉበት ፤ የኩላሊት ፤ የጅማት የጨብጥ፤ የቂጥኝና የቋቁቻ፤ የሚያዋልድ፤ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያከማል

አደጋዝማች ደስታ ዳምጠው ሱቅ ነው ።

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ባርባሬሶ

ኮ ኛ ክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ያሰናኟነት ፈቃድ የተቀበለ ።

ተቃላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በካፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በካፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው ።

ጉድ ደር ግዙ





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው ። በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ፤ ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አራተኛ ዓመት፤ ቍጥር ፴፫
4 me ANNÉE № 33

ሐሙስ ነሐሴ ፮ ቀን ፲፱፻፳ ዓ ም።
JEUDI 12 AOUT 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት
Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d'Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲረክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

አንድ የተሰወረ ፍርድ ።

ከመ ቅጽበተ ዓይን ፍርድ ተሰወረ።አስቀድሞውንም አንድ አንድ ጊዜ ይሰወር ነበረ ይልቁንም ከዚህ ዓለም ሰዎች ዘንድ ይሸሻል በዚህና በዚያ ይጕስሙታል እወህኒም ያገቡታል በማጥንም ይቆልፉታል ስለዚህ አጥብቆ ይሸሻል እንግዴህ መልካሙ ትክክለኛው ፍርድ ሸሽቶ በገጠር ነፍስ በሌለው ፍጥረት ውስጥ ተሸሽጎ ይኖራል ስለሆነ ምንም ርቆ ቢኖር ሰዎቹ ብልሆች ናቸውና ፈልገው አገኙትና ይዘውም በእሥር ቤት አኖሩት እንደፈቀዳቸውም ይሰሩበት ጀመር። ነገር ግን ይህ ትክክለኛው ፍርድ ከሰዎች እጅ አመለጠና ጸብ ጸጥ ወደአለበት አገር ኰብሎ ይኖራል ከሕዝቡም ሁሉ ያለ ፍርድ መኖር አይቻልምና ስለጠፋባቸው ሐፍረት ለበሱ በዚህ ጊዜ እንደየጨዋ ልጅ የሆነ አርበኛ ይኸንኑ ፍርድ ይዞ ለመምጣት ብዙ ወታደሮች ሰበሰበና ፈክሮ በውነት አምጥቼ ያላሰርሁት እንደሆነ ሰውም አይደለሁ ብሎ ይኸንንም መሐላ አደረገ ለማድረግ ከፊቱ ያገኘውን ሁሉ እየገፈተረ አገኘዋለሁ ሲል ደምም እስከ ማፍሰስ ደረሰ ደግሞ አንድ ከበርቴ የሆነ ሰው ፍርድን አገኘዋለሁ ሲል ብዙ ንዋይና ጌጥ ወርቅ ሁሉ በብዙ ግመል ጭኖ ተነሳ እንደዚሁም የጦር መሣሪያ ጠመንጃና ወርቅ ፍርድን ለማግኘት ይኸው ገና እስከ ዛሬ አላገኙትም ይፈልጉታል።ደግሞ አንድ ድሀ ሰው ልብሱ የቆሸሸ በገምባሩም ላይ ብዙ ችግር ያለበት መስሎ የሚታይ እንዲህ አለ ወርቅም ወርቅ ነው መሳሪያም መሳሪያ ነው ነገር ግን እኛ የተቸገርነው ፍርድን ለማግኘት ነውና አጥብቀን እንፈልገው ይህ ሰው በውነት ጨርሶ የደኸየ ነበረ እርሱም አንዲት ጠርሙስ አገኘ በዚያ በጠርሙስ ውስጥ ያንድ አባትና እናት የሌለው ልጅ እንባ ሞላበት ደግሞ የድኻነትን ሥቃይ እህታ ጨመረበት ደግሞም መራራውን የሠራተኛ ላብ ጨመረበት አሁንም የማያገኘውን ምኞት ቀላቀለበት እነዚህንም ሁሉ አንድ ላይ ቀመመና በጠርሙሱ ውስጥ ደፍኖባቸው ጠርሙሱን በጉያው አድርጎ ያን የጠፋውን የተሰወረውን እውነተኛ ፍርድ ለመፈለግ ሄደ እንዲሁም መንገዱን ጀመረ ብዙ ከተማም አለፈ ብዙውንም አገር አቋረጠ ይህንንም ሁሉ መንገድ ሲሄድ እውነተኛው ፍርድ ሆይ ወዴት ነህ እያለ ይጮህ ነበረ ከዚህ በኋላ ብዙ ደከመውና ባንድ ተራራ ላይ ወጥቶ በትልቅ ድንጋይ ላይ ተቀምጦ ያስብ ጀመር ከዚያውም ተቀምጦ እዬ በከንቱ ነው የምለፋው ከቶ አላገኘውም እርሱ አጥብቆ ድሀነትን ይሸሻል ። ይህንንም ብሎ ተናዶ በብብቱ የያዘውን ጠርሙስ አውጥቶ እተቀመጠበት ድንጋይ ላይ ሰበረው ። ወዲያውም እየጮኸ እንዲህ አለ ድኻነት እንባ መራራ ላብ ምኞት ጭንቀት የማይረቡ ናቸው ። ፍርድ ድኻነትን አይወድም ።

ጠርሙሱም በተሰበረ ጊዜ ድንገት የሰማይ ነጐድጓድ ሲያጉረመርም ተሰማ በዚያን ጊዜ ከጠርሙሱ ውሰጥ የፈሰሱት እንባ መራራ ላብ ድኻነት ጭንቀት የማይገኘውም ምኞት ሁሉም በዚያ በድሀው ሰው ፊት ጢስ ሆነው እንደደመና ቆሙ በደመናውም ውስጥ አንድ ትልቅ ረዢም ማለት እንደ ጐልያድ የረዘመ ሰው ቆመ ያም ረጋርም ሰው ይህን ድሀ ሰው አይዞህ አይዞህ አትፍራ ውጣ እኔ አንድ ጨዋሂ ማለት ተመራሪ ነኝ የተወለድኩት ከነዚህ ከጠርሙሱ ውስጥ ከፈሰሱት መኻከል ነው ። ከዓለምም የተሰወረውን እውነተኛ ፍርድ ያለበትን አመለክትሃለሁ ። በዚያም ጊዜ ኃይለኛ ዓውሎ ነፋስ ተነሳ ምድሪቱም ተናወጸች ወዲያው ያ ድኃ ሰው ዓይኑን ወደ ላይ አንስቶ ቢመለከት በደመና ውስጥ የተፈለገው እውነተኛ ፍርድ ኵስስ ብሎ ሰይፍና ሚዛን ሳይዝ ማናቸውንም በንቀት ዓይን ሲመለከት አገኘው በዚያም ጊዜ ያ ትልቅ ረዢም ሰው ፍርድን እንዲህ ሲል ለመነው የተወደድህ እውነተኛው ፍርድ ሆይ ከኔ

ዘንድ ና የኔ ድምጽ ሰይፍና ሚዛን ይሆንሃል እኔም አንድ ከሦራተኛ ላብ ከጭንቀት ከድኅነት መካከል የተወለድኩ ነኝ ነገር ግን ከተቀመጠበት የማይንቀሳቀሰውና ያዘነው ፍርድ ያን ደኃ ሰው ተመልክቶ እንዲህ አለው ። ወዳጄ ሆይ ገና ነው ገና ትንሽ ነህ ሂድና እንቦችን ድኅነቶችን አጠራቅም እንደው ቅያኖስ ትልቅ ይሆኑ ዘንድ ደግሞም እንደ ኃይለኛ ጉርፍ ያጉረመርሙ ዘንድ በዚያን ጊዜ ሰይፌንና ሚዛኔን ይዤ ወጥቼ እድንሃለሁ ። ይህንን ከተናገረ በኋላ ደመናው በዛና ያም ፍርድ ደግሞ ተሰወረ ከዚያ ቀን ጀምሮ ያ አርበኛ ፍርድን ከደም ውስጥ እንደፈለገ ነው ። ቃላቁም ከበርቴ በብርና በወርቁ ፍርድን እንደ ፈለገ ነው ።

ድኃውም በጭንቀት ውስጥ ይኖራል ። ይኸውም በእንባው ጨኸቱን ለማበርከትና ለማሳደግ ነው ። በዚሁ አደራረግ የተሰወረውን ፍርድ ለመጥራት ያስባል ።

እኔም ይህን ከሰማሁ በኋላ ክቡር ቄስ በዚህ ሳምንት ብዙ ነገር በሆዳቸው እንዳለ አወቅሁ ።

ካፒቴን ባቢኪያን ።

ባራተኛው ዓመት በ፴፮ ቁጥር ብርሃንና ሰላም ።

(መ አ) መምሬ አስፋው ለጻፉት ቃል የትሕትና መልስ።

ክቡር መምሩ ሆይ የመቃብር ዋጋ አለ ብለው ሲጽፉ መልስ መጻፍ አያስፈልገኝም ነበር ነገር ግን ምንም ጽሕፈትዎ ባይመስልና ባይሆንልዎ አሳብዎ የኔን ጽሕፈት ለመንቀፍ ነውና የመቃብር ዋጋ አለ የለም እያሉ ቃልዎ ስለ ተለዋወጠና የጻፉትን ቃል መልሰው እየነቀፉ ስለጻፉ በቀጥታ ልመልስልዎ ግድ ሆነብኝ ።

ወይ መርምሮ አለማስተዋል ሳያስቡ መኖር እንዴት ያገለግላል መጀመሪ የመቃብር ዋጋ ሁለት ቁና ካንድ እፍኝ ስንዴ ነው ብለው የመቃብር ዋጋ መኖሩን መስክረዋል ሁለተኛ አባታችን አብርሃም የመቃብር ቦታ ገዝቶ መቀበሩን አምነው ጽፈዋል ሶስተኛ የኢትዮጵያ የካህናቱ ሹም የመቃብር ቦታ ወስኖ ከኢትዮጵያ ልጆች አምስት አምስት ብር ይቀበልና ለተማሪ ቤት ማቆሚያ ይሁን ብለው አሣርገዋል ።

መምሩ እንግዲህ የመቃብር ዋጋ መኖሩን ተረድተውት ፈርመው አሣርገዋልና አንጣላም ነገር ግን ከጻፏቸው ቃሎች ውስጥ አልፈው አልፈው ወዲያና ወዲህ እያሉ የልጆች ጨዋታ መስለው የሚታዩ ሞልተዋል ። አምስቱ ብር ለተማሪ ቤት መርጃ ይሁን ያሉት መልካም ነበር ነገር ግን መጀመሪያ የመቃብሩ ቦታ ዙሯውን እንደሚያምር ጥሩ ሆኖ ታጥሮ አትክልት ከተደረገበት በኋላ ገንዘብ ቢተርፍ ለሥራው አላፊ ሆኖ የተሾመው ሹም ገንዘብ መትረፉን ለመንግሥት አስታውቆ የተረፈውን ገንዘብ ለተማሪ ቤት መርጃ ወይም ሌላ ሥራ ቢያሲዙት ይሆናል እንጂ መጀመሪያ የመቃብሩ ቦታ እንደሚገባው ሆኖ ሣይሰራ የመቃብሩን ዋጋ ለተማሪ ቤት ማቆሚያ ለማድረግ የሚሆን አይመስለኝም ።

ንግግርዎ ብዙ ጊዜ ተለዋውጦ አስቸግሯል (ማለት) ዋጋ የሌለው ሰው ሳይቀበር መቅረቱ ነው ይላሉ ምነው ባራተኛው ዓመት በ፴፮ ቁጥር ብርሃንና ሰላም ስለመቃብር ጽዳት በጻፍሁት ቃል ውስጥ ከባላገር ወደ ከተማ የመጣ ባይተዋር ድኃ ፡ ወይም ባገር ቤት ውስጥ ተቀምጦ የሚመገበውና የሚለብሰው ቸግሮት የሞተ እንደሆነ እውነት ችግረኛ መሆኑ ተመርምሮ ከታወቀ በኋላ ምሕረት ማድረግ ነው ። ምሕረት ለማድረግ የማይቻል ቢሆን ከዚያው ከገቢው ገንዘብ ወጭ አድርጎ ለድኃው ሰው መቃብር ገቢ ቢያደርጉለት መልካም ነው ። ይኸም ሲሆን ሬሳውን ቀብሮ ነው እንጂ ሬሳው ሳይቀበር ድኃ መሆኑንና አለመሆኑን ለመመርመር አይሆንም ብዬ ለድሆቹ የሚሆን ቃል ጽፌ ነበር ። ይኸንኑም የብርሃንና ሰላም ወዳጆች ተመልክተው ተረድተውታል ፡ መምሩ ግን በድሆቹ አመካኝተውና አስመስለው ሲናገሩ ዋጋ የሌለው ሰው ሳይቀበር መቅረቱ ነው ብለው ያወራሉ ። ይህ ባለመመልከት የተገኘ ጉዳት ነው የጻፏቸውን ተረቶች ግሩም ድንቅ ሲሉ ሳይመለከቱት የቀሩ ይመስለኛል ።

የመቃብር ዋጋ መኖሩን አውቀው ይከፈል ብለው ጻፉና መልሰው ደግሞ እውንስ በገዛ አገሩ ከተለመደው ዋጋ አብልጦ ሊሰጥ ነውን ብለው ተቆጡ ፡ ኋላ ከማን አገር ሄዶ ይቀበር ዋጋውንስ ለማን ይከፈል? ። ያ ሁለት ቁና ካንድ እፍኝ ስንዴ በሁኑ ሸመታ ጊዜ ቢታሰብ በግምት ሁለት ብር ታላድ ሳይሆን አይቀርም ።

የጻፉት ቃል ሁሉ ሌሊት ሲያዩት አድረው ጧት እንደ ሚጠፋ ሕልም ሆኖብዎታል ። አብርሃም ርስት እንዲሆንልኝ ብሎ አንድ ጊዜ ገዝቶ ርስት አድርጎ የሞቱበትን ሰዎች ሁሉ ሲቀብር ኖረ እንጂ በግድ አምጣ አላሉትም ብለው ያቤቱታ ቃል የሚመስል ነገር ጽፈዋል አሁንም ቢሆን አንድ ጊዜ ገዝቼ ርስት ይሁንልኝ ብሎ ለዘመዶቹ ሁሉ የሚገዛ ሰው ቢገኝ አለመከልከሉን አረጋግጥልዎታለሁ ቢፈልጉ መግዛት ነው ።

አብርሃም መልካም አድርጓል አሁንስ ቢሆን ሰው ለትዳሩ የሚበቃውን ያህል መሬት አስቦ አንድ ጊዜ ከገዛ ያንኑ ያርሳል ይቆፍራል እንጂ ሁለተኛ መግዛት ምን ያስፈልገዋል ። ደግሞስ የመሬቱን ዋጋ ሳይታዘዝ አውቆ ከሰጠ ማን አምጣ ይለዋል አይባልም ። መምሩ መሬት አይሸጥ አይገዛ በብላሽ ይቅር ብለው አዋጅ ለማውጣት ያሰቡ መስሎ ይታያል ከዚህ በፊት መሬት ዋጋ ሳይከፈልበት በብላሽ ሲገኝ አላየንም የኢትዮጵያ መንግሥት በቸርነቱ መጀመሪ መሬት ቢሰጥ በየመቱ የሚከፍለው ግብር የመሬቱ ዋጋ መሆኑን አላወቁም ይሆን? ።

ደግሞ አለፍ ብለው የሞተ ሰው ሳይቀበር ቢውል ቢያድር ወርዶ ነግዶ አርሶ ሠርቶ ለመቃብር ዋጋ አያደርስም ብለው ከጥልቅ አሳብዎ የወጣውን ቃል ጽፈውትበጉልሕ ይታያል ምነው መምሩንግግርዎ ያዋቂ ይመስላል ሰው ሞቶ ነፍሱ ከሥጋው ከተለየች በኋላ የሚያርስና የሚነግድ በድን ወዴት አይተው ይሆን?

ይልቁንም እንደ ተጻፈው ያለውን አለ የሌለውን የለም በማለት ፈንታ አንድ ጊዜ የመቃብር ዋጋ አለ አንድ ጊዜየለም እያሉ ሲያመነቱ ተሰምተዋል ላለፈው አስበው ያመረቱትን የዕውቀት ምርትዎን ስንዴውን ከእንክርዳድ ባለመለየት ሲወቁ ተገኙና ፈሰሰብዎ ስለዚህ በዚህ ነገር ለፍተው እንዳለፉ እንዳ

ይሆኑ ለወደፊቱ መርምረው ይመልከቱ መምሩ ምን ይሆናልና የፈሰሰ አልታፈሰ ነውና ወደፊት የዕውቀት ስንዴዎን ለይተው ይወቁ ስል እኔ የብርሃንና ሰላም ተማሪ ምክሬን አበረክትዎታለሁ ።

ደምሴ ወልደ ገብርኤል ።

የፍርድ ጥያቄ ።

አንድ ቀን አደባባይ ተቀምጬ ያቶ አምኘህ ልጅ አቶ አወቀና አቶ እንደ ልቡ ባንዲት ጊደር ስለ ተጣሉ ተከሰው ወደ ዳኛ መጡ ነገራቸውም ከዚህ ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው ያቶ አምኘህ ልጅ አቶ አወቀ አቶ እንደልቡን ከሶ አባቴ አንድ ጊደር አውሶህ ነበር የተዋስከውን ሳትመልስ በማህል አባቴ ሞተ አሁን እኔ ልጁ ወራሽ ነኝና ከባቴ የተዋስካትን ጊደር መልስልኝ ቢለው አቶ እንደልቡ አባትህ ጊደሯን የሰጠኝ በስጦታ ነው እንጂ በውሰት አይደለም የውሰት ሆኖ ቢሆን አባትህ ሳይሞት ያስመልሰኝ ነበር ግን ይህቺን ጊደር እወዳታለሁ መልስልኝ ትለኝ እንደሆን በሱዋ ምትክ ዋናዋን ላምህን ስጠኝና አባትህ የሰጠኝን ጊደር ልመልስህ አለው በዚህ ማህል ዳኛው ነገሩን ለማጥራት ብሎ ይህቺን ጊደር በፊት አቶ እንደ ልቡ ሲወስዳት በውሰት ወይም በስጦታ መሆኑን ተነጣጡሩ ስላላቸው ያቶ አምኘህ ልጅ አቶ አወቀ ይህቺን ጊደር ከባቴ ስትወስድ በውሰት እንደሆነ ማር እሰጥ ቢለው አቶ እንደልቡ አባትህ በስጦታ ቢሰጠኝ እንጂ በውሰት አለወሰድኳት አገባ ብሎ ምስክር ፈርማቸው በነገረ ተፈጣጥመው ፈርማቸው መጥቶ ከዳኛው ላይ ቢነበብ አቶ እንደልቡ ጊደሯን የወሰዳት በውሰት መሆኑን መሰከረ ከዚህ በኋላ ያቶ አምኘህ ልጅ አቶ አወቀ በውሰት አልወሰድኩም ብለህ ፈርማህ ከመሰከረብህ ውርርዱንም አንሳ እኔም ያባቴ ወራሽ ልጁ ነኝና አባቴ ያዋሰህን ጊደር መልስልኝ ቢለው አቶ እንደልቡ ውርርድህን አንሳ ነገርህን አትርሳነውናጊደሯን የወሰድኳት በስጦታ ነው በውሰት አይደለም ባልኩበት ውርርዴን አነሳሁ ግን ይህቺን ጊደር አባትህ በውሰትም ቢሰጠኝ ሳይቀበለኝ ከሞተ አንተም ወራሽ ልጁ ብትሆን አባትህ ያዋሰኝን መልስ አትለኝም በይሆን ጊደሯ በኔ እጅ ሆና ወተቷን አንተም እኔም እንጠጣለን ወይንም ጊደሯን ትወዳት እንደሆነ በሷ ምትክ ዋናዋን ላምህን አውሰኸኝ ጊደሯን ትወስዳለህ እንጂ አባትህ ያዋሰኝን ጊደር ሳይቀበለኝ ከሞተ በጭራሽ አያስመልሰኝም አለው ያቶ አምኘህ ልጅ አቶ አወቀ የበላችው ያገሳታል ደግሞ ደግሞ ያጕርሳታል እንደሚሉ ሁሉ አባቴ ያዋሰህን ጊደር አልመልስም ስትለኝ አሁን ደግሞ ዋናዋን ላምህን አውሰኝ ትለኛለህ? በፊት በስጦታ ነው እንጂ በውሰት አልወሰድኩምብለህ ውርርድ ተክዬ በውሰት መውሰድህን ፈርማህ መስክሮብህ ውርርድህን ታነሳህ እኔም ላባቴ ወራሽ ልጁ ከሆንሁ አባቴ ያዋሰህን ጊደር መልስ እንዲሉ ማር እሰጥ ቢለው አቶ እንደልቡ ያዋሰኝ አባትህ ሳይቀበለኝ ከሞተ አንተም ወራሽ ልጅ ብትሆን ጊደሯን ብትወዳት ዋናዋን ላምህን አውስና ውሰድ ያለዚያ ጊደሯ በኔው እጅ ሆና ወተቷን አብራችሁ ጠጡ እንዲሉ አንተ ምንትሰጥ እኔ እምባላይ ፈረስ እሰጥ ብሎ ውድር ስለ ወደረ ይህ ትልቅ ነገር ስለሆነ ። ብቻዬን የምፈርደው አይደለም ስለዚህ ፍርዱ እስኪፈረድ ድረስ ጊደሯ ባቶ እንደልቡ እጅ እንደሆነች ወተቷን አብራችሁ ጠጡ ብሎ ፍርዱ እንዲቆይ አድርጎ አቃጠራቸው ያቶ አምኘህ ልጅ አቶ አወቀም ተናዶ ጭቅጭቅ ያማረው ገንዘቡን ያውሳል ከብቱን ለጢስ ያለው ሲጋራ ይጠጣል ። እግዚአብሔር የተቆጣው ደባል ያስቀምጣል ። በገዛ ዳቦዬ ልብልቡን አጣሁት የተባለው በኔ ደረሰ ብሎ እየተከከዘ ሲሄድ አሳዘነኝና እኔም ፍርዱን ለማየት ስጓጓ ሳይፈረድ በመቆየቱ እያዘንኩ ወደቤቴ ስመለስ ድንገት አቶ ማስተዋል የሚባል ወዳጄ እመንገድ አገኘኝና እንዴት ዋልክ ምነው ተክዝሃል አለኝ እኔም ሰላምታዬን ከሰጠሁት በኋላ ያዘንኩንበትን ነገር ከስር ጀምሬ አጫወትኩትና የዚህን ፍርድ ለማየት ጓጕቼ ፍርዱ ሳይፈረድ በመቆየቱ በጣም አዘንኩ ብለው ማዘንህ ለምንድነው ይልቁንስ ነገሩን ወደ ብርሃን ብታስታውቅ የብርሃን ወዳጆች ፍርዱን በሰላም አሰናድተው ያስታውቁህ የለምን ? ስላለኝ በቶሎ ወደ ቤቴ ሄጄ ይህን ለመጻፍ ጀመርኩ ።

ክቡራን የብርሃንና ሰላም ወዳጆች እኔ እንደራሴ ቀኙ ያቶ አወቀ ይመስለኛል ደግሞ በፊት አባቱ ያዋሰውን ጊደርለ መመለስ እምቢ ሲል ሁለተኛ ዋናዋን ላም ለማዋስ ይችላልን ? የዚህን ሁሉ ፍርድ እናንተ አታጡትምና በብርሃን አሰናድታችሁ በሰላም እንድታስታውቁኝ በትህትና እለምናችኋለሁ ።

ታናሽ ወንድማችሁ ኃ ጊ ወልዳ ማኔል ።

ኵሉ ዘይገብራ ለጽድቅ ጻድቅ ውእቱ ።

ክቡር ዳጃዝማች ብሩ በሚገዙት አገር በሲዳሞና በቦረና አውራጃ ከተሾሙ እስካሁን የቀድሞ ልምድ የሚባል ከባድ ሸክም በሕዝቡ ላይ እንደበዛበት አውቀው እነሆ ለማቅለል ይተጋሉና ይህ የርኅራኄ ሥራቸው በመላዋ ኢትዮጵያ እንዲደርስ ከብዙ በጥቂቱ በየክፍሉ ያየሁትን ሥራቸውንና የሰማሁትን መልካም ምኞታቸውን ለመጻፍ እጋርምራለሁ ። ፩ኛ ዋና ጉዳት የፍርድ ነገር ነውና ለነገ ይደር ደጅ ይጥና ይጕላላ ሐብታምና ድሃ አይበል ሁላቸው ትክክል ኢትዮጵያውያን ናቸውና ሹማምንት እንዳያጕላሏቸው አቅርቡን ሲሉ ድሆች ገንዘባቸውን እንዳይጨርሱ ለችሎት መቅረቢያ ጉርድ አስደርገው ሳይውል ሳያድር ሳይርቅ በቅርቡ ደጅ ሳይጠና በተሰጠው ቀን ቀርቦ ነገሩ ተቆርጦለት ወደሥራው ይሄዳል ያሁን ሕዝብ ያልደከመበትን ገንዘብ ከሚሰጡት ፍርድ አግኝቶ ሠርቶ ቢበላ ይወዳል ቢረታም ቢረታም በቶሎ ከተቆረጠለት ስለማግኘቱ ይቆጥረዋል ከ፯ቱ ቀን ሰኞ ለወታደር ረቡዕ ለገባሮች ዓርብ ለእሥረኞች ደምብ ሰጥተው በችሎት ተቀምጠው ሥርዓት ያያሉ ። ማክሰኞ ሐሙስ ቅዳሚት የወምበሮች ችሎት ስለሆነ በተለየ አልፍኝ አዳራሽ ሁነው ድሃ ባለጸጋ ሳይሉ እንደመጣ ያላንድ እጅ መንሻ ባለጉዳይ ገብቶ ተናግሮ ይሄዳል ይህንንም ነገር በክቡር ራስ ካሣና በክቡር ደጃዝማች እምሩ ዘንድ እንዳመጣጡ በተራ እየተጻፈ ሀብታምና ድሃ ሳይለይ ገብቶ ተናግ

ሮ ይሄዳል ማለትን እሰማ ነበረ የሰማሁትን ባይኔ ለማየት ላበቃኝ አምላክ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ፪ኛ ገባሮች ያመት ግብራቸውን ከሰጡ በኋላ ከ፫ ቀን ፫ ቀን ለመልከኛ ሥራ ባ፭ ባ፭ቀን እንጨት ሰበሩ ፩ ቀን ላገረ ገዢው ሥራ ባለ ቀላዶችም ማር ከዳውላ ለመልከኛ ከሰጡ በኋላ በቀላዳቸው ውስጥ ያሉትን ጢሰኞች ይዘው ከ፫ቱ ቀን ፩ ቀን ላገረ ገዢው ይሠሩ ነበር አሁን ግን ክቡር ደጃዝማች ብሩ ገባሮች ፫ ቀን ለመልከኛ ከሠሩ ባ፭ ባ፭ ቀን እንጨት ከሰበሩ ባለቀላዶችም ማር ከዳውላ ለመልከኛ ከሰጡ ደግሞ ለኔ በ፫ በ፫ ቀን ፩፩ ቀን ከሠሩ ለራሳቸው መቼ ሠርተው ሊረዱና ጥቅም ሊያገኙ ነው ምንም ሥራቸው የሚጠቅመኝ ቢሆን ከሕዝቡ ይልቅ እራሴን አልወድምና ለኔ የሚሠሩት ይቅርብኝ ብለው በነጋሪት አዋጅ ስላደረጉ የሕዝቡ ደስታ ከመጠን ያለፈ ሁኑዋል ።

፫ተኛ አገራችን ኢትዮጵያን በሚያስፈልጋት ነገር የሚረዳ ያዲሱ ሥልጣኔ ትምሕርት እንደሆነ አውቀው በግዛታቸው ውስጥ ያሉትን መኳንንትና ወታደሮች ነጋዴዎችንና ባላገሮችን ለትምሕርት የደረሱ ሕፃናት ያሏችሁ አስቀድመው ያገራችንን ንባብና ጽፈት አውቀው ቀጥሎም የውጭ አገር ቋንቋ ተምረው ወደከፍተኛው ደረጃ እንዲደርሱ አሁን በቅርብ መምሕራኑ ይመጣሉና በትጋት እንድታስቡበት አስታውቃችኋለሁ ስላሏቸው ሕዝቡ በብዙ ደስ ብሏቸዋል ።

፬ተኛ ፊታውራሪ ጥላሁን የሚባል የጦር እንደራሴያቸው ከወለጋ ሲመጣ ሲዳሞ ሲደርስ ሕዝቡን አሰልፎ ክቡር ደጃዝማች ብሩም ባሩድ ቤቶችንና የቤት ልጆችን ይዘው በማዕርግ ተቀምጠው ተቀብለው ሕዝቡ ብዙ ስለሆኑ የሰፈርቦታ ሰጥተዋቸው ቆይተው ሳሉ ጊዜው ክረምት ስለሆነ ክዝናምና ክብርድ የተነሣ የሕዝቡ ጉዳት ስለተሰማቸው የደጃዝማች ባልቻን አሽከሮች ሰብስበው እሊህ የኔ ሰዎች ላገሩ እንግዳ ናቸውና ቤት የሚሠሩበት የከተማ ቦታ በንድ ወገን ስጡኝ ብለው ቢያስታውቋቸው ሁሉም ባ፩ ቃል አንሰጥም ብለው መለሱ ገዢ ሁነው በግድ የሚያዙ ሲሆኑ የሕዝቡን ፈቃድ ሳይጥሱ እንዳላችሁ ይሁን ብለው መተዋቸው እጅግ ያስገርማል ለተሾመ ሁሉ ዋና ገንዘቡ ትዕግሥት ሊሆን ይገባል የገዢና የተገዢ መስማማት ለመንግሥት ትልቅ ጥቅም ነው ለሀገርም ክብር ነው እንደዚሁ ሁሉ አገረ ገዦዎች ሊታገሡና የርኅራኄ ሥራ በሕዝብ ላይ ሊሠሩ ይገባቸዋል ።

፭ተኛ ቀድሞ በታላቁ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ ዘመን የነበሩ አርበኞችና የጦር አለቆች ለጀግኖች ወታደሮቻቸው በየቀኑ ግብር እያበሉ እያጠጡ የሚያስፈልገውን የጦር መሳሪያ እየሸለሙ ደስ አሰኝተው ያነቃቁት እንደነበረ ተቀማጭ ገንዘብ እናኑር ሳይሉ ለጊዜው ከሚያስፈልጋቸው በቀር ባሁኑ ዘመን ያለገንዘብ የሚጠቅም የለም የሚል ሥጋዊ መንፈስ ባደረብን ጊዜ ክቡር ደጃዝማች ብሩ ላስቀምጥ ሱቅ ልሥራ ሳይሉ ለትምሕርት ቤትና ለሆስፒታል አድርጌ ሕዝቡን እረዳለሁ የዕለት ምግቤንም ሕዝቡን ይዤ እካፈላለሁ ብለው ገንዘባቸውን ከድኃው ጋራ ተካፍለው ይበላሉ ባገር ያሉ የቀድሞ ጀግኖችም የዘነጉትን ነገር አሁን ከክቡር ደጃዝማች ብሩ ዘንድ ስላገኙ እንግዳ ነገር እየመሰላቸው ለደስታቸው ምሳሌ አላገኙለትም ።

ይህን መልካም ሥራቸውን እኔ አሳጥሬ እንደጻፍኩት እንኳን ብቻ አይደለም ለአእምሮዬ እንደተሰማኝ በጥቂቱ አመለከትሁ እንጂ ደግሞም እውቀት ኑሮኝ ከሳቸው ጋራ ተጫውቼ ወይም ሥጋዊ ተዘምዶ ኑሮኝ አድልቼ እንዳይመስላችሁ አንባቢዎችን አስገነዝባለሁ የሀገሬ የኢትዮጵያ ፍቅር ስለቆረቆረኝ አሁንም ላሉ ወደፊትም ለሚነሱ አገረ ገዦዎች ሁሉ እንደዚህ የማያኅድላቸውን በጎ ሥራ ቢሠሩ ሕዝቡም ደክመው ከሚያገኙት ሥራ መንግሥት ይጠቀማል አገሩም ይለማልና የሕዝቡን ጉዳት እንዲያውቁ አገራቸውንም እንዲጠብቁ ለማሳሰብ ያህል ነው ።

መ ኃ

ስለ መሐለቅና ቤሳ ሽረፋ ።

መንግሥት በሚገባ ከደነገገው ሽረፋ አጉድለው ዛሬ ቸርቻሪዎች መሐለቁን አዲስና አሮጌ እየመረጡ ሽረፋውን ስለሚያጓድሉ ደግሞ ፴፪ የነበረውን ቤሳ ፳፬ ስላደረጉት ብዙ የብርሃንና ሰላም ጠያቂዎች ምክንያቱ ምን ይሆን እያሉ ሲጠይቁ እንሰማለን ። ይልቁንም የመሐለቅና የቤሳ ሽረፋ መጥፋት ከሐብታሞቹና ከቱጃሮቹ ይልቅ ከቀን ወደ ቀን ሰርተው የድካማቸውን ወደ ጉሮሮዋቸው በሚያደርጉ መጻተኞች ላይ እጅግ አድርጎ ችግሩ ይብስባቸዋልና ስለዚህ የመጻተኞችና የብርሃንና ሰላም ወዳጅ የሆኑ ሁሉ ይህን የመንግሥት አዋጅ ቸርቻሪዎች እያፈረሱ ብዙ መጻተኞች መቸገራቸውን ተረድተውት በብርሃንና ሰላም ስለ ማስታወሳቸው እጅግ አመሰግናቸዋለሁ ።

ግን አዲስ አበባ ቤሳው በብር ፳፪ ነው ተብሎ ጋዜጠኛ ስለጻፈ በብርሃንና ሰላም ተረዳሁት እንጂ እዚህማ እኔ ባለሁበት በድሬዳዋ መጋላ ፈጽሞ የለም አይገኝም ስለ ቤሳችን መጥፋት ለሴትኛ አዳሪና ለሞያተኛ ሠሬ ለባላገሩም ሁሉ እጅግ ሆኖ ችግር ነበረ ለጋዝ መብራት ለክብሪት ለቡና ለሻይ እንዲሁ በቤሳ ለመግዛት የሚያስገድድ ማናቸውም ጉዳይ ሁሉ ሽረፋ ስለጠፋ የባላገሩና የባለመደብሩ ችግር እኩል ሆኖ ነበር ለጊዜው ባለመደብሩ ሁሉ ንግዱ እንዲከሄድለት ስለቤሳ እንጨት እየቀረጸ አንዳንዱን ቆርቆሮ በትንንሹ እየቆራረጠ እንደዚሁ አድርገው ስለ ቤሳ ሽረፋ ያን እንጨትና ቆርቆሮ በጥቂት ጊዜ አሰለጠኑት

የከተማውም ሕዝብ በዚሁ የለት ጉዳዩን ይገበያይበት ነበር ወደዚያው ይህ አንዳንድ አረቦች ለመለዋወጫ ስለ ቤሳ ያበጁት እንጨትና ቆርቆሮ ይቅር ተባለና አንድ ጆርጂ የሚባል ዳቦ ጋጋሪ በስሙ አጽፎ አላፊ ሆኖ የወረቀት ቤሳ አሳትሞ አወጣ ይኸውም የጆርጂ ወረቀት በመሐለቅ ሁለቱ በብር ፴፪ቱ ይሸረፋል ይኸንንም የቤሳ ወረቀት በጁ ይዤ ሳለ እስኪ ልየው ብሎ አንድ የውጭ አገር ሰው ከጁ ተቀበለኝና በዚያው በወረቀት ላይ የተጻፈውን ቡላንዠሪየ ጆርጂ ስኮቲስ ድሬ ዳዋ አብሲኒ በን ፑር ደሚ ፒአስትር የሚለውን አነበበና ዝምብሎ ይገረም ጀመር ምነው በምን ምክንያት ነው እንዲህ አድርጎ የሚገርምህ ብዬ ብጠይቀው እንዴት አድርጎ አንድ

ዳበ ጋጋሪ በራሱ ስም አሳትሞ የመለዋወጫ ገንዘብ ያወጣል?

ይህን ለማድረግ አለመንግሥት በቀር ማንም አይችልም በአውሮፓም ቢሆን ቱጃሮቹም የወረቀት ገንዘብ ቢያወጡ በባንክ ውስጥ እነሱ ይቀበሉታል እንጂ በገበያ ውስጥ መለዋወጫ ገንዘብ ሆኖ በከተማው ሊሰለጥንበት አይችልም ፈጽሞ ክልክል ነው ብሎ ቢያጫውተኝ ምንም ቤሳ ተወዶ ሳለ እኛ ለመለዋወጫ የጆርጂን ቤሳ ስለ አገኘን ከችግርና ሽረፋ ከማጣት በመዳናችን ደስ ቢለኝ ደግሞ ባንድ በኩል ባልተገባ ደምብ ይህን ወረቀት አምጥቶ በመንግሥትና በሕዝብ ጥቅም ላይ ሽረፋውን ስላስፋፋ እጅግ ያሳዝነኛል ፈጽሞ የኛ መንግሥት ቤሳ በመታጣቱና የጆርጂ ወረቀት ስለ ቤሳ ሆኖ በድሬዳዋ ውስጥ ስለ መሰልጠኑ ይህን የሚያስገርመውን ነገር ለሰሚዎች አስረዳችኋለሁ ። ገብረ ጊዮርጊስ አሸናፊ ድሬዳዋ ።

መወድስ ።

በወአሐቲ እመዋዕል መጽአ አለቃ መርሻ ዘውእቱ መርስዔ ኅዘን ምስለ ወልዱ ፍቅረ ሚካኤል ወበአ ቤተ ማኅተም ዘልዑል ተፈሪ መኰንን ወራሴ መንግሥት ወተማየጠ መጻሕፍተ ቅዱሳተ በአስበ ፃማሁ ። ወእንዘ ይወጽእ እምህየ ወደሰወይቤ።

ኃይለ ሥላሴ አዝነመ እምደመና ልቡ ።
ትርጓሜያቲ ቃል እሙን መዓረ ወሦከረ ።
ሊቀ ምርፋቃት ልብ እስከ ጥዒሞ አንከረ።
ወበትጋሁ መንፈሳዊት ።
ዘወለደ መጻሕፍተ ቃል በዓይኑ ነጸረ ።
ወበ ዘኢያእመረ ።
ፈሊጠ እሱ ጥዑመ ወኢፈሊጦን አጉስቋረ ።
ከሠተትሂ ንግሥተ ኩሉ በኃይለ ሥላሴ ዘከብረ ።
ቴዳ ትርጓሜ ቃል ዕመቀ ምሥጢራት ዘተቀብረ ።
ወትርብዕተ ቴዳ አድምዖ ባዓስበ ፃማሆሙ ምዕረ ።
ነዳያን ዘኢደፈኑ ወርቀ ወብሩረ ።

አለቃ መርሻ ዘውእቱ መርስዔ ኅዘን ።

የኦቶሞቢል ማቆሚያ መለዋወጥ ።

ከዚህ ቀደም ኦቶሞቢል ከዋናው ገበያ መካከል እመንገድ መተላለፊያ ላይ በመቆሙ አላፊ አግዳሚውን አስቸግሮ ነበር አሁን ግን ኦቶሞቢሉ በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ፊትለፊት ባለው ሜዳ እንዲቆም ትእዛዝ ተደርጎ እዚያው መቆም ጀምሯል ። ደግሞም በተለየ አዲስ የኦቶሞቢል ዘበኞች ልዩ ልዩ ዓይነት መለዮ ያደረጉ ጉመድ ጉመዳቸውን እየያዙ የኦቶሞቢል አካሔድ በስርዓት እንዲሆን በየመንገዱ ይጠብቃሉ የከተማችንም ሹማምንቶች አሁን በመጀመሪያው ጊዜ እንዲህ ከነቁበትለወደፊት በከተማ የኦቶሞቢል አደጋ እጅግ እንዳይጎዳ የታወቀ ነው ።

የከተማ መብራት ።

በዚህ ሰሞን ከማዘጋጃ ቤት ጀምሮ እስከ ራስ መኰንን ድልድይና ወደአራዳ የሚወስደው ዋና መንገድ በኤሌክትሪክ መብራት ስለተበራ ማታ ማታ አላፊ አግዳሚውን ሁሉ ደስ አሰኝቷል እንደዚሁ ሆኖ የኤሌክትሪክ መብራት በከተማው ሁሉ ቢዘረጋ ከተማው እንዴት ባማረ ሌሊት ለሚጠብቁ ዘበኞችም በተመቸ ነበር ይኸውም በቶሎ ይፈጸማል ብለን ተስፋ እናደርጋለን ።

የቀድሞ የመስኮብ ንግሥት ሚስጢር ያለው የሕይወት ታሪክ ባለሙዋሏ ዜኔት ጻፈችላት በከፒቴን ባቢኪያን ታርሞ ተጻፈ።

፪ኛ ክፍል ።

እኛም ወደ ተጠራንበት የንጉሡ ግብዣ እንዳንሄድ በብዙ ነገር አመኻኘን ይህንንም ማድረጋችን ወደውድ ወዳጆቻችን ለመሄድ ነበረ እነሱም ለኛ የታመኑና በጣም የተወደዱ ናቸው ይልቁንም ሩዶልፍ ባሰትሮም የተባለው ከልጋወራሺቱ አሊክስ ጋር ወሰን የሌለው ፍቅር የያዘው በዚያም ጊዜ ብዙ ቀንና ሌሊት ከተወደደው ፍቅራችን ጋራ አሳልፈን የምንለብሰው ልብስ ገረዳችን እኒታ የምትሠራው ነበረ እንደዚሁ የአልጋወራሺቱ አሊክስ ፍቅር እየደረ ይበረታ ጀመረ እኔም በዚህ ነገር በጣም ተቸገርኩ የዚህ የአሊክስ ወዳጅ መጨረሻው ነበረ የናፈቀኝ ይልቁንም ንግሥቲቱን ማርገሪታን ለመጐብኘት የተወሰነልን ጊዜ አለፈ ታላቁ ዱክ የአሊክስ አባት ደርምሽታድ ወደሚባለው ቤተ ንጉሥ ወደ ጀርመን አገር እንድንመለስ ወረቀት ጻፈላት ነገር ግን አሊክስ ያባትዋን ወረቀት ወዳንድ ቤት ጥግ ወረወረችውና ከወዳጆቻችን ክንድ ላይ እንከባለል ጀመርን በተለየ የቆሙትም የቤተ መንግሥቱ ምስጢር ዘበኞች በኛ ነገር ተቸግረውበት ነበረ ነገሩን አላገኙትምና እኛ ግን ሕይወታችንን በጠለቀው ፍቅር ለመኖር ነው እንጂ ሌላ አላሰብንም

የአልጋ ወራሺቱ የአሊክስ አባት ለኛው ሲል አንዲት ሄሮት ፊልት የምትባል ወይዘሮ ወደጀርመን አገር ይዛን እንድትሄድ ሰደደልን የሆነው ሆኖ ምንም ይህችወይዘሮ ተቆጪ ሴት ብትሆን እርስዋ የመጣችዕለት ማታውን መጨረሻውን የፍቅር ቀን ከወዳጆቻችን ጋራ ለማደር ምክንያት አገኘንና ከግቢው ወጥተን አደርን ።

ይህም ከዚህች ወይዘሮ ተለይቶ ማደር እንዴት ያለ ችግር ነበረ እኔም በዚያች ሌሊት በሐሳቤ እጅግ ተቸገርኩኝ አሊክስንና ወዳጁዋን ለማለያየት በጣም የሚያስቸግር ነገር ነበረ ይልቁንም ሁለቱ ሌቱን በመሳሳም ያነጉ ስለነበረ ነው ። ደግሞም እርሷዋ ባል ያላገባች ነበረች ወደሁም የንጉሥ ልጅ ስለሆነች ካንድ ከተራ ሰው ጋር ነውር ስታደርግ ብትገኝ እንዴት ያለ ውርደት ነው ፍቅራቸው ከወሰን የዘለለ ነውና መገለጹ አይቀርም የሆነው ሆኖ በዚያ ግዜ ገዢው ፍቅር ነው ይህ ድርጊት አድሪያኖ በሚባለው እልፍኝ ሆነ ።

ከፒቴን ባቢኪያን ።

በሚመጣው ሳምንት ይቀጥላል ።



ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

COGNAC S. E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



ዝኒት የእጅ ሰዓት

በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩግቢ

RUGBY

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆን በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

“ሩግቢ” የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ግልጽ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል “አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ” ብቻነው።

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዴልፊአ በቦስቶን በማድሪስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፡ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሸ ኦቤርላንድ አቶሞ ቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጦጦን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይ ጨርስም ።



አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባ ኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኜቶና ባለባተሪ ነው ክምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማ ደሻ መሣኘም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞ ቢል በኢ ዮጵያ በተለየ ወኪል «ዓረብያን ትሬዲነግ ኩምፓንያ» ነው

ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪከን ቤንዚን ይሸጣል ።

ማስታወቂያ

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲	ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር	፱	ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
የዓለም ጂዮግራፊ በአማሪኛ ደኅና ጥራዝ ዋጋው	፮	ብር
» » » መናኛ ጥራዝ ዋጋው	፭	ብር
ዶግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፬	ብር
ኅሐ ጽባሕ	፬	ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫	ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫	ብር
የሕይወት ታሪክ	፪	ብር ተኩል
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪	ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪	ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትርሜጓው	፪	ብር
የቁጥር ትምርት	፩	ብር
ያማሪኛ ሰዋስው	፩	ብር
ወዳጄ ልቤ	፩	ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን		አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ		አላድ
አጭር የዓለም ታሪክ		አላድ
ያማሪኛ ፊደል		ሩብ
አሳብና ምኞት		ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት		ሩብ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፪	መ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር		፪መ
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ		ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶ ግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ		ሩብ

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ፤ የልብ ፤ የደረት ፤ የጉበት ፤ የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ፤ የቂጥኝና የቋቁቻ፤ የሚያዋልድ፤ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል

እደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ሱቅ ነው ።

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥት ነገሥታት ዘውዲቱና ከልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ያሰናዷነት ፈቃድ የተቀበለ ።

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በከፓሡሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በከፓሡሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ጉድይር ግዙ





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው ። በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አራተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፴፬
4 me ANNÉE № 34

ሐሙስ ነሐሴ ፲፯ ቀን ፲፱፻፳ ዓ ም።
JEUDI 23 AOUT 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ታላቁ የማዘጋጃ ቤት ሥራ መሻሻል

የክቡር ክንቲባ ቁርጥ ሐሳብ

ክቡር ዲርክቴሩ ነጋድራስ አስታጥቄና ክቡር ካፒቴን ባቢክያን ሐሊናቸው በሥራ ስለተጸመደ ሌትና ቀን እረፍት የላቸውም ። እነሆ የከተማ ጽዳትና የአቶሞቢል አካሄድ ደምብ መጠባበቂያ ሥራ ቤት ሥራቸውን በየበኩላቸው ተጀመሩ አሁን የተጀመረው ማዘጋጃ ቤት ቀድሞ ያልቆመውን የሥራ ቤት ለማቆም ነው ።

የከተማ ጥዳት ቀድሞ የተበላሸ መሆኑ በሕዝቡ ፊት የተገለጸ ነው ስለዚህ የሕዝቡ ጉዳት ስለሆነ ክቡር ክንቲባ ተቸግረውበት ነበረ ። አሁን በቅርቡ ከክንቲባው የወጣው አንደኛው ትእዛዝ ስለከተማ ጽዳት ነበረ ይኸውም ትእዛዝ በዲሬክተሩ በኩል ለክቡር ካፒቴን ባቢኪያን ተሰጠ ወዲያውም ክቡር ክንቲባ አንድ እውነተኛ አገሩን የሚወድ ሰው መርጠው በሥራው ላይ ሾሙት ።

በቀድሞው ጊዜ በየመንገዱ ላይ ይልቁንም በራስ መኰንን ድልድይ አጠገብ የሚያልፍ ሰው ሁሉ ክፉ ሽታ አያጣውም ነበረ ። በአራዳውም ውስጥ በየሱቁ ደጃፍና በየመሸታው ቤት ደጃፍ ለሕይወት የማይስማማ ሽታ አይታጣም ነበረ ። ዛሬ ግን እንዲህ የመሰለ ክፉ ሽታ አይገኝም ።

ይልቁንም በራስ መኰንን መንገድና በየስፍራው የከተማ ጥዳት ዘበኞች ሥራቸውን ሲሠሩ ይገኛሉ ። ይኸውም የሥራ ቤት በያለበት መርማሪዎች አቁሞአል እነዚሁም መርማሪዎች የመሸታ ቤትን የመብል ቤቶችን ይመረምራሉ ደግሞም ለመብል የሚሸጠውን ቅቤ ወተትና ከወተት የሚወጣውን አይብ አርጎ ይህንንም የመሰሉ የሚበሉ አትክልቶችና ፍሬዎች ይመረምራሉ ይልቁንም የልኳንዳን ቤቶችና ሆቴሎችን የሚበላ ነገር የሚሸጥባቸውን ቤቶች ሁሉ መመርመር ጀምረዋል ።

ደግሞም ከዚህ ሌላ በከተማ ውስጥ የሚያስፈልገውን ያህል በየመንገዱ ላይ የሽንት ቤቶችና የሰገራ ቤቶች ለማሠራት ሥፍራውን አመልክተዋል ከሁሉ ይልቅ ደስ የሚአሰኘው በከተማ ውስጥ ያለውን ውሻ በልክ ለማረግና ሴትኛ አዳሪዎችን ከጠጅና ከአረቄ ንግድ ከልክሎ ሰፈራቸውንም ለመለየት ስለታሰበ ነው። ይህ የመጨረሻው ነገር እንዲፈጸም ትልቅ ተስፋ አደርጋለሁ ይህ ካልሆነ ግን በከተማ ውስጥ የጠጅና የመሸታ ቤት በዝቶ ሴትኛ አዳሪዎችም ቁጥራቸው ይበዛና ክፉው ዘር የሚያበላሸው በሽታ ቂጥኝና ጨብጦ ባገር ይበዛና መንግሥትና ሕዝብን ያጠፋል። ደግሞ አንዱ ዓይነተኛው የክንቲባው ትእዛዝ በዲሬክተሩ በኩል ለክቡር ካፒቴን የመጣላቸው ትእዛዝ የአቶሞቢልን አካሄድ ለመወሰን ነው ። አቶሞቢል ባገራችን ከገባ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ዋና ተጠባባቂ የሥራ ቤት አልተደረገለትም ነበረ ።

አንድ አገሩን የሚወድ ሰው በከተማ ያሉ ወስላቶችንና በመንግሥት ሥራ ውስጥ በእውነት የሚሠሩትን ያውቃቸው ኖሮአል ይልቁንም ከዛሬ ሶስት ዓመት ጀምሮ በአቶሞቢል አደጋ ፶፯ ሰዎች እንደሞቱ ፩፻፲፭ ሰዎች ወንዶችና ሴቶች አከላታቸው እንደጐደለ ፩፻፲፪ ሰዎች ወደ ሆፒታል ሄደው ታክመው እንደዳኑ አስታወቀኝ እንዲህ ያለውን ነገር መንግሥት ወይም አንድ መኳንንት ለማወቅ በፈለገ ጊዜ በዘበኝነትም ሥራ ቢሆን ወይም በሌላ ወገን አንድ ማስታወቂያ አለመገኘቱ የሚገርም ነው ። እንዴት ያለ ግሩም ነው ? በቀረው አገር ሕዝብን እያበረከቱ ታላላቅ ከተሞች ሲሞሉ ታናናሽ ከተሞችን ይሠራሉ እኛ ግን የተወደዱ ሕዝቦች ምን ያህል እንደጐደሉብንና እንደጠፉብን አናውቀውም።

ስለዚህ ክቡር ክንቲባ ይህ ጥፋት እንዳይበዛ ብለው አንድ ልጅ እግር አገሩን የሚወድ ለስራው የሚተጋ እንቅልፍ

የሌለው ሰው አቶ ካሣ ገብሬ የሚባል በሥራው ላይ አቁመዋል አሁን በቅርቡ ሀያ ያህል ዘበኞች ደኅና መለዮና ልብስ ሰፍተው የአቶሞቢል አካሄድ ያስጠብቃሉ እነዚሁም ዘበኞች አስራ አምስት ቀን ያህል የሥራውን አኳኋን ተምረዋል በየመንገዱም ቆመው የአቶሞቢሉን አካሄድ ይመዝናሉ የተወደዱት ከንቲባችን አሁን በቅርብ ቀን ቀድሞ የወጣውን ደንብ ተመልክተው ዛሬ በጭሩ የወጣውን ደምብ ፈርመዋል እንግዴህ ከዚህ በኋላ የአቶሞቢል አደጋ እያነሰ እንዲሄድ አይጠረጠርም። ይልቁንም ለወደፊቱ ጨርሶ እንዲቀር ተስፋ አለኝ ባለመታደል ብዙ ሰዎች ባፋቸው ብቻ አገራችንን እንወዳለን እያሉ ሥልጣን ባላቸው ጌቶቻችን ዘንድ ሲምሉና ሲገዘቱ ይታያሉ ይኸውም ደግሞ ዛሬ በዚህ በሥልጣኔ ሥራ ላይ እንቅፋት መሆንን ይጀምራሉ እነሱን ታምነው አሁን ባለፈው ሰሞን አቶሞቢል ነጂዎች አድማ አድርገው ዘበኞችን መደብደብ ጀምረዋል የሆነው ሆኖ አድሚ ለልዑል አልጋ ወራሽ የተሰጠው ደንብ እንዲጸና ለማድረግ ጆሮዎቻቸው ከመስማት አያዘነብሉም ዓይኖቻቸውም ከማየት አያንቀላፉም ይኸው ክቡር ከንቲባ ባቢኪያን ሥልጣኔን ለመጀመር የቀና ነው። ለመጨረስ ግን ችግር ነው ያሉትን ቃል የምናስታታውስበት ጊዜ ደረሰ ።

የክቡር ከንቲባ ሀሳብ ገና አልተወሰነም ደግሞ ዛሬ በማዘጋጃ ቤቱ የሂሳብ ሥራ ተጀምሮአል (ኮንታቤሌቴ)ማናቸውም ሰው ዛሬ ከማዘጋጃ ቤት በሂሳብ ሥራ ክፍል ገብቶ ቢመለከት እባንክ የገባ ይመስለዋል ።

እኛም ክቡር ከንቲባ የጀመሩትን መንግሥት የሰጣቸውን እምነት እንዲያጸኑት እንመኝላቸዋለን ደግሞም ዛሬ የከተማው ሕዝብ የፈለገው ከተማችንን ጸጥታ ያለው ማለት የማያስፈራና የማያጠራጥር እንዲሆኑ ነውና እንዲበረቱበት እምላክ ያግዛቸው ስንል እንለምናቸዋለን ።

ዘገየ ተገኝ ።

መልክም ደምብ

በሐረር አውራጃ ገበያ ሁሉ ሥጉያ የእርድ ከብት ስለ ተወደደ ለእርሻ የሚሆነውን በሬና ወይፈን እርጉዝዋንም ላም በመሲና ስም እየገዛ ለርሻና ለማርባት የሚገዛውን ባላገር ሥጉያ ስለ ከለከለው ይልቁንም ወተትና ቅቤ እየሰጠች የምትረባዋን ላም ሥጉያ ላንድ ቀን ጥቅሙ እያረደ አገር መበደሉን ስለመረመሩ የሐረር ጉምሩክና የየገበያው ሁሉ ዲሬክተር አቶ እሸቴ ተከትለው ቀጥሎ የተጻፈውን ደምብ ለየገበያው ሠራተኞች ሁሉ አስታወቁ ።ለእርሻ የሚሆነውን ወይፈንና የምትረባዋን ላም ሥጉያና የከተማ ሰው በሰንጋ፣ በመሲና ስም እየገዛ ለየድግሱና ለልኳንዳ ሥራ ስላረደው በጣም ጉዳት ሆኖአልና ከእንግዴህ ወዲህ ለድግሥና ለሉካንዳ ሥራ ወይፈንና መሲና መግዛት ክልክል ነው ባላገር ግን ለርሻና ለማሳደግ ለማርባት መግዛት ቢፈልግ እያስመሰከረና እየማለ ቢገዛ አይከለከልም ነገር ግን ለእርሻና ለማሳደግ ለማርባት ነው ብሎ ገዝቶ አርዶ ቢገኝ የገዛበት ዋጋ በመዝገብ ታይቶ በቀጋው እጥፍ ይከፍላል ያጋሆውም እንደደምቡ ይቀበላል ሥጉያውም የተሠረቀ ከብት ከውጭ እየገዛ ያርዳልና ቀረጡንም ራሱ ቢከፍል ሻጭና መድኑን ሳያቀርብ እንዳያርድ የሚል ደምብ ስለሰጡ በጣም አመስግነናል ይኸ ጉዳት በየሀገሩ ሁሉ ሳይሆን አይቀርምና እንደዚሁ ቢከለከል መልክም ይመስለናል።

ረታ ወልዴ ።

ስለ መቃብር ክርክር ።

ማንም ከላንተ ጥበብ ቢጐድለው ለሁሉ ሳይለይ የሚሰጠው እግዚአብሔርን ይለምን ። ሰነፍ ሆይ ይህቺ ከዓይንህ አትውደቅ ጥበብና ምክርን ጠብቅ ለነፍስህም ሕይወት ላንገትህም ጸጋ ትሆናለች ጥበብን አንቺ እመቤቴ ነሽ በላት ልባዊንም ወዳጄ ብለህ ጽራት፡ማነው ጠቢብ ይህቺንስ የሚያስተውል የሚያውቃትም እያለ ያስተምረሃልና ከሁሉ በፊት አስተዋይ ልቡና ተመልካች ሕሊና ይስጥህ አሜን፡ብለህ ተግሣፅን መቀበል አለብህ ተግሣፅን የሚወድ ዕውቀትን ይወዳል ዘለፋንም የሚጸላ ያ ሰነፍ ነው እንደ ወርቅ ፈርጽ እንደ ሚያንጸበርቅም ዕንቁ የምትሰማን ዡሮ የሚዘልፍ ጠቢብ ሰው ነው።የብልሓተኛን ተግሣፅ መስማት ይሻላል የሰነፎችን ምስጋና ከመስማት ደምሴ ፡ የቀደመው ሳይከናወንልህ ደግሞ የጉድለት አነጋገርህን ጻፍህ አሁንስ ባንተ ብቻ አይፈረድም አዬ እውቀት ሆዬ በመጀመሯው ስትጽፍ ብዙ የመንግሥት ጥቅም ያለበት ሥራ አልተዠመረም ብለህ ብትጽፍ የጊዜው አስተዋዮች ያላገኙት ምን አዲስ ነገር አገኘ፡ብዬ ስመለከት ዋናስረ ነገሩ መቃብር ግዙ ይላል፡ላበባ የለው ገለባ ለወሬ የለው ፍሬ እንደሚባል ሐሳብህ ትንሽ ስለሆነ ልንጽፍልህ አልተጋንም ነበር አሁን ግን ግድ አሳሰበን።አብርሃምም ከሬሣው ተነሣ ለኬትም ልጆች ተናገረ እኔ ስደተኛ መጻተኛም ነኝና እለምናለሁ መቃብር እንድታስገዙኝ እሬሳየን የምቀብርበት አለ።እነሱም አሉት ስማን ጌታችን ሆይ አንተ በኛ ዘንድ አለቃ ነህ ከእግዚአብሔር፡ ከመቃብራችን መርጠህ በመልካሙ ቦታ እሬሳህን ቅበር ከኛ የሚከለክልህ የለም ቢሉት እንዳሁኑ ሕዝብ ችግር የሌለበት ቸር ጌታ ነበርና እርስት እንዲሆንልኝ ግድ ዋጋ መስጠት እፈልጋለሁ ብሎ ኤፍሮንን ለመነ ። ኤፍሮንም ጌታዬ ሆይ የምትሻት ምድር ዋጋዋ ፬፻ ሚትቃል ብር ነው በኔና ባንተ መካከል ይህ ምድነው ብሎት ነበር እሱ በፈቃዱ ሰጠ እንጂ ዋጋ ካላመጣህ አትቅበር ያለው የለም ስደተኛ ስለሆነ በምክንያት እርስት እንዲሆንለት ነው ። አስተዋይ የመሰልከው ሰነፍ ሆይ እኛ ለኢትዮጵያ አገራችን ስደተኞች መጻተኞች አለመሆናችንን ዕወቅ ተረዳ ያንተን ግን አናውቅም ። መንግሥትስ ብዙ ጥቅም የሚያገኘው ከመቃብር ዋጋ መሰለህ አዬ ማስተዋል እንግዴህ ያገርህ ፋብሪካ ሕዝብ መሆኑ ነው እንዳንተ ሐሳብ መንግሥታችንስ ቸር ርኅሩኅ ይቅር ባይ ነው ስንኳን የመቃብር ዋጋ አዲስ ሕግ ሊያወጣብን ካሁን በፊት የከበደ ነገር ቢያይብንም እያቀለለልን መሄዱ በሁሉ ዘንድ የታወቀ ነው በዓለምም መንግሥታት ሁሉ የተመሰገነ ነው ። እውቀትህ እስከ መቃብር መሆኑ ለሰሚው ሁሉ ያሳዝናል ያሁን ጊዜ ያገራችን ልጆች ትምርት እስከ ወረቀት ጽፈት ድረስ ሆነና ሁሉ አረሰ ማን ይሸምት እ

ንደ ተባለው የጽሕፈት ሥራ ውድ ሲሆን ጊዜ የመቃብር ጸሐፊ መሆንን አሰብህ የኢትዮጵያ መንግሥት ለሕዝቡ መቶ ሁለት መቶ ጋሻ መሬት በከንቱ የሚሰጥ ባንድ ካሬ ሜትር ፪ ብር ይቀበል መሰለህን አዬ አዋቂነት ፩ካሬ ሜትር ለመቃብር አይበቃም በጐኑ ፩ሜትር በቁመቱ ፪ሜትር የሚያስፈልግ ነውና በ፩ሰው አራት ብር እየተቀበልሁ እረዳለሁ የማለት ሐሳብህ ከንቱ ነው ። የገበዞች ሹማምንት አያስቀርቡህ እንደሆነ ነው እንጂ ቢያቀርቡህ ግን መልካም ማኅደር ይሆንሃልና ቀና ብለህ ስማ ሰው ሁሉ ከዚህ ዓለም በሞት በመለየቱ ጊዜ ወደ መቃብር ሲወስዱት በራስጌው በስልቻ (ባቁማዳ) የሚቀመጠው እህል ስለ ደሞዝ ደግሞ በመሶብ እንጀራ በገንቦ ጠላ ከዚያው አለና ስለ ቀለብ እየተካፈላችሁ ከረዳትህ ከብልሁ ጋራ የሰው በልቶ አያድሩም ተኝቶ ነውና ሰው በሞተ ጊዜ ቦታ እንዳይበላሽ በተራ በተራው እንዲቀበር በትጋት መጠበቅ ያስፈልጋችኋል ማኅደርም ቢያንሳችሁ ከፍታት ጥር ይጨምርላችኋል ።

እንደዚህ እንደናንተ በትንሽ ሳይወሰኑ ያሁን ወጣቶች ልጆች በዚህ በዋና ከተማችንና በአውሮፓ ትምርት ቤት የሚማሩ ለጽፈትና ለቋንቋ ብቻ ሳይሆን ወደ ከፍተኛውም ደረጃ ደርሰው ከምድር የሚገኙ ማዕድናትን መርምረው የሚያውቁ ፋብሪካ ለማቆም የውጪ አገር ሰው ከመፈለግ የእጅ ሥራ አውቀው የሌለውን የሚያስገኙ የጠመመውን የሚያቀኑ የተሰበረውን የሚጠግኑ ሁነው በመጡልን ጊዜ አገር ይለማል መንግሥት ይጠቀማል ሕዝብም ይከብራል ። ለጽፈትና ለቋንቋስ ለውጪ አገር ሰው መንግሥት ገንዘብ ባልሰጠም የመቃብር ጽዳት ዋጋ የሚያሰጥአይምስላችሁእንደማይጠቅምግንበ፴፩ ቁጥር ከመጻሕፍት የተባበረ ቃል ከላንተ በቀር አዋቆችአንብበዋል ። ኃይለ ቃሉን በኃይለ ቃል መልስ እንደመስጠትከባልንጀራህ ጋር ስለ ምትናገረውን ነገር ለክፉ በጎ መመለስ ተጽፎልናልና እንታገሥ ይሆናል አንተ ግን ፪ተኛይቱን ትእዛዝ አለመማርህ ተገለጸብህ እንግዲህስ አንተን መሆን ነውና ባጭሩ ይቅር።

ተክለ አሚን እሼቴ ።

በአቶሞቢል የተደረገ አደጋ ።

በነሐሴ ፪ቀን ቀነአ ሙለታ የሚባለውን የወለጋ ሰው ሰይድ አብደላ የሚባል አቶሞቢል ነጂ በአቶሞቢል ከ፮ ኪሎ በታች አሥድጦ ሸሸ ። ይኸውም ቀነአ ሙለታ የሚባል የወለጋ ሰው በ፫ ሰዓት ተድጦ ሐኪም ቤት ሂዶ ታክሞ ከለሊቱ በ፫ ሰዓት ሲሆን ሞተ ከዚህ በኋላ አቶ ከማ ገብሬ አዲስ የተመለመሉትን የአቶሞቢል ደንብ ጠባቂዎች ይዞ ከዘበኛ አምልጦ በጠፋ በሁለት ቀኑ ከለሊቱ በ፫ ሰዓት ተኩል ከተኛበት ቤት ይዞት መግደሉን አምኖ ከወህኒ ገብቶ ታሥሯል በብርታት ይኸ ሰው ገድሎ የጠፋው አቶሞቢል ነጂ ተይዞ በመታሠሩ ብዙ ሰው በጣም ደስ ብሎታል የዚሁም የዳር አገር ሰው ደሙ በከንቱ ፈስሶ ቢቀር ጉዳቱ ለመንግሥታችን ነበር ።

፪ተኛ በነሐሴ ፯ ቀን የተደረገ የአቶሞቢል አደጋ ከአቡነ ማቴዎስ ቤት በታች ታቦር የሚባለውን ሰው አንድ አቶሞቢል ነጂ አስገፍቶት ሰውዬውንም ሳያነሣው ጠፋ ከዚህ በኋላ ለአቶሞቢል ደምብ ጥበቃ የተመለመሉት ሠራተኞች ይኸን ነገር ሰምተው ለአለቃቸው ላቶ ከማ ገብሬ ነግረው ይኸ የጠፋው አቶሞቢል ነጂ እንዲፈለግና እንዲያዝ በጣም አስበበት ወዲያው በጠቋሚ አሲዞ የታቦርን ዘመዶች ካሉበት አስፈልጎ እንዲቁራኙ አደረገና ከታከመና ሐኪሙ ለሞት እያስፈራውም ካለ በኋላ ታቦር ቀርቦ እንዲሟገት ቁራኛው በ፬ ቀኑ እንዲፈታ አደረገ ይኸውም ታቦር ደሙ ፈሶ እንዳይቀር ተከሶ ሂዶ ይኸው ሰው ተፈልጎ እንዲያዝ በሥራው ላይ ያሉ ሠራተኞች መበርታታቸውን ያስረዳል ። እንደዚሁ እንደ አጀማመራቸው ወደፊት ብርታት እንዲያገኙ ቢአግዟቸው ለወደፊቱ በየጊዜው ከሚሆነው የአቶሞቢል አደጋዎች እያነሱ መሄዳቸው አይቀርም ።

አንድ ታሪክ ያለው የማይረሳ የሕክምና ሥራ አኳኋን ።

ባለፈው ሳምንት ነሐሴ ፯ ቀን ፲፱፻፳ ዓ ም በልዑል አልጋ ወራሽ ሆፒታል አንድ የሚያስደንቅ ሕክምና ተደረገ ቀኑም እሁድ ነበረ ከማታው በሁለት ሰዓት ተኩል ክብርት ማዳም ባቢኪያን ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ሰውነታቸው በሕመም ምክንያት የተጐዳ ስለሆነ በሐኪም ትእዛዝ ወደድሬዳዋ ሂደው ፫ ወር ያህል ከተቀመጡ በኋላ ትንሽ ሕይወት አገኙ ከዚህ ወዲያ ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው አምስት ቀን ያህል እንደተቀመጡ ሰውነታቸው ስለሳሳ ይልቁንም ደማቸው አልቆ ስለነበረ ጤና ለማግኘት አልቻሉም ደግሞ ያ፬ ወር ነፍሰ ጡር ነበሩና አስወረዳቸው በዚሁ በውርጃው ምክንያት ደማቸው አልቆም ስላለ የቤታቸው ሐኪም ያለመጠን ተቸግሮ ነበረ ክቡር ካፒቴን ባቢኪያንም ምንም ቀኑ እሁድ ቢሆን በሥራ ምክንያት ከግቢ ስለነበሩ በስልክም እንኳ ቢፈልጉ አልተገኙም ከእኩል ቀን በኋላ ከማታው ባ፲ ሰዓት ወደቤታቸው መጡ ነገር ግን ማዳም ባቢኪያን እሳቸው እስኪመጡ ድረስ ደም አፍትቶባቸው በጸና በሽታ ተይዘው ነበረ ያን ጊዜ እኒህ ወጣት ሴት በፃዕር ተይዘው ሳሉ አምስቱንም ልጆቻቸውን ሰብስበው ከጠገባቸው አድርገው እየሳሙ ያለቅሱ ነበር ይልቁንም ደግሞ እረ ካፒቴንን ጥሩልኝ የምነግራቸው ነገር አለኝ እያሉ ሲያጣጥሩ እጅግ አድርገው ያሳዝኑ ነበር ።

ወዲያው ካፒቴን መጡና ባለቤታቸው ደህና መስለዋቸው ወደቤት ገብተው ሳሉ ሕመማቸውን ከተረዱት በኋላ ወደልዑል አልጋ ወራሽ ሆስፒታል በሩጫ እየበረሩ ሂደው የልዑልን ሐኪም አግኝተው በቶሎ ይዘዋቸው መጡና ቢያሳዩዋቸው ሐኪሙም ደማቸው ማለቁን ስለተረዱ አንድ መርፌ ወጋቸው ወዲያውም ወደ ሆፒታል ለመውሰድ ጊዜው ብርቱ ዝናብና በረዶ ይጥል ስለነበረ በግድ እኩል ሰዓት ያህል ለመቆየት የሚያስፈልግ ሆነ ደግሞ ሁተለኛ አንድ መርፌ ተወጉ በዚያን ጊዜ እኚህ ወጣት ሴት ጻዕር ስለበዛባቸው ዓይኖቻቸው ስልምልም አሉ አፋቸው ተዘጋ ያንጊዜ የሆነውንም ሁሉ አያውቁም ነበረ

የተከበሩ ክቡር ዶክቶር ሐነር የመጀመሪያውን ሕክምናቸውን (ኦፔራሲዮን) ደሙ እንዲቆም አደረጉ ቀጥለውም ካፒቴንን ጠሩና እንዲህ አሉዋቸው ካፒቴን ሆይ ባለቤትዎ ያለጥርጥር መሞታቸው ነው ነገር ግን እኔ እስከ ሁለት ሰዓት ድረስ ነፍሳቸውን ለማቆየት እችላለሁ ብቻ ከሰዎ ደም ለመስጠት እስቤአለሁና ፈቃድዎ እንደሆነ ይንገሩኝ ይህንንም የምጠይቅዎት በሕክምና በዳኝነት ሕግ ነው አሏቸው ካፒቴንም ይህን ቃል ሰምተው ብቻ ሚስቴ ትዳንልኝ እንጂ የተቻለዎን ያድርጉ ብለው መለሱላቸው ክቡር ዶክቶር ሃነርም ይህን ፈቃድ ተቀብለው የሁለቱን ባልና ሚስት ሚክሮስኮፕ በሚባለው መኪና መረመሩት ከመረመሩ በኋላ የሁለቱም ደማቸው የተስማማ መሆኑን ተረድተው ዋናው ሕክምና ከሴሊቱ በሁለት ሰዓት ይደረጋል ብለው ጊዜውን ቆረጡ ከዚህ በኋላ ካፒቴንም ሰዓቱ መቸ በደረሰ እያሉ ቸኩለው ነበር ግን መቸም የተለመደ ነገር ስለሆነ እንዲህ ስላሉዋቸው ፈጽመው አልደነገጡም ከሴሊቱ ሁለት ሰዓት ተኩል ከሆነ በኋላ ካፒቴንና ማዳም ወደሕክምናው ቤት ገቡ የካፒቴንም ቅርብ ዘመዶቻቸውና ወዳጆቻቸው ሠራተኞቻቸውም ከበረንዳው ላይ ቁመው ይጠባበቁ ነበረ በዚያ ጊዜ ዶክቶሩ ካፒቴን ባቢኬያንን በመድኃኒት ላስተኛዎ ብለው ቢጠይቋቸው አይሆንልኝም እኔው በይኔ የሚሆነውን ሁሉ እያየሁ ደሜን እሰጣለሁ ብለው መለሱላቸው ። ወዲያውም ዶክቶሩ ካፒቴንን በበሽተኛ መኝታ ጠረቤዛ ላይ አስተኟዋቸውና ከግራ ክንዳቸው የደም ሥራቸውን ቆረጡና ላስቲክ አግብተው በላስቲክ ይመጡት ጀምሩ ነገር ግን የተቆረጠው የደም ስር ትንሽ ኑሮ ሌላ ሁለተኛ የደም ስር ለመቁረጥ የሚያስፈልግ ሆነ እኛም ይህ የሕክምና ሥራ ከሚደረግበት ቤት ፊት ለፊት ከበረንዳ ላይ ቁመን ነበር መዝጊያውም በተከፈተ ቁጥር ስንመለከት የካፒቴን ፊት ትንሽ ቅጭም አላለም ነበር ይልቁንም ለመሳቅ እንዳሰበ ሁሉ ፊታቸው ፈገግ ፈገግ ይል ነበር ብዙም ደም ከቀዱለት በኋላ የማዳም ባቢኬያን የደም ስር ቀደው ከካፒቴን ላይ የቀዱትን ደም ወደሳቸው ላይ ይጨምሩላቸው ጀመር ። እንዲሁም ጥቂት በጥቂት ሲያገቡላቸው ጊዜ በድን የነበሩት ሴቲዮ እንዳንድ መኪና ቀስ እያሉ ዓይኖቻቸውን ከፈቱ ልባቸውም ተመለሰ አፋቸውም ሥራውን ጀመረ ሰውነታቸውም ሁሉ ወደ ስፍራው ተመለሰ ይህም ሕክምና አንድ ሰዓት ከሩብ ያህል ቆየ ከዚያም በኋላ ካፒቴን ይህ ነገር እንደ ምንድነው ብዬ ብጠይቃቸው ። ነገሩስ ምንም ክፋት የለው ከቤት ልጆች ብቻቸውን ናቸውና እንሂድ አሉኝ ማዳም ባቢኬያንም በጸጥታ ተነስተው ወደአንደኛው መታመሚያ ቤት ሄዱ. (ማለት ወሰዱዋቸው) ይህንን ሕክምና እኔው ራሴ ስላየሁት እንደዚህ ያለ ብልህ ዶክቶር በማግኘቷ ኢትዮጵያ መልካም እድለኛ ናት እኛም ሀብታሞች ነን ። ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንም ይህን የመሰለ ታሪክ ያለው ዶክቶር አስመጥተው በሆስፒታላቸው ውስጥ ያሉትን ሕሙማን በማስጉብኘታቸው በለማቋረጥ ልናመሰግናቸው ይገባናል በኛም ላይ ለማናቸውም በሽታ አንዳች ነገር የምንፈራው አይገኝም የምንሻው ሁሉ ያለጥርጥር ይደረግልናልና

አስፋው አብዲ ።

ያገር ውስጥ ወሬ

፲፱፻፳ ዓመተ ምሕረት ነሐሴ ፪ቀን የዓዳልና የከረዩ ሕዝብ አረማውያኑ) እርስ በርሳቸው ተዋግተው ከዓዳል ፺፪ ተከረዩ ፳ሰው ሞተ የቈሰሉት ግን ብዙዎች ናቸው ። የተዋጉበትም ምክንያቱ ከብቶቻቸውን ሲያግዱ ማር እኔ ላብላ እየተባባሉ ወሰን ተላልፈው ነው ይባላል ። ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ይኸን የሕዝብ እልቀት በሰሙ ጊዜ ዳግመኛ እንዳይዋጉና እንዳይተላለቁ ክቡር ፊታውራሪ ጣሰውን ለጥበቃ አዘዙዋቸው ፊታውራሪ ጣሰውም የልዑልን ትእዛዝ ነሐሴ ፫ ቀን በማለዳ ሰምተው ወደዚያው ፫፻፶ የሚያህል ወታደር በፍጥነት አስከትለው በ፫ኛው ሰዓት ለጋር በባቡር ተሣፍረው በተሐራ ጣቢያ ድረስ ሄዱና ያን ጊዜውን ለሠልፍ ተዘጋጅተው ሊዋጉ የነበሩትን አረማውያን በተከተላቸው ሠራዊት ኃይል ዘብ አስጠብቀው ውጊቱን ከልክለዋቸው አደሩ ። በማግሥቱ ከተዋጉበት ሥፍራ ሄደው በአምባጓሮ የሞቱትን ሰዎች እሬሳ አስቀብረው ወደ በተሐራ ሲመለሱ ሞጆ ጣቢያ አድሮ የነበረው አራት መቶ ወታደር በባቡር ተሣፍሮ ደረሰ ። ደግሞ ሹም ሳያዛቸው በፈቃዳቸው የዘመቱ ሰዎች እያሌ የሚሆኑ ነበሩና ሰይፋቸውን ታጥቀው ጦራቸውን ይዘው ሲፈክሩ ሲያቅራሩ ግሩማን ሆነው ይታዩ ነበር ። የወታደሩን ትጋት የአሠላለፉን ሥርዓት አዳሎቹ በየጫካው ውስጥ እየሆኑ ይመለከቱ ነበርና ፪ኛ ውጊት ቢያነሡ ዘመቻ እንዲሆንባቸው ስለ ተረዱት ዓዳልና ከረዩዎች በራሳቸው ደንጊያ እየተሸከሙ በእጃቸው ሣር እየጨበጡ ወደ ሠፈር መምጣት ጀመሩ ።

መጀመሪያ የአዳል ባላባቶች ከብዙ ፈረሰኞች ጋራ ሆነው መጡ ቀጥሎ ሁለት ሰዓት ያህል ቆይተን የከረዩ ባላባት ቆሮ ከብዙ ሰዎች ጋራ ሆኖ መጣ ይህ ሁሉ ሲሆን ክቡር ፊታውራሪ ጣሰው ገና በሩቅ ሳሉ በመነጽር ያዩ ነበርና ጥሩንባ አስነፍተው ወታደሩንዙሯውን በሠልፍ አቆሙት ሰልፈኛውም አረማውያኑ እርስበርሳቸው አምባጓሮ እንዳያነሱ በጥንቃቄ ይጠባበቃቸው ነበር ከዚህም በኋላ ባላባቶቹን ጺብእ አንስተው የተዋጉትን አቅርቡ ብለዋቸው ጠበኞቹም ቀርበው እንደተያዙ ቆይተዋል ክቡራን የሆናችሁ የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ዓዳሎች ኃያላን ሕዝብ ናቸው ኑሮዋቸውም በበረኃ ነው በየዓመቱ በአዳል ዘመቻ የሚሞተው ተክርስቲያንና ተአዳል ሕዝብ አንድሺ ሳይሆን አይቀርም ይህ መሆኑ ከሥልጣኔ ትምህርት ማነስ ነውና ለወደፊቱ በቆላ አገር በድሬ ዳዋ በአዋሽ በጨኖ በእሬሳ ይኸን በመሰለ ለአዳል አገር አቅራቢያ በሆነ አውራጃ ሁሉ የተማሪ ቤት ማቆም ያስፈልጋል ሁለተኛ በአዳል አገር ጠበንጃና ጥይት እንዳይገኝ ማናቸውም የጦር መሣሪያ በአዋጅ እንዲገባ ወደፊትም እንዳይሠራ መከልከል ያስፈልጋል የጦር መሣሪያቸውን ከስረከቡ በኋላ ከሥር ዓመት በታች ያሉትን ሕፃናት በቆላ አገር በቆመው ተማሪቤት ማስተማር ነው ወንድሞቻችንን አእምሮአቸውን አበርትተን በሥልጣኔ ብናስኬዳቸው ጥቅማችን ነው ብንጎዳቸውም ጉዳታችን ነውና ወድሞቻችንን አንድነት በፍቅር ሰንሰለት ለማስተሣሠር እንጣጣር

ዳዊት ንጉሥም ናሁ ሠናይ ወናሁ አዳም ሶበ ይሄልዩ አኀው ኅቡረ ብሏል

አጋፋሪ ዘቀለ

የከተማ ወሬ

የጭከና ሥራ

ነሐሴ ፲፰ ቀን ከሌሊቱ በ፲፩ ሰዓት ከአባታችን ሰፈር አብጼጌ የሚባሉ አንድ መነኩሴ ያባታችን መስቀል ያጋር የነበሩ ቤት ክርስቲያን እሄዳለሁ ብለው ከመኝታቸው ተነስተው የቤታቸውን ደጃፍ ሲከፍቱ አንድ አበበ የተባለ ጐረቤታቸው በቦታ ድንበር ይጣሉ ኖሮ ጠመንጃውን አጉርሶ ሲንደረደር መጣና ተኵሶ በጥይት መታቸው ። እሱም አመልጣለሁ ብሎ ሲሮጥ ዘበኞች ተከታትለው ይዘዉት እወህኒ ገብቷል ። አባጼጌም ወዲያው ነፍሳቸው አልወጣም ነበርና ዘመዶቻቸውና የንስሐ ልጆቻቸው ወደ ሐኪም ቤት አመጡአቸው ነገር ግን የቈሰሉት ከክፉ ቦታ ላይ ስለ ሆነ ሳይቈዩ ወዲያው አረፉ ። እንዲህ ያለውን የጭካኔ ሥራ የሚሠራ ሰው እንዳያመልጥ እግዚአብሔር አሳልፎ ለቅጣት ይሰጠዋል ።

የባቡር ጥቅም ።

አሁን በክረምት እህል እየተወደደ በመሄዱ እህል የሚሸምት ሰው ሁሉ በጣም ቸሮግት ነበር። ግን መንግሥት የሕዝቡን ችግር አይቶ ልክ የሌለው ማሽላ ከውጭ አገር በባቡር አስመጥቶ የባቡሩን ማገሬፊያ እህል ሞላውና ለሰው ሁሉ በርካሽ ዋጋ (አንዱን ጆንያ ማሽላ በስድስት ብር) እንዲሸምት ፈቀደለት ሸማቹም ሁሉ በእርሻ ሚኒስቴር በኩል ከዚያ እየሸመተ እህል አገኘና የገበያው እህል የሚሸምተው ስላነሰ እህሉና ዶቄቱ ዋጋውን ዝቅ እያደረገ ይሸጥ ጀምሯል።

የባቡር ይቅርና እስከ ዳር አገር የካሚዮን መንገድ ተገኝቶ እዳር አገር ያለ እህል ሁሉ ወደ ከተማ የሚመጣ ቢሆን በከተማ አቅራቢያ ያለ ገበሬና ቸርቻሪ እንደ ብዛቱ ልክ እህልን ባላስወደደብንም እንግዲህ የባቡር መንገድ በየዳር አገሩ እስኪዘረጋ ድረስ የካሚዮን መንገድ በቶሎ በየአውራጃው እንዲሠራለት ሕዝቡ ወደአገረ ገዦዎች ተስፋ እያደረገ ይጠብቃል ።

ማስታወቂያ

እኔ ታምሜ ሆስፒታል ተኝቼ ሳለሁ የማህተሜ ሳጥን ቊልፉ ተሰብሮ ማህተሙ ጠፋ ስለዚህ ከኔም ብድር ያለው ሰው እንዳለ በሌላም ምክንያት የተዋዋልኩት እንዳለ ከሁለት ሳምንት ወዲህ እንዲአመጣ አስታውቃለሁ ሐምሌ ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፩

ፊ ቀነኛ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ሐኪም የመጣ ዶክተር ኤፍ ኤርል ፌሬደሪለብ የሚባል በጀርመን አገር በህክምናው የተሸለመና የምስክር ወረቀት ያለው ከልጅ ይመኙ ቤት ውስጥ የመድኃኒት ቤት ከፍቷል ። የመድኃኒት መስሪያው ቤትም የሚገኘው በጋኖታኪስ ቤት ያለው መንገድ ወደ ግቢ የሚወስደው እፈርናዲስ ክት ሰፈው ቤት በታች ያለ አዲስ ፎቅ ከሆቴል በሎላጐስ ትይዩ የሆነው እምድር ቤቱ ያክማል ። ከመድኃኒት ቤት ለመታከም የሚፈልጉ ሰዎች ሐኪሙን ከ፪ ሰዓት ከጧዋቱ እስከ ፭ ሰዓት ተኩል ይገኛል ። ከ፮ ሰዓት በኋላ ከ፲ ሰዓት ጀምሮ እስከ ፲፪ ሰዓት ከመድኃኒት ቤት ያክማል ። ነገር ግን ከመለከትነው ሰዓት በተቀር ሌላውን ጊዜያት ሰዓታቶች እቤቱ ያክማል ። ቤቱም ያለበት አቶ አድነው ቤት ውስጥ ነው ከመድኃኒቱ ቤት ትንሽ ወረድ ብሎ ።

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፱ ብር ተኩል
ዝባድ	፩ ወቄት	፫ብር ተኩል
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፯ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፴ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፬ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፰ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፰ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፹፫ ብር
፡ ፡ ባለሰይጣን	፡ ፡	፻፹፩ ብር
፡ ፡ ባለ ድመት ።		፻፸፱ ብር
፡ ፡ ባለአህያ	።	፻፴፯ ብር
፡ ፡ ባለሳቢ ግመል	።	፻፵ ብር
ባለ አንበሳ	፡ ፡	፻፸፱ ብር
ሱካር	፩ ጁኒያ	፴፮ ብር
ቻይ	፩ ነጥር	፮ ብር

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፱ ፍራንክ ፲፱ ሳንቲም
አንድ ብር	ሊሬ ፲ ከ፳፯ ሳንቲም
በአንድ ጊኒ	፲ ብር ፯ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፸፭ ብር

ዓለም ሱቅ ፲፪ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃሸከላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

COGNAC SaEaA.METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሰ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



ዝኒት የእጅሰዓት

በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

“ሩግቢ” የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል “አሬቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ” ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ፤በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መጣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ፤ ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፡ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ኦቤርላንድ



ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሽ ኦቤርላንድ ኦቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጦጦን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባ ኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኜቶና ባለባተሪ ነው ካምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ ኦቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል «ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው

ወዲያውም የኦቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

ማስታወቂያ

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲	ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር	ፀ	ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
የዓለም ጅዮግራፊ በአማሪኛ ደኅና ጥራዝ ዋጋው	፯	ብር
» » » መናኛ ጥራዝ ዋጋው	፫	ብር
ደግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፫	ብር
ኅሐ ጽባሕ	፫	ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫	ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫	ብር
የሕይወት ታሪክ	፪	ብር ተኩል
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪	ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪	ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትርሚጓው	፪	ብር
የቁጥር ትምርት	፩	ብር
ያማሪኛ ሰዋስው	፩	ብር
ወዳጄ ልቤ	፩	ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን		አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ		አላድ
አጭር የዓለም ታሪክ		አላድ
ያማሪኛ ፊደል		ሩብ
አሳብና ምኞት		ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት		ሩብ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፪	መ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር	፪	መ
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ		ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶ ግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ		ሩብ

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ፤ የልብ ፤ የደረት ፤ የጉበት ፤ የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ፤ የቂጥኝና የቋቁቻ፤ የሚያዋልድ፤ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል

እደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ሱቅ ነው ።

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ ።



ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በካፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በካፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው ።

ጉድየር ግዙ





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድየር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያደጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው ። በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድየር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

አራተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፴፭
4 me ANNÉE № 35

ሐሙስ ነሐሴ ፳፬ቀን ፲፱፻፳ ዓ ም።
JEUDI 30 AOUT 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ጸሐፊተኑ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ስፈልግ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የኢትዮጵያ መንግሥት የንግድ ሚኒስቴር ።

አዋጅ ።

ስለ ንግድ አካሔድ ወደፊት የሚጸና ደንብ

የንግድ አካሔድ ለማጽናት የንግድ ሚኒስተሩ ያቆሙትን ደንብ ከዚህ በታች እንደሚፈጸም ተደንብቷል ።

ይኸ አዋጅ ከወጣ አንስቶ እስከ አንድ ወር ድረስ ነጋዴና የንግድ ማኅበር ያቆመ ከንግድ ሚኒስቴር መጻፊያ ቤት እየመጣ ስሙን እንዲያጽፍ ይሁን ።

፩ተኛ ።

መጀመሪያ ነጋዴው ወይም በወኪል የንግድ ቤቱን በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ሲያቆም አስቀድሞ የንግድ ቤቱን ስምና የወኪሎቹን ስም ከንግድ ሚኒስቴር መጻፊያ ቤት መጥቶ ማጻፍ አለበት ።

፪ተኛ ።

የንግድ ቤቱን ባቆመበቱ ሥፍራ ሁሉ ንግዱን ወይም ወኪሎቹን በለወጠ ቁጥር እየወጣ ከንግድ ሚኒስቴር መጻፊያ ቤት አኳኋኑን ያጽፍ ።

፫ተኛ ።

ከንግድ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት በሚያገኘው ሁለት የደንብ ጽሕፈት ወረቀት ጠያቂው ነጋዴ ጽፎ አንዱ ከንግድ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት ይቀመጣል ። ፪ተኛውን ይወስዳል ። ይኸውም የተጻፈው ዴክላራሲዮን የሚፈረመው በነጋዴውና የንግድ ማኅበርየሆነ እንደሆነ በወኪሉ ባድሚኒስትራተሩ ነው።

፬ተኛ ።

ነጋዴዎች መጀመሪያ ስማቸውን ከንግድ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት በመዝገብ ሲያጽፉ ፲ ፲ ብር ይከፍላሉ ። ነጋዴዎች ወይም የንግድ ማኅበረተኞች የሆኑ ካፒታላቸው (ገንዘባቸው) ከ፲ሺህ ብር የበለጠ እንደሆነ በሺህ ብር አንድ ትሙን ይከፍላሉ ።

፭ተኛ ።

ማንም ነጋዴ የሆነ በንግድ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት ከንግድ መዝገብ ላይ ስሙን ለመጻፍ የተደነባውን ደንብ የተላለፈ ከ፳ ብር እስከ ፪፻ ብር ድረስ ይቀጣል ።

፮ተኛ ።

በስሕተት የሆነ ነገር ሁሉ በጥፋት አይቆጠርም ግን በተንኰል አውቆ ስሙን አዘዋውሮ ወይም የማታለል ነገር በንግድ ደብተር ላይ ያጻፈ ከ፻ እስከ ፪ሺህ ብር ድረስ መቀጮ ይከፍላል ።

፯ተኛ ።

በዚህ በንግድ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት የወጣውን ደንብ ማንም ለማንበብ ፍቃድ ያለው ነጋዴ ሁሉ አንዳንድ ወረቀት ሊወስድ ይችላል ፤

ተጻፈ አዲስ አበባ ነሐሴ ፲፱ ቀን ፲፱፻፳ ዓ ም ።

ነጋድራስ መኰንን የንግድ ሚኒስትር ።

DECRET DE MISE EN VIGUEUR DU REGISTRE DU COMMERCE

Son Excellence le Ministre du commerce, afin de mettre en vigueur le Registre du commerce fondè au Bureau du Ministère du Commerce;

DECRETE

I

Que dans le délai d'un mois à partir de la publication du présent avis tous les commerçants individuels et toutes les sociétés commerciales doivent se faire inscrire au Registre du Commerce établi à cet effet au Ministère du Commerce.

II

Que l'immatriculation ou inscription primitive devront être effectuées toutes les fois qu'un commerçant aura son principal établissement en Ethiopie ou une succursale ou agence.

III

Que tous les changements ou modifications se rapportant directement aux faits qui ont pu être consignés dans l'immatriculation devront donner lieu à des modifications ou à des mentions complémentaires.

IV

Que la demande d'immatriculation sera établie sur papier en double exemplaire sous une formule délivrée aux intéressés par le Bureau du Registre du Commerce.

La déclaration sera signée par le commerçant ou, si elle concerne une société, par tous les gérants ou tous les administrateurs.

V

Que pour chaque immatriculation une somme de DIX thalers sera perçue augmantée; lorsqu'il s'agira d'une société commercial dont le capital est supérieur de 10. 000 thalers d'une taxe proportionnelle de UNE piastre par mille thalers de capital social.

VI

Que toute infraction à l'immatriculation au Registre du Commerce entrainera une ammade de 20 à 200 thalers

VII

Que toutes les inéxactitudes involontaires n'entraineront aucune sanction.

Qne toutes les inéxactitudes volontaires soit: toute inéxactitude donnée de mauvaise foi en vue de l'immatriculation ou de l'inscription dans le Registre du Commerce sera punie d'une amende 100 à 2.000 thalers.

VIII

Que le Bureau du Registre du Commerce tienne à la disposition des intéressés le Règlement légal concernant le Registre du Commerce.

Addis-Abeba, le 25 Août 1928

Le Ministre du Commerce.
NEGADRAS MEKONNEN.

ያዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ።

ስለ አቶሞቢልና ስለ ካሚዎን የመንገድ ተላለፊዎች ።

የተሰጠ ደምብ ።

የአቶሞቢል ነጂዎች ሁሉ የመንገድን ደምብና ያካሄዱን ሥርዓት ጠብቀው መሄድ የሚያስፈልጋቸው ስለሆነ ስላካሄዳቸው ቀጥሎ የተጻፈውን ደምብ ሰጥተናል ።

፩ኛ ። የመንገድ ተላላፊዎች በአቶሞቢልና በካሚዎን የሚሄዱ ሁልጊዜ የመንገድን ቀኝ መያዝ አለባቸው ።

፪ ። ምናልባት ጥቂት የሚያስቸኩል ጉዳይ ኖሯቸው ከወደ ኋላ መጥተው ወደ ፊት ለመቅደም የሚፈልጉ ባለ አቶሞቢሎች የመጡ እንደሆነ ከፊት ያለው ባለ አቶሞቢል ቀኙን መንገድ ይዞ እየጠበቀ በስተግራው በኩል የላይኛውን ማሳለፍ አለበት ነገር ግን የኋለኛው መንገደኛ ፈጥኖ ወደፊትም ስላለፈ ለፍጥነት የተሰጠውን ደምብ እንዳይተላለፍ መጠንቀቅ ይገባዋል ።

፫ኛ ። በየመንገድ ላይ ምናልባት መንገድ ፈርሶ ሲሠራ ሳለ ስለ ተላላፊዎች ማስጠንቀቂያ ምልክት የተደረገ ወይም በመንገዱ ላይ ለጊዜው ለማሳለፍ የሚከለክል የቆመ ነገር የተገኘ እንደሆነ ባለ አቶሞቢሎች በጠገቡ ሲያልፉ ቀኙን መንገድ መያዝ አለባቸው ።

፬ኛ ። መዛወሯና ማዕዘን የሆነ መንገድ ባለበት ቦታ ላይ ማቆም ተከልክሏል ።

፭ኛ ። በየመንገዱ መገናኛ ላይ አቶሞቢሎችን ወደ ኋላ ማስኼድ ተከልክሏል ።

፮ኛ ። በመዛወሪያ መንገድ ላይ ማናቸውንም አቶሞቢልና ጋሪም አቶቢስክሌትም ቢስክሌትም ቢሆን ይህንንም የመሰሉ ተላላፊዎች ሁሉ የመንገድ መዛወሯያ ቦታ ላይ ለማስቀደም አልተፈቀደላቸውም ።

፯ኛ ። የአቶሞቢል አካሄድ ፈታሽ ዘበኞች ተላላፊዎችን ባለ አቶሞቢሎች እንዲቆሙ ባዘዙ ጊዜ በፍጥነት ማቆም አለባቸው ።

፰ኛ ። በመንገድ ላይ የአቶሞቢሎችን መንገድ የያዙ ሰዎች ወይም መንገድን የሚከለክሉ ማናቸውም ከብቶች አጋ

ጣሚ ሆነው በመንገድ ላይ ክልተገኙ በቀር ጡሩንባ መንፋት አያስፈልግምና ክልክል ነው ።

ይህም ስለ ተባለ ከመንገድ ላይ እንዲዘሩ በጡሩንባ የሚታዘዙ ከብቶቹ የአቶሞቢሉ ጡሩንባ በተነፋ ጊዜ የሚደነብሩ የሆነ እንደሆነ ባለአቶሞቢሎቹ ወዲያው በፍጥነት እንዲያቆሙ ታዘአል ።

፱ኛ ። ባለ አቶሞቢል ሁሉ ሲተላለፍ ሳለ በመንገድ ላይም ሲገናኝ በቀኝ በሚያልፈው አቶሞቢል ውስጥ ያሉት ነጂዎች ሁሉ ቀጥሎ የተጻፉትን ምልክቶች ይሰጣሉ ።

፩ኛ ። ቀኝ ክንድን ወደ ቀኝ ግድም ቀጥ አድርጎ መዘርጋት።

፪ኛ ። ክንድን ወደ ቀኝ መታጠፊያ ከፍ አድርጎ ወደ ቀኝ ኋላ ወገን እያጠፉ መዘርጋት ።

፫ኛ ። ወደ ግራ መንገድ ለመታጠፍ የፈለጉ እንደሆነ ቀኝን ክንድ ወደ ግራ ወገን እያጠፉ ማሳየት ።

፬ኛ ። ከወደ ኋላ የሚመጣውን አቶሞቢል ለማስቀደም ወይም ደግሞ ከወደፊት የሚመጣውን አቶሞቢል ለማሳለፍ በሚሆነው ጊዜ ቀኝ እጁን ወደላይ አጠፍ አድርጎ አንስቶ በማህል እጁ እያወዛወዘ ወደሚሄድበት በታ መምራት ነው ። ነገር ግን ከዚህ በላይ የተሰጡት ምልክቶች በቀኝ ፍሬን ለሚነዱት አቶሞቢሎች ስለሆነ እንደዚሁም ደግሞ በግራ ፍሬን ለሚነዱት አቶሞቢሎች በቀኝ ክንድ ዓይነት ምልክት በግራ እጃቸው እያወዛወዙ ከዚህ በላይ የተጻፈውን ምልክት መስጠት አለባቸው ።

፲ኛ ። ማናቸውም አቶሞቢልና ጋሪ ሠረገላ ቢስክሌትም አቶቢሲክሌትም ቢሆን መገናኛ በሆኑ መንገዶች ላይ ሲደርስ ፍጥነቱን በጣም ቀንሶ ዝግ አድርጎ ማስኼድ ነው ።

፲፩ ። የአቶሞቢሎችን ነጂዎች ፍሬን በመልካም ጥንቃቄ እንዲይዙ ።

፲፪ ። ባንድ ጉዳይ ምክንያት ወይም ባንድ ነገር አቶሞቢሎችን በመንገድ ላይ ማቆም የሚያስፈልግ የሆነ እንደሆነ ከመንገድ ዳር ወደ ቀኝ ዘወር አድርገው እንዲያቆሙ ግዴታ አለባቸው ።

፲፫ ። ስለ ማናቸውም ጉዳይ ሁሉ በከተማ ውስጥ የሚተላለፉት ባለአቶሞቢሎች ከበር ግቢ ባለው በገበያው ስፍራ ውስጥ በሰዓት ከሥራ ሁለት ኪሎ ሜትር የበለጠ ከገበያው በር ውጪ ባለው ስፍራ ብዙ ሕዝብ በሚተላለፍባቸው መንገዶች ላይ በሰዓት ከ፳ ኪሎ ሜትር የበለጠ ብዙ ሕዝብ በማይተላለፍባቸው በከተማ ዳር ዳር በሆኑት መንገዶች ላይ ደግሞ በሰዓት ከ፴ኪሎሜትር የበለጠ እንዳያስኼድ ፈጽሞ ክልክል ነው ።

፲፬ኛ ። ማታ ጀንበር ከጠለቀ ከሥራ ሁለት ሰዓት በኋላ ማናቸውም አቶሞቢል ሁሉ ከኋላውና ከፊቱ መብራት የሌለው እንዳይሄድ ክልክል ነው ።

፲፭ኛ። ከምሺቱ ከራት ሰዓት በላይ በአቶሞቢል የሚተላለፉ ሰዎች የተገኙ እንደሆነ ለአቶሞቢል ሥራ አከሄድ የታዘዙት ፈታሾች ወይም ዘበኞች ከተላላፊዎቹ ባለ አቶሞቢሎች ወገን ዘበኞቹ ጠርጥረው የውስልትና ሠሪዎች በአቶሞቢል ውስጥ አለመኖራቸውን ለማወቅ የፈለጉ እንደሆነ የማቆሚያ ትእዛዝ ሰጥተው አቁመው ለመፈተሽ ይችላሉ ።

፲፮ኛ። ማዘጋጃ ቤት ለአቶሞቢል ማቆሚያ ተራ እንዲሆን በጽፈት ካመለከተው ሥፍራ በተቀር ክልታዘዘው ሥፍራ ላይ ባለከራዮች እንዳያቆሙ ክልክል ነው ።

፲፯ኛ ። የከራይ አቶሞቢል የራሱም አቶሞቢል ቢሆን ወይም እራሱ አከራይቶ ከማናቸውም ሱቅ ደጃፍ ሄዶ በቆመ ጊዜ ብዙ ጊዜ ለማቆም አልተፈቀደለትምና በቶሎ ጉዳዩን ጨርሶ ለመጪዎች ሥፍራውን እንዲለቅ ያስፈልገዋል ።

፲፰ኛ። በማናቸውም አቶሞቢል ቢሆን ለሰው መቀመጫ ሆኖ ከተወሰነው ልክ በላይ በአቶሞቢል ላይ ትርፍ ሰዎች እንዳይቀመጡ ፈጽሞ ክልክል ነው ፡ ለሰው መቀመጫ ከተወሰነው ሥፍራ በላይና በአቶሞቢሉ መቀመጫ ግራና ቀኝ ባለው ሥፍራ ላይም እንዲሁም ደግሞ ለሰው መቀመጫ ሆነ ብሎ ከተሠራለት አቶሞቢል በቀር በአቶሞቢሎች ላይ ሌላ ትርፍ ሰው እንዳይቀመጥና እንዳይንጠለጠል ክልክል ስለ ሆነ በትርፍ የተቀመጡ ሰዎች የተገኙ እንደሆነ ለዚህ መቀመጫ ነጂው ኃላፊ ነው ።

፲፱ኛ ። ከዚህ በላይ ባስራ ስምንቱ ክፍሎች የተጻፉትን የአትሞቢሎች አካሄድ ደምቦች ያልጠበቀና ያልፈጸመ ነጂ የተገኘ እንደሆነ በዘበኞች ተይዘ ወደ አቶሞቢል አካሄድ ደምብ ተጠባባቂ ጽሕፈት ቤት መሄድ አለበት ።

የአቶሞቢል ሥራ ጽፈት ቤት ዲሬክተር ፡
ፊርማ ፡
እነዚህ ፲፱ የደምብ ክፍሎች እንዲፈጸሙ አዝዣለሁ ።
የዋና ምርመራ ጽፈት ቤት ሹም ።
ፊርማ ።
እነዚህ ፲፱ የደምብ ክፍሎች እንዲፈጸሙ አዝዣለሁ ።
የከንቲባ።
የከንቲባ በታች ፊርማ ።
ፊርማ ።

እነዚህ በፈረንሳዊና ባማርኛ የታተሙ የአቶሞቢል ደምቦች በአቶሞቢሉ ውስጥ በነጂው ፊት ለፊት በመስታዎት ሆነው እንዲቀመጡ ደምብ ሆኑዋል ።

CODE DE ROUTE.

A distrbuer aux detenteurs de permis de circulation pour y être annexè

Toute Conducteur d'automobile doit connaitre et suivre le "Code de la Route,, et les règles de courtoisie de la route dont les plus importants sont

1) Tenir le droite.

2) Faire place la voiture qui va à une plus grande vitesse.

3) Tenir la droite en passant près des refuges en général et auter obstacle fixe.

4) Ne pas stationner aux tournants au aux coudes.

5) Ne pas employer la marche arrière dans les rues de grands traffic.

6) Ne jamais dépasser une autre voiture dans un tournant.

7) Arrêter immédiatement, a) sur la demande de la police,

b) àla suite d'un accident quelconque.

8) En s'approchant des obstales n'employer la trompe que lorqu'il est nécéssaire. On ne doit pas employer continuellement et sans nécéssité.

9) Employer les signaux suivant dans les voitures" Conduite à Droite"

a) Arrêter avant-bras droit vértical.

b) Virage à droit-bras droit horizontal.

c) Virage à guache-bras droit horizontal replié ensuite vers la gauche

d) Ralentir-bras droit horizontal, la paume de la main en dessous avec mouvement alternatif en sens vertical

e) Invitatio à dépasser bras-droit tendu au dessous de l'horizontal avec mouvement de derrière en avant

nota Pour les voitures „Conduites à Gauche" le bras gauche doit être employe.

10) Croisement des routes.

Toutes voitures débouchantsur une route principal doit ralentir et céder le pas aux traffics de la grande route.

11) Entretenir les freins en bon ètat.

12) Dans le cas d'une arret importante dans les rues fréquentées, se renger antant que possible à sa droite

13) Dans tous les cas la vitesse des autos ne peut dépasser dans la ville, que 20 kilomets par heure, et hors de la ville, 30 kilometrs. par heure et à ARADA 12 kmts,

14) Le soir après six heures tous les autos doivent porter de dèrrière et de devant des éclairages.

15) Stationner les autos dans une place que leur permet par un avis placardé dans le lieu.

16) Ne pas arrêter les autos taxis devant les magasins des marchandises plus que 10 minutes, et les autes privés 30 minutes.

17) obéir instrictement aux garde-autos

18) Tous les autos ne sont pas permis de prendre desclients plus que le nombre des laces réglementaire de leurs autos.

19 Les nuit aprés heures, les agents de la police et de Roulage ont le drot de vérifier les autos en cas de soupçons.

Les conducteurs qui ne se soumetteront pas à ces règlementsseront arrétès par les agent de bureau de Bureau de Roulage et seront obligès de venirau Bureau

Signé.

Chef de Bureau Roulage.

Lu et approuvé.

Chef de bureau de l'inspection général.

j'ordonne l'application de la présente.

Gouverneur de la ville d'Addis abeba.

Le Directeur du Gouvernerat.

ስለ ክቡር አቶ በቀለ ዛማኔልና ስለ ባለቤቱ ሞተ ።

በነሐሴ ፳፪ ቀን ፲፱፻፳ ዓ ም ማክሰኞ ከጧቱ በ፩ ሰዓት ሲሆን ከቤቴ ተነስቼ ወደ ቀበና ሰው ለመጠየቅ ስሄድ ከአፈ ንጉሥ ነሲቡ ድልድይ በላይ ከፍርድ ቤት አጠገብ ስደርስ አቶ ወልደ ማርያምንና ነጋድራስ እሼቴን በአቶሞቢል ውስጥ ሆነው በፍርድ ቤት መንገድ በኩል ሲሄዱ አገኘኋቸው ነገር ግን የአቶሞቢሉ ፍጥነት ራቀኝና ለመጠየቅ ስላልተመቸኝ እንዲያው ሰላምታ ብቻ ሰጠኋቸውና አለፉ በልቤ ግን ምናልባት የታመመ ሰው ይዘው ወደ ሆስፒታል መሄዳቸው ይሆን ብዬ ወደቀበና የምሄድበትን ጉዳዬ ተውሁና ወደሆስፒታል ሄጄ ብጠይቅ አቶ በቀለ ዛማኔል ከነሚስቱ ሆነው በአቶሞቢሉ ውስጥ ተቀምጠው ሲያቃስቱ ደረርስሁ በምን ምክንያት እንደ ሆነ ነጋድራስ እሸቴንና አቶ ወልደ ማርያምን ብጠይቃቸው በዚህ ሰሞን ስለውርዴንትበሽታ የመርፌ መድኃኒት ለማድረግ ይመላለሱ ነበር ሁለት ጊዜ ያህል ደኅና ተወግተው ትናንትና ብቻ የተወጉት መርፌ ሰውነታቸውን አሳብጦት ቢያድር ተቸግረን ለሐኪሙ ለማስታወቅ አመጣናቸው አሉኝ ሐኪሙንም ለጊዜው እንደ ደረስን ብንጠይቀው የመግቢያው ሰዓት አልደረሰ ኑሮ እስከ ፫ሰዓት ድረስ ጠበቅን ወዲያው ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴን ለዚሁ ነገር በስልክ አስታውቀናቸው ነበርና በፍጥነት በአቶሞቢል እንደ መጡልን ሐኪሙም በስተኋላ መጣ ።

ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ለሐኪሙ እንደ ነገሩት ወዲያው በፍጥነት የበሽተኛ መመርመሪያ በሚባለው ቤት እየታቀፍን አገባንና ወደ ውጪ ተመለስን ሐኪሙ ግን ለዚህ ነገር የሚያስፈልገውን አይቶ የማይሆንለት ቢሆን ወደ ልዑል ተፈሪ መኰንን ሆስፒታል እንድንወስድ ወረቀት ጽፎ ሰጠንና ይዘናቸው ሔድን ይህ ሁሉ ሲሆን አቶ በቀለ ዛማኔል እንደ በቱ ርቱዕ ነበርና ቀስ ቀስ እያለ በዚህ በኩል ወጋኝ በዚህ በኩል ቆረጠኝ እያለ ያነጋግረን ነበር ከዚህ በኋላ እሆስፒታሉ

እንዳገባነው አራት ሰዓት ተኩል ሲሆን እኔ ወደ ሥራ ተቻኩዬ ሔድሁ ።

ሐኪሙ ግን በሽታውን አይቶ ከመረመረ በኋላ አቶ በቀለ ዛማኔል ምንም የመዳን ተስፋ እንዳያገኝ ተናገረ አሉ ።

ስለዚህ ወዲያው ለ፮ ሰዓት ሩብ ሰዓት ያህል ሲቀርው አረፈና በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በብዙ ሐዘንና ልቅሶ ተደርጎለት ፲፩ ሰዓት ተኩል ሲሆን ተቀበረ ። ባለቤቱም ደግሞ እርሱ ከሞተ በኋላ በሐኪም ቤት አንድ ቀን አድራ ነሐሴ ፳፫ ቀን አረፈች ።

የአቶ በቀለ ዛማኔል ሞት በድንገት ስለሆነ እርሱ ከመጐዳቱ ይልቅ ለመንግሥት እንዴት ያሳዝን ይሆን? በቤተ ክርስቲያን ሥራ ማገልገል የዠመረ እንደሆነ በቃለ እግዚአብሔር ደስ በማሰኘቱ ሁለጊዜ ሽልማት አግኝቷል ። በያዘው የመንግሥት ሥራ የሆነ እንደሆነ ሥራ ማከናወኑና የሕዝብን ጉዳይ በመጨረሱ ደስ ያሰኛል ። የኛ ሐሳብ አቶ በቀለ ዛማኔል ብዙ ዘመን ቈይቶ መንግሥቱንና አገሩን ይረዳል ነበር ። ዳሩ ግን ምን ይደረጋል የሰውና የእግዚአብሔር አሳብ የተራራቀ ነውና መንግሥቴን አገለግላለሁ ፤ መንግሥቴን እረዳለሁ እያለ ሲመኝ ሳያስበው ድንገት በመሞቱ ለሁላችን የሚያሳዝን ነው ።

አሁንም ልዑል እግዚአብሔር ብድሩን አይቶ የሰማይ ቤቱን መንገድ ቀኙን ይምራው ስል ነገሬን እጨርሳለሁ ።

የብርሃንና ሰላም እንባቢ ኃይለ ኢየሱስ ።

ወካዕበ መጽአ አለቃ መርሻ ዘውእቱ መርስዔ ኀዘን ምስለ ወልዱ ፍቅረ ሚካኤል ወቦአ በከመ ልማዱ ። ቤተ ማኅተም ዘልዑል ተፈሪ መኰንን ወራሴ መንግሥት ዘኢትዮጵያ ። ወተማየጠ መጻሕፍተ ወእንዘ ይወጽእ እምህየ ባረከ ወይቤ። ይትባረክ እግዚአብሔር

እምላከ አበዊነ ስቡሕኒ ውእቱ ወልዑልኒ ውእቱ ለዓለም

ሲራክ ለለዓሙ ። አመ ይብል ወልድየ ዘኢወለደ ።

ጽድቀ ጥያቄሁ ያእምሩ እመኒ ሰብአ ጉልቄ ትውልድ ሐተቱ

ወልደ ሲራክ አንተ በአማን ተፈሪ ባሕቲቱ ።

ከመ ለሊሁ ያጠይቅ ልደቶ እምነ አበው ፪ቱ።

እስመ ወልደ አብርሃም በጊሩቱ ።

ወቀዳሚ በኵሩ ለሲራክ በአዕምሮቱ ።

እንዘ እሙ ኢሐተ ዘውዲቱ ።

አለቃ መርሻ ዘውእቱ መርስዔ ኀዘን ።

ያገር ውስጥ ወሬ ።

ክቡር ደጃዝማች መኰንን ወሰኔ በወለጋ በግዛታቸው ገባሩ የሚከፍለውን ግብር እንዳቀለሉለትና ዳኝነቱን በሥርዓት እንዳደረጉለት ገባሩ ሁሉም ደስ ብሎት እንዳመሰገነ ከደንቢዶሎ አንድ ወዳጃችን ጻፈልን

ደግሞ ከሰዮ ገምቤላ ድረስ ያለውን መንገድ ለአቶሞቢል እንደሚስማማ አድርገው እንዲሠራ ያስባሉ እየተባለ ይወራል

ማስታወቂያ ።

አዲስ ሐኪም የመጣ ዶክተር ኤፍ ኤርል ፌሬዶሬለብ የሚባል በጀርመን አገር በህክምናው የተሸለመና የምስክር ወረቀት ያለው ከልጅ ይመኙ ቤት ውስጥ የመድኃኒት ቤት ከፍቷል ። የመድኃኒት መስሪያው ቤትም የሚገኘው በጋኖታኪስ ቤት ያለው መንገድ ወደ ግቢ የሚወስደው እፈርናዲስ ከት ሰፊው ቤት በታች ያለ አዲስ ፎቅ ከሆቴል በሉላጐስ ትይዩ የሆነው እምድር ቤቱ ያክማል ። ከመድኃኒት ቤት ለመታከም የሚፈልጉ ሰዎች ሐኪሙን ከ፪ ሰዓት ከጧዋቱ እስከ ፭ ሰዓት ተኩል ይገኛል ። ከ፮ ሰዓት በኋላ ከ፲ ሰዓት ጀምሮ እስከ ፲፪ ሰዓት ከመድኃኒት ቤት ያክማል ። ነገር ግን ከመለከትነው ሰዓት በተቀር ሌላውን ጊዚያት ሰዓታቶች እቤቱ ያክማል ። ቤቱም ያለበት አቶ አድነው ቤት ውስጥ ነው ከመድኃኒቱ ቤት ትንሽ ወረድ ብሎ ።

ያዲስ አበባ ገባያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፯ ብር ተኩል
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፮ ብር ተኩል
ዝባድ	፩ ወቄት	፫ ብር ተኩል
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፹ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፬ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፰ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፵፪ ብር
፡፡ ባለሰይጣን	፡፡	፻፵፩ ብር ተኩል
፡፡ ባለ ድመት ።		፻፴፭ ብር
፡፡ ባለአህያ	።	፻፹፯ ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል	።	፻፺ ብር
ባለ አንበሳ	፡፡	፻፴፱ ብር
ሱካር	፩ ጁኒያ	፷፯ ብር
ቻይ	፩ ነጥር	፩ ብር

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ ፲፪ ሳንቲም
አንድ ብር	ሊሬ ፲ ከ ፯ ሳንቲም
ባአንድ ጊኒ	፲ ብር ፯ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፭ ብር

ዓለም ሱቅ ፲፪ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል ።

COGNAC S.E.& A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች ቡብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው·

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድሪስ በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪከን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፥ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



አቤርላንድ



ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመ ባለውሻ አቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባ ኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባተሪ ነው ካምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማኅደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል «ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው

ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

ማስታወቂያ

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲	ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮፓ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር	፱	ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
የዓለም ጅዖግራፊ በአማርኛ ደኅና ጥራዝ ዋጋው	፮	ብር
» » » መናኛ ጥራዝ ዋጋው	፭	ብር
ዶግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፭	ብር
ኀሐ ጽባሕ	፭	ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫	ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫	ብር
የሕይወት ታሪክ	፪	ብር ተኩል
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪	ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፬	ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪	ብር
የቁጥር ትምርት	፩	ብር
ያማርኛ ሰዋስው	፩	ብር
ወዳጄ ልቤ	፩	ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን		አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ		አላድ
አጭር የዓለም ታሪክ		አላድ
ያማርኛ ፊደል		ሩብ
አሳብና ምኞት		ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት		ሩብ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፪	መ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር	፪	መ
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ		ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶ ግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ		ሩብ

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደደም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ፤ የልብ ፤ የደረት ፥ የጉበት ፤ የኩላሊት ። የዐይማት የጨብጥ፤ የቂጥኝና የቋቁቻ፥ የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል

እደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ሱቅ ነው ።

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒከላ ።

ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ ።

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በከፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በከፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው ።

ጉድየር ግዙ





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድየር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው ። በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድየር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አራተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፴፮
4 me ANNÉE № 36

ሐሙስ ጳጉሜ ፩ ቀን ፲፱፻፳ ዓ ም ።
JEUDI 6 Septembre 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ለፊስን በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ፖስታ ቤት

ምረቃ።

ነሐሴ ፳፯ቀን የፖስታ ቤት ሚኒስቴር በከተማ መካከል አሁን የቆመው አዲሱን የፖስታ ቤት ለማስመረቅ የኢትዮጵያ ሚኒስቴሮችና መኳንንቶች የውጭ አገርንም ሚኒስቴሮችና ትልልቆች ሰዎችን ጠርቶ ነበር ። በዚሁም ቀን በ፱ሰዓት ቤቱን ለመመረቅ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ልዑል የኢ. መ አ ወ ተፈሪ መኰንን እንዲመጡ ተሰምቶ ነበርና የከተማው ሰው ሁሉ ለማየት ከፖስታ ቤት ፊት ለፊት ባለው ሜዳና በየመንገዱ ዳር ተሰብስቦ በየበረንዳውና በየቤቱም መስኮት አንገቱን ብቅ ብቅ አድርጎ ሲጠባበቅ ላየውና ለተመለከተው እጅግ የሚደንቅና የሚያስገርም ነበር የፖስታው ቤትም በኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ አጊጦ ተሸልሞ ሲያዩት እጅግ ያምር ነበር ከዚህ በኋላ ትንሽ ቈይተው ግርማዊት ንግሥትና ልዑል አልጋ ወራሽ ባማረ ሰልፍ መጡና የሰላምታ ሙዚቃ ባማረ ዜማ ተመታ ከሙዚቃውም ድምጽ ማማር የተነሣ አየሩ የተናወጸ ይመስል ነበር ሰውም ከብዛቱ የተነሣ ቀርቦ ለማየት እርስ በርሱ ይጋፋ ነበር ቀኑም የገበያ ቀን ስለሆነ ሰዉ በዝቶ ነበር ከዚህ በኋላ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ልዑል የኢ. መ አ ወ ተፈሪ መኰንን ለምረቃ ወደ ተሰናዳው ፎቅ ገቡና የፖስታ ቤቱ ዋና ዲሬክተር ክቡር አቶ ብርሃነ ማርቆስ ሰው ሁሉ በየመዐርጉ የሚቀመጥበትን ቦታ አሰናድተው ነበርና እየገባ በየመዐርጉ ተቀመጠ።

በሽምፓኝም ጊዜ ክቡር ጸሐፊ ትእዛዝ አፈ ወርቅ የፖስታ ምኒስቴር የሚከተለውን ቃል ተናገሩ ።

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ።
ልዑል አልጋ ወራሽ ሆይ ።
ክቡራን የውጭ አገር መልክተኞች ።
ክቡራን ወይዛዝርና መኳንንቶች ።

በዛሬ ቀን የፖስታ የቴሌግራፍና የቴሌፎን ሥራ ቤታችንን ከመጀመሸው ቀን አንስቶ አቋቋሙን ባጭሩ እንነግራችሁ ዘንድ ጊዜ በማግኘቴ የታደልሁ ነኝ ።

ከዚህም ቀጥሎ የምናገረውን ቃል እንዳትሰለቹኝ እለምናችኋለሁ ። ስለሆነ ግን አገራቸውን ከውጭ አገር ጋራ ለማቃረብ በመጀመሸ ይህንን ታላቅ አሳብ ያሰቡትን ታላቁን ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ አጼ ምኒልክን በዚህ ክብረ በዓል ምክንያት ለማንሳት ይገባኛል ።

የሀገራችን ሊመከበት ከሚገባው ከነገሥታቶቹ አንደኛው ታላቁ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ አጼ ምኒልክ ከሁሉ አስቀድሞ ባገርም ውስጥ ሆነ ከውጭ አገር መንግሥትም ጋራ ሆነ ለመገናኘትና ለመነጋገር ማናቸውም ሰው ቢሆን ከቤተ ሰውና ከወዳጅ ከዘመዱ ጋራ ለመገናኛ መንገድ እንዲአገኝ የሚላላክበት ፖስታን አቆሙ ።

በፖስታ በኩል አንድ ዘመድ ወይም ወዳጅ ሐሳቡን የላከበትን ብዙ ጊዜም የልቡን ገልጾ ያሳየበትን ወረቀት በተቀበለ ጊዜ ከመሐከላችን ደስ የማይለው ማነው በትንሽ አንቦሎፕ ውስጥ ሆኖ ሰውነቱ ተከፍሎ እንደመጣልን ወይም ራሱ መጥቶ እንዳየን ያህል ነው ።

ፖስታ ለኛ በሀገራችን ውስጥ ላለነው ሰዎች ይህንን ያህል ልዩነት ያለው ታላቅ ሥራ ከሠራልን የተወለዱበትን አገር ትተው ለመጡ በሀገራችን ውስጥ ተቀብለን ለምናስተናግ

ዳቸው ሰዎች የሚአገላግላቸው አገልግሎት ከኛ ሺ ጊዜ የበጠ አይሆንምን ።

በእርግጥ ፖስታ ለእነርሱ የሕይወታቸው እኩሌታ ነው

በ፲፰፻፫ ዓመተ ምሕረት አስቀድሞ ፖስታው ሁሉ ከጅቡቲ ጠረፍ ሐረር ድረስ ሌሊትና ቀን በግመል እየተጫነ ደግሞ በአገርም ውስጥ በእግረኛ እየተላከ በበቅሎም እየተጫነ ይመላለስ ነበር ።

ከ፲፱፻፫ ዓመት በኋላ ግን ዳግማዊ አጼ ምኒልክ በኢትዮጵያ መንግሥት ስም የፖስታ ሥራ እንዲቆም ብለው በመልካቸው ቴምብር አሠርተው የፖስታው ሥራ ይመላለስ ጀመር ከሐረርም እስከ አዲስ አበባ የስልክ ሽቦ ተዘረጋ በመጨረሻው በ፲፱፻ ዓመተ ምሕረት በሀገራቸው ውስጥ የውጭ አገር ሰዎች ቁጥራቸው እየበዛና ንግዱም እየሰፋ መሄዱን ተመልክተው የፖስታ ሥራ እውቀት ያላቸው ሠራተኞች ከፈረንሳዊ አገር እንዲመጡላቸው የፈረንሳዊን መንግሥት በወዳጅነት ጠየቁ ።

በጥቅምት ፳፪ ቀን ፲፱፻፩ ዓመተ ምሕረት በክቡር ቀኛዝማች በየነ ይመር ሥራ ጠባቂነትና መሪነት የኢትዮጵያ ፖስታ መሥሪያ ቤት በዓለም ሁሉ የፖስታ ማኅበር ገባ በዚሁም ምክንያት አዲስ ዓይነት ቴምብር ታትሞ ወጣ ከዚያም ወዲህ የፖስታ ማኅበር በሚሰበሰብበት ጊዚያት ሁሉ የኢትዮጵያም መንግሥት ስለ ራሱ በቀጥታ መላክተኞቹን እየላከ ይወክል ጀመር ።

በ፲፱፻፲፪ ዓመተ ምሕረት ማድሪድ ላይ ደግሞ በ፲፱፻፲፮ ዓመተ ምሕረት እስተኮሆልም ላይ መላው የዓለም ሁሉ የፖስታ ጉባዔ በተሰበሰበበት መንግሥታችን መላክተኞቹን ልኮ ስለ ፖስታ የተደነበውን ከደምቡ የተለወጠውንና የተጨመረውን በጉባዔው ተቀምጠው ደምቡን ለመፈረም ቻሉ ።

ከ፲፱፻፳ ዓመተ ምሕረት ጀምሮ እስከ ፲፱፻፴ ዓመተ ምሕረት ድረስ ለዓለም ሁሉ ጉዳት በሆነው ጦርነት የተነሳ ምንም ሥራው በደምብ ቢሠራ ፖስታ ቤቱ ወደፊት ለመግፋት አልቻለም ነበር ።

ከዚያም በኋላ ከ፲፱፻፲ ዓመተ ምሕረት ጀምሮ እስከ ፲፱፻፲፮ ዓመተ ምሕረት ድረስ በዓለም ላይ ያለው የገንዘብ ለውጥ በመውጣቱና በመውረዱ የተነሣ ስለ መጣው ችግር እንደዚሁ ወደፊት ለመግፋት አልቻለም ።

ከዚህ በኋላ ግን የሥራ መሪዎቹና ሠራተኞቹ በኅብረት በመረዳዳትና በተቻላቸው ፍጹም እውቀታቸው ስለተጉበት የቀድሞው ችግር ሁሉ አለፈ ።

ነገር ግን ይህ አሁን የገባንበት ቦታ ሰፊ ሆኖ ለሥራችን ሁሉ የሚበቃን ቦታ ስለሆነና ደግሞም አሁን አዲስ በሚቆመው በኤሌክትሪኩ ሥራ ሕዝቡ በሚገባ መንገድ ለሚፈልገው ነገር ሁሉ እንደተቻለን የልቡ ሐሳብ ይፈጸምለታል ስንል ተስፋ እንዳርጋለን ።

አሁንም ወደፊት የስልኩን ሥራ እንዲሻሻል ለማድረግ ከአዲስ አበባ እስከ ጅቡቲ ተጋጥሞ ከዓለም ሁሉ የሚገናኝ አዲስ የመንግሥት ቴሌግራፍ ሽቦ ለማቆም በአገርም ውስጥ ከ፲፰ሺ ኪሎ ሜትር የሚበልጥ ስልክ ለመዘርጋት በከተማውም ውስጥ የሚያነጋግር በአዲስ ሽቦ የተሠራ ተሌፎን ለማስገባት ይህነን ሁሉ በቅርብ ቀን ለማድረግ መንግሥታችን አስቧልና ይህ በተፈጸመ ጊዜ የንግድ መገናኛ መንገድ እየሰፋና ቀጥሎም ለሀገሩ ብልጽግና ታላቅ እርዳታ ይሆናል ብለን ተስፋ እናደርጋለን ።

የሕዝብን ሥልጣኔ ውጭውን ገልጾ የሚያሳይ በአገሩ ውስጥ ባለው የመገናኛ መንገድ ነው የሚል የቆየ ምሳሌ አለ።

ይህም የመገናኛ መንገድ ከተባለው ከዋኖቹ አንደኛው ፖስታ ቤት ነው ።

ግርማዊት ንግሥትና ልዑልነትዎም በብዙ ትጋት ለመንግሥታችሁ ባደረጋችሁት እርዳታ ሁሉ ፖስታ ቤት በቅርብቀን በዓለም ሁሉ የቴሌግራፍ አንድነት ማኅበር ሊገባ ይችላል።

በ፲፱፻፲፰ ዓመትና በ፲፱፻፲፱ ዓ ከአዲስ አበባ እስከ ለቀምትና እስከ ጐሬ ከአዲስ አበባ እስከ ባሌ ከአዲስ አበባም እስከ ደሴ ፖስታ አቁመን ይመላለሳል ።

ደግሞ ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ታስቦ የቆየውን ለመፈጸም ከጥር ወር ፲፱፻፳ ዓመተ ምሕረት አንስተን አስር ኪሎ የሚመዝን ኰሊ ለማስመጣትና ለመላክ መንግሥታችን ተስማምቶ ተቀብሎታልና የቆመውን ነገር ላስታውቃችሁ በመቻሌ እጅግ ደስ ይለኛል ደግሞ እንደዚሁ በሥራችን ውስጥ ሌላ አዲስ የሚሻሻል ሥራ ለማድረግ ተስፋ አለን ።

ይህም የፖስታ የተሌግራፍና የተሌፎን ቤት የተመረቀበት ቀን መታሰቢያ ሆኖ ለዘለዓለም ክብሮ እንዲኖር ከዛሬ ጀምሮ አዲስ ዓይነት ቴምብር አውጥተናል ።

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት፤ ልዑል ሆይ ።

እነዚህ በሁላታችሁ መልክ የተሠሩ ቴምብሮች ዓለምን አቋርጠው እየዞሩ በመልክም ሐሳብ ብቻ የተመሩ ሥራቸውን በእውቀትና በሥልጣኔ መንገድ የሕዝባቸውን ተድላ መጠበቅ ብቻ የሆነ ነገሥታት በኢትዮጵያ መኖራችሁን ለሚያያቸው ሁሉ የሚናገሩ ናቸው ።

የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት መልክዎ በታተመበት ቴምብር ላይ በኢትዮጵያ ነገሥታት ማኅተም ላይ ከጥንት ጀምሮ ተጽፎ የቆየው ቃል ምዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ የሚል ቃል ተጽፎበት ይነበባል ።

ግርማዊት ሆይ የዚሁም ትርጉም የታላቁን መንግሥትዎን ችግር ሁሉ አያሸንፈ መውጣትዎን ያስረዳል ።

ልዑል ሆይ በልዑልነትዎም መልክ ከታተመው ቴምብር ላይ ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር የሚል የታወቀ የነቢዩ የትንቢት ቃል ተጽፎ ይነበባል ።

ልዑል ሆይ ሃይማኖትዎ ጥልቅ ስለሆነ መጀመሪያ እጆችዎን ወደ እግዚአብሔር ዘረጉ ደግሞ መንግሥትዎን ወደ አዲሱ ሥልጣኔ ከፍታ ለማድረስ የሀገርዎ መውደድ ፍቅር የጋለ ሆኖ የማይደክም መጣጣርዎን እየደገፈው ለታላቁም ለታናሹም እጆችዎን እንደዘረጉ ይኖራሉ ።

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ልዑል ሆይ ።

እስቀድሜ ልዑላን ሰውነቶቻችሁን ደግሞም ለኢትዮጵያ ታላቅነት ክብርና ልማትም በራሴ ስምና በመላው በፖስታ ቤት ሠራተኞች ስም ሆኜ በታላቅ ማክበርና በእሙን አገልጋይነት የማቀርበውን ምስጋና እንድትቀበሉኝ እለምናለሁ ።

ክቡራን የውጭ አገር መንግሥት መኳንንትና ሹማምንት

የሴት ወይዛዝሮችም ።

የኢትዮጵያ መኳንንቶች ።

ለፖስታ ቤታችን ምርቃት ጥሪያችንን ተቀብላችሁ ለዚህ ክብረ በዓል በመምጣታችሁ መልክም ሐሳባችሁን ይገልጽልናል

ለኛም ታላቅ ደስታችን ለፖስታ ቤታችንም ለዘለዓለም መታሰቢያ የሚሆን ክብሩ ነውና ስለዚህም ጥልቅ የሆነ ምስጋናችንን እንድትቀበሉን እንለምናችኋለን ።

ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክና ለልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ዕድሜና ጤና ለሕዝብዋም ሰላምንና ዕረፍትን እንዲሰጥልን ሕያው እግዚአብሔርን እንለምናለን።ይኸንን ተናግረው ሲጨርሱ ተጨበጨበ።

ቀጥሎም ሙሴ ቡሰን የፖስታ ቤት አማካሪ የሚከተለውን ቃል ተናገሩ ።

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ሆይ ።

ልዑል ጌታዩ ።

ክቡራን የውጭ አገር መንግሥት መልክተኞች ።

ክቡራን መኳንንቶችና ወይዛዝርቶች ።

ክቡር የፖስታ የቴሌግራፍና የተሌፎን ሚኒስቴር በተናገሩት ቃል በታላቁ ንጉሥ በዳግማዊ ምኒልክ ዘመን የዛሬ ሠላሳ ዓመት የኢትዮጵያ ፖስታ ተመሥርቶ የተጀመረበት ነገር አሳሰቡን ።

ይህ ሥራ ለሥራው ሁሉ መጀመሪያ ባይሆን እንኳን በሀገሩ ውስጥ ተሻሽሎ ቀዳሚ ሆኖ በአዲሱ ስልጣኔ መዝገብ የቆመ የፖስታ ቤት ነው ።

እኔውም ራሴ በኤሮፓ ቁጥር ከ፲፱፻፳ ዓመት አንስቼ በኢትዮጵያ መንግሥት ፖስታ መስሪያ ቤት ሥራ መሥራት ከጀመርኩ ወዲህ አሁን ዛሬ በሥራ መሪዎቹ ትጋት ሥራው ተተክክሎ ከሄደበት ቀን ድረስ ያለው የፖስታ ቤት ሥራ ይልቁንም በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ትጋት ተከታትሎ እየተሻሻለ ለመሰልጠን መሄጠኑን አይቼ በመረዳቴ እጅግ ደስ ብሎኛል ።

ፖስታ የሕዝብን ዕውቀት ለመግለጽ ንግድንና ሥራን ለማስፋት እጅግ አድርጎ ይረዳል ።

ቴሌግራፍ የራቀውን አቅርቦ ከዓለም ዓለም ዳር ዕለት በለት የተደረገውን ያስታውቃል ።

ቴሌፎንም ልብ የሚያስበውን በቃል መነጋገር ብዙ ጊዜ ደስ የሚያሰኝና ሐሳብም የሚከፍል ስለሆነ ስለዚህ ከዚህ በፊት ላልኩት ለቴሌግራፍ ፍጥነት ቴሌፎን ደግሞ ቃል ለቃል አገናኝቶ የልብን ሐሳብ መነጋገርን ይጨምርበታል ።

መልክም ሥራ በቀና እንዲፈጸም ፖስታ ቴሌግራፍና ቴሌፎን ለዓለም ሁሉ ዋና መገናኛ መንገዱ ሆኖ ይኖራል።

ስለዚህ አገር ሁሉ እርስ በርሱ እየተወዳደረ ለሕዝቡ ሥልጣኔ ይሆናል ብሎ ለሚያስበው በኢትዮጵያ ከ፷፭ ዓመት ወዲህ የፖስታው ሥራ እንደዚህ አድርጎ መሰልጠኑ በተለየ የፖስታ ሥራ ሥራቸው የሆነ ጽኑ የሆኑ በሥራቸው የሚበላለጡና ሐሳባቸው መልክም በሆኑ ሠራተኞች ወደፊት ተስፋ ማድረግ እንዲቻል ያስረዳናል ።

በሥራ ከመሠልጠን የተነሣ በኢትዮጵያ መልክም ቡቃያ በቀለ የሀገርም መውደድ የጋለ ፍቅር ተወለደ ።

ስለዚህ ለሚመጣው ትውልድ የለማ መሬት ይቆየዋል። የዛሬን ቀን ጥሪ ተቀብለው በዓሉን ሊያከብሩልን ለመጡ ለውጭ አገር መንግሥት መልክተኞችና ለክቡራን መኳንንቶችም ለሴት ወይዛዝሮች ምስጋናዬን አድርሼ

ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ።

ለልዑልነትዎ ለልዑላን ቤተ ዘመድዎ ሁሉ ተድላና ስለ ኢትዮጵያ ወደፊት ልማትና ታላቅነት የሚደረገውን መልክም ምኞት በልዕልነትዎ እንዲቀበሉኝ ስል በማክበር እለምናለሁ ።ይኸንን ተናግረው ሲጨርሱ ተጨበጨበ ።

ደግሞም ሙሴ ዤራርድ የቤልጅክ መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስቴር የሚከተለውን ቃል ተናገሩ።

ግርማዊት ንግሥት ።

ልዑል ጌታዩ ።

ግርማዊት ንግሥተ ንግሥታትና ልዑል አልጋ ወራሽበመልካም ፈቃዳችሁ የውጭ አገርን መንግሥታት እንደራሴዎች ዛሬ የጋበዛችሁበት የክብረ በዓል ቀን የተሰጠውን የመንግሥቱን የመንግሥታትን ሥራ በትክክል በሚፈጸምበት መንገድ የኢትዮጵያ መንግሥት አዲስ እርምጃ መራመዱን ያመለክታል ።

ትምርህትን ባገር ውስጥ አውራጃን ከውራጃ የሚያገናኘውን የጥቅሟንም ልማት ለማጥጠን ለማስፋትና ለማበርከት ኢትዮጵያ መድከሟን ከዚህ ቀደም በማስተዋላችን እጅግ ደስ እያለን ተመልክተናል ።

ስለሆነ ግን ከሌላው የሥራ ክፍል ሁሉ ይልቅ ለሕዝብ ጥቅም የተመሰረተ በመሆኑ የፖስታና የቴሌግራፍ መሥሪ ቤት ለሠለጠኑ ሕዝቦች ክብራቸውን የሚገልጽ ሳይሆን አልቀረምና የግርማዊትነትዎና የልዕልናዎ መንግሥት ለዚህ የሕዝብ ጥቅም ለሆነው የሥራ ቤት የሚያስፈልገውን ልማት ሁሉ ሊሰጠው በተለይ ፈቃዱ ሆነ፡

እውነትም ይህ ሥራ ፍሬ ያለው ሥራ መሆኑንና ለዛሬውም ጊዜ እንደሚያስፈልገው ዓይነት ሆኖ መዘጋጀቱን ለመረዳት በአዲሱ ዓይነት ሆኖ የተሠራውን ይህን ያማረ ቤት እየተዘዋወሩ ማየትና የውጭውንና የግቢውን ሥራ መተከከል መመልከት ብቻ ይበቃል ።

ስለዚህ ሥራው እየለማ በሄደ ቁጥር ደስታቸውን ለመግለጽ የውጭ አገር መንግሥት እንደራሴዎችና ቀዳሚዎች

ውና ይህ ሥራ በመልካም እንዲቆም ለደከሙ ለታላላቆቹም ለታናናሾቹም ሠራተኞች ምሥጋናቸውንና ማበረታታቸውን ያቀርቡላቸዋል ።

ግርማዊነትዎ ልዕልናዎም ለከበሩ ሰውነቶቻችሁ ደስታን እንድታገኙ ለግዛቶቻችሁም ልማት እንዲሆን የምናቀርበውን መልካም ምኞት እንድትቀበሉን እንለምናለን። ብለው ሲጨርሱ ተጨበጨበላቸው ።

በመጨረሻም ልዑል የኢ መ አ ወ ተፈሪ መኰንን የሚከተለውን ቃል ተናገሩ።

ንግሥተ ነገሥታት ።

ክቡራን ወይዛዝሮችና መኳንንቶች ።

በኢትዮጵያ የፖስታ ቤት ከቆመ ዛሬ ፴ ዓመት ይሆናል ነገር ግን ዛሬ የተሰበሰብነው የቤቱን መለወጥ ብቻ ለማየት ነው ስለ ታላቁ ንጉሠ ነገሥት ስለ ዳግማዊ አጼ ምኒልክ መታሰቢያ የፖስታ ሚኒስቴራችን የተናገራቸውን መልካካም ቃሎችና ደግሞ በአገራችን የፖስታን ሥራ መጀመሪያ መሥራቾችና መሪዎች ለሆኑትም ላቀረበው የምሥጋና ቃል ሁላችንም በአንድነት በፍጹም ልብ ተካፋይ እንሆናለን ።

በሌሎቹ መንግሥታት ዘንድ በእርግጥ የሚገባውን ሥራ አገራችን ያገኘ ዘንድ ከሰለጠኑት ሕዝቦች ጋራ የሚያገናኘውን መንገድ በማስፋቱና በማልማት መሆኑ የታወቀ ነው ።

ከውጭ አገር መንግሥታት ጋራ በፖስታ ምክንያት የመገናኛ መንገድ በማግኘቱና ከውጭ አገሮችም ጋራ በመገናኘቱ ላገራችን ታላቅ ጥቅም ሆኖታል ።

ኢትዮጵያም በዓለም ሁሉ የፖስታ ማኅበር በመግባቱ ብቻ የሥራው አካሔድ በአንድ ቀን ሊተካከልና ሊደላደል አልቻለም ሥራውም በትክክል እንዳይሔድ አንዳንድ መሰናክል ሳያገኘው አልቀረም ነበር ። ስለሆነም አምነን ለሥራው መሪ ያደረግናቸው ሰዎች በርትተው በሥራቸው ጸንተው መሰናክሉን ሁሉ አልፈውታል ።

ዛሬም ይህን አዲሱን የፖስታ ቤት በምንመርቅበት በደስታው ቀን ግርማዊት ንግሥትና እኔም እራሴ ሚኒስትሩንና ታላላቆቹን እስከ ታናናሾቹ የፖስታ ቤትን ሠራተኞች ከብዙ ጊዜ ጀምሮ በሥራው በመጽናታቸውና በመበርታታቸው ሥራውን ወደ መልካም ፍሬ ስለ አደረሱት ደስ ብሎን እናመሰግናቸዋለን ።

ባለፈው ጊዜ አምነን በሥራው ላይ እንዳስቀመጥናቸው አሁንም ለወደፊቱ ሥራቸውን በትክክል እንዲሰሩ ተስፋ እናደርጋለን ። ከዚህ ቀደም የፖስታ ቤት ለሠራው ሥራ ስናመሰግነው ወደፊት በሚሠራው ሥራ ሁሉ እርዳታችንንና በጎ አድራጎታችንን እንድናደርግለት አደላድለን እናስታውቃለን ።

ክቡራን የውጭ አገር መንግሥት እንደራሴዎች መኳንንቶች ወይዛዝሮችም ይህን አዲሱን የፖስታ ቤት ለመመረቅ በመምጣታችሁ በግርማዊት ንግሥትና በኔም በራሴ ስም አመሰግናችኋለሁ ። ብለው ይኸንን ተናግረው ሲጨርሱ የጭብጨባው ድምቂያ ከልክ ያለፈ ሆነ ።

ከዚያም በኋላ የተጠራው ሰው ሁሉ ሻምፓኝ ተጋበዘና ለምረቃ የተጠሩት ሰዎች ሊቀበሉት የተሰናዳው ባንዱ ፊት ቴምብር ባንዱ ፊት የፖስታው ቤት ሥዕል ያለበት ወረቀት ከፖስታ ቤቶቹ እየተቀበለ በንግሥተ ነገሥታትና በልዑል አ ወ ተ መ ፊት እያለፈ ሄደ ። ወዲያውም ግርማዊት ንግሥትና ልዑል አ ወ ተ መኰንን የፖስታ ቤቱን አኳኋን በየክፍሉ እየዞሩ አዩ ። ሠራተኞቹም ሁሉ በየክፍላቸው የተከናወነ ሥራቸውን ግሩም አድርገው በማሳየታቸው ደስ አሰኙ በቴሌግራሙ ቤትም በሌላ አገር ያሉ የፖስታ ቤት ሠራተኞቹ የላኩትን የቴሌግራም ቃል ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ለልዑል አልጋ ወራሽ አቀረቡ ቃሉም ከዚህ በታች የተጻፈው ነው ።

እኛ በውጭ አገር ያለን የፖስታ ቤት ሠራተኞች ሁሉ የፖስታ ቴሌግራፍና ቴሌፎን መሥሪያ አዲሱ ቤት በሚመረቅበት ክብረ በዓል ቀን በሥራችን ምክንያት እበታው ላይ ለመገኘት ባለመቻላችን እጅግ እናዝናለን ።

አሁንም በዚህ ለኛ ለሠራተኞቹ ታላቅ መታሰቢያ በሆነበት ቀን የሥራችን መሪ የሆነውን ቤት ለመጐብኘት ለመጡልን ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ለልዑል እምልዑላን ጌታችን አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ከልባችን ጥልቅ የወጣ ወሰን የሌለው ምስጋናችንን በታማኝ አገልጋዮቻቸው ስም እንዲያቀርቡልን ክቡር የፖስታ ምኒስቴራችንን እንለምናለን ።

ይህ ሁሉ ከተፈጸመ በኋላ ግርማዊት ንግሥትና ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በማረ እጀብ ወደ ቤተ መንግሥት ገቡ ብርሃንና ሰላም ለክቡር ሚኒስቴሩና ለክቡር ዲሬክተሩ ለፖስታ ቤትም ሠራተኞች ሁሉ ሥራቸው እየሰፋ እንዲሄድ እየተመኘ ምሥጋናውን ያቀርብላቸዋል ።

ባሕረ ሐሳብ ።

በኢትዮጵያ ቊጥር በ፲፱፻፳፩ ዓም መስከረም ፩ቀን ማክሰኞ የዘመን መለወጫ የቅዱስ ዮሐንስ በዓል ነው ። በዚሁ ዘመን ፲መጥቅ ፳ አበቅቴ ይሆናል ፳፪ ሌሊት ፳፯ ጨረቃ ሆኖ ያድራል ።

የካቲት ፲፰ ቀን የነነዌ ጾም
መጋቢት ፪ ቀን ዓቢይ ጾም
መጋቢት ፳፱ ቀን ደብረ ዘይት
ሚያዚያ ፳ ቀን ሆሣዕና
ሚያዝያ ፳፭ ቀን ስቅለት
ሚያዝያ ፳፯ ቀን ትንሣኤ
ግንቦት ፳፮ ቀን ርክበ ካህናት
ሰኔ ፯ ቀን ዕርገት
፯ ቀን ጰራቅሊጦስ
ሰኔ ፲፯ ቀን ጾመ ሐዋርያት
ሰኔ ፲፱ ቀን ጾመ ድኅነት (ረቡዕና ዓረብ)

ይህንንም ጾም ለመጾምና ለማክበረ በዓሉ በሕይወትና በሰላም ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ከልዑል የኢ መ አ ወ ተ መ ረዳቶቻችንና ጠባቂዎቻችን ጋራ እንዲያደርሰን ጉ ፡ ልቡና እንጸልይ ። እግዚአብሔር ኢትዮጵያን

ለዘላለም ይጠብቃት ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ይህቺን ትንሽ ፅውቀቴን አበረክታለሁ። ቁም ጸሐፊ ገብረ ጻድቅ።

ምክር ።

ከሁሉ በፊት እግዚአብሔርን መፍራት ይገባችኋል እእምሮ ከእግዚአብሔር ነውና የሚገኘው አዋቂዎች የሆናችሁ እንደሆን ድህነት አያገኛችሁም ሁልጊዜ ምን እንደሆናችሁ እስቡ ራሳችሁም ምን እንደሆን እስታውቁ የሚቻላችሁንም ሁሉ አድርጉ እጅግ ለማወቅ የሚቸግረው ነገር ሰው ራሱን ያውቅ ዘንድ ነው እናንተም ምን እንደሆናችሁ ለማወቅ የፈቀዳችሁ እንደሆን በሬ አህላለሁ ብላ ተነፍታ እንደሞተችው እንቁራሪት አትሁኑ ከድኃም እንኳ ብትወለዱ ዘመዶቻችሁን መቀበል ይገባል ። እውነተኞች እስክትሆኑ ድረስ ትዕቢተኛ ኃጥእ ከመሆን እስክትርቁ ድረስ በሚቻላችሁ መጠን አጥብቃችሁ ጣሩ ። የጽድቅን መንገድ ለመያዝ የፈቀዳችሁ ብትሆኑ በሌላው የጨዋ ቤተ ዘመድ መቅናት አይገባችሁም ጨዋነት የሚመጣው ከዘሩ ነውና ጽድቅን ግን ሰው በገዛ እጁ ነው የሚያገኘው የጨዋ ልጅነትና ጽድቅ ዋጋቸው ልክ ነው። የራሳችሁን ብቻ ሐሳብ አትውደዱ የራሳቸውን ኃሳብ ብቻ የሚወዱ ያላዋቆች ሰዎች ናቸውና የተሰጠውን ደምብ መፈጸሚያ ጊዜ ሲገኝ በጥፋተኛ ላይ መጨከን መልካም አይደለም ርህራኄ ከሌለው ዳኛ ይልቅ ምሕረት ያለው ዳኛ ስሙ በመልካም ይጠራል ። የተፈረደበትን ሰው እሥራት ማላላት ይገባችኋል ግን ይህ ሲሆን በመለማመጫና በእጅ መንሻ አታድርጉት በምሕረት እንጂ በዳኝነታችሁ ውስጥ ጠላታችሁ የሆነ ሰው ቢቆም ያን ጊዜ ቂማችሁን አታስታውሱት ትክክለኛውን ፍርድ ጠብቃችሁ ፍረዱ እንጂ መተማመንን የመሰለ ደግ ነገር የለም ነገር ግን የምታምነውን ሰው ሁልጊዜ መርምረው ሰው ነውና እምነትን ካገኘ በኋላ መክዳ አይቀርም ማናቸውንም ሰው አስቀድማችሁ በእምነት ላይ ስታቆሙት በሕርዩን ዘሩን እውቀቱን መመርመር ይገባችኋል የምታምነውን ሰው ለማወቅ ብትፈቅድ የሕዝቡን ሐሳብ መመርመር ነው። ከፒቴን ባቢኪያን።

ስለ ክቡር አቶ ዘውድነህ አቦዬ ዕረፍት ።

ክቡር አቶ ዘውድነህ የኢትዮጵያ መንግሥት ማተሚያ ቤት ሹም በሥራቸው ትጋትና ጠንካሬነት በጣም የተመሰገኑ ሰው ነበሩ በኢትዮጵያ መንግሥት መተሚያ ቤት ሥራ ከጀመሩ እስከሁን ድረስ እየተጣጣሩ አሰሩት።ለወደፊቱም ሥራቸውን ለማከናወንና የበለጠ አድርገው ለማስፋት ብርቱ ሐሳብ ነበራቸው ግን የእግዚአብሔርና የሰው ሐሳብ እጅግ የተራራቀ ነውና ብዙ ቀን ከታመሙ በኋላ በነሐሴ ፳፱ ቀን አረፉና ኡራኤል ቤተ ክርስቲያን ክቡር ቢትወደድ ወልደገብርኤልና ክቡር ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደ መስቀል የጽሕፈት ሚኒስትር ብዙ ሌሎች መኳንንቶችና ወዳጆቻቸውም ተሰብስበው በክብር ቀበሯቸው።

ብርሃንና ሰላም ለክብርት እናታቸውና ለዘመዶቻቸው ሁሉ ለኢትዮጵያ መንግሥት ማተሚያ ቤት ሠራተኞችም እግዚአብሔር ያጽናችሁ ይላል ።

ማስታወቂያ ።

አዲስ ሐኪም የመጣ ዶክተር ኤፍ ኤርል ፈሬደሪለብ የሚባል በጀርመን አገር በህክምናው የተሸለመና የምስክር ወረቀት ያለው ከልጅ ይሙኑ ቤት ውስጥ የመድኃኒት ቤት ከፍቷል ። የመድኃኒት መስሪያው ቤትም የሚገኘው በጋኖታኪስ ቤት ያለው መንገድ ወደ ግቢ የሚወስደው እፈርናዲስ ኮት ሰፊው ቤት በታች ያለ አዲስ ፎቅ ከሆቴል ቦሎላጉስ ትይዩ የሆነው እምድር ቤቱ ያከማል ። ከመድኃኒት ቤት ለመታከም የሚፈልጉ ሰዎች ሐኪሙን ከ፪ ሰዓት ከጧዋቱ እስከ ፮ ሰዓት ተኩል ይገኛል ። ከ፯ ሰዓት በኋላ ከ፲ ሰዓት ጀምሮ እስከ ፲፪ ሰዓት ከመድኃኒት ቤት ያከማል ። ነገር ግን ከመለከትነው ሰዓት በተቀር ሌላውን ጊዚያት ሰዓታቶች እቤቱ ያከማል ። ቤቱም ያለበት አቶ አድነው ቤት ውስጥ ነው ከመድኃኒቱ ቤት ትንሽ ወረድ ብሎ።

ያዲስ አበባ ገባያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር ተኩል
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፪ ብር ተኩል
ዝባድ	፩ ወቄት	፫ብር ተኩል
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፳ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ክረጃ	፫ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ክረጃ	፲፫ ብር
አቡጀዲ መነጸር	፩ ክረጃ	፻፵፩ ብር
፡፡ ባለሰይጣን	፡፡	፻፵፪ ብር ተኩል
፡፡ ባለ ድመት ።		፻፴፩ ብር
፡፡ ባለአህያ	።	፻፳፫ ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል	።	፻፺ ብር
ባለ አንበሳ	፡፡	፻፴፱ ብር
ሱካር	፩ ጁኒያ	፳፮ ብር ተኩል
ቻይ	፩ ነጥር	፩ ብር

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ
አንድ ብር	ሊሬ ፰ ከ፹፮ ሳንቲም
ባአንድ ጊኒ	፲ ብር ፳፮ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፫ ብር

Odeon

ዓለም ሁሉ ፲፪ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃሽክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

COGNAC S.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሰ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል።

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቅዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

RUGBY

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፣ ቤንዚን በያይነቱ ቀባት ዘወትር ይገኛል



ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሽ ኦቤርላንድ ኦቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።



አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባ ኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኜቶና ባለባተሪ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ ኦቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል «ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው

ወዲያውም የኦቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

ማስታወቂያ

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲	ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር	፱	ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
የዓለም ጅዮግራፊ በአማርኛ ደኅና ጥራዝ ዋጋው	፮	ብር
» » » መናኛ ጥራዝ ዋጋው	፭	ብር
ደግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፭	ብር
ኀሐ ጽባሕ	፭	ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫	ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫	ብር
የሕይወት ታሪክ	፪	ብር ተኩል
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪	ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪	ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪	ብር
የቁጥር ትምርት	፩	ብር
ያማርኛ ሰዋሰው	፩	ብር
ወዳጄ ልቤ	፩	ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን		አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ		አላድ
አጭር የዓለም ታሪክ		አላድ
ያማርኛ ፊደል		ሩብ
አሳብና ምኞት		ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት		ሩብ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፪	መ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር		፪መ
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ		ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶ ግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ		ሩብ

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ፤ የልብ ፤ የደረት ፤ የጉበት ፤ የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ፤ የቂጥኝና የቋቁቻ፤ የሚያዋልድ፤ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል

እደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ሱቅ ነው ።

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ ።

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በካፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በካፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው ።

ጉድይር ግዙ





ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው ። በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አራተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፴፯
4 me ANNÉE № 37

ሐሙስ መስከረም ፫ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም ።
JEUDI 13 Septembre 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት
Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲረክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie
Un an 5 Thalers
Etranger
Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

አገርን ስለ መውደድ ።

ዘለፋ ረሲዓን ወምክረ ጠቢባን

ያዕቆብምዕራፍ ፬

እምአይቴ ለክሙ ፀብእ ወቀትል አኮኑ እምዝየ እምአፍቅሮ ዝሙት ዘይትገበር ውስተ አንጕዕክሙ ትፈትዉ ሂወኢ ትረክቡ ትትቃተሉሂ ወትትቃንኡሂ ወኢትክሉ ረኪበ ትትበአሱሂ ወትፃብኡሂ ትስእሉሂ ወኢይሁብክሙ እስመ ለእኪት ትስእሉ ያለው ንባብ በየጊዜው ሲገለጽ ይኖራል ። ማለት ላገርና ለሕዝብ ሁሉ እስከ ዘለዓለም ከሚሆን ብዙ ጥቅም ይልቅ የየራሳቸውን የዕለት ሆድ ብቻ በማሰብ መራራውን ጣፋጭ ጨለማውን ብርሃን እያሉ ባንድ ቀን ጌትነት የዘለዓለምን ባርነት የሚለውጡ ሰዎች ባሉበት አገር ጤና አለመገኘቱን አይጠረጠርም ነቅናቂ እያለ ማን ጥሩ ይጠጣል እንዲሉ እንዚያው መከራ ግድ ይመጣል ነገር ግን መከራን ለሚያመጣ ሰው ወዮለት ያለውን ባይመለከቱ ይመስለኛል አብሶም ከዱሮ ዘመን ጀግኖች ይልቅ የዛሬዎቹ ግብዞች አገራችንን እንወዳለን ስለአገራችንም እንሞታለን ይላሉ

ስለ ሆነ ነቢዩ ኢሳይያስ በከንፈሮቻቸው ይወዱኛል በልባቸው ግን ፈጽመው ከኔ የራቁ ናቸው ያለው በሳቸው ዘንድ ተፈጽሟል ማለት ላገሩ የሚቀናና ወገኖቹን የሚጠቅም ሰው ያንድ ራሱን ብቻ ጥቅም ሳይፈልግ ላገሩ ደኅንነት ለሕዝቡ ሥሕረት በሚሆን ገንዘብ ቀን በውኑ ሌት በሕልሙ ሲጥር ነው እንጂ ገቢ ገንዘቡን ለማበርከት አገርን እጠቅማለሁ እስመስሎ ፀገር ላይ ጥፋትን በሕዝብ ላይ ጉዳትን የሚያፋጥነው ሁሉ በአፉ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ እያለ ቢያወራ አቤቱ አቤቱ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያትን አይገባባትም ያባቴን ፈቃድ የሚፈጽም ነውእንጂ የተባለው በርሱ ላይ ተፈጽሞ ካገሩ አንድነት መለየቱን ያስተውል ፪ ጢሞ ፫ ም ፪ ወይከውኑ ሰብእ መፍቀርያነ ርእሶሙ መፍቀርያነ ፈጊዐ ወንዋይ ነበብያን ዝሁራን ጽሩፋን ዓላውያነ አዝማዲሆሙ እላ አልበሙ አኰቴት ውፅኡነ ጽድቅ እንዲል ።

ደግሞም ለክፉው በክፋት ለበጎውም በበጎነት የነገር መክሂጃ የሚሆነው ከጥንት የቄየ ነው ቅዱስ ጳውሎስም ተምያን ተጥባብ ይለዋል ይኸነንም የበጎነት መሪነቱ ቀርቶ አንዳንድ ሰነፎች ለራሳቸው ጥቅም ብቻ የሚያዘወትሩት ሁኗል ይህም እጅግ ያሳዝናል ማለት ጉልማሳ እንደ ወረወረው ፍላፃ ሄደው በሕሩን በመርከብ የብሱን በእግር እየጐበኙ ብዙ ጥቅም የሚያስገኙ እንደ ቀትር ንብ የሚናደፉ ብዙ አርበኞች የነበሩዋት ኢትዮጵያ ዘር ሲታመስ መሬቱም አይታረስ እንዲሉ ይህም ይህ ነው ከዚያም ጋራ እርስ በእርስዋ የምትለያይ መንግሥት ትጠፋለች እንጂ አትፀናም ቤተ ሰቦችም ያልተስማሙ እንደሆነ ቤታቸው ይፈርሳል ተብሎ በወንጌል የተነገረው በውኑ ከግብዞች ወገን ይህን ቃል ሐሰት ነው የሚል ይኖርን። የለም እንግዲያውማ ቀጥሎስ የሰውን ልጅ አሳልፎ እሰጣለሁ ለሚል ወዮለት ያንስ ሰው ባይወለድ በተሻለው ነበር የሰው ልጅ ግን ስለ እርሱ እንደ ተጻፈው ይሄዳል ይል የለምን ።በዚያውም ላይ በገንዘብ ክብረው ከእውቀት የደኸዩ አያሌ የኑዋሪ እንግዶች አሉብን እነዚሁም ሥራ ከመሥራት ይልቅ ባልሠሩት ሥራ መመስገንንና ተኝቶ እየዋሉ ገንዘብን ማድለብ ብቻ ይፈልጋሉ የወዲያ አገር ሰዎች ብዙ ድልብ ቢያበጁ በብዙ ትጋት እየሠሩ መሆናቸውን ባያስተውሉ ይመስላል ። ደግሞም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ አይሁድን በዘማ እንደመሰላት ይህ ምሳሌ የመንግሥት መናወጽ የሕዝብንም ሕፀፅ በሚፈልጉ ጕስቋሎች ላይ ይተረጐምባቸዋል

ማለት ይህች ዘማ ሥራው አንድ ሁኖ ሳለ ወንድ ቢለዋወጥላት እንድትወድ እነዚህም ግዛቱ አንድ ሳለ ገዢን ቢያለ

ዋጡጡ ይወዳሉና እውነተኛ አገሩን ወዳጅና ለሕዝቡ ተቈርቋሪ ግን በሥራው ይታወቃል እስመ እምፍሬሆሙ ተአምርዎሙ። እንዲል ይህንም የጻፍሁበት ምክንያት ምሰሶን ምስጥ ከበላው ቤት እንዳይጸና መንግሥትንም ቢነክኩት አገር አይቀናምና ነው አሁንም እውነተኛ ኢትዮጵያዊ የሆነ ሰው ትልቅም ትንሽም ቢሆን በየተቻለው አገሩን ከጥፋት ለማዳን እንዲጣጣር ዕውቀትና ኃይል ይስጠው

መኰንን ኢያቄም

የሙሴ ኤፍ ቲ ሬማይንደር ።
የሚያሳዝን ንግግር ።

ነገርን ነገር ያነሳዋል ሐምሌ ፳፮ ቀን ፲፱፻፳ ዓ ም በያመቱ በሱዳን በኩል አድርጎ በባሮ ወንዝ ውስጥ የሚመጣውን በላቦት የሚሄድ ጀልባ ለማየት ከሰዮ ተነስቼ ወደ ገምቤላ ስሄድ ሊልሞ ከሚባለው ቦታ ስደርስ ሙሴ ኤፍ ቲ ሬማይንደር ከሚባሉ የውጭ አገር ሰው እመንገድ ተገናኝተን ሰላምታ ከተሰጣጠን በኋላ ከወዴት ይመጣሉ ወዴትስ ይሄዳሉ ። ብዬ ብጠይቃቸው የመጣሁበትን ብነግርህ አታውቅም ግን የምሄደው ወደ ገምቤላ ነው ስላሉኝ እንግዲያውማ አብረን እንዘልቃለን እኔም በባሮ ወንዝ ውስጥ በላቦት የሚሄደውን ጀልባ ለማየት ወደዚያው ነው የምሄደው ብላቸው እዬ ጉድ ከማየት ይልቅ መሥራት አይሻልምን አሉኝ እኔም መሥራት የሚጀመረው ከማየት የተነሳ ነውና ከሥራ በፊት ማየት ይበልጣል አልኳቸው እንግዲያውስ መልካም ነው አሁን ልታይ መውረድህ ነውና ስትመለስ ትሠራዋለህ አሁንስ የመንገዳችንን ነገር እንጨዋወት አሉና ልዩ ልዩ ደስ የሚያሰኝ ጨዋታ እየተጫወትን ስንሄድ ሊልሞ ከሚባለው በታች ካለው ክፉ ቁልቁለት ዘንድ ስንደርስ የፊት ንግግራቸውን እንደ ገና አድሰው እንግዴህ ያየኸውን ሁሉ ለመሥራት ታስበለህና ስትመለስ ይህን ዳገትና ቁልቁለት የተሻለ እንዲሆን አድርገህ ሳትሠራው አትቀርም ይመስለኛል አሉኝ እኔም የንቀት ንግግራቸው በጣም አሳዘነኝና ምነው ጌታው በነገርዎ ውስጥ ሁሉ የንቀት ንግግር ያገቡበታል እውን የኢትዮጵያ ልጆች ለሀገራቸው መልካም የሚሆነውን ነገር ሁሉ ለመሥራት ይሰንፋሉ ብለው ነውን አሁንም እግዚአብሔር የኢትዮጵያን አባቢ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንን ያሰነብትልን እንጂ እንኳን ይኸን ብዙ ለመሥራት እናስባለን ልዑል አልጋ ወራሻችን ለሥራ የሚተጉ መሆናቸውን ባይሰሙ ይሆናል እንጂ ቢሰሙ ይኸንን አይናገሩም ነበር ይልቁንም አሁን በዚህ ሰሙን በጋዜጣ እንደሰማነው የገፈርሳን ድልድይ እሳቸው እራሳቸው እየሄዱ በጥቂት ቀን ውስጥ ያሠሩት እጅግ ያስገርማል አሉ ሌላሰው ቢሠራው ኖሮ እስከ ብዙ ቀን አያልቅ ነበር ይባላል ብላቸው ያሁኑስ ጨዋታህ በጣም ደስ አሰኘኝ ግን በጣም የሚያሳዝኑኝ እነዚህ በዚህ በረኃ ውስጥ በያለበት ወድቀው የማያቸው አህዮች ናቸው አሉኝ እኔም ነገራቸው አልገባኝም ነበርና አሁን በዚህ ሰፍራ ምን የወደቀ አህያ አዩ ብላቸው እዬ ለካ አንተ ከመንገድህና ከጨዋታህ በቀር ሌላ አትመለከትምና አሁንም ትንሽ ቆይ አሳይሀለሁ ብለውኝ ጥቂት ከሄድን በኋላ ከሰዮ ቡንና ሰም ተሸክመው ወደ ገምቤላ የሚወርዱና ከገምቤላ አቡጀዲ ጨውና ሸቀጣ ሸቀጥ ተሸክመው ወደ ሰዮ የሚወጡ ጋሎች ደክሟቸው ሸክማቸውን አንድ ላይ ከብሰው እነሱ እንደ ሞተ ሰው ተንጋለው እተኙበት ሥፍራ ስንደርስ ይኸውልህ ወንድሜ የሚያሳዝኑኝ በያለበት የወደቁት አህዮች እነዚህ ናቸው ስላሉኝ ለጊዜው በጣም ተናደድኩና እዬ ጉድ ጌታው አሁንስ እጅግ ለጆሮ የሚያስከፋ ነገር ይናገሩ ጀመር ሰውነታቸውን እያዩ እንዴት አህዮች ይሏቸዋል ለካ የሐገርዎ ስልጣኔ ሰው መሳደብና መናቅ ነው አሁን የተሳደቡት ጋሎቹን ብቻ አይደለም ግን እነሱ አህዮች ከሆኑ ሁላችንም እርስዎ ሳይቀሩ አህዮች መሆናችን ነው በሀገርዎ ሠርቶ የሚበላ ሰው ሁሉ አህያ ይባላልን ወይንስ ሰውን መሳደብ እውቀተኛ ያሰኛልን አሁን መሳደብ ከጀመሩ ጥቂት ቆይተው ለመማታት ሳያስቡ አይቀሩምና ከርስዎ ጋራ መሄድ አያስፈልገኝም ብላቸው ወንድሜ ከቁጣህ ታገሥና ላጫውትህ ለሞታቸውና ለድካማቸው ለማታዝኑላቸው ሰዎች ለስድባቸው ትናደዳላችሁ ግን ለነሱ ከስድባቸውና ከሞታቸው ማናቸው ይጐዳቸው ይመስልሀል ይልቁንስ በያመቱ ምንም ጥቅም በማያገኙበት ከባድ ሸክም እየተሸከሙ ወደ ገምቤላ (በረኃ) እየወረዱ በችጋርና በንዳድ የሚያልቁት ሕዝቦች እጅግ ብዙ መሆናቸው አንተም አትክዱኝ ።

ስለዚህ ለስድባቸው ከምታዝኑላቸው ይልቅ ከገምቤላ ሰዮ ድረስ እቃ የሚያመላልስ አቶመቢል እንዲቆም መንገድ አሰርታችሁ በከንቱ ከሚሞቱና ከሚደክሙ አታሳርፉአቸውምን ይኸውና እንደምታየው መንገዱ ከገምቤላ ሊልሞድረስ ሜዳ ስለሆነ የአቶመቢል መንገድ ለማሠራት ብዙ ከሳራ አያስፈልግም ትንሽ ከሳራ እንኳን የሚያስፈልገው ቅድም እወረድነው ሊልሞ እሚባለው በታች ያለው ዳገት ብቻ ነው ያውም መሐንዲስ ቢመረምረው ላይኛውን ወይንም ታችኛውን አቶመቢል የሚያስወጣ መንገድ አይታጣም ለዚሁም አቶመቢሉ ከቆመ ለአቶመቢል መንገድ ሥራ የሚወጣው ከሳራ እስከ ጥቂት ቀን ድረስ እንዲመለስ አይጠረጠርም ስለዚህ ከሰዮ ገምቢላ ድረስ አቶመቢል አቁማችሁ እነዚህን ሕዝቦች ከሞትና ከጉዳት ብታድኑዋቸው ለናንተም ብዙ ጥቅም ይሆንላችሁ ነበር ፩ኛ የነዚህ የሕዝቦች ከሞት መትረፍ ለሀገራችሁ ከብት ነው ፪ኛ የአቶመቢሉ ኪራይ ብዙ ጥቅም ነውና ወዲያውም የስማችሁ መጠሪ ነው ፫ኛ አቶመቢል ከቆመ ንግድ ይበረክታልና በኩቴ የምትቀበሉት ቀረጥ ገቢ ሲበዛ የመንግሥታችሁ ክብረት ነው እነዚህ ፫ጥቅሞች በንድነት የሚገኙበትን ነገር አላስተዋላችሁም ግን በማይጐዳው ስድባቸው ትናደዳላችሁ እኔ በልጅነቴ ከገሬ ወጥቼ ያደግሁት በዚህ አገር ስለሆነ ይህንን አገር በጣም አድርጌ እንደናንተ ልክ እወደዋለሁ ስለዚህ የሕዝባችሁ ጉዳት ቢያሳዝነኝ የብስጭት ንግግር ተናገርኩ እንጂ ለስድብ ብዬ አልተናገርኩትም ስላሉኝ ነገራቸው ክልቤ ገብቶ ስላስረቀረቀኝ በተቆጣሁበት ይቅርታዎን እለምናለሁ እኔ ለስድብና ለማሽሟጠጥ የተናገሩት መስሎኝ ነበር እንጂ ለሕዝባችን ጉዳት አዝነው በብስጭት የተናገሩት አልመሰለኝም ነበር ይኸ

ሉትን እስከ ጥቂት ቀን ድረስ መንግሥት ወይንም ለድኃ ጉዳት የሚያዝኑ የኢትዮጵያ ወዳጆች (ኩፓንያ ሆነው)ወዲያውም ለጥቅማቸው ሲሉ ሳያሰሩት አይቀሩም እያልኩ ሳጫውታቸው ወዲያው ገምቤላ ደረስን እንግዴህ እኔ የምሰፍረው ከወዲያማዶ ከፈረንጆች ክፍል ነው አንተ ወዲህ ማዶ ከሀበሻ ክፍል የምትሰፍር እንደሆነ መለያየታችን ነውና ደህና ሰንብት አሉኝ እኔም ደስ የሚያሰኝ ጨዋታችንን ሳንጨርስ በመለያታችን አዝኜ ምናልባት በዚህ ጀልባ ወዳገርዎ የሚሄዱ እንደሆነ ፖስታ እንድጽፍልዎ አድራሻዎን ይስጡኝ ብላቸው አዎን አሁን ወዳገሬ መሄዱን እሄዳለሁ ግን ብርቱ ጉዳይ ስላለኝ ቶሎ ብዬ በጅቡቲ በኩል ወደ አዲስ አበባ እመለሳለሁ ስለሆነ እዚያው ድረስም ፖስታ ስትጽፍልኝ አድራሻዬን(ፎርጐትን ሲንግ ሬማይደር) እያልክ ጻፍልኝ ይደርሰኛል ብለው አድራሻቸውን ሰጥተውኝ ተሰነባብተን ተለያየን ።

ክቡራን የብርሃንና ሰላም ወዳጆች እኚህ የውጭ አገር ሰው ለሐገራችን ሕዝብ ጉዳት አዝነው እንዲህ የሚያሳዝን ነገር ሲናገሩ እኛ የገዛ ሐገራችንን ሕዝብ ከሚጐዳበት ነገር ለማዳን ለምን እንሰንፋለን አሁንም ለሐገራችን ሕዝብ ጉዳት የሆነውን ሁሉ በሚቻላችሁ ለማሻሻል አትበዝኑ ስል የኢትዮጵያ ወዳጅ ለሆኑ ክብታሞች አስታውሳለሁ።

ታናሽ ወንድማችሁ ኃይለጊዮርጊስ ወልዳማኤል

ስለ ደጃዝማች ግርማይ መንገሻ ዕረፍት ።

ደጃዝማች ግርማይ የትግሬ ባላባት የራስ መንገሻ ዮሐንስ ልጅ ናቸው ለናታቸውም አንድ ናቸው ፤ ይብላኝላቸውና እናታቸው ወይዘሮ ታፈሰች ልጆች እየወለዱ ብዙ ጊዜ ቢሞቱባቸው ስለ ተቸገሩ ደጃዝማች ግርማይን እንደ ተወለዱ ሳያዩዋቸው በመስኮት ወጥተው ከሩቅ ስፍራ በሞግዚት አደጉና ወዲያው ከተማሪ ቤት ቈይተው ባሥራ አራት ዓመታቸው ከናታቸው ጋራ ዓይን ለዓይን ተያዩ ።

ኋላ ግን ወንድማቸው ራስ ሥዩም ፊታውራሪ ብለው ሽሬን ሰጥዋቸው ቀጥለውም በተምቤን ደጃዝማች ተብለው ኋላ ግን በየጊዜው አኵስምንም ዓድዋንም ገዝተዋል ።

ትግሬንም ሲሻሩ ለደጅ ጥናት ወደ አዲስ አበባ መጡና ቅምብቢት የሚባለውን አገር ተሹመው መንግሥትም አክብሮ ያኖራቸው ነበር ከዚየውም የጐጃም ባላባት የንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን የልጅ ልጅ የራስ መሥፍንን ልጅ አግብተው ነበር ከጥቂት ጊዜም በኋላ ብዙ ቀን ታመሙና ምሉ ጐልማሳ ሲሆኑ በ፴፫ ዓመታቸው ጳጉሜን ፪ቀን ዓረፉ የዚያን ጊዜም እቶቻቸው ወይዘሮ አስቴርና ወይዘሮ አልማዝ ባለቤታቸው ፥ አሽከሮቻቸውና ወዳጆቻቸውም ሁሉ እጅግ ሲያዝኑና ሲያለቅሱ የሞት መጀመሪያ መሰለ ወዲያውም ዓረፉ እንደተባለ በከተማው ያሉ የትግሬ ካህናትና መኳንንት በፍጥነት ተሰበሰቡ ቀጥለውም የሥላሴና የማርቆስ ካህናት መጡ ወዲያውም ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ከመኳንንቶቻቸው ጋራ ደረሱና እስከሬኑ ሲወጣ የሰልፉና የዓጀቡ ማማር እጅግ ያስገርም ነበር ።

ከቤ ፦ ክርስቲያኑም አጠገብ ሲደርስ ልክ የሌላቸው ብዙ ካህናትና መኳንንት ተሰበሰቡና በብዙ ልቅሶና ኀዘን ከትልቅ ክብሬታ ጋራ እሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተቀበሩ ብርሃንና ሰላም ለእናታቸውና ለወንድሞቻቸው ለእህቶቻቸውም ሁሉ እግዚአብሔር ያጥናችሁ ይላል ።

የተወለደበት ሀገርና የወገን ፍቅር ።
የሁለት ወገኖች ታሪክ ።

ባንድ ሀገር ለወሲጋ ኖሴና ቡኖ የሚባሉ ሀገሮች ወሰነተኞች አሉ እነዚህ ሀገሮች ግዛታቸው ለየራሱ ነው በወሰናቸው መሃከል አንድ ሆራ ወሃ አለች ይህችን ወሃ የሁለቱም ወገን ከብት የሚጠጡባት ነች ነገር ግን ሆራ ስለ ሆነ በየተራ ነውና የሚያጠጡ ስለ ዚህ እኛ ቀድመን እናጠጣ እኛ እናጠጣ በማለት ሁለቱ ወገኖች በመሃከላቸው ዘወትር ብርቱ ውጊት ነበር ብዙ ነፍስ እስኪወድቅ ድረስ ይህም ጠባቸው ብዙ ዘመን ሲኖር ከዕለታት አንድ ቀን ሽማግሌዎች በመሃል ገብተው ይህ ጠብ እስከመቼ ይጨረሳል ስምምነትስ በመሃከላችሁ መች ይጀመራል አሁንም ከሰልፉ ሳትነሱ ቀድሞ ኮርማ እምጥቶ በዚች ሆራ ላይ ያረደ እሱና ወገኑ አስቀድመው ያጠጡ ብለው በየኑ ሕዝቦቹም የሽማግሎችን ነገር ተቀብለው ሁለቱም ወገኖች ኮርማቸውን ለማስመጣት ሰው ላኩ ነገር ግን ከኖሴዎች ሀገር ይልቅ የቡኖዎች ሀገራቸው ቅርብ ስለ ነበረ ኮርማቸውን አስቀድመው አምጥተው ለማረድ ሲቀርብ የኖሴው ባላባቱ ከመሃከል ብድግ ብሎ አሁን የኛ ሀገር ሩቅ ስለ ሆነ እነሱ አርደው ሊወስዱ አለና ሽማግሎችን መቸም ደም ያፈሰሰ አይደለም ወይ ብሎ ጠየቃቸው እነሱም አዎን አሉት እሱም ጥቂት እንኳ ሳይሳሳ በያዘው ጦር ስለ ሀገሬና ስለ ወገኔ እኔ እሰዋለሁ ብሎ በወሃው ዳር አንገቱን ቆርጦ እውስጡ ወደቀ እንደ ዚህ አድርጎ ያችን ወሃ ለሀገሩ ሰዎች አስቀረ እስከ ዛሬም ሆራዋ በሱ ስም ትጠራለች ። ወጣቶች ሆይ አያችሁ ይህችን እውነተኛ ፍቅር እንዲህ ናት ሀገርን መውደድ ሕይወትን እስከ ማሳለፍ ቆርጦ ነው እንጂ እንደሌሎች ባፋቸው ብቻ ሀገራችን እንወዳለን እያሉ እንቅፋት የሚሆኑትና ለገንዘብ ብለው የሀገራቸውን ጥቅም ለውጭ ሰው ለማሳለፍ ይጥሩና ተመልሰው የሕዝብን አሳዳሪ መዘራዝር ያገባሉ ። እንዲህ አይሁን ወንድሞች ሆይ ሌሎች ሀገሮችስ እንኳን የሀገራቸውን ጥቅም የወገናቸውን ላንደኛው ወገን በገንዘብ ለሚወዳጃቸው ለማሳለፍ መርዳት ሚሊዮን ሚሊዮን ብር አያስታቸውም ስለ ዚህ ሀገራቸውን ከልብ የማይወዱ ምንም ቢወለዱበት ሰው አይባሉም ካፒቴን ባቢኪያን ሀገሩን የማይወድ ሰው ከሰውነት የወጣ እእምሮ ያጣ ነው አሉ አያችሁ ወንድሞች ሆይ ሙሴ የፈርዖን የልጁ ልጅ ተብሎ በክብሬታ ከመቀመጥ ከወገኔ ጋር ሆኜ መከራ ልቀበል ብሎ መረጠ ሀገርን የመሰለ ከወዴት ይገኛል ?

ልጅ በበት በናቱ ቤት ሳለ የናት ያባቱን ችግር አያውቅም ነገር ግን እራሱ ቤት ከያዘና ልጅ ከወለደ በኋላ ነው የነሱን መቸገር የሚያውቅ እንደሁም እኛ የሰው እጅ ሳናይ ሀገራችን የምትጠቅመን አይመስለንም ነገር ግን ሌሎች ጐረቤቶቻችንን ብናይ መሬታቸውን ማር እንጨታቸውን በገንዘብ እየገዙ ነው ይህ እንዳያገናኝ ተስማምተን ፍቅርን ለብሰን ሀገራችንን ፀቅን ልቦና እናገልግላት እንድታገለግለን ያለዚያስ የተወደዳችሁ አንባቢዎች ሆይ የናንተን ያህል አእምሮ አለኝ ብዬ ልመክራችሁ አይደለም ግን ይህችን ታሪክ ላሰማችሁ ነው እንጂ ። ደምሴ ወልደ አማኑኤል

ሁለተኛ ክፍል ።

የቀድሞው የመስኮብ ንግሥት ምስጢር ያለው የሕይወት ታሪክ ባለሙዋሏ ዘኒት የጻፈችላት በክፒቴን ባቢኪያን ታርሞ ታደሰ

አልጋ ወራሺቱ አሊክስ ኤልቤህ ትራስ ይባላል ብላ ለተወደደው ወዳጇ አድራሻዋን ሰጠችው እኔም እንደሷ ይህ ኤልባህ ትራስ የሚባለውን አድራሻዬ ነው ብዬ ለወዳጄ ነገርኩትና ከዚያ ቀን ጀምሮ ወረቀት ለመጻጻፍ ጀመርን በሮማ ከተማ ያገኘነው ሕይወት እጅግ ደስ የሚያሰኝና ነጻነት ያለው ስለሆነ ዓር ምሽታት ወደ ሚባለው በቀድሞው በጀርመን አገር ወዳለው ቤታችን በተመለስን ጊዜ እንዴት የሚያሳዝንና የሚቀፋን ነገር ሆነ ። ሮማ ባለን ጊዜ ጥንቺዮ በሚባለው ስፍራ ከተወደዱ የፍቅር ወዳጆቻችን ጋራ በሠረገላ ሆነን ዙሯያውን እየዞርን ያደረግነው ሽርሽር ከቶ የማይረሳ ነው ይልቁንም ክርሶ በሚባለው ስፍራ ብዙ ሕዝብ ተሰብስቦበት በነበረው ላይ ያደረግነው ደስታና በየሆቴሉ ሁሉ በነጻነት ገብተን ያየነው ፈንጠዝያና ደስታ እስከ እድሜ ልካችን ድረስ የማይረሳነው ።

አልጋ ወራሺቱም አሊክስ ከተወደደው ፍቅሯዋ ከተለየችበት ቀን ጀምራ እያደር ዝምታና ሐሳብ አደረባት ምንም ነገሩን ገልጻ ለኔ ባትነግረኝ ልቧ ከሮም እንደቀረ በውነት ስላወቅሁት እንድትረሳው ብዬ በብዙ ነገር ለማነጋገር ለማሳቅ እጣጣር ነበርኩ ነገር ግን ከሷ አንድ ቃል እንኳን ለማግኘትና ከፊቷ ፈገግታ የሳቅ ምልክት ለማግኘት አልቻልኩም ።

ከዕለታት አንድ ቀን የንጉሡ የክዘር ባለሙዋሎች አለቃ ባሮንፎን አያዘባህለ የተባለ አልጋ ወራሺቱ አሊክስ ወዳለችበት እልፍኝ ገባ እኛም ይህ ታላቅ የንጉሡ ባለሟል በሚመጣበት ጊዜ የእጅ ሥራ ስንሠራ ነበርን ይህም ሰው ዕድሜው አምሳ ዓመት ያህል ስለሆነው ራሱ ሸብቶ ነበር ይሁንና ሰውነቱ አቋቋሙ እጅግ የሚያስከፋ አልነበረም ።

ደስ የሚያሰኝና ውበት ያለው መሳይ ነው ። እኛም ጨዋታችን እንዲጋመስን ከመሐከላችን ገብቶ እንዲህ ሲል ተናገረ ልዕልት ምን ሆነዋል የታወከት ነገር ያለ ይመስለኛል ከቶ ምን ነገር ይሆን እስዎን ያሳዘነዎ ብሎ ጠየቀና ቀጥሎም በተንኰል አሳሳቅ እየሳቀ ምናልባት ፍቅር ይሆናል ።

እኛም ብዙ ጊዜ ይህ ክፉ ነገርና ለጊዜው ደስ የሚያሰኝ ነገር ደርሶብናል ነገር ግን ልዕልትን ይቀርታ እለምናለሁ ። ይህ እንዲህ የታደለውን ሰው ስሙን ለማወቅ ይቻላልን

በዚህ ጊዜ አልጋ ወራሺቱ አሊክስ ሰውነቷን አስቆጥታ እኔ እስከ ዛሬ ምንም ሰው አላውቅም በንደዚህ ያለ ሥራም ናልበት ለወደፊቱ እንደሆን የተመኙልኝ እንጂ በውነት እስከ ዛሬ ድረስ ከንድ ሰው ፍቅር የለኝም አለች ።

ግን አልጋ ወራሺቱ አሊክስ ንጉሠ ነገሥቱ ክዘር የሰማባት መስሎዋት በጣም ደነገጠች ያም የባለሙዋሎቹ አለቃ በተንኰል አሳሳቅ እያየ እንዴህ አለ ። ልዕልት ሆይ እኔ ግን በውነት በፊትዎ ላይ በዚህ ነገር እንደተቸገሩ ምልክት አግኝቻለሁ ። ይልቁንም ብዙ ጊዜ የኖርኩ ሰው ነኝና እንዴህ ያለው ነገር ከኔ ሊሠወር አይቻልም ብሎ በነገራት ጊዜ አሊክስ ተቆጥታ ከመቀመጫዋ ብድግ አለችና በቁጣ ቃል በሙሴ ባሮን መልስ ስር አንዳች ነገር አለን ? እንዴህ ያለ ነገር የሚያናግረው ብላ ተናገረች ወዲያውም ያው ሰው አይደለም ልዕልት ሆይ እኔ ደስ ቢለኝና ጨዋታ ቢያምረኝ ነው ቢላት ትታው ወደ ውጭ ወጣችና ይህ የሙሴ ባሮን ምንድነው የሚለው ብላ ጠየቀችኝ አዬ ይህ ሰው ምንም አያውቅ ሽማግሌ ስለሆነ እንዲያው ለመጫዋወት ነው እንጂ አልኳት።እሷም መልሳ አለችኝ ይኸው ታያለህ ከዛሬ ሳምንት ጀምሮ እንድም ወረቀት ከረዶልፍ አልደረሰኝም ከቶ ምን ሆኖ ይሆን በጣም ተቸግሬአለሁ አለችኝ ።

እኔም መልሼ አልኳት እሁቴ ሆይ ገና አንድ ሳምንት ነው ደግሞ ለዚህ ታስቢያለሽን እኔ ግን ከሮም ከተመለስኩ ጀምሮ ከካርሎ ከወዳጄ ዘንድ አንድ ወረቀት ብቻ ነው ያገኘሁት እርስዋም እንደኔ የጠለቀ ፍቅር ባይኖራችሁ ነው ብላ መለሰችልኝ ። በሚመጣው ሳምንት ይቀጥላል ።

ካፒቴን ባቢኪያን ።

ይትባረክ እግዚአብሔር እፃ ላከ ኃይለ ሥላሴ ስቡሕኒው እቱ ወልዑልኒ ውእቱ ለዓለም።

ኂሩትከ ኃይለ ሥላሴ ትንቢተ ነቢያት ይትረጉም
እንዘ ይብል የኃብር ይእዜ ዘምስለ ሠዊት ሠርፅ
ወይትራከብ ምስለ ማዕረር ዘርአ እክል ሕፁፅ
ዘንተኒ ናጠይቅ ዙለሄ ዓይነ ርኁባን አብያጽ
ተድባበ ክምረ እክል ይሔውፅ
እስመ ወርኃ ማዕረር ክነ ወርኃ ቈጽል ቅሩጽ
ወተሰብረ ላህ ሰብአ አንቀጽ

መልአከ ብርሃን ጽጌ ።

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዌድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO, Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg malmö och Karlstad

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ባርባሬሶ

ኮ ኛ ክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ያሰናዷኒት ፈቃድ የተቀበለ ።

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በከፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በከፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ማስታወቂያ ።

አዲስ ሐኪም የመጣ ዶክተር ኤፍ ኤርል ፌሬደሪ ኣብ የሚባል በጀርመን አገር በህክምናው የተሸለመና የምስክር ወረቀት ያለው ከልጅ ይመኙ ቤት ውስጥ የመድኃኒት ቤት ከፍቷል ። የመድኃኒት መስሪያው ቤትም የሚገኘው በጋኖታኪስ ቤት ያለው መንገድ ወደ ግቢ የሚወስደው አራርናዲስ ኮት ሰፈው ቤት በታች ያለ አዲስ ሮቅ ከሆቴል በሎላጐስ ትይዩ የሆነው እምድር ቤቱ ያክማል ። ከመድኃኒት ቤት ለመታከም የሚፈልጉ ሰዎች ሐኪሙን ከ፪ ሰዓት ከጧዋቱ እስከ ፫ ሰዓት ተኩል ይገኛል ። ከ፮ ሰዓት በኋላ ከ፰ ሰዓት ጀምሮ እስከ ፲፪ ሰዓት ከመድኃኒት ቤት ያክማል ። ነገር ግን ከመለከትነው ሰዓት በተቀር ሌላውን ጊዜያት ሰዓታቶች እቤቱ ያክማል ። ቤቱም ያለበት አቶ አድነው ቤት ውስጥ ነው ከመድኃኒቱ ቤት ትንሽ ወረድ ብሎ ።

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር ተኩል
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፪ ብር ተኩል
ዝባድ	፩ ወቄት	፫ ብር ተኩል
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺ ብር
ገበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፳ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፬ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፰ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፵፩ ብር
: : ባለሰይጣን	: :	፻፵፪ ብር ተኩል
: : ባለ ድመት ።		፻፴፩ ብር
: : ባለአህያ	።	፻፳፫ ብር
: : ባለሳቢ ግመል	።	፻፶ ብር
ባለ አንበሳ	: :	፻፴፱ ብር
ሱክር	፩ ጁኒያ	፳፮ ብር ተኩል
ቻይ	፩ ነጥር	፩ ብር

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ
አንድ ብር	ሊሬ ፲ ከ፹፯ ሳንቲም
በአንድ ጊኒ	፲ ብር ፳፯ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፭ ብር



ዓለም ሁሉ ቀ ፲፫ ዓይነት የተሰማ እሺቱ ሙዚቃሸከላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሲንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

COGNAC S. & E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሰ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩግበ

RUGBY

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራ ገ በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፥ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ኦቤርላንድ



ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ አቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የጎጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባ ኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባተሪ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል «ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው

ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

ማስታወቂያ

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲	ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር	፱	ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
የዓለም ጂዎግራፊ በአማርኛ ደኅና ጥራዝ ዋጋው	፯	ብር
» » » መናኛ ጥራዝ ዋጋው	፭	ብር
ድግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፭	ብር
ጎሐ ጽባሕ	፭	ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫	ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫	ብር
የሕይወት ታሪክ	፪	ብር ተኩል
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪	ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪	ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪	ብር
የቁጥር ትምርት	፩	ብር
ያማርኛ ሰዋስው	፩	ብር
ወዳጄ ልቤ	፩	ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን		አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ		አላድ
አጭር የዓለም ታሪክ		አላድ
ያማርኛ ፊደል		ሩብ
አሳብና ምኞት		ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት		ሩብ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፪	መ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር	፪	መ
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ		ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶ ግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ		ሩብ

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ፤ የልብ ፤ የደረት ፤ የጉበት ፤ የኩላሊት ። የድማት የጨብጥ፤ የቂጥኝና የቋቁቻ፤ የሚያዋልድ፤ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል

እደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ሱቅ ነው ።



ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ቆፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው ። በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤትነው።

ጉድይር ግዙ

GOODYEAR

2-28-14

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ።

አራተኛ ዓመት ፤ ቍጥር ፴፰
4 me ANNÉE № 38

ሐሙስ መስከረም ፲ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም ።
JEUDI 20 Septembre 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen , Héritier du trône d' Ethiopie , profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix , a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ከልብ አስተውላችሁ አንብቡት ።

የሰላምዋ ጥቅምና የእውነት ጉዳት ።

በጳጉሜን ፫ ቀን ፲፱፻፳ ዓ ም በተጻፈው አእምሮ ጋዜጣ ብዙ የዓለም መንግሥታት ጦርነት እንዳይነሣና ሰላም እንዲሆን ተፈራረሙ የሚል ቃል አነበብሁ ይኸውም የዓለም ሕዝብ በጣም ደስ የሚያሰኛቸው ነው ። ይህንንም መልክም የዓለም መንግሥታት ያቆሙትን ደንብ የዓለም ሕዝብ ሁሉ በደስታ ይቀበሉታል ። እውቀት ያላቸው ሕዝቦች እንደዚህ አንዱ መንግሥት ከሌላው ጋራ መስማማትን እያጸና ሰላምን እያከበረ ይኼዳል ግን እውቀት ያነሳቸው ሕዝቦች እርስ በርሱ ወንድም ከወንድሙ ሲጣሉ ትክክል መንገድ ሆኖ ይታያቸዋል እንደዚህም ያለ ነገር የሥልጣኔ ትምሕርት ባልተማረ ሕዝብ ዘንድ ይበዛል ። ይህንንም ቃል ከሚያነቡ ሰዎች ምነው ከጥቂት ዓመታት በፊት ጀርመንና ፈረንሳዊ በጣም የሥልጣኔ ትምሕርት የተማሩ ሲዋጉ አልነበረም ወይ የሚል ይኖራል ግን ጀርመን እርስ በርሱ ተከፍሎ ወይም ፈረንሳይ እርስ በርሱ ተከፍሎ አልተዋጋም ።

ለምሳሌ አሁን ከ፲ ከ፳ ዓመት ጀምሮ የቺና መንግሥት እርስ በርሱ ተከፍሎ ይዋጋ ጀመረ በዚሁ ጦርነታቸው መካከል የውጭ ሕዝብ የችናን ጉዳት የሚፈልጉ መሣሪያ እያቀበሉ የጠብ ወሬ እየዘሩ ያፋጅዋቸዋልእስከ አሁንም እንደ ተፋጁ ነው ከዚህም ሁሉ የባሰ እርስ በርሱ እየተዋጋ ኖሩ እንደ በረታ ባዩ ጊዜ የዓለም መንግሥት በየበኩላቸው እናንተ ስትዋጉ እኛ ዜጎቻችንን ለጋሲዮኖቻችንንማስጠበቅ ይገባናል ብለው አምሳ ሺ አርባ ሺ ወታደር በቺን አገር ያስገቡ ጀመሩ የቺን ሕዝብም ተዋግቶ እንዳይከለክል ለጋሲዮኖቻችንን ለማስጠበቅ ብንመጣ ደማችንን አፈሰሳችሁ ተብለው ክፉ ፍርድ የሚያገኛቸው ነው ዝም ባለውም እንዳያስገቡ ደግሞ ያነን ጦር ኋላ መልሶ ማስወጣቱ ችግር ነው ስለዚህ ብዙ ጦር በግድ ወደ አገራቸው ገባ በመኻከሉም በመንሹሬ በኩል ከገባው ከጃፓን ጦር ጋራ ተጣሉ መጋደል መጣ በዚሁም ምክንያት የጃፓን ጦር በብዙ መጥቶ ተዋግቶ የመንሹሬ አገር ያዙት ይህም ከሆነ አንድ ዓመት አልሆንም ይህም መንሹሬ የሚባለው አገር ጃፓኖች የያዙት ትልቅነቱ እንደ ኢትዮጵያ ይሆናል ።

እንግዲህ ጃፓን ከመንሹሬ የሚወጣ መቸ እንደሆነ የሚያውቅ የለም ወፍ እርስ በርስዋ ስትጣላት ያዛለች ይህንንም ማንም ያውቃል ። ደግሞም ከዚህ ቀደም ነጻነታቸውን ያጡ አገሮች እርስ በርሳቸው ተከፍለው ሲዋጉ ጠላት አግኝቶ በመጀመሪያ በፖሊቲካ ቀጥሎም በኃይል ገብቶ የያዛቸው አገሮች ናቸው የሥልጣኔ ትምሕርት ያልተማረ ሕዝብ የሠለጠነ ጠላት መጀመሪያ የሚያፋጃቸውን ነገር መሥርቶ አሰናድቶ እራሱን ሳይገልጽ እንዳይታወቅ ነገሩን በሌላ አፍ ይዘራዋል ሰይጣን አዳምን ሲያስተው እራሱ አልተገለጸም በእባብ አፍ ተናግሮ አሳተው እንደዚህ ሁሉ የሰለጠኑ ሕዝቦች ጠላታቸውን ሲያጠቁ መጀመሪያ ተከፍሎ እንዲጣላ ያደርጉታል ዳግመኛም ወዳጅ መስለው ጠቡ እንዲበረታ በመሳሪያም በምክርም ይረዱታል ። ፪ኛ እርስ በርሳቸው ተላልቀው ኃይላቸው ሲደክምም አገሩ እንዳይጠፋ ሽፍታ እንዳይበዛ እንርዳችሁ እንጠብቃችሁ ብለው ጠባቂ ወታደር ሱሞች ያመጡላቸዋል ። ተላልቀው ኃይላቸው ደክሞ ጠባቂ የመጣላቸውም ሕዝቦች ከዚያ በኋላ ባሮች መሆናቸው ነውና ባሮች ወደ ነዱዋቸው እንዲነዱ ማንም አይስተው ወገን ከወገኑ ወንድም ከወንድሙ ዘመድ ከዘመዱ መጣላት የሚያበዛ የሥልጣኔ ትምህርት የሌለው ሕዝብ መሆኑን ከላይም ጽፌዋለሁ ።

የሚያጣላቸውም የገንብ ጥቅምና የማዕረግ ጌትነት ነው ነገር ግን ነጻነታቸውን ከጡ በኋላ የሚጠጠቱን ሕዝቦች ያየ ሰው እጅግም ለዚህ አይጓጓም ። ሰውን ስንት ገንዘብ ቢያገኝ ይበቃዋል ። ምን ያህል ማዕርግስ በቃኝ ይላል ። ከቶ ይኸን የሚነግረኝ አላገኝም ። ላስተዋይ ግን ከነጻነት የበለጠ ማዕርግ የለም ደግሞ አንድ ጋሻ መሬት እንደ ትልቅ ግዛት ይቆጥራታል ። እኔን ደስ ካላለኝ ብሎ አገርን የሚጎዳ ነገር ማውራት ባገር ክፉ መምጣት ስሕተት ነው ። የሰው ልጅ ብርታቱና ቁምነገረኝነቱ አገር መውደዱ የሚታወቀው ደስ ባለው ጊዜ ብቻ አይደለም በከፋውም ጊዜ ነው እንጂ ። ግን ለየራስ ብቻ ማሰብና ደስ ያለው ሰው ብቻ ለአገሬ እሞታለሁ ማለት አይበቃም ዋና የአገር ጉዳት ከአገሩ ሕዝብ ከራሱ ተርፎ ለአገሩ የሚያስብ ሲታጣ ነው ። ፊ ዴሬሳ

ሞንሲኜር ኒኮላ
የግሪክ ጳጳስ ።

ስለ የግሪክ ጳጳስ ።
አዲስ አበባ መግባት ።

ሞንሲኘር ኒኮላ የግሪክ ኦርቶዶክስ ሜትሮፖሊ (ጳጳስ) በኢትዮጵያ ያለውን የግሪክ ሕዝብ መንፈሳዊ ሥራ ለመጐብኘትና ግሪካውያንን ስለሃይማኖታቸው ለማበርታት ከእስክንድርያው የግሪክ ሊቀ ጳጳሳት ተልከው መስከረም ፱ቀን አዲስ አበባ ገቡ

በዚሁ ቀን በአሥር ሰዓት ተኩል ክቡር ዶክቶር ዜርቦስ የግሪክ ቆንስልና በአዲስ አበባ ያሉ ግሪካውያን ሁሉ ከባቡር ማረፊያ ወርደው በክብር ተቀበሏቸው በኢትዮጵያ መንግሥት በኩልም ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዋና ዲረክተር እባቡር ማረፊያ ድረስ ወርደው ተቀበሏቸው ።

ከዚህ በኋላ በአቶሞቢል ሁነው ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን ገቡና ቡራኬ ተደረገ። ቡራኬውም ሲፈጸም ክቡር ዶክቶር ዜርቦስ የግሪክ ቆንስል የደህና መግባታቸውን የሰላምታ ንግግር አቀረቡ ቀጥሎም የግሪክ ማኅበር አለቃ የሰላምታ ቃልና ቤተ ክርስቲያኑ በስማቸው የተጠራው የአባ ሰላማን ታሪክ ተናገሩ በመጨረሻም ጳጳሱ ሞንሲኜር ኒኮላ የመጡበትን ነገር ተናግረው ስለ ተደረገላቸው አቀባበል ምስጋና ሰጥተው ባርከው ጨረሱ። መስከረም ፳ቀን ከልዑል አ ወ ተፈሪ መኰንን ጋራ ተገናኙ።

ሞንሲኘር ኒኮላ በሺ፰፻፺ ዓ ም በናዝሬት ከተማ ተወለዱ በኢየሩሳሌም በቅዱስ መስቀል ተማሪ ቤት ትምህርት ጀምረው በሺ ፱፻፬ ዓ ም በትልቁ የቍስጥንጥንያ ትምህርት ቤት ገቡ በሺ ፱፻፲ ዓ ም በቴዎሎጂ አካዴሚ በቍስጥንጥንያ ገብተው ትምህርታቸውን ፈጽመው በሺ ፱፻፲፬ ዓ ም የቴዎሎጂ ዲፕሎም ተቀበሉ በትምህርታቸውም የተመሰገኑ ስለ ሆነ የአንጾኪየ ፓትርያርክ ሞንሺኜር ጎርጎርዮስ ጠርተዋቸው በትልቁ ጦርነት ጊዜ በመላው የፓርትያርክ ጸሐፊ (ሻንሰሊዬ) ሁነው እስከ ሺ ፱፻፳ ዓ ም ቈዩ ኋላም ከሊቀ ጳጳሱ ሞን ሲኜር ሜሌቲዮስ ወደ እስክንድርያ ተጠርተው በስእክንድርያ ሊቀጳጳሳት ውስጥ ሥራ ያዙና ሺ ፱፻፳፯ ዓ ም ሲፈጸም ከእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ ከሞንሲኜር ሜሌዮስ ከፍ ያለውን የሜትሮ ፖሊስ መዓርግ ሲቀበሉ የአክሱም ጳጳስ ተብለው ተሠየሙ ።

ሞንሲኜር ኒኮላ በቴዎሎጂና በፍትሐ ነገሥት ማወቅ ሊቅ ናቸው ከቋንቋቸውም በላይ የፈረንሳዊ ቋንቋ የእንግሊዝ ቋንቋ ላቲን የቱርክ ቋንቋ የዓረብ ቋንቋ ያውቃሉ የኢትዮጵያንም ቋንቋ ማጥናት ጀምረዋል ኢትዮጵያንም በጣም እንዲወዱ በነጋገር ይገልጻሉ ።

ብርሃንና ሰላም ሞንሲኜር ኒኮላን እንኳን ደህና ገቡ ይላል.

ያልታወቀ ጉዳት

ባንዳንድ ስፍራ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የውጭ አገር ሰዎች ጠጅ ይሸጣሉ ይሉናል እነሱም እንደተለመደው በማር በጌሾ በውኃ እንደ መጣል ሱካር ተምር ሼብ ሲቢርቶ እንድ እጅ እንኳን የማይሆን ማር ይቀላቅሉና ሰርተው ይሸጣሉ ዋጋውም ያንዱ ታኒካ ጠጅ ፩ብር ተሩብ ስለሆነ ማር የምትገዛበት ገንዘብ ያጣች ሴት አዳሪ ሁሉ ከነዚህ ሰዎች እየገዛች

በየሰፈሩ ትሽጣለች ዋጋውም ስለቀለለ በጣም ያነሱላቸዋል ይሁን እንጂ ይህ ሁሉ ሲደረግ ሻጭዎችም ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ ገጋሮዎችም እንደዚሁ ከሽያጩ የሚያተርፉትን በማስተዋል የሕዝቡን ጉዳት የሚመለከት የለም ይኸንኑ የሚመሰክር አንድ ቀን በ፲፩ሰዓት ከሥራዬ ወደ ቤቴ ስመለስ ፪ሰዎች ይኸንኑ ጠጅ ጠጥተው ኖሮ ባንድ በይ ውስጥ ገብተው ተግር እስከራሳቸው በጭቃ ተለውሰው ሲተናነቁ ነበር ለጊዜው ፪ዘበኞች መጥተው ወደ ማረፊያ ቤት ሊወስዷዋቸው አስበው ቢያነሱዋቸው አንዱ ካንዱ እየነጠቀ እመሬት ይፈጠፈጥ ጀመር እዚያ የነበረውም ሰው እየትደነቀ የነዚያ ሰዎች ጠጅ ነው እኮ እንደዚህ የሚያደርጋቸው ይል ነበር ። አሁንም ስለ ዚህ እየተመራመረ የሕዝቡን ጉዳትና ጥቅም ለጤና የሚሆነውንና የከተማውን ሥራ ሁሉ የሚጠብቀው ማዘጋጃ ቤት ነውና ይከፋም ይበጅም እንደሆነ ይኸን ጠጅ ፈትሾ በቶሎ ማወቅ ያስገድደዋል ። እንግዲህ ከዚህ ወዲያ ለሕዝብ የሚጐዳ ተተግኖበት ይኸን የሚጥሉትን ሰዎች የሚገባ መቀጮአቸውን አስከፍሎ ማስተው ነው ማናቸውም ሰው ጥቅሙን ፈላጊ ስለሆነ እላይ የተባለውን ጠጅ ሥራ ተምሮ የሸጠ ጊዜ የባሰ ጉዳት ይመጣል ። አበበ በላቸው ።

ስለ ግሪኮች እርዳታ ።

በግሪክ አገር አሁን በቅርብ ቀን በሆነው በምድር መናወጽ የተነሳ ስለ ተጐዱት አያሌ ሰዎች እርዳታ የሚሆናቸውን ገንዘብ ለመሰብሰብ ተብሎ እዚህ ከተማ የቆመውን ማኅበር ሳይሰሙት አይቀሩም ይመስለኛል ። ይህም ማኅበር የቆመው በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና በልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ዋናነት በውጭ አገር መንግሥት መልክተኞች ተቀዳሚ ዲዩን ፕሬዚዳንነት ነው ። ለእንደዚህ ያለ ለሚያሳዝን አደጋ እርዳታ የሚሆን ገንዘብ መሰብሰብ ተዠምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የተሰበሰበው የገንዘብ ልክ እጅግ ደስ የሚያሰኝ ነው ። ነገር ግን ለመርዳት ፍቃዳቸው የሆኑ ሰዎች ይኖሩና ባለመስማታቸው ትንሽም ትልቅም ቢሆን ስጦታቸው እንዳይቀርብን ይህንን ቃል በጋዜጣዎ ውስጥ አሳትመው የጋዜጣዎ አንባቢዎች ሁሉ እንዲያውቁት እንዲያደርጉልንና የጋዜጣዎ አንባቢዎች ሁሉ ይህ ለጽድቅ የሚሆን በጎ ሥራ ምክንያት ሆኑዋቸው የቸርነታቸውን ሥራ እንዲሰሩልን ስል እለምንዎታለሁ ። ይህም የርዳታ ልመናዬ እንዲፈጸም ጥቂትም አልጠራጠርም ይልቁንም በርስዎ ጋዜጣ በኩል በመሆኑ ትንሽ ትልቁ አበሻ ፈረንጅ ስጦታዬ ትንሽ ነው ትልቅ ነው ሳይል እንዳቅሙ መጠን ሁሉም እርዳታውን አድርጎልን በችግርና በጭንቅ ውስጥ ያሉት የግሪክ አገር ወንድሞቻችን ለመከራቸውና ለችግራቸው መግፍያ የሚሆናቸውን ገንዘብ ለመሰብሰብ ሳይቻለን አይቀርም ብዬ ተስፋ አድርጊያለሁ ። ሙሴ ዠራር

አንድ ሕዝብ ጉዳት ሲያገኘው የቀሩትም ሕዝቦች የሚቻላቸውን እርዳታ ማድረግ መልካም የፍቅር ሥራ ነውና ክቡር ሙሴ ዤራር የቤልጅክ ሚኒስትር እንዳስታወሱን የጉዳት አደጋ ለደረሰባቸው ወንድሞቻችን የግሪክ ሕዝብ ፍቅራችንን የሚገልጽ የቸርነት ሥራ ለመሥራት እጃችንን ልንዘረጋ ይገባናል ።

የከተማ ወሬ ።

በልዑል አልጋ ወራሽ ተማሪ ቤት ፈተና በተደረገ ጊዜ በፈረንሣዊ አራተኛው ክፍል በሁለቱም ዓመት መጀመሪና ሁለተኛ የነበሩ ጐበናና ባሕሩ የሚባሉ ከወለጋ የመጡ ልጆች በልዑል አ ወ ፈቃድ ለትምሕርት ወደ ፈረንሣዊ አገር በ፲፱፻፳፩ ዓ ም በመስከረም ፯ቀን ሲሄዱ የነበሩ ታላላቆች ሰዎች እኒህ ነበሩ ።

ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ከነልጃቸው ግራዝማች ፍቅረሥላሴ ከተማ የባቡር ሹም ፊታውራሪ ደሬሳ ከነልጆቻቼው ። አቶ ታደሰ መሸሻ ። የተማሪቤቱ ዲሬክተር ሙሴ ቶማዚኒ ። በፈረንሳዊ ፫ኛ ክፍል አስተማሪ ሙሴ ጋሪኩይክሲ የተማሪቤቱ ዋና ሹም እንደራሴ ልጅ ቴዎድሮስ ወርቅነህ የቀሩትም የተማሪቤት ሠራተኞችና ተማሪዎች ብዙ ነበሩ ። ሕዝቡ ግን የትምሕርትን ጥቅም ስላወቀ እኒህን ከመሰሉ ከመሰኘት በቀር ፭ሰው እንኳን ሲአለቅስ አላየሁም ይልቁንም ቀኛዝማች ከባ የባሕሩ አባት ። አይዞህ እያሉ ልጃቸውን ከማጸናናት በቀርና ደስ ከመሰኘት በቀር ምንም አላዘኑም ነበር የባቡሩም መሄጃ ሰዓት በደረሰ ጊዜ እማይቸግረው አምላክ ጤናውን ሰጥቶ የሚጠቅም ትምሕርት ተምራችሁ በቅን አገራችሁን ለማገልገል ያብቃችሁ እያልን እንደ አገራችን ልማድ ተሰነባብተን ። ወዲያው ባቡር ተነሳ ። በየዓመቱ ተማሪዎችን ወደሮፓ ለመላክ የልዑል ፈቃድ መሆኑ በየዘመኑ የሚማሩ ልጆች በመላካቸው ያስረዳል ።

ዋናው ትልቁ የሮፓ ትምሕርት ፫ ጥቅም አለው ። መጀመሯ አገርን መውደድ ። ፪ተኛ መስማማት ። ፫ተኛ ። እውነትን ያስታውቃል ።

አገር መውደድም ማለት ከራሱ ጥቅም አብልጦ ያገርን ጥቅም መፈለግ ነው መሣሪንም እየወለወሉ ለወሰን መጠበቂያ ማድረግ ነው እንጂ ባገሩ ሰው ላይ ክፉ አለማሰብ ነው ። መስማማትም ማለት ጋላ ሻንቅላ ሺዬ ጐጃሜ ወሎዬ ላስቴ ትግሬ ጐንደሬ ሳይሉ ለሁሉ የሚገባውን ሥራውን መስጠት ነው እውነትም ማለት ባይድ ዘመድ ቅርብ ሩቅ ሳይሉ ለመንግሥት ሥራ የሚስማማውን የታመነውን መምረጥ ነው ። እኛስ እድሜአችንን እንደነገሩ ገፍተነዋል ። የሚመጣው ትውልድ ደግሞ እኛ ከነበርንበት ፈተና እንዳይደርስ የትምሕርትን ነገር እንደቀድሟችሁ እንድታሳስቡ ለብርሃንና ሰላም ወዳጆች አሳስባችኋለሁ የብርሃንና ሰላም ወዳጅ ማኅተመ ወርቅ እሼቴ ።

ስለ ትምሕርት ማስታወሻ

ባለፉት ዓመታት ስለአገራችን ጥቅም ለወንድሞቻችን ማሰልጠኛ ፊታውራሪ ዴሬሳ አስበው ኢትዮጵያውያንን ሁሉ ለጠሩበት እርዳታ እኔም ተማሪው እንዳቅሜ ካለሁበት አሩቅ በታ ጥሪውን ሰምቼ አቤት ስል ፶፭ ሌሬ ስለ ፹፪ መሐለቅ ሂሳብ ባሉኝ መጻሕፍቶቼና በእራሴ ቁጥር ሰደድኩኝ ። ምንም ሳገ

ሬና ለወንድሞቼ ለሚጠቅመው እርዳታ ነፍሴ እንደ ምትወደው ነፍሴ እንደምታስበው በብዙ ለመርዳት የማልችል ተማሪ ብሆን ባሉኝ አስተማሪዎቼ በሚሰጡኝ መጻሕፍቶቼ (ከብቶቼ) ቁጥር አንድ ፩ መሐ በየመቱ እሰጣለሁ ስል በፊርማዬ ኢየመሰከርኩ በሶስተኛው ዓመት ብርሃንና ሰላም ቁጥር ፹፯ ገጽ ፪፻፲ በ፪ተኛው መስመር እስከ ፵፯ተኛው መስመር አስረድቼ በስሜ መሰከርኩ ።

ይህንንም እኔ ድሀው በሰው እጅ አዳሪው ማድረጌ ላገሬን ትልቅነት መርዳት በመላሴ (በማለት) ተቻ ያይደል በማድረግና በመሥራት በተግባሬ ሁሉ መደገፍን የምወድ መሆኔን ለወንድሞቼ እንዳሳይና ሁለንተናችን ላገራችን አገራችን ለሁለንተናችን ለእኛ መሆኑን አስረዳለሁ ስል ነበር ። ከኔ ይበልጥ ባገራቸው ስምና በእሷ የከበሩ ወንድሞቼን እቀሰቅሳለሁ ስል ተነስቼ ነበረ ። መቼም የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲያውቅ የተኛ ቢጠሩት አይሰማ መሆኑን ይኸንን እርዳታዬን ሳላደርግ በፊት ብዙህ ወንድሞቻችን ሲጠሩአቸው ባለመንቃታቸው ተረድቼ ነበርና የሕዝብ አሳዳሪ አባትን እጠራ ብዬ በብርሃንና ሰላም ሁለተኛ ዓመት ቁ፴፱ገጽ ፫፻፰ ሁለተኛው አምድ መስመር ፳፫ የኢትዮጵያ መኳንንትና ሕዝቦች ፆ የእግዚአብሔር እንደራሴ የሆነ ዳኛ(አባት መንግሥት) ይኸንን ነገረኛ ወርቅ እንደሚከተሉት ፭ ቃላት እንዲያወጣልን በድንቁርናችን ተጐድታ የምታሳዝነዋን እናታችንን ኢትዮጵያን ይዘን እንጮህላታለን፡ ትንንሾቹ ልጆችዋ ።

ደሀ እንዳይጎዳ ።

ካብታም እንዳይቆጣ ።

አገር እንዳይጠቃ ።

ሕዝቡ ዘለዓለም በድንቁርናእንዳይቀበር ።

ጠላት ወዳገራችን እንዳይቃጣ ። የሚያስበው ዳኛ ፈቃዱ ሆኖ በነዚህ ሕግጋት አድርጎ የተማሪ የሥልጥንና ቤቶቻችንን ማሰናጃና ለየትምሕርታችን ማጀማመሪያ የሚበቃ ገንዘብ እንዲያስወጣ የታወቀ ነው ስል በኢትዮጵያ ሕፃናት ሁሉ ስም አባታችንን ብጠራው የዝሆን ጆሮ ይስጠኝ ሲል መንግሥትም አደፈጠ ።

ይኸ የሚከተለው ስለሥልጥንና አወጣጥ ደንብ የልጆች አሳብ ቢመስለው እንኳን የሚሻለውን ከልጆች አባት ያውቃልና ሌላ ደንብ ባወጣልን ነበር ። ሕዝቡም ዝም መንግሥቱም ዝም። ዝም አይነቅዝም ከሉ ማን ሊመጣልን ይሆን።

ደሀ የማይጎዳ ካብታም የማያስቆጣ የመሰለኝን ደንብ ለተቆርቋሪ አንባቢ አመለክታለሁ ።

፩ኛ እስላም ክርስቲያን ሴትንሽ መነኩሴ ልጅ ነህ ሽማግሌ ሳይባል በሰው ፩ ፩ መሐለቅ ነጋዴ የሆነ ፪ መ መኳንንትና ወይዛዝር እሩብ እሩብ

፪ኛ፡ በጐጆ ፩፩ መ በዳራሽ ፪መ በሱቅ ፪መ በባሕር እቃና በመጠጥ ሱቅ እሩብ በትልልቅ ሰቀላ ቤትና ፎቅ እሩብ እሩብ እጅግ ትልልቅ በሆኑ በግምት።

፫ኛ ። በከተማ በታ አላድ በባላገር በታ ፪ መ በኩርማን መሬት እሩብ በጋሻ ግማሽ አላድ ። ባንድ ጋሻ ብር ለም ነው ጠፍ ነው ሳይባል ባለቤቱ (በእውቀቱ ማነስ ባያለማው ነው እንጂ መሬቱስ ለም ነበር።)

፬ኛ ። በበቅሎ በፈረስ በላም በበሬ በግመል ፩ ፩ መ በ፫ አህያ ፪ መ በ፬ በግና ፍየል ፩ መ በ፮ ዶሮ ፩ መ ።

፭ኛ ። በጠመንጃ ፩ ፩ መ ። የመንግሥት ጠመንጃ የያዘ ወታደር ፩ መ ከራሱ ፩ መ ከመንግሥት የሻለቃ ብረት የያዘ ፩ መ ከእራሱ ፩ መ ባለ ብረቱ ።

እንደዚህ ሆኖ የተዋጣ እንደሁ ድሀ እንደ ድህነቱ ካብታም እንደ ካብቱ በዚህ ልክ ለሕዝቡ ማሠልጠኛ ገንዘብ ቢያዋጣ መልካም ነበር ይላል ። በዚህ አወጣጥ ደሀ አይጎዳም ካብታም አይቆጣም ማለቱን መረዳት የፈለገ በ፪ተኛው ዓመት ፫፻፱ ገጽ ይመልከት ።

ይኸንን አወጣጥ ደንብ የመረመሩ ከነገሮች አንዱ አንዱ መኰንን በሁለተኛው ዓመት ፶፩ ቍ በ፬፻፷ ገጽ በ፲ረኛው መስ እንዲህ ይላሉ ።እንግዲህ ወቀሰቹን ሁሉ ብርሃንና ሰላም ሆይ መንግሥት ሆይ እውነትም የተማሪ ቤት እንዲቆም የግድ የሚያስፈልግ ነውና ለማቆም የበቃ ገንዘብ ለማግኘት መ ስ ወ እንደጻፈው ገንዘብ አወጣጥ ትእዛዝ ቢሆን ካለኝ ገንዘብሁሉ እሱ በጻፈው አከኼድ እጥፍ ወይም ሶስት እጥፍ እንኳ ብሰጥ ቅር የሚለኝ አይደለም ይላሉ።

እኔ እንደሚመስለኝ ከመንግሥት ደንብ ብናጣ ነው እንጂ መኳንንቱና ሕዝቡ ሁሉ በደንብ ሊያወጣ የወደደ ነው ።

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል ።

ማስታወቂያ

አድነው ካሣዬ የሚባል ። መልኩ ቀይ ጥርሱ ዝርዝር ግራ ጆሮውን የተበሳ እጁን የተነቀሰ ዳዊት የደገመና ጽሕፈት የሚያውቅ የዘጠኝ ዓመት ልጅ የሥጋ ቤቱ የሻለቃ የግራዝማች ካሣዬ አልታዬ የወለደው ልጅ፡ ጳጉሜ ፩ ቀን ሐሙስ በ፰ ሰዓት አዲስ አባባ ከአባቱ ቤት ምክንያት ሳይኖረው ከቤቱ ጠፍቷልና ይህንን ልጅ ከዚህ በላይ በተጻፈው ምልክት እየተመራመረ ፈልጎ ያገኘ ሰው ሽልማትና ገንዘብ ይቀበላል ስልክ በተዘረጋበት አገር ሁሉ መንግሥት ለየአገረገዢው ሁሉ አስታውቋል ከዚህ በተቀር ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ለሚያነቡ ሰዎች በየጐረቤቶቻቸውና በየወዳጆቻቸው ሁሉ እንዲመራመሩበት ነው የልጁም አባት ግራዝማች ካሣዬ አልታዬ በሀገራችን እንደዚህ ያለ ነገር ስለ ሌለ አዲስ ጉድ ነውና ይህንን ጭንቅ ወላድ ይገምተኝ እያለ ኀዘኑን እጅግ አብዝቶታልና የሆነው ምክንያት እስቲታወቅ ድረስ ልዑል አምላክ ትዕግሥቱን ይስጠው

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጀኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዌድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg malmö och Karlstad

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ባርባሬሶ

ኮ ኛ ክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ ።

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በካፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በካፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ማስታወቂያ ።

አዲስ ሐኪም የመጣ ዶክተር ኤፍ ኤርል ፌሬደሪለብ የሚባል በጀርመን አገር በህክምናው የተሸለመና የምስክር ወረቀት ያለው ከልጅ ይመኙ ቤት ውስጥ የመድኃኒት ቤት ከፍቷል ። የመድኃኒት መስሪያው ቤትም የሚገኘው በጋኖታኪስ ቤት ያለው መንገድ ወደ ግቢ የሚወስደው አፈርናዲስ ኮት ሰፈው ቤት በታች ያለ አዲስ ፎቅ ከሆቴል በሉላጉስ ትይዩ የሆነው እምድር ቤቱ ያከማል ። ከመድኃኒት ቤት ለመታከም የሚፈልጉ ሰዎች ሐኪሙን ከ፪ ሰዓት ከጧዋቱ እስከ ፭ ሰዓት ተኩል ይገኛል ። ከ፮ ሰዓት በኋላ ከ፲ ሰዓት ጀምሮ እስከ ፲፪ ሰዓት ከመድኃኒት ቤት ያከማል ። ነገር ግን ከመለከትነው ሰዓት በተቀር ሌላውን ጊዚያት ሰዓታቶች እቤቱ ያከማል ። ቤቱም ያለበት አቶ አድነው ቤት ውስጥ ነው ከመድኃኒቱ ቤት ትንሽ ወረድ ብሎ ።

ያዲስ አበባ ገባያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር ተኩል
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፪ ብር ተኩል
ዝባድ	፩ ወቄት	፫ብር ተኩል
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፴ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፯ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፰ ብር
አቡጀዲ መነጸር	፩ ኮረጃ	፻፶፮ ብር
፡፡ ባለሰይጣን	፡፡	፻፶፬ ብር ተኩል
፡፡ ባለ ድመት ።		፻፶ ብር
፡፡ ባለአህያ	።	፻፳፫ ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል	።	፻፵ ብር
ባለ አንበሳ	፡፡	፻፸፱ ብር
ሱካር	፩ ጁኒያ	፳፮ ብር
ቻይ	፩ ነጥር	፩ ብር

ስለ ምንዛሪ

አንድ ብር	፲፮ ፍራንክ
አንድ ብር	ሊሬ ፰ ከ፹፯ ሳንቲም
ባንድ ጊኒ	፲ ብር ፸፬ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፵፰ ብር

ዓለም ሱቅ ፲፪ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዱኄ ለመሸጥ ይቻላል።

COGNAC S.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩግቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

RUGBY

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፥ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ኦቤርላንድ



ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሽ አቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጦጦን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባ ኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኜቶና ባለባተሪ ነው ካምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን ያለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል «ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው

ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

ማስታወቂያ

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሰተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲	ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር	፱	ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
የዓለም ጅኦግራፊ በአማሪኛ ደኅና ጥራዝ ዋጋው	፯	ብር
» » » መናኛ ጥራዝ ዋጋው	፭	ብር
ደግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፭	ብር
ጎሐ ጽባሕ	፭	ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫	ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫	ብር
የሕይወት ታሪክ	፪	ብር ተኩል
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪	ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪	ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትርሜንው	፪	ብር
የቁጥር ትምርት	፩	ብር
ያማሪኛ ሰዋስው	፩	ብር
ወዳጄ ልቤ	፩	ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን		አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ		አላድ
አጭር የዓለም ታሪክ		አላድ
ያማሪኛ ፊደል		ሩብ
አሳብና ምኞት		ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት		ሩብ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፪	መ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር	፪	መ
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ		ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶ ግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ		ሩብ

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ፤ የልብ ፤ የደረት ፤ የጉበት ፤ የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ፣ የቂጥኝና የቋቁቻ፣ የሚያዋልድ፣ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል

እደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ሱቅ ነው ።

ከ ቤጥ አዲስ ዓ
ይነት ላ አሜሪካን ቤት
ይሠራል ላስቲክ ስሙ
ጉድይ ሲሄድ እንደ
ማጭ ጉም በልክ ይ
ሃዳል ቅታም ላይ
በሆን እንደ ልብ
ያስኬ በጭራ አያድ
ጠው ላይ ሲሄድ
ከሌ ጠንካራ ነ
ው ላቲክ ብትፈ
ልግ ላስቲክ ጉ
ድይ ላስቲክ ሁሉ
ሁስ ል ዋጋው
ግን ሉም ርኸሽ
ነው ገኘው ዓረ
ብያ ቤትነው።

በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታተመ።

አራተኛ ዓመት፣ ቁጥር ፴፱
4 me ANNÉE № 39

ሐሙስ መስከረም ፲፯ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም።
JEUDI 27 Septembre 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።	የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሲገዛ ለፊስን በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።	Abonnements Ethiopie Un an 5 Thalers Etranger Un an 7 Thale:s le numero 2 piastres

ያጤ መስቀል በዓል አከባበር

መስከረም ፲ቀ'ን ከጥዋቱ በሶስት ሰዓት ልዑል የኢ. መ አ ወ ተፈሪ መኰንን ባማረ አጀብ ሆነው ወደቤተ መንግሥቱ ወረዱ. በቤተ መንግሥቱም የበዓሉን አከባበር ለማየት የመጣ ሰው ብዛቱ ከልክ ያለፈ ነበር የውጭ አገጋ ሚኒስትሮችና መኳንንቶች ወይዛዝሮችም የበዓሉን አከባበር ለማየት ወደ ቤተ መንግሥቱ መጡ በዚህም ጊዜ ያጤ መስቀል ፈንጠዝያ የሚታይበት ቦታ አምሮ ተነጠፈና በዙርያው ወንበር ተደረደረበት ከደረጃውምበታች ባለው ወለል ባንድ ትልቅ ጠረጴዛ ላይ ብዙ የተጐነጐነ አበባ በያይነቱ ተከምሮ ይታይ ነበረ ።

አራት ሰዓትም ሲሞላ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ልዑል የኢ. መ አ ወ ተፈሪ መኰንን በክቡራን መኳንንቶቻቸው ታጅበው መጡና ከደረጃው አምሮ በተሰናዳው አንበር ተቀመጡ የውጭ አገር ሚኒስትሮችና መኳንንቶችም በየመዓርጋቸው ከልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን በስተቀኝ ባለው ስፍራ ተቀመጡ በስተግራ በኩልም ብፁዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ የኢትዮጵያ ሚኒስትሮችና መኳንንቶችም በየመዓርጋቸው ተቀመጡ ሰውም ሁሉ በየመዓርጉ በተቀመጠ ጊዜ ካህናቱ ሥርዓታቸውን ጀመሩ ካህናቱም ባማረና በተስማማ ድምጽ ሲዘምሩ እጅግ ደስ ያሰኙ ነበር ። ሥርዓታቸውንም ሲጨርሱ ብፁዕ እጨጌ ገብረመንፈስቅዱስካህናቱ ያቀረቡትን አበባ ተቀብለው መጀመሯ ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ለልዑል አልጋ ወራሽ ሰጡ ቀጥሎም ለመኳንንቶቹ ሁሉ የቀረውንም አበባ ክዚያ ለተሰበሰበው ሠራዊት ይናኙት ጀመር። ካህናቱም ሲያሸበሽቡና ሠራዊቱ አበባ ሲሻማ ላየው የሚያስገርም ነበር ከዚህም በኋላ ብፁዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ባርከው አሳርገው ሕዝቡን አሰናበቱት የውጭ አገጋ ሰዎችም ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትንና ልዑል አልጋ ወራሽን እየተሰናበቱ ሔዱ. ግርማዊት ንግ ነገ ዘውዲቱና ልዑል የኢ. መ አ ተፈሪ መኰንንም ለየአድባራቱ ካህናትና ሊቃውንት ግብር ለማብላት ከትልቁ አዳራሽ ገቡ ያጤ መስቀል በዓል አከባበር በእንዲህ ያለ ደስታ ተፈጸመ ።

እንደዚሁም ደግሞ ለሚመጣው ዓመት በትልቅ ደስታ እንዲያደርሰን ተስፋ እናደርጋለን ።

ወኢይፃእ ዓቢይ ነገር እምአፉክሙ ።

በእግዚአብሔር መታመን በጣም የበረከት ተስፋ ያስገኛል እንደዚህም በታላቁ ቸሩ ጌታችን እየታመንን ሀገራችንን ለመጠበቅ ችላ አንልም ። የመንግሥታችንንም እድሜ በንጹሕ እንለምናለን ።

በኀዘናችንም ብዛት እግዚአብሔር መንፈሱን በሀገራችን አበርክቷል ስለዚህም ውዴታና ፍቅር ይደርብን እርስ በርሳችንም የቅንዓት አካሄድ ክፉ መንገድ እንዳንጀምር መልካም ሐሳብ ያሰስበናል ። አሁን ግን የሥልጣኔ በረከት በሀገራችን እንዲሰፋ እንደተደረገ እርግጥ ሆኖ ታውቋል ። ነገር ግን በጣሙ የእውቀትና የሥልጣኔ እጅዋን ይዘን ደስ እስኪለን ድረስ የስድብና የሐሚታ ስልቻ እንዳንሸከም ምኞታችን ነው ይልቁንም የስንፍና ስም ተሸክመን ለምንስ እንቀመጣለን በማለት የሥልጣኔ አነሣሥ እንነሣለን ። እንዲሁም አሁንም በጥሩ ሥልጣኔ መንገድ ለማዝገም የማይቻል እንደሆነ የማያስኬደውን ሐሳብ በብርቱ ማስተዋል ያስፈልጋል ።

ለዓለምም ሰዎች ጥሩ ምሳሌ ይሆናቸዋል ይህም ስለተባለ ሀገራችን ኢትዮጵያ ፍቅርዋን ከዓለም ሙሉ በነጻ እንድታለመልም ነው ሀገሩን የሚወድ ይህ ታላቅ ሰው ተብሎ ስሙን በደግ ቦታ እንዲጸድቅ አድርጎ የሚተክል እንዴት በውድ ዋጋ ለመግዛት ይፈለጋል ። ስለ ሆነ በለምለም ሀገራችን የሥ

ልጣኔ በረከት በፍጥነት እንዲሰፋ የፈለገ ይህን ታላቅሰው እየተመለከትን ብንፈጽምለት ታላቅ ክብርና ጥቅም ሳናገኝ አንቀርም ሰው ግን በልቡ ደግና ክፉን ይመኛል የብርሃኑን በጭለማ ይሁን እንጂ የሀገሩ ውዴታ ያደረበት የጭለማውን በብርሃን ይገልጸዋል ። ምኞቱም ሰላም እንዲሆን ሲያስብ ይናገራል ግን በጭለማ የሆነ ሐሳብ ሁሉ እንደማይታይ ነውና ከምንም ነገር ሊገባና ሊቈጠር አይችልም ወዳጄ ሆይ የልብህን ስለ ሀገርህ የሚሆነውን ደግ ሐሳብና ምኞት በግልጽ በብርሃን ብትገልጸው የደግ ሐሳብህ መንገድ እጅግ የቀና ይሆናል ። ደግሞ በፍጥረቶች መከከል ምንም እሚተናኰልና ያልተተካከለ ነገር ቢገኝ ይኸንን እንደዚህ ያለውን በፍጥነት ማደላደል ግዳችን ነው በሀገራችን በሽፍን ያሉ ነገሮች እነማናቸው ከልብ ሳይሆን መሳቀ ተንኰል ምቀኝነት ቅንዓት ናቸው እንደዚህም የመሰሉ ነገሮች በባልሆችና በእውቀተኞች በጣም የተጸሉና የተረገሙ ሳይሆኑ አይቀሩም በምኞት ግን ዋና ማደኛ ገንዘባቸው ነው ። ነገር ግን እለ እግዚአብሔር በተቀር ሁሉን የሚችልና የሚያደርግ አይገኝም ወደ ገደል መንጠራራት ይሆናል ።

የሀገሩን ጉዳት ሲአስብ በችግር ያለም ወይም በደስታ ወንድም ሴትም በእውነት የማያዝንና የማያለቅስ አይገኝም ክቡራን የኢትዮጵያ ልጆች አሁን በቅርብ ዘመን ልባችን አርፎ ሰውነታችን ታግሦ ሀገራችን የሥልጣኔ ዓይን አውጥታ ሳለች ዝም ብለን አንድነት ሁነን እማይሆነው ነገር ይህ አይሆንም እያልን ከልብ ሆነን ሀገራችንን ብንደግፍ መልካም ውብ ነው ። ከዚህ ወዲያ አንድነት ካልሆንን የኃይለኝነት የክፉ መንገድን ካሰብን ቆንጆዋ ኢትዮጵያ ከሥልጣኔ ብዙ ጊዜ እንድትቆይ አይጠረጠርም እውነት ነው በሥልጣኔ የተመሠረተው ሲፈርስ እውቀተኞች ልጆች በከንቱ ሲወድቁ ጥቅሙ ምንድነው? ።

ገና ሁለተኛ ሲሠራና ሲወለድ ይባል ይሆን? ያሳዝናል ወዳጆቼ ወንድሞቼ የኢትዮጵያ ልጆች አሁንም በሀገራችን ይህ የምናየው የሥልጣኔ ዓይናችን እንዳይጠፋብንና እንዳይፈስ ኀዘናችን ለዘወትር ይሁን ።

ሥዩም ወልደ ገብርኤል ።

የኀዘን ውበት ።

ከዕለታት አንድ ቀን ከንዱ ወዳጄ ቤት ሂጄ ባቀረበልኝ ወምበር ላይ ተቀምጬ ሳለ ከቤቱ ግድግዳ ላይ የተጻፈ ቃል አየሁ ቃሉም እንዲህ ይላል ልብን የሚወጋ እሾህ ኀዘን ነው። ከዚህ በኋላ እኔ ከወዳጄ ጋራ ይህ ጽሕፈት ልክ አይደለም ይህን መጻፍ የሚገባው ኀዘን የልብ አበባ ነው ተብሎ ቢጻፍ መልካም ነበር ብዬ አልኩት በዚሁ ነገር ብዙ ጊዜ ከተጣላንበት በኋላ እውነት ነው ሰው ሁሉ ከትልቅ ትዕግሥት የተነሣ ልቡን የሚወጋው የኀዘን እሾህ አበባ ለማድረግ ይችላል። ይህ የልብ ኀዘን እንጥረኞች ወርቅን በእሳት እንዲያቀልጡ እንዲሁም ጠባያችንና ፍቅራችንን የሚያነጥር ነበልባል መሆን ይገባዋል።

አዎን የጨዋ ልጅ በኀዘን ነበልባል ውስጥ የወደቀ እንደሆነ ፈጽሞ ይቃጠላል ነገር ግን ስለ ተቃጠለ አመድ ለመሆን አይችልም ይልቁንም እጅግ የተዋበና ያማረ ደስ የሚያሰኝና እውቀት ያለው ይሆናል። ከቶ ኀዘን ልብን የሚወጋ እሾህ አይሆንም ስለ ምነው ዓለም ሁሉ የናዝሬቱን ኢየሱስ ክርስቶስን የሚወድ? ። ይህም መሆኑ በጌታሴማኒ አትልክት በፍራ ውስጥ የልብ ኀዘን ሥቃይ ስላየ ነው።

ደግሞም በጎልጎታ ስለተሰቀለ እነሆ ይህነን ያህል ከሁሉ የበለጠ ሥቃይ ሰዎቹን ለማዳን ሲል ተቀበለ ይህ የልብ ኀዘን ነው ከፍ ያለና ትልቅ ውበት ያለው ያደረገው ።

ትልቅ ሰው በመከራው ጊዜ በዓለም ውስጥ ካለው ጊዜ ሁሉ ይልቅ ደስ ይለዋል ። ታላቁም የደስታ ኑሮ በመከራ ነውና የሚገኘው ሰው የመከራን በትር በድፍረት መቀበል ይገባዋል ።

እንዲሁም ሁል ጊዜ መከራን አሸናፊ መከራን ድል መንሳት ይገባዋል ።

ዋናው የታሪክ መጽሐፍ ።

ታላላቅ ሰዎች ሁሉ ልብን የሚወጋውን የኀዘንን እሾህ ተቀብለውታል ሲል ይነግረናል ዓውሎ ነፋስ በተነሣ ጊዜ ያበቡ አበቦች በየተራራው ላይ እንደሚገኙ ሁሉ እንዲሁም በመከራ ውስጥ ሆነው በጎልጎታ ላይ እንደተደረገው ያለ ጭንቀት (ሥቃይ) ወድቆባቸው ልቡናቸውን ከፍተው ሲያዩት መልካም አትክልትና አበባ ይገኙበታል ። እነዚሁም አበቦቹ በሕይወታቸው ጊዜ እንድ አክሊል ይሆኑዋቸዋል ።

ጎልጎታ ላይ የነበረ ማለት (በሥቃይ ስፍራ) ብፁዕ ነው የመከራውን ጊዜ በትዕግሥት ያሳለፈ ብፁዕ ነው ፣ በመከራ ጊዜ አትንቀጥቀጡ መከራንም ለመቀበል አይዞንልንም አትበሉ አትበሳጩም መከራ መፈተኑን አይተውምና ይፈትናችኋል ጉብዝናም ይሰጣችኋል ።

አንድ ታላቅ ሰው በዲስኩሩ (በምርቃቱ) ውስጥ እንዲህ ሲል የተናገረውን ቃል የማስታወሻ ጊዜ እነሆ አሁን ነው መቶ ዓመት በበርነት ውስጥ ከመቀመጥ ፩ ቀን እንደ አንበሳ ሆኖ መዋል ይበልጠዋል ።

ካፒቴን ባቢኪያን ።

መጀመሯ ስለ ኢትዮጵያ እህል መወደድና ተዱሮ ዘመን ሽመታ ማነስ ።

ከዚህ ቀድሞ ከጅቡቲ ጀምሮ እስከ ነጭ አባይ ድረስ ከዚያም እስከ ቋራ ጥግ ድረስ ኢትዮጵያ በመላው ሽመታ ረኪስ ነበረ ዛሬ ግን ውድ ሆነ ዱሮ ግን እህል ብዙ ስለ ነበረ በባላገር ዳውላው በአንድ ብር ይሸመት ነበረ በከተማ ግን ነጋዴ ስለ ከብቱና ስለ ጉልበቱ እያሰበ አሥር ቁና በተወደደ ጊዜ ፰ ቁና ይሸጥ ነበረ ከዚህ በላይ አሳንሶ የሚሸምት የለም ነበረ ዛሬ ግን ፩ ቁና በ፩ ብር ቢገኝ ነው እንጂ ከዚህ የሚበልጥ በከተማና በዳር በዳሩ አይገኝም እስከ ፲ቁና የሚሸመትበት የበለጠ በአሩሲ በሲዳሞ በጅማና በከንታ በማጅና በከፋ በጐሎና በወለጋ ነው የሚገኝ እንጂ በሌላ በታ አይገኝም ጐጃምና ትግሬ ወሎን ጨምሮ እጅግ እርካሽ ቢሆን ተ፰ በላይ አይገኝም ሸዋ በመላው በከተማው ፩ ፩ ቁና በከተማው ው

ጭ ግን ከ፱ እስከ ፲ ወይም ፩ ቁና ቢገኝ ነው እንጂ ከዚህ በላይ አይገኝም ከሐዋሽ በመለስ እስከ በርበሬ ድረስ ፩ ቁና ወይም ፪ ቢገኝ ነው ። ጨርጨር ግን ፫ ቢገኝ ነው እንጂ ከዚህ የበለጠ አይገኝም ። ፪ተኛ ፡ ይኸንን ነገር ልብ አድርገን ብናስበው አራሽ ብዙ ስለ ሌለ ሁሉም ገበሬ እርሻውን ትቶ ለንግድ ወታደርነት (አሽከርነት) አንዳንዱም ሽፍትነት አንዳንዱም ጫት ያለው ኮርቻውን ለምኖ ያለው ስልቻውን አያጣም ብሎ ሙሉ አካል ሳለው እየዞረ ይለምናል ወሬውን ስንሰማ በዚች ዓለም በየአገሩ ያለውን ደንብ ሲያወሩልን እግርና እጅ ያለው ሰው ሲለምን ቢገኝ በግዞት ቤት ተጨምሮ ለመንግሥት ይሠራል ብለው ያጫውቱናል ደህናው ሰው ሲለምን እያዩ ሽፍታም እንደ ዱሮ እጫካ ተቀምጦ ተዘርፎ መንገደኛንና ነጋዴን አይነጥቅም ዛሬ የመንግሥት ሥራት ስለ ጠነከረባቸውና ቅጣት ስለ በዛባቸው እጫካ ገብተው አይሸፍቱም ዛሬ ሌባና አታላይ የሚገኝ በከተማ ውስጥና በገበያ በአመንዝሮች ቤት እያደሩ ቀን ቀን ጋላና የባላገር ሰው እርስ በራሳቸው አንባጓሮ አንስተው ያንን ሞኝ ሰው አታለው ገንዘቡን ቀምተው ሰው ሳያውቃቸው በየቦታው ይበታተናሉ ። አሁን በኢትዮጵያ በየከተማው ሥራ ሳይዝ የተቀመጠ ብዙ አይነት ሕዝብ ይገኛል ።

፫ተኛ ፡ የቱጃር አሽከሮችና ያልሠለጠነ ወታደር ደመወዝ ፫ ወይም ፮ ቢአገኝ ነው እንጂ ከዚህ በላይ አያገኝም የቱጃር አሽከር ግን ልብሱን በሳሙና አንጽቶ ከመሔድ በቀር ገንዘብ አትርፎ ባለጸጋ ሁኖ የሔደ የለም ነጋዴ ገባያ የገባለት እንደሆነ ብዙ ትርፍ ያገኛል ገባያ ባይገባ ከስሮ ድኅነት ይገባል ጠንክሮ ባገሩ የሚአርስ ሰው ግን ትኩስ እንጀራ በልቶ ወተትና ጠላ ጠጥቶ በተድላ ይኖራል ። አዲስ የገባ ወታደርና የቱጃር አሽከር እንጀራ ጠግቦ ሳይበላ ለሰውነቱ ሳይመቸው ይኖራል ወታደር ግን ቆይቶ ተሹሞ ሽረት አያጣም ነገር ግን እንደዚህ በፈረንጅ ቤትና በሌላ ሥራ ተጨንቆ ተጠቦ ከማደር አርሶ ቢበላ ብዙ ጥቅም ያገኝበት ነበረ ደግሞ በጌቶቻችን በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በልዑል አልጋ ወራሽ በረከት ለ፩ ሰው ኩርማን እንጀራ ይበቃዋል በሰዎች ስንፍና እህል ተወደደ እንጂ ረሃብ አልሆነም ይልቁንም በየቤታችን በረከት በውሥጣችን ሞልቶ መሰቡ እንደ ሞላ ይመስላል ። የጥጋብ ዘመን መሆኑን በዚህ እንረዳለን ።

፬ተኛ ። ወታደሮች ሁሉ እባካችሁ በርቱ ። ገበሬ ሁናችሁ ብዙ እህል አምርቱ ። ጠመንጃ ይዛችሁ ተመንከራተቱ ። ነዶ ሰብስባችሁ ጐተራ ክተቱ ። ንግድ የሚነግድ ሰው እርሻ ካላረሰ ። እህል ውድ ሆነና ብርም ረከሰ ። ሕዝቡም ፍራት ይዞት ባዘን አለቀሰ ሞፈር ቀንበር ይዞ እርሻ ካላረሰ ። እኔ አላርስም ያለ እጁን አለስልሶ ። ጭንቀት ይቀበላል መልሶ መልሶ ። በችጋር ይሞታል አካሉ ከስሶ ። ሥራ የማይሠራ ሰው ምንም ትርፍ የለው ። አካሉ እያከከ መቅራመድ ነው ። ሥራ አልሠራም ብሎ አፉን አዘጋው ። እርሻን የጠላ ሰው ምንም ትርፍ የለው ። እኔ ስነግራችሁ ብትሰሙ ምነው ። ጌትነት የሚአገኝ የሚአርስ ሰው ነው ። ጌታችንም ለአዳም ሥራ ሲሰጠው በፊትህ ወዝ ብላ ብሎ ረገመው ። ብዙ ስጋት ያዘኝ እኔ እፈራለሁ ። እንጀራ ታልበላሁ ዛሬ እሞታለሁ ። ጠንክሬ ብሠራ ብዙ እከብራለሁ ። እርሻ አላርስም ብሎ የሚፈራ ብርድ ። ዶማ እየሰቀሉ ከገር መሰደድ ። ውርደት መቀበል ነው ቆይቶ በፍርድ ። ስደተኛ ሁሉ ተመለስ አገርህ ። ሞፈር አቀናብረህ እርሻ ካላረስህ ። ምን ትበላ ይሆን ትኒሽ ሥራ እባክህ ።

ተስፋ ገብረ ሥላሴ።

ብርሃንን ለማግኘት ሐሙስን ስለ መጠባበቅ ።

ክቡራን የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ሆይ ከዚህ ቀጥሎ በትንሽ ሐሳቤ የምጽፈው ከናንተ የተሰወረና ወይም እናንተ የማታውቁት ነው ብዬ አይደለም ። ግን ሰው በተቻለው መጠን ለአገሩ ጥቅም የሚሆነውን ነገር ሁሉ ማስታወስ የግድ የሚያስፈልገው ነውና እኔም በታየኝ መጠን የጻፍኩትን በጐደለ ሞልታችሁ ባነሰ ጨምራችሁ ልታነቡልኝ ክቡር ፈቃዳችሁን እለምናለሁ ። ልዑል አልጋ ወራሻችን ስለ ሕዝባቸው ጥቅምና ስለ መንግሥታቸው ስፋት ብለው ብርሃንና ሰላም የሚባል ጋዜጣ ላገራቸው ካወጡ ጊዜው እንደምናውቀው ቅርብ ነው ። አገራችን ኢትዮጵያ ግን በሱ የተጠቀመችው ጥቅም ይህን ያህል ነው ብለን ልንቆጥረው አንችልም ።

መጀመሪያ ነገር ደግሞ ጋዜጣ ለሕዝብ ጠቃሚና ዋና የሥልጣኔ መሪ መሆኑን ብዙ የተማሩ ሰዎች አይስቱትም ። ጃንሆይ አፄ ምኒልክም ላገራቸው ጥልቅ ሐሳቢ ስለ ነበሩ ከብዙ ዘመናት በፊት አእምሮ የሚባል የኢትዮጵያ መጀመሪያ ጋዜጣ አወጡ ። በዚሁም ጋዜጣ ብዙ የኢትዮጵያ ጥቅም እንደ ተገኘ ማንም አይስተውም ። ደግሞም በዚህ ላይ ብርሃንና ሰላምን ለማግኘት የሚናፍቁ ሰዎች መኖራቸውን ከብዙ በትቂቱ እገልጻለሁ ። ባገራችን ስለ ሀገራቸው ጥቅም ብዙ ሰዎች በብርሃንና ሰላም ጽፈው አንበናል ። ደግሞ ብዙ ሰዎች የሚጠቅም ነገር እየጻፉ እንዲታተምላቸው ያቀርባሉ ። ይሁን እንጂ ምንም እነኝህ ሰዎች እንዲታተምላቸው ቢልኩ ከላኪዎቹ መብዛትና ከጋዜጣው ማነስ የተነሳ ስፍራ እስኪይዝላቸው ብዙ ጊዜ ይቆያባቸዋል ። ሀለተኛ ለመጻፍ ያሰበ የመጀሪያው እንደቆየባቸው አይተዋልና ልባቸው ሳይሰነፍ አይቀርም ። ደግሞ ብርሃንና ሰላምን በሳምንት አንድ ጊዜ የሚያገኙ ሰዎች ፍቅሩ አድሮባቸዋልና ያ ሐሙስ መቼ በደረሰልን እያሉ እናቱ ገበያ እንደሄደችበት ልጅ በተስፋ ይጠባበቃሉ ። እነሆ ላገራቸው ጥቅም በትጋት የሚጽፉ ጋዜጣው ሰፊ ሁኖ ቢሆን ያለ መታገድ እንዴት ላገራቸው የሚጠቅም በጻፉ ነበር ። ይልቁንም ብርሃንና ሰላምን በየቀኑ ቢያገኙ እንዴት ደስ ባላቸው ነበር ። ክቡራን የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ሆይ የኢትዮጵያ ጓደኞችዋ የሚሆኑ አገሮች ልዩ ልዩ የሆኑ ብዙ ዓይነት ጋዜጣዎች በየቀኑ ያወጣሉ ። ግን እኛ ብርሃንና ሰላምን በሳምንት አንድ ቀን እናገኛለን እያልን በናፍቆት እንጠባበቃለን ። ይህንንም ማለቴ እነሱ በቀን ይህን ያህል ጋዜጣ ያወጣሉና እኛም እንደነሱ እናውጣ ማለቴ አይደለም ነገር ግን እንደተቻለን መጠን ጥቂት በጥቂት እናስፋ ማለቴ ነው እንጂ

እሁንም ይህ የብርሃን መሪ የሆነ ጋዜጣ በግርማዊት ንግሥታችንና በልዑል አልጋ ወራሻችን ኃይል ማዕዱ ይሰፋልናል ስንል በትልቅ ተስፋ እንጠባበቃለን ።

ዮሐንስ በ ።

የ፫፻፱ ገጽ ተከታይ ።

ስለ ትምህርት ማስታወሻ ።

እኔ ዛሬ ድሀ ተማሪ ነኝና ገንዘብ ያለው እንዲህ ያዋጣ እያልኩ መናገር ብቻ አይገባኝም ስል ባሉኝ ካብቶቼ(በመጻሕፍቶቼ) ቁጥር ፩ ፩ መ ባመት ባመቱ ላገሬ ጥቅም ተማሪው ላወጣ ወደድኩኝ ።(የሕዝቡስ አወጣጥ ላንድ ጊዜ ብቻ ነበር) ይኸውና አሁንም የሁለተኛውን ዓመት የዘጠና ሰባት መጽሐፍ የ፲፺ መሐለቅ ሂሳብ ፯ ብር ከ፩ መ ወንድሜ ቸሩ እንዲሰጥልኝ አድርጌአለሁና የሕዝብ ማሠልጠኛ ተማሪ ቤት ገንዘብ ያዥ እንዲቀበልልኝ እለምንዋሁ ።

የሚቻለኝ ቢሆን ስላገሬ ስለ ሕዝቧ ጥቅም እራሴን ወዳንድ ቦታ እግሬን ወዳንደኛው እጄን ወደላላው ልከፋፍላቸው እወድ ነበር አይቻለኝምና ነው እንጂ ።

ሠረቀ ብርሃን የሚባለው የሥራና የእውቀት ወዳጅ ወንድሞቼ ተማሪ ቤትም በኢትዮጵያ ትልልቅ ከተማዎች ብርሃኑን ሊነዛ ያስባል የሚል ወሬ ሌት ቀን ወዳገሩ አዘንብሎ የሚያዳምጠውን ጆሮየን መቶታልና ለዚህም ተማሪ ቤት ፩ ብር የዛሬ የድህነት እርዳታዬን አቶ በዛብህ እንዲሰጥልኝ አድርጌ አለሁ መቸም ብርሃን ላንድ ሰው ላንድ አገር ብቻ በተለየ አይወጣምና እንደዚሁ ሠረቀ ብርሃንም በመላ ኢትዮጵያ ሊያበራ ፋናውን አዲስ አበባ ላይ ተክሎአል ዘይት አንሰት የብርሃኑ ውጋገን እጭር እንዳይሆን ኢትዮጵያውያንን ሁሉ ያሳስበናልና ዝም አንበል ብርሃን ነውና የሚያስፈልገን በብርሃን ነገር ዝም ብንል ጨለማ እንዲውጠን አንርሳ ።

መንግሥታችን ባይወድ ባይፈልግ ነው እንጂ ለኢትዮጵያውያን ማሠልጠኛ ተማሪ ቤቶች መክፈቻና ለሥራው መጀመሪያ የሚበቃ ገንዘብ እላይ ባሉቱ አወጣጦች ቢዋጣ ለሁለቱም የተማሪ ቤቶች አመዳደብ በቅቶ እንዲተርፍ እኔ በውነት የተረዳሁ ነኝ ።

ክቡራን እንባቢዎች ሆይ መቸስ ምን ይደረጋል በማናቸውም ወገን መንግሥት ያገር ማሠልጠኛ ደንብ ለማውጣት ችላ ማለቱን እያሰባችሁ ሁላችሁ መርምሩት ጌቶቼ አባቶቼ ወንድሞቼ ።

እሳብ ።

ጠላት ሲወጣ በውድ ሆነ በግድ ሕዝቡ ሊዋጋ የተገባው የሚያስፈልገው እንደሆነ ሁላችን እናውቃለን አሁን በውስጣችን ያለው ጠላታችን ድንቁርና ነውና ከሱ ለመዋጋት በውድ የወጣው ወጣ በውድ ያልነውን ግን በግድ ማስወጣት የተገባው ነው መንግሥት ዝም ማለት አይገባውም ከድንቁርና የሚበልጥ ጠላት ለሰው እንደሌለው ይወቅ እንወቅ ።

ትንሹ ተማሪ መ ስ ወ።

በሚመጣው ሳምንት ይቀጠላል ።

ስለ መስቀል በዓል አከባበር።

መስከረም ፲፯ ቀን የመስቀል ዋዜማ ስለሆነ ደመራው ከቤተ መንግሥት አጠገብ በስተ ሰሜን በኩል ባለው ሜዳ ተተክለና በዚሁ ቀን ከስምንት ሰዓት ጀምሮ የከተማው ሰው ሰልፍ ለማየት ይጓዝ ጀመረ።በየመንገዱም እንደውሃ ይጐርፍ የነበረው ሕዝብ የብዛቱ ነገር ይደንቃል ።
ሠራዊቱም ከጧት ጀምሮ መሣሪያውንና ጌጡን አሰናድቶ የሰልፉ ጊዜ ይጠባበቅ ነበር ። ሕዝቡም ሁሉ የዘንድሮውን ሰልፍ ለማየት በጣም ይቸኩል ነበር እውነትም የዘንድሮ ሰልፍ ለማየት የሚያጓጓ ነው ።

ሰልፍ በሚደረግበት ቦታ ያማረ ድንኳን ተተክሎ አምሮ ተነጥፎ ወምበር ተደርድሮበት ነበር የሰልፉ ጊዜ እስኪደርስ የየአድባራቱ ካህናት መጥተው ይጠባበቁ ነበር የውጭ አገር ሰዎችም ሰልፉን ለማየት የተለየ ቦታ በድንኳን ውስጥ ተሰናድቶላቸው ነበርና እየመጡ ይገቡ ጀመር።ብፁዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስም በመጡ ጊዜ ሊቃውንቱና ካህናቱ እደመራው አጠገብ ተሰብስበው የልዑልን አመጣጥ ይጠባበቁ ነበር።ልዑል የሚመጡበትም ሰዓት በደረሰ ጊዜ ክቡር ሊጋባ ወዳጄ መጥተው ሰውን ሁሉ በሥርዓት እንዲቆም አደረጉና ዘጠኝ ሰዓት ተኩል ሲሆን ልዑል ተፈሪ መኰንን የሚያንጸበርቅ ነጭ ካባ ለብሰው በወርቅ ዕቃ የተንቈጠቈጡ በቅሎ ተቀምጠው ቀይ ጃንጥላ ተይዞላቸው በክቡራን መኳንንቶቻቸውና ሠራዊቶቻቸው ታጅበው መጡና አምሮ በተሰናዳው ቦታ ተቀመጡ።ከልዑልም በስተቀኝ በኩል ክቡር ራስ ካሣና የውጭ አገር ሚንስትሮችና መኳንንቶች ተቀመጡ ። በስተግራም በኩል ብፁዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስና መኳንንት ከሊቃውንቱ ጋራ ተቀመጡ። በዚያን ጊዜ ሰው ሁሉ ለማየት የተመቸ ቦታ እንዲይዝ ማዕበል እንደተነሳበት ባሕር እርስ በርሱ መጋፋቱና መጨናነቁ የሚያስደንቅ ሆነ ። ወዲያው ካህናቱና ሊቃውንቱ ሥርዓታቸውን አድርሰው ደመራውን ዞሩት ከዚህ በኋላ ልዑል በመኳንንት ታጅበው ደመራውን ዙረው በተመለሱ ጊዜ ሠራዊቱ በየደንቡና በየተራው እየገባ ሰልፉን እያሳየና ኢዮሃ እያለ ያልፍ ጀመር እንደ ጥንት ሥርዓት የለበሰ ወታደር ያማረ ሰልፉን አሳይቶ ካለፈ በኋላ የዘመኑን የሥልጣኔ ሰልፍ የተማረ ክት የለበሰ የልዑል ተፈሪ መኰንን ወታደር ሙዚቃ እያስነፋ በሥርዓት የሰልፍ አካሄድ የተማሩ ልጆች እየመሩት እግረኛውና ፈረሰኛው መትረየስ እንጋቹም በየተራው አለፈ ። ከብዛቱና ከሰልፉ ማማር የተነሣ ሰውን እጅግ አስገረመው በሜዳው ገብቶ ሰላምታ ሰጥቶ ሲያልፍ የሰውን ልብ እናወፀው ቀጥሎም የከተማው ዘበኛ ጥቁር ልብስ የለበሱ በሥርዓት የሰልፍ አካሄድ የተማሩ ልጆች እየመሩትና ሙዙቃ እየተነፋለት ፈረሰኛውና እግረኛው የሥልጣኔ ሰልፉን እያሳየ አለፈና ተደነቀ ።

ሠራዊቱ ሁሉ ሰልፉን አሣይቶ ከጨረሰ በኋላ የውጭ አገር ሰዎች ልዑልን እየተሰናበቱ ሔዱ ልዑልም ባማረ እጀብ ወደ ቤተ መንግሥቱ ተመለሱ።ስለ መስቀልም በዓል ለመኳንንቱና ለሠራዊቱ በቤተ መንግሥቱ ትልቅ የደስታ ግብር ተደርጎለት ዋለ ።

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥት ነገሥታት ዘውዲቱና ከልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ ።

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በከፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በከፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጀኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዌድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad



ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ አሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር ተኩል
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፪ ብር ተኩል
ዝባድ	፩ ወቄት	፫ብር ተኩል
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፲፬ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፰ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፭ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፰ ብር
አቡጀዲ መንጽር	፩ ኮረጃ	፻፵፫ ብር
:: ባለሰይጣን	::	፻፵፬ ብር ተኩል
:: ባለ ድመት ።		፻፵ ብር
:: ባለአህያ	።	፻፳፭ ብር
:: ባለሳቢ ግመል	።	፻፶ ብር
ባለ አንበሳ	::	፻፵ ብር
ሱካር	፩ ጁኒያ	፷፯ ብር
ቻይ	፩ ነጥር	፮ ብር

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፪ ፍራንክ
ባአንድ ብር	ሊሬ ፰ ከ፹፯ ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፲ ብር፴፫ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፭ ብር

COGNAC S.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



ዝኒት የእጅ ሰዓት ።

በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

“ሩግቢ” የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል“አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ”ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መጣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፡ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ኦቤርላንድ



ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሽ ኦቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባ ኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባተሪ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል «ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው

ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

ማስታወቂያ

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲	ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር	፱	ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
የዓለም ጅዖግራፊ በአማሪኛ ደኅና ጥራዝ ዋጋው	፯	ብር
» » » መናኛ ጥራዝ ዋጋው	፮	ብር
ደግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፮	ብር
ኅሐ ጽባሕ	፮	ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫	ብር
የቀድሞና የዘሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫	ብር
የሕይወት ታሪክ	፪	ብር ተኩል
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪	ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪	ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትርሜጓው	፪	ብር
ዋቁጥር ትምርት	፩	ብር
ያማሪኛ ሰዋስው	፩	ብር
ወዳጄ ልቤ	፩	ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን		አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ		አላድ
አጭር የዓለም ታሪክ		አላድ
ያማሪኛ ፊደል		ሩብ
አሳብና ምኞት		ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት		ሩብ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፪	መ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር	፪	መ
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ		ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶ ግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ		ሩብ

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ፤ የልብ ፤ የደረት ፤ የጉበት ፤ የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ፥ የቂጥኝና የቋቁቻ፥ የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል

እደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ሱቅ ነው ።



ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው ። በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤትነው።

ጉድየርግዙ

GOODYEAR

2·28·14

አራተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፵
4 me ANNÉE № 40

ሐሙስ መስከረም ፳፬ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም።
JEUDI 3 OCTOBRE 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Son Altesse Impériale Teferi Makonnen, Héritier du trône d' Ethiopie, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie
Un an 5 Thalers
Etranger
Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የብዙኀን ማርያም በዓል አከባበር

መስከረም ፳፩ቀን የብዙኀን ማርያምን በዓል ለማክበር ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን በክቡራን መኳንንትና ሠራዊት ታጅበው በጥዋት ወደእንጦጦ ቤተ ክርስቲያን ወጡ ወደ ቤተ ክርስቲያኑም በደረሱ ጊዜ መዘምራኑ መልክ ሲያመረግዱ ነበረና መልኩን ጨርሰው ስንክሣር ከተነበበ በኋላ ።

ዲያቆኑ መስቀል ይዞ ወጥቶ ምስባኩን በዜማ ሰበከ።ወንጌሉም ከተነበበ በኋላ ፫ሕፃናት ወደ ክህናቱ መካከል ገብተው አንገርጋሪውንና እስመ ለዓለሙን ሲቃኙ በድምፃቸው ማማር ሕዝቡ ሁሉ እጅግ አደነቀ በመካከልም መልአከ ገነት ወልደሐና መልአከ ፀሐይ ደስታ ቁመው ነበር ሊቀ ጠበብት መኰንን የሚባሉ እምመው ጠምጥመው ድርብ ለብሰው በተወረበ ቍጥር ክህናቱን እያነቃቁ ሲያስረግጡ ነፋስ የነካው ሸምበቆ ይመስሉ ነበር

ከዚህ በኋላ ዑደት ተደረገና ክህናቱ አስረግጠው በጨረሱ ጊዜ ብፁዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ አሳርገው ባርከው አሰናበቱትና ታቦቱ ሲገባ ሰባት ጊዜ መድፍ ተተኰሰ ።

ትንሽ ቈይተው ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ከቤተ ክርስቲያኑ ወጡና ባማረ ዓጀብ ሁነው ወደ ከተማ ለመመለስ ጕዞ ተጀመረ ግርማዊት ንግሥትንና ልዑልን በሥርዓት ተሰልፎ የሚያጅብ መኳንንትና ሠራዊት ወደታች ሲንቈረቈር ከጽዳቱና ከብዛቱ የተነሣ ተራራው በረድ የኛተበት መስሎ ይታይ ነበር በየመንገዱም ሰልፍ የተማረ ወታደር አልፎ አልፎ ተሰልፎ እየቈዩ ሰላምታ ይሰጥ ነበር ልክ ፮ሰዓት ሲሆን ከቤተ መንግሥቱ ደረሱ ።

የብዙኃንማርያም በዓል አከባበር እንዲህ ሆኖ በሰላምተፈጸመ

የኢትዮጵያ ዕድል ።

ልዑል ተፈሪ መኰንን ንጉሥ ተብለው የኢትዮጵያ መአል ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደ ራሴ እንዲሆኑ የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና የመኳንንቱ የሕዝቡም ፈቃድ ስለሆነ ልዑል ጌታችን ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢ. መአልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደ ራሴ ተብለው ዘውድ የሚደፉበትቀን መስከረም ፳፯ እንዲሆን ተቈርጧል ። የትልቁ የደስታችን በዓል ለማክበር የሚሆንም ብዙ ጌጥና በያይነቱ ሽልማት በከተማው ውስጥ ብዙ የመሰናዳት ሥራ ሲሠራ ሰንብቷል።ይህ የኢትዮጵያ ብርሃን የሆነ ንጉሥ በትልቅ ግርማ የሚታይበትንቀን ለማየት የማይጓጓና የማይቸኵል አይገኝም ።

ልዑልም እንዲነግሡ በመላ ኢትዮጵያ በተሰማ ጊዜ ብዙ ብልሆች ሰዎች ያማረ የደስታ ንግግርና ግጥም እየጻፉ ልከዋል። ከተጻፈልንም ቃል ትንሽ ከዚህ በታች አትመናል።

ኅሡ ሰላማ ለብሔር ።

እውነተኞች ኢትዮጵያውያን ሆይ በፈቃደ እግዚአብሔር አገርን ከነጻነት ሕዝብን ከሕይወት ስላስገኛችሁ ካሁን ዠምሮ እስከ ፍጻሜ ትውልድ ድረስ ምስጋናችሁ አያቋርጥም ። ሰላም የሰው ሕይወት ፀብ የሰው ጥፋት እንደ ሆነ በለባዊ ሰው ቀርቶ በደማዊ እንስሳ ሲታይ ይኖራል ። ሰውስ ታላቅ ቢሆን አእምሮ ባይኖረው እንደሚጠፋ እንስሳት ሆነ ማለት አልነበረምን ደግሞም በ፬ኛው ዓመት በ፴፰ቁ ፍቅረ ሀገር ያደረብዎ ክቡር ፊታውራሪ ዲሬሳ የጻፉትን ቃል በልማድ ማንበብ ብቻ አይደለም ማስተዋል እንጂ ሌላ አያሻም።ከዚህ ቀጥዬ ስለ ምጽፈው አዲስ ድርሰት በ፩ትልቅ ዛፍ ሥር ተቀምጠን ደስታችንን ስናካፍል የትልቁ ዛፍ ባለ ቤት አንዱ ወዳጄ ርእሰ ደብር ድንቄ ዘራጉኤል የደረሰውን ረቂቅ ተመልከት ብለው ስጡኝ እን

ፉ ተመለከትሁትም በኔ መስማት ብቻ እንዳይቀር ልገልጸው ፈቀድሁ ቃሉ እጅግ ያማረና የተከከለ ሁና ስለተሰማኝ ለብርሃንና ሰላም ወዳጆች ሁሉ ይድረሳቸው በማለት ጽፌዋለሁና ንባቡና ምስጢሩ የተባበረ መሆኑን ይመርምሩ ።

ንግሥት ዘውዲቱ እንዳማረብዎ ።
አያሌ ገስግሷል ይቀባ ራስዎ ።
ገና ሳይቀባ እንዲህ ያደገ ራስ ።
እነሆ ሲቀባ አድጎም አይመለስ ።
በከንቱ ይለፋል ካልጋዎ ላይ ቀስቃሽ ።
መቸ እንቀላፋና ልዑል አልጋ ወራሽ ።
ባልጋ የታመሙ ብዙ ሰዎች አሉ ።
መቼም በጎ አይሆኑ ጭራሽ ይደክማሉ ።
በፈቃድህ አይደል የወጣኸው በግድ ።
አንተን የሚል ማነው ደግሞ ካልጋ ውረድ ።
ብቻ እነደ ሰሎሞን እንዳባትህ ፍረድ። (ነገ ቀ ፫ ም ፳፰ቁ
የተባረከ ነው የመኰንን ዘር ።
ራስ ራስ ወልዶ እሸቱ ሲያምር ።
መኰንን ነው እንጂ ጠንካራ ገበሬ።
ዘሩ የሚበቃ ለሸዋ ለትግሬ ።
በማህለ ሥለሴ ባባቱ መንግሥት ።
እንግዳ መስሏቸው ሊሸኙ አሰቡት ።
ሸዋ ሊያጌጥ ነበር ልቡ ያሰበው ።
ዋጋው ቸገረ እንጂ የራስ ማሰሸው ።
እንዴት አማረብሽ ዛሬ ብትዳሪ ።
ተፈሪን የሚያህል ልክልሽ ፈጣሪ ።
የመጣበት ሸክም በተፈሪ ታዘ ።
መች የሚያልቅ ነበር ተግዘ ተግዘ ።
አቀለለው እንጂ መድኃኔ ዓለም አግዘ ።
ከከተማው ጥፋ ብለውህ ነበር ።
እንዲህ እንደ ፀሐይ ሞቀህ ልትኖር ።
እግርን ወደ ራስጌ ራስን ወደ ታች።
ማድረግ አይመችም አትድከሙ ሰዎች ።
በተፈሪ ሕመም ሲያዝን ነበር ሰው ።
እግዚአብሔር ይመስገን ላልጋው በጎ ነው ።
ጭምት ነው ተፈሪ የመኰንን ልጅ፡
እሱ ምን አወራ ግድ አውራ ኣሉት እንጅ።
የተፈሪን ሸማ ማንም አይለብሰው ።
ጥበቡ ረቂቅ ነው ሲጥል ላየው ሰው ።
ተፈሪ መኰንን ዋነተኛ ብርቱ ።
ያንን ሁሉ ባሕር ዋኝቶ የመውጣቱ ።
በቀናው ጐዳና አንተው አሻግረን ።
የየባሕሩ አዞ እንዳይጨርሰን ።
አበሻ በትርህ በርጥቡ ሳይደርቅ ።
ዘብቶ እንዳይሰበር በርታ ይታረቅ ።
ማር ይቅርብህ እንጂ መቸም አትጐዳ ።
ቀድሞ እጭ ያሉህ ሰዎች ከደረጉህ ከዳ ።
ሃይማኖት ነው እንጂ ማነው ጠበቃህ ።
በያደባባዩ የሚቆምልህ ።
ተፈጥመው ሄዱ ባለጋሮችህ ።
አሁን ምን ይሆናል በከንቱ ሐሜት ።
እንደ ራስ አያዩ መፍረድ ነው በውነት ። (፪ ሳሙ ፰ ም ፲፭
የጊዜውን መድረስ ተፈሪ መርምር ።
መቼም አትታወቅ ጥላ ስትዞር ። (ማር ፲፫ ም ፴፭ ቁ)
ያሸከሮችዎ ጌጥ አያሌ አማረኝ ።
ብር አፍሳሹ እጅዎ ለኔም ይሥራልኝ ።

ይህ ድካማቸው በከንቱ እንዳይቀር አስታውሳለሁ እግዚአብሔር ነግሠ ስብሐቲሁ ለብሰ።ለብሰ እግዚአብሔር ኃይሎ ወቀነተ። ወአጽንአ ለዓለም ኢትዮጵያ ከመ ኢታንቀልቅል።ድልው መንበርከ እግዚአ።እምትካት ወእስከ ለዓለም አንተ ከመ ክቡር ንጉሥ ፍትሐ ያፈቅር።አንተ አጽናእካ ለኢትዮጵያ በኃይልከ።ፍትሐ ወጽድቀ ለቤተ ያዕቆብ ገበርከ።እያልሁ ስጸልይ ባማርኛ ደግሞ እነድጽፍ አነቃቃኝ ምሳ ፳፱ም ፬ቁ ንጉሥ በፍርድ አገሩን ያጸናል ቀጥሎም ፲፬ቁ ለድሀ በውነት የሚፈርድ ንጉሥ ዙፋኑ ለዘለዓለም ይጸናል ኤርምያስ ፳፩ ም ፲፪ቁ እላንት የዳዊት ወገን እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ማልዳችሁ ፍርድ ፍረዱ የተበዘበዘውንም አድኑ ፩ ጢሞቴዎስ ፮ም ፯ቁ ወደ ዓለም አንዳች ይዘን አልገባንም ከዚም አንዳች ይዘን እንዳንወጣ ግልጽ ነው ስለዚህም መብልና ልብስን ካገኘን ይበቃናል እስከሚለው አድርሼ ለመተው በቃሁ። ኢትዮጵያዊ ።

መወድስ ።

መንግሥተ ዳዊት ዮሐንስ ቃለ ዓዋዲ ነቢየ ልዑል ይሰመይ ወአርከ መርዓዊ በግብር ።
እስመ ተፈነወ ያርሁ ኣናቅጸ ጥበብ ምሥጢር ።
ወይጸሕ ፍኖታ ለርኅቅት ጐንደር ።
በቃለ ኃይላሰ ወሥልጣና ወንጌለ መንግሥት ነዓ እንዘ ትብል ትትናገር ።
እንከሰ ንትመሐር ደቂቀ ዛቲ ሀገር ።
እስመ ቀሥምጥበበ ጋሬ ምስለ ማዕረርነ የሐብር ።
እመኒ ርኅብኩ አንሰ ኢይስእሎ ብሔር ።
እምጣነ ዘፀገበ ወኢፀገበ በረድኤተ ልዑል ዘየሐድር ።

ሁለተኛ ።

መንግሥተ ምኒልክ ሔዋን ወላዲተ መንታ ።
እታ ገበ ምኒልክ አዳም ትትፈጠር ወትትኔደስ ።
እስመ እምኔሃ ይወጽእ ኃይለ ሥላሴ ክርስቶስ ።
ይሥጥቅ መጽሐፈ ዕዳሃ ለሔዋን ተጽናስ ።
ወእጓለ ሳምን ዮሐንስ ።
እአሚሮ ሰገደ ወአንፈራጸ በከርሥ ።
ይትነበብሂ በሮማያ ወይተረጐም በፋርስ ።
ወንጌል ኃይለ ሥላሴ ዘዜነወ ማቴዎስ ።
ወእምድኅረዝ ይቤሉ ዘኢትዮጵያ አልባስ ።
አርትዕ ተሠራሕ ወንግሥ ።

ካሣ ተክሉ ማኀደረ ማርያም ።

ምቀኝነት ስለ ማራቅ።

የኢትዮጵያ ልጆች እርስ በራሳችን መቀናናትና በምቀኝነት ወንድሞቻችንን በተንኰል ለማጥፋት ስናደባ መዋላችን ከቶ እንዴት ያለ ጉድለት ቢኖርብን ይሆን ። ስናደባና እውነትን ትተን በሐሰት ወንድሞቻችንን በተንኰል ለማጥፋት በመዋላችን ለደግ ሥራ አስተዋይና ታጣቂ ለሆኑ ወንድሞቻችንስ እንዴት ይገርማቸውና ያሰቅቃቸው ይሆን ። ከቶ ምን ይረባናል ይጠቅመናል እስኪ እንመልከት አሁን በቅርቡ የሆነውን በማሱት ጉድጓድ የገቡ ስንት ናቸው ባጠሩት አጥር ተከበው የተቀመጡ ስንት ናቸው ባጠመዱትስ ወጥመድ የተያዙ ስንት ናቸው በእንደዚህ ያለ መንገድ የሄዱ ሁሉ አወዳደቁ ታላቅ እንደሆነ እያየነው በብዙ ጊዜ ያስፈራናል ይኸንን አለማስተዋልና በቶሎ አለ መተው እጅግ ድንቁርና ይሆናል ።

አሁንስ ለኛ የሚገባን ለምለም ሀገራችን ነፃነቷን ወደን በፍጥነት ለመፈለግ ትጉህ ብንሆን እንዲጠቅመን እንወቅ ብትጋት እንድናስብና ክቡራን ወንድሞቻችን በብርሃንና ሰላም እንደሚያስታውቁን ያለ ስንፍናና ባለመደከም ለሀገራችን ነፃነት እንዳስታወቁን ሁሉ ብንደክም የለምለም ሀገራችን መከበሯ የኛ የልጆቿ መፈሯ መሆኑ ጥርጥር የለውም ። ግን አስቀድሞ ምቀኝነትን በርትተን ካላጠፋን እውነትና ደግነት እውቀትና ትጋት ይገኛል ማለት የመናገሻን ጋራ ወደ የረር የየረርን ጋራ ወደ መናገሻ እንደ ማዛወር ይሆን ይመስለኛል ።

አሁን በከተማ ያሉ ብዙ እውቀት እያላቸው አስታዋሽ ለመንግሥት የሚያስታውቅላቸው አጥተው አውቀው እንዳላወቁ በመሆናቸው እየተመረሩና እየ ተበሳጩ የሚጉላሉ ብዙ ናቸው ።

ለነዚህ አስተዋሽ ፩እውነተኛ ደግ ሰው በተለየ ቦታ ተቀምጦ የሥራውን አጨባበጥና የትምሕርቱን ልክ እየመረመረ ለመንግሥትበእውነት በቀጥታ እያስታወቀ መንግሥትም አይቶ መርምሮ እንደ ሥራው ልክ ቢያዘው ለሀገራችን ነፃነት መሪ እንዲሆን ውልውል የለውም ስል ባነስተኛ እውቀቴ አስታውቃለሁ ። ነገር ግን በንግግሬ አለመተካከል ወንድሞቼ የብርሃንና ሰላም ወዳጆች በጐደለ ሞልተው የዘባውን አቃንተው ያነቡልኛል ስል ተስፋ አደርጋለሁ ።

ግዛው ደክር።

ስለ ከተማ ጽዳት ።

ባራተኛ ዓመት በቁጥር ፳፯ በ፪፻፲፩ ገጽ ብርሃንና ሰላም አቶደምሴ ወልደ ገብርኤል ምናልባት የመቃብር ቤት እንሠራለን የሚሉ ሰዎች ቢገኙ ከርሻ ምኒስቴር የተለየ ፈቃድ እንዲቀበሉ ማድረግ ነው ፈቃድ ከተቀበሉ በኋላም ባራቱ ማእዝን ባንድ ክሬ ሜትር ሁለት ብር እንዲከፍል የተወሰነ ሕግ መስጠት ነው ።

ሁለተኛም በየንዳንዱ ዓመት ውስጥ የሚሞቱት ሕዝቦች ቍጥራቸውና የሞቱበት ዕድሜያቸው ታውቆ በመዝገብ ይጻፋሉ ። ይህም ትልቅ ጥቅማችን ነው ብለው በብርሃንና ሰላም ስላስታወሱን የልቡን ሲነግሩት የኰረኰሩት ያህል ይስቃል እንደሚሉት ተረት ነውና የንግግራቸው ጣዕም ሕሊናዬን ስለ ቀሰቀሰው የሚከተለውን ያገዜታ ቃል በሚከተለው መስመር ላቶ ደምሴ ወልደ ገብርኤል አቅርቤላቸዋለሁ።እውነት ነው ይህ የመቃብር ቤት ደምብ በተተካከለ ሕግ ቁሞ በርሻ ምኒስቴር በኩል ጉርድ ወረቀት ተበጅቶለት ሟቹ ባንድ ክሬ ሜትር ሁለት ብር እየከፈለ ገቢው ገንዘብ በርሻ ምኒስቴር ሥራ ቤት ቢሰበሰብ ገንዘብ ብቻ አማይዶል ብዙ ጥቅም አለበት ግን ያዲስ አበባ ሕዝብ ብዙ ስለ ሆነ የመቃብሩ ቦታ በከተማው ውጭ በምሥራቅና በምዕራብ በሰሜን በደቡብ ባራቱ ማእዝን ላይ ማስበጀት በግድ የሚያስፈልገን ነው እንጂ ብዙ የተሣመረ ጥቅም እናገኝበታለን ።

እንደኛ ፡ ይህ የመቃብር ደምብ በትክክል ቁሞ በርሻ ምኒሲቴር በኩል እየተሠራ ገንዘቡ ከርሻ ምኒሲቴር የገባ እንደሆን መንግሥት ብዙ ገቢ ገንዘብ ያገኛል ።

ሁለተኛም ሁላችን እንደ ምናውቅ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሞተም ከቤተ ክርስቲያን ይቀበራል የተወለደም ከቤተ ክርስቲያን ይማራል ይልቁንም አጸድቃለሁ ባይ እመቃብር ቤት ላይ ሲተኛ ይኖራል በዚሁ በመቃብሩ ሽታ ሰበብም እኩሌቶቹ ይሞታሉ ግማሾቹ/ም ያብዳሉ ይህም ለኢትዮጵያ ትልቅ ጉዳት ሆኗ ስለ ዚህ የመቃብር ቤት ደምብ ቁሞ ከየቤተ ክርስቲያኑ ያለ አጥንት ተቈፍሮ ቢወጣና ሙታንና ሕያዋን በሚገባን ቦታ ተለይተን ብንቀመጥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሽታና ከበሽታ ድነን በመልካም ኑሮ እንኖር ነበረ ።

ሶስተኛም በየቤተ ክርስቲያኑ ያለ አስከሬን ሥጋው ሲበሰብስ ይልቁንም በክረምት ወራትየሬሳውመርዝ እየተንጠፈጠፈ ከጕድጓድ ወሀ ጋር እየተቀላቀለ ብዙ በሽታ የሚያመጣ ነው ። ስለ ዚህ ከሰገራ ይልቅ የመቃብር መርዝ እወሀ ጋር የሚከፋ ስለ ሆነ ያዲስ አበባ መቃብር ቤት ከከተማ ውጭ ማስበጀት በግድ የሚያስፈልግ ነው በዚሁ ሥራም ብዙ ገንዘብና ብዙ ጤንነት እናገኝበታለን ።

አራተኛ አቶ ደምሴ ወልደ ገብርኤል እንዳሉት በመቃብር ኪራይ ከሚገባ ገቢ ገንዘብ የመቃብር ዋጋ ለሌላቸው ድሆችከገቢው በወጭ መዝገብ ተጽፎ በመንግሥት ገንዘብ ቢቀበሩ ለመንግሥታችንና ለሕዝባችን ትልቅ የማዕርግ ክብረት ነው ።

ስድስተኛ ። የመቃብር ደምብ በትክክል ቁሞ የሞተው ሰው ሲቀበር ስሙ መልኩ አገሩ ያገሩ አውራጃ ዕድሜው የከፈለው ገንዘብ በጉርድ ወረቀት ተጽፎ ከመዝገብ መግባቱ አይቀርምና ባንድ ዓመት ውስጥ ስንት ሰው እንዲሞት ለማወቅ እንችላለን ። እንግዴህ የመቃብር ደንብ በርሻ ሚኒስቴር በኩል ቁሞ ባንድ ዓመት ውስጥ የሞተውን ሰውና የገባውን የመቃብር ኪራይ ለማወቅ ከፈለግን ደግሞ በማዘጋጃ ቤት በኩል ሥራውን አቁመን ባንድ ዓመት ውስጥ ስንት ሕፃናት እንደተወለዱ ለይተን ለማወቅ ያስፈልገናል ። ስለዚህ የኢትዮጵያ መንግሥት በማዘጋጃ ቤት ጉርድ ወረቀቱን አስበጅቶ ከሚወለዱቱ ሕፃናቱ ባንዳንድ ልጅ አምስት ብር መቀበል አለበት። ይኸውም ብዙ ገቢ ገንዘብ እምናገኝበትና የሕዝባችን ቁጥር የምናውቅበት ስለሆነ ለመንግሥታችን ብዙ ጥ

ቅም ይሆናል ። ሕዝቡም ሲወለድና ሲሞት ብንቆጥረው ነው እንጂ የሚወለደውን ትተን ሟቹን ብቻ ብንቆጥር ቆጥሮ የማይቀበል ሌባ ያሰኘናል ።

ሁለተኛም የኢትዮጵያ መንግሥት ባንዳንድ ሕፃን ልጅ አምስት ብር የሚቀበልበት ደንብ ሲደነግግ ሳለ ደግሞም ደሀ ሁነው ለተወለዱ ሕፃናት አካለ መጠን እስቲሆኑ ድረስ ከማዘጋጃ ቤት ገቢ ገንዘብ ወጭ እያደረገ ማሳደግና ማስተማር ግድ አለበት ይኸውም ሥራ በቶሎ የተደረገ እንደሆነ ዘይቤው የኢትዮጵያ ማሻሻል ነውና ማሰብና ማድረግ የሚያስፈልገን ነው። ደግሞም ባራተኛው ዓመት በቁጥር ፷፮ በ፲ኛው ዓምድ ፪፻፫ ገጽ ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ አቶ ገብረጻድቅ ጋሻው እስከ አሁን እንደምናውቀው ተስቦ የሚባል በሽታ አዲስ አበባና ሐረርን ያጠቃዋል ምክንያቱም ሕዝብ ስለበዛና ወሀው ንጹሕ ስላልሆነ ነው ። ደግሞም ዓይነ ምድር በጓሮ ዳርእየወደቀ ያያይነ ምድር ትል በዝናብ ጐርፍ እየገባ የኛ መጠጥ ስለሆነና በሥራት የንጽሕና ያይነምድር ሰገራ ስላልተበጀ ነው ። ሶስተኛም የምንጭ ወሀ ይልቁንም ወሀ ሲባል የበሽታ መፈጠሻ ነው ስለዚህ ባገራችን የተስቦ በሽታና ሌላ ዓይነት የሆድ በሽታ የሚነሣው ከነዚሁ ነው ብለው ለሰሚ ዦሮ ያስታውሳሉ ።ውነትም ይህ ነገር ከብዙ ቀን ዠምረን ብንመረምረው ያዲስ አበባ ሕዝብ የሚቀሰፍበት ምክንያት ካይነ ምድር ሰገራና ከመቃብር እየተንጠፈጠፉ እወሀ ጕድጓድ ውስጥ በሚገቡ በሁለቱ መርዞች ነው ። ማስረጃውም ሰው ከመሬት ሲቀበር ወሀዉም ከመሬት ሲወጣ መቃብርና የወሀ ጕድጓድም በተቀራረቡ ጊዜ መቀላቀል ካልሆነ ምንም ልዩነት የለባቸው ። ነገር ግን እረዳለሁ ብዬ አጥብቆ ጠያቂ አይጠፋምና ያዲስ አበባ ሕዝብ መቃብር ቤት ባንድ ከተማ ሲሆን የሰገራውንና የወሀውን ጕድጓድ ቅርብ ለቅርብ ሲሆን ደግሞ ያዲስ አበባ ሕዝብም ከወሀው ጕድጓድ ሲጠጣ የተስቦ በሽታ ከሕዝቡ ጋር እንዴት ብሎ እንደሚጋባ እየደጋገመ ይጠይቅ ይሆናል ።

እኔም ለጠያቂው እንደተቻለኝ ያህል በሚከተለው መስመር አስረዳዋለሁ ። አንደኛ ሁላችን እንደምናውቀው አራዳ ጊዮርጊስ ተሠርቶበት ያለ ከፍ ያለ ቦታ ስለሆነ በዚያ ውስጥ ተቀብሮ ያለ አስከሬን አጥንቱ በተቀር በሕዋሳቱ ውስጥ የነበረው ሁሉ እወሀው ጋር እየተቀላቀለ ባራዳ ከባቢ ያሉ የውሀ ጕድጓዶች ሁሉ ምንጫቸው ካራዳ ስለሆነ ደግሞም ወሀ የሚፈልቅበት ከፍ ካለ ቦታ ነውና ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን ዠምሮ እስከ መሐመድ አሊ ቤት ዙሪያ ያለ ሁሉ ካራዳ ጊዮርጊስ መቃብር ቤት የወረደ ወሀ ሕዝቡ እንደሚጠጣ ጠያቂው ቢያስተውል ለምሳሌ ይህ ብቻ ይበቃዋል ። ማለት በዮሐንስና በተክለ ሃይማኖት በመድኃኔ ዓለም በሥላሴ በገብረ መንፈስ ቅዱስ እንዲሁም በያድባራቱ ሁሉ ያለ የመቃብር ቤት በዙሪያው ባሉ የወሀ ጕድጓዶች አካሄዱና አኳሆኑ ልክ እንደ አራዳ ስለሆነ በዝርዝር ለመጻፍ ምንም አያስፈልገንም ጠያቂውም ከዚህ በላይ በጻፍነው አካሄድ ሐሳቡን መርምሮ በዝርዝር ለመረዳት ይችላል። ሁለተኛም በሰገራ ቤት ምክንያት ስለሚነሣ በሽታ ያዲስ አበባ ሕዝብ የወሀው ጕድጓድና የሰገራው ቤት ሲሞላ ወሀውንና ሰገራውን ከ፫ ሜትር የሚበልጥ አያራርቃቸውም ። ደግሞም ያዲስ አበባ ውሀ አነሰ ሲባል ከ፲፭ ሜትር በላይ አይገኝምና ባለ ቤቱ ውሀውን ለማግኘት ፲፭ ሜትር መማስ በግድ አለበት የሰገራው ቤት ደግሞ ረዘመ ሲባል ከ፫ ሜትር አይበልጥም (መልከም ሥራ) እንግዲህ አንባቢ አስተውል የወሀው ጕድጓድ ርቀቱ ፲፭ ሜትር ሲሆን የሰገራው ቤት ርቀቱ ፫ ሜትር ሲሆን ጊዜ ሰገራው ከወሀው በላይ እንደተቀመጠ ልብ በለው ማለት ውሀው ከሰገራው ፲፪ ሜትር ዝቅ ብሏልና የሰገራው ቤት መረቅ መረቁ ሁለ ጊዜ እውሀ ጕድጓድ ውስጥ እየተንጠፈጠፈ እንደሚገባ ለዚሁ ማንም አይስተውም ። ይልቁንም ዝናምጥሎ ፀሐይ ሲበረታ መሬቱ ከሁለት ይሰነጠቅና የዚያን ጊዜ ዓይነ ምድሩ እውሀው ጕድጓድ ውስጥ በትክክል ለማለፍ ይችላል ። ስለዚህ ለኔ እንደሚመስለኝ ያዲስ አበባ ወሀ እንኳንስ ሊጠጣና በሱ የታጠበ ልብስ እንኳ ሳይተኰስ መልበስ እንደማያስፈልግ መስሎ ይታየኛል ። ነገር ግን ሕመሙን ተናግሮ መድኃኒቱን መደበቅ ዋና ኃጢአት ነውና በዚሁ በቈሻሻ ወሀ ፈንታ ጥሩ ወሀ በቦምባ ከበረሀ እያስመጡ ምቹ ቦታ እያዩ ባራዳ ላይ እንዳለው እያስመሰሉ ማስበጀት ነው ። አሁን ግን ነገር ቢበዛ ባህያ አይጫንምና ረጅም ወራትና ሰፋፊ ዘመናት ለልዑል አልጋ ወራሻችን ይሁን በማለት መልከም ምኞቴን አቀርብላችኋለሁ ።

ተማኑ ረምሃ

ስለ አየር መለዋወጥ

ከዚህ ቀደም በክረምት ውስጥ ዝናብ ስለሆነና መሬቱ ስለጨቀዬ ተራራውም ዛፉም ሁሉ ጉምስለለበሰ አየሩ በጣም ይከብድ ነበረ ዛሬ ግን ክረምቱ እየቀለለና ዝናቡ እያባራ ስለ ሄደ የየዛፉ ሁሉ ልምላሜና በየተራራውም ያሉ ጽጌያት (አበቦች) ለዓይናችን እጅግ ያማሩ ሆነው ይታዩናል ይልቁንም ሽርሽር ለማድረግ አየሩ በጣም የቀለለና ደስ የሚያሰኝ ሁኖዋል በየባቡሩም መንገድ ለመዛወር ጭቃው ስለ ደረቀና አቧራም ስላልተነሣ እጅግ የተመቸ ሆኖዋል

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ፣ ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

ዓ ለ ም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ባ ር ባ ሬ ሶ

ኮ ኛ ክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ ።

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በካፑሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በካፑሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጀኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዊድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad



ዓለም ሱቅ ፲፪ዓይነት የተሰማ አሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ያዲስ አበባ ገባያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር ተኩል
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፱ ብር ተኩል
ዝባድ	፩ ወቄት	፫ ብር ተኩል
ሰም	፩ ፈረሲላ	፴ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፬ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፳ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፰ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፫ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፲፰ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፵፰ ብር
:: ባለሰይጣን	::	፻፵፬ ብር ተኩል
:: ባለ ድመት ።		፻፵ ብር
:: ባለአህያ	።	፻፳፫ ብር
:: ባለሳቢ ግመል	።	፻፶ ብር
ባለ አንበሳ	::	፻፵ ብር
ሱካር	፩ ጁኒያ	፳፪ ብር
ቻይ	፩ ነጥር	፩ ብር

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፱ ፍራንክ	
ባአንድ ብር	ሊሬ ፰ ከ፹፯ ሳንቲም	
አንድ ጊኒ	፲ ብር፴፫	ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፫ ብር	

COGNAC S.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሰ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።


ዝኒት የእጅ ሰዓት ።

በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቀቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል "አረቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

RUGBY

ደግሞ በኒዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፡ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ኦቤርላንድ



ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ ኦቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባ ኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኜቶና ባለባተሬ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማጎደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል «ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው

ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

ማስታወቂያ

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲	ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር	፱	ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
የዓለም ጂዮግራፊ በአማሪኛ ደኅና ጥራዝ ዋጋው	፮	ብር
» » » መናኛ ጥራዝ ዋጋው	፮	ብር
ጾግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፭	ብር
ኅሐ ጽባሕ	፭	ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫	ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫	ብር
የሕይወት ታሪክ	፪	ብር ተኩል
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪	ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪	ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትርሜንው	፪	ብር
የቁጥር ትምርት	፩	ብር
ያማሪኛ ሰዋስው	፩	ብር
ወዳጄ ልቤ	፩	ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን		አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ		አላድ
አጭር የዓለም ታሪክ		አላድ
ያማሪኛ ፊደል		ሩብ
አሳብና ምኞት		ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት		ሩብ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፪	መ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር	፪	መ
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ		ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶ ግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ		ሩብ

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ፤ የልብ ፤ የደረት ፤ የጉበት ፤ የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ፤ የቂጥኝና የቋቁቻ፤ የሚያዋልድ፤ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል

እደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ሱቅ ነው ።

ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው ። በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤትነው።

ጉድደርግዙ

GOODYEAR

2·28·14

አራተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፵፩
4 me ANNÉE № 41

ሐሙስ ጥቅምት ፩ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም ።
JEUDI 10 OCTOBRE 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voi regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ለፊስን በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres



ፎቶግራፍ አንሺ ሞዲ ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን በዙፋንዎ እንደተቀመጡ ።

ፎቶግራፍ አንሺ ሻህባዝ ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን በሥላሴ ቤተ
ክርስቲያን ክበረንዳ እንደ ተቀመጡ ።

የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ሥርዓተ ንግሥ ።

ባ፵ኛው ቍጥር ጋዜጣ እንዳመለከትነው መስከረም ፳፯ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ዘውድ ጭነው ታላቅ በዓል ሆኖ ዋለ ።

ሥርዓተ ንግሡም ከዚህ እንደሚከተለው ነው የከተማው መንገድና የከተማው ዋና ዋናው ቤት የመንግሥትም ጽሕፈት ቤቶች ሁሉ በሰንደቅ አላማና በልዩ ልዩም አበባ ሲጌጡ ሰንቁተው ነበር።ይልቁንም ከትልቁ ቤተ መንግሥት እስከ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ከሥላሴ ቤተ ክርስቲያንም እስከ ግርማዊ ንጉሥ ቤት ያለው መንገድ በግራና በቀኝ ያማረ ጌጥና አበባ የተገኑጉነበት መለል መለል ያለ እንጨት ተተክሎ በላዩ ሰንደቅ ዓማ ተሰቅሎ ሲውለበለብ የሚወረወር ኮከብ ይመስል ነበር። እየተመሳቀለውም ጐዳና ላይ ቁመቱ እጅግ የረዘመ ቅስት ተሠርቶ በልዩ ልዩ ጌጥ ተሸልሞ በጕልህ ፊደልም ዕድሜ ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የሚልና ሌላም ብዙ የምስጋና ቃል ተደርጎበት ነበር። ይህም ቅስት የሠራሩ ነገር የሚያስገርም ነው።

ከቤተ መንግሥቱም በስተ ምሥራቅ በኩል ባለው በር ሥርዓተ ንግሥ የሚደረግበት እጅግ ያጌጠና ሰፊ የሆነ ድንኳን ተተክሎ ነበር ። ከድንኳኑም ጀምሮ እስከ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን አዲስ መንገድ አቶሞቢል የሚያስኬድ ተሠርቶ በሰንደቅ ዓላማ አጊጦ ነበር ። በየመንገዱ ሁሉም በሌሊት እንደ ቀን ሆኖ የሚያበራ የኤሌትሪክ መብራት ስለ ተተከለ ሌሊቱ እንደ ቀን ሆኖ ላይታው ያምር ነበር ።

ከዘውዱም በዓል በፊት ቅብር በጅሮንድ ዘለቀ ዘውዱን ለብፁዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ አስረክበው እጨጌው ወደ መካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ወስደው እስከ መስከረም ፳፮

ቀን እየተቀደሰበትና እየተጸለየበት ቈይቶ ነበር ። መስከረም ፳፫ ቀን እሁድ ከሌሊቱ በ፲፩ ሰዓት እጨጌው ከሥራንዱ መምሕራን ጋራ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሔደው ዘውዱን በቀሳውስት እጅ አሲዘው በጅሮንዱ አጅበው አምጥተው ለዛውዱ በዓል በተዘጋጀው ስፍራ በመንበረ ዳዊቱ ፊት ባጌጠ ጠረጴዛ ላይ አስቀመጡት ። በዘውዱም አጠገብ በወርቅና ባልማዝ ያጌጠ ሰይፍ ተቀምጦ ነበር ።

ከሌሊቱም ፲፩ ሰዓት ጀምሮ እስከ ፲፪ ሰዓት የኢትዮጵያ መኳንንት ሁሉ የሰልፍ ልብስ እየለበሱ መጡ ። ወታደሩም የሰልፍ ልብስ እየለበሰ በታዘዘበት ስፍራ ተሰልፎ ቆመ ።

ከጧቱ በሩብ ሰዓት ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት መጥተው በመንበረ ዳዊቱ ላይ ተቀመጡ ።

ንጉሡም ልብሰ መንግሥትዎን ለብሰው በመንበረ ዳዊቱ በስተቀኝ በተዘረጋው ዙፋን ላይ ተቀመጡ።በዚሁ ሰዓት የውጪ አገር ሚኒስትሮች የመዓርግ ልብሳቸውን እየለበሱ መጥተው በንጉሡ ዙፋን በስተቀኝ በተዘጋጀላቸው ስፍራ ተቀመጡ። በዚያን ጊዜ ክቡር ፊታውራሪ ወልደ አማኑኤል የግርማዊ ንጉሥን የክብር ዘበኛ አሰልፈው መጥተው በግራና በቀኝ ቀጥ ብሎ እንዲቆም አደረጉት ።

ከዚህ በኋላ ካህናቱ ጸሎተ አኰቴት አድርሰው ወንጌል ተነበበና ሲፈጸም ብፁዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በፕሮግራሙ እንደተጻፈ ቃል ተናገሩ ።

ቀጥሎም እጨጌው ዘውዱን አንሥተው ባርከው ሰጡ ግርማዊት ንግሥትም ተቀብለው ለግርማዊ ንጉሥ ጫኑላቸው ።

ዘውዱንና ሰይፉንም ከሰጧቸው በኋላ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናገሩ ።

ልጄ ሆይ ።

እግዚአብሔር እኔን መርጦ በአባቴ በዳግማዊ ምኒልክ እልጋ ሲያስቀምጠኝ አንተም ለእኔ እጋዥና ረዳት እንድትሆነኝ እድርጎ መርጦኻልና ስለዚህ እነሆ ለክብርህ ዘውድ ሰጠሁህ ወደ ፊትም ለንጉሠ ነገሥቱ ዘውድ ወራሽ ለመሆን ያብቃህ በምትሠራውም ሥራ ሁሉ እግዚአብሔር ይርዳህ ብለው መረቋቸው።

ንጉሡም አሜን እንደ ቃልዎ ይሁንልኝ ብለው ምስጋና እቅርበው በዙፋንዎ ላይ ተቀመጡ ።

ከዚህ በኋላ መጋረጃው ተገለጠና በዚያ ስፍራ የተቀመጡ የኢትዮጵያ መኳንንትና የውጭ አገር ሚንስትሮች ሁሉ ንጉሡ ዘውድ እንደጫኑ አዩ ።

ከዚህ ቀጥሎ መኳንንቱ ከራሶች ጀምሮ ሁሉም ባንድነት በሊጋባ አቅራቢነት ቀርበው በየመዓርጋቸው ቆመው በዕድሜ የሚበልጡት ክቡር ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ ያገር ግዛት ሚንስትር ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናገሩ ። ግርማዊት ንግሥታችን ለሀገርዎ ለኢትዮጵያ ክብር ሲሉ ለልጅዎ ለንጉሥ ተፈሪ መኰንን ይህን ዘውድ ስለጫኑላቸው እግዚአብሔር ረጅም ዕድሜ ይስጥዎ ።የንግሥተ ነገሥታትንና የንጉሡን የፍቅር አንድነት እንደ አብርሃና እንደ አጽብሐ ያድርግላችሁ ዕድሜ ይስጣችሁ ንጉሡም ይኸን ዘውድዎን ይባርክልዎ ለንጉሠ ነገሥቱም መዓርግ ያብቃዎ ብለው ሲጨርሱ መኳንንቱ ሁሉ ባንድ ድምፅ እግዚአብሔር ይህን ቃል ይፈጽምልዎ ብለው እጅ ነሡ ።

በዚህም ጊዜ እጨጌው ከታላላቆች መምህራን ጋራ ቀርበው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናገሩ ።

ንጉሥ ሆይ

ይኸነን ዘውድዎን እግዚአብሔር ይባርክልዎ በተሰጠዎ ሥልጣን የሕዝብ ሁሉ መሪ ነዎትና የኢትዮጵያን ሕዝብ በሚገባ መንገድ መሪ ሆነው እንዲያሰማሩት እግዚአብሔር ይርዳዎ ከጥንት ከባቶቻችን የቆየውንም እውነተኛውን አርቶዶክሳዊ ሃይማኖት ለመጠበቅና ለመደገፍ ኃይልን ይስጥዎ የኢትዮጵያንም ቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና አኳኋን ሁሉ ለማጽናት ያብቃዎ ብለው ሲጨርሱ መምህራኑም ባንድ ድምፅ ሆነው እግዚአብሔር ይኸን ቃል ይፈጽምልዎ እያሉ እጅ ነሡ ።

ከዚህ በኋላ ብፁዕ እጨጌ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ጸሎት ጸለዩ ። ሁሉን የምትችል እግዚአብሔር አምላክ ሆይ የነገሥታት ንጉሥ የጌቶችም ጌታ የዓለምም ሁሉ ገዥ በመንበርህም ላይ ሆነህ በምድር ላይ ወደ እሚኖሩት ሁሉ የምትመለከት ከልባችን እንለምንኻለን በጸጋ ወደ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ወደንጉሥ ተፈሪ መንፈስ ቅዱስን እንድትመላባቸው ለፈቃድህ እንዲታዘዙ በመንገድኽም እንዲመላለሱ ሁል ጊዜ ሰማያዊ ስጦታህን መልተህ አልብሳቸው በደኅንነትም አኑራቸው ለብዙ ዘመንም ኃይልን ስጣቸው ጸላታቸውንም ያቸንፉ ዘንድ ከዚህች ሕይወትም በኋላ ወደ ዘለዓለም ደስታና ደኅንነት አድርሳቸው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አሜን ።

ከዚህ በኋላ ጸጋ ዘአብ የሚለውን እስከ መጨረሻው ደግመው ኑዛዜ አደረጉና ቡራኬውን በፈጸሙ ጊዜ ብዙ መድፍ ተተኰሰ ።

ከዚህ በኋላ ሊጋባ ወዳጄና ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደ መስቀል ከመኳንንቱ ጋራ ወደ አደባባይ ወጥተው ስለ ንጉሥነት የተጻፈውን የአዋጅ ቃል አናገሩ ። በዚያን ጊዜ ከትልቁ ቤተ መንግሥት ጀምሮ እስከ ንጉሡ ቤት ድረስ ጭብጨባው ቀለጠ ።

ይህም ሁሉ ከተፈጸመ በኋላ ግርማዊ ንጉሥ ተነሥተው ስለ ዘውዱ በዓል ክብር ቅዳሴ ለማስቀደስና ለእግዚአብሔር ምስጋና ለማቅረብ ዘውድዎን እንደጫኑ በተጌጠ ሠረገላ ሆነው ወደ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ሄዱ ። የኢትዮጵያ መኳንንትና የውጭ አገር ሚንስትሮችም በየመዓርጋቸው ሆነው በአቶሞቢል ተከተሉ ወደ ቤተ ክርስቲያንም እንደ ደረሱ ጸሎተ ቅዳሴው ተጀመረ ቅዳሴውም እስኪፈጸም ድረስ ግርማዊ ንጉሥ ዘውድዎን አውርደው ለማሳረፊያ በተሰናዳው ጠረጴዛ ላይ ቈዩ።

በ፫ ሰዓት ለዚሁ ለዘውዱ በዓል የየለጋሲዮኑ መኳንንትና ወይዛዝር እየመጡ በሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ለማረፊያ በተዘጋጀላቸው ስፍራ አርፈው ቆይተው ነበር ።

በሶስት ሰዓት ተኩል ንጉሡ ከቤተ ክርስቲያኑ ወጥተው በቤተ ክርስቲያኑ ደረጃ ላይ በተዘረጋው በወርቅ ወምበር ተቀመጡ ። በዚያ ጊዜ የየአድባራቱ አለቆችና መምህራን በካህናቱ ባልደረባ በመልአከ ገነት ወልደ ሐና አቅራቢነት እንደ መዓርጋቸው በተራ እየቀረቡ እጅ ነሡ ።

ከእነዚህም ቀጥሎ ከየሌጋሲዮኑ የተጠሩ መኳንንትና ወይዛዝሮች በየተራ እየቀረቡ እጅ ነሡ ።

ከዘውዱ ሥርዓትና ከቅዳሴውም በኋላ ፬ሰዓት ሲሆን ወደ ግርማዊ ንጉሥ ቤት ጉዞ ተጀመረ ። የሰልፉና የአቶሞቢሎች አከኼድ ተራ ከዚህ ቀጥሎ እንዳለው ነው ።

መጀመሪያ መለከተኞች እየነፉ አለፉ ። ቀጥሎ ከየደንቡ የተመረጡ የሻምበሎች ጎፈር ለብሰው በፈረስ እያናጠሩ አለፉ ። ቀጥሎ ነጋሪት መቺዎች በበቅሎ ሆነው እየጐሰሙ አለፉ ። ቀጥሎ እምቢልተኞችና ጥሩንባ ነፊዎች በየስልቱ እየነፉ አለፉ ። ቀጥሎ መትረየስ አንጋች ፈረሰኞች በሚያስደንቅ ሰልፍ አለፉ።ቀጥሎ የንጉሡ ፋንፋር ሙዚቃ እየመቱ አለፉ ። ቀጥሎ የክብር ዘበኞችና ሰማያዊ ከት የለበሱ ፈረሰኞች አለፉ።

ቀጥሎ የተፈሪ መኰንን ትምርት ቤት ተማሪዎች የተፈሪ መኰንንን ማርሽ እየመቱ አለፉ ።

ቀጥሎም ሰይፈ ጃግሬዎች ሰይፋቸውን እየመዘዙ ይዘው ከንጉሡ ሠረገላ ግራና ቀኝ ሆነው በግርማ እየታዩ አለፉ ።

ክቡር ሊጋባ ወዳጄና ክቡር አጋፋሪ ወልደ ማርያም ክቡር ቀኛዝማች አሥራተ ወ ገ ጐፈር ለብሰው ጠበንጃቸውን አንግተው ዘንግ ይዘው ሰልፉን ግራና ቀኝ እየጐበኙ ሲሄዱ ከደኑ የወጣ አንበሳ ይመስሉ ነበር ።

ከዚህ ቀጥሎ በ፮ ፈረሶች ከሚሳበው ከንጉሡ ሠረገላ ብስቱ ኋለኛው ክፍል ሊቀ መኳስ መንገሻ ውቤና ሊቀ መኳስ መኰንን ዋልቴ የማዓርግ ልብሳቸውን ለብሰው ቀኝና ግራ ተቀምጠው ይከተሉ ነበር ።

ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያ መኳንንትና የውጭ አገር የዲፕሎማቲክ ሰዎች የተጠሩ እንግዶችም በአቶሞቢል እየሆኑ እንደ መዓርጋቸው አለፉ ።

ባንድ አቶሞቢል ክቡር ሙሴ ዠራር የቤልጃግ መንግሥት ባለ ሙሉ ሥልጣን ሚኒስትርና የሚንስትሮች ተቀዳሚ ልውል ራስ ካሣ ።

በ፩ አቶሞቢል ክቡር ሙሴ ደረፌ የፈረንሳዊ መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትርና ክቡር ደጃዝማች ሙሉጌታ የጦር ሚኒስቴር ።

በ፩ አቶሞቢል ክቡር ምስተር ሳውታርድ የአሜሪካ ዩናይትድ ስቴት ሚኒስትርና ክቡር ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ ያገር ግዛት ሚኒስትር ።

በ፩ አቶሞቢል ክቡር ሙሴ ፕሩፈር የጀርመን መንግሥት ጉዳይ ፈጻሚና ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዋና ዲሬክተር ።

በ፩ አቶሞቢል ክቡር ሙሴ ኮራዶ ዞሊ የኤርትራ ገዥና ክቡር ከንቲባ ነሲቡ ።

በ፩ አቶሞቢል ክቡር ሙሴ ሻፖን ቤሳክ የጅቡቲ አገረ ገዥና ክቡር ጸሐፌ ትእዛዝ ወልደ መስቀል የጽሕፈትና የእርሻ ሚኒስትር ።

በ፩ አቶሞቢል ክቡር ምስተር ኪተርማስተር የእንግሊዝ ሶማሌ አገር ገዥና ክቡር ነጋድራስ መኰንን የንግድ ሚኒስትር ።

በ፩ አቶሞቢል ክቡር ምስተርዳንበር የእንግሊዝ መንግሥት ጉዳይ ፈጻሚና ክቡር በጅሮንድ ዘለቀ የገንዘብ ሚኒስትር ።

በ፩ አቶሞቢል ክቡር ሙሴ ፖርታ የኢጣልያ መንግሥት ጉዳይ ፈጻሚና ክቡር ጸሐፌ ትእዛዝ እፈ ወርቅ የፖስታና የስልክ ሚኒስትር ።

በ፩ አቶሞቢል ክቡር ሙሴ ዜርቦስ የግሪክ መንግሥት ቈንስል ዤኔራልና ክቡር አፈ ንጉሥ አረጋይ የፍርድ ሚኒስትር።

በ፩ አቶሞቢል ክቡር አፈ ንጉሥ ከተማና ክቡር ደጃዝማች ይገዙ ።

በ፩ አቶሞቢል ክቡር ሙሴ ሎብ የቱርክ መንግሥት የክብር ቆንስልና ክቡር አቶ ፋሲካ ።

በ፩ አቶሞቢል ክቡር ደጃዝማች ወንድ ይራድና ክቡር ደጃዝማች መታፈሪያ ክቡር ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ።

በ፩አቶሞቢል ክቡር ደጃዝማች አባሻውል ክቡር ሹም ተምቤን ገብረ መድኅን ክቡር ደጃዝማች ኃይሉ ከበደ ነበሩ ከአቶሞቢሎችም በኋላ የቀሩ የኢትዮጵያ መኳንንቶች የመዓርግ ልብሳቸውን እየለበሱና እያጌጡ በበቅሎ ተቀምጠው ይከተሉ ነበር።

ከመኳንንቱም በኋላ ብዙ ዘበኛ በዘበኞችም አጠገብ የውጭ አገር የዲፕሎማቲክ ሰዎች አስተርጓሚዎች ተከተሉ ።

አምስት ሰዓት ሲሆን ግርማዊ ንጉሥ ወደ ቤታቸው ደርሰው ከሠረገላ ወርደው በዙፋን ሲቀመጡ ሁሉም ባንድነት ፺፩ መድፍ ተተኰሰ በየመንገዱና በከተማውም ያለ ሰው ይህን በሰማ ጊዜ ጭብጨባውንና ዕልልታውን አቀለጠው።ከዚህ በኋላ የዲፕሎማቲክ ሰዎች ወደ ዙፋኑ እየቀረቡ ተሰናበቱ ።

የኢትዮጵያ መኳንንቶች ግን ለማረፊያ በተዘጋጀላቸው ስፍራ አርፈው ቈይተው በ፯ ሰዓት በተለየ ለመኳንንትና ለመላው ካህናቱ ሁሉ ሙሉ ግብር ተደረገ ።

ለግብሩም የሚሆን ሰፌ ዳስና ብዙ ድንኳን ተዘጋጅቶ በውስጡም ልዩ ልዩ ጌጥ ተደርጎበታል በውጭም ለመኰልኰያ የሚሆን ትልልቅ ድንኳን ተተክሎ ክቡር ሊጋባ ወዳጄና ክቡር አጋፋሪ ወልደ ማርያም ክቡር ፊታውራሪ ገብረ ማሪያም ክቡር ቀኛዝማች ከልክሌ በየማእርጉ እያደረጉ እንዳይጕላላ በየተራ በማስገባታቸው ተመስግነዋል። በግብሩም ጊዜ ሙዚቃ መቺዎች በአደራሹ መከከል ስፍራ ተዘጋጅቶላቸው በዚያ ላይ እየተመላለሱ ሙዚቃ ሲመቱ ሕዝቡን ሁሉ ደስ ያሰኙ ነበር በዚያውም ያለው ሕዝብ ሁሉ ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንንና ለልዕልት መነን ረጅም እድሜ ይስጥልን እያለ የደስታ ምርቃትና ጥልቅ ምኞቱን ያቀርብ ነበር ።

የግብሩም አኳኋን እንዲህ ነበር።እሁድ ለመኳንንትና ለካህናት፥ ሰኞ ለመኳንንትና ለወታደሩ ሁሉ ሙሉ ግብር ሆኖ ዋለ።

ሰኞ ማታ ለውጭ አገር ሚኒስትሮችና ለኢትዮጵያ ሚኒስትሮች ሆኖ አመሸ ።

መስከረም ፳፱ ማክሰኞ ለውጭ አገር ሚኒስትሮች ፥ በአዲስ አበባ ለሚኖሩ ለውጭ አገር ትልልቆች ሰዎችና ነጋዴዎች ሙሉ ግብር ሆኖ ዋለ ። በዚህም ቀን ምሳ የተጋበዙ የውጭ አገር ሰዎች ከዲፕሎማቲኮች ሰዎች ጋራ ፩ሺ ይሆናሉ ።

ደግሞ በጥቅምት ፩ ቀን ሐሙስ ስምንት መቶ አምሳ የሚሆኑ አረቦችና ሕንዶች ተጠርተው ምሳ ተጋብዘዋል ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ በነገሡበትም ቀን ከአውሮጳ ነገሥታት ልዩ ልዩ የሆነ የደስታ ቴሌግራም ለንጉሡ ደርሰውላቸዋል።

ቴሌግራም ያሳለፉላቸውም ነገሥታት እነዚህ ናቸው ።

ግርማዊ የእንግሊዝ ንጉሥ ጆርጅ ፭ኛ ።

ግርማዊ የኢጣሊያ ንጉሥ ቪክቶር አማኑኤል ፫ኛ ።

ግርማዊ የቤልጅክ ንጉሥ አልቤርት ።

ክቡር የፈረንሳዊ ፕሬዚዳንት ሙሴ ዱሜርግ ።

ክቡር የጀርመን ሬፑብሊክ ፕሬዚዳንት ማርሻል ሂንዳርቡርግ ።

ክቡር የአሜሪክ ዩናይትድ እስቴት ሬፑብሊክ ፕሬዚዳንት ካልቤን ኩሌጅ ።

ክቡር የግሪክ ሬፑብሊክ ፕሬዚዳንት ክንቶሪዮቲስ ።

ከነዚህም ከነገሥታቱና ከፕሬዚዳንቶቹ ቴሌግራሞች ሌላ ከመስከረም ፳፯ ቀን ጀምሮ እስከ ጥቅምት ፩ቀን ፳፬ የሚሆኑ ቴሌግራሞች ከአውሮጳና ከምድረ ግብጽ ለንጉሡ ደርሰውላቸዋል

የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ዘውድ በዓል ለት በመካነ ሥላሴ አለቃ በሻህ የተቀኙት ።

መወድስ ቅኔ ።

ተፈሪ ጽኑዕ አምደ ሃይማኖት ።
እመ አቀመከ ዮም በአንቀጸ መንግሥት አክሊል ።
ትጓትና ወፍቅር ጠበብተ ብዙኃ አምሳል ።
ኃይልከ መክን አንበሳ ተከብቶ ኢትክል ።
አምጣን ተሰዕለ በላዕሌከ ።
ገጸ አንበሳ መፍርሀ ወገጸ ግሩማን ኪሩቤል ።
ትነውምሂ እንዘ ትጉህ በጊዜ ማዕረር በቀል ።
ወዘየብሰ ተፋቅሮ በበዘመኑ ታሕመለምል ።
ባሕቱ ኢትርማአ በቀለ ርኅራኄ ወሣህል ።
ለእመ ተሐውር በጉባኤ እምኃይል ውስተ ኃይል ።

ማስታወቂያ

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲	ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር	፱	ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
የዓለም ጅዖግራፊ በአማሪኛ ደኅና ጥራዝ ዋጋው	፯	ብር
» » » መናኛ ጥራዝ ዋጋው	፭	ብር
ዶግሞ ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፭	ብር
ኅሐ ጽባሕ	፭	ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫	ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫	ብር
የሕይወት ታሪክ	፪	ብር ተኩል
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪	ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪	ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪	ብር
የቁጥር ትምርት	፩	ብር
ያማሪኛ ሰዋስው	፩	ብር
ወዳጄ ልቤ	፩	ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን		አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ		አላድ
አጭር የዓለም ታሪክ		አላድ
ያማሪኛ ፊደል		ሩብ
አሳብና ምኞት		ሩብ

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔራቶር ዶግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዊድን ፋብሪክ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO, Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad

ዓለም ሱቅ ፲፪ዓይነት የተሰማ አሸቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንፎር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

COGNAC S. & E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

RUGBY

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል "አረቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፣ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ኦቤርላንድ



ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ ኦቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባ ኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባተሪ ነው ካምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል «ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው

ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ ።

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በካፑሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በካፑሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።

ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስታክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንከራ ነው በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

በዓርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አራተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፵፪
4 me ANNÉE № 42

ሐሙስ ጥቅምት ፯ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም ።
JEUDI 17 OCTOBRE 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen , profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix , a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የሰውነት ምርመራ ።

ሶስት ልጆች የነበሩት ሊቅ ባንዲት አገር እናያለን ብግሩ የራስ ምታትና የልብ በሽታዎች ገብተው ብዙኅ ሕዝብ እየፈጁ አገሩን ባዶ ለማድረግ ሲጣጣሩ አይቶ እነዚህን በአካል ውስጥ ተሸፍነው ሕዝባችንን የሚጨርሱትን በሽታዎች ዓይነት አውቀን መድኀኒታቸውን መርምረን ፈልገን ማወቅ ያስፈልገናልና እነዚህን ደዌዎች ከማወቅ በፊት በሽታ ያልያዘውን ሰውነቱ ያልተበላሸውን ሰው ገድለንሁለንተናውን (ሰውነቱን) አጥብቀን ማወቅ ያስፈልጋል ። ደኅናውን አካላት ካወቅን በኋላ የታመመውን እየመረመርን ብናስተውል በሽተኛውን ህዋሳትና የደዌውን ዓይነት ለማወቅ እንችላለን ። በሽታው ከታወቀ መድኃኒቱ አይቶግርም ሲል ለሕዝቡ አመለከተ ። በሽታውን የሚደብቅ መድኃኒቱን ይደብቃል እንደሚባል ሁሉ አንተ ደኅናውን ሰው ገድለህ የሰውነቱን አኳሆን አጥንተህ በበሽታ የሚሞቱትን ደግሞ አርደህ የእመምተኛውን አካል ከደኅናው እያስተያየህ ገና በሽታውን ለይተህ አውቀህና መድኃኒቱን ፈልገህ አግኝተህ ብዙኅ ሕዝብ ከሞት ታድናለህ ብለን እንኳን ደኅናውን ሰው ልንገድልልህና ታሞ የሚሞተውን እንኳ እመሙን መርምረህ ለይተህ ለማወቅ ልታራርደው አንፈቅድም ሁላችን በበሽታው እንለቅና የከበቡን አራዊቶች እህላችንን ይመድምዱ ከብታችንን ይንዱ እንጂ አንተ እንደምትለው አድርገን ለመዳን አንፈቅድም ሲሉ ማፌዣያና መሳቂያ መቀለጃ አድርገው አባረሩት ።

ሊቁም በሽታዎቹ እንደጠኑና አገሩ ባዶዋን እንድትቀር እያሰበ እያዘነ እያለቀሰ በንዴት ተንገላቶ እቤቱ ሲገባ እነዚያ በአውቀት ያሳደጋቸው ልጆቹ አይተው አባታችንን ምን ነካው ሲሉ በእሩጫ ከመኝታ ቤቱ ገብተው ምን እንዳገኘው ጠየቁት እሱም ከሥር ጀምሮ እስከ ጫፉ ሊነግራቸው ጀምሮ በነዚህ በሽታዎች ጉዳት የሚያልቀውን ጅግና አኳሆን እስበ እያለቀሰ ሲነግራቸው ሳለ ገና ነገሩን ሳይጨርስ አባታችን ሆይ እንዴት እኛ እያለን ሕዝባችን በበሽታ አልቆ አገራችን ላራዊት ከብታችን ለስለት ወርቃችን ለጉዳት ይሄዳል?። እኔን ገድለህ የሰውን አከላት አኳሆን አጥናብኝና ያገሬን ሕዝብ ከበሽታ ለማዳን አድርግ ሲል በደስታ ላገሩና ለብዙኅ ሕዝብ ሲል በባቱ ፊት ወድቆ ትልቅ ሞት ተቀበለ ።

ሁለተኛው እራስ እመም ከገባበት ጉረቤት ሂጄ በሽታውን አምጥቼ ልሙትና የኔን እራስ ከደኅናው ካብዬ እራስ ጋር እያስተያየህ በሽታውን መርምረህ አውቀህ ላገር የሚረዱትን ብዙ ወታደሮች ለማዳን በሽታውንና መድኃኒቱን ለማወቅ ትችላለህ ሲል በደስታ እንደፌቆ እየዘለለ ታሞ ለመሞት ሲል በሽታውን ለማምጣት ሄደ ።

ሶስተኛው ግን ገና ያልተማረ ትንሽ ልጅ ነበርና ያገር ጥቅምና ጉዳት በሕዝቧ ጤንነትና መብዛት መሆኑን ስላልተማረ አያውቅምና እንዲያው ፈዞ አባቱ ፊት እኩል ሰዓት እንደቆመ ቆየና?። አባትዬ እረ ስለ ምንድነው አንተስ ታለቅስየነበረው? ። ጋሼና አብዬስ መሞትን የመረጡት ። እያለ ይጠይቀው ገባ ። አባትዬውም ንዴቱ አልፎለት በርዶ ነበርና ልጁን እጉኑ አስቀምጦ እነዚያን የፋፉ ጉንጮቹን እየሳመ ጀምሮ የነበረውን ነገር እስከ መጨረሻው በጥሙና ሲያጫውተው ሳለ ያገር ፍቅር በትንሹ ማሞም ልብ ገብቶ ሲያንቀጠቅጠው ሲያንዘፈዝፈው ሲያርበተብተው ጊዜ አባቱ በመጨረሻው የሚያዘውን ሳይሰማ አባትዬ ልቤ ተቃጠለ ሁለንተናዬ ተወረረ ። ብዙ የሚያውቁት ወንድሞቼ ሕዝቡን ለማዳን አገራችንን ለማግኘት ጠላታችንን ለማድበን፤ ከብቶቻችንን ለማርባት ፤ ወርቃችንን በሰንዱቃችን ለማግባት ፤ በአውቀታቸው በልጠውኝ በትልቅነታ

ቸው ቀድ መሙኝ ለሕዝብ ፍቅር ለገር ጥቅም ወደሚባለው መልከም ሞት ሄዱ ። እረ እኔ በምን ነገር ሙቼ ሕዝቡን እረዳለሁ ?። አገሬን እጠቅማለሁ እያለ ሲጨነቅና ሲያለቅስ አይቶ የልብ በሽታ የገደለውን ሰው መርምሬ በሽታውን አውቄ መድኃኒቱን መፈለግ ያስፈልገኝ ነበር ብቻዬን እንዳልቀርብህ ነው እንጂ ቢለው ምነው አባትዬ በአገራችን አረማዊ ከገባ ወዲህ የልብ በሽታ በግራ በቀኝ እስከ ዛሬ የፈጀው ሕዝብ ልክ እንደሌለው ስታጫውተኝ አልነበረምን እኛ ልባችን ደኅናና አንድ መሆን ያስፈልገን ነበር ስትል አልነበረምን ከዚህ ይበልጥ አገራችንን የሚጐዳ ዘወትር ልክ የሌላቸውን ወንድማማች እርስ በርሳቸው የሚያስተላልቅ አለሱ የለም ስትል አልነበረምን ። እባክህ ይኸ በሽታ ወደ ጠናበት ቦታ ውሰደኝና አምጥቼ ሳትጸየፍ የልጅህን ልብ ልትመረምር ትችላለህ ሲል ባንገቱ ላይ ተጠምጥሞ እያለቀሰ ያንን የሚያህል ሕዝብ ባገርህ ሲቀር እንዴት ብቻየን እቀራለሁ ትላለህ ቢለው እጅግ ተደንቆ በደስታ ግንባሩ ሲያበራ ቢያየው ደስታ ያረከቸውን ከንፈሮቹንና ፍስሐ ያበራቸውን ግንባር ጉንጮቹን ለሞ የልብ በሽታ አምጥቶ ሊሞት ወዳ መለከተው ስፍራ በረረ ።

ሊቁ አባትም የሰውነት ያካልን አኳሆን (አከናወን) አጠናና ሁለቱ ልጆቹ ባመጡት እመም ሞተው ደዌው የሚሰፍርበትን ሕዋሳት አይቶ የበሽታውን ልክና ዓይነት ጠንቅቆ መድኃኒቱን ለይቶ አውቆ ያገሩ ሰዎች ልጆቹን የልጅ የብልህ ደንቆሮ ሊፈጅን ነው እንጂ ምን ሊጠቅመን ነው እያሉ ሲቀልዱ ሲያፌዙበት ያድን ይፈውሳቸው ከጀመረ ብዙኀ ዘመናት ሆኖታል ።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ። መ ወ ሥ ።

ስለ ኢትዮጵያ ደስታ

፲፰፻፹፫ ዓመት ታሕሣሥ ፳፬ ቀን እሑስ ለት ታላቁ ዳግማዊ ምኒልክ የሥላሴ ቤተ ክርስቲያን የተሠራበትን ቈረቈሩ አቡነ ጴጥሮስ ቦታውን ባረኩ እሑስ ቦታው ተባርኮ ቅዳሚት ማታ ታቦቱ ገባ እሁድ ለቅዳሴው ዘውድ አጣኙ አባ ወልደ አማኑኤልና መምሬ ወልደ ማርያም ቀደሱ ለካህናት አራት እቴጌ ጣይቱ ላኩ ። ይህም ታላቁ ቦታ ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የተመረጠ ዕድል ሁኖ የዘውድ ገናና በዓል ዕለት ሁኖ ሲከበር እንዲኖር ሆነ ።

ኢትዮጵያ ስለ ወገኖቿ የደስታ ዝማሬ ታፈልቃለች ።

ስለ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ። ኢትዮጵያ ታላቅ ሆይ ከ፩ሺ፰፻፱ ዓመት በፊትም በኋላም ለነበሩ ወገኖቿ ለናግራንና ለካረሬ ለሉክስሮና ለበርባራ ለቀዛና ለሚድያን ለጀበል ሐበሻና ለውጋንዳ ለሙሺና ለባንዛ ተስፋችሁ ተፈጸመ ደስታችሁ ተስፋፋ የራቀው ቀረበ በጆሮ እንደ ሰማችሁ ባይናችሁም እዩት እነሆ ብርቱው ኃይለኛው ፈጣኑ ረዳቱ ግርማዊ ንጉሥ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ። ደሴቶችም ወንዞችም ተንቀሳቃሾችም በጣም ደስ ይበላችሁ፤ ትክክል ጠባቂ ወንድም ወጣላችሁ ታሪክ ተመልከቱ በጣም በርትታችሁ የተበተኑትን ሰብሳቢ እልክለሁ ሲል ታገኛላችሁ ። ኢትዮጵያ ትቁም ። ኢትዮጵያ ትፅና ። ኢትዮጵያ ትስፋ ። በመከከላችሁ። ሕያው ሆኖ ነግሡዋል ተፈሪ ልጃችሁ ። ደስታትን ይሁን ዘር እስከ ዘራችሁ ተፈሪ ነገሠ ለታላቅ ጥቅማችሁ ። ታሪካችን ቀስቅሱ ። በየቃሌታችሁ ። የፍቅር ጐተራ ሥሩ በርትታችሁ ። ሰራቂ ሳይመጣ በጣሙ ተግታችሁ ። ነጣቂ እንዳያነጥቅም እረኛ አለላችሁ ። የኢትዮጵያ አርበኞች የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማዎች ። ደስ ይበለን በደማችሁ የተዋጀች ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ። ልጅዋም ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ሕያው ይሁንልን ። ኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማዋ እጥንታዊ መከነዋ በደስታ እሕዝብዋ ጋር በመሸሻል ለመኖር አስቀድሞ የሚያውቃትን ፈጣሪዋን እጇዋን ዘርግታ ዓይኖቿን ገልጣ አዕይንትየሰ ዘልፈ ኀበ እግዚአብሔር ንዑ ንፈሣሕ በእግዚአብሔር እያለች ከአባቷ ከዳዊት ያገኘችውን ወራሹዋን ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንንን ሕያው አድርግልን ረጅም የደስታ ዘመን ስጥልኝ ። ሕዝቤንና ሠራዊቴን አስፋፋልኝ ወንዞችና ዛፎችን ሕፃናትና ሽማግሌዎችን አርበኞችና ኃይሎችን ጠብቅልኝ ሕያውነት ከኔና ከልጆቼ አትወስንብኝ ብላ ኢትዮጵያ ጸሎትዋን ለአምላክዋ አቀረበች ።

ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ሕያው ይሁኑ ።
ኢትዮጵያ ትለምልም ።
ኢትዮጵያ ትስፋ ።
ኢትዮጵያ ታፍራ አሜን ። ሚካኤል ካሣ ።

በደግነት አሸናፊ በእውቀት ድል አድራጊ ።

ልጅ ተፈሪ በትምህርት ቤት ሳሉ በእውቀትዎና በትዕግሥትዎ ይደነቁ ነበር ደጃዝማች ተብለው የሲዳሞ ገዢ ሆኑ ። ከዚህም በኋላ በደጃዝማችነትዎ ያባትዎን አገር አረርጌን ሲገዙ በ፲፱፻፱ ዓመተ ምሕረት በመስከረም ፲፯ ቀን አልጋ ወራሽ ሆኑ።

ደጃዝማች ተፈሪ የሲዳሞ ገዥ ።
ደጃዝማች ተፈሪ የሐረር ገዥ ።
ራስ ተፈሪ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ
ውለታዎ ያመስግንዎ

ከፍርድ ምኒስቴር ጋራ ሆነው የሌባሻይን ማታለልና የሰውን አካላት ከመቍረጥ አድነው ለባሮችም ነጻነትን ሰጡ ።

ከገር ምኒስቴር ጋራ ሆነው አገር አደላዳይና ቀላድ አስጣይ ወሰን ጠባቂ ሕዝብ አስተዳዳሪ ነዎ ።

ከትምህርት ምኒስቴር ጋራ ሆነው የተማሪ ቤቶችን አሠርተው ብዙ ልጆች ያስተምራሉ ።

ከጽሕፈት ምኒስቴር ጋራ ጸሐፊ ሆነው ብዙ መጻሕፍት አጻፉ ብዙ ዓይነት መጻሕፍቶች አሳትመው እውቀትን ይዘራሉ።

ከርሻ ምኒስቴር ጋራ ገበሬ ሆነው ከውሮፓ የከብትና የአህል ያታክልት ዓይነቶች እያስመጡ እንስሶችን እያራቡ ገበሬዎችን ይረዳሉ ።

ከሥራ ምኒስቴር ጋራ ሠራተኛ ሆነው መንገዶችና ድልድዮች ቤቶችና ቤተ ክርስቲያኖች አሠርተዋል ።

ከንግድ ምኒስቴር ጋራ ሆነው ሕዝብዎ በገንዘብ እንዲከብር ለመንግሥትዎም ጥቅም ቀረጥ እንዲበዛ እያሰቡ አገርዎን አበለጠጉ ።

ከገንዘብ ምኒስቴር ጋራ ሰጭና ተቀባይ ነዎ ።

ከስልክ ምኒስቴር ጋራ ሆነው በብዙ አገሮች ላይ ስልክ አዘርግተው የፖስታ ቤቶችን አቆሙ ።

ከውጭ ጉዳይ ምንስቴር ጋራ ሆነው ከውጭ ነገሥታት ጋራ በጣም ተፋቅረው እንግዶችን በደስታ ተቀባይ ነዎ

አልጋ ወራሽ ተፈሪ ከዘውድ የደረሱበት በትውፊ ድምና በመመረጥዎ ብቻ አይደለም በማገልገልዎም የሚገባዎ ነው እንጂ የዓለም ነገሥታት እውቀትዎን ተመልክተው አመሰገንዎ በደለኛ ሆኖ ክፉ ሥራ ሠርቶ ቢገኝ በኀዘን ቅጣት ፍርድ እንጂ በጭከና ፍርድ አይቀጡትም

አልጋ ወራሽ ከሆኑ ወዲህ ፩ነገር ሳይጋጭብዎ የተቈጣጠረው እንዳይበጣጠስ በብልሃትና በጥንቃቄ እየፈቱ እስከዚህ ደረሱ

በ፲፱፻፳፩ዓመተ ምሕረት በመስከረም ፳፯ቀን እናትዎ ኢትዮጵያ ጕረቤቶችዎን ጠርታ ያንድነትዎን ምልክት አዲስ አበባ አሳየች

ዓለሙ አ

ሥላሴ ።

ይትባረክ እግዚአብሔር አምላክ አበዊነ ።
ስቡሕኒ ውእቱ ወልዑልኒ ውእቱ ለዓለም ።
እግዚእ ወመሲሐ ።
ኃይለሥላሴ ዘተሰመይከ ።
በዘወልደ ንጉሥ አብ ወበወልደ ንግሥት እም ።
እስመ ኮንከ ብሑተ ልደት አሚሃ ወዮም ።
ወድኅረ ተሳተፉ ሕዝብ በነሚአ ሥጋ ወደም ።
ወበለቢስ ኃይል እምአርያም ።
ኢትዮጵያ ትብለከ በቃለ ሰላም ።
አሌዕለከ ንጉሥየ ወአምላኪየ ወእባርክ ለስምከ ለዓለም ።
ወዓለመ ዓለም ።

አለቃ ዳኜ ።

መወድስ ።

መክሊተ ጌራ ወርቅ ጽኑይ እለ ተውህበን ።
መጻሕፍተ ምሥጢር ኵሎን ያፈድፍዳ በፍሥሓ ።
ኃይለ ሥላሴ ንጉሥ እመ ይትዓሰብ ረባሐ ።
እንዘ መጻሕፍተ የዓቅብ ።
ወበዓቂቦቱ ይትዓሠይ ብዙኀ ።
እምጣነ መጻሕፍት በረባሐን መክሊተ ጌራ ወርቅ ንዐ ስ።
ለአክሊለ ስብሐት አብጽሖ ።
ዳዊትሰ ዘጸሐፈ እንዘ ይጸንሕ ጸኒሖ ።
ይሴፎ ተኀትምተ ለአክሊለ መንግሥት በጊዜሃ ።
እስመ ጌራ ወርቅ ኢነሥአ እምእደ ሳኦል አሚሃ ።
ሶበ ተበቀሎ ለጎልያድ ቅድሜሁ ዘተመክሖ ።

አለቃ መርሻ ዘውእቱ መርስዔ ኀዘን።

የአገር ውሥጥ ወሬ ።

በመስከረም ፳፯ ቀን ንጉሥ ተፈሪ መኰንን በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ ፈቃድ ለኢትዮጵያ በለሙሉ ሥልጣን እንደራሴና የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተብለው ስለ ነገሡ በሐረር ከተማ ታላቅ የደስታ ክብር ተደርጎ ነበረ ። ክቡር ደጃዝማች እምሩም ስለ ደስታቸው ብዛት ሸዋ በር የተባለውን ሜዳ አስደልድለው በዚያ ከፍ ባለ ቦታ ድንኳን ተተክሎ በያይነቱ ምንጣፍ ተነጥፎ የውጭ አገር መኳንንቶችም በተሰናዳላቸው ቦታ ተቀምጠው ሰልፉን ይመለከቱ ነበረ ። መኳንንቶችም ሁሉ የጦር ልብሳቸውን እየለበሱ በሜዳው ዙሪያ ሰልፉ መልክም ሁኖ ይታይ ነበረ ። በሐረር ያሉም ካህናት የክህነት ልብስ እየለበሱ በተሰናዳላቸው ቦታ ተቀመጡ። ከነዚያውም የሥላሴ ካህናቶች የክህነት ልብስ ለብሰው በመልክም ተሰልፈው በየማዕረጋቸው ሕፃን ሕፃናቱ ተፈት ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ቡሩክ አንተ ንጉሥ እስራኤል እያሉ በከበሮ ያመሰግኑ ነበረ ከዚያ ወዲያ ነጋሪት እየተጐሰመ አዋጅ ይነገር ጀመር ። ስለ ደስታውም ፻፩ ጊዜ መድፍ ተተኰሰ።ቀጥሎ የጊዮርጊስ ካህናቶች ምስባክ ከዳዊት መዝሙር ፸፩ ከቍጥር ፩ እግዚኦ ኵነኔከ ሀበ ለንጉሥ ወጽድቀከኒ ለወልደ ንጉሥ ከዚያ ወዲያ ከሉቃስ ወንጌል ፩ ምዕራፍ ቍጥር ፳፮እስከ ፴፫ ቍጥር ድረስ አንብበው ሰበኩላቸው።ይህም ከተፈጸመ በኋላ መምሬ ደጀን የምርቃት ቃል ተናግረው አሳረጉላቸው። ከዚያ ወዲያ የፈረንሳዊ ቋንቋ ተማሪዎች በመዝሙር አመስግነው ደስ ስላሰኙ ተጨበጨበላቸው ።

ሁለተኛ የእንግሊዝ ቋንቋ ተማሪዎች በመልክም ተሰልፈው ሰንደቅ ዓላማ ይዘው የሚከተለውን መዝሙር ዘመሩ ሕዝቦች ሁሉ ደስ ይሰኙ።አምላክን ይወድሱ የቆማችሁ በኪዳኑ በአንድነት ቅረቡ ። ቅረቡ በእልልታ ። ዘምሩ ለቸር ጌታ ። ይኸንም ከፈጸሙ በኋላ ከዳር እስከ ዳር ጭብጨባው ቀለጠ።ደግሞ የመንግሥት ተማሪዎች ባጭር ቃል አመስግነው ሕዝቡንና መኳንንቱን ደስ አሰኙት።ከዚያውም የነበሩ የውጭ አገር መኳንንቶች እጅግ አመሰገኑ ጭብጨባውም በብዙ ደምቆ ነበረ ። ይኸም ከተፈጸመ በኋላ የመኳንንቶች ሰልፍ ሆነ ሕዝቡም በየአለቃው ሆ እያለ በድንኳኑ በር ይሔድ ነበረ ይልቁንም በራሱ ላይ አንፋሮ ያሠረው ወታደር በቀረርቶ እየሸለለ ጕራዴውን መዞ እየፎከረ ይሔድ ነበር።ሰልፉም ከተፈጸመ በኋላ ክቡር ደጃዝማች እምሩ ወደ ታላቁ ቤተ መንግሥት ነጋሪትና እንቢልታው ሲቀልጥ በመልካም ዓጀብ ታጅበው ተመለሱ ከተማውም ሁሉ በመልካም አበባና ቅስት አጊጦ ነበረ። የጉሙሩክ አለቃ አቶ እሸቴ መልካም ቅስት በከፈይና በልዩ ልዩ አበባ ያጌጠ ሠርተው ነበር የምስጋናም ጽሑፍ በላዩ ተጽፎ ነበረ እንዲህ ሲል ሐረር የሺ እመቤት በጣም ደስ ይበልሽ ። በምሕረት አደገ የተቀባው ልጅሽ ። ሐረር ቤተ ልሔም ከሁሉም ከበሬ ትንቢትሽ ደረሰ በንጉሥ ተፈሪ።ሚክያስ ም ፭ ቁ ፪ በአደራሹም በር ላይ በመልካም የተሠራ ቅስት ነበረ በላዩም፱ ወርቅ ጣፋ ጋሻና ፩ ጦር ተሰቅሎበት ነበረ።የሕ

ንድ ነጋዴዎች በብዙ ጌጥ ያጌጠ የኤውሮፓ ያፍ ሥዕልና የግርማዊ ዳግማዊ ምኒልክና የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በላዩ ተቀምጦ ነበረ በዳር ከፊት የሚአስገርም ታላላቅ መስተዋት ተሰቅሎ ነበር ። የግሪክ ነጋዴዎችም ስለደስታ በመልካም አሠራር ተሠርተው ነበር ።

ከዚያ ወዲያ በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን አደራሽ ታላቅ ግብር ተደርጎ ነበርና መኳንንትና ክህናት ወታደርም በመልካም ተጋበዙ። ግንፉም ከተፈጸመ በኋላየሥራ ቤቱና አሽከር ሁሉ ዘፈኑንና እልልታውን ያቀልጥ ጀመር ።

በማግስቱም ፳፫ ቀን የሥላሴ ክህናት ስለ ደስታቸው መኳንንቶችን ሁሉ ጠርተው ታላቅ ግብር አድርገው ነበር። ከቤተ ክርስቲያኑም እስከ መንገድ ድረስ ንሴብሖ እያሉ በክብሮ እያመሰገኑ ወጡ ብዙ ቀኔም ደረሰና እየወረቡ ያመሰግኑ ነበረ ።

ተስፋ ገብረ ሥላሴ ዘብሔረ ቡልጋ።

የሥልጣኔ በረከት ሰላም በኢትዮጵያ ።

በሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በግርማዊ ንጉሥ ፊት የተነበበቃል ።

ትዕግሥቱ የማያልቅ አምላክ የሚሳነው የለም ። ክቡራን የኢብዮጵያ አለኝታ የሆናችሁ መኳንንቶችና ሺማግሌዎች ወጣቶች ልጆች አሁን በኢትዮጵያ እውቀት በራሳችን ጥልቅ ብላ ገባች ። መግባትዋም አይጠረጠርም ጉረቤቶቻችን በደስታ ሲጫወቱ ገና ዛሬ ኢትዮጵያ የሥልጣኔ ቤት መሠረተች ከአኒደኛው ደረጃ ወጣች ይህች ቆንጆ ኢትዮጵያ አበባዋ ያማረ ውበቷ የደመቀ በትክክል ስፍራ ተደላደለች ሲሉ የደስታቸውን ደስታ በሐገራችን ሲጥሉ ምስጋና ሲዘምሩ ይሰማሉ ። ይህም ሁሉ በሀገራችን ክብር ፍቅር በማጠንከራችን እናታችንን ወደ ሥልጣኑው ደረጃ ከፍ ከፍ በማድረጋችን እርግጥ መሆኑን ያመለክታል ። ይልቁንም ምሳሌዋ ያማረውን የሚያስደንቀው በመጠንከሩ የባዕድን ልብ ደስ እያሰኘች በማሳሰቧ ሀገራችን በመድመቋ ለማዬት የምታስጐመጅየሆነችውን በሥልጣኔ ባንዲራችንን ይዘን በመነሳታችን ምስጋናችንን ወደ እግዚአብሔር እናቀርባለን ። በኛ በልጆቹ ዕድሜ የምንለው ምን እንሆናለን ወደ ፊትስ ለሀገራችን የሚሆነውን ምን ያለው የስልጣኔ ጥቅም እናገኛለን ። ስንል የፍርሃትና የሐሳብ እንቅጥቅጥ በልባችን አርገን እናላውስ ነበር ።

አሁን ይኸን ሰሞን ለልባችን ተስፋ የሥልጣኔ ዓይን ስለ አገኘን ደስ ይለናል ክቡራን የኢትዮጵያ ሺማግሌዎችና ወጣቶች ልጆች እንዴት ያለው ለዘለዓለም የማይረሳ ወረታ ለለምለምዋ ሀገራችን ተደረገ ይህ ኩሉ ባንዲራዋ የጠነከረው አበባዋ የደመቀው ቆንጆዋ ኢትዮጵያ ልመናዋ ወደ እግዚአብሔር ባይታገሥ ነው እንግዲህ ወደፊታችን ሐሳባችን ሁሉ የሌላ ብልሃትና ጥበብ እንመለከታለን ይመስለኛል እንጂ ተንኰል ምቀኝነት ሊርቁ ይመስላል ነገር ግን ክቡራን በስልጣኔ የተመሰረታችሁ ወንድሞቼ ለወደፊት የግርማዊት ንግሥት ነገሥታትዘውዲቱንና የባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን እድሜ እየለመንን የሥልጣኔ መንገዳችንን ሄደን ለመጨረስ ያብቃን አሜን

ሥዩም ወልደ ገብርኤል

ጥቅምት ፩ ቀን የዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ፊት የዘመሩት መዝሙር

ለግርማዊ ።

ንጉሥ ተፈሪ መዝሙር

ከፍ ብለሽ በላይ በተራራው
ትልቁን ክብራሽን ተናገሪው
ኢትዮጵያ መልካም ባለዕድል
እልል እልል በዪ በታላቅ ቃል
እጅጉን ከልብሽ ደስ ይበልሽ
ተፈሪ መኰንን ነገሠልሽ ።

ኢትዮጵያ መልካም ባለዕድል
እልል እልል በዪ በታላቅ ቃል
አስተዋይ አሳቢ የሚሆንሽ
ተፈሪነው ያንቺ ደጉ አድልሽ
ኢትዮጵያ መልካም ባለዕድል
እልል እልል በዪ በታላቅ ቃል

ከበቀለ ሀብተሚካኤል

ማስታወቂያ

የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ትምህርትቤት በጥቅምት ፲፪ቀን መከፈቱን እናስታውቃለን

የትምህርት ቤቱ ዋና ሹም እንደራሴ ልጅ ቴዎድሮስ

አዛዥ ወርቅነህ

በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ማተሚያ ቤት ታትመው እስከ ጳጉሜ ፭ቀን ፲፱፻፳፰ ዓ ም የተሸጡና የተሰጡ መጻሕፍት ፲፬ሺ፱፻፺፫ ናቸው ።

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም ያድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

ኦቤርላንድ



ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሽ ኦቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጦጦን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባ ኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባተሪ ነው ካምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሬም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል «ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው

ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

ማስታወቂያ

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ላገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሊሆኑ ያሳተሟቸው በማተሚያ ቤታቸው የሚሸጡ መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲	ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ ደስታና ክብር	፱	ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
የዓለም ጅዖግራፊ በአማርኛ ዳጎስ ጥራዝ ዋጋው	፯	ብር
» » » መናኛ ጥራዝ ዋጋው	፮	ብር
ድጓም ፲፬ቱ ቅዳሴ ከነዘይቤው ወይም ነጠላ ትርጓሜ	፮	ብር
ጎሐ ጽባሕ	፭	ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫	ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫	ብር
የሕይወት ታሪክ	፪	ብር ተኩል
መዝሙረ ዳዊት ጥራዙ እጅግ ያማረ ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪	ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪	ብር
ትምሕርተ ኅቡዓትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪	ብር
የቁጥር ትምርት	፩	ብር
ያማሪኛ ሰዋሰው	፩	ብር
ወዳጄ ልቤ	፩	ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩	ብር
የልዑል አልጋ ወራሽ የአደን መንገዳቸው አኳኋን		አላድ
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ		አላድ
አጭር የዓለም ታሪክ		አላድ
ያማሪኛ ፊደል		ሩብ
አሳብና ምኞት		ሩብ
ትምሕርተ ሕፃናት		ሩብ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ጥሩ ሆኖ የተሠራ	፪	መ
ብርሃንና ሰላም አንድ ቁጥር		፪መ
የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ		ሩብ
የልዕልት ወይዘሮ መነን ፎቶ ግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ		ሩብ

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ። የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል

አደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ሱቅ ነው ።

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

“ሩግቢ” የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ገርምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይ ወኪል “አረቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ” ብቻነው·

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

RUGBY

ደግሞ በኒዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፥ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ባ ር ባ ሬ ሶ

ኮ ኛ ክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪመኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽናባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ያስናጂነት ፈቃድ የተቀበለ።

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በከፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በከፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ዓ ለ ም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዊድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO, Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad

ዓለም ሱቅ ፲፯ዓይነት የተሰማ አሽቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር ተኩል
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፱ ብር
ዝባድ	፩ ወቄት	፱ብር ተኩል
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፩ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፱ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፳ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፰ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ከረጂ	፯ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ከረጂ	፲፰ ብር ተኩል
አቡጀዲ መነጸር	፩ ከረጂ	፻፵፰ ብር
፡፡ ባለሰይጣን	፡፡	፻፵፰ ብር ተኩል
፡፡ ባለ ድመት ።		፻፵፰ ብር
፡፡ ባለአህያ	።	፻፵፱ ብር
፡፡ ባለሳቢ ግመል	።	፻፶ ብር
ባለ አንበሳ	፡፡	፻፵፭ ብር
ሱካር	፩ ጁኒያ	፳፰ ብር
ቻይ	፩ ነጥር	፩ ብር

ስለ ምንዛሪ

አንድ ብር	፲፱ ፍራንክ ፶ ሳን
በአንድ ብር	ሊሬ ፰ ከ፹፯ ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፲ ብር፹፫ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፴፭ ብር

ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬድንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አራተኛ ዓመት ፤ቁጥር ፵፫
4 me ANNÉE № 43

ሐሙስ ጥቅምት ፲፬ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም ።
JEUDI 24 OCTOBRE 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen , profondément désireux de voo regner dans son pays la lumière et la paix , a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የዘውድ በዓል መሰናዳት በሐረር ።

የዘውዱ በዓል በ፳፤ መስከረም እሁድ ሊሆን ከስምንት ቀን በፊት ክቡር ደጃዝማች እምሩ ለመኳንንቶቹና ለወታደሮቹ ሁሉ የመስቀልን ግብር አድርገው ነበርና በሻምፓኝ ጊዜም ክቡር ደጃዝማች እምሩ ተነሥተው ልዑል አልጋ ወራሽተፈሪ መኰንን ንጉሥ ሊባሉ ለዚሁም የዘውድ በዓል በ፳፤ መስከረም ሊሆን ተቆርጧል ይኸን ደስታ ስለ ሰማሁና ስላሰማኋችሁ በጣም ደስ ይለኛል ይኸንኑም በዓል በደኅና አክብረነው እንድንውል ተስፋ አደርጋለሁ ብለው በጨረሱ ጊዜ በታላቅ ደስታ ጭብጨባው ቀለጠና መኳንንቱ ሁሉ ዕድሚያቸውን ያርዝመው ከብዙ ደስታ ጋራ ብለው ተናገሩ ። ከዚያም ቀን በኋላ ክቡር ደጃዝማች እምሩ ከጥቂት መኳንንቶች ጋራ በዓሉ የሚደረግበትን ቦታ ለመምረጥ ሸዋ በር በወጡ ጊዜ የሸዋ በር አደባባይ መካከሉ ረባዳ ዳር ዳሩ ከረብታ አስተኔ የሆነውን አይተው ይኸ ለወደ ፊቱም የበዓል ማክበሪያ የሚሆን ማለፊያ ቦታ ነው ስለ ምን ዙሪያው ዳገት መካከሉ ረባዳ ስለ ሆነ ጌቶቹ ካሉበት ድንኳን የሚደረገው ሁሉ ለተመልካች አይደበቅም ብለው ከመረጡ በኋላ ድንኳን የሚተከልበትን ስፍራና እንዳንዱም ያልተተከከለው ቦታ ሁሉ እንዲደለደል የከተማውን ሹም አዘዙ።ከዚያም በኋላየመጋላው ገበያ የፊት በርና ደግሞ እመጋላው ላይ ወደያምስቱ በር የሚወስዱትን መንገዶች ሁሉ አምረው በእንጨትና ከያይነቱ በሆነ አቡቀዳዴ ተሠርተው እንዲያጌጡ አዘዙ ። የፊት በሩንም የሥራው አዛዥ በቅስት አስደርገው ከያይነቱ በሆነ አቡቀዳዴ አስጊጠው ፤እላዩም ትልቅ አንበሳ ተደርጎበት ግራና ቀኝ ጣፋ ጋሻችና ጦሮች ተሰቅለውበት ይታይ ነበር ። ይኸ ሥራ ሲጀመር ስለ ታላቅ ደስታቸው በፈቃዳቸው ከተማውን ያስጌጡ ወገኖች ቀጥለው የተጻፉት ናቸው ። መጀመሪያ፤ የሐረር ግምብ እስላሞች ሸዋ በርን እደጃፉ ላይ በሁለቱ ወገን መንገድ ሁለት ቅስት አድርገው እጅግ ባማረ ከያይነቱ በሆነ አቡቀዳዴ ሸፍነው አስጊጠው እላዩም የንጉሥ ተፈሪንሥዕል አድርገውበት ነበር።ሁለተኛ ፤ ከፈረስ መጋላ ወደ ሸዋ በር ከሚወስደው መንገድ እጉምሩክ ደጅ የጉምሩክ ሠራተኞች እጅግ ያማረ ቅስት አበጅተው እንደ ዘውድ አምሮ የተሠራ ወረቀት እላዩ አድርገውበት ነበር ። ሶስተኛ ፤ በከተማው ያሉ ግሪኮችና አርመኖች ከፈረስ መጋላ ወደ ሰንጋ በር የሚወስደውን መንገድ እንደዚያው በጣም አስጊጠው አበጅተው እላዩም የንጉሥ ተፈሪን ሥዕል አድርገውበት አምሮ ይታይ ነበር፤አራተኛ ፤ ከፈረስ መጋላ ወደ ቡዳ በር የሚወስደውን መንገድ በከተማ ያሉት የህንድ ቱጃሮች እጅግ ውብ አድርገው አስጊጠው አሳምረው አበጅተው፤እላዩም የንጉሥ ተፈሪን ስዕል አድርገውበት ነበር ። አምስተኛ ፤ ከፈረስ መጋላ ወደ ፊላና በር ከሚወስደው መንገድ ላይ የከተማ ዘበኞችና ደግሞ ከፈረስ መጋላ ወደ ኤረር በር ከሚወስደው መንገድ ላይ ስልከኞች አንዳንድ ረጃጅም እንጨት አቡቀዳዴ አልብሰው አቁመው እላይ እላዩም ለመጻፊያ የሚሆን ሰፊ ሰፊ ጨርቅ ተዘርግቶበት ነበር ። በሮቹንም አስጊጠው ያሠሩ ሰዎች ሁሉ በያሠሩዋቸው በሮች ላይ የሚጻፉትን ቃሎች አስናድተው አምጥተው ነበርና፤ ክቡር ደጃዝማች እምሩ አይተው እንዲጽፉ ፈቀዱላቸው ። በየክፍሉም የተጻፉት ቃሎች ከዚህ በታች ያሉት ናቸው ። ከፊት በር ከመጋላው ወገን የመኰንን ቡሩካኖች ግቡ ወደ ጌታችሁ ደስታ።ከግቢ ወገን በመንግሥቱ አዳራሽ ሕዝቡ ሁሉ ይበል ቡሩክ አንተ ንጉሠ እስራኤል።በሸዋ በር ከላይ ወገን አበባሽ አፈራ ሐረርጌ ኤፍራታ ፣ ከንቺ ተገኝቷልና የሠራዊት ጌታ ። ከታች ወገን ጽዮን

ሐረር ኃይልሽን ልበሺ ። ንጉሥ ተፈሪ ነው የቃኘው ልጅሽ። ከጉምሩክ ደጅ ላይ ወገን ሐረር የሺመቤት በጣም ደስ ይበልሽ። በምሕረት አደገ የተቀባው ልጅሽ። ከመጋላው ወገን ሐረር ቤተ ልሔም ከሁሉ እምትከብሪ ። ትንቢትሽ ደረሰ ለንጉሥ ተፈሪ። የህንድ ቱጃሮች በሠሩት ላይ በእንግሊዝ ቋንቋ ዕድሜ ለንጉሥ ተፈሪ።ግሪኮችና አርመኖች በሠሩት ላይ ሐረር ደስ ይበልሽ የቃኘው ከተማ። ተፈሪ ሆኑዋል ባለግርማ። ስልከኞች በሠሩት ላይ መድኃኔዓለም በቸርነቱ ። ወገብረ ኃይለ በመዝራዕቱ።የከተማ ዘበኞች በሠሩት ላይ ከንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ድምጽ መጣ እንዲህ ሲል ። ይህ ነው ልጄ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የምወደው በርሱም ደስታዬን የማይበት። በያጌጡት በሮች ላይ በየነጋዴዎቹ ቤትና በየመደብራቸው ሁሉ የኢትዮጵያና የየመንግሥቱ ባንዲራ ተደርጎበት ነበርና ከተማው ባበባ የተሸፈነ መስሎ ታየ ። ይልቁንም ፈረስ መጋላ ውበት ያፈነው ሆኖ ነበር ። ቅዳሜ ማታ በ፲ ሰዓትም የወታደር አለቆች ከነጭፍሮቻቸው ባማረ ሰልፍ ከሸዋ በር አደባባይ ወጥተው የሰልፍ ስፍራቸውን ተረክበው በ፲፪ ሰዓት ተመለሱ ። ደግሞ ማታ የኤሌክትሪክ መብራት ብሸዋ በር መንገድ ከግቢው በር አንሥቶ እስከ መድኃኔዓለም ደጅ ድረስ ይበራ ነበር። እፈረስ መጋላ መካከል ያለው ትልቁ የኤሌክትሪክ ፋኖስ የተጌጡትን በሮች ሁሉ እንደ ቀን አድርጎ ያሳይ ነበር።

የዘውዱ በዓል አከባበር።

ክቡር ደጃዝማች እምሩ እሑድ በ፳፯ መስከረም የጌታችንን የዘውድ በዓል ልናከብር ነው በዚሁ በደስታችን ቀን ማንም የኀዘን ልብስ ለብሶ ቢመጣ ቅጣት ያገኝዋል ወታደሮቻችሁን በጦር ልብስና በነጹሕ ልብስ አሰልፋችሁ በሁለት ሰዓት እተረከባችሁት ቦታ እንድትገኙ ብለው ሹሞቹን አዘው ነበርና በታዘዙት ሰዓት እንደተባለው ስለ ንጉሡ ደስታ ሁሉም የናቱን ያባቱን የእቱን የወንድሙን ኀዘን ትቶ የጦር ልብስ ያለው የጦር ልብሱን የሌለው ነጫጭ ልብሱን ለብሶ እተረከበው ቦታ ተሰልፎ ይጠብቅ ነበር ። ክቡር ደጃዝማች እምሩም ከኢትዮጵያና ከየነገሥታቱ የተሸለሙትን ኒሻን ሁሉ አድርገው ባማረ ዓጀብ ሁነው ወደ አደባባዩ ሲሄዱ በደስታ የተሞላ ፊታቸውና የኒሻኖቹ ፀዳል ባንድነት ሲታይ ለተመልካች ይደንቅ ነበር በሰልፉም አጠገብ በደረሱ ጊዜ ከሰልፉ ውስጥ ከጦር ልብስና ከንጹሕ ልብስ በቀር አንድ ስንኳ የኀዘን ልብስ ባለማየታቸው እጅግ ደስ አላቸው ሰልፉም በየ፫፻ው ሰው (የሻምበል) መለያ ባንዲራ ያለባቸው እንጨቶች ተተክለው አበባ መስለው ይታዩ ነበር ።

በዚያም መካከል አልፈው ከተሰናዳላቸው ድንኳን ውስጥ ገብተው ተቀመጡ። የውጪ አገር ሰዎችም በየቆንሲላቸው ተጠርተው በ፫ ሰዓት እንዲገቡ ማስታወቂያ ተጽፎላቸው ነበር። ለካህናቶቹም ባደባባዩ መካከል ትልቅ ድንኳን ተተክሎላቸው ነበር ለከተማው ትልልቆች እስላሞችም በጌቶቹ በስተ ግራ እልፍ ዝቅ ባለ ቦታ እንዲሁ ተተክሎላቸው ነበር ። ለክብርት ወይዘሮ ጽጌ ማርያምም ከሴት ወይዘሮች ጋራ እንዲመለከቱበት ከሰልፉ በስተ ኋላ ከፍ ባለ ቦታ ያማረ ድንኳን ተሰናድቶላቸው ነበር ። ለከተማ ሴቶችም የሚዘፍኑበትና እልል የሚሉበት በሜዳ በስተ ግራ ዝቅ ባለ ቦታ ድንኳን ተተክሎላቸው ነበር ። ደግሞ ነጋሪት መቺዎች እምቢልታና መለከት ነፊዎች ከፍተኛ ለመታየት የሚመች ቦታ ተቀብለው ነበር ። ፫ ሰዓት ሲሆን ሁሉም እተሰናዳለት ቦታ እንደገባ በዓሉ ተጀመረ ። ከዚህ በኋላ በጕፈር ያጌጡት ዋና ዋና ሹማምንቶች ከየሰልፋቸው ማህል ተጠርተው መጡና በጌቶቹ በስተግራ ባለው ድንኳን ተቀመጡ ። በግንባርም ወገን ከፍ ባለው ቦታ ላይ ደባይ ነጋሪት ተቀምጦ ያዋጅ አመታት እየቆየ ይመታ ነበር ። አጠገቡም ከፍ ያለ ጠረጴዛ ያማረ ልብስ ለብሶ ተዘርግቶ ነበር ። ከደባዩ ነጋሪትና ከጌቶቹ ድንኳን መካከል በረጅም እንጨት ላይ ትልቅ በወርቅ የተዘመዘመ ባለ መርገፍ ባንዴራ ተሰቅሎ ይግለበለብ ነበር ። ፫ሰዓት ተኩል ሲሆን በጕፈር ያጌጡት ሹማምንቶች ወርደው በደባዩ ነጋሪት ግራና ቀኝ ቆሙ። በዚያን ጊዜም ያዋጁን ቃል ለመስማት በሁሉ ስፍራ ግርማ ያለው ዝምታ ሆነ ። አዋጅ ነጋሪውም ባማረ ልብስ አጊጦ ከጸሐፊው ጋራ እጠረጴዛው ላይ ወጥተው ቆመው የጸሐፊው ሹም እየመራው ስማ ተስማማ ያልሰማህ መስማሚያ ይንሣህ ብሎ ላዋጅ የሚነገረውን የደምብ ቃል በተናገረ ጊዜ ፤ ክቡር ደጃዝማች እምሩና አብረዋቸው የነበሩ የውጪ አገር ሰዎች ባንድነት ተነስተው ቆሙ ። ከዚህ በኋላ አዋጅ ነጋሪው ድምፁን ከፍ አድርጎ (በእግዚአብሔር ቸርነት በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ፈቃድ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ሆነዋል) እያለ በራቱ ማዕዘን እየዞረ ተናገረ ። ይኸውም ቃል ለውጪ አገር ሰዎች በየቋንቋቸው ተተረጐመላቸው። ያዋጁም ቃል በተፈጸመ ጊዜ ዳር እስከ ዳር እልልታና ጭብጨባ ያለ ልክ ይቀልጥ ነጋሪቱም ይመታ እምቢልታና መለከት በየስፍራው ያወካ ጀመር ። በዚሁ ግምግምታ ላይ መድፎች በፍጥነት እየተከታተሉ ሲተኩሱ የነሐሴን ነጐድጓድ ይመስል ነበር ። በዚያን ጊዜም የንጉሥ ተፈሪ መኰንን ትልቅ ሥዕል ከያይነቱ ቀለም ባለው አበባ ዙሪያውን አጊጦ ሁለት መለዮ የለበሱ ወታደሮች ተሸክመውት ሃምሳ የሚሆኑ ባለ መለዮ ወታደሮች ዓጅበውት እምቢልታ በፊቱ እየተነፋ በሰልፉ ፊት ዙሪያውን እያዞሩ ለሕዝቡ ሁሉ ያሳዩ ነበር።ሥዕሉም በየደረሰበት ስፍራ ሁሉ እልልታው ሳያቋርጥ ይቀልጥ ነበር ። አንድ ጊዜም ዞሮ ፊት እነበረበት ቦታ በጌቶቹ በስተ ቀኝ ፊት ለፊት ወታደሮቹ እንደ ተሸከሙት ቆመ።

ከዚህ በኋላ ክቡር ደጃዝማች እምሩ አብረዋቸው ከነበሩ መኳንንቶችና ከውጭ አገር ሰዎች ጋራ ተነሥተው ቆመው ከፍ ባለ ድምፅ ክቡራን ጌቶቼና እመቤቶቼ ሆይ ስለ ዛሬው በዓል አንዳንድ ቃል ልናገር እወዳለሁ ። ግርማዊ አፄ ምኒልክ በብርቱ ሥራቸውና በመልካሙ አካሄዳቸው ኢትዮጵያን ከፍ ከፍ አደረጓት ከጉረቤቶቿም ጋራ በመልካም ወዳጅነት አቃረቧት ። ከሳቸውም በፊት ከነበሩት ነገሥታቶች ይልቅ

ለስማቸው መታሰቢያ የሚሆኑ ብዙ ነገሮች ተዉላት ፣ አሳባቸውም ሁሉ በትምህርትና በእውቀት አሰልጥነው ከጓደኞቿ ጋራ ለማስተካከል ነበር ። ለዚሁም ሥራቸው ሁሉ አጋዣቸው ስመ ጥሩው ራስ መኰንን ነበሩ ። እንደዚሁ አገራቸውንና ሕዝባቸውን በደህና ሲጠብቁ ቆይተው ሁሉም ወደ ማይቀሩበት ሥፍራ ሄዱ ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለ አፄ ምኒልክ ስም ክብር ልጃቸውን ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ብለው የልዑል ራስ መኰንን ልጅ የዛሬውን ንጉሣችንን ለመንግሥቱ ሥራ እንደራሴና ያልጋወራሽ አድርገው ሾሙዋቸው ። ይኸውም ከሆነ ዛሬ አሥራ ሁለተኛ ዓመቱ ነው።በነዚሁም ዓመታቶች ውስጥ የአፄ ምኒልክን ሃሳብ ተከትለው ለሕዝባቸው ልማትና ላገራቸው ስፋት ለሚሆን ነገር ሁሉ እንደሚጥሩ በሁላችንም ዘንድ የታወቀ ነው ።

እኔም ደስ የሚለኝ ዛሬ ንጉሥ በመሆናቸው ብቻ አይደለም ሥልጣኑን ሁሉ አግኝተው ለኢትዮጵያ ጥቅም የሚሆነውን ሁሉ እንዲሠሩ ታላቅ ተስፋ ስላለኝ ነው ። ሁሉም በእግዚአብሔር ፈቃድ ሆነ ያለሱም የሚሆን የለም ብለው (ዲስኩሩን) በጨረሱ ጊዜ የደስታ ጭብጨባ እያስተጋባ ይቀልጥ ጀመረ ። ከዚህም አስከትለው ሙሴ ፕላውመን የእንግሊዝ መንግሥት ቆንሰል እንደቆሙ ክቡር ደጃዝማች ሆይ እላንትም ጌቶቼና እመቤቶቼ ወደዚች እማትረሳው በዓል እኛም ስለ ተጠራን ብዙ ደስ ብሎኝ በዚች ዳስ የተሰበሰባችሁ የውጭ አገር ሰዎችም ሁሉ ብትፈቅዱልኝ የእንግሊዝ መንግሥት ደስታ አሁን የምገልጸው ነው ይህ የዛሬው ቀን ልዑል ተፈሪ መኰንን በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና በኢትዮጵያ ሕዝብ ፈቃድ ወደ አዲሱና ትልቁ የንጉሥነት ማዕርግ የደረሱበት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ታላቅ መታሰቢያ ሆኖ ይኖራልን መላ ኢትዮጵያም ይልቁን ደግሞ ይህቺ የሐረር አውራጃ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን በልዩ እስከ ዛሬ የወደዱት ምስጋናዋን በብዙህ ታቀርባለች ትልቁ ልዑል ራስ መኰንን ዛሬ ከኛ ጋራ ኖረው ቢሆን የጀመሩትን ሥራ ልጃቸው እንዳሻሻሉትና እንዳሳመሩ አይተው ምንኛ ደስ ባላቸው። ዛሬ የኢትዮጵያ ሰው እያንዳንዱ የምናከብረው በዓል ግርማዊ ተፈሪ መኰንን ፲፪ ዓመት ሙሉ ለሐገራቸው በብዙህ ስለደከሙ የሆነው ብቻ አይደለም በየጊዜው የሚነሣው ፖለቲካ ሁሉ መቅረቱና ከእንግዲህ ወዲያም ኢትዮጵያ ሰላምና ደስታ ማግኘቷን ያሳያል። ክቡር ደጃዝማች ሆይ ወደዚች የደስታ በዓል በተሰበሰቡት የውጭ አገር ሰዎች ሁሉ ስም መልካም ምኞታችንን ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ያደርሱልን ዘንድ እለምንዎታለሁ በነሱ ከእግዚአብሔር እርዳታ ጋራ ከሌሎችም መንግሥታት አብሮ የሚያሠራት ወዳጅነቷ ኢትዮጵያ ወደ ሥልጣንና ወደ መሻሻል ለመሄድ አትበዝንም እድሜ ለኢትዮጵያና ለገዢዎቿ ብለው በጨረሱ ጊዜ እጅግ ተጨበጨበላቸው ። ከዚህ አስከትለው ክቡር አባ እንድርያስ ስለ ንጉሡ የሚሆን የምረቃ ቃል ተናገረው የሞቀ ጭብጨባ ሆነላቸው ። ከዚህ በኋላ ሁሉም ባንድነት ሆነው ንጉሥ ተፈሪ ሺህ ዓመት ይኑር፤ ኢትዮጵያ ከፍ ትበል ብለው ተቀመጡ ይኸም ከሆነ በኋላ ከሰልፋቸው ላይ ተጠርተው የመጡት ዋና ዋና በጎፈር ያጌጡት ሹሞች ከቦታቸው ተመልሰው በተሰጣቸው ደምብና ሰዓት ወታደሮቻቸውን እያሰለፉ በጌቶቹ ፊት እንዲያልፉ አጋፋሪ አስታወቃቸው። የሰልፉም አሰላለፍ እንዲህ ነበር ብዬ ለመዘርዘር ይረዝማልና ሁሉ በየክፍሉ አምሮ አለፈ ። ይኸውም ሁሉ ሲሆን ሹማምንቶቹ ሳይቀሩ የደስታ ጭፈራ እየጨፈሩ እንደ እንቦሳ እየዘለሉ በጌቶቹ ፊት ሲያልፉ ከድምጻቸው ማማርና ከኳሁናቸው ደማም ከጦር ልብሳቸው መስማማትና ጽዳት የተነሣ ተቀምጠው ለሚያዩት መኳንንቶችና የውጭ አገር ሰዎች ከልክ ያለፈ ደስ አሰኘ ይኸውም በ፫ ሰዓት የተጀመረው በዓል ለ፮ ሰዓት ሩብ ጉዳይ ሲሆን ተፈጸመ።በዓሉም ከተፈጸመ በኋላ ክቡር ደጃዝማች እምሩ የውጭ አገር ሰዎችን በየቆንስላቸው አሰናበቱና ከመኳንንቱ ጋራ በድንኳኑ ውስጥ ፲፰ ደቂቃ ያህል ተቀምጠው የከተማ ሴቶች ሁሉ ከበሮ እየመቱና እየዘፈኑ ንጉሡን እያሞገሱ በጌቶቹ ፊት ሲያልፉ የድምጻቸው ማማር መድመቅ ለሕዝቡና ለመኳንንቱ በጣም ደስአሰኙ።እየተሰለፉም ፣ ሚያልፉ ሁሉንንጉሡን እያሞገሱ ይጨፍሩ ነበር የያንዳንዱንም ክፍል ምስጋና እንዳልጽፈው ላንባቢዎች ይሰለቻል ብዬ ተውኩት።የየክፍሉም ሹሞች ሥራቸውን በተወሰኑ ደቂቃዎች ውስጥ እየፈጸሙ እንዲያልፉ ከክቡር ደጃዝማች እምሩ የማመልከቻ ትእዛዝ ተቀብለው ነበርና ከዋጁ ጀምሮ እስከ ሰልፉ መጨረሻ ይህንኑ ሥራቸውን አንድ ቀቂቃ ስንኳ ሳያስተላልፉ በማማር በመቀልጠፍ ሲፈጽሙት እጅግ የሚያስገርም ነበር።የሰው ልብ ከልጅ እስካዋቂ ደስ ያላለው በዚህ ቀን አልነበረም።በሰልፍም ሲያልፉ የዋሉት ከዘበኛና ከጋፋሪ ባልደረባ ከነጋሪት መችዎችም በተቀር ሹማምንቶቹ ወታደሮቻቸውን አሰልፈው እፈረስ መጋላ ይጠብቋቸው ነበር ክቡር ደጃዝማች እምሩም የንጉሡን ሥዕል ከነጋሪቱ በኋላ ከሳቸው ፊት አሸክመው ነጋሪቱ እየተመታ እምቢልታ መለከት እየተነፋ በመኳንንቶችና መጨዮ ልብስ በለበሱ ወታደሮች ታጅበው ሲሄዱ በመንገዱ ዳር ዳርና በየግምቡ ላይ ሆነው የሚመለከቱ ሴቶች ሥዕሉን ባዩ እልልታ ያለ ልክ ይቀልጥ ነበር።የነጋሪቱና የምቢልታው የመለከቱና የእልልታው ድምጽ ባንድነት በተሰማ ጊዜ የሰልፉ ርምጃ በፈቃድ ይተካከል ነበር። ክቡር ደጃዝማች እምሩም ይኸ ሁሉ ሲሆን የከተማዋን ማጌጥ የሕዝቡን ጽዳትና አኳሁን እያዩ በልብ ሳቅ ፊታቸው ፈገግ ፈገግ ይል ነበር በእንደዚሁ አኳሁን አፈረስ መጋላ በሚጠብቃቸው ሰልፍ መካከል አልፈው ወደ ግቢያቸው ገብተው ለወታደሩ ደስ የሚያሰኝ ግብር አደረጉለት። ክብርት ወይዘሮ ጽጌ ማርያምም አብረዋቸው ለዋሉት ሴት ወይዛዝሮችና ለከተማ ሴቶች ሁሉ እንደ ማዕርጋቸው የደስታ ግብር አድርገውላቸው ደስ ብሏቸው ዋሉ።በማግሥቱም ሰኞ ለገሚሱ ወታደር ግብር ሆኖ ዋለ ፣ ማክሰኞ በ፲ ሰዓት በከተማ ያሉት የህንድ ቱጃሮች ሻይ ተጋበዙ ማታም ለቆንስሎችና ለትልልቅ ነጋዴዎች ግብር ሆኖ አመሸ ከራትም በኋላ ከያይነቱ ምግብና መጠጥ ተሰናድቶ ለባል ጨዋታ (ዳንስ) በከተማው የሚኖሩ የውጭ አገር ሰዎች ሁሉ ተጠርተው ነበርና እስከ እኩል ሌሊት

ሲጫወቱ ቆይተው ደስብሏቸው መርቀው ሄዱ እሮብም የስላሞች ግብር ሆኖ ዋለ።እንደዚህባሉ ደስታዎች የጌታችን የዘውድ በዓል ተፈጸመ። እስከ ዛሬ ድረስ በፈረስ መጋላ የሚታይ ሁሉ ከደስታ በቀር የከፋው ሰው አይገኝም ።ይኣቁንም የድሆቹ ደስታ ሐረር ከግርማዊ ንጉሥ በዓል መሰናዳት ጀምሮ በከተማዋና በዙሪያዋ ባሉ አገሮች ሁሉ እስከ ዛሬ ዝናቡ በብዛት ይዘንባልና ምነው ንግሡ ቀድም ባለል፣ ኖሮ አሁንም ተፈሪ ከነገሡልን ምሕረት ወረደልን እያሉ ነው።እኔ እንደማየው ከዛሬ በፊት የሐረር ከተማ እንዲህ ያለ ክብርና ደስታ ያየች አይመስለኝም ወደ ፊት ግን በእግዚአብሔር ፈቃድ ያሁኑን እጥፍ የሚሆን ክብርና ደስታ እንድታገኝ ተስፋ እናደርጋለን ።

አስፋው አበጀ

ኢትዮጵያ ከአውሮጳ ጋራ በጣም መቃረብ ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ የዘውድ ማዕርግ ተቀብለው ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ በመሆናቸው የሚገባቸውን ሥራ ለመሥራት የጀመሩት ሥራ ቀጥሎ የተጻፈው ነው ።

፩ኛ ፤ በእንግሊዝ ዋና ከተማ በሎንዶን ፤ በኢጣልያ ዋና ከተማ በሮማ፤ በፈረንሳዊ ዋና ከተማ በፓሪስ፤ የኢትዮጵያን ሌጋሲዮን ለማቆምና ሚኒስትሮች እየሾሙ ለመስደድ ቁርጥ አሳብ ማድረጋቸውን አሁን ባለፈው ሳምንት በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዋና ዴሬክተር በኩል አዲስ አበባ ለሚኖሩት ለውጭ አገር መንግሥቶች እንደራሴዎች አስታውቀዋል ።

የአውሮጳ መንግሥቶች ከብዙ ዘመን በፊት በአዲስ አበባ ሌጋሲዮን ሲያቆሙ ፥ ሚኒስትሮችና ቆንስሎችም ሲሾሙ እየታየ የኢትዮጵያ መንግሥት በአውሮጳ ሌጋሲዮን ባለመቆሙና ሚኒስትሮች ባለ መሾማቸው ብዙ ሰዎች ምክንያቱን ሲጠይቁ ነበርና አሁን የኢትዮጵያ መንግሥት ሌጋሲዮን በአውሮጳ እንዲቆም በመታሰቡ የኢትዮጵያ ወዳጆች የሆኑ ሁሉ ደስ ሳይላቸው አይቀርም ።

፪ኛ ፤ የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና ያገር ግዛት ሚኒስቴር፥የንግድ ሚኒስቴርም ሥራ እየሰፋ እንዲሔድ ስለፈለጉ ለነዚህ ለሶስቱ ሚኒስትሮች ትልቅ እውቀት ያላቸው አማካሪዎች ከውጭ አገር በደመወዝ ለማስመጣት ንግግር ጀምረዋል።

፫ኛ ፤ የርስትና የትምህርት አዋጅ እንዲነገር አድርገዋል ።

ይኸውም የንጉሥ ቸርነትና ደግነት የሕዝብም ደስታ ይባላል፤

አባትና እናት ልጅ መውለዳቸው ብቻ አያስመሰግናቸውም፥ነገር ግን ልጁ ከተወለደ በኋላ እንዳይርበውና እንዳይጠማው፤ እንዳይበርደውና እንዳይታመም፥ በሚቻላቸው ሁሉ መርዳትና መጠበቅ ይገባቸዋል ።

ንጉሥም በሕዝብ ላይ ነገሠ መባል ብቻ አያስመሰግነውምና ሕዝቡ ከችግር የሚድንበትን ፥ በረከትና ሀብት የሚያገኝበትን፥ ከጠላት የሚጠበቅበትን ደንብና ሥራ ማቆም ይገባዋል ።

ይህንኑም አውቀውና ተረድተው አሁን ባለፈው እሑድ በጥቅምት ፲፩ ቀን ግርማዊት ንግሥታችንና ግርማዊ ንጉሣችን ስለ ርስትና ስለ ትምህርት ያስነገሩት ያዋጅ ቃል የኢትዮጵያን ሕዝብ በሙሉ ደስ የሚያሰኝ ነው ።

ከዚህ ቀደም አንድ ሰው ከአባቱ የወረሰውን፥ወይም ለመንግሥት አገልግሎ ንጉሥ የተከለውን ርስቱን ባንድ ቀን ጥፋት ተነቅሎ ዕድሜውን በችግር ይጨርስ ነበር፤ ልጆቹም ያለርስት ይቀሩ ነበር ። አሁን ግን ማንም ሰው ቢያጠፋም በሌላ ቅጣት ይቀጣ እንጂ ርስቱን አይነቀል።እጅግ የበረታ ጥፋት ቢያጠፋ እንኳ ርስቱ ለልጁ ወይም ለዘመዱ ይለፍ ተብሎ አዋጅ መነገሩ ለሕዝባቸው ትልቅ የሆነ መልካም አሳብ ማሰባቸውን ያስረዳናል።

ስለ ትምህርትም ነገር ማንም ሰው ቢሆን ካልተማረ አያውቅም ካላወቀም እግዚአብሔርንና ንጉሡን አይፈራም ። እግዚአብሔርንና ንጉሡንም ካልፈራ በሥጋው ቅጣት፤ በነፍሱም ኵነኔ ይፈረድበታል ።

ስለዚህ ግርማዊት ንግሥትና ግርማዊ ንጉሥ ሕዝባቸው በሥጋው ቅጣት ፤ በነፍሱም ኵነኔ እንዳያገኘው አስበው ሰው ሁሉ ልጁን እንዲያስተምር አዋጅ መንገራቸው ለሕዝባቸው ትልቅ አሳብና እርዳታ መሆኑ አይጠረጠርም ።

ስለ ርስትና ስለ ትምህርትም የተነገረው ያዋጅ ቃል ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው ።

አዋጅ ።

ስለ ርስት ።

ማንኛቸውም ያገር ሰው ቢሆን እስካሁን ድረስ በእጁ የያዘው ርስቱ እንደማይነቀለው የርስት አገር ሁኖ የረጋና የጸና ይሁንለት ።

ከዛሬም ጀምሮ በደለኛ ሆኖ ጥፋት የሚገኝበት ሰው ሁሉ እጁን ከሰጠ እንደ ጥፋቱ መጠን በሚገባው ቅጣት በአካሉና በገንዘቡ ይቀጣል እንጂ በማናቸውም ወንጀል ቢሆን ርስቱን አይነቀልም።ነገር ግን ንጉሡንና መንግሥቱን የሚጐዳ ብርቱ ጥፋት ያጠፋ ሰው የሆነ እንደሆነ እጁንም ቢሰጥ ርስቱ ልጅ ቢኖረው ለልጁ ልጅ ባይኖረው መውረስ ለሚገባው እስከ ሶስት ትውልድ ላለው ዘመዱ ያልፋል እንጂ አይነቀልም ።

እጁንም ለሰጠው ወንጀለኛ ለቀለቡ ያህል መንግሥት በሚወስነው ልክ ርስቱን የወሰደው ልጁ ወይም ዘመዱ ይሰጠዋል።

ጥፋተኛውም በጥፋቱ ከተፈረደበት በኋላ ልጅ የወለደ እንደሆነ አስቀድሞ ርስቱ የተመረቀላቸው ዘመዶቹ ውርሱን ይዘው በገበሩበት፤ግማሹን አስቀርተው ግማሹን ለልጁ ይልቀቁ ። ጥፋተኛውም በቁጭትና በእልክ ያልወለደውን ዲቃላ እየተቀበለ ወራሾቹን ዘመዶቹን እንዳያስቸግር ከሚስቱ የተወለደ እውነተኛ ልጁ ካልሆነ በቀር ከሌላ ተወልጃለሁ ለሚል ዲቃላ ርስቱ አይለቀቅም ።

ስለ ትምህርት።

ልጅ ያለው ሰው ሁሉ ልጁ ክፉንና በጎን የሚለይበትን፥ ንጉሡንና ፈጣሪውን የሚፈራበትን እውቀትን ለማግኘት የንባብና የጽሕፈት ትምህርት ያላስተማረ መቀጫውን ፶ ብር እየከፈለ፥ የመቀጫው ገንዘብ ወደ ቤተ ክርስቲያን እየገባ ለነዳያን ምግብና ልብስ ይሆናል ።

የንስሐ አባትም የሆንክ ቄስ ሁሉ የንስሐ ልጆችህ ልጆቻቸውን እንዲያስተምሩ ምክር፥ሁለት ሶስት ጊዜ ልጆቻችሁን አስተ-

ምሩ ብለህ ከመከርክ በኋላ ምክርህን የማይቀበሉ ቢሆኑ ግን አዋጅ አፍራሾች መሆናቸውን ላገሩ ሹም አስታውቅ ።

/የገጠር መሬጌታም የሆንክ በየቤቱ ክርስቲያኑ ከሌላው ግብርህ ጋራ ቀላቅለህ የሰበካውን ሰዎች ልጆች የንባብና የጽሕፈት ትምህርት አስተምር ።

የደብርም አለቃ የሆንህ ሰው ፈጣሪውን አውቆ የሚጠቀምበትን በደብርህ መንፈሳዊ ዕውቀት ለምእመናን በሚገባው ልክ የስብከት ትምህርት በየደብርህ አስተምር ።

ሳታስተምር የቀረህ እንደሆን ግን በሹመትህ ትቀጣለህ። ደግሞ ልጅ ያለህ ሰው ሁሉ ልጅህ የንባብና የጽሕፈት ትምህርት ከተማረ በኋላ ለሕይወቱና ለኑሮው የሚያሻውን ገንዘብ ለማግኘት እንዳይቸገር ባገራችን ካለው የእጅ ሥራ ልብህ የሚወደውን አንድ አንድ የእጅ ሥራ እንዲማር አድርግ ። ለትዳሩ የሚሆን የእጅ ሥራ ሳታስተምረው የቀረህ እንደሆነ ግን በአክል ጉዳይ ካሣ ግማሽ ወደ ድሆች ተማሪ ቤት የሚገባ መቀጫ ፺ ፱ ብር ትከፍላለህ።ይኸንንም የተቆጠረውን ትምህርት ይማር የተባለው ልጅ ዕድሜው ከ፯ ዓመት እስከ ፲፭ ዓመት ድረስ ያለውን ነውና ከዚህ በላይ ላለው የትምህርት ዕድሜ በተላለፈው ልጅ አባቱ አላስተማርህም ተብሎ አይቀጣ ።

ጥቅምት ፲፩ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓመተ ምሕረት ።

የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ የአኖሲያድ ኒሻን መሸለም።

አኖሲያ ማለት ብስራት ወይም የምስራች ማለት ነው ።

ይህንኑም የሚያስረዳ ነገር ቅዱስ ገብርኤል እመቤታችንን እንደ አበሰራት ሆኖ በወርቁ ኒሻን ላይ ተሥሎ ይታያል ።

ይኸውም ኒሻን የተጀመረው የሳቦይ ዘር በሚሆን በንጉሥ አሚዴኦ ዘመን በ፲፫፻፶፬ ዓመተ ምሕረት ስለሆነ ከወጣ ፭፻፷፯ ዓመታት መሆኑ ነው ።

አሚዲኦ ማለት ፍቁረ እግዚእ(የእግዚአብሔር ወዳጅ) ማለት ነው ።

በእርሱም ዘመን የእስላሞች ኃይል በርትቶ ወደ ክርስቲያን አገር ይዘምቱ ነበርና በእስላሞች ጦርነት ውስጥ ከእርሱ ጋራ ሁነው ስለ ክርስቲያን ሃይማኖት የተዋጉትን የነገሥታት ዘርና፥ እራሱንም ለማስከበር ሲል ይህን አኖሲያድ የሚባለውን ኒሻን አውጥቷል ።

አሁንም ክርስቲያንነት በኢትዮጵያ ከተጀመረበት ከአብርሃና ከአጽብሐ ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ከአረማውያንና ከእስላሞች ጋራ ሲዋጉ የኖሩ የኢትዮጵያ አርበኞች መሬ ንጉሥ ተፈሪ ይህን የብስራት ኒሻን ከግርማዊ ንጉሥ ቢክቶር አማኑኤል በልዑል ሉይጂ ዲሳቦያ ዱክ ዴዛብሩዝ እጅ መጥቶላቸው ስለተሸለሙና ይልቁንም ጊዜ አጋጥሞ ዘውድ በሚኖበት ጊዜ ስሙ የምስራች የተባለ ኒሻን ስለ ተቀበሉ ብርሃንና ሰላም እንኳን ደስ አለዎ ይላል ።

በዚሁም ቀን ልዑል ሉይጂ ዲሳቦያ ዱክ ዲዛብሩዝ የሰሎሞንን ባለ አረንጓዴ ኮርዶ ኒሻን፥ የኢጣልያ መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ከማንዳቶር ኮራ የዳግማዊ ምኒልክን ባለቢጫ ኮርዶ ኒሻን ከኢትዮጵያ መንግሥት ስለተሸለሙ ብር/ንና ሰላም እንኳን ደስ አላችሁ ይላል ።

አቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ አቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።



አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባ ኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኜቶና ባለባተሪ ነው ካምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል «ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው

ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

COGNAC S.E.&A.METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ኦሜጋ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል "አረቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

RUGBY

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በ፡ ስቶን በማድራስ በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መጣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፣ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ባ ር ባ ሬ ሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪመኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽናባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ያሰናዷኸት ፈቃድ የተቀበለ።

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በካፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በካፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዌድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad



ዓለም ሱቅ ፲፪ዓይነት የተሰማ አሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንፎር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ፤በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል

አደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ሱቅ ነው ።

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ በለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለአንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬድንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

ጉድይር ግዙ

በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አራተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፵፬
4 me ANNÉE . № 44

ሐሙስ ጥቅምት ፳፪ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም ።
JEUDI 1 NOVEMBRE 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Sa Majesté le Roi Teferi Makonnen , profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix , a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ መላ ኢትዮጵያ ፍጹም ደስታ ።

በዚህ ወራት ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የንጉሥነት ማዕርግ ተቀብለው ዘውድ ስለ ጫኑ በመላ ኢትዮጵያ ከደብር እስከ ገጠር፤ ከከተማ እስከ ባላገር፤ ዳር እስከ ዳር ያለው ሰው ሁሉ፤ ከልጅ እስከ ሽማግሌ፤ ከጌታ እስከ ሎሌ፤ ማናቸውም ቢሆን ፈጽሞ ደስ ያላለው አለመገኘቱን አጥብቀን ተረድተዋል፡፡

ለዚሁም ማስረጃ ከየአውራጃው ሁሉ፤ በተደረገው የዘውድ ባዓል አከባበር፤ ሴቱ በዕልልታ፤ ወንዱ በድንፋታ፤ ካህናቱ በዜማ፤ መኳንንቱ በግርማ፤ ሁሉም በየአበባላቸው ከተደረገው ደስታ፤ ከየካህናቱ ብዙ መልክክም ቅኔና ደግሞ አጽም የሚያለመልም የደስታ ምረቃ፤ ከየመሳፍንትና መኳንንቱም እጅግ የተዋበ የደታ ንግግርና የሰልፍ አሰላለፍ የግብርም አገባብ ማሳመር ብዙ የብርሃንና ሰላም ተላላኪዎች እየጻፉ ላኩልናል፤ ነገር ግን ከቃላቱ ብዛት የተነሣ የማያደርሰን ስለሆነ ከሙሉ በከፍሉ፤ ከብዙ በጥቂቱ እንጽፋለን ።

የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪመኰንን ዘውድ ባዓል አከባበር በድሬ ዳዋ

በ፲፱፻፳፩ ዓመተ ምሕረት መስከረም ፳፯ ቀን ስለ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ዘውድ በዓል የከተማው ሕዝብ ሁሉ በድሬ ደዋ ከተማ ማዘጋጃ ቤት እንዲሰበሰብ ተጠርቶ ነበረና በዚሁ በተቈረጠው ሰዓት ሕዝቡ ተሰብስቦ ፊታውራሪ ዘሩፋም ወታደሩን አሰልፈው ሲጠባበቁ በራት ሰዓት የከተማው ዲሬክተር አቶ አስታጥቄ በጥቂት ወታደሮች ታጅበው፤ በመጡ ጊዜ ወታደሩ የሚገባ ሰላምታ ሰጠ ፤ መድፈኞችም የጥሩምባ ድምጥ በሰሙ ጊዜ አከታትለው መቶ አንድ ጊዜ ተኰሱ የጥሩምባውና የመድፉም ድምጥ የሰውን ልብ ሲያናውጠው ዋለ። የግብዣውም ሥርዓት የኢትዮጵያ መንግሥት ሹማምት በቀኝ የውጭ አገር መንግሥት ቆንሲሎችና ነጋዴዎች የምድር ባቡር ኩባንያ ሹማምቶች በግራ ሁነው ሲታዩ እጅግ ያምሩ ነበረ። በሽምፓኙም ጊዜ ዲሬክተሩ ቀጥሎ የተጻፈውን ቃል ተናገሩ

ክቡራን የኢትዮጵያ መ ሹማምቶችና ደግሞ የከበራችሁ የውጪ አገር መንግሥት ወኪሎችም የምድር ባቡር ኩባንያ ሠራተኞችና ነጋዴዎች ።

ስለ ግርማዊ ንጉሣችን ስለ ተፈሪ መኰንን ንግሥ በዓል በዛሬ ቀን ስለ ተሰበሰባችሁ በድሬ ደዋ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ስም ሁኜ ምስጋናዬን ላቀርብላችሁ እወዳለሁ ።

እንደ ሰማችሁትና እንዳወቃችሁት ሁሉ የኢትዮጵያ ክብሯና መመኪያዋ የሆኑ ዳግማዊ ምኒልክና የኢትዮጵያ ደገፏና ግርማ የነበሩ ታላቁ ልዑል ራስ መኰንን በአረመኔዎች ኃይል ተጠቅታና ተጨቁና ልትወድቅ ትፍገመገም የነበረችውን ኢትዮጵያን በኃይላቸው ደግፈው በጥቂት ቀን አቋቁመው ወሰኗን እንደ ነበረ መልሰው ታሪኳን አፅፍተው ስላቀኑ በዚ ቀን የሁለቱን ስም ለማንሣት ግዴታዬ ነው።

ግርማዊ ንጉሣችን የሁለቱን ልዑላን ኃይልና መልክም ፍለጋ ተከትለው ላገራቸው የሚቀኑትን ቅንዓትና ያላቸውን ፍቅር ሥራቸው ይመሰክራል ፤ ለዚሁም አንዳንዱን ባስታውሳችሁ ፈቃዳችሁ ስይሆን አይቀርም (መጀመሪያ) አገራችን ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምራ ምንም ነጻነቷን ጠብቃ ራሷን ችላ የኖረች ብትሆን ይህ አይበቃትም ብለው፤ የመንግሥታት ማኅበር የዓለሙን ደረጃ የሚያቀርብ፤ የሕዝብን ሕይወት የሚያድስ፤ የሚከክልነትን ሕግ በሥልጣኑ [illegible] ፤ የሕዝብንም ሕይሳት እንደ የማያደርግ ምህርትን ስለተረዱ በብዙ ኃይልና ጥበብ ኢትዮጵያ ከመንግሥታት ማኅበር እንድትገባ አደረጉ።

(ሁለተኛ) ግርማዊ ንጉሣችን ለሚወዷት አገራቸው የሚገባትን ሥራ ለመሥራት ከገራቸውና ከሕዝባቸው ከቤተ ዘመ

ዶቻቸውም ተለይተው ምን ይመጣልን ሳይጠረጥሩ ከገር መለየትንና ድካምን ሳይፈሩ ባሕረ ውቅያኖስን ተሻግረው ከዓለም ነገሥታት ተዋውቀው ቃል በቃል ተነጋግረው ተመለሱ።

(ሁኖ የማይታወቅ) በባሕር መርከብና በምድር ባቡር በየቤተ መንግሥቱና በየሆቴሉ ላይ በሶስት ቀለማት ያጌጠች ባንዲራችን ተሰቅላ ነፋስ ሲያውለበልባት ያዩ የየሮጳና የእስያ ሕዝቦች እስካሁን ከመገረማቸው አላቋረጡም።

እንግዴህ በግርማዊ ትጋትና መሪነት ኢትዮጵያ ወደ ዋነኛው ደረጃ ለመድረስ እግሮቿ እንዲፋጠኑ ያለጥርጥር ነው። አስቀድሜ ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ጥልቅ የሆነ ምስጋናዬን ካቀረብሁ በኋላ፤ ስለ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንንና ስለ ተወደዱ ሚስታቸው ስለ ልዕልት ወይዘሮ መነን ስለ ቤተ ሰዋቸው ሁሉ ጤና ፤ ስለ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብና አርበኞች ጤና ፤ በዛሬውም ክብረ በዓላችን ስለ ተሰበሰባችሁ ስለ ኢትዮጵያ መንግሥት ሹማምንቶችና ሠራተኞች ጤና ደግሞ ስለ የውጪ አገር መንግሥት ወኪሎችና ነጋዴዎች ስለ የምድር ባቡር ኩባንያ ሹማምቶችና ሠራተኞች ሁሉ ጤና ጽዋዬን አነሣለሁ። ብለው በተናገሩ ጊዜ ጭብጨባው ቀለጠ።

ደግሞ በኋላ ይኸንኑ ቃል በፈረንሳዊ ቋንቋ አቶ ወልደ ብርሃን የማዘጋጃ ቤት ዋና ጸሐፊ አነበቡና ፈረንጆቹ በደስታ አጨበጨቡ ።

ደግሞ ቀጥለው ሙሴ ደማዜሬየ የፈረንሳዊ ቆንሲል ተናገሩና ሰውን ደስ አሰኙት ።

ቀጥለውም የእንግሊዝና የግሪክ ቆንሲሎች በየቋንቋቸው የምረቃ ቃል ተናገሩ ። በዚያች በጠባብ ከተማ የተደረገውን በዓላና የደስታ ብዛት እንዴት አድረገን ልንናገረው እንችላለን። ንጉሥ በሕይወት ይኑሩ ። ኢትዮጵያ ዘለዓለም ትኑር ።

የብርሃንና ሰላም ተላላኪ።

የድሬ ዳዋ ታላቅ ደስታና ዕልልታ።

በፍጡር ሁሉ ዘንድ የተወደደ ግርማዊ ንጉሥ እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ ፈጥሮ እነቺ ጠባቂሽን ብሎ ቡሩክ የተቀደሰ የግርማዊ ንጉሥ ዘውድ ከሙሉ ረድኤቱ ጋራ ጨምሮ ቅብዐ ንግሥን ለተፈሪ መኰንን ቀብቶ ሲሰጥ ኢትዮጵያ ስለ ደስታዋና ዕልልታዋ ከተቀመጠችበት መሠረቷ ተረፍ ብላ ለመስፋፋት ትቃጣለች።

ልዑል በከበረ ልዕልናዎ ላይ ዘውድ የሚጭኑበት የክብር ቀን በጽጌ መስከረም እሁድ ለት ነው ተብሎ ይህ የምስራች በኢትዮጵያ ጎሳና ፊት ባሉ አገሮችና በኢትዮጵያም በዙሪያዋ ሁሉ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ከሰሜን እስከ ደቡብ በቅጽበት ማለዳ ተሰማ ግን አስቀድሞ እንዲያው ወሬው ሲተላለፍ የሚሰማ ሁሉ የንጉሥነት ዘውድ በልዕልናዎ እስከ እሚደረግልዎ ቀን ድረስ ፍጻሜውን ለመስማት ሁሉ ለጆሮው ደስ ሲለው ቆይቶ ነበረ ይናፍቅም ይቸኩልም ነበረ ። በድሬ ዳዋም ትንሹዋ ማዘጋጃ ቤት በብዙ ባንዲራዎች ተሸልማ ከውስጥ ለመግባት ውጭዋንና ዙሪያዋን ለማየት ደስ የሚያሰኝ ሆና በያይነቱ ልብስ የለበሰ ሰው ተቀላቅሎ በበረንዳው ሲተላለፍና ሲጋፋ በየመልኩ ልዩነት የባንዴራ ጌጥ መስሎ ይታይ ነበር ፤ አንድ ጊዜ የተከፈተውን ዓይን ሁሉ እንደ ብርቅ በማስተዋል የምታነሆልል ሆና ግርማና ደስታም ተሰጥቷት ነበር። ቦታዋ እንዲሁ በመድመቋ ያዲሱ ንጉሥ ግርማና ዋናው መንበር ከዚህ ብቻ ያለ መሰለ ዲሬክተሩ አቶ አስታጥቄም የመስከረምን ዕፀዋት መስለው ለምልመው በድሬ ዳዋም የሚኖሩ የውጭ አገር ቆንስሎችና ነጋዴዎች የከተማውንም ሹማምንቶችና ሠራተኞች ሁሉ ይዘው የንግሡ ሥርዓት በሚፈጸምበት ባራት ሰዓት ማዘጋጃ ቤት ሲገቡ ትልልቆቹ የጀርመን መድፎች ከስር እስከ መቶ አንድ ድረስ በተተኰሱ ጊዜ በዙሪያው ያለ ጋራ ሁሉ ደስ በሚያሰኝ በትልቅ ድምጽ እንደ ፒያኖ ዜማ ያጉረመርም ነበር። ወትሮ መከራ ፊታቸውን ያስከፋቸው ሰዎች አንዳንድ የምናያቸው የነበሩ ሁሉ ዛሬ ደስ ይበለን የሚል መንፈስ ልባቸውን መልቶት ዋለ ። በኢትዮጵያና ባውራጃዋ ያሉ ከተሞች ሁሉ ስለዚህ ስለትልቁ በዓል ያደረጉትን ዕልልታና ደስታ እየዞሩ ለመጎብኘት የሚያስመኝ ነበር ። ግን የልብ ሐሳብ በቅጽበት እሩቅ ደርሶ ቢመለስ እግርና ዓይን ይህንአያዳርሱትምና ከንቱ ነው።

ፍትሕን በውነት የሚጠብቅ በሕዝብም ላይ ግዛትን የማያጠብቅ መልካም ንጉሥ በኃይል ተቀጥቅጠው ግዛት ጠብቆባቸው በሚኖሩ በሌላው ነገድ ዘንድ ነገሮቱ ይናፈቃል ዙፋኑንም ነገሥታት ሁሉ ያከብሩታል።እንዲሁም ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ለኢትዮጵያ ነገድ በመልካም አገዛዝ እንዲያሳድሩት ዓመፃንም ከመካከል እንዲያበርሩት አይጠረጠርምና ሥርዓትዎና መንግሥትዎ በሁሉ ነገድ መንግሥታት ዘንድ የተወደደ የከበረም ነው። ብዙ ቀን ስለጤንነቱ በሕክምና ቆይቶ ከሕመሙ ቀና ያለ ገመምተኛ የውጭው አየርና ነፋስ ብርቅ እንዲመስለው እንዲሁም ኢትዮጵያ ብዙ ዘመን አንድ ጊዜቀና አንድ ጊዜ ዘምበል ስትል ስለ ጤንነቷ ሁከት ነበራት። ሁከቷ ለሕዝቧ ጥቂት በጥቂት ሳይገለጽም አልቀረም ። ግን ዛሬ በግርማዊት ንግሥትና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ሕክምና ጤንነቷ በጎ ስለሆነ እየደገፈ የጤና ነፋስና የደመቀ ብርሃን የሚያሳያትን ታላቁን ገዢዋን ስላገኘች ይህን እንደ ብርቅ የሚታይ ግርማዊ ንጉሥ ኢትዮጵያና ሕዝቧ ትምክሕት ያደርጉበታል።

ይህ አዲስ ብርቅ የሆነ ደስታ ሁልጊዜ ለኢትዮጵያ አዲስ ደስታ መስሎ ይታሰባል እንጂ የሚረሳ አይደለም። ሕዝብ ሆይ ይህ ታላቁ የልባችሁ ደስታ ሁልጊዜ በልባችሁ አዲስ ሆኖ ይኑር ።

ጀማ ወልደ ገብሬል

የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የዘውድ በዓል በዓስበ ተፈሪ

፲፱፻፳፩ ዓመተ ምሕረት መስከረም ፳፯ ቀን ስለ ልዑል ንጉሥነት በዓስበ ተፈሪ የተደረገው ቀጥሎ የተጻፈው ነው። የእግዚአብሔር አብ ቤተክርስቲያን አለቃ መምሕር ማፈኛ ከ ማታው ባ፩ ሰዓት አስደውለው ካህናቱም ተሰብስበው ማኅሌት ቁመው አደሩ ይልቁንም አክሊለ ጽጌ ማርያም ለኃይለ ሥላሴ ቀጽላ መንግሥቱ እያሉ ሲያሸበሽቡ አድረው ሲነጋ ዲያቆኑ እስመ በጸሕከ በበረከት ሠናይ ። ወአንበርከ አክሊለ ዲበ ርእሱ ዘእምዕንቍ ክቡር ሕይወ ሰአለከ ወሀብኮ። ብ

ሎ ሰበከኩ ኢትኰንኑ ከመ ኢትትኴነኑ እስመ በኵነኔ ዘከኰነንክሙ የሚለው ወንጌል ተነቦ አንገርጋሪ ርእዩ ዘከመ አፍቀርና እግዚእነ ንጉሡ በጽድቅ ወለብሱ ድርአ ጽድቅ የሚለው ተመልጥኖ ሥራተ ቅዳሴ ገብተው ቄሱም ቅዳሴ እግዚእን ቀድሰው ከወጡ በኋላ ያውራዱው ዲረክተር አቶ ተሻ ወርቅ የተቀኙት።

ክብር ይእቲ

እፎኑ ጸበብ ከርሠ አይሁድ እንዘ ጉቡእን ኵሉ ።
ሥጋ ፩በግዕ እስመ በሊዐ ኢክህሉ ።
ቤተ ኃጥአንኒ ሰነሂሆሙ አቀሙሱ።
አኮኑ ፈተዉ ከመ ይብልዑ እምድኅረ ሥጋ ሰቀሉ ።

ዕጣን ሞገር ።

ደናግለ ግብፅ ወዕርዕ አለ ይብልዎን ማርያ ።
ኵሎን ኢኮና እመ ኬንያ ።
በተጸውዖ ስም እምጣን አኮ ወበአሠንዮ አርአያ ።
አኮኑ ኢትዮጵያ ።
ወራስያኒሃ ዘአኮ ወራስያነ ሰሚያ ።
እምኵሎሙ ወራስያኒሃ ለዋሕድ ነያ።
ለዕለተ ሰንበት ዕድሜከ ኃይለ ሥላሴ ዘወልደ እምላከ
ሕዕበያ ።
ምኒልከ አብ ፋዲሙ ዕረፍተ ኃጥአን ረሰያ ።
እስከለ ማርያም እስክንድርያ
እስከነ ሰሚዓ ትነግር ለሮምያ
ወእምሮሚ ይደምፅ እስያ ። ።ብለው ተቀኙ ።

የጩርጩር አውራጃ ገዢ ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያትም አስቀደሰው ሲወጡ መኳንንቱና ወታደሩ የጦር ልብሱን ለብሶ ተሰልፎ አጅቦ ወደ ቤተ መንግሥቱ ሲሄዱ ለተመለከተው ሰው የመስከረምን አበባ መስሎ ታየ።ፊታውራሪም አዲስ በተሠራው ግምጃ ቤት ስለ ፈንጠዝያው እጅግ አምሮ ተዘጋጅቶ ነበርና ገብተው በዩት ጊዜ ልባቸው በደስታ ባሕር ተሰጥሞ ተቀመጡ።በዚያውም ውስጥ የተነጠፈው ስጋጃ የጽጌ ረዳ አበባ መስሎ ሲታይ እጅግ ያስደንቅ ነበረ ። በ፭ሰዓት ግብር ገባ መኳንንቱና ካህናቱ ሕዝቡና ሠራዊቱ በእየ ማዕረጉ ተቀምጦ ግብር ሲበላ ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት የልዑልን ንጉሥነት ላልሰማው ሕዝብና ሠራዊት እንደ አዋጅ ቃል አድርገው አስምተው የኢትዮጵያን መንግሥት እንደ ፀሐይ ያብራት እንደ ጨረቃ ያድምቃት ጥንከሬዋንም የብረት ምሰሶ ያድርጋት ።

ለንግሥነት ዘውዲቱም ረጅም ዕድሜ ይስጥልን ብለው በመረቁ ጊዜ ከዳር እስከ ዳር ፫ጊዜ ተጨብጭቦ ሽባኝ ተጠጣ በ፯ሰዓት ግብር ምላሽ ሆነ በ፰ሰዓት ፈረንጆችና እስላሞች ዓረቦችና ባንያኖች በሙዚቃ ዜማ እየዘፈኑ ወደተዘጋጀላቸው ፈንጠዝያ ገብተው በልተው ጠጥተው እንደ ደንባቸው መርቀው በ፲፩ ሰዓት በእየቤታቸው ተመለሱ። ይኸንን ያሳየንና ያሰማን አምላክ ይክበር ይመስገን። ጌታችንማ ለሀገራቸው ለኢትዮጵያ ልጆች እውቀትና ጥበብ እንዲገባቸው እራሳቸውን እንዲችሉ የእውቀት ጐዳና አውጥተው በየዓይነቱ የተማሪ ቤት አቁመው የኢትዮጵያ ሕዝብና ሠራዊት እንዲሰለጥን ወደ እውቀት ደረጃ እንዲደርስ መትጋታቸውን ተረድተነዋል ።

ፀና መንግሥቱ እየሰፋና እየበረታ ይሂድ ለጌታችንም ያብታቸው የአብርሃምን ዕድሜ ይስጥልን ።

ተፈራ ዳምጠው

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ በነገሡበት ቀን የኢትዮጵያ ። ቆንሰላ በአስመራ ያደረገው በዓል ።

በመስከረም ፳፫ቀን ፲፱፻፳፩ ዓመተ ምሕረት ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን እንደሚነግሡ ኮቲዲያኖ በተባለ በአስመራ ጋዜጣ ተጽፎ ነበርና የኤርትራ ሕዝብ ከመስከረም ፲፰ቀን ጀምሮ ሰምቶት ነበር ። ስለዚህ በኤርትራ ያሉት የኢትዮጵያ ዜጎችና የኤርትራም ሰዎች ወደ ኢትዮጵያ ቆንስላ እየመጡ ምረቃቸውን ለግርማዊ ንጉሥ እንዲያደርስላቸው የትዮጵያን መንግሥት ቆንስላ ጸሐፊ ለመኑት ።

የኢትዮጵያ ቆንስላ በመከረም ፳፫ቀን ትልቅ በዓል አድርጎ እንዲውል የኢትዮጵያ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስተር ዋና ዲሬክተር ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ትእዛዝ አሳልፈውለት ነበርና ግርማዊ ንጉሥ በነገሡበት ቀን ታላቅ በዓል አድርጎ ዋለ ።

በባንዲራና በልዩ ልዩ ጌጠኛ ወረቀት ያጌጡ ሁለት ዳሶች በቆንስላው ግቢ ተሰርተው ነበር ከእነዚህም ዳሶች አንደኛው ለአውሮፓ ሰዎች ሁለተኛው በአስመራ ለሚኖሩ ለኢትዮጵያ ዜጎችና ለአስመራ ሰዎች መቀበያ እንዲሆኑ የተዘጋጁ ነበሩ የኢትዮጵያ ቆንስላ በዓሉን ለአስመራ ካህናት ስላስታወቀ የኤርትራ መንግሥትም በዓሉን እንዲያከብሩ አዟቸው ነበርና ለሊቱን ሁሉ « እግዚኦ ኅንኬ ሀበ ለንጉሥ እያሉ ሲያመረግዱ ለንጉሥ የሚገባውንም አደራረስ ሁሉ ሲያደርሱ አድረው ሲነጋ አመልጥነው ሲጨርሱ ወደ ኢትዮጵያ መንግሥት ቆንስላ ቤት በ፭ ሰዓት መጡ ከእነርሱም ቀጥሎ ሕዝቡ ገባ ካህናቱም ተጋብዘው ከጨረሱ በኋላ ከበሮቻቸውን ይዘው ኵላ ምድር ትስግድ ወትገኒ ለከ በልዎ ለኃይለ ሥላሴ ግሩም ግብርከ እያሉ ሲያስረግጡ አምረው ይታዩ ነበር ማስረገጣቸውም የደመቀና የሚያምር ስለሆነ የኢትዮጵያ መንግሥት ቆንስላ ጸሐፊ እጅግ ደስ የሚያሰኝ ቃል ተናገረ ።

ካህናቱም የቆንስላው ጸሐፊ የተናገረውን እጅግ ደስ የሚያሰኝ ቃል በሰሙ ጊዜ እንደገና ኵላ ምድር ትሰግድ ወትገኒ ለከ በልዎ ለኃይለ ሥላሴ ግሩም ግብርከ እያሉ አስረግጠው ከጨረሱ በኋላ የካህናቱ አለቃ እጅግ ደስ የሚያሰኝ ቃል ተናግረው መርቀው አቡነ ዘበሰማያት አድርሰው ወደ ቤታቸው ተመልሰው ሄዱ ።

ከዚህ በኋላ የአውሮፓ ሰዎች መግባት ጀመሩ በኤርትራ መንግሥት ጽሕፈት ቤት ጸሐፊ የሆኑ ካበሌር ስጊኖዛ አስቀድመው መጥተው የኢትዮጵያ ቆንስላ ጸሐፊ የማያውቃቸውን እንግዶች እያቀረቡ ያስተዋውቁ ነበር መኳንንቱ ሁሉ በወርቅ የተንቆጠቆጠ የኦፊሲዬል ልብሳቸውን ለብሰው ስለመጡ ለዓይን እንደፀሐይ ያንጸበርቁ ነበር ።

በአስመራም የሚኖሩ ታላላቅ መኳንንቶችና ወይዘዝሮች ሁሉ ወደ ኢትዮጵያ ቆንስላ ቤት መጥተው ነበር ። የኤርትራ መንግሥት እንደራሴ ከሚስታቸውና ከልጆቻቸው ጋራ ሁነው የቀሺለት ፌዴራል ጸሐፊ ካበሌር ኮርቲዝ ያፌር ሲቢል ዲሬክተር ኮማንዳቶር ክሮሲሊ ፣ ያገረ ገዠ ጽሕፈት

ቤት እንደራሴ፣ ከባሴር ዳሎርሚ ተከትለዋቸው ባኀጠ ኦቶሞቢል ተቀምጠው በመንግሥት ፈረሰኞች ታጅበው ልክ በ፲፩ ሰዓት ወደቆንስላው ቤት ደረሱ ። በዚያን ጊዜ ሙዚቀኛና እምቢልታው እጅግ ደመቀ። የኢትዮጵያ ቆንስላ ጸሐፊና ከባሴር ሰፔናዛኖ ከበሩ ላይ ሆነው ይጠብቁ ነበርና የኤርትራ መንግሥት እንደራሴ እንደመጡ የቆንስላው ጸሐፊ ተቀብሎ ወደተዘጋጀላቸው ሥፍራ ወሰዳቸው። ከዚህ በኋላ የኤርትራ መንግሥት እንደራሴ ክቡር ኮማንዳቶር ሙቲኔሊ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናገሩ ።

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና እንደራሴ ተፈሪ መኰንን በነገሡበት ቀን በዓል ለማድረግ ዛሬ በተደረገው ግብዣ ከኤርትሪያ መኳንንት ጋር አብሬ መምጣቴ ደስታዬ እጅግ የተለየ ስለሆነ ነው።የኢትዮጵያ መንግሥት እንደራሴ ከፍ ባለው በመንግሥት መዓርግ ስለ ተቀመጡ ኢጣልያኖች ሁሉ እጅግ ደስ ብሏቸዋል።ይህ በመንግሥቱ መዓርግ መቀመጫቸው በኢትዮጵያ ሕዝብ የሠሩትን ደግነት ብቻ ያይደለ በዓለም ሕዝብ ሁሉ የሠሩትን የሰላም ፖሊቲከና ትክክለኛ አስተዳደር የሥልጣኔ ሥራ ያሳያል።ይህነኑ ሥራቸውም በሁኑ ጊዜያችን ካሉት በጣም ከላቁትና እውቀተኞች ከሆኑት ነገሥታት አስቆጠራቸው ። ለኛ ለኢጣልያኖችም የተለየ ደስታ የሆነልን ኢጣልያ እውነተኛና ትልቅ ወዳጅ ስላገኘች ነው ። መጀመርያ ዱክ ዴዛብሩስ አዲስ አበባን በመጐብኘታቸው ሁለተኛም የፍቅር መስማማት በማድረጋችን በመሃከላችን ያለው መስማማት እርግጠኛ ሁኑዋል ዘሬም አገረ ገዢያችን በኦፌሲየል አካሄድ ወደ አዲስ አበባ መሄዳቸው አብልጦ ያስረግጠዋል።ስለዚህም የልብ የፍቅር ሰላም ብቻ ያይደለ የፖሊቲካና የኤኮኖሚ መስማማት በመሃከላችን ጸንቶ እንዲኖር ለማስረገጥ እንችላለን።ባዲስ አበባ ቤተ መንግሥት ክቡር ዞሊእና የኢጣልያ ሚኒስቴር ላዲሱ ለትልቁ ንጉሥ ምሪቃቸውን ሲያቀርቡ እኔም እዚሁ ሁኘ በርስዎ በዚሁ ቆንስላ ወኪል በኩል በስሜና በቀኝ አገሩ ስም ምሪቃየን ላቀርብ በጣም ደስ አለኝ።ብለው እንደጨረሱ የኢትዮጵያ ቆንስል ጸሐፊ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናገሩ ።

ክቡር የመንግሥት እንደራሴ ክቡራን ወይዛዝሮችና መኳንንቶች ሆይ በዚሁ ለኢትዮጵያ ትልቅ ጸጋ በተገለጸበት ቀን የኢትዮጵያ ቆንስላ በዓል ባደረገበት ጊዜ ክቡር የመንግሥቱ እንደራሴ መኳንንትም የማዕርግ ልብሳችሁን ለብሳችሁ መምጣታችሁ በኢጣልያና በኢትዮጵያ መከከል ያለውን የጠና የፍቅር ማሠሪያ የሚገልጥ ነውና በኢትዮጵያ መንግሥት ስም ምስጋናየን አቀርብላችኋለሁ።ካሁን ቀደም ኢትዮጵያ በብልሁ ግርማዊ ንጉሥ መኰንን አልጋ ወራሽነቱና እንደራሴነት እየተመራች ከፍ ወዳለ የሥልጣኔ ደረጃ በፍጥነት እንደተራመደች የሚያስረዳ ብዙ ሥራ ተሠርቷል ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ያገሬቸው ፍቅር በተለየ የሚሰማቸው ስለ ሆነ ለወደ ፊቱ ኢትዮጵያን ከፍጹም ሥልጣኔ ሊያደርሷት እርግጠኛ የሆነ ብርታትና እውቀት አላቸው። ስለዚህ በጣም የታደለችና የኰራች አገር ናት። ግርማዊ ንጉሥ ለሚወዱዋት አገራቸው ላሁኑም ለወደ ፊቱም የሚጠቅማትን ነገር ሁሉ ለይተው የሚያውቁ ስለ ሆኑ አሁን በቅርቡ ከኢጣልያ ጋር እውነተኛ የልብ ፍቅርና ወዳጅነት በሁለቱ አገር እንዲሰለጥን የመስማማት ውል ተዋዋሉ ። ኢጣልያ የኢትዮጵያ ነጻነትና ሥልጣኔ ልማትም የምትወድ አገር ናትና በዚሁ በኢትዮጵያ የፋሥሐ ዕለት በጣም ደስ እንዳለቱ በክቡር የመንግሥቱ እንደራሴ በክቡራን ወይዛዝሮችና መኳንንቶችም ፊት ተስሎ ይታያል ክቡር የመንግሥት እንደራሴ ሆይ ይህንኑ የርስዎና የቀኝ አገሩ የጠለቀ የልብ ምሪቃ ለትልቁ ግርማዊ ንጉሥ እንዳስታውቅ እርግጥ ይሁንዎ ብሎ የቆንስላው ጸሐፊ ዲስኩሩን እንደጨረሰ ሸምፓኙ ተዘጋጅቶ ነበርና የመንግሥቱ እንደራሴ ኮማንዳቶር ሙቲኔሊ የቆንስላውም ጸሐፊ ስለ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጤንነት ኢጣልያና ኢትዮጵያ ለዘላለም ይኑሩ ። ፍቅራቸውም ይጽና እያሉ ብርጭቆዋቸውን አነሡ ።

ግብዣውም ከተፈጸመ በኋላ እየተሰነባበቱ ተለያዩ ።

የቆንስላው አጥርም ጉልቀ በሌለው ሕዝብ ተከቦ እልልታው እየጐላ በዓሉ እጅግ ደምቆ ዋለ። የብርሃንና ሰላም ተላላኪ ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ስለ ነገሡ የተደረገ የደስታ ጨዋታ ።

ጥቅምት ፲፰ ቀን ክቡር ከንቲባ ነሲቡ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ስለ ነገሡ ትልቅ ደስታቸውን ለማሳየት የኢትዮጵያና የውጭ አገር ሚኒስትሮች ብዙ ወይዛዝሮችና መኳንንቶች አብረዋቸው በደስታ እየተጫወቱ እንዲያመሹ ጠርተው ነበርና ከማታው በሰስት ሰዓት የተጠራው ሰው ሁሉ በአቶሞቢል እየሆነ መጣ ። ክቡር ልጅ አስፋ ወሰን ተፈሪም መጥተው ነበር።በዚያ የነበሩ የኢትዮጵያ ሚኒስትሮችና መኳንንቶችም ከዚህ በታች የተጻፉት ናቸው ። ክቡር ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ ያገር ግዛት ሚኒስትር ። ክቡር በጅሮንድ ዘለቀ የገንዘብ ሚኒስትር ። ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዋና ዲሬክተር። ክቡር ደጃዝማች እምሩ የሐረርና ያውራጃዋ ሁሉ እንደራሴ። ክቡር ነጋድራስ መኰንን የንግድ ሚኒስትር።ክቡር ሊቀ መኳስ መንገሻ ። ክቡር ቀኛዝማች ተፈራ በለው ። ክቡር ቀኛዝማች አጽናፍ ሰገድ ሌሎችም ብዙ ነበሩ።ሰውም ሁሉ ተሰብስቦ ሳለ ሽምፓኝ ተከፈተና ወዲያው በሽምፓኙ ጊዜ ክቡር ከንቲባ ነሲቡ ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናገሩ ።

ክቡራን ሚኒስትሮችና
ወይዛዝሮች
ክቡራንም መኳንንቶች ሆይ

የደስታዬን ተካፋይ ለመሆን በዚህች ቀን በዚህ አዳራሽ ውስጥ ስለ ተሰበሰባችሁልኝና ጥሪዬንም ስላከበራችሁልኝ በልዩ ላመሰግናችሁ ይገባኛል

እንደዚሁም ይህ መሰብሰብ ከላንተም ጋራ ያለጥርጥር የወዳጅነትን ምልክት የሚሰጥ መሆኑን በፍጹም ልቤ እረዳዋለሁ

ይህነኑም ደጉን ንጉሣችንን ለመመረቅ የተሰበሰብንበትን የደስታ በዓል ምክንያት አድርጌ ለኢትዮጵያ ግርማዊት ንግ

ሥት ነገሥታት ዘውዲቱና ለኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ለንጉሣችን ለግርማዊ ተፈሪ መኰንን እረጅም ዕድሜና ጤና እንዲሰጥልን አጥብቄ እየተመኘሁ ስለ ንጉሣችን ክብር ብርጭቆዬን አነሳለሁ ። ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ብለው በጨረሱ ጊዜ ተጨበጨበ ።

ከንግግሩም በኋላ ትያኖ እየተመታ ጨዋታው ተጀመረና ዘፋኞቹ አንድ ሴት አንድ ወንድ እየሆኑ እንደ እንዝርት ሲሽከረከሩና ሲያሸበሽቡ ላይታው ደስ ያሰኝ ነበር ። እንደዚሁ እየተጠጣና እየተዘፈነ አመሸና እኩለ ሌሊት ሲሆን የቸኰለ የቸኰለው ሔደ ። የበረታ የበረታው ግን ሲጫወት አደረ ። ይልቁንም ሙሴ ጋሪቦዶስ ከፕያኖ ጋራ ባማረ ድምጽ ግሩም አድርገው በዘመሩ ጊዜ ሰዉን ሁሉ ደስ አሰኝተውት በጣም ተጨበጨበላቸው የጌጡም ማማርና የቤቱ መሰናዳት የድግሱም ብዛት የብርሃኑም መድመቅ እጅግ ደስ የሚያሰኝ ስለነበረ ሰው ሁሉ እጅግ አደነቀና አመሰገነ ።

የደስታ መግለጫ

፩ኛ፤ እኛ አረቦች ሁላችን ንጉሥ ተፈሪ ስለ ነገሡ ደስ ብሎናል ። ዓረቦችና ቱጃሮች ሌሎችም ሕዝቦች ሁሉ በዚሁ ደስ ብሏቸዋል ። ገንዘባቸውና ንግዳቸው ራሳቸውም ሳይበደሉ በደኅና ስለተጠበቀላቸው ይኸም ሁሉ በንጉሥ ተፈሪ ፍርድ ጥንቃቄ ነው ። እነሆ በሐረር ክርስቲያንና እስላሞች ባንድ ሀገር በመወለድና በፍቅር ወንድማማቾች እንደሆኑ ይታያል ።እንደዚሁም ሁሉ የሐረር ሰዎች እሹራ ስለበዛባቸው አቤት ቢሉ አቀለሉላቸው ። ከበሬታም አደረጉላቸው ። ስለዚህ እነሱም ፍርድ የመጠንቀቃቸውን ውለታ ሊመልሱላቸው ይገባል።

፪ኛ፤ ንጉሥ ተፈሪ የኢትዮጵያ ስም ከታላላቆች መንግሥታት እስኪቆጠር ድረስ ከፍ ከፍ አረጓት ። መጀመሪያ በኢትዮጵያና በኢጣልያ መካከል የመስማማት ፍቅር አድርገዋልና ። ይኸውም እጅግ መልካም ነው ። ጉረቤት ስለሆኑ ሁለተኛ ጦርነት ለማስቀረት ከፈረሙ ካርበ መንግሥታት ጋራ ማኅበር ስለገቡ ። ሶስተኛ ከምስርና ከአውሮጳ መምህራን አምጥተው የተማሪ ቤት ስለከፈቱ መንገድም ለማሠራት ስላዘዙ እንደዚሁም ታላላቅ ቤቶች በዘመናቸው ስለተሠሩ አዲስ አበባ በመጥዳትና በሥርዓት ፓሪስንና ሮማን እስክትመስል ድረስ ። አራተኛ አዲስ ከተማ አሰበ ተፈሪንና ረባሕ ቡርን ሌሎችንም ሁሉ ስለከፈቱ ደግሞ መንገደኞችን ከጉርፍ ለማዳን ዕቃም ሁሉ ካንዱ አገር ወዳንዱ አገር በቶሎ እንዲተላለፍ በታላላቆች ወንዞች ብዙ ድልድይ አሠርተዋል ። በዚሁም ሥራ ሁሉ የዓለም መንግሥታት ሰው ለማሠልጠን የሚነማማ ቻይ ንጉሥ ነው ብለው ያመሰግኑዋቸዋል ይኸንኑም በየጋዜጦቻቸው እናነባለን።

የከተማ ወሬ ።

ጥቅምት ፲፮ ቀን የአርመን ሊቀ ጳጳሳት ሞንሲኜር ኬዎርክ አዲስ አበባ ገቡና በአዲስ አበባ ያሉ አርመኖች ሁሉ ተሰብስበው በክብር ተቀበሏቸው።የመጡበትም ምክንያት አርመኖች ቤተ ክርስቲያን ያሠሩትና የመሠረቱን መጀመሪያ ድንጋይ ለማቆም ነው

ብርሃንና ሰላም ሞንሲኜር ኬዎርክን እንኳን ደኅና ገቡ ይላል ።

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ብለውሽ ኦቤርላንድ ኦቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።



አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባ ኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባተሪ ነው ክምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማኅደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል «ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው

ወዲያውም የኦቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

COGNAC S.&E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ኦሜጋ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩግቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

RUGBY

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በየይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፣ ቤንዚን በየይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪመኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽናባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ያሰናኟነት ፈቃድ የተቀበለ።

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በከፓሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በከፓሉ ላይ ፡ ለለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዊድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad



ዓለም ሱቅ ፲፪ዓይነት የተሰማ አሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንፎር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኲላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ፤በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያከማል

እደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ሱቅ ነው ።

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ቢሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንከራ ነው በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬድንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አራተኛ ዓመት ፡ ቁጥር ፵፭
4 me ANNÉE № 45

ሐሙስ ጥቅምት ፳፱ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም ።
JEUDI 8 NOVEMBRE 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen , profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix , a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ለፊስን በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie
Un an 5 Thalers
Etranger
Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

እውነተኛውን ያገር ፍቅር ለመሥራት የሚያሳስብ ።

የሰሎሞን መጽሐፈ ምሳሌን ሳነብ ለሁም ጊዜአለው ለመናገርም ለዝምታም ጊዜ አለው ከሚለው ላይ ስደርስ ይኸነን ለመጻፍ የሚያሳስበኝ ሐሳብበሕሊናየ ስለተሰማኝ ብእሬን አነሣሁ

ኢትዮጵያ ከሚመጣብሽ ክፉ ነገር ሁሉ እግዚአብሔር ጠብቆሽ ስለሆነ ግን ዘወትር ያለማወቅን ገንዘብ አድርገን መያዝ ገንዘባችን አይሁን ።

በዛሬ ጊዜ ኢትዮጵያን የሚያስፈልጋት የሥልጣኔ ትምህርት መሆኑን ከልጆቿም ከውጭም ሰው ከወዳጆቿ ቢሆን ያልተናገረና ያልመከረ የለም ያውም ኢትዮጵያን የሥልጣኔ ትምህርት ማግኘት እንደ ጃፓን በፍጥነት ያስፈልጋታል ይኸነኑም አውቆ መንግሥታችን ልጆች እንዲማሩ አዋጅ አውጅዋል ይኸነኑም አዋጅ ለመፈጸም መንግሥታችን የሥልጣኔ ትምህርት ቤት በአያሌው እንዲያቆም ሙሉ ተስፋ አለን ።

በኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም የትምህርት ቤት የመንፈሳዊ፤ የሃይማኖት ትምህርት ቤት ብቻ ነው ያለው እንጂ የዓለም ጥበብ የትምህርት ቤት አልነበረም በቅርቡ ግን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ በአዲስ አበባና በሐረር ፪ የትምህርት ቤት አቁመዋል ደግሞም ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ፩የትምህርት ቤት በአዲስ አበባ አቁመዋል እነዚሁም በቅርብ ቀን (ኮሌጅ) ሐይእስኩል እንዲሆኑልን ተስፋ አለን ።

የሰው ልጅ በዓለም ላይ እውቀትና ጥበብ መማር ያስፈልገዋል ይኸ ካልሆነ ግን የመንፈሳዊ ትምህርት ብቻ ተምሮ ቢቀር ለሥጋ ማደርያ ሲቸገረው ሲሰርቅ፤ሲቀማ፤ሲገድል፥ሲሟገት፤ ሲሸፍጥ፤ያኙ የተማረውን የመንፈሳዊ ትምህርት ሲያፈርስ፤ ይገኛልና ስለዚህ በግድ የሥልጣኔ ትምህርት ቤት ማስፋት ያስፈልገናል። የኢትዮጵያ መንግሥት በቀድሞ ጊዜ በታሪክእንደምንሰማው ብልህና ብርቱ መንግሥት ነበረ እንምስርን ደግሞም በዚህ በአሰብ በኩል አዱሊስ የሚባል በር ነበራቸውና በዚያ በመርከብ ተሻግረው የዓረብን አገር የመንን ሁሉ ሲገዙ ነበረ። ይኸ ይኸ የቀድሞ አባቶች ወሬ ብርታታቸውና እውቀታቸው እስከ ወሬውም ተረስቷል በውጭ አገር ታሪክ እንሰማለን እንጂ ።

አሁንም ደግሞ ከዋናው ከሥልጣኔ ትምህርት በፊት አስቀድሞ የብልጠትና የጌጥ መውደድ፥የገንዘብ አለልክ መውደድ፥ትምህርት እጃቸውን ዘርግተውብናልና ከነዚህ ኃይለኞች እጅ የሚያድነን የሥልጣኔን ትምህርት በትጋት ማስፋት ብቻ ነው። በቀረ እንኳን እኛን ትልቁን የሮምን መንግሥት ሌላም ብዙ መንግሥታት ያጠፋ ይኸ ነገር ነው። ምቅኝነትም የሚበዛ እነዚህን በመከተል ነው። ለአገር ነጻነት ማሰብ የሚቀር፥ለራስ ብቻ ማሰብ የሚመጣ፥በነዚህ ነው ከነዚህ ቀጥሎ የሚመጣውንና የሚሆነውን ግን ሁሉም ያውቀዋል ።

የሥልጣኔ ትምህርት ብለን ሁልጊዜ መወትወታችን ያለሱ እንዳንረብ ብንረዳው ነው። አሁን ለምሳሌ ብረት ሁሉ ብረት ነው፥ ከብረትም ደጅኖ ትልቅ ነው። ግን ሥጋ እንቁረጥበት ቢሉ አይችልም ጥፍር ስንኳ አይቆርጥም ብቻ ድንጋይ ይፈልጣል ሰንጢ ግን ምንም ትንሽ ብትሆን ይኸን ሁሉ ትሠራለች

መሥራቷም በብረትነት ከድጅኖ በልጣ አይደለም በሞረዷና በመሳሏ ነው ። ሰውንም እንደዚሁ የሥልጣኔ ትምህርቱ ይስለዋልና ስለዚህ ነው የሥልጣኔ ትምህርት የሚፈለገው፥ጃፓንን እያመላለስን ምሳሌ አድርገን መጻፋችን ከዓለም ሁሉ የሥልጣኔ ትምህርት የበዛበት አገር ጃፓን ቢሆን አይደለም ።ነገር ግን የጃፓን መንግሥት ከጥቂት ዓመታት በፊት እንደኛ ነበረ። የሥልጣኔ ትምህርት በገሩ እንዲገባ ተግቶ ከጀመረ ከ፶ና፯ዓመት አይበልጥም እነሆ ዛሬ መድፍ መትረየስ ባቡር መርከብ ሌላም ትልልቅ ፋብሪካና ትንንሽም ሥራ ሁሉ ልክ በኤውሮፓና በ-

አሜሪካ እንደሚሠራው ይሠራል ስለዚህ እኛም የኢትዮጵያ ሰዎች ለምትጠፋው ለምታልፈው ንብረታችንና ክብረታችን ብቻ ማሰብን ትተን እስከ ኅልፈተ ዓለም ልትኖር ለሚገባት ለአገራችን ነጻነት በትጋት ብናስብ በጥቂት ቀን ልክ እንደነጃፓን እንሆናለን የጃፓን ሥልጣኔና ብርታት በተማሪ ቤት ብዛት መሆኑን ከዚህ ቀጥሎ ያለው የትምህርት ቤት ቁጥር ያስረዳናል ፵፫ሺ፰፻፷፫ የትምህርት ቤትና ፲፰ ዩኒበርስቲ አለ በነዚህ ውስጥ የሚማሩ ልጆች ወንዶች ፭ሚሊዮንና ፰፻፹፬ሺ ፱፻፷፯ ናቸው ልጃገረዶች ደግሞ ፬ ሚሊዮንና ፭፻፺፬ሺ ፬፻፷፯ ናቸው ።

በድምሩ ተማሪዎች ፲ሚሊዮን ፬፻፸፱ሺ ፬፻፴፬ ልጆች ናቸው።

አሁን በጃፓን ፵፫ሺ የትምህርት ቤት መኖሩን ስንሰማ በትምህርት ቤቱ ቁጥር ልክ ፵፫ሺ ተማሪዎች ልጆት ማጣታችን ምን ያህል የሚያሳዝን ይመስለናል ሌላ ቀርቶ የጋዜታ ማተሚያ ቤቶች ፫ሺ ፫፻ ፴፪ ናቸው።ደግሞም የትልቁ የብርቱው የጃፓን መንግሥት ይቆይ አልጀርያ የሚባል የፈረንሳይ ግዛት የሆነ አገር በምስር በኩል አለ ያገሩም ሕዝብ ፮ሚሊዮን ይሆናሉ በዚያ አገር ስንኳ ከባላገሮቹ የሃይማኖታቸው ተማሪ ቤት ሌላ የሥልጣኔ ትምህርት ቤቶች ፬ሺ ፫፻ የተማሪ ቤቶች አሉ። ደግሞም ከነዚህ ሌላ ትልቁ የትምህርት ቤት ፭ዩኒበርስቲ አለ ከዚያም ውስጥ መሐንዲስነት ሐኪምነት ይኸነንም የመሰሉ ትልልቆች ትምህርት የሚማሩ አንድ ሺ፫፻ልጆች ናቸው ከዚያ ውስጥም ፩፻ ትልልቆች መምህራኖች(ፕሮፌሶሮች)አሉበት ።

ደግሞ የአልጄሪያ ይቆይ ከሱ አጠገብ ቱኒስ የሚባል ሕዝቡ ፪ሚሊዮን የማይሞላ አገር የፈረንሳይ ግዛት አለ በዚያ አገር ስንኳ ፬፻፫ የኤውሮፓ የሥልጣኔ ትምህርት ቤት አለ እንግዲህ ኤውሮፓዎች(ለኰሎንያን)ለቅኝ አገራቸው ይኸን ያህል ለምህርት ቤት ሲደክሙ ገንዘባቸውን ሲያጠፉ እኛ ለተወለድንበት አገራችን ለለምለሚቱ ኢትዮጵያ ምን ያህል መድከምና ገንዘብ ማውጣት ይገባን ይሆን ።

ይኸም ስለተባለ ደግሞ ሕዝቡ ትምህርት ከማጣት የተነሣ ደሃ ነው ከአገሩ ድህነት የተነሣ ደግሞ ብዙ የትምህርት ቤት ለማቆም ለመንግሥት ገንዘብ ችግር ነው ይኸ ነገር እንደ ሰንሰለት የተሣሠረ መሆኑ በጉልህ ይታያል ።

እንግዴህ ይኸን ነገር እንደ ሐኪም ሥራ ማድረግ ያስፈልገናል ። በሽተኛ በጣም የደከመ መሆኑ የታወቀ ነው ። ሐኪም ግን በሽተኛው እንዲድን ለማድረግ የግድ ሌላ ድካም ሊጨምርበት ያስፈልገዋልና መድኃኒት አድካሚና መራራ መሆኑን ኢያወቀ ያጠጣዋል ወይም ቁስል የሚያደክም መሆኑ እየታወቀ ይቀደዋል ይኸ የግድ ቢሆንበት ነው ።

ስለዚህ አሁንም የኢትዮጵያ ሕዝብ በብዙ ደሃና የተጐዳ መሆኑን ኢያወቅን መንግሥት ለትምህርት ቤት ጉዳይ ትንሽ የገንዘብ ጥሎሽ እንዲጨምርበት በትልቅ ኃዘን እንናገራለን ይኸን ማለቴም ሕዝቡ ያለዚህ መታከሚያና መዳኛ እንዳያገኝ እርግጥ ስላወቅሁ ነው።ይኸን ከሕዝብ የሚፈለገውንም ከዚህ እስከትዬ ጽፌዋለሁ ወይ መ ስ ወ በ፳ኛ ዓመት በ፲፱፻ኛ ቁጥር እንደ ጻፈው ቃል ብናወጣ ወይም ደግሞ ጢሰኛ በቤት ጢስ ቁጥር አላድ አላድ ባለመሬት ደግሞ በጋሻ በለም ፪፻ብር በጠፍ ፩፩ ብር በያመቱ ብናወጣ ጉዳቱም ትንሽ ነው ፤ ደግሞ በእንድ የሻለቃ አገር ፵ሺ ፳ሺ ጢሰኛ ፭ሺ ፲ሺ ጋሻ መሬት ሳይኖር አይቀርም በትልልቁ የሻለቃ ፳ሺ በትንሹ የሻለቃ ፲ሺህ ጋሻ መሬት ሳይኖር አይቀርም በትልልቁ የሻለቃ ፳ሺህ በትንንሹ የሻለቃ ፲ሺህ ብር ሳይገኝ አይቀርም ይኸም ገንዘብ በዓመት በመት እስከ ጥቂት ዘመናት ድረስ ይወጣል ። በዚህም በወጣው ገንዘብ በያገሩ በዚያው ባወጣው አገር በሻለቃው ከተማ አጠገብ ልጅ በመሸታና በሌላም ነገር ባሕርዩ እንዳይበላሽ ከከተማ ትንሽ ራቅ አድርጎ የትምህርት ቤት ይቆማል ይኸም ፲ና ፳ሺህ ብር ከ፩ሻለቃ ግዛት የወጣ ገንዘብ ለመምህራኑ፥ለመጽሐፉ፥ ለወረቀት፥ ለቀለም፥በቂ ነው ፤ ምግብ ግን ትምህርቱ በያገሩ ስለ ሆነ ልጅ ካባቱ ከዘመዱ ቤት እየበላ ይማራል ይኸም የሚሆነው በኢትዮጵያ አውራጃ ሁሉ በሻለቃው ቁጥር ነው ከዚህም ቀጥሎ ከጉምሩክ ለትምህርት ቤት በሚወጣው ገንዘብና መንግሥትም ሌላ ገንዘብ ከንዳው ረድቶ በከተማው ጢስና ቦታም እንደ ባላገሩ ደንብ አስወጥቶ ዛሬ በአዲስ አበባ ያሉትን የትምህርት ቤቶችና ሌላም ፩ ፪ ጨምሮ አቁሞ እነዚህን ሐይ እስኩል እንዲሆኑ ማለት በነምስር እንዳሉት እንደነ ቢክቶርያ ኮሌጅ እንደነ ሊሴ ፍራንሴ ማድረግ በባላገር በየሻለቃው ከተማ በሚሠራው አነስተኛ የትምህርት ቤት ከተማሩት ልጆች ብልሆች ንቁዎች ልጆች በአስተማሪ እየተመረጡ ጥቂቶቹ ከሁሉም አውራጃ ወደ አዲስ አበባ ኢየመጡ ከፍተኛውን ትምህርት ይማራሉ ከነዚሁም ደግሞ ጥቂቶቹ የሚቻል ያህል በዩኒበርስቲ ወደ ኤውሮፓ ኢየሄዱ ቢማሩ በኢትዮጵያ አውራጃ በኢየጕሳቸው መብራትና አውታር ይሆናሉ የዚህ አካሄድ ይጠቅመናል ።

ይኸም ሥራ ሲቆም ለሁሉም ተማሪ ቤቶች የሚረዳ የሥልጣኔ ትምህርት የምንስቴር ቤት ቆሞ ለሥራው ሥልጥንና ኃላፊነት ያለው ሹም ተደርጎ አማካሪ ተቆጥሮለት አንድ ትልቅ እንደ ማኅበር ያለ ሥራ ተደርጎ አርጋንዜሽን ተበጅቶለት ነው ይኸን ማድረግ ዛሬ ለኢትዮጵያ ጊዜውም ነው ይገባታልም ይጠቅማታልም እንደዚህ ጥቂት ሰፋ አድርገን የትምህርት ቤትን ነገር ቶሎ ካልጀመርን የኢትዮጵያ ሕዝቦች የምንሠራው ሥራ ሁሉ መሠረቱ ብርቱ ያልሆነ ሥራ ይሆንብናል የሥልጣኔ ሥራ ሁሉ መሠረቱ ሥሩ የትምህርት ቤት ነው የቀረው አበባና ቅጠል ነው ለጊዜው ከጕረቤት በልመናና በውሰት ብናገኘው ስንኳ አይረባንም መሠረት የለውምና ።

ፊ ዴሬሳ ።

ስለ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ንግሥ።
በይሉባቦር የተደረገ ደስታ ።

መዠመሪያ ክቡር ራስ ናደው መስከረም ፳፯ቀን ከጧቱ ባ፩ ሰዓት መኳንንቱም ሠራዊቱም የሰልፍ ልብስ እየለበሰ እንዲመጣ፤ካህናቱም የማዕርግ ልብሳቸውን ለብሰው እንዲመጡ ትእዛዝ አደረጉና ወዲያው እንደትእዛዙ ሁሉም ያማረ የሰልፍ ልብሱን እየለበሰ መጣና በግቢው ፫ና ፬ድርብ ሆኖ ተሰለፈ። ከዚህ በኋላ ክቡር ራስ ናደው ያማረ የማዕርግ ልብሳቸውን ለ-

ብሰው ወጡና በመኳንንቱና በካህናቱ በሠራዊቱ መካከል ቁመው የቴሌግራሙን ቃል አስነበቡ ። የተሰበሰበውም ሰው ሁሉ ከዳር እስከ ዳር ሺህ ዓመት ያንግሥልን ኢትዮጵያ በለምለምነት ለዘለዓለም ትኑር ብሎ በደስታ አጨበጨበ። ክቡር ራስ ናደውም ከደስታቸው ብዛት የተነሣ ሕዝቡን ደስ የሚያሰኝ ቃል ተናገሩ ቃሉም ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈው ነው ። የኢትዮጵያ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ የዳግማዊ ምኒልክ ሀብትና እግዚአብሔር ያልተለያቸው ይህንኑ ሐሳባቸውን አስቀድመው በቴሌግራም ስለአሳሰቡኝና አሁንም ቸርነቱ የማያልቅበት አምላክ የታሰበውን ፈጽሞ የልጃቸውን ደስታ ባይናቸው ለማየት ስለአበቃቸውና አስቀድመው ዛሬ መስከረም ፳፯ ቀን የንጉሥነት ማዕርግ ለኢትዮጵያ መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን አድርገው የደስታውን ነገር ዛሬ ስለሰማሁት ለደስታዬ ልክና መጠን የለውም ። ምንም ለጊዜው ያገሩ ርኅቀት ባያደርሰኝ አንደኛ የደስታ ተካፋይ እኔ ስለሆንሁ ክቡራን የኢሉባቡር መኳንንትና ፈረንጆች በዙሪያ ያላችሁት ሁሉ ደስታዬን እንድንካፈል በሙሉ ልቤ ሳላቋርጥ አስታውቃችኋለሁ ዕድሜ ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ለንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ እንደራሴ ይሁን ስል እግዚአብሔርን እለምናለሁ ብለው በጨረሱ ጊዜ ሕዝቡም እንኳን ሆነልን እንኳን ተደረገልን እያለ አጨበጨበ። ከዚህ በኋላ የተጠመደው መድፍ ፳፩ጊዜ ተተኰሰ መትረየሱ እንደዝናብ ስለወረደ ቍጥሩ አልታወቀም ። ካህናቱም ንሴብሖ ለእግዚአብሔር ስቡሐ ዘተሰብሐ እያሉ ባማረ ሽብሸባ ደስታቸውን አሳዩ። ከዚህ ወዲያ ግብር ተደረገና መኳንንቱም ካህናቱም በየማዕርጉ ከበላ በኋላ ካህናቱ ለንግሥ የሚሆነውን እየወረቡ በከበሮ ሲያናግሩበት ቆይተው በአዳራሹ ግብር የሚበላውና የካህናቱን ወረብ ለማየት የቆመው ቦታውን የሚያጣብብ ስለሆነ ክቡር ራስ ናደው መኳንንቶቻቸውንና ካህናቱን በአበባና ልዩ ልዩ በሆነ ምንጣፍ ወደተሸለመ እልፍኛቸው ይዘውት ገቡና እንደዚያው ወረቡን ይረቀርቀው ጀመረ ። ከዚህ ወዲያ እምከመ ተፈሥሐ ልብ ይበርህ ገጽ እንደተባለው የዛሬዋ ዕለት የተባረከች የደስታዬ ቀን ናት ብለው አንድ ሺ ብር አስመጥተው ለካህናቱ ስጦታ በመከከላቸው እንደምርት እንጣለሉት ለብዙ መኳንንትና ካህናትም እንደማዕርጋቸው ደስ የሚያሰኝ ሽልማት ሸለሙ ።

ደስታውም ያለልክ ሆኖ ልባቸው በደስታ ቢነካ አለቃ ቢረሳው የሚባሉ የደብረ ገነት ማርያም አለቃ ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን መወድስ ሰጡ ።

ባሕረ ምክረ ዳዊት ኢሐፀ በመዋዕልኪ ።
ወኃይለ ሦላሴ ወልድኪ እምልእተ ሰሎሞን ቀደሐ ።
አንተ ኢየሐፀፀ ክብረ ወዘኢዮትቤሰን ምክሐ ።
እስመ እሙ ዳዊት ንጉሠ ጽድቅ ለሰሎሞን ወልዱ ወሀበ ሕሚሃ ።
መንግሥተ በሕይወቱ አስካለ ማርያም ወሀብኪ ዘበዝኀ ።
ንሕነሰ እመ ሰማዕነ ድምፀ ቀርነ መንግሥት ዘከልሐ ።
ምውታነ እልባቢነ እንሥእ ወአንቀሐ ።
ኃይለ ሦላሴ ፍቅርከ ዘእምነ ወርቅ ነጽሐ ።
ዜናከ ሐዋርያ አድያመ እዝነ ሰብአ አምሳነ በጽሐ ።

ደግሞ ስለደስታው በጐሬ ያሉ የውጭ አገር ነጋዴዎች ተጠርተው ነበርና ባ፲፩ ሰዓት መጥተው ሻምፓኝና ሻይ ተጋብዘው ምርቃቱን በደስታ አንጐደጐዱትና ያለልክ ተጨበጨበ ። የምርቃቱ ንግግር ሳይጻፍ የቀረው ስለበዛ አንባቢ ይሰለቻል በማለት ቀርቷል ። ሁለተኛ ተከተማው አለፍ ብሎ የተቀመጠው የደጃዝማች ከበደ አሽከር የነበረው የመድፍና የመትረየስ ተኩስ ሰምቶ ወደ ከተማው በሩጫ እየተሽቀዳደመ መጥቶ ለፊተኛው ሰልፍ ስላልደረሰ ቀጠሮ ተቀብሎ አድሮ በማግሥቱ በ፳፰ቀን በጐፈርና በጣፋ በሙጣ ተንቆጥቁጦ ተሰልፎ ባለቃ ባለቃው እያለፈ ፉከራውን እየደቀደቀ የወታደርነት ንግግር ራበኝ ጠማኝ ብሎ ክቡር ራስ ናደውን ደስ ስለአሰኛቸው ሁለት ሺ ብር ያንጊዜውን ዳረጎት ሰጡትና ደስታውን እያደነቀ ተመለሰ። ደግሞ የልዕልት ወይዘሮ መነን ርስት ጠባቂ ቀኛዝማች እንዳሮም ማለፊያ ሙሉ ልብስ ሸለማት ተሸለሙ ።

ስለ ደስታ የተደረገውን ሁሉ ብንጽፈው አንባቢ ይሰለቻል በማለት ነው እንጂ የተደረገውማ ልክ መጠን የለውም ዕፁብ ድንቅ ነው ። እኔም ደስታው ሁለ ጊዜ ከልቤ የማያቋርጥ ስለ ሆነ አስበው ተስፋ ላደረጉልን ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ እረዢም ዕድሜና ጤና ለንጉሣችን ተፈሪ መኰንንም ለሰሎሞን የተሰጠ ሀብተ መንግሥት ያድላቸው ብዬ ልመናዬን ለእግዚአብሔር አደራ እሰጣለሁ ።

ወርቄ ተገኝ

ሰላመ ኢትዮጵያ ።

የቀድሞዪቱና የዛሬዪቱ ኢትዮጵያ ብታውቂስ ሰላምሽ ዛሬ ነው። በሲዳሞ አውራጃ በዋናው ከተማ ባገረ ሰላም የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ሥርዓተ ንግሥ ሁኔታ መጀመሪያ መስከረም ፳፯ ቀን ቅዳሜ ድንኳን ተተክሎ ሥፍራው ተዘጋጅቶ እንደሚገባ አምሮ በ፳፯ተኛው ቀን ክቡር ደጃዝማች ብሩ የማዕርግ ልብሳቸውን ለብሰው የጦር መሣሪያቸውን ታጥቀው ማለዳ እምቢልታና መለከት እየተነፋ ለበዓሉ ወደተዘጋጀው ቦታ መጥተው ሕዝቡን በያለቃው ሠራዊቱን በየጭፍራው ሲያሰልፉ ነበር ። ከዚህ በኋላ ባሩድ ቤቶችና የቤት ልጆች የክቡር ደጃዝማች ብሩም አሽከሮች የማዕርግ ልብሳቸውን እየለበሱ ተሰልፈው ይቆዩ ነበር። ይህም ሆነና ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የተላከ ክብር የተመላውን ባለምሥራቹን ደብዳቤ ለመስማት መኳንንቱና ሹማምንቱ ከየሰልፋቸው እየተጠሩ ክቡር ደጃዝማች ብሩ ወዳሉበት ቀረቡና ግራዝማች አምኃ የሚባል ባለዕድል ጸሐፊ ትእዛዝ ከፍ ባለ ድምጽ አሰምቶ የምስራቹን ቃል አነበበ ። ከዚህም ቀጥሎ ያለውን ቃል ክቡር ደጃዝማች ብሩ አስምተው አነበቡ የኢትዮጵያ ንግሥተ ነገሥታት ግርማዊት ዘውዲቱ ልጃቸውን ወዳጃቸውን አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንን አነገሥሁት ብለው ስላስታወቁኝ እኔም ልዑል ጌታዬ አልጋ ወራሽ ከያዙ ጀምሮ አሁን

ድረስ ለኢትዮጵያ ሕዝባቸው ብርሃን ሁነው በአውቀትና በግዕ ግሥት አገራቸውን ጠብቀው ዳኝነታቸውም እንደቆስጠንጢኖስ ንጉሥ ሁኖ በትክክል ፈርደው ሕዝባቸውንና ድሐቸውን ደስ አሰኝተው ወደ ሥልጣኔ ደረጃ አድርሰው እንዳቈዩት ሁላችሁም ታውቁታላችሁ ። አሁንም ንጉሡ ቅዱስ ዳዊት በዙፋኑ ተቀምጦ ልጁን ሰሎሞንን ባ፲፱ ዓመቱ በልጋው ላይ አስቀምጦ እንዳነገሠው ግርማዊት ንግሥተነገሥታትም ልጃቸውን ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንንን ዘውድ ሰጥተው ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ አድርገው ስላነገሡልን ብዙ ደስ ብሎኛልና ይህም ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚሆን ታላቅ ደስታ ነው እናንተም እንድትሰሙትና ንጉሡ ለዘለዓለም ሕያው ሁነው ይኑሩ ሺህ ዓመት ያንግሣቸው እያልን በደስታ በዕልልታ በዓሉን ልናከብር ይገባናል ባሉ ጊዜ ሕዝቡና መኳንንቱ እጅ ነሥተው ባ፩ ቃል ንጉሥ ለዘለዓለም ይኑሩ ሺህ ዓመት ያንግሥልን እያሉ መላልሰው ሲያጨበጭቡ የሕዝቡና የመኳንንቱ ዓይን በደስታና በሙሉ ፍቅር ተመልቶ ነበርና በዚያን ጊዜ አስተውሎ ለተመለከተው አጥብቆ ያስደንቃል ይኸም ሆነና መድፍ ተተኰሰ መኳንንቱም ቀድሞ ለሰልፍ ተዘጋጅተው ወደነበሩበት ሥፍራ ተመልሰው እንዲሄዱ ታዘዙ ቀጥሎም ጭፍራቸውን አሰልፈው እንደገና በረድፍ በረድፍ ሁነው እንዲያልፉ ትእዛዝ ተሰጠ ። መኳንንቱና ሕዝቡም እንደታዘዘው ሁነው በሰልፍ ክቡር ደጃዝማች ብሩ ወዳሉበት እየቀረቡ ባ፩ ወገን ግባት እየተኰሱ ያልፉ ነበር። ይህም ሲጨረስ ክቡር ደጃዝማች ብሩ ተዘጋጅተው ወደነበሩ መትረየሶቻቸው ቀርበው በተለየ መከከለኛውን መትረየስ ይተኰሱ ነበር ግራ ቀኝ የነበሩት መትረየሶች አንድነት ሲተኰሱ ድምፃቸው እንደ ሐምሌ ጐርፍ ይተም ነበር ለሥርዓተ ንግሥም የተገባው ሰልፍ ሲፈጸምና ወደቤታቸው ሲመለሱ የከተማው ወይዛዝርና ያገሩ ቆንጃጅት በየመንገዱ ዳር ሁነው ንጉሣችንን ሺህ ዓመት ያንግሥልን ለዘለዓለም ያኑርልን እያሉ ዕልልታውን ያቀልጡት ነበር ። የክቡር ደጃዝማች ብሩ ባለቤት ክብርት ወይዘሮ አማከለችም ለበዓሉ የተሰበሰቡትን ወይዛዝርና ደንገጥሮችን በወርቅና በብር የተንቆጠቆጠ ያማረና የተዋበ ልብስ አስጊጠው ሸልመው ንጉሥ ለዘለዓለም ይኑሩ ሺህ ዓመት ይንግሡ እያሉ ሰልፈኛውን በዕልልታ ተቀበሉ ወደዚያውም ክብርት ወይዘሮ አማከለች እጅግ የሚያስደንቅ ሙሉ ግብር አዘጋጅተው ኑሮ ክቡር ደጃዝማች ብሩ ለሰልፉ የተሰበሰበውን ሠራዊት ሕዝብና መኳንንት አንድ ሳይቀር ካህናቱም አንድነት ወደግብሩ ገቡ በዚህም ጊዜ የነበረ የሕዝብ ብዛት የምግቡ መዘጋጀት ምን ተብሎ ይነገራል ። በዚያም ቀን ክቡር ደጃዝማች ብሩ ስለ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የሥርዓተ ንግሡ በዓል ለማክበር የልባቸው ደስታ በፊታቸው እንደፀሐይ ፀዳል አንጸብርቆ ያስታውቅ ነበር ። የምስራቹንም ቃል ተቀብሎ ያመጣውን ስልከኛ ከግር እስከ ራሱ በወርቅ አንቆጥቍጠው ሸለሙት የቀሩትንም ስልከኞች እንደማዕርጋቸው ያማረ የተዋበ ሸልማት ሸለሙዋቸው ። ከዚህም ቀጥሎ ጀግኖችና አርበኞች ተራ ወታደር ሳይቀር ዛሬ የኢትዮጵያ ዕድል የሚባልበት የመንግሥታችን በዓል የሚከበርበት ቀን ነውና ለምኑ ይሰጣችኋል እያሉ ክቡር ደጃዝማች ብሩ ሕዝቡን በፍቅር ቃል ባማረ ጨዋታ ያነቃቁት ነበርወታደሩም ልቡ የተመኘውን አፉ የተናገረውን ፈረስ በቅሎ የወርቅ ጋሻ ጠመንጃ ሰይፍ ሲለምን እንደምኞቱና እንደቃሉ ተፈጸመለት (ተደረገለት) አልተከለከለም አንድ ስንኳ ይህም ሲሆን ባዳራሹ ለተቀመጠው ሕዝብ ከሊቅ እስከደቂቅ የሐርመሐረብ እየታደለ ሽቱ እየተረጨ ሲሰጥ ቤቱ በሽቱ መዓዛ መላ ። ከዚህም በኋላ እያንዳንዳቸው መኳንንቱና ካህናቱ ሕዝቡም ምስጋናቸውን እያቀረቡ መርቀው ሄዱ ።

አንድ ኢትዮጵያዊ

በዓድዋ ከተማ ስለተደረገ የንግሥ በዓል ።

በዓድዋ ከተማ የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን መንገሣቸው ተሰማ በዚሁም ጊዜ ክቡር ራስ ሥዩም መንገሻ በበዛ ደስታ ልባቸው ተነክቶ የከተማው መንገዶች ሁሉ አልፎ አልፎ ሰንደቅ ዓላማ ተተክሎባቸው ምድረ ግቢውም በሚውለበለቡ ወረቀቶች አበባና ዘንባባ አጊጠው የንግሥተ ነገሥታታችንና የንጉሣችንም ሥዕል በየስፍራው ተተክሎ በእንደዚህ ያለ ጌጥ ሁሉ አምሮ አጅግ ለልብ ደስ የሚያሰኝ ነበር ። የኢትዮጵያ መንግሥት የስልክ ቤትም በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማና በንጉሦቿ ሥዕል ተጌጦ ለተመለከተው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ነበር ከዚህም በኋላ በ፳፯ መስከረም የመንገሣቸው ቀን በደረሰ ጊዜ ሠራዊታቸውን አሰልፈው ነጋሪት እያስጐሸሙ በከበሩ ኒሻኖች አጊጠው የደስታ መድፍና መትረየስ ማስተኰስ ጀመሩ ይህንኑም ደስታ ለመካፈል በዓድዋ ያሉ የውጭ አገር ሰዎች መጥተው ነበር ። ተኵሱም ከአራት ሰዓት ተኩል ጀምሮ እስከ ፯ሰዓት ሳያቆም ቈየ ከዚህም በኋላ በተሰናዳላቸው አዳራሽ የውጭ አገርም ሰዎች ለምሳ ተጠርተው ነበርና አብረው ገቡ። የደስታ ምግብ ሕዝቡ ሲመገብ ዋለ መብሉም ከተፈጸመ በኋላ ሽምፓኝ ቀርቦ ክቡር ራስ ሥዩም ቁመው ከዚህ በታች የተጻፈውን ቃል ተናገሩ ።

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ለትጉህ ልጃቸው ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪመኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ በግርማዊት ቃል ሁነው በቀድሞ ነገሥታት ያልተሠራ ሥራ ከአውሮፓ ነገሥታቶች ካንድ ፍቅር የመላበት ጽዋ ለመካፈል ኢትዮጵያን ስለ አበቋት ለግርማዊነታቸውና ለታዛዡ ልጃቸው ለንጉሥ ተፈሪ መኰንን ፍጻሜ በሌለው ምስጋናየን ለልዕልናችሁ አቀርባለሁ ። ደግሞ ይህንኑ የታሰበውን ደስታ በመስከረም ፳፯ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም በታደለችው በደጉ በታላቁ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ በቆረቆሯዋት ከተማ ስለ አሳቢዋ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ደስታ ክብር ኢትዮጵያ አብራ ከልብ የማይጠፋ ደስታ በመካፈልዋ ለእግዚአብሔር ምስጋናየን አቀርባለሁ ። ነገር ግን ከእናትዋ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ፊት ቁሜ የጌታየን የኢትዮጵያን መሪ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ደስታ ከዚያ ኑሬ ይህን የጋለ ደስታ ባለመካፈሌ ቀኑ አጥር አገሩ ስለ ራቀ በጣም ሳሳሁ ። አሁን ግን ይህነኑ ደስታ በትግሬ አውራጃ ካለው መኳንንቱ አብሬ ቁሜ ስለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ስለ ግርማዊ ንጉሥ

ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ም እረጅም እድሜና ጤና ሰጥቶ ከመስማማት ጋራ በደስታ ዓም እስከ ዓለም የኢትዮጵያ ባንዲራ በቀኝ ትኑር ብዬ ጽዋ እነሣለሁ ብለው በጨረሱ ጊዜ ዳር ከዳር ተጨበጨበ ።

ከዚህ በኋላ ክብርት ወይዘሮ ዓፀደ አስፋው ከዚህ በታች ያለውን ቃል ተናገሩ ።

ግርማዊት ንግሥት ነገሥታት ዘውዲቱ። ልጃቸው የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ግርማዊት እናታቸው ባዘዟቸውና በላኳቸው ስፍራ ሂደው የላኳቸውን ትእዛዝ ፈጽመው ለሚመጡ ልጃቸው ይህንን የጋለ ጥልቅ የሆነ ደስታ አስበው ንጉሥ ብለው ሰይመው መስከረም ፳፯ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም ስለ አደረጉላቸው ለግርማዊት ንግሥታችን እግዚአብሔር እረጅም እድሜና ጤና ሰጥቶ እንዲሁ በግዛታቸው አቆይቶ ብዙ ዘመን ያኑርልኝ ብዬ ምርቃኔን አቀርባለሁ ። ደግሞ ስለ ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ደስታና ክብር መስከረም ፳፯ ቀን ፲፱፻፳፩ዓም ስለ ሰማሁ በጣም ደስ አለኝ ይህነኑም ወሰን የሌለው ደስታ እግዚአብሔር ለደጎቹ ገዢዎች ጌቶቹ ብዙ እረጅም እድሜና ጤና ሰጥቶ በሀገራችን ባዕድ እንዳይገባበት በአንድነት ፍቅር አጽንቶ አሰማምቶ እንዲያኖርልንና እንዲገዙን ያድርግልን በማለት ምኞቴን አቀርባለሁ ብለው በጨረሱ ጊዜ ተጨበጨበ

ኃይሉ ገብረ ማርያም።

የከተማ ወሬ ።

ስለ ሹመት ።

ጥቅምት ፳፮ ቀን ክቡር ግራዝማች ማህሌ የባሻ ተሰማ የነበረውን የመድፈኞች አለቃ ሆነው ተሾሙ ።

ክቡር ነጋድራስ ፀምሩ የቀኛዝማች ደኅኔ የነበረውን የጽሕፈት ሚኒስቴር ዲረክተርነት ተሾሙ ።

ክቡር ባሻ ተሰማ የመታሰቢያ ቤት ዘበኝነት ተሾሙ ።

ክቡር ግራዝማች ካሣ አባውቃው ያባታቸው የነበረውን የመንግሥት ዘበኛ አለቅነት ተሾሙ ።

ብርሃንና ሰላም አዲስ ሹመት ለተቀበሉ መኳንንቶች መልካም ምኞቱን እያቀረበ እንኳን ደስ አላችሁ ይላል ።

ማስታወቂያ ።

እኔ ባላምባራስ ጠይቃቸው አዝልቅ መስከረም ፳፱ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም ሐረር አውራጃ ጠይቃቸው አዝልቅ የሚል ማኅተሜ ጠፍቶብኛልና ከዚህ ቀደም በማኅተሜ የተዋዋለ ሰው እስከ ፲፭ ቀን የውሉን ወረቀት ያምጣ ከእንግዲህ ወዲያ ታትሞ ቢገኝ አይረጋብኝም ጥቅምት ፳፱ቀን ፲፱፻፳፩ ዓመተ ምሕረት ።

ባላምባራስ ጠይቃቸው አዝልቅ ።

ኦቤርላንድ



ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሽ ኦቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጦጦን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባ ኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኜቶና ባለባተሪ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል «ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው

ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

COGNAC S. E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



ዝኒት የእጅ ሰዓት ።

በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩግቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንዲልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በ፣ስቶን በማድራስ በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፣ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪመኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽናባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ።

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በካፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በካፕሱሉ ላይ የለ ለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔራቶር ደግሞ ትራንስ ፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዌድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad



ዓለም ሱቅ ፲፪ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሲንፎር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ፤ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል

እደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ሱቅ ነው ።

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ሕፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬንግ ኩባንያ ቤት ነው ።



ጉድይር ግዙ

በማርማሪ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አራተኛ ዓመት ፤ቁጥር ፵፮
4 me ANNÉE № 46

ሐሙስ ኅዳር ፮ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም ።
JEUDI 15 NOVEMBRE 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ደረስተኛ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ስፈስን በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ሳይታወቅ ኑሮ ባለ ማስተዋል አወዳደቅ የተጣለ ማዕድን

ኢትዮጵያ በእህልና በማዕድን ከብታም እንደሆነች በዓለምም የእህል አገር በመሆንዋ ጐተራ ያሉዋታል። ማዕድኗም በጣም የሞላበት አገር ስለሆነች በመታወቅዋ ስሙንና አይነቱን ዋጋውም የከበረ በመሆኑ ባለማወቅ የተነሣ የአገራችን ሰዎች ኢያንጓለሉ በልዩ በሆነ ስም ኢየጠሩ ከወርቅ ጋር ከአሥሩ ወቄት አራት አግብተው ሲነግዱበት ብዙኀ ዘመን ሲሠራ ኑሮ የሰው ልጅ መቼም ኀፍረት ነውና ከባልንጀራው ጋር የሚአጋጨው ስድስት ወቄት ወርቄ ነጃሳ በአስሩ ወቄት ወርቅ ውስጥ ኢየቀላቀለ መሸጥ ቢጀምር የኢትዮጵያ ወርቅ ሽያጭ ቢአበላሽ የዛሬ ኻያ አምስት ዓመት ይኸንይነቱና ስሙ ያልታወቀ ማዕድን ባዋጅ ተከልክሎ ማንም እንዳያንጓልለው ሲኖር በኤሮጳች ጦርነት ጊዜ ያንዱ ወቄት ዋጋ እስከ ሶስት መቶ ደረሰ። በዚህም ጊዜ የወርቅ ንግድ ሥራቸው የሆነ ሙሴ ዛፓ የሚባሉ በነጆ የሚኖሩ የማዕድንን ዋጋ በኤሮጳ እንዴት እንደሚሸጥ የሚአመለከት ጋዜታ ሲያነቡ በድንገት (Platinium) ፕላቲኒዩም አንዱ ወቄት ሶስት መቶ ብር ነው የሚል ዓይተው ምናልባት ጋላ ወርቄ ነጃሳ የሚለው እሱ ይሆን ብለው ከአሉበት አገር ነጆ ቢያስጠይቁ ይኸን የሚአውቁ በጉሊሶ ፍርዲ ገርባ በዓይራ ሆርዳ ሲዳ ናቸው ቢሉዋቸው ወደነዚህ ሰዎች መጥተው ሙሴ ዛፓም ዓይነቱን አያውቁትም ነበረና ከየትስ ነው የሚገኝ ምንስ ይመስላል ብለው ፍርዲ ገርባን ቢጠይቁት ዓይነቱንና የሚገኝበትን ቦታ መርቶ አሳያቸው በዚህም ቦታ ቢርቢር ዩብዶ በሌሎችም አራት የሚሆኑ ስርፋ በየካቲትና በመጋቢት ወር በቢርቢር አውራጃ ያለ ጋላ ሁሉ በዚሁ ወንዝ ተሰማርቶ ብጥልቆሽ ይኸን ማዕድን ኢያወጣ በብዙኀ በመገኘቱ ሥራቸው በዚህ የሆኑም የወርቅ ነጋዴዎች ደግሞ አሞሊያቸውንና የአርድ ሰንጋ ይዘው ወደ ቢርቢር መጥተው በርካሽ ዋጋ ይገዙዋቸው ነበረ፡እነዚህ የወርቅ ነጋዴዎች ከወርቅ ጋር ኢየቀላቀሉ ይነግዱበት ነበረ በድንገት የወርቅ ዋጋ ስለ ከበረ በዚያን ጊዜ ስቡ ወይም ወርቄ ጉትቻ ይሉት ነበረ። ከብረት በዓይነቱ የማይለይ በመሆኑ ወርቄ ነጃሳ የሚመስል ዓይነቱ ጋላ ዩብዶ በሚለው ቀይ ቀለም የሚመስል አፈር ጋር ኢያሹና እንዳለም ኢየቀላቀሉ ከስቡው ጋር ይሸጡላቸው ጀመረ።እነዚያም የወርቅ ነጋዴዎች መለያ መሳሪያ የላቸውምና እንደገዙት ከወርቅ ጋር ቀላቅለው እንደሸጡላቸው ሰዎች እነሱም እንዲሁ በመሸጣቸው የኢትዮጵያን ወርቅ ዋጋ በዓለም ያበላሸዋል ሲሉ ታላቁ ንጉሣችን ግርማዊ ዓጼ ምኒልክ ምናልባት ኻያ አምስት ዓመት ይሆነዋል ከዚህ በታ ጋላ እንዳያንጓልል ቢከለክሉት ያን ጊዜ በእጁ የቀረ ጋላ ገዢ ቢያጣ ወርቄ ነጃሳ ፈላጊ የሌለው ብለው ስሙ ስቡ ወይም ወርቄ ጉትቻ ሲሉት የነበረውን ወርቄ ነጃሳ አሉት።በዚህ ምክንያት በዓለም በሚጠራው ስም ባለመግጠሙ የተነሳ ተደብቆ የኖረውን እነ ፍርዲ ገርባና ሆርዳ ሲዳ ወርቄ ነጃሳ ያሉትን ሙሴ ዛፓ ፕላቲን ብለው ገለጹት።እንደዚሁ ስማቸው ያልታወቁ ማዕድናት በኢትዮጵያ ሞልተዋልና አደራረጉን የሚአውቁ በአገራችን ብዙህ ሰዎች አሉ። የሚገኙበትንም ቦታ ለአገረ ገዢም ሆነ አዲስ አበባ ለመንግሥታችን እንዲያመለክቱና የሚያመለክቱትን የድካማቸውን ዋጋ እየሰጡ ቢያተጋጉዋቸው ተሰውሮ ያለውን ለገለጹ ሰዎች ታላቅ ጥቅም ለአገር በማሳየታቸው የጉልበቱን ዋጋ አጥቶ ለሚቀረው ሕዝብና አገር ልማት ያመጣል ስለዚህ በኢትዮጵያ ያሉ አገረ ገዢዎች ቢተጉበት ዛሬ በዚህ ቢርቢር የኢትዮጵያ መንግሥት አዛጋር ወርቅነህና ለፊታውራሪ ዴሬሳ ኩባኒያና ለሙሴ ፕራቦ በውል ፈቅደው ስለሰጡዋቸው በወለጋ ያለ ሠራተኛ ለጉልበቱ ዋጋ አጥቶበት አገሩን ጥሎ የተሰደደ ሁሉ በቢርቢር ቆላ የፕላቲን

ሥራ ስለተገኘና በመጀመሩ እየተመለሰ ገብቶ እዳ ያለበትም እዳውን ከፍሎ በየበድማው በመገባቱ እራሹም ለዚህ ፕላቲን ለሚሠራው እህሉን በመሸጡ ይልቁንም ደጃዝማች መኰንን ወሰኔ ግብሩን እኩል በኩል በማኰየላቸው የራቀውም ሰምቶ በቴመለስ ጊዜ በዚህ በፕላቲን ሥራ ላይ ብዙን ገንዘብ በአገር ሲገባ ንግዱም ሲየሰፋ አገሩም ሲየለማ ይሄዳል ።

አሁን በስድስት ቀን ሠርቶ እሑድ እሑድ ፕላቲን ሸጦ በእጁ የሚገባ ገንዘብ ከሰስት ሽህ ብር ይበልጣል። በዚሁ በጉልበቱ ዋጋ በሚያገኘው ላም ለመግዛት እንጂ ብር ለማስቀመጥ ባለመትጋቱ የቀንድ ከብት ዋጋ በጣም ተወዶ አንድ ጥገት ላም በሠላሳ አምስት ብር እንኳ አልገኝ አለ ። ለመንግሥታችን ማዕድን ያለበትን አገርና የተገኘበትን ቦታ ዓይነቱን በይውራም እንኳን ተሰውሮ እንደ ቢርቢ ፡ ቆላ ከመኖር አውቆት ቢቀመጥ ይሻላል እንጂ እንዲያው ሳይታወቅ ከሚቀር በዚህም ነገር አገረ ገዢዎች በየግዛታቸው እያስፈለጉ ያገኙትን ዓይነትና ቦታ ወደ ማዕድን ሥራ ቤት እየላኩ ከመዝገባቸው ላይ በእንዲህ ያለ አገር ይኸ ዓይነት ማዕድን ይገኛል ብለው ጽፌውት ቢቀመጥ ለማንላቸውም ነገር ታውቆ የቆየ እንደሆነ የት ብታ ነው አገሩስ ወየት ነው ስፋቱ ርዝመቱስ ምን ያህላል ተብሎ ከማለት አስቀድሞ ማወቅ ይገባል ። ይልቁንም የማዕድን ካርታ ማድረግ ደግ በሆነ ነበር ። ለሚመጣው ትውልድ የት እንደሆነ እንዲያውቀው በተቀረም ጥንት የኢትዮጵያ ሕዝብ ቱሉ ክጹ ገንጂ ወርቅ ሲያወጡበት የነበረ ፍራሽና የድንጋይ ጠገራቸው በዚህ ቦታ ተበትኖ የሚገኝበት ስርፋ ሳይታወቅ እንደቀረ እንዲሁ በሌላም አገሮች ውሥጥ ያለ ማዕድን ቦታና ፍራሽ ሳናውቅ የቀረን እንደሆነ ታላቅ ሞኝነትና ጉዳት ይሆንብናል። በብልሁ ፍርዲ ገርባ ወርቂ ነጻሳ ፈላጊ የሌለው ብሎ ሲጠራው በትጉሁ ሙሴ ዛፓ ፕላቲን ብሎ በዓለም መጠሪያው ስም ሲገልጸው ባዚህ ዓለም የለፋበት ቀርቶ ያልደከመበትን ነውና የሚበላው ጥንትም በኤሮጳች ታሪክ እንደምናየው አንዱ የደከመበትን ከብታም ወይም ተንኰለኛ ሰው የብዙዎቹን ብልኃት በገንዘብ ሲያሞኙ በተንኰል ሲያስከስሱ ጥበባቸውን ነጥቀው ሌሎቹ ሲበሉባቸው ዓይተው የከብታሞች ገንዘብ የፈራጆችን ዓይን ያሰውራልና አንዱ የለፋበትን ሌላው በተንኰል እንዳይወስድበት ጠንካራ ሕግና ደምብ አቁመው የብልሆቹን ጥበብ ይጠብቁበታል።እንዲሁም የኢትዮጵያ መንግሥት አንዱ የለፋበትን ሌላው እታለሎ እንዳይወስድበት ሕግና ደምብ ማቆም ይገባል ። እንደ ፍርዴ ገርባ የድካሙን ዋጋ እንዳያጣ ። የብርሃንና ሰላም አንባቢ ወለጋ ሰዮ ። ኃይሉ ክብረት።

ይባቤ ዘአባ ገብርኤል ።

ተፈሥሒ ጽዮን ወተሐሠዩ ኢትዮጵያ ።
ነዋ ንጉሥኪ ተፈሪ ኬንያ ።
እንኳን ደህና ገባህ የነገሥታት ዘውድ ።
ብተፈሪ ዙፋን ሰንብት አትሂድ ።
ዘውዲቱ መከን ናት ማነው ይህን ያለ ።
ተፈሪን ወልዳለች ፀሐይ የመሰለ ።
ኢትዮጵያ ንግሥት እንግዲህ አትፍሪ ።
ንግሥልሻልና የምሥራቅ ተፈሪ ።
ተፈሪ ይላታል ልዕልት ሙንን።
ቴኒሣ ምክረው ቃኘው መኰንን ።
ይገበታልና እቴጌ መሆን ።
ዱሮ የሺ እመቤት ዛሬ የአዕላፍ ።
ተነሺና እዩው የተፈሪን ሰልፍ ።
መስሎ የሚጓዘው የተከዚን ጎርፍ ።
የጃንሆይ ትእዛዝ ደረሰ አሁን ።
ወንድሜ ነውና ይልማ መኰንን ።
ሐረር ልጠይቅህ ዋና ዋናውን ።
ጃርሶ ለምን አልኸው ፀሐይ መውጫውን ።
ኢትዮጵያ ሞላው አሁን ተቀደሰ ።
አሥራ ሁለተኛው በአዋጅ ነገሠ ።
እንግዲህ አለብስም ያለቀ ጨርቅ ።
ሸልሞኛልና የተናኘ ወርቅ ።
ተመልከቱ እንደኔ በሐረር ምሥራቅ ።
በጣሙ ይፈልቃል የመኰንን ጽድቅ ።
ዱሮ የሺ መቤት ዛሬ የሁሉን ።
እንደምን ወለድሽው ሰንቄ ባሕርዩን ።
እጅግ አመዘነ ከወርቅ ሚዛን ።
ወንድምህ ነገሠ በአዋጅ በዜማ ።
ተነሣ እምሩ ወጥተህ እየውማ ።
አርዕድ አንቀጥቅጥ ነው የንጉሥህ ግርማ ።
ዳኘውና ቃኘው በትእዛዝ ዋሉ ።
ዘውዲቱ ተፈሪን አንግሡናል ሲሉ ።
ሰውና መላእክት አሜን ይሁን አሉ ።
በሐረር ታየህ ዙፋን ላይ ሁነህ ።
እያንጸባረቀ የብርሃን ዘውድህ ።
ይገባዋል አለ ሰው ሁሉ ያየህ።
እያማረ መጣ በገናው ድርድር ።
መኰንን በቃኘው ባሕር እስከ ባሕር ።
ተፈሪ ገረፈው በድኅንፃ ግብር ።
የሺ ማነው ያለሽ የሁሉ እመቤት ።
ያወጣሽው አሥራት ከአሥራ ሁለት ።
በክብር ነገሠ በጽጌ ማኅሌት ።
ሰውየው ተፈሪ ፈረሱ ጠቅል ።
አገርን ጨበጠ በእጁ እንደ ሉል ።
ሁላችን በኅብረት እልል እንበል ።
ምስጋና እናብዛ ለአምላክ ልዑል ።
ለጻደቁ ሰዎች ምልክት አላቸው ።
አምላክ ይቀበሏል ደጉ ምግባራቸው ።
ከዘውዲቱ ጋራም ይነግሣል ልጃቸው ።
ተመልከት ፈጣሪ መንግሢ ነገሥት ።
እጁዋን የዘረጋች ኢትዮጵያ ናት ።
ተቀበለኝ ብላ ምግባር ሃይማኖት ።
ወደህ ባርከላት ይህነን መንግሥት ።

ብስራተ ገብርኤል ተፈሪ ነገሠ ።
ምድርና ሰማይ ሠምሮ ተቀደሰ ።
አምላክ መሰከረ ምልክት ደረሰ ።
ነፍን የነበረ ዝናሙ ለገሠ ።
አምላክ የሚወደውን ተፈሪ አትርሳ ።
የወደቁ ሰዎች አልተነሡምሳ ።
ሁለ ጊዜ ማር አትጻፍ አበሳ ።

ጉባዔ ቃና ።

ናሁ ጽልመት እምኢትዮጵያ ተሰደ ።
እስመ ለተፈሪ አምላክ አንብሮ በመንበረ ፀሐይ ገሃደ።

ቡሩኬ ዘአባ ገብርኤል ።

ስብሐት ለእዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ።
ይእዜ አእመርኩ ከመ አድኃኖ እግዚአብሔር ለመሢሑ።
እግዚኦ በኃይልከ ይትፌሣሕ ንጉሥ ።
ወአንበርከ አክሊለ ዲበ ርእሱ ዘእምዕንቍ ክቡር።
መንበርከ እግዚኦ ለዓለመ ዓለም።
በትረ ጽድቅ ወበትረ መንግሥትከ ።
አፍቀርከ ጽድቀ ወዓመፃ ጸላእከ ።
በእንተዝ ቀብዐከ እግዚአብሔር እምላክከ ።
እግዚአ ኰነኔከ ሀቦ ለንጉሥ ።
ወአልዓልኩ ኅሩየ እምሕዝብየ ።
ወረከብክዎ ለተፈሪ ገብርየ ።
ወቀባዕክዎ ቅብዐ ቅዱሰ ።
በሀየ አበቍል ቀርነ ለኃይለ ሥላሴ ።
ወአስተዴሉ ማኅቶተ ለመሢሒየ ፡
ወአለብሶሙ ኃፍረተ ለጸላእቱ ።
ወቦቱ ይፈሪ ቅድሳትየ ።
ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ ኢትዮጵያ ።
ዘተማኅለነ ወገብረ መድኃኒተ ለሕዝበ ዚአሁ ።
እንሆ ለነ ቀርነ መድኃኒትነ እምቤተ መኰንን ገብሩ።
ሶበ አኮ እግዚአብሔር ምስሌነ ።
ይብል ኢትዮጵያ ሰበ አኮ እግዚአብሔር ምስሌነ ።

አባ ገብርኤል በሐረር ።

ስለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪበደብረ ብርሃን የተደረገው ደስታ

መጀመሪያ ካህናቱ የበዓል ልብስ ለብሰው ቀሳውስቱም ዲያቆናቱም ደብትሩም ልብሰ ተክህኖዋቸውን ለብሰን ከቤተ መንግሥቱ ገብተን ምስባክ እስመ በጸሕከ በበረከተ ሠናይ ወአንበርከ አክሊለ ዲበ ርእሱ ዘእምዕንቍ ክቡር ሐይወ ሰአለከ ወሀብኮ ወንጌል ዘሉቃስ።ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ዘተማኅለነ ወገብረ መድኃኒተ ለሕዝበ ዚአሁ።ኢንግርጋሪ ርእዩ ዘገብረ እግዚአብሔር።እስመ ለዓለም ናሁ ሠናይ ወናሁ አዳም በዝ መክን መዓዘሆሙ ለቅዱሳን ።

ግሥ። ምኒልክ ያቤላ አብርሂ አብርሂ ደብረ ብርሃን ነጽሪ ዓውደኪ. ወተፈሥሒ. በሕዝብኪ. አስከለ ማርያም አልጸቀ መድኃኒትኪ. ኃይለ ሥላሴ ወረሰየ ሰላመ ለበሐውርትኪ. አብርሂ ኢየሩሳሌም ብለን ከዚህ በኋላ ።

መወድስ ።

ምጽአተ ብርሃን ይስብከ ንቅወተ ዶርሆ ።
ኃይለ ሥላሴ ትጉሀ ዘወልደ እምላከ ሰንበት ።
እስመ ነቅዐ ንጹሕ ዘእም አንቅዕተ ሕግ መንግሥት ።
ወዝውእቱ ዜና ግብሮሙ ለሐዋርያት ልዕልና ወሀብት።
እስመ ተፋቅሮ ዘነቢያት ።
ላኣሌሁ ኅደረ ወእንተ ንግሥት በረከት ።
በላዒሂ ለዓማፅያን ልብሰ መንግሥቱ እሳት ።
ዘኢይክሉ ለኪሮቶ እሳታውያን መኳንንት ።
ወያስተፌሥሕ ብዙኃ ሀገረ ምኒልክ ዳዊት ።
እምደብረ ብርሃን ዘይውኅዝ ኃይለ ሥላሴ ማየ ሕይወት።

ቀኝ ጌታ አኃለ

መወድስ ።

ኃይለ ሥላሴ ነገሥት እግዚአብሔር።
ዓዲ ይነግሥ ለዓለም ደብረ ጽዮን ።
ውስተ ባሕረ ብርት ግብጽ ምልእተ ብክይ ሐዒን ።
እስመ ቦአ ሠረገላ ፀሩ እንተ ፈርዖን ዓይን ።
ወከነት መራሒተ አስከለ ማርያም ድንግል ለኃይለ ሥላሴ አሚን ።
አማሰንሂ እምቅድመ ገጹ ፍኖተ ኃጥአን ባዕዳን ።
አከኑ ኃይለ ሥላሴ እግዚአብሔር መኰንን ።
ይቤ በቃል ለካህናቲሁ ጻድቃን ።
በምንት አስተማስላ ለመንግሥት ሰማይ ደብረ ብርሃን ።

መምህር መኩሪ

መወድስ ።

ምኒልክ ይብሎሙ ለሕዝበ አእምሮ
ለኃይለ ሥላሴ ወልድየ ነፍስየ ዘሠምረቶ ።
ሎቱ ስምዕዎ ከመ ይፈጽም ሠናይቶ ።
ወይዝራዕ ፍቅረ ወትሕትና ውስተ ልበ ሰብእ ሐቋሁ ቀኒቶ።
ምድር አዕኰተቶ ፤ ምስለ እለ ሐደሱ ሕዝብ ዘኢይሠዓር መንግሥቶ ።
እምትክትሂ ሣህለ ሥላሴ እንዘ ይሰፍሕ መዝራዕቶ ።
ለኤፍሬም ኃይለ ሥላሴ አቅደመ በርኮቶ ።
እስመ ከመ ይእዜ ይትዓወቅ ስምዓ በረከቱ ባሕቲቶ ።
አስኪለ ማርያም ዲበ ርእሱ አክሊለ ዳዊት ከለለቶ ።

መሪጌታ ገብረ ጻድቅ

ከዚህ በኋላ ካህናቱ ይህንን ቅኔውንም ግሡንም በክብሮ በጭብጨባ ብለው ሲጨርሱ ቄሱ ቀሞው የምስጋና እርጋታቸውን አሳርገው ካህናቱም እቡነ ዘበሰማያት ተቀብለው ደግመው በየቤታቸው ገቡ።በከተማው ያለውንም የሕዝብ ደስታና የካህናቱን አኳሁን አብዝቼ እንዳልጽፈው አታሚ እንዳላሰለች ብዬ ነው

ደብተራ ገብረ ማርያም
ዘደብረ ብርሃን ካልእተ ኒቅያ መካነ ጉባኤ።

በአውራጃው ሁሉ የትምህርት ቤት ለማቆም ።
እስበንግ ብናስብ።

ከዚህ ቀደምም ስለ ቤተ ክርስቲያን ገቢና ስለትምህርት ቤት ትንሽ ቃል አስታውቄ ነበር። አሁንም ቀጥሎ ያቀረብኩት ስለ አገረ ገዦዎችና ስለ እያውራጃው ገቢ ነው። በዋና ከተማችን እንደተለመደው ከንግድ ምኒስቴር ገቢ ለተማሪ ቤት እርዳታ እንደተወሰነው ልክ በያውራጃውም በንግድ ረገድ ባለው ገቢ እንዲሁ ተወስኖ ትምህርት ቤትና ሆፒታልን በያውራጃው ክፍል ማቆም የሚያስፈልግ ነው ።

ስለአገረ ገዢዎች ደግሞ ከዚህም ቀደም ግዛት ላላቸውም ወደ ፊትም በሚቀበሉት አውራጃ ብዛቱና ማነሱ መጠኑ ተወስኖ አገሬውን ይኸንን ያህል ገንዘብ እርዳታ ስጥቻለሁ ብለው እንዳያስቸግሩ ማስታወቂያ ተደርጎ ስለ ትምህርት ቤትና ለመንገድ ሥራ የሚሆን ግብር በየጊዜው መርዳትና ማቋቋም የሚያስፈልጋቸው ነው። አገሬውን እንዳያስቸግሩ ማስታወቂያ ይደረግ ማለቴ ሕዝቡን ከማስቸገር ባለገንዘብ ደጃዝማቾችና ራሶች ገንዘባቸው ስም ለሌለው ነገር ከሚጠፋና ከሚቀመጥ ስማቸው በሕዝብ ታሪክ ክፍል ውሎ ኑሮ እንዲታወስ አንዳንድ መታሰቢያ ቢጥሉ ይሻላል ለሠሪዎችም ስም ለኢትዮጵያም መቅደሚያ ለወንድሞቻቸውም ዕውቀት ስለሆነ የኢትዮጵያ መኳንንቶች ሕዝቡን ሳያስጨንቁ እንደ አፈ ንጉሥ ጥላሁንና እንደ አፈ ንጉሥ ከተማ በዚያን ጊዜ ቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልግ ስለሆነ በአዲስ አበባ ሠሩ። ስማቸውም ይታወሳል ብሰማው ነው የጻፍኩት ። አሁን ግን በዛሬ ጊዜ ትምህርት ቤትና ሆፒታል መንገድ ንግድ እርሻም ለሕዝብ የሚጠቅምና እውቀት የሚሆን ነገር ስለአስፈለገ በቍጥር አርባ አምስት እንደተጻፈው ቃል መሠረቱ ሥሩ የትምህርት ቤት ነውና ሕዝቡን ሳናስቸግር ትምህርት ቤቶች እንዲኖሩን ለክቡራን መኳንንቶች አሳስባለሁ ። ይኸንኑም ክቡር ደጃዝማች ብሩ የንጉሥን አጀማመር አይተው ላገር ጥቅም መሆኑን ስለተረዱት የንጉሥን መንገድ ተከትለው በግዛታቸው ትምህርት ቤት ሊያቆሙ ነው ማለትን ሁላችንም ሰምተናል በክቡር ደጃዝማች ብሩ ብቻ እንዳይቀር በሌሎችም እንዲለመድ ተስፋ እናደርጋለን ። አርመን ያዕቆብ

ሹመት ።

ክቡር አቶ ማሀሌ ፀዳሉ ጥቅምት ፳፱ ቀን የጥበብና የትምህርት ሚኒስቴር ዲሬክተር ሁነው ተሾሙ ።

ክቡር አለቃ አርአያ ተክለ ሥላሴ ኅዳር ፫ ቀን የአባታቸውን ሹመት ሐረር ከምበልሽ ማርያምን ተሾሙ።

ብርሃንና ሰላም ክቡር አቶ ማሀሌ ፀዳሉንና አለቃ አርአያ ተክለ ሥላሴን እንኳን ደስ አላችሁ ይላል ።

በ፬ኛ ዓመት ጥቅምት ፳፱ ቀን ፵፭ ቍጥር ፫፻፶፮ ገጽ ብታተመው ጋዜጣ ክቡር ግራዝማች ካሣ አባውቃው ያባታቸው የነበረውን የመንግሥት ዘበኛ አለቅነት ተሾሙ ብሏል ግን ክቡር ግራዝማች ካሣ ያባታቸው አሽከሮች የነበሩትን ባልደረብነት ተቀብለው ሰዶ ውሥጥ ማደሯ ተደርጎላቸው ተሾሙ።

መወድስ ዘወልደ ኪዳን

ኢትዮጵያ ኅደገት ግዕዘ ሰማርያ ።
ወአሐረት ክዕበ በዘሰማርያ ፍኖት ።
እስመ ዕደዊሃ ታበጽሕ ለኃይለ ሥላሴ መንግሥት ።
ወበዕደ ኢታንግሥ ኢትሐሱ ግብራ ከማሃ ለዘይት ።
ወሕዝብ ኢትምክሩ።
በዘመርከሙ ምክር እስመ ትውዕዩ በእሳት ።
ሰማይሂ እመ ወረደ ወእመ ዓርገ መሬት ።
ኢይወርድ እመንበሩ ኃይለ ሥላሴ ወልደ ዳዊት ።
ወአስከለ ጥበብ ተፈሪ ምድረ ምኒልክ ሠናይት ።
ነሡአ ኃይል ቄናጽል አምጣነ ተሠግሩ በመሥገርት።

የሀብት ዕውቀት

፩ኛ ክፍል ምዕራፍ ፩

፩ኛ። ኤኮኖምያ ፖሊቲክ ማለት ምንድር ነው? ቃል በቃል እንደ ፊደሉ ትርጓሜ በግሪክ ቋንቋ የቤት ሕግ አገዛዝ ወይም የቤተ ዘመድ መልክም የጥበብ አገዛዝ እንደ ማለት ነው ። ዋናው የአሳቡ ትርጓሜ ግን ኤኮኖሚያ ፖሊቲክ ማለት የሀብት እውቀት ነው ። ይህች ትርጓሜ ግን እንደ ሐሳባችን አካሄድ በትክክል ግልጥ ስላይደለች ዋናውን እውነተኛ ትርጓሜዋን ለይቶ ማወቅ የሚያስፈልግ ነው ። ግልጥ አይደለችም ያልኩበትም በኤኮኖሚያ ፖሊቲክ ሀብት የሚባልና እኛ ሀብት ብለን የምንጠራው የተለያየ ስለ ሆነ ነው ።

ኤኮኖሚያ ፖሊትክ ማለት የመንግሥት ሀብት ናት። አንዱን መንግሥት ከሌላው መንግሥት ዝቅተኛ ወይም ከፍተኛ ድኃ ወይም ሀብታም የሚያደርገው ነገር ትመረምራለች። የተሻለውንም መንገድ ታሳያለች የሕዝቦችን መልክም አኑዋዋር የሥራቸውንም ዋጋ ከፍ አድርጎ በመስጠት ሕይወታቸውንም ለማሻሻል ማለት በበለጠ ሕይወት ለመኖር ታስተምራለች።

ስለዚህ ብዙ ሕዝቦች በመልካም አናንዋር ለመኖር የሀብት እውቀት የምታስፈልጋቸው ናትና ብዙ ዕጥፍ አድርገው ሊያገኙዋት በጣም ይጥራሉ። እርስ በእርሳቸውም ሊከፋፈልዋት በተሻለ መንገድ ሊፈጽምዋት በጣም ከፍተኛ ትርፍዋንም በትንሽ ድካም ለማግኘትዋ ይጥራሉ ።

ሌሎችም እውቀቶች እንዲሁ የመሰለ ብዙ ጥቅም ይሰጣሉ ። የሚኔራል እውቀት በመሬት ሆድ ውሥጥ ያለ ሰውን የሚጠቅም ነገር ሁሉ፤ የከዋክብት እውቀት ለትልልቆች ባሕር የመንገድ ፤ የሜካኒኬ እውቀት ኃይሉ እንዴት አድርጎ እንዲሰበስብና ማኪናውን እንዴት አድርጎ እያዘዋወረ እንደሚሠራ- የኪሚኬ እውቀት እኛ የማይረባ ከሚመስለን ነገር የሚጠቅም ሁሉ እንዴት አድርጎ እንደሚወጣ ያሳየናል፤ ይመራናልም።

እንዲሁም የተከከለች እውቀት የሰው ደግነት ለበጎነት ሥራ (ሞራሊቴ) የሚገባ እውነተኛን መንገድ የምታመለክት የፍትሐ ነገሥት እውቀት የዚህ ዓለም ሰዎች ሊያደርጉት የሚገባቸውና ቢያገኙት ያላቸውን እውነተኝነትን የሚጠብቁበት የፍላስፋነት እውቀት የልዩ ልዩ መንግሥታት መሠረትና አኳ

ኋን ወይም እያንዳንዱ መንግሥት አቋቋምና ጥቅሙን አፈላለግ፤ የመድኃኒት እውቀት የበሽታንም ምክንያት ሁሉ ማስረገጥ የስታትስቲክ እውቀት የመንግሥት ዓይነት ስብሰባ መግለጥ ይጠቅማል ።

እነዚህ ያመለከትኩዋቸውና እነሱንየሚመስሉ ያላመለከትኩዋቸው እውቀቶች ሁሉ ባጣም የሚጠቅሙ መሆናቸውን ጥርጥር የለበትም በጭሩ በጤና ለመቀመጥ እንዴት ብለን መኖርእንደሚገባንና አስተዋዮችና ሀብታሞች እንድንሆን ያስተምሩናል።

የሀብት እውቀት ግን ከነዚህ ሁሉ በተለየች ነች ማለት ሁለት ሥርዓት በፍርድ የተሰማማ አላት አንደኛይቱ የሀብትን ሁሉ ተአምራት አፈላለግ ሥርዓት ታስተምራለች ሁለተኛይቱ እያንዳንዱ (ነፍስወከፍ) ሰው ይሁን መንግሥት ለጥቅሙ በቀጥታ ምንሊያደርግ እንደሚያስፈልገው ትነግራለች ።

የፊተኛይቱ ሥራ ረቂቅ ነች ሁለተኛይቱ ግን የምትታይ ጉልህ ነች ማለት ለሰው ለመንግሥት ለሕግ አውጪ ለኢንዱስትሪ ጌታ እነሱን የመሰሉ ሁሉ በጊዚያቸው የሚመጣና የሚከተለውን የአኳሆናቸውን ነገር ማለት የሀብት እውቀት ፕሮብሌም አውጥቶ ማግኘት ትሰጣለች

በዚህ ዘመን ብዙ ልዩ ልዩ የሆኑ እየተፈተኑ አዲሶች እውቀቶች ይፈጠራሉ ። እንዲሁም ኤኮኖሚያ ፖለቲክ ለማቆም ዕጥፍ የሆነ ክፍል ሥርዓት ያመለክታል።አንደኛው ሥርዓት በዋናው የሚፈጸመውና የሌሎችን አሠራርና አደራረግ። ሁለተኛው ሥራት ባህል ፈተና ልምድ ታሪክ ለመሆን ይችላሉ ባጭሩ) የኤኮኖሚያ ፖሊቲክ ታሪክ ማለት የኢንዱስትሪ የንግድ የእርሻ የባንክ የግምጃ ቤት ፊናንሳ ሥራትና መሠረት አኳሆንና አፈጻጸም ነው ።

ሚካኤል ተሰማ።

ከዚህ የቀረ በሚከተለው ይታተማል

ስለ ክቡር አዛዥ ወርቅነህ መግባት

ክቡር አዛዥ ወርቅነህ ከክብርት ባለቤታቸው ከወይዘሮ ቀፀላ ወርቅ ጋራ ወደ አውሮጳ ሒደው ነበርና ሕዳር ፰ ቀን አዲስ አበባ ገቡ ።

ብርሃንና ሰላም ለክቡር አዛዥ ወርቅነህና ለክብርት ወይዘሮ ቀፀላ ወርቅ እንኳን በደኅና ገባችሁ ይላል ።

ማስታወቂያ ።

እኔ ባላምባራስ ጠይቃቸው አዝልቅ መስከረም ፳፪ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም ሐረር አውራጃ ጠይቃቸው አዝልቅ የሚል ማኅተሜ ጠፍቶብኛልና ከዚህ ቀደም በማኅተሜ የተዋዋለ ሰው እስከ ፲፰ ቀን የውሉን ወረቀት ያምጣ ከእንግዲህ ወዲያ ታትሞ ቢገኝ አይረጋብኝም ጥቅምት ፳፱ቀን ፲፱፻፳፩ ዓመተ ምሕረት ።

ባላምባራስ ጠይቃቸው አዝልቅ ።

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ ኦቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጦጦን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።



አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባ ኪሎሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባትሪ ነው ክምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል «ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው

ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ፡ ሱቅ ይገኛል ።

COGNAC S.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA



ዝኒት እጅ ሰዓት ።

በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቀቅዎታል

“ሩግቢ” የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጸ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል“አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ” ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

RUGBY

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ሳስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፥ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ባርባሬሶ

ኮ ኛ ክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪመኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽናባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ።

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በካፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በካፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዊድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad



ዓለም ሱቅ ፲፪ ዓይነት የተሰማ እሺቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዳቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቀደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ፤ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል

አደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ሱቅ ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

ድ ራ ሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ በዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪከን ቤት ይሠራል ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ሲሔድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራነው በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬንግ ኩባንያ ቤት ነው ።



2-28-15

ጉዩየር ግዙ

በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አራተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፵፯
4 me ANNÉE № 47

ሐሙስ ኅዳር ፲፫ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም ።
JEUDI 22 NOVEMBRE 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voi regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ቢገዛ ስለአንዱ ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ታላቅ የደስታ ምስራች ።

ሠረቀ ለነ ብርሃን እምሥራቅ እስከ ምዕራብ ።

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ተፈሪ መኰንን መስከረም ፳፯ ቀን ንጉሥ ስለ ተባሉ የዚያች ዕለት እሁድ በ፲ ሰዓት ወለጋ ሰዮ ከተማ በቴሌግራም የምስራች ቢሰማ ከተማዋ በደስታ ተናወጠች።ስልከኞችም በከተማ ላሉት ሹማምንቶችና መኳንንቶች ጉምሩክ ድረስ እዲሰበሰቡ ነግረውነበርና የከተማው ዳኛ ጠሩምባ ባስነፋ ጊዜ የከተማው ሰው ሁሉ እጉምሩክ አጥር ግቢ ገባ ወዲያውም የስልኩ ሹም አቶ ብዙ ወርቅ ዜና ይህችን ልክ የሌላት የደስታ ምስራች ልዑል ጌታችን ንጉሥ ተብለው ዘውድ ጫኑ ብለው በተናገሩ ጊዜ የተሰበሰበው ሰው ሁሉ አንድ ጊዜ ግባት ቢተኩስ መሬቷ አረገደች ቀጥሎም የከተማው ሴቶች የደስታ ድምፅ በዕልልታ ቢሞሉ የከተማዋ በደስታ ማሸብሸብ ከቶ እጅግ ያስደንቃል። ቀኑም ከጧት ጀምሮ ዝናብ ስለነበረ ብርድ ቆይቶ ነበርና በ፱ሰዓት ፀሐይ ወጥታ ምድሩ ሁለመጠጠ የጊዜው ደስ ማሰኘት እንደ አንድ ታላቅ ዓመት በዓል የከበረ ሆነ የተሰበሰበውም ሰው በደስታ ጨዋታ እስከ ፲፪ ሰንት በጉምሩክ አመሸ በኋላም የሰዮ ጉምሩክ ግምጃ ቤት ሹም ክቡር በጅሮንድ መኰንን ወደቡና ቤት ሄደን ስለ ደስታው በዓል እንጨዋት ስላሉ የተሰበሰበው ሰው ተነሥቶ ወደ ቡና ቤት ሄደ ቡና ቤቱንም ክቡር በጅሮንድ መኰንንና የግምጃ ቤቱ ጸሐፊ አቶ ስነ እንደ ሚገባ አሰናድተውት ነበርና መኳንንቱም ገቡና በተሰናዳው ስፍራ ተቀመጡ በቤቱም ውሥጥ የልዑል አልጋ ወራሽ ፎቶግራፍ በተቀማጩ ፊት ለፊት በግርግዳው ላይ ነበር። ሰውም ያንን እያየ በደስታ ፈንጠዚያ ደስ ብሎት በያይነቱ መጠጥ ቀርቦ ሲጫወት ቆየ። የከተማውም ሰው በየቤቱ የደስታ ዘፈን እየዘፈነ ፈንጠዚያ አድርጎ ሌሊቱን ሁሉ በጠመንጃ ተኩስ አደረ።በቡና ቤቱም የተሰበሰቡት የከተማ ዋና ዋኖች ሽማግሌዎች ሹማምንትና ሠራተኞች ነበሩ እንደዚህ በታላቅ ደስታ አምሽተው በሸምፓኝ ጊዜም ልጅ ደምሴ ወልደ አማኑኤል ያልከል መኖፖል በምዕራብ በኩል ሹም ስለደስታው፩ዲስኩር ቀጥሎ ያለውን ለመናገር በቆመ ጊዜ ሰው ሁሉ በጸጥታ ይሰማ ነበር ።

ክቡራን መኳንንትና ጌች ሆይ ።

የዛሬ ቀን ይህችን ለደስታዋ ልክ የሌላትን የምስራች ያገኘንበትና በዚህ ስፍራ የተሰበሰብንበት በተለየ የደስታ ቀን ተብላ ለልጅ ልጅ እንደ መታሰቢያ ሁና ለመኖር የተገባት ነው ማለት ዛሬ በዚህ ስፍራ እጅግ ወሰን በሌለው ደስታ መሰብሰባችን የልባችን ሐሳብ አንድ መሆኑን ለገናናው መንግሥታችን የሚገልጥልን ነው። ጓን ሰውነታችን በደስታ ግርማ ተይዞ እየ ተንቀጠቀጠ ከተማችንም ገና ወሬው ሳይደርስላት በደስታ ማሸብሸቧን ለሀገራችን ደስታችንን ለመግለጥ የደስታው ድንጋጤ ምንም አፋችንን ቢዘጋው ታግለን የወጣነው ደስታ የሚበቃን አይመስለኝም።አንድ ምሳሌ የታላቅ ደስታና የታላቅ መከራ የወሬው ማስደንገጥ አንድነው ይባላል እንዲሁም እኛ የኢትዮጵያ ልጆች አገልጋዮችም በደስታ ከነከተማችን ተጨንቀን ልክ በሌለው የደስታ ማሸብሸብና በዕልልታ በማምሸታችን ለከፍተኛው መንግሥታችን ደስታው ታላቅ ነው ለማለት ያስደፍረኛል ።

ይህችንም የመላ ኢትዮጵያን ልብ ዘልቃ የምትነካ የደስታ የምስራች የዋለችበት በሺ ፱፻፳፩ኛው ዓመት በመጀመሪያው ወር ከወሩም በ፳፯ተኛው ቀን መሆኑዋን ለልጅ ልጅ መታሰቢያ እንድናስቀምጣት አሳስባችኋለሁ ጌቶቼ ሆይ ዛሬ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ጌታችን የሥልጣን

ክብርና ታላቅ የበለጠውን ሹመት ማግኘት ከእግዚአብሔር በውነት የተፈቀደ መሆኑን አጽንቶ ገለጠልን።ይህውም በእርግጥ ለኢትዮጵያ በፍጹም ልባቸው ተጨንቀው እንዳገለገሏት ለኢትዮጵያ ሰው የሚያስረዳ ነውና ስለዚህ ለደስታችን ወሰን የለውም።ክልክም አልፍዋል ዳግም ሕዝብ ሁሉ አንድ ልብ መሆኑን ያስረዳን እኛ የደስታውን የምስራች ገና ስንሰማ ከተማችን በዕልልታ መናወጥ ደስታዋን በመግለጧ ቀደመችን። መኳንንቶች ሆይ ዛሬ ቀን በመሃከላችን ክቡር ጌታችን ደጃዝማች መኰንን ወሰኔ ደግሞ ክቡር ነጋድራ ታፈስ ቢኖሩልን እንዴት ደስታችንና ድምቀታችን በበዛልን ኖሮአል ቢሆንም ደግሜ ለደስታችን ወሰን የሌለው መሆኑን እገልጣገሁ ። ጌቶች ሆይ ምንም በደስታ ብዛት በልባችን የበለጠ ደስታ መኖሩን ለመግለጥ የበቃ ምሳሌ ባለመናገሬ ኀዘኔ ብዙ ነው። አሁንም ልዑል ጌታችን የመደምደሚያውን ማዕረግ ለማግኘታቸውም ምንም ልቤ ባይጠረጥር ንጉሥነታቸውን አዳብሮ ጤናና ሰላምነት ያድላቸው ስል ምኞቴን እገልጻለሁ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታታችንም ረጅም ዕድሜ ሰጥቶአቸው ከስተዋዩ ክብ ልሁ ልጃቸው ጋራ ኢትዮጵያን በብርሃን ጉዳና በሰላም አራምደው ከጎደኞችዋ እስኪያደርሷት እግዚአብሔር ነጻነቷን ለዘላም ይጠብቅልን ። ንጉሥ ሆይ እንኳን ደስያለዎ ብዬ ስለጤናዎ እዚህም ስለተሰበሰባችሁት ክቡራን መኳንንቶችም ስለ ኢትዮጵያም ሰላምነት በልዑል ፎቶግራፍዎ ፊት ቆሜ ጽዋዬን እነሣለሁ።ብሎ በጨረሰ ጊዜ ሶስት ጊዜ ከዳር ዳር ጭብጨባው ቀለጠ ። ቀጥሎም የሰዮ ጉምሩክ የጸሐፊዎች ሹም ክቡር አቶ ደመቀ ኪዳኔ ከዚህ በታች ያለውን ተናገሩ ።

ጌቶቼ ሆይ የዛሬ ቀን ቀድሞም በነቢያት ክቡር ዳዊት ዛቲ ዕለት እንተ ገብረ እግዚአብሔር ንትፌሣሕ ወንትሐሠይ ባቲ ብሎ ተናግሮላታል።ዛሬም ደግሞ የልዑል ጌታችን ደስታ ስለተደረገበት እጅግ ደስ ይለናል። እግዚአብሔር ልዑል ጌታችን አሰንብቶልን ስለግርማዊት ንግሥት ነገሥታችንም እረጅም ዕድሜ ስለ ኢትዮጵያም ሰላምነት ብዬ ስለጤናችሁ ጽዋዬን እነሣለሁ ብለው ሲጨርሱ ተጨበጨበላቸው። ቀጥሎም የግዳሚ ስልክ ቤት ሹም አቶ ሙላቱ ከዚህ በታች ያለውን ቃል ተናገሩ ። መኳንንቶች ሆይ የልዑል ልዕልናታቸው በትዕግሥታቸው ነውና እግዚአሔር ትግዕሥታቸውን አሰንብቶላቸው ወደ ሥልጣኔ ብርሃን እንዲያደርሱን እንለምናለን አሁንም ስለተቀመጣችሁት ክቡራን መኳንንቶችና ስለልዑል ንጉሣችን ስለ ግርማዊት ንግሥታችን ጤና ጽዋዬን እነሣለሁ ብለው ሲጨርሱ ተጨበጨበ።

ቀጥሎም የቡና ቤቱ ባለቤት ሙሴ ቴዎፋኒ ደቢስ ለደስታው ደስ የሚያሰኝ ነገር ተነጋገሩና ተጨበጨ። ከዚህ በኋላ ዓቢይ ኃይሉ የሚባል ደብተራ ቀጥሎ ያለውን መወድስ ስለደስታው ሰጠና ተጨበጨበ

መወድስ

ኃይለ ሥላሴ ወንጌል ክብረ መኳንንት ።
ዲበ አትሮንስ ደብር ይትነበብ ለለጽባሑ ።
እምጣነ የሐሮ ሰበአ ትርጓሜ ዘእሁ ።
በቅጽበት እስከነ ተነግረ መለኮት ዜናሁ።
ወዓፀፍተ ክብር መኳንንት ።
በበደወሎሙ ቆሙ ጠፈረከ ከመ ያብርሁ ።
መኳንንትሂ አመ ሐተቱ ቃለ ጳውሎስ አቡሁ።
ለኃይለ ሥላሴ መልከ ጼዴቅ እያአመሩ ክዋኔሁ ።
መንግሥቱ ክህነት እስመ ኢይሠዓር ናሁ ።
ለዓለም ተክህኖቱ ድኅረ ኮነ ኬንያሁ ።

ቀጥሎም የከተማው ጭቃ ሹም አቶ ቦሮ ጃራ ተነሥቶ ስለጌታችን ደስታና ክብር እኔ ነገ መኳንቶችን ሁሉ ግብዣ እችላለሁ ብሎ ስለተናገረ ተጨበጨበለት እንዳለውም በነጋው በቤቱ ታላቅ ፈንጠዚያ አድርጎ ሌሊቱን ሁሉ በደስታ አሳደረ ።

የሰው ደስታ ነገር እንዲህ ነው ተብሎ አይነገርም የተሰበሰበውም መኳንንት ሁሉ በየተራ ስለ ደስታው ምርቃት እየተናገረ በሰላም ወደ ቤቱ ተመለሰ እንዲህ አድርጎ የሕዝቡ ልብ በደስታ መናወጥ እጅግ ያስደንቃል እግዚአሔር ልዑል ጌታችንን ንጉሣችንን አስንብቶልን እኛን ሕዝቦቹንና ሃገራችንን ኢትዮጵያን በብርሃን ጉዳና በቶሎ አራምደው ከጎደኞቿ እንዲያስተካክሏት እግዚአብሔር ይርዳቸው ዕድሜ ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዕድሜ ለልዑል ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር ።

የብርሃንና ሰላም ተላላኪ።

በከተማ ስለሚገኝ ጉዳት ።

እህል የሚወደድበት ምክንያት ይህ ነው ከአገሩ ሲወጣ ወደአዲስ አበባ ሔደን ለጌታ እናድራለን ወይም እትምህርት እንገባለን እያሉ በየገሩ ያለ ጐበዛዝት ይመጣና ጌታ አዳርነት ይገበና ወይም ትምህርት ቤት ያላገኘው ግን ነገ አገኝ ሲል ጊዜውን ሲያሳልፍ ይቆይና የሚበላውና የሚጠጣው የሚለብ ሰው ያጣና ኋላ ግን በእናት አባቱ ሌብነት ያልነበረው የግድ ወደ መስረቅ ይሔዳል እነዚያም እንደሱ ተጨንቀው ተጠበው ወደ መስረቅ የገቡት ሰዎች እንደ አንድ እውቀት ተምረው ይቆዩና ያሰው ወደእነሱ ሲገባ ሳለ በደስታ ይቀበሉትና እንዳይከዳቸው ማልልን ይሉታል ከዚያ ወዲያ እነዚያ ሰዎችና እርሱም በርሳቸው እየጠነከሩና እየበረቱ ይሔዳሉ ።

ምን አልባት ፩ ወታደር ለወር ተራ ወይም ለጉዳይ ሲመጣ እንድ ቀን ወደ ገበያ የወጣ እንደሆን ብቻውን መሆኑን ያውቁና አንድ ከርሳቸው ይመጣና በጥፊ ሲመታው ሰማይና ምድር ይዞርበትና ፊቱን እስኪያባብስ ድረስ ጥይቱን ከወገቡ ይሞሽልቁታል እና የታባቱ ይህ ሌባ እያሉ ያልሰረቀውን ወታደር ከየትም ተሰብስበው ይሰድቡታልና ከርሱም ይሰወራሉ ። በፊት ሲመቱት በመድኃኒት ስለሆነ አፉ ይዘጋና ዝም ብሎ ወደ ሰፈሩ ይኼዳል ነገር ግን መስረቅና የተንኰልን ሥራ ትተን እርስ በርሳችን ብንፋቀር ለለምለሚቱ ለኢትዮጵያ ጥቅም እንሆን ነበር ።

ደግሞም መስረቅና የተንኰል ሥራ ለነፍስ ሆነ ለሥጋ ሆነ ጉዳት ነው እንጂ ጥቅም አይዶለም ለሥጋም ሆነ እስከ ሚታይበት ቀን ድረስ ነው እንጂ በእሥራት ይቀጣል ለነፍስም ሆነ አትስረቅ ብሏልና ታላቅ ቅጣት ይቀጣል ነገር ግን እግዚአብሔር አምላካችን ለሰው ልጆች ይራራልና ቁጣውም በሰው ልጆች ላይ ይዘገያል እግዚአብሔርን አመስግኑ መልካም ነውና ቸርነቱም ለዘላለም ናት መዝሙር ፻፲፰ ቁጥር ፩ተመልከት

ሰው ግን እንደ እግዚአብሔር ቢታገሥና ቢራራ ዋጋችን እንዴት ታላቅ ይሆንልን ነበር ሰው ግን እንኖራለንነው እንጂ እንሞታለን የሚል የለም

ነገር ግን በልጅነታችን ዘመን ወደ አምላካችን ብንቀርብና በትእዛዙ ብናደር ለሥጋችን (ለዋጋችን)እንዲረዳን ጥርጥር የለውም።በልጅነትህ ወራት ፈጣሪህን አስብ፡መክ። ፲፪ ፩ተመልከቱ።

ምናልባት ደግሞ እየጌቶቹ ቤት ገብቶ ኑሮ ደምወዙ ወይም ስለ ሥራው ጉዳት ተጣልቶ ይወጣልና ሥራ እስኪያገኝ ድረስ ጊዜውን ምንም ጥቅም ሳያገኝበት ያሳልፋል ወደ ብር አላፈራ ወይም የእጅሥራ አልተማረ ጥቂት ቋንቋ የተማሩትንና ልብሳቸውን አንጥተው በሥራቸው ያሉትን አሽከሮች እያየ ዘመኑን ሁሉ ሲጸጸት ይኖራል ነገር ግን መንግሥታችን እንደሌሎች አገሮች ሥራ ለአጡት ሥራ ቢሰጥና አንድ ሰው በከተማ ውሥጥ አለ ሥራ እንዳይሔድ ቢከለከል በየአገሩ ገብቶ እኩሉ አረሽ እኩሉ ነጋዴ ይሆን ነበር ።

ይህንንም ማለቴ ሰው ሠርቶ እንዲበላ ነው እንጂ እንዲያው ሳይለፉ እንዱ የለፋበትን እንዱ ሲቀማ ነው ጉዳቱ እንጂ ጠንክሬ ሥራ እንኳ ቢያገኝ ሠርቶ ቢበላና ለኑሮው ቢያስብ የተገባ ሥራ ነው አሁንም ቢሆን መንግሥታችን እንደዚህ ያለ ሥራ እንዳይሠራ ሥራ ላጣው ሥራ ቢሰጥና ቢከባከበው ሰውም እየእንዳንዱ ሥራ ወዳጅና ላገሩም አሳቢ ይሆን ነበር። መቼስ ሥልጣኔ በአንድ ጊዜ አይመጣምና ጥቂት በጥቂት አንዱን አሳብ ከፈጸሙ በኋላ ሌላውን ቢጀምሩ ይሻላል አዲስ ብልኃት ከቆሙ በኋላ ሌላውን ቢጀምሩ ያ የፊተኛውን ጥበብ ያየ ሁሉ እውቀት ወዳጅና አዲስ ጥበብ ይሻል በየግዛቱ ያሉትን ገገሮች ሁሉ ተማሪ ቤት እንዲያቆሙ ሰው ሁሉ በሥራው እንዲጸና ገበሬ እንዲያርስ ነጋዴም እንዲነግድ ሰው አለሥራ እንዳይኼድ ደንብ ማቆም የተገባ ነው ድኃ አበሳውን አይቶ ያከማቸውን መቀማት አይገባም ። ድኃ ጥቃት የበዛበት እንደሆነ የለፋሁበትን ይቀሙኛል እያለ አገሩን ትቶ ወደ ባዕድ አገር እንዳይሰደድ ድኃውን እንርዳ ለአገራችን ለለምለሚቱ ኢትዮጵያ ሕዝቡ እንደ ልቡ ቢሆን ነው እውቀት የሚመጣና ከሁሉ በፊትም መንግሥታችን ይህን ሐሳብ እንዲፈጽመው በተስፋ አይን እንጠብቃለን ። ወልደ ሥላሴ ።

ስለ አማርኛ መዝገበ ቃላት (ዲክሲዮኔር)

ይድረስ ለክቡር አቶ ሣህሌ ፀዳሉ የትምህርትና የጥበብ ሚኒስቴር ዲሬክተር

ብዙ ሊቃውንት መርምረው እንደሚናገሩ እንደ ሰው ትውልድ ሁሉ ቋንቋም ወላጅና ዘመድ ወገንና ወንድም እንዳለው ያውቃሉ እንደዚሁ ዕብራይስጥና ግዕዝ አንድ ወገን አንድም ወንድማማች ይመሰሰላሉ የግዕዝም ቋንቋ አማርኛን አረብኛን ትግርኛን ደግሞ ሌሎችንም እንደ ወለደ በብዙ ማስረጃ ተገልጸዋል ቋንቋም የቀድሞው እየጠፋ አዲስ እየተወለደ ይኸውም አዲስ የተገኘው በየሐገሩ እየተለዋወጠ ሲለያይ የሚኖር የልሳንን ቃላት ጠንቅቆ የሚያቆይ መዝገብ እየተጻፈ ባለ መቀመጡ ነው ከብዙኅ ዘመን ጀምረው የሠለጠኑ የአውሮፓ መንግሥታት ከዚህ ታላቅ ጥፋት ለመዳን ብለው ቋንቋቸውን እንደ ፊደሉ ተራ በመዝገብ አስጽፈው ዲክሲዮኔር የሚባል መጽሐፍ ስላቆሙ ይኸው መጽሐፍ ለብዙ ጥበብ ምንጭ ሁኖዋቸው ይኖራል የሰዋስው መንገዳቸውንና የግሥ እርባታቸውን ሌሎችን አገባቦችንም ሁሉ የሚያስተካክሉ የጠመመውን የሚያቀኑ የጐደለውንም የሚሞሉ አርባ ሊቃውንት ተመርጠው ከዘመን እዘመን ሥራቸውን ሳያቋርጡ እንደሠሩ አሉ አሁንም ያማርኛ ቋንቋ እንደ ሌሎች ሕዝቦች ቋንቋ ሰፊ ነው ይባላልና የኢትዮጵያ መንግሥት እንደዚሁ እንዲያደርግልን ሙሉ ተስፋ አለን ለጊዜውም ይህን ሥራ ለመጀመር ከሐገራችን ሊቃውንት ሐያ አዋቂዎች ቢመረጡ ይበቁ ይመስለኛል ባስፈለገም ጊዜ ቁጥራቸውን ከፍ ለማድረግ ይቻላል መቼም ይኸው መጽሐፍ ቢወጣና ቢታመም ለመንግሥት ከራሱ ይልቅ ዋናው ጥቅሙ ለመላ ለኛው ለሕዝቡ ነውና ይህኑ ሥራ በቶሎ እንዲከናወን ለማድረግ ማናችንም ኢትዮጵያዊ የገንዘብ እርዳታ እንዳቅማችን ለዚህ ለመልካም ሥራ ለማድረግ የተዘጋጀን መሆናችንን ለክቡርነትዎ አሳስባለሁ ። የዚሁም መጽሐፍ (ዲክሲዮኔር) ስም የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ለኢትዮጵያ ሕዝብ መታሰቢያ ሽልማት ተብሎ ሊሰየም የተገባ ነው ።

ክቡራን የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ሆይ ከዚህ በላይ በጠባብ ዕውቀቴ የታየኝን ሐሳብ የጻፍኩትን በጐደለ እንድትሞሉበት በጠፋ እንድታርሙልኝ እለምናለሁ

አክባሪዎ ብርሃን ሐብተ ሚካኤል

መልካም ነገር ።

አንተና ወዳጅህ መልካም ወዳጅነት ማግኘት ብዙ ገንዘብ የማግኘት ያህል ነው።ወዳጅም ማለት የልብን አሳብ ሁሉ የሚፈጽም ነው ። ሰው ላንተ መልካምና ደግ የሚያስብ ማለፊያ ወዳጅ ማለት ነው ። በዚሁ በመኖር ዓለም ውሥጥ ኰራተኛ ምቀኛ አጮላይ ቀማኛ በያለበት መልቷል ። መልካም ወዳጅ ማግኘት ግን በጣም ያስቸግራል ። ስንትና ስንት ሰዎች ትዳርህንና ገንዘብህን ጤናህንም መንጠቅና ማጥፋት ይፈልጋሉ ። እውነትም ባያሌ ሰዎች ውሥጥ አለ ጥርጣሬ ችግርህንና የልብህን አሳብ ሁላ አውጥተህ ለመናገር እውነተኛ መልካም ወዳጅ ብታገኝ ትልቅ ደስታና እምነተኛ አገኘህ ማለት ነው ። እውነተኛ መልካም ወዳጅ አግኝተህም እንደሆነ ዕድለኛ ትባላለህ። ስለ ሆነ ግን ወዳጅህን ካላከበርክ እሱም አንተን ካላከበረ ያ ወዳጅህ በቶሎ ይሸሽብሃል። ወዳጅህም ገራምና እምነተኛ ኰራ-

ትም የሌለበት የሆነ እንደሆነ አንተ ግን በልብህ ክፉና አሳብቂ ወይም ሹራት የኖረብህ እንደሆነ አንድ ቀን ካንድ ቀን ያወዳጅህ ካንተ መሸሹ አይቀርም ። ብዙ የሚያሳዝን ገንዘብ የጠፋብህም እንደሆነ አያሳዝንህ ፡ነገር ግን መልካም ወዳጅ ቢጠፋብህ እውነት የሚያሳዝንህ ነው ። አለ ወዳጅ መኖር አለ ደስታ መኖር ያህል ነው ። ይልቁንም ሰው በተቸገረ ጊዜ ወዳጅ ያጣ እንደሆነ አሥር ሀብታም ቢሆን ድኅነት የመጣ ያህል ነው ። ብዙ ሰው እጅግ ገንዘብ አግኝቶ ወዳጅ አጥቶ የሚኖር አለ ። እንደዚሁም የሆነው ሰው ቢሞትም የሚያዝንለት ይጠፋል ። ወዳጅን መውደድና የማግኘቱን አእምሮ ልመድ በመልካምና በደስታ በዚህ ዓለም መኖር የፈለገህ እንደ ሆነ እበክዎ የሚባል እውቀትና እንዲህ ያለም ሌላ ለመልካም እውነተኛ ወዳጅህ ችግርህን ያጫወትክ እንደ ሆነ ችግርህ ይጋመሳል። ደስታህንም ያጫወትክ እንደ ሆነ ደስታህ የበዛ ይሆናል ።

ክሬክር ዳረክድያን

የሃይማኖት የፍቅር ሥራ ።

የተዋሕዶ ሃይማኖት ነገር ከጥንት ከባቶቻችን ሲነገር የመጣው የባሕርይ አምላክ ለሰው ልጆች ሲል ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ በጥምቀት የሥላሴ ልጆች የምንሆንበትን በማይናወጥ ኪዳን አትሞ ሰጠን ።

ለምለሚ ኢትዮጵያ ከብዙኅ ዘመናት ጀምሮ በነበሩት ኃያላን ነገሥታቷ ሁሉ በእግዚአብሔር ቸርነት የኦርቶዶክስ ሃይማኖቷንእንዳጸናችና የከበረ ነፃ መንግሥቷን ስትጠብቅ የቆየች መሆኑዋን በልዩ ልዩ ታሪክ ተጽፎ ትገኛቷል ።

ደግሞ ያለም ነገሥታት ሁሉ በውቀት ደረጃ ላይ ወጥተው የሥጣኔ ሥራቸውን ሲያደራጁ ኢትዮጵያ ወደኋላ እንዳትቀር የሙቀት ፍለጋቸውን ይዛ እንድትከተል ሲሉ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ ከውጭ አገር ወደ ኢትዮጵያ የመጣነውን ሁሉ በፍቅር መቀበል ጀመሩ ። ከዚያም ወዲህ ለኢትዮጵያ የውቀት ብርሃን እየተገለጠላት እንዲሄድ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክንና ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን እነገሠላት ። አሁን ዛሬ ከዚህ ያለ ነው የውጭ አገር ሰዎች ለኢትዮጵያ ከልባችን አሳቢ መሆናችን የታወቀ ስለሆነ ይልቁንም ግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱና ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንንን ከዓለም ነገሥታት ጋራ በጠበቀ ዝምድና አስተማሥረው ፍቅረ ሰላምን ባወረዱላት ጊዜ የተባረከች መንግሥት አሰኙዋት እኔም የኢትዮጵያን ምስጋና ጨርሶ ለመጻፍ እንኳ ባይሆንልኝ የልቤን ፍቅር የገለጥኩበት ምክንያት በመጀመሪ ከዛሬ ፲፫ ዓመት በፊት የሙሴ ኬዎርኮፍና የሌሎችም ኩፓንዮች ወኪል ሁኜ በአልዩ አምባ ተቀመጥሁ

ከብዙኅ ቀን በኋላ እግዚአብሔር ልጅ ቢሰጠኝ በኦርቶዶክሳዊ ሃይማኖትና በፍቅር ከኢትዮጵያ አንድነት መሆኔን ለማስረዳት የመጀመሪ ልጄን ክርስትና አንከበር ለመስቀልኢየሱስ ሰጠሁ አሁን ከቅርብ ዘመን ወዲህ ባዲስ አበባ ተቀምጬ ደግሞ እግዚአብሔር ልጅ ሰጠኝ ።

የሃይማኖታቸውን ጥናትና የትክክል ሰውነታቸውን ነገር ተመልክቼ የሾሎ ገዢ ክቡር ደጃዝማች ወንድ ይራድ ልጄን ክርስትና እንዲያነሡልኝ ለመንኳቸው ።እሳቸውም የተማሩ ናቸውና ወዳጄ ሆይ በኦርቶዶክስ ሃይማኖትማ ከኔ ጋራ አንድ ተሆንክ እንዲህ ያለውን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ለመሥራት ዋና ፈቃዴ ነው ብለው ደስ አሰኙኝ በዚያው በተቆረጠው ቀን በ፲፱፻፳፩ ዓመተ ምሕረት ጥቅምት ፲፫ ቀን እሑድ ከሌሊቱ በ፲፪ ሰዓት ከየካ ሚካኤል ገስግሰው መጥተው በገነተ ጽጌ ገዳም በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን እንደሚገባው ሕግ አድርገው ልጄን ስሙን ገብረ ማርያም ብለው አሰይመው የመንፈስ ቅዱስ ልጅ አደረጉልኝ ይህ ደስታዬ አይወሰንምና እንግዲህ ከኢትዮጵያ የልቤ ፍቅር የማይነቃነቅ ሆነ ። ክቡር ደጃዝማች ወንድ ይራድ ክርስትናውን አስነሥተው ወደቤተ ክርስቲያን ከኛ ጋራ ገብተው ሥራቱ ቅዳሴው ሲፈጸም ተሰነባብተን ወደቤተ መንግሥቱ ሄዱ እኔም የውጭ አገር ሰዎች ብዙ ለክርስትናው ማቋቋም የመጡትን ይዤ ወደ ቤቴ ገብተን ብዙ ደስታ አድርገን ዋልን ።

ክቡር ደጃዝማች ወንድ ይራድ ለልጃቸው ለገብረ ማርያም የሰጡትን ቸርነት ሁሉ ከዚህ ላይ እንዳልጽፈው ላንባቢ ይሰለቻል ብዬ ነውና ክብራን አንባቢዎች ሆይ የኦርቶ ዶክስ ሃይማኖት የሠራልኝን ያንድነት ፍቅር የልቤን ደስታ ለመግለጥ ነውና ቃሉ በተሳሳተኝ ይቅርታ እለምናችኋለሁ ።

ሙሴ ሐይቅ ፖሙክያን የሙሴ ኬዎርኮፍ ዋና ጸሐፊ ።

(፪)በኤኮኖሚያ ፖሊቲክ ዙሪያ መሰሰት ።

ሊያውቁዋት ከሚገባቸው የሠለጠኑ ሕዝቦችም ብዙ ይሳሳታሉ። ማለት ብዙ ሰዎች ምንም ሳያጠንዋት ጥቅምዋን ሊያገኙ ይፈልጋሉ ለምሳሌ ብዙዎች ሰዎች ጉድለት የሚያፈራ ሥራቸውን ሳያስተውሉ ለለማኞች ምጽዋት ቢሰጡ እውነተኞች የሆኑ ይመስላቸዋል እነሱ የደግ ሥራቸውን ብቻ ነው እንጂ የሚያስቡ እነዚያ ለማኞች ከሩት ይልቅ እያደሩ እንደሚበዙ አያዩም የሚበልጥ ችግርና ቅምያ ሌብነትና መጋደል በፊት በለጥንቃቄ አሳብ ከተመጸወቱ መምጣቱንእያስተውሉም ማለት ከሕዝቡ የሚበልጥክፍል ተለግሞ ያድጋል አላስተዋይና ታካችም ይሆናል። ኤኮኖሚያ ፖለቲክ ግን ምን ያህል ቁም ነገር የሌለው ምጽዋት ለያንዳንዱ መስጠት በጅምላ ለሕዝቡ በሥራና በገንዘብ ማጠራቀም (መቆጠብ) ማሠልጠን ትርፍ እያገኘ እእዲኖርና ለሽምግልናው ጊዜ መጦርያ የሚሆነውን እየቈጠበ በአንድ ወገን እንዲያስቀምጥ ማስተማር ታሳያለች ርኅርኆች ነን የሚሉ አላስተዋዮች ሰዎች ግን የሀብት እውቀት ጨካኝና ደረቅ ነች ለሀብታም ሁሉ ጊዜ የበለጠ ሀብታም ልታደርግ ሀብታም ለድኃ አያግዝ ትላለች ብለው ይፈርዱባታል ይህ አሳብ ግን ጭርሱ ስተት ነው ።

ኤኮኖሚስታ ሀብትን በተመቹና የቀና መንገድ ለማግኘት ነው እንጂ ታካች ሰው ሊይዝ ወይም ገንዘቡ እንደ ስስታም ሰው ቀብሮ ሊያስቀምጥ ወይም እንደምናምንቴ ሰው በማይረባ ነገር ያጠፋውና ሊያባክነው አያስተምርም ።

ግን በማስተዋል ዘመዶቹንና ወዳጆቹን ሊያግዝ ለሕዝቡ ጥቅምም ሥራትና ሕግ ትምርትና የሕክምና ቤት (ሆፒታል) የተተከከለ መንገድና የከተማ ጥዳት መጻሕፍትና(ቢብሊዮቴክ)የትልልቆች ሰዎች ማስታዋሻ ሐውልት ሊያቆም እርሻና ኢንዱስትሪ ሊያሰፋ ንግድና የአገሩን ቋንቋ ሊያሠለጥን የማይገባቸውን ዕድላቸው የከፋ ሰዎች ሊያግዝ ማለት ዕውራን ሐንከሳን ድውያን ድኆች እነሱን የመሰሉ ሌሎችም ሁሉ ባጭሩ ራሳቸውን በገዛ ራሳቸው ሊጦሩ የማይችሉ ለሆኑ ሰዎች ሊያግዝ ያስተምራል ፡ኤኮኖሚስታ መሥራት ለሚቻላቸው ሰዎች ምጽዋት መስጠት ለተቀባዮቹ ጉዳት እንደሆነ በግልጥ ሊያስረዳ ነው እንጂ የሚፈልገው ፍቅር ርኅራኄ ውነተኛነት ከሁሉ መብለጡን አይቃወምም።

ሳይሠሩ ጥቅም (ገንዘብ) ለሚፈልጉ በሰው ጫንቃ ተጭነው የሚኖሩ በዘንተኞች ሰዎችና ብዙ ሺ አእላፋት ሰዎች ኑሮዋቸውን ለመሻሻል የድካማቸውና የጣራቸውን ብዛት አስበ ማመዛዘን ስንት ያሳዝናል ግን በሠለጠኑ አገር ከነዚሁ ሠራተኞችም ብዙ ገንዘብ ሳያፈሩ ብዙ ሀብት ይፈልጋሉና በጌቶቻቸው ላይ አድማ ይመታሉ በመንግሥታቸውም ላይ ሁውከት ያነሳሉና የአገራቸውን ኤኮኖሚያ (ሀብት) በጣም ይጐድዋታል ማለት ብዙዎቹ እውቀት ያነሳቸው ሠራተኞች ደመወዛችንን አብዙልን የየሥራችንን ሰዓት አሳንሱልን ሲሉ አድማ መትተው እንሠራም ይላሉ ጌቶቹም ሲርባቸው ይመለሳሉ ሲሉ ሥራውን ያቆማሉ ቤቱን ይዘጋሉ ከዚያ ወዲያ የሚከተለውን ሁውከትና ጠብ ችግርና መከራ ብዙ ነውና ለኤኮኖሚያ ፖሊቲክ በጣም ብዙ ጉዳት ይሆናል ስለዚህ አዲሶችን ባህሎች ወዲያው ከመከተል በፊት የኤኮኖሚያ መሠረት ማወቅ በግድ የሚያስፈልግ ነውና በቀጥታ ተምሮ ጠንክሮ መመርመር ይገባል ።

፫ የኤኮኖምያ ፖሊቲክ ጥቅም ።

የኢኮኖሚያ ፖሊቲክ ጥቅም የሚባል ለሰው የሚያስፈልግ የተተካከለ የትምርት አሳብ ብድር ለሰው ዘር ጥቅም የሚሆን ሁሉ ነውና ወደላይ የሚያደርሰን ምልክት (ማለት) ለትልቅ ሐመልማልነት ለሁላችን የዓለም ሰዎች የሥልጣኔ የሆነ ነገር ያስተምረናል ።

ለምሳሌ) የአሁኑዋ የእንግሊዝ ሐመልማልነትዋ(ጌትነትዋ) ከሁሉ ይልቅ የሀብትን እውቀት ሸንሴ ፖሊቲክ አዳሞ ዝሚትህ የሚባል ልጅዋ ስለ ሰጣት ነው ይባላል ይህንን ስሙ ለዘለዓለም የማይሞት ትልቅ ብልህ ሰው የኤኮኖሚያ ፖሊቲክ አብት መሥራች የመንግሥታት ሀብት የሆነውን የአእምሮውን ፍሬ ይሄው ዓለምን እንደ ፀሐይ ሲያበራ ይታያል መጽሐፉ ከታተመ እስከዛሬ ድረስ ፻፶ ዓመት ምሉ ከዓለም ሁሉ ብዙ ሊቃውንቶች ቢወጡም ከሱ ባህልና መሠረት አልወጡም በሥልጣኔ ሁሉ መንግሥታት የታላቅ አእምሮውን የሥራ ፍሬውን ቀድቶ የማይሠራለትና ለልጆቹ የማያስተምርለት አንድ ስንኳ አይገኝም። ከዚህ የቀረ በሚከተው ይታተማል ።

ሚካኤል ተሰማ።

ኦቤርላንድ



ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሽ ኦቤርላንድ ኦቶሞ ቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባ ኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኜቶና ባለባተሪ ነው ካምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ ኦቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል «ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው

ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

COGNAC S. & E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅስ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማተክ ከምርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



ዝኒት ፡ እጅ ሰዓት ።

በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፊረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬምርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩግቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ግልጹ ሰያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል "አረቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

RUGBY

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፡ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ባርባሬሶ

ኮ ኛ ክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽናባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ያሰናኟነት ፈቃድ የተቀበለ።

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በከፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በከፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዊድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad



ዓለም ሱቅ ፲፪ዓይነት የተሰማ አሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሲንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ፣ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል

አደጋዝማች ደስታ ዳምጠው ሱቅ ነው ።

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ሲሔድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራነው በሴላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬንግ ኩባንያ ቤት ነው ።



ጉድይር ግዙ

በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አራተኛ ዓመት ፤ቁጥር ፵፰
4 me ANNÉE № 48

ሐሙስ ኅዳር ፳ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም ።
JEUDI 29 NOVEMBRE 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen , profondément désireux de vo.) regner dans son pays la lumière et la paix , a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሊገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres



ስለ ሕዝብ አነዋወር ጥቅም የተሠራ ደንብ ።

አዋጅ

፩ኛ፤ ስለ ሀገር ማቅኛ

መሬት እያረሱ የሚኖሩ አራሾች የሕዝብ መጋቢዎች ስለሆኑ ከእንግዲህ ወዲህ የመንግሥቱ ያዋጅ ሥራ ይቅርላቸው

የሻለቃም የሆንክ ስለሁዳድ እርሻህ ገበሬው ቢወድ ባመት ሶስት ቀን ይረስልህ፤ ባይወድ ግን በተወሰነው ቁና ልክ ሶስት ቁና እህል ብቻ ይስጥህ እንጂ በጁ የሚያርሰውን ገበሬ ጭነት ጫን፡እርሻ እረስ፡አጥር እጠር፡ሸክም ተሸከም፡መጥን አግብ፡አልፍ አንግዳ እያልህ ከገበሬ ደጅ አትድረስ ።

ያሥራት ጐተራም የቤተ ክርስቲያንም ሥራ ለመሥራት ቢሆን እርሻ በማይታረስበት መከር በማይሰበሰብበት ወር ከየካቲት ፩ ቀን እስከ ሚያዝያ ፩ ቀን በ፪ ወር ውሥጥ በተለመደው ልክ ይሥራ እንጂ የርሻና የመከር ሥራ በሚሠራበት በሌላው ባ፲ሩ ወር አይታዘዝ ።

ያፈር መልከኛና ባለምድርም የሆንክ ከተለመደው ባመት ከምስቱ ቀን እርሻህ በቀር ከዚህ አልፈህ ገበሬውን ሌላ እርሻና ሥራ አትዘዘው። ባለርስትም ምድርህን ገበሬም እርሻህን ጥቅሙ ላንተም ለመንግሥትም ነውና በትጋት መሬትክን እረስ፡አሣርስ፡መከር ስቶብህ ችግር አግኝቶህ በታወቀ ምክንያት ካልሆነ በቀር በስንፍናህ መሬትክን ሳታርስ ሳታሣርስ ቀርተህ አሥራትህ መሬቱን በትጋት ካረሰውና ካሳረሠው በመልክምነትም ከሚመሳሰለው ከሌላው መሬት ላይ ከወጣው አሥራት የጐደለብህ እንደሆነ በዚያው ልክ ሞልተህ መክፈልህ አይቀርምና ጠንክረህ እረስ ።

ባለመሬትም መሬትህን ሊያርስልህ ያጋዛኸውን ጭሰኛህን በደምቡ ከሚሠራልህ እርሻ በቀር ውለታ እንዳለህ እንደ ውለታህ የቤት ሥራህንና ያጥር ሥራህን አዝመራውን በማይሠራበት ጊዜ ይሥራልህ እንጂ በሚአርስበትና በሚሠራበት መከር በሚሰበስብበት ጊዜ እያዘዝህ አዝመራውን ያጠፋህ እንደሆነ ላራሹ የበሬ ጫንቃውን ለመንግሥትም አሥራቱን አንተ ትከፍላለህ ።

ባለገንዘብም ሁኖ ራሱ ሳያርስ በገበሬ የሚአሳርስ ጭሰኛ ግን ለመንግሥቱም ፤ ለሻላቃውም እንደጥንቱ ይገብር ላራሹ ገበሬም ቁጥሩ የሚታወቅበትን ከትእዛዝ የሚድንበትን እርሶ አዳሪ ነው አይነካ እያልክ አገረ ገዢው የማኅተምህን ጉርድ እየሰጠኸው ይዳን ።

ከዚህ ቀደም ያልታረሰና ያልቀና የውድማ መሬት ርስት ያለው ሰው ሁሉ ወደፊት እየረሰ እንዲአቀና መሬቱ ቈላ ሆኖ የሣር ዋጋ ለባለቤቱ ገቢ የሌለው ተበይ ያለበት ውድማ ያቀና እንደሆነ በመጀመሪያው ዓመት ግብርም አሥራትም አይከፍል።

በሁለተኛው ዓመት የግብሩን እራተኛ እጅ ከፍሎ አሥራቱን ከ፴ አንድ ያውጣ ።

በ፫ኛው ዓመት የግብሩን ግማሽ ከፍሎ አሥራቱን ከ፳ አንድ ያውጣ ።

በ፩ኛው ዓመት ግን ግብሩን በሙሉ ከፍሎ አሥራቱን ከ፲ አንድ ያውጣ።መሬቱ ወይና ደጋ ወይም ደጋ ሆኖ ጭራሽ ያልታረሰ ጠፍ ተበይ የሌለበትን የሚያቀና መጀመሪያው ዓመት ግብሩም ግማሽ አሥራቱም ከ፳አንድ ይሁን ።

በሁለተኛው ዓመት ግብሩም ፩እጅ ጉድሎለት ፫እጅ አሥራቱም ከ፲፭ አንድ ይስጥ ።

በሶስተኛው ዓመት ግን ግብሩን በሙሉ ከፍሎ አሥራቱንም ከ፲አንድ ያውጣ ። ከዚህ ቀደም ያልታረሰና ያልቀና የውድማ መሬት ርስት ያለው ሰውም ግብሩና አሥራቱ ከቀረልኝ ብሎ የርሻ በሬው ሳይሞትበት፥ እርሱ ሳይታመም በስንፍናው እርሻውን ትቶ አላቀና ያለ እንደሆነ በፊተኛው ዓመት አለመጀመሩ ታይቶ ሲሶ ግብሩን፤ በ፪ኛው ዓመት ግማሽ ግብሩን፤ በ፫ኛው ዓመት ሙሉ ግብሩን፤ ለየባለ ማደሪያው ከፍሎ አሥራቱንም እንደ ግምቱ ያወጣል እንጂ ውድማ ሁኖበታል ተብሎ ምሕረት አይደረግለትም ።

ከዚህ ቀደም የታረሰና የቀና መሬት ያለው ግን ግብሩንም አሥራቱንም ከዚህ ቀደም እንደነበረው እንደደምቡ ይክፈል።

፪ኛ፤ ስለ ከብት ማርባት ።

ለአገራችን የሚበቃ የርሻ መኪና እስኪሰናዳድረስ የምትወልድ ላም የሚአርስ በሬ ያለው ሰው ሁሉ በዝክር በተዝክር አመክኝቶ ላሙን በሬውን አይረድ። ነገር ግን ላሙ መሲና በሬው ሰባያ ወይም አሮጌ ወይም ፈጋ የሆነበት እንደሆነ ላገሩ ሹም እያስታወቀ ጉረቤት እየመሰከረ ቢአርድ አይከለከልም።የከብቱን መርባትና መብዛት ሲታወቅ ከገር የሚተርፈውን መንግሥት ካልፈቀደው በቀር ማንም ሰው ቢሆን በፈቃዱ ከብቱን ወደውጭ አገር እንዳያወጣ ተከልክሏል።

፫ኛ፤ ስለ ሥራ ፈት ማሠሪያ ።

ካህን፤ ወይም በየዓይነቱ በመንፈሳዊ አኗኗር ለእግዚአብሔር እየገለገለ ከሚኖርና ገበሬ ሁኖ ከሚአርስ፥ነጋዴ ሁኖ ከሚነግድ፥ወታደር ሁኖ ብረት ይዞ አገር ከሚጠብቅ፥ባለጥበብ ሁኖ በእጅ ሥራው ከሚገበር፥ባለ ጡር ሁኖ ስለ ማዕርጉ ከሚታፈር፥በደዌና በእርጅና ከሚቸገር በቀር፥መሥራት እየተቻለው፥ጤና እያለው ሥራ ፈት ሁኖ በባላገር የሚኖር ሰው ሁሉ ስለ ሥራ ፈትነቱ ቅጣት እንዳይሆን፥በግድ እየተያዘ የዕለት ምግቡን ብቻ እየተቀበለ ከየአራሹ ገበሬ ላይ ሲአሠራው ለነበረው ጉልበት በሁኑ ደምብ ስለቀረበ የምትክ ሁኖ፥ላገረ ገዢው ሸክም ተሸካሚ፥ቤት ሠሪ፥አጥር አጣሪ፥አራሚ፥አጫጅ፥ሁኑው።

በከተማም ነዋሪ ቢሆን፥ በዚሁ ዓይነት በግድ እየተያዘ የከተማ መንገድ ሲሠራ እየዋለ የዕለት ምግቡን ይቀበል እንጂ ሥራ ፈት ሁኖ በውስልትና አይቀመጥ ።

፬ኛ፤ የቤተ ክርስቲያን ሕግ ።

እስከሁን ድረስ ጸንቶ የቆየው የክርስቲያንነታችን ምልክቱ ጾም መጾም፥በዓል ማክበር፥ ስለ ሆነ ክርስቲያን የሆነሰው ሁሉ በክርስቲያን የታዘዘው የጾምን ሕግ በመብላት አይድፈር በሕግ የታዘዙ ሰንበትና በዓላትን እያሻረ ይህን ሕግ ከሚአፈርስ ሰው እንደ ኃጢአቱ ግምት በተወሰነው ደምብ እየተቀጣ የመቀጮው ገንዘብ ሲሶው ለሚይዘው ባላጋራና ለሚጠብቀው ዳኛ ይሁን ፪ እጁ ለመንፈሳዊ ተማሪ ቤት ገቢ ይሁን ።

፭ኛ፤ ስለ እጅ ሠራተኛ ዋጋ ።

የእጅ ጥበብና ሥራ የሚያውቅ ሰው ሁሉ ግብር ሁኖ በደምብ ከተወሰነለት በመቱ ውሥጥ ከሚሠራውና ከሚገብረው በቀር በፈቃዱ በዋጋ እየተስማማ ይሥራ እንጂ በባላገር ጭቃ ሹምና ምስለኔ በከተማም ከንቲባውና የሰፈሩ ሹም ማናቸውንም ዓይነት የመንግሥትና የቤተክርስቲያን ሥራ የራስህንም ሥራ በግድ ያለዋጋ አታሠራው ፤

ይህን ቃል አፍርሰህ በግድ እያዘዝህ ያሠራኸው እንደሆነ ሠራተኛው ሲረታህ የሠራበትን ዋጋ በጥፍ ትከፍላለህ የእጅ ጥበብና ሥራም የምታውቅ ሰው ሁሉ በድንገት የሚአስቸኩል ለመንግሥት ወይም ለሕዝብና ለሀገር ጥቅም የሚሆን ሥራ ተገኝቶ ሹሙ የሚአስቸኩል ሥራ መሆኑን ካስታወቀህ በኋላ የሚገባህን ዋጋ ተቀብለህ ሥራ እንጂ እምቢ ብለህ የቀረህ እንደሆነ ትቀጣለህ ።

በዋጋም ተስማምተህ ሥራ የምታሠራ ሰው ሁሉ ከቀኑ ፲፪ቱን ሰዓት ለሠራተኛው ዕረፍት እየሰጠህ ፰ሰዓት ብቻ አሠራው እንጂ ከጧት እስከ ማታ ሥራ ብለህ አታስገድደው።

የወለጋ ተስፋ ።

ክቡር ደጃዝማች መኰንን ወሰኔ በወለጋ ለባላገሩ ግብር አቅለውለታል።በሰዮና በጎምቤላ መካከል የአውቶሞቢል መንገድ ሊያሠሩ አስበዋል የሚል ቃል በብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ዘነበብን ጊዜ ደስታችን ከልክ ያለፈ መሆኑን ልባችንና እግዚአብሔር ያውቀዋል ። ከዚህም ለባላገሩ ግብር መቅለሉንና በደስታ መኖሩን ሁላችንም ፈጽመን ተረድተነዋል። ስለ አውቶ መቢሉም መንገድ እንኳን ፍጻሜውን ጅማሬውን ለማየት እየጓጓን የምንጠባበቅ ሰዎች ብዙ ነን፥ ግን ከዚህ በፊት ሰዎች አንጕተውን ተሳቀናልና እንደዚያው ይሆንብን ይሆን እያልን ስጋት ገብቶናል ። የሆነ ሁኖ እግዚአብሔር የሕዝቡን ጉዳት ተመልክቶ ነውና ምናልባት ክቡር ደጃዝማች መኰንን ወሰኔን መንግሥት ወደዚህ አገር መስደዱ የወለጋን ሕዝብ ለመታደግ ይመስለናል ። ከሕዝቡ የሚበዛው ዛሬ እርሻን ትቶ ንግድና መሸከም ይዞዋል።በሰዮና በጎምቤላ መካከል የሚመላለሰውን የንግድ ዕቃ በራሱ እየተሸከመ አራት ቀን አምስት ቀን እየተጓዘ በየመንገዱ በወባና በተቅማጥ በሽታ ያልቃል።ምናልባት በቂንሹ ቢገመት ታሞ ደክሞ ከሚሆነው በቀር በመት የሚሞተው ብቻ ከሰባት መቶ አያንስም ። በዚህ ምክንያት በየመቱ ሕዝብ እያነሰና አገር ጠፍ እየሆነ ሔዷል። ክቡር ደጃዝማች መኰንን ወሰኔም ግብር ማቅለላቸው በዚህ ምክንያት ይመስለናል እንጂ እውነትም ከሕዝቡ የሚበቃ ግብር ተቀብለው ስለ በቃቸውና ስለ ተረፋቸው አይደ-

ለም ። ግን እንዳሰቡት ይኸን ለንግድ ማመላለሻ የሚሆን የአውቶሞቢል መንገድ በቶሎ ቢያሠሩና ሕዝቡን ከማለቅ ቢያድኑት እስከ ሁለትና ሶስት ዓመት ድረስ በወለጋ ጠፍ መሬት ይገኝ አይመስለኝም ። እኔም በጠባብዋ እውቀቴ ወለጋን በብልጽግና ለኢትዮጵያ መጀመሪያ አገር ናት ለማለት እደፍራለሁ ። ሰዎችዋ ግን ወርቁና ብሩ እግራቸውን እያደናቀፈው፥ ዓይናቸውን አንጋጠው፤በሰው እጅ ያለውን ገንዘብ ብቻ ሲመለከቱ፥ወድቀው ሊቀሩ ጥቂት ቀርቷቸዋልና ክቡር ደጃዝማች መኰንን ወሰኔ መልካም መሪ ቅን ሐሳብ ያላቸው ሰው መሆናቸውን ከዚህ ቀደም በደረጉት የቸርነት ሥራና ሊጀምሩት በሰቡት ሥራ ይታወቃሉና የሚያደናቅፍ ነገር እንዳያገኛቸውና ያሰቡትን ሥራ እንዲፈጽሙት የብዙ ሰዎች ምኞት መሆኑን እገልጻለሁ ። አሁን በቅርቡ በመስከረም ወር አንድ ጋላ ከገምቤላ ወደ ሰዮ ያንዲት ሴት ዕቃ ተሸክሞ ሲመጣ የተሸከመው ከባድ ነገር አግተርትሮት በሊልሞ ቁልቁለት በሐው ስለታም አለት ላይ ወድቆ ጉልበቱ ከሁለት ተለይቶ ወንድሙ እያዘገመ ሰዮ ወደ ሐኪም አደረሰው።ከሐኪሙ እስኪደርስ ሰውነቱ ተጉድቶ(ተመርዞ)ነበረና ጥቂት ቀን እንደ ታከመ ሞተ። የተሸከመበትም አንድ ብር ካምስት መሐለቅ ነበርና ያች ሴት ለሱ ሁለት መሐለቅ ብቻ ሰጥታ በተረፈው ሌላ ተሸካሚ ቀጥራ ጥላው አለፈች።ይኸም ሰው ከዚያ በፊት ወደ ገምቤላ ያልወረደ አዲስ ወራጅ ነበርና አንድ ጊዜ በመውረዱ ለሁለት መሐለቅ ሕይወቱን አጣ ።

ይኸን የመሰለ ነገር የደረሰባቸው ብዙ ናቸው።እያንዳንዱን ለመጻፍ ጊዜ ያስፈልጋል።ነገር ግን መልካም ሐሳብ ያለው ሰው በነዚህ በተሸካሚዎች የሚደርስባቸው መከራ ምንኛ ክፉ እንደሆነና ለድካማቸው የሚቀበሉት ገንዘብ ለዕለት ምግባቸው እንኳ የማይበቃ መሆኑን ባያየው ም በሩቅ ሆኖ ለመረዳት ይችላል።እንዲህ ያለውንም የማያውቅ ችግረኛ ሕዝብ ወደ እውቀት ደረጃ የሚመራ ሰው ስሙ ለዘላለም ፀንቶ ይኖራል።ይህም ለመሥራት የታሰበው የአውቶሞቢሉ መንገድ በፍጥነት ቢጀመርና ቢፈጸም፡ሕዝብ እየበዛ፡አገር እየለማ፡ንግድ እየሰፋ፥ ይሄድ ነበር።ወለጋም ከባሕሪዋ ባገኘችው ብልጽግና ላይ የሥራ ብልጽግና ብትጨምር በጣም የምታስደንቅ አገር እንድትሆን የታወቀ ነገር ነው።ክቡር ደጃዝማች መኰንን ወሰኔም ገንዘብ ለኢትዮጵያ አገልጋይዋ እንጂ ጌታዋ እንዳልሆነ የተረዱ ሰው መሆናቸውን ዛሬ የሚያደርጉትና የሚያስቡት ሥራቸው ይመሰክራልና ይኸን የመንገድ ሥራ በቶሎ እንዲያደርጉት ብዙ ሰዎች በተስፋ ይጠባበቃሉ።ደግሞ የጥንት ሻለቆች መኖሪያ ከተማቸው ከጠረፍ የራቀና እማኸል አገር ስለ ነበረ በየሠሩበት ቦታ ሁሉ ከተማው ያልተተከለና ያልለማ ሆኖ ይኖር ነበር።ምክንያቱም ቦታቸው በአገር ውሥጥ ካለው መተላለፍያ ሁሉ የራቀ ስለሆነ እነሱን ያለ ሰው ብቻ ወደ ከተማቸው ይሄዳል እንጂ ተላላፊ ነጋዴ ወይም መንገደኛ አይደርስበትም ነበርና መቼም ሰው የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ ራሱ ብቻውን ሊያደርገውና ሊፈጽመው ሁለጊዜ አይችልም። ሌሎችም ሊረዱትና የሚያስፈልገውን ሊያርዱትለት ይገባል እንጂ ከተማ የሚለማው ነጋዴ ሲበዛ፡ ንግድ ሲሰፋ፥ መንገድ ተላላፊ ሲደርስበት እያየ እየተረዳ ሲመጣና ሲሠራበት ነው። ክቡር ደጃዝማች መኰንን ወሰኔ ይኸን ስለ ተረዱት ወደ ጠረፉ ቀረብ ብለው ከሰዮ አንድ ሰዓት ተኩል በምታስሄድ ቦታ ላይ አዲስ ከተማ ቈርቍረዋል።ሰዮም ዋና የመናገሻ ቦታ ናትና በዚያ የሚኖሩ የውጭ አገር ነጋዴዎችና የውሥጥ አገር ነጋዴዎች ከብዙ ዘመን ጀምረው የአገረ ገዢዎች ከተማ እንዲቀርባቸው ይመኙ ነበርና ዛሬ ምኞታቸው ስለ ሆነላቸው በጣም ደስ ብሎዋቸዋል። የነዚህም የሁለቱ ከተሞች መቀራረብ እያደር ንግድን እያሰፋት፡ከተማውን እንዲያሳድገው፥ ጠረፍም ነውና አገርን ለመጠበቅ እንደሚመች፡ጥርጥር የለበትም በጣም የሚያስደንቀን በዚህ በቦታ ላይ ለነበሩ ባለ ርስቶች ገንዘብ ከፍለው ርስት እንጥፈው መሥራታቸው ነው ይኸም ለወደፊቱ መልካም ምሳሌ ይሆናል።

የብርሃንና ሰላም ተላላኪ።

ዝኒት የምትባለው የጻፈችው የቀድሞ የመስኮብ ንግሥት ምሥጢር ያለው የሕይወት ታሪክ ።

በካፒቴን ባቢኪያን ታርሞ ተጻፈ ።

፪ኛ ክፍል ።

እኔም አሊክስን አልኋት እውነት ነውን እንዲህ አጥብቀሽ ትወጂዋለሽን? ። ይህንንም ስላት አሊክስ አለመጠን አዝና ነበረችና አንድም መልስ አልሰጠች።ይልቁንም እኔ ስታለቅስ እንዳላያት ከተቀመጠችበት ቦታ ተነስታ ወደ አንደኛው ቤት ገብታ ታለቅስ ጀመር።እኔም አለመጠን በፍቅር እንደተጎዳች አወቅሁ በፊት ግን ቀላል ፍቅር የያዛት መስሎኝ ነበር ።

በማግሥቱ አኔት አንድ አምበልፕ በላዩ የኢጣልያ ቴምብር የተለጠፈበት ለአሊክስ ሰጠቻት በዚያን ቀን አሊክስ ደስ ብሏት ዋለች።ከንጉሡ ልጅ ከኤርኔስት ጋርም ወደ ጨዋታ ቤት ገብታ እስክስታ (ዳንስ) ስትጫወት ዋለች የንጉሡም ልጅ ኤርኔስት ደስ ስለአለው አክብሮ ከእኔም ጋር ዳንስ እንድንጫወት ለመነኝ።

ጨዋታችንም ካለቀ በኋላ ወደ አሊክስ እልፍኝ ገባን ከዚያም አኔት ሁለተኛውን ደብዳቤ ለአሊክስ ሰጠቻት እርስዋም እየተንቀጠቀጠች ተቀብላ አምበልፑን ቀዳ አነበበችውና ለኔ አሳየችኝ፤ ይህም ወረቀት የአሊክስ ወዳጅ ሪያልፍ የጻፈው ነው ንባቡም እንዲህ ይል ነበረ ።

ክብርት ፍቅሬ ሆይ ከአንድ ሳምንት በኋላ ወደ ጀርመን አገር መጥቼ አንቺ ካለሽበት ከተማ በትሮፕ ሆቴል አርፋለሁና የከበረውን ፈቃድሽን ለቀጠሮችን ጊዜ የሚያመለክት ወረቀት እንድትጽፊልኝ እለምናለሁ ።

ይህን ወረቀት ካነበብሁ በኋላ እህቴ ሆይ የዚህ ሰው መምጣት ደስ አላለኝም በኋላ ላንቺ አጉል ነገር ይሆንብሻል አልኋት።እሷም ይህን ቃል ሰምታ በቁጣ ቃል ምን አለበት የመጣ እንደሆን ብላ መለሰችልኝ፤ እኔም መልሼ አልኋት እህቴ ሆይ ይህ ሰው በፊት ከንጉሥ ወገን መሆንሽን አያውቅም እኛ

ም ያንድ ፋብሪካ ዲሬክተር ልጆች ነን ብለንነው የነገርነው ከዚህ በኋላ አሊክስ አለችኝ እወቂ እኔ ምንምቢሆን ቀላል ሰው የልጆች ሥራ የምሠራ አይደለሁም የንጉሥ ልጅ መሆኔን እደብቀዋለሁ አልነግረውም ይህንንም ብላ እንደተራ ሰው ለብሳ በዚያ በተቃጠሩበት ሆቴል በሥውር ከወዳጅዋ ከሬዶልፍ ጋር ለመገናኘት ሄደች።

በሚመጣው ሳምንት ይቀጥላል ።

የሁለት ሰዎች ንግግር

አንድ ሰውዬ ዓለምን ዞሮ ማየት ስንት መልካም ነበር አለ ሁለተኛውም ዓለምን ለማየት መዞር አያስፈልግም አለው እንዱም እንግዲያስ እንዴት ይሁን ዓለምን ዞረው ታላዩት እርሱ እንዲታይ ብሎ ወዳሉበት አይመጣ አለ ያኛውም ባታውቅ ነው እንጂ ዓለምስ ባጠገብህ ነው ያለ አለው ። ያም እንዴት ብሎ ጠየቀው ። እርሱም ዓለም ማለት ዓርፎ መቀመጥ ነው አለው አንድ መንገድ አላፊም ነገራቸውን ሰምቶ ወንድሞቼ ዓለም ለራሱ ይዞራል እንጂ ዓርፎ አይቀመጥም ስለዚህ ዓለምን ማየት የሚፈልግ መዞር ያስፈልገዋል አንደኛውን ዓለም ማየት የፈለገውበእግር ይዞራል ሁለተኛውን ዓለም የሚያይ ግን በሐሳቡ ይዞራል ብሎዋቸው አለፈ ።

ስለ እግዚአብሔር የተደረገ ምሕረት

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ በመስከረም ፳፯ ቀን በእግዚአብሔር ቸርነት ዘውድ ጭነው ስለ ነገሡ ከዚህ አስቀድሞ ለበደላቸውና ክፉ ሥራ እየሠሩና እየበደሉ ለተፈረደባቸው መኳንንቶች በቸርነታቸው ምሕረት ስለ አደረጉላቸው ቸርነታቸውን ልናመሰግን ይገባናል ።

እንደ ሥራቸውም መጠን ከተፈረደባቸው በኋላ አሁን ምሕረት ያገኙ መኳንንቶች ደጃች ባልቻ አዲስ አበባ መጥተው እተፈቀደላቸው በታ በደስታ ሔዱ። ደጃች በየነ፥ በጅሮንድ ውብሼት ፥ ነጋድራስ ሠርፀ ወልድ፥ ነጋድራስ ፋላስ፥ አቶ መልሴ ፥ አቶ ፋንቄብ፥ ናቸው ።

ደጃች አባ ውቃውም ገንዘባቸውና ርስታቸው እንዲወረስ ፤ በሰውነታቸውም ይሞት በቃ ከተፈረደባቸው በኋላ አሁን ሌሎች መኳንንቶች ምሕረት ሲያገኙ የርሳቸውም ገንዘባቸውና ርስታቸው ተለቀቀላቸው ። እርሳቸውም እስከ ጊዜው በአንኮበር ቆይተዋል ።

እነዚህም ከዚህ በላይ የተጻፉት መኳንንቶች በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ላይ የሠሩትን ክፉ ሥራ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ አውቆታልና አሁን እንደገና ለመጻፍ አያስፈልግም ።

ደግሞ ስማቸው በዚህ ያልተጻፈ በገንዘብ ዕዳና ይህን በመሰለ ታሥረው የነበሩ ብዙ ሰዎች በግርማዊ ንጉሥ ቸርነት ምሕረት እያገኙ ከእሥራት ተፈትተዋል ።

በዚህ ዓለም ሰው ሆኖ የማይበድል አይገኝምና የግርማዊ ንጉሣችንን ልብ ታጋሽና ይቅር ባይ ላደረገልን ለእግዚአብሔር ምስጋና እናቀርባለን ።

አገርን ስለ መጥቀም ።

አገር በምን ምክንያት ይለማል በምን ምክንያትስ ይጠፋል? ።

አገር የሚለማበት ለዕለት ጥቅማቸው ብቻ ሳያስቡ አርቀው ለሚመጣ ትውልድ የሚያስቡና የሚሠሩ እውነተኛው የእግዚአብሔር ፍርሃት የተሳለበት ሕሊና ያላቸው ብርቱዎች ሰዎች ቢገኙ ሕዝቡም በመላው ሥራ ሠርቶ መብላትን ቢወድ ሐኬትንም ቢጠላ ሥራ እንደ በረከት እንጂ የኃጢአት ዋጋ ሆኖ እንዳይታየው ያስፈልጋል። ሹመትና ባላምዋልነት ለጥቂቶች ነው ሠርቶ መብላት ግን ለሁሉም የተገባው ነው የተሾመ ሰው የገበሬና የነጋዴ የሠራተኛም ሁሉ ጠባቂና ረዳት ነው እንጂ ዓለቅት በጉሮሮ ገብቶ ደም እንደሚመጥ ሆኖ ሊያጡክ አይደለም ።

አገርም የሚጠፋ ያገር ሰዎች ራሳቸውን ወዳጆች ብቻ ሲሆኑ ላጭሩ ዕድሜያቸው ምቾትን ብቻ ወስነው እያሰቡ «እኔ ከሞትኩ በኋላ ሰርዶ አይብቀልበት የሚል ተረት እየተረቱ እንደሚሠሩ ሲሆኑ ነው እንደዚህ ያሉ ሰዎች ላገር ልማት የሚሆን ሥራ መሥራት ይቀርና ላገር ጥቅም የሚሆን ነገርም ቢሆን ስለ ዕለት ጥቅማቸው ሲሉ ያጠፉታል።

አገርን የሚያጠፋ ነገር አስወግደን አገር የሚለማበትን ሕዝብ የሚጠቀምበትንና በሚመጣ ትውልድ የምንመሰገንበትን ሥራ እንሥራ ።

ስለ ልዕልት መነን ወደ ጅቡቲ መሔድ

ኅዳር ፲፰ ቀን ልዕልት መነን ልዩ የሆነ ባቡር ተሰናድቶላቸው ከተከታዮቻቸው ጋራ ወደ ጅቡቲ ለመሔድ ተሳፈሩ ። ልዕልት መነንንም ለመሸኘት ብዙ መኳንንትና ሠራዊት እባቡር ማረፊያ ድረስ ወርዶ ነበር።ብርሃንና ሰላም ልዕልት መነን ከሔዱበት አገር በደህናና በደስታ እንዲመለሱ ምኞቱን ያቀርባል ።

የ፫፻፸፫ ገጽ ተከታይ

የሀብት ዓይነት አከፋፈል

ከሁሉ በፊት የሀብትን እውቀት አስተካክሎ መከፋፈል ግድ ነው መጀመርያ የሀብትን እውቀት ምን እንደሆነች በሁለተኛ ስፍራ ሀብትን በልዩ ልዩ ዓይነት እንዴት እንደምታስብ እናሳያለን ማለት ሀብትን እንዴት አድርጋ በሦስት ነገሮች እንደምታፈራ መሬት፥ሥራ፥ ገንዘብ፥ ከሚያስገኙበት ሠራተኞች እንዴት አድርጋ እንደምትከፋፈል ከአንዱ እጅ ወደ ሌላው እጅ እንዴት አድርጋ እንደምትዞር (እንደምታልፍ) ከአንዱ ስፍራ ወደ ሌላ እንደምን እንደምትሄድ (እንደምትጓዝ) በመጨረሻው ለያንዳንዱ (ነፍስ ወከፍ ሰው)ይሁን ለሕዝብ ሁሉ በጅምላ እንዴት አድርጋ የሚያስፈልገውን ሁሉ እንደምትሰጥ እናስረዳለን ኤኮኖሚያ ፖሊቲክ ባጭሩ እንዲህ ነው ።

ሀብት ።

ማፍራት ፥ መከፋፈል ፥ መዘዋወር ፥ (መተላለፍ) መጨረስ ።

ለአገሩ ሁሉ ጥቅም ለሆነ የቀረጥ ነገርም ማለት ከሀብቱ ፍሬ አንድ ወገን ለመንግሥት መስጠት የተገባ ነውና ስፈሩ

እዚሁ ይገባ ነበር።ግን በጣም ረዢም ሁኖ ቦታ ስለማይበቃው ብሁለተኛው መጽሐፍ ላሳያችሁ ተስፋ አለኝ።

የሀብት እውቀት እንደምን ወጣ ።

የኤኮኖምያ ፖሊቲክ ነገር የሚጠና ሁሉ ጥንታዊ ነውና በነዚያ የጥንት ደንቆሮች ሰዎችም ነበረች ማለት ከፍ ባለ ደረጃ ባይደርሱም ሥራ ማፍራት ማጠራቀም መቈጠብ እንደነበራቸው ትንሽ ትንሽ የሚመሳሰሉ ምልክቶች በብሉይ በሐዲስ በቊርዓን በግሪኮችና በሮማውያን በቤተክርስቲያን የታሪክ ጸሬዎች ይገኛል። ትክክለኛውን መከናወን ለማግኘት ግን ወደ ጊዜያችን መድረስ ነው ።

ከዋኖች የኢኮኖሚያ ፖሊቲክ መሥራቾች አዳም ስሚትህ ማልቱስ ሴርራ ኩዌስሬይ ሴኒዮር ኤንዴርሶን ስትዋርት ሚል የሚባሉ ትልልቆች ሰዎች ልናስታውስ ይገባናል የነዚህና እነሱን የመሰሉ የሌሎች ሰዎችም ባህል አሜሪካ ከተገኘች ወዲህ ብዙ የወርቅ ምንጭ ቢፈልቅና የዓለም ንግድ ሁሉ ወደስዋ ቢሳብም ወርቅና የከበረ ዕንቍ ሁሉ ሀብት እንዳልሆነ ከደው እውነተኛይቱ የሀብት መሠረት መሬት እንደሆነች በትክክል ያስረዳሉ። እውነት ነው ባህል ሁሉ ዘቀጥታ መመልከትና ባንድነት ማሰብ በማስተዋል መመርመርና በእውነት ማረም በፍቅር መሥራትና በስምም መፈጸም ያስፈልጋል ።

ስለምን በኢኮኖሚያ ፖሊቲክ ባህል በብዙ ሰዎች መኻከል ብዙ ክርክር አለና ከሁሉ በፊት እውነተኛይቱን መንገድ አግኝቶ ለመያዝ የትኛይቱን መከተል እንደሚሻል መፈለግ ያስፈልጋል ነፍስ ወከፍ(እያንዳንዱ)ታላቅ ጥቅም የሚመስለውን ይመርጣል የሚያስፈልገው የሆነ ነገር ጥቂት ይሁን ብዙ ደስታ ሊሰጠው(ሊያገኝ) ይፈልጋልና ።

ከዚህ የቀረ በሚከተው ይታተማል ። ሚካኤል ተሰማ።

ማስታወቂያ ።

ወደ አገር በመግባት ምክንያት በሐራጅ የሚሸጥ ዕቃ

የሚመጣው እሑድ ኅዳር ፳፫ ቀን ከጧቱ ፬ ሰዓት ተኩል ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ድረስ ከስድስት ሰዓት በኋላ በስምንት ሰዓት ተኩል ጀምሮ እስከ ማታ ድረስ እቤልጋርክ ሌጋሲዮን የሙሴ መ ፫ እጅግ የሚያምረው የቤት እቃቸው ጨርሰው ወደ አገራቸው የሚገቡ ስለሆኑ በሐራጅ ይሸጣል ።

የሚሸጠውም የዕቃ ዓይነት ዕስት አልጋ ከነፍራሹ በሙሉ በለመስተዋት ትልልቅ የቁም ሳጥን በእብነ በረድ የተሠራ የፊት መታጠቢያ ገበታ የራስጌ ገበታ።ልዩ ሆኖ የሠተራ የጽሕፈት ገበታ።እጅግ የሚያምር ከነቁም ሳጥኑ ከነወምበሮቹ።የመብልያ ገበታ ከነመሣርያው በሙሉ ። ብርጭቆና ሳህን።አንድ ድንቅ ሁኖ የተሠራ የዕቃ ማስቀመጫ የቁም ሳጥን ። ሌላም ልዩ ልዩ ዓይነት የቁም ሳጥን ። በጋዝና በቤንዚን የሚበራ ትልልቅ ፋኖስ። ሠላሳ ያህል ስጋጃ ምንጣፍ። በጉሬዛ ቆዳ የተሠራ ምንጣፍ ። ትልቅ የነሐስ ያበባ ማስቀመጫ ። ፍኖግራፍ ሙዚቃ ። በእጅ የተሣለ ትልልቅ ሥዕል።ብዙ የፈረንጅ ኵርቻ አዳዲስ ። ሌላም እንደዚሁ ያለ ብዙ እቃ ከፈረንጅ አገር የመጣ ይሸጣል ። ለማናቸውም ነገር መጠየቅ የፈለገ ሰው ከስድስት ሰዓት በኋላ ከስምንት እስከ ፲ሥራ አንድ ሰዓት ድረስ እሙሴ ሻኑዋ ቤት ድረስ እየሄደ ለመጠየቅ ይቻለዋል ።

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ ኦቤርላንድ ኦቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።



አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባ ኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም በለማግኜቶና በለባተሪ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማነደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል «ዓረብያን ትሬዲነግ ኩምፓንያ» ነው

ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

COGNAC S.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



ዝኒት እጅ ሰዓት ።

በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩግቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ግልጸ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

RUGBY

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ በአደንና በጀበቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬስ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ።

ተቃላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በካፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በካፕሱሉ ላይ ለለበት ኮኛክ ክልስ ነው ።

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወዮ ዓለም ቤት ይገኛል ኒክላ ።

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጀኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዌድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad



ዓለም ሱቅ ፲፪ ዓይነት የተሰማ አሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራ ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የዶማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ፣ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል

አደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ሱቅ ነው ።

ማስታወቂያ

ድራሴ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሴ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሴን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሴ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሴ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለአንበሴት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ ብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረ ከተማም የድራሴ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።

ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ሲሔድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራን ። በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬንግ ኩባንያ ቤት ነው ።



ጉድይር ነው

በዳግማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አራተኛ ዓመት ፤ቁጥር ፵፱
4 me ANNÉE . № 49

ሐሙስ ኅዳር ፳፯ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም ።
JEUDI 6 NOVEMBRE 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen , profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix , a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ደረክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ለፈለገ በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ሕዋሳቶችን ስለሚቀሰቅሱ የሀገር ሀብቶች ።

በኢትዮጵያ ሀገራችን ውሥጥ ብዙኅ ጥቅም ያለባቸው መሬቶችና የሀገር ሀብቶች ሞልተዋል በአሠሪና በሠሪ ባስታዋሽ እጦት ሀብቷ ተቀብሮ ምድራችን መካን እየመሰለች ትኖራለች። ይኸንኑም ለማለትና ለመናገር ያደፋፈረኝ ምክንያቱ በአራሾችና አትክልተኞች በኩል ያሉት ሥራዎች ያለመከናወናቸውንና ያለ መፈቀዳቸውን እያየሁ ለሀገራቸው ጥቅም ብለው ለሚያስቡ ሰዎች ለማመልከት ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን ቃሎች ሐሳቤና እርስሴ አደፋፍረውኝ ለመጻፍና ለብርሃንና ሰላም ለማቅረብ ግድ ሆነብኝ ።

እስከ ዛሬ ድረስ በኢትዮጵያ ሀገራችን ውሥጥ ዕጣን፥ከርቤ፥ድኝ፥ጨው፥ላስቲክ፥ ይኸንንም የመሳሰለው ሁሉ፥ከውጭ፥ አገር እያመጡ በኛ አገር ይሸጣሉ።የውጭ አገር ሰዎችም በእንደነኝህ ያሉት ንግዶች ሀብቷን ይሰበስባሉ።ነገር ግን በሀገራችን ውሥጥ ኡጋዴን በሚባለው ክፍል ዕጣን፥ከርቤ፥ድኝ፥ጨው፥ላስቲክ፥ ያለመጠን የሞሉ ናቸው ይላሉ። እነኝህን እንደነዚህ ያሉትን የሀገር ፍሬዎችና ኃብቶች ስለምን ይሆን የሀገራቸውን ጥቅምና ብልጥግናዋን የሚያስቡ ሰዎች ያለመጐብኘታቸውና ያለመሥራታቸው?ከጅቡቲ የሚመጣው ጨው እንኳን አንዱ ጆንያ ከ፯ እስከ ፲ ብር ድረስ ይሸጣል።በሀገራችን የሌለውንና የማይገኘውን ነገር ብንገዛ ይሻል ነበር እንጂ እንዴት በሀገራችን ውሥጥ ያለውን የራሳችንን ሀብቶች መሰብሰብ አቅቶን ከባዕድ እጅ እንግዛ? ።

ይኸንን ጉልቄ መሳፍርት የሌለውን የሀገራችንን ጨው የተሾሙት ሹሞች እየሰበሰቡ ለመላው ኢትዮጵያ ቢሸጡ አረት ጥቅም አለን፡፩ኛ የጨው ሺያጭ ዋጋ ለመንግሥት ገቢ በመሆን ። ፪ኛም የኢትዮጵያ ሕዝቦች በቀላል ዋጋ በመግዛታቸው ። ፫ኛም መላዋ ኢትዮጵያችን በጨው በኩል እራሷን መቻልዋና ለባዕድ ገቢ የሚሆነው ሀብቷ ለራሷ ስለሚቀረው ነው ።የዕጣን፥የከርቤ፥ የድኝና የላስቲኩ ዋጋ ግን አሁን እንደሚሸጠው አሳንሰን ብንገምተው ከጨው ዋጋ አምስትና ስድስት እጅ እንዲበልጥ ጥርጥር የለውም። ከየምድራችን ጥቅም እነኝህን የተናገርኳቸውን ሀብቶች ለመሰብሰብ ቢያስቡም የሌላው ገቢ ቀርቶ ከነኝሁ ብቻ የሚገኘው ገንዘብ ለወታደር ቀለብ ለመኪናዎች መግዣ ለመንገዶች ማሠሪያ የሚበቃቸውን ገንዘብ አግኝተው ከነኝሁ ሥራዎች ተርፎ ለመንግሥት ገቢ የሚያደርጉት ፬እጅና ፭ እጅ ባገኙ ነበር ይመስላል።እነኝህን በትጋት ፈጥነው ቢያሠሩና ቢያከናውኑ የውጭ አገር ሕዝቦች ክብረታቸውና ሥራቸውም ደግሞ የመንግሥታቸውም ሀብት መብዛቱ በሀገር ውሥጥ የሚገኙትን ሀብቶች በጥንክሬና በትጋት በመሰብሰባቸው ነው እንጂ የሰውነትስ ከሀገራችን የበለጡ ሀብቶች ኑሯቸው አይደለም ።

እዚሁ ባቅራቢያችን በግብጽ አገር ያለውን ሀብት ወሬ እንኳን ስንሰማ ጥጥ ይዘሩና ጥጡ አፍርቶ፥ተለቅሞ ሲያልቅ፥ የጥጡን ዛፍ ቅጠል ለጋውንና ቀንበጡን እያጨዱ ለከብት መኖ እንዲሆን እያሰናዱ እሩቅ አገር ድረስ በመርከብ እየወሰዱ ይሸጣሉ ይላሉ ።

ሁለተኛም ለጋሪ ጉታቾች ፈረሶች መና የሚሆን ሣር አሳምረው አሰናድተው ከፈረንጅ አገር የመጣ አጅቡቲ ሲሸጥ እየሁና ይሄ ምንድነው ብዬ ብጠይቅ የከብት መና ነው ከፈረንጅ አገር የመጣ አሉኝ።እኔም ይኸንን ባየሁና በሰማሁ ጊዜ እጅግ አድርጌ አዘንኩ።ያዘንኩበትም ምክንያቱ ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው ።

የሀገራችን ሣር በሐረር አውራጃ ከደወሌ እንሥቶ እስከ ሐዋሺ ከሐዋሺ እስከ ውልንጭቲ ድረስ፥(የኢሳ የጉርጉራ የ

ረዩና አዳል በረኃ በሐዲዱ ግራና ቀኝ በያመቱ የሚያጭደውና የሚሰበስበው እየታጣ እየተቃጠለ በመቅረቱና ከፈረንጅ አገር የስንት ወራቶች መንገድ በመርከብ እየተጫነ እየመጣ ሣራቸው እንኳ ሲሸጥ እኛ ግን ያንድ ቀን መንገድ ይኸንን ኍልቈ መሳፍርት የሌለውን ሣራችንን እየወሰድን መሸጥ እያቃተን በከንቱ እየተቃጠለ መቅረቱ ያሳዝናል።

ምንም እንኳን ሕዝቡ የሣር ሺያጩን ጥቅምና ጉዳት ባያውቀው የምድር ሀብት ነውና የግድ የምድር በብት ጠባቂና አሠሪዎች ተብለው የተሾሙት ሹሞች ለሕዝቡ ጥቂት በጥቂት ቢያስተምሯቸው ሕዝቦቹም በጣማቸው ጊዜ ይህ የሣር ሺያጭ እያደር ሣራቸውን በጥንቃቄ እየሰበሰቡ ንግዳቸውንም እንዲያሰፉ ጥርጥር የለውም ነበር ።

ደግሞ የምድርን ሀብት ለመጠበቅ ሥልጣን የተሰጣቸው ወደ ባላገር አራሾች ዘንድ እየሔዱ ጠንካራውን ገበሬና ሰነፉን አሳምሮ የሚያርሰውንና የግብር ይውጣ የሚያርሰውን ገበሬዎች መጐብኘት ይገባቸዋል።ለጠንካራውም ገበሬ የማጠንከርና የሥራው ምስክር የሚሆነው ሽልማት ባገኘ ጊዜ ሰነፉም ዘንድሮስ በስፍናዬ ጓደኞቼ ሲሸለሙና የድካማቸውን ዋጋ ሲያገኙ እኔ ቀረብኝ ለሚመጣው ዓመት የአራሾች አለቆች የሠራተኞቹን ሥራ እየዞሩ ሲጐበኙ እኔም እንደ ጓደኞቼ የማዕርግ ሽልማት እንዳገኝ ሲል ሥራውን በጣም በትጋት እንዲሠራ ጥርጥር የለውም ነበር ። ለዚሁም የምድርን ሀብት እንዲጠብቁ ሥልጣን የተሰጣቸው ሹማምቶቻቸውን እየላኩ አራሹንና ሰነፉን ገበሬዎች የግድ መጐብኘትና እንደ ትጋቱ መጠን የክብርና የትጋት ሽልማቱን መስጠት ያስፈልጋል እንጂ ዝም ለማለት አይገባቸውም። ለገበሬዎቹም የትጋታቸው ምስክር ሥራቸው ነውና ።

በሀገራችን (በሐረር ባሩሲ በባሌ) ደግሞም በየሌላውም አገር ብዙኅ የሆኑ የጌሾ ጫካዎች አሉ ። እነኚህንም የጌሾ ጫካዎች ማንም እየቈረጠ ይነግድባቸዋል።በአዲስ አበባ ውስጥ ፩ቁና እስከ አንድ ሩብ ይሸጣል። እነኚህን የጌሾ ውድማዎች የምድርን ሀብት የሚጠብቁ ሥልጣን የተሰጣቸው እያስጠበቁ ቢያሸጡት ሌላው ቀርቶ ከቀረጡ እንኳን በጭነት ሩብ እሩብ ቢቀበሉት ገቢው ትልቅ ነበርና ይኸንንም ሥልጣን የተሰጣቸው ሰዎች እንዲያስቡበት አሳስባቸዋለሁ ። ሥራቸውንም በትጋት ማከናወናቸውን እየተማመንኩ በኢትዮጵያ ሀገራችን ውሥጥ ብዙኅ ሀገሮች የቡን አትክልቶች ያሉባቸው ደገላ ለብሰው ፥ የዝሆን፥ የጐሽ የንኚህንም የመሳሰሉ አውሬዎች መኖሪያ ሁነው የሚታዩ አሉ ይላሉ።በባሌ፥በሲዳሞ፥በጃንጅሮ፥በይሉባቦር፥በጐማ፥በነኚህ ሀገሮች ውሥጥም የቡን ጫካዎችአሉ ይላሉ።እኔ እንኳ ባይኔ ያየሁት በባሌ አውራጃ ደሉ በሚባለው ክፍል ውሥጥ ጭራሹን ቡና የሞላው ጫካ አይቻለሁ። ደግሞ በዚያው ሀገር በዚያው አውራጃ ሎሚና ትርንጎም አለ በአረናም አውራጃ ኍልቈ መሰፍርት የሌላቸው የጌሾ ጫካዎች አሉ።

እነኚህን አትክልቶች ደገላ ሁነው የጐሽና የዝሆን መዋያ ናቸው እንጂ የአትክልትነታቸውን ጥቅም አውቆ አረማቸውን አርሞ ሥራቸውን ኰትኵቶ የሚጠብቃቸው የለም። እነዚህንም በባሌ አውራጃ ደሉ በሚባለው ክፍል ያሉት የቡን ጫካዎች ባፈሩ ጊዜ ባላገሮቹና አዳኞቹም እንደፈቀዱ ይለቅሟቸዋል ያለቃቀማቸውም አኳኋን እጅግ ያሳዝናል እስሩ ያለውን ቅጠል አጭደው የቡናውን ዛፍ በረዣዥም ሸመል እምድር ሁነው እየጨፈጨፉ እመሬት የወረደውን ፍሬ ይሰበስባሉ እንጂ እንደ አታክልተኞች አለቃቀም አይለቅሙትም።እነኚህም ይህን የደገላ ቡን የሚለቅሙት ሰዎች እንዲህ እየጨፈጨፉ መልቀማቸው ሳያርሱ፥ ሳይቆፍሩ፥ ሳይደክሙ፥በብላሽ ያገኙት ስለሆነ ነው እንጂ የውነትስ የደከሙበትና የለፉበት በሆነ እንደዚህ ባልጨፈጨፉት ነበር ይመስላል ።

እኔም ይኸንን ያለቃቀማቸውን አኳኋን ባየሁ ጊዜ ይህ ሳይሠራና ሳይታረም እንዲሁ በመጐሳቈል በመሬቱ ደግነት እያፈሩ ባፈሩም ጊዜ እንደዚህ እያደረጉ የሚለቅሟቸውን አትክልቶች ቢሠሯቸውና እንደ አትክልቶች ቢጠብቋቸው እንዴት በሆኑና ብዙኅ ፍሬም በሰጡ ነበር እያልኩ አሰብኩኝ ።

ለንደዚህ ያለውም የቡን ጫካ ሁሉ ባላባት ነን የሚሉ ባላገሮች እንኳን ቢኖሩ ስሙን እንጂ ከፍሬውና ከሀብቱ ማንም ፍሬውን ስለሚዘርፈው ምንም አይጠቀሙለትም ይመስለኛል ።

የውጭ አገር አትክልቶችን ወሬ እንደምንሰማው እንኳንስ እንደዚህ ያሉ ሳይኰተኰቱና ሳይታረሙ የሚያፈሩ አትክልቶች አግኝተውና ሳያገኙም ቢሆን በሀገራቸው አትክልት ለመትከል ሲያስቡ ብዙኅ ዘበኞች ወደትምህርት ቤት ኖረው ተምረው ይኸንን ትምህርት ሲማሩ ብዙኅ ገንዘቦች በተማሪ ቤት እየከፈሉ ትምህርታቸውንም ታከናወኑ በኋላ በብዙኅ እሣርና ድካም አትክልት ተክለው ቀጥለውም ጧትና ማታ ሥራውን በጥንቃቄ እየሠሩ፥የታመመውንም እየከተቡ፥ ደህናውንም በትጋት እየጠበቁ፥ ውሃ የጠማውንም በየጊዜው እያጠጡ አሣራቸውን እየጨረሱ፥ጉልበታቸውንም እያደከሙ፥ላባቸውንም እያፈሰሱ፥መጠን በሌለው ድካም የአትክልታቸውን ፍሬ እየሰበሰቡ በዚች ዓለም እስካሉ በሥራቸው ለትዳራቸው የሚበቃቸውን እያገኙ ይኖራሉ ይባላል።ይኸነኑም የሚያገኙት በሥራቸው ትጋትና በድካማቸው ብዛት ነው እንጂ በምድራቸው መልካምነት ያለመሆኑን ሥራቸውና ድካማቸው ይመሰክራል።እኛ ግን እንደነኚህ ያሉትን በትጋት ያለመጠበቃችንና ያለመሥራታችን ለሚመለከቱን በጣም ያሳዝናል ይመስላል ።

መቼም ከምድር የሚወጣውና የሚገኘው ሁሉ ሥልጣኑና ሥራው፥ ደንቡም፥ በምድር ሀብት ጠባቂዎች በኩል ስለሆነ በንደነኚህ ያሉት ሀገሮች ሁሉ የተማሩ ሠራተኞች የታመኑ ጸሐፊዎችና ተቈጣጣሪዎች እየላኩ ማስጠበቅና ማሠራት ይገባቸዋል እንጂ ችላ ማለት አይገባቸውም ነበር ።

ይኸንኑም እንደነኚህ ያሉ የአትክልት ውድማዎችየምድርን ሀብት ለመጠበቅ የተሰጣቸው እያስጠበቁና እያሠሩ ቢያሰበስቡት ለተወዳጅዋ ኢትዮጵያችን ምን ያህል ጥቅምና ስም በሆነላት ነበር

የምድርን ሀብት ለመጠበቅ ሥልጣን የተሰጠው እነኚህን አትክልቶች ቢያስጠብቃቸው ባላባቶቹ እርስታችን ነው ብለው ይከለከላሉ ቢባል ለዚሁም አንድ ጥያቄ አለው መሬት ከእጁ

ዚአብሔር በታች የመንግሥት ነው።ስለዚህ ይህን ውድማ ከጥንት ጀምረው እነሱ ቡና መትከላቸውንና ማብቀላቸውን የሚመሰክር ምስክራቸውን አምጡ ብሎ ይላቸዋል፥የሚበቃ ምስክር ያገኙ እንደሆነ አጣፍጠውና አሳምረው እንዲሠሩ የሚያጠነክር ደንብ አድርገውላቸው እንደ አትክልት ደንብ አሥራት እየጠበቁ መቀበል ነው።የበቃ ምስክር ከሌላቸው ግን እንዲያው በስደት ያገኙት አትክልት ነውና የግድ የመንግሥት ሁዳድ ይሆናል እንጂ ይህ ሀብት የሞላበ መሬት ደገላ ለብሶ አይኖርም።ለዚሁም ለነኛ በዚያ ሀገር ለሚኖሩ ባላገሮች እንደ መጠናቸው አጣፍጠውና አከናውነው የሚሠሩትን ያህል ጉልማ እየሰጥዋቸው የተረፈውን የምድር ሀብት ለመጠበቅ ሙሉ ሥልጣን የተሰጠው እንዲያሠራው ስል አሳስባለሁ ።

ክቡራን የብርሃንና ሰላም ወዳጆች ሆይ በተገደፈው ሞልታችሁ፥በጠፉም አቃንቃችሁ እንድትመለከቱት ስል ይቅርታችሁን እየለመንኩ አሳስባችኋለሁ ። በቀለ ዘለቀ።

የምድር መንቀጥቀጥ ።

መስከረም ፳፱ቀን ፲፱፻፳፩ ዓመተ ምሕረት ሐሙስ ዕለት ከማታው ለሰስት ሰዓት አምስት ደቂቃ ጉዳይ የመሬት መንቀጥቀጥ ሆነ። መንቀጥቀጡም ከአንድ ደቂቃ የሚበልጥ አልነበረም።የምድርም መንቀጥቀጥ ምክንያቱ ምን እንደሆነ የሳይንቲፊክ ሰዎች እንደሚያምኑት ከዚህ በተጻፉት አጭር ቃሎች እገልጽላችኋለሁ።ለዳበ ቀ ፊት እንዳለው እንዲሁ ለመሬት ቅርፊት አላት ይላሉ ። ስለዚህ የምድርን ጠባይ የሚያውቁ ዲምሎጂስቶች ምድር በድንጋይ የተሞላች ስለሆነች ይኸ አፈር የሚባለው ነገር የደቀቀ ድንጋይ ነው ይላሉ ። አንዳንዶቹም ድንጋዮች እነ አሸዋ አስሌት ፤ በውሃ ሥራ የተበጁ ስለ ሆኑ የውሃ ድንጋዮች ይሏቸዋል ። ሌሎቹንም እነ በሯ ድንጋይ፥ ቡሌ ድንጋይ፥በእሳት የተበጁ ስለ ሆኑ የእሳት ድንጋዮች ይሏቸዋል። የቀሩትም የድንጋይ ከሰል ጠመኔ፥ ከእንስሳ ወይም ከበሰበሰ ሐመልማል የተበጁ ድንጋዮች ይባላሉ። ምድርን አጥልቀን እየቆፈር ንብንከተላት ሙቀት እየባሰ ይሄዳል።ከምድርም ውሥጥ ቃላቅ ትኩሳት አለና ይኸውም ትኩሳት ቃላላቁን ቋጥኝ ያቀልጠዋል ይባላል።ከውቅያኖስ በታች ባለው መሬት ቀዳዳ ይገኝና ብዙ ወሀ በዚያ እየሾለከ ወደ ውሥጥ የሠረገ እንደሆነ ወሃውና ሙቀቱ ሲገናኝ በአነዳፍ ታወደ እንፋሎት ይለወጥና ኃይል ሲዘረጋ ምድርን በጥቂቱም ሆነ በብዙ ለማንቀጥቀጥ ይችላል ። የምድር መንቀጥቀጥ በጣም ፈጣን ስለሆነ አንዳንድ ጊዜ እምብዛም አይታወቅም አንዳንድ ጊዜ ግን ከተማ ይገለባብጣል፥መሬትም ይሰነጥቃል ሞገድም ያስነሳል። ይኸውም የምድር መናወጥ የዛሬ መቶ ሰባ ሰስት ዓመት የፓርቱጋልን ዋና ከተማ ሊስቦን ለፋት አድርሷት ነበር ። ምናልባት በዚያ ውሥጥ ስልሳ ሺ ነፍስ ጠፍቷል ይባላል ። ደግሞ የዛሬ ስልሳ ዓመት ፔሩንና ኤኩዋዶርን አጠፋ።ከተማው በጭራሽ ፈርሶ ብዙ ሺህ ሰዎች ተደፈሩ እንዲሁም በቅርቡ የዛሬ ሀያ ዓመትና የዛሬ ሀያ አምስት ዓመት ሳን ፍራንሲስኮና ባልፓሬሶ፥ ደግሞም ኪንግሥቶን፥ በምድር መንቀጥቀጥ የተነሣ ተገለበጡ።አንዳንድ ጊዜም እንፋሎቱ በኃይል ሲዘረጋ አለት እያፈነዳ የሚፈላ የእንፋሎቱ ደመናና የረመጥ ውሺንፍር፥ደግሞም ላቧ የተባለውን የቀለጠ ድንጋይ ፈሳሽ፥ያደርጋል። እንዲህ ያለው ማዕድን ሁሉ ከመሬት ውሥጥ ወደ ሜዳ እየተወረወረ ይቆለላል።በቀን ብዛትም ተራራ ወይም ቦልካኖ ይሆናል ። በቦልካኖ (ወይም ይኸው የሚፈላው ነገር በሚወጣበት ቦታ) በጫፉ ላይ ወደ መሬት ውሥጥ የሚመራ ቀዳዳ አለበትና ስለዚህ በዚህ በቀዳዳው የሚዘው እንፋሎትና የቀለጠው ድንጋይ ረመጡም ወደ ውጭ ስለሚወጣ ተውሥጥ መሬትን በጣም የሚጨቁነውን ኃይል ይከፍልለታልና የምድርን መንቀጥቀጥ ያሳንሰዋል ወይም በጭራሽ ያስቀረዋል።ስለዚህ ቦልካኖ ታዳጊ ይባላል በዓለምም ብዙ ጊዜ ምድር በምትንቀጠቀጥበት አገሮች ውሥጥ ቦልካኖ ይገኛል ። በየጊዜውም ሁሉ ይህ የምድር መንቀጥቀጥ በብዙ አገሮችና ከተሞች ላይ ጥፋት እንዳደረገ ታሪክ ይነግረናል፥ከነዚህም በጣም ታሪካቸው የሚነገረው ከክርስቶስ ልደት በኋላ በ፸፱ ዓመት የፓምፔንና የሂርኩላኔዩምን ከተሞች ያጠፋ የቬሲቢዩስ ቦልካኖ ነው።ሌሎችም ብዙዎች አሉ። ከነዚሁም በጥቂቱ የምድርን መንቀጥቀጥ ምክንያቱ ምን እንደሆነ የምድርን ጠባይ የመረመሩ የሳይንቲፊክ ሰዎች እንደ ጻፉት ለማስረዳት ስል ጊዜው ስለ አጋጠመኝ ጽፌአለሁ ።

(የብርሃንና ስላም ተላላኪ)

ሞን ሲኘር ኒኮላ ሥራዎችን እንደ ጐበኙ ።

የአክሱም ጳጳስ የተባሉት የግሪክ ሜትሮፖሊ.(ጳጳስ)ሞን ሲኘር ኒኮላ ኅዳር ፳፩ ቀን የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንንን ሆስፒታል ቤት ሳይዱ በየክፍሉ እየዞሩ የሥራውን ሁሉ አኳሆን ክቡር ዶክቶር ሐነር እያስረዷቸው አዩና እጅግ ደስ እያላቸው አመሰገኑ ። ከዚያም ከወጡ በኋላ የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንንን ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤትና መጻሕፍት ቤት በየክፍሉ እየዞሩ የሥራውን ሁሉ አኳሆን አይተው ደስ ብሏቸው አመሰገኑ ። ለወደ ፊትም ሥራው እየሰፋ እንዲሔድ መልካም ምኞታቸውን አቅርበው ሔዱ ።

ሞን ሲኘር ኒኮላ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ያቆሞዋቸውን ሥራዎች አክብረው ስለ ጐበኙ ብርሃንና ሰላም ምስጋናውን ያቀርባል ።

የአርመኖች ቤተ ክርስቲያን መመሥረት

ኅዳር ፳፫ ቀን አርመኖች በቅዱስ ጊዮርጊስ ስም አዲስ የሚሠራውን ቤተ ክርስቲያናቸውን የሚመሠርቱበት ቀን ስለ ሆነ በምረቃው ጊዜ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ግርማዊ ንጉሥ፤የኢትዮጵያሚኒስቴሮችና መኳንንቶችም፤ የውጭ ከገር ሚኒስቴሮችና ወይዛዝሮችም እንዲመጡ ጠርተው ነበር።ቤተ ክርስቲያኑም በሚሠራበት ቦታ አምሮ በተሠናዳው ድንኳን ሥርዓተ ቅዳሴ እንዲደረግ ተዘጋጀ፥ በዚሁ ቀን ከጧቱ በ፫ ሰዓት የአርመን ሊቀ ጳጳስና ቄሶች አርመኖችም ሁሉ በተሰናዳው ቦታ ተሰበሰቡና ሥርዓተ ቅዳሴው ተጀመረ ።

ሞን ሲኜር ኪዎርክ የአርመን ሊቀ ጳጳሳት።

ከዚህ በኋላ የውጭ አገር ሚኒስትሮችና ወይዛዝሮች መኳንንቶችም ተሰበሰቡ ። ብፁዕ ዕጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስና የግሪክ ጳጳስ ሞንሲኜር ኒኮላም በዚሁ ጊዜ መጡ። ለየመዓዝኑ ለመሠረት የሚሆኑ ፲፪ ድንጋዮችም የሐዋርያትና የወንጌላውያን፣የቅዱስ ጎርጎርዮስም ስም ተደርጎላቸው በጠረጴዛ ላይ ተቀምጠው ነበርና ሊቀ ጳጳሱ ቀርበው ቡራኬ አድርገው በወይን አጥምቀው ከጨረሱ በኋላ ብፁዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ እንዲባርኳቸው ሊቀ ጳጳሱ ለመኑና ባረኳቸው።ይህም ከተደረገ በኋላ ግርማዊት ንግሥተ ነግሥታትና ግርማዊ ንጉሥ በብዙ አጀብ ታጅበው መጥተው አምሮ በተሰናዳው ቦታ ተቀመጡ።

ከዚህ በኋላ ልብሰ ተክህኖ የለበሱ ሰዎች ፲፪ቱን ድንጋዮች በሰሐን በሰሐን ይዘው በየመዓዝኑ ቆሙና ሊቀ ጳጳሱና ካህናቱ ማዕጠንት እያጠኑና እየዘመሩ በየመዓዝኑም እየዞሩ የመዓዝኑን ድንጋይ ሜሮን ቀቡ ። አንዱን ድንጋይም ብፁዕ እጨጌ ሜሮን ቀብተው ባረኩት።በዚያን ጊዜ የሚሠራውን የቤተክርስቲያንን ሥዕል ስለመታሰቢያ ለሰው ሁሉ ሰጡ።

ይህን ከፈጸሙ በኋላ ሊቀ ጳጳሱ ሥርዓተ ቡራኬ አድርሰው ሰዉን አሰናበቱት።ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ግርማዊ ንጉሥም በአማረ ዓጀብ ወደ ቤተ መንግሥቱ ተመለሱ ።

ሥርዓተ ቅዳሴ ሲደረግም ወንዶችና ልጃገረዶች በሙዚቃ እየተመሩ ባማረ ዜማ ይዘምሩ ነበር።የመዝሙሩም ማማርና የልጃገረዶቹ ድምጽ መተካከል ሰውን ሁሉ አስደነቀ ። ባዲስ አበባ ያሉ አርመኖች በጣም ብዙ ስለሆኑ የግድ አንድ ቤተ ክርስቲያን ያስፈልጋቸዋልና ይኸ ቤተ ክርስቲያናቸው በመመሥረቱ ታላቅ ደስታ አድርገዋል። እውነትም በአዲስ አበባ ያሉ አርመኖች ከሴቶችና ከሕፃናት ጋራ ወደ ሺ ሳይጠጉ አይቀሩምና ደስታ ይገባቸዋል።ቤተ ክርስቲያኑም የሚሠራበት ገንዘብ ወደ መቶ አምሳ ሺ ብር ተገምቷል።ይህንንም ገንዘብ ለቤተ ክርስቲያኑ የሚሰጡት ስለ ሟቹ አባታቸው መታሰቢያ ኾ ዲሆን ሙሴ ሚህራን ሞራዳያን ናቸው ።

ብርሃንና ሰላም አዲስ የተመሠረተው ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር በረከት የሚያርፍበት እንዲሆን እየተመኘ ለሊቀ ጳጳሱ ሞንሲኜር ኪዎርክና ለአርመን ሕዝብ ሁሉ እንኳን ደስ አላችሁ ይላል ።

ስለ መልከም አዋጅ ምስጋና።

ባራተኛው ዓመት ቁጥር ፶፫ የተጻፈልንን ስለ ሕዝብ እነዋወር ደምብ ካንድ እስከ ሶስትና እስከ አምስት ባየሁ ጊዜ የደስታዬን ብዛት እንዴት አድርጌ በጽሕፈት ልገልጽላችሁ ብችሎ ለመቻሌ እጅግ አዝናለሁ፣ተግተን ብርሃንና ሰላምን ለማገልገል የጀምርነ ብዙ ሰዎች ነበርን።ነገር ግን የተጻፈው ያልተሰማ መስሎን ማገልገላችንን ተወት አድርገነው ነበር። ለካስ የመንግሥትና የእግዚአብሔር አሳብ የማይታወቅ በመሆኑ ኑሯል ። አሁን ግን ያራቱን ዓመት እርምጃ ባንድ ጊዜ መንግሥታችን በመራመዱ እጅግ ደስ ይለናል ። ለሌላውም ነገር ሁሉ እንዲሁ ደምብ እንዲደረግለት ተስፋ እናደርጋለን ። ማገልገላችንንም እንጀምራለን ። በትግሬ፣በጐንደር፣ በጐጃም፣በወሎ፣ ሁለት ቀን ለራስህ አንድ ቀን ለኔ ሥራልኝ የሚባል ደምብ የለም። በሸዋ ግን በማህለ ሥላሴ ጊዜ የጦር ዘመን ስለ ነበረ ወታደሩ ደስ ብሎት እንዲዋጋና ወታደር እንዲበዛላቸው ባላገሩን አዋርደው ድኃውን ወታደር አክብረውት ነበር ። ለጊዜውም ቀንቷቸው ብዙ አገር ተጋላ አስለቀቁ።አማራም ወደ ደጋ የወጣ በሳቸው ጊዜ ነው ይባላል ። ነገር ግን መንግሥት ከተደላደለ በኋላ እሚአስበው ጠፍቶ ብዙ እሚአስነውር ሕግ ደግ መስሎ ቆየ ። አሁን የዳር አገርን ሕዝብ ያየ ሰው እንዴት ያዝን ነበረ?፤ይልቁንም የሲዳሞ ሰው የሚአየው መከራ እጅግ ያሳዝናል።ባገሩ የሚለፋው ልፋት ይቅርና ወደ አዲስ አበባ ሲመጣ ወታደሩ አህያ አይገዛም ባላገሩን እንደ አህያ ይጭነዋል እንጂ ። የከተማውም ሰው የሲዳሞ ጋላ ሰው አይባልም ከብት ነው እንጂ እያለ ያላግጥ ነበር። ወይ በግድ አለመያዝ፤ ቀድሞም አማራ እናስገባም ብሎ ተዋጋ ሲሸነፍ ጊዜ እንዲህ ያለ መከራ አገኘው።ቢከዳ ያው ማለቁ ነው ። እንደ እሁኑ መንግሥት መከልከያ ደምብ ካልሰጠው ምን ያድርግ? ። ቀድሞ የንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስ ገባር ከሊሙ መጥቶ አዲስ አበባ ድርቆሽ ሲአጭድ አይቻለሁ ። ያን ጊዜ መቸም ለሱም አዝመራው ነበር በግድ ስለተያዘ ነው እንጂ ። በሁለትና በሶስት ወር ሲመለስ እህሉ ተበላሽቶ፣ቤቱ ጠፍቶ ይቆየዋል። እ

ንዲህ ሲሆን ጊዜ ሕዝብ እንዴት ይከበር።ሽንቅላም በዚህ ምክንያት ነበር እየሸፈተ እሚአስቸግር።ግን ይህን የመሰለ ያገር ጥቅም ሲደረግ አንዳንዱ አእምሮ የሌለው ወታደር ሕዝቡን መከራ ታላሳየሁ ብሎ ያዝን ይሆናል ። ግን አያስደንቅም ልጅና ወታደር በሰው ገንዘብ ያለቅሳልና ። የሕዝብን ነፃ የሚፈልጉ ብልሆች እነ ብላታ ገብረ እግዚአብሔርና እነ ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ይህን ሰምተው ባለመሞታቸው እጅግ እናዝናለን ። ይህንስ ሰምተው ቢሆን ወይም ይቈዩልን ነበር።አሁንም እኛ ሳለን የአራሾችን ጤና ስለ አሰሙን ለግርማዊት ንግሥት ነገሥታትና ለግርማዊ ንጉሥ አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ተፈሪ መኰንን ዕድሜ ይስጥልን፤ ደግ እሚመክሯቸውን መኳንንትም ደግ ዕድል ይስጥልን፤ ኢትዮጵያን ያኑርልን፤ለሕዝባችን ጽናት፥ለሕፃናቱ ትምህርት ፥ ለጅግኖች ፍቅር፤ መስማማት፤ ያድልልን እያልሁ እርሳሴን አነሣለሁ።

ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ።

ማስታወቂያ

ወደ አገራቸው ስለ እሚሔዱ ምክንያት በሐራጅ የሚሸጥ ዕቃ እሑድ ኅዳር ፴ ቀን ከጧቱ በ፫ ሰዓት ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ድረስ ይታረጃል።ከስድስት ሰዓት በኋላ በስምንት ሰዓት ተኩል ጀምሮ እስከ ማታ ድረስ እቤልገርከ ሌጋሲዮን የሙሴ መ ጀ የሚአምረው የቤት እቃቸውን ጨርሰው ወደ አገራቸው የሚገቡ ስለሆኑ በሐራጅ ይሸጣል ።

የሚሸጠውም የዕቃ ዓይነት ሁለት አልጋ ከነፍራሹ በሙሉ ባለ መስተዋት ትልልቅ የቁም ሳጥን፤ በእብነ በረድ የተሠራ የፊት መታጠብያ ገበታ ከነሙሉ መጓሪያው፤ወምበርና ጠረጴዞቹ ለገበታ የሚገባው ሙሉ ሳህንና ብርጭቆ፤ አንድ ድንቅ ሁኖ የተሠራ የዕቃ ማስቀመጫ የቁም ሳጥን ሌላም ልዩ ልዩ ዓይነት የቁም ሳጥን ባለ መስተዋት፤ ልዩ ሁኖ የተሠራ የጽሕፈት ገበታ፥ብዙ ወምበሮች፤ በከፈይ የተጌጡና ከፈይ ላይ የተሠራ ሥዕል፤ ሌላም በቤንዚን የሚበራ ትልልቅ ፋኖስ፤ እግሩ ነሐስ የሆነ በእጅ የተሠራ በጋዝ የሚበራ ፋኖስ፤ ትልልቅ መቀመጫ መከዳ ና በጉሬዛ የተሠራ መከዳ ትልልቅ የነሐስ ማስቀመጫ ስለ አበባ የሚሆን እንደ ቁም ሳጥን ያለ ፎኖግራፍ ሙዚካ በሳፊርና በመርፌ የሚዘፍን በእጅ የተሠራ የተጣለ ትልልቅ ሥዕል በብረት ብሮንዝ የተሠራ የሰው ሥዕል ሌላም እንደዚሁ የቤት ዕቃ የሚኒስቴር መ ጀ

ይህውም ዕቃ ሁሉ በሐራጅ ይሸጣልና ለሁሉምነገር ዕቃውን ለሚአርጅውና ለሚሸጠው ለባለ ኰሚሲዮኑ ለሙሴ ሻንዋ ማናቸውም ነገር መጠየቅ የፈለገ ሰው ከስድስት ሰዓት በኋላ ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ድረስ እሙ ሴ ሻንዋ ቢሮ ድረስ ለመጠየቅ ይቻላል።ሐራጅ ሳይደረግ ዕቃ ለመግዛት የፈለገ ሰው ቅዳሜ በ፳፱ ኅዳር ከጧት ከ፫ ሰዓት እስከ ፮ ሰዓት ድረስ ከ፱ ሰዓት እስከ ፲፩ ሰዓት ድረስ እቤልገርከ ሌጋስዮን ድረስ እየሔደ ለመጠየቅ ይችላል።ኅዳር ፳፱ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም።

ሹመት ።

ኅዳር ፳፭ ቀን ክቡር መምሬ አስፋው በሐረር አውራጃ በቀኝ ክፍል ግራ ወምበርነት ተሾሙ ።

ብርሃንና ሰላም እንኳን ደስ አለዎ ይላል ።

ኦቤርላንድ



ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ ኦቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባ ኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባትሪ ነው ካምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል «ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው

ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

COGNAC S&E&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONJAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መጾቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



ዝኒት ፡ እጅ ሰዓት ።

በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኀይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኀይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ብቻነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

RUGBY

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ በአደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አለው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ፥ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪመኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽናባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ።

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በካፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በካፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኗኗ ።

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዊድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad



ዓለም ሱቅ ፲፪ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሲንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ፤ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያከማል

አደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ሱቅ ነው ።

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።



ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይነዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው ። በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

ጉዲይር ነዙ

GOODYEAR

2-28-14

አራተኛ ዓመት ፤ቁጥር ፶
4 me ANNÉE № 50

ሐሙስ ታኅሣሥ ፬ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም ።
JEUDI 13 DECEMBRE 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና
ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays
la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ጸሐፊው ይጠይቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ቢገዛ ለአንዱ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የመንግሥት ማስታወቂያ ።

መጀመሪ

በጅቡቲ ወይም በኢጣልያ ኤርትራ በኩል ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት የሚፈልግ የውጭ አገር ሰው ሁሉ በጅቡቲ ወይም በአስመራ ወደ አለው ወደ ኢትዮጵያ መንግሥት ቆንስላ እየሔደ አስቀድሞ የይለፍ ወረቀቱን እንዲያስፈርም የኢትዮጵያ መንግሥት ደንብ አድርጓል ።

ሁለተኛ ።

የኢትዮጵያ ባለ ሥልጣን ሹማምንቶች እንደ ደንቡ የፈረሙበት የይለፍ ወረቀት ሳይዝ በጅቡቲ ወይም በኢጣልያ ኤርትራ ወሰን በኩል ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት የሚመጣ ማናቸውም የውጭ አገር ሰው ሁሉ ወደ ኢትዮጵያ ግዛት እንዳይገባ ይከለከላል።

ሶስተኛ።

በእንግሊዝ ሱማሌና በኢጣልያ ሱማሌ በእንግሊዝ ምስራቃዊ አፍሪቃና በሱዳን በኩል ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ለመግባት የሚፈልግ የውጭ አገር ሰው ሁሉ የይለፍ ወረቀት ለመፈረም ሥልጣን ባለው ለወሰን ጠባቂ እያሳየ ያስፈርማል ።

አራተኛ

ይህ ደንብ ጸንቶ ከሚቆምበት ቀን ጀምሮ ከዚህ በላይ ባለው በሶስቱ ክፍል እንደተጻፈው ደንብ የይለፍ ወረቀቱን ሳያስፈርም ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ገብቶ የተገኘ የውጭ አገር ሰው ሁሉ እየተያዘ ከኢትዮጵያ ግዛት ይወጣል ።

ይኸውም ደንብ ከጥር ፩ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓመት ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

ታኅሣሥ ፩ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም አዲስ አበባ ።

AVIS OFFICIEL

Art I.

Tout Etranger qui de la côte Française des Somalis ou d'Erythrée Italienne, désire se rendre en Ethiopie doit préalablement se présenter personnellement au Consulat Impérial d'Ethiopie à Djibouti ou à Asmera pour faire viser son Passeport.

Art. II

Toute personne Etrangère qui se présentera à la frontière de la Côte Française des Somalis ou d'Erythrée Italienne sans être en possession d'un Passeport régulièrement visé par les Autorités Ethiopiennes, sera refoulée.

Art. III

Toute personne Etrangère qui de la Somalie Britannique, de la Somalie Italienne, de l'AFrique Orientale Anglaise ou du Soudan, veut se rendres ur le territoire de l'Empire d'Ethiopie présentera son Passeport au poste frontière Ethiopien qui a compétence pour donner le visa d'entrée.

Art. IV

Toute personne Etrangère trouvée sur le territoire Ethiopien, ayant pénétré dans l'Empirec postérieurement à la mise en vigueur du présent avis, sans avoir obtenu le visa régulier de son Passeport comme il est prévu aux trois articles précedents sera reconduite à la frontière. Les présentes dispostions entreront en vigueur le 1er Ter 1921 (9 Janvier 1929).

Fait à Addis-Abeba le 1er Tahssas 1921.
(10 Decembre 1928).

የመንግሥት ማስታወቂያ ።

የሕዝብን ጤና ለመጠበቅና የከብት በሽታ እንዳይጋባ ለማድረግ ከኢትዮጵያ ውሥጥ ወደ ውጪ አገር የሚሄዱትንና ከውጪ አገር ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡትን ለማዳዎች እንስሳዎችና ለማዳ ያልሆኑ እንስሳዎች፡በወሀ ውሥጥም የሚኖሩ ሕዋሳቶች፡ እንዚህን የመሰሉ ከነሱም የሚገኙትን ሸቀጦች፡ ጤንነታቸውን ለማስረዳትና ለመረዳት የርሻና የመሥሯ ሚኒስቴር ቀጥሎ የተጻፈውን ደንብ አቁሟል ።

ከኢትዮጵያ ወደ ውጪ አገር ስለመስደድ ።

፩ኛ ፡

ለማዳዎች የሆኑ እንስሳዎችና ወይም ለማዳዎች ያልሆኑ ማናቸውም እንስሳዎች፡በወሀ ውስሥም የሚኖሩት ሕዋሳቶችና ሌሎችም እንዚህን የመሰሉ ከነሱም የሚገኙ ሸቀጦች ሁሉ፡ የርሻና የመሥሯ ሚኒስቴር የከብት ሐኪም ሳይመረምራቸው ወደውጪ አገር ለመሔድ አይችሉም ።

፪ኛ ፡

እንዚህን ከዚህ በላይ የተጻፉትን እንስሳዎች ወደ ውጪ አገር ለመስደድ የሚፈልግ ሰው አስቀድሞ ለርሻና ለመሥሯ ሚኒስቴር የከብት ሐኪም አስመርምሮ ጤንነታቸውንና የመጡበትን አገር የሚያስረዳ የምስክር ወረቀት መቀበል አለበት።

፫ኛ ፡

እንስሳዎቹን ወይም ሸቀጡን በላከ ቁጥር እያስመረመረ ሶስት ብር ከፍሎ የምስክሩን ወረቀት ይቀበላል ።

ከውጪ አገር ወደ ኢትዮጵያ ስለማግባት ።

፬ኛ።

ማናቸውንም ለማዳዎች እንስሳዎችንና ለማዳ ያልሆኑ እንስሳዎች፡ በወሀ ውሥጥም የሚገኙትን ሕዋሳቶች፡ እነሱንም የመሰሉና ከነሱ የሚገኙትን ያልተሠሩ ወይም ያልተሰናዱ ሸቀጦች ሁሉ፡ ከውጪ አገር ወደ ኢትዮጵያ የሚያመጣ ሰው የመጡበትን አገርና ተመርምረው ለጤንነታቸው ማስረጃ የተቀበለውን የምስክር ወረቀት ለርሻና ለመሥሯ ሚኒስቴር የከብት ሐኪም አስቀድሞ ማሳየት አለበት።የጤንነታቸውንም የምስክር ወረቀት ያልያዘ ሰው እንዳያመጣ ተከልክሏል።

፭ኛ ።

የጤንነታቸውን ልክ የሚያስረዳ የምስክር ወረቀት ሳይኖራቸው ፡ ከውጪ አገር መጥተው የተገኙ እንስሳዎችና አውሬዎች፡በወሀ ውሥጥም የሚኖሩ ሕዋሳቶች ፡ ከነሱም የሚገኙ ማናቸውም ያልተሠሩ ወይም ያልተሰናዱ ሸቀጦች፡ አስቀድሞ የርሻና የመሥሯ ሚኒስቴር የከብት ሐኪም መርምሮ ወደ ሰውና ወደ ከብት የሚተላለፍ በሽታ የተገኘባቸው እንደሆነ የከብት ሐኪሙ ለሕዝብና ለከብት ጤንነት መከላከያ የሚያስፈልገውን ያደርጋል ።

፮ኛ፡

እንዚህ ከዚህ የተጠሩትን እንስሳዎችና ሸቀጦች ከገር ውሥጥ የሚያወጡ ወደ አገር ውሥጥም የሚያገቡ ሰዎች ሁሉ የርሻና የመሥሯ ሚኒስቴር የከብት ሐኪምና ሠራተኞች ሲመረምሩ የምስክሩን ወረቀት በጠየቁ ጊዜ ማሳየት ይገባቸዋል።የምስክሩን ወረቀት እንደ ተጠየቁ ያላቀረቡ ሰዎች ግን እንስሳዎቹ ወይም ሸቀጦቹ ይያዙባቸዋል።የተያዙትንም እንስሳዎች ወይም ሸቀጦች የከብት ሐኪሙም መርምሮ ጤናማ ሁነው የተገኙ እንደሆነ ለምስክር ወረቀት የሚከፈለውን በጠሬታ ከፍለው ስለጤንነታቸው የምስክር ወረቀት ይቀበላሉ።ለሰው ወይም ለከብት ጉዳት የሚያመጣ በሽታ የተገኘባቸው እንደሆነ ግን ባ፭ኛው ክፍል እንደ ተጻፈው የርሻና የመሥሯ ሚኒስቴር የከብት ሐኪም ለሕዝብና ለከብት ጤንነት ጥበቃ የሚያስፈልገውን አደራረግ ይፈጽማል ።

፯ኛ ፡

ይኸውም ደንብ ከኅዳር ፳ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓመት ጀምሮ የጸና ሆኑዋል ።

በጭር ቃል ረጅም ማስታወሻ ።

እንባቢዎች ሆይ እንደለማነው እንደምታውቁትም ጋዜጣ ጸሐፊዎች በማናቸውም አገር ይህን ሥራ ማደሯ አድርገው የሚኖሩ ናቸው።ይሁን እንጂ መንግሥታቸውን የሚያጉዳውን

ገርና የሚጠቀመውን እያለዩ በቶሎ እንዲሆን የሚያቻኩለውን ለወደፊትም እንዲሆን የሚያስፈልገውን ሲጽፉ አስቀድሞ የተጻፈውን ቃል የሚመስል ነገር እየተጻፈ ሲከታተል ይህ ነገር የሕዝብ ሁሉ ሐሳቡ አንድ ቃል መሆኑ ነውና ያ የተጻፈው ቃል እንዲፈጸም መንግሥት በነገሩ ይተጋበታል። ስለዚህም የኢትዮጵያ ምሁራን በሥራቸው ላይ ሥራ ለሀገር ጥቅም ለመንግሥት ክብር በየሐሳባቸው ከዚህ ቀደም ከጻፉት ከመቶ ሁለት የተፈጸመ ነገር ቢኖር ወየው የስንት ብልሆች ብዕር በተነሳሳ ነበር ። የሊቃውንት ብዕር ተቀለማቸው ጋራ ተጣብቆ አልጽፍም ቢል በፍጥነት ይጽፍ የነበረው የብልሆች ብዕር አዝጋሚ ሆኖ ከቶ ጋዜጣችን ቀዘዝ ያለው ላይሆን ነገር ምን አጻጻፈኝ በማለት ይሆንን? ።

እኔ እላለሁ ሰው ምንም አዋቂ ባይሆን የዘወትር ጸሎቱ ወደ እግዚአብሔር እንዲደርስለት እውቀ ነውና ላይፈጸም ብሎ ለመንግሥት የሚጠቀመውን ንጹሕ ሐሳብ አለመጻፍ በጣም ስሕተት ነው ጊዜ የመጠነውን ጊዜ እንዲፈጽመው በየሰዓቱ ታይቷልና ሊጻፍ የሚገባውን ነገር ሲያውቅ የማይጽፍ ሰነፈው ከስናፈነት የሚቆጠሩትን ይመስላል ።

ከነገር ሁሉ ምን ያስጨንቃል ቢባል ያበደረ ሰው እመንገድ ሲያገኙት ነው የሚባል ተረት አለ ይህን አስቦ የተናገረ ሰው እንዴት ያለ ታላቅ ፈላስፋ ነው ።

የኢትዮጵያ ልጆች ሆይ ኢትዮጵያ አበዳሪ ናት እኛ ተበዳዋሪዎቿ ነን እስቲ ምን እንክፈላት ባበደረችን ዋጋ ግምት የሚሆነው የቱ ነው ከኛ በፊት የነበሩ ተበዳሪዎች ራስ ጎበናና ራስ አሉላን የመሰሉ ሁሉ ለዚያን ጊዜ ለኢትዮጵያ የሚያስፈልጋትን ዋጋዋን በየጊዜያት ከፈሏት ።

እነኛ የሠሩትን አይነት ሥራ አሁን ለመሥራት ሰዓቱ አይደለምና ለጊዜው አሁን የሚያስፈልጋትን ሥራ አይነት መርጠን ዋጋዋን እንክፈላት ዘንድ እንትጋ ።

ያበደረን ሰው እወድሃለሁ ቢሉት ገንዘቡ ታልገባው የሚያፈቅር አይደለምና ኢትዮጵያን እወድሻለሁ ቢሏት በየአቅማቸው ሊከፍሏት የሚገባትን ዋጋ ካልሰጥዋት ከቶ ከአንጀቷ ጠብ አይልም ብር የተበደረ ሰው የተበደረውን ባይመልስ በዋ እጅ ማለፍን የሚያውቅ የለምና የኢትዮጵያ ብድር ለመመለስ የሚያተጋ እዛጋዋ ታዛጋዋ ለመሆን ያስፈራዋልና ንቃትና ትጋት ነው ሰዓቱ ።

ማህሉ ጽጌ

ስለ መተባበር ክፉና መልካሙን በበግና በፍየል ምሳሌ አገልጻለሁ ።

በግ ተፈቃቃሪ ነች እረኛዋን አታስቸግርም፡ ከሩቅ መንገድም ብትሄድ አደጋ ቻይ ነች፤ በተሰመራችበት ስፍራ ተሰብስባ ትበላለች፤ አውሬም ባየች ግዜ እረኛዋ ወዳለበት ስፍራ ሸሽታ ታመልጣለች፡ መልካም ሰውም ተፈቃቃሪ ነው አደጋ ይችላል፤ ወደእግዚአብሔር ይጸልያል፡ መንግሥቱን ያከብራል፤ ለደሃ ይራራል፤ አገሩን ይወዳል፤ በተሾመበት ስፍራ ተባብሮ ይበላል በዕድም ቢመጣበት ለሃገሩ ይረዳል፤ መንግሥት ከጠላው ነገር ይርቃል፤ ፍየል ጠበኛ ነች፡ እረኛዋን አስቸጋሪ ነች፤ አደጋ አትችልም፤ በተሰመራችበት ስፍራ አርፋ አትበላም፤ የሰው ጎመን ትበላና፡ የሰው አትክልት ታጠፋና፡ ከጎረቤት ታጣላለች፡ አፈላማ ታስበላለች፡ አንድም ካንዱ ዱር ወዳንዱ ዱር ስትዘወር ነብር ያገኛታል፤ ለጊዜው ትሸሽና በኋላ ተመልሳ ቲፍቲፍ እያለች አንገቷን እየመዘዘች ስታስተውል አንገቷን በጥፍሩ እየወጋ ደሟን እየመጠጠ ይጨርሳታል። ነገር ግን ለባለቤቱ ዋና ገንዘቡ ነች፤ ክፉም ሰው ጠበኛ ነው፡ መንግሥቱን አስቸጋሪ ነው፤ ጌታን ከሎሌ፡ ወንድምን ከወንድም፡ መንግሥትን ከመንግሥት ያጣላል። አንድም ይሰርቃል፡ ይቀማል ይሸፍታል፡ ነፍሰ ገዳይ ይሆናል። ነገር ግን ሁሉንም እንደ ኃጢአቱ ታስሮ መንግሥት አይቶት ንጉሥ መሐሪ ነው ገንዘቡ ሕዝቡ ነውና ሁለት ሶስት ጊዜ ይምራል። በኋላ ግን እንደለመደው ክፉ ሥራ ሲሠራ ይገኝና ይታሠራል። ይወረሳል፡ ይገረፋል፡ ይቆረጣል፡ ይሰቀላል፡ በግ መልካም ምግብ ባገኘች ጊዜ ተባብራ ተሰብስባ ትበላለች አትነፍግም፡ መልካም ሰውም ጣፋጭ ምግብ ባገኘ ጊዜ ከወዳጅ ከዘመዱ ጋር ተሰብስቦ ተባብሮ ይበላል አይነፍግም፡ ፍየል መልካም ምግብ ባገኘች ጊዜ ተባብራ አትበላም፡ ዘመዷን ትጠላለች፡ ትነፍጋለች፡ ክፉ ሰውም መልካም ምግብ ባገኘ ጊዜ ዘመድ ወዳጁን ይጠላል፡ ንፍገቱ ነንደዶሮ ቅንቅን በሰውነቱ ይነዛበታል፤ ተባብሮ አይበላም፤ በግ ሥጋዋ ጣፋጭ ነው፤ ሰውነት አይቀሰቅስም፡ ሕይወት ያለው ጤናማ ነው። መልካም ሰውም ግብዣው ጣፋጭ ነው ምግቡ ኅብስተ መና ጠላና፡ ጠጁ ወይን ነው፤ ሕይወት ያለው ጤናማ ነው፤ ፍየል ሥጋዋ ለሰውነት ጤና አይሰጥም በሽታ ይቀሰቅሳል ሰውነት ያደቃል ክፉ ሰውም ግብዣው ለሰውነት ጤና አይሰጥም ምግቡ ጨውና በርበሬ ይበዛበታል መጠጡ አስክርትና ሲበርቶ ይበዛበታል የተጋበዘው ሰው ይሳከርና እርስ በርሱ ይከሰሳል ይማታል ይጋደላል ይታሰራል በግ ሃፍረቷን በላቷ ትከልላለች መልካም ሰውም ሐፍረቱን በትእግሥቱ ይከልለዋል መዋሸት መሳደብ መጣላት መስረቅ መቀማት በሐሰት መመስከር የለበትም እውነት ይናገራል ቁም ነገር ይሰራል መንግሥቱን ያፈቅራል ወደ እግዚአብሔር ይሰግዳል ፍየል ለሐፍረቷ መከለያ የላትም ክፉም ሰው ለሐፍረቱ መከለያ የለውም ሲቀማ ሲሠርቅ በሐሰት ሲመሰክር ሲሰስን ሲዋሽ ለጣዖት ሲሰግድ ነውሩ ይገለጽበታል በግ ክፉና መልካሙን ቅጠል ለይታ ስለበላች ሥጋዋ ጣፋጭ ጥቅም ያለው ምግብ ነው መልካም ሰውም መንግሥት የሚጠቀምበትን ድሃ የሚለማበትን ክፉና ደጉን ለይቶ ስለተናገረ ምክሩ ጥቅም ነው ፍየል የማትቀምሰው ቅጠል የለምና ሥጋዋ የሰውነት በሽታ ይቀሰቅሳል ክፉ ሰውም የማይገባበት ስፍራ የለምና ድሃ የሚጠፋበትን መንግሥት የሚጎዳበትን የጥፋት ስራ ሲመኝ ይኖራል ጥቅምም የለውም።

ክፉውን ትቶ መልካሙን ስመከተል የምክር እርዳታዬን አበረክታለሁ ።

ኃይለ ሚካኤል አያልቅበት ።

ስለ ኢትዮጵያ እርዳታ ።

ባለተኛው ዓመት ቁጥር ፵፭ እውነተኛውን ያገር ፍቅር ለመሥራት የሚያሳስብ ክቡር ፊታውራሪ ደሬሳ ያስተመትን

ባነበብኩ ጊዜ ከዚህ በታች ያለውን ባጭሩ ለማሳሰብ ፈለግሁ። ብርሃንና ሰላም በሃገራችን ከገቡ እስከ ዛሬ ድረስ የኢትዮጵያ ልጆች ይኸን የመሰለ መልክሙን ሐሳባቸውን በዚህ ጋዜጣችን ለመግለጥ አላሰቡም ነበር።ነገር ግን ለሥልጣኔ ትምሕርት ቤቶች ማበዛት የሚያስፈልገውን ገንዘብ ግማሹ ከመሬቶች፥ግማሹ ከቤቶች ግብር ይውጣ እያለ ይጽፍ ነበርና ለጌቶቹ ይኸን የመሰለን ግብር ለመትከል ብዙ ድካም የሚያስፈልግ ስለሆነ በማመዛዘን የቆየ ይመስላል ። ይሁን እንጂ ለኢትዮጵያ ለናታችን የሚሆነውን ጥቅም ሁላችን እንደ ሐሳባችን እንዲህ ቢደረግ ይሻላል እያልን እንጽፋለን እንጂ እንዲህ እናድርግ ብለን አንጽፍም ። ስለምን ለኢትዮጵያ አንድ ረዳት ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን እንዳሏት እናውቃለንና ተናግረን እሳቸው ያስቡበት በማለት ይመስላል። የኢትዮጵያ ልጆች ሆ እንዲያውስ ብናስበው ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኛን የያንዳንዳችንን ያህል ዕረፍት ያገኙ ይመስችኋልን ? አያገኙም ። ስለምን ለያንዳንዳችን ከወር የሚያልፍ የተቆረጠ ደሞዝ አለን ፤ በዚሁ ደስ ብሎን እንኖራለን ። ግርማዊ ንጉሥ ግን የኢትዮጵያ አልጋ ወራሽ ከሆኑ ጀምረው እስከ ዛሬ ድረስ ይኸን ለራሴ ጥቅም ላድርግ ሳይሉ በሙሉ ሐሳባቸው ለኢትዮጵያ ሥልጣኔ እንዲጥሩ በመላው ዓለም የታወቀ ነው። ቸርን ቢያጠቁት ቢስ ይሆናል እንደሚሉ ሁላችን ሐሳባችንን ባንድ ሰው ላይ ጥለን ብንቀመጥ እሱም ይበሳጫል።ያለሐሳብ የምንበላውም እንጀራ ይወቅሰናል። ስለዚህም በኢትዮጵያችን የሥልጣኔ ትምህርት ቤቶች ለማስፋት የሚያስፈልግ ገንዘብ መሆኑን ካወቅን የገንዘብማ ፍቅር ትተን ባገር ፍቅር ብንጠመድ ያለ ችግር ብዙ ገንዘብ ለማግኘትና እናታችንን ለመርዳት እንችላለን እስኪ እንመልከት ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የያንዳንዳችንን ያህል ዕረፍትና ምቾት ሳያገኙ ቀንና ሌሊት ለሃገራቸው ሲረዱ እኛ ዘወትር በምቾትና ያለ ሐሳብ ስንኖር ሲሆን አንድ ቀ ለራሳችን ሁለተኛው ቀን ግን ለሃገራችን ብናገለግል ይገባን ነበር።ደግሞ ቢቀር ከወር አንድ ቀን ለሃገራችን ብንሠራ ትልቅ ነገር አይደለም ። ከወር አንድ ለሃገራችን እንሥራ ማለቱም የ፳፱ኙን ቀን ደሞዛችንን ለራሳችን መርጃ አድርገን ያንዱን ቀን ደሞዛችንን ለሃገራችን እናድርግ ማለቴ ነው)።ይኸውም የቀን ድርሻችን ታስቦ በወር በወር ገቢ ቢሆን መቶ ለሚ ለመቶ ሰው ሽታ ነው ። ላንድ ሰው ግን ሸክም እንዲሆን እንዲሁ ለያንዳንዳችን ያንድ ቀን ደሞዝ አይጎዳን። ለሃገራችን ግን በመላ ኢትዮጵያ ባጭር ሒሳብ ፻፶ ሺ ብር የወር ወጭ ቢኖር ድርሻዋ በወር ፲ሺ ብር ባመት ፻፳ ሺ ብር ሲሆን ታላቅ ጥቅም አላት።ወደ ጓደኞችዋ ለመድረስም።እርምጃዋን ታፈጥናለች።ይኸንን ሐሳብ የኢትዮጵያልጆች በደስታ ከተቀበላችሁ ለጌቶቹ የሚያስቸግር አይደለምናበቶሎ እንዲጀመር ጥርጥር የለውም። ይኸውም ትንሽ (አድሚኒስትራሲዮን) ሆኖ ጥቂቶች ወንድሞቻችን በዚሁ ገንዘብ መሰብሰብ ሥራ ያገኛሉ በማለት ታላቅ ተስፋ አለኝ። የብርሃንና ሰላምወዳጆች ሆይ ይኸ ለኛ ቀላል ለሃገራችን ብዙ ጥቅም የሚሆን ሐሳብ ፈቃዳችሁ ሆኖ የሥራው ደምብ እስከ ሁለት ወር ቆሞ በሶስተኛው ወር ገንዘቡ መሰብሰብ እንዲጀመር ፈቃዳችሁ ይሁንልኝ መፈቀዱንም የየሥራው ክፍል ሹሞች በብርሃ ና ሰላም እንዲያስታውቁኝ እለምናለሁ። አስፋው አሰጀ።

ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

በዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ።
የበአታ ማርያም አከባበር ።

፲፱፻፳፩ ዓ ም ታኅሣሥ ፫ቀን እግዝእትነ ማርያም ደወ ቤተ መቅደስ የገባችበት ቀን ነው ። በዚሁም ቀን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ ያረፉበት ቀን ስለ ሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብና መኳንንት በመት ባመቱ ያከብራል ። በአዲስ አበባ ያሉ ካህናትም በዚሁ ቤተ ክርስቲያን ተሰብስበው ማኅሌት ቁመው አደሩ ። ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትም ወርደው ማኅሌቱን ሲሰሙ አድረዋል።ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንንም ከጥዋቱ በአራት ሰዓት ወረዱና ከቤተ ክርስቲያኑ ገብተው እንደ ቆዩ ዑደት ተደረገ።ከዑደቱም በኋላ ሊቃውንቱና ካህናቱ አሸበሸቡና ወዲያው ብፁዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ሕዝቡን ባርከው ኦሳርገው አሰናበቱትና ታቦቱ ገባ ያንጊዜም ብዙ መድፍ ተተኰሰ ።

መወድስ ።

ለመኑ አምሳል ናስተማስለኪ ለሰማይኑ ሐዳስ ወሚመ በገነት ።

ባሕቱ ዕራግ አንተ ወምሥራቀ ነቢይ ዕፁት ።
ዝኪ እስመ ተሐደሰ ምኒልክ ፍጥረት ።
መቅደሰ ንግሥትነ ግርማዊት ።
ዘእግረ ምሳሌኪ ቦአ አንቀጸ ደበረ ታቦር ቤት ።
ተራከባሂ ወተሰዓማ በከተማ ንጉሥ ዳዊት ።
ሰላመ ምኒልክ ዳግማዊ ወጽድቀ ማርያም ዳግሚት
ወቤተ ምኒልክ ሐወፀ ጽድቀ ሰማያዊት ንግሥት ።
እስመ ለምኒልክ ቤተ መቅደሱ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት።
ብላታ መኰሬያ ።

የከተማ ወሬ

የግሪክ ኦርቶዶክስ የአኵስም ሜትሮፖሊት ።

የግርማዊ ንጉሥ ተ መ ትምህርት ቤት እንደጐበኙ ።

የግሪክ ጳጳስ ሞን ሲኘር ኒኮላ የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንንን ተማሪ ቤት ለመጐብኘት በሔዱ ጊዜ የተማሪ ቤቱ ዋናሹምክቡርአዛገርወርቅነህናአስተማሪዎቹም በክብር ተቀበሏቸው።የአኵስም ሜትሮፖሊስ ሞን ሲኘር ኒኮላም ከተማሪ ቤቱ ገብተው በየክፍሉ ዞረው አዩ፤ ተማሪዎቹም የተማሩትን ትምሕርት አሳቸው ራሳቸው ጠየቋቸውና በምላሻቸውና በአውቀታቸው ደስ አሰኛዋቸው።ከዚህ በኋላ የምኝታ ቤቱንና የመሥሪያ ቤቱን ዞረው አይተው፡የተከናወነና ንጹሕ በመሆኑ እጅግ አመሰገኑ።ተማሪዎቹም ደግሞ ስለ ጳጳሱ ክብር በተማሪ ቤቱ በር ተሰልፈው በየዓይነቱ የተማሪ ቤት መዝሙር ዘመሩላቸው ። ሞን ሲኘር ኒኮላም በተማሪዎቹ ማማር እኳኋን ልባቸው ተነክና ቀጥሎ ያለውን ተናገሩ ። ልጆቼ ሆይ እኔ በናንተ በጣም እቀናለሁ ፤ የምቀናበትም ምክንያት ሕፃናት ስለ ሆናችሁና የሚከብድ ሐሳብ ስለሌላችሁ አይደለም ፤ ወይም ተማሪዎች በመሆናችሁ አይደለም ። ነገር ግን የኢትዮጵያ ልጆች በመሆናችሁና ወደ ፊት ልትሠሩት የሚገባ ብርቱ ሥራ ስላላችሁ ነው ፤ ከሌላ አገር ተማሪዎች ይልቅ እናንተ ልትፈጽሙት የሚገባችሁ ሥራ ይበረታልና ። በታሪክ እንደምታውቁት አባቶቻችሁ የኢትዮጵያን ነጻነት ጠብቀው አስረክበዋችኋል ፤ እናንተም እንደ ቀድሞው ታሪክ ሁሉ ኢትዮጵያን ጠብቃችሁ ወደ ከፍተኛው ደረጃ አድርሳችሁ ለልጆቻችሁ ማስረከብ ግዴታ አለባችሁ ።

ከዚህ በኋላ ተማሪዎቹን ባርከው የትምርት ቤቱን ዋናሹም ክቡር አዛዥ ወርቅነህና አስተማሪዎቹንም አመሰገኑ ። ደግሞ ይህ ለኢትዮጵያ ብርሃን የሚሆነው ተማሪ ቤት ላቆሙ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጥልቅ ምስጋቸውን አቀረቡ ።

በመጨረሻም አንድ ትልቅ መጽሐፍ በእንግሊዝ ቋንቋ የተጻፈ የኢትዮጵያ ታሪክ ፤ ሁለት የወርቅ መስቀል ከነሠንሰለቱ፤ አንድ ሰዓት ፤ በትምሕርት ለበለጡ ልጆች እሰጣለሁ ብለው ተስፋ ሰጡ። ከዚህ በኋላ ክቡር አዛዥ ወርቅነህ በራሳቸውና በአስተማሪዎችም በተማሪዎችም ስም ለአኵስም ሜትሮፖሊስ ለሞን ሲኘር ኒኮላ ምስጋና አቀረቡላቸው ።

ማስታወቂያ ።

ወደ አገራቸው ስለ እሚሄዱ ምክንያት የሚሸጥ እቃ ። እቤልጋርክ ሌጋሲዮን በሐራጅ አለመሸጡን በሐራጅ መሸጡ ቀርቲል ዕቃ ለሚገዙት ሰዎች ሙሴ ሽንዋ በማክበር ያመለክታሉ ። ለመሸጥ የተረፉት ዕቆች ሁሉ እሙስ መ ጀ ሳይታረጅ ይሸጣል ሙቼሁም ቀን ለመግዛት የፈለገ ሰው ከ፮ ሰዓት – በኋላ ከ፰ ሰዓት እስከ ፲፩ ሰዓት ድረስ እቤልጋርክ ሌጋሲዮን ሙሴ ገሮራር ቤት ይሸጣል ። ሙሴ ገሮራር እስኪሔዱ ድረስ ዕቃ ለመግዛት የፈለጋችሁ ለመጠየቅ ይችላል ። የተረፉትም እቆች የከፈይ ወምበሮች በየዓይነቱ ጥሩ ጥሩ ሥዕሎች ፋኖሶች ለመብል ከበታ የሚሆን ሙሉ እቃ እስከ ብርጭቆቹ ብዙ የቤት መጣሪያና በየዓይነቱ በቆርቆሮ ያለ ምግብ ኮንሰርብ) ይሸጣል ታኅሣሥ ፫ ቀን ፲፱፻ ዓ ም

ኦቤርላንድ



ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ ኦቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።

አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባ ኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኜቶና ባለባትሪ ነው ካምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ፮ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል «ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው

ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

COGNAC S.E.& A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



ዝኒት እጅ ሰዓት ።

በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆኑ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

“ሩግቢ” የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጸ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይ ወኪል “አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ” ብቻ ነው·

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው ።

RUGBY

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዴልፊአ በቦስቶን በማድራስ በኤደንና በጅቡቲ በነዚህ ከተሞችና፣ በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አሉ ።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለዋወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ባርባሬሶ

ኮ ኛ ክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪመኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽናባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ።

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በከፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በከፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ዓለም

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዊድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad



ዓለም ሱቅ ፲፪ዓይነት የተሰማ አሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ። የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ፤ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል

አደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ሱቅ ነው ።

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሸቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ ብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።



ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይነዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው ። በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላሰቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው።

ጉድይር ግዙ

GOODYEAR

2-28-14

በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት ኀልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አራተኛ ዓመት ፤ ቁጥር ፶፩
4 me ANNÉE , № 51

ሐሙስ ታኅሣሥ ፲፩ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም ።
JEUDI 20 DECEMBRE 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት

Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen , profondément désireux de voir régner dans son pays
la lumière et la paix , a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix "

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ ሲገዛ ለፊስን በ፪ መሐልቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

አዲሱ የእንግሊዝ ሚኒስትር ምስተር ወተርሎ የሹመታቸውን ደብዳቤ ለግርማዊት ንግሥትና ለግርማዊ ንጉሥ እንዳቀረቡ ።

PRESENTATION OF CREDENTIALS BY THE NEW BRITISH MINISTER TO THEIR MAJESTIES THE EMPRESS AND THE KING,

በአዲስ አበባ የእንግሊዝ መንግሥት ሚኒስትር የነበሩት ምስተር ቤንቲንክ ወደ ሌላ ስፍራ ስለ ተዛወሩ የታላቅ ብሪታኒያ ንጉሥ ግርማዊ ጆርጅ ፭ኛ ሌላ ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ምስተር ወተርሎን ወደ አዲስ አበባ ስለላኩ ምስተር ወተርሎ የሹመታቸውን ደብዳቤ ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ በኅዳር ፳፪ ቀን ይዘው ለመቅረብ ተፈቅዶላቸው ነበርና በዚሁ ቀን ከጧቱ በ፬ ሰዓት ያገር ግዛት ሚኒስትር ክቡር ደጃዝማች ወልደ ጻድቅና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዋና ዲሬክቴር ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወደ እንግሊዝ ሌጋሲዮን ሒደው በታላቅ ክብር ይዘዋቸው ወደ ቤተ መንግሥቱ መጡ ። ምስተር ወተርሎም በግርማዊት ንግሥትና በግርማዊ ንጉሥ ፊት በቀረቡ ጊዜ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ዲስኩር ተናገሩ ።

Owiag to the transfer of Mr. Charles Bentinck His Britannic Majesty's envoy extraordinery and Minister Plenipotentiary at Addis-Abeba eleswhere, His Britannic Majesty King GEORGE V **has** appointed Mr. Sydney Philip Perigal Waterlow C. B. E; in his place at Addis-Abeba.

On **the** lst. December 1928, at ten o'clock a. m. Mr. Waterlow prsented his credentials to Their Majesties the Empress **ZAWDITOU** and King TAFFARI.

Their Excellencies the Minister of Interior Dejazmatch Wolde-Sadik and the Director General for Foreign Affairs Blaten-Geta Herouy together with a large escort proceeded to the British Legation and accompanied Mr· Waterlow to the Imperial Palace with great honour. On the Occasion of presenting himself before Their Majesties Mr. Waterlow pronounced the following speech:-

Madam and Sire,

It is with feelings of the deepest gratfication that I enter, at this singularly auspicious moment in the history of Ethiopia, upon the task entrusted to me by my Gracious Sovereign His majesty King George V. by the Crace of God, of Great Britain, Ireland and the British Dominions beyond the Seas King, Defender of the Faith, Emperor of India, etc. etc , etc; of cementing still more closely the relations of cordial friendship that so happily subsist between the Government of the Empire of Ethiopia and that of my country. I have the honour to assure Your Majesties that, during my sojourn at Your Majesties Court. you may rely upon my unremitting effortis and upon my loyal collaboration with Your Government in the work of carrying this task to a successful conclusion.

His Majesty my Gracious Sovereign, at the audience accorded to me before my departure from England, was pleased to charge me with a personal message from Himself to your Majesties, expressing his warm good wishes for the health and prosperity of your Majesties and for the peaceful

development of the dominions and of the people over Which you hold SWay. It is His Majesty's earnest Wish that this development' to Which he confidently looks forward, may contribute materially to the progress of civilisation and the peace of the World. I need hardly say that it is a source of much satisfaction to myself to deliver this gracious message to Your Majesties.

May I be permitted to add on my own behalf that I have long desired to visit Your Majesties country and that the prospect which now opens before me is therefore one that gives peculiar pleasure? Especially as I feel confident that I may count upon the support of Your Majesties and Your Government in establishing upon a firm basis that International harmony and goodwill which, as Your Majesties are aware, it is the fixed policy of my Government to promote.

I have the honour to present to Your Majestes two letters under the Sign Manual of my Gracious Sovereign; the one accrediting me to Your Persons, the other announcing the recall of my predecessor.

ግርማዊት ንግሥትና ግርማዊ ንጉሥ ሆይ ።

በኢትዮጵያ ታሪክ ውሥጥ በተለየ መልካም ምልክት በሚታይበት በዚህ በአሁኑ ጊዜያት ከታላቁ ንጉሜ በእግዚአብሔር ጸጋ የታላቂቱ ብሪታንያና የአየርላንድ ከባሕርም ማዶ ያሉት የእንግሊዝ ግዛቶች ንጉሥ የሃይማኖት ጠባቂ ፡ የሕንድ ንጉሠ ነገሥት ከሆኑት ከግርማዊ ንጉሥ ፭ኛ፡ጆርጅ ተልኬ ፡ በኢትዮጵያ መንግሥትና በአገሬ መንግሥት መካከል እስከ ዛሬ ድረስ በደስታ ጸንቶ የኖረውን የልብ ወዳጅነት በጣም እያጠበቅሁ ለመሔድ በእምነት የተሰጠኝን ሥራ ለመሥራት ጥልቅ የሆነ ደስታ እየተሰማኝ አጀምራለሁ ።

አሁንም በግርማዊ ንግሥተ ነገሥታትና በግርማዊ ንጉሥ ቤተ መንግሥት እስከምኖርበት ጊዜያት ድረስ ይኸንኑ የተላኩሁበትን ሥራ ወደ መልካም ፍጻሜ ለማድረስ ያለ መቋረጥ ዘወትር እንደምጥርና ከኢትዮጵያም መንግሥት ጋራ አንድነት በእምነት ለመሥራት አሳቤ መሆኑን ለግርማዊት ንግሥትና ለግርማዊ ንጉሥ በማክበር አረጋግጣለሁ ።

ከእንግሊዝ አገር ሳልነሳ ከግርማዊ ንጉሜ ጋራ ስገናኝ ለግርማዊት ንግሥትና ለግርማዊ ንጉሥ ጤንነትና፤ልማት ግዛቶቻችሁን ከሥልጣናችሁ በታች ያሉት ሕዝብ ሰላም በመላበት እውቀት ወደ ፊት እየገፋ እንዲሔድ መልካም ምኞታቸው መሆኑን የሚገልጽ የራሳቸውን መልክት እንዳቀርብላችሁ በደስታ አዘዙኝ ።

እንዲሁም ግርማዊ ንጉሥ ጆርጅ በእምነትና በናፍቆት የሚጠባበቁት የኢትዮጵያ በእውቀት ወደ ፊት መግፋት ለሥልጣኔና ለዓለም ሰላም ዓይነተኛ ጥቅም እንዲአመጣ ብርቱ ምኞታቸው ነው ።

እኔም ይህነን የንጉሡን መልካም መልክት ለግርማዊት ንግሥትና ለግርማዊ ንጉሥ ሳቀርብ ለእኔ ለራሴ የደስታ ምንጭ መሆኑ የተገለጸ ነው ፤ ልናገረው አያስፈልግም። ደግሞ የኔን የራሴን ሐሳብ እንድናገር ፈቃድ እንድታደርጉልኝ እለምናለሁ።

የግርማዊት ንግሥትንና የግርማዊ ንጉሥን አገር መጥቼ ለማየት ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ምኞቴ ነበር ። አሁንም በፊቴ ቀርቦ የሚታየኝ ነገር ሁሉ በተለየ ደስ የሚያሰኝ መሆኑን ለመግለጽ እወዳለሁ ።

ይልቁንም ታላቁ ደስታዬ በዓለም መንግሥታት መካከል ያለውን ስምምነትና በጎ ፈቃድ በጽኑ መሠረት ላይ ለመመሥረት፤ ግርማዊት ንግሥትና ግርማዊ ንጉሥ የኢትዮጵያ መንግሥት እንዲረዱኝ እምነት ስለ አለኝ ነው ። እንዲሁም ግርማዊነታችሁ እንደሚያውቀው የመንግሥቴ ዋናው ፖሊቲክ ይህንኑ ነገር ከፍ ከፍ ለማድረግ ነው ።

አሁንም እነሆ በግርማዊ ንጉሜ እጅ የተፈረሙ ሁለት ደብዳቤዎች ለግርማዊት ንግሥትና ለግርማዊ ንጉሥ አቀርብለሁ ። ደብዳቤዎቹ አንዱ የእኔን መሾም የሚያስታውቅ ነው። ሁለተኛውም፡ከእኔ በፊት የነበሩትን ሚኒስትር ከኢትዮጵያ መጠራታቸውን የሚያውስታውቅ ነው ። ኅዳር ፳፱ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም

ሚኒስትሩም ድስኩራቸውን ተናግረው ሲጨርሱ ፡ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ፡ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን መለሱ ።

After the Minister pronounced his speech· His Majesty King Taffari made the followlng speech:

ክቡር ሆይ ።

የግርማዊ የእንግሊዝ ንጉሥ የሕንድ ንጉሠ ነገሥት ከፍ ያሉ እንደራሴ ወደ ኢትዮጵያ ስለመጡ በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና በእኔም በራሴ ስም በደህና ለመድረስዎ የወዳጅነት ምኞታችንን እንገልጻለን ።

ከታላቁ ንጉሥዎ ከግርማዊ ጆርጅ አምስተኛ ፡ ክቡርነትዎ ለእኛ ለማድረስ በታዘዘው መልእክት በተለየ ደስ ብሎናል።

ክቡር ሆይ ። የወዳጅነት ሐሳባችንንና ለግርማዊነታቸው ለንጉሣዊ ቤተ ዘመዳቸውም ደስታ የምናደርገውን ምኞታችንን ፈቃድዎ ሆኖ ለግርማዊ ንጉሥ እንዲያደርሱልን እንለምናለን ።

ክቡርነትዎ ራሱ በሚገባ እንደ ገለጸው ኢትዮጵያ ፍጹም ሰላማዊ በሆነ መንገድ በስልጣኔ ወደ ፊት ለመቅደም መንግሥታችን ያሰበውን አሳብ ለመፈጸም ከሌሎች መንግሥቶች ጋራ እየተስማማች ለመኖር ፈቃዱ ነው ።

ተልከውም ስለ መጡበት ሥራ አፈጻጸም የገለጹት አሳብ ታማኝ በሆነ መረዳዳት መሥራትዎ እርግጥ መሆኑን አይሰልን ለሀገርዎና ለጥንታዊ መንግሥታችን ልማት የሚጠቅሙትን ልዩ ልዩ ነገሮች ከክቡርነትዎ ጋራ ወደ ፊት የምንመረምረው እርስ በርሳችን በመተማመንና በወዳጅነት መንገድ ይሆናል ።

ዛሬ በያዙት ክፍ፡ ባለ ሥራ ላይ ከርስዎ በፊት ከነበሩ ክቡር ሙሴ ሻርል ቤንቲንክ ጋራ መልካም የሆነ መቀራረብና ፍጹም የሆነ የትህትና ሥልጣኔ የተመላባቸው መገናኛዎች መንግሥታችን ዘወትር እንደያዘ ነበር ። ከክቡርነትዎም ጋራ እነዚሁ መልካም መገናኛዎች እንደገና እንዲታደሱ እናምናለን።

የግርማዊ ንጉሥ ከፍ ያለ መልክተኛና ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ሆነው ወደ ንጉሡ ነገሥታት መንግሥታችን ስለ መጡ ዛሬ በመቀበላችን የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና የእኔም የራሴ ደስታ መሆኑን እንገልጽልዎታለን ።

Your Excellency the Envoy Extraordinary of His Majesty the King of England and Emperor of India.

We wish to express to you, on behalf of Her Majesty the Empress and on my own behalf, our friendly feelings and congratulations on your safe arrival in Ethiopia,

It is a special pleasure to us to receive the message with which Your Excellency was charged to deliver to us from your Gracious Sovereign. His Majesty King George V.

In this connection we beg Your Excellency to be so good as to convey to His Majesty the King our friendly feelings and happiest wishes to His Majesty and the Royal Family.

As your Excellency has so well said, Ethiopia is very anxious to develop on peaceful lines and to progress towards civilization, to carry out the intentions of our Government, and to remain on terms of friendship with the other Governments.

The intention now expressed to us inregard to the conclusion of the task entrusted to you has reneWed to us the true fact of your loyal collaboration. The various questions Which may be discussed in the future With Your Excellency and are beneficial alike to the advantage and prosperity of Your country and our ancient Empire. Will be conducted bettween us in mutual confidence and in a friendly manner

Our GOuvernment alwys had very close friendly relations and courteous connections With your predecessor, His Excellency Mr Charles Bentinck, in the high post Which you now hold, and We beg that these friendly relations may be renewed with Your Excellency.

At the same time, We should like to express to you that it is a pleasure to Her Majesty the Empress and to myself to receive you this day at Our Imperial Court as His Britannic Majesty's Envoy Extraordinary and Minister plenipotentiary.

30th November 1928.

21st Hidar1912

ደስኩሩም ከለቀ በኋላ ወደ ግርማዊት ንግሥትና ወደ ግርማዊ ንጉሥ ቀርበው የሹመታቸውን ደብዳቤ አስረከበው መድፎች ተተኰሱ ፤ ከዚህም በኋላ እንደፊተኛው ታጅበው ወደ ሌጋሲዮን ተመለሱ ።

His majesty having finished His speech the Minister stepped to ward Their Majesties deliverd His credentials, and at the same time guns were fired in honour of the occasion. After the ceremony he was escorted in the same manner to the Legation·

የአቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን በዓል አከባበር በግሪኮች ቤተ ክርስቲያን ።

ታኅሣሥ ፯ ቀን እሑድ ከጥዋቱ በ፫ ሰዓት ተኩል የግሪክ ኦርቶዶክስ ማኅበር የአቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃንን በዓል የሚያከብርበት ቀን ስለሆነ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱንና ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪን ፤ ብዙዎቹንም የኢትዮጵያ መኳንንት ጠርቶ ነበር ። በዚሁም ቀን ሰዓቱ ሲደርስ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ግርማዊ ንጉሥ በክቡራን መኳንንቶቻቸውና በሠራዊቶቻቸው ታጅበው መጡ ። ወደ ቤተ ክርስቲያኑም እንደ ገቡ ሥርዓተ ቅዳሴ ተጀመረ ። የሥርዓተ ቅዳሴውም አደራረግና የካህናቱም አኳኋን እጅግ ያምር ነበር ። ሜትሮፖሊስ ዘአኩስም ሞን ሲኘር ኒኮላም ሲቀድሱ በየንባቡ ውሥጥ አንዳንድ ጊዜ በግዕዝ ሲናገሩ ይሰማ ነበር። ሌሎቹም ግሪኮች በአንድነት ሁነው ተሠጥዎ ሲቀበሉ የመስማማታቸውና የድምፃቸው ማማር እጅግ መልካም ነበር።ከቅዳሴውም በኋላ ሜትሮፖሊስ ዘአኩስም ሞን ሲኘር ኒኮላ የአቡነ ሰላማን ታሪክ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ አሳምረው ተናገሩትና በአማርኛ ተተርጉሞ ለየሰው ተሰጠ ። ከዚህም በኋላ ሜትሮፖሊስ ዘአኩስም ሞን ሲኘር ኒኮላ ብፁዕ አቡነ ሚሊቴዎስ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ለግርማዊ ንጉሥ የላኩላቸውን ሽልማት ባርከው ይዘው ቀርበው የሚከተለውን ቃል ተናገሩና ሽልማቱን አስረከቡ ።

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ግርማዊ ንጉሥ ሆይ ።

የልቤን ደስታ አፌ ተናግሮት አይዘልቅም፤ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱንና ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ከዚሁ ከቅዱሳኑ ቤተ ክርስቲያን እኔ ከኢትዮጵያ ባሉት ለግሪካዊ ኦርቶዶክስ አቡንና ለእስክንድርያና በሙሉ አፍሪካ ፓፓ ወፓትርያርክ ሊቀ ጳጳሳት ለሆኑት ለብፁዕ ሜሌቲዎስ እንደ ራሴ የሆንሁት እናንተን በመቀበሌ ምስጋናዬ እጅግ ነው ። አሁንም በአቡነ ሰላማ ለኢትዮጵያ የመጀመሪያ ሐዋርያ ሆነው በግሪኮችና በኢትዮጵያውያን መካከል ፍቅርንና ወዳጅነትን ያጸኑልን ዛሬ በዚሁ በክብረ በዓላቸው ቀን በእስክንድርያ የኦርቶዶክሳዊ ቤተ ክርስቲያን ስም በኩል እጅግ የከበረ ምስጋናው-

ን በጉባኤ ልናገረው ምክንያት ሆነኝ ። ለምስጋናውና ለወዳጅነቱም ምልክት ሊሆን የእስክንድርያና በሙሉ አፍሪካ ፓፓ ወፓትርያርክ ክቡር ወብፁዕ ሜሌቲዎስ አሁን አዲስ የእስክንድርያ አርቶዶክሳዊ ቤተ ክርስቲያን ያቆመውን ሐዋርያ ወንጌላዊ የቅዱስ ማርቆስን ሁለት የወርቅ መስቀል ንሻንን ይሰጣሉ በዚህ በተቀደሰችው ቀን በቤተ ክርስቲያናቸው ውሥጥ ይህነኑ የወርቅ መስቀል ንሻን ከምስክር ወረቀቶቹ ጋራ ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ለግርማዊ ንጉሥ ክብረ በዓላቸውን ለማክበር ከመጡት ሕዝብ ክርስቲያናት ፊት በጉባኤ በመስጠቴ እድግ የታደልኩ ነኝ።እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ በረከቱንና ምሕረቱን፥ ሕይወቱንና ዕድሜውን፥ ከሰላም ጋራ ይስጣችሁ። አሜን ።

በዚያን ጊዜም በዚያ የነበሩ የግሪክ ሕፃናት ብዙ አበባ በትንንሽ የስፌት እቃ እየያዙ መጥተው በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና በግርማዊ ንጉሥ ላይ ነዙት ። ያን ጊዜም የተደረገው የአቡነ ሰላማ በዓል አከባበር ሰውን ሁሉ ደስ አሰኘው። ይልቁንም የግሪክ አርቶዶክስ ማኅበር ደስታቸው ከልክ ያለፈ ነው።



የእስክንድርያና የሙሉ አፍሪካ የግሪክ ኦርቶዶክስ ሊቀ ጳጳሳት ብፁዕ አቡነ ሜሌቴዎስ።

ስለ ዶክተር ጋሪበድያን ነገር አንድ ስለ ወሮበላ የሚሆን የዘበኛ ትምህርት ማን ይሆን ወሮበላ።

ቤቱን ያለጠባቂ ትቶት ብዙ ዘመን ለመዞር ከዓለም ጫፍ ወደ ዓለም ጫፍ ሲንከራተት ይኖራል ክፉም መንገድ ቢሆን በደግም መንገድ ቢሆን ገንዘብን ለማግኘት ብቻ የሚጥር የወሮበላ ሥራ ነው ሙሉ እውቀት አለው ልዩ ልዩ አገር በመዞር ልዩ ልዩ አይነት ቋንቋ ያውቃል በገባበትም አገር ፈጥኖ ያገሩን ልማድ ያውቃል በገባበትም አገር ሁሉ እንግዳ መስሎ አይታይም ብዙ ንግግር አያበዛም ነገር ግን ቅንድቦቹ ከንፈሮቹ እጅ እግሮቹ ይናገራሉ ይህንንም ምልክት ሌላ ሰው ሊአውቀው አይችልም ከወሮበላ በተቀር ። መልኩንም ለመለወጥ ባሰበ ጊዜ የሰይጣን ያህል ችሎት አለው ሌላ ሰውም ለመምሰል ቢፈቅድ ማንም ማንም ሰው ሊአውቀው አይችልም ከመሰሉ ከወሮበላ በተቀር የወሮበላ መልክ ሁሉጊዜ የተለወጠ ነው ከቶ መልኩ አድሮ አይገኝም በልዩ ልዩ አገር በገባ ጊዜ ሥራውን ለመሥራት ልዩ ልዩ መልክና ልብስ ያበጃል በሚአስፈልገው ጊዜ ሁሉ አዲስ መልክና አዲስ ልብስ አያለዋወጠ ለማድረግ ይቻለዋል ።

ወሮበላ በመላው ዓለም ያለውን የሰውን ጠባይ መልክምም ሆነ ክፉ በልቡ መልቶታል በሕዝብ መካከል የሚአስደንቅ ሁኔታ ወደላይ ከፍ ይላል ሲዋረድም ይፈጥናል በማናቸውም ማኅበር ትልቅም ሆነ ትንሽ የማኅበሩ ክፍል ይሆናል ከማናቸውም ጋራ የመስማማት እውቀት አለው በጨዋ ማኅበርም ለመግባት ባሰበ ጊዜ እንደጨዋዎች መስሎ ይልቁንም ኩሩና አዋቂ ተከባሪ መስሎ ይታያል ።

በተዋረደውም ሥፍራ መግባት ባሰበ ጊዜ የዋህ መስሎ ይታያል ። ከአዋቂ ጋራ ንግግር በጀመረ ጊዜ የፈላስፋውያን ጥያቄ ያመጣል ። ወሮበላ አንድ ቀን ብርሃን ይሆናል በማግስቱ ግን ጨለማ ነው ። አንድ ቀን ደግ ይሆናል በሁለተኛው ቀን ክፉ ይሆናል ። አለመጠን የማያቀርቡት የሰይጣን ፍጥረት ነው የመንገድ ላይ አታላይ ነው በሌሊት ጨለማ በሆነ ጊዜ እንት ያለ ነው ከእጆቹ የሚያመልጥ መንገደኛ ። ቀን በብርሃን ጻድቅ ሰው ነው ድሆችን ባገኘ ጊዜ ምጽዋት ይሰጣቸዋል ። ደግሞ በተዋረደ የመሸታ ቤት ውስጥ ከተዋረዱት ጋራ ጠጥቶ ሰክሮ ይታያል እንዲሁም በሌላ ቀን በማዕርገኛ መቀመጫ ገብቶ ታላቅ ሰው መስሎ ይታያል በዚያም ጊዜ የቀረበለትን መብልና መጠጥ መምረጥ ይጀምራል የክበርቴዎችን አቀማመጥ ጠባይሁሉ ይይዛል።ወሮበላ በየዓይነቱ ኑሮ ይጀምራል ነገር ግን አይጨርሰውም ማታለል ያውቃል ይልቁንም ማምለጥ መሰወርያ ይሆንለታል የመልካሞቹ የብልሆቹ ዘበኞች አይኖች እንኳ ፍለጋውን ማግኘት አሆይንላቸውም ከመ ቅጽበተ ዓይን እንደ አንድ ሰይጣን ይሰወራል እንደ መልአክም ይታያል ነገር ግን ዕድሉ በጠፋ ጊዜ ወህኒ የናቱና ያባቱ ቤት ይሆናል ከቶ ሰንሰለት አይፈራም ወሮበላ አምላክ የፈጠረውን አገር ሁሉ እንደራሱ መሬት ሁሉ ሰብል ይመለከተዋል መላው ዓለም በድካም ያገኛል ወሮበላ ግን ያለንዳች ችግር ምግቡን ያገኛል ። አይዘራም ግን ያጭዳል እሱ አንዱ ባመረተው አንዱ በሰፋበት

ይመገባል በተቻለው መጠን ገንዘብ ለማግኘት ይጥራል የማይመቸው ከሆነ ግን ደም ለማፍሰስ የተዘጋጀ ነው ወሮበላ ሁሉን ነገር ያገኛል ደግሞም ሁሉንም ያጣል እንደ አንድ ጨክኝ በሥጋ የሚኖር አውሬ ነው ። ከብት ገድሎ ሥጋውን ትቶ ደሙንና ሳንባውን ብቻ በልቶ እንደሚሔድ አውሬ ነው ከዚያም ወዲያ ደግሞ ብዙ ቀን ራብተኛ ይሆናል እንዲሁም ወሮበላ አንድ ቀን ይጠግባል አንድ ቀን ደግሞ ይርበዋል አንድ ቀን ይከብራል በሁለተኛውም ቀን ይደኸያል አንድ ቀን ጻድቅ ይሆናል አንድ ቀን ኃጥእ ይሆናል ወሮበላ በያገሩ ሚስቶች ያገባል ልጆችም ይወልዳል ከማናቸውም ነገር ጋራ የተስማማ መኪና ነው ከፖለቲከኞች ጋራ የሚስማማ ነው ። ሽብርም ለማድረግ ባስፈለገ ጊዜ ቀልጣፋ ነውና እሱ ይመረጣል በማናቸውም መንገድ አምባገሮ የሽፍታ ሥራ ለፀሥራት ባስፈ ገ ጊዜ የተመቸ መሣሪ ነው ። አንዱን መንግሥት እርስ በርሱ ለማጣባስፈለገ ጊዜ ደስ የሚአሰኝ መኪና ነው ።

የዋሁ ንጹሑ ሕዝብ ሆይ ተጠንቀቅ በመኻከልህ በኪስህ ብዙኅ ወሮበላ አለና ብዙ ክፉ ነገር ይሠራብሃል በፊታቸው በሮች ሁሉ የተከፈቱ ናቸው በቀን የኢትዮጵያ ወዳጆች ናቸው በሌሊት ግን መቃብር ይምሳሉ ታምር የሚደረግበት ዘመን ቀድሞ አልፎአል ዘመኑ የሥራ አዋቂዎችና የብልሆች ዘመን ነው ። እርግጠኛውን ነገር ለመምረጥ የምንችልበት ዘመን መቼ ይሆን? ለሚጠቅም ወዳጅ ለሚጐዳ ወዳጅ እንደሥራው መጠን የምንሰጥበት ጊዜ መቼ ይሆን? አታላዮች ደስ ብሏቸው ያጨበጭባሉ የታመኑ ግን አዝነዋል ። ሞት ስለ አታላዮች ትሁን ። ክብርም ለታመኑ ትሁን ።

ከፒቴን ባቢኪያን ።

ስለ ልዕልት መነን ።
ወደ አዲስ አበባ መግባት ።

ልዕልት መነን ከሔዱበት አገር ታኅሣሥ ፱ ቀን ከተከታዮቻቸው ጋራ አዲስ አበባ ገቡ ። ልዕልትንም ለመቀበል ልጅ እስፋ ወሰን ተፈረና ብዙም መኳንንትና ሠራዊት ወደ ባቡር ማረፊያ ወርዶ ነበር ። ልዕልትም በገቡ ጊዜ በባቡር ማረፊያ የተሰበሰበው ሕዝብና ሠራዊት በዕልልታና በደስታ ተቀበላቸው ።

ልዕልትም ከባቡሩ ማረፊያ ወደ ቤታቸው ባማረ አቶሞቢል ሁነው ሲጓዙ በፊትና በኋላ ፈረሰኞች አጀቡዋቸው ነበር ። ቀጥሎም ልጅ እስፋ ወሰን ባማረ አቶሞቢል ሁነው ይከተሉ ነበር ፡ ከዚያም በኋላ ብዙ መኳንንት በየአቶሞቢላቸው ሁነው አጅበው ይጓዙ ነበር ። አቶሞቢሉም ሁሉ በሥርዓት ሲጓዝ መንገዱ የአቶሞቢል ሰንሰለት የተዘረጋበት መስሎ ላይታው ያስገርም ነበር ። ብርሃንና ሰላም ልዕልት መነንንና አብረዋቸው የሔዱትን መኳንንት እንኳን ደኅና ገባችሁ ይላል

የውጭ አገር ወሬ

የጀርመን ሌጋሲዮን ራድዮ የታኅሣሥ ፰ ቀን የዕለት ወሬ

ሉጋኖ ፡ ስትሬስመን ከቲቱሌስኮ የሩማንያ ሚኒስትር ጋራ ስለ ጀርመንና ሩማንያ የንግድን ጠቀሜታ መስማማት ተነጋግረዋል ።

ማርሴይ ፡ ጀኔራል ጉሮድ (የፈረንሳይ) ወደ ቦምባይ ለመሔድ በመርከብ ተሳፈረ የእንግሊዝ ጋዜጣ እንደሚያወራው ወደ ህንድ የሔደበት ምክንያት የእንግሊዝንና የፈረንሳዊን የቅኝ አገር ነገር ለማደላደል ነው ይላል ።

አቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ አቤርላንድ አቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።



አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባ ኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኜቶና ባለባትሪ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል «ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው

ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

COGNAC SaEsA. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅስ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማተክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



ዝኒት የእጅ ሰዓት ።

በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማተክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩ ግ ቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬድባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዠምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጾ ሳያስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ ብቻነው

የዘህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

RUGBY

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዲልፊአ በቦስቶን በማድራስ በአደንና ባጅበቲ በነዚህ ከተሞችና፤በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አሉው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ላስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንደር ኩምፓንያ ጋዝ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ።

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በካፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በካፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ኒኮላ

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዌድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden

Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad



ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሲንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ፣ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያከማል

አደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ሱቅ ነው ።

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።



ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድይር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይሄዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደ ልብ ያስኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋይም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንክራ ነው ። በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድይር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው ።

ጉድዩር ግዙ

GOODYEAR

2-28-14

በዳግማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አራተኛ ዓመት ፣ ቊጥር ፶፪
4 me ANNÉE № 52

ሐሙስ ታኅሣሥ ፲፰ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም ።
JEUDI 27 DECEMBRE 1928

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé " Lumière et Paix ".

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ደረክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሲገዛ በፈረንጅ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ብርሃንና ሰላም ።
አራተኛ ዓመት መጨረሻ ።

ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ መታተም ከተጀመረ ይኸው አራተኛው ዓመት በዚሁ ቊጥር መፈጸሙ ነው ብርሃንና ሰላም ጋዜጣችን ባለፉት በአራቱ ዓመታት ሰዎች ሁሉ እየወደዱትና ማኅበረተኞቹ እየተጨመሩ በመሔዳቸው ብዙ ደስ ይለናል።አሁንም ለወደ ፊት ማኅበረተኞቹ በዝተው ጋዜጣው ከሁን የበለጠ እንዲሰፋ ተስፋ እናደርጋለን ።

ለሕዝባቸው ጥቅም እያሰቡ መልክካም ቃላት እየጻፉ የሚልኩልን ተላላኪዎችንም በጣም እናመሰግናቸዋለን ። ይህም ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ መልከም ዕድለኛ ነው ።ትልልቅ ነገር ይጽፋል ፤ ደግሞም የበለጠ ነገር እንዲጽፍ ተስፋ አለው ። አራተኛውን ዓመት አስጀምሮ ላስጨረሰን እምላክ ምስጋና እናቀርባለን

ዕድሜ ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ዕድሜ ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር

ለብርሃንና ሰላም የተሰጠ መወድስ ።

በማዕከለ አኃው ወእኅት ወአዝማደ ሥጋ ።
እመ ተሐፅኖትከ ኮነ በክብር እንበለ ኅማር ።
ብሉያነ ዘመን ትጌሥጽ ወኢ ተኃፍር ።
አምጣነ ገሠጽከ በቃልከ በትር ።
ለዘወለደተከ ኢትዮጵያ፤ ዘእምነ ፀሐይ ትብርህ ወትትሌዓል እምአድባር ።
ሐሊብከ ጣዕመ ቃልከ ወነገርከ መዐር ።
ያጠልል አዕጽምተ ወነደ ሕሳት ያቈርር ።
ብርሃንና ሰላም ወልድ እንተ አግእዚት በዙር ።
ዘበመኳንንት መኰንን ወዘበሊቃውንት መፈክር ።

ንጉሥ ተፈሪ የነገሡበት ቀን በዓል በጎጃም ።

መስከረም ፳፯ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ የኢልማ ፤ ደንሳ ከተማ አደት መድኃኔ ዓለም ላይ ትልቅ በዓል ተደረገ። የኢልማና ደንሳ ሠራዊትና አብሮ ያለው ደጅ ጠኚው መኳንንት ከሠራዊት ጋራ ጥዋት የጀመረ እስከ አራት ሰዓት ድረስ ሰልፉ ጨርሶ ተሰናዳና ሺና ወንዝ ጀምሮ እስከ ግቢ ድረስ ደረሰ።ምድረ ግቢውም በሐርና በግምጃ ታጥሮ አጊጦ ነበረ።ተግምጃ በላይም ብቅ ብቅ ባሉት እንጨቶች አበባ ተሰክቶባቸው አልፎ አልፎም ሰንደቅ አላማ ቁሞበት ነበረ።አራት ድንኳንም ነበረበት። አንዱ እንደ ትልቅ አዳራሽ ያለ ነው ስጋጃና የከበረ ምንጣፍም ተነጥፎበት ነበረ።በዙፋኑ አልጋ ላይም ፍትሎ ወርቅ ዘቦ ያልጋ ሰርፍ ነበረበት፤አጎበሩም በጥሩ ሐር ያጌጠ ነበረ፤ሁለተኛውም በሥርዓት ተነጥፎ ለትልልቆች መኳንንትና ለእንግዶች ማረፊያ ነበር፤ ሶስተኛውም ጠጅና ሽምጋኝ፤መደከሳና ኩመል፤የወይን ጠጅም፤ሌላም አረቂ በየይነቱ ብርሌና ብርጭቆ ነበረበት።የመኳንንትም ማለፍያ ወጥ በጎጃም የተሠራ ሸሀላ ድስት ስፋቱ ተሁለት ክንድ ተርፍ ነበረ፤በስተሥሩም ጥላት እንዳያደርግ የቀርቅሃ ጥራር ተሠርቶለታል ።

አራት ሰዓትም ሲደርስ ክቡር ራስ ኃይሉ ራስ ወርቅ በራሳቸው ደፍተው እንደ ፀሐይ የሚያበራ እጅግ ያማረ የመዓርግ ልብሳቸውምን ለብሰው ተእልፍኝ ብቅ አሉ ። ተመንግሥትም ተሸልማ የመጣችላቸውን በቅሎ ተቀምጠው እስከ ሰልፉ መጨረሻ ሰልፉን ፈቅደው ከዚያ በኋላ ጠበንጃቸውን አንግተው፤ጋሻቸውን አንግበው፤ በዱንጉላ ወጡ፤የለበሱትም የመዓርግ ልብሳቸው ግርማ በጣም በሚያስደንቅ አኳኋን ሁነው ታዩ፤ፊታቸውም (ደስታቸው ምልክት ፈገግ ፈገግ ንያ) (ጥበት የገግን ይመስል ነበር፤በፈረሰኞች መኳንንቶቻቸውና በነጭ ከተ

ለበሽ ዘበኞቻቸው በሰልፍ ማኸል ሁነው ግቢ ድረስ መጡ፤ ከፈረሳቸውም ወርደው ከድንኳኑ ዘንድ ቆሙ፤ መኳንንቱም በቀኝና በግራ ቁመው ነበር፤ ተከታትለውም ክቡር ግራዝማች ገብረ ዮሐንስ ደረሱና እጅ ነሥተውም ተግርማዊት ንግሥተ ነገሥት የመጣውን ወረቀት ሰጡ፤ የራስ ጸሐፊ ትእዛዝ ክቡር አለቃ አምሳሉም ተቀብለው በአዋጅ አነበቡት ።

መነበቡም ከተጨረሰ በኋላ ክቡር ራስ ኃይሉ ጠበንጃቸውን እንዳነገቱ፡ ጋሻቸውንም እንዳነገቡ ከመኳንንት ሁሉ ጋራ ሁነው እጅ ነሥተው ከዚያ በኋላ ወደ አልጋው ሔደው ተቀመጡ። በውጭም መትረየስ ሲተኰስ ይሰማ ነበር፡ ይህም ሲሆን አምስት ሰዓት ይሆን ነበር። እምቢልታ፡ መለከት፡ ጥሩምባም ይነፋ ጀመር። የገዳማቱ ካህናቶችም ልብሰ ተክህኖዋቸውን ለብሰው በሥርዓት ሁነው ንሴብሖ ያሉ ነበር ።

ምድረ ግቢና የሰፈሩ ሰውም እልልታውን ያቀልጡት ነበር። ወታደሩም ሰንደቅ አላማውን ኢየያዘ ሆ እያለ አዲስ አበባ ያብባል ገና ኢያለ በየአለቃው ሁኖ በራስ ፊት ያልፍ ነበር የሠራዊቱም ብዛት ሲያዩት የከተማ እንጂ የጉዞ አይመስልም ነበር። ስለዚህ ሴቶች አቋርጠው ኢየገቡ ይዘፍኑ ነበር፤ የሰፈሩ እልልታ ግን ፈጽሞ አይበርድ፡ ሠራዊቱ የፎሥሐ ሆታ፡ ሴቱ የደስታ እልልታ ሲያደርግ የራስ ልጅ ወይዘሮ ድንቅነሽ የመኳንንቱን ወይዛዝርና ገረዶቻቸውን ያዘው ተእልፍኝ ወጥተው በአቋራጭ ውሥጥ ሁነው ያስዘፍኑ ነበር፤ ከዚያ በኋላ በስድስት ሰዓት ግብር ገባ፡ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስም ግብር ሁኖ ዋለ፡ ድንኳኑ በጣም ሰፊ ስለነበረ የሰው እኵሌታ የገባ ይመስለኛል ዳሩ ግን የቀረው እኵሌታው ሳይገባ ያ ግብር ገብቶ የወጣ ሰው አቋርጦ ዘፈኑን ጀመረ ያልበላውም ግብሩን ትቶ ተዘፋኙ ጋራ አንድነት ሁኖ ከደስታው ብዛት መብሉን ስለ ቀረበት ሳይቈረቈርበት ያጨበጭብና ይዘፍን ጀመር ።

በኤሌትሪክ መብራቶች በዙርያው አብርተውላቸው እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ ዘፈኑ ደምቆ ነበረ፤ እንዲሁም በዙርያ ያሉቱ የገዳሞች ካህናት ኢየመጡ ንሴብሖ ይሉ ነበር፡ ደስታውና ዘፈኑ ሳያቋርጥ በሳምንቱ እሑድ ቀን እንደገና ሰልፍ ሆነ፡ ድንኳንም በስፍራው ተተከለ፡ ምንጣፍም በሥርዓት ተነጠፈበት ። ራስም በተሸለሙቸው በቅሎ ሁነው ዓይን የሚወጋ እንደ ፀሐይ የሚያንጸበርቅ ካባ ለብሰው ወጡና ወደ ድንኳኑም መጡና ክቡር እቶ ተሰማ የዚያን ጊዜ ደረሱ። በስተቀኝ ባጠገባቸው ቆሙ፤ መኳንንቶቻቸውም በቀኝና በግራ ቆመው ነበር ። ጸሐፌ ትእዛዙም ተግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ የመጣውን ወረቀት በዋጅ አነበቡት ።

መነበቡም ከተጨረሰ በኋላ ክቡር ራስ ኃይሉ መኳንንቱም ሁሉ እጅ ነሡ፤ ከዚያ በኋላም መትረየስ በውጭ ይተኰስ ጀመር፤ እምቢልታና መለከት ጥሩምባም ይነፋ ነበር። አምስት ሰዓት ከሆነ በኋላም ከትልቁ አዳራሽ ግብር ገባ፤ ከግብርም በኋላ የእምቢልታ ነፊዎች ጨወታ ሆነ፤ ቀጥሎም የሴቶች ዘፈን ተጀመረ፤ አዳራሹም በሰው ብዛት ጠበበ ዘፋኞችን አላንቀሳቅስ እስኪል ድረስ ። ራስም አዶኩሉኝ ኢየከፈቱ በትልቅ ሰሐኒ ኢያስገለበጡ ሰውን ሁሉ በሽቱ ያስረጩት ነበር ። ትልልቆች መኳንንትም እቶ ተሰማም ማኸል ገብተው ሲዘፍኑ ራስ ከበሮውን ከፊታቸው አስቀምጠው ያስመቱላቸው ነበር ። ከዚያ በኋላም ከእጅግ ደስታና እልልታ መኻከል ብዙ ትልልቆች ከዘፈኑ ውሥጥ ገብተው ይዘፍኑ ጀመር ። የዚያን ጊዜ የነበረው የደስታና የእልልታ የዘፈኑም ድብልቅልቅ አይቼ አላውቅም፤ አኳኋኑን ላልነበረ ሰው ባይኑ ካየው ሰው ጋራ ለማስተካከልና ጽፎ ለማስታወቅ ቃላት ይገኝ አይመስለኝም ።

በጉዞ እንዲህ ሁኖ ያማረ ከከተማቸው ከማርቆስ ሁኖ ቢሆን እንዴት በሆነ ።

ኢትዮጵያ ሆይ ደስ ይበልሽ፤ እልልም በይ፤ ትናንት መሬዮችሽ እኔ እነግሥ እኔ እነግሥ በማለት፡ ሕዝብሽም ለዚህ እገዛለሁ ለዚያ አልገዛም በማለት በሚነሣው ሁከት የልጆችሽ ደም በከንቱ እንደ ውኃ ይፈስ ነበር ። አሁን ግና ፀሐይሽ ደመቀ የመለያየትም ጉም ለቀቀሽ፤ የፍቅር መጐናጸፍያ ተዘረጋብሽ፤ ያንድነት ጉልበትም ነገሠብሽ ።

ኢትዮጵያ እንደ ኰራችን ንጉሣችንም በሕይወት ይኑሩልን። ያየ።

ስለ አንድ ሊቅ ተረት ።

እውቀትን በተረት ፡ ጽሕፈትን በወረቀት ፡ ነውና አንድ የተማረ ሊቅ በአንድ ደብር ቤተ ክርስቲያን ሲኖር እሑድና በዓላት በሆነ ቀን ከቤተ ክርስቲያን ሕዝቡ ሲሰበሰብ ጉባኤ አድርጎ ትሕትና ልበሱ ወደ እግዚአብሔር ጸልዩ እርስ በእርሳችሁ ተፋቀሩ እያለ ያስተምር ነበር ። ከዕለታት አንድ ቀን ከመንደር ገብቶ ኃጢአት ሲሠራ ሰዎች አገኙትና ምነው ወንድሜ ትሕትና ልበሱ ፡ ወደ እግዚአብሔር ጸልዩ ፡ እርስ በእርሳችሁ ተፋቀሩ ፡ እያልክ ስታስተምር እንደዚህ ያለውን የማይገባ ሥራ ለምን ሠራህ ብለው ቢጠይቁት መጽሐፉ ይላል እያልኩ ነው እንጂ ያስተማርኩት እኔ ነኝ መቼ አልኩ ብሎ መለሰላቸው ይባላል ። ነገር ግን ምንም ቢማሩና ቢመራመሩ መንፈሳዊ እውቀት ካልተጨመረ ማናቸውም ነገር በዓለማዊ እውቀት አይወሰንም ። መጽሐፍም ይላል ለመብል ብቻ አልተመሠረተም እላለሁ ብሎ ተዘክሮ ሞትን፡ ፈሪሃ መለኮትን፤ ተመልክቶ ድሀ የሚነግበትን ፡ መንግሥት የሚጠቀምበትን ፡ ለማሳሰብ ነው ። ሕዝብ እርስ በእርሱ ሲፋቀር ብዙ አገር ያለማል፤ ገበሬ ከበሬው ጋራ ሲስማማ ብዙ መሬት ይታረሳል፤ መሬት ከዝናም ጋራ ሲስማማ ብዙ እህል ያፈራል ።

ገበሬው ፦ ፈሬ ይሂልና አዝመራ ። አትረዱትምይ በተራ በተራ።

ግራዝማች ቀኛዝማች ራስ ደጃዝማቹ አለማረሳቸው። እውቀት አይዘሩምይ በገዛ አገራቸው። ድንቁርና ረኃብ ሕዝቡን ሲፈጃቸው። በጥበብ ገበታ አለማብላታቸው። ቀኑ እስቲመሽ ነወይ ጊዜ እስቲያልፍላቸው።

ዳሩ ግና ቢሆን ሰዎች የሰሙት እንኳ በትንሽ ቃል ቁሜ ላመልከት። በዚህ ተወስኖ የኛማ አገር ቤት። ፍቅርና ትሕትና ተጠልተውበት። ይህ ሁሉ እንብላ ባይ ንጉሥ አውቀውት። የማይችሉት ሆነ የማይጣሉት። በልቡ እየከዳ ሲምል ሲገዛት። የማያልፍ ይመስላል ሞት የሌለበት።

ድንቁርና እውቀትን ሲያማው ሰምቼ። ይኸን ጽፌያለሁ ከልቦና አውጥቼ

ኃይለ ሚካኤል እያልቅበት ።

ነጋ፡ ጎህ ቀደደ ።

እስከሁን የኢትዮጵያ ሥልጣኔዋ የጨረቃ ጥላ ነበር፡ አሁን ግን ነጋ፤ አእዋፋት ተንጫጩ፤ ጌታችን ሆይ ክብር ተመስገን ያን ጨለማ ወስደህ ይህን ብርሃን ያመጣህ ሲሉ ጮራ ፍንትው አለች፤ በማናቸውም አገር የሥልጣኔ መሠረት የሰው ነጻነት ነውና ይህንኑ መሠረት ለማድረግ ከጥቂት ዓመቶች በፊት የባሮች ነጻነት ተመሥርቶ የባላገሮች ባርነት እስከሁን በመቆየቱ ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ዘርግታ እንባዋ በደረቷ እየጐረፈ ብታለቅስ የእግዚአብሔር ፍርድ በንጉሥ አፍ ነው እንደተባለው እነሆ ባላገሮች ነጻነትን አገኙ ከቀሩት አገሮች ይልቅ ኢትዮጵያ ባለመና ባለንዋይ መሆኗን ማንም አይስተው ። ንዋይ ሳላት ንዋይዋ መና ሳላት መናዋ አሁን ከሰስት ዓመት ወዲህ እህል፡ ጥጥ፡ ቅቤ፡ ሥጋ፡ ይህንንም የመሰሉ ለመኖና ለልብስ የሚሆኑ የሩቅ ማቅረቢያ ወደሩቅ ማድረሻ የተፈጥሮ ተንቀሳቃሽ መሳሪዎች ዋጋቸው እያደገ በመሄዱ አብዛኙ ኢትዮጵያዊ የእግዚአብሔር መዓት ነው የሚል ነው ።ይህን የሚል የተሳሳተ ነው ቢያውቀውስ ያገዛዝ መዓት ነው። እንዴት ቢሉኝማ መጀመሪያ ማስረጃ አንድ ባላገር ልጅ የሌለው ነው እሱ ሲሶ እርሻ ሲያርስ ሚስቱ ያመት በዓል ዱቄት ስትፈጭ ሁለቱ ለሌላ ሲሠሩ ውለው ማታ ምግባቸውን ቆሎ በልተው ይህንኑ ተመስገን ብለው አድረው ማለዳ እደጃፍ መቶ አለቃቸውም ዋስ ጥራ ይለዋል፡የሚዋሰው ጠፍቶ የሚከፍለው አጥቶ ይታሠራል፡ እንግዲህ የዚህ ሰው መሬት ጠፍ በመሆኑ እህል ጎደለ።

ሁለተኛው ባላገር አንድ ልጅ አለው ልጁ እጭት ሄዶ አባቱ ሲሶ እርሻ ሄዶ ሚስቱ፡ ለሻለቃ ወይም ለመልከኛ ዱቄት ተፈጫለች እንግዲህ ሁሉም ባሮች ናቸው

ሶስተኛው ባላገር ብዙ ልጆች የወለደ ነው እነዚህ ልጆች ምንም አባታቸውን ለማገልገል ቢቀመጡ በጭስ የሚባል እገዛ አለና ለጭስ መጻኛ ወታደርነት መጥተው ብረት አንሳ እንሱ ተብለው የወታደርነት ሥራ ሳይማሩ ወታደር ተብለው የወር ተራቸው ቀን እስኪደርስ በማውደልደል የወስላትና ሥራ ይማራሉ እንግዲህ ገበሬ አንሶ በላተኛ ስለበዛ ምግብ ውድ ሆነ ። አሁን ግን ለሰው ነጻነት ስለተሰጠ እኛ መራባችን ቀርቶ ተርፎን ለተራበ ልውጫ ተቀብለን ለመስጠት የምንችልበት ጊዜ ደረሰ የርሻ ሚኒስቴር በየጊዜያቱ ለገበሮች ማትጊያ ነጻነታቸውን መጠበቂያ ደምብ ስላገኘ ተንግዲህ ወዲህ ብንራብማ ለሐላፊነቱ ግዴታውን ያውቀዋል።አሁን በጠቅላላው ኢትዮጵያ ለሰው ሁሉ ነጻነት ሰጠች መባሉ ባላገር ነጻነት አግኝቶ የሺአለቃና መልከኛ ባለ ግደዥ ነጻነት በማግኘታቸው ነው፡ ምንም የቀና ደስ የሚያሰኝ ነገር ቢሆን ልማድ ቅርታውን አይተውም እንጂ በየቀኑ ዋስ ተማግት አንድ ቀን የተገባ ውመቀበል ከፍ ያለ ጌትነት ነው ።

ሰው በዚህ ዓለም ሲኖር ጭንቁ ምንድነው? እሱ ተጠቅሞ ዘመዱ ሲጠቃ ነው ። ደስታውስ ምንድነው? እሱ አግኝቶ ዘመዱን መጥቀም ነው፤ ቅርታው ምንድነው? አንዱ ሲጠቀም አንዱ ሲጠቃ ነው፡እነሆ ኢትዮጵያ ተደላደለች በሁሉም ደስ አላት ።

ማሀሉ ጽጌ

ጅዮግራፊ

ባለ ጅዮግራፊዎች ምድር ትዞራለች እያሉ ስለሚናገሩ አንዳንድ ሰዎች ሲአጉረመርሙ እንሰማቸዋለን ። ይህ ምን ያስጐረመርማል ። ምድር ትዞራለች ማለት ከኃጢአት ተቈጥሮ አስፈርዶ ገሃነመ እሳት አያወርድ ። ደግሞም ምድር አትዞርም ማለት ከዋና ሃይማኖት ተቆጥሮ ለመንግሥተ ሰማያት የሚበቃ ዋጋ ሁኖ መንግሥተ ሰማያት አያገባ ። እንዲያውስ ምድር ብትዞርስ ባትዞርስ እኛ ምን ቸገረን ፤ የአፍሪካ ምድር ወደ አውሮፓ፡የአውሮፓ ወደ እስያ ፡ የእስያ ወደ እስጳንያ፡ የእስጳንያ ወደ አሜሪካ፡ አልተዛወረ፡ ሁሉም በየሀገሩና በየርሥቱ ይኖራሉ ፤ የፈለገ ሰው ተምሮ ተመራምሮ እስከ መጨረሻው መድረስ ነው፡ አለዚያ የሚሆነውን እያዩ የሚባለውን እየሰሙ አርፎ መቀመጥ ይሻላል ።

አስታጥቄ ወልደ አማኑኤል ።

ስለ ዘበኞች ትጋት።

ከእለታት አንድ ቀን ወደ ኮሚሳርያ ዘበኞች ቢሮ ሄጄ ያየሁትን ለብርሃንና ሰላም ወዳጆች አቀርባለሁ፤ ሁለት ሌቦች አንድ በቅሎ ሰርቀው አንደኛው እየሳበ ሁለተኛውም እየነዳ ባለገንዘቦች መስለው ሲሔዱ የከተማዋን ሕይወት ጥበቃ የተሰጣቸው ዘበኞች እነኚህን ሁለት ሌቦች አግኝተው በመንገድ ላይ ይዘዋቸው በቅሎዋ የነሱ መሆኗን ለማስረገጥ ቢጠይቋቸው በቅሎዋ የራሳችን ገንዘብ ናት ብለው መለሱላቸው።ዘበኞቹም ምርምራቸው የተተከለ ስለሆነ ውነቱን ነገር ሲመረምሯቸው ጊዜ ሁለቱም ሌቦች ለጊዜው እኛም ሐሰቱን ውነት አስመስለን የተናገርነው ያሉ ለጥን መስሎን ነበር፤ ግን ምንም ከእናንተ እጅ ልናመልጥ እንዳልቻልን ጥያቄአችሁ ያስረዳናልና በቅሎዋም የኛ አይደለች ሰርቀን መሄዳችን ነው ብለው ሌቦቹን ውነቱን ተናግረው ተያዙና ታሠሩ። ባለበቅሎውም በቅሎውን በዘበኞቹ ትጋት ስለተገኘለት መንግሥቱን እያመሰገነ በቅሎውን ይዞ ሄደ።

የከተማ ተላላኪያችን

መተባበር ኃይል ይሰጣል ።

ብቻውን የተተከለ ዛፍ ዝናብ እንደቀጠቀጠውና ቅጠሉን እንዳረገፈ ይኖራል፡ ቅጥዮቹም እንደ መለምለም ይገነጠሉ መስለው ወደ መሬት ያጐነብሳሉ

ማናቸውም አታክልት ቢሆን ብቻውን ሲሆን ከፀሐይ የሚከለክለው ሲያጣ ይጠወልጋል። ይደርቃልም በመጨረሻው ፈጽሞ ይሞታል ።

አንድ ሰው ብቻውን ሲሆን በነፍስኃይል ብቻ ሊወድቅ ይቃጣዋል ። መጠን የሌለው ራስን መውደድ የወሀ ጥሙን መቁረጫ ይመጣበታል ።

ጨርሰን ብንለያይ አንድ አንዳችን ከራስ በላይ ነፋስ ካልን ምንም ተስፋ የምናረግበት የለንም ። ምን ያህል ጭንቀት፤ምን ያህል መከራ፤ምን ያህል ጭንቅት፤ያለብን ይመስላችኋል።

ከድንቢጥ ፤ የደከመ ከእርግብ፡ መሣሪያ የሌለው የለም። ቢሆንም ጭልፊትን ብዙ ጊዜ ድንቢጥና እርግብ ሊያባርሩት ይደርሳሉ። ዙሪያውን ከበው አንድ ላይ እየተከታተሉ፤እንዲሁ የድንቢጥና የርግብን ምሳሌ እንውሰድ ተወንድሞቹ የሚለይ ሲሔድ ፍርሃት ይከተለዋል፡ቢያርፍ አጠገቡ ይቀመጣል፡ በእንቅልፉም ጊዜ ትቶ አይሔድ ስንት ናችሁ ብለው ሲጠይቁን አንድ ነን ወንድሞቻችን ማለት እኛ ነን እኛ ማለት ወንድሞቻችን ነን ብለን ለመመለስ እንድረስ እግዚአብሔር ሲፈጥረን ትንሽ ትልቅ ባርያ አርድነ አልፈጠረንም ሁሉንም ትክክል አድርጎ ነው ። ግን ከሰዎች መሀከል ግማሹ ጉልበታም ከአእምሮ ከአሳላቱ ወይም ከገደደ የማይመለስ ይሆናል ። ክብረት የጠና ፈቃድ ይሰጠዋል ። እንደነዚህ ያሉ ናቸው ከበታች ለማድረግ የሚፈልጉ የወንድሞቻቸውን ፍቅር ጫፍ የሌለው ትዕቢት ያፍነዋል፤ ያስረሳቸዋልም ። ፈጣሪያችንም እንዲህ መሆኑን ያውቃል ስለዚህ ተዋደዱ እንዳትለያዩ ደካሞች በኃይለኞች ቀንበር እንዳይወድቁ ብሎ አዘዘ ።

ለአንድ ብርቱ ሁለት መድኃኒቱ ፡ ለሁለት ብርቱ አራት መድኃኒቱ ነው ። እንደዚህ ሲሆን ደካሞች ይጎብዛሉ በአምነት ተባበረው ይኖራሉ ።

፪ኛ፡ አንድ ሰው በተራራ መንገድ ሲሔድ አንድ ትልቅ ድንጋይ ከመጣበት የማይታወቅ ተንከባሎ ጎዳናውን ዘግቶበት አገኘው በግራም በቀኝም ማለፊያ አልነበረውም ።

ይህንም ብዙ ጊዜ ፈንቅሎ መንገዱን ሊሔድ አሰበ ገፍቶ ገፍቶ ላቡን ሲጨርስ ተወው በጉልበት መድከሙን ብቻውን ሲያየው በጣም አዝኖ ተቀመጠ ። ምን እሆን ይሆን ሲመሽ ብቻየን አለስንቅ አለ መከለያ አለመሣሪያ ዓይኑን ዘግቶ ይህንን ሲያስብ ቀጥሎ ሌላ ሰው መጣ። የመጀመሪያው ያደረገውን ሞከረና እሱም ብቻውን ለመፈንቀል አለመቻሉን አይቶ እራሱን አቀርቅሮ በዝምታና በኃዘን ተቀመጠ ።

ከዚህ በኋላም ብዙዎች በኋላ በኋላ እየደረሱ አንድ አንዳቸው ለመፈንቀል ሞከሩ ግን አንዳቸውም አልተጠቀሙም ፍርሀታቸው እያደር ያድግ ጀመር ።

በመጨረሻው ተመሀከላቸው አንዱ ተነሥቶ እንደዚህ አለ ወንድሞቼ ሆይ አሁን ለአንድ አንዳችን እምቢ ያለን ሁላችንም ብንነሣ ልንፈንቀለው እንችል ይሆናል አላቸው በዚህ ጊዜ ሁሉም ተነሥተው ገፉ ትልቁም ደንጋይ ተፈንቅሎ ጎዳናቸውን ለቆ መንገደኞቹም በሰላም ተጓዙ (ትርጓሜ) አንደኛው መንገደኛ አንድ ሰው ነው ጎዳናው ዕድሜ ነው። ወይም ኑሮ ድንጋይ በዕድሜያችን በኑሮዋችን ሳናውቅ እየተደቀነ የሚያገኝን ችግር ነው ።

ይህንን ትልቅ ደንጋይ አንድ ሰው ብቻውንምንም ቢሆን ለመፈንቀል አይችልም ግን እግዚአብሔር አንድ ላይ የሚጓዙ መንገደኞች እንዳያግድ ኃይሉን ገምቶ ሰጥቶታል ።

የበዙ ። ጥለው ተጓዙ ። ብቻውን የቀረ ። ሳያልፍለት ቀረ።
ተብዙ ነኝ ። ማን ሊከለክለኝ ። ስብቻዬ ። ብዙ ነው ዕዳዬ።

ተረፈ ባንቲዋሉ ።

የፍቅር መታሰቢያ

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ መልክም ፍቅራቸውን ለምለሚቱ ሀገራቸውን ለማሥፋት ሲደክሙ ነበሩና ጥልቅ በሆነ ፍቅራቸው ሙሴ ሞዶንን ስላፈቀሩዋቸው ሙሴ ሞዶን ደግሞ ለመልክሚቱ ኢትዮጵያ ኪሊፍቶስ የሚባል ዛፍ መልኩ ያማረ ሥራው የተመሰገነ ለዘለዓለም የማይጠፋ መታሰቢያ አምጥተው መሠረት ስለ ተከሉ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና የኢትዮጵያ ብርሃን ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን ፈቃዳቸው ሁኖ ለሙሴ ሞዶን በመልክሙ ሥራቸው እንዳይረሱ መታሰቢያ በመልካቸው ሐውልት እንዲቀረፅላቸውና የሚሠሩበትም ገንዘብ እርሳቸው ያመጡትን አትክልት በየቦታው ከብዙው ብዙ ከጥቂቱ ጥቂት በበ እሩብ በማምቱ ኪሊፍቶስ ባለበት በከተማ በሀገርም ውሥጥ በሙሉ ኢትዮጵያ የጸና አዋጅ ተደርጎ ለዚሁም ሥራ በቶሎ የሚያሠሩ ሹም ተሹሞ እየተቀበለ እንዲያሠሩላቸው የማክበር ምኞቴን አመለክታለሁ

ይግለጡ ዳምጤ

የከተማ ወሬ ።

ታኅሣሥ ፲፯ቀን ኤውሮጶች እንደ አገራቸው ቁጥር የእግዚእን ኢየሱስ ክርስቶስ የልደቱን በዓል የሚያከብሩበት ስለ ሆነ በካቶሊኮች ቤተ ክርስቲያንና በየሌጋሲዮኑም ሁሉ በየትልልቆቹም ነጋዴዎች ቤት ብዙ ጌጥና ፈንጠዝያ ተደርጎ የደስታ በዓል ሁኖ ዋለ ።

ብርሃንና ሰላም የእግዚእን ኢየሱስ ክርስቶስ የልደቱን መታሰቢያ በዓል አክብረው ለዋሉ ክርስቲያኖች ወንድሞቻችን እንኳን የደስታና የበረከት በዓል ሆነላቸው እያለ ደስታውን ይገልጻል ።

የባቡር አደጋ ።

ታኅሣሥ ፲፯ቀን ከሞጆ ወደ አዲስ አበባ የሚመጣ ባቡር ተጋጭቶ አሥራ አምስት ሰዎች ቈሰሉ ። ከነዚሁ ሁለቱ ሞቱ ለሞትም የደረሱ አሉ ።

ያገር ውሥጥ ወሬ ።

በድሬ ደዋ የቆመ የንግድ ሥራ ማኅበር ለሥራቸው አስተዳዳሪዎች የሚሆኑት ቀጥሎ የተጻፉትን ሹምዋል።

ፕሬሲዳን (ሹም) ያዕቆብ የጀም ሙሐመድ ዓሊና ኩባንያ ወኪል ።
ሴክሬቴር (ጸሐፊ) ጀ ፒያፔትሮ የሙሴ ሬዩና የልጆች ወኪል።
ትሬዘሪዬ (ግምጃ ቤት) ናቱ ሙልጂ ።

አማካሪዎች ሙሴ አ ሻዊንኪልና ባሳብሬን ናቸው። ብርሃንና ሰላም አዲስ ለተሾሙትና ለመላው ማኅበር የሥራቸው መከናወን እየተሻለ እንዲሔድ ይመኝላቸዋል ።

ያገር ውሥጥ ወሬ

በጐጃም አገር ከብዙ ዘመንና ዓመት ጀምሮ እህልና ማር፡ቅቤ፡ የቀንድ ከብትና የጋማ ከብት ርካሽ ነበር ሒደው ያዩት ሰዎችም ስለ ሀገሩ ፍሬያምነት ብዙ ያደንቃሉ፡ ያላዩት ሰዎችም ወሬውን በጣም ሰምተውታል ፡ ባለፈው ዓመት ግን እህልና ቅቤ ማርም የቀንድ ከብትና የጋማ ከብትም ውድ ሁኖ ከረመ ይባላል ።

ከብቱ መውለዱን ሳይተው አራሹም እንደ ድሮው ሲያርስ እህልና ከብት እንዲህ መወደዱ ምን ይሆን ።

ይልቁንም ባለፈው ክረምት እህል በጣም ውድ ስለሆነ ድኃው ከገበያ ሸምቶ የማይዘልቀው ቢሆን ክቡር ራስ ኃይሉ ጐተራቸውን በያለበት አስከፍተው ቋናውንም ከገበያው ቁና ከፍ አድርገው ስፍሩንም ገበያ ከሚሸመተው ዕጥፍ አብልጠው ድኆቸው እ ዳይጐዳ በእህል ሲረዱት ከረሙ ።

ከድሆችም እውቀት ያላቸው ሰዎች ከመንግሥትና ከመኳንንት ጐተራ የሚቀመጥ እህል ከግምጃ ቤታቸውም ያለ ወርቅና ብር ለአሽከሮቻቸው ሽልማትና ጌጥ ለድሆችም በችግራቸው ጊዜ እርዳታ ለአገሩም ከችግር መጠበቂያ መሆኑን ስለ ተረዱ ጌታቸውን በጣም ሲያመሰግኑ ከረሙ፡ ወደ ሩቅ አገር ሳይደክሙ እህል በየደጃቸው ስላገኙ ፡ ለወደፊቱ ግን እህል በቆላውና በደጋው መልካም ሁኖ በቅሎ ፍሬውም ደስ አሰኝቷልና እህል እንደ ድሮው ይረክስልናል ብለው ብዙ ተስፋ አላቸው ።

አምና ወደ ጐጃም ሒጄ ነበረና ባይኔ ያየሁት የክቡር ራስ ኃይሉ መልካም ሥራቸው ባላገሩ በማይገባ ጭቅጭቅ እየተከሰሰ ወደርሳቸው ሲሔድ ለራሱና ለመንግሥት ጥቅም የሆነውን ሥራውን ትቶ ከዚህ በከንቱ እንዳይቀመጥ ብለው ሥራቱን በቶሎ እየጨረሱ ድኃው ወደቤቱ ሒዶ ሥራውን እንዲሠራ ያሰናብቱታል ። እንዲሁም ድኃ ጠባቂ ለሆኑት ሹማምቶች ሁሉ ድኆቻቸውን በጥንቃቄ እንዲጠብቁና አገራቸውን በእርሻ በአታክልትና በከብት ማርባት ረድተው ሀብታም እንዲያደርጓት እግዚአብሔር ይርዳቸው የኢትዮጵያ ልጆች ዋና ጥቅማቸው እርሻ አታክልትና ከብት ማርባት እንደሆነ የታወቀ ነው ።

ቄስ በደማ ያለው

ማመልከቻ

ክቡር ዶክቶር ሐነር ነጭ ሰሎጊ ውሻ ስለ ጠፋባቸው አግኝቶ ላመጣው ሰው የሚገባውን ጉርሻ ይሰጣሉ ። ያገኘው ሰው ወደ ቤተ ሳይዳ ሆስፒታል ዘተፈሪ መኰንን እንዲያመጣ እናመክታለን ።

በጀርመን ሌጋሲዮን የመጣ ራዲዮ የታኅሣሥ ፲፮ቀን የለት ወሬ

ከስታንቲኖፕል፤በመንግሥት ላይ አድማ ያደረጉትን ብዙ ሰዎች ፖሊስ አሠራቸው ።

መስኮው ፡ የሩስያና አፍጋን የአየር ባቡር ሥራ በታሽኬንድና በካቡል መካከል ተጀምሯል ። የአፍጋን የጠብ መነሣት እየበረደ ይሔዳል ።

ከስታንቲኖፕል ፡ በአፍጋን በሆነ መነሣት ሁለት የቱርክ ኦፊሰር (የወታደር አለቆች) ሙተዋል ። የአፍጋንን ወታደሮች የሚያስተምሩ የቱርክና የሩስያ አማካሪ ክፉኛ ይዟቸዋል ።

ለንደን ፡ ንጉሡ የጤናቸው አኳኋን እየተሻለ ይሔዳል ።

ኦቤርላንድ

ማስታወቂያ ።

አዲስ ዓይነት የመጣ ባለውሻ አቤርላንድ ኦቶሞቢል ከሁሉ የሚበልጥ ነው ።

መንገዱ እጅግ የፈጠነ ነው ። የንጠጠን ዳገት በቶሎና አለድካም ለመውጣት ይችላል ። ቤንዚንም ብዙ አይጨርስም ።



አንድ ቆርቆሮ መቶ ሰባ ኪሎ ሜትር ያስኬደዋል ወዲያም ባለማግኔቶና ባለባተሪ ነው ከምስት ላስቲክ ጋራ ይሸጣል ዋጋውም ርካሽ ነው አራት እግሩ ላይ መጠበቂያ ፍሬን አለው ማሳደሻ መሣሪያም በየዓይነቱ እኛ ዘንድ ይሸጣል ለዚህ አቶሞቢል በኢትዮጵያ በተለየ ወኪል «ዓረብያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ» ነው

ወዲያውም የአቶሞቢል ዘይትና ያሜሪካን ቤንዚን ይሸጣል ።

COGNAC S. & E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ ተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሩግቢ

ማስታወቂያ።

በኢትዮጵያ አገር የሚኬዱባቸው መንገዶች በብዙ ተራሮች ላይ ስለ ሆነ በነዚህ መንገዶች ላይ ያለችግር እንደ ልብ የሚወጣ ኃይልና ብርታት ያለው አቶመቢል ያስፈልጋል ።

ነገር ግን ይህን የመሰለ ኃይለኛ አቶመቢል ብዙ ቤንዚን የሚፈጅ እንዳይሆን ጥቅምዎን ያስጠነቅቀዎታል

"ሩግቢ" የተባለው አቶመቢል በኢትዮጵያ ከመጣ ዝምሮ ላገርዎ የሚያስፈልግዎ ምሳሌ የሌለው መሆኑን ገልጸ ሰያ ስረዳዎ ቀርቷል ተብሎ አይጠረጠርም ።

በኢትዮጵያ የዚህ አቶሞቢል በተለይ ወኪል "አራቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ" ነው

የዚህም ኩምፓንያ ዋና የንግድ ቤቱ በሎንዶን ከተማ ነው።

RUGBY

ደግሞ በኔዮርክ በፊላዴልፊአ በቦቶን በማድራስ [illegible] ከተሞችና፡በአዲስ አበባም የንግድ ቤቶች አሉው።

በአዲስ አበባ ቤታቸው ለዚህ አቶመቢል የሚያስፈልጉት የመለዋወጫ መሣሪያዎችና በያይነቱ ሳስቲክ ። ደግሞ የአሜሪካን የታላቁ ስታንዳር ኩምፓንያ ጋዝ ቤንዚን በያይነቱ ቅባት ዘወትር ይገኛል



ባርባሬሶ

ኮኛክ ።

ከሁሉም የኮኛክ ፋብሪካ የበለጠ በግሪክ አገር የባርባሬሶ ፋብሪካ ነው ።

ብቻውን በተለየ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ያሰናጂነት ፈቃድ የተቀበለ።

ተታላችሁ ክልስ እንዳትገዙ ይህን በካፕሱሉ ያለውን ምልክት መርምሩ ይህ ምልክት በካፕሱሉ ላይ የሌለበት ኮኛክ ክልስ ነው።

ኒለሀ

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒከላ ።

ማስታወቂያ ።

የበለጡ የኤሌክትሪክ ሞተርና ጄኔራቶር ደግሞ ትራንስፎርማተርና በየዓይነቱ የራዲዮ መኪና ከኤሌክትሮሜካኖ ከሚባል የስዊድን ፋብሪካ ይገኛሉ ።

አድራሻውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ።

ELEKTROMEKANO. Hälsingborg(Sweden)
Agents: Stockholm, Göteborg, Malmö och Karlstad



ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ። የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቁጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ፤ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል

አደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ሱቅ ነው ።

ማስታወቂያ

ድራሌ ።

በጀርመን አገር በሀምቡርግ ከተማ የሚሠራው የድራሌ ሽቱ በኢትዮጵያ ከሠላሳ ዓመት ወዲህ ስሙ የተጠራና የተወደደ ሁኖ ይኖራል ።

ሽቱ ለሚሸጥላችሁ ሁሉ ድራሌን አምጣ በሉት ። ድንገት ግን ላይሆንለት የኛውን አስመስሎ አበጅቶ ድራሌ ነው እያለ ሊሸጥላችሁ ቢከጅል እሺ አትበሉት ። የድራሌ ሽቱ ባለ መለዮ ነውና ስትገዙ እንዲህ ብላችሁ ጠይቁ ባለእንጨት ። ባለወረቀት ባለምኒልክ ። ባለወርቅ የብርሌ ሎሲዮን ።

ጥሩ ሱቅ ከሆነ ባዲስ አበባና በድሬ ዳዋ በሐረር ከተማም የድራሌ ሽቱ የማይገኝበት የለም ።



ከሁሉ የሚበልጥ አዲስ ዓይነት ላስቲክ አለ አሜሪካን ቤት ይሠራል። ይኸውም ላስቲክ ስሙ ጉድዩር ይባላል ። ሲሄድ እንደ ማጭድ ይይዛል ደግሞ በልክ ይነዳል ። በገደልም በጭቃም ላይ ቢሆን አያስፈራም ። እንደ ልብ ያሰኬዳል በድጥም ስፍራ አያድጠውም በድንጋዩም ላይ ሲሄድ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ጠንካራ ነው ። በሌላ ጊዜ ላስቲክ ብትፈልጉ የዚህን ዓይነት ላስቲክ ጉድዩር ግዙ ከሌላው ላስቲክ ሁሉ ሁለት እጅ ይበረክታል ዋጋው ግን እኩል ነው ። ከሁሉም ርካሽ ነው ይህ ላስቲክ የሚገኘው ዓረብያን ትሬዲንግ ኩባንያ ቤት ነው።

ጉደደ[illegible]

BRITISH MUSEUM 8 NOV 29

GOODYEAR

2-28-14

በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን (ኢትዮጵያ) መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።